# የማርክሲዝም ሌኒኒዝም

# መዝገበ ቃላት

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
አዲስ አበባ ፣ ፲፱፻፸፰

# መግቢያ

ቃላት ይወለዳሉ ፤ ያድጋሉ ፤ ይራባሉ ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ የማደግና የመራባት ዕድል ሳይገጥማቸው በአጭሩ ይቀጫሉ ። ይህ የሰው ልጅ ታሪኩን ፣ የዕለት ተዕለት ክንውኑን ፣ ዕውቀትና ልምዱን ፣ በአጠቃላይ ባህሉን በሚገለጽበትና እርስበርሱ በሚግባባበት መሣሪያው ማለትም በቋንቋ ውስጥ ተደጋግሞ የሚታይ ክስተት ነው ።

የሰው ልጅ ተፈጥሮን በይበልጥ እየገራና በቁጥጥሩ ሥር እያደረገ ሲሔድ ፣ በየጊዜው አዳዲስ የተፈጥሮና ማኅበራዊ ሕጐችን እየተገነዘበ ፣ የአዳዲስ ግኝቶች ባለቤት እየሆነ ልምዱን እያዳበረና የዕውቀት አድማሱን እያሰፋ ይሔዳል ። የሰው ልጅ ማኅበራዊ ግንኙነት፣ የሚከተለው ፍልስፍና ፣ ወግና ልማዱ ፣ ለምርት ተግባር የሚገለገልባቸው መሣሪያዎችና የአመራረት ዘዴዎች ፣ በአንድ ደረጃ ላይ የሚቆሙ ሳይሆኑ የሚያድጉና የሚለወጡ ናቸው ።

የሚገኙትን አዳዲስ ዕውቀቶችና ልምዶች የሚያንፀባርቁ ጽንሰ ሐሳቦችን የሚገልጹ አዳዲስ ቃላት የመፍጠር ፍላጐትም በለሚከሰት ቋንቋ ያንኑ ያህል እያደገ ይሄዳል ።

እያንዳንዱ ወቅት ፣ ዕውቀትና ልምድን ለማዳበር የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ቢኖረውም ፣ የሰው ልጅ ያሳለፋቸው ዘመናት ሁሉ በእኩል ደረጃ ዛሬ ላለበት ከፍተኛ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘመን አብቅተውታል ማለት ያስቸግራል ። ሥር ነቀል ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች የሚታዩባቸው ፤ አዳዲስ ሐሳቦች የሚፈልቁባቸውና ነባሮቹም በፋትና ምልዓት የሚያገኙባቸው አንዳንድ ዘመናት አሉ ። ሰአዳዲስ ጽንሰ ሐሳቦች አዳዲስ ቃላት የመፍጠሩም ሆነ እነዚህን ጽንሰ ሐሳቦች በዝርዝርና በጥልቀት የማብራራቱ ፍላጐትም ከሌሎች ይልቅ በእነዚህ ዘመናት አይሎ ይታያል ።

አዳዲስ ጽንሰ ሐሳቦችን የሚያንፀባርቁ አዳዲስ ቃላትን የመፍጠር ፍላጐት መኖሩና የቃላትም መፈጠር የማይታለፍ ቢሆንም ችግሮችም አሉበት ። እያንዳንዱ ግለሰብ ፤ ቡድን ወይም ተቋም ለአንድ ጽንሰ ሐሳብ የራሱን ስያሜ ከሰጠ ማለትም የስያሜ አሰጣጥ ደንብና ሥርዓት ሳይከተል የመሰለውን ካደረገ መግባባት ሊኖር አይችልም ። በአብዛኛው ተቀባይነት ያገኙ አዳዲስ ስያሜዎች ሙሉ በሙሉ እንዲሠራባቸውና ከመደበኛው ቋንቋ መድበለ ቃላት ውስጥ እንዲካተቱ ለማድረግ መዝገበ ቃላት ማዘጋጀትና ማሰራጨት ፤ በመገናኛ ብዙኃን ማስተዋወቅ ፤ ወዘተ. አስፈላጊ ነው ።

የኢትዮጵያ አብዮት ከተቀጣጠለ ከ1966 ወዲህ ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ለማስተማር የሚያግዙ በርካታ መጻሕፍት ወደአማርኛና ወደሌሎችም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ተተርጉመዋል ። ይህ ተግባር ለተወሰኑ ዓመታትም ቢሆን አንድ አስተባባሪ ማዕከል ሳይኖረው በተለያዩ ግለሰቦችና ቡድኖች ቢከናወን ቆይቷል ። ስለዚህም ጽንሰ ሐሳቦችንና መልዕክቶችን በትክክልና ወጥነት ባለው መልክ በማስተላለፍና በስያሜ ቃላት በኩል የታዩት ችግሮች ቀላል አልነበሩም ።

ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሳይንስ እንደመሆኑ በየትኛውም ቋንቋ ሲገለጽ ሳይንሳዊነቱን እንዳያጣ ብርቱ ጥንቃቄ መደረግ አለበት ። በተለይ በዚህ ሳይንስ ንድፈሐሳብ ኅብረተሰቡም ሆነ ቋንቋው እንግዳ በሆኑበት አካባቢ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው ።

በዚህ ረገድ ገና ከአብዮታችን መባቻ ጀምሮ አንዳንድ ጥረቶች መደረጋቸውና የማ ይናቅ ጠቀሜታ መገኘቱ ዕውቅ ነው ። ሆኖም ጉዳዩ ጠለቅ ያለ ትኩረት የሚያሻው በመሆኑ ለዚሁ ይረዳ ዘንድ ይህ መዝገበ ቃላት ሊዘጋጅ ችሏል ።

የኢትዮጵያ አብዮታውያን ለአብዮቱ አንድ ማዕከል ፈጥረው በኢትዮጵያ ሠርቶአደ ሮች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን (ኢሠፓአኮ) ሥር ለመሰባሰብ ሲወስኑ ፤ ይህ ድርጅት ከነበ ሩት ሁለት ዓላማዎች አንዱ "...በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ መካከል የማርክሲዝም ሌኒኒ ዝም ፍልስፍና እንዲሠራጭና እንዲሰርጽ ማድረግ" የሚል ነበር ። ይህንኑ በተግባር ለመ ግለጥ በሚደረጉት ጥረቶች ፤ በተለይም በጽንሰ ሐሳቦች ፍቺና በቃላት አጠቃቀም ረገድ ወጥነት እንዲኖር ልዩ ልዩ እርምጃዎች ተወስደዋል ። እነዚህም እርምጃዎች ለርዕዮተ ዓለሙ በጥራት መሰራጨት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

ይሁን እንጂ ለታቀደው ዓላማ ሙሉ በሙሉ በሚፈለገው መልክ መከናወን ይህ ብቻ በቂ ሆኖ አልተገኘም ። ስለዚህም የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ርዕዮተዓለም መምሪያ አንድ ማርክሳዊ ሌኒናዊ መዝገበ ቃላት ለማዘጋጀት አቀደ ። ለመነሻም እንዲሆን በኢት ዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ የተጠናቀረ 600 ያህል ቃላት ያሉት ረቂቅ መዝገበ ቃላት ተመረጠ ። የቀረበው ረቂቅ በቅርጽም ሆነ በይዘቱ ተሻሽሎና ተጨማሪ ጽንሰ ሐሳቦ ችን ይዞ እንዲወጣ ተወሰነ ። በዚሁ መሠረት ከኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት ፣ ከየካቲት 66 ፖለቲካ ት/ቤት ፣ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚና ከአዲስ አበባ ዩኒቨ ርሲቲ የተውጣጣ አንድ የዝግጅት ኮሚቴ ተቋቁሞ ሥራው በ1973 ተጀመረ ። ቅድሚያ በሚሰጣቸው ልዩ ልዩ ተግባሮች ምክንያት ዝግጅቱ በተፈለገው ፍጥነት ሊከናወን ባይ ችልም በብዙዎች አስተዋጽኦ እነሆ ሊጠናቀቅ በቅቷል ።

ይህ የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት ብዙ ጊዜ እንደምንገለገልባቸው መዛግብተ ቃላት ፤ ቃላትን ከፍችዎቻቸው ጋር በማጐዳኘትና ከተቃራኒዎቻቸው ጋር በማመሳከት የሚወሰን አይደለም ። በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሳይንስ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚያጋጥሙ ቃላት ተመርጠው እያንዳንዱ ቃል ያቀፈውን ጽንሰ ሐሳብ ፤ ወይም እያንዳንዱ ቃል እንዲያ ንፀባርቅ የሚፈለገውን ጽንሰ ሐሳብ በማብራራትና በመተንተን የሚያቀርብ ነው ። ይህ ስልት እምብዛም የተለመደ ባይሆንም ለቃላት ወይም ለሐረግ መፍቻነት ብቻ ሳይሆን አንባቢ ስለእያንዳንዱ ጽንሰ ሐሳብ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ያገኝበታል ተብሎ ይታመናል ።

ይህ የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት የሳይንሳዊ ኮሚኒዝም፣የፖለቲካዊ ኢኮኖሚና የፍልስፍና ጽንሰ ሐሳቦች የሚያንፀባርቁ ቃላትን ፤ እንዲሁም በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሳይ ንስ ውስጥ ተዘውትረው የሚጠቀሱ ስሞችን ያካተተ ነው ። የቃላቱም ሆነ የስሞቹ አደራ ደር በአማርኛ ፊደል ቅደም ተከተል መሠረት ሆኖ ተመሳሳይ ድምፅ ያላቸው ሆሄያት በአንድ ተራ ተሰባስበው እንዲቀመጡ ተደርጓል ።

የመዝገበ ቃላቱን አጠቃቀም በሚመለከት የሚከተሉትን ነጥቦች ማጤን አስፈላጊ ነው ።

ሀ. በመዝገበ ቃላቱ ውስጥ የተካተቱ ቃላት በአብዛኛው ሲሠራባቸው የቆዩና ተቀባይነት ያገኙ ናቸው ።

ለ. አንድን ጽንሰ ሐሳብ እንዲያንፀባርቁ በየአካባቢው በዘፈቀደ ሲነገሩ ከነበሩት ቃላት ውስጥ የበለጠ ተቀባይነት ያላቸውንና በቀላሉ ሊሰመዱ የሚችሉትን መርጠናል ።

ሐ. ስያሜ ላልነበራቸውና ቢኖራቸውም በተወሰነ ክልል እንጂ ሰፊ ተደማጭነት ላልነበራቸው ጽንሰ ሐሳቦች አዳዲስ ስያሜ ሰጥተናቸዋል ።

መ. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለአዳዲስ ስያሜዎች ፤ የስያሜውን ሥርወ ቃልና ፍች ለመጠቆም ተሞክሯል ።

ሠ. ለንጽጽር እንዲረዳ ነባሮቹም ሆኑ አዳዲሶቹ ስያሜዎች ከእንግሊዝኛ አቻዎቻቸው ጋር በአማርኛና በእንግሊዝኛ ፊደል ቅደም ተከተል መሠረት በመዝገበ ቃላቱ የመጨረሻ ገጾች በዝርዝር ቀርበዋል ።

ረ. የዘመን አቆጣጠርን በተመለከተ እ.ኢ.ት.አ. ካልተባለ በቀር በጎርጎርዮሳውያን መሠረት ነው ።

አንድን መዝገበ ቃላት ለማዘጋጀት የቱንም ያህል ጊዜ ፣ ጉልበት ፣ ዕውቀትና ገንዘብ ቢጠይቅም ታትሞ መውጣቱ ብቻ የመጨረሻ ግብ ሊሆን አይችልም ። በስፋት ግልጋሎት ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ፤ በየጊዜው መገምገምና ማሻሻል ይገባል ። ይህም ማርክሳዊ ሌኒናዊ መዝገበ ቃላት ለተዘጋጀበት ዓላማ መብቃቱን ማረጋገጫው ዘዴ ይኸው ነው ።

በአገራችን ፍትሕና ብልጽግና የሰፈነበት አዲስ ኅብረተሰብ ለመገንባት የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ (ኢሠፓ) የቀየሰው ትልምና የሚሰጠው አመራር ተግባራዊነት ወሳኝ መሆኑ ግልጽ ነው ። ስለዚሁ መሳካት የማርክሲዝም ሌኒኒዝም በሰፊው መስራጨት የማይታለፍ ሁኔታ ሲሆን ይኸው በበለጠ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ይህ መዝገበ ቃላት ድርሻ እንደሚያበረክት እሙን ነው ።

አዘጋጅ ኮሚቴው

# ሀ

## ሁለተኛው ኢንተርናሽናል
*(Second International)*

አንደኛው ኢንተርናሽናል ከፈረሰ በኋላ ከ1889—1914 ለነበረው የወዝአደሮች ዓለም አቀፋዊ የትግል ድርጅት የተሰጠ መጠሪያ ነው ።

ሁለተኛው ኢንተርናሽናል የአውሮፓና የአሜሪካ ሠራተኞችን የሶሻሊስት ፓርቲዎች የሚወክሉ 393 መልእክተኞች ተካፋይ የሆኑበት በሐምሌ 1889 ፓሪስ ከተማ በተደረገው የመጀመሪያው ጠቅላላ ጉባኤ ተመሠረተ ። ለሁለተኛው ኢንተርናሽናል መመሥረት የነበሩት ቅድመ ሁኔታዎች ከካፒታል የመጀመሪያ ደረጃ ማለትም ከነፃ ውድድር ወደ ሞኖፖል ካፒታል ወይም ወደ ኢምፔሪያሊዝም በሚደረገው የሽግግር ወቅት የሠራተኛው ንቅናቄ ማደግና በአንደኛው ኢንተርናሽናል ዝግጅት ሳቢያ የሠርቶ አደር ፓርቲዎች በብዙዎቹ የአውሮፓ ሀገሮች መቋቋምና የማርክሳዊ ሐሳቦች መሰራጨት ናቸው ፤ ኤንግልስ ሁለተኛው ኢንተርናሽናል እንዲቋቋም ከፍተኛ ጥረት አድርጓል ።

ሁለተኛው ኢንተርናሽናል በ1889 ተመሥርቶ በአንደኛው የዓለም ጦርነት መጀመሪያ ላይ (1914) ነባራዊ ህልውናው እስከአከተመበት ወቅት ድረስ የአከናወናቸውን ተግባራት በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል ።

አንደኛ ፣ ሁለተኛው ኢንተርናሽናል ከተመሠረተበት ጊዜ አንሥቶ በ1896 በለንደን አራተኛው ጠቅላላ ጉባኤ እስከተደረገበት ድረስ ያለው ነው ። በዚሁ ወቅት ኤንግልስ በኢንተርናሽናሉ ዘንድ ከፍተኛ ተደማጭነት ስለነበረው ማኅበሩ በተከታታይ በተደረጉት ጉባኤዎች በአመዛኙ ማርክሳዊ አቋም ይዞ ለመቆየት ችሏል ።

አራቱ ጉባኤዎች ካስተላለፏቸው ውሳኔዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ፤

1. የስምንት ሰዓት የሥራ ቀን በአስቸኳይ እንዲወሰንና ሜይ ዴይ የወዝአደሮች የትግል መዛሪያ ሆና በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲከበር ማድረግ ፤
2. ጦርነት የካፒታሊስት ሥርዓት የማይቀር ውጤት መሆኑንና ሰላም የሚገኘው በሶሻሊዝም መሆኑን በውሳኔ ማሳወቅ ፤
3. የኢኮኖሚና የፖለቲካ ትግል ቅንጅትን አስፈላጊነት በውሳኔው ማሳለፍ ፤
4. የፖለቲካ መብት የካፒታልን የበላይ ገዥነት ማስወገጃና ሥልጣን የመንጠቂያ መዛሪያ መሆኑን ማረጋገጥ ፤
5. ሥርዓት አልበኞችን ከሁለተኛው ኢንተርናሽናል ማስወገድ ።

ሁለተኛ ፣ በ1896 ለንደን ላይ ከተካሄደው አራተኛው ጉባኤ በኋላ በኢንተርናሽናሉ ውስጥ አድርባዮች ሰርገው በመግባት አመራሩን በመያዛቸውና በተጨማሪም በሞኖፖል ካፒታሊዝም መስፋፋት ምክንያት የወዝአደሩ መሳፍንት እየተጠናከሩ በመምጣታቸው ሁለተኛው ኢንተርናሽናል ሳይንሳዊውን የትግል አቅጣጫ በመሳት የውድቀቱን ጉዳና የተያያዘበት ነው ።

በመስከረም 1896 በፓሪስ በተደረገው አምስተኛ ጉባኤ ላይ የፈረንሳይ ሶሻሊስት መሪ ሚሊራ ለመደቦች እርቅ በመቆሙና የአድኃሪው የቡርዧ መንግሥት የሥልጣን ተካፋይ በመሆኑ ሲወገዝ ፣ ካውትስኪና በርንስታይን ግን እሱን በመደገፍ ለአድርባዮች በር ከፈቱ ። በመጨረሻም በአድርባዮች የቀረበው ውሳኔ ጸደቀ ።

ከዚህም በኋላ በተከታታይ በተደረጉት ጉባኤዎች በመጀመሪያ የሩሲያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ሌበር ፓርቲ ፣ በኋላም የቦልሼቪክ ፓርቲና ሌሎችም ሐቀኛ ማርክሳውያን ከአድርባዮች ጋር ባደረጉት ትግል ብዙ ትክክለኛ ውሳኔዎች ሊተላለፉ ቢችሉም ተግባራዊ የሆኑት ግን በከፊል ነበር ።

ለምሳሌ በነሐሴ 1907 በእሽቱትጋርት የተደረገው ሰባተኛው ጉባኤ በቦልሼቪኮች ከፍተኛ ጥረት ለጦርነት ዝግጅት የሚደረግ ወጪን በመቃወም ፣ መደበኛው ጦር በሕዝባዊ ሚሊሺያ እንዲተካ በመጠየቅ ውሳኔ አስተላልፏል ፤ በኢምፔሪያሊስቶች መካከል ጦርነት ቢነሣ ሶሻሊስቶች የፖለቲካና የኢኮኖሚ ቀውሱን ካፒታሊዝምን ለመጣል ሊጠቀሙበት እንደሚያስፈልግም አስታውቋል ።

እንደዚሁም ስምንተኛውና ዘጠነኛው ጉባኤዎች ጦረኝነቱን በመቃወም ፣ የእስያን ሕዝቦች የብሔራዊ አርነት ትግል በማድነቅና በመደገፍ ትክክለኛ ውሳኔዎችን አስተላልፈው ነበር ። በተለይም ዘጠነኛው ጉባኤ ያጸደቀው “የባዝል ማኒፌስቶ” በሚል አጠራር የሚታወቀው ውሳኔ “ሶሻሊስት ፓርቲዎች ሁሉ በኢምፔሪያሊዝም ላይ የማያቋርጥ ትግልና የአንድነት ተግባር እንዲያካሂዱ የጉባኤው ተካፋዮች በጥብቅ ይጠይቃሉ” የሚል ነበር ።

ነገር ግን በአንደኛው የዓለም ጦርነት መጀመሪያ ላይ አድርባይ ሶሻሊስት ፓርቲዎች የጉባኤዎቹን ውሳኔዎች በተግባር ላይ በማዋል ፋንታ የጦር በጀት በማጽደቅ ለየሀገራቸው ኢምፔሪያሊስት ቡርዧዚ አጉበደዱ። ለምሳሌ የጀርመን ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ ተወካዮች የቡርዧው መንግሥት ለጦርነት ዝግጅት ያቀረበውን በጀት አጸደቁ ። የቤልጅግ ፣ የእንግሊዝ ፣ የፈረንሳይና የሌሎችም ሀገሮች ሶሻሊስት ፓርቲዎች ይህንኑ ፈለግ ተከተሉ ። በአብዛኛው መሪዎቹ የቡርዧ መንግሥት ካቢኔ አባላት በመሆን የኢንተርናሽናሉን ውሳኔዎች በመጣስና በማፍረስ ወዝአደሩን ሙሉ በሙሉ ጦርነቱ ውስጥ ማገዱት ። ስለዚህም የሁለተኛው ኢንተርናሽናል ገቢራዊ ህልውና በ1914 አከተመ ።

የሶሻሊስትና የሠራተኛ ፓርቲዎችን አመራር በመያዝ በሁለተኛው ኢንተርናሽናል የአድርባይነትና የክላሽነት አዝማሚያ ያራምዱ ከነበሩት መካከል ካውትስኪ ፣ በርንስታይን ፣ ሂንደማን ፣ ማክዶናልድ ፣ ቶማስ ቫንደርቬልድና ባወር ሲገኙበት በሁለተኛው ኢንተርናሽናል የተከሰተውን ይህንን ክላሽነትና አድርባይነት ለመቋቋም ሌኒን ፣ ሜሪንግ ፣ ሉክሰምበርግ ፣ ፕሌኻኖቭ ፣ ሊብክኔኽት ፣ ብላጐቬና ሌሎችም ከፍተኛ ትግል አድርገዋል ።

## ሁለተኛ ደረጃ ቅራኔ
(*Secondary Contradiction*)

በአንድ በተወሰነ የሂደት ወቅት ላይ ለጊዜውም ቢሆን ተቻችሎ ፣ ቀዝቀዝ ብሎ ዋንኛ ደረጃን ሳይዝ መለስተኛ በሆነ የመካረር ደረጃ ላይ የሚገኝ ቅራኔ ነው ።

ይህ የቅራኔ ደረጃ በአንድ በተወሰነ የዕድገት ወይም የትግል ወቅት የሚኖረውን ሁኔታ የሚያሳይ እንጂ ሁልጊዜም በዚህ ሁኔታ የሚከሰት አይደለም ። የቅራኔዎች ቦታ እንደየትግሉ ይዘትና እንደየግንኙነቱ ባሕርይ ይለዋወጣል ። በተገላቢጦሽ ዋነኛ የነበረው በሂደት ላይ ቦታውን ቀይሮ ወደ ሁለተኛ ፣ ሁለተኛው ደግሞ ወደ ዋነኛ ቅራኔነት የሚለወጡበት ሁኔታ አለ ።

በአጠቃላይ አመለካከት መሠረታዊ ቅራኔዎች እንደ አንደኛ ደረጃ ቅራኔ ፣ ሌሎች ደግሞ እንደየሁኔታው እንደ ሁለተኛና እንደ ሦስተኛ ደረጃ ቅራኔ ይታያሉ ። ግን ሁልጊዜም መሠረታዊ ቅራኔዎች ሁሉ አንደኛ ደረጃ ቅራኔዎች ናቸው ወይም በአንድ በተወሰነ ወቅት በአንደኛ ደረጃ የሚታዩት ቅራኔዎች ሁልጊዜ መሠረታዊ ናቸው ማለትም አይደለም ። የሀገራችንን ሁኔታ ብንወስድ ፊውዳሊዝምም ሆነ ኢምፔሪያሊዝም የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ መሠረታዊ ጠላቶች በመሆናቸው በነሱና በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ መካከል ያለው ቅራኔ መሠረታዊ ወይም የማይታረቅ ቅራኔ ነው ። ግን በአንድ ወቅት እንበል በየካቲት ሕዝባዊ አብዮት መጀመሪያ ላይ ዋነኛው ቅራኔ በፊውዳሊዝምና በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ መካከል የነበረው ነው ። በኋላ ግን በሂደት ላይ አንደኛውን ቅራኔ በአብዮታዊ ትግል እየፈታን ፊውዳሊዝም እንዳያንሰራራ ሆና ሲደመሰስ ፣ ይልቁንም የአብዮታዊው መንግሥትና የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ፀረ ኢምፔሪያሊስት አቋም ይበልጥ እየተጠናከረ ሲመጣ ከኢምፔሪያሊዝም ጋር የነበረው ቅራኔ ተካርሮ ወደ አንደኛነት ደረጃ ከፍ እያለ መጣ ። ትግሉም በቀጥታና በተዘዋዋሪ ከፖለቲካዊና ከኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ አልፎ ከኢምፔሪያሊዝም ኃይሎች ጋርም ባይሆን የነሱ መሣሪያ ከሆኑት ተስፋፊዎች ፣ ገንጣዮችና ከሌሎችም ፀረ አብዮት ኃይሎች ጋር የትጥቅ ፍልሚያን ጭምር

እስከተለ። ባንፃሩም ቀድሞ በአንደኛ ደረጃ ይታይ የነበረው በፊውዳሊዝምና በሰፊው ሕዝብ መካከል የነበረው ቅራኔ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ዝቅ አለ። በተለይም አሁን ባለንበት ደረጃ የኢምፔሪያሊዝምና የፊውዳሊዝም ጭቃኝ ከሆነው ከቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ጋር የሚደረገው ትግል የፊውዳሉን ሥርዓት ርዝራዥ ለማጽዳት ከሚደረገው ትግል የጠነከረ ስለሆነ የቅራኔዎች ደረጃ መሸጋሸግ በግልጽ ይታያል።

የካፒታሊስቱን ኅብረተሰብ ሁኔታ ብንመለከት በሁለቱ መሠረታዊ ኃይሎች ማለትም በካፒታልና በጉልበት (በካፒታሊስቱና በወዝአደሩ) መካከል ያለው ቅራኔ ዋነኛው ወይም በአንደኛ ደረጃ የሚታይ ነው። ምክንያቱም የሥርዓቱ የብዝበዛ ግንኙነት መሠረትና የካፒታሊዝም ህልውና የሚወሰንበት ግንኙነት ይህ በመሆኑ ነው። ሌሎች ቅራኔዎች ለምሳሌ በፊውዳሉ መደብ ርዝራዦችና በቡርዧዚው፣ በወዝአደሩና በንዑስ ከበርቴ ገበሬው፣ በኢምፔሪያሊስት ሀገሮች መካከል ወዘተ... ያሉት ቅራኔዎች በሁለተኛ ወይም በመለስተኛ ደረጃ የሚታዩ ናቸው።

(ቅራኔን፣ አንደኛ ደረጃ ቅራኔን ይመለከቷል።)

## ሁለታዊነት
### (*Dualism*)

በዓለም ውስጥ የሚገኙ ነገሮችና ክስተቶች የህልውና መሠረት አንዱ ከሌላው ነፃ የሆነና ምንም ግንኙነት የሌላቸው፣ ሁለት የእኩልነት ደረጃ ያላቸው ማለትም ቁስአካልና መንፈስ ናቸው የሚል ፍልስፍና ነው። ሁለታዊነት ቁስአካል በመንፈስ ላይ ያልተመሠረተ እንዲሁም መንፈስ በቁስአካል ላይ ያልተገነባ፣ በርሱም የማይወሰን አድርጎ የሚያቀርብ ንድፈ ሐሳብ ነው። ሁለታዊነት ቁስአካላዊ አንዳዊነትንም ሆነ ሐሳባዊ አንዳዊነትን ይቃወማል።

ሁለታዊነት የአንዳዊነት ተቃራኒ ፍልስፍና ነው። አንዳዊነት የማናቸውም ህልውና ያለው ነገር መሠረት ቁስአካል ወይም መንፈስ ነው ሲል ሁለታዊነት ግን ሁለቱም በእኩልነት መሠረቶች ናቸው ይላል። ይሁንና ይህ ፍልስፍና ቁስአካልና ሐሳብ በእኩል ደረጃ የዓለም መሠረቶች ናቸው ቢልም የኋላ ኋላ ሁለቱም በአንድ መለኮታዊ ኃይል እንደተፈጠሩ ስለሚናገር ሁለታዊነት በሐሳባዊ ፍልስፍና ውስጥ ይጠቃለላል።

(አንዳዊነትን፣ ካርቴዥያኒዝምን ይመለከቷል።)

## ሁለንታዊ
### (*Universal*)

ይህ ጽንሰ ሐሳብ የፍልስፍና ፈርጅ የሆነ፣ በግንዛቤ ዕድገት ሂደት ውስጥ የተከሰተና በዓለም ውስጥ ያሉት ነባራዊ ግንኙነቶች ማለትም ክስተቶች የሚመሳሰሉበትንና አንድ የሚሆኑበትን ባሕርይ የሚያመለክት ነው። ነገሮች ከሌሎች ነገሮች የሚለያቸውን ባሕርይ ሲይዙና በብቸኛነት ሲታዩ የግላዊነት ባሕርይ ይኖራቸዋል። ይሁንና እነዚህ ግላዊ ባሕርይ የሚታይባቸው ነገሮች የጋራ የሆኑ ባሕርያት ሊኖሩአቸው ይችላሉ። ይህም ግላዊው ነገር አጠቃላይ የሆኑ ባሕርያት ይይዛል ማለት ነው። አጠቃላይ ባሕርያትና ገጽታዎች አንዳንድ ጊዜ በተወሰኑ ነገሮች ላይ ሊያተኩሩ ስለሚችሉ ልዩ ባሕርይ ይይዛሉ። እነዚህ ባሕርያትና ገጽታዎች በማንኛውም ነገርና ክስተት ሁሉ ሲገኙ ሁለንታዊ ይሆናሉ።

እያንዳንዱ ሰው የራሱ የሆነ ችሎታ፣ ልማድ፣ ፍላጎት፣ ዝንባሌ፣ የአነጋገር ስልት ወዘተ... አለው። እነዚህ ግላዊ ባሕርያት እንዳሉት ሁሉ ሰው የአንድ መደብ አባል፣ የአንድ ሀገር ዜጋ ወዘተ... በመሆኑ ደግሞ ከሌሎች ጋር የሚዛመድባቸው ሁለንታዊ ባሕርያትም አሉት።

ግላዊ፣ ልዩና ሁለንታዊ ባሕርያት የማይነጣጠሉና እርስ በርስ የተያያዙ ናቸው። በመሀከላቸው ያለው ልዩነት ዲያሌክቲካዊና ተወራራሽ ነው። ይህም ማለት ማንኛውም ነገር ግላዊ በመሆኑ ሁለንታዊ ነው፤ ሁለንታዊ ደግሞ ከግላዊ ውጭ ስለማይኖር ግላዊና ሁለንታዊ ተወራራሽ ፈርጆች ናቸው።

(ፈርጆችን፣ አርቅቆትን ይመለከቷል።)

## ሁልአምላክነት
(*Pantheism*)

የእግዚአብሔርን ሰብአዊ ባሕርይ በመ
ካድ እግዚአብሔር ከተፈጥሮ ጋር አንድ
ነው የሚል የፍልስፍና አስተምህሮ ነው ።
ሁልአምላክነት ተፈጥሮ በንቁ አምላክ የተ
ፈጠረና ከአምላክም ውጭ የሚገኝ ነው
የሚለውን አመለካከት አይቀበልም ። እንደ
ሁልአምላክነት ተፈጥሮና አምላክ አይለያ
ዩም ፤ በሁለቱ መካከል ያለው ግንኙነት
የመንሥኤና የተገብሮት ግንኙነት አይደለም ።
የተፈጥሮ ኃይልና እንቅስቃሴ እንዲሁም ተፈ
ጥሮአዊ ነገሮች በሙሉ የሚገልጹት የአም
ላክን ኃይልና ምንነት ነው ። ይህ አመለካከት
የአምላክን ዲበተፈጥሮአዊ ባሕርይ የሚክድ
በመሆኑ ከሃይማኖት ተከታዮች ብዙ ተቃ
ውሞ ደርሶበታል ።

(ስፒኖዛን ፣ አምላከኛነትን ይመለከቷል ።)

## ሁሰርል ፣ ኤድመንድ
*(Husserl, Edmund)*

ከ1859 እስከ 1938 የኖረና ወቅቱም ሐሳ
ባዊ ፍልስፍና በከፍተኛ ቀውስ ውስጥ የተዘ
ፈቀበት በመሆኑ ሐሳባዊነትን ከቀውስ ለማው
ጣት የሥነ ክስተት ንድፈ ሐሳብ በመቀመር
በጀርመን ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሀገሮችም
በሐሳባዊነት ፍልስፍና ውስጥ ከፍተኛ ሚና
የተጫወተ ጀርመናዊ ሐሳባዊ ፈላስፋ ነው ።
ሁሰርል በጐይቲንቲንና በፍራይቡርግ ፕሮፌ
ሰር ሆኖ ሠርቷል ። ፍልስፍናው በአፍላጦ
ንና በላይብኒትዝ አስተሳሰቦች ላይ የተመሠረተ
ነው ። ፍልስፍናውም ሳይንሳዊ ጥራት እንዳለው
ሁሰርል ከመግለጹም በላይ "ንጹህ" ሥነ
አመክንዮ ለመፍጠር የሥነ አመክንዮ ፈርጆ
ችንና ሕግጋትን "በንጹህ " መልካቸው
መተርጐም ያስፈልጋል ይላል ።

በፍልስፍና አቋሙም ገለልተኛ ሆኖ
ለመቅረብ "ንጹህ ንቃተ ኅሊና" በማለት
ከኑባሬና ከግለሰቡ ንቃተ ኅሊና ነፃና የበላይ
ከሆነ ንቃተ ኅሊና ላይ ለመድረስ ሞክ
ሯል ። በእርሱ አባባል "ንጹህ" ማለት
ድንግል ፣ ቱባ ሲሆን ንጹህ ንቃተ ኅሊናም
አፍላጦን "ንጹህ ሐሳብ" ብሎ የጠራውን
ጽንሰ ሐሳብ ለመገንዘብ የሚያስችል ነው ።
ይሁንና ይህ "ንጹህ ሐሳብ" ፍች እንጂ
በራሱ ህልውና የለውም ይላል ።

በአጠቃላይ ሁሰርል የግንዛቤ ተገብሮ
ከግለሰቡ ንቃተ ኅሊና ውጭ ህልውና የለ
ውም ስለሚል ኅሊናዊ ሐሳባዊ ነበር ። እው
ነታ የሚታወቀው በጭልታ እማካይነት ነው
ማለቱም ዕውቀት በግለሰቡ ስሜት የሚወሰን
መሆኑን ይገልጻል ። ይህም ግላዊነት ለህል
ውናነት መከሰት ድጋፍ ሰጥቷል ።

(ሥነ አመክንዮን ፣ ክስተትን ፣ ህልውናነትን
ይመለከቷል ።)

## ሂንዱኢዝም
*(Hinduism)*

ከመካከለኛው ዘመን አጥቢያ ጀምሮ
እስከአለንበት ዘመን የህንድ ፍልስፍና ፣ ግብ
ረገብና ሃይማኖት የተመሠረቱበት የሐሳቦ
ችና የጽንሰ ሐሳቦች ሥርዓት ሂንዱኢዝም
ይባላል ። የሂንዱኢዝም አመለካከት ቪሽኑና
ሲቫ በተባሉት አምላኮች አምልኮት ላይ የተ
መሠረተ ሲሆን የህንዳውያንን አመለካከቶ
ችንና ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችንም የሚያጠ
ቃልል ነው ። ለሂንዱኢዝም መከሰት ምክ
ንያት የሆነው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ6ኛ
ውና በ4ኛው ምዕት ዓመት የነበረው የንጽ
ረተ ዓለም ቀውስ ነው ። የሂንዱኢዝም
የጽሑፍ ምንጮች በሳንስክሪት የተጻፉ
በጥንትና በመካከለኛው ዘመን የኖሩ የሀ
ንድ የሃይማኖት ፣ የፍልስፍናና የሥነ ጽሑፍ
ምሁራን ድርሰቶች ናቸው ።

አትማን— የግለሰብ ነፍስ ፣ ብራሐማን
—የዓለም ነፍስ የሂንዱኢዝም መሠረታዊ
ፈርጆች ናቸው ። እነዚህ ነፍሶች በነባራዊ
ነት ይኖራሉ ፤ ከቦታ ፣ ከጊዜና ከምክንያት
ሕግም ነፃ ናቸው ስለሚል አመለካከቱ በአ
ጠቃላይ የሚያንፀባርቀው የነባራዊ ሐሳብ
ዊነትን አቋም ነው ። የማንኛውም ሂደት
የመጨረሻ ዓላማ የአትማን ከተፈጥሮ መላ
ቀቅና ከብራሐማን ጋር መዋሃድ ነው ።
ነፍስ ከተፈጥሮ ጋር ያለው ግንኙነት የሚገ
ዛው በካርማ ሕግ ነው ። አትማን አካላዊ
ነገር ውስጥ ሲገባ መጥፎ ወይም ጥሩ የሆኑ
ተግባሮች ይፈጽማል ። የካርማ ሕግ የሚገ
ልጸው ነፍስ ክባዊ በሆነ መንገድ በማያቋ
ርጥ በመወለድና በመሞት ሂደት ውስጥ
መሆኑንና የመጪው የመወለድ ሁኔታ ፣ ለም

ላሌ ሰው ሀብታም ወይም ደሀ ሆኖ የሚወለደው በፊት ነፍሱ በፈጸማቸው ጥሩ ወይም መጥፎ ተግባሮች አንፃር በሽልማት ወይም በቅጣት መልክ የሚወሰን መሆኑን ነው ።

የሂንዱኢዝም ሐሳቦችና ጽንሰ ሐሳቦች የሚያንፀባርቋትና የሚያጠናክሩት የሀንድን የካስት ሥርዓት ነው ። ይህ ሥርዓት ማኅበራዊ መደቦች በተለይም የበታች መደቦች ከላዮቹ መደቦች ጋር እንዳይቀላቀሉ የሚከለክል ነው ። በመሆኑም ሂንዱኢዝም ሀብታምነትንና ድህነትን መለኮታዊ ሽልማት ወይም ቅጣት አድርጎ በማቅረብ የመደቦች ክፍፍል በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ያደርጋል ።

## ሂዩም ፡ ዴቪድ
## (*Hume, David*)

ከ1711 — 1776 የኖረ ፣ የዘመናዊ ጠርጣሪነት ፍልስፍና መሥራች በመሆን የታወቀ የእንግሊዝ ኅሊናዊ ሐሳባዊ ፈላስፋ ነው ። "ኤ ትሪቲዝ ኦቭ ሂዩማን ኔቸር" ፣ "አን ኢንኳይሪ ኮንሰርኒንግ ሂዩማን አንደርስታንዲንግ" ፣ "ፖለቲካል ዲስኮርስ" ፣ "ዲያሎግ ኦን ናቹራል ሪሊጅን" በሚባሉት ጽሑፎቹ ውስጥ የጠርጣሪነት መሠረታዊ ሐሳቦችን የቀመረና ያስፋፋ ከመሆኑም በላይ የፍልስፍናውን ጠቃሚነት በዝርዝር ለመግለጽ ሞክሯል ።

እንደ ሂዩም አባባል የማሰብና የመመራመር ችሎታ ትክክለኛውን አቅጣጫ ይዞ ጠቃሚ ሊሆን የሚችለው በመጀመሪያ ደረጃ የችሎታችንን ድንበር በትክክል ስናውቅ ነው ። በተለይም ከሰው ዓቅም በላይ የሆኑትን ረቂቅና ዲበአካላዊ ጥያቄዎች በመተው ግንዛቤያችን በተጨባጩ ላይ ብቻ እንዲወሰን ስናደርግ ነው ጠቃሚ የሆነ ዕውቀት ለማግኘት የምንችለው ። የዕውቀት ፋይዳ የሚለካው ለተግባር በሚሰጠው አገልግሎት እንጂ በረቂቅነቱ ወይም በውስጣዊ ጥልቀቱ አይደለም ። እንደ ሂዩም አባባል የሰው ልጅ ኃይሉም መሣሪያውም ስለሌለው ስለ ነባራዊ እውነታ ምንነት ሊያውቅ ከቶ አይችልም ። ለዚህም አባባሉ የሚያቀርባቸው ምክንያዊ መረጃዎች የሚከተሉት ናቸው ።

የዕውቀት መነሻ በሕዋሳት አማካይነት የምናገኛቸው ሕውስቶች ናቸው ። እነዚህ ሕውስቶች ነገሮች በኛ ላይ የሚፈጥሯቸው ኅሊናዊ ክስተቶች እንጂ ነገሮችን ይመስላሉ ማለት አይደለም ። አንደኛ ፣ ሕውስት በመሆናቸው በኛ ኅሊና ውስጥ ብቻ የሚኖሩ ስለሆኑ ፤ ሁለተኛ ፣ እኛም ከራሳችን ወጥተን ሕውስቶቻችን ከነገሮች ጋር መስማማታቸውን ማረጋገጥ የማንችል በመሆናችን የተመሳሳይነቱ ጉዳይ በኛ በኩል መልስ ሊያገኝ አይችልም ። በእዚህ ጉዳይ ላይ ትክክለኛው ፍልስፍናዊ አቋም ከኛ ውጭ ያለው ነገር ሐሳብም ይሁን ቁስአካል የማይታወቅ መሆኑን መግለጹ ነው ።

እንደ ሂዩም አባባል ሕውስታዎች እየቆዩ ሲሄዱ ደብዛዛና ቅርፃዊ እየሆኑ ወደ ረቂቅ ሐሳብ እንደሚለወጡ እናያለን ። በተጨማሪም የልምድን ድግግሞሽ እየተከተሉ ሐሳቦች እርስ በእርሳቸው ይተሳሰራሉ ። ሆኖም ይህ መተሳሰር ከልምድ የሚመነጭ እንጂ አንድ ሐሳብ ከሌላው ሐሳብ ጋር የሚተሳሰረው በሥነ አመክንዮአዊ መስተጋብር አንፃር አይደለም ። ለምሳሌ የመንሥኤንና የተገብሮትን ግንዛቤ እንውሰድ። ነባራዊ ሐሳባውያን እንደሚሉት ከሆነ አንድ ነገር መንሥኤ ነው ሌላው ተገብሮት ነው የምንለው በሁለቱ መካከል ያለውን የግዴታ ግንኙነት በማስተዋል ነው ። እንደሂዩም አባባል ነባራዊ ከሆነ ግዴታ ላይ ግንዛቤያችን ሊደርስ ከቶ አይችልም ። አንድን ኳስ በእግር ስንመታው ወደፊት ሲንቀሳቀስ እናያለን ። ይህ ከልምድ የምናውቀው እንጂ ከግዴታ የምንረዳው አይደለም ። ምክንያቱም ኳሱ ሲመታ ወደኋላ ወይም ወደግራ ወዘተ... የሚንቀሳቀስ ሊሆን ይችላል የሚለው አግራጭ አሁንም ይሰማናል ። ወደፊት መሄዱ ግዴታ ሆኖ ስለማይታየን ኳሱ ቢመታ ወደፊት ይሄዳል ብለን ስንበይን አነጋገራችን ከልምድ የተገኘ መሆኑን እንረዳለን ። ግዴታ ያለ የሚመስለን ከመደጋገም የተነሣ በልምድ የሐሳቦች መያያዝ ኃይለኛና ጠንካራ በመሆኑ ነው ። በአጠቃላይም ሕግ የምንለው ከልምድ የምናገኘውን የሐሳቦችን መቆላለፍ በመሆኑ የተፈጥሮ ሕግ ማለት ነባራዊ የተፈጥሮ ሕግ ማለት ሳይሆን የሐሳቦችን መያያዝ ማለታችን ነው ሲል ሂዩም ገልጿል ። ሆኖም ይህ የሐሳቦች መያያዝ ከነባራዊው እውነታ ጋር ስምምነት ከሌለው እንዴት ዕውቀት ለተግ

ባር ሊያገለግል ይችላል ለሚለው ጥያቄ ሂዩም ሲመልስ በዓለም ሥርዓትና በሐሳብ ሥርዓት መካከል ያለው መስማማት ከየት እንደሚመነጭ ለማወቅ አይቻልም በማለት ተናግሯል ። ሆኖም የሰው ልጅ መኖር ፣ መንቀሳቀስ ስላለበት ተፈጥሮ የእምነት ኃይል ሰጥታዋለች። በኅሊናችን ውስጥ ያለው የሐሳብ ሁኔታ የነባራዊው እውነታ ግልባጭ እየመሰሰን በሙሉ እምነት እንድንንቀሳቀስ የሚያደርገን ይህ ከልምድ የሚገኘው እምነት ነው ። ነገም ፀሐይ ትወጣለች ስንል ይህ እነጋገር ምክኑያዊ ሳይሆን ከልምድ የመጣ እምነት ነው ።

ሂዩም ሃይማኖትን ፣ ግብረገብን ፣ ውበትንና ኅብረተሰብን ሲያጠና ይህንኑ ጠርጣሪነት አንፀባርቋል ። ሃይማኖት የሚመነጨው ከምክኑያዊ ግንዛቤ ሳይሆን ከመፍራትና ተስፋ ከመሻት በመሆኑ የእግዚአብሔር መኖር አለመኖር በዕውቀት የሚደረስበት ሳይሆን የእምነት ጉዳይ ነው ሲል ተናግሯል። ሥነ ምግባርን በሚመለከትም የግብረገባዊ ፋይዳዎችን አንፃራዊነት በመጠቆም ጥሩ ፣ መጥፎ ፣ ውብ ፣ ጥፉ የተባሉትን የምናገኛቸው ከምክኑያዊ ግመዛዘን ሳይሆን እንደየጊዜው ፣ እንደየሁኔታው ስሜቶቻችንን በመከተል ነገር ግን ማኅበራዊ ይዘት እንዲኖራቸው ምክኑያዊ ትርፅ በመስጠት የምንደነግጋቸው ግላዊና ስሜታዊ አስተሳሰቦች ናቸው ሲል አንፀባርቋል ። በፖለቲካ መስከም አጥብቀን መዋጋት ያለብን ቀናናዊ አመለካከቶችን ነው ሲል ሂዩም ተናግሯል ። የማኅበራዊ ኑሮ ሥርዓትን አስመልክቶ በየጊዜው የሚሰነዘሩት ሐሳቦችና አንዱ ከሌላው ትክክለኛ ነው በማለት የሚነሡ ክርክሮች እስካሁን ከግጭትና ከረብሻ በስተቀር ያስገኙት ጠቃሚ ውጤት የለም ። መንግሥት የሚኖረው ትክክል በመሆኑ አይደለም ፤ ሥርዓት እንዲኖር አስፈላጊ በመሆኑ ብቻ ነው ። ተቀባይነትም የሚኖረው ለሁሉም የሚጠቅመውን ሥርዓት ሲያስከብር ነው ። ሥርዓትም ማለት ሁሉም በግላዊነቱ የሌላውን ግላዊነት ሳይነካ እንደልቡ መንቀሳቀስ መቻሉ ነው በማለት ሂዩም ነፃዊ አመለካከቱን ገልጿል ።

ሂዩም በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ የተጫወተው ሚና ከፍተኛ ቦታ ሊይዝ የቻለው የጠርጣሪነቱን አዝማሚያ እስከ መጨረሻ በማድረሱ ነው ። በተለይም መንፈሳዊ ጉዳዮችን ምንም ምክኑያዊ መሠረት የሌላቸውም ማለቱና ከእምነት ብቻ የሚመነጩ አድርጎ ማቅረቡ ሐሳባውያንን ሳያስደነግጥ አልቀረም ነበር ። ዲበአካላዊ የሆኑ ጉዳዮችን ወደ ጎን በመተው ለተግባር ጠቃሚ የሆነ ዕውቀት መሻት አለብን ብሎ መናገሩ በፍልስፍና ውስጥ ሰፍኖ የነበረውን የአውጠንጣኝነት አዝማሚያ እንዲዋጋ አድርጎታል ። ሆኖም የሂዩም ጠርጣሪነት ሐሳባውያንን ቢያስደነግጥም ጨርሶም ተስፋ የሚያስቆርጣቸው አልነበረም ። እንዲያውም የነባራዊው እውነታ ግንዛቤ ሊኖረን አይችልም በማለት ዕውቀትን ከእምነት ላይ በማሳረፍ ሳይንሳዊነቱን መካዱ ሂዩም ለሐሳባውያን በቀጥታ ወገናዊ መሆኑን ያሳያል ። ጠርጣሪነት ምንንም ከምን ሳይለይ ሁሉንም አብሬ እደመሰሳለሁ ብሎ መነሣቱ የሚጠቅመው ሐሳባዊነትን ነው ። ምክንያቱም በመጨረሻ ሁሉን ነገር የሚተወው ለእምነት በመሆኑ ፣ እምነት ደግሞ ለሐሳባውያን ሁሌም አገልጋይ በመሆኑ ፣ አመለካከቱ የሚጠቅመው እነሱኑ ነው ። የሂዩም ጠርጣሪነትም ዝም ብሎ የፈለቀ አይደለም ፤ የሥነ ምግባርና የፖለቲካ አመለካከቱን ስናይ የሚያንፀባርቀው ነፃዊነትን ነውና ። የግላዊ ጥቅም የበላይነትን መሻት ፣ ማኅበራዊ ሥርዓት ለዚህ ጥቅም አስከባሪ እንዲሆን ማድረግ ለካፒታሊስት ሥርዓት የሚጠቅም አመለካከት መሆኑ ግልጽ ነው ። ቀናና አያስፈልግም በማለት የሐሳብ ግጭቶችን ማጥላላት ሥር ነቀል የሆነ የለውጥ አቅጣጫ እንዳይቀየስና የኅብረተሰቡ ለውጥ ከጥገና እንዳያልፍ መደንገግ ነው ።

(ዳሳሽነትን ፣ ጠርጣሪነትን ይመለከቷል ።)

## ሂደት
(*Process*)

ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ ፣ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ፣ ከቀላል ወደ ውስብስብ በመሸጋገር ፣ በማደግ ወይም በመለወጥ ላይ የሚገኝ የማንኛውም ነገር ክንዋኔ ነው ። ለምሳሌ ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም የሚደረገው ሽግግር የኅብረተሰቡ ዕድገት ታሪክ ሂደት ነው ።

(ቅስቃሴን ፣ ዕድገትን ይመለከቷል ።)

## ሃይማኖት
(*Religion*)

ሃይማኖት ዓለምን በማናቸውም ረገድ ለመምራትና ለመተንተን የሚያልም፣ ተፈጥሮ ከሷ በላይ በሆነ መለኮታዊ ኃይል የምትገዛና የምትመራ ናት በሚል ቀኖና ላይ የተመሠረተ ኢሳይንሳዊ አመለካከት ነው። በቀኖናዎች ላይ የተመሠረተ በመሆኑም እምነቱን ለማይከተሉ ዘለቄታቸው የከፋ የሚሆን አስመስሎ በማቅረብና በመለኮታዊ ኃይል በማስፈራራት ሰዎች በጭፍን እንዲያምኑ በማድረግ ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ የሚጥር የሳይንሳዊ ዕውቀት ፍጹም ተፃራሪ የሆነ አመለካከት ነው። ሰዎች ስለራሳቸውና ስለአካባቢያቸው ምንነት በጣም ዝቅተኛ ዕውቀት በነበራቸው ጊዜ የመታመማቸውና የመሞታቸው ምክንያት ምን እንደሆነ ባለመረዳት ሁኔታዎችን የሚቆጣጠርና የሚገዛ አንድ ኃይል እንዳለ አድርገው ያመልኩ ነበር። የመሬት መንቀጥቀጥን፣ የሰደድ እሳትን፣ የጐርፍን፣ የመብረቅን ምንነት ካለመረዳታቸው የተነሣ አለ የሚሉትን ኃይል ይማፀኑ ነበር። በአጭሩ የተፈጥሮ ክስተቶች ኃያልነት፣ የሰውም በተፈጥሮ ኃይል ሥር መውደቅ፣ ስለነርሱም በቂ ዕውቀት ማጣት የአምልኮ መሠረት ነው። ኅብረተሰብ ወደተሻለና ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ሽግግር ባደረገ መጠን ሃይማኖትም የተለያዩ መልኮችን እየያዘ መጥቷል።

ኅብረተሰብ በመደብ ከመከፋፈሉ በፊት ማለትም በጥንታዊ ጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የነበሩት የአምልኮ ዓይነቶች ነፍሳዊነትና ሥነ ተረት ተብለው የሚጠሩት ነበሩ። በዚህ ወቅት የሰው ልጅ በመሥራት ኃይሉ አማካይነት እራሱን ከተፈጥሮ መለየት የቻለ ቢሆንም በተፈጥሮ ላይ ግን ገና ቁጥጥር ለማድረግ አልቻለም ነበር። ስለሆነም ሰዎች ስለራሳቸው ሆነ ስለተፈጥሮ የነበራቸው ዕውቀት እጅግ ዝቅተኛ ነበር። ግዑዝ ነገሮችን ሁሉ ሕይወትና እእምሮ ያላቸው አድርገው በመገመት ለሚገጥሟቸው የተለያዩ ችግሮችና ጉዳዮች የተለያዩ ጣዖቶችን እየሠሩና ንግርት ወይም ተረት እየፈጠሩላቸው መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ይመሩ ነበር። በዚህም መሠረት ለውሃ ሙላት፣ ለጦርነት፣ ለሰላም፣ ለፍትህ ወዘተ... የተለያዩ ጣዖቶችና ንግርት ነበሯቸው። ባጭሩ በዚህ ዝቅተኛ የኅብረተሰብ ዕድገት ደረጃ የኅብረተሰቡ ሕይወት ልዩ ልዩ ገጽታዎች የሚመሩት በአምልኮ ጣዖት ነበር።

ከረጅም ጊዜ በኋላ ግን የሰው ልጅ በተለያየ አቅጣጫ በተፈጥሮ ላይ ቁጥጥሩን እያሳደገና እያሰፋ በመምጣት ለልዩ ልዩ የአምልኮ ጣዖቶች ተሰጥተው የነበሩት ችሎታዎች በአንድነት ሆነው በአንድ ረቂቅ ጣዖት ወይም አምላክ (ፈጣሪ፣ እግዚአብሔር፣ አላህ፣ አንድ ኃይል ወዘተ...) በአዲስ የሃይማኖት አስተምህሮ ላይ በመመሥረት ተጠቃልለዋል። በዚህም መሠረት በሁሉም ረገድ ፍጹም በሆነ ማለትም የፍጹም ዓዋቂነት፣ የፍጹም ሚዛናዊነት፣ የፍጹም ደግነት ወዘተ... ችሎታ ባለው አንድ ረቂቅ ኃይል እምነት ላይ የተመሠረቱ ሃይማኖቶች ተቀነባበሩ። ባለ አንድ አምላክ ሃይማኖቶች ከአምልኮ ጣዖቶች (ሥነ ተረት) እምነት በዕድገት ሂደት የመነጩ ይሁኑ እንጂ ኅብረተሰቡ በመደብ ከመከፋፈሉ የተነሣ በማኅበራዊ ሚናቸው አንፃር ከቀድሞው የተለየ ግልጋሎት አላቸው። በመደብ ኅብረተሰብ ውስጥ ሰው ቁጥጥሩን በተፈጥሮ ላይ ከበፊቱ በበለጠ ስለአሳደገ የሃይማኖት ዋንኛው ምንጭ እንደቀድሞው ተፈጥሮአዊ ሳይሆን ማኅበራዊ ሊሆን ችሏል።

በሰዎች ላይ የሚደርሰው ጭቆናና ብዝበዛ፣ እርዛትና ስቃይ እየከፋ ሲሄድ ችግሮች እንደ "የአርባ ቀን ዕድል" ይተረጐማሉ። ሰዎች በማኅበራዊ ሕይወታቸው ውስጥ የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች "በወዲያኛው ዓለም" እንደሚያገኙአቸው አድርገው ይገምታሉ። ገነትንም በወተት፣ በማርና በማናቸውም በዚህ ዓለም ባላገኙአቸው ጥሩ ነገሮች አንደተሞላች አድርገው በዓይነ ኅሊናቸው በመመልከት በተስፋ ይኖራሉ። በዚህ ኅብረተሰብ ውስጥ ሃይማኖት ሰው በላዩ ላይ የተጫኑበትን ማኅበራዊ ኃይሎች በተለይም የብዝበዛ ግንኙነቶችን የሚያንፀባርቅበትና የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ዝቅተኛ የንቃተ ኅሊና ደረጃ የሚገለጽበት ነው። ሃይማኖት ገዥ መደቦች የሚጠቅማቸውን ሥርዓት ለማቆ

የትና ለማጠናከር ዋነኛ የርዕዮተዓለም መሣሪያም በመሆን ሰፊውን ሕዝብ አደንዝዘውና አደንቁረው ለመግዛት እንዲቻላቸው ለማድረግ ያገለግላል ። በተለይም በኢምፔሪያሊዝም የዕድገት ደረጃ ላይ ብዝበዛን ለማስንበት ሲባል በጣም የረቀቁና አወናባጅ ፣ አደንዛዥና አዘናጊ የሆኑ በርካታ የሃይማኖት መስኮች እየተፈጠሩ በተለያዩ መንገዶች እንዲስራጩ ይደረጋል ።

ፍልስፍናዊ ሐሳባዊነት ለማስተማር እንደሞከረው ሃይማኖት የአንድ ዘላለማዊ መለኮታዊ ኃይል ነፀብራቅ በመሆን የተከሰተ ሳይሆን የተለየ የማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና መልክ ነው ።

ሃይማኖት ዝንተዓለም የነበረና ዝንተዓለምም የሚኖር አይደለም ። የሰው ልጅ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕድገትን እያፋጠነና እያዳበረ በተፈጥሮ ላይ ቁጥጥሩን እያጠናከረ ሲሄድ የሃይማኖት ማኅበራዊ መሠረት የሆኑት ጭቆናና ብዝበዛ ከነርሱም ጋር በዝባዥ መደቦች ሲጠፉ ሃይማኖትም አብሮ ይከስማል ። ይህ እውን ሊሆን የሚችለው ደግሞ በኮሚኒስት ኅብረተሰብ ግንባታ ሂደት ውስጥ ብቻ ነው ። ስለሆነም ከሶሻሊስት አብዮት ድል በኋላ ሃይማኖት ቀስ በቀስ በኅብረተሰብ መንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ ያለውን ተፅዕኖ እያጣ ይሄዳል። ይሁንና የሃይማኖት መጥፋት ወይም መደምሰስ ቅጽበታዊ ሂደት አይደለም ። ይህ ተግባር ማለትም ሰፊውን ሕዝብ በኢአማኒነት መንፈስ የማነጹ ተግባር ሰፊ የሳይንስን ዕውቀት ፣ የማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተዓለም ትምህርትንና ፕሮፓጋንዳን ባልተቋረጠ ሁኔታ አጠናክሮ ማካሄድን ይጠይቃል ።

(ነፍሳዊነትን ፣ ኢአማኒነትን ፣ ሥነ ተረትን ፣ ሥነ መለኮትን ይመለከቷል ።)

## ሄልቬትዩስ ፣ ክሎድ አድርየን

(*Helvétius Claude Adrien*)

ከ1715—1771 የኖረ ዕውቅ የፈረንሳይ ቁስአካላዊ ፈላስፋ ነው ። ከታወቁት ጽሑፎቹ መሀከል "ደ ሌስፕሪ" (1758) እና "ደ ሎም" (1773) ይገኙበታል ። ሄልቬትዮስ የሎክን ሕውስታዊነት ከሐሳባዊ ይዘቱ በማላቀቅ የራሱ ፍልስፍና መሠረት አድርጐ ተጠቅሞበታል ። እንደሱ አስተሳሰብ በነባራዊነት የሚኖረውን ቁስአካል የምንገነዘበው በሕዋሳት አማካይነት ነው ። ትውስታ ዘላቂነት ያለው ፣ ነገር ግን ደከም ያለ ሕውስታ ሲሆን የማንዛቤም አንዱ መሣሪያ ነው በማለት ገልጾታል ። በሄልቬትዮስ አመለካከት ሐሳብ ራሱ የሕውስታዎች ጥምረት ውጤት ነው ።

ሄልቬትዮስ ማኅበራዊ አካባቢ የሰዎችን ባሕርይ (ጠባይ) ለመለወጥ (ለማሳደግ) ከፍተኛ ሚና እንዳለው ያምናል ። የካፒታሊስቱ ግንኙነት የፊውዳሉን ግንኙነት መተካት እንዳለበት ቢቀበልም የሰዎች ንቃተ ኅሊናና ጠንካራ ስሜቶች የማኅበራዊ ዕድገቶች አንቀሳቃሽ ኃይሎች ናቸው የሚል እምነት ነበረው ።

ሄልቬትዮስ አካባቢ የሰውን ጠባይ ለመግራት ወሳኝ ኃይል ስለመሆኑ ፣ በግለሰብና በማኅበረሰብ ፍላጐቶች መካከል ሊኖር ስለሚችለው መጣጣምና እንዲሁም የሰው የማሰብ ችሎታ በተፈጥሮ እኩል ስለመሆኑ አስመልክቶ በሰነዘራቸው ሐሳቦች ለተምኔታዊ ሶሻሊዝም መንገድ ጠርጓል ። ሆኖም ስለሐሳብና ስለሰው የነበረው ግንዛቤ ሙርቃ ነበር ።

(ሕውስታዊነትን ይመለከቷል ።)

## ሄራቅሊጦስ (የኤፌሶኑ)

(*Heraclitus of Ephesus*)

ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ544—483 የኖረ ጥንታዊ የግሪክ ቁስአካላዊና ዲያሌክቲካዊ ፈላስፋ ነው ።

በሄራቅሊጦስ አመለካከት በዓለም የመጀመሪያው ነገር ወይም የዓለም ምንጭ እሳት ነው ፤ እሳት በማንም የተፈጠረ አይደለም ፤ የነበረና ሁልጊዜም የሚኖር ነው ። ዓለም በእንቅስቃሴና በማያቋርጥ ሂደት ላይ ትገኛለች ፤ ነገሮች ወደ ተቃራኒያቸው ይለዋወጣሉ ፤ ትግል የሁሉም ነገር መገኛ ነው ። ሁሉም ነገር የሚመነጨው ከቅራኔ ሕግ ነው ፤ ቅራኔ አውዳሚ ሳይሆን ነገሮች ባሕርይ እንዲኖራቸው ያደርጋል ፤ ለምሳሌ ላይ ታች ፣ ሙቀት ቅዝቃዜ ፣ ቀን ሌሊት ፣ ሕይወትም ሞት ነው ። ምክንያቱም አንዱ ወደ ሌላ ይለወጣልና ።

የዕውቀት መነሻ ሕዋሳት ናቸው ፤ በማሰብ የማይታወቅ ነገር የለም ፤ ምክንያቱም

የሁሉም ነገር ምንጭና ምንነት የሚገለጸው በተቃራኒ አንድነትና ትግል ሕግ ነው፤ ስለዚህም ዓለም ሙሉ በሙሉ ልትታወቅ ትችላለች የሚልም የዕውቀት ንድፈ ሐሳብ አለው ።

ሄራክሊጦስ የመደብ ምንጩ ከመኳንንቱ ቢሆንም ተራማጅ አመለካከት ነበረው፤ የመኳንንቱን ያልተጻፈ ልማዳዊ ሕግ በደንብ በተደነገገ የመንግሥት ሕግ መለወጥ ያስፈልጋል የሚል አቋም ነበረው ።

ሄራክሊጦስ የዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነትን መሠረተ ሐሳብ በግርድፉና በእንጭጩ የጨበጠ መሆኑን ሌኒን ገልጾአል ። በእርግጥም የተቃራኒዎችን አንድነት ፍጹማዊ አድርጎ መመልከቱ የዕድገትን ሕግጋት ሊረዳ አላስቻለውም ነበር ፤ በተለይም ቅራኔዎች አድገው ለአዲስ ክስተት መንሥኤ መሆናቸውን ባለመገንዘቡ ቅራኔዎች በዑደት ላይ ብቻ እንዳሉ አድርጎ በመመልከት የአዲስ ነገሮችን መፈጠር ሊያጤን አልቻለም ።

(የዲያሌክቲክስ ሕግን ይመለከቷል ።)

## ሄግሊያኒዝም
## (*Hegelianism*)

በሄግል የተቀመረው ነባራዊ ሐሳባዊ ዲያሌክቲክስ ሄግሊያኒዝም ይባላል ። ይህ ፍልስፍና በይዘቱም ሆነ በቅርፁ የተሟላ ከመሆኑም በላይ ሐሳባዊ ፍልስፍናን አጠቃሎ የመጨረሻ መልኩንና ወሰኑን የሰጠው በመሆኑ በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ ታላቅ ቦታ የያዘ ነው ።

የሄግሊያኒዝም መነሻውና መድረሻው ሐሳብ ነው ። ሐሳብ ከተፈጥሮ ተለይቶ መታየት እንዳለበትና የራሱ ህልውናና ሕግጋት እንዳሉት ሄግሊያኒዝም ያምናል ። በዚህ ፍልስፍና መሠረት የሐሳብ ዋናው ፍላጎት የራሱን ምንነትና የራሱን የተሟላ ንቃተ ኅሊና ማግኘት ነው ። ዕውቀት ደግሞ የዐዋቂና የታዋቂን ግንኙነት ስለሚጠይቅ ሐሳብ እራሱን ለማወቅ ሲል ወደ ተቃራኒው ማለትም ወደ ተፈጥሮ ይቀየራል ። ሆኖም በተፈጥሮ ውስጥ ታስሮ አይቀርም ። ዘዴው ተፈጥሮን እንደ መሰናክል በመጠቀም ባሸናፊነት ለመውጣት በመሆኑ የሚያደርገው ትግል ያለውን ውስጣዊ ችሎታና ፋይዳ ትንጅት ባለው መንገድ እንዲገለጽ ያደርገዋል ። ስለራሱ ምንነት ክፍጹማዊ ዕውቀት ላይ ይደርሳል ። ተፈጥሮ ባለው የተሳሰረ መዋቅርና የስፋት ጠባይ ሐሳብን ከጭፍን ረቂቅነት ወደ ዓይነት ይለውጣል ፤ ከዚያም ቅራኔውን በሽረት ሽረት ሕግ በመፍታት ሐሳብ በአሸናፊነት ወደ ራሱ አንድነት ይመለሳል ። ሐሳብ በአሸናፊነት ሲወጣ የሚከሰተው ወይም የሚኖረው በመጀመሪያ ደረጃ በፍልስፍና ከዚያም በመንግሥት ውስጥ ሲሆን እንዲሁም ባልተሟላ ሁኔታ በውበትና በሃይማኖት ውስጥ ይንፀባረቃል ። በሄግሊያኒዝም አመለካከት የፍልስፍናና የመንግሥት ታሪክ የሐሳብ እንቅስቃሴና የበላይነት አመጣጥ ታሪክ ነው ።

እንደ ምሳሌ መንግሥትን እንውሰድ ። ተፈጥሮን ለመቆጣጠር ግለሰቦች የሚያደርጉት ትግል በነሱ ውስጥ ቶክክር ስለሚፈጥር ኅብረተሰቡ በገዥና በተገዥ ይከፋፈላል ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የአንዱ ነፃነት የሚመሠረተው የሌላውን ነፃነት በመግፈፍ ነው ። ይህ ቅራኔ ሊፈታ የሚችለው መንግሥት በበላይነት ኅብረተሰቡን ሲመራ ነው ። መንግሥት ከግለሰቦች በላይ የሆነ ሁለንታዊ አቋም ያለው የኅብረተሰቡ የበላይ ዳኛና አስተዳዳሪ ነው ። በመሆኑም መንግሥት በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች በማለፍ በካፒታሊስቱ ዲሞክራሲ አሠራር ውስጥ እውነተኛ መልኩን ያገኛል ። ይህ የሚገልጸው በመዋቅሩና በአሠራሩ መንግሥት የነፃነት ጽንሰ ሐሳብ ነባራዊ እውነታ መሆኑን ነው ። ነፃነት ረቂቅ ፍላጐት መሆኑ ቀርቶ በሕግ ተደንግጐና በተደራጀ ኃይል ላይ ተመሥርቶ መከሰቱ የራሱን ዕውቀትና ህልውና እንዳገኘ የሚያስረዳን ይሆናል ። ተፈጥሮ ያስከተለውን ግጭት በበላይነት የሚዳኝ ኃይል መገኘቱ ሐሳብ በአሸናፊነት የራሱን ሥርዓት ሊመሠርት መቻሉን ያስረዳል ይላል ።

በሄግሊያኒዝም አባባል ታሪክ የምንለው የሰውን ልጅ ታሪክ ሳይሆን የሐሳብ ታሪክ መሆኑ ግልጽ ነው ። የሰው እንቅስቃሴና ማኅበራዊ ኑሮ የሚገልጹት የሐሳብን ፍላጐትና ሂደት ነው ። በተፈጥሮና በሰው እንዲሁም በሰዎች መሀል ያለው ቅራኔና ትግል ከመደብ ክፍፍል የሚመጣ ሳይሆን ሐሳብ እራሱን ለማወቅ የሚፈጥረው ውስጣዊ ቅራኔ ነው ። ሰው መሣሪያ እንጂ የራሱ ባለቤት ሆኖ የራሱን ፍላጐት የሚያስፈጽም አይደለም ። ይህ የሐሳባዊ ፍልስፍና መጨረሻ አቋም መሆኑ

ግልጽ ነው ። ምክንያቱም ሐሳብ ወይም እግዚአብሔር በሌላ ዓለም የማይኖርና በአሸናፊነትና በበላይነት የፈጠረውን ዓለም ለመግዛት የሚፈልግ ከሆነ የሰውን ልጅ የሱ ዕድገት መሣሪያ ማድረጉ የማይቀር ነው ።

ማርክስ እንዳለው የሄግል ትልቁ አስተዋጽኦ የዲያሌክቲክስ አመለካከትንና ሕጐችን ግልጸትና ቅንጅት ባለው መልክ ማስቀመጡ ነው ። ትልቁ ድክመቱ በሐሳባዊነት ላይ በመመሥረቱ ዲያሌክቲክሱ የቆመው በእግሩ ሳይሆን በጭንቅላቱ መሆኑ ነው ። ዲያሌክቲክስ የሐሳብ እንቅስቃሴ ብቻ ሆኖ በመተርጐሙ በእርግጥም በጭንቅላቱ እንዲቆም ተገዷል ። እንደ ሄግሊያኒዝም ቅራኔና ትግል ቁሳዊ ይዘትና ፍች የላቸውም ፤ የሚገልጹት የሐሳብ ግጭቶችን ሲሆን ምንጫቸውም እራሱ ሐሳብ ነው ። ሐሳብ እራሱን የማወቅ ዓላማ ብቻ ያለውና ከተጨባጩ የተለየ ረቂቅ በመሆኑ የዲያሌክቲክስ ዕውቀትም ከተጨባጩ ውጭ መሆኑ አልቀረም ። ነገሮችን ረቂቅ በሆነ አመለካከት ይነካቸዋል እንጂ ተጨባጭነታቸውን ሊገነዘብና ዋጋ ሊሰጣቸው አይችልም ። የሰው ልጅ ተጨባጭ ሁኔታ ከሐሳብ ጥያቄና ፍላጐት ውጭ በመሆኑ ነው የወዛደሩን መደብ ሁኔታ ወደ ጐን በመተው ለሄግሊያኒዝም የካፒታሊስት ሥርዓት መከሰት የታሪክ መጨረሻ የመሰለው ። በሌላ አነጋገር ሐሳብ እራሱን እንደ ነባራዊ እውነታ በመውሰዱ እራሱን ለማወቅ የሚያደርገው ጥረት ዕውቀትን ከተጨባጩ ይሰየዋል ፤ ነባራዊነትና ተግባራዊነትም ያሳጣዋል ።

በወዛደሩ መበዝበዝና መጨቆን የካፒታሊዝም አስከፊ ሁኔታ በይፋ እየታየ ሄግሊያኒዝም ሐሳብ እራሱን ዐወቀ ፤ ታሪክ አበቃ ብሎ መናገሩ የሚያስረዳን ከተጨባጩ የራቀ መሆኑን ብቻ ሳይሆን የፍልስፍናውን ቀጥተኛ የመደብ አቋም ነው ። ምክንያቱም የሐሳብ የበላይነት የሚከሰተው በካፒታሊስት አገዛዝ ከሆነ ሐሳብ የተባለው የሚያመለክተው የገዥውን መደብ ጥቅምና የበላይነት ፍላጐት መሆኑ ግልጽ ነው ። የሐሳብ የበላይነት የብዝበዛን ሥርዓት ማረጋገጥና ሕጋዊ ማድረግ እንደሆነ የሄግሊያኒዝም አቋም በቀጥታ ያስረዳል ።

ሄግሊያኒዝም በዲያሌክቲክስ አስተሳሰብ መጠቀሙ በአንድ በኩል ተራማጅ አመለካከት ሊሰጠው ሲችል ዲያሌክቲክሱ በሐሳብ የበላይነት ላይ መመሥረቱ ፍልስፍናውን የተዛባ አድርጐታል ። ይህ ሁኔታ የፍልስፍናው ተከታይ ወይም አስተካካይ ነኝ ብለው ለተነሡ ፈላስፎች በሁለት መከፈል ምክንያት ሆኗል ። የቀኝና የግራ ሄግሊያኒዝም ተብሎ የፍልስፍናው መከፈል የሚያስረዳን ሄግሊያኒዝም የማይጣጣሙ አዝማሚያዎች እንደነበሩት ነው ።

ሆኖም ሄግሊያኒዝም ያስገኘውን የዲያሌክቲክስ አመለካከት አርሞና አስተካክሎ በትክክል ሊጠቀምበት የቻለው ማርክስ ነው። የሐሳብ የበላይነትና ፋይዳ የተመሠረቱት በወዛደሩ የሥራ ኃይል ብዝበዛ ላይ መሆኑን ማርክስ በመረዳቱም የሠራተኛው መደብ ማለትም የሀብቱ አምራች በበላይነት የመንግሥት ሥልጣን እንደሚገባውና ታሪካዊ ተልዕኮውም መደብ አልባ የሆነ ኅብረተሰብ መመሥረት መሆኑን የሚያስረዳ የቁስአካላዊ ዲያሌክቲክስን ንድፈ ሐሳብ ለመቅረፅ ችሏል።

(ሐሳባዊነትን ፣ ሄግልን ፣ ፍጹማዊ ሐሳብን ፣ ሐሳባዊ ዲያሌክቲክስን ይመለከቷል ።)

## ሄግል ፣ ጊዮርግ ቪልሄልም ፍሪድሪሽ

(*Hegel*, *Georg Wilhelm Friedrich*)

ከ1770 እስከ 1831 የኖረ ፣ ከታላላቆቹ የጀርመን ብሉይ ፈላስፎች መካከል ጐልቶ የሚታይና በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ የሐሳባዊ ዲያሌክቲክስን መሠረታዊ ሐሳብ የቀመረ ነባራዊ ሐሳባዊ ፈላስፋ ነው ። የሄግል ፍልስፍና መሠረታዊ ሐሳብ ከሰዎች ኅሊና ውጭ በነባራዊነት የሚገኝ "ፍጹማዊ ሐሳብ" የሚባል የዓለም መሠረትና ፈጣሪ የሆነ ነገር አለ የሚል ሲሆን ዕድገቱም ዲያሌክቲካዊ ነው በሚል ሐሳብ ላይ የተገነባ ነው ። ከሄግል ዐበይት ሥራዎች ውስጥ "ፌኖሚኖሎጂ ኦቭ ዘ ማይንድ" "ዘ ሳይንስ ኦቭ ሎጂክ" ፣ "ዘ ሂስትሪ ኦቭ ፊሎሶፊ" እና "ዘ ፊሎሶፊ ኦቭ ራይት" የተባሉት ይገኙበታል።

(ሄግሊያኒዝምን ይመለከቷል ።)

## ህልውናነት

(*Existentialism*)

በ20ኛው ምዕት ዓመት በተለይ በአውሮፓ የተስፋፋ ሐሳባዊ ፍልስፍና ነው ። የሰው ህልውና ከተፈጥሮአዊ ክስተቶች

ውጭ የሆነ የራሱ የተለየ እውነታ ያለውና ሆኖም የተነጣ ልዩ ግንዛቤ የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑን ለማሳመን የሚጥር ፍልስፍና ነው ።

ፍልስፍናው ሐሳባዊነትንና ቁስአካልነትን የሚቃወም እንደሆነ ይናገራል ። የሚያምነው የክርክር ነጥብም እንደሚከተለው ነው ። በሀልውናነት አባባል በቁስአካላዊም ሆነ በሐሳባዊ ፍልስፍና የሰው ልጅ ኑሮ ምንነት የሚወሰነው ከሱ ውጭ በሆኑ ምክንያቶች ነው ። ሀልውናን እንደማንኛውም ቁጥርአዊ ክስተት በመቁጠር ከሱ ውጭ በሆነ እውነታ የሚገዛና የሚገለጽ መሆኑን ሁለቱ ተቀናቃኝ ፍልስፍናዎች ታምናበታል ። ለሐሳባዊ ፍልስፍና ወሳኙ ኃይል ሐሳብ ሲሆን ለቁስአካልነትም ቁስአካል መሆኑ ይታወቃል ። እነዚህ አመለካከቶች በምክንያቱ ላይ ቢለያዩም ሀልውናን ውጤትና መድረሻ እንጂ መነሻ አድርገው አለመቀበላቸው ገሀድ ነው ። ሀልውናን ሕይወት በሌለው ምክንያት በመወሰናቸው ስለ ሰው ምንነት ከተሳሳተ አመለካከት ላይ እንዲደርሱ ተገደዋል ።

እንደሀልውናነት አባባል የሰውን ሕይወት ከተፈጥሮ የሚለየው ዋናው ቁም ነገር በግዴታ ሕግ ያልመገዛቱ ጉዳይ ነው ። ማንኛውም ክስተት በግዴታ የሚገዛ ሲሆን ሰውን ግን የንቃተ ኅሊናው መኖር ከግዴታ ግዛት ውጭ ስለሚያደርገው የሰው ህልውና የሚገለጠው በምርጫ ችሎታ ሆኖ እናገኘዋለን ። አንድን ነገር ጥሩ ወይም መጥፎ ፣ እውነት ወይም ሀሰት የሚያደርገው ህልውና ነው ። በግዴታ ጥሩ ወይም መጥፎ የሆነ ነገር የለም ፤ እነዚህን ፍችዎች ለመስጠት የሚችለው የምርጫ ችሎታ ወይም ህልውናዊ ምክንያት ብቻ ነው ። በመሆኑም ህልውና ከሱ ውጭ በሆነ ምክንያት ሊገለጽ አይችልም ። ህልውናነት እራሱን የቻለ ራሱን በራሱ ብቻ ሊያስረዳ የሚችል የተለየ እውነታ ነው ።

ህልውናነት ሁለት አመለካከቶችን አጣምሮ የያዘ ነው ፤ እነሱም ሃይማኖታዊ ህልውናነትና ኢእምነታዊ ህልውናነት ናቸው ። የመጀመሪያዉ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ሙሉ ነፃነት ሰጥቶታል የሚል ሲሆን ፣ ሁለተኛዉ እግዚአብሔር ባለመኖሩ ሰው ለሚሠራው ሁሉ ብቸኛ ተጠያቂ ነው ይላል ።

ህልውናነት ከሐሳባዊነትና ከቁስአካልነት ባሻገር እንደ ሦስተኛ አማራጭ የሚቀርብ ፍልስፍና ነው ። ነገር ግን የሀልውናነት መነሻ የሰው ኅሊናዊ ባሕርይ በመሆኑና ይህም ንቃተ ኅሊና የራሱ ህልውና ኖሮት የሰውን ልጅ ኑሮ የሚመራ ተደርጐ በመታሰቡ ፍልስፍናው ከሐሳባዊነት የተለየ አመለካከት እንደሌለው እንረዳለን ። በእርግጥ ሰው የመምረጥ ችሎታ አለው ፤ ሆኖም በነባራዊ ሕግጋት ግዴታ ደግሞ የሚገዛ መሆኑም ሊካድ አይችልም ። አንድን ሰው ቡርዧ ወይም ወዛደር የሚያደርገው የግለሰቡ ምርጫ አይደለም ። ሰውን በመደብ የሚከፋፍለው ከሱ ፍላጐት ውጭ የሆነው የምርት ግንኙነት ሁኔታ ነው ። በመሆኑም ህልውና ከተጨባጩ ተገንጥሎ ሊታሰብ አይችልም ።

በሌላ በኩል የሰው የምርጫ ችሎታ ጠቃሚ ወይም ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ባለው ቁሳዊ ኃይል ላይ የተመሠረተ ሲሆን ነው ። ሰው ነፃ ነው ወይንስ አይደለም የሚለው ጥያቄ ከተጨባጩ ውጭ ሊቀርብ አይችልም ። ሰው በምን ግዴታ እንደሚገዛ ካወቀ ነው በዕውቀቱና ባለው ቁሳዊ ኃይል ግዴታውን ተቆጣጥሮ ለፍላጐቱ ምቹ የሚያደርገው ። ግዴታ ከሌለ የነፃነት ጥያቄ ሊነሣ አይችልም ፤ ምክንያቱም ካለግዴታ መብት ትርጉም የለውምና ። የሁለቱ ዲያሌክቲካዊ ቅራኔ የሚፈታው በታሪካዊ ሂደት ይሆናል ማለት ነው ።

የሀልውናነት ዋና ድክመት ሀልውናን ምሥጢራዊ ወይም ከሳይንሳዊ ዕውቀት ውጭ የማድረጉ ሁኔታ ነው ። ሀልውናን በሳይንሳዊ ግንዛቤ የማይገለጽ አድርጐ መውሰድ የሀልውናነትን መደባዊ ይዘት የሚያንፀባርቅ አቋም ነው ። የካፒታሊስት ሥርዓት ታሪካዊ ተልዕኮ ማብቃትና ፣ የህልውናው አጠያያቂነት በይበልጥ መከሰት ፣ ለተወሰኑ ግለሰቦች የራሳቸው ህልውና አጠያያቂ ሆኖባቸዋል ። በሥርዓቱ ውስጥ የተፈጠረው ቀውስ በግለሰቡ ውስጥ ስለሚንፀባረቅ ኢምክኑያዊ ወይም ኢሳይንሳዊ የሆነ አስተሳሰብ ማስከተሉ አይቀርም ። በቀውስ የተወጠረ ማኅበራዊ ኑሮ ለህልውና የሚሰጠው ፍች የተዛባ ስለሚሆን ከሱ ውጭ ግለሰቡ የራሱ የሆነ ትርጉም ለመፍጠር ፍላጐት ያድርበታል ። ሆኖም ህልውናን ከነባራዊ ሕግጋት ውጭ ማድረጉ ጭፍን

የኑሮ እምልከት ከመፍጠር በስተቀር ሌላ ውጤት ሊኖረው አይችልም ። የአርጌው መፍረክረክ ቋሚ መሠረት ስለሚያሳጣው ኑሮ አልጨበጥም ይላል ፤ ተስፋ መቁረጥ ንም ያስከትላል ። ይህንኑ ሁኔታ ነው ሀልውናነት የሚገልጸው ።

(ግዴታንና አጋጣሚን ፣ ኪርከጋርድን ፣ ሳርትርን ይመለከቷል ።)

## ሆልባኽ ፣ ፓውል ሃንሪ ዲትሪኽ
(*Holbach, Paul Henri Dietrich*)

ከ1723 — 1789 የኖረ ፣ ከአንድ ጀርመናዊ ባላባት ቤተሰብ ተወልዶ አብዛኛውን ዕድሜውን በፈረንሳይ ያሳለፈ የፈረንሳይ ኢአማኒ ቁስአካላዊ ፈላስፋ ነው ። "ለ ሲስቴም ደ ላ ናቱር" (1770) የተባለው በጣም የታወቀበት መጽሐፉ በፈረንሳይ ፓርላማ ትእዛዝ ባደባባይ እንዲቃጠል ተደርጓል ።

በእነዚህና በሌሎችም ጽሑፎቹ ውስጥ ሃይማኖትንና በተለይም የበርክሌይን አስተምህሮዎች በመቃወም ሐሳባዊነት ማንም ሰው ሊጨብጠው የማይችልና መሠረት የሌለው ምናባዊ ፈጠራ ነው ሲል ተናግሯል ። ሃይማኖትም በአብዛኛው ከድንቁርናና ከፍርሃት የሚመነጭና ለአንዳንዱም የማታለያ መሣሪያ ነው ብሏል ።

በሌላ በኩል ቁስአካል ማለት በማናቸውም ሁኔታ በሕዋሶቻችን ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር ማንኛውም ነገር ነው ። ቁስአካል ሊለወጡና ሊከፋፈሉ የማይችሉትን አቶሞች ያካተተ ሲሆን የነዚህም አቶሞች ዓይነተኛ ጠባይ ስፋት ፣ ክብደትና ቅርፅ ያላቸው መሆኑ ነው ። የቁስአካል ባሕርይ የሆነው ቅስቃሴም አካሎች በስፍራ ውስጥ የሚያደርጉት ቀላል ተናክአታዊ ቅስቃሴ ነው ይላል ።

ሆልባኽ ሰው የተፈጥሮ ክፍልና ለተፈጥሮም ሕግጋት ተገዥ ነው ስለሚል የወሳኛዊነትን ፍልስፍና የሚደግፍና የነገሮችን እንቅሥና ፍጻሜ በተናክአታዊ መንገድ የሚተረጉም ነው ። በሱ አመለካከት ዕድል (አጋጣሚ) የሚባለው በራሱ ነባራዊነት የሌለውና መነሻው ምን እንደሆነ ለጊዜው ለማናውቀው ለማናቸውም ክስተት የምንሰጠው ስያሜ ነው ።

በሥነ ዕውቀት አመለካከቱ ወደሕውስታዊነት በማዘንበል ዓለምን ማወቅ አይቻልም የሚለውን የኢታዋቂነትን አቋም ተቃውሟል። በፖለቲካ አመለካከቱም ሕገ መንግሥታዊ የዘውድ አገዛዝን ሲደግፍ በተለይ ደግሞ አብራሂ የሆነ የዘውድ አገዛዝን ይመርጣል ።

በአንድ ወቅት ሰፍና የሚገኝ አስተሳሰብ ዓለምን ይገዛታል ፤ በታሪክ ውስጥ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱት ሕግ አውጭዎች ናቸው ፤ ለሰው እርኩነት መሣሪያው ትምህርት ነው ፤ የመንግሥት አምባገነንነት መሠረቱ የሰዎች ድንቁርና ነው ወዘተ... በማለቱ ሆልባኽ ቁስአካላዊ ነበር ቢባልም ስለኅብረተሰብ የነበረው አመለካከት በአጠቃላይ ሲታይ ሐሳባዊ ነው ።

(ተናክአታዊ ቁስአካልነትን ይመለከቷል ።)

## ሆብስ ፣ ቶማስ
(*Hobbes, Thomas*)

ከ1588—1679 የኖረ እንግሊዛዊ ቁስአካላዊ ፈላስፋ ሲሆን በ17ኛው ምዕት ዓመት የተካሄደው የእንግሊዝ ቡርዧ አብዮት በፍልስፍናው ውስጥ ተንፀባርቋል ። ዋና ዋና ጽሑፎቹ "ዴ ሲቬ" (1642) እና "ሌቪያታን" (1651) ናቸው ። ሆብስ የተናክአታዊ ቁስአካልነትን አስተምህሮ ከማስፋፋቱም ሌላ የቢከንን ቁስአካላዊ ፍልስፍና ሥርዓት ለማስያዝ ሞክሯል ።

እንደ ሆብስ አባባል ዓለም በተናክአታዊ እንቅስቃሴ ሕግጋት የሚገዙ አካሎች አጠቃላይ ድምር ውጤት ናት ። በተጨማሪም የሰውንና የእራዊትን ልቡናዊ ሕይወት የተናክአታዊ እንቅስቃሴ ውጤት አድርጉ ስለሚረዳ ሕይወት ሙሉ በሙሉ በውጫዊ ኃይል የሚገዛ ውስብስብ ተናክአት ነው ይላል ። ከዚህም በመነሣት 1/ ነፍስ እንደ ራሱን የቻለ ልዩ ነገር ሆኖ እንደማይኖርና እግዚአብሔርም የሰው ምናባዊ ፈጠራ እንደሆነ ፣ 2/ ቁሳዊ አካሎች እንደ ወጥ ነገሮች እንደሆኑ ፣ 3/ በነገሮች መካከል ያለው የዓይነት ልዩነት ነባራዊነት እንደሌለውና ተናክአታዊ እንቅስቃሴ በአንጐላችን ውስጥ የሚፈጥረው ኅሊናዊ ክስተት እንደሆነ ይገልጻል ።

በዕውቀት አቋሙም ሐሳብ በሰው አእምሮ ውስጥ በእግዚአብሔር "ይታተማል"

የሚለውን የዴካርትን ሐሳብ የሚቃወም ነው ። ሐሳብ ከሕውስታ እንደሚመነጭ አድርጎ በመውሰድና አንዱን ሐሳብ ከሌላው ሐሳቡ ጋር በማወዳደር ፣ በመገጣጠምና በመከፋፈል ዕውቀት እንደሚገኝ አስተምሯል ።

ሆብስ የኅብረተሰብ መነሻው መለኮት ነው የሚለውን አመለካከት በመቃወም የኅብረተሰብ መሠረት "የሰዎች ማኅበራዊ ኮንትራት" (ሶሻል ኮንትራት) ነው የሚለውን ሐሳብ ይደግፋል ። የማኅበራዊ ኮንትራትን ምንነት ሲያስረዳ ሰው በተፈጥሮው ማኅበራዊ ባለመሆኑ ኅብረተሰብ ሰው ሠራሽ ሲሆን ሰዎች በገዛ ፈቃዳቸው የሚፈጥሩት ማኅበር (ኅብረት) ነው ። ሰው ኅብረተሰብን ከመፍጠሩ በፊት የግል ሕይወቱን ለማቆየትና ለመጠበቅ የሚረዳውን ማናቸውንም ጠቃሚና አስፈላጊ ነገር የመፈጸም ነፃነት ነበረው ። በተፈጥሮ "ሰው ለሰው አጥፊው" በመሆኑ ሰዎች በሰላም ሊኖሩ የሚችሉት በመካከላቸው አንድ ዓይነት በሕግ የሚገዛ ማኅበራዊ ኮንትራት ሲመሠረት ነው ። ከዚህም የተነሣ ሰዎች መሀከል በሚፈጠረው "ማኅበራዊ ኮንትራት" መሠረት ኅብረተሰብ ሊከሰት ፣ ንብረቶች ፣ አለቃዎች ፣ ሹሞች ወዘተ . . . ሕጉን ለማስከበር (በኃይልም ቢሆን) ብቃት ያላቸው ቻሉ ይላል ። ስለሆነም ኅብረተሰብ ሰዎች መብትና ነፃነታቸውን በገዛ ፈቃዳቸው ለሰላም ሲሉ የሚያጡበትና ሰላምም የሚያስገኙላቸው ጠቀሜታዎች አባላት ሁሉ የሚደሰቱበት ሥርዓት ነው ይላል ።

ሆብስ በፖለቲካዊ አመለካከቱ ፍጹማዊ የዘውድ አገዛዝን ቢመርጥም ስለዘውድ አገዛዝ በሚሰጠው ትንታኔ ውስጥ አንዳንድ ዲሞክራት ነክ ሐሳቦችን አንፀባርቋል ። ዘውዳዊ አገዛዝን የመረጠበት ዋናው ምክንያት አገዛዙ ከሁሉ የተሻለ ሆኖ አግኝቶት ሳይሆን ጠንካራ የመንግሥት ሥልጣን እንዲኖር በመሻቱ ነበር ። የመንግሥት ሥልጣን ከእንግሊዙ ቡርዧ መደብ ፍላጐት ጋር ተስማሚ መሆን አለበት ማለቱ ይህንኑ የሚያስረዳ ነው ።

ሆብስ ቁስአካላዊ ፈላስፋ ቢሆንም የኅብረተሰብ ግንዛቤው ግን የተሳሳተ ነበር ። ምክንያቱም ሰው በተፈጥሮው ማኅበራዊ መሆኑን በመካዱና ኅብረተሰብን " የሰዎች ስምምነት ውጤት" አድርጎ ማቅረቡ ነው ።

ይህ ስለኅብረተሰብ ያለው አመለካከት የቡርዧዚውን ግላዊነት የሚያንፀባርቅ ነው ።

(ተናከአታዊ ቁስአካልነትን ይመለከቷል።)

## ሆ ቺ ሚን

*(Ho Chi Minh)*

ከ1890—1969 የኖረ የቬትናም ኮሚኒስት ፓርቲ መሥራችና መሪ ነበር ።ሆቺሚን ከወጣትነት ጊዜው ጀምሮ ለአብዮታዊ ተግባራት የቆመ ነበር ።

ሆቺሚን በሥራ ምክንያት ፈረንሳይ ውስጥ በነበረበት ወቅት የካፒታሊስት ሥርዓት ምን ያህል ሠርቶአደሩን ሕዝብ ለሥቃይና ለመከራ እንደዳረገውና የዓለም ወዛደሮች በቀለም ፣ በቋንቋና በባህል ቢለያዩም ብሶታቸው አንድ መሆኑን በቅርብ ተገነዘበ ። በአፍሪካና በእስያ የኢምፔሪያሊስቶች መምጣት ምን ያህል ሥቃይና ውርደት በእነዚህ ሕዝቦች ላይ እንዳደረሰ ተረዳ ። በዚህም ምክንያት ሆቺሚን የቬትናም ሕዝብ ጠላት የፈረንሳይ ኢምፔሪያሊዝም እንጂ የፈረንሳይ ሰፊ ሕዝብ አለመሆኑን ደጋግሞ ገልጿል ። ሆቺሚን በ1917 በፈረንሳይ ወዝአደሮች ትግል ውስጥ በቀጥታ ተሳታፊ በመሆን የፈረንሳይ ሶሻሊስት ፓርቲ አባል ሆነ ። ከዚህም በላይ በፈረንሳይ የቬትናም አርበኞችን ማኅበር በማቋቋም በፈረንሳይ ይኖሩ የነበሩትን ቬትናማውያን በማንቃትና በማስተማር ለሀገራቸው ነፃነትና ክብር እንዲታገሉ ያነሣሣ ነበር ።

የጥቅምቱ የሩሲያ አብዮት ለእያሌ ዓመታት በዓለም ሰርና የነበረውን የኢምፔሪያሊዝም ብቸኛ የበላይነት ሰባብሮ አዲስ ዘመን በማብሰሩ ሆቺሚን የጀመረውን ትግል ከግብ ለማድረስ የቦልሼቪኮችን ፈለግ መከተል እንዳለበት አመነ ።

በሆቺሚን አስተሳሰብ የቬትናም ብቻ ሳይሆን የሌሎች ቅኝ ተገዥ የሆኑ ሀገሮች ነፃነት የሚገኘው የወዝአደሩን የአብዮት ጐዳና በመከተል ብቻ እንደሆነ አጥብቆ ያምን ነበር ። የነዚህ ሀገሮች ብሔራዊ ነፃነት ከማኅበራዊ ነፃነት ጋር መያያዙንና ይህም ነፃነት ከሶሻሊዝምና ከኮሚኒዝም ጋር በጥብቅ የተሳሰረ መሆኑን አስገንዝቧል ።

ሆቺሚን ከ1924—1930 በቻይናና በቬትናም በመዘዋወር ለዚህ ውስብስብ ትግል ግንባር ቀደም አመራር ሊሰጥ የሚችለውን ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ ለማቋቋም ከፍተኛ ትግል አደረገ ። በመጀመሪያም የቬትናም አብዮታዊ ወጣቶች ማኅበር የተባለውን በማቋቋም "ወጣት" በተባለው ጋዜጣ ወጣቱን ለትግል ቀሰቀሰ ። በዚህ ዓይነት ከብዙ ፓረትና ትግል በኋላም በ1930 የኢንዶቻይና ኮሚኒስት ፓርቲን (ኋላ የቬትናም ሠራተኞች ፓርቲ ፣ ዛሬ ደግሞ የቬትናም ኮሚኒስት ፓርቲ) መሠረተ ።

በ1935 ሞስኮ ውስጥ የተካሄደው የኮሚኒስቶች ስብሰባ አንድ ሰፊ ፀረ ኢምፔሪያሊስት የሆነ ዲሞክራሲያዊ ግንባር እንዲቋቋም በወሰነው መሠረት ሆቺሚን ቬትሚን የተሰኘውን ሰፊ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ግንባር በማቋቋም መላውን ሕዝብ በትግሉ ለማሳተፍ ችሏል ።

ዲየን ቢየን ፉ በተባለው ታሪካዊ ስፍራ የቬትናም አርበኞች የፈረንሳይን ጦር በማሸነፋቸው ፈረንሳይ በጀኔቩ ስምምነት መሠረት የቬትናምን አንድነት በማወቅ የሰላም ውል ፈረመች ። ነገር ግን ከ1955 ጀምሮ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በፈረንሳይ እግር በመተካት የደቡቡን ክፍል ለመቁረስ የጦር ሰፈር በመሥራትና በውስጥ አርበኞች በመጠቀም ጦርነት ከፈተ ። የቬትናም ሕዝብ በዓለም ተራማጅና ሰላም ወዳድ ኃይሎች እየታገዘ በቆራጥነት እብሪተኛውን የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ተቋቋመ ። ከግማሽ ሚሊየን ወታደሮች በላይና በብዙ ቢሊየን የሚቆጠር ገንዘብ ቢያፈስም የቬትናምን ሕዝብ ሊያንበረክክ አልቻለም። ሕዝቡም ይህን ድል ሊቀዳጅ የቻለው በቬትናም ኮሚኒስት ፓርቲ አመራር ነው ። የዚህ ፓርቲ ዝነኛ መሪ የነበረው ሆቺሚን የሕይወት ዘመኑን በሙሉ በትግል ያሳለፈና ታሪኩም ከቬትናም ሕዝብ የትግል ታሪክ ጋር በቅርብ የተሳሰረ ታላቅ መሪ ነበር ።

# ሐ

## ሐሳበ ግትር
*(Die–hard)*

አዳዲስ ነባራዊ ሁኔታዎች በሚጠይቁት መንገድ ሐሳቡን ለመለወጥ የማይሻ፣ ኋላቀር አስተሳሰብን የሙጥኝ ብሎ የሚይዝ ሐሳበ ግትር ይባላል ። ሐሳበ ግትር ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ ከማድረግ ይልቅ ቀኖና እንደሆነ አድርጎ የሚወስድ ነው ። ይህ ዓይነቱ አቋም በየትኛውም መልክ ቢሆን አብዮትን ከፋኛ ሊጎዳ ስለሚችል አብዮታውያን አጥብቀው ይዋጉታል ።

(ቀኖናዊነትን ይመለከቷል ።)

## ሐሳባዊነት
*(Idealism)*

መንፈስ ወይም ኅሊና ከቁስአካል ቅድሚያና የበላይነት አለው የሚል የፍልስፍና አቋም ነው ። ሐሳባዊነት ፣ ንቃተ ኅሊናን ከቁሳዊው ዓለም ነጥሎ በመመልከት የተጨባጩን ዓለም ህልውና ወደመጠራጠርና ብሎም ተፈጥሮን በከፊልም ሆነ በሙሉ የማወቅ ችሎታን ወደመካድ ያመራል ። ከዚህም የተነሣ ሐሳባዊነት በሰው ልጅ የዕውቀት ዕድገት ሂደት ውስጥ ዕንቅፋት እየሆነ ሳይንስንና ቴክኖሎጂን ይገታል ።

ሐሳባዊነት ቀደም ሲል በአምልኮት የተጀመረ ሲሆን የኋላ ኋላ ግን ሥርዓት በመያዝ የተከሰተ የፍልስፍና ዘርፍ ነው ። ዓለም በአምላክ እንደተፈጠረች ፣ በስፍራና በጊዜም እንደተወሰነች (ማለትም ፍጻሜ እንዳላት) አድርጎ የሚመለከተው ሃይማኖትም በሐሳባዊነት ፍልስፍና ውስጥ የታቀፈ ነው ።

ሐሳባዊነት በተለይም በአምልኮ ገጽታው ይበልጥ ሰፍና የሚታየው በኋላ ቀር ኅብረተሰቦች ውስጥ ነው ፤ ይሁን እንጂ የምርት ኃይሎች በዳበሩባቸውና ሳይንስና ቴክኖሎጂ በተስፋፋባቸው የካፒታሊስት ኅብረተሰቦችም ውስጥ በዝባዥ መደቦች ለሥርዓታቸው ህልውና መቀጠል በሚያመች መልክ ረቂቅ የሆኑ የሐሳባዊነት አመለካከቶችን እያሰራጩ ሕዝቡ በተጨባጩ ሁኔታ ላይ እንዳያተኩር በማድረግ በመደብ መጣሪያነት ይገለገሉባቸዋል ።

ሐሳባውያን ፈላስፎች ስለተፈጥሮና ስለዕውቀት አንዳንድ ንድፈ ሐሳቦችን በማንሣትና የማንዛቤን ሂደት ለመረዳት በመፈለግ ብዙ የተለያዩ አዝማሚያዎችን ያንፀባርቃሉ ፤ ሆኖም እነዚህን የተለያዩ የሐሳባዊነት አመለካከቶች ከሁለት ከፍሎ መመልከት ይቻላል ። እነዚህም 1/ ነባራዊ ሐሳባዊነት 2/ ኅሊናዊ ሐሳባዊነት ናቸው ። የሁለቱም አመለካከቶች መሠረታዊ መነሻ መንፈስ በቁስአካል ላይ የበላይነት አለው የሚል ነው።

ነባራዊ ሐሳባውያን የተጨባጩ ዓለም መሠረት አንድ ሰዋዊ ወይም ኢሰዋዊ የሆነ ታላቅ አእምሮ ያለው መንፈስ ነው ብለው ያምናሉ ፤ በአንፃሩ ኅሊናዊ ሐሳባውያን የተጨባጩ ዓለም መሠረቱ አንድ ታላቅ መንፈሳዊ ኃይል ሳይሆን የያንዳንዱ ግለሰብ አእምሮ ነው ብለው ያምናሉ ።

እንደ ኅሊናዊ ሐሳባዊነት ተጨባጩ ዓለም ከሰው ልጅ የማወቅ ወይም የመገንዘብ ሂደት ውጭ ራሱን ችሎ ሊገኝ አይችልም ፤ ቁስአካላዊውም ዓለም አለ የምንለው በአእምሮአችንና በሕውስታችን ውስጥ ብቻ ነው ። በነባራዊና በኅሊናዊ ሐሳባዊነት መካከል ያለው ልዩነት ጉልህና ግልጽ አይደለም ። ብዙ የነባራዊ ሐሳባዊነት ጠባያት በኅሊናዊ ሐሳባዊነት ውስጥ ይንፀባረቃሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ ብዙ ኅሊናዊ ሐሳባውያን ከማያፈናፍን የአስተሳሰብ ጣብቂያ ለማምለጥ የነባራዊ ሐሳባዊነትን አቋም ይይዛሉ ።

የነባራዊ ሐሳባዊነት አስተምህሮ በመጀመሪያ የመነጨው ከምሥራቅ ቢሆንም ብሉይ ነባራዊ ሐሳባዊነት የአፍላጦን ፍልስፍና ነው ። ሃይማኖትና የሥነ ተረት አስተሳሰቦች የአፍላጦንና በአጠቃላይ የጥንታዊው ነባራዊ ሐሳባዊነት ዋና ጠባ

ዮች ነበሩ ። ነባራዊ ሐሳባዊነት ከሃይማኖትና ከሥነ ተረት ጋር ያለው ዝምድና እስከ ዘመናችን መጀመሪያ ድረስ ቆይቷል ። በተለይም ፍልስፍና በክርስትናና በእስልምና ሃይማኖት (ሥነ መለኮት) ተፅዕኖ ሥር በወደቀበት በመካከለኛው ዘመን ይህ ዝምድና በጣም ጉልቶ የሚታይ ጠባዩ ነበር ። ስለነባራዊ ሐሳባዊነት በሰፊው ከአተቱት መካከል እንደቅዱስ አውግስጦስና እንደ ቶማስ አኩናስ የመሳሰሉት የሃይማኖት መሪዎች ይገኙበታል ። ኅሊናዊ ሐሳባዊነት ደግሞ የግለኝነት ስሜቶች እየበረቱ ሲሄዱ ከዴካርት ጀምሮ በቡርዧ ፍልስፍና ውስጥ እያደገ መጥቷል ። በኋላም ካንት፣ ፊኽተ፣ ሼሊንግና በተለይም ሁል አቀፍ የሆነውን የዲያሌክቲካዊ ሐሳባዊነትን ሥርዓት የቀመረው ሄግልና ሌሎችም ሐሳባዊነትን በልዩ ልዩ ዘርፉና መልኩ አራምደውታል ።

የቡርዧው መደብ በመጀመሪያ ላይ ያሳየውን የተራማጅነት ጠባይ እየተወ ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነትን መዋጋት በጀመረበት ጊዜ በቡርዧዚው አካባቢ ተስፋ መቁረጥ፣ በሰው ልጅ የማሰብ ችሎታና በወደፊት የተስፋው ብሩህነት ላይ መጠራጠር እየተስፋፋ ሄደ ። በተጨማሪም የካፒታሊዝም እስከፊ ገጽታዎች በጉልህ መታየት ሲጀምሩ በሐሳባዊነት አስተሳሰብም ውስጥ የተለያዩ ለውጦች ተከስተዋል ። ከእንዚህም የአመለካከት ለውጦች ውስጥ እንደ ሀልውናነት፣ እንደ ተጨባጫዊነትና እንደ ኒዮቶሚዝም ያሉት በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው ።

(ኅሊናዊ ሐሳባዊነትን፣ ነባራዊ ሐሳባዊነትን ይመለከቷል ።)

## ሐሳባዊ ዲያሌክቲክስ

*(Idealist Dialectics)*

በአንደኛ ደረጃ የሚመለከተው የሄግልን ዲያሌክቲክስ ነው ። ሄግል በፍልስፍና አቋሙ ሐሳባዊ ሆኖ ሳለ የሚጠቀምበት የምርምርና የአስተሳሰብ ዘዴ ዲያሌክቲክስ ነበር ። ይህም ማለት ሄግል ለመጀመሪያ ጊዜ የዲያሌክቲክስን አስተሳሰብና ሕጎች ሥርዓት ባለው ሁኔታ በማስቀመጥ ከሙሉ ግንዛቤ ደረጃ ላይ ሊያደርሳቸው ችሏል ። ሆኖም ሐሳባዊ ከመሆኑ የተነሣ ዲያሌክቲክስን የቁስአካል እንቅስቃሴና ዕድገት ሕግ እንደሆነ ሳይሆን ዓለምን በበላይነት እንደሚገዛ በገዛ እራሱ የሚኖር የሐሳብ እንቅስቃሴና ዕድገት አድርጐ ተርጉሞታል ። በዚህም አመለካከት ተፈጥሮ ከሐሳብ የመነጨ ቅራኔ እንደሆነና የዲያሌክቲክስም እንቅስቃሴ ሐሳብ ተፈጥሮን አሸንፎ የበላይነቱን የሚያረጋግጥበት መግሪያ ነው በማለት ተናግሯል ። በመሆኑም ፍልስፍናው የተገላቢጦሽ የሆነ ንጽረተ ዓለምን የሚገልጽ ነው ።

ማርክስ ይህንኑ በመገንዘብ ዲያሌክቲክስ ትክክለኛ መልኩን እንዲይዝ ሄግል የገለበጠውን በማስተካከል የሐሳብ ዲያሌክቲክስ የቁስአካል ዲያሌክቲክስ ነፀብራቅ መሆኑን አስረድቷል ።

(ሄግሊያኒዝምን፣ ቁስአካላዊ ዲያሌክቲክስን፣ ሳይንሳዊ ዲያሌክቲክስን ይመለከቷል ።)

## ሐሳብ

*(Idea)*

የአሳቦትንና የኑባሬን ግንኙነት የሚገልጽና በፍችና በምንነት ሊተረጉም የሚችል የፍልስፍና ፈርጅ ነው ። በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ ለሐሳብ የተለያዩ ትርጉሞች ተሰጥተውታል ። ሐሳብ የሚኖረው በአእምሮ ውስጥ ብቻ ነው የሚለው አመለካከት በሁለት አዝማሚያዎች ይከፈላል ። ከነገሮች የመጣና የነገሮች ምስል ነው የሚለው አንዱ አዝማሚያ ሲሆን ሁለተኛው በነገሮች ምክንያትነት የመነጨ ቢሆንም ሐሳብ እራሱን የቻለ ኅሊናዊ ክስተት ነው የሚለው ነው ። የመጀመሪያው አቋም የሚገልጸው ግልብ እውነታዊነትን ሲሆን ሁለተኛው የኅሊናዊ ሐሳባውያንን አቋም ነው ። በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ የተከሰተው ሌላው አመለካከት የነባራዊ ሐሳባውያን አቋም ነው ። በነሱ አመለካከት ሐሳብ የነገሮች ውስጣዊ ምንነት በመሆኑ በነባራዊነት የሚኖር ነው ።

ስለ ኑባሬና ስለ አሳቦት ግንኙነት ትክክለኛውን መልስ የሰጠ ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ነው ። የነባራዊ ሐሳባውያን አመለካከት የመነጨው ነገሮችን በተገላቢጦሽ ከማየት ነው ። ሐሳብ ነፀብራቅ መሆኑ ቀርቶ በነባራዊነት ያለና አድራጊም ሆኖ መታየቱ ስህተት ነው ። ሆኖም ይህ አመ

[illegible] የያዘው አንድ ነጥብ አለ ፤ ይኸውም ሐሳብ ነገሮችን የመለወጥ ችሎታ አለው የሚለው ነው ። ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ይህን ነጥብ በመያዝ ሐሳብን የግንዛቤ [illegible]ት በማድረግና ከተግባር መመንጨቱን በማሳየት የሐሳብን ትክክለኛ ሚና ያስረዳል ። የኅሊናዊ ሐሳባውያን አቋም የሚያመራው ወደ ኢታዋቂነት በመሆኑ የተሳሳተ ነው ። አቋማቸው የሚታረመውም ሐሳብ ኅሊናዊ ቢሆንም ያለ ነባራዊው ዓለም [illegible] ወይም ይዘት እንደሌለው በማስገንዘብ ነው ። ሐሳብ የነባራዊው እውነታ ነፀብራቅ በመሆኑ የሚገልጸው የኑባሬን ውስጣዊ ሕጎችና ግንኙነቶች ነው ።

(ኅሊናዊ ሐሳባዊነትን ፤ ነባራዊ ሐሳባዊነትን ፤ ነፀብራቅን ይመለከቷል ።)

## ሐሳቦች ግጥምጥሞሽ (የ—)
(*Association of Ideas*)

በልቡና ውስጥ አንድ ሐሳብ ከሌላ ሐሳብ ጋር በመያያዙ በራሱ ግፊት ለአእም[illegible]ችን የመገለጽን ሁኔታ የሚያመለክት ሌላ ሐሳብ ነው ። ለምሳሌ ደመና ስናይ ዝናብን እናስባለን ፤ እንጠብቃለን ። የሐሳቦች ግጥምጥሞሽ ከሦስት ሕጎች አንፃር የሚፈጸም ነው ። እነሱም 1/ መመሳሰል (ለምሳሌ የአንድን ሰው ፎቶግራፍ ስናይ ሰውየውን ያሳስበናል) ፤ 2/ በጊዜና በቦታ መነ[illegible]ት (የአንድን ቤት ክፍል ስናይ ጎኑ ያለውን ክፍል ያስታውሰናል) ፤ 3/ የመንሥኤና የተገብሮት ግንኙነት (ጢስ ስናይ እሳት አለ እንላለን) ናቸው ።

በሥነ ልቡናና በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ የአስተሳሰብን ሥርዓት በግጥምጥሞሽ ሕግ አስረዳለሁ የሚል የሥነ ዕውቀት አዝማሚያ ተከስቷል ። ሥነ ዕውቀቱ የሚያንፀባርቀው ኅሊናዊ ሐሳባዊነትን ነው ፤ ምክንያቱም [illegible]ት ከአንድ ሐሳብ ወደሌላ የሚሸጋገረው በሥነ አመክንዮ ሕጎች ሳይሆን በልምድ በተገኘ የሐሳቦች ግጥምጥሞሽ ብቻ ነው ስለሚል ነው ። የሐሳብንና የእውነታን ሥነ አመክንዮ ሥርዓት የሚክድና የሐሳብን ሂደት ተናክአታዊ የሚያደርግ ነው ። ዳሳሾች የዚህ ሥነ ዕውቀት አራማጆች ናቸው ። ማርክሲዝም የሐሳቦች ግጥምጥሞሽን የሚክድ አይደለም ። ሆኖም ከምክኑያዊና ከነባራዊ ሕጎች አኳያ የሚፈጸም መሆኑን በቅድሚያ እንድንገነዘብ ይጠይቃል ።

(ዳሳሽነትን ፣ ሂዩምን ፣ በርክሌይን ይመለከቷል ።)

## ሐሳዊ መሢህ
(*Demagogue*)

ሐሳዊ መሢህ ማለት በሐሰት የሚናገር የሚደልል ፣ የተናገረውን የሚክድ ማለት ነው ።

ተወዳጅነትና ተቀባይነት ለማግኘት ሲሉ የውሸት ተስፋ ለሚሰጡ ፣ በሕዝብ ስብሰባዎች ላይ እውነትነት በሌለው የሙገሳ አነጋገር ለሚጠቀሙና ለማኅበራዊ ዕድገት ዕንቅፋት የሚሆኑ ሌሎች ተመሳሳይ ድርጊቶችን ለሚያከናውኑ ወገኖች የተሰጠ መጠሪያ ነው ።

ሐሳዊ መሢህነት ደግሞ በሠራተኛው ንቅናቄ ውስጥ በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት ሲሉ ሊጨበጥ የማይችል ተስፋ የሚሰጡ ፣ ያልሆነውን ሆነ ብለው ሕዝቡን በማሞኘስ የሚደልሉና እውነትን በማጣመም ወደተሳሳተ አቅጣጫ የሚመሩ የቡርዧዚ ፖለቲከኞችና የጥቅም ተባባሪዎቻቸው የሚያራምዱት ስብከት ነው ። ይህ ዓይነቱ አቀራረብ በተለይ በምርጫ ወቅትና በአጠቃላይም በቡርዧዚው ዜና ማሰራጫዎች የተለመደ ነው ።

## ሕሡም
(*Ugly*)

ሕሡም የግዕዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙም የከፋ ፣ ክፉ ፣ መጥፎ ፣ ጥፉ ማለት ነው ።

የውበት ተቃራኒ የሆነና የሰውን የጥላቻ ፣ የእምቢታ ወዘተ ... ስሜቶችን የሚገልጽ የሥነ ውበት ፈርጅ ነው ።,በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ሕሡም የሚያመለክተው የሰውነፃ እንቅስቃሴ መቀጨቱን ወይም በሚያጣምሙና በሚያዛቡ ማኅበራዊ ኃይሎች ሥር መውደቁን ነው ። በዚህ ፍችው መሠረት ሕሡም የመደብ ትግል ስሜታዊ ክስተት

ነው ። በአንፃሩም በሥነ ውበት ውስጥ የሕሡም መታየትና መገለጽ በሰዎች ዘንድ የውበትን ፍላጐት ይፈጥራል ፤ ነፃ ለመውጣት የሚያደርገ·ትንም ትግል ያጠናክራል።

(ሥነ ውበትን ይመለከቷል ።)

## ሕውስታ
(*Sensation*)

የስሜት አካላት የሚያከናውኑትን ተግባር ፦ ማሽተትን ፣ ማየትን፣ መስማትን ፣ መዳሰስን የሚገልጽ ፣ ሕዋስ ከሚል የግዕዝ ቃል የመጣ ነው።

ነባራዊው ዓለም በሰው ሕዋሳት ላይ የሚያደርሰው የመጀመሪያውና ቀጥተኛው ተገብሮት ነው ። የአካባቢው የተለያዩ ተፅዕኖዎች በሕዋሳት ተቀባይነትና በነርቭ አውታሮች አስተላላፊነት ከአንጐል ሲደርሱ ወደ ሕውስታ ይቀየራሉ ። ሕውስታ ከቁስ አካላዊው ዓለም, የሚመነጭ በመሆኑ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ነው ። ውጭ ካለው ቀስቃሽ ነገር ባሕርይና ከተቀባዩ የነርቭ አውታር ዓይነት አንፃር ሕውስቶች በአምስት ዓይነት ይከፈላሉ ። እነርሱም ከማየት ፣ ከመስማት ፣ ከማሽተት ፣ ከመቅመስ ፣ ከመንካት የምናገኛቸው ሕውስቶች ናቸው ። እነዚህም ሕውስቶች የተለያዩ ናቸው ፤ ቀለም ከክብደት ፣ ክብደት ከድምፅ ወዘተ... ይለያል ። ካሉን ሕውስቶች ሁሉ ዳብሮ የሚገኘው ሕውስት ከማየት የምናገኘው ነው ።

ነባራዊውን ዓለም የማወቅ ሂደት የሚጀምረው ከሕውስታ ነው ። ከዚህም አኳያ ሕውስታ ሁለት ዓይነት ሚና ይኖረዋል ። በመጀመሪያ ደረጃ ስለነገሮች ምልክት ወይም መረጃ ይሰጠናል ። ለምሳሌ የብረት ቅላት ሙቀትን ያመለክታል ። እነዚህ መረጃዎች ለኑሮ የምንፈልጋቸውን ወይም አጥፊ በመሆናቸው መሸሽ ያለብንን የነገሮችን ጠባዮች ይገልጹልናል ። በሁለተኛም በልባዊ ደረጃ በአንጐላችን ውስጥ የሚፈጠረው የነገሮች ምስል አካል በመሆን በነባራዊ ዓለም ውስጥ የሚገኙትን ግንኙነቶች ያስተላልፉል ።

(ልባዊን ፣ ነፀብራቅን ፡ ሕውስታዊነትን ይመለከቷል ።)

## ሕውስታዊነት
(*Sensationalism*)

የዕውቀት ምንጭ ሕውስት ብቻ ነው የሚል የሥነ ዕውቀት አስተምህሮ ነው ። ይህ ሥነ ዕውቀት ሕውስታዎች የነባራዊው ዓለም ነፀብራቅ መሆናቸውን የሚቀበል ከሆነ የሕውስታዎች ምንጭ ከነሱ ውጭ የሚገኝ ቁስአካል ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ ስለሚደርስ ወደ ቁስአካልነት ያመራል ። ነገር ግን ሕውስታዎችን ኅሊናዊ ብቻ በማድረግ ከውጫዊ ምንጫቸው ጋር ማገናዘብ አይቻልም የሚል ከሆነ የሚያመራው ወደ ኢታዋቂነትና ወደ ኅሊናዊ ሐሳባዊነት ነው ።

ስለሆነም ሕውስታን የዕውቀት መነሻ ማድረጉ ብቻ ቁስአካላዊ የሆነ ፍልስፍና ለመመሥረት አያበቃም ። የሕውስታን ትክክለኛ ሚናና ትርጉም ማሳየቱ ጠቃሚ ቢሆንም ወደ ሕውስታዊነት ማዘንበሉ ግን ትክክል ካለመሆኑም በላይ ሐሳባዊነትን ለመዋጋት አይጠቅምም ። ሕውስታ ዕውቀትን ከሚያስገኙልን መሣሪያዎች አንዱ መሆኑንና ከነዚህ መሣሪያዎች (አርቅቆት ፣ ተግባር ፣ ሥነ አመክንዮ ወዘተ...) ጋር በጣምራ ሲሠራ ብቻ ትክክለኛውን ሚና የሚጫወት መሆኑን ማስረዳት ያስፈልጋል ።

(ዳሳሽነትን ፣ ኅሊናዊ ሐሳባዊነትን ፣ ኢታዋቂነትን ፣ ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀትን ፣ በርክሌይን ፣ ሂዩምን ይመለከቷል ።)

## ሕዝባዊ ሠራዊት
(*People's militia*)

ከጭቁን መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጣ ፣ ወታደራዊና ርዕዮተዓለማዊ ትምህርት የተሰጠው ፣ የሀገር ፀጥታ ከውስጥም ሆነ ከውጭ ሲደፈርስ ወታደራዊ ተግባር የሚያከናውን ፣ በሰላም ጊዜ በመደበኛ ሥራው ላይ የሚገኝ መደበኛ ሠራዊት ያልሆነ የታጠቀ ሕዝባዊ ኃይል ነው ።

የሕዝባዊ ሠራዊት ዓይነተኛ ተግባር የሰፊውን ሕዝብ ጥቅምና ፍላጎት መንከባከብና መጠበቅ ነው። ሕዝባዊ ሠራዊት በሳይንሳዊ ርዕዮተዓለም የታጠቀ ፣ ለማንና ለምን እንደሚዋጋ

የሚገባ የተገነዘበ በመሆኑ በድርጅታዊ አቋሙና በሙሉ ብቃቱ ተጠናክሮ የሀገርን አንድነት ፣ ነፃነትና የሰፊውን ሕዝብ አብዮት በመጠበቅ ረገድ ከፍተኛ ሚና ያለው ታላቅ ኃይል ነው ።

## ሕዝባዊ ቁጥጥር
(*People's Control*)

በሶሻሊስትና የዕድገት ፈለጋቸውን የያዙ አቅጣጫ በቀየሱ ሀገሮች ሠርቶ አደር ሕዝብ ንቁ ተሳትፎ ብሔራዊ ሀብትን ለመንከባከብና ለመጠበቅ ፣ ዲሲፕሊንና ሕግ እንዲከበር ፣ መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች በተቀናጀና በተቀላጠፈ አሠራር ሕዝቡን የሚያገለግሉ መሆናቸውን ለመከታተል ፣ ለማስተግበርና ለመቆጣጠር የተዘረጋ የቁጥጥር ሥርዓት ነው ።

ሕዝባዊ የቁጥጥር ሥርዓት በተዘረጋባቸው ሀገሮች በሕዝብና በመንግሥት ይዞታ ሥር የዋሉት የሀብት ማፍሪያ መሣሪያዎች ፍሬያማ በመሆን ለሰፊው ሕዝብ የበለጠና የተሻለ ጥቅም እንዲሰጡ ማድረግ ዋንኛ ዓላማው ነው ። ይህም በሥልጣን ያለአግባብ መጠቀምን ፣ በልዩ ልዩ ሕገ ወጥ መንገድ የሕዝብንና የመንግሥትን ንብረት ለግል ጥቅም ማዋልን ፣ የአሠራር ዝርክርክነትን ለማስወገድና ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ምርትንና ምርታማነትን እያሳደገ ራሱን በራሱ ተቆጣጥሮና ራሱን የመምራት ባህሉን አዳብሮ በብሔራዊ ሀብት አጠባበቅና አስተዳደር ተግባሮች ሙሉ ተካፋይ ለመሆን ያስችለዋል ።

በሀገራችንም ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ እንደ ኢት. አ. በ1973 በአብዮታዊው መንግሥት በወጣው የሠርቶአደሩ ቁጥጥር ኮሚቴ አዋጅ ለዚህ ዓላማ ከግብ መድረስ ተገቢው ሥልጣንና ኃላፊነት ያለውና ማዕከላዊ አመራር የሚሰጥ የሠርቶ አደሩ ቁጥጥር ኮሚቴ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተቋቁሟል ። ከዚህም በላይ የክፍለ ሀገር ፣ የአውራጃ ፣ የወረዳ የቁጥጥር ኮሚቴዎችና በልዩ ልዩ ድርጅቶችም መሠረታዊ የቁጥጥር ኮሚቴዎች እንዲዋቀሩ ተደርጓል ።

## ሕዝባዊ አመፅ
(*Insurrection*)

ሰፊውን ሕዝብ ከበዝባዥ መደቦች ለማላቀቅና ሙሉ መብቱን ለማጎናፀፍ በአንድ ወቅት በቁጣ የሚነሣ ሕዝባዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ነው ። ሕዝባዊ አመፅ በጠንካራ አብዮታዊ ድርጅት ከተመራ ፍትህና እኩልነት የሰፈነበት ኅብረተሰብ ለመመሥረት ወደሚያስችል ግብ የሚያመራ ይሆናል ።

ለሕዝባዊ አመፅ ግብ መምታት የፓርቲው ትክክለኛ መሥመር መከተል ፣ የአብዮታዊ ሁኔታዎች መሟላት ፣ የፓርቲው በሰፊው ሕዝብ መካከል ዘልቆ መግባትና በሰፊው ሕዝብ መታቀፍ ፣ የቆራጥ ካድሬዎች መኖር ፣ የጠላትንና የራስን የኃይል አሰላለፍ በሚገባ ማጤን አስፈላጊ ሁኔታዎች ናቸው ።

ከላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች መሠረት አድርጎ በሚነሣ ሕዝባዊ አመፅ ውስጥ ሊተኮርባቸው የሚገቡ ጉዳዮች አሉ ። ከነዚህም የመጀመሪያው ጠላትን እስከ መጨረሻው ለመጋፈጥና ለመቋቋም ቁርጠኛ ካልሆኑ በስተቀር አመፅ መጀመር በጠላት ክፉኛ የሚያስመታና አብዮታዊ እንቅስቃሴውንም ክፉኛ ወደኋላ የሚጐትት መሆኑ ነው ። ሕዝባዊ አመፅ አንድ ጊዜ ከተጀመረ ከስትራቴጂ አንፃር የአጥቂነት ቦታ በመያዝ ሳያቋርጥ በተጧጧፈ መልክ መቀጠል ይኖርበታል ። በታሪክ ተደጋግሞ እንደታየው የሕዝባዊ አመፅ ከአጥቂነት ወደ ተከላካይነት ማዘንበል አደገኛ በመሆኑ የሚያስፈልገውን መሥዋዕት ከፍሎ የበላይነቱን ማረጋገጥ አለበት ። በቁርጠኝነት ወደፊት መግፋት ፣ የጠላት ኃይል ሲበታተን ዕረፍት ነሥቶ በየቦታው መምታትና ምንም አነስተኛ ቢሆን በየጊዜው አዳዲስ ድሎችን ማስቆጠር አስፈላጊ ነው ። እንዲሁም በየጊዜው የሚገኙት ድሎች በሚያስገኙት የሞራል ጥንካሬና አመቺ ሁኔታ በመጠቀም ሕዝቡን በበለጠ ወደ ትግሉ መሳብና ጠላት ኃይሉን አሰባስቦ እንደገና እንዳያንሰራራ ጊዜ ሳይሰጡ ሽንፈቱን በማከታተል የመጨረሻ ተስፋውን አስቆርጦ በቁጥጥር ሥር ማዋል የሕዝባዊ አመፅ ዓይነተኛ ዓላማ ነው ።

(አብዮትን ፣ ተናሥኦትን ፣ ስትራቴጂንና ታክቲክን ፣ ነባራዊ ሁኔታን ፣ ኅሊናዊ ሁኔታን ይመለከቷል ።)

## "ሕዝባዊ" ካፒታሊዝም
*("People's" Capitalism)*

በካፒታሊስት የጋራ አክሲዮን ኩባንያዎች ውስጥ ሠራተኞች የአነስተኛ አክሲዮኖች ባለቤቶች እየሆኑ በመምጣታቸው የግል ሀብት ባለቤትነት ከጥቂቶች ወደ ብዙኀን እጅ እየገባ በመሄዱ ካፒታሊዝም ወደ "ሕዝብ" ካፒታሊዝምነት እየተለወጠ ነው የሚለው የቡርዧ ንድፈ ሐሳብ "ሕዝባዊ" ካፒታሊዝም ይባላል ።

"ሕዝባዊ" ካፒታሊዝም ወይም ፣ የ"ካፒታል ዲሞክራሲያዊ መሆን" የሚለው የቡርዧ ንድፈ ሐሳብ በ1940ዎቹ ውስጥ የተጀመረና ከዚያም በኋላ በቡርዧ አፈቀላጤዎች በስፋው የሚሰበክ ነው ። የዚህ ንድፈ ሐሳብ መሥራች ተብለው ከሚታወቁት መካከል አሜሪካዊውን ኢኮኖሚስት ናድለርን ፣ ኢጣሊያዊውን ኢኮኖሚስት ኤም ሳልቫዶሪን ፣ ምዕራብ ጀርመናዊውን ኢኮኖሚስት ኤርሃርድን ለመጥቀስ ይቻላል ። ከነዚህ ሌላ በተለይ አሜሪካዊው ጆን ኬኔዝ ጋልብሬዝ በካፒታሊዝም ውስጥ እያደገ በመሄድ ላይ ያለው የአነስተኛ አክሲዮን ባለቤቶች ቁጥር በካፒታሊስት ባለብዙ ብሔር ኩባንያዎችና ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ውስጥ ወሳኝ ተፅዕኖና ሚና እያስከተለ በመሆኑ ካፒታሊዝም "ሕዝባዊ" እየሆነ መጥቷል በማለት ላይ ይገኛል ።

በካፒታሊስት የጋራ አክሲዮን ኩባንያዎች ውስጥ የአክሲዮን ባለቤቶች የሆኑት በዓመታዊው የአክሲዮን ባለቤቶች ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የመገኘት መብት ስላላቸውና በዚህም መሠረት በኩባንያው ውስጥ የአነስተኛ አክሲዮን ባለቤቶች የሆኑትም በዚሁ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ሊገኙ የሚችሉ በመሆናቸው የቡርዧ አፈቀላጤዎች ይህንን ሁኔታ ካፒታሊዝም "ዲሞክራሲያዊ" ሆነ ፣ ካፒታሊዝም ወደ 'ሕዝባዊ" ካፒታሊዝም ተለወጠ በማለት ይሰብካሉ ። ነገር ግን በነዚህ ዓይነቶቹ የካፒታሊስት ድርጅቶች ውስጥ ባለቤትነቱ ያው ካፒታሊስታዊ ነው ። ይዞታው የግል ካፒታሊስትም ሆነ የቡድን ካፒታሊስት መሆኑ የካፒታልን የበላይነት አይሰርዘውም ። እንዲያውም እንደዚህ ዓይነቶቹ የካፒታሊስት ድርጅቶች የከፍተኛ የፋይናንስ ካፒታሊስቶች ይዞታና ቁጥጥር በከፍተኛ ደረጃ የሰፈነባቸው ናቸው ።

በአክሲዮን ባለቤቶች ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ሁሉም ድምፅ የመስጠት መብት አለው ይባላል ። ሆኖም የድምፁ የመብት ደረጃ እንደይዞታው ከፍተኛነትና አነስተኛነት ይለያያል ። የአነስተኛ አክሲዮን ባለቤቶች በዛ ያለ ቁጥር ሲኖራቸው የድምፅ መብታቸው የመወሰን ዓቅም የለውም ። በአንፃሩ ጥቂቶቹና ከፍተኛ የአክሲዮን ይዞታ ያላቸው ግን የድምፅ መብታቸው የመወሰን ዓቅም ያለው ነው ፤ ከዚህም በላይ እነዚህ ጥቂቶች የኩባንያውን የዕለት ተዕለት ሥራ ፖሊሲ የሚያወጡና የአመራር አካላት የሚሰይሙና የሚሾሙ ናቸው ።

በአንዳንድ ካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ ጥቂት ወዛደሮች ከዕለት ጉርሳቸው በመቆጠብ ዝቅተኛ ዋጋ ያለውን አክሲዮን ቢገዙ ወይም ገንዘባቸውን በቁጠባ ባንክ ቢያስቀምጡ ወዛደሮቹ በካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ያላቸውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ስፍራ አይለውጠውም ። ካፒታሊስቶቹ አነስተኛ ገቢ ላላቸው ወገኖች አክሲዮን በመሸጥ ካፒታላቸውን ያሳድጋሉ ። ይህም ዘዴ የጥቂት የፋይናንስ ካፒታሊስቶችን ጥቅምና የበላይነት ለማስጠበቅና ለማጠናከር ይጠቅማል ። አነስተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች በካፒታሊስት ኩባንያዎች ውስጥ አክሲዮን መግዛት ኩባንያዎቹ ብዝበዛ የሚያካሂዱ የመሆናቸውን ባሕርይ አይለውጠውም ።

"ሕዝባዊ" ካፒታሊዝም የሚለው የቡርዧ ንድፈ ሐሳብ ዓላማ ወዛደሩ የካፒታል "የወል ባለቤት" ሆኗል እያሉ ወዛደሮቹን ለመደለልና ለመከፋፈል ቡርዧዎች የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው ። ከዚህም ሌላ በወዝአደሩ ውስጥ ውዥንብር በመንዛት ወዝአደሩ ከካፒታሊስቱ ጋር "ተመሳሳይ ዓላማ" አለው በማለት ወዝአደሩ የሚያካሂደውን ፀረ ካፒታሊስት ትግል እንዲተው ለማድረግ የሚሰራጭ ንድፈ ሐሳብ ነው ። የቡርዧ አፈቀላጤዎች በዚህ ንድፈ ሐሳብ አማካይነት ካፒታሊዝም "ዘለዓለማዊ" መሆኑን የሚያስተምረውንና በዚህም የተነሣ ወዝአደሩን ለፀረ ካፒታሊስት ትግል የሚያዘጋጀውን ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን ለመዋጋት የሚጠቀሙበት ዋና ዘዴ ነው ። የቡርዧ አፈ

ቀጣጮዎች እምነት ካፒታሊዝም የግል ይዞታ መሠረቱን ሳይለቅ ሠራተኛውን በማቀፍ ወደ ሕዝባዊነት ይለወጣል እንጂ ኮሚኒስቶች እንደሚሉት አይጠፋም የሚል ነው ። ከዚህ ንድፈ ሐሳብ ጋር የተሳሰረው ሌላው የቡርዧ ንድፈ ሐሳብ የካፒታሊስቶች የጋራ አክሲዮን ኩባንያ የሚመራው በተቀጠሩና የካፒታል ባለቤቶች ባልሆኑ ፣ ዓላማቸው የጠቅላላውን ኅብረተሰብ ፍላጐት ለማርካት በሆኑ ማኔጀሮች በመሆኑ የካፒታል ባለቤቶች ተፅዕኖ ቀርቶአል የሚለው ንድፈ ሐሳብ ነው ። ሆኖም ማኔጀሮቹን የሚሾሙትና የሚሽሩት በካፒታሊስት የጋራ አክሲዮን ኩባንያዎች ውስጥ የመቆጣጠሪያ አክሲዮን ባለቤቶች የሆኑት በጣት የሚቆጠሩት የፋይናንስ ካፒታሊስቶችና ታላላቆቹ ካፒታሊስቶች ናቸው ።

## ሕዝባዊ ውሳኔ (ውሳኔ ሕዝብ)
*(Referendum)*

በአንድ ሀገር ውስጥ ከፍተኛ ሕገ መንግሥታዊ ፣ ሕጋዊና ሌሎችም ላቅ ያሉ ብሔራዊና ዓለምአቀፋዊ ጉዳዮችን የሚመለከት ፖሊሲ ወይም አቋም በሕዝብ ድምፅ የመጨረሻ ውሳኔ የሚያገኝበት አሠራር ነው ። ስለሕዝባዊ ውሳኔ አፈጻጸም በዓለምአቀፍ ደረጃ የጋራ መርሆችና እመለካከቶች ቢኖሩም ፣ ይኸው የሚካሄድበት ሁኔታና በአፈጻጸምም መከተል የሚገባው ሥርዓት በእያንዳንዱ ሀገር ሕግ መሠረት ይደነገጋል ።

ሕዝባዊ ውሳኔው እንደቀረበው ጉዳይ ፣ እንደሚከናወንበት ሁኔታና እንደሚፈጸምበትም አካባቢ የሚከተሉት መልኮች ይኖሩታል ፣

አዲስ ሕገ መንግሥት ለማጽደቅ ወይም ያለን ሕገ መንግሥት ለማሻሻል የሚዘጋጁ አንቀጾች ረቂቅ ሕዝቡ የውሳኔ ድምፅ የሚሰጥበት ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሕዝብ ይባላል ።

በረቂቅ ሕግ ላይ ሕዝቡ ምርጫውን እንዲገልጽ የሚደረግበት ደግሞ የሕግ ሕዝባዊ ውሳኔ ሲባል ፣ አንድ ከፍተኛ ርምጃ እንዲወሰድ ሲፈለግ በድርጊቱ ላይ ሕዝቡ አቋም እንዲወስድበት የሚቀርበው ልዩ ውሳኔ ሕዝብ ፣ እንዲሁም የአንድ ሀገር የተለያዩ ክፍሎች የጋራ አቋም መውሰዳቸውን ለማረጋገጥ ሁሉም ድምፅ የሚሰጡበት ሕዝባዊ ውሳኔ ይባላል ።

እነዚህ ሁሉ የቀጥተኛ ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ መግለጫ ስልቶች ሲሆኑ በእያንዳንዳቸው አፈጻጸም ሕዝቡ የሚያደርገው ተሳትፎ እውነተኛነትና የውጤቱ አስተማማኝነት ግን ውሳኔ ሕዝብን በሚመራው መንግሥት መደባዊ ይዞትና የድርጊት ዓላማ ይወሰናል ። ለምሳሌ አንዳንድ የቡርዧ ሴረኞችና አምባገነን ኃይሎች ሕዝባዊ ውሳኔው የሚካሄድበትን ሁኔታ ለራሳቸው በሚያመች መልክ ከአቀነባበሩ በኋላ ለይስሙላ ውሳኔ ሕዝብ በማቅረብ ዓላማቸው ሕዝባዊ ድጋፍ ያለው ለማስመሰል ይጠቀሙበታል ። በሶሻሊስት ሀገሮች ደግሞ ሕዝባዊ ውሳኔን በትክክለኛ የሕዝባዊ ዲሞክራሲ መድረክነቱ ይጠቀሙበታል ።

## ሕዝባዊ ዲሞክራሲ
*(People's Democracy)*

ኢምፔሪያሊዝም በተዳከመበትና የኃይል ሚዛኑ ወደ ሶሻሊዝም ባጋደለበት ወቅት የሶሻሊስት አብዮት የተለየ ዕድገት የተንፀባረቀበትና ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በብዙ የምሥራቅ አውሮፓና በአንዳንድ የእስያ ሀገሮች የተከሰተ አዲስ የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት ቅርፅ ነው ። ሕዝባዊ ዲሞክራሲ የተከሰተው በነዚህ ሀገሮች በተካሄዱት ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቶች በመሆኑ የየሀገሮቹን የተለዩ ታሪካዊና ብሔራዊ ሁኔታዎች ያንፀባርቃል ። በእነዚህ አብዮቶች በአንድ በኩል በኢምፔሪያሊስቶች ፣ በውስጥ ትላልቅ ቡርዧዚዎችና የመሬት ከበርቴዎች ፣ በሌላም በኩል በነዚህ ኃይሎች በተጨቆኑ መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል የነበሩት ቅራኔዎች የተፈቱ ሲሆን ትግሉም የተመራው በወዝአደሩ መደብና በግንባር ቀደም ድርጅቱ በኮሚኒስት ፓርቲው ነው ።

ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ጥልቀት እያገኘ ሲሄድ የማምረቻ መሣሪያዎች በሕዝብና በመንግሥት ይዞታ ሥር በመዋል የቡርዧዚውን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ የበላይነት በማዳከም ለማኅበራዊ ይዞታ መስፈንና ለሕዝባዊው ሥልጣን መጠናከር አመች ሁኔታን ለመፍጠር አስችሏል ።

በገጠር የተካሄዱት የመሬት ይዞታ ለውጦችም የፊውዳል ቅሪቶችን በማጥፋት የወዝ አደሩንና የአርሶአደሩን ኅብረት በማጠናከር ለሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ዕድገት ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል ። በዚህ መሠረት በነዚህና በሌሎችም መስኮች የተደረጉት ዲሞክራሲያዊ ለውጦች ለነዚህ አብዮቶች ወደ ሶሺሊስት አብዮት መሸጋገር መሠረት ሆነዋል ። በዚህም ከአንግሥው የሕዝብ ዲሞክራሲያዊ የበላይ ገዥነት የነበረው የሕዝባዊ ዲሞክራሲ ሥልጣን የወዝአደሩን የበላይ ገዥነት ሚና መጫወት ጀመረ ።

ሕዝባዊ ዲሞክራሲ በአጠቃላይ መልኩ ይህን ቢመስልም የአብዮቱ ሂደት በእያንዳንዱ ሀገር የራሱ ልዩ ጠባዮች ነበሩት ። ስለዚህ ሕዝባዊ ዲሞክራሲ በየሀገሩ የሚይዘው መልክ የተለያየ ቢሆንም ሰፊ መደባዊ መሠረት ያለውና (የወዝአደሩንና የአርሶአደሩን ብቻ ሳይሆን ከቡርዧውም መደብ የተወሰነውን ክፍል ይጨምራል) በአንፃራዊ መንገድ ሲታይ በሰላማዊ ሁኔታ ወደ ሶሺሊስት አብዮት የሚያድግ ነው ። ይህ ሰፊ መደባዊ መሠረት አብዮቱ እንደ ፓርላማ ባሉት ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ተቋሞች ለመጠቀም አስችሎታል ። በዚህም መሠረት ዛሬ በብዙዎቹ የሕዝባዊ ዲሞክራሲ ሀገሮች ከኮሚኒስት ፓርቲው ሌላ የሶሺሊስት ግንባታን በመደገፍ እገዛ የሚያደርጉና የኮሚኒስት ፓርቲውን አመራር የሚቀበሉ ብዙ ፓርቲዎች እንዲሁም የነዚህን ፓርቲዎችና የሰፊውን ሕዝብ ኅብረትና አንድነት ለማጠናከር የሚረዱ ሕዝባዊ ግንባሮች መኖር የሕዝባዊ ዲሞክራሲ ዓይነተኛ ገጽታዎች ናቸው ። በነዚህ ሀገሮች የቀድሞውን መንግሥታዊ መዋቅር ለማፈራረስ ረጅም ጊዜ የወሰደ መሆኑም ሌላው የዚህ ሂደት ነፀብራቅ ነው ። በአሁኑ ጊዜ የሕዝባዊ ዲሞክራሲ ሀገሮች የዳበረ ሶሺሊዝም በመገንባት ለኮሚኒዝም ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት በመጣል ላይ ናቸው ።

(ዲሞክራሲን ፣ ግንባርን ፣ የወዝአደሩ የበላይ ገዥነትን ፣ ይመለከቷል ።)

## ሕዝባዊ ድርጅት
## (*Mass Organization*)

ከሙያ ፣ ከሥራ መስክ ፣ ከፆታ ፣ ከዕድሜ ፣ ከአካባቢ ወዘተ... ግንኙነት በመነሣት ሰዎች የጋራ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ የሚፈጥሩት አንድነት ወይም ኅብረት ሕዝባዊ ድርጅት ይባላል ። ለምሳሌ አኢወማ ፣ አኢሴማ ፣ መኢገማ ፣ ኢጋማ ወዘተ... ሕዝባዊ ድርጅቶች ናቸው ።

ሕዝባዊ ድርጅቶች አባላቱ ለተወሰነ የጋራ ዓላማ የሚደራጁባቸው መዋቅሮች ቢሆኑም የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ስለሚያቅፉ ለአንድ የተወሰነ መደብ ጥቅም የቆሙ አይደሉም ። ስለሆነም ምንም እንኳ ሕዝባዊ ድርጅቶች ከፖለቲካ ውጭ ባይሆኑም አቋማቸው የብዙኀን ድርጅት እንጂ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ፓርቲ አለመሆኑን ያስረዳል ። ሚናቸውም በተወሰነ ክልል የሚገታ ነው ። ሆኖም የአባሎቻቸው ፍላጐት የሠርቶ አደሩ ሕዝብ አጠቃላይ ፍላጐት አካል በመሆኑ ዓላማቸው ከሠራተኛው ፓርቲ ዓላማ ጋር የሚደጋገፍ እንጂ የሚፃረር አይሆንም ። የወዛደሩ የበላይ ገዥነት በተረጋገጠባቸው ሀገሮች የፓርቲና የመንግሥት የልማት ዕቅድ ማስፈጸሚያ በመሆን ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ ። ከዚህም የተነሣ በውስጣቸው የሚያሰባስቧቸውን ሠርቶ አደሮች ከመንግሥትና ከግንባር ቀደም የፖለቲካ ድርጅት ጋር የሚያገናኙ ድልድዮች በመሆን ከፖለቲካ ድርጅቱ በሚያገኙት አመራር የጋራ ትግላቸውን ለማራመድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መድረኮች ናቸው ። ፓርቲውም አባላቱን ከነዚህ ሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ይመለምላል ፤ በአባላቱ አማካይነት ደግሞ ሕዝባዊ ድርጅቶችን ለዓላማውና ለዕቅዱ ማስፈጸሚያ ያውላቸዋል ።

(የሙያ ማኅበራትን ይመለከቷል ።)

## ሕዝብ ደኅንነት ጥበቃ ኮሚቴ (የ—)
## (*People's Defenece Committee*)

በአብዮታዊ ሁኔታ ውስጥ የተወለደና በሕዝብ ተመርጦ በተወሰነ ክልል (በቀበሌ፣ በማምረቻ ፣ በማከፋፈያና በአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ወዘተ...) ውስጥ የሚቋቋም ፣ ማንኛውንም የሕዝብና የመንግሥት ንብረት እንዲሁም የአካባቢውን ሕዝብ ደኅንነትና ሰላም የሚጠብቅ ፣ አብዮትን ከመደብ ጠላቶች ጥቃት የሚከላከልና በክልሉ ካለው የአመራር አካል (ለምሳሌ የቀበሌ ጽሕፈት ቤት) የሚ

ወጣውን መመሪያና ውሳኔ የሚያስከብር የታጠቀ የጥበቃ ኃይል ነው ።

የሕዝብ ደኅንነት ጥበቃ ኮሚቴ አብዮት ባካሄዱ ሀገሮች በልዩ ልዩ መጠሪያ ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን በሀገራችንም ከየካቲቱ ሕዝባዊ አብዮት ጋር ተያይዞ የከተማ ቦታንና ትርፍ ቤትን እንዲሁም የገጠር መሬትን ለሕዝብ ባደረጉት አዋጆች መሠረት ሰፊው ሕዝብ ራሱን በራሱ የማስተዳደርና የመምራት መብት ለመጎናፀፍ በመቻሉ በከተማና በገጠር ቀበሌ ማኅበራት እንዲሁም በትላልቅ የማምረቻ ፣ የማከፋፈያና በሌሎች የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ውስጥ ተቋቁሞ ሕዝባዊውን አብዮትና የእናት ሀገርን ሀልውናና ነፃነት እንዲሁም የሕዝብንና የመንግሥትን ንብረት በመጠበቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ። በዚህም መሠረት የሕዝብ ደኅንነት ጥበቃ ኮሚቴ ቀስ በቀስ ከመደብ ትግሉ መፋፋምና ከአብዮቱ የዕድገት ደረጃ አንፃር በየወቅቱ በተወሰዱት የማጠናከሪያ እርምጃዎች እያደገና እየተጠናከረ መጥቷል ። በተለይም በኢሠፓአኮ አመራር የሕዝብ ደኅንነት ጥበቃ ኮሚቴ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴ በመባል ግልጽ የሆነ መመሪያ እንዲኖረው በመደረጉ አቋሙ ፣ አመራሩና አሠራሩ ተጠናክሮ በንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ የተጣለበትን አብዮታዊ ተግባር በማከናወን ላይ ይገኛል ።

## ሕይወታዊነት
(*Vitalism*)

ሕይወትና የሕይወት እንቅስቃሴ ሂደት የሚመነጩት ኢቁስአካላዊ ከሆነ ኃይል ነው የሚል የሐሳባዊ ፍልስፍና አዝማሚያ ነው ። ሕይወታዊነት ሕይወትና እንቅስቃሴው በአካላዊና በኬሚካላዊ ሕጎች መገዛታቸውን የሚክድ ነው ። በሕይወታውያን አባባል ሕይወት ነፍስ ከሌለው ነገር በዓይነት የሚለይ በመሆኑ በድን ከሆነ ነገር ሊመነጭ አይችልም ። በመሆኑም ሕይወትና ሕይወታዊ ክስተቶች ሕይወታዊ ከሆነ ጥንተ ግፊት ወይም ኃይል እንደመነጩ መቀበል ይኖርብናል ። በተለይም ሕይወታዊ ክስተቶች የሚያሳዩት የግብ ክንዋኔና የዘር መተላለፍ ሁኔታ ቁሳዊ እንዳልሆኑ ያስረዳናል ። ይህም ሲባል ሐሳብ ወይም መንፈስ በቀጥታ የሕይወት ምንጭ ነው ማለት አይደለም ይላሉ ። በሕይወታውያን አመለካከት የሕይወት ሂደትና ክስተቶች ሙሉ በሙሉ ንቁ ባለመሆናቸው ከመንፈስ የተለዩ ናቸው ።

ሕይወታዊነት ሕይወትን ምሥጢራዊ ከማድረግ በስተቀር ስለሕይወት አመጣጥና ምንነት የሚሰጠው ግልጽ ዕውቀት የለውም ። በተለይም በድን በሆነና ሕይወት ባለው መካከል ሽግግር ሊኖር አይችልም ብሎ በቅድሚያ መናገሩ የሕይወትን አመጣጥ እንዳይረዳ አድርጎታል ። በአንፃሩም ሳይንስ የሕይወታዊ ክስተቶችን ቁሳዊነትና በቁስአካል ሕጎች መገዛታቸውን በይበልጥ እያስገነዘበ መምጣቱ የሕይወታውያንን አመለካከት አዳክሞታል ። አፍላጦን ፣ አርስጣጣሊስና ፣ በርግሰን የዚህ ፍልስፍና አራማጆች ነበሩ ።

## ሕገ መንግሥት
(*Constitution*)

የመንግሥትን አደረጃጀት ፣ ባሕርይና አመራር በአንፃሩም የኅብረተሰቡን አካሎች መብትና ግዴታ በማሳወቅ ማድረግ የሚገባቸውንና የማይገባቸውን ለይቶ የሚደነግግ መሠረታዊ የሕግ ቅምር ነው ። ምንም እንኳ በአንዳንድ ምዕራባውያን ሀገሮች በተለይም በእንግሊዝ ባልተጻፈ ሕገ መንግሥትና በሌሎች ሕጎች የመጠቀም ልምድ ቢኖርም መንግሥታት በተወሰኑ ሥርዓቶች መሠረት የሚሻሻል የተጻፈ ሕገ መንግሥትና ሌሎችም ከዚሁ ጋር የተያያዙ ሕጎች ሊኖሯቸው ይችላሉ ። ይሁን እንጂ በጦርነትና በከፍተኛ የኅብረተሰብ ቀውስ ወቅት ወይንም ደግሞ በአንድ ሀገር የመንግሥት መሠረታዊ ለውጥ ሲደረግ የነበረው ሕገ መንግሥት ተሽሮ ከአዲሱ መንግሥት አደራጃጀት ጋር የሚጣጣም ሌላ በቦታው እስኪተካ ድረስ ሕገ መንግሥት የማይኖርበት ሁኔታም ይኖራል ።

ሕግ የገዥ መደቦች ፍላጎትና ጥቅም የማስከበሪያ መሣሪያ ስለሆነ ይዘቱ እንደ የሥርዓተ ማኅበሩ ይለያያል ። በዚህም መሠረት

በባሪያ አሳዳሪው ኅብረተሰብ ውስጥ የባሪያ አሳዳሪውን ፣ በፊውዳሉ ኅብረተ ሰብ የፊውዳሉን ፣ በካፒታሊስቱም ኅብረተ ሰብ የካፒታሊስቱን ፣ በሶሻሊስቱ ኅብረተ ሰብ ደግሞ የሠራተኛውን መደብ ጥቅምና ፍላጎት የሚያስከብር ነው ።

መደቦች ፣ ቡድኖችና ሌሎችም የኅብ ረተሰቡ ክፍሎች በኅብረተሰብ ያላቸው ስፍራ በሕግ ይወሰናል ። ሕግ በየደረ ጃውም የኅብረተሰብን ማኅበራዊ ግንኙነት ችና ጠባይ እንዲሁም ቅርፅ ይገልጻል ። ከዚህም ሌላ ሕግ በአንድ ወቅት አንድ ሀገር በዓለም አቀፍ ደረጃ ከጐረቤት ሀገሮ ችና ከሌሎች መንግሥታት ጋር ያለውን ግን ኙነት ያመለክታል ።

መንግሥት ያለ ሕግ ተግባሩን እንደ ማያከናውን ሁሉ ሕግ ደግሞ ያለ መንግ ሥት ተግባራዊ ሊሆን አይችልም ። መንግ ሥት እስካለ ድረስ ሕግ ይኖራል ፤ የሕግ መኖርም የመንግሥትን መኖር ያመለክታል። ሕግ የመደብ መጨቆኛ መሣሪያ በመሆኑ የኅብረተሰቡን የምርት ግንኙነት ለውጥ በመከተል አብሮ ይለወጣል ። መንግሥት ዘለዓለማዊ እንዳይደለ ሁሉ ለመንግሥት መከሰት ምክንያት የሆነ የግል ሀብት እየጠፋ ሲሄድ ሕግም ከመንግሥት ጋር ይከስማል ።

(ሕጋዊ ንቃተ ኅሊናን ፣ ላዕላይ መዋቅርን ይመለከቷል ።)

## ሕጋዊ መድረክ
(*Legal Forum*)

ሕጋዊነት ያለው የመማርና የማስተ ማር ፣ የመወያየትና የመከራከር በአጠቃላይ ሐሳብንና አቋምን ለማሳወቅና ሌሎችንም በዚሁ አሳምኖ ድጋፍ ለማግኘት የመቻል መብት ወይም ይህንን መብት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታ ነው ። አብ ዮት በተካሄደባቸው ሀገሮች ታጋዮች ከሚ ጠቀሙባቸው የትግል ስልቶች አንዱ የሆነ፣ ሕጋዊ ሰውነት ባለው መንገድ በአደባባይ የፖለቲካና የርዕዮተዓለም ትግል የሚደረግ በት ፣ የወዘደሩን የበላይ ገዥነት ለማረጋ ገጥ ሲባል ከአድኃሪዎችና ከቀልባሾች ጋር ፖለቲካዊ ክርክር የሚካሄድበት ነው።

አብዮታዊ መድረክ ሰፊው ሕዝብ እንዲነቃ ፣ እንዲደራጅና እንዲታጠቅ ፣ ብሎም ለወሳኙ ፍልሚያ ዝግጁ እንዲሆን ለማድ ረግና በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ለማስታጠቅ በአብዮቱ ሂደት የሚከሰቱትን ሁኔታዎች ለማስገንዘብ ፣ የአብዮትና የፀረ አብዮት ወገኖችን አሰላለፍና የየወቅቱን የኃይል ሚዛን ለመገምገም ፣ በአጠቃላይም አብዮ ቱን የሚመለከቱ ነጥቦችን በማንሣት ውይ ይትና ክርክር የሚደረግበት በመሆኑ ከፍ ተኛ ግምት የሚሰጠው የፖለቲካ መሣሪያ ነው ። በሀገራችንም የተለያዩ ሕዝባዊ ድር ጅቶችና እንደ ውይይት ክበብ የመሳሰሉት የአብዮታዊ መድረክነት ሚና የሚጫወቱ ናቸው ።

አብዮታውያን በሕጋዊ መድረክ በመ ጠቀም የሰፊውን ሕዝብ ዓላማ የሚያራም ዱት መድረኩ ትግላቸውን የሚያጠናክርና ወደፊት የሚያራምድ እስከሆነ ድረስ ብቻ ነው ። በሕጋዊ መድረክ መጠቀሙ ለአብ ዮቱ ወገኖች ሳይሆን ለአድኃርያንና ለፀረ አብዮተኞች ጊዜና ፋታ የሚሰጥና የሚያጠ ናክራቸው ከሆነ ግን በኅቡእና በሕገ ወጥ መንገድ መታገልን ይመርጣሉ ። በአንድ አብዮታዊ ሁኔታ ውስጥ ሕጋዊና ሕጋዊ ያል ሆነ የትግል ስልትን መከተል ያለ ቢሆንም የትኛውን መንገድ መቼ መጠቀም እንደሚ ቻል የሚወሰነው ትግል በሚካሄድበት ሀገር ያለው ነባራዊና ኅሊናዊ ሁኔታ ፣ እንዲሁም በወቅቱ ያለው የኃይል አሰላለፍ ነው ።

(ኅቡእን ይመለከቷል ።)

## ሕጋዊ ማርክሲዝም
(*Legal Marxism*)

በ1890ዎቹ ዓመታት በሩሲያ ናሮዲ ዝም ("ሕዝባዊነት") የተሰኘው የንዑስ ከበርቴ አመለካከት በፕሌኻኖቭ ፣ በሌ ኒንና በሌሎችም ማርክሳውያን ጨርሶ በተ መታበትና ማርክሲዝም በመስፋፋት ላይ በነ በረበት ጊዜ በአንዳንድ ቡርዧ ምሁራን አካባቢ የተከሰተ አዝማሚያ ነው ። በትሩቭ፣ ቱጋን ባራኖቭስኪ ፣ ቡልጋኮቭና በርድያዬቭ የታወቁ የሕጋዊ ማርክሲዝም ተጠሪዎች ነበሩ ። ሕጋዊ ማርክሳውያን በአፍ የማርክሲ ዝም ደጋፊዎች ነን ቢሉም በተግባር ግን ፀረ ማርክሳዊ ነበሩ ። በዚህ አቋማቸው የሠራ ተኛውን መደብ እንቅስቃሴ ለቡርዧዚው ጥቅ ም አሳልፎ ለመስጠት የተነሡ ፣ የሶሻሊስትን

አብዮት አስፈላጊነትና የወዛደሩን የበላይነትነት ያልተቀበሉ ፣ በካፒታሊዝም ላይ ትግል ለማድረግና እንዲደረግም ጥሪ ከማድረግ ይልቅ ካፒታሊዝምን በማወደስ ወዛደሩ ራሱ መልሶ ለካፒታሊዝም እንዲያጐበድድ ያስተማሩ በፈላጭ ቆራጩ የቄሳር መንግሥት ፈቃድ በሚወጡ መጽሔቶችና ጋዜጦች ላይ አሳሳች ጽሑፎችን በማውጣት ሕዝቡን ያወናበዱ የነበሩ አስመሳይ ማርክሳውያን ናቸው ።

ሕጋዊ ማርክሳውያን የሩሲያ ለዘብተኛ ቡርዧዚ አፈቀላጤዎች ናቸው ። ስለሆነም ምንም እንኳ ናሮድኒኮችን የተቃወሙ ቢሆኑም ከንዑስ ከበርቴው ወይም ከገበሬው ሶሻሊዝም ወደ ወዛደራዊ ሶሻሊዝም የተሸጋገሩ ሳይሆን ወደ ቡርዧ ለዘብተኝነት ያዘቀጡ ሐሳውያን ናቸው ።

(አስመሳይ ተራማጅን፣ናሮዲዝምን ይመለከቷል።)

## ሕጋዊ ንቃተ ኅሊና
## (*Legal Consciousness*)

የላዕላይ መዋቅር አካል የሆነና በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ ሰዎች ማኅበራዊ ኑሮን አስመልክተው ሕጋዊ ነው አይደለም ፣ ትክክል ነው አይደለም በማለት የሚሰጡትን ብያኔ የሚመለከት ነው። እንደ ሐሳባውያን አመለካከት ማኅበራዊ ሕጎች መለኮታዊ ምንጭ ያላቸው በመሆኑ ወይም ደግሞ በሁለንታዊነታቸው ከመደቦች በላይ በመሆናቸው የኅብረተሰቡን አባል በሙሉ በእኩልነት የሚያገለግሉ ናቸው ። ይህም ማለት ሕጎች የተሳሳተ ፍች ወይም ይዘት ሊኖራቸው ቢችልም በመሠረቱ ግን በሕግነታቸው ከመደቦች በላይ ናቸው ። ይህ አመለካከት በብዝበዛ ሥርዓት ውስጥ የሕግን መደባዊ ጠባይ ለማዘናጋት የሚጥር ነው ።

ሆኖም የሕግ መደባዊ ምንጭ ሊካድ አይችልም ። ለምሳሌ የሰውን ጉልበት መበዝበዝ ለቡርዧዚው ሕጋዊ ሆኖ ሲታየው ለወዛደሩ ግን ሕጋዊ ወይም ትክክል አይደለም ። የግል ንብረትን የሚያስከብሩ ሕጎች በሙሉ ዋና ግባቸው የቡርዧዚውን ኅብረተሰብ ሥርዓት በማስያዝ ለቡርዧዚው ጠቃሚ የሆኑትን የምርት ግንኙነቶች ማስከበር ብሎም ማጠናከርና ማሳደግ ነው ። ሕግም በሕግነቱ ብቻ የሚሠራ ባለመሆኑ አስከባሪና አስፈጻሚ ኃይል ያስፈልገዋል ። በዚህ የተነሣ በሕግና በመንግሥት መካከል የጠበቀ ግንኙነት አለ። ለሕግ አስፈጻሚ ኃይል ማስፈለጉም የሚገልጸው የሕግን የመደብ ይዘት ነው ። የመደብ ሥርዓት እስካለ ድረስ ሕግ የአስገዳጅነት ጠባዩን አይተውም ።

በኮሚኒስት ሥርዓት ውስጥ የመንግሥት መክሰም የሕግንና የሕጋዊ ንቃተ ኅሊናን መክሰም ያስከትላል ። ይህ ማለት ግን ኮሚኒዝም ሥርዓት የለውም ማለት አይደለም ። ሥርዓቱ በኃይልና በመደብ ጭቆና ላይ የተመሠረተ ባለመሆኑ ሕግና ሕጋዊ ንቃተ ኅሊና ያላቸውን የማስገደድ ፍች ያጣሉ ። ኮሚኒስታዊ ንቃተ ኅሊና የሚገልጸው ራስን በራስ የማስተዳደር ደረጃን በመሆኑ ሕግና ሕጋዊ ንቃተ ኅሊና ከግለሰቦች ነፃ በሆኑና በዳበሩ ግብረገባዊና ባህላዊ አመለካከቶች ይተካሉ ማለት ነው ። ሕግ ከውጭ ሆኖ በኃይል የሚገዛ ሳይሆን ግለሰቦች በውስጣዊ ፍላጐትና ነፃ በሆነ መንገድ ወደው የሚያከናውኑት ይሆናል ።

(ኮሚኒዝምን ፣ ላዕላይ መዋቅርን ይመለከቷል ።)

## ሕግ
## (*Law*)

ሕግ በነገሮችና በክስተቶች መካከል ያሉ ውስጣዊ ፣ መሠረታዊ ፣ አስፈላጊና ቋሚ ግንኙነቶችን የሚገልጽና የነገሮችን ተፈጥሮአዊ ዕድገት የሚወስን ነው ። በክስተቶች ወይም በቁሳዊ ነገሮች ባሕርያት መካከል የሚገኙ መንሥኤንና ተገብሮትን እንዲሁም ተደጋጋሚ ግንኙነቶችን የሚገልጽ ጽንሰ ሐሳብ ነው ።

ውጫዊና አጋጣሚ ፣ አስፈላጊና ተደጋጋሚ ያልሆኑና በክስተቶች መካከል ያሉ ግንኙነቶች በሕግ የሚገለጹ ግንኙነቶች አይደሉም ። ምክንያቱም ከነገሩ ወይም ከክስተቱ ውስጣዊ ባሕርይ የማይመነጩ በመሆናቸውና ለክስተቱ ዕድገት ወይም መለወጥ አይቀሬ ባለመሆናቸው ነው ።

ሕግ በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ ተፈጻሚነት ያገኛል ። ለሕጉ የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች ሲጓሉ ግን በነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ

ሕጉ ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ። የስንዴ ዘር እርጥበት ፣ ሙቀትና አፈር ካገኘ ስንዴ ያበቅላል እንጂ ሌላ ነገር አያበቅልም ፤ መደቦች እስካሉ ድረስ መደቦችና የመደቦች ግንኙነት ቢቀየርም የመደብ ትግል በመደብ ኅብረተሰቦች ውስጥ ይኖራል ፤ ይህም የኅብረተሰብ ዕድገት ሕግ ነው ። የሸቀጥ ምርት እስካለ ድረስ የእሴት ሕግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ። ስለሆነም ሕግ የነገሮችን ባሕርይ በውል የሚያሳይና በመካከላቸው የሚገኙትንም መሠረታዊና አስፈላጊ ግንኙነቶች የሚገልጽ ነው ።

በሌላም በኩል የሕጐች ተፈጻሚነት በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ በመሆኑ እነዚህን ሁኔታዎች መፍጠር የሕጐችን ተፈጻሚነት ከይሁንታ ወደ እውነታ ለማሸጋገር ያስችላል ። ሕጐች በነባራዊ ዓለም ውስጥ በሚገኙ ነባራዊ ነገሮችና ክስተቶች መካከል ያሉትን ግንኙነቶች የሚገልጹ በመሆናቸው ነባራዊ ናቸውና ከሰዎች ኀሊናና ፍላጐት ውጭ ተፈጻሚነት አላቸው ። ይሁን እንጂ ሰው በተግባራዊ ክንዋኔው ውስጥ በሚያውቃቸው ሕግጋት ይጠቀማል ፤ ሕጐቹ ተፈጻሚ በሚሆኑባቸው ሁኔታዎች ላይ ተፅዕኖ በማሳደር በተፈጻሚነታቸው ባሕርይና ውጤቶች ላይ ለውጥ ለማድረግ ይችላል ። በኅብረተሰብ ውስጥ ሕጐች ተፈጻሚነት የሚያገኙት ሰዎች ዐውቀውትም ሆነ ሳያውቁት በሚያከናውኑት የመፍጠር ወይም የማጥፋት እንቅስቃሴ አማካይነት ነው ። ሰዎች ሕጐችን የመፍጠር ችሎታ ባይኖራቸውም የሕጐቹን የተፈጻሚነት መስክ ከፍላጐታቸውና ከጥቅማቸው አንፃር የማጥበብ ወይም የማስፋት ችሎታ ግን አላቸው ። ስለሆነም ሰዎች የማኅበራዊ ሕይወት ሕጐችን በመረዳት ዓላማ ባለው እንቅስቃሴያቸው አማካይነት በታሪክ ዕድገት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ ። ሕጐችን ማወቅ በታሪክ ግስጋሴ ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር ቢረዳም የሕጐች ዕውቀት ግን ረቂቅ አስተሳሰብን ፣ ከክስተቱ ወደ ፍሬ ነገሩ ሰርጾ መግባትንና የሚያስፈልጉትን ከማያስፈልጉት ባሕርያት ነጥሎ ማየትን ይጠይቃል ።

በነባራዊው ዓለም ውስጥ ተፈጻሚነት ያላቸው በርካታ ሕጐች ይገኛሉ ። እነዚህም ሕጐች ተፈጻሚነት በሚያገኙበት ዘርፍ ወይም ባላቸው የአጠቃላይነት መጠንና ደረጃ በልዩ ልዩ መልክ ይከፈላሉ ። ስለዚህም ግላዊ (የተወሰኑ) ፣ አጠቃላይና ሁለንታዊ ሕጐች ተብለው ይከፈላሉ ። ግላዊ የሚባሉት ሕጐች በተወሰኑ ክስተቶች መካከል ያሉ ግንኙነቶችን ብቻ ወይም የቁስ አካልን የተወሰኑ ባሕርያት ብቻ የሚገልጹ ናቸው ። አጠቃላይ የሚባሉት ሕጐች ደግሞ ሰፋ ባሉ ሁኔታዎች ውስጥ የሚታዩና ዓበይት ክስተቶችና ነገሮች ያሏቸውን አጠቃላይ ግንኙነቶች የሚገልጹ ናቸው ። ለምሳሌ አጠቃላይ ሕጐች ሕይወት ያላቸውንና ሕይወት የሌላቸውን ነገሮች ፣ በአንድ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ያሉ ነገሮችንና ክስተቶችን ግንኙነት የሚገልጹ ናቸው ። ሁለንታዊ የሚባሉት ሕጐች ደግሞ የዲያሌክቲካዊ ዕድገት ሕጐች ሲሆኑ እነርሱም በቁስአካል ዕድገት ሁለንታዊ ባሕርያትና አዝማሚያዎች መካከል የሚታዩትን ሁለንታዊ ግንኙነቶች የሚገልጹ ናቸው ።

ሕጐች በኅብረተሰብ ውስጥ የሚከሰቱበት ሁለት ገጽታ አላቸው ። አንደኛው ቀደም ብሎ ተገልጾአል ። ሁለተኛው ግን የመንግሥት ሕጐችን የሚመለከት ነው ። ሕጐች ግንኙነቶችን የሚገልጹ እንደመሆናቸው የንብረት ግንኙነቶችን የሚገልጹ (የወንጀልና የፍትሐብሔር) ሕጐች አሉ ። እነዚህም ሕጐች (በገዥው መደብ ፍላጐትና ጥቅም ተወስነው) የገዥው መደብ ፍላጐት ማስከበሪያ በመሆን በሥነ ሕግ አማካይነት ይገለጻሉ ፤ የአስገዳጅ ደንብነትንም መልክ ይይዛሉ ። የሕጋዊ ደንቦች ልዩ ባሕርይ በመንግሥት የሚደነገጉና በመንግሥት ኃይል አማካይነት ተፈጻሚነት የሚያገኙ መሆናቸው ነው ። ይህ ዓይነቱ ሕግ የላዕላይ መዋቅር ክፍል እንደመሆኑ በኅብረተሰቡ ሰፍኖና የበላይነት ይዞ በሚገኘው የምርት ግንኙነት ላይ የሚመሠረትና በርሱም የሚወሰን እንዲሁም ይህንኑ የምርት ግንኙነት በማጠናከር የገዥውን መደብ የሚያገለግል ነው ። ስለሆነም በታሪክ ውስጥ የታዩት የሕግ ዓይነቶች ከሥርዓተ ማኅበራት ጋር የሚጣጣሙ ናቸው ። እያንዳንዱም ሥርዓተ ማኅበር በምርት ግንኙነቶች የሚወሰን የራሱ የሆነ ሕግ አለው።

(ተፈጥሮን ፣ ላዕላይ መዋቅርን ፣ ፍሬነገርና ክስተትን፣ የዲያሌክቲክስ ሕጐችን ፣ የተፈጥሮ ሕግጋትን ይመለከቷል ።)

# ን

## ኂስና ግለኂስ
(*Criticism and Self-criticism*)

ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን መመሪያቸው ያደረጉ አብዮታዊ ፓርቲዎችና ሌሎች የሠራተኛ ድርጅቶች አብዮታዊ ተግባራቸውን በሚያካሂዱበት ጊዜ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የሚፈጽሙትን ስህተት በግልጽ እያነሡ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚተቻቹበት ፣ የሚወቃቀሱበት ፣ የሚተራረሙበትና ትምህርት የሚወስዱበት ዘዴ ኂስና ግለኂስ ይባላል ። ኂስና ግለኂስ በመመሪያቸው መሠረት ሕዝባዊ ዓላማቸውን ከግቡ እንዳያደርሱና ተግባራቸውን በትክክል እንዳይፈጽሙ ዕንቅፋት የሚሆኑባቸውን ስህተቶችና ድክመቶች የሚያስወግዱበት ፣ የድርጅታቸውን ዲሞክራሲያዊ አመራር የሚያጠናክሩበት ፣ የግል ወይም የቡድን ፈላጭ ቆራጭነትን ፣ አድርባይነትንና ለዘብተኝነትን የሚዋጉበት ውስጣዊ የትግል መሣሪያ ነው ።

ኂስና ግለኂስ በሚደረግበት ጊዜ ፓርቲው ባጠቃላይ ወይም የፓርቲው አካላት ወይም አባላት የፈጸሟቸውን ስህተቶችና የተከሰቱትን ድክመቶች እያነሡ እርስ በርስ በመተቻቸት ይተራረማሉ ፤ ይማማራሉ ፤ ሥራቸውንም በትክክል በመገምገም ለስህተታቸው መፍትሄ ይሻሉ ። ኮሚኒስታዊ ኂስና ግለኂስ በካፒታሊስቱ ኅብረተሰብና ድርጅቶች ውስጥ ከሚታየው በግል ጥቅም ማሳደድና ፉክክር ላይ ከተመሠረተውና የኅብረትና የመደጋገፍ ስሜት ከሌለው ግብዝና አፍራሽ ነቀፋ ፍጹም የተለየ ነው ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ኂስና ግለኂስ የሶሻሊዝም የማይፃረሩ ቅራኔዎች መፍቻና የአዲስ ኅብረተሰብና የአዲስ ሰው መገንቢያ መሣሪያ ነው ።

ኮሚኒስታዊ ኂስ ቂም በቀል የሌለበት ፣ እውነት ላይ የተመሠረተ ፣ የተፈጸመውን ስህተት ለማረም ሲባል የሚቀርብ እንጂ የተሳሳተውን ወገን ለማዋረድ ፣ ሞራሉን ለመስበር ፣ ተስፋ ለማስቆረጥና እርባና ቢስ ሆኖ እንዲቀር ለማድረግ ስበብ ፈልገው የሚያጠፉ ተንኮለኞች መሣሪያ አይደለም ። ኂስ ለፓርቲው ዕድገትና መሻሻል እንጂ ድርጅቱን የሚጎዳና አባላቱን የሚበታትን መሆን አይገባውም ። ስለሆነም ኂስ ሲቀርብ የሚቀርብበትን ጊዜ ፣ ቦታና ኂስ የሚቀርብበት አካል ወይም ግለሰብ ያለበትን ሁኔታ ማጤንና ወደ ባሰ ጥፋት የሚገፋፋው እንዳይሆን ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል ። ኂስ አድራጊው ብቻ ሳይሆን ኂስ የሚቀርብበትም አካል ወይም ግለሰብ ምንም ዓይነት ቅሬታ ሳይሰማው ኂሱን መቀበል ብቻ ሳይሆን በቀረበለት ኂስ መሠረት አመለካከቱንና አሠራሩን በማስተካከል ለመጠናከር ቀና ጥረት ማድረግ አለበት ። በአጠቃላይ ኂስ ለማድረግም ሆነ ለመቀበል ከፍተኛ ንቃትና ብስለት ይጠይቃል ።

ኂስ ፣ አፍራሽም ገንቢም ገጽታ አለው ። አፍራሽ ኂስ የተፈጸሙትን ጥቃቅን ስህተቶች ምክንያት አድርጎ የማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ፈር ለማሳት ፣ ድርጅትን ለማዳከም ፣ አባላቱን ለመበታተን ፣ የተሠሩ ሥራዎችን ለማንኳሰስ ፣ ተስፋ ለማስቆረጥና ግለሰቦችን ለመጉዳት የሚቀርብ ትችትና ነቀፋ ነው ። በአኳያው ደግሞ ገንቢ ኂስ ስህተትንና ድክመትን ለመጠቆምና ለማረም እንዲቻል በቀና አስተሳሰብ የሚሰነዘር ወቀሳ በመሆኑ ለመሻሻልና ለዕድገት ጠቀሜታ አለው ። ይህም ስህተቶች ሳይድበሰበሱ ያለምንም ይሉኝታ በግልጽ እንዲወጡ ፣ ምክንያታቸው ታውቆ የሚታረሙበትን መንገድ በውይይት ለመፈለግ ሲባል የሚቀርብ አጠናካሪ ትችት ነው።

በማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ አሠራር ኂስ በሌሎች ላይ ብቻ ሳይሆን በራስም ላይ ይካሄዳል ። ግለ ኂስ ራስን በራስ መተቸት ፣ መውቀስ ፣ ሳይፈሩና ሳያፍሩ የራስን ስህተትና ድክመት በራስ ተነሣሥቶ ይፋ አውጥቶ መናገርና ዓላማንና ተግባርን የሚያደናቅፍ ፣ ድርጅትን የሚጎዳ ስህተት መፈጸሙን ተገንዝቦ በቅንና በአብዮታዊ መንፈስ ራስን በራስ መውቀስና ከስህተትም በመማር ለመታረም ዝግጁ መሆንን ያረጋግጣል ። ሌኒን እንዳለው አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በራሱ ላይ

የሚያካሂደው ትክክለኛ ኂስ ሐቀኝነቱንና በር ግጥም ለመደቡና ለሠርቶአደሩ ሕዝብ ጥቅ ምና ደኅንነት መቆሙን ለማየት ከሚያስ ችሉ መንገዶች ዋነኛው ነው ።

## ኃብር

ኃብር ፤ በወላንድ ውስጥ የሚገኝ አንድ ግብረ ኃይል ነው ። በወልባ ደረጃ የተደ ራጁ የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት በውህደት ወላንድ ሲመሠርቱ እያንዳንዱ የአ ምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር (ወልባ) መሆኑ ቀርቶ የወላንድ ኃብር ወይም ግብረ ኃይል ይሆናል ። አንድ ኃብር በአማካይ 800 ሄክታር ይዞታና 500 አባላት ይኖሩታል ። የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት በረጅም የዕድገት ደረጃ ሂደት ውስጥ ኃብር የሚመ ሠርቱት ግብርና በከፍተኛ ቴክኖሎጂ እየተረዳ ሰፊና ጥቅል የሆነ የእርሻ፣ ሥራ ክፍፍል ለምሳሌ የከብት ርቢ ፣ የዶሮ ርቢ፣ የአዝርዕት ምርት ወዘተ... ሲፈጠር ነው ። እንደአስፈላጊነቱና ለሥራ አመች በሚሆን መንገድ ኃብር በሥሩ የሥራ ቡድኖች ሊኖ ሩት ይችላሉ ።

(ወልባን ይመለከቷል ።)

## ኃይል ማቀላቀል (በ—)

*(Annexation)*

በከፊልም ሆነ በሙሉ አንድ መንግሥት የሌላውን መንግሥት ግዛት በኃይል በመጠቀም በቁጥጥሩ ሥር የማድረጉን ሁኔታ ያመለክታል። ይህም አድራጐት በእብሪት የሚፈጸም ነው ። ግዛቱን በኃይል የያዘውም መንግሥት በያዘው ግዛትና ሕዝብ ላይ ሙሉ ሥልጣን ይኖረዋል ። የጀርመን ናዚዎች በ1938 ኦስትሪያን ፣ በ19 39 ደግሞ ብዙ የቼኮዝሎቫኪያን ግዛቶች በኃይል መያዝና የጀርመን ግዛት አካል ማድ ረግ ፣ የፋሺስት ፕሪቶሪያ መንግሥት ከ19 68 ጀምሮ ናሚቢያን በኃይል ይዞ እስከዛሬ መቆየት ፣ የጽዮናዊት እስራኤል የአረብ ግዛ ቶችን በቁጥጥሯ ሥር በማዋል አልለቅም ማለት ወዘተ... ለዚህ ምሳሌ ሊሆኑ የሚ ችሉ ናቸው ። እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት በሁለት ሀገሮች መካከል በሚደረግ ስምም ነት ፣ በግዥ ፣ በኪራይና በመሳሰሉት ተይ ዘው የሚገኙ ግዛቶች በኃይል እንደተያዙ የማይቆጥሩ መሆናቸው ነው ። ኢምፔሪያሊስ ቶችና አድኅሮት ኃይላት በየጊዜው በእብ ሪት ተነሣሥተው የሌላውን ግዛት በኃይል መያዛቸው ዛሬም አልፎ አልፎ የሚታይ ቢሆንም ድርጊቱ በዓለም አቀፍ ሕግ በጥ ብቅ የተከለከለና የተወገዘም ነው ።

## ኅሊና

*(Conscience)*

ኅሊና የሰው ልጅ በኅብረተሰብ ውስጥ ሲኖር ስለአካባቢው የሚኖረው ግንዛቤና በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ኃላፊነት የሚ ያውቅበት ፣ ግለሰቡም ስለራሱ ድርጊትና ጠባይ የሚያጤንበት ልዩ ልዩ መልክ ያለው ስሜታዊ ክስተት ነው ። ኅሊና በተ ፈጥሮ የሚገኝ ሳይሆን የሰው ልጅ በኅብ ረተሰብ ውስጥ ባለው ስፍራ ሊጫወተው ከሚገባው ሚና ጋር አብሮ የሚፈጠርና የሚ ያድግ ነው ። ለምሳሌ የኑሮው ሁናቴ ፣ ገጠመ ኙና አስተዳደጉ ወዘተ... ኅሊናው እንዲኑ ለምስ ያደርጉታል ። አንድ ግለሰብ ሊፈጽ መው የሚገባውን ተግባር ማከናወኑን መገ ንዘቡ ኅሊናው ነው ። በአንፃሩም ተግባሩን ባለማሟላቱ ጸጸት ያድርበታል ፤ ይህም ኅሊና ነው ። ግለሰቡ በኅብረተሰቡ የሚፈለ ግበትን ግዴታ እንዲያሟላ ኅሊና የግፊት ኃይል ሆኖ ይሠራል ።

(ሥነ ምግባርን ይመለከቷል ።)

## ኅሊናዊ

*(Subjective)*

በሰው ንቃተ ኅሊና ውስጥ የነባራዊው ዓለም ነፀብራቅ የሆኑ ፣ ግላዊና ማኅበራዊ ኑሮን የሚገልጹ አስተሳሰቦች በሙሉ ኅሊ ናዊ ይባላሉ ። ኅሊናዊ በንቃተ ኅሊና ውስጥ ብቻ የሚከሰት አምሳላዊ ህልውና ያለው ነገር ነው ።

ነባራዊው ከኅሊናዊው የሚለየው ነባራ ዊው ከንቃተ ኅሊና ውጭ በመሆኑ በራሱ ነፃ ህልውና ያለው መሆኑ ነው ። ኅሊናዊ ከንቃተ ኅሊና ውጭ ህልውና የሌለው በመ ሆኑ የንቃተ ኅሊና ክስተት ነው ። ኅሊናዊ የነገሮች አምሳል ብቻ በመሆኑ የራሱ ህል ውና የሌለው ቢሆንም በተግባር ነባራዊ ሊሆን ይችላል ። ሰዎች ነባራዊውን ዓለም

በመለወጥ ለነሱ ተስማሚ የሚያደርጉት በንቁ እንቅስቃሴ አማካይነት በመሆኑ ይህ ንቁ እንቅስቃሴ ያዘለው ዕቅድ ፣ ፍላጐትና ዕውቀት በተግባር ሲተረጐም ኅሊናዊ የነበረው ነባራዊ ሆነ ማለት ነው ።

(አምሳልን ፣ ነባራዊን ይመለከቷል ።)

## ኅሊናዊ ሁኔታ
## (*Subjective Condition*)

የማኅበራዊ ሕይወት ነባራዊ ሁኔታዎችን ለማቆየት ፣ ለመለወጥና ለማሳደግ ሰዎች (ሰፊው ሕዝብ ፣ መደቦች ፣ ፓርቲዎች) የሚያደርጉት ንቁና ዓላማ ያለው እንቅስቃሴ ነው ። የአብዮት ኅሊናዊ ሁኔታዎች ዋና ዋና ገጽታዎች የፖለቲካ ንቃትን ፣ ድርጅትንና ሰፊው ሕዝብ በግንባር ቀደም አብዮታዊ ፓርቲው አመራር ሥር ለትግል ያለውን ቁርጠኝነት ፣ ዝግጁነትና ፍላጐት ያጠቃልላሉ ።

አብዮት እንዲፈነዳና ግቡንም እንዲመታ ከነባራዊ ሁኔታ ሌላ የኅሊናዊ ሁኔታ ተሟልቶ መገኘትም የግድ አስፈላጊ ነው ። ማናቸውም ማኅበራዊ አብዮት የነባራዊና የኅሊናዊ ሁኔታዎች አንድነትና ተባባሪነት ቢያስፈልጉትም የኅሊናዊ ሁኔታ በተሟላ መልኩና በሰሉ የመገኘቱ አስፈላጊነት ግን የሶሻሊስት አብዮት ዓይነተኛ ባሕርይ ነው ።

ኅሊናዊ ሁኔታ ዘርዘር ባለ መልኩ ሲታይ አብዮቱን በድል አድራጊነት ከግቡ ለማድረስ የሰፊውን ሕዝብ አብዮታዊ ንቃት ፣ ዝግጁነትና ቆራጥነት ፣ አብዮታዊ ኃይሉን በተናጠል ሳይሆን አሰባስቦ በአንድነት እንዲታገሉ የሚያደርግ ድርጅት መኖርን ያጠቃልላል ። ይህም አብዮታዊ ፓርቲ በትግል የተፈተነ ፣ በቂ ልምድ ያለው ፣ ታክቲኩና ስትራቴጂውን በመቀየስና በተግባር በመተርጐም ትክክለኛነቱን ሲያሳይና የሰፊውን ሕዝብ ድጋፍና ትብብር ሲያገኝ ኅሊናዊ ሁኔታ ተሟልቷል ይባላል ።

ነባራዊ ሁኔታ ወሳኝ ቢሆንም ከንዋኔ የሚያገኘው በኅሊናዊ ሁኔታዎች አማካይነት ነው ። ኅሊናዊ ሁኔታ በተራው የወሳኝነት ሚና የሚኖረው ለከንዋኔው የሚያስፈልጉት ነባራዊ ሁኔታዎች በሰለውና ተመቻችተው ሲገኙለት ብቻ ቢሆንም ኅሊናዊ ሁኔታም ነባራዊ ሁኔታን የማመቻቸት ሚና ሊጫወት ይችላል ። የኅሊናዊ ሁኔታ ተፅዕኖ ጉልቶ የሚታየው ከአንድ ሥርዓተ ማኅበር ወደ ሌላ አዲስና ተራማጅ ሥርዓተ ማኅበር ሽግግር በሚደረግበት ወቅት ነው ። በሶሻሊስት አብዮትና ከዚያም በግንባታው ውስጥ በማናቸውም የማኅበራዊ ሕይወት ዘርፍ የሚታይ ዕድገት በዕቅድ ላይ የተመሠረተና ለተግባራዊነቱም የሰፊው ሕዝብ ተሳትፎ የሚያስፈልገው በመሆኑ የኅሊናዊ ሁኔታ አስፈላጊነት ጉልቶ ይታያል ።

ካፒታሊዝም ዕድጉ ወደ መጨረሻው ደረጃ ማለትም ወደ ኢምፔሪያሊዝም ደረጃ በተሸጋገረበትና ከዚህም የተነሣ በተለይ በበለጸጉት ሀገሮች የሶሻሊስት አብዮት ነባራዊ ሁኔታ ተሟልቶ በሚገኝበት ወቅት አብዮት አለመካሄዱ የኅሊናዊ ሁኔታን ወሳኝነት ከመቸውም ጊዜ አጉልቶ ያሳያል ። ይህም ማለት ኅሊናዊ ሁኔታ በካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ አሁን ያለውን የወሳኝነት ሚና ብቻ ሳይሆን ኅሊናዊ ሁኔታ ከነባራዊ ሁኔታ ጋር ሁልጊዜ በእኩል ሊራመድ የማይችል መሆኑንም ጭምር የሚያሳይ ነው ።

(ነባራዊ ሁኔታን ይመለከቷል ።)

## ኅሊናዊ ሐሳባዊነት
## (*Subjective Idealism*)

ከነባራዊ ሐሳባዊነት ጋር አግባብ የለኝም የሚልና ይህንኑ አመለካከት የሚቃረን ፣ በእንፃሩም ከነባራዊ ሐሳባዊነትና ከቁስ አካልነት የተሻለ አመለካከት አለኝ በማለት እራሱን እንደ ሦስተኛ አማራጭ አድርጐ የሚያቀርብ ሐሳባዊ የፍልስፍና አዝማሚያ ነው ።

የኅሊናዊ ሐሳባውያን መሠረታዊ አስተሳሰብ እሳቦት ሊገናኝ የሚችለው ከኅሊናዊ ክስተቶች ጋር ብቻ ነው የሚለው ነው ። ኅሊና ከራሱ ክልል መውጣት ስለማይችል የግንዛቤ መነሻ ተደርጎ መወሰድ ያለበት ነባራዊው ዓለም ሳይሆን ለግንዛቤ የሚቀርቡት ሕውስታዎችና ሐሳቦች ናቸው ። ልናውቅ የምንችለው ኅሊናዊ ነገርን ብቻ በመሆኑ ለኛ የዓለም መኖርና ምንነት በኅሊናዊ እይታው ብቻ የሚወሰን ነው ።

በኀሊናዊ ሐሳባውያን አመለካከት የሕውስታዎችና የሐሳቦች ምንጭ ምንድነው የሚለው ጥያቄ መልስ ሊያገኝ አይችልም ። በእነሱ አመለካከት ቁስአካላውያንና ነባራዊ ሐሳባውያን ለዚህ ጥያቄ የሚሰጧቸው የተለያዩ መልሶች አንዳቸውም ሊረጋገጡ አይችሉም ። የሕውስታዎችና የሐሳቦች ምንጭ ቁስአካል ነው የሚለው የቁስአካላውያን መልስ ሊረጋገጥ አይችልም ፤ ምክንያቱም ከራሳችን ኀሊና መውጣት የማንችል እስከሆን ድረስ ቁስአካል በነባራዊነት ለመኖሩ መረጃ የለንም ። ነባራዊ ሐሳባውያን የሚሉትም ከተጨባጩ የራቀ ነው ። ሐሳብ እኛ ውስጥ እንዳለ እናውቃለን እንጂ ከኛ ውጭ በነባራዊነት በመኖር የሕውስታዎችና የሐሳቦች ምንጭ ለመሆኑ ምንም ማስተማመኛ የለንም ይላሉ ።

ለዕውቀት ዋጋ መስጠት ያለበት በነባራዊነቱ ወይም የነባራዊው ትክክለኛ ግልባጭ በመሆኑ አይደለም ። የዕውቀት ተደራጊ ኀሊናዊ ክስተቶች በመሆናቸው ማወቅ ማለት የነዚህን ክስተቶች የአመጣጥ ፣ የሥርዓትና የለውጥ ሕጎችን ማጤን ማለት ነው ። ዕውቀት የሚለካው ለተግባር በሚሰጠው ጥቅም እንጂ የነባራዊውን ዓለም ምሥጢር በመፍታቱ አይደለም ። ኀሊናዊ ሐሳባዊነት ዕውቀትን ኀሊናዊ ብቻ በማድረጉ የሚያመራው ወደኢታዋቂነት ነው ።

በኀሊናዊ ሐሳባውያን አመለካከት ቁስአካልነትና ነባራዊ ሐሳባዊነት ቀኖናዊ አስተሳሰቦች ናቸው ። የዓለምን ምሥጢር እናውቃለን ማለታቸው የሰው የዕውቀት ችሎታ ውሱን መሆኑን ባለመገንዘባቸው ነው ። ስለዚህም ሰዎች ካፈሯቸው አስተሳሰቦች ውስጥ ረቂቅና አከራካሪ የሆኑትን ወደጎን በመተው ጠቃሚ የሆኑትን ብቻ ማስቀረት ይኖርብናል ።

ኀሊናዊ ሐሳባውያን የዓለም ምሥጢር ለሰው ልጅ ታዋቂ አይደለም በሚል ሳቢያ ትክክለኛው አስተሳሰብ ከቀኖና የራቀ ነፃዊ አመለካከት መያዝ ነው የሚለው አቋማቸው ኅብረተሰብ ፣ ተፈጥሮና ሰዎች እራሳቸው ለሰዎች ምሥጢራዊና እንግዳ ሆነው እንዲታዩ የሚያደርግ ነው ። ለሕጎች ኀሊናዊ ፍች ብቻ በመስጠት ሰዎች በነገሮች እይታ ብቻ እንዲወሰኑ የሚገፋፋ ነው ። ሰው በነባራዊነት የሚያውቀው ነገር ከሌለ የሚመሰለውን ፣ የሚታዘዘውንና የሚነገረውን መቀበል ብቻ ነው ። ሰው ስለእውነት ፣ ስለስህተት ፣ ስለጥሩና ስለክፉ ወዘተ... ልዩነት በትክክል የሚያውቀው ነገር የለም ማለት ነው ።

ይህ አመለካከት ለበዝባዥ መደብ አገዛዝ አመች ነው ። እውነት የማይታወቅ ከሆነ ፣ ስለመብትና ስለግዴታም ሰው የሚጠይቀው ፣ የሚከራከረውና የሚታገለው ነገር የለም ። የኀሊናዊ ሐሳባዊነት ውስጠ ምሥጢር ሰውንና ኅብረተሰብን ጥርጣሬ ውስጥ በመክተት ልቅ በሆነ አስተሳሰብ ውስጥ እንዲዋኙ ማድረግ ነው ።

(ፍልስፍናን ፣ ካንትን ፣ በርክሌይን ፣ ሂዩምን፣ ኢታዋቂነትን ፣ ተጨባጫዊነትን ፣ ገቢራዊነትን ይመለከቷል ።)

## ኅሩያን ምስፍና (የ—)
*(Aristocracy)*

በኅብረተሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ባላቸውና “ምርጥ” ነን በሚሉ ጥቂት በዝባዥ ሰዎች የመንግሥት ሥልጣን የተያዘበት የአገዛዝ ቅርፅ ነው ። ይህ አገዛዝ በአብዛኛው እውን የሆነው በባሪያ አሳዳሪውና በፊውዳሉ ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ ነው ።

የኅሩያን ምስፍናን መንግሥታዊ አመራር የሚደግፉ ባለሥልጣኖችና የፖለቲካ ፈላስፎች (አፍላጦን ፣ ስፒኖዛ ፣ ሆብስ ወዘተ...) የሰነዘሩአቸው አስተያየቶች በተለያዩ ገጽታዎች ቢቀርቡም ሁሉም የሚነሡት ከአንድ መሠረታዊ ሐሳብ ነው ። ይህም የሀገር አስተዳደርና የመንግሥት ሥልጣን አመራር ውስብስብ በመሆኑ ከፍተኛ ችሎታና ልዩ ሰዎችን የሚጠይቅ ነው ፤ ስለዚህም ከማንኛውም ዜጋ የተውጣጣ ኃይል ሊያካሂደው አይችልም ። የዚህ ዓይነቱ ኃላፊነት በትውልድ ለተመረረጡ ፣ በተለየ ስጦታቸውና የችሎታ ብቃታቸው ለላቁ ለተወሰኑ ምርጥ ሰዎች ብቻ መሰጠት አለበት የሚል ነው ። እርግጥ እያንዳንዱ የመንግሥት ሥልጣን በኅሩያን መሳፍንት የተያዘበት ሀገር እንደ ታሪካዊ ዕድገቱና በወቅቱ እንደሰፈነው ተጨባጭ ሁኔታ አንዳንድ የተለዩ ባሕርያት ታይተውበታል ። በዚህ ረገድ የጥንታዊ ስፓርታ ፣ የሮም ፣ የካርቴጅ ፣ በኋላም የእንግሊዝ ፣ የፈረንሳይና የሩስያ ፊውዳላዊ ሥርዓቶችና ሌሎችም ሲጤኑ አንዱ

ይበልጥ በሥርወ ትውልድ ሐረግ ላይ ያተኮረ ፥ ሌላው ደግሞ አንዳንድ ሰዎች በጀግንነት ፥ በጋብቻ ፥ በኢኮኖሚ ኃይላቸውና በመሳሰሉት የሚታከሉበት ፥ ሌላው ደግሞ በተወሰነ የቤተመንግሥት አካባቢ ውሳኔና ምርጫ እስከተወሰነ እርከን ሰፋ ያለ ተሳትፎ የሚደረግበት ሆኖ ይገኛል ።

ይሁን እንጂ የኅሩያን ምስፍና መሠረታዊ ባሕርይ ሠርቶ አደሩን ሕዝብ የመናቅ ፥ ከፖለቲካና ከአስተዳደር ሕይወት ጨርሶ የማግለል፥ ሕዝቡ በምርጫ እንደራሴዎች የሚወከልበትን ሁኔታ የመከልከል ወይም የማጥበብ ወይም ምርጫ ለይስሙላ ቢኖርም ተመራጮችን ሥልጣንና ተሰሚነት መንሣት ፥ በነዚህና በመሳሰሉት ስልቶችም በመጠቀም የጥቂት "ምርጥ ዜጎች"ን አምባገነንነት በማስፈን ሠርቶ አደሩን ሕዝብ መጨቆንና መበዝበዝ ነው ።

በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የዘር ግንድ እየቆጠሩ በፈላጭ ቆራጩ አገዛዝ ሥር ንጉሣውያን ቤተሰብ ፥ መሳፍንት ፥ መኳንንት ወዘተ... በመባባል የፊውዳሉ ሥርዓት አቀንቃኞች ሲሞካሹና በአእምሮ ሆነ በጉልበት ሥራ አስተዋጽኦ ሳያደርጉ ፥ ባላመረቱት የሀገሪቱ ሀብትና ንብረት ሲንደላቀቁ የነበሩት አድኃሪያን ሁኔታም ይህንኑ ይመስል ነበር ። ኋላቀር በሆነችው ሀገር ጥቂት ኅሩያን መሳፍንት በዚያ መልክ ሊዘባነኑ የቻሉት ሰፊውን ሕዝብ ለችግርና ለጉስቁልና በመዳረግ ነበር ፥ ብዝበዛ የመረረው ሕዝብ እንደ ኢት. ዘ. በ1966 በአመፅ ተነሣሥቶ ገርስሷቸዋል ።

## ኅቡእ
(*Clandestine*)

ድብቅ ፥ ምሥጢር ፥ ይፋ ያልሆነ ማለት ነው ። በፖለቲካ አጠቃቀሙ ብዙውን ጊዜ በሁኔታዎች አስገዳጅነት በስውር እንጂ በይፋ የማይሠራ ፥ ሕጋዊ መድረክ የሌለው፥ ውስጥ ለውስጥ የሚታገል ተቀናቃኝ ኃይል ነው ። በዓላማና በይዘት ቢለያዩም አብዮታውያንም ሆኑ ፀረ አብዮታውያን በዚህ የትግል ስልት የሚጠቀሙ መሆናቸው ይታወቃል ።

(ሕጋዊ መድረክን ይመለከቷል ።)

## ኅብረት ሥራ ማኅበር (የ—)
(*Cooperatives*)

አነስተኛ የኢኮኖሚ ይዞታ ወይም ገቢ ያላቸው ግለሰቦች ገንዘባቸውን ወይም የማምረቻ መሣሪያቸውንና ጉልበታቸውን በማስተባበር ምርታቸውን ለማሳደግና የኑሮ ደረጃቸውን ከፍ ለማድረግ ወይም የተሻለ አገልግሎት ለማግኘት በፈቃደኝነት የሚያቋቁሙት ድርጅት ኅብረት ሥራ ማኅበር ይባላል ።

ሰው አብዛኛውን ሥራ የሚሠራው በኅብረትና በትብብር መሆኑ የታወቀ ነው ። በሀገራችን በማኅበራዊም ሆነ በኢኮኖሚያዊ መስክ በጋራ መረዳጃ ማኅበራት ማለትም እንደ ዕድር ፥ እንደ ዕቁብ ፥ እንደ ወንፈል ፥ እንደ ጅጌ ፥ እንደ ደቦ በመሳሰሉት መሳተፍ የተለመደ ነው ። ሆኖም የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ከነዚህ ልማዳዊ መረዳጃ ማኅበራት የሚለያቸው የተወሰነ ቁጥር ያላቸውን ግለሰቦች በአባልነት የሚያቅፉ ሆነው ለአንድ የተወሰነ ግብ ፥ አንፃራዊ ዘለቄታና ጠቀሜታ ላለው ዓላማ በጋራ የሚያስልፉ የኢኮኖሚ አካል ድርጅት መሆናቸው ነው ።

የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ይዘት ፥ ሚና ፥ ቦታና ዕድገት የሚወስነው የሚገኙበት የምርት ግንኙነት ነው ። በዚህም መሠረት የካፒታሊስትና የሶሻሊስት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ይገኛሉ ። ከካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር በፊት በነበሩት ሥርዓተ ማኅበራት የኅብረት ሥራ ማኅበራት አልነበሩም።

የኅብረት ሥራ ማኅበራት መቋቋም የጀመሩት የካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር እያደገ በሄደበት በ19ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ላይ ነበር ። በዚህ ወቅት በወዝአደሩ ላይ ይካሄድ የነበረው ብዝበዛ እየተባባሰ በመምጣቱ በቡርዧዚውና በወዝአደሩ መካከል የነበረው ቅራኔ ተፋፍሞና ተካሮ ነበር ። ስለዚህም በኅብረት መደራጀት ወዝአደሩ በወቅቱ ይደርስበት የነበረውን ብዝበዛ ለመከላከል የፈጠረው ዘዴ ነው ።

የኅብረት ሥራ ማኅበራት ወዝአደሩን አሰባስቦ በማኅበር የመሥራት ልምድ እንዲያገኝ በማድረግና አንዳንድ ውሱን የሆኑ ጊዜያዊ ችግሮችን በመቋቋም ረገድ ያገለገሉ

# ለ

## ለውጥ
(*Change*)

ቁስአካል ፣ ኅብረተሰብና የሰው አስተሳሰብ ጭምር የሚያደርጉት ወይም የሚያሳዩት የመጠን ወይም የዓይነት ቅየራ (መቀየር) በአጠቃላይ ለውጥ ይባላል ። ለውጥ እንደ ቅስቃሴ ፣ እንደ ጊዜና እንደ ቦታ ሌላው የቁስአካል የህልውና ገጽታ ነው ።

ለውጥ ማንኛውንም አካልና ክስተት ፣ ማንኛውንም ቅስቃሴና (እንቅስቃሴ) መስተጋብር ያቅፋል ። ስለሆነም ለውጥ እንደ ቁስአካል ሁለንታዊ ፣ ፍጹማዊ ፣ ዝንተዓለማዊና ሊፈጠር ወይም ሊጠፉ የማይችል ነው ። ለውጥ በተለያዩ ቅርፆች ፣ ይዘቶች ፣ ሥርዓቶች ወዘተ... ውስጥና መሀከል ባለው መስተጋብር አማካይነት ይከናወናል ። የለውጥ አቅጣጫውና የውጤቱ ባሕርይ የተለያየ ሊሆን ይችላል ። ለምሳሌ ፣ ውሀ ወደ በረዶ ፣ ወደ እንፋሎት ይለወጣል ። ሰው ሲሞት ወደ አፈርነትና ወደ ሌሎች ንጥረ ነገሮች ይለወጣል ። የካፒታሊስት ሥርዓት ወደ ሶሻሊዝም (ኮሚኒዝም) ይለወጣል ።

ይሁንና የሐሳባውያን የለውጥ ትርጉም ከዚህ የተለየ ነው ። አንዳንዶቹ የለውጥን መኖር ሲክዱ ፣ ሌሎቹ ደግሞ የለውጥን መኖር ቢቀበሉም እንኳ የመጠን ብቻ እንጂ የዓይነት ለውጥ እንደማይኖር ፣ ዕድገትን ደግሞ የመጠን መጨመር ብቻ እንደሆነ አድርገው ይወስዳሉ ፣ የዚህ ለውጥ ምንጭም ውጫዊ ኃይል ነው ይላሉ ። ነገር ግን የሰው ፣ የኅብረተሰብ እንዲሁም በአጠቃላይ የተፈጥሮ ዕድገት አመጣጥ የሐሳባውያንን አመለካከት ኢሳይንሳዊነት በግልጽ ያሳያል ። ለምሳሌ ሰው ከእንስሳነት አሁን ወደአለበት ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ መድረሱ የዓይነት ለውጥ መኖሩን በገሀድ ይመሰክራል ። ይህም ለውጥ የሚመጣው በያንዳንዱ ቁስአካል ወይም ማኅበራዊ ግንኙነት ውስጥ ከሚካሄደው የነገሮች አሰሳሰፍና ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት ፣ ትግል ወይም ፍጭት እንጂ ሐሳባውያን እንደሚሉት ከውጭ በሚመጣ መንፈሳዊ ኃይል አይደለም ። ለምሳሌ በአንድ ቁስአካል ውስጥ ያሉ የተቃራኒዎች ባሕርያት ትግል የለውጡ ምንጭ ነው ። በኅብረተሰብም ውስጥ በመደቦች መካከል የሚካሄደው ውስጣዊ ትግል እንደቅራኔው ሁኔታ የተለያዩ ለውጦችን ያስከትላል ።

(ዲበአካልን ፣ የቅራኔዎች አንድነትና ትግል ሕግን ይመለከቷል ።)

## ለዘብተኝነት
(*Liberalism*)

በማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ ውስጥ የተሰለፉ አባላት ለፓርቲው ደንብና ሥርዓት ግድየለሽ በመሆን ወይም በይሉኝታ በመያዝ ወዘተ... የሚያሳዩት የምንቸገረኝነት ስሜት ነው ።

በሠራተኛው እንቅስቃሴ ውስጥ ለዘብተኝነት በብዙ ዓይነት መንገዶች የሚከሰት ሲሆን ምንጩም የንዑስ ከበርቴው ራስ ወዳድነት ነው ። የለዘብተኝነት ምልክቶች በሚከተሉት ነጥቦች ሊጠቃለሉ ይችላሉ ። ድርጅቱንና አጥፊ ግለሰቡን ራሱንም ቢሆን የሚጐዳ ስህተት ሲሠራ እያዩ በጓደኝነት ፣ በዝምድናና በአጠቃላይም ባለመቃረን ሲሉ ነገሩን አድበስብሶ ማለፍ ፣ ፊት ለፊት በግልጽ ሂስ ከማቅረብ ተቆጥቦ ውስጥ ውስጡን ሐሜት ማካሄድ ፣ ከኅብረተሰቡ ጥቅም ይልቅ ለግል ጥቅም መገዛት ፣ ራስን እስካልነካ ድረስ ማንኛውንም ስህተትና የሰፊውን ሕዝብ ደኅንነት የሚጐዳ ድርጊት ሲፈጸም እያዩ እንዳሳዩ ሆኖ ማለፍ ፣ ስህተትን በትክክል ማረም ሲቻል ለመወደድ ሲባል መሠረተ ቢስ መከላከያ ማቅረብ ፣ ለራስ ሐሳብ ብቻ ከፍተኛ ግምት በመስጠት የድርጅቱን ትዕዛዝ አለማክበርና ዲሲፕሊን አለመጠበቅ ፣ ለአንድነት ፣ ለዕድገትና ለሥራ መቃናት ሲባል በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ በግልጽ ከመወያየትና ከመከራከር ይልቅ በግለሰብ ላይ ጠብ መጫርና የቆየ ቂምን ለመወጣት መሞከር ፣ ገለልተኛ በመሆን የተሳሳተ ትችት እየሰሙና ፀረ አብዮት ቅስቀሳ ሲደረግ እያዩ ሁኔታውን በወቅቱ ከመጠቆምና ከማጋለጥ መቆጠብ ፣ በሰፊው ሕዝብ

መሃል እያሉ የሕዝቡን ችግር በማጥናት ለመፍትሔው ተገቢውን ትስተሳና ጥረት አለማድረግ ፤ ዕቅድ የሌለው የግብር ይውጣ ሥራ መሥራት ፤ ራስን የአብዮት ባለውለታ አድርጐ በመቁጠር ተላል ሥራዎችን መናቅና በአንፃሩ ግን ለከፍተኛ ሥራዎች ደግሞ ደካማ ሆኖ መገኘት ፤ የሠሩትን ስህተት እያወቁ ለመገለጽና ለማረም አለመፈለግ ናቸው ። በአጠቃላይ ለዘብተኝነት የአድርባይነት መከሰቻ ሲሆን የርዕዮተዓለም ትግልን የማይቀበል፣ የፖለቲካ ድርጅትን አንድነት የሚያናጋና ጠላትን ብቻ የሚጠቅም አድኃሪ ፈለግ ነው ።

(አድርባይነትን ይመለከቷል ።)

## ሉዓላዊነት
## (*Sovereignty*)

ሉዓላዊ የግዕዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙም የበላይነት ያለው ማለት ነው ።

አንድ መንግሥት የውስጥና የውጭ ፖሊሲውን ለመንደፍና በተግባር ላይ ለማዋል ያለው የመጨረሻው ከፍተኛና ነፃ የሆነ ሥልጣን ወይም ኃይል ነው ። ሕገ መንግሥታዊ ሕግን በሚመለከት ረገድ ሉዓላዊነት የሚለውን ቃል በአሥራ ስድስተኛው ምዕት ዓመት በጥቅም ላይ ያዋለው ዦን ቦዳ የተባለ ፈረንሳዊ ምሁር ነበር ። ከዚያም ቡርዧዚው ከፊውዳሊዝምና ከነገሥታት የሥልጣን ፍጹማዊነት ጋር በሚያደርገው ትግል የሕዝብን ድጋፍ ለማግኘት ሲል የሉዓላዊነትን ጽንሰ ሐሳብ በሰፊው ተጠቅሞበታል ። መደባዊ እንደሆነው እንደ መንግሥቱ ሥልጣን ጠባይና እንደ ኅብረተሰቡ የኢኮኖሚ መዋቅር ሉዓላዊነትም በተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓቶች የተለያየ ይዘት ይኖረዋል ። በሶሻሊስት ሀገሮች የሉዓላዊነት መሠረት የሕዝብ ሥልጣን ነው ።

ሉዓላዊነት የሚገለጸው በአንድ መንግሥት አሠራር ቢሆንም በይፋ ግልጽ ሆኖ የሚታየው ግን ነፃ የመሆን መብትን ጨምሮ መንግሥት በሚቀይሰው የመብት ሥርዓት ነው ። መንግሥት ሥልጣኑንና የበላይነቱን የሚያረጋግጠው ባለው ኃይል ነው ። በአንድ ኅብረተሰብ የመንግሥት ሙሉ ሥልጣን የሚታወቀው በሥራ ላይ በሚያውላቸው ሕጐችና ደንቦች ፤ ለመንግሥት ሹማምንት ፤ ለሕዝባዊ ድርጅቶችና ለዜጐች በሚሰጣቸው መብቶችና በሚጥላቸው ግዴታዎች ነው ። ይህም የመንግሥትን ኃይል ከሌላው ለምሳሌም ከቤተሰብና ከማኅበራዊ ቡድኖች ሥልጣን የተለየ ያደርገዋል ። በኅብረተሰብ የሕይወት ዘርፍ ሁሉ የሥልጣን ተፅዕኖ ሊያሳድርና ሲያስፈልግም በኃይል ሊጠቀም የሚችል መንግሥት ብቻ ነው ።

የአንድ መንግሥት የሀገር ውስጥ የሉዓላዊነት ሙሉነት ከውጭ ኃይል ነፃ ከመሆን ጋር በቅርብ የተሳሰረ ነው ። አንድ መንግሥት በውጭ ኃይል ተፅዕኖ ሥር እስከ ወደቀ ድረስ በሀገር ውስጥ የሚኖረው ሉዓላዊነት ውሱን ይሆናል ማለት ነው ። የተሟላ ሉዓላዊነት አንድ መንግሥት በዓለም ዓቀፍ ግንኙነቶች ሕጋዊ ጉዳዮች ላይ የራሱን አቋም እንዲይዝ ያስችለዋል ።

(መንግሥትን ፤ ዲሞክራሲን ይመለከቷል ።)

## ላ ሜትሪ ፣ ዡሊየ አፍሯ ደ
## (*La Mettrie, Julien Offroy de*)

ከ1709 — 1751 የኖረ የፈረንሳይ ተናከእታዊ ቁስአካላዊ ፈላስፋ ነው ። የዴካርትን ሁለታዊነት በመተው በተለይ የሐሳብን የበላይነት በመሰረዝ ፤ ተናከእታዊ አስተሳሰቡን ብቻ በማስቀረት የሁሉ ነገር መሠረትና ምንጭ ቁስአካል ነው በማለት ተናግሯል ። በቁስአካላዊ አቋሙ ከፈረንሳይ ፤ በኋላም ከሆላንድ እንዲባረር ተደርጓል ።

በደረሳቸው ጽሑፎች ውስጥ በተለይም “ሎም ማሺን” (የሰው አሠራር እንደማሽን ነው) በተባለው መጽሐፍ ውስጥ ነገሮች ፤ ሰውና ሐሳቡ ሳይቀሩ የቁስአካል እንቅስቃሴ ውጤት መሆናቸውን አስረድቷል ። በዚሁ አመለካከቱ ላይ በመመርኮዝ እግዚአብሔርና ነፍስ ምንም እውነታ የሌላቸው ነገሮች ናቸው በማለት ተናግሯል ።

ሆኖም ዲያሌክቲካዊ አስተሳሰብ ስላልነበረው በተናከእታዊ እንቅስቃሴ ብቻ የክስተቶችን አመጣጥ ለማስረዳት መሞከሩ ዓይነተኛ ድክመቱ ነበር ።

(ከርቱዥያኒዝምን ፤ ተናከእታዊ ቁስአካልነትን ይመለከቷል ።)

## ላሳሊዝም
(*Lassallism*)

በጀርመን ሠራተኛ መደብ እንቅስቃሴ ውስጥ የተከሰተ ፣ በንዑስ ከበርቴው ሶሻሊስት ፌርዲናንድ ላሳል (1825—64) የተቀመረና ከካፒታሊዝም ጋር በሚደረገው ፍልሚያ ከመደብ ትግል ይልቅ የመደብ እርቅን በመስበክ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያደረገ አድርባይ አቋም ነው ። ላሳል መላውን አውሮፓ ካጥለቀለቀው ከ1848ቱ ቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮት በኋላ በጣም ተዳክሞ የነበረውን የጀርመን ሠራተኛ እንደገና በፖለቲካ ለማደራጀት በተደረገው ትግል ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል ። በ1863 "አጠቃላይ የጀርመን ሠራተኞች ማኅበር"ን በማቋቋም ፕሮግራሙንና ታክቲኩን ቀይሷል ። በዚህም መሠረት ላሳል የሕዝቡን የመምረጥና የመመረጥ መብት ማስከበር የፖለቲካ ፕሮግራሙ ሲሆን የሠራተኞችን በመንግሥት ድጋፍ በአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት መደራጀትና በነዚህም አማካይነት ቀስ በቀስ ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም መሸጋገር ደግሞ የኢኮኖሚ ፕሮግራሙ አድርጎ ወስዷል ። ይህ አቋሙም ከኦቶ ፎን ቢስማርክና ከፕሩስያ አድኃሪ ኃይሎች ጎን አሰልፎታል ።

የላሳል የፍልስፍና አመለካከት ሐሳባዊ ሲሆን ለዚህ አቋሙም ትክክለኛ ማረጋገጫ አድርጎ ያቀረበው የሄግልን አስተሳሰብ ነው ። መንግሥትንም የተመለከተው ከመደቦች በላይ እንደሆነ አድርጎ ነው ። በሥነ ኅብረተሰብም የማልቱዚያኒዝምን አመለካከት ይጋራል ። ሌላው ቀርቶ ሠራተኛው ጊዜያዊ ጥቅሙን ለማስከበር በራሱ ድርጅት ተደራጅቶ የሚያደርገውን ትግል ስለማይቀበል ትግሉን እንደ ፋይዳቢስ ነገር አድርጎ ቆጥሮታል ። ይህንኑ አቋሙን "አይረን ሎው ኦቭ ዌጅስ" በሚለው ንድፈ ሐሳቡ ትክክለኛ አስመስሎ ለማቅረብ ሞክሯል ። ማርክስ እነዚህን የተሳሳቱ የላሳልን አስተሳሰቦች "በጎታ ፕሮግራም ላይ የተሰነዘረ ሒስ" በሚለው ጽሑፉ ፣ ሌኒንም "ፊሎሶፊካል ኖትቡክስ" በተሰኘው መጽሐፉ አቋሙን ነቅፈውታል ።

(አድርባይነትን ፣ ጠጋኝነትን ይመለከቷል ።)

## ላዕላይ መዋቅር
(*Superstructure*)

ላዕላይ መዋቅር በኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ የኢኮኖሚ ግንኙነቶች ነፀብራቅ የሆኑትን ሐሳቦች ፣ ድርጅቶችና ተቋሞች የሚያመለክት ጽንሰ ሐሳብ ነው ። ላዕላይ መዋቅር ፖለቲካዊ ፣ ሕጋዊ ፣ ግብረገባዊ ፣ ውበታዊ ፣ ሃይማኖታዊ ፣ ፍልስፍናዊ ወዘተ . . . የማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና መልኮችን የሚያጠቃልል ነው ። እነዚህም የማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና መልኮች የሚከናወኑባቸው ወይም የራሳቸው የሆኑ ቁሳዊ ክስተቶች ማለትም እንደ መንግሥት ፣ እንደ ቤተ ሃይማኖት ፣ እንደ ባህል ተቋሞች ፣ እንደ ትምህርት ቤቶችና እንደ ፍርድ ቤቶች የመሳሰሉ ድርጅቶችና ተቋሞች አሏቸው ።

የማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና መልኮች በሙሉ በልዩ ልዩ መንገድና ደረጃ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶችን የሚያንፀባርቁ ቢሆንም አንዳንዶቹ ለምሳሌ ፖለቲካዊና ሕጋዊ የንቃተ ኅሊና መልኮችና ከነሱም ጋር ተያይዘው የሚገኙት ድርጅቶች ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶችን በቀጥታና ወዲያውኑ የሚያንፀባርቁ ናቸው ። ሌሎች እንደ ኪነት ፣ እንደ ፍልስፍና ወዘተ … ያሉት ደግሞ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶችን በተዘዋዋሪና በረዥም ጊዜ የሚያንፀባርቁ ናቸው ። ከዚህም የተነሣ ከኢኮኖሚያዊ መሠረቱ ጋር ያላቸው ግንኙነት የሚመሠረተው በፖለቲካው አማካይነት ነው ። ይህም ላዕላይ መዋቅሩ በመሠረቱ የሚወሰን ቢሆንም የተወሰነ አንፃራዊ ነፃነት እንዳለው ያሳያል ።

ላዕላይ መዋቅራዊ ግንኙነቶች የማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና መልኮች ግንኙነቶች ናቸው ። ይህም የላዕላይ መዋቅራዊ ግንኙነቶችን ነባራዊ ከሆኑት ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች የተለዩ ያደርጋቸዋል ።

እያንዳንዱ ማኅበራዊ ሥርዓት የራሱ የሆነ ላዕላይ መዋቅርና መሠረት አለው ። የማኅበራዊ ሥርዓት ለውጥ የላዕላይ መዋቅርና የመሠረት ለውጥን ያስከትላል ። ይሁን እንጂ የእያንዳንዱ ማኅበራዊ ሥርዓት ላዕላይ መዋቅር የተገነባበትና የሚያንፀባርቀው ኢኮኖሚያዊ መሠረት እንዲጠናከር ፣ እንዲስፋፋና ዕድሜው እንዲራዘም ይታገላል ። ስለዚህም

ነው የላዕላይ መዋቅር አካል የሆነው የመንግሥት ሥልጣን ጥያቄ የአንድ ማኅበራዊ አብዮት ዋነኛ ጥያቄ ነው የሚባለው ። ሆኖም ላዕላይ መዋቅሩ የተገነባበት ኢኮኖሚያዊ መሠረት ሲለወጥ ላዕላይ መዋቅሩ ወዲያውኑና አብሮት ሙሉ በሙሉ ባይለወጥም ቀስ በቀስ የሚለወጡ ክፍሎች አሉት ።

(ንቃተ ኅሊናን ፣ ርዕዮተዓለምን ፣ መሠረትና ላዕላይ መዋቅርን ፣ መሠረትን፣ አብዮትን ይመለከቷል ።)

## ላይብኒትዝ ፣ ጐትፍሪድ ቪልሄልም (*Leibniz, Gottfried Wilhelm*)

ከ1646 እስከ 1716 የኖረ ፣ በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ ታላቅ አስተዋጽኦ ያደረገ ፣ በፊዚክስ ፣ በሥነ አመክንዮ በተለይም በማቴማቲክስ ባደረገው ምርምርና ባገኛቸው ግኝቶች ሁለንታዊ እድናቆትን ያተረፈ ጀርመናዊ ሐሳባዊ ፈላስፋ ነው ። የፍልስፍናው መሪ ሐሳብ ሁለንታዊ መግባባት የሚለው ጽንሰ ሐሳብ ነው ። ይህ ሐሳብ ተገልጾ የሚገኘው "ሞናዶሎጂ" ፣ "ቴኦደሲ" ፣ "ዲስኮርስ ኦን ሜታፊዚክስ" በሚሉት ጽሑፎቹ ውስጥ ነው ። እንደ ላይብኒትዝ አባባል ይህ ሐሳብ እስካሁን ድረስ በፍልስፍና ውስጥ የተነሡትን የአመለካከት ልዩነቶች የሚያስታርቅ ነው ።

የልዩነቱ ምንጭ የሚገኘው በሁለታዊነት ላይ ነው ። ፈላስፎች ቁስአካልንና መንፈስን በጣም ልዩ የሆኑ ነገሮች በማድረግ አራርቀው ከማስባቸው የተነሣ ስለዓለም እንድነት ሲጠየቁ የተዛባ መልስ ለመስጠት ተገደዋል ። ለምሳሌ ዴካርት ቁስአካልንና መንፈስን ለያይቶ ካስቀመጠ በኋላ ማገናኘትና ማስማማት ስለተሳነው የሱ ተከታይ የሆነው ስፒኖዛ ሐሳብንና ቁስአካልን የአንድ ነገር የማይነጣጠሉ ጠባዮች በማድረግ እግዚአብሔርንና ተፈጥሮን በማዋሃዱ የእግዚአብሔርን መለኮታዊነት ከዷል ። ይህ ልዩነት ሊታረቅ የሚችለው ነገሮች መንፈሳዊም ሆኑ ቁስአካላዊ ፣ ከአንድ ነገር የተሠሩ ሲሆኑና በነገሮች መካከል የሚታየው የጠባይ ልዩነት ከሁለታዊነት የሚመነጭ ሳይሆን ከራሱ ከነገሩ ግላዊ መሆን የመጣ ሲሆን ነው ። ይህን ነገር ላይብኒትዝ "ሞናድ" ብሎ ሰይሞታል ። ማንኛውም ነዋሪ ነገር ግላዊ በመሆኑ እሱም ደግሞ በሚያቅፋቸው መጨረሻ በሌላቸው ግላዊ ነገሮች ሊከፋፈል ስለሚችል ሞናዶች ቁጥር ስፍር የላቸውም ። እነዚህ ቁጥር ስፍር የሌላቸው ግላዊ ሞናዶች ተሰባስበው ግዙፍና የተለያዩ ባሕርያት ያሏቸው ነገሮችን ፣ ረቂቅና ራሳቸውን ዐዋቂ የሆኑ ኅሊናዎችን ሊፈጥሩ የሚችሉት እርስ በርስ ከሚያግባባቸው ሕግ አኳያ የተዋቀሩ እንደሆነ ነው ። ቁስአካል የሞናድ አነስተኛው ደረጃ ከመሆኑ በስተቀር ከአእምሮአዊ ባሕርያት ውጭ የሆነ ነገር አይደለም ። እንደ ላይብኒትዝ አባባል እነዚህ ግላዊ ሞናዶች እርስ በርስ ሊስማሙ በሚችሉበት ደረጃ ሁሉ ሊዋቀሩ የሚችሉት ፣ ሁሉም ሞናዶች በግላዊነታቸው ጸንተውና ተዋቅረው አንድ ሥርዓት ያለውና በሁለንታዊ ሕጎች የሚገዛ ዓለም ሊመሠርቱ የሚችሉት ለዕውቀቱና ለችሎታው ገደብ የሌለው ፍጹም ጥበበኛ አምላክ ሲኖር ብቻ ነው ።

ይህ ፍልስፍና በቀጥታ የሚቃወመው ተናከኦታዊ አመለካከትን ነው ። ተናከኦታዊነት እንደሚለው አንድ ነገር የሚለወጠው ፣ የሚንቀሳቀሰው በሌላ ነገር ሲነካ ማለትም አንዱ መንሥኤ ሌላው ተገብሮት በመሆን ሲገናኙ ነው ። በላይብኒትዝ አባባል ይህ አመለካከት የዘለለው ነገር ቢኖር ነገሮች ሁሉ ግላዊ በመሆናቸው አንዱ ነገር በሌላው ላይ ተፅዕኖ ሊኖረው እንደማይችል ነው። ነገሮች የሚነካኩ የሚመስለን ከግላዊነታቸው ሳይወጡ በፕሮግራምና በመግባባት ስለሚሠሩ ነው ። ለምሳሌ ነፍስንና ሥጋን እንውሰድ ። ስነፍስ በስሜትና በሐሳብ የሚገለጸው ነገር ሁሉ በሥጋዊ እንቅስቃሴ ይተረጐማል ። ፍርሐት መንቀጥቀጥን ያስከትላል ፤ በተገላቢጦሽም በሽታ የመሠቃየትን ስሜት ይፈጥራል ። ይህ ሁኔታ አንዱ በሌላው ላይ በሚያደርገው ቀጥተኛ ተፅዕኖ የሚፈጠር ይመስላል ። እንደ ላይብኒትዝ አባባል መምስሉ የሚያስረዳው የሁለቱን መነካካት ሳይሆን ሁለቱም በረቀቀና ጥበብ በተሞላው ሁኔታ በቅድሚያ እንዲሰማሙ ተደርገው የተሠሩና በፕሮግራም የሚንቀሳቀሱ መሆናቸውን ነው ። አንዱ የሚደርስበትን ሌላው የሚገልጸው ከመነካካት የመጣ ሳይሆን ሁለቱም በግላዊነታቸው የተስማሙ ሆነው በመፈጠራቸው ነው ።

በቅድሚያ ሁሉ ነገር የታቀደ ከሆነ ሰው ነፃ አይደለም ማለት ነው የሚለው

እስተሳሰብ ላይብኒትዝን ያስቸገረው ቢሆንም የሰው ነፃነት የሚመሠረተው ከግላዊው ባሕርይ ባለመውጣቱ ማለትም በሌላ ኃይል ተፅዕኖ ሥር ባለመውደቁ ነው ሲል መልሷል። ከዚህም በተረፈ እግዚአብሔር በፕሮግራሙ ሞናዶችን ሲያዋቅር በይበልጥ ሊስማሙ የሚችሉትን የሚመርጥ በመሆኑ ይህ የተሻ ለውን የመምረጥ ችሎታ ለሰውም የተሰጠ ነው ። በላይብኒትዝ አስተሳሰብ ይህ የምንኖ ርበት ዓለም ከብዙ ሊኖሩ ከሚችሉ ዓለሞች የተሻለው በመሆኑ ነው በእግዚአብሔር ተመርጦ እውን የሆነው ። ማንኛውም ነገር ህልውና የሚኖረው በቂ ምክንያት ስላለው ነው ። የአንድን ነገር ህልውና ከይሁንታ ወደ እውነታ የሚለውጠው በቂ ምክንያት ከመ ግባባት አኳያ ከሁሉ የተሻለውን ሁኔታ መፍጠር መቻሉ ነው ።

ሁለንታዊ መግባባት የሚለው ጽንሰ ሐሳብ በሐሳባውያን መካከል የሚታየውን ልዩነት ፣ በሃይማኖትም በኩል በፕሮቴስታን ቶችና በካቶሊኮች መካከል የተነሣውን ግጭት ፣ በተለያዩ የአውሮፓ መንግሥታት መካከል የሚደረጉ ጦርነቶችን እንዲሁም በኅብረተሰብ ውስጥ የሚታየውን የመደብ ክፍፍልና ግጭት ለማስታረቅ የሚጠቅም ሐሳብ ነው ብሎ ላይብኒትዝ ይገምት ነበር ። ሆኖም በጊዜውም ቢሆን ሐሳቡ ተቀባይነት አላገኘም ነበር ። ከሐሳባውያንና ከሥነ መለ ኮታውያን የተሰነዘረው ዋናው ተቃውሞ ሁሉ ነገር የሚስማማ ከሆነ ፣ ስምምነቱንም የነ ደፈው አምላክ ከሆነ ፣ ጥፋት ፣ ችግር ፣ በሽታ ፣ ሞት ፣ ጦርነትና የመሳሰሉት ነገሮች እንዴት ሊኖሩ ቻሉ የሚል ነበር ። አምላክን ራሱን ተሳሳችና ለነዚህ ነገሮች ተጠያቂ ከማ ድረግ ሌላ አማራጭ ላይብኒትዝ አልሰጠም በማለት ተወቅሷል ። በአጠቃላይ ሳይነካካ ፣ ሳይደራረስ ፣ ነገር ግን በቅድሚያ በዕቅድ እንዲግባባ በመደረጉ ማንኛውም ነገር ህል ውናው ሳይደፈር በአንድ ዓለም ውስጥ ራሱን ሊገልጽ ይችላል የሚለው አመለካከት ጥል ቀት ያለው ቢመስልም ከተጨባጩና ከሚታ የው ሁኔታ ጋር ግን ማዛመድ የማይቻል ነው ። አመለካከቱ የነገሮችን በርስ በርስ ቅራኔ ውስጥ መነከርን የሚክድ መሆኑ ብቻ ሳይ ሆን ሥርዓት የሚገኘው ከመግባባት ነው የሚ ለው መላምት ራሱ አጠያያቂ መሆኑ ነው ። ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት የሚያስተምረው ቅራኔ ራሱ አንድነትን የሚጠይቅና በዚህም የተነሣ የሥርዓት መሠረት መሆኑን ነው ። የተናከአታዊ አመለካከትን ውሱንነት ማየቱ ጥሩ ሲሆን "በቅድሚያ የተዘጋጀ መግባባት" በሚል ዲበአካላዊና ሐሳባዊ አቋም መተካቱ ግን ሊመረጥ አይችልም ። ከቅራኔ ሕግ እን ደምንረዳው የአዲስ ነገሮች መከሰት በቅድ ሚያ የተወሰነ ፕሮግራም ከንውን ሳይሆን የተፈጥሮ ዕድገትን የሚያመለክት ነው ።

በእርግጥ ዕድገት በፕሮግራም ሲመራ ነው ሙሉ ተፈጻሚነት የሚያገኘው ። ሆኖም ፕሮግራም የማውጣቱ ሥልጣን የሰው የራሱ ካልሆነና ሥልጣኑ ለሌላ ኃይል ከተሰጠ ሰው ራሱን በራሱ የመወሰን መብቱ ተነ ፍጐታል ማለት ነው ። ይህ ፕሮግራም የሚለው ሐሳብ ጠቃሚ ቢሆንም የእውጭ ነቱን ሥልጣን ላይብኒትዝ ለአምላክ መስ ጠቱ የሚያሳየን ሰው የሚኖርበትን ሁኔታ እንደማይቆጣጠር ነው ። ሰዎች ተፈጥሮን ሆነ ኅብረተሰብን መቆጣጠር ባለመቻላቸው የሚደርስባቸው ነገር ሁሉ ከሌላ ኃይል የመጣ ውሳኔ ይመስላቸዋል ። በተጨማሪ በላይብኒትዝ አስተሳሰብ ቁስአካል የሞናድ የመጨረሻ ዝቅተኛ ደረጃ መሆኑን ስናይ በስምምነት ኑሩ የሚለው መርህ የበላይ እን ዛዝ ሥርዓትን የሚደግፍ መሆኑን እንረዳ ለን ። እምራቹ ሕዝብ በቁስአካላዊነቱ የበታ ችና ተገዥ እንዲሆን ከመጠየቅ በስተቀር ፍልስፍናው ሌላ ማኅበራዊ ፍች የለውም ።

(አንጻኝነትን ፣ ተናከአታዊ ቁስአካልነትን ፣ ካርቴዥያኒዝምን ፣ ስፒኖዛን ይመለከቷል ።)

## ሌሴፌር
*(Laissez-faire)*

ሌሴፌር በጥሬ ትርጉሙ ሰዎች እንደ ፈለጉ ይሁኑ ፤ እትከልክሏቸው ፤ ቁጥጥር አታ ድርጉባቸው ማለት ነው ። በኢኮኖሚ ጽንሰ ሐሳብነቱ በ18ኛው ምዕት ዓመት የፈረንሳይ ቡርዧ የኢኮኖሚ ሊቃውንት በወቅቱ በኢ ንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥ የመንግ ሥትን ቁጥጥርና ጣልቃ ገብነት በመቃወም ለወሰዱት አመለካከት የሰጡት ስያሜ ነው ። የሌሴፌር የኢኮኖሚ አመለካከት መንግሥት ሰላምንና የንብረትን ይዞታ በመጠበቅ ብቻ ተወስኖ ካፒታሊስቶች እንደፈለጉ እንዲሠሩ መተው እንጂ በኢኮኖሚ ውስጥ ጣልቃ መግ

ባቱን በጽኑ የሚቃወም አመለካከት ነው ። የሌሴፌርን የኢኮኖሚ አመለካከት በሰፊው ያብራራውና ለአጠቃላይ የኢኮኖሚ አመለካከቱም እንደመሠረት ድንጋይ አድርጐ የተቀበለው እንግሊዛዊው የኢኮኖሚ ሊቅ አዳም ስሚዝ (1723—1790) ነው ። የስሚዝ የሌሴፌር ወይም እሱ እንደተጠቀመበት 'የተፈጥሮ ነፃነት' ጽንሰ ሐሳብ የእያንዳንዱ ሰው በግል ጥቅሙ ላይ የተመሠረተ የተናጠል የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ተጠቃሎ በመጨረሻ የኅብረተሰቡን ጥቅም የሚያሳድግ ነው ከሚል አስተሳሰብ የሚመነጭ ነው ።

በስሚዝ አመለካከት ነፃ ውድድርና ነፃ ንግድ የኢኮኖሚ ጽንሰ ሐሳብ አልፋና ኦሜጋ በመሆናቸው ነፃ የሆነ የሸቀጦች ፥ የገንዘብና የሥራ ኃይል ዝውውር እስካለ ድረስ የኅብረተሰቡ ቁሳዊ ፥ የገንዘብም ሆነ የሰው ኃይል አጠቃቀም በትክክለኛ መንገድ ይከናወናል ። በዚህ አመለካከት መሠረት በወቅቱ አዳም ስሚዝ በእንግሊዝ ሀገር የሥራ ኃይል እንቅስቃሴን ይገድቡ የነበሩ እርምጃዎችንና መንግሥት በኢንዱስትሪና በንግድ ውስጥ ያደርግ የነበረውን ጣልቃ ገብነት በጽኑ በመቃወም ፥ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ንግድ ልቅና ነፃ በሆነ መንገድ መካሄድ እንዳለበት ያስተምር ነበር ።

ይህ አመለካከት በሂደተ ምርት ውስጥ በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚዘነጋ ከመሆኑም በላይ ኢኮኖሚ ለኅብረተሰቡ ፍላጐት መሟላት አትኩሮት ማድረግና በዕቅድ መመራት አለበት ከሚለው ማርክሳዊ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ ጋር በፍጹም ተፃራሪነት የቆመና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ሥርዓት አልባ እንዲሆን የሚያደርግ ነው ። በግላዊ ጥቅምና በስግብግብነት ላይ የተመሠረተው የካፒታሊስት ኢኮኖሚ መሠረተ ሐሳብም ይህ ሌሴፌር ነው ።

(ሜርካንቲሊዝምን ፥ ክላሉታዊነትን ፥ የእሴት ሕግን ፥ ሶሻሊስት የኢኮኖሚ ዕቅድን ይመለከቷል ።)

## ሌኒኒዝም
*(Leninism)*

የሩስያና የዓለም ወዝአደሮች አብዮታዊ መሪና መምህር በነበረው ቭላዲሚር ኢሊዩች ኡሊያኖቭ ሌኒን የተቀመረና የዳበረ የዘመነ ኢምፔሪያሊዝም ማርክሲዝም ነው ። ሌኒኒዝም ባጠቃላይ የወዝአደሩ አብዮትና የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት ንድፈ ሐሳብና ታክቲክ ነው ። የወዝአደሩ አብዮት መሠረታዊ ይዘት የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት በመሆኑ የሌኒኒዝም መነሻ ወይም ፍሬ ሐሳብ በወዝአደሩ የበላይ ገዥነት አመሠራረትና ስፍነት ላይ የሚያተኩር ነው ። ባጠቃላይ ይህ ትርጉም የሌኒኒዝምን ታሪካዊ ምንጭ ፥ ዓለምአቀፋዊ ባሕርይና ከካርል ማርክስ አስተምህሮዎች ጋር ያለውን አንድነት በትክክል የሚያንፀባርቅ ነው ።

ሌኒን ማርክሲዝምን በሩስያና በዓለም አቀፍ የሠራተኛው ሕዝብ ትግል ልምድ ላይ በመመሥረት በጊዜው ከነበረው አዲስ ታሪካዊ ሁኔታ ጋር ሳይንሳዊ በሆነ መንገድና ፈጠራ በተሞላበት ስልት በማገናዘብ አዳብሮታል ። በዚህም ማርክሲዝምን ለማዳበርና ለማበልጸግ ባደረገው ታላቅ አስተዋጽኦ ሳይንሱ ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ተብሎ ሊጠራ ችሏል ።

ሌኒን ለማርክሲዝም ዕድገት ያበረከታቸው ታላላቅ አስተዋጽኦዎች ከሞላ ጐደል ስለ ኢምፔሪያሊዝም ፥ ስለወዝአደሩ አብዮትና ስለ አዲሱ ዓይነት ፓርቲ ባፈለቃቸው ንድፈ ሐሳቦች ዙሪያ ሊጠቃለሉ ይችላሉ ።

ሌኒን በወቅቱ ተጨባጭና ታሪካዊ ሁኔታና ተግባር ላይ ሳይንሳዊ ምርምር በማካሄድ ፥ ካርል ማርክስ በታላቁ ጽሑፉ በ"ካፒታል" ያካሄደውን የካፒታሊስት ስልተ ምርት ትንተና በመቀጠል የካፒታሊዝምን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዕድገት የሚገዙትን ሕጐች ዕውቀት አዳብሯል ። በዚህ ጥናቱም ካፒታሊዝም ውስጣዊ ቀውሱን ለመቋቋም ብሔራዊ ድንበሩን በመዝለል ወደኢምፔሪያሊዝም ማለትም ወደ ካፒታሊዝም ከፍተኛውና የመጨረሻው የዕድገት ደረጃ መሸጋገሩን አሳይቷል ። በዚህም በኢምፔሪያሊዝም ደረጃ በተከሰተው የካፒታሊዝም ያልተመጣጠነ ዕድገት የተነሣ የሶሻሊስት አብዮት በአንድ ጊዜ በሁሉም ሀገሮች የሚካሄድ ሳይሆን በጥቂት ሀገሮች ወይንም በአንድ ሀገር ብቻ ባጠቃላይ የኢምፔሪያሊዝም ሰንሰለት በላላበት ቦታ በተከታታይ ድል ሊያደርግ መቻሉን አብስሯል ።

ከላይ ከተገለጸው ፍሬ ሐሳብ ጋር በተያያዘም ሌኒን በኢምፔሪያሊዝም ወቅት የቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮት በተድሞው መልኩ ሊካሄድ አለመቻሉንና በዚህም አብዮት ውስጥ የወዛደሩን ግንባር ቀደም አመራር መያዝና ዲሞክራሲያዊ አብዮቱን በማጠናቀቅ ወደሶሻሊስት አብዮት የመሸጋገር ሕጐችንና እንቅሲቃሴ ኃይሎችን በመግለጽ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ንድፈ ሐሳብ አቀነባብሯል ። ከዚህም በመነሣት ካፒታሊዝም ወደሚገባ ባላደገባቸው ሆነ በቅድመ ካፒታሊስት የዕድገት ደረጃዎች ውስጥ የሚገኙ ሀገሮች የውስጥ ተራማጅ ኃይሎችና የውጭ ሶሻሊስት ሀገሮችን ኅብረት ካገኙ ካፒታሊዝምን በመዝለል የሶሻሊስት ኅብረተሰብን ሊገነቡ እንደሚችሉ አመልክቷል ።

በተጨማሪም ሌኒን ከማርክሲዝም መሠረተ ሐሳቦች በመነሣት የአዲሱን የወዝአደር ፓርቲ አወቃቀር ፣ አደረጃጀትና አሠራር አስተምህሮዎች አቀነባብሯል ። አዲሱ ዓይነት ፓርቲም የሶሻሊስት አብዮት ብቸኛ መሪና አደራጅ ኃይል መሆኑንና ያለዚህ ፓርቲም የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት ብሎም የኮሚኒስት ኅብረተሰብ ምሥረታ ከቶውኑ እውን ሊሆን እንደማይችል በግልጽ በማሳየት የሶሻሊስት አብዮትን ንድፈ ሐሳብ አዳብሯል ።

(ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ፣ ሌኒንን ፣ ፓርቲን፣ ኢምፔሪያሊዝምን ፣ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ይመለከቷል ።)

## ሌኒናዊ የፓርቲ ሕይወት ድንጋጌዎች

*(Leninist Standard of Party Life)*

በዓለም ኮሚኒስት ንቅናቄ ውስጥ በንድፈ ሐሳብና በተግባር ስፋትና ጥልቀት እያገኙ በመምጣት በሌኒን ይበልጥ ተቀናብረውና ዳብረው ዛሬ ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን መመሪያቸው ያደረጉ ኮሚኒስትና የሠራተኛ ፓርቲዎች የሚመሩባቸው መሠረታዊ ድንጋጌዎች ናቸው ። ከነዚህም መካከል የፓርቲ አመራር አካላት በምርጫ መቋቋምና ለመረጣቸው ክፍል ተጠያቂ መሆን ፣ የመወያየት መብት መረጋገጥ ፣ የኂስና የግለኂስ መስፈን ፣ በፓርቲ ሕይወት ግልጽ የመሆን አስፈላጊነትና ከሕዝብ ጋር የቀረበና የጠበቀ ግንኙነት መፍጠር ፣ የወል አሠራር መጠናከር ፣ የፓርቲ አባላት ርዕዮተዓለማዊና ድርጅታዊ አንድነት ዋስትና ማግኘት ፣ በፓርቲ ተግባራት ውስጥ የሁሉም ኮሚኒስቶች ተሳትፎ መኖር ፣ ለኮሚኒዝም ዓላማዎችና ለድል አድራጊነታቸው ፍጹም ታማኝና ተገዥ መሆን የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው ።

(ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን ፣ ዲሲፕሊንን፣ ፓርቲን ይመለከቷል ።)

## ሌኒን ፣ ቭላዲሚር ኢሊች

*(Lenin, Vladimir Ilyich)*

ከ1870—1924 የኖረ ፣ የማርክስና የኤንግልስ ግንባር ቀደም ደቀ መዝሙር ፣ የሩሲያና የዓለም ወዛደሮች መሪ ፣ የሶቪዬት ኅብረት ኮሚኒስት ፓርቲንና የሶቪዬትን መንግሥት የመሠረተ ታላቅ አብዮታዊ መሪና መምህር ነው ።

ሌኒን ማርክሲዝምን በጥልቀት መርምሮ በማጥናት ለሳይንሱ መስፋፋትና መዳበር ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጓል ። ማርክሲዝምን ከአዲሱ ታሪካዊ ሁኔታ አንፃር ፈጠራ በተሞላበት አኳኋን በማዳበር በሩሲያ አብዮቶችና በዓለም አቀፍ የሠራተኛው ሕዝብ አብዮታዊ እንቅስቃሴዎች ተግባራዊ ልምድ ላይ ተመሥርቶ ተጨባጭ ትርጕ በመስጠት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል ። ሌኒን ከማርክስና ከኤንግልስ ሞት በኋላ የቁስአካላዊ ዲያሌክቲክስን ጽንሰ ሐሳቦች ማለትም የዲያሌክቲክስን ፣ የሥነ አመክንዮንና የዕውቀትን ንድፈ ሐሳብ ለማዋሀድ ፣ ለማዳበርና ለማጥራት ብዙ ጥረት አድርጓል። በታሪካዊ ቁስአካልነት ንድፈ ሐሳብ ላይ በመመሥረትም ሌኒን የሶሻሊስት አብዮትን ንድፈ ሐሳብ በግልጽ በማሳየት ስለወዛደሩ መደብ ታሪካዊ ተልዕኮ በተለይም ስለወዛደሩ የበላይ ገዥነትና ስለወዛደሩ ፓርቲ ሳይንሳዊ የሆኑ አመለካከቶች በመንደፍ ለተግባራዊ እንቅስቃሴው ተገቢውን መመሪያ ሰጥቷል ። ሌኒን ማርክሲዝምን ከበራዦችና ከከላሾች ለመጠበቅ ትልቅ ትግል አካሂዷል ። ዕውቅ ከሆኑ ጽሑፎቹም መካከል "ማቴሪያሊዝም ኤንድ ኢምፔሪዮክሪቲሲዝም" ፣ "ፊሎሶፊካል ኖትቡክስ"፣ "ዘ ዲቨሎፕመንት ኦቭ ካፒታሊዝም ኢን ራሺያ" "ኢምፔሪያሊዝም ፣ ዘ ሀየስት ስቴጅ ኦቭ ካፒታሊዝም"፣ "ዘ ስቴት ኤንድ ሪቮሉሽን" ፣ የተባሉት ይገኙባቸዋል ።

ሌኒን ባጠቃላይ የማርክሲዝምን ንድፈ ሐሳቦች ያዳበረና በተግባርም የተረጐመ ሲሆን በሚከተሉት ጉዳዮች (መስኮች) ማለትም ስለመደቦችና ስለመደብ ትግል ፣ ስለ መንግሥትና አብዮት ፣ በሶሻሊስት አብዮት ዘመን ስለሰፊው ሕዝብ ሚናና የኮሚኒስት ኅብረተሰብ ግንባታ ፣ በሰፊው ሕዝብ ፣ በፓርቲውና በመሪዎች መካከል ስለሚኖረው ግንኙነትና ስለ ሶሻሊስት ሥነ ጥበብ መርሆች ያካሄዳቸው ምርምሮችና ያፈለቃቸው ንድፈ ሐሳቦች ዋነኛ አስተዋጽኦዎቹ ናቸው ።

(ሌኒኒዝምን ፣ ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ይመለከቷል ።)

## ልምድ

*(Experience)*

ተደጋጋሚ ከሆኑ ሕውስታዊ መረጃዎች የምናገኘውን ዕውቀት የሚገልጽ የፍልስፍና ፈርጅ ነው ። በዳሳሾችና በሕውስታውያን አስተሳሰብ የዕውቀት ብቸኛ ምንጭ ልምድ ነው ። ስለነገሮች ልናውቅ የምንችለው ከሕውስታችን በመነሣት በመሆኑና አንድ ነገር በእርግጥ ይህ ዓይነት ጠባይ አለው ብለን ለመናገር የምንችለው በተደጋጋሚ ሲገለጽልን በመሆኑ ልምድ የዕውቀት ብቸኛ ምንጭ ነው ፤ ለምሳሌ የእሳትን የማቃጠል ጠባይ የምናውቀው ከልምድ ነው ፤ ማለትም በተደጋጋሚ ከሚያሳድርብን ሕውስታ ነው ፣ ይላሉ ።

ሆኖም ይህ አመለካከት ወደ አሳሳች መደምደሚያ ማለትም ወደ ኅሊናዊነትና ወደ ኢታዋቂነት አቋም የሚወስድ ነው ። ምክንያቱም ልምድ የነገሮችን ውጫዊ መልክ ያሳያል እንጂ ለምን እንዲህ እንደሆኑ ጠልቆ ለመመርመር አያስችልም ። ይህም ድክመት የዕውቀት ብቸኛ ምንጭ አመክንዮ ነው ለሚለው ሐሳባዊ ለሆነው ምክኑያዊነት መከሰት መንሥኤ ሆኗል ።

በዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት አመለካከት ልምድ አስፈላጊና ጠቃሚ ቢሆንም የዕውቀት ብቸኛ ምንጭ አይደለም ፤ ምክንያቱም ዕውቀት በምርምር አማካይነት ከውስጣዊ ግንኙነቶች ላይ መድረስ ስላለበት በአእምሮአዊ ሥራ ማለትም በመላምት፣ በአርቅቆት ፣ በአስተፃምሮ ፣ በብያኔ ፣ በሙከራ ወዘተ... ይጠቀማል ። ዕውቀት ሲከሰት የሚችለው ታዋቂውን በማስተዋል ብቻ አይደለም ፤ አዋቂው እራሱ አድራጊ ሆኖ መቅረብ ይኖርበታል ።

(ዳሳሽነትን ፣ ምክኑያዊነትን ፣ ጭብጥን ፣ ዕውቀትን ይመለከቷል ።)

## ልሳን

*(Organ)*

አንድ ድርጅት ወይም ተቋም ዓላማውን የሚያሳውቅበት ፣ ለዚህም ዓላማው መሬመድ አባላቱን ወይም ኃይሉን ለማስተባበርና የሕዝቡንም ድጋፍ ወይም ትብብር ለማግኘት እያዘጋጀ በኅቡእ ወይም በይፋ የሚያሰራጨው ብቸኛ ጋዜጣ ነው ።

ይህ ለማንኛውም ድርጅት በአጠቃላይ የሚነገር ቢሆንም በተለይ የአንድ ማርክሳዊ ሌኒናዊ የፖለቲካ ድርጅት ልሳን የድርጅቱን ርዕዮተዓለም በማሰራጨት ፣ ድርጅታዊ ተግባራትን በማስተባበርና አጠቃላይ የትግል አቅጣጫንና የየወቅቱንም የትግል ስልት እያሳወቀ ለበለጠ ውጤት ኃይልን በማቀነባበር ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ። ይልቁንም ድርጅታዊ መዋቅር በሰፊው ባልተዘረጋበትና ባልተጠናከረበት ደረጃ ላይ ልሳን የርዕዮተዓለም መድረክ ብቻ ሳይሆን የድርጅታዊ መመሪያም ማዕከል የመሆን ሚናን በመጫወት ኃይሎችን በዙሪያው እያስተባበረ ድርጅታዊ አንድነትን በማጠናከር የሚያበረክተው ድርሻ የላቀ ነው። ይህንንም በሚመለከት አብዮታዊው ምሁር ሌኒን የዚህ ዓይነቱ ጋዜጣ ንቁ ቀስቃሽና ፕሮፖጋንዲስት ብቻ ሳይሆን ንቁ አደራጅም እንደሆነ ገልጿል ። ከዚህ ዓይነቶቹ የፖለቲካ ድርጅት ልሳናት የቦልሼቪኮችን ልሳን "ኢስክራንና" የኢሠፓን ማ/ኮ ልሳን "ሠርቶ አደርን" መጥቀስ ይቻላል ።

## ልቡና

(*Psyche*)

ልቡና የግዕዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙም ዕውቀት ፣ ማስተዋል ማለት ነው ።

በአድራጊና በተደራጊ መስተጋብር ውስጥ የአድራጊውን ውስጠ ሁኔታ ፣ ከንዋኔዎችና ችሎታዎች የሚገልጽ ጽንስ ሐሳብ ነው ።

በተለመደ አነጋገር ልቡና በውስጣዊ ልባዌ የምንገነዘባቸውን ኅሊናዊ ክስተቶች (ሕውስታን ፣ ልባዌን ፣ ስሜቶችን ፣ ምናብንና ጽንሰ ሐሳቦችን ወዘተ . . . ) የሚያጠቃልል ነው። ጥናቱም የልቡናን ፍልስፍናዊ ፍች ከሳይንሳዊ ፍቹ መለየት ጠቃሚ ነው ። በፍልስፍና [illegible] ከፍልስፍና መሠረታዊ ጥያቄ ጋር በመያያዝ ሐሳብ ፣ ኅሊና ፣ ግንዛቤ የሚለውን ፍች ይይዛል ። በዚህ ጊዜ ልቡና መታየት ያለበት የቁስአካል ከፍተኛ የአደረጃጀት ደረጃ እንደሆነ ተደርጎ ነው ። ዋናው ተግባሩም ነባራዊውን ዓለም በምስሎችና በጽንሰ ሐሳቦች ማንፀባረቅ ነው ። በሳይንሳዊ ፍቺው የልቡና ሕላዌና ሥነ ሕይወታዊ (የሕዋሳት ነርቭ፣ አንጎል ወዘተ . . .) ማኅበራዊ (ቋንቋ ፣ ሥራ ወዘተ . . .) መሠረቶችና የአሠራሩ ሕግጋት የሚጠኑበት የምርምር ተደራጊ ይሆናል ።

(ሐሳብን ይመለከቷል ።)

## ልባዌ
*(Perception)*

> ልባዌ ከግዕዝ የመጣ ቃል ሲሆን ትርጉሙም ልብ ማድረግ ፣ ማስተዋል ማለት ነው።

ነባራዊው ዓለም በሕዋሳት ላይ በሚያደርሰው ተፅዕኖ በኅሊናችን ውስጥ የሚፈጠረው የነገሮች ነፀብራቅ ልባዌ ይባላል ። ሕውስታዎች የልባዌ ጥንተ ነገሮች ሲሆኑ ልባዌም የሚገለጸው በማየት ፣ በማዳመጥና በመንካት ነው ። በዕውቀት ሂደት ውስጥ ከፍተኛውን ሚና የሚጫወተው የማየት ልባዌ ነው ። የማየት ልባዌ ስለ ነገሮች የሚሰጠው ምስል ከማዳመጥና ከመንካት የሚመጡትን ሕውስታዎች የሚያጠቃልል በመሆኑ የዳበረ ነው ። በሕውስታዎች መካከል ያሉትን ግንኙነቶች ለማገናዘብ ስለሚያስችልም ልባዌ ወደ ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀት የሚያመራ ነው ። በመሆኑም ልባዌ የሚሰጠው ምስል በቅርጻዊነቱ ጽንሰ ሐሳቦችን (ሰው ፣ ቤት ወዘተ ...) በይዘትነቱ ግንኙነቶችን በመጠቆም የንድፈ ሐሳብ መሠረት በመሆን በግንዛቤ ሂደት ውስጥ ያለው ድርሻ ከፍተኛ ነው ።

(ሕውስታን ፣ ግንዛቤን ይመለከቷል ።)

## ልብወለዳዊነት
*(Romanticism)*

ይህ አመለካከት ከምክኑያዊ ግንዛቤ ይልቅ በይበልጥ ስለነገሮች ጠልቆ የማወቅ ችሎታ ያላቸው ስሜቶች ናቸው የሚል ነው ። ልብወለዳዊነት ተፈጥሮአዊ ግፊቶች የአገናኝነት ችሎታ አላቸው በማለት ለደመነፍሳዊና ለምናባዊ ስሜቶች ቅድሚያ የሚሰጥ ነው ። የነገሮችን ውስጠ ምሥጢር ለማወቅ በተለይም ዲበተፈጥሮአዊ መንሥኤያቸውን ለመገንዘብ የሚቻለው በፍቅር አማካይነት ነው በማለት ሰዎች ከተፈጥሮና ከኪነ ጥበብ ሥራዎች እንዲሁም ከሃይማኖት ልምዶች ጋር ተማልሎታዊ ግንኙነት እንዲኖራቸው ግፊት አድርጓል ።

ሆኖም ልብወለዳዊነት በሁለት አዝማሚያዎች የተከፈለ ነበር ። አንደኛው አዝማሚያ ፀረ ቡርዧዚ አቋም ያለው ቢሆንም ስለካፒታሊዝም የሚሰጠው ትችት አድኃሪ ነበር። የሥርዓቱን መጥፎ ጐን እንጂ ተራማጅ ጐኑን ባለመገንዘቡ ወደኋላ ማለትም ወደ ፊውዳሊዝም የመመለስ ምኞት ሊፈጥር ሞክሯል ። ሁለተኛው አዝማሚያ ተራማጅ ነበር ። ስሜቶችን በማጉላት ፣ አሳዛኝ ሁኔታዎችን በመፍጠር በኪነ ጥበባዊ ሥራዎች ውስጥ የቡርዧ ኅብረተሰብ ቅራኔዎችን ለማሳየትና ተምኔታዊ በሆነ መንገድ ቢሆንም ለተሻለ ሁኔታ ሰዎች እንዲነሣሡ ግፊት ለመፍጠር ሞክሯል ።

## ልውውጥ
*(Exchange)*

ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል ባለበት ኅብረተሰብ ውስጥ በተለያዩ የሥራ መስኮች የተሰማሩ የኅብረተሰቡ አባላት ያፈሯቸውን የተለያዩ ምርቶች ሲቀያየሩ ድርጊቱን ልውውጥ እንለዋለን ።

በጥንታዊ የጋርዮሽ ኅብረተሰብ ውስጥ ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኝ ስለነበር ልውውጥ የተስፋፋ አልነበረም ፤ እንዲያውም በመጀመሪያ ላይ የሥራ ክፍፍል ተፈጥሯዊ (በፆታና በዕድሜ ላይ የተመሠረተ) በነበረበት ወቅት እያንዳንዱ ቤተሰብ ፣ ቤተ ዘመድ ፣ ጎሣ ወዘተ... ራሱን የቻለ

ስለነበር ልውውጥ አልነበረም ። የሥራ ክፍፍል ከተፈጥሯዊ ወደ ማኅበራዊ ደረጃ ሲያድግ ልውውጥም ቀስ በቀስ እየተስፋፋ መጣ ።

የልውውጥ ምንጭ ወይም መነሻ ተረፈ ምርት ሲሆን በመጀመሪያ ላይ የተከሰተውም ይህንን ከፍጆታ በላይ የሆነ ምርት ለሌላው ሰጥቶ የተለየ ምርት ለፍላጐት ማሟያ በመውሰድ ነበር ። ልውውጥ የሸቀጥ መለዋወጥን መልክ የወሰደው ግን በኅብረተሰቡ ውስጥ ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል እየተስፋፋና የማምረቻ መሣሪያዎች እየተሻሻሉ ፣ ተረፈ ምርት እየዳበረ መምጣት ከጀመረ ወዲህ ነው ። በዚህም ሁኔታ እያንዳንዱ ሰው ሸቀጡን ለማምረት ላፈሰሰው የሥራ ኃይል ተመጣጣኝ የሥራ ኃይል የወጣበት ሌላ ሸቀጥ በለውጥ ማግኘቱን ማረጋገጥ ጀመረ ።

ልውውጥ አንድ ሸቀጥ በሌላ አንድ ሸቀጥ ቀጥታ ከሚለዋወጥበት ዝቅተኛው የእሴት መልክ ጀምሮ በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ውስጥ ከተጓዘ በኋላ ዛሬ በወረቀት ገንዘብ አማካይነት ወደምንለዋወጥበት ደረጃ ቢደርስም የልውውጡ መሠረት ሸቀጡን ለማምረት የወጣው ማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ ነው ። የሸቀጥ ምርት ዋነኛ የምርት መልክና የሰው የሥራ ኃይልም ሸቀጥ በሆነበት በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ልውውጥ ገንኖ ይታያል ። በካፒታሊስት ሥርዓት ቡርዧዚው የወዝአደሩን የሥራ ኃይል በዝቅተኛ ዋጋ (ምንዳ) በመግዛትና ምርቱን በከፍተኛ ዋጋ በመሸጥ (ከፍተኛ የጠቀሜታ እሴት ያለውን የወዝአደሩን የሥራ ኃይል እሴት ዝቅተኛ በሆነ ሸቀጥ በመለወጥ) በዚህ ሂደት ልውውጥ ውስጥ ወዝአደሩ የፈጠረውን ተረፈ እሴት በመውሰድ ይበዘብዘዋል ።

ዛሬ ኢምፔሪያሊዝም በፈጠረው ዓለም አቀፍ የሥራ ክፍፍል ኋላ ቀር ሀገሮችን ለካፒታሊስት ፋብሪካዎች የሚያገለግሉ ጥሬ ዕቃዎችን እንዲያመርቱ በማድረግና እነዚህን ሸቀጦች በዝቅተኛ ዋጋ በመግዛት ፣ የራሳቸውን የኢንዱስትሪ ሸቀጦች በከፍተኛ ዋጋ በመሸጥና በዚህም የተዛባ የንግድ ግንኙነት በመፍጠር ካፒታሊስቶች ከፍተኛ ብዝበዛ ያካሂዳሉ ።

የሸቀጥ ልውውጥ የኮሚኒስት ሥርዓተ ማኅበር የመጀመሪያ ደረጃ በሆነው በሶሻሊዝም ውስጥም ይኖራል ። ምክንያቱም በዚህ ደረጃ ጠቅላላውን የኢኮኖሚ ይዞታ ወደ አንድ ወጥ ሕዝባዊ ይዞታነት መለወጥና ምርትንም በተትረፈረፈ ሁኔታ ማቅረብ ስለማይቻል ነው ። በመሆኑም በዚህ ደረጃ በሚኖሩት ሁለት የማኅበራዊ ይዞታ ቅርፆች መካከል የሚኖረው የኢኮኖሚ ግንኙነት የሸቀጥ ግንኙነት ይሆናል ። የሸቀጥ ግንኙነት በሶሻሊዝም ውስጥ ያለ ቢሆንም በካፒታሊስቱ ዓለም ውስጥ ካለው የሸቀጥ ልውውጥ ግን በዓይነት የተለየ ነው ። ምክንያቱም በሶሻሊዝም ውስጥ ያለው የሸቀጥ ምርት ፣

ሀ. በሶሻሊስት ይዞታ ላይ የተመሠረተና አዲስ ዓይነት ግንኙነት የሚያንፀባርቅ በመሆኑ ፣

ለ. በማዕከላዊ ዕቅድ የሚመራና የሠራተኛውን ሕዝብ ፍላጐት የተንተራሰ እንጂ በካፒታሊዝም ውስጥ እንዳለው የሸቀጥ ምርት በትርፍ ላይ የሚያተኩርና ሥርዓት አልባ በሆነ መንገድ የሚከናወን ባለመሆኑ ፣

ሐ. የሸቀጥ ምርት በሶሻሊዝም ውስጥ ሁለንታዊ ስለአይደለ በመሠረቱ በካፒታሊዝም ውስጥ ካለው የሸቀጥ ምርት በዓይነት የተለየ በመሆኑ ነው ። (ሁለንታዊ አይደለም ስንል በሶሻሊዝም ውስጥ የመንግሥት ማምረቻ ድርጅቶችና ሕንፃዎች ፣ መሬት ፣ የሥራ ኃይልና የመሳሰሉት አይሸጡም አይለወጡም ማለታችን ነው ።)

የሸቀጥ ልውውጥ የሚያከትመው የተመረተውን ምርት በሽያጭና በግዥ መልክ ለተጠቃሚው ማዳረስ አስፈላጊ በማይሆንበት ፣ ከእያንዳንዱ እንደ ችሎታው ለእያንዳንዱ እንደፍላጐቱ የሚለው መርህ ሥራ ላይ በሚውልበት በኮሚኒስት ኅብረተሰብ ብቻ ነው ። በዚህ የዕድገት ደረጃ ምርትና ክፍፍል ሙሉ በሙሉ ማኅበራዊ ከመሆናቸውም በላይ ምርት በጥራት ፣ በዓይነትና በመጠን የኅብረተሰቡን ፍላጐት ለማርካት ከሚችልበት ሁኔታ ላይ ይደርሳል ።

## ልውውጥ እሴት (የ—)

*(Exchange Value)*

የአንድ ሸቀጥ በገበያ ውስጥ በተወሰነ መጣኔ ከሌሎች ሸቀጦች ጋር የመለዋወጥ

ባሕርይ የልውውጥ እሴት ይባላል ። ለምሳሌ ደብረ ማርቆስ ከተማ የአንድ ኩንታል ጤፍ ዋጋ ብር 40 ነው እንበል ፤ የአንድ ሊትር ዘይት ዋጋ ብር 5 ፤ የአንድ ብርድ ልብስ ዋጋ ደግሞ ብር 20 ነው እንበል ። በእነዚህ ዋጋዎች መሠረት የአንድ ኩንታል ጤፍ ዋጋ 8 ሊትር ዘይት ወይም 2 ብርድ ልብስ ለመግዛት ያስችላል ። ስለዚህ በዚህ ምሳሌ መሠረት የአንድ ኩንታል ጤፍ የልውውጥ እሴት 8 ሊትር ዘይት ወይም 2 ብርድ ልብስ መሆን ነው ።

በዚህ ዓይነት በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ውስጥ ዕቃዎች ሲለዋወጡ እናያለን ። እርግጥ የሚለዋወጡት ዕቃዎች የተለያየ የጠቀሜታ እሴት ያላቸው ናቸው ። ስለዚህ ለልውውጥ መካሄድ የተለያዩ ዕቃዎች በተወሰነ መጠን እኩልነት ማግኘት አለባቸው ። ማናቸውም የልውውጥ እሴት ያላቸው ሸቀጦች ሁሉ የጋራ ወይም የወል ባሕርይ የሥራ ኃይል ውጤት መሆናቸው ነው ። ስለዚህ አንዱ ሸቀጥ ከሌላው ሸቀጥ ጋር ሊመዛዘንና የልውውጥም መጠን ሊተመንለት የሚችለው እያንዳንዱ ሸቀጥ የተወሰነ የሥራ ኃይል ውጤት በመሆኑ ነው ። ስለሆነም የሸቀጦች የልውውጥ እሴት የሚወሰነው ሸቀጦቹን ለማምረት በፈሰሰው አስፈላጊ ማኅበራዊ የሥራ ኃይል ወይም ጊዜ ነው ።

(የሥራ ኃይልን ይመለከቷል ።)

## ልዩነት ኪራይ (የ—)

*(Differential Rent)*

የእርሻ ሠራተኞች ከሚፈጥሩት ተረፈ እሴት ውስጥ መሬትን በሞኖፖል በግል ባለቤትነት ለያዙ ባለመሬቶች የሚከፈል ካፒታሊስታዊ የመሬት ኪራይ የሚይዘው አንድ መልክ የልዩነት ኪራይ ይባላል ። የልዩነት ኪራይ ለማግኘት የሚያስችሉ ምክንያቶች ሦስት ናቸው ። እነዚህም የተለያዩ ማሳዎች በአፈር ለምነት መበላለጥ ፤ ማሳዎች ከመገበያያ ቦታዎች ያላቸው ርቀት መለያየትና ካፒታሊስቶች የማሳዎቹን ምርታማነት ለማሳደግ የሚያደርጓቸው ወጪዎች ናቸው ። የተለያዩ ማሳዎች በአፈር ለምነት በመበላለጣቸውና ማሳዎች ከመገበያያ ቦታዎች ያላቸው ርቀት በመለያየቱ የሚገኘው የልዩነት ኪራይ አንድ ሲባል ፤ ካፒታሊስቶች የማሳዎቹን ምርታማነት ለማሳደግ በሚያደርጓቸው ወጪዎች አማካይነት የሚገኘው ደግሞ የልዩነት ኪራይ ሁለት ይባላል ።

የልዩነት ኪራይ ከሚገኝባቸው ምክንያቶች አንደኛው የተለያዩ ማሳዎች በአፈር ለምነት መበላለጥ ነው ። እንደሚታወቀው በእርሻ ተግባር ዋነኛውን ሚና የሚጫወተው መሬት ነው ። መሬት ከሌሎች የምርት መገልገያዎች የሚለይበት ዋና ምክንያት እንደሌሎቹ የምርት መገልገያዎች የሥራ ውጤት ባለመሆኑና መጠኑ የተወሰነና እንደ ተፈለገ መጠኑን ለማሳደግ አለመቻሉ ፤ በማንኛውም ሀገር ውስጥ ያለው መሬት ለም ፤ ለምጠፍና ጠፍ መሆን ነው ። ለም የሆኑ ማሳዎች መጠን የተወሰነ በመሆኑ ከእነዚህ ማሳዎች የሚገኘው ምርት ፍላጐትን ሙሉ በሙሉ ሊያረካ አይችልም ። ስለዚህ ካፒታሊስቶች በለምነታቸው ዝቅተኛ የሆኑትን ማሳዎች ለማልማት ይገደዳሉ ። ሆኖም ካፒታሊስቶች እነዚህን ማሳዎች በምርት ሥራ ላይ ለማዋል ፈቃደኛ የሚሆኑት ወጭአቸውን ሸፍነው ካፒታላቸውን በሌላ መስክ ቢያውሉ ኑሮ ሊያገኙ የሚችሉትን አማካይ ትርፍ ሊያስገኝላቸው በሚችል ዋጋ ምርታቸውን ለመሸጥ ሲችሉ ነው ። አማካይ ትርፍ ካላገኙበት ግን ካፒታላቸውን ወደ ሌላ የሥራ መስክ ለማዛወር ይገደዳሉ ።

ካፒታሊስቶች እነዚህን ከማልማት ይልቅ ካፒታላቸውን ወደሌላ መስክ ሲያዛውሩ የእርሻ ምርት እጥረት ይፈጠራል ። ስለዚህም የእርሻ ምርት የገበያ ዋጋ ከፍ ይልና ጠፍነት የሚያጠቃቸውን ማሳዎች ማልማት አማካይ ትርፍ ሊያስገኝ ስለሚችል ካፒታሊስቶቹ እነዚህኑ ማሳዎች ለማልማት እንደገና ፈቃደኛ ይሆናሉ ። በጠፍ መሬት ላይ የፈሰሰው ጉልበት ለም አፈር ባላቸው ማሳዎች ላይ ከፈሰሰው ጉልበት ምርታማነት ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ነው። በማንኛውም ዓይነት ማሳ ላይ የተመረተ አንድ የእርሻ ምርት ዓይነት የገበያ ዋጋው አይለያይም ። ስለዚህ ጠፍነት የሚያጠቃቸውን ማሳዎች በምርት ተግባር ላይ ያዋሉ ካፒታሊስቶች ከሚያገኙት አማካይ ትርፍ ለም ማሳዎችን በምርት ተግባር ላይ ያዋሉ ካፒታሊስቶች የሚያገኙት የትርፍ መጠን ከአማካይ ትርፍ ይበልጣል ። ይህም በአፈሩ ለምነት ምክንያት የሚገኘው ተጨማሪ ትርፍ

ለካፒታሊስቱ የሚቀር ሳይሆን በልዩነት ኪራይ መልክ ለባለመሬቱ የሚገባ ነው ። የዚህም ምክንያት ባለመሬቶች በሰም መሬቶች ላይ የሞኖፖል ባለቤትነት ያላቸው መሆን ነው ።

የልዩነት ኪራይ የሚገኝበት ሁለተኛው መንገድ ማሳዎች ከገበያ ቦታ ያላቸው የርቀት ልዩነት ነው ። ለም አፈር ባላቸው ማሳዎች ላይ የሚመረተው ምርት መጠን የኅብረተሰቡን ፍላጐት ሙሉ በሙሉ ለማርካት ባለመቻሉ የለምነታቸው ደረጃ ዝቅተኛ የሆኑ ማሳዎች እንደሚታረሱ ሁሉ ፣ በገበያ አቅራቢያ የሚገኙ ማሳዎች ምርት በቂ ባለመሆኑ ከገበያ ቦታ ርቀው የሚገኙ ማሳዎችንም ማረስ አስፈላጊ ይሆናል ። እነዚህ ማሳዎች ከገበያ በራቁ መጠን የማጓጓዣ ወጪያቸው ይጨምራል ። ከመገበያያው ቦታ እጅግ ርቆ የሚገኘውን እርሻ የሚያካሂደው ካፒታሊስት ወጪውን ሸፍኖ አማካይ ትርፍ ማግኘት ይኖርበታል ። ለዚህ ካፒታሊስት አማካይ ትርፍ ለማስገኘት የሚችለው የገበያ ዋጋ ደግሞ በገበያው አቅራቢያ የሚገኘውን እርሻ ለሚያካሂደው ካፒታሊስት ተጨማሪ ትርፍ ያስገኝለታል ። ምክንያቱም በገበያው አቅራቢያ የሚገኘውን እርሻ የሚያካሂደው ካፒታሊስት ምርቱን ወደ ገበያው ለማጓጓዝ የሚያወጣው ወጪ አነስተኛ ስለሆነ ነው ። አሁንም ባለመሬቶች በገበያ አካባቢ በሚገኙ የእርሻ መሬቶች ላይ የሞኖፖል ባለቤትነት ያላቸው በመሆናቸው ይህን ተጨማሪ ትርፍ በልዩነት ኪራይ ስም ይወስዳሉ ።

ሦስተኛው የልዩነት ኪራይ የሚገኝበት መንገድ ካፒታሊስቶች የተከራዩዋቸውን ማሳዎች ምርታማነት ለማሳደግ ከሚያደርጉት ወጪ ጋር የተያያዘ ነው ። ካፒታሊስቶች ማሳዎቹን ከባለመሬቶች ላይ ከተከራዩ በኋላ ትርፋቸውን ለማሳደግ የማሳዎቹ ምርታማነት እንዲጨምር ጥረት ያደርጋሉ ። አዳዲስ የአሠራር ዘዴዎችን በሥራ ላይ ያውላሉ ። በዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎች ፣ በማዳበሪያ ፣ በመስኖ ውሀ ይጠቀማሉ ። በእንፃሩ እነዚህንና የመሳሰሉትን ተግባራት ለማከናወን ተጨማሪ ወጪ የማያስወጡ በተሰይ ለም አፈር ያላቸውን ማሳዎች የተከራዩ ካፒታሊስቶች ከሌሎቹ የተለየ ተጨማሪ ትርፍ ሊያገኙ ይችላሉ ። ሆኖም ካፒታሊስቶቹ ይህን ተጨማሪ ትርፍ የራሳቸው ለማድረግ የሚችሉት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው ። ምክንያቱም ባለመሬቱ መሬቱን ለካፒታሊስቱ ሲያከራይ ውል የሚዋዋለው ለተወሰነ ጊዜ በመሆኑ ነው ። የውሉ ዘመን አልቆ አዲስ ውል ሲፈረም ግን የመሬቱ ምርታማነትና የካፒታሊስቱ ገቢ የጨመረ መሆኑን በመገንዘብ ካፒታሊስቱ ያገኘው የነበረው ተጨማሪ ትርፍ ወደ ልዩነት ኪራይ ይለወጣል ።

የልዩነት ኪራይ ምንጭ የሆኑት ለምሳሌ እንደ ማሳ ለምነት ልዩነት ያሉት ፣ በሶሻሊስቱም ሥርዓት ውስጥ ይኖራሉ ። ሆኖም በካፒታሊስቱ ሥርዓት የሚፈጠረው የልዩነት ኪራይ ብቸኛ ተጠቃሚ ትላልቅ ባለመሬቶች ሲሆኑ መሬት የሰፊው ሕዝብ ንብረት በሆነበት በሶሻሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ግን የሚፈጠረው የልዩነት ገቢ ተጠቃሚ ሰፊው ሕዝብ ነው ።

(ፍጹማዊ ኪራይን ይመለከቷል ።)

## ልዩና ሁለንታዊ
*(The Particular and Universal)*

በአካባቢያችን ያለ ማናቸውም ክስተት ከሌሎች የሚለይበትንና የሚመሳሰልበትን ባሕርያት የሚገልጹ ዲያሌክቲካዊ ፈርጆች ናቸው።

ልዩ የምንለው እያንዳንዱ አካል ወይንም ክስተት በጠባይ ፣ በጊዜና በቦታ ከሌላው የሚለይበትን ባሕርይ ነው ። ይሁንና በተፈጥሮ ነገሮች በተናጠል የሚኖሩና እርስ በርሳቸው የማይገናኙ አይደሉም ። እያንዳንዱ ነገር ከሌሎች ጋር የሚያመሳስለው ሁኔታ አለ ። ከሌሎች ጋር የወል ባሕርያትን ይጋራል ። ይህ በነገሮች መካከል ያለ ተመሳሳይነት በአንድ አካል ውስጥ በሚገኙ ልዩ ልዩ ክፍሎች ወይም በሁለት አካሎች መካከል ያለ ግንኙነትና ተመሳሳይነት የክስተቶች ሁለንታዊ ባሕርይ ነው ። ለምሳሌ ለማንኛውም ዛፍ የወል ጠባይ የሆኑ አጠቃላይ ባሕርያት ሲኖሩ ፣ ግራርን ከባህር ዛፍ የሚለዩ ልዩና ግላዊ ባሕርያትም አሉ ።

ልዩ ጠባዮች አንድን አካል ወይንም ክስተት ከሌሎች አካሎችና ክስተቶች የሚለዩትን ያህል ሁለንታዊ ደግሞ አንድን ነገር ከሌሎች ጋር ያመሳስላል ። ልዩና

ሁለንታዊ ዲያሌክቲካዊ በሆነ ቅንጅት በያንዳንዱ ነገር ውስጥ ይኖራሉ ። ግላዊ ከሁለንታዊ ፣ ሁለንታዊም ከግላዊ ጋር እንጂ ተነጣጥለው አይኖሩም ። አንድን ሰው ከጠቅላላው ሰው ፣ ጠቅላላውን ሰው ከእንስሳት ፣ እንስሳትን ሕይወት ካላቸው ነገሮች ፣ ሕይወት ያለውን ነገር ደግሞ ከጠቅላላው ተፈጥሮ ጋር የሚያስተሳስሩና የሚለዩ የግልና የጋራ ባሕርያት አሉ። በልዩና በሁለንታዊ መካከል የሚገኘውን ዲያሌክቲካዊ አንድነትና ልዩነት ማወቅ ሁለንተናዊ ምርምር ለማካሄድና ውስብስብ የሆኑ ችግሮችን ለመፍታት ያገለግላል ።

(ፈርጆችን ፣ ሁለንታዊን ይመለከቷል ።)

## ሎክ ፣ ጆን
*(Locke, John)*

ከ1632 — 1704 የኖረ ፣ በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ ገንቢ አስተዋጽኦ ያደረገ የእንግሊዝ ሐሳባዊ ፈላስፋ ነው ። በነበረው የዳሳ ዊት አቋሙ ፍልስፍና ከአውጠንጣኝነትና ከተምህርነት አዝማሚያ ተላቆ ትኩረቱን ወደተጨባጩ እንዲያዞር የታገለ ፈላስፋ ነው።

ሎክ በይበልጥ የታወቀው ሥነ ዕውቀትን አስመልክቶ ባደረገው ጥናት ሲሆን “አን ኤሴይ ኮንሰርኒግ ሂዩማን አንደርስታንዲንግ” የሚለው ዓቢይ ጽሑፉ ውስጥ የጥናቱን ውጤት አብራርቷል ። በጽሑፉ ውስጥ በተለይም የዴካርትን “አብረው የተወለዱ ሐሳቦች” የሚለውን አመለካከት በመቃወም ሐሳቦች የሚመጡት ከልምድ ፣ የዕውቀትም ምንጭ ልምድ እንደሆነ ለማስረዳት ሞክሯል ። የዕውቀት ትክክለኛነትና ጠቃሚነት የሚለካው ለተግባር በሚሰጠው አገልግሎት እንደሆነና የሰው ልጅ ከዲበአካላዊ አስተሳሰብ ተላቆ ተጨባጩን ለማወቅ መጣር እንዳለበት ገልጿል ።

የጆን ሎክን አቋም ዘመናዊ ያደረገው በመወለድና በማደግ ላይ ያለውን የሙከራዊ ሳይንስን አመለካከት በማብራራቱና በመደገፉ ነው ። በሥነ ዕውቀት መስክ የተምህሮነትን አመለካከት እንደተቃወመ ሁሉ በፖለቲካውም መስክ የፊውዳሉን ፍጹማዊ አገዛዝ በጥብቅ ነቅፏል ። ነፃ የሆነ አቋም በመያዝ ፍጹማዊነትን ለማጥፋት የፓርላማን ፖለቲካዊ ሥልጣን ማጠናከር አስፈላጊ መሆኑን አስተምሯል ። ይህ አመለካከቱ ለቡርዧው የፖለቲካ ሥርዓት ዕድገት ዓይነተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

ሆኖም የሎክ ዘመናዊ አቋም የተመሠረተው ዳሰሳዊ በሆነ አመለካከት ላይ በመሆኑ ሥነ ዕውቀቱ ውሱንና እርስ በርሱ የሚቃረን ነበር ። በአንድ በኩል የልምድን ወሳኝነት ሲያረጋግጥ በሌላ በኩል የሰው ዕውቀት የዓለምን ምሥጢር ጠልቆ ለመረዳት አይችልም የሚል እምነት ነበረው ። ልምድ የነገሮችን መከታተል ቢያሳይም ምሥጢራቸውን የማይናገር በመሆኑ የሰው አእምሮ ከባድ ጥያቄዎችን ለመመርመር እንዳልተፈጠረ ያስረዳል በማለት ተናግሯል ። እንደሎክ አባባል ጠቃሚ ሳይንስ ልንመሠርት የምንችለው ለዕለት ተግባር የሚበቃንን ዕውቀት እንድናገኝ ከእግዚአብሔር የተሰጠንን ኃይል ወሰኑን በማወቅ ከክልሉ ሳንወጣ ስናስብ ነው ። በዚህ አመለካከቱ ሎክ የዘመናዊ ኢታዋቂነት ፍልስፍናን የቀየሰ ነው ማለት ይቻላል ።

(ዳሳሽነትን ይመለከቷል ።)

# መ

## መላምት
*(Hypothesis)*

ነገሮችን ተመልክተን በምናገኛቸው ሕውስታዊና የመነሻ መረጃዎች አማካይነት ስለውስጣዊ ምንነታቸው ፣ ግንኙነታቸውና አወቃቀራቸው ለማወቅ የምናደርገው የግንዛቤ ሙከራ መላምት ይባላል ። መላምት ከሐሳብ ዝም ብሎ የሚፈልቅ ሳይሆን መነሻ መሠረቱ ከነባራዊው ዓለም ከምናገኘው ሕውስታዊ ግንዛቤና ሕዋሶቻችን ከሚሰጡን መረጃዎች ነው ። የመረጃዎቹ ዋና ባሕርይ ሁኔታዎችን በተለያዩና በተነጣጠሉ ማለትም በግላዊ መልካቸው የሚያሳዩን በመሆናቸው የነገሮችን ውስጣዊ ግንኙነት ለመገንዘብ ራሳቸው በቂ አይደሉም ። ለምሳሌ አንድ የፈረሰ ቤት ብናገኝ የተበታተኑትን ፍርስራሾች መልሶ ለማዋቀርና አንዱን ከሌላው ለማገናኘት መነሻ የሆነ መሪ ሐሳብ (ግምት) እንዲኖረን ያስፈልጋል ። ሆኖም በአንድ ጊዜ ቤቱን መልሰን የምንገነባበት ትክክለኛው ሐሳብ ላይከሰትልን ይችላል ። በሙከራ መልክ ልዩ ልዩ ሐሳቦችን በማፍለቅ የማያዛልቁትን በመተው ፣ የሚበጁትን በመያዝ ሐሳባችን ቀስ በቀስ ጥራትና ትክክለኛነት ያገኛል ፤ ቤቱንም መልሰን እናቋቁማለን ። ዕውቀትም እያደገና እየሰፋ የሚሄደው በዚሁ ሁኔታ ነው ። ከሕውስታዊ መረጃዎች በመነሣት የነገሮችን ውስጣዊ ግንኙነት ለመገንዘብ መላምትን እንደመነሻና እንደ መንደርደሪያ አድርገን እንጠቀምበታለን ። ይሁን እንጂ የመላምት ትክክለኛነት የሚረጋገጠው በመላምቱ መሠረት በምናደርገው ምርምር አማካይነት ነገሮችን መልሰን ስንፈጥርና ትክክለኛነቱን በተግባራዊ ውጤት ስናረጋግጥ ነው ።

(ዕውቀትን፣ ጭብጥን፣ አርቅቆትን ይመለከቷል።)

## መልማት ላይ ያሉ ሀገሮች (በ—)
*(Developing Countries)*

ቀደም ሲል የኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ቅኝ ግዛት ወይም የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት የነበሩ ፣ ዛሬም በዚሁ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ፣ ከዳበሩ ካፒታሊስትና ሶሻሊስት ሀገሮች ውጭ ያሉ የአፍሪካ ፣ የላቲን አሜሪካና የእስያ ሀገሮች በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮች በመባል ይታወቃሉ ። ከሶሻሊስት ሀገሮችና በኢምሪያሊዝም ቀጥተኛ የፖለቲካ ተፅዕኖ ሥር ከሚገኙት በዘረኞች ከሚተዳደረው የደቡብ አፍሪካ ሪፐብሊክ ፣ ከጃፓንና ፣ ከአንዳንድ የእስያ ሀገሮች በስተቀር በእነዚህ አህጉራት ውስጥ የሚገኙ ሀገሮች አብዛኛዎቹ በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮች ናቸው ። ከዚህ በፊት "ያልሰሙ ሀገሮች" ፣ "የሦስተኛው ዓለም ሀገሮች" እየተባሉ ይጠሩ የነበሩት ሁሉ "በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮች" በሚለው ስያሜ ተጠቃልለዋል ።

በመልማት ላይ ካሉ ሀገሮች መካከል ከጥንት ጀምሮ የፖለቲካ ነፃነታቸውን አስከብረው የኖሩና በቅርቡ የፖለቲካ ነፃነታቸውን የተጐናፀፉ ሀገሮች ይገኙባቸዋል ። ከነዚህም ውስጥ ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ሀገሮች ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ቅኝ አገዛዝ ተፍረክርኮ ባብዛኛው ባከተመበት ወቅት የፖለቲካ ነፃነታቸውን የተቀዳጁ ናቸው ። በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ ዕድገት ደረጃቸውም እነዚህ ሀገሮች በአመዛኙ የቅድመ ካፒታሊስት የምርት ግንኙነት የሰፈነባቸው ሲሆን ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢያቸው እጅግ ዝቅተኛ ከሆነ ኋላ ቀር ሀገሮች እንሥቶ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ በመካከለኛ ደረጃ እስከዳበረባቸው ሀገሮች ድረስ ይገኙባቸዋል ።

በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮች ለብሔራዊ ነፃነት ባካሄዱት ትግል ነፃነታቸውን ሊጎናፀፉ ችለዋል ፤ ይሁን እንጂ ብዙዎቹ በተለያየ ደረጃ የዓለም ካፒታሊስት ኢኮኖሚ ተቀጥላ በመሆን ከዳበሩ ካፒታሊስት ሀገሮች ጋር በእኩልነት ላይ ያልተመሠረተ ግንኙነት በመመሥረታቸው በኋላቀርነት ወጥመድ ተጠምደው ይገኛሉ ። ስለዚህም ትግላቸው በተቀዳጁት ነፃነት ብቻ የሚያበቃ ሳይሆን በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች ላይ ትኩ

ረት የሚያደርግና በዚህም መስክ ድል አስከተገኘ ድረስ የሚቀጥል ነው ። ይህ ትግል ከኢምፔሪያሊዝም ጭቆናና ብዝበዛ ነፃ የመውጣት ዓለማ ያለው ነው ።

በእነዚህ ሀገሮች ውስጥ መጠነኛ የምርት ኃይሎች ዕድገት መታየቱ ባይካድም የብዙዎቹ ኢኮኖሚ አሁንም ኋላቀርና በእርሻ ላይ የተመሠረተ ነው ። ለኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ጥሬ ዕቃ ለማቅረብ ተብሎ የሚካሄደው ከማዕድን ቁፋሮ ባሻገር በተለይ ከቴክኖሎጂ መዳበር ጋር በቅርብ የተሳሰሩት የምህንድስናና የፍብረካ ኢንዱስትሪዎች እምብዛም ናቸው ። የለሙ ካፒታሊስት ሀገሮች የነፍስ ወከፍ ገቢና በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮች የነፍስ ወከፍ ገቢም ንጥጥር አንድ ለመቶ ሲሆን ይህም የነፍስ ወከፍ ገቢ እያደር ሲራራቅ ይታያል ።

በሚገኙበት ኋላቀር ሥርዓትና በኢምፔሪያሊዝም ተፅዕኖ ምክንያት የብዙዎቹ በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የተገታ ነው ። በእነዚሁ ሀገሮች ውስጥ የሚገኙ ሕዝቦች በአብዛኛው የኑሮ ደረጃቸው እጅግ ዝቅተኛ በመሆኑ ረሃብ ፣ በሽታ ፣ ማይምነትና ሥራ አጥነት በከፍተኛ ደረጃ ይታዩባቸዋል ።

በመልማት ላይ ባሉ ሀገሮች ውስጥ በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኘው ካፒታሊዝም የዓለም ካፒታሊስት ኢኮኖሚ ተቀጥላና ጥገኛ በመሆኑ ዕድገቱ አዝጋሚ ነው። ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች የኢኮኖሚ የበላይነትን በመያዝ ፣ በመልማት ላይ ባሉ ሀገሮች ውስጥ የሞኖፖሎች ኅብረት በመፍጠር ፣ ከእነዚሁ ሀገሮች ጋር የተዛባ የንግድ ፣ የገንዘብና የፋይናንስ ግንኙነቶችን በማካሄድ ፣ እነዚህኑ ሀገሮች ባለከፍተኛ ዕዳና የሳይንስና የቴክኖሎጂ ጥገኞቻቸው እንዲሆኑ በማድረግ ፣ ባጠቃላይም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን በማጠናከር የበታችና ጥገኞቻቸው ሆነው እንዲቀሩ ለማድረግ የማይሸርቡት ደባ የለም ።

በመልማት ላይ ባሉ ሀገሮች ውስጥ የሚገኙ ሕዝቦች መካከል ከኋላቀርነትና ከጥገኝነት ለመላቀቅ የካፒታሊዝም ዕድገት ፈለግ ሊያዋጣቸው የማይችል መሆኑን የተረዱ ሀገሮች ቁጥር በመጨመር ላይ ይገኛል ። ወዝአደሮች ፣ አርሶ አደሮችና ሌሎችም የኅብረተሰቡ ክፍሎች ሶሻሊስት የዕድገት ፈለግን ለመከተል በመታገል ላይ ይገኛሉ ። ይህንንም ትግል በግንባር ቀደምነት የሚመሩት የኮሚኒስትና የሠራተኛ ፓርቲዎች ቁጥር እየጨመረ ነው።

(ኢካፒታሊስታዊ የዕድገት ፈለግን ይመለከቷል።)

## መሠረተ ልማት
*(Infrastructure)*

መሠረተ ልማት የእርሻንና የኢንዱስትሪን ክፍላተ ኢኮኖሚ የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ቅርንጫፎችን በጥቅሉ ለማመልከት በኢኮኖሚ ነክ ጽሑፎች ውስጥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሥራ ላይ የዋለ ቃል ነው ። በመሠረተ ልማት ውስጥ የሚጠቃለሉት መንገዶች ፣ ወደቦች ፣ ድልድዮች ፣ አውሮፕላን ማረፊያዎች ፣ መጋዘኖች ፣ ቦዮች ፣ የኃይል ማመንጫዎች ፣ የባቡር ሃዲዶች ፣ ልዩ ልዩ የመገናኛ አውታሮች ፣ የውሃና ፍሳሽ ተቋሞች ፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎቶችና የመሳሰሉት ናቸው ።

ቃሉ በመጀመሪያ ያመለክት የነበረው በግንባር የተሰለፉ ወታደሮችን የሚያግዙና ድጋፍ ሰጪ የሆኑ እንደ ስንቅ ዝግጅት ፣ እንደ መሣሪያ ማከማቻ በታዎች ፣ እንደ ተዋጊ አውሮፕላን ማረፊያዎችና የመሳሰሉትን ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ተቋሞችን በማመልከት ትርጉሙ ከልማት ጋር ሊያያዝ ችሏል ።

በመሠረተ ልማት ውስጥ የሚጠቃለሉ ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ተቋሞች የአንድን ሀገር ቁሳዊ ሀብት በማሳደግ ረገድ በሚጫወቱት ሚና ምርታዊና ኢምርታዊ መሠረተ ልማት ተብለው ይከፈላሉ ። ምርታዊ መሠረተ ልማት የሚባሉት ከቁሳዊ ምርት ጋር በቀጥታ የተገናኙ እንደ መንገዶች ፣ እንደ ባቡር ሃዲዶች ፣ እንደ ኃይል ማመንጫዎችና እንደ መጋዘኖች የመሳሰሉትን ሲያጠቃልል ፣ በኢምርታዊ መሠረተ ልማት ውስጥ የሚጠቃለሉት ደግሞ ከቁሳዊ ምርቱ ጋር ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የሚገናኙ እንደ ትምህርትና እንደ ጤና አገልግሎቶች የመሳሰሉት ናቸው ።

በካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ ያለውን መሠረተ ልማት የተለየ የሚያደርገው ያለው ሁለት ዓይነት ባሕርይ ነው ። በአንድ በኩል የኢኮኖሚ ቅልጥፍናና በአጠቃላይም በእርሻ ፣

በኢንዱስትሪ ፣ በኮንስትራክሽንና በመሳሰሉት ቁሳዊ ምርት በሚመረትባቸው ክፍላተ ኢኮኖሚ ተረፈ እሴት ለማስገኘት የነዚህ ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ አውታሮች መኖር አስፈላጊ ሲሆን ይህም የሙአለ ንዋይን በሥራ ላይ መዋል አስፈላጊ ያደርገዋል ፤ በሌላ በኩል ግን በእነዚህ መስኮች ከሚያስፈልገው ሙአለ ንዋይ ከፍተኛነት አንፃር ለካፒታሊስቶቹም በፍጥነት ትርፍ የሚያስገኝ ባለመሆኑ ሊሰማሩበት አይፈልጉም ። ይህም ሁኔታ ለካፒታሊስት ምርት አስፈላጊ የሆኑ የመሠረተ ልማት አውታሮች መዘርጋት በአብዛኛው በካፒታሊስት መንግሥታት እንዲካሄድና ለዚህም የሚያስፈልገው ወጪ በመንግሥት በጀት እንዲሸፈን አድርጎታል ። ስለሆነም እነዚህን አውታሮች ለመዘርጋት አስፈላጊ የሆነው ወጪ በታክስ መልክ በሠርቶ አደሩ ሕዝብ ጫንቃ ላይ እንዲወድቅ ተደርጓል ። ዛሬ በኢምፔሪያሊስት መንግሥታት እጅ የእነዚህ መሠረተ ልማት አውታሮች መከማቸት በዓለም ላይ ሰላምን ለማደፍረስ ያላቸውን ፍላጎት ለማርካት በሚያስችላቸው መንገድ ይበልጡኑ ከወታደራዊ ጠቀሜታቸው አንፃር በማደራጀት ላይ ስላተኮሩ ለከፍተኛ የሀብት መባከንና ለሠራተኛው ሕዝብ ኑሮ ማሽቆልቆል ምክንያት ሆኗል ።

በሶሻሊዝም ውስጥ ግን የመሠረተ ልማት አውታሮች ስርጭት የተመጣጠነ ክፍላተ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ዕድገት እንዲኖርና የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሳደግ ካለው ተቀዳሚ ዓላማ አንፃር በማዕከላዊ ዕቅድ አማካይነት ደረጃ በደረጃ በተስተካከለ መንገድ የሚዘረጉ በመሆናቸው ለተፋጠነ የኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ናቸው ።

በኋላቀር ሀገሮች ውስጥ የመሠረተ ልማት ዕድገት በአጠቃላይ ሲታይ እንደ ሌሎቹ የኢኮኖሚ ክፍሎች ሁሉ ያልዳበረ ሲሆን ያለውም ቢሆን በኢምፔሪያሊስቶች ግፊት ለውስጥና ለውጭ ካፒታሊስቶች ሙአለ ንዋይ በሚያመች መንገድ እንዲዘረጋ የተደረገ በመሆኑ ከእነኝህ ሀገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት ፍላጎት ጋር በአብዛኛው የተጣጣመ አይደለም ።

## መሠረታዊ ቅራኔ
*(Basic Contradiction)*

ከክስተቶች መጸነስ እስከ መክሰም የሚዘልቀውና በዚህ ሂደት ውስጥ ወሳኙን ሚና የሚጫወተው ቅራኔ መሠረታዊ ቅራኔ ይባላል ። በተፈጥሮ ፣ በኅብረተሰብና በሰዎች ውስጥ ለሚታየው ቅስቃሴና ዕድገት ቅራኔዎች አንቀሳቃሽ ሞተሮች ቢሆኑም ቅራኔዎች ሁሉ ለክስተቱ መወለድና ማደግ ፣ ብሎም መክሰም እኩል ሚና አይጫወቱም ። የወሳኝነት ሚና የሚጫወተው መሠረታዊ ቅራኔ ነው ። የዚህ ቅራኔ መፈታትም አዲስ ክስተት ያስከትላል ። ሕይወት በሌላቸው ነገሮች ውስጥ ለአዳዲስ ንጥረ ነገሮች መከሰትና መጥፋት መንሥኤው ሁለት ልዩ ባሕርያት ያሏቸው ንጥረ ነገሮች መዋሃድ ወይም መለያየት ነው ። ለምሳሌ ውሃ እንዲኖር ኦክስጂንና ሀይድሮጂን የተባሉት አቶሞች መዋሀድ አለባቸው ። ሁለቱ ሲለያዩ ውሃ አይኖርም ። ከዚያ ውጭ ግን ውሃ ከውጫዊ አካሎች ጋር የሚያደርገው መስተጋብር ውሃነቱን አይለውጠውም ። ሕይወት ባላቸው ነገሮች ውስጥም ለህልውና ወሳኙን ሚና የሚጫወተው በአሮጌ ሕዋሶች መወገድና በአዳዲስ መተካት ፣ ጠቃሚ ምግብን ከአካል ጋር የማዋሃድና የማይፈለገውን የማስወገድ ውስጣዊ ሂደት ነው። ይህ ተቃራኒ ባሕርይ ያለው ሂደት ሲያቆም ሕይወት ያቆማል ። በኅብረተሰብ ዕድገትም እንዲሁ ወሳኝ ሚና የሚጫወት ቅራኔ አለ ። ይህም በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል ያለው ቅራኔ ነው ። ለምሳሌ በካፒታሊስቱ ኅብረተሰብ በምርት ኃይሎች ማኅበራዊ ባሕርይና በምርት ግንኙነቶች ግላዊ ባሕርይ የተነሣ እነዚህን ሁለት ክፍሎች በሚወክሉት በወዝአደሩና በካፒታሊስቱ መካከል መሠረታዊ ቅራኔ አለ ። የካፒታሊስቱ ሥርዓት እስካለ ድረስ ይህ መሠረታዊ ቅራኔ ይኖራል ። የዚህ ቅራኔ መፈታትም የሚከሰተው በማኅበራዊ አብዮት እንደምርት ኃይሎች ሁሉ የምርት ግንኙነቱን ማኅበራዊ (በጋራ አምርቶ በጋራ የመጠቀም) ባሕርይ እንዲኖረው በማድረግ ሲሆን ይህም በዓይነቱ ልዩ የሆነ የኅብረተሰብ ሥርዓትን (ሶሻሊዝም) መከሰት ያስከትላል ። በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ መሠረታዊ ቅራኔ ሊኖር የሚችለው በመሠረታዊ መደቦች መካከል ነው ። ለምሳሌ በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት

በባሪያ አሳዳሪውና በባሪያው መካከል ፣ በፊውዳሉ ሥርዓት በመሬት ባለቤቱና በገባሩ መካከል ፣ በካፒታሊስቱ ሥርዓት በካፒታሊስቱና በወዝአደሩ መካከል ማለት ነው ።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ካሉ በርካታ ቅራኔዎች ሁሉ የዘመናችን መሠረታዊ ቅራኔ ለአዲስ ሥርዓት የሚታገሉ አብዮታዊ ኃይሎችን ባቀፈው በሶሻሊዝምና የታሪክን ሂደት ለመግታት የሚሞክሩ አድኃሪ ኃይሎችን በሚወክለው በኢምፔሪያሊዝም መካከል ያለው ነው ።

(የቅራኔዎች አንድነትና ትግል ሕግን ፣ የዲያሌክቲክስ ሕጐችን ይመለከቷል ።)

## መሠረታዊና ኢመሠረታዊ መደቦች

*(Basic and Non-Basic Classes)*

በመደብ በተከፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ ለኅብረተሰቡ ዋናና ወሳኝ በሆነው ስልተ ምርት ውስጥ የሚገኙት መደቦች መሠረታዊ መደቦች ይባላሉ ። ተፃራሪ በሆነ የመደብ ኅብረተሰብ ውስጥ መሠረታዊ መደቦች የሚለዩት ከምርት መገልገያዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት ነው ። በአንድ በኩል የማምረቻ መሣሪያዎች ባለቤት የሆነው በዝባዥ መደብ በሌላ በኩል ንብረት አልባ በመሆን ብዝበዛ የሚፈጸምበት አምራች መደብ የኅብረተሰቡ መሠረታዊ መደቦች ናቸው ማለት ነው ። ለምሳሌ በባሪያ አሳዳሪው ስልተ ምርት ውስጥ ባሪያ አሳዳሪውና ባሪያው ፣ በካፒታሊስት ስልተ ምርት ውስጥ ቡርዧዚውና ወዝአደሩ መሠረታዊ መደቦች ናቸው ።

መሠረታዊ የተባሉበት ምክንያት የመደቦቹ ግንኙነት የማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓትን ምንነትና የብዝበዛውን ዓይነትና ስልት የሚወስን በመሆኑ ነው ። በባሪያ አሳዳሪው ስልተ ምርት ውስጥ በባሪያውና በባሪያ አሳዳሪው መካከል ያለው የብዝበዛ ግንኙነት የሚፈጸመው ባሪያው የባሪያ አሳዳሪው የግል ንብረት በመሆኑ ነው ። የካፒታሊስትን ስልተ ምርት የወሰድን እንደሆነ አምራቹ መደብ ማለትም ወዛደሩ ነፃ ሲሆን የማምረቻ መሣሪያዎች ባለቤት ባለመሆኑ ግን የሥራ ኃይሉን ለመሸጥ የሚገደድበት ነው ። የኅብረተሰቡ አጠቃላይ ፖለቲካዊ ሥርዓትና የአመለካከት ዓይነት የሚወሰኑት በመሠረታዊ መደቦች ግንኙነት ነው ። የስልተ ምርት ለውጥ የሚከሰተው በመሠረታዊ መደቦች መካከል በሚካሄደው የመደብ ትግል ነው ።

ኢመሠረታዊ መደቦች የሚባሉት ደግሞ መሠረታዊ መደቦችን ባቀፈው ስልተ ምርት ውስጥ የማይጠቃለሉ ነገር ግን ከነሱ ጋር በአንድ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ውስጥ የሚገኙት ናቸው ። ኢመሠረታዊ መደቦች በኅብረተሰቡ ዋነኛ ስልተ ምርት ውስጥ የተሰማሩ አይደሉም ማለት ነው ። ከዚህም የተነሣ አጠቃላይ ሚና ኖሯቸው የኅብረተሰቡን ታሪካዊ ሂደት የሚወስኑ አይደሉም ። በመደብ ትግል ውስጥ ጥቅማቸውን በራሳቸው ብቻ ለማራመድ ስለማይችሉ ብዙውን ጊዜ ወላዋይ አቋምና አመለካከት ያላቸው ናቸው ። ትግሉ ወሳኝ ደረጃ በሚደርስበት ወቅት ከአንዱ መሠረታዊ መደብ ጐን ለመሰለፍ የሚገደዱ መደቦች ናቸው ። ለምሳሌ በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ኢመሠረታዊ መደቦች ተብለው የሚጠሩት አነስተኛ ገበሬዎች ፣ የእጅ ሥራ ባለሞያዎች ፣ አነስተኛ ነጋዴዎች ወዘተ...ናቸው።

(መደብን ይመለከቷል ።)

## መሠረታዊ ፍላጐቶች

*(Basic Necessities)*

በአንድ ኅብረተሰብ ማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ወሳኝና አስፈላጊ የሆኑ ቁሳዊ ፍላጐቶች መሠረታዊ ፍላጐቶች ይባላሉ ። እነዚህ ቁሳዊ ፍላጐቶች እንደ መጠለያ፣እንደ ምግብ፣ እንደ ልብስ ወዘተ... ያሉት ሲሆኑ እነሱም ያለ ማኅበራዊ እርባታ ሊሟሉ የማይችሉ ናቸው ።

ማኅበራዊ ምርት በኅብረተሰቡ ውስጥ መሠረታዊ ፍላጐቶች የሚነሡበትንና የሚዳብሩበትን አጠቃላይ ሁኔታ ይወስናል ። በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚከሰቱ የኢኮኖሚ ፍላጐቶች ዕድገት በኅብረተሰቡ ውስጥ ካለው ተጨባጭ የምርት ኃይሎች የዕድገት ደረጃ ጋር የተያያዘ ነው ።

የኅብረተሰቡ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ የዕድገት ደረጃ እያደገ ሲሄድ መሠረታዊ ፍላጐቶቹም እንደዚሁ እያደጉ ይሄዳሉ ። ለምሳሌ በጥንታዊ የጋርዮሽ ኅብረተሰብ ውስጥ ያለው መሠረታዊ ፍላጐት በባሪያ

አሳዳሪውና በፊውዳሉ ኅብረተሰብ ውስጥ ካሉት መሠረታዊ ፍላጐቶች ያነሰ ነው ። በካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ያለው የመሠረታዊ ፍላጐት ደረጃ ደግሞ በቅድመ ካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ከተከሰቱት እጅግ የላቀ ነው ።

በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ያለውን ቁሳዊ ፍላጐት የማርካት ሂደት በምርትና በፍጆታ መካከል ባሉት ግንኙነቶች የሚገለጽ ነው ። በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ መደቦችና የኅብረተሰቡ ክፍሎች የሚኖሯቸው ፍላጐቶች የተለያዩና ተፃራሪም ናቸው ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ኢኮኖሚው በማዕከላዊ ዕቅድ የሚመራ ፣ ዕድገቱም ሚዛናዊና የተመጣጠነ በመሆኑ ግላዊና ማኅበራዊ ፍላጐትን ለማቀናጀትና ለማስማማት አመች ሁኔታ ይፈጠራል ።

ባንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ባለው የማምረት ችሎታ መሟላት የሚችሉና መሟላትም የሚገባቸው ፍላጐቶች የኅብረተሰቡ ተጨባጭ ፍላጐቶች ናቸው ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ በየጊዜው ያሉትን ተጨባጭ ፍላጐቶች እያጤኑ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕድገትን በምርት ሂደት ውስጥ ተግባራዊ በማድረግ መሠረታዊ ፍላጐቶችን በይበልጥ ለማሟላትና የኑሮ ደረጃን በየጊዜው ለማሻሻል ያስችላል ።

## መሠረት (ታህታይ መዋቅር)

*(Basis)*

በኅብረተሰብ ውስጥ በሰዎች መካከል በምርት ፣ በልውውጥ ፣ በክፍፍልና በፍጆታ መስኮች ያሉትን ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች የሚያመለክት ጽንሰ ሐሳብ ነው ። በኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ ክስተቶች ፣ አስተሳሰቦች ፣ አመለካከቶችና እነዚህም የሚከናወኑባቸው ድርጅቶችና ተቋሞች በመሠረቱ ላይ የሚገነቡና በርሱም የሚወሰኑ ናቸው ። ለምርት ኃይሎች ዕድገት አመችና ተስማሚ የሆኑ የምርት ግንኙነቶች (ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች) ስለሚያስፈልጉ የምርት ኃይሎች ዕድገት የምርት ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶችን ለውጥ ያስከትላል ። የኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶችም ለውጥ የመሠረትን ለውጥ ያስከትላል ።

በቅድመ ሶሻሊስት ሥርዓቶች ውስጥ በርካታ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች አሉ ። የአሮጌው (የቀድሞው) ሥርዓት የምርት ግንኙነቶች ፣ በወቅቱ ያለው ሥርዓት የምርት ግንኙነቶችና የወደፊቱ ሥርዓት ጥንስስ የምርት ግንኙነቶች አብረው ይገኛሉ ። ይሁን እንጂ ኢኮኖሚያዊ የሆኑት የምርት ግንኙነቶች በሙሉ በአንድ በተወሰነ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኝ ኅብረተሰብ ላዕላይ መዋቅር መሠረት ሆነው አያገለግሉም ። በዚህ ጊዜ መሠረት ተብለው የሚጠሩት ኢኮኖሚያዊ የሆኑት የምርት ግንኙነቶች ላዕላይ መዋቅሩ የተገነባባቸው ግንኙነቶች ብቻ ናቸው ። ያለፈው ሥርዓት ርዝራዥና የወደፊቱ ሥርዓት ጥንስስ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች ግን የኅብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊ ክፍሎች ተብለው ይጠራሉ ። በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ክስተቶች ፣ አስተሳሰቦች ፣ አመለካከቶችና ከነርሱም ጋር ተያይዘው የሚገኙት ተቋሞችና ድርጅቶች በምርት ግንኙነቱ የሚወሰኑ እንደመሆናቸው መጠን በአንድ ጊዜ አንድ ዓይነት የምርት ግንኙነት ብቻ የበላይነትን ይዞና ሰፍኖ የሚገኝ ይሆናል ። ይህም የምርት ግንኙነት የላዕላይ መዋቅሩ መሠረት ነው ።

የምርት ኃይሎች ዕድገት የሚፈጥረው የምርት ግንኙነት የንብረት ይዞታውን የግል ወይም የወል ሊያደርገው ይችላል ። የምርት መገልገያዎች ይዞታ የግል በሚሆንበት ኅብረተሰብ (በባሪያ አሳዳሪው ፣ በፊውዳሉና በካፒታሊስቱ ሥርዓት) ውስጥ የሰው በሰው ብዝበዛና ጭቆና ይኖራል ። የምርት መገልገያዎች ይዞታ የወል ወይም ማኅበራዊ በሆነበት ኅብረተሰብ ውስጥ (ጥንታዊ ጋርዮሽና ኮሚኒዝም) የሰው በሰው መበዝበዝና መጨቆን አይኖርም ። እኩልነት ፣ መረዳዳትና የወል ጥቅም የሚከበርበት ሥርዓት ነው ።

(ላዕላይ መዋቅርን ፣ የምርት ግንኙነቶችን ይመለከቷል ።)

## መሠረትና ላዕላይ መዋቅር

*(Basis and Superstructure)*

መሠረትና ላዕላይ መዋቅር በኅብረተሰብ ውስጥ በኢኮኖሚያዊና በሌሎች ማኅበራዊ ግንኙነቶች መካከል ያለውን ቁርኝት የሚገ

ልዩ የታሪካዊ ቁስአካልነት ፈርጆች ሲሆኑ ሁለቱም በአንድ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ውስጥ ታቅፈው የሚገኙ ናቸው ። መሠረት ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶችን ሲያመለክት ላዕላይ መዋቅር ደግሞ የማኅበራዊ ንቃተ ኅሊናን ልዩ ልዩ መልኮችና ቁሳዊ ገጽታቸውን (ድርጅትን ፣ ተቋምን ፣ መንግሥትን ፣ ፓርቲን ወዘተ...) የሚያጠቃልል ነው ።

ላዕላይ መዋቅር በመሠረቱ ላይ የተገነባ ፣ መሠረቱን የሚያንፀባርቅ ፣ መሠረቱ እንዲጠናከርና እንዲስፋፋ የሚያገለግል ነው ። ላዕላይ መዋቅር በኅብረተሰቡ ውስጥ ሰፍኖና የበላይነትን ይዞ የሚገኘው ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት (መሠረት) ነፀብራቅ እንደመሆኑ ዕድሜው ፣ አጠቃላይ ባሕርዩና ለውጡ በኢኮኖሚያዊ ግንኙነቱ ለውጥ ይወሰናል ። ሆኖም ላዕላይ መዋቅር ልዩ ልዩዎቹን የማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና መልኮችንና የነርሱም ቁሳዊ ገጽታዎች የሆኑትን ድርጅቶችን ፣ ተቋሞችንና መንግሥትን የሚያቅፍ በመሆኑ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በእኩል ደረጃ ላይ ላይገኝ ይችላል ። ይህም የላዕላይ መዋቅርን አንፃራዊ ነፃነት ያሳያል ። ላዕላይ መዋቅር በመሠረቱ የሚወሰን ቢሆንም መልሶም በመሠረቱ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል ። ላዕላይ መዋቅር ለመሠረቱ ዕድገት የሚያመቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ዕድገቱን የማፋጠን አለበለዚያም የማያመቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ለመሠረቱ ዕድገት ዕንቅፋት ሊሆን ይችላል ።

መሠረት (ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች) በመደብ ኅብረተሰቦች ውስጥ ቅራኔን ያቀፈ ነው ። በኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች ባሕርይ የተነሣ በተፃራሪ መደቦች መሀከል የሚኖረው ቅራኔ የኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶቹ ነፀብራቅ በሆነው በላዕላይ መዋቅርም ውስጥ ይከሰታል። በወዝአደሩ መደብና በቡርዧው መደብ ፓርቲዎች መሀከል በሚደረገው ትግል (የርዕዮተዓለም ፣ የፖለቲካ) በወዝአደሩ መደብ የሙያ ፣ የመረዳጃ ፣ የብዙኃን ድርጅቶችና በካፒታሊስቱ መንግሥትም መሀከል በሚካሄደው ትግል ይገለጻል ። የዚህም ትግል ውጤት የወዝአደሩን መደብ አሸናፊነት ካስከተለ በማኅበራዊ አብዮት አማካይነት ኢኮኖሚያዊ መሠረቱ ይለወጣል ። ቡርዧዚው የበላይነቱን ካላጣ ግን መዋቅሩን በመጠቀም መሠረቱ ይበልጥ እንዲጠናከርና እንዲደላደል ያደርጋል ። ይህም የመሠረትና የላዕላይ መዋቅር ዲያሌክቲክስ ነው ።

እያንዳንዱ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት የራሱ የሆነ የመሠረትና የላዕላይ መዋቅር ቅንጅት አለው ። የማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ለውጥም የሁለቱንም ለውጥ ያስከትላል ። ሆኖም መሠረቱ ከላዕላይ መዋቅር አንፃር ሲታይ ከሞላ ጐደል በአፋጣኝ ሲለወጥ ላዕላይ መዋቅሩ አንፃራዊ ነፃነት ስላለው ዘግይቶ ይለወጣል ። በተለይም ከኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች ጋር የቅርብ መያያዝ የሌላቸው ክፍሎች ለምሳሌ ባህላዊ አመለካከቶች ዘግይተው ይለወጣሉ ። ፖለቲካዊና ሕጋዊ የላዕላይ መዋቅር ክፍሎች ግን ወዲያውኑ ይለወጣሉ ።

(መሠረትን ፣ ላዕላይ መዋቅርን ፣ ታሪካዊ ቁስአካልነትን ፣ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓትን ይመለከቷል ።)

## መስተጋብር

*(Interaction)*

ነገሮችና ክስተቶች እርስ በርሳቸው ወይም አንዱ በሌላው ላይ በሚያሳርፉት ተፅዕኖ ፣ በተለያዩ ቁሳዊ ነገሮችና ክስተቶች መሀከል የሚገኝ ማናቸውም ግንኙነትና መያያዝ እንዲሁም አንዱ የሌላውን እንቅስቃሴ በማፋጠን ወይም በመግታት ለአንድ ሂደት የሚያደርገውን ጠቃሚ ወይም ጉዳት አስተዋጽኦ የሚገልጽ ጽንሰ ሐሳብ ነው። መስተጋብር የማናቸውንም ቁሳዊ ነገሮች ሥርዓት ፣ ህልውናና አወቃቀር ፣ እያንዳንዱ ቁሳዊ ሥርዓት ከሌሎች በርካታ ቁሳዊ ሥርዓቶችና በነርሱም ውስጥ ከሚገኙ አካሎች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት የሚያስከትላቸውን ባሕርያት ወይም የሚፈጥራቸውን አዲስ ነገሮች ቅርፅና ይዘት የሚገልጽ ነው ።

መስተጋብር የማናቸውም ነገር ህልውና የሚከሰትበት እንደመሆኑ ከመስተጋብር ውጭ ህልው ሆኖ የሚገኝ ነገር የለም ። መስተጋብር በቁሳዊ ሥርዓቶች ውስጥ የሚፈጠሩት የመንሥኤና የተገብሮት ግንኙነቶች በማያቋርጥ ሁኔታ የሚከሰቱበት ሂደት ነው ። ይህንንም የመስተጋብር ሁለንታዊ ባሕርይ በተለይ የቁስአካልን እንቅስቃሴ በምናጤንበት ጊዜ በሚገባ መገንዘብ ይቻላል ።

ለምሳሌ ክእንቅስቃሴ ዓይነቶች ተናክአታዊ እንቅስቃሴን ፣ ሙቀትን ፣ ብርሃንን ፣ የኤሌክትሪክ ኃይልን ፣ ማግኒቲዝምን ፣ የኬሚካል ውህደትንና መነጣጠልን ፣ የአካላት ቅንብርን ወዘተ... ብንመለከት በተለያዩ ገጽታዎች የሚከሰቱት እንቅስቃሴዎች አጠቃላይ ድምር ሳይለወጥ ነገር ግን አንዱ ወደሌላው የሚሸጋገርበት ፣ አንዱ የሌላውን ባሕርይና ምንነት የሚወስንበት ፣ በአንድ ሁኔታ መንሥኤ የሆኑት በሌላ ሁኔታ ተገብሮት እየሆኑ ለምሳሌ ትናክአታዊ እንቅስቃሴ ወደ ሙቀት ፣ ወደ ኤሌክትሪክ ኃይል ፣ ወደማግኒቲዝም ፣ ወደ ብርሃን ወዘተ... ሲለወጥ በተገላቢጦሽ እነዚህ ደግሞ ወደሱ የሚለወጡበትን የያዘ ግንኙነትና እንቅስቃሴ ማለትም መስተጋብራዊ ሂደትን መረዳት ይቻላል ።

ተፈጥሮ በአጠቃላይ እጅግ የተለያዩና በርካታ የሆኑ ቁሳዊ አካላት በተለያዩ መልኮች ተያይዘውና ውሁድ ግንኙነት ፈጥረው የሚገኙበት ሥርዓት ነው ። ይህ ከከዋክብት እስከ አቶሞች ያሉበት ሥርዓት ልዩ ልዩ ቁሳዊ አካላት በተለያዩ ግንኙነቶች ተቀነባብረው የሚገኙበት እንደመሆኑ ደግሞ አንዱ ቁሳዊ አካል በሌላው ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖ አለ ። እንዲያውም ለእንቅስቃሴ መንሥኤ የሚሆነው ይህ የቁሳዊ አካላት ውስጣዊ ግንኙነት ፣ መተሳሰርና አንዱ በሌላው ላይ ወይም ከሌላው ጋር የሚፈጥረው ተፅዕኖ ነው ።

በተፈጥሮ ውስጥ አንዳችም ድርጊት በተናጠል አይከናወንም ። ስለሆነም እያንዳንዱ ነገር ከሌላው ጋር ባለው ግንኙነት ወይም ከሌላው በተያያዘ ሁኔታ የሚደርስበትን መስተጋብራዊ የይዘት ወይ የቅርፅ ለውጥ ከዚህም ጋር የእንቅስቃሴን አያሌና የተያያዙ መስተጋብራዊ ባሕርያት ሳይገነዘቡ ስለሁኔታዎች ትክክለኛ አመለካከት መቅረፅ አይቻልም ። የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለማዊ አመለካከት አንዱ ዋንኛ መሠረት የሆነው የዲያሌክቲክስ ዋንኛ ሕግም የሁለንታዊ መስተጋብራዊ ግንኙነት የሆነው ከዚህ የተነሣ ነው ።

(የዲያሌክቲክስ ሕግን ፣ ፈርጆችን ፣ ሥርዓትን ይመለከቷል ።)

# መስተጋብአዊ ሥነ አመክንዮ

*(Inductive Logic)*

መስተጋብእ የግዕዝ ቃል ሲሆን ትርጉም የሚሰበሰብ ፣ ሰብሳቢ ማለት ነው።

ከአንድ መለስተኛ መረጃ ወይም ሐሳብ ወደ ከፍተኛና አጠቃላይ እንዲሁም ከቀላል ወደ ውስብስብ ፣ ከተናጠል ወደ አጠቃላይ ሐሳብ ሽግግር የሚደረግበት የትንታኔና የሐሳብ ሥነ አመክንዮአዊ ሂደት መስተጋብአዊ ሥነ አመክንዮ ይባላል ። እንደ አሰባሰቡ ደረጃም የተሟላ ወይም ከፊል መስተጋብአዊ ሥነ አመክንዮ ሊሆን ይችላል ።

የተሟላ መስተጋብአዊ ሥነ አመክንዮ ማለት የነገሮችን ወይም የክስተቶችን ስብስብ በተናጠል በማጥናትና በጥናቱ ግኝት ላይ በመመሥረት ስብስቡን ከሚመለከት አጠቃላይ ከሆነ የመደምደሚያ ሐሳብ ላይ መድረስ ማለት ነው ። በዚህ መልክ የሚገኝ የመደምደሚያ ሐሳብ አባላቱን በሙሉ በዝርዝር በማጥናት የሚገኝ ነውና ትክክለኛነት ያለው ቢሆንም የአገልግሎቱ መስክ ግን ጠባብ ነው ። ምክንያቱም ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለው አነስተኛ ቁጥርና ሊጠኑ የሚችሉ አባላት ባሉት ስብስብ ላይ ብቻ በመሆኑ ነው ።

ከፊል መስተጋብአዊ ሥነ አመክንዮ በጣም በርካታ አባላትን ያቀፈ ስብስብን በሚመለከት አባላቱን በሙሉ በማጥናት ሳይሆን ከነርሱ ውስጥ ከፊሎቹን ብቻ በማጥናትና በውጤቱም ላይ በመመሥረት ስብስቡን በሞላ ከሚመለከት አጠቃላይ መደምደሚያ ሐሳብ ላይ መድረስ ማለት ነው ። የስብስቡ ጥቂት አባላት ስብስቡን የሚወክሉ ባሕርያትን እንደሚያንፀባርቁ ተደርጐ ለመደምደም ቢቻልም የዚህ መደምደሚያ ትክክለኛነት ግን የበለጠ ጥናት የሚጠይቅና በተከታታይ ምርምር መረጋገጥ ያለበት ነው። ከዚህ ዓይነት ችግር ለመላቀቅ ግን ለናሙና የሚመረጡትን አባላት መሠረታዊ ግንኙነቶችና የእርስ በርስ መደጋገፍ በበቂ ማጥናት ያስፈልጋል ። በዚህም ጊዜ ትኩረት መደረግ ያለበት በሚጠኑት አባላት መሠረታዊ ባሕርያትና ፍሬ ሐሳቦች ላይ ሊሆን ይገባል ። ስለ

ሞገም የዚህ ዓይነቱ ከፊል መስተጋብአዊ ሥነአመክንዮ ዋነኛ ባሕርይ የክስተቶችንና የነገሮችን መሠረታዊ ግንኙነቶች ግልጽ የማድረጊያ ዘዴ መሆኑ ነው ።

ለምሳሌ ውሀና ሕይወት ግንኙነት አላቸው ከሚለው ሕውስታዊ መረጃ በመነሣት ሕይወት ባለበት ቦታ ውሀ አለ ። ስለ ሆነ ያለውሀ ሕይወት ሊኖር አይችልም ወደሚለው አጠቃላይ ሐሳብ ለመሸጋገር ይችላል ። ይህ ግን ፍጹማዊ አይደለም ።

(ሥነ አመክንዮን ፣ ምንጩታዊ ሥነ አመክንዮን ፣ ዲያሌክቲካዊ ሥነ አመክንዮን ይመለከቷል ።)

## መሪር

*(Tragic)*

መሪር የግዕዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙም የሚያሳዝን ፣ የሚያበሳጭ ፣ የሚከነክን ማለት ነው።

በኅብረተሰብ ዕድገት ውስጥ በግለሰቡና በኅብረተሰቡ መካከል ያሉትን ቅራኔዎች ፣ በውበትና በሕሡም መካከል የሚካሄደውን ትግል የሚገልጽ የሥነ ውበት ፈርጅ ነው ። መሪር የሚያንፀባርቀው ለጊዜው ሊፈቱ ያልቻሉ ቅራኔዎችን ነው ። በመሆኑም አስፈላጊ በሆነ ታሪካዊ ሁኔታና በሰዎች ተግባራዊ እንቅስቃሴ መካከል የሚኖረው አለመጣጣም በተለይ የሚጠቀስ መሪር ሁኔታ ነው ። መሪር የጭንቀትና የሥቃይ ስሜቶችን የሚቀሰቅስና ብዙውንም ጊዜ የቅራኔውን ውስብስብነት ወደ ሞት የሚወስድ ነው ።

የመሪር ምክንያት በማኅበራዊ ኃይሎችና በኅብረተሰብ የዕድገት ሕጐች መካከል የሚነሡት ግጭቶች እንደሆኑ ማርክሳዊ ሥነ ውበት ያስረዳል ። ለምሳሌ አንድ ተራማጅ መደብ ከሁኔታዎች አለመብሰል ወይም አለመመቻቸት የተነሣ በትግሉ ማሸነፍ ሲያቅተው መሪር ሁኔታ ይፈጠራል ፤ ወይም ደግሞ የአረጀው መደብ አንዳንድ አባሎች የመደባቸውን መውደቅ በመረዳት ተራማጅ በሆነው መደብ ውስጥ በመቀላቀል የነበራቸውን ሥልጣን ለማስቀረት ሲታገሉ ማየት መሪር ይሆናል ።

መሪር ሐዘን የሚፈጥር ቢሆንም ሥነ ውበታዊ ደስታንም ያቀፈ ነው ። ለዚህ ደስታ ምክንያት የሚሆኑት መሪር የሚፈጥረው የስሜቶችና የንቃተ ኅሊና ጥራት ፣ መጥፎ ነገሮችን አስመልክቶ የሚያስከትለው ጥላቻና ለፈቃድ የሚሰጠው ድፍረት ናቸው ። በሶሻሊስት ሥርዓት ግንባታ ውስጥ አዲስ የተጋድሎ ሁኔታ ተፈጥሯል ። የኮሚኒስት ሥርዓት አይቀሬ መሆኑን የተገነዘቡና በሕዝብ ኃይል ላይ ሙሉ እምነት ያላቸው የታጋይ አብዮታዊ ጀግኖች ፈቃድ በጣም አስቸጋሪ ፣ አደገኛና ውስብስብ ከሆነ ሁኔታ ጋር የሚያደርገው ትግልና ትግሉ የሚፈጥራቸው ቅራኔዎች ለመሪር ሁኔታ መንሥኤ ናቸው ።

(ሥነ ውበትን ይመለከቷል ።)

## መሬት ከበርቴ (የ—)

*(Landlord)*

የሰፋፊ መሬት ባለቤት የሆኑ ፣ በምርት ተግባር ምንም ተሳትፎ ሳያደርጉ ሌሎች ማለትም ገባሮች ወይም ጭሰኞች የደከሙበትን ምርት የሚያጋብሱ ሰዎችን የሚያጠቃልል መደብ ነው ። የዚህ መደብ አባሎች መሬት በማሳረስ ፣ በማከራየት ፣ በመግዛትና በመሸጥ እንዲሁም ገንዘብና እህል በወለድ በማበደር ከፍተኛ ሀብት የሚሰበስቡ ከባሪያው ሥርዓተ ማኅበር ቀጥሎ በተከሰተው በፊውዳሉ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የሚገኙ የገዥ መደብ አባላት ናቸው ።

ንጉሣውያን ቤተሰብ ፣ መሳፍንት ፣ መኳንንት ፣ ከፍተኛ የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች ፣ የብዙ መሬት ባለቤት የሆኑ ባላባቶችና ሌሎችም የነዚህ ሁሉ የጥቅም ተካፋዮች በዚሁ መደብ ውስጥ የሚጠቃለሉ በመሆናቸው የለውጥ ከፍተኛ ዕንቅፋት ናቸው ። በታሪክ እንደታየው በብዙ ሀገሮች ተራማጅና አብዮታዊ ኃይሎች ይህን አድኃሪ መደብ ከሥልጣን ለማስወገድ መሥዋዕትነት የተመላው ትግል አካሂደዋል ።

(መደብን ፣ ፊውዳሊዝምን ይመለከቷል ።)

## መብትና ግዴታ

*(Right and Duty)*

ሰዎች በሚገኙበት ማኅበራዊ ሥርዓት ውስጥ ባላቸው ቦታና ኃላፊነት ማድረግ ያለባቸውንና ሊደረግላቸው የሚገባውን የሚገልጹ ፈርጆች ናቸው ። የመብትና የግዴታ ስፋትና ግንኙነት የሚወሰነው በማኅበራዊ ሁኔታ ነው ።

ሐሳባውያን ይህን ሐቅ ስለማይቀበሉ ስለመብትና ስለግዴታ ያላቸው አመለካከት የተዛባ ነው ። በነሱ አባባል ሰው ፣ ሰው በመሆኑ ብቻ ተፈጥሮአዊ መብቶች አሉት ። በዚህም አመለካከታቸው መሠረት ሰው በተፈጥሮ በማኅበራዊና በታሪካዊ ዕድገት የሚወሰን መሆኑን ስለማይገነዘቡ በግዴታና በመብት መካከል ያለውን መስተጋብር ሊረዱ አልቻሉም። በእርግጥ በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የመብትና የግዴታ ግንኙነት ሚዛናዊ ሊሆን አይችልም ። የገዥው መደብ መብቱ የሰፋ ፣ ግዴታው ያነሰ ሲሆን የተገዥው መደብ ደግሞ ግዴታው የበዛና መብቱ በዚያው አንፃር የጠበበ ነው ። መብት የሚገልጸው የበላይነትን በመሆኑ ግዴታ የተጨቋኝነትን ፍች ይይዛል ። ይህ በተሸፋፈነ መደባዊ አመለካከት ሲገለጽ የመብቱ ስፋት ከግለሰቡ ኃላፊነትና አስተዋጽኦ ስፋት እንደሚመነጭ ተደርጐ ይነገራል ። ትክክለኛ ግንዛቤው ግን ይህ የግዴታና የመብት የተዛባ ግንኙነት የሚያንፀባርቀው የምርት ግንኙነትን ሁኔታ ነው ። ባለንብረትና ንብረት አልባ የሆኑት ግዴታንና መብትን አስመልክቶ እኩል ከሆነ ሚዛን ላይ ሊቀመጡ አይችሉም ።

የሁለቱን ግንኙነት በትክክል ሊያዋቅር የሚችለው የኮሚኒስት ሥርዓት ብቻ ነው ። የማምረቻ መሣሪያዎች ከግል ይዞታ መላቀቅ ሰዎች እኩል መብት እንዲኖራቸው ያደርጋል ። የተራድኦ ግንኙነት ሰዎችን የጋራ ኃላፊነት ተገዥ ስለሚያደርግ የግዴታቸው መሠረት ይሆናል ። ግዴታ ማለት በግድ መሥራት ሳይሆን መብት ለማግኘት ግለሰቡ የሚያደርገው ማኅበራዊ አስተዋጽኦ ነው ። መብት ደግሞ ግለሰቡ ነፃ ዕድገት እንዲያገኝ ከኅብረተሰቡ የሚሰጠው ነው ። የግለሰቡ ግዴታ የኅብረተሰቡ መብት ነው ፤ የግለሰቡም መብት የኅብረተሰቡ ግዴታ ነው ። የተራድኦ ግንኙነት መብትንና ግዴታን ያስማማል ማለት ነው። ይህ የግዴታና የመብት መስተጋብራዊ ግንኙነት የራስን በራስ ማስተዳደር መርህ እውን የሚያደርግ በመሆኑ የሰው ባህልና ንቃተ ኅሊና ከከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሳቸውን የሚያመለክት ነው ።

(ኮሚኒዝምን ፣ ሥነ ምግባርን ይመለከቷል ።)

## መንሥኤና ሁኔታ
*(Cause and Condition)*

ሁኔታ ከተግብሮት ቀድሞ የሚገኝ ፣ ነገር ግን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የተግብሮት ወሳኝ ክስተት አይደለም ። ሁኔታ የአንድ ነገር ውስጣዊ ቅራኔ የሚከናወንበት አካባቢ ነው ። ሁኔታ ውስጣዊ ቅራኔ የሚከናወንበት ውጫዊ ቅራኔም ሊሆን ይችላል ። ሁኔታ በርካታ ነገሮች ለአንድ ነገር መገኘት አስፈላጊ ሆነው ነገር ግን አንዱ ወሳኝ ሆኖ ሌሎች እራሳቸው በራሳቸው የወሳኝነት ሚና ባይኖራቸውም ለነገሩ ወይም ለድርጊቱ መከናወን ወይም ለተግብሮቱ መገኘትና መጓላት ባለባቸው ነገሮች መስከ ሊገኝ ይችላል ።

ሙቀት ፣ አፈርና እርጥበት ስንዴን ወደ ቡቃያነት እንዲለወጥ ቢያስፈልጉም የስንዴው ወደ ቡቃያነት የመለወጥ ጉዳይ የውስጣዊ ባሕርይ ተግብሮት እንጂ በተጠቀሱት ነገሮች መንሥኤነት አይደለም ። አስበለዚያ የተጠቀሱት ነገሮች ሁኔታዎች መሆናቸው ቀርቶ መንሥኤዎች ከሆኑ ግናቸውንም ስንዴን መሰል ነገር ወደ ቡቃያነት መለወጥ በቻሉ ነበር ። የሥራ ተግብሮች ፣ የሥራ ማከናወኛ ቁሳቁሶችና ሥራ አንድ ላይ ሀብት ለማፍራት ቢያስችሉም ከሥራ ተገንጥለው ሁለቱ ብቻቸውን ሀብት ሊያፈሩ አይችሉም ።

መንሥኤ ከተግብሮት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለውና በጊዜ አንፃር ተግብሮትን በመቅደም ብቻ የሚገኝ ሳይሆን ተግብሮትም እንዲኖር ወይም እንዲገኝ በቀጥተኛ መንገድ የሚወስንም ጭምር ነው ። ሁኔታ ግን ተግብሮትን በጊዜ አንፃር ቢቀድምም በቀጥተኛ መንገድ አይወስንም ። ይሁን እንጂ ያለ ሁኔታ ተግብሮት ከቶውንም ሊታሰብ አይችልም ።

መንሥኤ ፣ ሳቢያና ሁኔታ እንዲሁም በተወስነም መስከ መንደርደሪያ ተግብሮትን በመቅደማቸው ተመሳሳይ መስለው ቢታዩም ልዩነት አላቸው ።

ሳቢያና ሁኔታ ተግብሮትን ቀድመው መገኘታቸውና ተግብሮትን የማይወስኑ መሆናቸው ተመሳሳይነታቸው ሲሆን ልዩነታቸው ግን ሁኔታ ለተወሰነ ተግብሮት የግድ መገኘት ወይም መጓላት ያለበት መሆኑ ነው ። ለአ

ንድ ማኅበራዊ አብዮት የግድ ነባራዊና ኅሊናዊ ሁኔታዎች በተለያየ የብስለት ደረጃ ቢሆን መሟላት አለባቸው ። ሳቢያ ግን እንደ ድርጊቱ ወይም እንደተገብሮቱ አለበሰ ሊያም እንዳታሪካዊ ሁኔታው የተለያየ ሊሆን እሊያም ሳያስፈልግ ይችላል ።

የውጫሌን ስምምነት መፍረስ ሰበብ በማድረግ ኢምፔሪያሊስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ልትወር ችላለች ። የውጫሌ ስምምነት ባይፈርስም ኖሮ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን መውረሯ የማይቀር ነበር ። ስለዚህ የውጫሌ ስምምነት ለኢትዮጵያ መወረር ሰበብ እንጂ መንሥኤ ወይም ሁኔታ አልነበረም ።

(ፈርጆችን ይመለከቷል ።)

## መንሥኤና ተገብሮት

*(Cause and Effect)*

ተገብሮት ተገብረ ከሚለው ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ድርጊት ፣ ከንውን ማለት ነው ።

መንሥኤ ማለት አዲስ ክስተትን የሚያስገኝና ከርሱም ጋር ካለው ግንኙነት አንፃር ሲታይ ቀድሞት የሚገኝ ክስተት ነው ። ተገብሮት መንሥኤ የሚያስከትለውና የርሱም ድርጊት የሚፈጥረው ክስተት ነው ። መንሥኤው ራሱ የሌላ ክስተት ተገብሮት በመሆኑ መንሥኤና ተገብሮት ተለዋዋጭ ናቸው ። ግናቸውም መንሥኤ ተገብሮትን ቀድሞ የሚገኝ ቢሆንም ግናቸውም ተገብሮትን ቀድሞ የሚገኝ ክስተት ግን የተጠቀሰው ተገብሮት ምክንያት ነው ማለት አይደለም።ለምሳሌ የተወረወረ ድንጋይ ወደ መሬት ይወድቃል። ሆኖም ለድንጋዩ ወደ መሬት መውደቅ ምክንያት የድንጋዩ መወርወር ሳይሆን የመሬት ስበት ነው። መርወራው ከድንጋዩ መውደቅ የሚቀድም ቢሆንም የተገብሮቱ መንሥኤ አይደለም ።

መንሥኤ ተገብሮትን የሚያስከትል ቢሆንም ከተገብሮቱ ጋር የሚወራረስ ነው ። አንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ መንሥኤና ተገብሮት ሊሆን የሚችል ከመሆኑም በላይ በአንድ ወቅትና ሁኔታ መንሥኤ የነበረው በሌላ ወቅትና ሁኔታ ተገብሮት ሊሆን ይችላል። እንዲሁም ተገብሮት ወደ መንሥኤነት ሊለወጥ ይችላል። ተገብሮት በመንሥኤ በመወሰን ብቻ የሚቀር ሳይሆን ተገብሮት መልሶ በመንሥኤው ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል ። ካፒታሊዝም (መንሥኤ) በገጠር ውስጥ ዘመናዊ እርሻን በማስፋፋት ገበሬውን ወደ ወዝአደርነት ቢለውጠውም ( ተገብሮት) የወዝአደሩ ቁጥር መጨመር በተራው የቡርዧዚውን ትርፍ በማሳደግ የካፒታሊዝምን ዕድገት ያፋጥናል ።

ግናቸውም ከስተት የተወሰነ መንሥኤ ተገብሮት እንጂ መንሥኤ የሌለው ተገብሮት ከቶውንም ሊኖር አይችልም ። የመንሥኤና የተገብሮት ግንኙነት ውስጣዊ ፣ ነባራዊና ሁለንታዊ ነው ።

አንድ መንሥኤ በርካታ ተገብሮቶችን ሊያስገኝ የሚችለውን ያህል አንድ ተገብሮት ደግሞ በርካታ መንሥኤዎች ሊኖሩት ይችላል ። ሆኖም እነዚህ መንሥኤዎች በሙሉ ተገብሮቱን በማስገኘቱ ረገድ እኩል ሚና አይኖራቸውም ።

መንሥኤ ከሳቢያ ይለያል ። ሳቢያ አንድን ድርጊት ቀድሞ የሚገኝና ድርጊቱም እንዲፈጸም የሚያስችል ግን ይህንን ድርጊት በግድ የማያስከትል ወይም የማይወስን ክስተት ነው ። በሳቢያና በተገብሮት መሀከል ያለው ግንኙነት ውጫዊና መሠረታዊ ያልሆነ ነው። ለምሳሌ የውጫሌ ስምምነት ከአድዋ ጦርነት የቀደመ ቢሆንም የስምምነቱ መፍረስ ግን የአድዋ ጦርነት ምክንያት አይደለም ። የጦርነቱ ምክንያት የጣሊያን ኢምፔሪያሊዝም የመስፋፋት ፍላጎት ነበር ። በሳቢያና በተገብሮት መካከል ያለው ግንኙነት ውጫዊ እንዲሁም የአጋጣሚ ጉዳይ ሊሆን ይችላል ።

(ፈርጆችን ይመለከቷል ።)

## መን ፣ ቶማስ

*(Mun, Thomas)*

ከ1571—1641 የኖረ እንግሊዛዊ ኢኮኖሚስትና የዳበረ ሜርካንቲሊስት አስተሳሰብ መሥራች ነው ። መን "ኢስት ኢንዲያ ካምፓኒ" የተባለው ኩባንያ ዲሬክተርና የእንግሊዝ መንግሥት የንግድ ኮሚሽነር በመሆን ሠርቷል ።

" ኢንግላንድስ ትሬዠር ባይ ፎሪን ትሬድ " በሚል ርዕስ በ1664 በታተመው መጽሐፍ ውስጥ ለገቢ ንግድ ከሚወጣው ወጪ ከወጭ ንግድ የሚገኘው ገቢ እንዲበልጥ ማድረግ ያሻል የተሰኘውን ሐሳብ በመ

ደገፍ ማብራሪያ ሰጥቷል ። ካርል ማርክስ የመንን ሥራ የሜርካንቲሊዝም ወንጌል ሊሆን የበቃ የዘመኑ ትልቅ ሥራ ነው ሲል ገልጾታል ።

መን እንደቀደሙት ሜርካንቲሊስቶች ሁሉ ሀብትንና ገንዘብን አንድ አድርጐ ይመለከታል ። ይሁንና ቀደምት ሜርካንቲሊስቶች በየዓመቱ ወደ ሀገር የሚገባው የወርቅና የብር መጠን ከሀገር ከሚወጣው እንዳይበልጥ ማድረግ ያሻል ያሉትን ሐሳብ ግን አልተቀበለውም ። እንደመን አስተሳሰብ ሀብትን (የወርቅን ክምችት) ማሳደግ የሚቻለው በቀጥታ በወርቅና በብር ዝውውር ላይ በሚጣል ገደብ ሳይሆን ወርቅንና ብርን በሚያስገኘው የውጭ ንግድ መስከ የወጪ ንግድን ከገቢ ንግድ በማስበለጥ መሆን ይኖርበታል ባይ ነው ። መን ወርቅንና ብርን የሚያያቸው እንደ "ክቡር ድንጋይነታቸው" ብቻ ሳይሆን እንደዝውውር መሣሪያነታቸውና እንደካፒታልነታቸውም ጭምር ነው ።

(ሜርካንቲሊዝምን ይመለከቷል ።)

## መንደርደሪያና ክትያ

*(Ground and Consequence)*

በሁለት ሐሳቦች መካከል ያለ ግንኙነት ፥ አንዱ ሐሳብ ከሌላው ሐሳብ የሚንደረደር ፥ ከርሱም ጋር ሳይፋለስ ወይም የዚህን ሐሳብ ይዘት ሳያናጋ ሐሳቡን ሥርዓት ባለው መንገድ በማዋቀርና በማዳበር የሚደመድም ሐሳብ ማለት ነው ። ሁለት ሐሳቦች ካላቸው ግንኙነት አንፃር ሲታዩ የመጀመሪያው መንደርደሪያ ሲሆን ቀጥሎ የሚመጣውና ከመንደርደሪያው የሚመነጨው ሐሳብ ክትያ ይባላል ። ስለዚህ በመንደርደሪያና በክትያ መካከል ያለው ግንኙነት የሐሳቦች ግንኙነት ነው ።

በመንደርደሪያና በክትያ መካከል ያለው ግንኙነት በሁለት ሐሳቦች መካከል ያለ ግንኙነት ቢሆንም ሐሳቦችና በመሀከላቸው ያለው ግንኙነት ግን የእውነታ ነፀብራቅ ናቸው ። በመንደርደሪያና በክትያ መካከል ያለው ግንኙነት የሐሳብ ግንኙነት እንደመሆኑ የሁለቱ ግንኙነት ትክክለኛነት በሐሳቦች ትክክለኛነት የሚወሰን ነውና ከእውነታ ጋር ሊመሳሰሉ ወይም ሊቃረኑ ይችላሉ ። ክትያ ሐሳቡ ከመንደርደሪያው ሐሳብ ተነሥቶ ፥ እርሱንም በማያፋልስ ሁኔታ ሥነ አመክንዮአዊ በሆነ መንገድ ቢዋቀርም ክትያው ግን የተሳሳተ ሊሆን ይችላል ።

መንደርደሪያ

ሰው ሁሉ ሟች ነው ፤
አበበም ሟች ነው ፤
ስለዚህም አበበም ሰው ነው ።

ይህንን ምሳሌ ካለን ዕውቀት አንፃር ሳይሆን ከምሳሌው ሐሳብ ብቻ በመነሣት ብንተነትን ክትያ ሐሳቡ የመንደርደሪያውን ሐሳብ የማያፋልስና እርሱንም አዳብሮ በሥነ አመክንዮአዊ ሥርዓት የሚደመድም በመሆኑ ትክክል ነው ። በሌላ አንፃር ግን ክትያ ሐሳቡ ከእውነታ ጋር የሚቃረን በመሆኑ ትክክል ወይም እውነት አይደለም ። ምክንያቱም በዚህ ምሳሌ ውስጥ አበበን ሰው ያደረገው ሟችነቱ ሲሆን ሟች የሚሆን ሕይወት ያለው ነገር በሙሉ ግን ሰው አይደለም ።

(ፈርጆችን ይመለከቷል ።)

## መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም

*(State Monopoly Capitalism)*

መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም በካፒታሊስት ሞኖፖል ኃይልና በቡርዧው መንግሥት ኃይል ጥምረት የሚፈጠር ከፍተኛው የሞኖፖል ካፒታሊዝም ቅርፅ ነው ። ለመጀመሪያ ጊዜ ቃሉን የተጠቀመበትና ንድፈ ሐሳቡን ያጠናቀረው ሌኒን ሲሆን እሱም ሞኖፖል ካፒታሊዝም ወደ መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም ማደጉ የማይቀር መሆኑን አሳይቷል ።

የመንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም መፈጠርና መዳበር መሠረቱ በካፒታሊስቱ ስልተ ምርት ውስጥ የሚገኙ የማይታረቁ ቅራኔዎች በተለይም በምርት ማኅበራዊነትና ካፒታሊስቱ ምርቱን የግሉ በማድረጉ መካከል ያለው ቅራኔ እየከረረ መሄድ ነው ። በዚህ ሁኔታ የቡርዧው መንግሥት ሞኖፖሎችን የተዘፈቁባቸው የማይታረቁ ቅራኔዎች ከሚያስከትሉባቸው ችግር ለማውጣት ጣልቃ

[illegible]ነቱን ያጠናክራል ። ሞኖፖሎች የዓለምን ገበያ በመካከላቸው ለመቀራመት በሚያደርጉት እየተካረረ በመሄድ ላይ በሚገኘው ውድድርም የቡርዧውን መንግሥት ድጋፍ ይጠይቃሉ ። የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ እየተካረረ መምጣትም የመንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝምን ዕድገት አፋጥኖታል ። የሶሻሊዝም እያደላ በመምጣት ላይ ያለውን የዓለም ኃይል አሰላለፍ ለመግታት በሚያደርጉት ከንቱ ሙከራ የኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ገዥ መደብ አባላት የሞኖፖል ኃይልና የቡርዧ መንግሥታት ኃይል ጥምረት እንዲጠናከር ያደርጋሉ ። እንዲሁም ሞኖፖሎች በቡርዧ መንግሥታት ረዳትነት በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮችን ሠርቶ አደር ሕዝቦች በቡርዧ ርዕዮተዓለምና ፖለቲካ ቁጥጥር ሥር በማዋል የብዝበዛ ሥርዓቱን ለማቆየት ይጥራሉ ።

መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም ከሞኖፖሎች መዳበር ጋር ማቆጥቆጥ የጀመረው በያዝነው ምዕት ዓመት መጀመሪያ አካባቢ ላይ ነው ። ሁለቱ የዓለም ጦርነቶችና በጦርነቶቹ መካከል በነበረው ጊዜ ውስጥ የታየው ታላቁ የዓለም ኢኮኖሚ ቀውስ መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም እንዲዳብር ረድተዋል ። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም አዳዲስ ገጽታዎችን በመያዝ ሊስፋፋ ችሏል ። እንቅስቃሴውንም ከሶሻሊስቱ ዓለም ጋር ከሚደረገው ትግል ጋር በበለጠ በማገናዘብ ላይ ይገኛል።

በአሁኑ ጊዜ መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም ልዩ ልዩ ቅርፆችን ይዞ ይገኛል። የቡርዧ መንግሥት በመንግሥታዊ በጀት ፣ በድጎማ ፣ በታክስ ፣ በብድርና በገንዘብ ፖሊሲ ፣ በሸቀጦች ዋጋና በምንዳ ፖሊሲ እንዲሁም በሌሎች ኢኮኖሚ ነክ እንቅስቃሴዎቹ አማካይነት የብሔራዊ ገቢ ክፍፍል ተጠቃሚ ሞኖፖሊስቶች እንዲሆኑ ያደርጋል ። የቡርዧ መንግሥት ለሞኖፖሊስቶች እንደ አንድ ዋና የሸቀጥ ማራገፊያ ያገለግላል ። በሞኖፖሊስቶችና በቡርዧ መንግሥት መካከል በሚደረገው ውል መሠረት ሞኖፖሎች የጦር መሣሪያዎችን በገፍ እያመረቱ በከፍተኛ ዋጋ ለቡርዧው መንግሥት በመሸጥ ከፍተኛ የሞኖፖል ትርፍ እንደሚያገኙ የታወቀ ነው ። የቡርዧው መንግሥትም የውጭ ፖሊሲውን ፣ በተለይም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ፖሊሲውን ለማራመድ በሞኖፖል ካፒታል ይገለገላል ። የቡርዧ መንግሥትና የሞኖፖል ካፒታል ተወካዮች ባንድነት ዓለምን በመካከላቸው ዳግመኛ ለመከፋፈል በሚያደርጉት መሯሯጥ ዓለም አቀፍ ኅብረቶችንና ስምምነቶችን እንዲሁም ካፒታሊስት ኅብረትን ይፈጥራሉ ፤ ያጠናክራሉ ።

መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም የሚይዘው አንድ ሌላ ቅርፅ በሞኖፖሎች ተወካዮችና በቡርዧ መንግሥታት ባለሥልጣኖች መካከል የሚፈጠረው ኅብረት ነው ። የመንግሥት ባለሥልጣኖች በኮርፖሬሽኖች ውስጥ ቁልፍ ቦታዎችን እንዲይዙ ይደረጋል። የኮርፖሬሽን ከፍተኛ ኃላፊዎች ሞኖፖሊስቶችም በመንግሥታዊ መዋቅር ውስጥ በአመራር ደረጃ ሥራ ይመደባሉ ። በዚህ አኳኋን በመንግሥታዊ መዋቅር ውስጥ በመግባት ጥቅማቸውን ያስጠብቃሉ ።

የቡርዧው መንግሥት ራሱ ከብሔራዊ ገቢና ከሀገሪቷ የምርት ኃይሎች ከፍተኛ የሆነውን ክፍል በቀጥታ በቁጥጥሩ ሥር የሚያውል መሆኑ አንድ ሌላ የመንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም ዋና ቅርፅ ነው ። የቡርዧው መንግሥት በበጀት ይዞ የኢኮኖሚ ድርጅቶችን በማቋቋም አንዳንድ ድርጅቶችን ከግል ይዞታ ወደ መንግሥት ንብረትነት በግዥ በማዛወርና በሞኖፖሊስቶች ድርጅቶች ውስጥ የአክሲዮን ባለቤት በመሆን የምርት ኃይሎች ባለንብረት ይሆናል ። ይህ የቡርዧው መንግሥት የምርት ኃይሎች ባለንብረትነት የሞኖፖሊስቶችን ጥቅም የሚያዳብር እንጂ ጥቅማቸውን የሚፃረር አይደለም ። የቡርዧው መንግሥት እንደ ኃይል ማመንጫና መጓጓዣ የመሳሰሉትን ተቋሞች አቋቁሞና ከግል ካፒታሊስቶች ገዝቶ ከሠርቶ አደሩ ሕዝብ በሚሰበስብ ታክስ እየደጎመ በማካሄድ አገልግሎታቸውን ለሞኖፖሊስቶች በአነስተኛ ዋጋ እንዲያቀርቡ ያደርጋል ። ከግል ንብረትነት ወደ መንግሥት ንብረትነት በግዥ የሚያዛውራቸው ድርጅቶችም በአብዛኛው የከሰሩ ወይንም ሊከስሩ የተቃረቡ ሲሆኑ የባለቤትነቱ ዝውውር ዋና ዓላማም ሞኖፖሊስቶቹ ካፒታላቸውን ይበልጥ አትራፊ ወደሆኑ መስኮች ለማዛወር ማስቻል ነው ። በሞኖፖሊስቶች ድርጅቶች ውስጥ የአክሲዮን ባለቤት በመሆንም የቡርዧው መንግሥት ጥቅሙን ከሞኖፖሊስቶች ጋር በቅርብ በማስተሳሰር ድርጅቶቹ ድጎማ

እንዲያገኙ፣ በአነስተኛ ወለድ ብድርና የብድር ቅድሚያ እንዲሰጣቸው፣ አነስተኛ ታክስ እንዲከፍሉ በማድረግ ትርፋቸውን እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል ። የቡርዧው መንግሥት በንብረትነት ከያዛቸው የምርት ኃይሎች የሚያገኘውንም ገቢ በአብዛኛው ሞኖፖሎችን ለመደጐሚያና ከሞኖፖሎቹ ልዩ ልዩ ሸቀጦችን ለመግዣ ያውለዋል ።

መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም ባንድ በኩል የምርት ኃይሎች የዳበሩበትና ማኅበራዊ አመራረት ከላቀ የዕድገት ደረጃ ላይ የደረሰበት ነው ። ይህም ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም ለመሸጋገር ቁሳዊ ቅድመ ሁኔታ የተመቻቸበት ሲሆን መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም በሌላ በኩል የሠርቶ አደሩ ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ የበለጠ እንዲቆረቁዝ የሚያደርግ ነው ። ሞኖፖሊስቶች ከቡርዧ መንግሥት ጋር በማበር በሠራተኛው መደብና በገበሬዎች ላይ የሚፈጽሙት ጭቆናና ብዝበዛ እየተባባሰ ሲሄድ በበዝባዥና በተበዝባዥ መደቦች መካከል ያለው ቅራኔ የበለጠ እየተካረረ ይሄዳል ። ይህም ለሶሻሊስት አብዮት ጎሊናዊ ሁኔታን ለማሟላት የሚረዳ ነው ።

(ኢምፔሪያሊዝምን ይመለከቷል ።)

## መንግሥታዊ ሶሻሊዝም

*(State Socialism)*

በአንዳንድ ሀገሮች ሥርዓተ ማኅበሩ ካፒታሊስት ሆኖ የመንግሥቱ ሥልጣን በቡርዧ መደብ እጅ እንዳለ የተወሰኑ የማምረቻና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ይደረጋል ። በዚህ ወቅት "ለነፃ ውድድርና ላልተገደበ የግል ባለቤትነት" የቆሙ የካፒታሊስት ሥርዓት አቀንቃኞች የተወሰኑ የኢኮኖሚ ተቋሞች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር መዋላቸውን ብቻ በመመልከት ሥርዓቱ ሶሻሊስት እንደ ሆነ አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ ። ሁኔታውንም "መንግሥታዊ ሶሻሊዝም" በሚል ይገልጹታል ።

ይህ ጽንሰ ሐሳብ የቡርዧ የጥገና ለውጥ አስተሳሰብና የአድርባይነት ውጤት ነው ። ይህም አመለካከት አንድ መንግሥት በኢኮኖሚው ውስጥ ጣልቃ በመግባት በይዞታ ወይም በቁጥጥር በሚያደርገው ተሳትፎ ወይም ተፅዕኖ ብቻ ሶሻሊዝም እንደሚገነባ ይቀበላል ። የካፒታሊስቱ መንግሥት አንዳንድ የኢኮኖሚ ተቋሞችን በባለቤትነት ከያዘና ቁጥጥሩን ካጠናከረ የቡርዧው መደብ በ"ነፃ ውድድር" ሳቢያ በሠርቶ አደሩ ሕዝብ ላይ የሚያደርሰውን የኢኮኖሚ ብዝበዛና ማኅበራዊ ቀውስ ማስቀረት፣ በዚህም ገዥው መደብ ከላይ ሶሻሊዝምን የሚያሰፍንበት ሁኔታ መፍጠር ይቻላል የሚል ሲሆን ይህም በንጉሡ ከበርቴ ተምኔታዊ ሶሻሊስቶች አስተሳሰብ የተበከለ ነው። የዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ አራማጅ ከነበሩት መካከል የፈረንሳዩ ብላንክ፣ የጀርመኑ ሮድቤርቱስና ላሳል ይገኙበታል ።

(ተምኔታዊ ሶሻሊዝምን፣ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን ይመለከቷል ።)

## መንግሥታዊ ካፒታሊዝም

*(State Capitalism)*

መንግሥታዊ ካፒታሊዝም የሚለው ጽንሰ ሐሳብ በካፒታሊስት ዕድገት ሂደት የገንዘብ ካፒታሊስቶች ከቡርዧው መንግሥታዊ ቢሮክራሲ ከፍተኛ ክፍሎች ጋር ያላቸውን የጥቅም መተሳሰር እንዲሁም የፖለቲካን ሥልጣንና የኢኮኖሚን ኃይል ቅንጅት የሚያሳይ ነው ። የመንግሥታዊ ካፒታሊዝም ይዘት የሚገለጸው ባለው መንግሥት የመደብ ጠባይ፣ በወቅቱ ተጨባጭና ታሪካዊ ሁኔታ፣ መንግሥታዊ ካፒታሊዝም ባለበት ሀገር ውስጥ በሰፈነው የኢኮኖሚ አጠቃላይና ልዩ ሁኔታዎች ነው ። በቅድመ ሞኖፖል ካፒታሊዝም የነበረው መንግሥታዊ ካፒታሊዝም በወዝአደሩ የበላይ ገዥነት ዘመን ካለውና እንዲሁም በአሁኑ ጊዜ በኋላቀር ሀገሮች ከሚገኘው መንግሥታዊ ካፒታሊዝም የተለየ መልክ አለው ።

በቅድመ ሞኖፖል ካፒታሊዝም የነበረው መንግሥታዊ ካፒታሊዝም የቡርዧውን መንግሥት የካፒታል ክምችት ለማፋጠን በካፒታሊስቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ጣልቃ ለመግባት የሚገደድበት ሁኔታ ነበር ። በዚያ ወቅት መንግሥታዊ ካፒታሊዝም በይዘቱ በመንግሥት ኃይል እማካይነት በተለያየ መንገድ ካፒታሊስቶች የሚያስፈልጋቸውን ርካሽ ጉልበት በቀላሉ ሊያገኙ የሚችሉበ

ቶን ሁኔታ ማመቻቸትን ፣ ይህም ርካሽ ጉልበት ከፍተኛ ተረፈ አሴት ሊያስገኝ እንዲችል የሥራ ሰዓትንና ሁኔታን በሚመለከት ለካፒታሊስቶች ሕጋዊ ድጋፍ መስጠትን ፣ የመንግሥትን መሬት ለግለሰብ ካፒታሊስቶች ማደላደልን ፣ ቅኝ ግዛቶች መያዝንና መዝረፍን ፣ የግል ካፒታሊስቶች ብቻቸው አነስተኛ ካፒታል ሊያቋቁሟቸው የማይችሏቸውንና ለካፒታሊስቱ ኢኮኖሚ መስፋፋት አመች ሁኔታ ሊፈጥሩ የሚችሉትን እንደ ባቡር ሐዲድና እንደ መንገድ የመሳሰሉትን ማስፋፋትን ፣ የኃይል ማመንጫዎች መሥራትንና ትላልቅ ከተሞችን በመንግሥት ሞኖፖል ማቋቋምን ፣ ካፒታሊስቶች ከመንግሥት ድጎማ እንዲያገኙ ማድረግንና በአነስተኛ ወለድ ከፍተኛ ብድር ሊያገኙ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠርን ፣ የሀገር ውስጥ ካፒታሊስቶች በውጭ ሀገር ካፒታሊስቶች ውድድር እንዳይዳከሙ የሚከላከል ታሪፍ መጣልንና የመሳሰሉትን እርምጃዎች መውሰድን የሚያጠቃልል ነበር ።

በካፒታሊስት ሀገሮች የነበረው መንግሥታዊ ካፒታሊዝም በአሁኑ ጊዜ በነዚሁ ካፒታሊስት ሀገሮች ካለው መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም በዓይነት የተለየ ነው ። የካፒታሊስት ሀገሮችን በሚመለከት መንግሥታዊ ካፒታሊዝም በካፒታሊዝም የመጀመሪያ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚከሰት ነው ። የመጀመሪያው (መንግሥታዊ ካፒታሊዝም) ከግል ካፒታሊስቶች የከምችት ዓቅም ደካማነት የተነሣ የቡርዧው መንግሥት የካፒታልን ክምችት ለማፋጠን ከወሰደው እርምጃ የመነጨ ሲሆን መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም የተከሰተው ግን በሞኖፖሎች የበላይነት ሥር የተከማቸውን የደለበ ካፒታል መሠረት በማድረግ ነው ። በመጀመሪያው ሁኔታ ካፒታሊስቱ መንግሥት በኢኮኖሚው ውስጥ ጣልቃ የሚገባው አልፎ አልፎና ሥርዓት በሌለው ሁኔታ ሲሆን በመንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም ወቅት ግን መንግሥት በካፒታሊስቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ጣልቃ የሚገባው ካፒታሊዝም አሁን በደረሰበት የዕድገት ደረጃ ላይ በዓለም የሶሻሊስት ሥርዓት መዳበርና በኢምፔሪያሊዝም የቅኝ አገዛዝ ሥርዓት መፈራረስ የተነሣ የደረሰበትን አጠቃላይ ቀውስ ለማስታገስ በመሆኑ ጣልቃ ገብነቱ የሚካሄደው በማያቋርጥና በተቀናጀ መልክ ነው ።

ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም በሚደረገው ሽግግርና በወዝአደሩ የበላይ ገዥነት መንግሥት ሥር መንግሥታዊ ካፒታሊዝም እንደ አንድ ይዞታ የሚኖር ሲሆን ይህ ይዞታ በወዝአደሩ መንግሥት ቁጥጥር ለሶሻሊስት ኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽኦ የሚያደርግ ነው ። የሚከሰተውም ለውጭ ካፒታል ኮንሴሽን በመስጠት ፣ የመንግሥት የኢኮኖሚ ተቋሞችን በማከራየት ፣ በጋራ አክሲዮን ተቋምና በመንግሥት ተቋሞች የተመረቱ ሸቀጦችን የግል ነጋዴዎች በኮሚሽን እንዲያከፋፍሉ በማድረግ ፣ በአጠቃላይ የመንግሥት የኢኮኖሚ ዓቅም ደከም ብሎ በሚገኝባቸው በተወሰኑ የኢኮኖሚ ዘርፎች ውስጥ መንግሥት ከግል ካፒታል ጋር በተወሰነ ስምምነት አማካይነት አብሮ በመሥራት መልክ ነው ።

የመንግሥታዊ ካፒታሊዝም ይዞታ ወደ ሶሻሊዝም በሚደርገው የሽግግር ወቅት የሶሻሊስቱን ኢኮኖሚ በማደራጀትና በማዳበር ረገድ አስተዋጽኦው ከፍተኛ ነው ። የምርት ኃይሎች በጣም ከዳበረ የዕድገት ደረጃ ላይ ሳይደርሱ ወደ ሶሻሊዝም የሚደረገውን ሽግግር በተያያዙት ሀገሮች ውስጥ (ለምሳሌ ሩሲያ በ1917) በሽግግር ወቅት ከሚኖሩት ከግል የካፒታሊስት ይዞታ ፣ ከአነስተኛ የሸቀጥ ምርት ይዞታና ከጥንታዊ የኢኮኖሚ ይዞታ ይልቅ የመንግሥታዊ ካፒታሊዝም ይዞታ ተራማጅ የሆነና ለሶሻሊዝም ይዞታ የሚቀርብ ነው ። የግል የኢኮኖሚ ይዞታው የመንግሥታዊ ካፒታሊዝምን ፈር መከተሉ የሽግግሩን ወቅት ሊያፋጥነው ይችላል ። ምክንያቱም የዚህ ዓይነት ይዞታ መስፋፋት የቡርዧዚውን የገንዘብ ክምችት ፣ የዕውቀት ፣ የልምድና የድርጅታዊ አሠራር ስልት ለሠራተኛው መደብ ጥቅም ግልጋሎት እንዲውል ከማድረጉም በላይ ለሶሻሊስቱ ኢኮኖሚ መሠረት የሆነው የተስፋፋ የማሽን አመራረት እንዲዳብር ይረዳል ።

በኋላቀር ወይም ታዳጊ ሀገሮች ውስጥ ደግሞ መንግሥታዊ ካፒታሊዝም ለየት ያለ መልክ አለው ። በነዚህ ሀገሮች መንግሥታዊ ካፒታሊዝም ማለት በኢኮኖሚው መስክ መንግሥታዊ የኢኮኖሚ ተቋሞችንና ድርጅቶችን ማቋቋም ፣ በኢኮኖሚው ዘርፍ የሀገር ውስጥንም ሆነ የውጭ የግል ካፒታልን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር የሚያስችል የኢኮኖሚ እርምጃ መውሰድ ፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ

ለኢኮኖሚው ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊኖራቸው ለሚችሉ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ሥራ አስፈላጊ የሆነውን የሰው ኃይልና ገንዘብ የማሰባሰብ እርምጃዎችን የሚያጠቃልል ነው ።

በታዳጊ ሀገሮች የመንግሥታዊ ካፒታሊዝም ኢኮኖሚ ይዘት ሀገሮቹ እንደሚከተሉት የዕድገት ፈለግ (ማለትም ካፒታሊስት ወይም ሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ ፣ እንደ መንግሥታቱ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ይዘትና አዝማሚያ እንዲሁም ሠራተኛው ሕዝብ ባለው ተሳትፎ) የተለያየ ይሆናል ። የካፒታሊስቱን የዕድገት ፈለግ በሚከተሉ ታዳጊ ሀገሮች ውስጥ መንግሥታዊ ካፒታሊዝም ከብሔራዊ ቡርዧው መደብ ጥቅም ጋር የሚጣጣምና የሠራተኛውን መደብ ጥቅም የሚፃረር ነው ። ከዚህም በተጨማሪ በነዚሁ የካፒታሊስቱን የዕድገት ፈለግ በሚከተሉ ታዳጊ ሀገሮች ውስጥ የብሔራዊ ቡርዧዚው ዓቅም የተወሰነና ትላልቅ ፕሮጀክቶችን በሕዝብ ለመደጎም የሚችል ባለመሆኑ ይህንን ችግር በማቃለል ረገድ መንግሥታዊ ካፒታሊዝም ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ። የሶሻሊስቱን የዕድገት ፈለግ በሚከተሉ ሀገሮች መንግሥታዊ ካፒታሊዝም የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማፋጠንና ይህንን የዕድገት ፈለግ የሚከተሉ ሀገሮች የዓለም ካፒታሊስት ኢኮኖሚ ጥገኝነታቸውን ለመቀነስ የሚረዳ ነው ።

## መንግሥታዊ ዱማ

*(State Duma)*

ከ1905---07 በተካሄደው በሩስያ ቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ወቅት በሕዝቡ ጥያቄና ግፊት የተነሣ የሰፊውን ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብት ለማረጋገጥ መሣሪያ ይሆናል በሚል ሽፋን በቄሳሩ መንግሥት የተቋቋመ የሕግ ምክር ቤት ወይም ሸንጎ ነው ። ምክር ቤቱ ወይም ሸንጎው የይስሙላ እንጂ ምንም ሥልጣን ያልነበረውና የተቋቋመውም በሕዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ ሳይሆን በተዘዋዋሪና በተወሳሰበ የምርጫ አፈጻጸም ነበር ። ከዚህም በላይ የመምረጥና የመመረጥ ዕድል የተሰጠው ለብዙኃኑ ሠራተኛና ገበሬ አልነበረም ። ከሩሲያ ብሔር ውጭ የነበሩ ብሔሮችና ብሔረሰቦች አልተሳተፉበትም ። በመሆኑም ምርጫው ለጥቂት ዘውደኞች ፣ ለመሳፍንትና መኳንንት ፣ ለመሬት ከበርቴዎች ፣ ለቡርዧዚዎችና ለግብረ አበሮቻቸው ብቻ በመሆኑ ዱማው ሙሉ በሙሉ የአድኃሪ ገዥ መደቦች መሣሪያ ነበር ለማለት ይቻላል ።

በዚህ መሠረት የመጀመሪያው ዱማ ከሚያዝያ—ሐምሌ 1906 ፣ ሁለተኛው ከየካቲት—ሰኔ 1907 ቆይተው በቄሳሩ መንግሥት እንዲፈርሱ ተደረገ ። ከዚያም በኋላ እንደገና የተቋቋሙትና ከ1907—1912 እንዲሁም ከ1912—1917 የቆዩት ዱማዎችም ቢሆኑ የቄሳሩን ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ በሚደግፉ ዘውደኞችና ጸለምት መቶዎች የተሞሉ ስለነበሩ ለሕዝብ የፈጸሙት የረባ ተግባር አልነበረም ።

ቦልሼቪኮች በዱማው መድረክ በመሳተፍ የቄሳሩን መንግሥት አድኃሪ ፖሊሲና ለዘብተኛ ቡርዧዎች ለዚህ መንግሥት ያደርጉት የነበረውን ስውር ድጋፍ ለማጋለጥ ተጠቅመውበታል ። በ1914 በዱማው ውስጥ የነበሩ ቦልሼቪኮች የኢምፔሪያሊስቱን ጦርነት (አንደኛው የዓለም ጦርነት) በጽኑ በመቃወማቸው የእስራት ቅጣት ተበይኖባቸው ታስረው ነበር።

## መንግሥት

*(State)*

ኢኮኖሚያዊ የበላይነት ያለው መደብ ፖለቲካዊ ድርጅት ሲሆን ዓላማውና ተግባሩም በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ያለውን ሥርዓት ለማስጠበቅና ለማጠናከር ፣ የሌሎች መደቦችን ተቃውሞና አሻፈረኝ ባይነት ለማፈን የሚያገለግል የመጨቆኛ መሣሪያ ነው። ሆኖም መንግሥት ኢኮኖሚያዊ የበላይነት ያለውን መደብ ፍላጐትና ፖለቲካዊ ጥቅም የሚያስጠብቅ የሥልጣን መዋቅር ብቻ ሳይሆን የመደብ ኅብረተሰብን ፖለቲካዊ አደረጃጀት ፣ በመደቦች ፣ በማኅበራዊ ክፍሎችና ቡድኖች እንዲሁም እነዚህ ማኅበራዊ ኃይሎች በጨቋኝና በተጨቋኝ የግንኙነት ሥርዓት ውስጥ ያላቸውን ስፍራ የሚያመለክት ነው ።

መንግሥት ሥልጣኑን በኃይል ከሚያስከብርባቸው መሣሪያዎቹ (ፖሊስ ፣ ወታደር ፣ ሕግ ፣ እስር ቤት ወዘተ...) ሌላ ርዕዮተ ዓለማዊ መሣሪያዎችም (ትምህርት ቤት ፣ የሃይማኖት ተቋሞች ፣ የዜና ማሠራጫዎች

የባህል ማዕከሎች ወዘተ...) አሉት ። እንደ ወታደር፣ ፖሊስ፣ ፍርድ ቤት ወዘተ... ያሉት ኃይሎች ኅብረተሰቡን በኃይል ከገዥው መደብ ጥቅም አኳያ የሚያስገድድባቸው ሲሆኑ ርዕዮተዓለሙ ደግሞ የአገዛዙን ሕጋዊነት፣ አስፈላጊነትና ጠቃሚነት የሚያረጋግጥበትና የኅብረተሰቡን ኅሊናዊ ሕይወት የሚገራበት መገሪያ ነው ። ከዚህ አንፃር ሲታይ መንግሥት የውጭና የውስጥ ተግባሮች ያሉት ሲሆን ከውስጥ ተግባሮቹ ዋነኛው ገዥው መደብ በኢኮኖሚው የበላይነት አማካይነት የተቆጣጀውን የላዕላይ መዋቅር የበላይነት ማጠናከርና ማስከበር ነው ። በተጨማሪም መንግሥት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግባሮች አሉት፤ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕቅድ ይቀይሳል ። እንደ መንገድ፣ እንደ ድልድይ፣ እንደ ትምህርት ቤት ወዘተ... ያሉትን መሠረተ ልማቶች ያከናውናል ። አስተዳደርን በሚመለከት በገዥው መደብና በተለያዩ ማኅበራዊ ክፍሎች መካከል ያሉትን ልዩነቶችና ቅራኔዎች ይፈታል፤ በተፃራሪዎች መካከል የሚነሡትን የማይታረቁ ቅራኔዎች ከገዥው መደብ ጥቅምና ከሥርዓቱ ዕድገት ጋር በማይቃረን መንገድና የተጨቋኝ መደቦችን አመፅ በማያሰጋ ሁኔታ ለማብረድ ጥረት ያደርጋል ። መንግሥት የሚያራምደውም የውጭ ፖሊሲ የሀገር ውስጥ ፖሊሲውና ተግባሩ ነፀብራቅ ነው።

መንግሥት በቅድመ መደብ ኅብረተሰብ ውስጥ የነበረውን የአረጋውያን (አዛውንቶች) አስተዳደር በመተካት ከመደቦች መፈጠር፣ ከማምረቻ መሣሪያዎች በግል መያዝ፣ ከማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል ማደግና መስፋፋት ጋር ተያይዞ የመጣ ፖለቲካዊ ድርጅት ነው ። መንግሥት ከማይታረቅ የመደቦች ቅራኔ የመነጨ በመሆኑ ሁሌም የነበረና የሚኖር ሳይሆን በኅብረተሰብ የዕድገት ሂደት ውስጥ የተከሰተና ከመደቦች መጥፋት ጋር አብሮ የሚከስም ነው ። አንድ ስልተ ምርት አንድ መንግሥት ብቻ ሲኖረው በርካታ የአገዛዝ ወይም የአስተዳደር መልክ ሊኖረው ይችላል ። ለምሳሌ በቡርዧው ኅብረተሰብ ውስጥ የተከሰቱት መንግሥቶች በዓይነታቸው ቡርዧ ሲሆኑ በቅርፅ ሪፑብሊካዊ፣ ሕገ መንግሥታዊ የዘውድ አገዛዝ ወዘተ... ሊሆኑ ይችላሉ ።

በሶሻሊስት ሥርዓት ውስጥ የወዛደሩ መንግሥት አድኃሪዎችንና ፀረ አብዮት እንቅስቃሴዎችን መደምሰሻ እንጂ የመበዝበዣ መሣሪያ አይደለም ። ምክንያቱም የወዝአደሩ መደብ ፀረ ብዝበዛ በመሆኑና የማምረቻ መሣሪያዎችም ከግል ካፒታልነት ወደ ወል ንብረትነት የተለወጡ በመሆናቸው ነው ። ሰፊ ማኅበራዊ መሠረት ያለው የሽግግር መንግሥት በሰፈነበት በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ደረጃም ቢሆን መንግሥት የመበዝበዣ መሣሪያ ሳይሆን እንደየሀገሩ ተጨባጭ ሁኔታ የተወሰኑ መደቦችንና የኅብረተሰብ ክፍሎችን ጥቅም የሚያራምድ ወገናዊ ድርጅት ነው ።

ኢኮኖሚያዊ፤ ማኅበራዊ ኅሊናዊ ዕድገት ከከፍተኛ ደረጃ ላይ በሚደርስበት ማለትም በኮሚኒስት ሥርዓት ውስጥ ኅብረተሰቡ ራሱን በራሱ ለማስተዳደር ስለሚበቃ የመንግሥት ታሪካዊ አስፈላጊነት ያከትማል ።

(ላዕላይ መዋቅርን፣ ፖለቲካዊ ትግልን ይመለከቷል ።)

## መንግሥት በጀት (በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም) (የ—)

*(State Budget—Under Capitalism and Socialism)*

በአንድ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ መንግሥት ከልዩ ልዩ ምንጮች አገኛለሁ ብሎ የሚጠብቀው ገቢና በዚህ ገቢ ላይ በመመሥረት ልዩ ልዩ ሥራዎችን ለማካሄድ የሚያወጣው የወጪ ግምት ወይም ፕሮግራም የመንግሥት በጀት ይባላል ። የአንድን ሀገር መንግሥት የበጀት ይዘት የሚወስነው ያለበት ሥርዓተ ማኅበር፣ የመንግሥቱ ይዘት፣ የቆመለት ዓላማና ተግባር ነው ።

በካፒታሊዝም የመንግሥትን በጀት በዝባዥ መደቦች የኢኮኖሚና የፖለቲካ የበላይነታቸውን ለመጠበቅ ይጠቀሙበታል ። በካፒታሊስት ሀገሮች የመንግሥት በጀት በአብዛኛው የሚውለው ምርታዊ ላልሆኑ ተግባራት በተለይም የጦር መሣሪያዎችን ለማስፋፋትና ሌሎች የመጨቆኛ መሣሪያዎችን ለማጠናከር ነው ።

ዛሬ በኢምፔሪያሊስት ሀገሮች መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም ከመስፋፋቱ የተነሣ መንግሥት በኢኮኖሚ ዘርፍ የሚያደርገው ተሳትፎ ጨምሯል ፤ በመሆኑም በመንግሥት እጅ የሚገባው የብሔራዊ ገቢ መጠን አድጓል ።

በካፒታሊስት ሀገሮች የመንግሥት በጀት ዋነኛ ምንጭ ቀረጥ ነው ። ከቀረጥ

የሚገኘው ከ85—95% ሲሆን ይህም ቀረጥ የሚወድቀው በአብዛኛው በሰፊው ሕዝብ ማለትም በወዝአደሩ ፣ በገበሬው ፣ በቢሮ ሠራተኛው ወዘተ... ትከሻ ላይ ነው ። በካፒታሊስት ሀገሮች የመንግሥት በጀት ገቢ ተለዋዋጭ ነው ። በኢኮኖሚ ቀውስ ጊዜ ገቢው አነስተኛ ሲሆን ወጪው ግን ከፍተኛ ነው ። በካፒታሊስት ሀገሮች አብዛኛውን ጊዜ ከወጪ ጋር ሲነፃፀር የበጀት ገቢ እጥረት ይታያል ። ይህን የገቢ እጥረት ለመሸፈን መንግሥት ተጨማሪ ቀረጥ በሕዝቡ ላይ ይጥላል ፤ ይበደራል ፤ የወረቀት ገንዘብ ያትማል ። ይህም የካፒታሊዝምን ውስጣዊ ቅራኔ ያባብሰዋል ።

በካፒታሊስት ሀገሮች በአጠቃላይ ለማኅበራዊና ለባህላዊ ፍላጐቶች ማሟያ የሚወጣው በጀት አነስተኛ ነው ። አንዳንድ ጊዜ የበጀት እጥረት ሲኖር ለማኅበራዊና ለባህላዊ ጉዳዮች የተያዘው በጀት ይቀነሳል ወይም እስከናካቴው ይሰረዛል ።

በሶሻሊዝም የመንግሥት በጀት የሀገሪቱ የገንዘብ ምንጮች በሙሉ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ውለው ብሔራዊ ምርት የሚስፋፋበትና ሌሎች የኅብረተሰቡ የፍጆታ ፍላጐቶች የሚሟሉበት የገቢና የወጪ ድልድል አሠራር ነው ።

በሶሻሊስት ሀገሮች ዋነኛው የመንግሥት በጀት ምንጭ ከመንግሥት ኢኮኖሚ ድርጅቶች የሚገኝ ትርፍ ነው ። እንደዚሁም ከሽያጭ ታክስ ፣ ከኅብረት ሥራ ማኅበራት የገቢ ቀረጥ ፣ ከማኅበራዊ መድንና ከሌሎች ምንጮች ይገኛል ። በሶሻሊስት ሀገሮች ከሕዝብ የሚገኘው ግብር አነስተኛ ከመሆኑም በላይ በየጊዜው በመቀነስ ላይ ያለ ነው ፤ ወደፊትም በአጠቃላይ የሚቀር ይሆናል ።

በሶሻሊስት ሀገሮች የመንግሥት በጀት የሚውለው ብሔራዊ ኢኮኖሚን ለማሳደግ ፣ ማኅበራዊ ፣ ባህላዊና የሳይንስ ፕሮጄክቶችን ለማስፋፋት ፣ የሕዝቡን ቁሳዊና ባህላዊ ፍላጐቶች ለማሟላት ፣ የመንግሥትን አስተዳደር ለማከናወን ፣ ሀገርን ከጠላት ለመከላከልና የወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት ግዴታን ለመወጣት ነው ። የሶሻሊስት በጀት አወጣጥ እንደየሀገሩ ሁኔታ ቢለያይም በሶሻሊስት ሀገሮች ብሔራዊ ኢኮኖሚን ለማስፋፋትና ማኅበራዊና ባህላዊ ጉዳዮችን ለማሟላት ከፍተኛ ወጪ ይደረጋል ።

## መንፈሳዊነት

*(Spiritualism)*

የግዙፉ ዓለም መሠረትና ምንጭ መንፈስ ነው ፤ የሰው ነፍስም መንፈሳዊ ነው የሚል የሐሳባዊ ፍልስፍና አንዱ ገጽታ ነው።

ሰው መንፈሳዊና ሥጋዊ ባሕርያት ያሉት ፣ መንፈሳዊ ባሕርዩም በዓይነት ከሥጋዊ ባሕርዩ የሚለይና ነፍስ ከቁሳዊው ሁኔታ ተላቆ የሚኖርና የራሱ ህልውና ያለው ነው ። በመሆኑም ነፍስና ሥጋ ተመሳሳይ ዕድል የላቸውም ፤ ሥጋ ሟችና ጠፊ ሲሆን ነፍስ ግን ዘላለማዊና መለኮታዊ ባሕርይ አለው ይላል ። እርግጥ በዚህ ዓለም ውስጥ ነፍስ ለመንቀሳቀስና እራሱን ለመግለጽ በሰው ሥጋዊ አካል ቢጠቀምም ከሥጋ የተለየ ጠባይ ፣ እውነታና መለኮታዊነትም አለው ይላል ።

ቁስአካልነት "ነፍስ" ብሎ የሚጠራው የቁስአካልን ነፀብራቅ በመሆኑና የራሱም ህልውናና እውነታ እንደሌለው በማስረዳቱ የመንፈሳዊነትን ፍልስፍና ይቃወማል ። የመንፈሳዊነት ዋና መከራከሪያ ነጥብ ግን አንጐል የሐሳብ መግለጫና መዛሪያ እንጂ በራሱ የሚያስብ ስላይደለ ሐሳብ የሚጠነስ ሰው አንጐል ውስጥ አይደለም የሚል ነው ።

መንፈሳዊነት ባለው ሐሳባዊ አቋም የተነሣ የነፍስንና የሥጋን አንድነትና ልዩነት በትክክል ሊገነዘብ አይችልም ። ነፍስን ከቁሳዊ ሁኔታ የመገንጠል አቋሙ ሳይንሳዊ መሠረት የሌለውና ከእምነትና ከአምልኮ የመነጨ ነው ። ሰው ከቁሳዊው ሁኔታ ውጭ መንፈሳዊ ኑሮ አለኝ ብሎ ማመኑ የሚያስረዳው ዓለማዊው ኑሮ እንዳልተዋሀደው ነው ። ይህችን ዓለም ጥሎ ሌላ መንፈሳዊ ዓለም መመኘትም የዓለማዊ የኑሮ ሁኔታ ውስጣዊ ቅራኔ ውጤት ነው ። መንፈሳዊና ዓለማዊ ኑሮን ሙሉ በሙሉ ለማዋሀድ የሚቻለው ተፈጥሮን በመቆጣጠርና የመደብን ልዩነት በማጥፋት ነው ። በመሆኑም መንፈሳዊ ፍልስፍና የሚሻረውና ስለቁሳዊና ስለመንፈሳዊ ዓለም ውህደት ትክክለኛ መልስ የሚገኘው የኮሚኒስት ሥርዓት ሲመሠረት ነው ።

(ሃይማኖትን ይመለከቷል ።)

## መካከለኛ የኅብረተሰብ ክፍሎች *(Middle Strata)*

በካፒታሊስት ሥርዓት በወዝአደሩና በቡርዧዚው መካከል የሚገኙ መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች ናቸው ። የእጅ ጥበብ ባለሙያዎች ፣ ዝቅተኛ ነጋዴዎች ፣ ትናንሽ የግምሬቻ ድርጅቶች ባለቤቶችና መካከለኛ ገበሬዎች እንዲሁም የግል ሀብት የሌላቸውና ለካፒታሊስቶች ተቀጥረው ዕውቀታቸውን በመሸጥ የሚተዳደሩ ምሁራንና የቢሮ ሠራተኞችና የሙያ ሠራተኞች ፣ በግለሰቦች ቤት ተቀጥረው የሚሠሩና ሌሎችም ከተለያዩ መደቦች የተንጠባጠቡ ክፍሎች ሁሉ በመካከለኛ የኅብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ይጠቃለላሉ ።

በአጠቃላይ መካከለኛ የኅብረተሰብ ክፍሎች በኅብረተሰቡ ውስጥ በያዙት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቦታ የተነሣ በፖለቲካ አቋማቸው አንድ ጊዜ ከሠራተኛው መደብ ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከቡርዧዚዎች ጋር የመቆምን ባሕርይ ስለሚያንፀባርቁ ወላዋይነትና የአለመረጋጋት ባሕርይ ይታይባቸዋል ። ከነዚህ ውስጥ አብዛኛዎቹ የካፒታሊስቱ ሥርዓት ብዝበዛ እየከፋና የኑሮ ሁኔታቸውም እያዘቀጠ ሲሄድ ወደ ወዝአደርነት እየተለወጡ የሚሄዱ ናቸው ። ለሶሻሊዝም በሚደረገው ትግል ሠራተኛው መደብ መካከለኛ የኅብረተሰብ ክፍሎችን እንደቅርብ አጋሮቹ ይመለከታቸዋል ። በደረጁ ካፒታሊስት ሀገሮች ዛሬ እንደሚታየው የነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች ወደሠራተኛው መደብ እየተቃረቡ የመምጣታቸው እርምጃ በመፋጠን ላይ ይገኛል ። በታዳጊ ሀገሮችም ምሁራንና ሌሎችም የመካከለኛው የኅብረተሰብ ክፍሎች በብሔራዊ የአርነት ትግልና በሀገር ግንባታው ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል ፤ እየተጫወቱም ናቸው ።

(ንዑስ ከበርቴን ፣ መሠረታዊና ኢመሠረታዊ መደቦችን ይመለከቷል ።)

## መዋቅራዊነት

*(Structuralism)*

በአውሮፓና በአሜሪካ ከ20ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ጀምሮ የተስፋፋ ፍልስፍና ነው ። ፍልስፍናው የተመሠረተው በሥነ ልሳንና በሥነ ኅብረተሰብ ጥናቶች ውጤት ላይ ነው ። ኅብረተሰብን በተለይም ታሪክ የሌላቸውን ኅብረተሰቦች ለማጥናት መዋቅር የሚለው ጽንሰ ሐሳብ ወሳኝ ሚና እንዳለው ፍልስፍናው ይናገራል ። መዋቅር ማለት እንድ ራሱን የቻለ እውነታ በሚያቅፋቸው ክፍሎች የእርስ በእርስ ግንኙነትና ሥራ ምንነቱን የሚገልጽና ህልውናውን የሚጠብቅ ነገር ማለት ነው ። ለምሳሌ የሰውን አካል ብንወስድ እራሱን የቻለ ሕይወት ያለው ነገር ሲሆን ይህ ሕይወት የሚንቀሳቀሰውና እራሱን የሚጠብቀው ባሉት የተለያዩ አካሎች የእርስ በእርስ ግንኙነት ነው ፤ የአንዱ አካል ብልሽት ለሁሉም ጠንቅ ይሆናል።

በመዋቅራውያን አስተሳሰብ ይህ አመለካከት የኅብረተሰብ ሳይንሳዊ ጥናት መሠረት ነው ። በኅብረተሰብ ውስጥ ግለሰቦች ይገኛሉ፤ እነዚህ ግለሰቦች ደግሞ በተለያዩ ክፍሎች (ለምሳሌ ሚስት ፣ ባል ፣ ልጅ ፣ አባት ፣ አሠሪ ሠራተኛ ፣ አስተማሪ ፣ ተማሪ) ይመደባሉ ። እነዚህ ክፍሎች በእርስ በእርስ ግንኙነታቸው አገልግሎት ይለዋወጣሉ ። አንዱ ክፍል ብቻውን ሊኖር ካለመቻሉም በላይ አገልግሎት የመለዋወጡ ሁኔታ መዋቅሩን የሚገልጽና ህልውናውን የሚጠብቅ አሠራርና አደረጃጀት ነው ። የበላይነት ያለው መዋቅሩ ነው ። የኅብረተሰብ ሕግም መዋቅራዊ ነው ። ሕግ ማለት ክፍሎቹ እንዴት እንደሚገናኙና በግንኙነታቸው መዋቅሩን እንዴት እንደሚገልጹና እንደሚጠብቁ መረዳት ነው ።

ከዚህም ለመገንዘብ እንደሚቻለው መዋቅሩ ተለዋዋጭ ጠባይ ስለሌለው ከታሪክ ሂደት ውጭ ነው ። ክፍሎቹም የራሳቸው ነፃነት ስለሌላቸው በግንኙነታቸው ያውመልሰው መዋቅሩን ስለሚያስቀምጡ ታሪካዊ ሚና የላቸውም ። በእርግጥ ኅብረተሰብ ሊቀያየር ይችላል ። ሆኖም ለውጡ በታሪካዊ ግፊትና ሂደት የተገኘ ሳይሆን የክፍሎቹ የተለያየ የአቀነባበር ውጤት ነው ። በቦታና በጊዜ የክፍሎች አወቃቀር ሊለያይ ይችላል ። ነገር ግን አወቃቀሩ ከመዋቅሩ ፍላጐትና ቋሚ ሕግጋት ሊወጣ አይችልም ። የቅርፅ እንጂ የይዘት ለውጥ ሊከሰት አይችልም ። በመዋቅራዊነት መሠረት ታሪክ የሚባለው ጽንሰ ሐሳብ ለኅብረተሰብ ጥናት አስፈላጊ አይደለም ።

ይህ የሚያስረዳን መዋቅራዊነት ማርክሲዝምን ለመዋጋት የተነሣ ርዕዮተዓለም መሆኑን ነው ። ታሪክን ተጨባጭነት የሌለው

ነገር ማድረግ የማርክሲዝምን ዋና አመለካከት መቃወም ከመሆኑም በላይ የሠራተኛው መደብ ታሪካዊ ተልዕኮ ሳይንሳዊ መሠረት የለውም ማለት መሆኑ ግልጽ ነው ። እዚህ ላይ መጠቀስ የሚገባው መዋቅር የሚለው ጽንሰ ሐሳብ ከማርክስ የተወሰደ መሆኑን ነው ። ነገር ግን የማርክስ መዋቅር በራሱ ውስጣዊ ቅራኔ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የሚያፈርሰው ኃይል አብሮ በውስጡ እንደሚገኝ አስረድቷል ። ለምሳሌ ካፒታል መዋቅር ነው ፤ ምክንያቱም የሚያቅፉቸው የምርት ግንኙነትና ማኅበራዊ ሥርዓት ራሱን ለመጠበቅና ለማሳደግ የሚጠቅሙት ናቸው። ሆኖም እራሱን ሲያሳድግ የሱን ተቃራኒና አጥፊ ኃይል ማለትም ወዛደሩን እያደራጀና እያሳደገ ስለሚመጣ ቋሚ ሳይሆን ኃላፊ መዋቅር ነው ። ይህን ዲያሌክቲካዊ አስተሳሰብ ነው መዋቅራዊነት የማይቀበለው ።

በመሆኑም የመዋቅራዊነት መደባዊ ተልዕኮ ግልጽ ነው ። የታሪክን ጽንሰ ሐሳብ ሳይንሳዊ በሚመስል አቀራረብ ለመሻር መሞከር የካፒታሊስትን ሥርዓት ዕድሜ ለማራዘም የሚደረግ ጥረት ነው ። መዋቅሩን ቋሚ ነገር አድርጎ መውሰዱ እሱን ለመቀየር የሚደረገውን ማንኛውንም ጥረት ከንቱ ወይም አደገኛ ለማስመሰል መሆኑ የማይካድ ነው ። በሌላ መልኩ ደግሞ የሰውን ፍላጎትና ትግል ከንቱ አድርጎ ሰውን በመዋቅር ማስገዛት የሚገልጸው እራሱ መዋቅራዊነት የካፒታሊስት ሥርዓት የጭቆና ነፀብራቅ መሆኑን ነው ።

(ባሕርዮትን ይመለከቷል ።)

## መደባዊ ንጽረት
*(Class Outlook)*

በተወሰነ ማኅበራዊ ሥርዓት ውስጥ እያንዳንዱ መደብ ማኅበራዊ ስፍራውን ፣ ጥቅሙንና ፍላጎቱን የሚገልጽበት የራሱ የሆነ የአመለካከት ሥርዓት ነው ።

ሰዎች ስለሚያካብቧቸው ነገሮች ፣ ክስተቶችና ሁኔታዎች የሚቀርጿቸው አመለካከቶች በሙሉ ተዳምረው ርዕዮተዓለም በመባል ይታወቃሉ ። ርዕዮተዓለም በመሠረቱ የማኅበራዊ ኑባሬ ነፀብራቅ በመሆኑ በተፃራሪ መደቦች በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የማኅበራዊ ኑባሬ ነፀብራቅ ማለትም ርዕዮተዓለም ምን ጊዜም ቢሆን የመደብ ጠባይ ያለው ነው ። የኅብረተሰቡ የተለያዩ መደቦች ንጽረትና ንድፈ ሐሳብ ያሉትን ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶችና ማኅበራዊ እውነታ ከመደቦች ጥቅም ፍላጎት አንፃር የሚያንፀባርቁ ናቸው ። ስለዚህም የመደብ ንጽረት በነባራዊ መሠረት ላይ የቆመና የአንድን መደብ ቁሳዊ ጥቅም ፣ ፍላጎት ፣ ምኞት ፣ ስሜት ወዘተ... አጠቃላይ ነፀብራቅ የሚገልጽና በአንድ በተወሰነ ታሪካዊ ማኅበራዊ ግንኙነት ውስጥ የመደብ አባላት የያዙት ስፍራና የፍላጎታቸው ግንዛቤ ደረጃ ነው ።

በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የበዝባዡንና የተበዝባዡን መደብ ሐሳቦች የሚያንፀባርቁ ፍጹም ተቃራኒ የሆኑ ሁለት ንጽረቶች ይኖራሉ ። ሆኖም በየትኛውም ወቅት ቢሆን የበላይነቱን የሚይዘው የመደብ ንጽረት የኢኮኖሚና የፖለቲካ የበላይነቱን የያዘው መደብ ንጽረት ነው ። የኅብረተሰቡ ቁሳዊ ኃይል ተጠቃሚና የበላይ የሆነው መደብ የኅብረተሰቡ መንፈሳዊ ሕይወት ገዥ ኃይል እንደመሆኑ በኅብረተሰቡ ላይ የራሱን የመደብ ንጽረት በመጫን ባለው የማሰራጫ መንገድና ስልት በመጠቀም ለማስፋፋት ይጥራል ።

በቡርዧ ርዕዮተዓለማውያን አስተሳሰብ ማኅበራዊ ሐሳቦችና ንድፈ ሐሳቦች የመደብ ጠባይ የሌላቸውና አጠቃላይ ወይም ሁለንታዊ ባሕርይ ያላቸው ናቸው ። ይሁን እንጂ የቡርዧው መደብ ንጽረት አቀንቃኞች ሐሳቦቻቸውን በተለያዩ ዘዴዎችና ስልቶች አማካይነት በማሰራጨት የቡርዧውን መደብ ጥቅም ለመጠበቅና ለመንከባከብ ፣ በአንፃሩም ሠራተኛው ለእርነቱ የሚያደርገውን ትግል ለማደብዘዝና ፈር ለማሳት ያላሰለሰ ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ ። የቡርዧዚው አፈቀላጤዎች የሚሰነዝሯቸው ሐሳቦች የፈለገውን ያህል ረቂቅና ሽፍን ቢመስሉም ዞሮ ዞሮ ለቡርዧው መደብ ወገናዊ ከመሆን አያመልጡም ። በሌላ በኩል ደግሞ ቡርዧዚው አመለካከቱን ለማሰራጨት ምንም እንኳን በተራቀቁ መሣሪያዎችና ስልቶች ቢጠቀምም አመለካከቱ ከእውነት የራቀ በመሆኑ በሰፊው ሕዝብ ዘንድ የዘለቄታ ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም ።

ከታሪክ መድረክ የሚሰናበቱ መደቦች አፈቀላጤዎች የማኅበራዊ ዕድገትን እርምጃ

አቅጣጫና ሂደት ለማጣመምና ለማውገርገር፣ ያረጀውንና ያፈጀውን አድኃሪ ሥርዓት ለመጠበቅና ለማቆየት መፍጨርጨር ልማዳቸው እንደሆነ የኅብረተሰብ ዕድገት ታሪክ ያሳያል ። በአንፃሩ ደግሞ የተራማጅ መደቦች ደጋፊዎች የሆኑ ክፍሎች የኅብረተሰቡን ማኅበራዊ ግንኙነቶች በትክክል ለመተንተንና ለመተርጐም በሚያደርጉት ጥረት ታሪካዊ እውነትን የሚያራምዱ ንጽረቶች ለመቅረፅ እንደሚጥሩ ከታሪክ እንረዳለን ። ይሁን እንጂ ከነማርክስ በፊት በጠባብ የመደብ ንጽረት ውሱንነት የተነሣ ለኅብረተሰቡ አብዮታዊ ለውጥ መሠረት የሚሆን ዘላቂና ሳይንሳዊ የመደብ ንጽረት ሊቀረፅ አልተቻለም ነበር ። ይህ ተግባር ለመጀመሪያ ጊዜ ሊከናወን የቻለው በታላቆቹ የወዝአደር መደብ ርዕዮተዓለማውያንና መሪዎች ማለትም በማርክስና በኤንግልስ አማካይነት ነው ።

ማርክሲዝም የሠራተኛው መደብ ሳይንሳዊ ንጽረት ነው ። የሠራተኛው መደብ ንጽረት የማኅበራዊ እውነታ ትክክለኛ ነፀብራቅ ነው ። የሠራተኛው መደብ ጥቅምና ፍላጐት ከነባራዊ ታሪካዊ እርምጃ ጋር የተጣጣመ በመሆኑም እውነተኛ ጥቅሞቹንና ፍላጐቶቹን ከሌሎች መደቦች የሚደብቅበት ምንም ምክንያት የለውም ። ስለዚህ ማርክሲዝም ለዚሁ መደብ ጥቅምና ፍላጐት የዘለቄታ መሟላት ያለውን ጽኑ የወገናዊነት አቋም ያለምንም ማድበስበስ በአስተሳሰብም ሆነ በተግባር መስከ በግልጽ ያራምዳል ።

(መደብን ፣ ርዕዮተዓለምን ይመለከቷል ።)

## መደባዊ ፍልስፍና
*(Class philosophy)*

በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ ፍልስፍና በመሠረቱ መደባዊ ይዘት አለው። ነገሮችንና ሁኔታዎችን ከመደብ አቋምና ጥቅም ጋር በማገናዘብ የሚመለከት ፍልስፍና መደባዊ ፍልስፍና ይባላል ። አንዳንዶቹ ፍልስፍናዎች የመደብ ባሕርያቸውን ወይም የቆሙለትን መደብ ጥቅምና አቋም ለማንፀባረቅ ቢሞክሩም ከሁሉም ይበልጥ ግን የማርክሳዊ ፍልስፍና የወዝአደሩን መደብ ጥቅም ፣ በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ስፍራና ወደ ሶሺሊዝም ሽግግር በሚደረግበት ጊዜ ያለውን የመሪነትና የበላይነት ሚና በቀጥታና በግልጽ ያንፀባርቃል ። ሐሳባዊ ፍልስፍና የአድኃሪ ገዥ መደቦችን ጥቅምና የበላይነት የሚያንፀባርቅ መሆኑ ባይካድም ከመደብ ጥቅም በላይ እንደሆነና ወገናዊ መስሎ ሳለመታየት ይሞክራል ፤ ይሰብካልም ።

መደባዊ ፍልስፍና ከመደቦች ጥቅም ጋር የተያያዘ ፣ ይህንንም ጥቅም የሚያንፀባርቅ ፣ የሚንከባከብ ፣ ተቀባይነትም እንዲያገኝ የሚጥር ፣ ተፃራሪ መደቦችንም ለመታገል የሚያገለግል መሣሪያ በመሆኑ የፖለቲካ ባሕርይ ሲኖረው ከመንግሥትም ጋር የተያያዘ ነው ። ይሁን እንጂ መደቦች በሚከስሙበት ጊዜ በኮሚኒስት ሥርዓት ውስጥ ፍልስፍና የፖለቲካ ባሕርዩን ማለትም የመደብ ወገናዊነቱን ከመተው በቀር አይጠፋም።

(የፍልስፍና መሠረታዊ ጥያቄን ፣ ፍልስፍናን፣ የፓርቲ ፍልስፍናን ይመለከቷል ።)

## መደብ
*(Class)*

የኅብረተሰብን ማኅበራዊ ክፍፍል የሚያመለክት ጽንሰ ሐሳብ ነው ። ሰዎች በታሪክ በተወሰነ የማኅበራዊ ምርት ሥርዓት ውስጥ በሚይዙት ስፍራ ፣ ከምርት መሣሪያዎች ጋር (በአብዛኛው በሕግ የሚወሰንና የሚቀረፅ) ባላቸው ግንኙነት ፣ በማኅበራዊ የሥራ አደረጃጀት ውስጥ በሚጫወቱት ሚናና ከዚህም የተነሣ ከማኅበራዊው ምርት በሚያገኙት ድርሻና መጠን በተለያዩ መደቦች ይከፋፈላሉ ።

መደቦች የሰዎች ስብስብ ቢሆኑም ማናቸውም የሰዎች ስብስብ ግን መደብ አይደለም ። ለምሳሌ ሴቶች ፣ ወጣቶች ፣ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ወዘተ... በርካታ አባላት ያሉዋቸው ቡድኖች ቢሆኑም መደቦች አይደሉም። ምክንያቱም አንዳንዶቹ ተፈጥሮአዊ መሠረት ያላቸው በመሆኑና ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች ደግሞ ለሰዎች እኩል አለመሆን ምክንያት ሊሆኑ ስለማይችሉ ነው ። አንዳንዶቹ ማኅበራዊ መሠረት ቢኖራቸውም እራሳቸውም ወሳኝ በሆነው ኢኮኖሚያዊ ልዩነት የተነሣ በመደብ የተከፋፈሉ በመሆናቸው ነው ። መደቦች የሚፈጠሩት ሰዎች የወል ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅም እንዲኖራቸው ሲያው

ቁና እነዚህን ጥቅሞቻቸውንም ከሌሎች ሰዎች ጥቅሞች የተለዩ ብቻ ሳይሆን ተፃራሪ እንደሆኑ ተረድተው የወል ጥቅማቸውን በጋራ ለማስከበር ሲነሡ ነው ። ስለሆነም የወል ኢኮኖሚያዊ ጥቅማቸውን መረዳትና የፖለቲካ ድርጅታቸውን መመሥረት ፣ በርሱም መመራት የኅሊናዊ ሁኔታን መሟላት ያሳያል ። የመደቦች በኢኮኖሚ ጥቅም መለያየት በፖለቲካ ፣ በርዕዮተዓለም ፣ በፍልስፍና ፣ በባህል ወዘተ... ዘርፎች እንዲታገሉ ያደርጋቸዋል ።

መደቦች ሁሌም የነበሩና የሚኖሩ ሳይሆኑ በማኅበራዊ የምርት ዕድገት ሂደት ውስጥ የተከሰቱና የሚጠፉም ናቸው ። የመደቦች መከሰት መንሥኤ የማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል ማደግና የማምረቻ መሣሪያዎች በግል መያዝ ነው ። የመደቦች መፈጠር ኅብረተሰቡን በገዥና በተገዥ ፣ በበዝባዥና በተበዝባዥ ኃይሎች እንዲከፋፈል ያደርጋል ። ፀረ ብዝበዛ አቋም ያለው የወዛደሩ መደብ በሶሻሊስት አብዮት አማካይነት ሥልጣን ሲጨብጥ በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚታየውን መደባዊ ክፍፍል እየደመሰሰው ይሄዳል ።

በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ በአንድ ወቅት ሰፍኖ የሚገኘው ስልተ ምርት ከሚፈጥራቸው መሠረታዊ መደቦች ሌላ መሠረታዊ ያልሆኑም መደቦች ሊገኙ ይችላሉ። በቡርዧው ኅብረተሰብ ውስጥ የገበሬውን መደብ ፣ በፊውዳሉ ኅብረተሰብ ውስጥ የቡርዧውን መደብ እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል ። ከነዚህም በተጨማሪ በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ መደብ ያልሆኑ ነገር ግን የወል ባሕርይ ያላቸው እንደ ተማሪና እንደ አስተማሪ ያሉ ማኅበራዊ ቡድኖች ይገኛሉ ። በሌላም በኩል ደግሞ የአንድ መደብ አባላት የሆኑ ነገር ግን ከአጠቃላዩ የመደብ ባሕርይና ጥቅም ባሻገር እርስ በርሳቸው የሚለያዩበት ባሕርይና ጥቅም ያላቸው ክፍሎች አሉ ። ለምሳሌ የቡርዧው መደብ አባላት ሆነው ግን የራሳቸው የተለየ ጥቅምና ባሕርይ ያላቸው የሞኖፖል ቡርዧዚ ፣ የኢንዱስትሪ ቡርዧዚ ፣ የንግድ ቡርዧዚ ወዘተ... የሚባሉ ክፍሎች ይገኛሉ። በወዝአደሩም ውስጥ የኢንዱስትሪ ወዝአደር ፣ የእርሻ ወዛደር ፣ በገበሬው ውስጥ ደግሞ ከፍተኛው ፣ መካከለኛውና ዝቅተኛው ገበሬ የሚባሉ ክፍሎች ይገኛሉ ።

የገቢ መጠንና ዓይነት የመደብ ውጫዊ ገጽታ ሲሆን የሚወስነውም ሰዎች ከምርት መገልገያ መሣሪያዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት ነው ። በኅብረተሰብ የዕድገት ሂደት ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች ላይ የንብረት ይዞታው ዓይነት መለዋወጥ የመደቦቹን ዓይነት ፣ የብዝበዛውን ስልትና በመደቦቹ መሀከል የሚደረገውን ትግል ይሰውጠዋል ። በዚህም ሂደት ውስጥ የመደቦች ህልውና መሠረት የሆነው የግል ይዞታ መጥፋት በአንድ ደረጃ ላይ (በኮሚኒስት ስልተ ምርት) የማይቀር የታሪክ ግዴታ ይሆናል ። ስለሆነም በማምረቻ መሣሪያዎች በግል መያዝ ምክንያት የመጣው የመደብ ክፍፍል የወል ይዞታ ሲፈጠር ይጠፋል ፤ ይህም ማለት በገጠርና በከተማ ፣ በጉልበትና በአእምሮ ሥራ መካከል ያሉት ልዩነቶች ይወገዳሉ ማለት ነው ።

(ታሪካዊ ቁስአካልነትን ፣ መሠረታዊና ኢመሠረታዊ መደቦችን ይመለከቷል ።)

## መደብ ትግል (የ—)

*(Class Struggle)*

ጥቅማቸው የማይጣጣም ወይም ተቃራኒ የሆኑ መደቦች የሚያደርጉትን ትግል የሚገልጽ ጽንሰ ሐሳብ ነው ። ከባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት ጀምሮ የኅብረተሰብ ታሪክ የመደብ ትግል ታሪክ ነው ። በማርክሲዝም ሌኒኒዝም አመለካከት ኅብረተሰብ ተቃራኒ በሆኑ መደቦች መከፋፈሉና የመደቦች ትግል ማካሄዱ የዕድገቱ መሠረትና አራማጅ ኃይል ሆኖ ቆይቷል ። የዚህ አመለካከት ሳይንሳዊነትም የሚረጋገጠው ትግሉ ከቡርዧ ኅብረተሰብ ላይ ሲደርስ በማይቀር ሁኔታ ወደ ወዝአደሩ የበላይ ገዥነት በማምራት መደቦችን የሚያጠፋ ኅብረተሰብ እንደሚመሠረት ማስረዳቱ ነው ። ይህም ማለት መደቦችን ያመጣ ታሪካዊ ሁኔታ መደቦች ሚናቸውን ሲያጠናቅቁ መልሶ ያስወግዳቸዋል ።

ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ርዕዮተዓለማዊ ትግሎች የመደብ ትግል ዋና ዋና ቅርፆች ናቸው ።

በወዝአደሩ የበላይ ገዥነት ብቻ ሠራተኛው ሕዝብ ከብዝበዛ የሚላቀቅ በመሆኑ በቡርዧው ኅብረተሰብ ውስጥ ወሳኙነት

ያለው ፖለቲካዊ ትግል ነው ። ኢኮኖሚያዊና ርዕዮተዓለማዊ ትግሎች ለዚህ ለፖለቲካ ግቡትም የመንግሥት ሥልጣን ለመያዝ የሚደረገው ትግል አጋዥ ኃይል ናቸው ። [illegible]ገበት ዘመን ወዝአደሩ የሚዋጋው ከሞኖፖሊስቶች ጋር በመሆኑ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች በሙሉ ከወዝአደሩ መደብ ጋር ይሰለፋሉ ።

የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት ሲመሠረት የመደብ ትግሉ አዳዲስ መልኮችን ይይዛል ። እነሱም 1/ የበዝባዥ መደቦችን መፍጨርጨር ማስወገድ ፤ 2/ የወዝአደሩና የቡርዧዚው ትግል መጨረሻ ምዕራፍ የሆነውን የመጣፉያ ትግል ማካሄድ ፤ 3/ ገበሬውንና ወዝአደር ያልሆኑትን የሠራተኛ ክፍሎች በወዝአደሩ አመራር ሥር ማድረግ ፤ 4/ የቡርዧዚ ባለሞያዎችን አዲሱ ሥርዓት እንዲጠቀምባቸው ማድረግ ፤ 5/ ሰዎችን በአዲሱ ሶሻሊስታዊ የሥራ ዲሲፕሊን ማስተማርና ማነጽ ናቸው ።

የሶሻሊዝም የመጨረሻ ድል የመደብ ትግልን ከዳር አድርሶ ኅብረተሰቡ ፖለቲካዊ ፣ ማኅበራዊና ርዕዮተዓለማዊ አንድነት እንዲኖረው ያደርጋል ። ሆኖም የውስጥ ትግሉ ቢያበቃም ከካፒታሊስት ሀገሮች ጋር የሚደረገው የመደብ ትግል ግን ይቀጥላል ።

(መደብን ፣ ርዕዮተዓለማዊ ትግልን ፣ ፖለቲካዊ ትግልን ፣ ኢኮኖሚያዊ ትግልን ይመለከቷል ።)

## መደብ ንቃተ ኅሊና (የ—)

*(Class Consciousness)*

ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ክስተቶችንና ዕድገቶችን ከመደብ ጥቅም አንፃር የሚመለከትና የሚተነትን የአስተሳሰብ ሥርዓት ነው ። ማንኛውንም ማኅበራዊ ሕይወትና ክስተት የሚያጠናና የሚተነትን አመለካከት ፣ ፍልስፍና ፣ ርዕዮተዓለም ወዘተ... ወገናዊ እንደሆነ በመረዳት የመደብ ንቃተ ኅሊና ተግባሩን የዚህ ሁኔታ ተገዥ ለማድረግ ያስችላል ። ይህ ንቃተ ኅሊና ከዕለት ተዕለት ኑሮና ከተግባር ባሻገር ከጥናትና ከምርምር የሚገኝ በመሆኑ በአንድ መደብ አባላት በሙሉ ሳይሆን በመደቡ ግንባር ቀደምና ርዕዮተዓለማውያን የሚተረዕ ነው ። የመደቡ ርዕዮተዓለም ፣ ፍልስፍና ወዘተ... በሰፊው ሕዝብ ውስጥ ሲሰራጭና በንድፈ ሐሳባዊ ትንታኔና ዕውቀት ላይ የተመሠረተ አመለካከት ሲፈጥር የተቀነባበረ ንቃተ ኅሊና ይሆናል ። በመሆኑም የመደብ ንቃተ ኅሊና ሰዎች የመደባቸው ጥቅም ከሌሎች መደቦች ጋር ተፃራሪ ወይም የማይፃረር መሆኑን ለመረዳትና የመደብ ጥቅማቸውን ለማስከበር የሚረዳቸውን ሁኔታ ለመፍጠር እርምጃ ለመውሰድ ያገለግላል ።

(ንቃተ ኅሊናን ፣ የመደብ ትግልን ፣ መደባዊ ንድረትን ይመለከቷል ።)

## መደብ ዕብረት (የ—)

*(Class Collaboration)*

ዐበረ ፣ አንድ ሆነ ፣ በሐሳብ በሥራ ገጠመ ማለት ነው ።

በዓለም አቀፍ የሠራተኛው መደብ ንቅናቄ ውስጥ የተከሰተና ሊታረቁ የማይችሉ ተፃራሪ ወገኖችን ማለትም የወዝአደሩንና የካፒታሊስቱን መደብ ፍላጐቶች ለማስታረቅ የሚሻ የጠጋኞች የቅልበሳ 'ንድፈ ሐሳባዊ'ና ተግባራዊ መመሪያ ነው ። ይህ ሲባል ግን ሊታረቁ በማይችሉ ተፃራሪ መደቦች መካከል ምንም ዓይነት ዕብረት መቼም ጊዜ ሊኖር አይችልም ማለት አይደለም ። ለምሳሌ ብሔራዊ ነፃነትን ለማስከበር ፣ ፋሺዝምን ለመደምሰስ ፣ ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር ለመውጣት በሚወሰዱ እርምጃዎች ላይ የተፃራሪ መደቦች አቋም ተመሳሳይ ከሆነ ለጋራ ጥቅማቸው ሲሉ ተስማምተው ለተወሰነ ጊዜ አብረው ሊሰለፉ ይችላሉ ። ይሁን እንጂ በእንደዚህ ያለው ጊዜያዊ ስምምነት ወቅት እንኳ ቢሆን ሠራተኛው መደብ ድርጅታዊ ነፃነቱን ነቅቶ መጠበቅ አለበት ። ስለዚህ ሠራተኛው መደብ ከጠላት መደቦች ጋር የዚህ ዓይነት ዕብረት ሲመሠርት ግንኙነቱን ፣ ዓላማውንና የፖለቲካ መሥመሩን የማያስተው ፣ ወቅታዊ መሰናክሎችን ለማሸነፍና የመደብ ትግሉን ወደፊት ለማራመድ የሚረዳው ከመሆኑ እርግጠኛ ሊሆን ይገባል ።

(ጠጋኝነትን ፣ ከላሽነትን ይመለከቷል ።)

## መድልዎ

*(Segregation)*

ሰዎችን በዘራቸው ፣ በቀለማቸው ፣ በእምነታቸውና በመሳሰሉት በተመደበ ስፍራ እንዲኖሩ የመወሰን ፣ በተለዩ ማኅበራዊ ድርጅቶችና ተቋሞች (ለምሳሌ ትምህርት ቤት፣

 መጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት

ቤተ ክርስቲያን ፣ መናፈሻና መዝናኛ ሆቴል ወዘተ...) ተነጥሰው እንዲገለገሉ የማድረግ ተግባር ነው ።

ዘርን ፣ ሙያን ፣ ልምድንና ሃይማኖትን አጣምሮ የያዘው እጅግ የከፋው መድልዎ በህንድ የሚሠራበት የካስት ሥርዓት ነው ።

የመድልዎ ዋና ዓላማው የፖለቲካ የበላይነት ያለውን ወገን ፣ ቡድን ወይም የኅብረተሰብ ክፍል ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ደረጃ የላቀ ማድረግና ይህንንም የበላይነት መጠበቅ ነው ። ስለዚህም በአካልና በስፍራ መለያየትን ወይም ማግለልን ብቻ ላይመለከት ይችላል ። በተለይ ኢንዱስትሪዎች በተስፋፉባቸው ዘመናዊ ከተሞች የተለያዩ ዘሮችን በአካልና በስፍራ መለያየት አስቸጋሪ ከመሆኑም ሌላ በዝባዥ የገዥ ክፍሎችን ጥቅምም ሊጐዳ ስለሚችል መድልዎ በአብዛኛው የሚሠራበት በተቋሞች ፣ በአገልግሎቶችና በልዩ ልዩ ማኅበራዊ ከንዋኔዎች አማካይነት ነው ። ገዥ ወገኖች ከሚጠቀሙባቸው ተቋሞች የተገለሉት ልዩ ልዩ አገልግሎት የተነፈጉት ፣ ከልዩ ልዩ ማኅበራዊ ከንዋኔዎች የተለዩት ወገኖች የበታችና ተገዥ ሆነው እንዲቀዩ ይገደዳሉ ። በሁለቱ ወገኖች መካከል የአካልና የስፍራ ቅርበት ሊኖር ቢችልም በዚህ ዓይነት መድልዎ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ይኖራል ማለት ነው ።

ለመድልዎ መሠረቱ የግል ሀብት ባለቤትነት መስፈን ስለሆነ መፍትሔ ሊያገኝ የሚችለው በሶሻሊስት ኅብረተሰብ መመሥረት ነው ።

(አፓርታይድን ፣ ጽዮናዊነትን ፣ ዘረኝነትን ይመለከቷል ።)

## መጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት

*(Primitive Accumulation of Capital)*

የምርት ማከናወኛ ባለቤትነት የነበራቸውን አነስተኛ አምራቾች ከምርት መገልገያ ባለቤትነታቸው በማፈናቀልና የሥራ ኃይላቸውን በመሸጥ እንዲበዘበዙ ፣ ሀብት በጥቂቶች እጅ እንዲከማች የማድረግ ሂደት የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት ይባላል ። ይህ ሂደት የምርት መገልገያዎችንና ገንዘብን ወደ ካፒታልነት የለወጠ ሂደት ሲሆን ለካፒታሊስት ስልተ ምርት ቅድመ መነሻ የነበረ ነው ። ማርክስ የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት ማለት አምራቹን ሕዝብ ከምርት ማከናወኛ መሣሪያዎች ባለቤትነት ቀስ በቀስ ማግለል ማለት ነው ሲል ገልጾታል ።

ለመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት መነሻ ምክንያቶች የምርት ኃይሎች መዳበር ፣ የሸቀጥ—ገንዘብ ግንኙነት መስፋፋትና ሰፋ ያሉ ብሔራዊ ገበያዎች መቋቋም ነበሩ ። በፊውዳሉ ስልተ ምርት ውስጥ የሸቀጥ—ገንዘብ ግንኙነት መስፋፋት አነስተኛ ሸቀጥ አምራቾች እየከሰሩ እንዲሄዱ አደረገ ። በሌላ በኩል በዚህ ወቅት የምርት ኃይሎች ማደግና የፋብሪካ አመራረት መስፋፋት በዛ ያለ የቅጥር ሥራ ኃይል መገኘትን ጠየቀ ። በዛ ያለ የቅጥር ሥራ ኃይል አነስተኛ ሸቀጥ አምራቾችን በኢኮኖሚ ተፅዕኖ ማከሰርና ከምርት መገልገያ ባለቤትነታቸው ማፈናቀል ለካፒታሊዝም ማደግ ወሳኝነት ነበረው ።

አነስተኛ አምራቾችን ከምርት መገልገያ ባለቤትነታቸው የማፈናቀሉ ሁኔታ እንደየሀገሩ የተለያየ ቢሆንም ዓይነተኛው በእንግሊዝ የተከናወነው ነው ። የእንግሊዝ ቡርዧ መደብ በአሥራ ስምንተኛው ምዕት ዓመት ያወጣው "አስከሌ ሕጐች" በመባል የሚታወቀው ሕግ ገበሬዎችን ከመሬታቸው በማፈናቀሉ ለካፒታሊስቶች ተቀጥረው እንዲሠሩ በማድረጉ እንደምሳሌ የሚጠቀስ ነው ። ሰፋፊ የመሬት ይዞታ የመፈጠሩ ሂደት በገጠር ለካፒታሊዝም መስፋፋት ብቻ ሳይሆን በከተማም ለታዳጊ ኢንዱስትሪዎች አስፈላጊውን የሰው ኃይል በማስገኘት በኩል ከፍተኛ ድርሻ አበርክቷል ።

የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት ሌሎችም ገጽታዎች አሉት ። የአውሮፓ መንግሥታት በወቅቱ ለካፒታል መከማቸትና መዳበር እንዲሁም ለወዝአደሩ ቁጥር መብዛት አጋዥ የሆኑ ሕጐችን በማውጣት የሀገር ውስጥ ካፒታሊስቶች በውጭ ሀገር ካፒታሊስቶች ውድድር እንዳይዳከሙና የሀገር ውስጥ ገበያ እንዳይጣበብ የተለያዩ ከላሉታዊ እርምጃዎችን በመውሰድ በተለይ

ከ16ኛው እስከ 18ኛው ምዕት ዓመት ድረስ ባለው ወቅት ለካፒታል መከማቸት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል ። ቅኝ ግዛቶችን በማስፋፋትና የንግድ ጦርነቶችን በማካሄድ ለካፒታል መዳበርና ለካፒታሊዝም መስፋፋት አስፈላጊ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል ። የባሪያ ንግድን በማስፋፋት በተለይ እንግሊዝ ፥ ሆላንድና ሲፓኝ በቅኝ ግዛቶቻቸው ውስጥ በተቋቋሙ ትላልቅ እርሻዎችና የማዕድን ስፍራዎች ውስጥ የባሪያን ጉልበት እስከፊና አሰቃቂ በሆነ መንገድ መበዝበዛቸው የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት አንደኛዉ ገጽታ ነበር ። ከዚህም በላይ ቅኝ ገዢዎች በቅኝ ግዛት ሥር ካዋሉዋቸውና በአጠቃላይ በዕድገት ደረጃዎች ወደኋላ ከቀሩት ሀገሮች ጋር ያካሒዱት የነበረው ያልተመጣጠነ ንግድና ዝርፊያ ለካፒታል ክምችት በከፍተኛ ደረጃ ረድቷቸዋል ። በአጠቃላይ የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት እየተባለ የሚታወቀው የካፒታሊስት ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ከመዳበሩ በፊት ለሦስት መቶ ዓመታት ያህል ሲከናወን ቆይቷል ። በንግድ መስፋፋት የጀመረው ካፒታል ወደ ዓይነተኛው ባሕርዩና ቅርፁ ወደ ኢንዱስትሪ ካፒታል ለማደግ ችሏል ፤ የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት በሂደቱም በከፍተኛ ብዝበዛ አማካይነት ለካፒታሊስት ስልተ ምርት መከሰትና መዳበር አስፈላጊውን ክምችት አዘጋጅቷል ፤ እንዲሁም የወዝአደሩም ሆነ የቡርዧው መደቦች ቅርፃቸውን እንዲይዙ ከማድረጉም በላይ ለካፒታሊስቱ የምርት ግንኙነት መንሰራፋት ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን አመቻችቷል ።

(ሶሻሊስት ክምችትን ፥ የምርት መገልገያዎችን ፥ ቅኝ ግዛትን ፥ ይመለከቷል ።)

## መገንጠል

*(Secession)*

ከአንድ መንግሥታዊ አስተዳደር ወይም ሀገር በስምምነት ወይም በኃይል መለየት መገንጠል ይባላል ።

የመገንጠል ጥያቄ ሁለት ወይም ብዙ ብሔሮች ባሉበት መንግሥት ውስጥ በጨቋኝ መንግሥት ሥር ያለ የተጨቆነ ብሔር ከሚደርስበት አስከፊ ብዝበዛና ጭቆና ለመላቀቅ የራሱን መንግሥት በማቋቋም መብቱን ለማስከበር የሚያነሣው ጥያቄ ነው ። ይህም ጥያቄ ጭቁን ብሔሮች በአድኃሪው መንግሥት ሥር ፈጽሞ ለመኖር በማያስችላቸው አስከፊ ሁኔታ ውስጥ ሲገኙ እንደ አንድ መፍትሔ አድርገው የሚያነሡት ነው ። የጭቁን ብሔር ቡርዧ መደብ ግን የጨቋኙን ብሔር ጨቋኝ መደብ ጭቆና በማስታከክ የራሱን ብሔር ጭቁን መደብ ከጨቋኝ ብሔር ጨቋኝ መደብ አላቆ በራሱ የኢኮኖሚ ፥ የፖለቲካና የአስተሳሰብ ተፅዕኖ ሥር ለማዋልና ለመበዝበዝ የሚያነሣው ጥያቄ ነው ። በዚህም አድኃሪ አቋሙ የጨቋኝ ብሔርን ጭቁን መደብ ጭምር የጭቁን ብሔር የመደብ ጠላት አድርጎ ያቀርባል ። በዚህም ለመላው ብሔረሰብ የጋራ ጥቅም በሚል ሽፋን የሁለቱን ብሔሮች ጭቁን መደቦች የትግል አንድነት ይበርዛል ።

ማርክሳውያን የብሔርን የመገንጠል ጥያቄ የሚመለከቱት ከአጠቃላይ የካፒታል ተፅዕኖ ፥ ከኢምፔሪያሊዝም መዳከምና ከወዛደራዊው አብዮት መጠናከር አንፃር ነው ። የነርሱ ዓላማ ምን ጊዜም ጭቆናን በማንኛውም መልኩ ማስቀረትና የሁሉም ብሔሮች ሕዝቦች የተሟላ ነፃነት ፥ መብትና እኩልነት እንዲከበር ማድረግ ነው ። የብሔር ጥያቄ በዚህ ዲሞክራሲያዊ ይዘቱ ይህንን ሁኔታ ለመፍጠር በሚደረገው ትግል አስተዋጽኦ እስካደረገ ድረስ የማርክሳውያንን ድጋፍ ያገኛል ። ይህንን የሚቃረን ሆኖ በፀረ አብዮት አመራር ሥር ሲወድቅ ግን ፀረ ወዛደር በመሆኑ እስከ መጨረሻው ይታገሉታል ።

የመገንጠል መብትን ማወቅና መብቱ በሥራ እንዲተረጐም መታገል የተለያዩ ነገሮች ናቸው ። ማርክሳውያን የመገንጠልን ጉዳይ በመርህ ደረጃ የሚቀበሉት ቢሆንም በተግባር እንዲተረጐም የሚታገሉበት ጊዜ እንዳለ ሁሉ በሥራ ላይ እንዳይውል የሚታገሉበት ጊዜም ይኖራል ። የመገንጠል መብት ተግባር ላይ መዋል አስፈላጊነት ከወቅቱ የፖለቲካ ፥ የኢኮኖሚና የታሪክ ሁኔታዎች አንፃር መገምገም አለበት ። የብሔር ጥያቄ ለብቻው ራሱን እንደቻለ ሳይሆን የአጠቃላዩ የመደብ ትግል አካል እንደሆነ ተደርጎ መታየት አለበት ። ለምሳሌ በ19ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ አካባቢ ፖላንድ ከቄሳራዊት

ሩሲያ እንድትገነጠል ማርክስ ይሰጥ የነበረው ድጋፍ ትክክለኛ ነበር ። በዚያን ጊዜ በሩሲያና በተቀሩትም የስላቭ ሀገሮች ዲሞክራሲያዊ የሆኑ የሕዝብ ንቅናቄዎች ባለመኖራቸው በአውሮፓ ዲሞክራሲ እንዲኖር የፖላንዱ ንቅናቄ ትልቅ አስተዋጽኦ ነበረው ። በኋላ ግን የዚህ አቋም ትክክለኛነት አከትሟል ። ምክንያቱም በ20ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ላይ በሩሲያም ሳይቀር የሠራተኛውና የሌሎች ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄዎች በመፋፋማቸው ፣ ፖላንድም ወደካፒታሊዝም በመሸጋገሯና ቀድሞ የነበራትን ቦታ በማጣቷ የተለየ ሁኔታ ተፈጠረ ። ከዚህም የተነሣ የፖላንድ ሶሻሊስት ፓርቲ የሩሲያና የፖላንድ ወዛደሮች የመደብ ትግል ኅብረት ይፍጠሩ ብሎ የፖላንድን ንዑስ ከበርቴ ብሔረተኝነት በማውገዝ የወሰደውን አቋም ሌኒንም ደግፎታል ።

(የብሔር ጥያቄን ይመለከቷል ።)

## መጠን ለውጥ (የ—)

(*Quantitative Change*)

ማንኛውም ለውጥ በመጠን ለውጥ ላይ የተመሠረተ ወይም ከሱ የሚመነጭ ነው ። የመጠን ለውጥ ማለት ነገሩ ዓይነቱን ሳይቀይር መጠኑ ብቻ ሲጨምር ወይም ሲቀንስ ነው ። ይህ የመጠን መጨመር ወይም መቀነስ በብዙ መልኮች ማለት በቁመት ፣ በስፋት ፣ በኃይል ፣ በመዋቅራዊ ቅራኔ ውስጥ ወዘተ . . . ሊከሰት ይችላል ።

በዲበአካላውያን አመለካከት በተፈጥሮ ውስጥ የሚታየው የለውጥ ዓይነት የመጠን ለውጥ ብቻ ነው ። ይህ አቋም የሚገልጸው ለዲበአካላውያን ዓለም እንደተፈጠረ በመሆኑ የነገሮች ዓይነታዊ ለውጥ ሊኖር እንደማይችል ነው ። ሆኖም ሊካድ የማይችል ነገር ቢኖር የመጠን ለውጥ በተወሰነ ደረጃ ላይ ወደዓይነት ለውጥ እንደሚያመራ ነው ። ይህም ሊሆን የሚችለው የመጠን መጨመር ወይም መቀነስ በተወሰነ ደረጃ ላይ የነገሩን ውስጠ ችሎታና ጠባይ ስለሚቀይረው ነው።

(ከመጠን ወደ ዓይነት ከዓይነት ወደመጠን ለውጥ ሕግን ይመለከቷል ።)

## መጠን ወደ ዓይነት ከዓይነት ወደ መጠን ለውጥ ሕግ (ከ—)

*(The Law of Transformation of Quantity into Quality and Vice Versa)*

ይህ ሕግ ከዲያሌክቲክስ መሠረታዊ ሕጎች አንዱ ነው ። ማንኛውም ነገር በመጠንና በዓይነት ይገለጻል ፤ ሕጉ የሚያጠናው በነሱ መካከል ያለውን ግንኙነትና አንዱ ወደሌላው የመቀየሩን ሁኔታ ነው ።

በዲበአካላውያን አስተሳሰብ በመጠንና በዓይነት መካከል ልውውጥ ሊኖር አይችልም ። ዓይነት ከመጠን የተለየ በመሆኑ አንዱ ወደሌላው ሊቀየር አይችልም ። አንድ ነገር መጠኑ ሲለውጥ ትንሽ ወይም ትልቅ ይሆናል እንጂ ዓይነቱን አይቀይርም ። ለምሳሌ ዛፍ ትልቅ ወይንም ትንሽ ሊሆን ይችላል ፤ እውነቱ ግን መጠኑን እንደፈለገ ቢቀይርም ወደሌላ ነገር እንደማይለወጥ ነው ። ይህ የዲበአካላውያን አመለካከት የሚገልጸው ዓለምና በዓለም ውስጥ ያሉ ነገሮች ከዕድገት የተገኙ ሳይሆን እንዳሉ የተፈጠሩና በተፈጥሮ ባሕርይ ለሁሌም እንደሚጸኑ ነው ።

አስተሳሰቡ በቀላል ልናያቸው ከምንችላቸው ሁኔታዎችም ጋር አይገጥምም ። ከልምድ እንደምናየው መጠን ሲጨምር ወይም ሲቀንስ ከተወሰነ ደረጃ ላይ ሌላ ክስተት እንደሚያስከትል ነው ። ለምሳሌ ውሃ ሲሞቅና የሙቀቱ መጠን እየጨመረ ሲሄድ በተወሰነ ደረጃ ላይ ውሃው ወደእንፋሎት ይቀየራል ። ከዚህ የምንረዳው ነገሮች ሁሉ የራሳቸው ወሰን እንዳላቸው ነው ። ወሰኑን ሲተላለፉ አመርታ በማሳየት የዓይነት ለውጥ ያደርጋሉ ።

የዓይነት ለውጥ የተባለበትም ምክንያት ነገሩ በፊት ያልነበሩትን ጠባዮች ስለሚያሳይ ነው ። ለውጡ የመጠን ብቻ ሳይሆን የችሎታና የጠባይም በመሆኑ የዓይነት ለውጥ ይባላል ። እንፋሎት ከውሃ የተለየ ችሎታና ጠባይ አሉት ።

ሕጉ የተመሠረተው በነገሮች ውስጣዊ ባሕርይ ላይ ነው ። የአንድ ነገር ጠባይና ባሕርይ የሚወስነው በሚያቅፋቸው ብናኝ ነገሮችና ተጋጣሚዎች ነው ። የመጠን ለውጥ እነዚህን ብናኞችና ተጋጣሚዎች በቁጥር በማብዛት ወይም በመቀነስ ወይም ደግሞ

ኃይላቸውን በመጨመር ወይም በማሳነስ በተወሰነ ደረጃ ላይ የነገሩ ዓይነት እንዲለወጥ ያደርጋል ። የመጠን ለውጡ በመጠንና በዓይነት መካከል ያስከተለው አለመጣጣም በዓይነት ለውጥ ይስተካከላል ማለት ነው ። ይህ የሚያስረዳን ዓይነትና መጠን ውህደት እንዳላቸው ነው ። አንድ ነገር የሚያቅፋቸው የብናኞች መጠን የነገሩን ዓይነት ሲወስን የነገሩ ዓይነት ደግሞ የሚገልጸው የብናኞቹን ውስጣዊ ግንኙነትና መዋቅር ነው ። በመሆኑም የዓይነት ለውጥም በመጠን ለውጥ ይገለጻል ።

የዚህ ሕግ ፍች ቁስአካላዊ መሆኑን በቀጥተኛ መንገድ ያሳያል ። ነገሮች ሁሉ የቁስአካል የተለያዩ መልኮችና በዕድገት ተዋረድ የተያያዙ መሆናቸውን የሚያስረዳ ሕግ ነው ። ተፈጥሮአዊ ነገሮች ፥ ሰውም ጭምር ፥ በዓይነት የተለያዩት በአንድ ፈጣሪ ፍላጎት ሳይሆን መጠን ወደዓይነት ፥ ዓይነት ወደመጠን በመቀየሩ ነው ። አብዮት ከመጠን የሚመጣ የዓይነት ለውጥ ነው ። ቅራኔዎች በየጊዜው እየሰፉና እየተወሳሰቡ ሲሄዱ ፈንጂ የሆነ ሁኔታ በመፍጠር ኅብረተሰቡ በአመርታ ወደ አዲስ ሁኔታ መሸጋገሩ የዓይነት ለውጥ ነው ።

(እመርታን፥ የዲያሌክቲክስ ሕጎችን ይመለከቷል።)

## መፈብረክ

*(Manufacture)*

ከቀላል የካፒታሊስት ትብብር ያደገ የካፒታሊስት አመራረት ሁለተኛው የዕድገት ደረጃ ነው ። መፈብረክ በሥራ ክፍፍልና በእጅ ባለሙያዎች ቴክኒክ ላይ የተመሠረተ የካፒታሊስት አመራረት ሲሆን ከቀላል የካፒታሊስት ትብብር ሊያድግ የቻለው በሁለት መንገድ ነው ።

አንደኛው መንገድ ካፒታሊስቱ በተለያየ የሙያ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሙያዎችን በአንድ የሥራ ቦታ በማሰባሰብ አንድ ዓይነት ሸቀጥ እንዲያመርቱ ማድረጉ ነው ። ለምሳሌ ሠረገላ ለማሠራት ካፒታሊስቱ የሠረገላ ጐማ ሠሪዎችን ፥ የብረት ሠራተኞችን ፥ የሰፋ መቀመጫ ሠራተኞችን ፥ የመስታወት ሠራተኞችና ሌሎችንም ለሠረገላ ሥራ የሚያስፈልጉ ሠራተኞችን በአንድ ላይ ያሰባስባል ማለት ነው ፤ ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ካፒታሊስቱ በአንድ ሙያ ላይ የተሰማሩ በዛ ያሉ ሠራተኞችን በማሰባሰብ በተወሰነ የሥራ ድርሻ መሠረት አንድ ሸቀጥ እንዲሠሩ ያደርጋል ። ለምሳሌ መርፌ ለመሥራት አንዱ ሽቦውን ያመቻቻል ፤ ሌላው ሽቦውን ይቆርጣል ወዘተ... በዚህ መሠረት እያንዳንዱ ሠራተኛ በመርፌው ሥራ ውስጥ አንድ አነስተኛ ድርሻ ይኖረዋል ማለት ነው ።

በሁለቱም መንገድ ቢሆን ሸቀጡ የሚመረተው በሥራ ክፍፍል ላይ ተመሥርቶ ነው ። ማለትም እንደ ቀድሞው ሠራተኛው የሚሠራው መላ ሸቀጡን ሳይሆን የሸቀጡን የተወሰነ አካል ብቻ ነው ማለት ነው ። በዚህ ወቅት የተከሰተው የሥራ ክፍፍል የሥራ ምርታማነት በይበልጥ እንዲያድግ አደረገ ። በሥራ ክፍፍሉ መሠረት የተለያዩ የማምረቻ መሣሪያዎች ለተወሰኑ ሥራዎች በተደጋጋሚ የሚያገለግሉ በመሆናቸው ለእነዚህ የማምረቻ መሣሪያዎች መሻሻል አመቺ ሁኔታ ተፈጠረ ። የማምረቻ መሣሪያዎች መሻሻልና የሠራተኞች በተወሰኑ ሥራዎችና የሥራ ዘርፎች መሠልጠን የማኅበራዊ ሥራን ምርታማነት ይበልጥ እንዲያድግ አደረገ ።

በሌላ በኩል ይህ ዓይነት የካፒታሊስት አመራረት ካፒታል በሥራ ላይ ያለውን የበላይነት ይበልጥ ከማጠናከሩም በላይ ለካፒታሊስቱ ብዝበዛ አመች ሁኔታን ፈጠረ ። መፈብረክ ወዝአደሩን እጅግ በጣም ከማድከሙም በላይ አእምሮውም እንዲደነዝዝ ፥ በአእምሮና በጉልበት ሥራ መካከልም የነበረው ልዩነት ይበልጥ እንዲሰፋ ያደርጋል ።

መፈብረክ ከፍተኛ የምርት ኃይሎች ዕድገትን ቢያስገኝም መሠረቱ (የእጅ ባለሙያዎች ቴክኒክ) በእጅ የሚንቀሳቀሱ መሣሪያዎች ነበሩ ፤ ይህ ያልዳበረ ቴክኒካዊ መሠረት በወቅቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም እያደገ የሚሄድን ገበያ ፍላጐት ለማርካት የሚችል ከፍተኛ ምርት ለማስገኘት አልቻለም ።

የማምረቻ መሣሪያዎች ለረጅም ጊዜ ይሠሩ የነበሩት በእጅ ባለሙያዎችና በእጅ በሚንቀሳቀሱ መሣሪያዎች ነበር ። ይህ ሁኔታ ግን ቀደም ሲል ወደተጠቀሰው ችግር አመራ ። ካፒታሊስቶች የሚያገኙትን ትርፍ በይበልጥ ለማሳደግ የማምረቻ መሣሪያዎችን ማሻሻል ነበረባቸው ። በዚህ መሠረት የማምረቻ መሣሪያዎች በሌሎች ማምረቻ መሣሪ

ያዎች ተሠርተው መውጣታቸው የግድ ሆነ ። የማምረቻ መሣሪያዎችን በእጅ ከመሥራት በሌሎች የማምረቻ መሣሪያዎች መሥራት ሲጀመር የካፒታሊስት አመራረት ከመፈብረክ ደረጃ ወደ ማሽን ምርት ደረጃ ተሸጋገረ ።

የካፒታሊዝም የመፈብረክ የዕድገት ደረጃ ለተስፋፋ የማሽን አመራረት መፈጠር ሁኔታዎችን አመቻችቷል ። አንዳንድ በእጅ የሚንቀሳቀሱ የማምረቻ መሣሪያዎችን በማስተዋወቅ የሥራ ክንዋኔ እንዲቀላጠፍና እንዲቃለል አድርጓል ። የሥራ ክፍፍል ለተለያዩ ሥራዎች የሚያገለግሉ መሣሪያዎች በማሽን ተሠርተው እንዲወጡ አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል ። ለተስፋፋ የማሽን አመራረት የሚያስፈልገውን የሠለጠነ የሰው ኃይልም በማፍራቱ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

(ቀላል የካፒታሊስት ትብብርን ፣ የማሽን ምርትን ይመለከቷል ።)

## መፈንቅለ አገዛዝ

*(Coup d'Etat)*

በአንድ ሀገር ውስጥ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በኃይል በመጠቀም የሚያካሂዱት ድንገተኛ የመንግሥታዊ አገዛዝ ለውጥ ነው ። መፈንቅለ አገዛዝ በመደብ ትግል ላይ ያልተመሠረተ የሰፊው ሕዝብ ተሳትፎ የሌለበትና በአንድ መደብ አባሎች ፣ ግለሰቦች ወይም በቡድኖች መካከል የሚደረግ የሥልጣን ሽሚያ ነው ። በዚህም መፈንቅለ አገዛዝ ከአብዮት ይለያል ።

መንግሥታዊ አገዛዝ በአንድ ሀገር በከፍተኛ ደረጃ የመንግሥቱን የዕለት ተዕለት የአስተዳደር ሥራ የሚመራ ፣ የተወሰኑ ሰዎች ያሉበት አካል እንደመሆኑ የመንግሥት የተለየ ክፍል ነው ። ስለዚህም መንግሥት ሳይለወጥ አገዛዙ ሊለወጥ ይችላል ። ዛሬ በአሜሪካ (ዩ. ኤስ. ኤ.) አንዴ ዲሞክራቲክ ፓርቲው ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሪፑብሊካን ፓርቲው እየተፈራረቁ የአገዛዙን ስፍራ ይይዛሉ ። መንግሥቱ ግን ዞሮ ዞሮ ያው በካፒታሊስቱ መደብ እጅ ነው ። ይህ በምርጫ መልክ የሚከናወን የአገዛዝ ለውጥ ቢሆንም ፣ በኃይል በመጠቀም የሚደረገውም የመንፈቅለ አገዛዝ ውጤት ያው ነው ። ስለዚህ አንድ መንግሥታዊ አገዛዝ ሌላውን በኃይል ሲተካ ሁኔታውን መፈንቅለ መንግሥት ብሎ ከመሰየም ይልቅ መፈንቅለ አገዛዝ ማለቱ የበለጠ ትክክለኛነት ይኖረዋል ። ምክንያቱም በመፈንቅለ አገዛዝ የተወገደው የገዥው መደብ ሳይሆን በወቅቱ በሥልጣን ላይ ያሉት መንግሥቱን በበላይነት የሚመሩት ሰዎች ናቸው ። የመንግሥት ለውጥ የሚመጣው በአብዮት እንጂ በአገዛዙ መለወጥ አይደለም ። አብዮታዊ የመንግሥት ለውጥ ተደረገ የሚባለው የነበረው አድኃሪ መደብ ተደምስሶ በቦታው ይጨቆን የነበረው መደብ ሥልጣን ሲጨብጥ ብቻ ነው ።

(አብዮትን ይመለከቷል ።)

## መፈክር

*(Slogan)*

የአንድን ትግል ወይም እንቅስቃሴ የቅርብም ሆነ የሩቅ ዓላማና አቅጣጫ ለማመልከት በአጭር ሐረግ ወይም ዐረፍተ ነገር የሚቀርብ መሪ ሐሳብ ነው ። መፈክር በጉልህ ተጽፎ በሕዝብ ሊታይ ፣ በቃል ሊሰማ ፣ ወይንም በመገናኛ መሣሪያዎች ሊገለጽ ይችላል ።

መፈክር አንድ ሕዝባዊ ትግል የቆመለት ዘላቂ ዓላማና ትግሉ ፣ በየጊዜው ከሚደርስበት ደረጃ አኳያ የሚለነዘር በመሆኑ ስትራቴጂያዊና ታክቲካዊ ግብ አለው ። የስትራቴጂው መፈክር የረጅም ጊዜን የትግል አቅጣጫ የሚተልምና በዚህ ዓላማ መሠረት ሕዝቡን የሚቀሰቅስ የፕሮፓጋንዳ መፈክር ነው ። ለምሳሌ "ኢምፔሪያሊዝም፣ ፊውዳሊዝምና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም በጭቁን ሕዝቦች ክንድ ይደመሰሳሉ!" ፣ "ዓለም የሠርቶ አደሮች ትሆናለች !" ፣ የሚሉት የስትራቴጂ መፈክሮች ናቸው ። በሌላ በኩል ደግሞ የወቅቱን የትግል ስልት የሚያመለክቱ ፣ እንደጊዜው ፣ እንደ ቦታውና እንደሁኔታው አመችነት የሚቀ

ርቡ በረጅም የትግል አቅጣጫ አንድ እር
ምጃ ወደፊት የሚያራምዱ ወቅታዊነትና ተግ
ባራዊነት ያላቸው የታክቲክ መፈክሮች
አሉ ። ከነዚህም ውስጥ "ሁሉም ነገር ወደ
ጦር ግንባር!" ፣ "ለሠራተኛው ፓርቲ
ምሥረታ ወደፊት!" የሚሉት ወቅታዊነት
ላቸው አብዮታዊ ተግባሮች ሰፊውን ሕዝ
የሚያነሣሡ የታክቲክ መፈክሮች ናቸው።

(ፕሮፓጋንዳን ፣ ቅስቀሳን ይመለከቷል ።)

## ሙአለ ንዋይ
(*Investment*)

ትርፍ ለማግኘት ሲባል ካፒታልን
ሞላ ጐደል ረዘም ላለ ጊዜ በኢንዱስትሪ ፣
እርሻ ፣ በትራንስፖርት ፣ በኮንስትራክሽንና
መሳሰሉት የኢኮኖሚ መስኮች የማዋል
ንዋኔ ሙአለ ንዋይ ይባላል ። ሙአለ ንዋይ
ሁለት ይከፈላል ። እነሱም የገንዘብ ሙአለ
ንዋይና እውን ሙአለ ንዋይ ናቸው ።

የገንዘብ ሙአለ ንዋይ የሚባለው ለአረ
ቦናች ፣ ለአክሲዮኖችና ለሌሎች የዋስትና
ሰነዶች ግዥ የሚውል ካፒታል ሲሆን
እውን ሙአለ ንዋይ የሚባለው ደግሞ
ለሕንፃዎች ፣ ለልዩ ልዩ ማሽኖችና ለመሳሰ
ሉት ቋሚ ንብረቶች ግዥ የሚውለው ካፒታል
ነው ።

በካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ ከሙአለ
ንዋይ ጋር የተያያዙ የገንዘብ እንቅስቃሴዎ
ችን የሚያካሂዱ ወይንም የሚቆጣጠሩ የንግ
ድና የሙአለ ንዋይ ባንኮች ይገኛሉ ። እንደ
ቁጠባ ባንኮች ፣ እንደ መድን ድርጅቶች ፣
እንደጡረታ ገንዘብ አስቀማጮች ወዘተ...
ያሉት የገንዘብ ማከማቻ ተቋሞች እያሌ
ሞኖፖሊስቶች ለሙአለ ንዋይ የሚጠቀሙ
ባቸው ተጨማሪ አካሎች ናቸው ።

## ሙከራዊ ሳይንስ
(*Experimental Science*)

በአውሮፓ የፊውዳሊዝም መውደቅና
በቡርዧው ሥርዓት ቀስ በቀስ መተካት
የፈጠረው የአመለካከት ለውጥ ያስከተለው
"ሙከራ" በመባል የተሰየመው አዲስና
ጠቃሚ የሆነ የምርምር ዘዴ የሳይንስ መሠረት
መሆኑን የሚገልጽ ጽንሰ ሐሳብ ነው ። እውጠ
ንጣኝ የነበረው የፊውዳሊዝም ርዕዮተዓለም
ለሳይንስ ዕድገት አመች አልነበረም ። የቡ
ርዧዚው የምርት ኃይሎችን የማሳደግ ፍላጐት
ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው በተጨባጭ
ዕውቀት አማካይነት በመሆኑና ንድፈ ሐሳ
ቦችና ጽንሰ ሐሳቦች ለተግባር የሚያገለግሉት
በሙከራ የተፈተነ ግንዛቤ ውጤት ሲሆኑ
ብቻ በመሆኑ የቡርዧዚው አመለካከት ለሙ
ከራዊ ሳይንስ መጸነስ ዓይነተኛ አስተዋጽኦ
አድርጓል ።

ሙከራ የተፈጥሮ ሳይንስ የጥናት ስልት
ወይም ዘዴ ነው ። ሙከራ ማለት መላምት
ማፍለቅ ብቻ ሳይሆን መላምቱ የሚረጋ
ገጥበትንም ሁኔታ አብሮ ማዘጋጀት ማለት
ነው ። ሙከራ ነገሮችን ከማስተዋል የተለየ
ነው ፤ ምክንያቱም ሙከራ በመላምት የሚ
መራ በመሆኑ ነገሮችን ዝም ብሎ የሚመ
ለከት ሳይሆን ዕቅድ አዘል አድራጐትን
የመግለጽ ማለትም ነገሮችን የማመቻቸት ፣
የመለካት ፣ የማወዳደር ወዘተ... ባሕርይ
አለው።ሙከራ ቀጥተኛ የሆነ ቴክኒካዊ ፍችና
መሠረት ስላለው የሚከናወነው በላቦራቶሪ
ውስጥ ነው ። በሙከራ ዘዴ በመጠቀሙ
ነው የተፈጥሮ ሳይንስ ከፍተኛ ዕድገት ፣ተግ
ባራዊነትና ተደማጭነት ያገኘው ።

## ሙያ ማኅበራት (የ—)
(*Professional Associations*)

ተመሳሳይ ሙያ ያላቸው ሰዎች የሚስ
ባስቡባቸውና ለአባላቱ ጥቅም መከበርና
ለሚወከሉትም ሙያ መዳበር የቆሙ የብዙ
ኃን ድርጅቶች የሙያ ማኅበራት ይባላሉ ።

የሙያ ማኅበራት ከሌሎች ሕዝባዊ
ድርጅቶች የሚለዩት የአባሎቻቸው መመዘ
ኛዎች ዕድሜ ፣ ፆታ ወይም የሥራ ቦታና
የመሳሰሉት ሳይሆኑ በአንድ የተለየ ሙያ
የሠለጠኑና የተሰማሩ መሆናቸው ነው ። ለም
ሳሌ የመምህራን ፣ የጋዜጠኞች ፣ የደራስያን ፣
የጤና ባለሙያዎች ማኅበራት የመሳሰሉትን
መጥቀስ ይቻላል ።

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ የሚገኙ
የሙያ ማኅበራት ምንም እንኳ ለአባሎቻ
ቸው ጥቅም መከበርና ለሚወክሉት ሙያ
መዳበር ጥረት ቢያደርጉም ቅድሚያ የሚስ

ጡት ለዚህ መሟላት መሠረት ለሆነው ለኅብረተሰቡ የጋራ ዕድገት ነው ። በዚህ የጋራ መድረካቸው አማካይነት አባላቱ ከሙያቸው ጋር የተያያዘ ሳይንሳዊ ምርምርን ያበረታታሉ ፤ የፈጠራ ችሎታቸውንም ያዳብራሉ ። ሶሻሊዝም የሠርቶ አደሩን ሕዝብ በየዘርፉ መደራጀት የሚያበረታታ በመሆኑ የሙያ ማኅበራትም መጠናከር ለአጠቃላይ ግቡ እንደሚያግዝ በማመን ዕድገታቸውን በሚቻለው ሁሉ ይደግፋል ። ለዚህም እውን መሆን ፓርቲው ርዕዮተዓለማዊና ድርጅታዊ አመራር በመስጠት ሂደታቸው ከጠቅላላ የሠርቶአደሩ ዕድገት ዓላማ ጋር መያያዙን ያረጋግጣል ።

(ሕዝባዊ ድርጅትን ፤ ፓርቲን ይመለከቷል ።)

## ሚል ፡ ጀምስ
*(Mill, James)*

ከ1773—1836 የኖረ እንግሊዛዊ የታሪክና የኢኮኖሚ ተመራማሪ ነው ። ጀምስ ሚል የጆን ስትዋርት ሚል አባት ነው ።

ጀምስ ሚል በእንግሊዝ ሀገር በወቅቱ በኢኮኖሚ ዘርፍ የፊውዳሉን ሥርዓት ቅሪት የተቃወመና ለታዳጊው የካፒታሊስት መደብ ጥቅም የቆመ ምሁር ነበር ። "ኤለመንትስ ኦቭ ፖለቲካል ኢኮኖሚ" ከተሰኘው መጽሐፉ ለመገንዘብ እንደሚቻለው የጀምስ ሚል የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አመለካከት ከሪካርዶ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ አንዳንድ ነገሮችን ቢወስድም የሪካርዶ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ጥናት ዋነኛና መሠረታዊ መነሻ ለሆነው የእሴት የሥራ ንድፈ ሐሳብ ጨርሶ ቦታ ያልሰጠው ከመሆኑም በላይ የሪካርዶን የኢኮኖሚ አስተሳሰብ ያጣመመና ዋጋቢስ ያደረገ ነው ።

በሌላም በኩል ጀምስ ሚል ከብሔራዊ ገቢ ውስጥ የምንዳ ድርሻ የሚወሰነው በባህላዊ ፤ በታሪካዊ ፤ በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ የዕድገት ደረጃ ሳይሆን በተፈጥሮ ሁኔታዎች አማካይነት እንደሆነ ለማሳመን ሞክሯል ።

## ሚል ፡ ጆን ስትዋርት
*(Mill, John Stuart)*

ከ1806—1873 የኖረ የእንግሊዝ ፈላስፋ ፤ ኢኮኖሚስትና ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን የነበረ ሰው ነው ።

የጆን ስትዋርት ሚል የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ እንደ አባቱ እንደ ጀምስ ሚል የዴቪድ ሪካርዶ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አስተምህሮ ተፅዕኖ ያለበት ነው ። ጆን ስትዋርት ሚል የካፒታሊስት ሥርዓት ውጤት የሆኑትን አምልኮ ገንዘብን ፤ የሀብት አለመመጣጠንን ፤ የሠርቶ አደር ሕዝቦችን የኑሮ ደረጃ ዝቅተኛነትን የሚቃወም ቢሆንም ቅዋሜው ከቡርዧ ጥገናዊ ለውጥ አላለፈም ። በ1865 በጻፈውና "ፕሪንሲፕልስ ኦቭ ፖለቲካል ኢኮኖሚ" በተሰኘው መጽሐፉ ውስጥ በጊዜው የነበረውን የቡርዧ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አመለካከት በተቀነበባረ መልክ አስቀምጧል ።

በወቅቱ ተስፋፍቶ በነበረው በብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አመለካከት ውስጥ ተከስቶ ከነበረው ቅራኔ ለማምለጥ በማሰብ ጆን ስትዋርት ሚል የብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን አስተምህሮ ከተዛባውና ከተምታታው ከሴይ ፤ ከናሳው ፤ ከሲኒየርና ከቶማስ ሮበርት ማልተስ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አመለካከት ጋር ለመቀላቀልና ለማዳቀል ሙከራ አድርጓል ። ይህንንም በማስመልከት ማርክስ በጆን ስትዋርት ሚል የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አመለካከት ላይ ኂስ ሰንዝሯል ።

## ሚና
*(Role)*

ግለሰብ ፤ ቡድን ፤ ወይም ድርጅት ብኅብረተሰብ ውስጥ በልዩ ልዩ መስክና ደረጃ የሚያከናውነው ወይም የሚጠበቅበት ተግባራዊ ድርሻ ነው ። በበጐ ገጽታው ሲታይ አንድ ሰው ከቤተሰብ ጀምሮ በሥራ ቦታውና በአጠቃላይም በኅብረተሰብ ውስጥ በተወሰነ ወቅት ወይም በየጊዜው የሚፈጽማቸው ጠቃሚ ሥራዎች አሉ ። የተለያዩ ማኅበራዊ ፤ ፖለ

ቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ቡድኖችና ድርጅቶችም እንደዚሁ ከቆሙለት ዓላማ አንፃር በየፊናቸው በሚያከናውኗቸው ተግባሮች የሚጫወቱት ሚና አለ። በዚህም መሠረት ለምሳሌ ስለ አንድ ዜጋ ወይም መሪ ፣ ስለሠራተኛው ማኅበር ወይም ስለሠራተኛው መደብ ፓርቲ ፣ አንድ ዓለም አቀፍ ድርጅት በሚያከናውነው ተግባር ስለሚኖረው ሚና መናገር ይቻላል ።

## ማኅበራዊ ሕግጋት

*(Social Laws)*

በማኅበራዊ ሕይወት የተለያዩ ዘርፎች ውስጥ በሚገኙ ማኅበራዊ ክስተቶችና ሂደቶች መሀከል ያሉትን ግንኙነቶች የሚገልጹ ሕግጋት ናቸው ። እነዚህ ማኅበራዊ ክስተቶች (የማምረት ፣ የልውውጥ ፣ የፍጆታ ፣ የክፍፍል ወይም የምርት ግንኙነቶች ተግባር ፣ ማኅበራዊ አብዮት ፣ የኅብረተሰብ ዕድገት ወዘተ...) ከሰዎች ፍላጐትና ኅሊና ውጭ የሚገኙ እንደመሆናቸው በመሀከላቸው የሚገኙ ግንኙነቶችንና እነዚህንም ግንኙነቶች የሚገልጹት (የሚገዙት) ሕግጋት ከሰው ፍላጐትና ኅሊና ውጭ የሚገኙ ናቸው ።

ማኅበራዊ ሕግጋት ከተፈጥሮ ሕግጋት የሚለዩባቸው ባሕርያት አሏቸው ። የመጀመሪያው ለማኅበራዊ ክስተቶች ማኅበራዊ ምክንያት ያላቸው መሆኑ ነው ። ማለትም ማኅበራዊ ክስተቶች የሰዎችን ዓላማ ያለው ንቁ ከንዋኔን የሚጠይቁና በሰዎች መሀከል የሚካሄዱትን መስተጋብሮች የሚያጠቃልሉ ናቸው ። ሰዎች ዓላማ ያለው ንቁ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ እንደመሆናቸው እንቅስቃሴያቸውን ከመጀመራቸው በፊት ዕቅድ የማውጣት ፣ የተግባራቸውን ውጤቶች በቅድሚያ የመመልከት ፣ ለዓላማቸው መሳካት የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎች የመፍጠርና የመጠቀም ችሎታ አላቸው ። ከዚህም የተነሣ የሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ፍላጐታቸውን የሚያረኩ ፣ በተፈጥሮ ላይ ያላቸውን የበላይነትና ቁጥጥር ከፍ የሚያደርጉ ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያ ችግሮቻቸውን የሚፈቱላቸውና የሚያቃልሉላቸው በመሆናቸው ማኅበራዊ ጠቀሜታ አላቸው ።

ሁለተኛው የማኅበራዊ ክስተቶች ባሕርይ እንዳሉ የሚለዋወጡ ፣ የማይደጋገሙና እያንዳንዳቸው የራሳቸው የሆነ ልዩ ባሕርይና ገጽታ ያላቸው መሆኑ ነው ።ለምሳሌ የፈረንሳይና የእንግሊዝ ቡርዧ አብዮቶች በቡርዧ አብዮትነታቸው ተመሳሳይ ቢሆኑም የተካሄዱበት ወቅት ፣ ያስገኟቸው ውጤቶች ፣ የተሳተፉባቸው መደቦችና የነዚህ መደቦች የኃይል ሚዛን አሰላለፍ ወዘተ... የተለያዩ በመሆናቸው ክስተቶቹ በነበራቸው ልዩ ባሕርይና መልክ አልተደጋገሙም ። ሆኖም እነዚህና ተመሳሳይ ማኅበራዊ ክስተቶች ባይደጋገሙም ማኅበራዊ ሳይንሶች የሉም ማለት አይደለም ፤ ምክንያቱም ክስተቶቹ የሚገዙት በነባራዊና በሁለንታዊ ማኅበራዊ ሕግጋት ነው ። እንደ ተፈጥሮአዊ ክስተቶች ሁሉ በታሪክ ውስጥ የማኅበራዊ ክስተቶችን አሳቦት የግላዊነትና የሁለንታዊነት ፈርጆች ባሕርይ በጥሞና ማገናዘብ ያስፈልጋል ።

በመጨረሻም የማኅበራዊ ክስተቶችና የማኅበራዊ ሕግጋት ዕውቀት ይዘት የመደብ ጥቅምን የሚያንፀባርቅ በመሆኑ የማኅበራዊ ሕግጋት (የድርጊቶችና የክስተቶች) ፍልስፍና ትንታኔ ፍች ወገናዊ የሆነ የመደብ ባሕርይ አለው ።

የማኅበራዊ ክስተት ተመራማሪዎች በተወሰነ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ የአንድ የተወሰነ መደብ ወይም ማኅበራዊ ቡድን አባላት ናቸው ። ስለሆነም ለማኅበራዊ ክስተቶች በሚሰጡት ትንታኔ ላይ አባል ሆነው የሚገኙበት መደብ ወይም ማኅበራዊ ቡድን ፍልስፍና ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳድራል ። በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ ተመራማሪዎች ስለማኅበራዊ ክስተቶች ያላቸው ግንዛቤ የተለያየ ብቻ ሳይሆን ተቃራኒም ሊሆን ይችላል ። አንዳንዶቹ (በሚገኙበት መደብ ጥቅም ወይም ነባራዊ ሁኔታ ተከልለው) የመደብ ኅብረተሰቦችን ሲያወድሱ ሥርዓቱ ለወለዳቸው ችግሮችም የሚሰጡት መፍትሔ ሥርዓቱን የሚያሻሽል እንጂ የሚለውጥ አይደለም ። ሌሎቹ ደግሞ የሥርዓቱ ተጠቃሚ ባለመሆናቸው ማኅበራዊ ሥርዓቱ እንዲሻሻል ብቻ ሳይሆን መሠረታዊ ወይም አብዮታዊ በሆነ መንገድ እንዲለወጥ የሚታገሉ ናቸው ። ስለሆነም ማኅበራዊ

ሕግጋት ነባራዊነት ቢኖራቸውም የትንታኔያቸው ፍች ግን የመደብ ባሕርይ አለው ።

(ማኅበራዊ አብዮትን ፣ የምርት ግንኙነቶችን ፣ ተግባርን ፣ ሕግን ይመለከቷል ።)

## ማኅበራዊ ምርት ክፍል አንድና ክፍል ሁለት (የ—)

*(Department I and Department II of Social Production)*

በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የምርት መገልገያዎችን የሚያመርቱ የኢኮኖሚ ክፍሎች ባጠቃላይ የማኅበራዊ ምርት ክፍል አንድ ሲባሉ የፍጆታ ዕቃዎችን የሚያመርቱ የኢኮኖሚ ክፍሎች ደግሞ በአጠቃላይ የማኅበራዊ ምርት ክፍል ሁለት በመባል ይታወቃሉ ። ማኅበራዊ ምርት በእሴት መልኩም በሁለት መንገድ የሚገለጽ ሲሆን ይኸኛው የማኅበራዊ ምርት አከፋፈል ግን ከቁሳዊ ቅርፁ አንፃር የቀረበ ነው ።

የክፍል አንድ ምርቶች ለማምረት ተግባር የሚውሉ ጥሬ ዕቃዎች ፣ ማሽኖች ፣ የምርት መሣሪያዎች ፣ ነዳጅ ፣ የኤሌክትሪክ ኃይልና የመሳሰሉት ሲሆኑ ፤ የክፍል ሁለት ምርቶች ደግሞ የሰዎችን ፍላጐት በቀጥታ የሚያረኩ እንደምግብ ፣ እንደ ልብስ ፣ እንደ ጫማ ፣ እንደ መኖሪያ ቤት የመሳሰሉት የፍጆታ ዕቃዎች ናቸው ። ስለዚህ ሁለቱ የማኅበራዊ ምርት ክፍሎች የሚለዩት ምርቶቻቸው ከሚውሉበት ጥቅም አንፃር ነው ። የክፍል አንድ ምርቶች ምርት ለማምረት ፣ የክፍል ሁለት ምርቶች ደግሞ የሰዎችን ፍላጐት በቀጥታ ለማርካት ይውላሉ ።

ማኅበራዊ ምርት በሁለቱ ክፍሎች መከፈሉን ለመጀመሪያ ጊዜ የገለጸው ካርል ማርክስ ነው ። በማንኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ የሚካሄድ ዋናው የምርት ዓይነቶች ልውውጥ በእነዚህ በሁለት ክፍሎች መካከል የሚካሄድ በመሆኑ የማንኛውም ኅብረተሰብ ማኅበራዊ ምርት በሁለት ክፍሎች ይከፈላል ።

(ቀላል እርባታን ፣ የተስፋፋ እርባታን ይመለከቷል ።)

## ማኅበራዊ ትምክህተኝነት

*(Social Chauvinism)*

በዓለም አቀፍ ሶሻሊስት እንቅስቃሴ ውስጥ የተከሰተ የአድርባይነት አዝማሚያ ነው። ማኅበራዊ ትምክህተኝነት በተለይ ተጠናክሮ የታየው አብዛኛዎቹ የሁለተኛው ኢንተርናሽናል ፓርቲዎች መሪዎች ዓለምአቀፋዊውን የወዝአደሮች የትግል አንድነት ፖሊሲ ክደው ለየመንግሥቶቻቸው ኢምፔሪያሊስታዊ ፖሊሲ በቆሙበት በአንደኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ነበር ። እነዚህ የሁለተኛው ኢንተርናሽናል ፓርቲዎች መሪዎች ወዝአደሩ "እናት ሀገርን መከላከል" በሚለው መፈክር ሥር ተሰልፎ የኢምፔሪያሊስቱ ጦርነት ተሳታፊ እንዲሆን የመደብ ዕርቅን ሰብከዋል ።

ለምሳሌ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ቦልሼቪኮችና ሌሎች አብዮታውያን ኢምፔሪያሊስታዊውን ጦርነት ወደአብዮታዊ የመደብ ጦርነት ለመለወጥ ሲታገሉ በአውሮፓ የሚገኙ አብዛኛዎቹ የሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲዎችና መሪዎቻቸው ወደማኅበራዊ ትምክህተኝነት በማዘቀጥ በሶሻሊዝምና ሀገርን በመከላከል ሽፋን ሠራተኛው መደብ ለየሀገሩ ቡርዧዚ እንዲያጐበድድ አድርገዋል ።

ከነርሱም ውስጥ የመሀል ለፋሪነት አቋም ያራምዱ የነበሩት ደግሞ ነገሮችን በዝምታ በማለፍ ፣ አለበለዚያም ማርክሳዊ ሐረጐችን በማነብነብ የማኅበራዊ ትምክህተኞችን የክህደት ድርጊት ትክክለኛ እንደሆነ አድርገው ለማቅረብ ሞክረዋል ። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላም ቀኝ ክንፍ ማኅበራዊ ዲሞክራቶች በሚከተሏቸው ፖሊሲዎች ማኅበራዊ ትምክህተኝነትን ሲያንፀባርቁ ይታያሉ ።

(ማኅበራዊ ዲሞክራሲን ፣ ሁለተኛው ኢንተርናሽናልን ይመለከቷል ።)

## ማኅበራዊ ኑባሬ

*(Social Being)*

ኅብረተሰብን በሚመለከተው የፍልስፍና መሠረታዊ ጥያቄ ማለትም በቁስአካልና በንቃተ ኅሊና መሀከል ያለው ግንኙነት አንዱና ወሳኙ ክፍል ነው ። ማኅበራዊ ኑባሬ የኅብረተሰብ ቁሳዊ ሕይወትን ፣ ቁሳዊ የሆኑ ክስተቶችን ፣ የሀብት ምርትንና በዚህም ሂደት

ውስጥ በሰዎች መሀከል የሚፈጠሩ ግንኙነቶችን የሚመለከት ፈርጅ በመሆኑ በኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ የኅሊናዊ ክስተቶች መሠረት ነው ።

ማኅበራዊ ኑባሬ በሰዎች መሀከል በቁሳዊ ሀብት ምርትና ክፍፍል ሂደት ውስጥ የሚፈጠሩ ግንኙነቶችን ማለትም የምርት ግንኙነቶችን (በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የመደብ ግንኙነቶችን ወይም በመደብ አልባ ሥርዓት ውስጥ ደግሞ የጋርዮሽ ግንኙነቶችን) ያጠቃልላል ። ሆኖም የምርት ግንኙነቶች የማኅበራዊ ኑባሬ ዋነኛና ወሳኝ ክፍል ቢሆኑም ማኅበራዊ ኑባሬ በሰዎች መሀከል የሚፈጠሩ ቁሳዊ ግንኙነቶችንም (በባልና በሚስት ፣ በአባትና በልጅ ፣ የዕለት ተዕለት ኑሮና ባህላዊ ግንኙነቶችንም) ያጠቃልላል ።

ሰዎች በኅሊናዊ ሕይወታቸው ውስጥ የሚቀርጿቸው ሐሳቦች ፣ ዝንባሌዎች ፣ ግምቶች ፣ ማኅበራዊ ሥነ ልቡናዎች (ፍልስፍና ፣ ኪነታዊ አስተሳሰቦች ፣ ሃይማኖት ፣ ሥነ ምግባራዊ አመለካከቶች ወዘተ...) የሚመነጩትና የሚያንፀባርቁት አኗኗራቸውን ፣ ማኅበራዊ ሕይወታቸውንና እርስ በርሳቸውና ከተፈጥሮ ጋር ያሳቸውን ግንኙነቶች ነው ። በመሆኑም ማኅበራዊ ኑባሬ ቀዳማይና ወሳኝ ሲሆን ማኅበራዊ ኅሊና ደግሞ የርሱ ነፀብራቅና በአጠቃላይና በመጨረሻው ላይ ሲታይ በርሱ የሚወሰን ነው ። ለምሳሌ በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ አስተሳሰቦች ፣ ርዕዮተዓለማዊ ግንኙነቶች ፣ ተራ አስተሳሰቦች (ወጎች ፣ ፈሊጦች) የሚመሠረቱትና መልሰውም የሚያንፀባርቁት የተገኙባቸውን ቁሳዊ ግንኙነቶች ማለትም ማኅበራዊ ኑባሬን ነው ። ይህንን ሲገልጽ ነው ማርክስ ማኅበራዊ ኑባሬ በማኅበራዊ ኅሊና የሚወሰን ሳይሆን ማኅበራዊ ኅሊና ራሱ በማኅበራዊ ኑባሬ የሚወሰን ነው ያለው ። በሐሳባዊ ፍልስፍና ውስጥ ግን የማኅበራዊ ኑባሬን ወሳኝነት ባለማጤን ማኅበራዊ ኅሊና የኅብረተሰብ ሕይወት ወሳኝ እንደሆነ ተደርጐ ይወሰዳል ።

ሆኖም በማኅበራዊ ኑባሬና በማኅበራዊ ኅሊና መሀከል ያለው ግንኙነት በርካታ መልኮችና ውስብስብ ባሕርያት ያሉት ነው ። ከኅብረተሰብ ዕድገት ጋር ማኅበራዊ ሕይወት እያደገና እየተስፋፋ ሲሄድ በዚያው መጠን በሁለቱም መሀከል ያለው ግንኙነት ይበልጥ የተወሳሰበ ይሆናል ። ለምሳሌ በጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት ውስጥ በሰዎች መሀከል የነበሩ ቁሳዊ ግንኙነቶች ቀጥተኛ ውጤት የነበረው ማኅበራዊ ኅሊና በመደቦች መከሰት ፣ ከዚህም ጋር በፖለቲካ ፣ በሕግ ወዘተ... ግንኙነት መፈጠር የተነሣ ማኅበራዊ ኑባሬ በሰዎች አእምሮ ላይ የወሳኝነቱን ሚና የሚጫወተው በመንግሥት ፣ በሕጋዊና በፖለቲካዊ ወዘተ... ግንኙነቶች አማካይነት ነው ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ማኅበራዊ ኅሊናን በሰዎች መሀከል ከሚገኙት ቁሳዊ ግንኙነቶች ብቻ ለመረዳት መሞከር የግንኙነቶቹን ግንዛቤ ግልብና ተናካኦታዊ ያደርገዋል ።

(የምርት ግንኙነቶችን ፣ ማኅበራዊ ንቃተ ኅሊናን ይመለከቷል ።)

## ማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና

*(Social Consciousness)*

በተግባር ሂደት ውስጥ ሰዎች ስለ ነባራዊ ዓለምና ስለማኅበራዊ ኑሮአቸው (ማኅበራዊ ሀልውናቸው) በአእምሮአቸው ውስጥ የሚቀርጿቸው ልዩ ልዩ መልክ ያላቸው ነፀብራቆችን ያመለክታል ። ማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና ሰዎች በአስተሳሰባቸው የሚቀርጿቸውን ፖለቲካዊ ፣ ሕጋዊ ፣ ሥነውበታዊ አስተሳሰቦችን ፣ ጽንሰ ሐሳቦችንና ፍልስፍናዊ ፣ ሥነ ምግባራዊ ፣ ሃይማኖታዊ ወዘተ... ንድፈ ሐሳቦችን ያጠቃልላል ።

በቁስአካልና በንቃተ ኅሊና መሀከል ያለው ግንኙነት ከኅብረተሰቡ አንፃር ሲታይ በማኅበራዊ ኑባሬና በማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና መሀከል ያለው ግንኙነት ነው ። ሐሳባዊ ፍልስፍና የኅብረተሰብ ሕይወት በማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና ይወሰናል ይላል ። ማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና ሰዎች ስለማኅበራዊ ሀልውናቸው በኅሊናዊ ሕይወታቸው ውስጥ የሚቀርፁት ነፀብራቅ እንደመሆኑ ማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና ማኅበራዊ ኑባሬን ይወስናል ለማለት አይቻልም ።

ማኅበራዊ ኑባሬ ቁሳዊ ክስተቶችን የሚመለከት በመሆኑ ነባራዊ ነው ። ሰዎች ስለማኅበራዊ ሀልውናቸው ያሳቸው አስተሳሰብ ግን የኑሮአቸው ነፀብራቅ ነው ። የማኅ

በራዊ ንቃተ ኅሊናችን ይዘት በማኅበራዊ ህልውናችን ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል ። የአስተሳሰባችን ይዘት ስለኑሮአችን ያለን ግንዛቤ ነውና ። ማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና በማኅበራዊ ኑባሬ ይወሰናል ቢባልም ቅሉ ማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና አንፃራዊ ነፃነት የለውም ማለት አይደለም ።

የማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና አንፃራዊ ነፃነት የሚገለጠው ቁስአካላዊ የኅብረተሰብ ሕይወት ለውጥ በማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና ውስጥ ወዲያውኑ አዳዲስ ክስተቶችን የማይፈጥር በመሆኑ ነው ። ምክንያቱም ኅሊናዊ ክስተቶች ሰዎች በሚያጠራቅሟቸው መረጃዎች (ተፈጥሮአዊና ማኅበራዊ) ላይ የሚመሠረቱና የራሳቸው የሆነ የዕድገት ሥነ አመክንዮ ያላቸው በመሆኑ ነው ። በሌላ በኩልም ኅሊናዊ ጽንሰ ሐሳቦች የሚያንፀባርቁት ቁስአካላዊ ክስተት በሌለበት ወቅት እንኳን ያለመጥፋት ፣ ያለመለወጥ ወይም ዘግይቶ የመለወጥ ባሕርይ አላቸው ። በአሮጌዎቹ ጽንሰ ሐሳቦችና በአዳዲሶቹ መሀከል የሚካሄደው ትግል በተለይም አዲሱ ቁስአካላዊ ሕይወት የሚፈጥራቸው ክስተቶች ናቸው አሮጌዎቹን እንዲጠፉ ፣ ሙሉ በሙሉ እንዲለወጡ የሚያደርጓቸው ። ይህ በማኅበራዊ ኑባሬና በማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና መሀከል ያለውን ልዩነት በተለይም የማኅበራዊ ንቃተ ኅሊናን አንፃራዊ ነፃነት ያሳያል ።

ማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና በማኅበራዊ ኑባሬ የሚወሰንና እርሱንም የሚያንፀባርቅ ቢሆንም ማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና መልሶ በማኅበራዊ ኑባሬ ላይ ተፅዕኖ የማሳደር ችሎታ አለው ፤ ይህም የአንፃራዊ ነፃነቱ አንዱ ገጽታ ነው ። በተለይም ሕጋዊና ፖለቲካዊ አስተሳሰቦች ከኅብረተሰቡ ታሪካዊ የዕድገት ደረጃ ጋር ሲጣጣሙ ለዕድገት የሚረዱ አመቺ ሁኔታዎችን በመፍጠር በኅብረተሰቡ ቁስአካላዊ ሕይወት ዕድገት ላይ አፋጣኝ ተፅዕኖ ሊያደርጉ ይችላሉ ። ለምሳሌ የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መሰራጨት ንቁ ዲሲፕሊንን ያጠናክራል ፤ ሳይንሳዊ ዕውቀት በማሳደግና የፈጠራ ችሎታን በማሻሻል የምርት ኃይሎች እንዲያድጉ ይረዳል ።

(ማኅበራዊ ኑባሬን ፣ ላዕላይ መዋቅርን ይመለከቷል ።)

## ማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ

*(Socially Necessary Labour Time)*

በተወሰነ የምርት ዘርፍ በአንድ ወቅት አምራቹ ክፍል ባለው አማካይ ዕውቀትና የምርታማነት ደረጃ ፣ አንድ የተወሰነ ሸቀጥ ለማምረት የሚወስድበት የሥራ ጊዜ ነው ። ለምሳሌ በአንድ መንደር አሥር ሰንደል ጫማ ሠሪዎች ቢኖሩና ተመሳሳይ የሆኑ ሰንደል ጫማዎች ለመሥራት ሰባቱ ለእያንዳንዱ ሰንደል ጫማ አራት ሰዓት ቢፈጅባቸው ፣ በዚህ ሁኔታ አንድ ሰንደል ጫማ ሠርቶ ለማውጣት የሚወስደው ማኅበራዊ ተቀባይነት ያለው የሥራ ጊዜ አብዛኞቹ የፈጀባቸው አራት ሰዓት የሥራ ጊዜ ነው ማለት ነው ። በመሆኑም ይህ አራት ሰዓት የሥራ ጊዜ በዚያ መንደር ውስጥ በወቅቱ ባለው የሰንደል ጫማ አምራቾች የሥራ ችሎታና የአሠራር ዘዴ ፣ የማምረቻ መሣሪያዎች የቴክኒክ ደረጃ አንፃር እንደማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ ይወሰዳል ማለት ነው ።

የማናቸውም ሸቀጥ እሴት የሚወሰነው በዚሁ በማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ ነው። ማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ ከሠራተኛው የሥራ ችሎታና ከቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር እየቀነሰ የሚመጣ በመሆኑ የሸቀጦችም እሴት ከማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ መጠን መለወጥ ጋር አብሮ የሚለወጥ ይሆናል ።

(ትርፍ የሥራ ጊዜን ይመለከቷል ።)

## ማኅበራዊ አብዮት

*(Social Revolution)*

በማኅበራዊ የዕድገት ሂደት ውስጥ አሮጌው ማኅበራዊ ሥርዓት ተወግዶ አዲሱ ፣ ተራማጁና ታዳጊው ማኅበራዊ ሥርዓት የሚተካበት መሠረታዊ ለውጥ ማኅበራዊ አብዮት ይባላል ። አድኃሪው መደብና የእርሱም መጠቀሚያ የነበረው የኢኮኖሚ ሥርዓት የሚፈርሱበት ፣ በምትካቸውም አዲስና ተራማጅ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሥርዓት የሚመሠረትበት እመርታዊ የኅብረተሰብ ዕድገት ወቅት ነው ። ከአንድ የመደብ ኅብረተሰብ ወደ ሌላኛው መደብ ኅብረተሰብ የሚደረገው ሽግግር ያለ ማኅበራዊ አብዮትና ያለ ሰፊው

ሕዝብ ተሳትፎ ሊከናወን የሚችል አይደለም ። የአዲስ ሥርዓት ቅድመ ሁኔታዎች በአሮጌው ሥርዓት ውስጥ ከተጸነሱ በኋላ የሚያሳዩት አዝጋሚ ለውጥ ከፍተኛው ደረጃ ላይ ደርሶ በእመርታ አዲሱ አሮጌውን ሥርዓት በመሻር የሚተካበት ወቅት ነው ።

ማኅበራዊ አብዮት የመደብ ኅብረተሰብ ዕድገት አይቀሬና አስፈላጊ ውጤት ነው ። ማኅበራዊ አብዮት በአሮጌው የምርት ግንኙነቶችና በአዲሶቹ የምርት ኃይሎች መሀከል ያለውን ቅራኔ የሚፈታ ሲሆን ይህም ቅራኔ ለአዲሶቹ የምርት ኃይሎች ዕድገት የሚያመቹ የምርት ግንኙነቶችን ይመሠርታል ። ማኅበራዊ አብዮት የምርት ግንኙነቶች ከምርት ኃይሎች የዕድገት ደረጃና ባሕርይ ጋር መጣጣም አለባቸው የሚለው የመጣጣም ሕግ የሚረጋገጥበት የማኅበራዊ ዕድገት ደረጃ ነው ።

በኅብረተሰብ ዕድገት ሂደት ውስጥ የአሮጌው ሥርዓት ተጠቃሚ የሆኑት መደቦች በመንግሥት አማካይነት የአሮጌው ሥርዓት ኢኮኖሚያዊ መሠረቶች (የምርት ግንኙነቶች) እንዳይለወጡ ሲታገሉ ተራማጅ መደቦች ግን በማኅበራዊ ሁኔታ አስገዳጅነት በወቅቱ ጊዜው አልፎበት የሚገኘውን የመንግሥት ሥርዓት ለመገርሰስ ይታገላሉ ። ለዚህ ነው የማናቸውም የማኅበራዊ አብዮት መሠረታዊ ጥያቄ የመንግሥት ሥልጣን ጥያቄ ነው የሚባለው ። ስለዚህም ማኅበራዊ አብዮት የመደብ ትግልን ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚያደርስና የመደብ ሹም ሽርን የሚያስከትል ነው ። የአብዮት ወቅት የተፋፋመ የማኅበራዊ ዕድገት ደረጃ ነው የሚባለው በቅድመ አብዮት በፖለቲካው መስክ ተሳትፎ ያልነበረው ሰፊው ሕዝብ በትግሉ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ስለሚጀምር ነው ።

ማኅበራዊ አብዮት ከመፈንቅለ አገዛዝ ይለያል ። መፈንቅለ አገዛዝ የምርት ግንኙነቶች ሳይለወጡ የፖለቲካ ሥልጣን ከአንድ መደብ የተወሰነ ክፍል ወደ ዚሁ መደብ ሌላ ክፍል ሲሸጋገር ነው ። መፈንቅለ አገዛዝ የመንግሥትን የበላይ አባላት ወይም ግለሰብ ብቻ በሌላው መተካት ማለት ነው ።

ማኅበራዊ አብዮቶች እንደሚያፈርሱትና እንደሚገነቡት ሥርዓትና እንዲሁም እንደሚሳተፉባቸው መደቦች ይለያያሉ ። የቡርዧው መደብ የፊውዳሉን ሥርዓት አፍርሶ የካፒታሊስቱን ሥርዓት የሚገነባበት ማኅበራዊ አብዮት የቡርዧ አብዮት ሲባል በወዝአደሩ መሪነት የካፒታሊስቱን ሥርዓት አፍርሶ የሰው በሰው ብዝበዛ የሌለበት የሶሻሊስት ሥርዓት የሚገነባበት አብዮት የሶሻሊስት ወይም የወዝአደሩ አብዮት ይባላል ።

በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የካፒታሊስት ሀገሮች ያልተመጣጠነ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሁኔታ መኖር አብዮት በተለያዩ ሀገሮች ውስጥ በተለያየ ጊዜ እንዲፈነዳ ያደርጋል ። ስለሆነም ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም የሚደረገው ሽግግር በአንድ ወቅት በአንድ ወይም በጥቂት ሀገሮች ውስጥ ብቻ የሚደረግ ሽግግር ይሆናል ።

አሁን ባለንበት ዘመን ከሶሻሊስት አብዮት ሌላ ብሔራዊ የአርነትና ዲሞክራሲያዊ የነፃነት እንቅስቃሴዎች ከፍተኛ ሚና አላቸው ። በአጠቃላይ ሲታይ አሁን ያለንበት ዘመን የወዝአደሩ አብዮት ዘመን ነው ። ሆኖም በተለያዩ ሀገሮች ውስጥ የአብዮቱ ዕድገት ይሁንታዎች በተለያዩ ሁኔታዎች ማለትም በሠራተኛው መደብና በአጋሮቹ ኃይል ላይ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአድኃሪ መደቦች የአልሞት ባይ ተጋዳይነት ደረጃ ላይ ይመሠረታል ።

(አብዮትን ፣ የመደብ ትግልን ፣ የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች ዲያሌክቲክስን ይመለከቷል ።)

## ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት
*(Socio-Economic Formation)*

አንድ ኅብረተሰብ የተመሠረተበት የስልተ ምርት ባሕርይ በሚጠይቀው መሠረት ኅብረተሰቡ የሚያቅፋቸው የተለያዩ ክፍሎችና ክስተቶች በተጣመረና ሥርዓት ባለው ሁኔታ የሚሠሩና በተወሰኑ ሕጎች አንፃር የሚያድጉ መሆናቸውን የሚገልጽ የኅብረተሰብ ጥናት መሠረታዊ ፈርጅ ነው ። የማኅበራዊ ሥርዓት አካል የሚቀረፀው የታሪክ ሂደት ውጤት በሆኑት በምርት ግንኙነቶች ሲሆን

ሙሉ አካሉ የሚገነባው የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችና ክስተቶች የእርስ በእርስ ግንኙነቶች በሚፈጥሩት ጥምርና ውስብስብ መዋቅር ነው ።

ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት የሚለው ፈርጅ በመጀመሪያ ደረጃ የሚገልጸው ኅብረተሰብ ጥምር እውነታ እንደሆነ ነው ። ማንኛውም የኅብረተሰብ ክፍልና ክስተት (ቋንቋ ፥ ብሔር ፥ ግብረገብ ፥ ሕግ ፥ መንግሥት ወዘተ..) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከስልተ ምርት ጋር የተያያዙና በሱም የሚወሰኑ ከመሆናቸውም በላይ በእርስ በእርስ ግንኙነቶችም የተሳሰሩ ናቸው ። ኅብረተሰብ የግለሰቦች ወይም ደግሞ የማኅበራዊ ክስተቶች ተናክአታዊ ስብስብ ባለመሆኑ ማንኛውንም ክፍል ወይም ክስተት ነጥሎ ማየት አይችልም ። ማንኛውም ክፍል ወይም ክስተት ከሌሎች ጋር የሚጣመር መሆኑንና የሚጫወተውም ሚና የሚወሰነው በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች መሆኑን የሚያስረዳው ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት የሚለው ፈርጅ ነው ።

ፈርጁ በአይታ የሚለያዩ ኅብረተሰቦች ያላቸውን መሠረታዊ ተመሳሳይነት ለመገንዘብና በወል ባሕርይ ውስጥ ለመመደብ የሚጠቅም ነው ። ለምሳሌ በአቀማመጣቸው፥ በተፈጥሮ ሀብታቸው፥ በባህላቸው፥ በቋንቋቸው፥ በፖለቲካ ቅርፃቸው ወዘተ...የሚለያዩ ሀገሮች ባላቸው መሠረታዊ የካፒታሊስት የምርት ግንኙነት አንፃር በካፒታሊስት የዕድገት ደረጃ ላይ ይገኛሉ ማለት ይቻላል ። ማለትም ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት የሚለው ፈርጅ መሠረታዊና ተደጋጋሚ በሆኑ ሕጎች አንፃር ኅብረተሰቦችን ለማጥናት የሚጠቅም ነው ።

ይህ የወል ባሕርያትን በማስተዋል ኅብረተሰቦችን በአንድ የዕድገት ደረጃ ውስጥ ለማስለፍ የሚያስችል ፈርጅ በአንፃሩም በዕድገት ደረጃቸው አኳያ የተለያዩ ኅብረተሰቦችን ለመለየት ይጠቅማል ። ማለትም ጽንሰ ሐሳቡ በታሪክ ሂደት ውስጥ ወሳኝና ሁለንታዊ የሆኑ የዕድገት ምዕራፎችን ለመተንተን ያስችላል ። የኅብረተሰብ ታሪክ የሚከሰተው አንድ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ከፍተኛ በሆነው እየተተካ ታሪኩ ወደ ውስብስብነት እየተለወጠ ሲሄድ ነው ። በዚህም ሂደት ውስጥ አምስት መሠረታዊ የሆኑ ደረጃዎች ይገኛሉ ። እነዚህ የዕድገት ደረጃዎች በመጀመሪያ የሚለዩት በምርት ግንኙነቶቻቸው ነው ። የባሪያ አሳዳሪ ፥ የፊውዳልና የካፒታሊስት ሥርዓቶች ተፃራሪ መደቦችን ያቀፉና ብዝበዛ የሚካሄድባቸው ሲሆኑ የጥንታዊ ጋርዮሽና የኮሚኒስት ሥርዓቶች ግን ብዝበዛ የሌለባቸው ፥ ሰዎች በጋራ ጥቅም የሚተዳደሩባቸው ናቸው ። የነዚህ አምስት ሥርዓቶች መከታተል ተጨባጭ የዕድገት ሕግ ሲሆን እንደ ሁኔታው አንዱን ደረጃ በፍጥነት የማለፍ ሁኔታ ሊከሰት ይችላል ።

በአጠቃላይ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት የሚገልጸው የታሪካዊ ሂደትን አንድነትና ሙሉነት ነው ። ሀገሮች የተለያዩና ግላዊ ታሪካዊ መንገዶችን የሚከተሉ ቢሆኑም በአንድ የዕድገት ሕግ የሚገዙና በተመሳሳይ ሂደት ውስጥ የሚያልፉ መሆናቸውን ማለትም ታሪክ በሕግ የሚገዛ መሆኑን የሚያስረዳ ነው ። በተጨማሪም ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት የተለያዩ የታሪክ ዕድገት ደረጃዎች የዓይነት ልዩነት ያላቸው ሥርዓቶች መሆናቸውን የሚገልጽ ጽንሰ ሐሳብ ነው ።

(ስልተ ምርትን ፥ ታሪካዊ ቁስአካልነትን ፥ ማኅበራዊ ሕግጋትን ይመለከቷል ።)

## ማኅበራዊ ካፒታል

*(Social Capital)*

በአንድ ካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ካፒታሊስቶች በአጠቃላይ ያላቸው የካፒታል መጠን ማኅበራዊ ካፒታል ይባላል ። በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ እያንዳንዱ የማምረቻ ድርጅት በአንድ ካፒታሊስት ወይንም ቁጥራቸው በተወሰነ ካፒታሊስቶች በግል በመያዙ ከሌሎች አምራች ድርጅቶች የተለየ ሆኖ እንደሚሠራ የታወቀ ነው ። ነገር ግን በእያንዳንዱ የማምረቻ ድርጅት ውስጥ የሚካሄደው እንቅስቃሴ በሌሎች የማምረቻ ድርጅቶች ውስጥ ከሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ጋር የሚያያዝበትም ሁኔታ አለ ። ለምሳሌ በአንድ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ውስጥ የሚካሄደው የማምረት ተግባር ለፋብሪካው የሚያገለግሉ መሣሪያዎችን በሚያመርቱ ድርጅቶች ፥ ጥጥ በሚመረትባቸው እርሻዎች ፥ በጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካው

ውስጥ ተቀጥረው ለሚሠሩ ሠራተኞች የፍጆታ ዕቃዎች በሚያመርቱ ድርጅቶችና በመሳሰሉትም ድርጅቶች ውስጥ ከሚካሄደው የማምረት ተግባር ጋር የተሳሰረ ነው ።

ማኅበራዊ ካፒታል የምንለው በአንድ የካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኙትን እነዚህን እርስ በርሳቸው የተሳሰሩና የግል ካፒታሊስቶች በተናጠልም ሆነ የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ካፒታሊስቶች በጋራ ባለቤትነት የያዙትን ካፒታል በጥቅል ነው ። በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ካፒታሊስቶች በዚህ መልክ አንድ የተባበረ መደብ በመፍጠር ሠርቶአደሩን ይበዘብዙታል ። የማኅበራዊ ካፒታል ማደግም ካፒታሊስቶች በአጠቃላይ በወዛደሩ ላይ የሚያካሂዱትን ብዝበዛ ማባባሳቸውን ያመለክታል ። ስለዚህ የሠራተኛው መደብ ከብዝበዛ ሙሉ በሙሉ ለመላቀቅ ይችል ዘንድ የካፒታሊስቱን መደብ በአጠቃላይ መታገል ያለበት መሆኑ ግልጽ ነው ።

በካፒታሊስቱ ሥርዓት በአንድ በኩል በእያንዳንዱ የማምረቻ ድርጅት ውስጥ የሚካሄደው እንቅስቃሴ በሌሎች የማምረቻ ድርጅቶች ውስጥ ከሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ጋር በዚህ ዓይነት የተያያዘ ነው ይባል እንጂ በሌላ በኩል ግን በብሔራዊ ኢኮኖሚ ደረጃ ምንም በዕቅድ የሚመራ የምርት አደረጃጀት የለም ፤ ሊኖርም አይችልም ። በዚህ ምክንያት የኢኮኖሚው እንቅስቃሴ በአጠቃላይ ሥርዓት አልባ ይሆንና የተመረተው ሸቀጥ ዓይነትና መጠን ከኅብረተሰቡ ፍላጐት ጋር የማይጣጣም ይሆናል ። በአንዳንድ የኢኮኖሚ ክፍሎች ሸማቾች ከሚፈልጉት በላይ ይመረታል ። በሌሎች የኢኮኖሚ ክፍሎች ደግሞ ሸማቾች የሚፈልጉት ዓይነትና መጠን አይመረትም ። ይህም አለመጣጣም በሚባባስበት ጊዜ የሚመረቱት ሸቀጦች በወቅቱ ተሸጠው የማምረት ተግባር በተፈለገው ደረጃ እንዳይቀጥል ዕንቅፋት በመሆን የኢኮኖሚ ቀውስ ያስከትላሉ ።

(ግላዊ ካፒታልን ይመለከቷል ።)

## ማኅበራዊ ዲሞክራሲ

*(Social Democracy)*

በ19ኛው ምዕት ዓመት መጨረሻ ላይ በዓለም ሠራተኞች እንቅስቃሴ ውስጥ የተከሰተውን አድርባይ ንድፈ ሐሳባዊና ተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚያራምዱ የጠጋኝ ፓርቲዎች አጠቃላይ የፖለቲካ አዝማሚያ ነው ። ለምሳሌ በኦስትሪያ ሌበር ፓርቲ ፣ በፈረንሳይ ሶሻሊስት ፓርቲ ፣ በጀርመን ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ ወዘተ... የዚሁ አዝማሚያ አራማጆች ናቸው ። በመደብ ጠላት ፊት መርበድበድ ፣ ሕጋዊነት በሚል ሰበብ ጠንከር ያሉ ተግባራዊ እርምጃዎችን ከመውሰድ መቆጠብ ፣ በአጠቃላይ ለካፒታሊስቶች ማጎብደድና የሠራተኛውን መደብ መክዳት የማኅበራዊ ዲሞክራሲ መለያዎች ናቸው ።

ማኅበራዊ ዲሞክራሲ ከእነሥሡ አብዮታዊ አቋም የነበረውና ለሶሻሊስት አስተሳሰቦች መስራጨት ፣ ለሠራተኛው ማኅበራት መስፋፋትና መጠናከር የሚታገል ነበር ። ኋላ ግን ቀስ በቀስ በውስጡ ከላሸና አድርባይ አዝማሚያዎች እያየሉ በመምጣታቸው አብዛኛዎቹ ማኅበራዊ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎችከአብዮታዊ ትግል ይልቅ ከቡርዧው መደብ ጋር የመደብ ዕርቅ እንዲፈጠር ፣ ለመሠረታዊ ለውጥ ሳይሆን ለጥገናዊ ለውጦች መታገልን ዋንኛ ስልታቸው አደረጉ ። ካፒታሊዝምም ከጊዜ በኋላ ታሪካዊ ሚናውን ተጫውቶ የሚያልፍ ሳይሆን እየተሻሻለና እየዳበረ በራሱ ወደ ሶሻሊዝም እንደሚያድግ ተደርጐ ተወሰደ ። በዚህም አቋሙ ማኅበራዊ ዲሞክራሲ በእያንዳንዱ ሀገርና በአጠቃላይም በዓለም አቀፉ የሠራተኛው አብዮታዊ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል ።

ነገር ግን በዚህ በማኅበራዊ ዲሞክራሲ ንቅናቄ ውስጥ በሐቀኛው መሥመር ጸንተው የቆሙት ግራ ክንፍ ማኅበራዊ ዲሞክራቶች (ለምሳሌ በሌኒን የተመሩት የሩሲያ ማኅበራዊ ዲሞክራቶችና የሌሎችም ሀገሮች አብዮታውያን )ይህን አድርባይ አቋም እስከመጨረሻው በቆራጥነት ታግለዋል ። ከታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት በኋላም በጠጋኝ ማኅበራዊ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎች ውስጥ የነበሩት አብዮታዊ ኃይሎች ከአድርባዮች በመለየት በኮሚኒስት ኢንተርናሽናል (ሦስተኛው ኢንተርናሽናል) ውስጥ ተሰባስበዋል ። ኮሚኒስት ፓርቲዎች በተቻላቸው ሁሉ አድርባይነትን እየተከላከሉ ለሠራተኛው መደብ የበላይነት ቆራጥ ትግል ማድረጋቸውን ቀጠሉ ። የፋሺዝም አደጋ ባንዣበበበትም ወቅት የአድኅሮትን ኃይል ለመዋጋት የዲ

ሞክራሲያዊ ኃይሎች መሰባሰብ አስፈላጊ በመሆኑ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ከማኅበራዊ ዲሞክራሲ ኃይሎች ጋር በመተባበር ፋሺዝምን ተዋግተዋል ።

የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ እየተባባሰ በመሄድ ላይ ባለበት በዛሬው ሁኔታም በማኅበራዊ ዲሞክራሲ ውስጥ የተለያዩ አዝማሚያዎች ሲንፀባረቁ ይታያሉ ። ባለፉት ጥቂት ዓመታት የግራ ኃይሎች እንቅስቃሴ እያደገ መምጣት በካፒታሊስት ሀገሮች ከፍተኛ ተደማጭነት ባላቸው ማኅበራዊ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎች ፖሊሲ ላይ አንዳንድ ጤናማ አዝማሚያዎችን አስከትሏል ። የነዚህ ፓርቲዎች አባሎች የብዙ ካፒታሊስት ሀገሮች መንግሥታት አባሎችና መሪዎች በመሆናቸው ይህ ሁኔታ መጠነኛም ቢሆን አንዳንድ ጥገናዊ ለውጦችን ለማምጣት እንደሚረዳ ይታመናል ። ይህም በሚሆንበት ጊዜ ኮሚኒስት ፓርቲዎች በአንድ በኩል ከሳሽነትንና አድርባይነትን ያስአንዳች ለዘብተኛነት እየተዋጉ በሌላው በኩል ደግሞ ለሠራተኛው መደብ በአጠቃላይም ለሠርቶአደሩ ሕዝብ ጥቅም እንዲሁም ለሰላምና ለማኅበራዊ ዕድገት ሲሉ ለጊዜውም ቢሆን እንደሁኔታው ከማኅበራዊ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር ለመተባበር ይገደዳሉ ።

(ጠጋኝነትን ይመለከቷል ።)

## ማኅበራዊ ዳርዊኒዝም

*(Social Darwinism)*

የዳርዊንን ንድፈ ሐሳብ በቀጥታ ለኅብረተሰብ ጥናት በማዋል በ19ኛው ምዕት ዓመት የተቀመረ አስተምህሮ ማኅበራዊ ዳርዊኒዝም ይባላል ። ማኅበራዊ ዳርዊኒዝም "ተፈጥሮአዊ ማጣሪያና ለህልውና መታገል"ን የማኅበራዊ ዕድገት ዋነኛ አንቀሳቃሽ ኃይል አድርጐ የተነሣና ዛሬም ያለ አመለካከት ነው ።

በአንዳንዶቹ አመለካከት በኅብረተሰብ ውስጥ ተፈጥሮአዊ ማጣሪያ በትክክለኛ መልኩ ተፈጻሚነት የነበረው ቀደም ባለው ጊዜ ነበር ። ዛሬ ግን ከሳይንስና ከቴክኖሎጂ እርምጃና ግስጋሴ የተነሣ ለህልውና መታገል ወሳኝነት የለውም ፤ ምክንያቱም በቀድሞ ሁኔታዎች ይጠፉ የነበረው በሚደረግለት እንክብካቤ ህልውናውን ለመጠበቅ አመች ሁኔታ ተፈጥሮለታል ብለው ያምናሉ ። የዚህ ንድፈ ሐሳብ አራማጆች በቀድሞው ሁኔታ ጠፊ የነበሩት ሁሉ ዛሬ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ባስገኘው ውጤት ሳቢያ ህልውና አግኝተው ከጠንካራው እኩል ለመኖር ችለዋል ይላሉ ። ባጠቃላይ ማኅበራዊ ዳርዊኒዝም የካፒታሊዝምን ሥርዓት ዘላለማዊና የማይሻር ባሕርይ ለማረጋገጥ የሠራተኛውንና የሠርቶአደሩን ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለመንጠቅ ፣ ዲታዎችንና ጀግኖችን ዲበኩሉ አድርጐ ለማቅረብና ሠራተኛውንና ሠርቶአደሩን ሕዝብ ባጠቃላይ እንደ ሁለተኛ ደረጃ ዜጋ ለመመደብ የሚጥር አድኃሪ አመለካከት ነው ። አስተምህሮው በተለይም የካፒታሊዝምን ሥርዓት ህልውና ፋሺስታዊ በሆነ ኃይል ጭምር በመጠቀም ለማረጋገጥና ለማቆየት በሚሹ ክፍሎች ይገለጻል ። ስለዚህ ፍልስፍናው ዛሬ የፋሺዝምና የዘረኝነት አስተሳሰቦች መነሻ በመሆን የሚያገለግል ነው ።

(ዳርዊኒዝምን ፣ ፋሺዝምን ፣ አፓርታይድን ይመለከቷል ።)

## ማልባ

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የመጀመሪያ ደረጃ የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበርን ለማመልከት የተሰየመ ቃል ነው ። የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር የዕድገት ደረጃ የሚለካው በማኅበሩ ክልል ውስጥ ካሉት ጠቅላላ የምርት ማከናወኛዎች ምን ያህሉን ማኅበሩ የጋራ እንዳደረገና ማኅበሩ ለአባላቱ ገቢውን የሚያከፋፍለው በምን ሁኔታ እንደሆነ በማጤን ነው ።

አብዛኞቹ ገበሬዎች የንቃት ደረጃቸው እስኪዳብርና ግላዊ አስተሳሰባቸው ቀስ በቀስ እስኪወገድ ድረስ የእርሻ መሬታቸውንና መሣሪያዎቻቸውን ሙሉ በሙሉ በማኅበሩ ቁጥጥር ሥር እንዲያውሉ ለማድረግ ፈቃደኝነት በአንድ ጊዜ ማግኘት አዳጋች ሊሆን ይችላል ። ስለዚህ ማልባ (የመጀመሪያ ደረጃ የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር) አስፈላጊ ይሆናል ።

በማልባ ደረጃ እያንዳንዱ አባል ቤተሰብ ለግል መጠቀሚያ እስከ ሁለት ሺህ ካሬ ሜትር መሬት ይሰጠዋል ። ሌላውን መሬት ግን ማኅበሩ ይዞታው ከማድረጉም ሌላ በግል ይዞታ ሥር ባሉት የእርሻ እንስሳትና መሣሪያዎች ደግሞ የመጠቀም መብት ይኖረዋል ። በዚህ ደረጃ ማኅበሩ በግል ይዞታ ሥር በሆኑት የእርሻ እንስሳትና መሣሪያዎች ሲጠቀም ለባለንብረቶቹ ኪራይ ይከፈላቸዋል ። ማኅበሩ በኪራይ ለሚጠቀምባቸው የጭነትና የእርሻ እንስሳት በቂ ጥንቃቄ ባለመወሰዱ ቢሞቱ ተገቢውን ግምት ለባለንብረቱ ይከፍላል ። ስለዚህ በማልባ ደረጃ የአንድ አባል ገቢ የሚወሰነው በሚሠራው ሥራ መጠንና ጥራት ብቻ ሳይሆን በተጨማሪ ለማኅበሩ ባከራያቸው የእንስሳትና የመሣሪያዎች መጠንም ነው ። በመሆኑም "ከእያንዳንዱ እንደ ችሎታው ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው" የሚለው የሶሻሊስት የክፍፍል መርህ በዚህ ደረጃ ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ አይውልም ።

(ወልባን ፣ ወላንድን ይመለከቷል ።)

## ማልተስ ፣ ቶማስ ሮበርት
## *(Malthus, Thomas Robert)*

ከ1766—1834 የኖረ ፣ እንግሊዛዊ የግልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መሥራች ነው ። ማልተስ በ1793 ከካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ በሥነ መለኮት ዲግሪውን አግኝቶአል ። ከ1793 እስከ 1803 ባለው ጊዜ ውስጥም ስሪ በምትባል ሥፍራ በደብር አለቅነት ሲያገለግል ከ1805 እስከ 1834 ባለው ጊዜ ውስጥ በኢስት ኢንዲያ ኮሌጅ በዘመናዊ ታሪክና በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መምህርነት ሠርቷል ።

ማልተስ በካፒታሊዝም ሂደተ ዕድገት ውስጥ የተከሰተው የኢንዱስትሪ ተጠባባቂ ሠራዊትና በላጥ ምርት ያስከተለውን ቀውስ ለማቃለልና የካፒታሊዝምን የማይቀር ውድቀት ለጊዜውም ቢሆን ለማዘግየት አያሌ ጥገናዊ የኢኮኖሚ መፍትሔዎችን የሰነዘረ ምሁር ነው ።

ማልተስ በካፒታሊዝም ውስጥ የተፈጠረውን "የበላጥ" ምርት ቀውስ በካፒታሊዝም ውስጥ ያለውን ክፍፍል በማሻሻል ማስወገድ ይቻላል የሚል እምነት ነበረው ። ቡርዧዚው የሚያገኘውን ትርፍ ሁልጊዜ ለማከማቸት የሚፈልግ በመሆኑና ይህ ደግሞ በምርትና በገበያ መካከል ያለውን "የተመጣጠነ" ዕድገት ስለሚያዛባ ገቢው በመጠኑ መቀነስ ፣ በሌላ በኩል የወዝአደሩም መደብ ገቢ ለኑሮ በሚያስፈልገው መጠን መገታት አለበት ባይ ነው ። ስለዚህ እንደማልተስ አስተሳሰብ በካፒታሊዝም ውስጥ የተከሰተውን የበላጥ ምርት ቀውስ ለማስወገድ የሚቻለው ለፍጆታ ብቻ የሚውለው የመሬት ከበርቴው ገቢ ማደግ ሲችል ነው ። ይህም የገቢ ክፍፍል የምርትና የገበያውን ዕድገት እኩል እንዲጓዙ ለማድረግ ይረዳል የሚል የተሳሳተ እምነት ነበረው ።

ሌላው የማልተስ ዝና የገነነበት ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ ስለሕዝብ ቁጥር ዕድገት የሰጠው አስተያየት ነው ። ማልቱስያዊ የተሰኘው የቡርዧ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ንድፈ ሐሳብ ስያሜውን ያገኘውም ከማልተስ ነው ። "አን ኤሴይ ኦን ዘ ፕሪንሲፕል ኦቭ ፖፑሌሺን" በተባለው መጽሐፉ ውስጥ በካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ የሚገኙት ሥራ አጦች ሥራ ሊያጡ የቻሉት በተባዥ ክትትል የማደግ አዝማሚያ ባለው በሕዝብ ቁጥርና በተደማሪ ክትትል በሚያድገው ለሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጐት አርኪታ በሚውለው ምርት መካከል ምን ጊዜም በሚኖረው የመዛባት የተፈጥሮ ዝንባሌ እንጂ ከካፒታሊስት ስልተ ምርት ባሕርይ በመነጨ ምክንያት አይደለም የሚል አስተያየት ሰንዝሯል ።

ማልተስ በሰው ልጅ የመራባት ፍጥነትና ለህልውናው አስፈላጊ በሆኑ ምርቶች ዕድገት መካከል የሚኖረውን ያለመጣጣም ሐሳብ ከሰነዘረ በኋላ "ፈጣሪ" የፈጠረውን ችግር ራሱ መፍትሔ ስጥቶታል ብሎም ያምናል ። በማልተስ እምነት ይህ መፍትሔ በሕዝብ ቁጥር ዕድገት ላይ በተፈጥሮ ተቆጣጣሪነት የሚሠሩት እንደ ጦርነት ፣ እንደ በሽታ ፣ እንደ ድርቅ ፣ እንደ ረሀብ የመሳሰሉት ናቸው ። የሰው ልጅ ችግሩን አውቆና ተገንዝቦ መውሰድ ያለበትን እርምጃ ማልተስ "የመከላከያ ገደብ" ሲለው ለምሳሌ ሰዎች ድንግላዊ በመሆን ወይንም ጋብቻን ዕድሜያቸው ከገፉ በኋላ በመፈጸም በሚወ

ስዱት እርምጃ የሕዝብን ቁጥር ዕድገት መቋቋም ይቻላል ባይ ነው ።

የቶማስ ሮበርት ማልተስ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ንድፈ ሐሳብ ከታሪክ አንፃር ሲታይ አንድ ቁም ነገር አለው ። ይኸውም ካፒታሊዝም ገና በማቆጥቆጥ ላይ በነበረበት ጊዜ "ሥራ አጥነት" በሥርዓቱ ውስጥ ሊኖር አይችልም የሚለውን የጊዜውን የቡርዧ ምሁራንን አባባል መፃረሩ ነው ። ማልተስ ካፒታሊዝም ያቀፋቸው ውስጣዊ ቅራኔዎች ገሀድ መውጣት በጀመሩበት ወቅት የኖረ ግለሰብ በመሆኑ "ሥራ አጥነት" በተፈጥሮ ያለ ችግር ነው የሚል ስንኩል አስተሳሰብ ቢኖረውም "ሥራ አጥነት" መኖሩን ተቀብሏል ። ስለዚህም ነው ካርል ማርክስና ፍሬደሪክ ኤንግልስ ማልቱዚያኒዝም በተዛባ መንገድ ይሁን እንጂ የካፒታሊዝምን ቅራኔዎችና ድክመቶች በገሀድ ያሳያል ያሉት ።

## ማመዛዘን ሥርዓት በዕቅድ (የ—)
*(System of Balance in Planning)*

በዕቅድ የማመዛዘን ሥርዓት የአንድ ሀገር የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ለምሳሌ ፣ ፋብሪካዎች፣ የትራንስፖርት ፣ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ፣ የመንግሥት እርሻዎች ወዘተ... የሚጠበቅባቸውን ግብ ለማሟላት ይቻላቸው ዘንድ የሚያስፈልጋቸው የሰው ኃይል ፣ ጥሬ ዕቃ ፣ ገንዘብና የመሳሰሉት በቅድሚያ መሟላት መቻላቸውን ለማወቅ የሚረዳ የአሠራር ስልት ነው ።

ለምሳሌ በአንድ ሀገር በ10 ዓመት ውስጥ አንድ መቶ ሺ ቤቶች ለመሥራት ቢታቀድ ፣ መጀመሪያ ቤቶቹን ለመሥራት ያለው የአሠራር ቴክኒክ ፣ የሰው ኃይል ፣ ፋይናንስ እንዲሁም ለሕንፃ ሥራ የሚያገለግሉ ዕቃዎች ዓይነትና ብዛት መታወቅ አለበት ። ነገር ግን ለምሳሌ የሕንፃ መሣሪያ ዕቃዎችን የሚያመርቱ ድርጅቶች የተፈለገውን ያህል ለማቅረብ አለመቻላቸው ከታወቀ ለሕንፃ ሥራ የሚያገለግሉ ዕቃዎች የሚያመርቱና የሚያከፋፍሉ ድርጅቶችን ለማስፋፋት ዕቅድ ይወጣል ። በዕቅድ የማመዛዘን ሥርዓትም ዝበትን ለማስወገድ ከመርዳቱም በላይ በአጠቃላይ ዕቅዶች በተስተካከለ መንገድ ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ያገለግላል ።

በዚህ ሁኔታ በዕቅድ የማመዛዘን ሥርዓት ከብሔራዊ ዕቅድ አንሥቶ እስከ አንድ የኢኮኖሚ ድርጅት ዕቅድ ድረስ ያለውን ሁሉ የሚያጠቃልል ይሆናል ።

ዕቅድ አውጪ አካሎች ዕቅድ ሲያወጡ የቁሳቁስ ፣ የፋይናንስና የሰው ኃይል ሚዛን ያወጣሉ ። የቁሳቁስ ሚዛን ፣ በጣም አስፈላጊ የሆኑት ምርቶች ለምሳሌ ብረት ፣ የማሽን መሣሪያዎች ፣ ከሰል ፣ ነዳጅ ፣ እህል ፣ ቅቤ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል ። ሚዛኑ በሚሠራበት ጊዜ የእያንዳንዱ ምርት ምን ጭና ብዛት ከመጠናቱም በላይ ምርቱ ከኅብረተሰቡ ፍላጐት ጋር ሲነፃፀር ያለው ሁኔታም አብሮ ይታያል ። የፋይናንስ ሚዛን የብሔራዊ ገቢን ሚዛን ፣ የሕዝቡን ገቢና ወጭ ፣ የመንግሥቱን ባጀትና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል ። የሰው ኃይል ሚዛን ለብሔራዊ ኢኮኖሚው የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል በሙያ አንፃር በየክፍላተ ኢኮኖሚው በአጠቃላይ የሚመለከት ሲሆን እንደዚሁም ለብሔራዊ ኢኮኖሚው ግንባታ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ምንጭ ያጠናል ።

ከቁሳዊ ፣ ከገንዘብና ከሰው ኃይል ሚዛኖች ጋር የተገናዘበ አጠቃላይ የብሔራዊ ኢኮኖሚ ሚዛንም ይወጣል ። ይህ የብሔራዊ ኢኮኖሚ ሚዛን በተለያዩ ክፍላተ ኢኮኖሚ መካከል መኖር የሚገባውን የተስተካከለ ግንኙነት ያመለክታል ። ይህም በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ የሚታየውን የአመራረት ግብታዊነት የሚያስወግድና ለተመጣጠነ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መሳካት የሚረዳ የአሠራር ስልት ነው ።

## ማምረት
*(Production)*

በሥራ ኃይል በመጠቀም ተፈጥሮን ለውጦ የሰውን ልጅ ቁሳዊ ፍላጐት ለማርካት የሚችሉ ዕቃዎችን ወይም የምርት መገልገያዎችን መሥራት ማምረት ይባላል ። የዚህ የማምረት ሂደት ውጤት የሆኑት ዕቃዎች ወይም ቁሶች ደግሞ ምርት ይባላሉ ። ማምረት የሰው ልጅ ተፈጥሮን ለራሱ በሚጠቅመው መልክ የሚለውጥበትና በሂደቱም ውስጥ ራሱንም የሚያጐለብትበት እንቅስቃሴ እንደመሆኑ የማያቋርጥና ከሰው ልጅ ህል

ውና ጋር የተቆራኘ ተግባር ነው ። ስለዚህ ማምረት የኅብረተሰብ ህልውናም ሆነ ዕድገት መሠረት ነው ።

የሰውን ልጅ ቁሳዊ ፍላጐት ለማርካት የሚካሄደው የማምረት ሂደት በባሕሪው ምንጊዜም ማኅበራዊ ነው ። የማምረት ባሕርይ ማኅበራዊነት የሥራ ማኅበራዊነትን የሚያንፀባርቅ ነው ። ሰዎች በማምረት ተግባር ላይ የሚሰማሩት ከሌሎች ተገልለውና ተለይተው ሳይሆን ከሌሎች የኅብረተሰቡ አባሎች ጋር በመተባበርና በመተጋገዝ ነው ። ይህም በመሆኑ በማምረት ሂደት የአንድ ግለሰብ ሥራ ፍሬ ለመስጠት ወይም ውጤት ለማሳየት በሌሎች አያሌ ግለሰቦች ሥራ መሳካት የሚወሰን ነው ። ስለሆነም የአንድ ግለሰብ ሥራ ምንጊዜም ቢሆን የአጠቃላዩ የኅብረተሰቡ ሥራ ጥረት ግለትም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለኅብረተሰቡ ህልውና አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎችን የሚያመርተው የማኅበራዊ ሥራ አንድ ክፍል ነው ።

ማምረት ከክፍፍል ፣ ከልውውጥና ከፍጆታ ጋር የተቆራኘ ወይንም ከነርሱ ተነጥሎ ሊታይ የማይችልና በነርሱም ላይ የወሳኝነት ሚና ያለው ነው ። ምክንያቱም አንድ ነገር ሊለወጥ ፣ ሊከፋፈል ወይንም ለፍጆታ ሊውል የሚችለው ሲመረት ብቻ በመሆኑ ነው ። ከዚህ አንፃር ሲታይ ምርት መነሻ ነጥብ ሲሆን ፍጆታ መድረሻ ፣ ክፍፍልና ልውውጥ ደግሞ ሁለቱን የሚያገናኙ ናቸው ። ምርት ምንጊዜም ከክፍፍል ፣ ከልውውጥና ከፍጆታ ጋር ያለው ግንኙነት በስልተ ምርቱ ዓይነት የተለያዩ መልኮች ይኖሩታል ። ለምሳሌ በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ያለው አመራረት ፣ ክፍፍል ፣ ልውውጥና ፍጆታ በሶሻሊዝም ካለው አመራረት ፣ ክፍፍል ፣ ልውውጥና ፍጆታ የተለየ ነው ።

(ሥራን ይመለከቷል ።)

## ማምረቻ መሣሪያዎች (የ—)

*(Instruments of Production)*

ከምርት መገልገያዎች መካከል የሰዎች ፈጠራ የታከለባቸውና በምርት ሂደት ውስጥ ዋነኛ ስፍራ ያላቸው የፋብሪካ ማሽኖች ፣ የእርሻ መሣሪያዎችና የመሳሰሉት የማምረቻ መሣሪያዎች ይባላሉ ። ፍራፍሬን ከመሳሰሉት ከእጅ ሌላ የተለየ የማምረቻ መሣሪያ ከማይጠይቁት የምርት ዓይነቶች በስተቀር የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጐቶቹን ለማርካት ከሁሉም በፊት የማምረቻ መሣሪያዎች እንዲኖሩት ያስፈልጋል ። ስለሆነም የሰውን ልጅ ዕድገት ከማምረቻ መሣሪያዎች ዕድገት ለይቶ ማየት ያስቸግራል ።

የማምረቻ መሣሪያዎች የሰው ልጅ በተፈጥሮ ላይ ያለውን የበላይነትና የደረሰበትንም የዕድገት ደረጃ የሚያመለክቱ ናቸው ። ስለዚህም በኅብረተሰብ ዕድገት ታሪክ ውስጥ የተለያዩ ወቅቶችን ወስዶ አንዱን ከሌላው መለየት የሚቻለው በጊዜው በተመረተው የምርት ዓይነት ሳይሆን ኅብረተሰቡ በተጠቀመባቸው የማምረቻ መሣሪያዎች ዓይነት ነው ። ለምሳሌ በቆሎን ወይም ማናቸውንም የእርሻ ሰብል ዓይነት ብንወስድ ሰብሉ በእንጨት መቆፈሪያ ፣ በበሬ ወይም በሌሎች እንስሶች በሚጐተት ማረሻ ወይም በትራክተር ሊመረት ይችላል ፤ ሆኖም ከተመረተው ሰብል ዓይነት ይልቅ የተመረተበት የማምረቻ መሣሪያ ዓይነት ኅብረተሰቡ የሚገኝበትን የዕድገት ደረጃ ያመለክታል ።

## ማምረቻ ወጪ (የ—)

*(Cost Price of Production)*

ካፒታሊስቱ ለምርት መገልገያዎችና ለሥራ ኃይል መግዣ ያወጣው ካፒታል ወይንም የቋሚ ካፒታልና የተለዋዋጭ ካፒታል ድምር የማምረቻ ወጪ ይባላል ።

የማምረቻ ወጪ ከተመረተው ሸቀጥ ተረፈ እሴት መጠን ያንሳል ። ምክንያቱም ተረፈ እሴቱ ባልተከፈለ ወይንም በተበዘበዘው የወዝአደሩ ትርፍ የሥራ ጊዜ ስለሚመረት በካፒታሊስቱ የማምረቻ ወጪ ውስጥ ስለማይደመር ነው ። ለዚህም ነው ካርል ማርክስ አንድን ሸቀጥ ለማምረት በካፒታሊስቱ ወጪና በኅብረተሰቡ ወጪ መካከል ልዩነት አለ ያለው ። የካፒታሊስቱ ወጪ የሚለካው ባወጣው የካፒታል መጠን ሲሆን ሸቀጡን ለማምረት የወጣው የኅብረተሰቡ ወጪ የሚለካው ግን በፈጀው የሥራ ጊዜ መጠን ነው ።

የማምረቻ ወጪ ባጠቃላይ በቡርሺዚው ወጪ መልክ ስለሚታይና በቋሚና በተለዋዋጭ ካፒታል መካከልም ልዩነትን ስለማያሳይ ፣ የተረፈ እሴትንም ምንጭ የጠቅላላው ካፒታል ወጪ አድርጐ ስለሚያቀርብ በካፒታሊዝም ውስጥ ያለውን ብዝበዛ ይሸፍናል ።

## ማርሻል ፣ አልፍሬድ

*(Marshall, Alfred)*

ከ1842 - 1924 የኖረ ፣ በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ፕሮፌሰር የነበረና የካምብሪጅን ግልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አስተምህሮ የመሠረተ እንግሊዛዊ ኢኮኖሚስት ነው ። ማርሻል ስለኢኮኖሚክስ መሠረተ ሐሳቦች ፣ ስለ ኢንዱስትሪ ፣ ስለንግድና ስለገንዘብ ልዩ ልዩ መጻሕፍትን ጽፏል ። ካሳተማቸው መጻሕፍት መካከል በይበልጥ የታወቀለት “ፕሪንስፕልስ ኦቭ ኢኮኖሚክስ” የተሰኘው በ1890 የታተመው ነው ።

ማርሻል ራሱን የሪካርዶ ተከታይ አድርጐ ቢቆጥርም የሪካርዶን አስተሳሰብ የተረጐመው በተዛባ መንገድ ነው ። ስለ ማምረቻ ዋጋ ፣ ስለአቅርቦትና ፍላጐት ፣ ስለ ምርታማነትና ስለቁጠባ ከርሱ በፊት ተሰንዝረው የነበሩትን ግልብ ንድፈ ሐሳቦች በጊዜው በመስፋፋት ላይ ከነበሩት ተጨማሪ እርካታ ከተሰኘው ሐሳባዊ ንድፈ ሐሳብና ከተጨማሪ ምርታማነት ጋር በማያያዝ በተለይ ስለሸቀጦች ዋጋና ክፍፍል አወሳሰን የሰነዘራቸው አስተሳሰቦች በቡርሿ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ውስጥ እስካሁን ድረስ ከፍተኛ ቦታ ይዘው ይገኛሉ ።

እንደማርሻል አስተሳሰብ አቅርቦትና ፍላጐት በአንድነት የአንድን ሸቀጥ ዋጋ ይወስናሉ ። ክፍፍልንም በሚመለከት በካፒታሊስቱ ሥርዓት ሠራተኛው ፣ ባለካፒታሉ፣ ባለመሬቱና የማምረትን ተግባር የሚያደራጀው ለማምረት ተግባር በሚያደርጉት አስተዋጽኦ ልክ የአንድን የካፒታሊስት ድርጅት ገቢ በመካከላቸው ይከፋፈላሉ በማለት የካፒታሊስቱ ሥርዓት ከብዝበዛ ነፃ እንደሆነ ፣ በካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ መደቦች ጥቅማቸው የማይጋጭና ቅራኔም በመካከላቸው እንደሌለ አድርጐ ለማቅረብ ሞክሯል ።

የአዝጋሚ ዕድገት ንድፈ ሐሳብ የኅብረተሰብ ዕድገት የሚመራበት ብቸኛ ንድፈ ሐሳብ ነው በማለት ማርሻል ያምናል ። በዚህም ላይ በመመሥረት የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ያለ ውጣ ውረድ የሚያድግና ዘለዓለማዊነት ያለው ነው የሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ ሊሰነዝር ችሏል ።

## ማርክሲዝም

*(Marxism)*

ስለተፈጥሮ ፣ ስለኅብረተሰብና ስለሰው አስተሳሰብ በካርል ማርክስና በፍሬደሪክ ኤንግልስ የተቀነባበረውና የተቀመረው ሳይንሳዊ ንድፈ ሐሳብ ማርክሲዝም ይባላል ። ማርክሲዝም በሦስት ውሁድ ክፍሎች የተገነባ ሲሆን እነዚህም ማርክሳዊ ፍልስፍና ፣ ሳይንሳዊ ኮሚኒዝምና ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ናቸው ።

(ማርክስን ፣ ኤንግልስን ፣ ሌኒንን ፣ ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ፣ ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነትን ፣ ታሪካዊ ቁስአካልነትን ይመለከቷል ።)

## ማርክሲዝም ሌኒኒዝም

*(Marxism–Leninism)*

ፍልስፍናዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ አመለካከቶችን በተሟላና በተቀናጀ ሁኔታ የሚያጠቃልልና በማርክስ ፣ በኤንግልስና በሌኒን የተቀመረ አብዮታዊ አስተምህሮ ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ይባላል ። አስተምህሮው የሠራተኛውን መደብ መሠረታዊ ጥቅሞች የሚያንፀባርቅና የመደቡን ታሪካዊ ሚና ማለትም ኮሚኒዝምን ለመመሥረት የሚያስፈልጉ ንድፈ ሐሳባዊ መመሪያዎችንና ተግባራዊ ዕቅዶችን ያቀፈ ነው ።

ማርክስና ኤንግልስ ዲያሌክቲካዊና ታሪካዊ ቁስአካልነትን በመመሥረት በፍልስፍና ውስጥ አብዮታዊ የአመለካከት ለውጥ በማስከተላቸው ፣ ለፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሳይንሳዊ መሠረትና የአጠናን ዘዴ በመስጠታቸው፣ ለሶሻሊዝም አመሠራረት ሳይንሳዊ መንገድ በመቀየሳቸው የአስተምህሮው መሥራች ናቸው ። ሌኒን በበኩሉ የማርክሲዝምን አስተምህሮና የአጠናን ዘዴ በማዳበር በተለይም

ለዘመኑ ኢምፔሪያሊዝም ተስማሚ የሆነውን አብዮታዊ ንድፈ ሐሳብና የትግል ዘዴ በመ ቀየስና የሩሲያ ሶሻሊስት አብዮት መሪ በመ ሆን አስተምህሮውን በተግባር የተረጐመ በመሆኑ ይህ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አስተም ህሮውን ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ተብሎ እንዲ ጠራ አድርጐታል ።

(ማርክስን ፡ ኤንግልስን ፡ ሌኒንን ይመለከቷል ።)

## ማርክስ ፡ ካርል
*(Marx, Karl)*

ከ1818 — 1883 የኖረ ፡ የቁስአካላዊ ዲያሌክቲክስን ፍልስፍና፡ ሳይንሳዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚንና ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን ከፍሬደ ሪክ ኤንግልስ ጋር የቀመረና የመሠረተ ጀርመናዊ የዓለም ወዛደሮች መሪና መም ህር ነው ።

ካርል ማርክስ ከመካከለኛው ቡርዧ ቤተሰብ የመጣ ቢሆንም ገና ተማሪ ሳለ ተራማጅ ለሆኑ አስተሳሰቦች የተለየ ዝንባሌ ነበረው ። በጊዜው በሄግል ፍልስፍና ውስጥ ማለትም ወጣት ሄግልያውያን በሚባሉት ክፍ ሎች ይራመድ የነበረው የግራ አዝማሚያም ለማርክስ መንፈሳዊ ዕድገት አስተዋጽኦ ነበረው ። ይሁንና የሄግል ፍልስፍና በውስጡ ያስታራቂነት አዝማሚያዎችን በመያዙ ፡ ለወግ አጥባቂ ፖለቲካ ያጐበደደ በመሆኑ ፡ መርሆቹ ካሉት ነባራዊ ማኅበራዊ ግንኙነቶች የተገ ነጠሉ በመሆናቸውና በዚህም የተነሣ ተግ ባራዊ ተልዕኮ ሊኖራቸው ባለመቻሉ አመለካከ ታቸው ከማርክስ ተራማጅ አመለካከት ጋር ሊጣጣም አልቻለም ። በሌላም በኩል ማርክስ ከሱ በፊት በቁስአካላዊ ፍልስፍና ውስጥ (በፎ የርባኽም ጭምር) ይንፀባረቅ የነበረውን ዲበአ ካላዊ ጠባይ በሙሉ ቁስአካልነትን ከዲበአካ ላዊ ጠባይ ሙሉ በሙሉ አላቅቆታል ። በዚ ህም ጊሱ ሳቢያ ወደ ሳይንሳዊ ቁስአካላዊ አመለካከት ሊሸጋገር ችሏል ። ለዚህም ስለ ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ ዕድገቶችና በፎየር ባኽ ፍልስፍና ላይ ያካሄደው ጥናት ወሳኝ ሚና ተጫውቷል ። ባጠቃላይ ካርል ማር ክስ የሄግልን ዲያሌክቲክስና የፎየርባኽን ቁስአካልነት በመለወጥና በማዋሀድ የዲያሌ ክቲካዊና የታሪካዊ ቁስአካልነትን ፍልስፍና ቀምሯል ። ፍልስፍናውም በውስጡ ቁስአካ ልነትንና ዲያሌክቲክስን ፡ የተፈጥሮንና የኅብ ረተሰብን ቁስአካላዊ ግንዛቤ ፡ የኑባሬንና የዕውቀትን ግንኙነት ፡ የንድፈ ሐሳብንና የተግባርን አንድነት ያካተተ ሳይንሳዊ ፍልስ ፍና ነው ።

ካርል ማርክስ የአዲሱን ሳይንሳዊ አመ ለካከት ዋነኛ መርሆች በሚከተሉት ጽሑፎቹ ውስጥ አስፍሯቸዋል ። “ዘ ኢኮኖሚክ ኤንድ ፊሎሶፊካል ማኑስክሪፕትስ ኦቭ 1844” ፡ “ዘ ሆሊ ፋሚሊ” ፡ “ዘ ጀርመን አይዲኦ ሎጂ” ፡ “ዘ ፖቨርቲ ኦቭ ፊሎሶፊ” እና በተለይም በዝነኞቹ “የኮሚኒስት ማኒፌስ ቶና” “በካፒታል” ውስጥ አዲሱን ንጽረተ ዓለም ቀምሯል ።

በዚህም የማኅበራዊ ሕይወት መስክን አካቶ ያቀፈውን ዘላቂ የቁስአካልነት አጠቃ ላይ የዕድገት ንድፈ ሐሳብ የሆነውን ዲያሌክቲ ክስን ፡ የመደብ ትግልን ንድፈ ሐሳብና የእ ኩልነት ኅብረተሰብ መሥራች የሆነውን የወ ዛደሩን መደብ አብዮታዊ ፡ ዓለምአቀፋዊና ታሪካዊ ሚና ነድፎአል ። ማርክስ በሳይንሳዊ ንድፈ ሐሳብ አፍላቂነቱ ብቻ የተወሰነ ሳይ ሆን ለወዛደሩ መደብ ታሪካዊ ተልዕኮ እውነትነት በግንባር ቀደምትነት በመሰለፍ ታግሏል ። በ1848ቱ የቡርዧ አብዮት ልም ድና በመጀመሪያው የወዝአደሩ መንግሥት በፓሪስ ኮሚዩን ልምድ ጥናት ላይ በመመር ኮዝ “ክሪቲክ ኦቭ ዘ ጐታ ፕሮግራም” በሚለው ጽሑፉ የሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን ንድፈ ሐሳብ የበለጠ አዳብሯል ። ዋነኛ ትኩረቱንም በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መስክ ላይ በማድረግ መላ ሕይወቱን ለዚሁ ተግባር በማዋል በሦስት ቅጽ የተጠቃለለውን “ካፒታል” የተባለውን ታላቅ ሥራ አበርክ ቷል ። በዚህ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሥራውም ካፒቲሊዝምን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በመ ኀስ የወዛደሩን መደብ ንቃተ ኅሊና በማሳ ደግና በማዳበር ለወደፊቱ የኮሚኒስት ሥርዓት ግንባታ ሳይንሳዊ መሠረተ ጥሏል ። በተጨማሪም በዚሁ ሥራው ውስጥ የዲያሌክ ቲካዊ ምርምር ዘዴን በመከተልና የታሪክን ቁስአካላዊ ግንዛቤ ፍሬ ነገር በማንፀባረቅ የፍ ልስፍናውን መሠረተ ሐሳቦች ትክክለኛነት በተግባር አሳይቶበታል ። ባጭሩ ማርክስ በካፒ ታል ሥራው የፍልስፍና መሠረታዊ ንድፈ ሐሳቦች ከመላምትነት ወደ ሳይንስነት እንዲ

ለወጡ አድርጓል ። የእስከ ዛሬውም ታሪካዊ ልምድ እንዳሳየው የማርክስ ርዕዮተዓለም ብቃት ያለው የዓለም መገንዘቢያና የመለወጫ መሣሪያ መሆኑን በተግባር በማስመስከር የማርክስን ሥራ ሕያውነት አረጋግጧል ።

(ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነትን ይመለከቷል ።)

## ማሽን ምርት (የ—)

*(Machine Production)*

የማሽን ምርት በመፈብረክ ደረጃ ያደገ በካፒታሊስት አመራረት ሦስተኛው የዕድገት ደረጃ ነው ። በዚህ ደረጃ ሽቀጥ የሚመረተው በእጅ በሚንቀሳቀሱ መሣሪያዎች ሳይሆን በሞተር ኃይል በሚንቀሳቀሱ የማምረቻ መሣሪያዎች ነው ። ይህ የአመራረት ዘይቤ የሥራ ክፍፍል በከፍተኛ ደረጃ የተስፋፋበት ከመሆኑም በላይ ለካፒታሊዝም ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት በመጣል የካፒታሊስት ስልተ ምርት በፊውዳሉ ስልተ ምርት ላይ የበላይነትን እንዲጐናፀፍ ረድቷል ።

ማርክስ እንዳመለከተው አንድ ዘመናዊ የሆነ ማሽን ሦስት ክፍሎች አሉት ። እነሱም አንቀሳቃሽ የሆነው ሞተር ፣ የኃይል ማስተላለፊያውና የማምረቻ መሣሪያው ክፍሎች ናቸው ። የማምረቻ መሣሪያው የማሽን አመራረት ዋንኛው ክፍል ሲሆን ይህ ክፍል የሥራ ተገብሮችን በመለወጥ በሥራ ኃይል አማካይነት ሸቀጡ የሚመረትበት ክፍል ነው።

በዚህ መሠረት የተቋቋመው የካፒታሊስት ፋብሪካ ከፍተኛ ዘመናዊ የምርት ድርጅት ሲሆን የተመሠረተውም በተለያዩ ማሽኖች ቅንብር ነው ። በአሁኑ ወቅት የማሽን አመራረት የተለያዩ ክፍሎች በሳይንስና በቴክኖሎጂ ዕድገት ምክንያት በከፍተኛ ደረጃ እየዳበሩ መጥተዋል ። የአውቶሜሺን መስፋፋት ለማሽን አመራረት ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ሦስት ክፍሎች በተጨማሪ አራተኛ ክፍል እንዲጨምር አድርጓል ። ይኸውም የቁጥጥርና የቅንጅት ክፍል ነው ። በአሁኑ ወቅት የማሽን አመራረትን በይበልጥ የሚቆጣጠሩት ለዚሁ ተግባር የተሠሩ የተለዩ መሣሪያዎች ናቸው ።

የማሽን ምርት እዚህ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ ቢደርስም የሠራተኛውን ወሳኝ ሚና ሊተካ አልቻለም ። እንዲያውም ሥራ ይበልጥ ውስብስብ እየሆነና የሠራተኛውም ምርታማነት እያደገ መጥቷል ። ሠራተኛው የምርቱን ሂደት ፣ የማምረቻ መሣሪያዎቹ በትክክል መሥራት አለመሥራታቸውን ይቆጣጠራል ። የመሣሪያዎችን የተዛባ አሠራርና ብልሽት ወዘተ... ያስተካክላል ።

የማሽን አመራረት ከፍተኛው የካፒታሊስት የሥራ አደረጃጀት መልክ ነው ። በዚህ ደረጃ በካፒታልና በሥራ ኃይል መካከል ያለው ቅራኔ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ይደርሳል ። የካፒታሊስት የማሽን አመራረት በሂደተ ምርት ውስጥ ማሽንና ሠራተኛው በተፃራሪነት እንዲቆሙና ሠራተኛው የማሽኑ ተገዥ እንዲሆን ያደርጋል ። በካፒታሊስት ሥርዓት ማሽን ሠራተኞችን በከፍተኛ ደረጃ ለመበዝበዝና ለካፒታሊስቶች ከፍተኛ ተረፈ እሴት ለማስገኘት የሚረዳ ነው ።

(መፈብረክን ፣ የኢንዱስትሪ አብዮትን ይመለከቷል ።)

## ማኦ ትሴ-ቱንግ

*(Mao Tse–tung)*

ከ1893—1976 የኖረ ፣ ከገበሬ ቤተሰብ የተወለደ የኮሚኒስት ቻይና መሥራች ነበር ።

ማኦ ራሱ እንደሚናገረው አስተሳሰቡን በማርክሳዊ ፍልስፍና ያጠናከረው በ1920 ሲሆን በዚሁ ጊዜ “ኮሚኒስት ማኒፌስቶን” እንባበ ከሌሎች ጋር ተወያይቶበታል ። በዚህም ዓላማ በመነሣሣት በቻይና ልዩ ልዩ ከተሞች በመዘዋወር ከማነቃቃቱም በላይ የሺክ የማዕድን ሠራተኞችን አድማ በዝግጅት ረድቷል ።

ማኦና ሌሎችም ታጋዮች ቻይናን ከነበረችበት የከፊል ቅኝ ግዛት ቀንበርና ከኋላ ቀርነት አላቆ ወደተሻለ የዕድገት ደረጃ ለማድረስ በነበራቸው ዓላማ መሠረት የኮሚኒስት ፓርቲን አመራር አስፈላጊነት የተገነዘቡ ነበሩ ። በመሆኑም በ1919 ቤጂንግ ውስጥ በፈረንሳይ ለጋሲዮን በሚገኘው የሴቶች ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ተሰብስበው የቻይናን ኮሚኒስት ፓርቲ መሠረቱ ።

ከ1927 ጀምሮ ማኦ በገጠር ውስጥ ከገበሬዎች ጋር በመተባበር የደፈጣ ውጊያውን ማካሄድ ጀመረ ።

ኮሚኒስት ፓርቲው በነፃ አውጭው ጦር ብዙ ክፍላተ ሀገርን ነፃ በማውጣት በአብዮቱ ኃይሎች ቁጥጥር ሥር አዋለ ። ከዚሁ ጋርም ነፃ በወጡት መንደሮችና ከፍሎች የጤናና የትምህርት አገልግሎት እንዲያገኙ ባለሙያዎችን በማሰማራት የገጠሩን ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ያልተቆጠበ ጥረት በማድረጉ የሕዝቡን ድጋፍና ንቁ ተሳትፎ ለማግኘት ችሏል ። በዚህ ከፍተኛ የለውጥ ግስጋሴ በመደናገጥም ቻንግ ካይ ሼክ ሕዝባዊውን ትግል በኃይል ለመግታት ብዙ ሙከራ አድርጓል ። ነፃ የወጡትን አካባቢዎች በወታደሮች በማስከበብ ስንቅና ትጥቅ እንዳይደርሳቸው ለማድረግ ባይሳካለትም ተደጋጋሚ እርምጃዎችን ወስዷል ።

ከዚህ የተነሣ በ1934 ሕዝባዊው ነፃ አውጭ ጦር (ቀይ ጦር) ለትጥቅ ትግሉ ስትራቴጂያዊ ይዞታውን ለማጠናከር በወሰደው እርምጃ በመላው ዓለም ተደናቂነትን ያገኘውንና ''ረጅም ጉዞ'' (1934—35) የተሰኘውን የእግር ጉዞ ጀመረ ። በዚህም በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ ሴት ፣ ወንድ ፣ ሕፃን ፣ ሽማግሌ ሳይል ጓዙን ይዞ ሌትና ቀን 3,000 ማይልስ በችግርና የጠላትን ጥቃት እየተከላከለ ብዙ ጉዳት ከደረሰበት በኋላ ሞንጐሊያ አጠገብ ሻንሲ ከምትባል ክፍለ ግዛት ደረሰ ። በጉዞውም ወቅት ከፍተኛ የፕሮፓጋንዳ ሥራ ከመሠራቱም በላይ በትጥቁም ትግል ድሎች ተገኝተዋል ። ከዚሁ ጉዞ መጨረሻ እስከ 1947 ድረስ ማኦ ትግሉን የመራው በዚሁ ክፍለ ግዛት ውስጥ ካለው ከዩናን ሆኖ የደፈጣ ውጊያውንና ሀገሪቱን ነፃ የማውጣቱን ተግባር መምራት ቀጠለ ።

በዚህ ወቅት የጃፓን ጦር ቻይናን መውረር ጀምሮ ስለነበር ማኦ ከቻንግ ካይ ሼክ ጋር ግንባር ፈጥሮ በሀገራቸው ላይ የተነሣውን ጠላት ለመዋጋት ተነሣ ። በትብብሩ መሠረት ኮሚኒስት ፓርቲውና ኮሚንታንግ ለተወሰነ ጊዜ በአንድ ላይ ሆነው ጃፓኖችን ቢወጉም ትብብሩ እስከመጨረሻው ሊቀጥል አልቻለም ። ኮሚኒስት ፓርቲው በዚህ ጊዜ በአንድ በኩል የጃፓን ወራሪዎችን እየተዋጋ ሲያባርር በሌላ ወገን ደግሞ በየደረሰበት መንደር መሬት ለድሀ ገበሬዎች በማከፋፈልና ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችን በማካሄድ መላ ሀገሪቱን ነፃ የማውጣቱን ተግባር ተያያዘው ። ይህንን የተረዳው ቻንግ ካይ ሼክም ኮሚኒስት ፓርቲውን ለማዳከምና ከተቻለውም ለማጥፋት እያሌ ዘመቻዎች ቢያደርግም አብዮቱ ሴራውንና ጥቃቱን ሁሉ እየደመሰሰ ወደፊት ገፋ ። በመጨረሻም በ1949 ማኦና ተከታዮቹ በድል አድራጊነት ቤጂንግ በመግባት ቻንግ ካይ ሼክን ዛሬ ታይዋን ወደምትባለዋ የቻይና ደሴት አባረው ሥልጣን በመያዝ ቻይናን በሶሻሊስት የዕድገት ጐዳና መምራት ጀመሩ ።

የማኦ ትሴቱንግ ሕይወት የቻይና ሕዝብ ከአካሄደው ረጅም አብዮታዊ ትግል ጋር በጥብቅ የተቆራኘ በመሆኑ በቻይና ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ አለው ። ማኦ በኮሚኒስት ፓርቲው አማካይነት ለትግሉ አመራር በመስጠት ብቻ ሳይወሰን ስለደፈጣ ውጊያ ስልት ፣ ስለ አዲሱ ዲሞክራሲ ፣ ስለቅራኔ ፣ ስለተግባር ወዘተ... ጽሑፎችን አቅርቧል ። ይሁንእንጂ እያደር ከማርክሲዝም ሌኒኒዝም ጋር የማይጣጣም አስተሳሰብ በመሰንዘሩና በተግባርም የሶሻሊስቱን ጎራ ለመከፋፈል በመሞከሩ ከየአቅጣጫው ነቀፌታ ተሰንዝሮበታል ።

## ማዕቀብ
*(Sanction)*

የፖለቲካና የኢኮኖሚ እገዳ ሲሆን ሕጋዊ በሆነ የውሳኔ ኃይል ተጠቅሞ አንድን ሰው ፣ ሀገር ወይም ተቋም ከያዘው አፈንጋጭ አስተሳሰብ ወይም ድርጊት እንዲመለስ ፣ የሚጠበቅበትን መሥመር እንዲከተል ወይም ለትክክለኛው ሕግ ተገዥ እንዲሆን ለማድረግ በፖለቲካና በኢኮኖሚ እገዳ አማካይነት የሚወሰን ቅጣት ነው ። ይህ ዓይነቱ ቅጣት በተለይ የሚጣለው ዓለም አቀፋዊ ውሳኔዎችን በማያከብር ወገን ላይ ሲሆን በሙሉ ተፈጻሚነት ሊያገኝ የሚችለው የውሳኔው ደጋፊዎች ቅጣቱ ከተጣለበት ወገን ጋር ያላቸውን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ግንኙነት ሲያቋርጡና እንዲሁም ሕገወጥ ድርጊቱን በማንኛውም በታና ጊዜ በማጋለጥና በማውገዝ ሲተባበሩ ነው ።

## ማኪያቬሊ ፣ ኒኮሎ ዲ ቤርናርዶ
*Machiavelli, Niccolo di Bernardo*

ከ1469 እስከ 1527 የኖረ የታዳጊውን የቡርዧ ርዕዮተዓለም ያንፀባረቀ ኢጣሊያዊ ፖለቲከኛና ፈላስፋ ነው።በማኪያቬሊ አመለካከት የኅብረተሰብ ዕድገት የሚወሰነው በእ

ግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን በተፈጥሮአዊ ምክንያቶች ሲሆን የታሪክ ግፊት ኃይሎችም ቁሳዊ ጥቅምና የሥልጣን ፍላጐት ናቸው ። ይህም በመሆኑ በተራው ሕዝብና በገዥ መደቦች መካከል አይቀሬ የሆነ የጥቅም ግጭት አለ ሲል ተናግሯል ። እንደማኪያቬሊ አስተሳሰብ ገዥው መደብ የበላይነቱን መጠበቅ የሚችለው ከፊውዳል መኳንንት የእርስ በእርስ ግጭት ተላቆ ብሔራዊ መሠረት ያለው ሥልጣን ሲመሠርት ነው ። በፖለቲካ ትግል ውስጥ ቁም ነገሩ አሸናፊ ሆኖ መገኘት በመሆኑ የፖለቲካ ሰው ይህን ውጤት ለማግኘት በማንኛውም ዘዴ (ውሸት ፣ ጭካኔ ወዘተ . . . ) መጠቀም አለበት በማለት ፖለቲካን ከግብረገባዊ አመለካከት ውጭ ለማድረግ ጥሯል ። በመሆኑም የማኪያቬሊ ታሪካዊ አስተዋጽኦ መንግሥትን መሆን ካለበት ሳይሆን በእውንነቱ ለመመለከት ያደረገው ሙከራ ነው ።

## ማዟዟሪያ ወጪ (የ—)

*(Cost of Circulation)*

በካፒታሊስት ኢኮኖሚ የንግድ ዘርፍ ውስጥ ሸቀጦችን ወደ ገንዘብ ለመለወጥ በሚደረገው የንግድ ሥራ የሚወጣው ወጪ የማዟዟሪያ ወጪ ተብሎ ይጠራል ። ይህ ወጪ ሸቀጦች ወደ መጨረሻው ተጠቃሚ ዘንድ እንዲደርሱ ያስችላል ። የንግድ ካፒታሊስቱም በሸቀጡ ውስጥ የተጠናቀረውን ተረፈ እሴት ወደገንዘብ በመቀየር ጥቅሙን እንዲያገኝ ያስችለዋል ።

የንግድ ካፒታሊስቱ ሸቀጦቹን ለተገልጋዮች ለማቅረብ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ ሁለት ዓይነት የማዟዟሪያ ወጪዎች አሉ ። እነርሱም ተጨማሪ የማዟዟሪያ ወጪ እና የተጣራ ወይም ንጹህ የማዟዟሪያ ወጪ ናቸው ።

(ተጨማሪ የማዟዟሪያ ወጪን ፣ የተጣራ የማዟዟሪያ ወጪን ይመለከቷል ።)

## ሜርካንቲሊዝም

*(Mercantilism)*

ሜርካንታይል ማለት ንግድ ወይም የንግድ እንቅስቃሴ ማለት ሲሆን ሜርካንቲሊዝም ደግሞ በተራ ትርጉሙ በንግድ ላይ የሚያተኩር አመለካከት ማለት ነው ።

የሜርካንቲሊዝም የኢኮኖሚ አመለካከት ሁለት ገጽታዎች አሉት ። እነዚህም አንደኛው የኢኮኖሚ ንድፈ ሐሳብ ፣ ሌላው ደግሞ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በመሆን ከ15ኛው እስከ 18ኛው ምዕት ዓመት ድረስ በተለያዩ የአውሮፓ ሀገሮች በተግባር ላይ የዋሉ ናቸው ።

በኢኮኖሚ ንድፈ ሐሳብ ገጽታው ሜርካንቲሊዝም ለቡርዧው ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ቅድመ መነሻ የሆነ ፣ ንግድ በዓለም ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ ተስፋፍቶ በነበረበት ወቅት የአውሮፓ መንግሥታት በወቅቱ ለነጋዴዎች እንዲስማሙ ላወጧቸው የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች የንድፈ ሐሳብ ድጋፍ ለመስጠት የተነሣ የኢኮኖሚ አመለካከት ነው ። ከዚህም በመነሣት በፖሊሲነቱ መንግሥታት በአጠቃላይ በኢኮኖሚና በተለይም በንግድ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ጣልቃ እየገቡ ለብሔራዊ ቡርዧዚ ዕድገት ሁኔታዎችን የሚያመቻቹበት ስልት ነው ።

የሜርካንቲሊዝምን የኢኮኖሚ ንድፈ ሐሳብ በማስፋፋቱ ረገድ ከታወቁት የእንግሊዝ ኢኮኖሚስቶች መካከል ቶማስ መን (1571—1641) የተባለው ዋንኛው ነው ። ንድፈ ሐሳቡን ወደ ኢኮኖሚ ፖሊሲነት በመተርጐም በተግባር ላይ ያዋሉት አብዛኞቹ የአውሮፓ ሀገሮች ቢሆኑም የሜርካንቲሊዝምን የኢኮኖሚ ፖሊሲ በመንደፍና በዚህ በሚገባ በመጠቀም የታወቀው ደግሞ በ17ኛው ምዕት ዓመት የነበረው የፈረንሳይ የገንዘብ ሚኒስትር ኮልበር ነው ።

ሜርካንቲሊዝም ሸቀጦች የሚመረቱበትን ሂደትና ይኸውም ሂደት የሚገዛበትን መሠረታዊ ሕግ ወደጐን ትቶ በሸቀጦች ሂደተ ዝውውር ላይ ብቻ የሚያተኩር ነው ። ትንተናውም በአንድ ሀገር ውስጥ ሊጠራቀም በሚችለው በወርቅ ፣ በብርና በከበሩ ማዕድናት ክምችት ላይ የተመሠረተ ሲሆን የኢኮኖሚ ሕጐቹም የተመሠረቱት በንግድና በገንዘብ ልውውጥ ፣ በአጠቃላይም በሸቀጦች የዝውውር ሂደት ውስጥ ነው ከሚል የኢኮኖሚ ግምገማ የሚነሣ ፣ ገንዘብ በብዛት በንግድ መስክ መሰራጨት በጀመረበት ወቅት ገና የነበረ የኢኮኖሚ አመለካከት ነው ። በሜር

ካንቲሊዝም ወቅት በሀገር አቀፍ ደረጃ ገንዘብ በብዛት በማከማቸቱ ሂደት መንግሥት ከፍተኛ ሚና ስለነበረው ሜርካንቲሊዝም በሌላ ገጽታው መንግሥት በኢኮኖሚ ውስጥ ጣልቃ በመግባት የሀገር ውስጥ ነጋዴዎችን ከውጭ ውድድር ለመከላከል እንዲረዳ ያደረገ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ነበር ።

ሜርካንቲሊዝም በተለይ በኢኮኖሚ ንድፈ ሐሳብነቱ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን የንግድ ተመጣጣኝነትን እንደሚያጠና ሳይንስ አድርጐ የሚመለከት ፣ ሀብት ሲባል ወርቅና ነሐስ ማለት እንደሆነ አድርጐ የሚተረጉምና ገንዘብንና ካፒታልን አንድ እንደሆኑ አድርጐ የሚወስድ አመለካከት ነው ። ሜርካንቲሊስቶች የአንድ ሀገር የሀብት ምንጭ ነው ብለው የሚያመለክቱት የከበሩ ማዕድናትን መሆኑም ከዚህ የተነሣ ነው ። ስለሆነም የመጀመሪያዎቹ ሜርካንቲሊስቶች ወርቅና ነሐስ በተለያዩ መንገዶች ከውጭ ወደ ሀገር በብዛት እንዲገቡና ከሀገር ውስጥም እንዳ ይወጡ ይከላከሉ ነበር ። ይህንንም የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ በመንግሥት የአስተዳደራዊ እርምጃዎች (ተፅዕኖ) ይጠቀሙ ነበር ። የኋለኞቹ ሜርካንቲሊስቶች ደግሞ የአንድን ሀገር የወጪ ንግድ ከገቢው ንግድ በማበላለጥ የሀብት ምንጭ ነው ብለው የሚያምኑበት ወርቅና ብር መካበት አለበት ይላሉ ። የወጪ ንግድንም ለማስፋፋት በመንግሥት የአስተዳደራዊ እርምጃዎች በቀጥታ ከመጠቀም ይልቅ ወደ ውጭ የሚላኩ ዕቃዎችን ለሚያመርቱና ይህንንም ወደ ውጭ ለሚልኩ ድርጅቶች ተስማሚና አመች የሆነ የኢኮኖሚ ሁኔታ መፍጠርን ይመርጣሉ ። የሜርካንቲሊዝም የኢኮኖሚ አመለካከት መሠረታዊ ድክመት ሀብት ከምርት መስክ የሚገኝ ሳይሆን በሂደተ ዝውውር ውስጥ እንደሚፈጠር አድርጐ መውሰዱና የኢኮኖሚ ግንኙነቶችን በዚሁ አንፃር መመልከቱ ነው ።

## ሜንሼቪኮች
*(Mensheviks)*

የሩሲያ ማኅበራዊ ዲሞክራያዊ ሌበር ፓርቲ በ1903 ሁለተኛ ጉባኤውን ባደረገበት ጊዜ ከሁለት ተከፈለ ። በፓርቲው ማዕከላዊ አካሎች ምርጫ አብዛኛውን ድምፅ ያገኘውና በሌኒን የተመራው አብዮታዊ ክንፍ ቦልሼቪክ (ብዙኀን) ሲባል ፣ አነስተኛ ድምፅ ያገኘውና በማርቶቭ የተመራው አድኃሪ ክንፍ ሜንሼቪክ (ንዑሳን) ተባለ ።

ከ1905 እስከ 1907 ባለው የሩሲያ አብዮት ወቅት ሜንሼቪኮች የወዛደሩን መሪነት ፣ የአርሶአደሩን አጋርነት እንዲሁም የቡርዧው ዲሞክራሲያዊ አብዮት ወደ ሶሻሊስት አብዮት ለመሸጋገር መቻሉን ተቃውመዋል ። በተጨማሪም ለዘብተኛውን ቡርዧዚ የአብዮቱ መሪ ለማድረግና ወዝአደሩ ከቡርዧዚው ጋር ስምምነት እንዲፈጥር አብዮቱ በቁሳሩ መንግሥት ከተመታ በኋላም አብዛኛዎቹ ሜንሼቪኮች በኅቡእ የሚሠራውን አብዮታዊ ፓርቲ ለመበታተንና በጠጋኝ የቡርዧ ፓርቲ ለመተካት ጥረዋል ። በአንደኛውም የዓለም ጦርነት ጊዜ ሜንሼቪኮች የማኅበራዊ ትምክህተኝነት አቋም ፖሊሲ በመያዝ የኢምፔሪያሊስቶችን ጦርነት ደግፈዋል ። በመጨረሻም ከቦልሼቪኮች ጋር በአብዮት ጉዳና ጨርሶ ለመጓዝ የማይችሉ በመሆናቸው በጥር 1912 በፕራግ በተደረገው የፓርቲው ስድስተኛ የመላ ሩሲያ ስብሰባ ላይ ከፓርቲው ተወግደዋል ።

የየካቲት 1917 የቡርዧው ዲሞክራሲያዊ አብዮት ድል ካደረገ በኋላ ሜንሼቪኮች የቡርዧው ጊዜያዊ መንግሥት አባል በመሆን የመንግሥቱን ኢምፔሪያሊስታዊ ፖሊሲ በመደገፍ ለሶሻሊስት አብዮት የሚደረገውን ዝግጅትና ትግል ተፃርረዋል ። ከጥቅምቱ ሶሻሊስት አብዮት በኋላም ሜንሼቪኮች በግልጽ ፀረ አብዮት ፓርቲ በመሆን የሶቭዬትን ሥልጣን ለመገልበጥ በታለመው ሴራና አመፅ ተካፍለዋል ። በዚሁ ሁሉ ግን ሜንሼቪኮች ለሶሻሊዝም የሚደረገውን የትግል ሂደት ሊገቱ አልቻሉም ።

(ቦልሼቪክን ይመለከቷል ።)

## ሜይ ዴይ
*(May Day)*

የዓለም ሠራተኞች "የሁሉም ሀገር ሠራተኞች ተባበሩ!" በሚለው የወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት መርሀ መሠረት መብታቸውንና ጥቅማቸውን ለማስከበር በዓለም

አቀፍ ኢምፔሪያሊዝምና በአድኀሮት ኃይሎች ላይ ትግላቸውን ፣ መደባዊ አንድነታቸውንና የጋራ ዓላማቸውን የሚገልጹበት ቀን ነው ።

ወዝአደሮች ካፒታሊስቶች ይፈጽሙባቸው የነበረውን አሰከፊ ብዝበዛ በተለያዩ መንገዶች ሲታገሉ ቆይተዋል ። በ1856 የአውስትራሊያ ወዝአደሮች የሥራ ሰዓት በቀን ከ8 ሰዓት እንዳይበልጥ የሚልና ሌሎችም የማሻሻያ ጥያቄዎችን አቀረቡ ። ሌሎችም ይህንኑ ፈለግ በመከተል ልዩ ልዩ ውሳኔዎችን በማስተላለፍ የጋራ አቋማቸውን አጠናከረዋል ። በመሆኑም ከ1880ዎቹ ዓመታት በኋላ የአሜሪካና የአውሮፓ ወዝአደሮች አድማና አመፅ በተናጠል በፋብሪካዎች አካባቢ መወሰኑ ቀርቶ በተቀነባበረ ጥሪ እየዳበረና መደባዊና ድርጅታዊ ይዘቱም እየጐላ ሊመጣ ችሏል ።

በዚህ ሂደት የወዝአደሩ ትግሎች የተፋፋሙት በተለያዩ ቦታዎች ቢሆንም በተለይ በሜይ መጀመሪያ በ1886 የኢንዱስትሪ ከምችት በነበረበት የአሜሪካ መካከለኛ ምዕራብ ከተማ በቺካጐ የተደረገው የሥራ ማቆም አድማ ከፍተኛው ነበር ።በመሆኑም በሠራተኛው መደብ አመፅ የተደናገጡት ቡርዧዚዎች ባላቸው መንግሥታዊና ወታደራዊ ኃይል በመጠቀም በወዝአደሩ ላይ ገደብ የለሽ ጭፍጨፋ አካሄዱ ፤ ከቺካጐ የሠራተኛው ማኅበር ንቅናቄ መሪዎችም አራት ግንባር ቀደም ታጋዮችን ሰቀሉ ፤ ሌሎችንም ለሥቃይና ለእሥራት ዳረጓቸው ።

ይሁን እንጂ የካፒታሊስቶቹ የአፈና ጥረት የሠራተኛውን መደብ ሊገታው አልቻለም ። እንዲያውም ትግሉ እየተጠናከረ ሄዶ በ1888 የአሜሪካ ሠራተኞች ፌዴሬሽን በሴንት ሉዊስ ከተማ ተሰብስቦ ለስምንት የሥራ ሰዓት በተጀመረው ትግል ሊገፋበት ከመወሰኑም በላይ በ1890 የሥራ ቀን እንዲያጥር የሚጠይቅ የሠራተኛው ሀገር አቀፍ አድማ ተመታ ።

ሐምሌ 14 ቀን 1889 በፓሪስ ውስጥ የሠራተኛውና የሶሻሊስት እንቅስቃሴ በአንደኛው ኢንተርናሽናል መፍረስ የደረሰበትን የመሪ ድርጅት እጦት ለማስወገድ የተደረገው የሁለተኛው ኢንተርናሽናል የሠራተኞች ድርጅት መመሥረቻ ጉባኤ ቀደም ሲል የተደረጉትን የሠራተኛውን ትግሎች በማውሳትና በተለይም የሴንት ሉዊስን ውሳኔ በመደገፍ ሜይ አንድ ቀን 1890 ሊደረግ የታሰበው የሠራተኛው አቋም መግለጫ በዓለም አቀፋዊ ስልፍ እንዲደገፍና የየሀገሩ ሠራተኞች እንደየተጨባጭ ሁኔታቸው የትግል አንድነታቸውን እንዲያንፀባርቁ ውሳኔ አስተላለፈ ። ከዚያ ወዲህ ሜይ ዴይ በአውሮፓና በአሜሪካ የወዝአደር ቀን ሆኖ መከበር ቀጠለ ።

ከዚያ በተከታታይ በተከበሩ የሜይ ዴይ በዓላት የሠራተኛው ጥያቄ እየሰፋና ይበልጥም መደባዊ ይዘቱ እየጐላ መጣ ። ምንም እንኳ በሁለተኛው ኢንተርናሽናል ሂደት ውስጥ የታዩት ውጣ ውረዶች በዚህም በዓል አከባበር ባሕርይ ላይ ተፅዕኖ የነበራቸው ቢሆንም ሜይ ዴይ ከሠራተኛውም መደብ የትግል ዕድገት ጋር እየተጠናከረ ዛሬ የዓለም ሠርቶ አደር ሕዝቦች የዓለም አቀፍ ትግላቸውን ዓላማ የሚያሳውቁበት ፣ ክንዳቸውን የሚያስተባብሩበት ዋነኛ መድረክ ለመሆን በቅቷል።

ሜይ ዴይ በካፒታሊስት ሀገሮች ጐልቶ እንዳይከበር ፣ ወይም ተድበስብሶ እንዲቀርብ ካፒታሊስቶች በልዩ ልዩ ረቂቅ ዘዴዎች ይጠቀማሉ ። ሶሻሊስትና ተራማጅ ኃይላት ሥልጣን በያዙባቸው ሀገሮች ግን ቀኑ በብሔራዊ ደረጃ በከፍተኛ ድምቀት ይከበራል። ለምሳሌ በኢትዮጵያ እንደ ኢት. አ. ጥር 2 ቀን 1967 ሜይ ዴይ ከሀገሪቱ ብሔራዊ በዓላት አንዱ እንዲሆን ከተወሰነ ወዲህ በታላቅ ድምቀትና ስሜት በየዓመቱ ይከበራል ።

## ምሁራን

(*Intelligentsia*)

ዶክተሮችን ፣ መሐንዲሶችን ፣ የሕግ ሰዎችን ፣ ኢኮኖሚስቶችን ፣ ከያንያንን ፣ ደራስያንን ፣ መምህራንንና የመሳሰሉትን በአእምሮ ሥራ ላይ የተሰማሩትን የሚይዝ የኅብረተሰብ ክፍል ነው ። በካፒታሊስቱ ኅብረተሰብ ውስጥ ምሁራን ራሱን በቻለ የተለየ መደብ የሚጠቃለሉ ሳይሆኑ ከተለያዩ መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ፣ በሠለጠኑበት ሙያ ዕውቀታቸውን በመሸጥ የሚኖሩ ናቸው ።

የቡርዧው ምሁራን ከፍተኛው ክፍል በኑሮ አቋሙም ሆነ በአስተሳሰቡ ብዙውን ጊዜ ከገዥ መደቦች ጋር የሚጣመር ነው ። በካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የመደብ ትግል እየተስፋፋና እየከረረ ሲሄድ አብዮታዊ ምሁራን ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን በመቀበል ከሠራተኛው መደብ ጐን ተሰልፈው ንቁ የትግል ተሳትፎ ሲያደርጉ ፥ አድኃሪዎቹ ግን ለካፒታሊስት ሥርዓት ጥብቅና በመቆም አብዮታዊውን እንቅስቃሴ ይወጋሉ ። አብዮታዊ ምሁራን በአብዮታዊ ትግል ውስጥ የሚኖራቸው ከፍተኛ ሚና በሶቪዬት ኅብረትና በሌሎች ሶሻሊስት ሀገሮች እንዲሁም እስከዛሬ በፀረ ኢምፔሪያሊዝም የብሔራዊ አርነት ንቅናቄ ውስጥ ባደረጉት ንቁ ተሳትፎና በሰጡት አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ አመራር በግልጽ ታይቷል።

በካፒታሊስት ሀገሮች ዛሬ ምሁራኑ በቁጥር እያደጉ ቢሄዱም በኅብረተሰቡ ውስጥ ቀድሞ የነበራቸው ቦታና የኑሮ ደረጃ ግን በማሽቆልቆል ላይ ይገኛል ። ምሁራን በምርት ቦታና በመንፈሳዊ ተቋሞች ሁሉ አገልግሎታቸውን የሚሰጡ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ በካፒታሊስት ሀገሮች እንደሚታየው የቀድሞውን ጥቅምና ሥራቸውን አጥተው በኑሮ ሁኔታቸው ወደሠራተኛው መደብ እየተቃረቡ በመሄድ ላይ የሚገኙት ቁጥራቸው በየጊዜው ሲጨምር እንጂ ሲቀንስ አይታይም ።

## ምርታዊ ሥራ ፥

*(Productive Labour)*

በአንድ ኢኮኖሚ ውስጥ ቁሳዊ ሀብት ለማምረት የዋለ ሥራ ምርታዊ ሥራ ይባላል ። ይህም የምርት መገልገያዎችንና የፍጆታ ዕቃዎችን ለማምረት የዋለን ሥራ ያጠቃልላል ። ምርታዊ ሥራ በኢንዱስትሪ ፥ በእርሻ ፥ በኮንስትራክሽንና በመሳሰሉት ቁሳዊ ሀብት በሚመረትባቸው የሥራ መስኮች ላይ በመዋል አዲስ ቁሳዊ ሀብት እንዲፈጠር ያደርጋል ። የምርት ዕድገት መስፋፋት ከምርታዊ ሥራ ማደግ ጋር የተያያዘ ነው ። በአንድ ሀገር በምርታዊ ሥራ የሚሳተፈው የኅብረተሰቡ ክፍል ቁጥር መብዛት ለብሔራዊ ሀብት ማደግ ወሳኝ ከሆኑት ምክንያቶች አንዱ ነው ።

በካፒታሊስት ኢኮኖሚ የካፒታሊስቱ ትርፍ ምንጭ ምርታዊ ሥራ ነው ። አምራቹ ወዝአደር በምርታዊ ሥራ በሚያደርገው ተሳትፎ ለካፒታሊስቱ አዲስ ሀብት በመፍጠር ትርፍ ያስገኛል ። ካፒታሊስቱ ከሚያገኘው ትርፍ ውስጥ የተወሰነውን የበለጠ ትርፍ ለማግኛ በሚረዳ መንገድ በተጨማሪ በምርታዊ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ሠራተኞችን በመቅጠርና በተጨማሪ የምርት መገልገያዎች በመታገዝ የካፒታል ክምችቱን ያዳብራል ። በምርታዊ ሥራ ላይ የተሰማሩት ወዝአደሮች ቁጥር መብዛትና የሥራ ምርታማነት ማደግ በቀጥታ የካፒታሊስቱን ቁሳዊ ሀብት ማደግ ያስከትላል ። ካፒታሊስቶች በምርታዊ ሥራ ላይ የተሰማሩትን ሠራተኞች የሥራ ዕምቀት እንዲጨምር በማድረግ የሚመረተውን ቁሳዊ ሀብት ያሳድጋሉ ። በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ በምርታዊ ሥራ መስክ የሚመረተው ቁሳዊ ሀብት ለካፒታሊስቱ መደብና ለአጋሮቹ ጥቅምና ድሎት የሚውል ነው ። በእንፃሩ ቁሳዊ ሀብቱን የፈጠረው ወዝአደር የተጐሳቆለ ኑሮ ይኖራል ።

በሶሻሊስት ሥርዓት ውስጥ በምርታዊ ሥራ የተሰማራው ሠርቶ አደር የሚሠራባቸው የምርት መገልገያዎች በኅብረተሰቡ የጋራ ባለቤትነት ይዞታ ሥር ያሉ በመሆናቸው የሚመረቱት ቁሳዊ ሀብቶች የጠቅላላው ሠርቶ አደር ሕዝብ ሀብት ናቸው ። ስለዚህም በምርታዊ ሥራ የሚመረተው ቁሳዊ ሀብት የኅብረተሰቡን አባሎች ቁሳዊና ባህላዊ ፍላጐት ለማሟላትና የኅብረተሰቡን ዕድገት ለማፋጠን ይውላል ።

(ኢምርታዊ ሥራን ይመለከቷል ።)

## ምርት ኃይሎች (የ—)

*(Productive Forces)*

የምርት መገልገያዎችና እነዚህን የሚያንቀሳቅሰው የሰው ኃይል በጥቅል የምርት ኃይሎች ይባላሉ ። የምርት መገልገያዎች ማለትም የሥራ ተገብሮችና የሥራ መገልገያዎች በራሳቸው የምርት ውጤት ሊያስገኙ አይችሉም ። ቴክኖሎጂው ምንም ያህል የተራቀቀ ቢሆን ያለ ሰው ዋጋ የለውም ። በመጀመሪያም ያለ ሰው ተሳትፎ የሥራ ተገብሮች ወደማምረቻ መሣሪያነት ሊሰወጡ አይችሉም ። ስለሆነም በምርት ኃይሎች ውስጥ ሰው ወሳኝ ኃይል ነው ። የምርት ኃይሎች

ስንል ከምርት መገልገያዎች ጋር የሰው የምርምር ውጤት የሆኑትን ሳይንስን ፣ ቴክኖሎጂንና ጥበብን ያጠቃልላል ።

የምርት ኃይሎች ሰው ተፈጥሮን የራሱ መጠቀሚያ ለማድረግ የሚያካሂደውን ትግል ይገልጻሉ ። ሰው የተፈጥሮን ባሕርይ ይበልጥ እየተገነዘበና ለጠቀሜታው እያዋለ የሚሄደው በምርት ኃይሎች ዕድገት አማካይነት ነው ። በምርት ኃይሎች ውስጥ ዋናውና ወሳኙ ሰው ነው ። የምርት ኃይሎች በስልተ ምርት ውስጥ ካሉት መዋቅሮች ዋነኞቹና ከፍተኞቹ የኅብረተሰብ ዕድገት መሠረቶች ናቸው ። የማምረቻ መሣሪያዎች መሻሻል የሰዎች ጥረት ውጤት እንደመሆኑ ሁሉ ከማምረቻ መሣሪያዎች መሻሻል ጋር የአምራቹም ሕዝብ ሙያና ምርታማነት ያድጋል ።

የምርት ኃይሎች ዕድገት መሠረት ሰው ፍላጎቱን ለማሟላትና ኑሮውን ከጊዜ ወደ ጊዜ በማሻሻል ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ የሚያደርገው ጥረት ነው ። ከዚህም የተነሣ የምርት ኃይሎች በየጊዜው የመሻሻልና የመቀየር ባሕርይ አላቸው ። ተፃራሪ መደቦች ባሉበት ኅብረተሰብ ውስጥ በምርት ሂደት እየተሻሻሉና እየዳበሩ በሚሄዱት የምርት ኃይሎችና የኋላቀርነት ሚና በሚጫወተው የምርት ግንኙነት መካከል የሚኖረው ቅራኔ የመጨረሻ መፍትሔ የሚያገኘው በሶሻሊስት አብዮት ነው ። በዚህም አብዮት የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች የሚጣጣሙበት አዲስ ስልተ ምርት ይወለዳል ። ለምሳሌ በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የነበረው የፊውዳል የምርት ግንኙነት ለምርት ኃይሎች ዕድገት ከፍተኛ ዕንቅፋት ሆኖ ቆይቶ ነበር ። አብዮታችን ይህንን አድኃሪ የምርት ግንኙነት በማስወገድ ለምርት ኃይሎች ዕድገት አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል ።

(የምርት ግንኙነቶችን ፣ ስልተ ምርትን ይመለከቷል ።)

## ምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች ዲያሌክቲክስ (የ—)

*(Dialectics of Productive Forces and Relations of Production*

በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል ያለውን መስተጋብርና የእርስ በርስ የመወሳሰን ሁኔታ የሚገልጽ የማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓቶች መሠረታዊ ሕግ ነው ። የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች የስልተ ምርት የማይነጣጠሉ ክፍሎች እንደመሆናቸው የምርት ግንኙነቶች የሚወሰኑት በምርት ኃይሎች የዕድገት ደረጃ ሲሆን የምርት ግንኙነቶች በበኩላቸው የምርት ኃይሎችን ዕድገት ይመራሉ ።

የምርት ግንኙነቶች በአንድ ወቅት የምርት ኃይሎችን የሚያላድጉ ናቸው ። ለምሳሌ በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ በተለይም በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የአምራቹ መደብ መበዝበዝና የፍጆታ ችሎታው መቀነስ ተረፈ ምርት ለማከማቸትና የምርት ኃይሎችን ለማሳደግ ይጠቅማል ። ሆኖም ይህ የምርት ግንኙነቶች ሁኔታ የምርት ኃይሎች እያደጉ በሄዱ ቁጥር ተቃራኒ ተግባሮት በመፍጠር በተወሰነ ደረጃ ላይ ለዕድገታቸው መሰናከል ይሆናል ። ለምሳሌ ካፒታሊዝም ብዙ ሸቀጦች ያመርታል ፤ ነገር ግን ብዙኀኑን የሚበዘብዝ ከመሆኑ የተነሣ ሸቀጦችን ለመግዛት ባለመቻሉ ኅብረተሰቡ በኢኮኖሚያዊ ከዚያም በማኅበራዊ ቀውስ ውስጥ ይወድቃል ። ማለትም የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች አለመጣጣምና መጋጨት ኅብረተሰቡን ወደ አብዮታዊ ሁኔታ ይወስደዋል ።

የአብዮት ዐቢይ ተግባር የምርት ግንኙነቶችን በመለወጥ ከምርት ኃይሎች ጋር ተመጣጣኝ አድርጎ ቀውሱን መፍታት ነው። መፍትሔውም የብዝበዛ መሠረት የሆነውን የግል ይዞታ ወደ ወል ንብረትነት በመለወጥ ሶሻሊስታዊ የሆነ የምርት ግንኙነት መመሥረት ነው ። አብዮቱ በምርት ማኅበራዊነትና በክፍፍል ግላዊነት መካከል ያለውን የካፒታሊዝም ቅራኔ ይፈታል ። ይህም የሚሆነው የምርት ኃይሎች በደረሱበት ማኅበራዊ ደረጃ አንፃር የምርት ግንኙነቶችን ማኅበራዊ ማለትም ሶሻሊስታዊ በማድረግ ነው ። የምርት ግንኙነቶች ከብዝበዛ መላቀቅ የኅብረተሰቡን ፍላጎት በአጠቃላይ ለሟሟላት የሚያስችል ሁኔታ ስለሚፈጥር ለምርት ኃይሎች ማደግ ከፍተኛ ግፊት ይሰጣል ።

የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች ግጭት የዕድገት ሕግ በመሆኑ በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥም ይከሰታል ። ሆኖም ግጭቱ አብዮታዊ ሁኔታ የሚፈጥርና አብዮታዊ

መፍትሔ የሚጠይቅ አይደለም ። በዝባዥ መደቦች የጠቀሙበትና የጋራ ብልጽግና የሰፈነበት በመሆኑ የምርት ግንኙነቶች እንዳሉ እንዲቀሩ ወይም እንዳያድጉ የሚፈልጉ ኃይሎች ባለመኖራቸው ቅራኔው በዕቅድ ፣ በውይይትና በንቁ ውሳኔ የሚፈታ ነው ።

ይህ በማርክስ የተቀነባበረው የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች ዲያሌክቲክስ የታሪክ ሂደትን ቁሳዊ መሠረትና ግፊት የሚያረጋግጥ ነው ። ሐሳባውያን በተለያየ አነጋገር ቢሆንም ታሪክን የተመለከቱት የሐሳብና የዕውቀት ዕድገት ውጤት አድርገው ነው ። ሆኖም ይህ የሐሳብ ዕድገት ከየት እንደመጣ ማስረዳት ስለተሳናቸው የታሪክ ንድፈ ሐሳባቸው ምሥጢራዊ ሆኖ ቀርቷል ። ማርክስ የሐሳብ ዕድገት የሚመጣው ከምርት ኃይሎችና ከምርት ግንኙነቶች አለመጣጣምና ሐሳቦችም ኃይል የሚኖራቸው አዲሱን የምርት ግንኙነቶች ሲያንፀባርቁ መሆኑን ማስረዳቱ በአጠቃላይ የማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓቶችን የታሪክ ሂደት ሳይንሳዊ ዕውቀት ለሰው ልጅ አስገኝቷል ።

(የምርት ኃይሎችን ፣ የምርት ግንኙነቶችን ፣ ታሪካዊ ቁስአካልነትን ይመለከቷል ።)

## ምርት መገልገያዎች (የ—)
## *(Means of Production)*

ቁሳዊ ሀብት ለማምረት ሰው የሚጠቀምባቸው የሥራ መገልገያዎች ወይም የማምረቻ መሣሪያዎችና የሥራ ተገባሮች ባንድነት የምርት መገልገያዎች ይባላሉ ።

ለምሳሌ ባገራችን ገበሬው ሰብል ለማምረት የሚጠቀምበት በሬ ፣ ሞፈር ፣ ቀንበር ፣ ወገል ፣ ማረሻ ፣ ገጀራ ፣ ማጭድ ወዘተ... የሥራ መገልገያዎች ሲሆኑ መሬትና (እንደ ሁኔታው) ዘር ደግሞ የሥራ ተገባሮች ናቸው ። እነዚህ በጥቅል የምርት መገልገያዎች ይባላሉ ።

የምርት መገልገያዎች ለምርት ሥራ ሂደት አስፈላጊ በመሆናቸው ለአንድ ኅብረተሰብ ህልውና ቁሳዊ መሠረቶች ናቸው ። ስለሆነም የአንድ ኅብረተሰብ የቁሳዊ ሕይወት መሠረት በመሆናቸው የኅብረተሰቡ አባላት በምርት መገልገያዎች ላይ ያላቸው የይዞታ ሁኔታና የምርት ውጤት ድርሻቸውንና (ገቢ) በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚኖራቸውን ማኅበራዊ ስፍራ ይወስናሉ ።

ለምሳሌ በጥንታዊ ጋርዮሽ ኅብረተሰብ ውስጥ የምርት መገልገያዎች በጋራ ይዞታ ሥር ስለነበሩ የምርት ውጤቶች በአባላት መሀከል በእኩልነት መከፋፈል ችለዋል ። ይሁንና የተቀሩት የምርት መገልገያዎች በግል ንብረትነት በተያዙባቸው ሥርዓተ ማኅበሮች ምዝብር መደቦች (ባሮች ፣ ገባሮች ፣ ወዝአደሮች) ከአመረቱት ምርት ድርሻቸው ዝቅተኛ ሲሆን የበዝባዥ መደቦች (ባሪያ አሳዳሪዎች ፣ ፊውዳሎች ፣ ቡርዧዚዎች) ድርሻ ግን ከፍተኛ ነው ። በኅብረተሰብ ውስጥ ተበዝባዥ መደቦች ዝቅተኛ ስፍራ በመያዝ ሲናቁና ሲጨቆኑ የበላይነቱን ግን በዝባዥ መደቦች በመያዝ ይንደላቀቃሉ ።

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የምርት መገልገያዎች በጋራ ይዞታ ሥር ስለሚሆኑ ብዝበዛ አይኖርም ፤ በኅብረተሰቡ አባላት መካከል ያለው ግንኙነትም በእኩልነትና በወንድማማችነት ላይ የተመሠረተ ነው ።

(የሥራ ተገባሮችን ፣ የሥራ መገልገያዎችን ይመለከቷል ።)

## ምርት ሥርዓት አልባነት (የ—)
## *(Anarchy of Production)*

የምርት ሥርዓት አልባነት ዕቅድ በሌለበት የኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ በግል አምራቾች የሚመረቱ ሸቀጦች ለነዚህ ሸቀጦች ካለው ማኅበራዊ ፍላጐት ጋር የማይጣጣምበት ፣ በዚህም ምክንያት የማኅበራዊ ምርት እርባታ በየጊዜው የሚሰናከልበትና የኢኮኖሚ ቀውስ የሚፈጠርበት ሁኔታ ነው ። የምርት ሥርዓት አልባነት የግል ሀብት የሰፈነበት ,የሸቀጥ አመራረት ዓይነተኛ ጠባይ ሲሆን ሁለንታዊ ገጽታውን ይዞ በተሟላ መልኩ የሚከሰተው ግን በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ነው ።

የምርት ሥርዓት አልባነት እንግሥ ከአነስተኛ የሸቀጥ ምርት ዕድገት ጋር የተያያዘ ነው ። አነስተኛ ሸቀጥ በማምረት ላይ የተሰማራው ግለሰብ በገበያ ውስጥ ስላለው ፍላጐትም ሆነ በገበያ ላይ ሊሸጥ ስለመቻሉና

አለመቻሉ ፣ ሌሎች ተመሳሳይ ሸቀጥ አምራቾች ስለሚያመርቱት ሸቀጥ መጠን ምንም አያውቅም ። በዚህ ዓይነት ሥርዓት በሌለው የአመራረት ዘዴ በተለያዩ የምርት ዘርፎች መካከል ማኅበራዊ የሥራ ኃይል የሚሰራጭበት መጠንና በፍላጐትና በአቅርቦት መካከል ያለው ግንኙነት ይዛባል ። ማለትም በገበያ ውስጥ ያንዳንድ ሸቀጦች አቅርቦት ከፍላጐት በላይ ሲሆን የሌሎች ሸቀጦች አቅርቦት ደግሞ ከፍላጐት በታች ይሆናል ።

በአነስተኛ የሸቀጥ ምርት ደረጃ የሸቀጥ ምርትና ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍሉ ያልዳበረ ነው ። በዚህም ምክንያት የተዋሃደ ብሔራዊ ገበያ ሊፈጠር ስለማይችል በዚህ ደረጃ የሚከሰተው የምርት ሥርዓት አልባነት ወደ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ቀውስና ወደ ማኅበራዊ ምርት ተናጎት አያመራም ።

የምርት ሥርዓት አልባነት ከፍተኛ የሆነ ተፅዕኖ የሚከሰተው በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ነው ። የምርት ሥርዓት አልባነት የካፒታሊዝም መሠረታዊ ቀውስ የሆነው "የበላጥ ምርት" ቀውስ የሚገለጽበት ዓይነተኛ መልክ ነው ። የካፒታሊዝም መሠረታዊ ቅራኔ በአመራረቱ ማኅበራዊነትና በምርቱ ውጤት ክፍፍል ግላዊነት መካከል ባለው ቅራኔ ይገለጻል ።

በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ እያንዳንዱ የካፒታሊስት ተቋም በምርት ሂደት ሥራ ላይ በሚያውለው የማሽን ቴክኖሎጂ ከፍተኛነትና በምርት አደረጃጀቱም ቀልጣፋነት የተነሣ በሚኖረው ከፍተኛ የሥራ ምርታማነት ተመርተው ወደ ገበያ የሚገቡ ሸቀጦች መጠን እጅግ ከፍተኛ ነው ። ይሁንና በካፒታሊስቱ ኢኮኖሚ ውስጥ በአጠቃላይ የምርት ሥርዓት አልባነት የሰፈነ በመሆኑ ማኅበራዊ ምርትን በዕቅድ ለመምራት አይቻልም ። በመሆኑም በገበያ ውስጥ የማኅበራዊ ምርት ሙሉ በሙሉ አለመጣራት ለተስፋፋ እርባታ ጤናማ እንቅስቃሴ አይፈጥርም ።

እያንዳንዱ ካፒታሊስት የገበያውን ዓቅም ለማወቅ በማይችልበት ሁኔታ የግል ትርፍን ለማካበት ካለው ፍላጐት ብቻ በመነሣት ምርቱን የሚያሳድግ በመሆኑ በተለያዩ ዘርፎች መካከል መኖር የሚገባው ሚዛናዊ ግንኙነት በየጊዜው ይናጋል ። በዚህ ሁኔታ ማኅበራዊ ምርትን ለማጣራት የሚያጋጥሙት ችግሮች ከካፒታሊዝም ዕድገት ጋር እየጨመሩ ይሄዳሉ ። በካፒታሊዝም የምርት ሥርዓት አልባነት ከውድድሩ ጋር የተሳሰረ ነው ። የካፒታሊስት ውድድር የሚያስከትለው ሥርዓት አልባነት ምርት ተጨባጭ በሆነ ፍላጐት ላይ ሳይመረኰዝ እንዲመረት ያስገድደዋል ።

በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም በሞኖፖል ተቋሞች ውስጥ ባለው የምርት አደረጃጀትና በኢኮኖሚው ውስጥ በአጠቃላይ ሰፍኖ በሚገኘው የምርት ሥርዓት አልባነት መካከል ያለው ቅራኔ በይበልጥ ይከራል ።

የምርት ሥርዓት አልባነት የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ዓይነተኛ ባሕርይ እንደመሆኑ ተፅዕኖው የአንድን ሀገር ክልል በማለፍ በዓለምአቀፍ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ፣ ከዚህም በሚመነጨው ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነትና ይህ ግንኙነት በሚያጠቃልላቸው ሀገሮች ውስጥ ሁሉ ይንፀባረቃል ። የዓለምአቀፍ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ያልተመጣጠነ ዕድገት የሚመነጨውም በዚሁ በዓለምአቀፍ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ተንሰራፍቶ በሚገኘው የምርት ሥርዓት አልባነት ነው ።

በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ሰፍኖ የሚገኘውን የምርት ሥርዓት አልባነት በመንግሥታዊ ሞኖፖል ቁጥጥር ሥር በማድረግ ለማስወገድ ወይም ተፅዕኖውን ለመቀነስ ይቻላል በማለት የቡርዧ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ቢስብከም ፣ የቡርዧ መንግሥታትም ይህንን ምክር ተቀብለው የምርት ሥርዓት አልባነትን የመቆጣጠሪያ ስልት እናወጣለን ቢሉም በኢኮኖሚው ውስጥ ሰፍኖ የሚገኘውን የምርት ሥርዓት አልባነት ሊያስወግዱ ቀርቶ ተፅዕኖውንም ሊቀንሱ አልቻሉም ።

## ምርት ግንኙነት (የ—)

*(Relations of Production)*

ሰዎች በማኅበራዊ የምርት ሥራና ምርት ከመመረት እስከ ፍጆታ በሚያደር

ገው እንቅስቃሴ ውስጥ እርስ በርሳቸው የሚያደርጓቸው ጠቅላላ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች የምርት ግንኙነቶች ይባላሉ ። ሰዎች በምርት ሂደት ውስጥ ከተፈጥሮ ጋር ብቻ ሳይሆን እርስ በርሳቸውም ግንኙነት ለመፍጠር ይገደዳሉ ። በማኅበራዊ ግንኙነትም አማካይነት የምርት ተግባር ይከናወናል ።

የምርት ግንኙነት ባሕርይ በምርት መገልገያዎች ባለቤትነት ይወሰናል ። የምርት መገልገያዎቹ በግል ባለቤትነት የተያዙ ከሆኑና የሚያመርቱት ባለቤቶቹ ካልሆኑ በአምራቾችና በባለቤቶቹ መካከል ያለው ግንኙነት በብዝበዛ ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ይሆናል ። ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ ሰዎች ከምርት መገልገያዎቹ ጋር ያላቸው ግንኙነት በጋራ ማኅበራዊ ባለቤትነት ላይ የተመሠረተ ከሆነ በሰዎቹ መሀከል ያለው ግንኙነት በመተባበርና በመደጋገፍ ላይ የተመሠረተ የእኩልነትና የወንድማማችነት ግንኙነት ይሆናል ።

የምርት ግንኙነት በተጨባጭና በቁሳዊ መሠረት ላይ የተገነባና በኅብረተሰብ ዕድገት ውስጥ ከሌሎችም ጠቅላላ ማኅበራዊ ግንኙነቶች ሁሉ ወሳኝነት ያለው ነው ። ሌሎች ማኅበራዊ ግንኙነቶች የምንላቸው ለምሳሌ የቤተሰብ ግንኙነት ፣ የሃይማኖት ግንኙነት ፣ የሥጋ ወይም የደም ግንኙነት ፣ የብሔረሰብ ግንኙነት ወዘተ... ናቸው ። ሆኖም ለነዚህ ዓይነቶቹ ማኅበራዊ ግንኙነቶች ሁሉ ዋነኛው መሠረቱ የምርት ግንኙነት ነው ። ከጠቅላላ የማኅበራዊ ግንኙነት ውስጥ የምርት ግንኙነትን ለይቶ ማወቅና ማጥናት የታሪክ ሂደትን በትክክል ለመረዳትና የኅብረተሰብ ዕድገትን ለማቀድና ማኅበራዊ ሕይወትን ለማበልጸግ ያስችላል ።

(ስልተ ምርትን ፣ የምርት ኃይሎችን ይመለከቷል ።)

## ምትሀት
(*Illusion*)

ምትሀት ፣ ሳይሆን የሆነ መስሎ ፣ ግዘፍ ነሥቶ ፣ መልክ ገዝቶ የሚታይ ነገር ፣ ሐሰት ወይም የሚያታልል ነገር ማለት ነው ።

ምትሀት የተጣመመ ፣ የተሳሳተ የእውነት ልባዌ ወይም ግንዛቤ ማለት ሲሆን በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ ቁስአካላውያንና ሐሳባውያን ልዩነታቸውን ፣ አንዱ ከሌላው ትክክል መሆኑን ለመግለጽ የተጠቀሙበት ጽንሰ ሐሳብ ነው ።

በሐሳባውያን አመለካከት ቁስአካልነት ምትሀት ነው ፤ ምክንያቱም ለነሱ የቁስአካል ቀዳሚነት በተለይም ቁስአካል የሐሳብ ፈጣሪ ሆኖ መታየቱ የተሳሳተ የእውነት ግንዛቤ ነው ። ለዚህም የሚያቀርቡት መረጃ ቁስአካላውያን ሙሉ በሙሉ እምነት የሚጥሉባቸው ሕዋስታዊ መረጃዎች ብዙውን ጊዜ ምትሀታዊ መሆናቸውን በመግለጽ ነው ። ለምሳሌ ፀሐይን ትንሽ ነገር አድርጎ የሚያሳየን የዓይን ሕዋስ ምትሀታዊ ነው ። ከተሳሳተው ግንዛቤ ወደትክክለኛው የምንተላለፈው በምክኑያዊ አስተሳሰብ ሕዋሱን በማረም መሆኑ ለሐሳባውያን ይህ የሚያስረዳው ምክኑያዊ ሐሳብ ብቻ የእውነት ምንጭ መሆኑን ነው ።

በአንፃሩም በቁስአካላውያን አመለካከት ሐሳባዊነት ፍጹም የሆነ ምትሀት ነው ። ሐሳብ ራሱን ችሎና ባለሙሉ ሥልጣን ሆኖ ዓለምን ፈጥሯል የሚለው ሐሳባዊ አነጋገር የዓለም የተገላቢጦሽ ግንዛቤ በመሆኑ ምትሀት ነው ። በእርግጥ ሕዋሳት የተሳሳቱ ሊሆኑ ይችላሉ ፤ ሆኖም የሚሰጧቸው መረጃዎች እርስ በእርስ ሊተራረሙና በተግባር ሊረጋገጡ የሚችሉ ናቸው ። የሐሳባውያን ጽንሰ ሐሳቦች ግን (ነፍስ ፣ እግዚአብሔር ፣ የሐሳብ የበላይነት ወዘተ...) ምናባዊና ዲበተፈጥሮአዊ ከመሆናቸው የተነሣ ጨርሶ ሊረጋገጡ የማይችሉ ናቸው ።

ይህን የቁስአካላውያንን አቋም በማስፋት ፣ በተለይም የምትሀትን ማኅበራዊ ምንጭ በማሳየት ለጽንሰ ሐሳቡ ከፍተኛ ፍች የሰጠው ማርክስ ነው ። በማርክሲዝም አመለካከት የሐሳባውያን ምትሀት የሚመነጨው ከአስተሳሰብ ስህተት ብቻ አይደለም ። ለስህተቱ ማኅበራዊ ወይም መደባዊ ምክንያትና ፍች አለው። ማርክስ እንዳስረዳው ንቃተ ኅሊና ምትሀታዊ ሐሳቦችን የሚያመነጨው ምድራዊ መሠረቱ በቅራኔ በመወጠሩ ነው ። ቅራኔው ኑሮንና ንቃተ ኅሊናን የሚያለያይ በመሆኑና ለቅራኔው ለጊዜው ምድራዊ መፍትሔ ባለመገኘቱ ንቃተ ኅሊና ከምድራዊ ኑሮ በመለየት የራሴ ህልውናና ዓለም አለኝ ወደሚለው ሐሳባዊ ምትሀት ያመራል ። በሌላ በኩል የሐሳብ የበላይነት ሊታመንበት የሚችለው ሐሳብ ምድራዊ ሳይሆን መለኮታዊ ተልዕኮ እንዳ

ሰው ሲታመንበት በመሆኑ የሐሳብ ቀዳማ ይነት ለመደብ አገዛዝ አስፈላጊ ምትሀት ነው ። ይህ የምትሀት ትንተና በግልጽ የሚ ያስረዳውም ቁሳዊ ኑሮንና መንፈሳዊ ኑሮን ሊያዋህድ የሚችለው የኮሚኒስት ሥርዓት አሳቦችን ከምትሀት ነፃ የሚያደርግ መሆኑ ነው ።

(ሐሳባዊነትን ይመለከቷል ።)

## ምናብ

*(Imagination)*

> አንድን ነገር በሐሳብ ውስጥ ማየት ማለት ነው ።

ከእውነታ ከተገኙ ስሜቶች በመነሣት እውን ያልሆነ አዲስ ስሜታዊ ወይም ሐሳ ባዊ ምስል በኅሊና ውስጥ መፍጠር ምናብ ይባላል ። ምናብ የሚገኘው ከጥረትና ከሥራ ሲሆን ሥራም ካለምናብ ግባዊና ፍሬያማ ሊሆን አይችልም ። ምናብ በፈቃድ ወይም ከፈቃድ ውጭ ሊከሰት ይችላል ፤ እንዲሁም ሙሉ በሙሉ ፈጠራ ሊሆን ወይም በቅጂ ብቻ ሊወሰን ይችላል ። ለሳይንሳዊ ምርምር ለሥነ ጥበብ ፣ ለሃይማኖት ወዘተ... ግንዛቤ ጠቃሚ የሆነ የማጠቃለል ሚናም ሊጫወት ይችላል ።

ለሳይንቲስቱ ምናብ መላምቶችን ለማ ቀነባበር ፣ ሞዴል ጽንሰ ሐሳቦችን ለመቅረፅ ፣ የሙከራ ሐሳቦችን ለማመንጨት ይጠቅመ ዋል ። ምናብ በተለይ በሥነ ጥበብ ውስጥ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው ። በሥነ ጥበብ ውስጥ ምናብ የሚያገለግለው ለማጠ ቃለል ብቻ አይደለም ፤ ኪነ ጥበብ የሰውየውን የእውነታ ግንዛቤ የሚገልጹ ሥነ ውበታዊ የሆኑ ምስሎችን ለማፍለቅ ይጠቅማል ። ሰዎች መሆን አለበት ብለው የሚፈልጉት ነገር ሁሉ የምናብ ውጤት ነው ። ምናብ ከቅዠትና ከሕልም የተለየና ከኅብረተሰብ ፍላጎት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ኑሮን ለማወ ቅና ለመለወጥም ይጠቅማል ።

## ምንነትና እይታ

*(Essence and Appearance)*

ምንነት የማንኛውንም ነገር አስፈላጊና የተስጥኦ ጠባዮች የሚያንፀባርቅ የፍልስፍና ፈርጅ ነው ። ምንነት የሚገልጸው የአንድን ነገር ውስጣዊና በይበልጥ ቋሚ የሆኑትን ጠባዮችና ግንኙነቶች ሲሆን የነገሩን አመ ጣጥ ፣ ባሕርይና የዕድገት አቅጣጫ የሚወስን ነው ። እይታ የሚያመለክተው በቀጥታ ለሕዋሳት የሚገለጹትን የአንድን ነገር የተለያ ዩና ተለዋዋጭ የሆኑ ውጫዊ መልኮችንና ግንኙነቶችን ነው ። እይታ ምንነት ራሱን የሚገልጽበት መንገድ ወይም ሁኔታ ነው ።

ሐሳባውያን ስለነዚህ ፈርጆች ያላቸው አስተሳሰብ የተሳሳተ ነው ። ነባራዊ ሐሳባው ያን ምንነት ከእይታ ውጭ እንደሚገኝ አድ ርገው ሲወስዱ ኅሊናዊ ሐሳባውያን ደግሞ እይታን ኅሊናዊ ብቻ በማድረግ ምንነትን ኢታዋቂ ነው ይላሉ ። ሕውስታውያን ደግሞ ሁለቱን በማዋሃድ ልዩነታቸውን ይክዳሉ ።

ምንነትና እይታ አንድነት አላቸው ። የማይገለጽ ምንነት እንደማይኖር ሁሉ ምንነ ትን የማያንፀባርቅ እይታም ሊኖር አይችልም። በተጨማሪም አንድነታቸውን የሚያረጋግ ጠው አንዱ ወደ ሌላው የመቀየሩ ሁኔታ ነው ። በአንድ ወቅትና ሁኔታ ምንነት የነበ ረው በሌላ ወቅትና ሁኔታ ወደ እይታ ይቀ የራል ። በተገላቢጦሽም እይታ የነበረው ወደ ምንነት ይለወጣል ። ለምሳሌ ዘር ወደ እይታ (አካል) ይቀየራል ፤ እይታ ደግሞ ዘርን ይሰጣል ።

የምንነትና የእይታ አንድነት የተመሠ ረተው በውስጣዊ ቅራኔ ላይ ነው ። ምንነት ወሳኝ ሲሆን እይታ ተወሳኝ ነው ። እይታ በቀጥታ የሚገለጽ ሲሆን ምንነት የተደበቀ ነው ። እይታ በመልክ ብዛት ከምንነት ይበ ልጣል ፤ ሆኖም ይበልጥ ውስጣዊነት ያለው ምንነት ነው ። የአንድ ነገር ምንነት ሁሌም አንድ ሲሆን በተለያዩ እይታዎች ግን ሊገለጽ ይችላል ። እይታ በይበልጥ ተለዋዋጭ በመ ሆኑ ያው እይታ ከተለያዩና ተቃራኒም ከሆኑ ምንነቶች ሊመነጭ ይችላል ። እይታ ባልተስ ተካከለና ባልተጣራ ሁኔታ ምንነትን ሊያን ፀባርቅ ይችላል ። ምንነት እራሱ ቅራኔ አዘል በመሆኑ በእይታና በምንነት መካከል ያለው ቅራኔ ከራሱ ከምንነት ቅራኔ ጋር ተደምረው ነው የአንድን ነገር የዕድገት ጉዳና የሚቀይሱት ።

ዲያሌክቲክስ የዲበአካልን አቋም በመ ቃወም ምንነት ተለዋዋጭነት እንዳለው ይቀበላል ። የእይታና የምንነት ቅራኔ የዕው

ቀትን ውስብስብና ተቃራኒ ሂደት የሚያስረዳን ነው ። የውጭው መልክና የነገሩ ውስጣዊ ምንነት ባይለዩ ኖሮ ሳይንስና ምርምር አስፈላጊ ባልሆኑ ነበር ። የዕውቀት ዓላማ በማያቋርጥ ሁኔታ ከእይታ ወደ ምንነት መሸጋገርና ምንነቱ ለምን በዚህ እይታ እንዴት እንደተገለጸ ማስረዳት ነው ። ይህ የምንነት ዕውቀት የሚገኘው በረቂቅ ሐሳቦች አማካይነት ነው ።

ለምሳሌ በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚታዩት የተለያዩ የኑሮ ደረጃዎች እይታ ሲሆኑ የነዚህን ልዩነቶች ምክንያትና ዓይነተኛ መልኮች የሚያስረዳው የምርት ግንኙነቶች ሁኔታ የኅብረተሰቡን ምንነት የሚገልጽ ነው ።

(ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀትን ፣ ነባራዊ ሐሳባዊነትን ፣ አፍላጦንን ፣ ኢታዋቂነትን ፣ ፈርጆችን ይመለከቷል።)

## ምንዳ
*(Wages)*

ምንዳ በካፒታሊዝም ውስጥ የሥራ ኃይል ዋጋ ነው ። በካፒታሊዝም ውስጥ የወዝአደሩ የመሥራት ችሎታ ወይንም የሥራ ኃይል እንደማንኛውም ሸቀጥ ለገበያ የሚቀርብ በመሆኑ እሴት አለው ። የሥራ ኃይል እሴት የሚወሰነው ለወዝአደሩ መሠረታዊ ፍላጐት ማርኪያ የሚያስፈልጉ ሸቀጦችን ለማምረት በሚወጣው ማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ ነው ።

ምንዳ የዚህ ማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ የገንዘብ መልክ ነው ። ወዝአደሩ አካላዊ ፣ ባህላዊና ማኅበራዊ ፍላጐቶች አሉት። እነዚህንም ፍላጐቶቹን ማርካት ወይም ማሟላት ይኖርበታል ። የወዝአደሩ ቁሳዊ ፣ መንፈሳዊና ባህላዊ ፍላጐቶች መሟላት አለባቸው ቢባልም ይህ ሁኔታ እንደየሀገሩ የዕድገት ደረጃ የሚወሰን ነው ። ለምሳሌ ባልዳበሩ የካፒታሊስት ሀገሮችና በዳበሩ የካፒታሊስት ሀገሮች ለወዝአደሩ የሚከፈለው ምንዳ በጣም የተለያየ ነው ። እንደአሜሪካ ፣ እንደ እንግሊዝ ፣ እንደጀርመንና እንደካናዳ በመሳሰሉት የዳበሩ ካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ ወዝአደሩ የሚያገኘው ምንዳ ባልዳበሩ እንደ ግብፅ ፣ እንደኬንያና እንደብራዚል ከመሳሰሉት የካፒታሊስት ሀገሮች ከሚከፈለው ምንዳ እጅግ የላቀ ነው ።

በቅድመ ማርክስ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ምንዳን እንደጠቅላላ የሥራ ዋጋ የመመልከት አቋም በመኖሩ እንደ አዳም ስሚዝና እንደ ዴቪድ ሪካርዶ ያሉት ምሁራን እንኳን በሥራና በሥራ ኃይል መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት ተስኗቸው ነበር ። በካፒታሊዝም ውስጥ የቡርዧዚው የትርፍ ምንጭ ምን እንደሆነ ለማሳየት አልቻሉም ። ወዝአደሩ የሚሸጠው የሥራ ኃይሉን እንጂ ሥራውን ፣ በምንዳ መልክ የሚከፈለውም የሥራ ኃይሉን ዋጋ እንጂ የሥራውን ዋጋ አለመሆኑን ለመጀመሪያ ጊዜ ያሳየው አብዮታዊው ምሁር ካርል ማርክስ ነው ። ማርክስ ይህንንም ልዩነት ማሳየት መቻሉ ወዝአደሩ የሚከፈለው ምንዳ ከሥራ ኃይሉ ውጤት ውስጥ የተወሰነው ክፍል ብቻ እንደሆነና የተቀረው ግን በትርፍ መልክ ወደ ካፒታሊስቱ ኪስ የሚገባ መሆኑን እንዲገነዘብ አድርጐታል ። በካፒታሊዝም ውስጥ የብዝበዛው ምንጭ ያልተከፈለ የወዝአደሩ የሥራ ጊዜ መሆኑንም በግልጽ አሳይቷል ።

በሶሻሊዝም ምንዳ የሥራ ኃይል ዋጋ ሳይሆን በቁሳዊ የምርት መስክ የተሰለፉ አምራቾች ለአመረቱት አስፈላጊ ምርት እንደ ሥራቸው ጥራትና መጠን የሚሰጣቸው ክፍያ ነው ። የምርት መገልገያዎች በሕዝቡ የጋራ ባለቤትነት ሥር ያሉ በመሆናቸው የአምራቾች ተረፈ ምርት ወደግለሰቦች ኪስ የሚገባ ሳይሆን ባጠቃላይ ለኅብረተሰቡ ጥቅም በሚሰጡ መስኮች ላይ የሚውል ነው ።

(የጊዜ ምንዳን ፣ የቁርጥ ሥራ ምንዳን ፣ የይስሙላ ምንዳን፣ እውን ምንዳን ይመለከቷል።)

## ምንዳ ደረጃ አወሳሰን ሥርዓት በሶሻሊስት ሀገሮች (የ—)
*(Grading System of Wages in Socialist Countries)*

በሶሻሊዝም ምንዳ አስፈላጊ ሥራ ለመሥራት ለወጣው የሥራ ኃይል ከአጠቃላይ ማኅበራዊ ምርት በሥራ መጠንና ጥራት በገንዘብ መልክ ለሠራተኛው የሚከፈል የተወሰነ ክፍያ ነው ። በሶሻሊዝም የሥራ ኃይል

ሸቀጥ ባለመሆኑ የሚገዛ ወይም የሚሸጥ
አይደለም ። ስለዚህ ምንዳ የሥራ ኃይል ዋጋ
ሳይሆን ቁሳዊ ሀብት እንደ ሥራ መጠንና
ጥራት የሚከፋፈልበት የክፍያ ዓይነት ነው ።
በሶሻሊዝም የደመወዝ ደረጃ አወሳሰን
ሥርዓት ዋና ዋና ዘዴዎች የተወሰነ ሥራን
ከተወሰነ አማካይ የሥራ ጊዜ አንፃር ማወ
ዳደርና ሥራን እንደክብደቱና እንደሠራተ
ኛው ችሎታ በደረጃ መከፋፈል ናቸው ።

መንግሥት ጠቅላላውን የምርት መጠን
በማጤን እንዲሁም የግለሰቡንና የኅብ
ረተ ሰቡን ፍላጐት በማየትና በማመዛዘን
ምንዳ በምን ያህል መጨመር እንዳለበት
ይወስናል ። በሶሻሊዝም የምንዳ አከፋፈል
ቀላልና ግልጽ በሆነ ሥርዓት ወጥቶ ሁሉም
ሠራተኛ እንዲረዳው ይደረጋል ።

በሶሻሊዝም ሁለት ዓይነት የምንዳ ቅር
ፆች አሉ ። እነሱም የጊዜ ምንዳና የቁርጥ
ሥራ ምንዳ ናቸው ።

በቁርጥ ሥራ ምንዳ መሠረት የሠራተ
ኛው ምንዳ የሚወሰነው በሚያስገኘው ምርት
ውጤት ነው ። ይህም የአከፋፈል ዘዴ የኅብ
ረተሰቡ ምርት እንዲጨምርና የሠራተኛውም
ገቢ ከፍ እንዲል ያደርጋል ። በዚህ የአከፋፈል
ዘዴ ለኮከብ አምራቾች ልዩ የገንዘብና የሌ
ሎች ሽልማቶች ስጦታ ይደረጋል ።

የጊዜ ምንዳ ክፍያ የሚደረገው በተሠ
ራባቸው ሰዓቶችና በሥራ ችሎታ መጠን
ነው ። የጊዜ ምንዳ ሥራ ላይ የሚውለው
የሥራን ውጤት በአኀዝ ለመተመን በማይ
ቻልበት የሥራ ዓይነት ላይ ነው ። ለምሳሌ
ሥራ አስኪያጆች ፣ መሐንዲሶች ፣ የቢሮ ሠራ
ተኞች የሚከፈላቸው በጊዜ ተመን መሠረት
ነው ። ሆኖም እንደውጤታማነቱ በፋብሪካ
ውስጥ በሚሠሩ ሠራተኞችም ሊሠራበት
ይችላል ። በጊዜ ተመን የሚሠሩ ሠራተኞችን
ለማበረታታት ፣ ወጪን በመቀነስ የምርቱን
ዕቅድ ላሟሉ ወይም ከዕቅድ በላይ ሥራቸ
ውን ላከናወኑ የገንዘብና ሌሎች የማበረታቻ
ሽልማቶች ይሰጣሉ ።

## ምንጪታዊ ሥነ አመክንዮ
*(Deductive Logic)*

*መንጪ ማለት ፈለቀ ፣ ወጣ ማለት ሲሆን
ምንጪታዊ የሚያፈልቅ ፣ የሚያወጣ ማለት
ነው ።*

ምንጪታዊ ሥነ አመክንዮ ከአንድ
ወይም ከአንድ ከሚበልጡ አጠቃላይ መን
ደርደሪያ ሐሳቦች በመነሣትና በነርሱም ላይ
በመመርኮዝ ዝርዝር መደምደሚያ ሐሳብን
በማፍለቅ የዚህን ሐሳብ ትክክለኛነት በሥነ
አመክንዮአዊ ሥርዓትና ትንታኔ መሠረት
የማረጋገጥ ወይም የማሳየት ስልት ነው ።

ምንጪታ ቀደም ብለው በአንድ ነገር
ውስጥ ከታቀፉ ሐሳቦች በመነሣትና ከሥነ
አመክንዮአዊ ሕግጋት ጋር ሳይቃረን ወደ
ጠባብ ወይም ወደ መለስተኛ መደምደሚያ
ሐሳብ ሽግግር የሚደረግበት የትንታኔ ፣
የክርክር ፣ የውይይት ወዘተ... ዘዴ ነው ።
ለምሳሌ በምርቱ ተግባር ላይ ያልተሳተፈበትን
የሌሎችን የሥራ ውጤት መመዝበር ብዝበዛ
ነው ከሚለው አጠቃላይ ሐሳብ በመንደርደር
የሠራተኛውን ምርት ቡርዧዚው ፣ የገበሬውን
ምርት ፊውዳሉ መመዝበራቸው ብዝበዛ ነው
ወደሚለው መለስተኛ መደምደሚያ ሐሳብ
ለመድረስ ይቻላል ።

ምንጪታዊ ሥነ አመክንዮ አጠቃላይ
መስለው ከሚታዩ ሐሳቦች በመነሣት የሕ
ይወትን ተጨባጭ ሁኔታዎች ለማጤንና በነ
ርሱም ላይ ተመሥርቶ የበለጠ ምርምር ለማ
ድረግ ወይም የተወሰነ እርምጃ ለመውሰድ
የሚረዳ ዘዴ ነው ። ሆኖም በዚህ መንገድ
የተደረሰባቸው መደምደሚያዎች ከጊዜ ፣
ከስፍራ ፣ ከሁኔታ ፣ ከልምድና ከተግባር
ለውጥ ጋር መገናዘብና ከለውጡም የተነሣ
በሚገኙ አዳዲስ መረጃዎች መሠረትም መዳ
በር ይኖርባቸዋል ። አለበለዚያ ግን የምንጪ
ታዊ ሥነ አመክንዮ ስልት ከመረጃና ከተግ
ባር ውጭም በሚገኙ ሐሳቦች ላይ በመመሥ
ረት ትክክለኛነታቸው ሊረጋገጥ ከማይችሉና
ከጊዜ ጋር ካልተገናዘቡ የተሳሳቱ መደምደ
ሚያዎች ላይ ሊያደርስ ይችላል ። ለምሳሌ
በአንድ ወቅት ቡርዧዚው አብዮታዊ ሆኖ
በመታየቱ ምንጊዜም ቢሆን አብዮተኛ
ነው ከሚለው መደምደሚያ ላይ መድረስ
ስህተት ይሆናል ፤ ምክንያቱም ኢምፔሪያሊ

ዝም ከተከሰተ ጀምሮ የቡርዧዚው አብዮተኛነት አከትሟልና ።

(መስተጋብአዊ ሥነ አመክንዮን ፣ ሥነ አመክንዮን ፣ ዲያሌክቲካዊ ሥነ አመክንዮን ይመለከቷል ።)

## ምክንያ
*(Rationalization)*

አንድን ሁኔታ ፣ ክስተት ወይም አስተሳሰብ ከአመክንዮ ጋር በማስማማትና በማስታረቅ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ማለት ነው። አንድን ሁኔታ ጠንቅቆ ለመረዳት የሚቻለው ለሁኔታው መከሰት ምክንያት ከሆነው ድርጊት ወይም ክስተት በመነሣት ፣ ትንታኔ በመስጠትና ግንኙነታቸውን በመግለጽ በመሆኑ የነገሮችን ግንዛቤ ከአመክንዮ ሕጋጋት አንፃር ለማግኘት የምናደርገው የሐሳብ ጥረት ምክንያ ይባላል ። ክስተቶችን ከማስተዋል አልፎ ምክንያታቸውን ፣ አመጣጣቸውን ፣ ውስጣዊ ግንኙነታቸውንና ሚናቸውን አብጠርጥሮና አቀነባብሮ ማሰብ የምክንያ ዋነኛ ጥረት ነው ።

ለምሳሌ (በሥነ ምግባር ውስጥ) አንድን ጥሩ ወይም መጥፎ ተግባር ከፈጸምን በኋላ ይህ ተግባር ለምን እንደተፈጸመ ራሳችንን በመጠየቅ ድርጊቱን ለመፈጸም የገፋፉንን ሁኔታና ምክንያት ለማግኘትና ለመግለጽ የምናደርገው ጥረት ሁሉ ምክንያ ይባላል ።

(አመክንዮን ይመለከቷል ።)

## ምክኑያዊነት
*(Rationalism)*

ሥነ ዕውቀትን በሚመለከት በኢመዛኙ በሐሳባዊ ፍልስፍና መርህ ላይ የተመሠረተ ንድፈ ሐሳብ ነው ። በምክኑያዊነት መሠረት ዕውቀት የሚገኘው በሕዋሳት አማካይነት ሳይሆን በተፈጥሮ ከሐሳብ መመሪያዎች ወይም ከአመክንዮ ነው ። ሕዋሳት ስለ ነገሮች ልዩ ልዩ ባሕርያት (ክብደት ፣ ቁመት ፣ ቀለም ወዘተ...) መረጃዎችን ቢሰጡም የነዚህን ባሕርያት ምክንያቶች ግን ሊገልጹ አይችሉም የሚል ንድፈ ሐሳብ ነው። ለምሳሌ አውሮፕላን በመሬት ላይ ሆኖ ሲታይ ትልቅ ይመስላል ፤ በሰማይ ላይ ሲታይ ደግሞ ቁመቱ ያንሳል ። የአውሮፕላኑ ቁመት መቀያየር እውን አለመሆኑን የምናውቀው በተፈጥሮ ያለን ያስተሳሰብ መርህ ማለትም ያለመለዋወጥ መርህ በቅድሚያ እኛው ውስጥ ስለሚገኝ ነው ። ይህም በመሆኑ የዕውቀት ምንጭ አመክንዮ እንደሆነ እንገነዘባለን ። የዕውቀት ምንጭ አመክንዮ በመሆኑ ዕውቀት ከውጭ የሚመጣ ሳይሆን እኛው ውስጥ ያለ ነው የሚል አስተምህሮ ነው ።

እንደምክኑያዊነት ማወቅ ማለት ነገሮችን በማጥናት ፣ በመማር ሳይሆን በተፈጥሮ ያለንን ዕውቀት ማለትም አመክንዮን በመጠቀም ስለ ነገሮች ትክክለኛውን ብያኔ መስጠት ነው ። አንድ ዳኛ ሁኔታውን ካደመጠ በኋላ በሕጉ መሠረት እንደሚፈርድ ሁሉ አመክንዮም በማይለዋወጡ ዘላለማዊ የተፈጥሮ ሕጎች አንፃር ስለ ክስተቶች ትክክለኛውን ፍርድ ይሰጣል ፤ ማለትም የነገሮችን ምንነትና ምክንያት ይገልጻል ፤ ምክንያቱም ነገሮች እራሳቸው ከሐሳብ የሚመነጩና በሐሳብ የሚገዙ በመሆናቸው ነው ። የዕውቀት ትክክለኛነት የሚለካው ዘላለማዊ በሆኑ የሥነ አመክንዮ ሕጎች ነው ። የተሳሳተ ሐሳብ ሊኖረን የሚችለው የአመክንዮን ሕጎች ሳናከብር ስንቀርና እኛ ውስጥ ያለው ሐሳብ ከሐሳብ ሕጎች ጋር ሳይጣጣም ሲቀር ነው ። እውነት የሚፈጠረው የሁለቱ መስማማት ሲከሰት ነው ይላል ።

ከላይ በተጠቀሰው ትንታኔ እንደሚታየው ምክኑያዊነት ሐሳባዊ ሥነ ዕውቀት ነው ። ምክንያቱም አመክንዮ የዕውቀት ምንጭ ነው ማለት ሐሳብ ቀዳማይ ወይም ነገሮችን የፈጠረ ሐሳብ ነው የሚለውን መርህ በቅድሚያ መቀበል ነው ማለት ነው ። የዚህም ንድፈ ሐሳብ ድክመት ይኸው መሠረታዊ ሐሳብ ነው ። ምክንያቱም ዕውቀት ከሐሳብ የሚመነጭ ከሆነ የዕውቀት ይዘት ነባራዊ መሆኑ ስለሚቀር ነው ። ዕውቀት ያለንን ሐሳብ ማወቅ ሳይሆን በአእምሮአችን ውስጥ የሚገኝ የነባራዊ እውነታ ነፀብራቅ ነው ፣ አገልግሎቱም እውነታን መለወጥ ነው ።

በምክኑያዊነት አስተሳሰብ ግን ዕውቀት ከእውነታ (ከነገሮች) ጥናት የሚገኝ ባለመሆኑ ስለ እውነታ ትክክለኛ ግንዛቤ ካለመፍጠሩም ሌላ በእውነታ ላይ ምንም ዓይነት ኃይል እንዳይኖረው ያደርጋል ። ስለሆነም ምክኑያዊነት ሐሳባዊ ፍልስፍናን ያጠናክራል ። የዚህም ማስረጃ ነገሮችን (እውነታን) በማውገርገር ባለቤታቸው ሐሳብ ነው ማለቱ በቂ ነው ። ይህንን ሐሰት ለማጋለጥም ጭምር ነው ማርክሲዝም ዕውቀት (ሐሳብ) የነገሮች ነፀብራቅ ነው የሚለው ። ዕውቀትን ከተግባር መገንጠል ሌላው የምክኑያዊነት የተሳሳተ እመለካከት ነው ፤ ምክንያቱም ተጨባጭነት የሌለው ነገር በመታሰቡ ብቻ ህልውና እንዳለው በመቆጠሩ ዕውቀትን ወደ እምነትና ወደ እምልኮት ይለውጠዋል ።

የዚህ ንድፈ ሐሳብ የመደብ ይዘት ግልጽ ነው ። የሐሳብ ሕጐች ነገሮችን ይገዛሉ ማለት በምርት ከንውን ውስጥ የማይሳተፈውን የገዥ መደብ የፖለቲካና የበላይነት ሥልጣን ማጠናከርና ሕጋዊ ማድረግ ነው ። በእእምሮ ሥራ ብቻ የተሰማራው የገዥ መደብ የምርት ውጤት ተጠቃሚ መሆን "ሐሳብ" ስለሚያውቅ ያዛል ይገዛል፤ ተግባርንና ነገሮችን የርሱ አገልጋይ ያደርጋል ከሚለው አስተሳሰብ ጋር በቅርብ ይዛመዳል ። የሐሳባዊ ፍልስፍና ሥነ ዕውቀት ዋነኛው ምሥጢር ዕውቀትን ከአገዛዝ ጋር በማዋሀድ የገዥው መደብ መሣሪያ ማድረጉ ነው ።

(ሥነ ዕውቀትን ፣ አመክንዮን ፣ ዳሳሽነትን ይመለከቷል ።)

## ሞር ፣ ቶማስ
(*More, Thomas*)

ከ1478—1535 የኖረ እንግሊዛዊ ተምኔታዊ ሶሺያሊስት ነው ። ቶማስ ሞር የኖረው ካፒታሊዝም ጨቅላ በነበረበት ዘመን ቢሆንም በብዝበዛ ላይ የተመሠረተና ለጥቂቶች ብቻ የቆመ መሆኑንና ለሰው በተለይም ለሠራተኛው ሕዝብ እውነተኛ ሰብአዊ ኑሮ ሊያስገኝ እንደማይችል ተረድቷል።

ከዚህ እመለካከት በመነሣት "ዩቶፒያ" በሚለው ጽሑፉ ውስጥ የግል ንብረት እስካለ ድረስ ሠራተኛው ያፈራው ሀብት ለጥቂቶች ብቻ እንደሚጠቅም ፣ የሰው እኩልነት ፣ ደስታ ፣ አካላዊና መንፈሳዊ ዕድገት እውን ሊሆን እንደማይችልም፣ ማኅበራዊ ፍትህ ምትሀታዊ እንደሚሆንና የኅብረተሰቡን ጉዳዮች ንቁ በሆነ መንገድ ለመምራት እንደማይቻል አስረድቷል። በመሆኑም የግል ይዞታን በወል ንብረትና ሥራ ላይ በተመሠረተና በዲሞክራሲያዊ አመራር በተዋቀረ ኅብረተሰብ መተካት ያስፈልጋል ሲል ተናግሯል ።

"ዩቶፒያ" ብሎ ከሰየመው ምናባዊ ደሴት ላይ ባቀደው ኅብረተሰብ ውስጥ ሕዝቡ የካፒታል ተገዥ ሳይሆን የእእምሮንና የጉልበትን ሥራ እያጣመረ በጋራ የሚሠራ ነው ፤ የሥራውንም ፍሬ በጋራ ማከማቻ ውስጥ ያስቀምጣል ፤ ሳይከፍልም የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ከዚያው ይወስዳል ። ቶማስ ሞር ፍላጎትን ውሱን አድርጎ የተመለከተ ቢሆንም ይህ የሚያስረዳው "እያንዳንዱ እንደፍላጎቱ" ከሚለው ኮሚኒስታዊ የክፍፍል መርህ ግንዛቤ ላይ መድረሱን ነው ።

(ተምኔታዊ ሶሻሊዝምን ይመለከቷል ።)

## ሞንተስኪየ ፣ ሻርል ደ
(*Montesquieu, Charles de*)

ከ1689 — 1755 የኖረ የፈረንሳይ ሐሳባዊ ፈላስፋ ነው ። ከደረሳቸው መጻሕፍት ውስጥ በይበልጥ ታዋቂ ያደረገው "ደ ሌስፕሪ ደ ልዋ" የሚባለው ነው ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የኅብረተሰብን ሕግ አመጣጥና አመሠራረት ለመረዳት የተለያዩ ሀገሮችን ሁኔታ በማወዳደር ጥናት አድርጓል ።

ሞንተስኪየ ከጥናቱ ያገኘው ውጤት በኅብረተሰቦች ውስጥ ያሉት ማኅበራዊ ሕጋጋት የተለያዩ ቢሆኑም በሰው ፈቃድ ላይ የተመሠረቱ እንዳልሆኑ ነው ። በአጠቃላይ የሕግጋቱ መንፈስ አንድ ሲሆን አንፃራዊነታቸው የሚመነጨው ግን ከሕዝቡ ጠባይ፣ ከመንግሥቱ ባሕርይ ፣ ከአካባቢውና ከኢኮኖሚው ሁኔታ መሆኑን ለማሳየት ሞክሯል ።

ሞንተስኪየ ፍጹማዊ የፊውዳል አገዛዝን አጥብቆ የሚቃወም ነበር ። የፖለቲካ ፍልስፍናውም በሥልጣን ክፍፍል ላይ የተመሠረተ ሲሆን ሥልጣን በሕግ አውጪ ፣ በአስፈጻሚና በተርጓሚ መለያየቱ የፖለቲካ ነፃነት መሠረት ነው የሚል ነበር ። ሞንተስኪየ ይህ ፍልስፍናው በወቅቱ ለቡርዧው ዲሞክራሲ መከሰት አስተዋጽኦ ቢያደርግም የቡርዧውን መንግሥት ከሁሉም ምርጥ አድርጎ መውሰዱ ፣ ሃይማኖተኛነቱና አካባቢውን ወሳኝ አድርጎ መገመቱ ሐሳባዊነቱን ያሳያል ።

## ሞኖፖል ትርፍ (የ—)
*(Monopoly Profit)*

ሞኖፖሊስቶች ባላቸው ዓላማና በሚያደርጉት እንቅስቃሴ መሠረት የሚያገኙትና አንድን የተወሰነ የካፒታል መጠን በሥራ ላይ በማዋል በውድድር ሁኔታ በአማካይ ሊገኝ ከሚችለው ትርፍ ብልጫ ያለው ትርፍ የሞኖፖል ትርፍ በመባል ይታወቃል ። ሞኖፖሊስቶች ከአማካይ ትርፍ በተጨማሪ የሚያገኙት የሞኖፖል ትርፍ ክፍል የሞኖፖል ልዕለ ትርፍ ይባላል ።

ማንኛውም ካፒታሊስት ትርፍ የማሳደግ ዓላማ ያለው መሆኑ የታወቀ ነው ። ሆኖም በቅድመ ሞኖፖል ካፒታሊዝም በልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ክፍሎች ውስጥ አንድን የተወሰነ የካፒታል መጠን በሥራ ላይ በማዋል የሚገኘው ትርፍ መጠኑ አማካይ ትርፍ የመሆን አዝማሚያ ነበረው ። ይህ ሁኔታ በሞኖፖል ካፒታሊዝም መሠረታዊ የሆነ ለውጥ አሳየ ። በምርት ፣ በዝውውርና በሌሎችም መስኮች የተሰማሩትና ተወዳዳሪዎቻቸውን እየደመሰሱ ኃይላቸውን ያጠናከሩት ሞኖፖሎች ያለማቋረጥ ልዕለ ትርፍ ማግኘት ቻሉ ። ይህም የሞኖፖል ልዕለ ትርፍ ቋሚ የሆነ የሞኖፖሊስቶች ትርፍ አካል ሆኖ ይገኛል ።

የሞኖፖል ትርፍ ምንጮች በርካታ ናቸው። አንዱ ዋና የሞኖፖል ትርፍ ምንጭ በሞኖፖል ድርጅቶች ውስጥ አዳዲስ የማምረቻ መሣሪያዎችንና የማምረት ዘዴዎችን በሥራ ላይ በማዋል ፣ የሥራ ዕምቀትን በማሳደግ ፣ ለሠራተኞቻቸው ከሥራ ኃይል እሴት በታች የሆነ ምንዳ በመክፈል የሚካሄድ ብዝበዛ ነው ። ሞኖፖሎች በሸቀጦች ዝውውር አማካይነት በሌሎች ድርጅቶች ውስጥ የሚፈጠር የተረፈ እሴትን ክፍል የራሳቸውም በማድረግ ትርፋቸውን ያሳድጋሉ ። ይህንንም የሚያደርጉት በአንድ በኩል የሚያስመርቷቸውን የምርት መገልገያዎችና የፍጆታ ዕቃዎች ለልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በከፍተኛ ዋጋ በመሸጥና ከአርሶ አደሩና ከሌሎች ጥቃቅን ሸቀጥ አምራቾች ጥሬ ዕቃዎችን በዝቅተኛ ዋጋ በመግዛት ነው ። በመልማት ላይ ባሉ ሀገሮች ሕዝቦች ላይ በልዩ ልዩ ዘዴዎች የሚካሄድ ብዝበዛም አንድ ሌላ ዋና የሞኖፖል ትርፍ ምንጭ ነው ። ሞኖፖሊስቶች በመልማት ላይ ወዳሉ ሀገሮች ካፒታል በማሸጋገር አምራቾችን በዝቅተኛ ምንዳ ቀጥረው በከፍተኛ ደረጃ በመበዝበዝ ፣ በእኩልነት ላይ ባልተመሠረተ የንግድ ፣ የፋይናንስና የገንዘብ ግንኙነት አማካይነትና በሌሎችም ዘዴዎች ከፍተኛ ትርፍ ያገኛሉ ።

(ሞኖፖልን ይመለከቷል ።)

## ሞክሬቲየ ፣ አንቷን ደ
*(Montchretien, Antoine de)*

ከ1575 — 1621 የኖረ “ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ” የሚለውን ቃል በኢኮኖሚክስ ጥናት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመ የሚርካንቲሊዝም አስተሳሰብ አራማጅ ነበር ። ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የሚለውን ቃል አሰፍሮ የተገኘው በ1615 በጻፈው “ትሪቲስ ኦን ፖለቲካል ኢኮኖሚ” በተሰኘው ጽሑፍ ውስጥ ነበር ።

ሞክሬቲየን በፈረንሳይ ውስጥ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ ስለነበር በወቅቱ በነበረው የፖለቲካ ችግር የተነሣ ወደ እንግሊዝ ሀገር ተሰድዶ ለአራት ዓመታት ያህል ቆይቷል ። በእንግሊዝ ሀገር በቆየበት ጊዜ የእንግሊዝን የካፒታሊስት ኢኮኖሚና ፖለቲካ ዕድገት በማየት በኢኮኖሚ ፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ጥናቱንና ምርምሩን በሰፋት ተያያዘው ። በእንግሊዝ ውስጥ በወቅቱ የነበሩት የፈረንሳይ የፕሮቴስታንት ስደተኞች የእደ ጥበብ ሙያ

ያላቸው ስለነበሩና እነርሱ የሚሠሩዋቸው የእደ ጥበብ ውጤቶች ለእንግሊዝ ከፍተኛ ገቢ ማስገኘታቸውን በማየት ፈረንሳይ እነ ዚህን ዜጐቿን እንዲሰደዱ በማድረጓ ያጣቸ ውን ገቢ በማጤን ከፍተኛ ብሔራዊ ቁጭት በሞክሬቲየን ላይ አደረ ። ሞክሬቲየን በእ ንግሊዝ ውስጥ ለአራት ዓመታት ያህል ብቻ ከቆየ በኋላ ወደ ፈረንሳይ በመመለስ የብሔ ራዊ ኢንዱስትሪና የብሔራዊ ንግድ መስፋ ፋት ዓላማን በመደገፍ በወቅቱ ቡርዧዚውንና ንውስ ከበርቴውን ይወክል ለነበረው ለ"ፓር ላማው ሦስተኛ ክፍል" ። ስርድ እስቴት ጥቅምና ፍላጐት በከፍተኛ ደረጃ ይታገል ጀመር ።

ሞክሬቲየን በፓሪስ ከተማ ውስጥ የግሉ የሆነ የእደ ጥበብ መሥሪያ ድርጅት በመክፈት ፣ የእደ ጥበብ ውጤቶችን በመሸጥ መኖር ጀመረ ። በዚህ ሥራውም ላይ እያለ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጥናት ያካሂድ ነበር ። የጽሑፉ ዋና ዓላማ ኢኮኖሚ በመንግሥት ወይም በብሔራዊ ደረጃ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው የሚል ሲሆን የሀገርና የመንግ ሥት ዋናው የገቢ ምንጭ ደግሞ የውጭ ንግድ ነው የሚል ነበር ። በጽሑፉም ውስጥ የፈረንሳይ መንግሥት የፈረንሳይ ፋብሪካ ዎችንና ነጋዴዎችን በከፍተኛ ደረጃ ማገዝና መርዳት አለበት በማለት ጠይቋል ። ከዚህም በተጨማሪ ከሌሎች ሀገሮች ወደ ፈረንሳይ በሚገቡ ሸቀጦች ላይ ከፍተኛ የገቢ ቀረጥ እን ዲጣል አጥብቆ ተሟግቷል ። የዚህ ጥያቄም ዓላማ የፈረንሳይ ፋብሪካዎች በሀገራቸው ገበያ ውስጥ ከውጭ አቅራቢዎች በሚመጣ ፉክክር እንዳይጐዱ የሚል ነበር ። ሞክሬቲ የን የፈረንሳይ ንጉሥ የሉዊ አሥራ ሦስተኛ አማካሪ ሆኖም ሠርቷል ።

# ሠ

## ሠራተኛ ማኅበር (የ—)
*(Trade(s) Union)*

በአንድ የሥራ ቦታ ወይም በተለያዩ የሥራ መስኮች የተሰማሩ ሠራተኞች ጥቅማቸውን ለማስከበር የሚመሠርቱት የአንድነት ድርጅት የሠራተኛ ማኅበር ይባላል ። የሠራተኛ ማኅበር ወዝአደሮች ከካፒታል ጋር ያደረጉት የረዥም ጊዜ የትግል ውጤት ነው ። በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ሠራተኛው የመደብ ጥቅሙን ተገንዝቦ በተቀናጀ ሁኔታ ትግል ማድረግ ሲጀምር ትኩረት ያደረገው ማኅበሩን በማቋቋም ላይ ነው ። ወዝአደሮች በካፒታሊስቶች የሚደርስባቸውን ብዝበዛ በመቃወም ለማኅበራዊና ለሥራ ሁኔታዎች መሻሻል (ለምንዳ ጭማሪ ፣ ለሥራ ሰዓት መቀነስ ፣ ለካሣ ፣ ለጡረታ መብት ወዘተ...) ዲሞክራሲያዊ ጥያቄዎችን በማቅረብ በማኅበራቸው መሪነት እንዲሟሉላቸው በልዩ ልዩ መንገድና ዘዴ ይታገላሉ።

በሠራተኛው ማኅበር ደረጃ የሚካሄደው ፀረ ካፒታሊስት ትግል በመሠረቱ ኢኮኖሚ ጥያቄ የማያልፍና አብዛኛውን ጊዜም ግብታዊነት የሚያጠቃው ነው ። የሠራተኛው ንቃተ ኅሊና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየዳበረ ሲሄድ ግን በማኅበሩ የሚቀርበው ጥያቄ በኢኮኖሚ ላይ ብቻ ማትኮሩ ቀርቶ ፖለቲካ ነክ ጥያቄዎችንም ጭምር የሚያነሣ ይሆናል ። በዚህ የትግል ሂደት ውስጥ በሠራተኛው መደብና በካፒታሊስቱ መደብ መካከል ያለው ቅራኔ እየተባባሰና እየከረረ ይሄዳል ። በመጨረሻም የሠራተኛው የፖለቲካ ትግል በተደራጀና በተቀነባበረ መንገድ መካሄድ ፣ ለካፒታሊስቱ የምርት ግንኙነት መለወጥና ለሠራተኛው ብዝበዛና ጭቆና መወገድ የመደብ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፓርቲ አመራር ወሳኝ ይሆናል ። በዚህ ረዥምና የተወሳሰበ ትግል ውስጥ የሠራተኛው ማኅበራት ሠራተኛው ራሱን በራሱ የማስተዳደርና የኢኮኖሚ ሥራ አያያዝ ጥበብ የሚቀስምባቸውና ኮሚኒዝምን የሚማርባቸው ልዩ ትምህርት ቤቶች ናቸው ።

የሠራተኛው ማኅበር ሕጋዊ በሆነ መንገድ ለመጀመሪያ ጊዜ የተመሠረተው በ19ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ አጋማሽ ላይ በእንግሊዝ ነበር ። ኋላም ከካፒታሊዝም መስፋፋት ጋር በሌሎች ሀገሮች የሠራተኛው ማኅበራት እየተስፋፉ መጡ ።

ካፒታሊዝም በደረጀባቸው ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች የሠራተኛውን አድማና አመፅ በመፍራት የሞኖፖል ቡርዧዚዎች ከቅኝ ግዛት ሀገሮች በገፍ ከሚያገኙት የሞኖፖል ትርፍ መደለያ በመስጠት የሠራተኛው ትግል በጊዜያዊ የኢኮኖሚ ጥያቄ ላይ ብቻ እንዲያተኩር ፣ ከፖለቲካ ትግል እንዲዘናጋና እንዲርቅ በማድረግ ትግሉን ያዳክማሉ ። በነዚህ ሀገሮች የሠራተኛው ኑሮ የተሻሻለና የበለጠ መሆኑን ለማሳመን በጥቅም አከፋፈልም ሆነ በአስተሳሰብ ከቡርዧዚው የማይለዩ የወዛደር መሳፍንት ከራሱ ከሠራተኛው በመመልመል በማኅበራት አመራር ላይ ያስቀምጣሉ ፤ በነርሱም እማካይነት ሠራተኛውን በማወናበድ የአድኃሪ ዓላማቸው ተባባሪና ደጋፊ ያደርጉታል ።

የሠራተኛ ማኅበራት በሶሻሊስት ሀገሮችም አሉ ። ነገር ግን የሶሻሊስት ሀገሮች የሠራተኛ ማኅበራት በካፒታሊስት ሀገሮች ካሉት የሠራተኛ ማኅበራት በዓላማና በግብ የተለዩ ናቸው ። በሶሻሊስት ሀገሮች የምርት መገልገያዎች የሕዝብ ንብረት በመሆናቸው በዝባዥና ተበዝባዥ የለም ፤ የማምረት ዓላማም ምርትን በዕቅድ በማሳደግ የኅብረተሰቡን ፍላጎት ማሟላት ነው ። የሠራተኛ ማኅበራትም ሕዝባዊ ድርጅቶች እንደመሆናቸው የፓርቲውን መመሪያ በመከተል እንደ ሌሎች ሕዝባዊ ድርጅቶች ለኅብረተሰቡ የጋራ ጥቅምና ዕድገት የሚታገሉ ናቸው ።

## የሠራተኛው መደብና የአርሶ አደሩ ኅብረት (የ—)

*(Alliance of the Working Class and the Peasantry)*

በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ ጨቋኝ መደቦች ለጋራ ዓላማቸው መሳካት በተለያዩ መንገዶች ኅብረት ይፈጥራሉ ። ይህ በታሪክ ተደጋግሞ የታየ ሐቅ ነው ። በዝባዥ መደቦች ለፀረ ሕዝብ ዓላማቸው እንደሚተባበሩ ሁሉ ጭቁን መደቦች ከሚደርስባቸው አስከፊ ብዝበዛና ጭቆና ለመላቀቅ በሚያደርጉት ፍልሚያ የትግል አንድነት ይፈጥራሉ ። በታሪክ ከታዩት የምዝብር መደቦች ኅብረት ትልቁና ታሪካዊ ተልዕኮ ያለው በወዝአደሩና በሠርቶ አደሩ ሕዝብ በተለይም አርሶ አደሩ በብዛት በሚገኝበት ሀገር በሠራተኛው መደብና በአርሶ አደሩ መካከል የሚመሠረተው ዘላቂነት ያለው ኅብረት ነው ።

በካፒታሊስትም ሆነ በከፊል ካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ሠራተኛው መደብ በግንባር ቀደም ፓርቲው መሪነት ከአርሶአደሩ መደብ ጋር የቀረበና የጠበቀ ኅብረት በመፍጠር አድኃሪ ሥርዓትን ገርስሶ ለመጣል ይታገላል ። በተለይ በፊውዶ ካፒታሊስት የዕድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ ሀገሮች ውስጥ የአርሶ አደሩ ቁጥር እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ ሠራተኛው መደብ ከኢምፔሪያሊዝም ፣ ከፊውዳሊዝምና ከቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ጋር የሚያደርገውን ትግል ብቻውን ለማካሄድና ሶሻሊዝምን ለመገንባት አይችልም ። በእንደዚህ ያሉ ኅብረተሰቦች ውስጥ አርሶ አደሩ የኅብረተሰቡ አብዛኛው ክፍል በመሆኑ በዚህ አብዮታዊ ትግል ከፍተኛ አብዮታዊ ሚና ይኖረዋል ። በሠራተኛው መደብ ፓርቲ የሚደራጅና የሚመራ በመሆኑም አርሶአደሩ ዋና አጋር ኃይሉም ይሆናል ። የሠራተኛው መደብ የፖለቲካ ሥልጣን መግለጫና የሶሻሊዝም መገንቢያ መሣሪያ የሆነው የወዝአደሩ የበላይነትም የሚመሠረተው በሁለቱ መደቦች ጠንካራ ኅብረትና የትግል አንድነት ላይ ነው ።

በሶሻሊስት ሥርዓት ውስጥ ያለው አርሶአደር በፊውዳልና በካፒታሊስት ሥርዓቶች ውስጥ ካለው አርሶአደር በንቃቱ ፣ በባህል የዕድገት ደረጃው ፣ በአኗኗሩና በፖለቲካ ተሳትፎው በአጠቃላይ በዓላማውና በተግባሩ በጣም የተለየ ነው ። የሶሻሊስቱ ሥርዓት አርሶአደር በሶሻሊስት የኅብረት ሥራ ማኅበራት የተደራጀ ፣ ሶሻሊስት የምርት ግንኙነት በገጠሩ መስፈን የሚታገልና በአዲስ ኅብረተሰብ ግንባታ ውስጥ በሚያደርገው ንቁ ተሳትፎ ከኋላ ቀር አስተሳሰብና ከግል ሀብት ቁራኛነት ተላቆ ወደወዝአደርነት እየተለወጠ የሚሄድ ነው ። ለዚህም የግንባር ቀደሙ የሠራተኛው መደብ አመራር ወሳኝ ነው ።

የሠራተኛው መደብና የአርሶ አደሩ ጥንካሬ ምንጭ በመካከላቸው የሚፈጠረው ኅብረትና የትግል አጋርነት ነው ። በትግል አርማቸው ላይ ደምቀው የሚታዩት ማጭድና መዶሻ የሚያመለክቱትም ይህንኑ መደባዊ ኅብረትና የትግል አጋርነት ነው ።

(ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ፣ ግንባርን ይመለከቷል ።)

## ሠርቶ አደር

*(Working People)*

ሠርቶ አደር የሚለው አጠራር በፋብሪካና መሰል ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞችንና ሌሎችንም ፣ ማለትም ሰውን ሳይበዘብዙ እንደችሎታቸው በተለያዩ የሥራ መስኮች ተሰማርተው በጥረታቸው የሚተዳደሩትንም የሚያቅፍ ነው ። በዚህ መሠረት ሠርቶ አደር የሚለው ቃል ባላቸው ችሎታ ሠርተው ደሞዝ የሚያገኙ ምሁራንን፣ የቢሮ ሠራተኞችን ፣ ጸሐፊዎችን ፣ መለዮ ለባሾችን፣ ሌላውን ሳይበዘብዙ ባላቸው የማምረቻ መሣሪያ በመጠቀም ሠርተው ራሳቸውን የሚያስተዳድሩ ገበሬዎችን ፣ የእጅ ጥበብ ሠራተኞችንና ሌሎችንም በተመሳሳይ ሁኔታ የሚተዳደሩትን ያጠቃልላል ።

በሕዝባዊ አብዮት ውስጥ ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ ዓላማ ከግብ መድረስ የሠራተኛው መደብ በራሱ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ ተደራጅቶ አመራር መስጠቱ ወሳኝ ነው ። ሠራተኛው መደብ የግል ሀብት ስሜት ያልተቆራኘው በመሆኑ ለብዝበዛና ለጭቆና ዋና መን

ሥኤ የሆነው የግል ሀብትና ከዚሁ ጋር ተያይዞ የመጣው የመደብ ጭቆና ጨርሶ እንዲወገድ በግንባር ቀደም የሚታገል ኃይል ነው ። ከሠርቶ አደሮችም ውስጥ ንቃተ ኅሊናቸውና ተግባራዊ ተሳትፎአቸው በፈቀደላቸው መጠንና የሠራተኛው መደብ ፓርቲ አባልነት መለኪያዎችን ባሟሉ ቁጥር የማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ አባላት የመሆን መብት አላቸው ። ስለዚህ የሠራተኛው መደብ ዓላማ የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ዓላማ ነው ።

(ወዝአደርን ይመለከቷል ።)

## ሥራ
## *(Labour)*

ሰው መሠረታዊ ፍላጐቶቹን ለማሟላት የተፈጥሮን ልዩ ልዩ ክፍሎች የሚለውጥበትና አዳዲስ ቁሶችን ወይም ነገሮችን የሚፈጥርበት ዓላማ ያለው የማምረት ሂደት ሥራ ይባላል ። ማርክስ ስለሥራ ምንነት ሲያብራራ ሥራ በመጀመሪያ ሰውና ተፈጥሮ የሚሳተፉበት ፣ ሰው በራሱ አነሣሽነት በእርሱና በተፈጥሮ መካከል የሚፈጠረውን ተደጋጋሚ ቁሳዊ ድርጊት የሚቆጣጠርበትና የሚያርቅበት ሂደት መሆኑን ገልጿል ። ሰው የተፈጥሮ የራሷ አንዱ ኃይል ሆኖ ራሱ መልሶ ከተፈጥሮ ጋር በመታገል የተፈጥሮን ልዩ ልዩ ክፍሎች (ፍሬዎች) ለራሱ ፍላጐቶች ማርኪያ ለማዘጋጀት ክንዶቹንና ቅልጥሞቹን ፣ አእምሮውንና እጆቹን ፣ የሰውነቱን ተፈጥሮአዊ ኃይል ያንቀሳቅሳል ይላል ። ሥራ ለሰው ልጅ የሰውነት ቅርፅ የሰጠውና የህልውናው መሠረት መሆኑን በማስገንዘብ ኤንግልስ ሰውን ሰው ያደረገው ሥራ መሆኑን ተናግሯል ። በመሆኑም ሥራ ፣ ሰው ከእንስሳ የሚለይበት ልዩ ባሕርዩ ነው ። ሥራ በተመረተ ሸቀጥ ወይም ዕቃ ውስጥ የተጠናቀረ ያለቀ ድርጊት ከመሆኑም በላይ የእሴት ፈጣሪም ነው ። የሸቀጥ ምርት ባለበትና በተስፋፋበት ሁኔታ ሥራ በተጨባጭና በረቂቅ ፣ በግልና በማኅበራዊ ገጽታው ይከሰታል ።

ሰዎች ለሥራ ያላቸው አመለካከትና ግምት እንደየሥርዓተ ማኅበሩ ይለያያል ። በዝባዥ መደቦች ባሉበት ሁኔታ ሥራ ለጭቁን መደቦች የተተወና የተናቀ ነው ። በተለይ በባሪያው አሳዳሪና በፊውዳሉ ሥርዓቶች ውስጥ ይህ ሁኔታ በገሃድ የታየ ነው ። ለምሳሌ በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የግብርናና የእደ ጥበብ ሥራ የኅብረተሰቡ ህልውና የተመሠረተበት ሆኖ ሳለ የፊውዳሉ ሥርዓት ባህልና አመለካከት እነዚህን አምራች ክፍሎች ዝቅ አድርጐ የሚያይ ፣ ገበሬውን አፈር ገፊ ፣ እደ ጠቢቡን ጠይብ ፣ ቡዳ በማለት የሚያንቋሽሽ ነበር ። የሥራን ክቡርነት የባህላችን አካል ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት የተደረገው ከአብዮታችን ፍንዳታ ወዲህ ነው ።

በካፒታሊስት ሥርዓት የሀብት ፈጣሪ የወዝአደሩ መደብ ሆኖ ሳለ የቡርዧው መደብ የምርት መገልገያዎች ባለቤት በመሆኑ የወዝአደሩን የሥራ ኃይል ይበዘብዛል ። ቡርዧዚው ለሀብት ከፍተኛ ፍቅርና አምልኮት ያለው ሲሆን ይህንን ሀብት ለፈጠረው ወዝ አደር ግን ያለው ግምት ዝቅተኛ ነው ። የኮሚኒስት ኅብረተሰብ የመጀመሪያው ደረጃ የሆነው ሶሻሊዝም የሥራ ክቡርነት የሚረጋገጥበት ፣ ወዝአደሩም ከብዝበዛ ነፃ የሚሆንበት ፣ "ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያንዳንዱ እንደሥራው" የሚለው መርህ ተግባራዊ የሚሆንበት ሥርዓት ነው ። ሥራ ለመኖር ሲባል በግዴታ የሚከናወን ድርጊት መሆን ቀርቶ የሕይወት ተቀዳሚ ፍላጐት የሚሆነው የሰዎች እውነተኛ እኩልነትና ነፃነት በሚረጋገጥበት በኮሚኒስት ኅብረተሰብ ይሆናል ።

(ተጨባጭ ሥራን ፣ ረቂቅ ሥራን ፣ ሥራን፣ የሥራ ኃይልን ይመለከቷል ።)

## ሥራ ኃይል (የ—)
## *(Labour Power)*

በምርት ሂደት ውስጥ ሰው ለሥራ ያለው አካላዊና አእምሮአዊ ችሎታ የሥራ ኃይል ይባላል ። ይህ ለመሥራት ያለ ችሎታ በማንኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ ቁሳዊ ሀብትን ለማምረት ዓይነተኛና አስፈላጊ ወይም ወሳኝ ነገር ነው ።

የሥራ ኃይልና ሥራ የተለያዩ ነገሮች ናቸው ። ሥራ በሸቀጥ ውስጥ በአጠቃላይ

የተጠናቀረና ያለቀ ድርጊት ሲሆን የሥራ ኃይል ግን ለመሥራት የተዘጋጀ ፣ የሁኔታዎችን መሟላት የሚጠብቅ ያልተፈጸመ ድርጊት ነው ። ወዝአደሩ ለካፒታሊስቱ የሚሸጠው ሥራውን ሳይሆን ከሌሎች የምርት መገልገያዎች ጋር ሲዋሃድ እሴት ብሎም ተረፈ እሴት የሚፈጥረውን የሥራ ኃይሉን ነው ።

ይህ በሥራና በሥራ ኃይል መካከል ያለው ልዩነት በካፒታሊስት ሥርዓት የትርፍ ሁሉ ምንጭ ምንድን ነው የሚለው ጥያቄ የሚፈታበት ቁልፍ የሆነ ጽንሰ ሐሳብ ነው ። በሁለቱ ቃላት መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት ለመጀመሪያ ጊዜ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በማብራራት የካፒታሊዝምን ምሥጢር ይፋ ያወጣው ካርል ማርክስ ሲሆን ይህም ለኢኮኖሚ ሳይንስ ካደረጋቸው አስተዋጽኦዎች መካከል ከፍተኛውን ቦታ የሚይዝ ነው ።

የሥራ ኃይል ሸቀጥ ሊሆን የበቃው በካፒታሊስት ሥርዓት ነው ። በዚህ ሥርዓት ውስጥ ሸቀጥ ሊሆን የቻለበትም ምክንያት 1ኛ/ ወዝአደሩ ከምርት መገልገያ ባለቤትነት በመወገዱና ለመኖር የሥራ ኃይሉን ለመሸጥ በመገደዱ ፣ 2ኛ/ ወዝአደሩ በግለሰብ ደረጃ የሥራ ኃይሉን ለፈለገው ቀጣሪ ለመሸጥ ወይም ላለመሸጥ "መብት"ና "ነፃነት" ያለው በመሆኑ ነው ።

በካፒታሊስት ሥርዓት የሥራ ኃይልን ሸቀጥ የሚያደርጉ ሁኔታዎች በተፈጥሮ ሕግ አስገዳጅነት የመጡ ሳይሆኑ የፊውዳሉ ሥርዓት መፈራረስ ያስከተላቸው የኢኮኖሚ ይዞታ ለውጦችና የኅብረተሰብ የታሪክ ዕድገት ውጤቶች ሆነው ነው ።

በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የሥራ ኃይል ሸቀጥ እንደመሆኑ ማናቸውም ሸቀጥ የሚኖሩት ጠባዮች ይኖሩታል ። እነርሱም የሥራ ኃይል የጠቀሜታ እሴትና የሥራ ኃይል የልውውጥ እሴት ናቸው ።

በሶሻሊስት ሥርዓት ውስጥ የምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነትና የቅጥር ሥራ ስለማይኖር የሥራ ኃይል ሸቀጥ መሆኑ ያከትማል ።

(የሥራ ኃይል የጠቀሜታ እሴትን ፣ የሥራ ኃይል (የልውውጥ) እሴትን ይመለከቷል ።)

## ሥራ ኃይል (የልውውጥ) እሴት (የ-)
## (*Exchnge Value of Labaur Power*)

የሥራ ኃይል እሴት የሚወሰነው አንድን ወዝአደር በሕይወት ለማቆየትና እንዲሠራ ለማድረግ የሚያስችሉትን የራሱንና የቤተሰቡን መሠረታዊ የሆኑ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ፍላጎቶች ለማርካት እንዲሁም በሙያ የሠለጠነበትን ወጪ ለመሸፈን በሚያስፈልጉት ነገሮች እሴት ነው ።

የሥራ ኃይል እሴት አንድ የተወሰነ ሀገር በደረሰበት ታሪካዊ የዕድገት ደረጃ የወዝአደሩን መደብ ባህላዊ ፍላጎት ለማርካት የሚያስፈልጉ ነገሮችን እሴትም ይጨምራል ። ማርክስ ይህንኑ ጉዳይ አስመልክቶ ሲጽፍ እንደሌሎች ሸቀጦች ሳይሆን የሥራ ኃይሉን እሴት በመወሰኑ ረገድ ታሪካዊና ሥነ ምግባራዊ ሁኔታዎች እንደሚጨመሩበት አስረድቷል ።

እንደማናቸውም ሸቀጥ በካፒታሊስት ሥርዓት የሥራ ኃይል እሴት የሚወሰነው ይህንኑ የሥራ ኃይል በማደስ ወዝአደሩ እየሠራ እንዲቆይ ለማድረግ የሚያስችሉ ሸቀጦችንና አገልግሎቶችን ለማግኘት መሥራት በሚያስፈልገው ማኅበራዊ የሥራ ጊዜ መጠን ነው። በሌላ አነጋገር የሥራ ኃይል እሴት የሚወሰነው ለወዝአደሩና ለቤተሰቡ ኑሮ አስፈላጊና መሠረታዊ በሆኑ ሸቀጦች እሴት ነው ።

የእነዚህ ሸቀጦች እሴት ደግሞ ከቴክኖሎጂ ዕድገትና ከምርታማነት መጨመር ጋር የሚቀንስ በመሆኑ ፣ በዚያው መጠን የሥራ ኃይል፡ እሴትም ይቀንሳል ። በሌላ በኩል በተለይ በካፒታሊዝም የመጀመሪያ የዕድገት ደረጃ እንደታየው ፣ የሴቶችና የሕፃናት በምርት መስክ በብዛት መሰማራት የቤተሰብን ገቢ በማሳደግ የሥራ ኃይል እሴትን የመቀነስ አዝማሚያ አሳይቶ ነበር ።

የሥራ ኃይል እሴት በገንዘብ ሲተመን የሥራ ኃይል ዋጋን የሚያስገኝ ሲሆን በካፒታሊዝም ይህ የሥራ ኃይል ዋጋ ምንዳ በመባል ይታወቃል ።

## ሥራ ኃይል የጠቀሜታ እሴት (የ—)
*(Use Value of Labour Power)*

የሥራ ኃይል የጠቀሜታ እሴት የሥራ ኃይሉን የሚሸጠው ወዝአደር በሂደተ ምርት ውስጥ ለካፒታሊስቱ ተረፈ እሴት የመፍጠር ችሎታው ነው ። ለምሳሌ አንድ ወዝአደር በቀን ስምንት ሰዓት ቢሠራና ከስምንቱ ሰዓት ውስጥ አራቱ ለራሱና ለቤተሰቡ ኑሮ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለማግኘት ወይም የራሱን እሴት ለመተካት የሚሠራበት ፣ የተቀረውም አራት ሰዓት ተረፈ እሴት የሚፈጥርበት ጊዜ ቢሆን ይህ ተረፈ እሴት የሚፈጥርበት ጊዜ የወዝአደሩን የሥራ ኃይል የጠቀሜታ እሴት ያስገኛል ። የተረፈ እሴት ብሎም የትርፍ ምንጭ በመሆን ከምርት መገልገያዎች በግል ከመያዝ ጋር ለካፒታሊስቱ ብዝበዛ መሠረት የሆነውም ይኸው የሥራ ኃይል ጠባይ ነው ።

(የጠቀሜታ እሴትን ፣ የሥራ ኃይል የልውውጥ እሴትን ይመለከቷል ።)

## ሥራ መገልገያዎች (የ—)
**(*Means of Labour*)**

ሰው የሥራ ተገብሮችን በሂደተ ምርት ውስጥ ለመለወጥ ወይም ለማምረት በቀጥታ የሚጠቀምባቸው የማምረቻ መሣሪያዎችና በቀጥታ በሂደተ ምርት ውስጥ ባይጠቀምባቸውም ለምርት መከናወን አስፈላጊ የሆኑ መገልገያ ነገሮች ሁሉ የሥራ መገልገያዎች ይባላሉ ። የሥራ መገልገያዎች በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀሱትንና ሌሎችንም የማምረቻ መሣሪያዎችን ፣ ለምርት ተግባር የሚያገለግሉ ሕንፃዎችን ፣ መሬትን ፣ መንገድን ፣ መጋዘንን ፣ የትራንስፖርት መገልገያዎችን ፣ የመስኖ መገልገያዎችን ፣ የኃይል ምንጭንና የመሳሰሉትን ያጠቃልላሉ ። ለምሳሌ በሀገራችን አብዛኛው ገበሬ የሚጠቀምባቸው የማምረቻ መሣሪያዎች በሬ ፣ ሞፈር ፣ ቀንበር ፣ ወገል ፣ ማረሻ ወዘተ... ሲሆኑ በቀጥታ ለማምረት ተግባር ባይውሉም ለሂደተ ምርት መከናወን የሚያስፈልጉ ለምሳሌ ስልቻና ጐተራ ፣ አህያና የመሳሰሉት አሉ ። እነዚህም በአንድነት የገበሬ የሥራ መገልገያዎች ናቸው ።

## ሥራ ማቆም አድማ (የ—)
*(Strike)*

ወዝአደሮች አንድን የሥራ ሁኔታ በመቃወም ያ ሁኔታ ካልተለወጠ አንሠራም በማለት የሚወስዱት አቋም የሥራ ማቆም አድማ ይባላል ። አድማ በካፒታሊስት ሀገሮች የሚገኙ ወዝአደሮች በላያቸው የተጣለውን ጭቆናና ብዝበዛ ለመዋጋት ከሚጠቀሙባቸው የትግል መሣሪያዎች አንዱ ነው ።

የወዝአደሩ የሥራ ማቆም አድማ ዓላማ ኢኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ ሊሆን ይችላል ። የሥራ ማቆም አድማ ከስድስት መቶ ዓመት በላይ ታሪክ አለው ። ለምሳሌ በአውሮፓ የመጀመሪያው የሥራ ማቆም አድማ የተካሄደው በ1345 በኢጣሊያ በፍሎሬንስ ከተማ ውስጥ በሱፍ ፀጉር አበጣሪነት ይሠሩ በነበሩ ሠራተኞች ሲሆን የተመራውም ቺዮቶ ብራንዲኒ በተባለ ወዝአደር ነበር ። ይህ ወዝአደር ለመደቡ ሲታገል በጊዜው በነበሩ ባለሥልጣኖች ተረሽኗል ።

ከ16ኛው እስከ 18ኛው ምዕት ዓመት የተካሄዱ የሥራ ማቆም አድማዎች በይበልጥ ኢኮኖሚያዊና ግብታዊ ነበሩ ። እያደር ግን ወዝአደሩ ንቃተ ኅሊናው እየዳበረና ዲሲፕሊኑ እየጠነከረ ሲሄድ የሥራ ማቆም አድማዎችም በይበልጥ እየተደራጁና የፖለቲካ ዓላማም እየያዙ መጥተዋል ።

ለምሳሌ በ19ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ላይ በእንግሊዝ የወዝአደሩ የሥራ ማቆም አድማ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር ። በሩሲያም ከተካሄዱት ዓበይት የወዝአደሩ አድማዎች አንዱ በጥቅምት 1835 በካዛን ውስጥ ኦስኪን በተባለው ፋብሪካ ይሠሩ የነበሩ ወዝአደሮች ያካሄዱት ነው ።

ከልምድ ከተገኙ የሥራ ማቆም አድማ ስልቶች ዋና ዋናዎቹ በአንድ ድርጅት ውስጥ በየክፍሉ አልፎ አልፎ ሥራ ማቆምና ዕንቅፋት መፍጠር ፣ በአጠቃላይ ከሥራ ቦታ ሳይለዩ ሥራን ማቀዝቀዝ ፣ የሥራ ቦታውን (ለምሳሌ ፋብሪካውን) መያዝና ለተወሰነ ጊዜ በወዝአደሩ ቁጥጥር ሥር ማዋል ፣ አሠሪውን አካል ሳያስታውቁ ከሥራው ቦታ ድንገት መውጣት ፣ የሌላ ቦታ ወዝአደር

አድማ ሲያደርግ የድጋፍ አድማ ማካሄድ ወዘተ ... ናቸው ። እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ በየዘመናቱ የተካሄዱ የወዝአደሩ አድማዎች ለወዝአደር የሠራተኛ ማኅበራት መፈጠር ምክንያት ሲሆኑ ለሠራተኛው ሕዝብ የፖለቲካ ፓርቲዎች መከሰትም አመች ሁኔታን ፈጥረዋል ። በተጨማሪም የወዝአደሩን መደባዊ ንቃተ ኅሊና ከፍ በማድረግ ለሶሻሊስታዊ ርዕዮተዓለም አዘጋጅተውታል ።

ቡርዧዚው አድማዎችን ለማከሸፍ ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋል ። ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ያፍናል ፤ በኃይል ይጠቀማል ፤ ፀረ አድማ ደንቦችን ያወጣል ። የቡርዧውም ርዕዮተዓለማውያን አድማን ወቅቱ ያለፈበት ፀረ ዕድገትና ኅብረተሰብን የሚጐዳ ተግባር ነው በማለት ወዝአደሩን ከትግሉ ለማዘናጋትና በወዝአደሩና በካፒታሊስቱ መካከል ያለውን ቅራኔ ለማድበስበስ ይጥራሉ ። ማርክሳዊ ምሁራን ግን አድማ በወዝአደሩና በካፒታሊስቱ መካከል ያለውን መደባዊ ቅራኔ ለማጉላትና ቡርዧዚውን ለመዋጋት የሚረዳ ዓይነተኛ መሣሪያ ነው ብለው ያስተምራሉ ።

(ፖለቲካዊ የሥራ ማቆም አድማን ይመለከቷል ።)

## ሥራ ማከናወኛዎች (የ—)
*(Instruments of Labour)*

ከሥራ መገልገያዎች መካከል የሰዎች ፈጠራ የታከለባቸውና በምርት ሥራ ላይ ዋነኛ ግልጋሎት ያላቸው መሣሪያዎች ለምሳሌ የፋብሪካ ማሽኖች ፣ የእርሻ መሣሪያዎች ወዘተ... የሥራ ማከናወኛዎች ይባላሉ ። ሰው በሂደተ ምርት ውስጥ የሚታገዝባቸውና በእርሱና በሥራ ተገብሮች መካከል አድርጎ የሚጠቀምባቸው የማምረቻ መሣሪያዎች የሥራ ማከናወኛዎች ናቸው ። የሰው ልጅ ራሱን ከአውሬ ለመከላከልና የሚፈልጋቸውን ነገሮች ለመቁረጫና ለመፍለጫ የሠራቸው የድንጋይ መጥረቢያዎችና የእንጨት ቀስትና ጦር ከተፈጥሮ ያገኛቸውን ቁሶች በማሻሻል የሠራቸው የመጀመሪያዎቹ የማምረቻ መሣሪያዎች ናቸው ። የማምረቻ መሣሪያዎች የሰው ልጅ የደረሰበትን ቁሳዊ የዕድገት ደረጃና በተፈጥሮ ላይ ያለውንም የበላይነት የሚያመለክቱ በመሆናቸው ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ ናቸው ። ካርል ማርክስ እንዳለው የተለያየ የኅብረተሰብ የኢኮኖሚ ዘመን አንዱ ከሌላው የሚለየው በጊዜው በተመረተው ምርት ሳይሆን በማምረቻ መሣሪያዎች ዓይነት ነው ። ለምሳሌ በቆሎ በበሬ ወይም በትራክተር ሊመረት ይችላል ። ስለሆነም የማምረቻ መሣሪያዎች ዓይነት ኅብረተሰቡ በተፈጥሮ ላይ ያለውን የበላይነት ደረጃና የአምራቹንም ሕዝብ ምርታማነት ያመለክታል ።

(የሥራ መገልገያዎችን ይመለከቷል ።)

## ሥራ ምርታማነት (የ—)
*(Productivity of Labour)*

የሥራ ምርታማነት በአንድ በተወሰነ የሥራ ጊዜ በአንድ አምራች የሚመረቱት የጠቀሜታ እሴቶች መጠን ማለት ነው ። ለምሳሌ አንድ አምራች በአንድ የሥራ ሰዓት ውስጥ አንድ ጥንድ ጫማ ቢያመርት ይህ የሥራ ምርታማነቱን ያሳያል ። በአንድ በተወሰነ ወቅት በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ያለን የሥራ ምርታማነት ከሚወስኑት ሁኔታዎች ውስጥ የሚከተሉት ይገኛሉ ።

ሀ. የአምራቾቹ አማካይ የምርት ሙያ ደረጃ ።

ለ. የሳይንስና የቴክኖሎጂ የዕድገት ደረጃና በሂደተ ምርት ውስጥ ያለው ተግባራዊነት ፣

ሐ. የምርት ሥራው ማኅበራዊ አደረጃጀት ፣

እነዚህ ሁኔታዎች እየተሻሻሉና እየዳበሩ በሄዱ ቁጥር የሥራ ምርታማነት ያድጋል ። የሥራ ምርታማነት ማደግ አንድ ምርት ለማምረት የሚፈጀውን ማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ሰዓት መቀነስንና በተመረተው ምርት ውስጥ የተጠናቀረው እሴት ማነስን ያስከትላል ። በምሳሌ ለመግለጽ ቀደም ሲል በነበረ የሥራ ምርታማነት አንድ አምራች በአንድ ሰዓት ውስጥ አንድ ጥንድ ጫማ ያመርት የነበረ ቢሆንና አሁን ባደገ የሥራ ምርታማነት ሁኔታ በአንድ የሥራ ሰዓት ሁለት

ጥንድ ጫማ ቢያመርት አሁን በያንዳንዱ ጥንድ ጫማ ውስጥ ያለው እሴት የግማሽ ሰዓት እሴት ይሆናል ። ቀድሞ ግን በአንድ ጥንድ ጫማ ውስጥ የነበረው እሴት የአንድ ሰዓት እሴት ነበር ። ስለዚህ በአንድ ምርት ውስጥ የተጠናቀረው እሴት እያነሰ መሄዱ የሥራ ምርታማነት ማደጉን ያመለክታል ።

የሥራ ምርታማነት የዕድገት መጠን እንደየስልተ ምርቱ የተለያየ ነው ። በጥንታዊ ጋርዮሽ ስልተ ምርት ውስጥ የሥራ ምርታማነት መጠን እጅግ ዝቅተኛ ነበር ። ዘመናዊ የማሽን የምርት ሥራ በተከሰተበት ወቅት የሥራ ምርታማነት ዕድገት ከፍተኛ እመርታ አሳይቷል ። በዝባዥ መደቦች ባሉበት ኅብረተሰብ ውስጥ ከሥራ ምርታማነት ዕድገት የሚገኙ ውጤቶች በቀጥታ የበዝባዥ መደቦችን ድሎትና ጥቅም ለማሟላት ሲውሉ በሶሻሊስት ሥርዓት ግን የሠራተኛውን ሕዝብ እያደገ የሚሄድ ፍላጐት በይበልጥ ለማሟላት ያገለግላሉ ።

የካፒታሊስት ስልተ ምርት ከቀደምት ስልተ ምርቶች በተሻለ ሁኔታ የምርት ኃይሎችና የሥራ ምርታማነት የሚያድጉበትን ሁኔታ ቢፈጥርም ሥራ አጥነትን ስለሚያስከትልና የተወሰኑ የምርት መገልገያዎችም ማምረት ከሚችሉት በታች እንዲያመርቱ ስለሚያደርግ አጠቃላይ የሥራ ምርታማነትን ዕድገት ያቀጭጫል ። የሶሻሊስት ስልተ ምርት ግን አጠቃላይ የሥራ ምርታማነት ዕድገት እንዲያገኝ አስፈላጊና አመቺ ሁኔታዎችን ያሟላል ። በዚህም የሥራ ምርታማነት በየጊዜው እያደገ እንዲሄድ ያደርጋል ።

## ሥራ ተገብሮች (የ—)
*(Objects of Labour)*

የሰው ልጅ በጉልበቱና በመሣሪያዎች አማካይነት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለማምረት በሂደተ ምርት ውስጥ ወደ ዕቃነት የሚለውጣቸውና የሥራ ኃይሉን የሚያውልባቸው ተፈጥሮአዊ ሆኑ ሰው ሠራሽ ቁሶች ሁሉ የሥራ ተገብሮች ይባላሉ ። የሥራ ተገብሮች በሦስት መልክ የሚገኙ ቁሶችን ያጠቃልላሉ ። እነዚህም ፤

1. የሰው ጉልበት ሳይፈሰባቸው በተፈጥሮ የምናገኛቸው ቁሶች (ለምሳሌ እፈርና ውሃ) ፤
2. ባሕርያቸውን በሥራ ኃይል ሳንለውጥ ከአካባቢያችን በመቁረጥ ፣ በመቆፈር ፣ በማሥገር ወዘተ... የምናገኛቸው ቁሶች (ለምሳሌ ፣ እንጨት ፣ ማዕድንና አሣ) ፤
3. የሰው ጉልበት የፈሰሰባቸውና ዕቃ ለማምረት የምንጠቀምባቸው ጥሬ ቁሶች ፣ ለምሳሌ ቁሳዊ ነገሮችን ለማምረት የሚያገለግሉ የሲንቴቲክ ዕቃዎች ናቸው ።

## ሥራ አጥነት
*(Unemployment)*

ሥራ አጥነት ከካፒታሊዝም ስልተ ምርት ውስጣዊ ባሕርይ የሚመነጭና ከሠርቶ አደሩ ሕዝብ የተወሰነው ክፍል ሊሰማራ የሚችልበት ሥራ ከማጣቱ የተነሣ ተረፈ ሕዝብ የሚሆንበት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ክስተት ነው ። የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕድገት በካፒታሊስት ክምችት ሂደት ውስጥ ከሥራ ኃይል ይልቅ የተሻሻሉ ዘመናዊ የምርት መገልገያ መሣሪያዎች ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ስለሚፈጥር አንፃራዊ በሆነ መንገድ ለሥራ ኃይል ያለው ፍላጐት እንዲቀነስና በኢኮኖሚው ውስጥ ሥራ ለማግኘት የማይችል ተረፈ ሕዝብ እንዲፈጠር ያደርጋል ። በተጨማሪም የሥራ ሰዓት መርዘምና የሥራ ዕምቀት መጨመር ለሥራ አጦች ቁጥር መበርከት አስተዋጽኦ አለው ።

በካፒታሊዝም ውስጥ ይህ ክስተት ላይ ላዩን ሲታይ በካፒታሊስት የሥራ ኃይል ገበያ ውስጥ በሥራ ኃይል ፍላጐትና በሥራ ኃይል አቅርቦት መካከል የሚፈጠር አለመጣጣም ሲሆን መሠረታዊው ምክንያቱ ግን ከካፒታሊዝም ውስጣዊ ቅራኔ የሚመነጭ ነው ። ቡርዧዚዎች ከፍተኛ ትርፍ ለማግኘት ያላቸው ፍላጐትና በመካከላቸው ያለው ውድድር በየጊዜው የተሻሻሉ መሣሪያዎችን ሥራ ላይ በማዋል የወዝአደሩን ቁጥር ለመቀነስ ፣ የምንዳ ወጭያቸውን ለማሳነስ እንዲጥሩ ስለሚገፋፋቸው ይህ እርምጃ በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ያለው የሥራ ኃይል ሙሉ በሙሉ በሥራ ላይ ለመሰማራት የማይችልበትንና ሥራ አጥነት የሚከሰትበትን ሁኔታ ይፈጥራል ።

በካፒታሊዝም ውስጥ በየጊዜው የሚፈጠረው የኢኮኖሚ ቀውስ የሥራ ኃይል ፍላጐት በበለጠ እንዲቀንስና የሥራ አጦች ቁጥር እንዲበረከት አስተዋጽኦ ያደርጋል ። የሥራ አጦች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበረከተ መሄድም በሥራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ወዝአደሮች ምንዳ እንዲቀንስ ፣ የሚካሄድባቸው ብዝበዛ እያደገ እንዲሄድ ያደርጋል ። የኑሮና የሥራ ሁኔታቸው አንፃራዊ በሆነ መንገድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያቆለቆለ ይሄዳል ። ስለዚህም ሥራ አጥነት የካፒታሊስት ስልተ ምርት ውጤት ብቻ ሳይሆን ለካፒታሊስት ስልተ ምርት መኖርም እጅግ አስፈላጊ ሁኔታ ነው ።

ወዝአደሩ ሥራ አጥነት የሚያስከትለውን ችግር ለመቀነስ በተለያዩ መንገዶች ታግሏል ፤ በመታገልም ላይ ይገኛል ። ይሁንና የትግሉ ውጤት ፍሬያማ የሚሆነው ሥራ አጥነት በሚያስከትላቸው ችግሮች ላይ ብቻ በማተኮር ሳይሆን ለሥራ አጥነት መንሥኤ የሆነውን ካፒታሊስታዊ የምርት ግንኙነት ማስወገድ ሲቻል ነው ።

ሥራ አጥነት በኋላቀር ሀገሮችም ውስጥ ጐልተው ከሚታዩት ማኅበራዊ ችግሮች መካከል አንዱ ነው ። የነዚህ ሀገሮች የምርት መገልገያ መሣሪያዎች ከዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ከመሆናቸውም የተነሣ ያላቸውን አምራች የሰው ኃይል ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ ለማሰማራት አለመቻላቸው አንዱ የሥራ አጥነት ምንጭ ነው ። ከዚህም በላይ ኢኮኖሚያቸው በኢምፔሪያሊስቶች ተፅዕኖ ሥር የሚገኝ በመሆኑ የሚጠቀሙበት ቴክኖሎጂ ይህን ብሔራዊና ማኅበራዊ ችግራቸውን ከማቃለል አኳያ የተቀየሰ ባለመሆኑ የሥራ አጥነት ችግር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ሲሄድ ይታያል ።

የሥራ አጥነት ችግር ለዘለቄታው የሚወገደው የምርት መገልገያ መሣሪያዎች የሕዝብ በሚሆኑበትና የሥራ ኃይል ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ሊውል በሚችልበት በሶሻሊዝም ውስጥ ብቻ ነው ።

## ሥራ ዕምቀት (የ—)
(*Intensity of Labour*)

የሥራ ዕምቀት በአንድ በተወሰነ የሥራ ጊዜ የሚፈስ የሥራ ኃይል መጠን ነው ።

በአንድ በተወሰነ የሥራ ጊዜ ውስጥ የሚፈሰው የሥራ ኃይል ሲጨምር የሥራ ዕምቀት ጨመረ እንላለን ። በአንፃሩ ደግሞ በአንድ በተወሰነ የሥራ ጊዜ ውስጥ የሚፈሰው የሥራ ኃይል መጠን ሲቀንስ የሥራ ዕምቀት ቀነሰ ይባላል ።

የሥራ ዕምቀት በማሳደግ የምርት ውጤትን ከፍ ማድረግ ይቻላል ። ለምሳሌ አንድ አምራች በአንድ የሥራ ሰዓት በአማካይ የሥራ ዕምቀት ደረጃ አንድ ጥንድ ጫማ ያመርታል እንበል ። በሌላ ጊዜ ደግሞ በአንድ የሥራ ሰዓት ውስጥ የሥራውን ዕምቀት ደረጃ በማሳደግ ሁለት ጥንድ ጫማ ያመርታል እንበል ። በዚህ ዓይነት የሥራ ዕምቀቱን በማሳደግ በዚያው በአንድ ሰዓት ውስጥ ተጨማሪ ጥንድ ጫማ ሊያመርት ችሏል ። በዚህ ምሳሌ መሠረት በአንድ ጥንድ ጫማ ውስጥ የተጠናቀረው እሴት በአማካይ የሥራ ዕምቀት ደረጃ የአንድ ሰዓት እሴት ነው ። በሁለቱ ጥንድ ጫማ ውስጥ የተጠናቀረው እሴት ደግሞ ምንም እንኳን ሥራው የተከናወነው በአንድ ሰዓት ውስጥ ቢሆን ፣ የሥራው ዕምቀት ደረጃ በመጨመሩ በአማካይ የሥራ ዕምቀት ደረጃ ሲሰላ የሁለት ሰዓት እሴት ነው ። ስለዚህም የሥራ ዕምቀትን በማሳደግ የሚገኘው ጠቅላላ እሴት መጠን ሲጨምር በእያንዳንዱ ምርት ውስጥ የተጠናቀረው እሴት መጠን ግን አይለወጥም ። ካፒታሊስቶች የሥራ ዕምቀትን በማሳደግ ወዝአደሩን እያደከሙ ያሠሩታል ። የሚፈጠረውንም አጠቃላይ የእሴት መጠን በማሳደግ ብዝበዛውን ያባብሱታል ። በዚህ ዓይነት ወዝአደሩ በካፒታሊስቶች የሚደረግበት ብዝበዛ የአእምሮ ጉዳት በቀላሉ እንዲደርስበት ያደርጋል ። እነዚህን ሁሉ ለመቋቋምም የተለየዩ ትግሎች ያካሂዳል ።

በሶሻሊስት ሥርዓት እያንዳንዱ አምራች ዜጋ የላቡ ውጤት ተጠቃሚ ራሱ መሆኑን ስለሚያውቅና ንቃተ ኅሊናውም ከፍተኛ በመሆኑ ተግባሩን በትጋት ያከናውናል ። ሆኖም ከሥራ ዕምቀት ከመጠን በላይ ማደግ የተነሣ የአካልና የአእምሮ ጉድለት እንዳይደርስበት አስፈላጊው ጥንቃቄ ይደረጋል ። ስለዚህም በሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የሥራ ዕምቀቱ መጠን ከተወሰነ ደረጃ በላይ እንዲያልፍ፡ አይደረግም ።

በሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ

በዘመናዊና በሳይንሳዊ የምርት ሥራ አደረጃጀት ስልቶችና የአመራረት ዘዴዎች በመጠቀም እያንዳንዱ አምራች የሥራ ዕምቀቱን ከመጠን በላይ ሳያሳድግ የምርት ውጤት መጠኑን ያሳድጋል ።

## ሥራ ክፍፍል (የ—)
*(Division of Labour)*

በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የተለያዩ የሥራ ዓይነቶች መከናወን የኅብረተሰቡን ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጐት ለማሟላት ያስችላል ። በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የተለያዩ የሥራ ዓይነቶች መስፋፋት በኅብረተሰቡ ውስጥ ከተደረሰበት የምርት ኃይሎች ዕድገት ደረጃ ጋር የተያያዘ ነው ። ከፍተኛ የምርት ኃይሎች የዕድገት ደረጃ በሚገኝበት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የሥራ ዓይነቶች እጅግ በጣም ብዙ ናቸው ።

የኅብረተሰብ ዕድገት ደረጃ እጅግ ዝቅተኛ በሆነበት ሁኔታ የነበረው የሥራ ክፍፍል የተፈጥሮ የሥራ ክፍፍል ነበር ፤ ይህም በፆታና በዕድሜ ላይ የተመሠረተ ነበር ። በዚያን ወቅት ይህ ዓይነቱ የሥራ ክፍፍል የሥራ ምርታማነትን ለማሳደግ ዋና መሣሪያ ሆኖ አገልግሏል ። ከተፈጥሮ የሥራ ክፍፍል በኋላ የተከሰቱት የሥራ ክፍፍሎች በየደረጃው የምርት ኃይሎች ዕድገት አስገኝተዋል ፤ የሥራ ምርታማነትንም አስከትለዋል ።

የመጀመሪያው ዋነኛ ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል የከብት አርቢዎች ከእርሻ ተለይተው የወጡበት ሁኔታ ነበር ። ሁለተኛው ዋነኛ ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል ደግሞ የእደጥበብ አምራቾች ከእርሻ ሥራ ተለይተው የወጡበት ሲሆን ሦስተኛው ዋነኛ ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል የንግድ ሥራ ከምርት ሥራ ተለይቶ የወጣበት ሁኔታ ነበር ። በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የምርት መገልገያዎችን በግል ባለቤትነት መያዝ ከተጀመረ በኋላ ኪታከሉት ልዩ ልዩ ማኅበራዊ ለውጦች ጋር ተያይዞ የአእምሮና የጉልበት ሥራ መለየትም ተከትሏል ። እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የሥራ ክፍፍሎች እያንዳንዳቸው የሥራ ምርታማነትን በማሳደግ በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚደረግ የሸቀጥ ልውውጥ በኅብረተሰቡ ውስጥ የሥራ ክፍፍል መኖሩን ያመለክታል ። በኅብረተሰብ ውስጥ የሥራ ክፍፍል መኖር ደግሞ ለምርት ዕድገት ወሳኝ ከመሆኑም በላይ የኅብረተሰቡን ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጐት ለማሟላት ያስችላል ። የምርት ሥራ ክፍፍል በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ በአንድ ሀገርና በሌላ ሀገር ወይም በአንድ ሀገርና በብዙ ሀገሮች መካከል ሊደረግ ይችላል ።

በካፒታሊስቱና በሶሻሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ያለው ዓለምአቀፍ የሥራ ክፍፍል ይዞታ የተለያየ ነው ። በካፒታሊስቱ ዓለም ውስጥ ያለው የሥራ ክፍፍል ሀብታሞችንና የበለጸጉትን ካፒታሊስት ሀገሮች የበለጠ ሀብታም እያደረገና እያዳበረ ሲሄድ የካፒታሊስቱን የዕድገት ጐዳና የሚከተሉትን ኋላቀር ሀገሮችን ደግሞ እያቀረቀዘና ጥገኛ እያደረጋቸው ይሄዳል ። በመሀከላቸውም ያለው ጠቅላላ ግንኙነት በእኩልነት ላይ ያልተመሠረተ በመሆኑ አንደኛው የማምረቻ መሣሪያዎችና ቴክኖሎጂ አቅራቢ ሲሆን ሌላው የጥሬ ዕቃ አቅራቢ ይሆናል ። በሶሻሊስት ዓለም ውስጥ ያለው ሶሻሊስታዊ የሥራ ክፍፍል በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ፣ የጋራ ጥቅምንና የጋራ ብልጽግናን የሚያዳብር ፣ የያንዳንዱን ሀገር ሕዝብ የኑሮ ደረጃ ለማሻሻልና ለማሳደግ በመታገል ላይ የተመሠረተ የሥራ ክፍፍል ነው ። የሶሻሊስቱ ዓለም የሥራ ክፍፍል የያንዳንዱን አባል ሀገር አመች የኢኮኖሚ ሁኔታ በማሳደግና ኋላቀር የሆነውን የኢኮኖሚ ክፍሉን በማዳበር ላይ የተመሠረተ የሥራ ክፍፍል ነው ።

የሥራ ክፍፍል በአንድ የምርት ድርጅት ውስጥ ሊከናወን ይችላል ። ይህ ዓይነቱ የሥራ ክፍፍል በድርጅቱ ውስጥ ያለውን ጠቅላላ ሥራ ለማሳደግና ለማሻሻል አመች ሁኔታን ይፈጥራል ። በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ በየምርት ድርጅቱ ዘርፍ አንድ ዓይነት ሥራ ብቻ ሁልጊዜ የሚሠሩ ወዛደሮች ሥራቸውን ከመሰልቸትና ከመጥላት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ ። የሌሎችም ሥራዎች ዕውቀት ስለማይኖራቸው ባጠቃላይ የሚኖራቸው የሥራ ዕውቀት አነስተኛ ይሆናል ። እነዚህ ሁኔታዎች በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የወዝአደሩን ምሬት ያባብሱታል ።

በሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር እያንዳንዱ አምራች በሚሰማራበት ሙያ የሠለጠነበት

የሥራ ዕውቀት እንዲኖረውና ስለሌሎችም ሁኔታዎች መሠረታዊ ዕውቀት እንዲያገኝ በልዩ ልዩ መዋቅሮች አማካይነት ይሠለጥናል ። በተለይም በሠራተኛው ማኅበርና በፓርቲው አማካይነት እያንዳንዱ አምራች በፖለቲካዊ ፥ በባህላዊና በማኅበራዊ መስኮች የሚያደርገውን እንቅስቃሴ እንዲያዳብር ይደረጋል ።

## ሥርዓት

*(System)*

በአንድ ቅንብር ውስጥ በሚገኙ ክፍሎችና አካሎች መሀከል ያለው መያያዝና ግንኙነት በሕግ የሚመራ መሆኑን የሚገልጽ ጽንሰ ሐሳብ ነው ።

ማናቸውም ቁስአካላዊ ነገር ወይም ሐሳብ በውስጡ የተለያዩ ክፍሎችን ያቀፈ በመሆኑ ሥርዓት ያለው ወይም እራሱ ሥርዓት ነው። ሆኖም ሥርዓቱ በውስጡ ባቀፋቸው ነገሮችና በነርሱም መሀከል ባሉት ግንኙነቶችና ባሕርያት አማካይነት ሊገለጽ ቢችልም የሥርዓቱ ምንነት ግን ውስጡ ባሉት ልዩ ልዩ ክፍሎች ወይም ግንኙነቶች ብቻ ሊገለጽ አይችልም ። ምክንያቱም የነርሱ ድምር ውጤት አይደለምና ነው ።

የማናቸውም ሥርዓት ጥናት በሥርዓቱ ውስጥ የታቀፉትን ክፍሎች መደመር ሳይሆን በመሀከላቸው ያሉትን ውስብስብ ግንኙነቶች መተንተን አለበት ። ለጥናቱም ሲባል በሥርዓቱ ውስጥ ከታቀፉት ክፍሎች ውስጥ የተወሰኑትን "ነጥሎ" ለማጥናት ይቻላል ። ሆኖም ጥናቱ አንዱ የሥርዓቱ ክፍል ከሌሎቹ ክፍሎች ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያገናዝብ ሊሆን ይገባል ። ይህም "የተነጠለው" ክፍል በተራው በርካታ አካሎችን ያቀፈ በመሆኑ እራሱም ሥርዓት ያለው ወይም ሥርዓት ነው ። የትልቁ ሥርዓት አንድ ክፍል የሆነው ሌሎች አካሎችን የሚያቅፍ በመሆኑ ራሱም ሥርዓት ነው ። ለምሳሌ ኅብረተሰብን ብንወስድ የተለያዩ መደቦችን ማቀፉ የራሳቸው ሥርዓት ባላቸው ክፍሎች የተከፋፈለ መሆኑን ሲያሳይ ኅብረተሰቡ ግን የነሱ ድምር ሳይሆን የውስብስብ ግንኙነታቸው መሠረት ነው ።

ትንሹ ሥርዓት የትልቁ ሥርዓት አካል ፥ ትልቁም በተራው ከርሱ የሚበልጠው ሥርዓት አካል በመሆኑ ማናቸውም ነገር በሥርዓት ውስጥ ተቀናጅቶ የሚገኝ ነው ። የዚህ ዓይነቱ የሥርዓት ቅንጅት ነባራዊ እንጂ በዘፈቀደ የነገሮች መሳካት ውጤት አይደለም ። ማናቸውም ሥርዓት በሕግጋት የሚመራና የሚሠራ ነው ። ሆኖም የሕግጋቱ ዓይነትና ባሕርይ ተፈጻሚ እንደሚሆኑበት ሥርዓት ባሕርይ የተለያየ ነው ።

በአንድ ሥርዓት ውስጥ የሚገኝ ክፍል ሲለወጥ በአጠቃላዩ አካል (ሥርዓት) ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድርና ሥርዓቱ በጠቅላላው ይለወጥ ዘንድ የሚረዳውን ቅድመ ሁኔታ ያመቻች እንጂ ሥርዓቱን የሚለውጥ አይደለም። ነገር ግን የአጠቃላዩ ሥርዓት መለወጥ በውስጡ የሚያቅፋቸውን ነገሮች (በእኩልና ሁሉንም ወዲያውኑ ባይሆንም) እንዲለወጡ ያደርጋል ። ለምሳሌ የካቢኔ መቀያየር አንድን የኅብረተሰብ ሥርዓት አይቀይረውም ፤ የምርት ግንኙነት ለውጥ ግን ሥርዓቱን ይለውጠዋል ።

ማናቸውም ሥርዓት ከተለያዩ በርካታ ሥርዓቶች ጋር ስለሚገናኝ ማናቸውም የቁስ አካል ክፍል በሁለንታዊ ሥርዓት ውስጥ ይገኛል ። ቁስአካል ከሥርዓት ውጭ ስለማይገኝ ዕውቀት ፥ አስተሳሰብ ፥ ንድፈ ሐሳብ ወዘተ... በሥርዓት መገለጻቸው ይህንኑ ነባራዊ እውነታ ማንፀባረቅ ነው ።

(ትንታኔን ፥ ንድፈ ሐሳብን ፥ መስተጋብርን፥ ቁስአካልን ይመለከቷል ።)

## ሥርዓት አልበኝነት

*(Anarchism)*

ማናቸውንም ዓይነት ሥልጣን ወይም መንግሥት ፥ የወዝአደሩን የበላይ ገዥነት መንግሥት ጨምሮ ፥ የሚቃወምና የመንግሥትንም መጥፋት የሚሻ ንዑስ ከበርቴያዊ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ አመለካከትና አዝማሚያ ነው ። ፍልስፍናዊ መሠረቱም ግለሰበኝነት ፥ ኅሊናዊነትና በነባራዊ ሁኔታዎች ሕግጋት ላይ ያልተመሠረተ ባዶ ፈቃደኝነት ነው ።

ሥርዓት አልበኝነት አነስተኛ የግል ንብረት ባለቤትነትን ቢደግፍም በሰፋፊ የምርት ይዞታ ላይ የተመሠረተውን የኅብረተ

ሰብ ዕድገት ሂደት ግን ይቃወማል ። የበዝባዥ መደብ መንግሥት የመጨቆኛ መሣሪያ ቢሆንም የወዝአደሩ መንግሥት ደግሞ ለኅብረተሰቡ ነፃ የመውጫ መሣሪያ መሆኑን አይረዳም። ከዚህም የተነሣ በአመፅ ፣ ረብሻ በመፍጠር፣ ቦምብ በመወርወር ወዘተ... መንግሥትን ለማጥፋት ይጣጣራል ። ይህም ጥረት የኅብረተሰብ ዕድገት ሕግጋትን ነባራዊነት ካለመረዳት የሚመነጭ ነው ።

ማርክሲዝም ሌኒኒዝም የመንግሥትን ክስመት በመቀበሉና በዚህም ሥርዓት አልበኝነት ከማርክሲዝም ጋር የተጣጣመ መስሎ ቢታይም የመንግሥትን ክስመት በሚመለከት ረገድ በሁለቱም መካከል መሠረታዊ ልዩነት አለ ። የወዝአደሩ መንግሥት ታሪካዊ ሚና ብዝበዛንና መደቦችን ማጥፋት ሲሆን መደብ ባለበት ኅብረተሰብ ውስጥ ለመንግሥት ክስመት መቆም ግን ሳይንሳዊነት የሌለውና እንዲያውም የቡርዧውን መንግሥት ዕድሜ የሚያራዝም ይሆናል ። ስለሆነም ሥርዓት አልበኝነት መደብንና የመደብን ትግል የማይቀበል ፣ ምዝበራንና የምዝበራን መሠረት የማይረዳ በመሆኑ ፀረ ብዝበዛ የሆኑ መፈክሮችን ከማንሣት ባሻገር ስለማያልፍ የወዝአደሩን የፖለቲካ ትግል ያዳክማል ፤ ኃይላቸውንም ይከፋፍላል ። በዚህም አቋሙ የቡርዧው ሥርዓት አገልጋይ ይሆናል ።

የሥርዓት አልበኝነት ዋነኛ መሥራቾች ጀርመናዊው ካስፐር ሽሚት (ማክስ ሽቲርነር)፣ ፈረንሳዊው ጆሴፍ ፕሩዶንና ሩሲያዊው ሚካኤል ባኩኒን ሲሆኑ በአብዛኛው በላቲን ሀገሮችም ማለትም በኢጣሊያ ፣ በስፓኝ ፣ በላቲን አሜሪካ ሀገሮች ውስጥ ይታያል ። ሥርዓት አልበኝነት በዛሬውም ወቅት ልዩ ልዩ ገጽታዎችን ይዞ በአያሌ ሀገሮች ፣ በወዝአደሩና በተራማጅ ንቅናቄዎች ውስጥ የተከሰተ ሲሆን ፀረ ቦልሼቪዝምነቱ ፣ ፀረ ዲሲፕሊንነቱ ፣ ፀረ ኮሚኒዝምነቱና ፀረ ሶቭዬትነቱ ዓይነተኛ መለያዎቹ ናቸው ።

## ሥርወ መንግሥት
(*Dynasty*)

ከአንድ ቤተሰብ የዘር ግንድ በተከታታይ የወጡና አንድን ሀገር በአንድ የፖለቲካ አቅጣጫ የሚገዙ መሪዎች የዘር ሐረግና የግዛታቸው ዘመን ነው ። ይህም በባሪያ አሳዳሪውና በተለይም በፊውዳሉ ሥርዓት ውስጥ ገኖ የሚታይ ነው ። ለምሳሌ በእንግሊዝ የስቱዋርት ፣ በጀርመን የሆሄንዞለርን ፣ በሩሲያ የሮማኖቭ ፣ በኢትዮጵያ የዛጉዌና የሰለሞን የሚባሉ ሥርወ መንግሥቶች እንደነበሩ ታሪክ ይናገራል ።

## ሥነ ልቡናዊ ዘይቤ
(*Psychological make-up*)

የአኗኗር ስልት ፣ አካባቢያዊና የአብሮ አደግ ልማድ ፣ የተለመደ ወግና ሥርዓት ፣ እምነትና ፈሊጥ ወዘተ...ሆነው በኅብረተሰቡ አእምሮ ውስጥ የሚፈጥሩት ወይም የሚቀርፁት ስሜት ነው ። እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የልምድ ጥርቅሞች የሰዎችን አእምሮ በመግራት በአመለካከታቸው ላይ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ናቸው ።

## ሥነ መለኮት
(*Theology*)

በመለኮታዊ ፀጋ ተገኝተዋል በተባሉት ሐሳቦች ላይ በመመሥረት የአምላክን ባሕርይና ተግባራት የሚያጠና ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ነው ።

የጥናቱም ይዘት የእግዚአብሔርን ባሕርይና በእግዚአብሔርና በሰው መሀከል ያሉትን ግንኙነቶች የሚመለከት ሲሆን የሰዎችን ጭፍን እምነት በሚጠይቁ ቀኖናዎች ላይ የተመሠረተ ነው ። ባጭሩ ሥነ መለኮት በአንድ በተወሰነ ሃይማኖት ውስጥ ያሉ ቀኖናዎችን ሥርዓት የሚያስይዝና የሚገልጽ ነው ። ለምሳሌ የክርስትና ሥነ መለኮት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረቱ የተለያዩ ቀኖናዎችን ፣ ግብረገቦችንና አምልኮን ወዘተ . . . ያቀፈ ነው ።

የሥነ መለኮት አስተሳሰቦች ሁለት መነሻዎች አሏቸው ። አንደኛው መነሻ ስለራሱ ታዋቂነት መለኮታዊ ምሥጢርን በተመረጡ ሰዎች አማካይነት በራዕይ የሚገልጥና የሚያስተላልፍ አምላክ አለ የሚል ነው ። ይህም አመለካከት ከሳይንስና ከሳይንሳዊ አመለካከት ጋር የሚፃረር ነው ። ሁለተኛ መነሻው

ደግሞ ከሐሳባዊ ፍልስፍና የሚመነጨው ሃይማኖታዊ ፍልስፍና በሚያስገኛቸው አስተሳሰቦች ላይ መመሥረቱ ነው ። ሃይማኖታዊ ፍልስፍናም ሥነ መለኮትን ከሳይንስ ጋር ለማዛመድና እንደማይቃረኑ አድርጎ ለማሳመን ይሞክራል ። ሆኖም ሥነ መለኮት መሠረታዊ እውነት ተጨባጭ መሆን አሰበት የሚለውን ሳይንሳዊ መርህ የማይከተልና በማይለወጡ ቀኖናዊ ጽንሰ ሐሳቦች ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ከሳይንስ ጋር ጨርሶ ሊጣጣም አይችልም ።

(ሃይማኖትን ፥ ሐሳባዊነትን ፥ ቀኖናዊነትን ፥ አማኒነትን ይመለከቷል ።)

## ሥነ ምግባር
(*Ethics*)

የሰውን ተግባር አስመልክቶ የጥሩና የመጥፎ ፥ መሆን ያለበትና የሌለበት ወዘተ . . . ሳይንስ ነው ። ሥነ ምግባር መሆን የሚገባውን የሚደነግግ ሲሆን የግብረገብነትን ንድፈ ሐሳቦችንም ያጠቃልላል ። የመጀመሪያው የጠቃሚነትን ፥ የጥሩነትንና የመጥፎነትን ጥያቄዎችና የሰዎች ጠባይ የሚመራበትን ግብረገባዊ ደንብ የሚቀርፅ ፥ በዚህም ጊዜ ሰዎች ሊጣጣሩላቸው የሚገባቸውን ፥ ለሕይወት ትርጉም የሚሰጡትንና ጥሩ የሚባሉትን ባሕርያት ለማሳየት የሚሞክር የሥነ ምግባር ክፍል ነው ። የግብረገብነት ንድፈ ሐሳብ ደግሞ የግብረገብነቱን ፍሬ ሐሳብ አነሣሥና ዕድገት እንዲሁም የግብረገብነት መለኪያዎችን ፥ ታሪካዊ ባሕርያቸውን የሚወስኑ ሕግጋትን የሚመለከት ነው ። መሆን የሚገባውን የሚደነግገው ሥነ ምግባርና የግብረገብነት ንድፈ ሐሳቦች በተለያዩ ነጥቦች ላይ ቢያተኩሩም የማይነጣጠሉ ናቸው ።

ሥነ ምግባር በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት ውስጥ ብቅ ያለና የግብረገብ ባሕርያት አስተምህሮ ሲሆን ግብረገብ ግን በጥንታዊ ጋርዮሽ ሥርዓት ውስጥም የነበረ ነው ። ስለሆነም ግብረገብ ከሥነ ምግባር ይቀድማል ። ከዚህም የተነሣ ሥነ ምግባር የፍልስፍና አካል የሆነ ንድፈ ሐሳብ ነው ። የፍልስፍና ንድፈ ሐሳብ በመሆኑም በቁስአካላዊና በሐሳባዊ የሥነ ምግባር አስተሳሰቦች ይከፈላል ፤ በሁለቱም መሀከል ትግል ይካሄዳል ። ቁስአካላውያን በሥነ ምግባር ውስጥ የተከሰቱትን ሥነ መለኮታዊ አመለካከቶች በተለይም ሥነ መለኮታዊና ሐሳባዊ የሕይወት ትርጉምን በመታገል የግብረገብ መለኪያዎች "ምድራዊ" መንሥኤ ያላቸው መሆኑን ያሳያሉ ።

ለሥነ ምግባራዊ አስተሳሰቦች ዕድገት ከፊውዳሉ ሥርዓት ይልቅ ካፒታሊዝም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ። ቡርዧዚው አብዮታዊ በሆነበት ወቅት የነበሩ የቡርዧ ርዕዮተዓለማውያን በተለይም ካንትና ሄግል ሐሳባዊ ቢሆኑም ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው ሥነ ምግባራዊ አስተሳሰቦችን አፍልቀዋል ። ተምኔታዊ ሶሻሊስቶችም ቢሆኑ በበኩላቸው በዓለሙት ፍትህ በሰፈነበት ኅብረተሰብ ውስጥ ይከሰታሉ ያሏቸውን ሥነ ምግባራዊ አስተሳሰቦችን ቀምረዋል ።

ማርክሳዊ ሥነ ምግባር ቀደም ብለው ከተቀመሩት ሥነ ምግባራዊ ንድፈ ሐሳቦች ውስጥ ጠቃሚ የሆኑትን በመውረስ በዚህ ረገድ በሚታየው ዕድገት ውስጥ አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል ። ከማርክስ በፊት የነበሩት ፈላስፎች ስለ ሥነ ምግባር የነበራቸው አመለካከት ሐሳባዊ ነበር ፤ ምክንያቱም የሰው ንቃተ ኅሊና ከዳበረ ፥ አስፈላጊው ትምህርት ከተሰጠው ወይም የመንግሥት ቅርፅ ከተለወጠ ሥነ ምግባራዊ አስተሳሰቦች በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት ይኖራቸዋል ብለው ያምኑ ነበርና ነው ። ማርክስና ኤንግልስ ግን ግብረገብ የሚወሰነው በማኅበራዊ ሥርዓት መሆኑንና የታሪክ ዕድገት ውጤትም እንደሆነ አስተምረዋል ። በተጨማሪም ሌኒን ከኮሚኒዝም ግንባታ ጋር ሊዛመድ የሚችለውን ሥነ ምግባር በማዳበር ረገድ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

የቡርዧ ሥነ ምግባር በዲበአካልና በሐሳባዊነት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የሰብአዊነትን ፥ የፍትህንና የጥሩነትን ጥያቄዎች ረቂቅ በሆነ መንገድ ከመመልከቱም በላይ ሥነ ምግባራዊ ጠቀሜታዎችን ከእውን የሕይወት ሁኔታዎች ገንጥሎ ያያቸዋል ። ግላዊነትንም በመሰበክ የወል ወይም ማኅበራዊ ሥነ ምግባርን ይቃወማል ።

(ሰናይና እኩይን ይመለከቷል ።)

## ሥነ ተረት
*(Mythology)*

ነገሮችን በማጋነን ወይም አስደናቂ ፍጡሮችን በመፍጠር ወይም ደግሞ አስገራሚ ተረቶችን በማውሳት የተፈጥሮና የኅብረተሰቡ ሁኔታ በምሳሌ የሚገለጽበት ዘዴ ሥነ ተረት ይባላል ። ሥነ ተረት ከጥንት የመጣ ሲሆን ዋና ምንጩም ምናብ ነው ። ለተፈጥሮና ለኅብረተሰብ ኃይሎች ዲበ ተፈጥሮአዊ መልክና ፍች በመስጠት በሰዎች ዘንድ ኃይለኛ ስሜቶችን (አድናቆትን ፣ ፍርሃትን ፣ ሐዘንን ወዘተ...)የሚቀሰቅስ ነው ። ሥነ ተረት በዲበተፈጥሮአዊ አዝማሚያው የሃይማኖትን ጥንተ ነገሮች ያቀፈ ቢሆንም ሥነ ውበታዊ ፍችም አለው ። ከሚቀሰቅሳቸው ሥነ ውበታዊ ስሜቶችና ከሚጠቀምበት ምናባዊ ፈጠራ አንፃር ሥነ ተረት ንቁ ያልሆነ የእውነታ ሥነ ጥበባዊ አመለካከት ነው ለማለት ይቻላል ።

(ምናብን ፣ ሥነ ውበትን ይመለከቷል ።)

## ሥነ ኑባሬ
*(Ontolgy)*

የኑባሬን አጠቃላይ መርህ ፣ አወቃቀርና ሕግጋት የሚያጠና ሲሆን መሠረታዊ ሐሳቡም የማናቸውም ነገር የመኖር መሠረት የሚገለጸው በክስተቱ (ቀለሙ ፣ መጠኑ ወዘተ...) ሳይሆን የክስተቶቹ ተሸካሚ በሆነው ባሕርዮት ነው የሚል የፍልስፍና አንድ ክፍል ነው ። ሥነ ኑባሬ በአንድ በተወሰነ ዘመን ውስጥ የሚገኙ የፍልስፍና ፈርጆችን ሥርዓት የሚያስይዝና ስለ እውነታም ብተገኘው ዕውቀት ላይ በመመሥረት ስለእውነታ አጠቃላይ ግንዛቤ የሚሰጥ ነው ። ከዚህ አንፃር ሲታይ ማናቸውም ፍልስፍናና ባጠቃላይም ማናቸውም ንድፈ ሐሳባዊ ሥርዓት የሚመሠረተው በሥነ ኑባሬ ጽንሰ ሐሳቦች ላይ ነው ። ሆኖም ስለእውነታ በየጊዜው የሚቀረፀው የግንዛቤ ደረጃ ሲያድግ የሥነ ኑባሬም ግንዛቤ በዚያው መጠን ይዳብራል ።

በቅድመ ማርክሳዊ ፍልስፍና ውስጥ ሥነ ኑባሬ የሚያጠናው ስለኑባሬ ባጠቃላይ ማለትም ከግላዊ ክስተቶች ውጭ በመሆኑ የዲበአካል አቻ ተደርጐ ይወሰድ ነበር ። በዚህ መልክ ለሥነ ኑባሬ ይህን ፍች የሰጠው አርስጣጣሊስ ነበር ። ከዚያም በመካከለኛው ዘመን ተምህሮአዊ ፈላስፋዎች በአርስጣጣሊስ ዲበአካላዊ አስተሳሰብ በመጠቀም የሃይማኖትን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚረዳ የሥነ ኑባሬ አስተምህሮ ቀምረዋል ። ከ16ኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ ግን ሥነ ኑባሬ የዲበአካል አንዱ ክፍል በመሆን የማናቸውም ህልው ነገር ዲበ ሕውስታዊና ኢቁስአካላዊ የሆነው መዋቅር አስተምህሮ እንደሆነ ተደርጐ ተወስዷል ።

በሆብስ ፣ በስፒኖዛና በሎክ ከዚያም በ18ኛው ምዕት ዓመት በነበሩ ቁስአካላውያን አማካይነት ሥነ ኑባሬ የተለየ ግንዛቤ አግኝቷል ። ይህም ተቃራኒ አስተምህሮ በምርመራዊ ሳይንስ ውጤት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ሥነ ኑባሬን ዲበሕውስት ወይም የነገሮች ኢቁስአካላዊ መዋቅር ነው የሚለውን የቀድሞ ግንዛቤ አፋልሶታል ።

የጀርመን ብሉይ ሐሳባዊ ፈላስፎችም የሥነ ኑባሬ ፍች በአንድ በኩል ትርጉም የለሽና ከንቱ የሐሳብ ድግግሞሽ ነው ሲሉ በሌላ በኩል ግን ከዲበአካል የተሻለ ትርጉም እንዲያገኝ ሞክረዋል ። በዚህም በሁለተኛው አስተሳሰብ መሠረት የሥነ ኑባሬን ፍች ሄግል ደግሞ በሥነ አመክንዮ ለመተካት ጥሮአል ። የሄግል የሥነ አመክንዮ ሥርዓት በሐሳባዊነት ላይ የተመሠረተ ቢሆንም ሥነ ኑባሬን የሥነ አመክንዮ (የዲያሌክቲክስ) እና የዕውቀት ንድፈ ሐሳብ ውህደት አድርጐ አቅርቦት ነበር ።

ማርክሲዝም ሥነ ኑባሬን ፣ ሥነ ዕውቀትንና ሥነ አመክንዮን በማዋሃድና በሳይንሳዊ ግኝቶች በመጠቀም ተጨባጭ ማለትም ቁስአካላዊና ዲያሌክቲካዊ የሆነ የዓለም ግንዛቤ ቀምሯል ።

(ዲበአካልን ፣ ባሕርዮትን ፣ ሄግሊያኒዝምን ይመለከቷል ።)

## ሥነ አመክንዮ
(*Logic*)

እርስ በርሳቸው የተያያዙና የማይፋለሱ ሐሳቦች ከአንድ መንደርደሪያ ሐሳብ በመመንጨትና ከርሱም ጋር በመያያዝ በተወሰኑ

የአስተሳሰብ ሕግጋት መሠረት ወደ ትክክለኛው መደምደሚያ የሚያመሩበትን ሁኔታና የዚህም ውጤት ሆኖ የሚቀረፀውን የሐሳብ ቅርፅና ሥርዓት የሚያጠና ሳይንስ ነው ።

በቅድመ ማርክሳዊ ፍልስፍና ውስጥ ሥነ አመክንዮ ከሥነ ምግባርና ከውበታ ጋር ተዳምሮ ሌላው የፍልስፍና አንድ አካል በመሆን ቅርፃዊ ሥነ አመክንዮ ተብሎ ይጠራ ነበር ። ያጠናም የነበረው የእሳቦትን መዋቅራዊ ክፍሎችና የተወሰኑ መደምደሚያዎች (ብያኔዎች) ከሌሎቹ መደምደሚያዎች የሚመነጩበቸውን ሕግጋት ነበር ። እነዚህም ሕግጋት የሚያሳዩት በአንድ መደምደሚያ ውስጥ ባሉ ሐሳቦች መሀከል ያሉትን መሠረታዊ ግንኙነቶች ነው ።

በሥነ ኑባሬ ፤ በሥነ ዕውቀትና ፣ በሥነ አመክንዮ መካከል ቀደም ብሎ ፈላስፎች የፈጠሩትን ልዩነት በመሻር በመሀከላቸው ያለውን ግንኙነትና አንድነት ለመጀመሪያ ጊዜ ለማሳየት የሞከረው ሄግል ነበር ። ሆኖም ሄግል ሐሳባዊ በሆነ መንገድ ሐሳብንና ኑባሬን አንድ እንደሆኑ አድርጎ በመውሰድ የእሳቦት ሕግጋት የእውነታም ሕግጋት ናቸው ብሏል ። ምክንያቱም በእርሱ አስተምህሮ መሠረት ማናቸውም ነገር የሐሳብ ነፀብራቅ ነበርና ነው ። በእርሱ አመለካከት ጠቅላላው የኑባሬ ዕድገት ሐሳቦችን የመገንዘብ ሂደት በመሆኑ ፍልስፍናን ወደ ሥነ አመክንዮ ለውጦታል ።

ቅርፃዊ ሥነ አመክንዮ የእሳቦት ተግባሮች የማይለወጡና ትክክለኛውም አስተሳሰብ ከቅራኔ የነፃ ነው የሚል ሲሆን ዲያሌክቲካዊ ሥነ አመክንዮ ግን የተመሠረተው በተቃራኒዎች ውህደት ላይ በመሆኑ የእንቅስቃሴና የለውጥ ግንዛቤ ነው ፤ ማለትም ዲያሌክቲካዊ ሥነ አመክንዮ በማያቋርጥ ዕድገትና ለውጥ ላይ ያለው ነባራዊ ዓለም እንዴት እንደሚንፀባረቅ የሚያሳይ ሳይንስ ነው ። ዲያሌክቲካዊ ሥነ አመክንዮ የአስተሳሰብ ቅርፆችን ዕድገትና የጽንስ ሐሳቦችን እነማሥ ፣ እንቅስቃሴና ባሕርያትን የሚያጠና ነው ።

በማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍና መሠረት ኑባሬና ግንዛቤ የማይነጣጠሉና ውህደት ያላቸው ቢሆኑም ፍጹማዊ አንድነት የላቸውም ። የዚህም ውህደት መሠረት በነባራዊው ዓለምና የርሱም በንቃተ ኅሊና ውስጥ በተግባር አማካይነት የመንፀባረቁ ዲያሌክቲክስ ነው ። ለዚህም ነው በማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍና ውስጥ ዲያሌክቲክስ ፣ ሥነ አመክንዮና የዕውቀት ንድፈ ሐሳብ አንድ ናቸው የሚባለው። ምክንያቱም እውነታ በዲያሌክቲክስ ሕግ የሚገዛ በመሆኑ በሐሳብ አማካይነት ሊንፀባረቅ የሚችለው ሐሳብ ራሱ በዲያሌክቲክስ ሕጎች ሲገዛ ነው ።

(ቅርፃዊ ሥነ አመክንዮን ፣ ዲያሌክቲካዊ ሥነ አመክንዮን ይመለከቷል ።)

## ሥነ ዕውቀት
*(Epistemology)*

የዕውቀት ጥናት ምርምር ንድፈ ሐሳብ ማለት ነው ። ጥናቱ የሚያተኩረው በዕውቀት ምንነትና መሠረቶች ላይ ሲሆን በተለይም የዕውቀትን ወሰንና ትክክለኛነቱን የሚመዝኑ ነጥቦችን ይመረምራል ። እውነታ ከነባራዊ ሁኔታ ጋር ምን ግንኙነት አለው? የዕውቀት መነሻና መሠረቶች ምንድናቸው? የዕውቀትስ አመጣጡ እንዴት ነው? የዕውቀት ዳር ድንበሩ እስከየት ነው? እውነትነቱስ በምን ይለካል? የሚሉትን ጥያቄዎች የሚያጠና የፍልስፍና ክፍል ሥነ ዕውቀት ይባላል ።

በሐሳባዊ ፍልስፍና አመለካከት የዕውቀት ምንጭ ሐሳብ በመሆኑ አስቀድሞ ከሐሳብ ድንጋጌዎች በመነሣት የነባራዊ እውነታ ይዘት በቀጥታ ከነዚህ ድንጋጌዎች እንደሚገኝ ሆኖ ይቀርባል ። ይህም የሚያመለክተው ነባራዊው እውነታ የራሱ ህልውና እንደሌለውና የሚገዛውም በሐሳብ ድንጋጌዎች መሆኑን ነው ። በሐሳባዊ ፍልስፍና አመለካከት የዕውቀት መሠረቶች የሐሳብ ድንጋጌዎች በመሆናቸው በሐሳባዊ ፍልስፍና የዕውቀት ስፋትና እውነትነት የሚወሰነው በሐሳብ ኃይል ጥራትና ጥበብ ፣ በሥነ አመክንዮአዊ ትክክለኛነት ይሆናል ።

በዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት አመለካከት ግን የዕውቀት ምንጭ ቁስአካል ነው ። ቁስአካል የራሱ ህልውናና የራሱ ሕግጋት ያሉትና ከሰው ስሜትና ሐሳብ ነፃ በመሆኑ የሐሳብ ድንጋጌዎች የሚገዙት ሳይሆን እነዚህ ድንጋጌዎች ከሱ የሚመነጩና የሱ

ነፀብራቅ መሆናቸውን ያስረዳል ። ዕውቀት ተፈጥሮንና አካባቢን ለመቆጣጠር የሚረዳ ነው ፤ ዕውቀት የሚገኘው በግለሰብ ጥረት ብቻ ሳይሆን ዋናው መሠረቱ የኅብረተሰቡ ፍላጐት በመሆኑ ቀጥታ ማኅበራዊ ይዘት ያለው ነው ። የዕውቀት ወሰን ይህ ነው የማይባል ፣ ታዳጊና ታሪካዊ መሆኑን የሚያስረዳን የሰው ልጅ ፍላጐትና ቁሳዊ ኃይል እያደገ ሲሄድ ዕውቀትም አብሮ ስፋትና ጥልቀት ማግኘቱ ነው ። ይህም የሚያመለክተው የእውነት መለኪያ ተግባር መሆኑን ነው ። አንድ ሐሳብ ትክክለኛነቱ የሚረጋገጠው ለተግባር በሚሰጠው አገልግሎት ሲሆን ይህን አገልግሎት ሊሰጥ የሚችለው የነባራዊ እውነታ ትክክለኛ ግንዛቤ ሲሆን ብቻ ነው ።

የሰው ልጅ አካባቢውን የማንፀባረቅ ችሎታው በተግባር ግፊት የተነሣ የመንቀሳቀሻው ሜዳ በሰፋ ቁጥር ረቂቅ ሐሳቦችን እስከ መገንዘብ ደርሷል ። ስሜታዊ ሆኑ ረቂቅ ሐሳቦች በአጠቃላይ የነባራዊ ሁኔታ ነፀብራቅ ናቸው ።

(ዕውቀትን ፣ ዳሰሳዊ ዕውቀትን ፣ ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀትን ፣ አንፃራዊና ፍጹማዊ እውነትን ይመለከቷል ።)

## ሥነ ክስተት

*(Phenomenology)*

በ20ኛው ምዕት ዓመት በጀርመናዊው ፈላስፋ በኤድመንድ ሁስርል የተመሠረተ ብዙ ተከታዮች ያሉት ሐሳባዊ ፍልስፍና ነው ። የፍልስፍናውም መሠረታዊ ጥያቄ የሰው ህልውናና ምንነት ሲሆን ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ የሚያስገኝ አዲስ የአስተሳሰብ ዘዴ አለኝ የሚል ፍልስፍና ነው።

እንደ ሥነ ክስተት አባባል እስካሁን ፍልስፍና የተጠቀመባቸው ሁለቱ ዘዴዎች ልዩና ተቃራኒ ናቸው ። አንዱ የሰው አስተሳሰብና ሁኔታ የሚወስኑት በውጭ ኃይሎች (በአካባቢው ፣ በማኅበራዊ ኑሮ ፣ በኢኮኖሚ ወዘተ...) ነው የሚል ሲሆን ይህ ዘዴ ሰውን ተገብሮትና ተወሳኝ በማድረጉ የሰው ዕውቀት ነባራዊ እውነት ላይ ሊደርስ አይችልም ለማለት ተገድዷል ። ሁለተኛው ደግሞ ሰውን ምንም የሚወስነው የውጭ ኃይል የለም የሚል ሲሆን የሰው ተወሳኝ አለመሆን እውነትን ከሐሳባችን ውስጥ ብቻ የምናገኝ በማድረጉ ዘዴው የተጨባጩን ነፃ መሆንና የልምድን አስፈላጊነት መካዱ አልቀረም ።

የነዚህ አስተሳሰቦች ድክመት ዋናው ምንጭ የመነጣጠላቸው ሁኔታ ነው ። በእንፃሩ ሁለቱም የእውነትን አንዳንድ ክፍል የሚገልጹ በመሆናቸው ማዋሃድና ማስማማት ያስፈልጋል ። ክስተት የሚለው ጽንሰ ሐሳብ በሁለቱ መዋሃድ ማለትም የሰው በውጭ መወሰንና የሰውን የውስጥ ነፃ ህልውና አብሮ በማሰብ የሚገኝ ጽንሰ ሐሳብ ነው ። ክስተት ማለት ሰው በሚገኝበት ተጨባጭ ሁኔታ አማካይነት ነገሮች ኅሊናዊ ፍች በማግኘት ለዕውቀት የመቅረባቸውን ሁኔታ የሚገልጽ ነው ። ክስተት ፍች ያለው ጭብጥ ማለት ሲሆን ሥነ ክስተት ደግሞ የክስተቶችን ፍሬ ነገርና ፍች የማንበብና የመገንዘብ ዘዴ ነው።

ለምሳሌ የሰው ኃይለኛ ስሜት የሆነውን ፍርሃትን እንውሰድ ። በፊት በነበረው አስተሳሰብ ለፍርሃት ሁለት የተለያዩ ምክንያቶች ይሰጡታል ። አንዱ ፍርሃት የሚሰማን ሰውነታችን በሚያሳያቸው ሁኔታዎች (መንቀጥቀጥ ፣ የልብ በፍጥነት መምታት ወዘተ...) የመረበሽ ስሜት ይፈጠርብናል ሲል ተቃራኒው ደግሞ እነዚህ የሰውነት ሁኔታዎች ከማሰብ ግንዛቤ የሚመነጩ ማለትም ሁኔታው አደገኛ መሆኑ በመታመኑ የሚፈጠሩ ሥጋዊ ክስተቶች ናቸው ይላል ። እንደ ሥነ ክስተት አባባል በመጀመሪያ ደረጃ የፍርሃት ፍች ምን እንደ ሆነ ሳይታወቅ ሐሳባዊ ወይም ሥጋዊ ምክንያት አለው ብሎ ክርክር መፍጠሩ ትክክል አይደለም ። በእርግጥ ከተጨባጭ ሁኔታ ውጭ ሰው የፍርሃት ስሜት ሊኖረው አይችልም ፤ ሁኔታም ብቻውን በራሱ የአስፈሪነት ስሜት ሊፈጥር አይችልም ፤ የአስፈሪነት ፍች ከሰው ኅሊና ማግኘት አለበት ። ይህም ፍች የሚሆንበት ምክንያት ዕቅድ አዘል በመሆኑ ነው ። ለምሳሌ አንድ ሰው አደገኛ አውሬ ቢያጋጥመው ከፍርሃት የተነሣ ኅሊናውን ሊስት ይችላል ። በእርግጥ ኅሊናውን መሳቱ ከአደጋው አያድነውም ፤ ሆኖም አደጋው እንዳይሰማው፣ እንዳያውቀው ለማድረግ ችሏል። መረበሽ ከመወሰን ወይም ከመፍረድ ብቻ የሚመጣ ሳይሆን በራሱ ፍች ያለውን ተግባርና ዕቅድ የሚገልጽ ክስተት ነው ። ይህን ዕቅድ ማግኘትና ማወቅ የሥነ ክስተት ዋና ዓላማ ነው ።

ማንኛውም የሰው እንቅስቃሴና ተግባር (ዕውቀት ፥ ሐዘን ፥ ደስታ ፥ ፍቅር ፥ ቋንቋ ፥ ኅብረተሰብ ወዘተ...) ዕቅድ ያዘለ በመሆኑ ሥነ ክስተት የሰው ሳይንስ መሠረታዊ ፍልስፍና ነው ። ነገሮች በራሳቸው ታዋቂ ፥ አሳዛኝ ፥ አስደሳች ወዘተ... አይደሉም ፤ እነዚህ ጠባዮች ፍች የሚኖራቸው ከኛ ጋር የዕቅድ ግንኙነት ሲኖራቸው ብቻ ነው ።

እንደምንመለከተው ሥነ ክስተት ሐሳባዊና ቁስአካላዊ ፍልስፍናን ለማስታረቅ የሚጥር ወይም ሦስተኛ መንገድ አለ የሚል ፍልስፍና ነው ። የቁስአካልነት አመለካከት ላስገኘው የሰው በውጭ ኃይል መወሰን ጉዳይ ቦታ በመስጠት ነገር ግን የሐሳባዊነት ረቂቅ አዝማሚያን በማረምና ሁኔታዎችን የሐሳብ ዕቅድ ተገዥ በማድረግ የሐሳባዊ ፍልስፍንና መሠረታዊ እምነት ለማቆየት የታቀደ ፍልስፍና መሆኑ ግልጽ ነው ።

በእርግጥ ሥነ ክስተት የሚለው ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት የለውም ማለት አይደለም ። ለምሳሌ ቦታ ስንል በእውነትም ፍች አዘል ነው ፤ ምክንያቱም ቦታ ስንል ለኛ ርቀት ፥ ቅርበት ፥ ስፋት ወዘተ... ያለው ማለት ነው ። ዋናው ጥያቄ ከፍችው ላይ ሳይሆን ከፍችው ምንጭ ላይ ነው ። ምክንያቱም ሐሳብ ነፁብራቅ መሆኑ ቀርቶ የፍች ለጭነት ፍጹም ሥልጣን ካለው የሚሰጠው ፍች እንዴት ቁስአካላዊ ወይም ወሳኝ ሊሆን ይችላል? ማንኛውም ሁኔታ አስፈሪ ሊሆን የሚችለው በዘፈቀደ አለመሆኑ ከታወቀ ሐሳብ ስለ አስፈሪው ሁኔታ መረጃ ይሰጣል እንጂ ዕቅዱን አያወጣም ። ማለትም ችሎታ የሚሰጠን የምንገኝበት ሁኔታ ዕቅድም ይሰጠናል ። መወሰን ማለት ይህ ሲሆን ሐሳብ ደግሞ ይህን በትክክል ሲገልጽ ነው እውነተኛና ተግባራዊ ዕውቀት ሊሰጥ የሚችለው ።

ለቡርዧዚው ዕቅድ የሚሰጠው ሐሳብ ነው ወይስ ያለው ቁስአካላዊና ማኅበራዊ ኃይል? የወዛደሩ ዕቅድ ውሱን መሆን የሚመነጨው ከመጨቆን አይደለምን? በአንፃሩም ለወዛደሩ አብዮታዊ ዕቅድ የሚሰጠው በሚገኝባቸው የምርት ኃይሎች ውስጥ በሚጫወተው ግንባር ቀደም ሚና አይደለምን? የሁኔታን አስገዳጅነት ስንረዳ ነው ስለሰዎች እንቅስቃሴ ፥ ተግባርና አስተሳሰብ ትክክለኛውን ፍች ልንገነዘብ የምንችለው ። ከሕጋት የማፈንገጥ አዝማሚያ በግልጽ ስለሚታይበት የሥነ ክስተት ሐሳባዊነት አያጠራጥርም ። በዚሁ በሐሳባዊነቱ ተጨባጩን ነባራዊ ዕውቀት በማድበስበስ ኅሊናዊ ትርጉም ለመስጠት መሞከሩ የገዥው መደብ ተርጓሚነቱን ራሱ ያረጋግጣል ።

## ሥነ ውበት

*(Aesthetics)*

ስለ ውበት ምንነትና ፥ አመጣጥ ፥ የዕድገትን ሕግና ሚና ዘርዝሮ በማጥናት ስለኪነጥበብ አጠቃላይ ግንዛቤ የሚሰጥ የፍልስፍና ክፍል ነው ። ሥነውበት እንደማንኛውም ፍልስፍናዊ ጥያቄ በቁስአካላዊና በሐሳባዊ አቀራረብ የተከፈለ ነው ፤ የንድፈ ሐሳብ ታሪኩም የሚገልጸው የሁለቱን ትግል ነው።

ስለውበት ምንነትና ነባራዊነት ሐሳባውያን ሁለት የማይጣጣሙ አመለካከቶችን ሰንዝረዋል ። እንደነባራዊ ሐሳባውያን ውበት ነባራዊ ሲሆን የሚገልጸውም የሐሳብን ጠባዮችና ችሎታዎች ነው ። በነሱ አመለካከት ቁስአካል ውበትን ለመግለጽ እንደ ጥሬ ዕቃ ያገለግል እንጂ በራሱ የውበት ፍች የለውም ። በኅሊናዊ ሐሳባውያን አስተሳሰብ ውበት ኅሊናዊ ነው ፤ ማለትም ውበት የነገሮች ነባራዊ ጠባይ አይደለም ። ውበት የምንለው ስሜት እስከሆነ ድረስ የኅሊናን ውስጣዊ ሁኔታ እንጂ የነገሮችን ነባራዊ ሁኔታ የሚገልጽ አይደለም ይላሉ ። ወጣም ወረደ በሁለቱ የሐሳባዊነት አዝማሚያዎች የተሰጠው የውበት ፍች መንፈሳዊ ብቻ ነው። በዚህም አቋማቸው ውበት ከቁስአካላዊ ኑሮ ጋር ያለውን ግንኙነትና የሚጫወተውን ትክክለኛ ሚና ሊገነዘቡ አልቻሉም ። ውበት የደስታ ምንጭ መሆኑን እንጂ የእውነታን ግንዛቤ ማቀፉን አልተረዱም ። በመሆኑም በነሱ ዘንድ ኪነጥበብ ምናባዊና አዝናኝ ከመሆን በስተቀር ቁም ነገር አዘል አይደለም ።

ሥነ ውበት የሚቀሰቅሳቸው ስሜቶች (ደስታ ፥ ሐዘን ፥ ሣቅ ፥ ንዴት ወዘተ...) ከሰው ተጨባጭ ኑሮ ጋር ባይያያዙ ኖሮ ለሰዎች ፍች ባልሰጡ ነበር ። እነዚህ ስሜቶች የሚመነጩት ከቁሳዊ ኑሮ ሁኔታ በመሆኑ የሥነ ውበት ግንዛቤያዊ ተልዕኮ ሊካድ አይችልም ። በሌላ በኩል የኪነ

ጥበብ ሥራዎች የሚቀርቡት ለኅብረተሰቡ በመሆኑ የማገናኘትና የመግለጽ ማለትም ማኅበራዊ ፍች አላቸው ። በኪነ ጥበባዊ ምስል ውስጥ የሚንፀባረቁት ሐሳቦችና ስሜቶች የማኅበራዊ ኑሮ ሁኔታን የሚገልጹ በመሆናቸው ሥነ ውበት የመደብ ትግልን የሚያንፀባርቅ ነው ። ብዙውን ጊዜ ኪነጥበብ እማቂ ፣ አሳዛኝ ፣ አስደሳች ወዘተ... እድርጐ የሚያቀርባቸው ሁኔታዎች የሚገልጹት የገኙውን መደብ አመለካከቶች ከመሆኑም በላይ በኪነ ጥበባዊ ዘዴ በመጠቀም ገዥው መደብ ራሱን በማሞገስ ለራሱ ፋይዳ ይስጣል ፤ በዚህም ከሕዝብ ኅሊናዊ ተቀባይነትን ለማግኘት ይጥራል ።

ይህ የኪነ ጥበብ ማኅበራዊ ሚና የሚገልጸው ሥነ ውበት ከእውነታ ጋር ያለውን የቅርብ ግንኙነት ነው ። ማርክሲዝም ሥነ ውበትን የላዕላይ መዋቅር ክፍል በማድረግ በኑሮ ሁኔታ የሚወሰንና እሱኑ የሚያንፀባርቅ ለመሆኑ አጠቃላይ ንድፈ ሐሳባዊ መመሪያ ቀምሯል ። ውበት ከኪነ ጥበብ ሥራዎች የምናገኘው ስሜት በመሆኑና እነዚህም ሥራዎች የሰው የሥራ ውጤት በመሆናቸው ውበት ነባራዊ ፍች አለው ። የሰዎችን ሕይወታዊ ግፊት ፣ ጥቅምና ክብር ፣ አስደናቂ ፣ አሳዛኝ ወዘተ ... በሆነ መልክ የሚያቀርቡ በመሆናቸው ሥነ ውበታዊ ስሜቶች የሰውን ንቃተ ኅሊና ያዳብራሉ ፤ ለተሻለ ሁኔታ ፍላጐትን ይፈጥራሉ ። በመሆኑም የውበት ርዕዮተዓለማዊና ትምህርታዊ ሚና ከፍተኛ ነው ። የውበት መጨረሻ ፍች የሚገልጸው የሰው ደስታው ራሱ ሰው መሆኑን ነው ። ምክንያቱም ውበት ሰው ለሰው የሚሰጠው ደስታ በመሆኑ የሰውን የውስጥ አንድነትና መተሳሰርን ስሜታዊ በሆነ መንገድ ቀርፆ የሚያቀርብ ነው ።

ሥነ ውበት ግንዛቤ ያዘለ ነው ሲባል ከሳይንሳዊ ግንዛቤ የሚለይበት ነጥብም አለው ። ውበት የሚቀርበው በኪነ ጥበባዊ ሥራዎች በመሆኑ የነገሮች ንድፈ ሐሳባዊ ነፀብራቅ ብቻ ሳይሆን በቀጥታ ፈጠራ በሆነ ተግባርና የቴክኒክ ክንውኖች ላይ የተመሠረተ ነው ። ቁስአካላዊ ነገሮችን (ድምፅ ፣ ቀለም ፣ ድንጋይ ወዘተ...) በመቅረፅ የተለየና የተደራጀ መልክ እንዲኖራቸው ማድረግን ይጠይቃል ። በሌላ በኩል ውበት ንድፈ ሐሳቦችን ፣ ጽንሰ ሐሳቦችን የሚያንፀባርቅ ቢሆንም ስለነገሮች የሚሰጠው ዕውቀት ንድፈ ሐሳባዊ አይደለም ። ከሥነ ውበታዊ ቅርፆች የሚመነጭ ኅሊናዊ ሁኔታ በመሆኑ ውበት ስሜታዊ ነው ። የነገሮችን አሳዛኝ ፣ አማቂ ፣ አስደሳች ወዘተ... የመሆን ምክንያት የማይገልጽ ቢሆንም አሳዛኝ ፣ አስደሳች ፣ አማቂ ወዘተ... ስሜት በመፍጠር ስለነገሮች አቋምና አመለካከት እንዲኖረን ያደርጋል ። በእነዚህ በሚቀሰቅሳቸውና በሚፈጥራቸው ኃይለኛ ስሜቶች ሥነ ውበት ግንዛቤያዊ ተልዕኮ እንዳለው ለመረዳት ይቻላል ።

(ኪነ ጥበብን ይመለከቷል ።)

## ሥነ ግብ

*(Teleology)*

ማንኛውም ተፈጥሮአዊ ፣ ማኅበራዊና ኅሊናዊ ነገር ያለውና የሚኖረው ፣ አመጣጡና ምንነቱ የሚወሰነው በሚያከናውነው ግብ ነው የሚል የሐሳባዊ ፍልስፍናን አጠቃላይ አመለካከት የሚገልጽ ጽንሰ ሐሳብ ነው ። ግብን ቀዳሚ ስለሚያደርግ ተፈጥሮን በአጠቃላይ ለግብ አገልጋይ መሣሪያ አድርጎ የሚመለከት ነው ። በዚህ አመለካከት መሠረት ግብን የሚፈጥረው መሣሪያው አይደለም ፤ ይልቁንም የግብ በቅድሚያ መኖር ለመሣሪያው ምክንያት ነው ።

ይህ አመለካከት ጠንካራ መሠረት አለኝ የሚለው በተለይ የእንስሳትና የሰው ክንዋኔዎች በግብ መመራታቸውን በማስመልከት ነው ። ሕይወት ያለው ነገር ሁሉ ፍላጐቱን ለማርካት አመቺ የሆኑ የአፈጻጸም መሣሪያዎች አሉት ። ለምሳሌ ዓይን ለማየት ይጠቅማል ፤ የዓይንን አመጣጥ ፣ ጠባይና አሠራር ሊያስረዳን የሚችለው የሱ ፈጣሪ የሆነው የማየት ግብ ነው ። ዓይን ዝም ብሎ ከጭፍን ክንዋኔ ወይም ከዕድል የተገኘ አይደለም ። የሚያስፈልገውን ሁኔታ ሁሉ አሰባስቦና ተስማሚ መሣሪያ አድርጎ የቀረፀው የማየት ግብ ነው ።

ሥነ ግብ የሚቃወመው በተለይ ተናክሶታዊ ቁስአካልነትን ነው ። በሥነ ግብ አመለካከት ተናክሶታዊ ቁስአካልነት ሕይወት ያላቸውን ውስብስብ ክስተቶች በተናክሶታዊ መንገድ ብቻ ለማስረዳት ያደረገው ጥረት

ከንቱ ነው። ቃላት በዕድል ተሰብስበው መጽሐ
ፍ መሆን እንደማይችሉ ሁሉ በሥነ ግብ አመለ
ካከትም ቁሳዊ ብናኞች በጭፍን ሁኔታ ተገጣጥ
መው ሕይወት ያለው ነገር ሊፈጥሩ ጨርሶ
አይችሉም። በተለይ የውስብስብ ነገሮችን ውስ
ብስብነት ልንረዳ የምንችለው በግብ የሚመራ
የሂደት ውጤት መሆናቸውን በመቀበል ነው።

ሥነ ግብ አዘውትሮ የሚቃወመው የተና
ክኦታዊ ቁስአካልነትን ድክመት ነው። ተናክ
ኦታዊ ቁስአካልነት ሁሉን ነገር ውስብስብ
ክስተቶችንም ጭምር በተናክኦታዊ አሠራር
አስረዳለሁ ማለቱ ስህተት ነው። ይህ ማለት
ደግሞ ሥነ ግብ ትክክል ነው ማለት አይደ
ለም። ሥነ ግብ የሐሳባዊ ፍልስፍናን ድክመ
ትና መሠረታዊ ስህተት የሚያንፀባርቅ ነው።
በቁስአካል የዕድገት ሂደት ውስጥ የተገኙት
መሣሪያዎች ግብን ማምጣታቸው ተክዶ
በተገላቢጦሽ ማለትም ተገብሮት ወደ መን
ሥኤ በመቀየር የግብ ተገብሮት ማድረግ የሐሳ
ባውያን የተለመደ አስተሳሰብ ነው። የተፈ
ጥሮ ዕድገት በሳይንሳዊ መረጃ መረጋገጥ
ሥነ ግብን መሠረት አሳጥቶታል። በመሆኑም
የቅራኔ ሕጎች ተፈጥሮን ወደ ውስብስብ ደረጃ
በመውሰድ ሕይወት ያላቸውና በግብ የሚ
መሩ ነገሮች ሊከሰቱ ችለዋል የሚለው የዲ
ያሌክቲካዊ ቁስአካልነት አመለካከት ትክክል
ሆኖ ይገኛል።

(ተናክኦታዊ ቁስአካልነትን ፣ ሐሳባዊነትን ይመለከቷል ።)

## ሥነ ፋይዳ
(*Axiology*)

የፋይዳዎችን አመጣጥ ፣ ይዘት ፣ ፍች ፣
ተዕዕኖ ወዘተ... የሚያጠና የፍልስፍና
ክፍል ሲሆን በሐሳባዊና በቁስአካላዊ አቀ
ራረብ የተከፈለ ነው። ኅሊናዊ ሐሳባውያን
የፋይዳዎችን ነባራዊነት በመካድ ጥሩ ፣
መጥፎ ፣ ውብ ወዘተ... ስንል የምንገልጸው
የነገሮችን ነባራዊ ጠባይ ሳይሆን የራሳችንን
ውስጣዊና ኅሊናዊ ስሜትና ብያኔ ነው
ይላሉ። ነባራዊ ሐሳባውያን ግን ፋይዳዎችን
በማዕረግ ከተፈጥሮ እጅግ የላቁ በማድረግ
ምንጫቸው መንፈሳዊው ዓለም ነው ይላሉ።
ራሳቸውን ችለው በነባራዊነትም የሚኖሩ
አድርገው ይመለከቷቸዋል።

ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ስለፋይዳ የሚ
ሰጠው ግንዛቤ የተመሠረተው በፋይዳዎች
ማኅበራዊና ታሪካዊ ጠባይ ላይ ነው። ፋይዳ
ኅሊናዊ ብቻ አይደለም ፤ ምክንያቱም የሚ
ገኘው ከሰው ድካምና የሥራ ውጤት በመ
ሆኑ ነው። ፋይዳ ሰዎች በኅብረት የሚያገ
ኙትና በኅብረት የሚቀበሉት ክስተት ነው።
ሰው በታሪክ ሂደት ውስጥ የሚያፈልቃቸው
በመሆኑ ነባራዊ ሐሳባውያን እንደሚሉት
ፋይዳዎች ከሰዎች በፊት የሚኖሩ አይደ
ሉም። የኮሚኒስት ሥርዓት ግንባታ ለሰው
ደስታንና ነፃነትን የሚሰጥ በመሆኑ ከፋይዳ
ዎች ሁሉ ከፍተኛው ነው።

(ፋይዳን ይመለከቷል ።)

## ሦስተኛው ኢንተርናሽናል
(*Third International* 1919–1943)

እንደ አንደኛውና እንደ ሁለተኛው
ኢንተርናሽናሎች ይህም ኢንተርናሽናል የወ
ዝአደሩ ዓለም አቀፋዊ የትግል ድርጅት
ሲሆን ብዙውን ጊዜ በአጭር አጠራር
ኮሚንተርን በመባል ይታወቃል።

ሦስተኛው ኢንተርናሽናል ይፋ በሆነ
መንገድ መጋቢት 1919 በሞስኮ ከሃያ አንድ
ሀገሮች በመጡ ሠላሳ አምስት የወዝአደሩ
የፖለቲካ ድርጅቶች ተመሥርቶ ሥራውን
ይጀምር እንጂ ሐሳቡና ዝግጅቱ ቀደም ካለ
ጊዜ ጀምሮ ሲብላላና ሲካሄድ ቆይቷል።
ከዚህ በላይ በሌላ ስፍራ እንደተመለከተው
ሁለተኛው ኢንተርናሽናል እንደካውትስኪ ፣
እንደሻይደማን ፣ እንደ ሎንካን ወዘተ... በመሳ
ሰሉ አድርባዮችና ከላሾች አመራር ሥር
በመዋሉ እነሌኒን አብዮታውያን ማርክሳ
ውያንን የሚያሰባስብ አዲስ ኢንተርናሽናል
እንደሚያስፈልግ አስቀድመው ተገንዝበውት
ነበር። በኢምፔሪያሊስቶች የተቀሰቀሰው
አንደኛው የዓለም ጦርነት በ1914 ሲጀመር
ከሁለተኛው ኢንተርናሽናል መሪዎችና አባል
ፓርቲዎች አብዛኞቹ ጦርነቱን በመደገፋ
ቸው ዓለም አቀፋዊው የወዝአደሩ አንድነት
ሀልውናውን አጣ። ቦልሼቪኮችና ከሌሎችም
ሀገሮች የወዝአደር ፓርቲዎች ሐቀኞቹና
አብዮተኞቹ ከአድርባዮች በመለየት ቀስ
በቀስ መሰባሰብ ጀመሩ። በ1915ና በ1916

ሁለት ስብሰባዎችን በዚመርቫልድና በኬንታል (በስዊስ) አድርገው ለአዲሱ ኢንተርናሽናል ዝግጅት ሲያደርጉ ቆዩ ። ቦልሼቪኮች በጥቅምት 1917 ሶሻሊስት አብዮት አካሄደው በጥር 1918 በርከት ያሉ ኮሚኒስቶችን በፔትሮግራድ ሰብስበው ስለአዲሱ ኢንተርናሽናል ምሥረታ ተወያዩ ። ከላይ እንደ ተመለከተው የኮሚኒስት ፓርቲዎች ተወካዮች በመጋቢት 1919 ሞስኮ ላይ ተሰብስበው ሦስተኛውን ኢንተርናሽናል መሠረቱ ። ከሐቀኛ ማርክሳውያን ውስጥ ካርል ሊብክኔሽትንና ፣ ሮዛ ሉክስምበርግን የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል ። ሦስተኛው ኢንተርናሽናል ከበፊቶቹ ሁለት ኢንተርናሽናሎች ልዩ የሚሆንበት ወዝአደሩ ሥልጣን በጨበጠበት ወቅት የተካሄደ መሆኑ ነው ። ኮሚንተርን ባደረጋቸው ጉባኤዎቹ የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት አከናውኗል ።

## የመጀመሪያው የኮሚንተርን ጉባኤ

ኮሚንተርን በመጀመሪያው ጉባኤው ከታላቁ የጥቅምት 1917 የሶሻሊስት አብዮት በኋላ የነበረው ወቅት የካፒታሊስት ሥርዓት የሚወድቅበት ፣ የወዝአደሩ አብዮት የሚያብብበትና ድል የሚቀዳጅበት በመሆኑ ፣ የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት ምን እንደሆነና አስፈላጊነቱ በሚገለጽበት ፣ ወዝአደሩ ከከፊል ወዝአደርና ከደሃ ገበሬ ጋር የጠበቀ ትብብር በሚፈጥርበት ፣ የካፒታሊስት ሀገር የወዝአደር የትግል ድርጅቶችን ከጭቁን ሕዝቦች ፀረ ኢምፔሪያሊስት የትግል ንቅናቄዎች እንደዚሁም ሶሻሊስት ሀገሮች እርስ በርሳቸውና ከወዝአደሩና ከጭቁን ሕዝቦች የትግል ድርጅቶች ጋር የትግል አንድነታቸውን በሚመሠርቱበትና በሚያጠናክሩበት የሶቭዬት ዓይነት ሥርዓት በየሀገሩ በሚቋቋምበት ሁኔታ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል ።

ከያንዳንዱ አባል ፓርቲ አንዳንድ ተወካይ ፣ ከተወካዮች አምስት አባላት ያሉበት ቢሮ አቋቁሟል ፤ ግሪጎሪ ዚኖቭዬቭ የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት ፣ አንጀሊካ ብላባኖቭ የመጀመሪያው ፀሐፊ ሆነው ተመርጠዋል ። ፕሮግራሙንም አጽድቋል ።

## ሁለተኛው የኮሚንተርን ጉባኤ

በ1920 (ነሐሴ) የተደረገው 2ኛው የኮሚንተርን ጉባኤ ደንቡን ፣ በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ላይ የተመሠረተውን ድርጅታዊ መዋቅሩንና አባል ለመሆን መሟላት ያለባቸውን 21 ነጥቦች አፀደቀ ። ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ፦—

- የወዝአደሩን የበላይ ገዥነት መቀበል፤
- ከመሐል ሰፋሪዎችና ከጠጋኞች ጋር የነበረውን ግንኙነት ሙሉ በሙሉ ማቋረጥ ፤
- ሕጋዊና ሕጋዊ ባልሆነ የትግል ስልት መጠቀም ፤
- በገጠር ፣ በጦር ኃይል፣ በሙያ ማኅበሮችና በፓርላማ ውስጥ ያላሰለሰ ትግል ማድረግ ፤
- ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን መቀበልና ሥራ ላይ ማዋል ፤
- የኮሚንተርንን ውሣኔዎች ማክበርና ሥራ ላይ ማዋል ፤
- ለሶሻሊስት ሀገሮች ተገቢውን ድጋፍ መስጠት ፤

ከነዚህም ሌላ ሁለተኛው የኮሚንተርን ጉባኤ በብሔራዊ ቅኝ ግዛታዊ ጥያቄ ላይ የሌኒንን በኩረ ሐሳብ አጽድቋል ።

## ሦስተኛው የኮሚንተርን ጉባኤ

ከሐምሌ 22 — ነሐሴ 12 ፣ 1921 የተካሄደው ሦስተኛው የኮሚንተርን ጉባኤ ዓለም አቀፍ የወጣት ኮሚኒስት ሊግንና ቀዩን ዓለም አቀፍ የሠራተኛ ማኅበር አጸደቀ ። የቡርዧዚውን ኅብረትና ፋሺስታዊ ድርጊት ለመቋቋም የሠራተኞች ግንባር መፈጠር እንዳለበት አሳሰበ ።

## አራተኛው የኮሚንተርን ጉባኤ

ከኅዳር 9 እስከ ታኅሣሥ 5 ፣ 1922 የተካሄደው አራተኛው የኮሚንተርን ጉባኤ በሁንጋሪና በኢጣልያ የተከሰተው ፋሺስታዊ አምባገነንነት ሊያስከትል በሚችለው አደጋ ላይ ከፍተኛ ትኩረት በማድረግ ፋሺዝምን ለመቋቋም የሠራተኞች ኅብረት ግንባር እንዲፈጠር ጥሪ አደረገ ።

## አምስተኛ የኮሚንተርን ጉባኤ

አምስተኛው የኮሚንተርን ጉባኤ (1924) በማንሠራራት ላይ የነበረውን ፋሺዝም ለመቋቋምና ድል ለመምታት በየሀገሩ የኮሚኒስት ፓርቲዎች እንዲቋቋሙና በርዕዮተ ዓለምና በድርጅት የቦልሼቪኮችን አርአያ እንዲከተሉ መመሪያ አወጣ ። በመከሰት ላይ የነበረውን ትሮትስኪዝምንም መዋጋት ጀመረ ።

## ስድስተኛዉ የኮሚንተርን ጉባኤ

ስድስተኛው ጉባኤ (1928) መደብ ለመደብ ፍልሚያ ( ክላስ ቨርሰስ ክላስ) የሚለውን አዲስ የትግል ታክቲክ በመቀየስ ወዝ አደሩ አጋሮቹን አሰባስቦና አሰልፎ የቡርዧዚውን ጭቆናና ብዝበዛ እንዲቋቋም መመሪያ አወጣ ።

## ሰባተኛዉ የኮሚንተርን ጉባኤ

ሰባተኛው ጉባኤ የፋሺዝምን መስፋፋት ለመቋቋም የሚያስችል የሕዝባዊ ኃይሎች ግንባር የሚቋቋምበትን ዘዴ ቀይሶ በብዙ የአውሮፓ ሀገሮች እስከ 1939 ድረስ ፋሺስቶችን ለመቋቋም ተችሏል ።

በ1943 (ሰኔ) በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ፀረ ፋሺስት ግንባሩን በማጠናከር ድልን ለመቀዳጀትና የኮሚንተርን አባላት የሶቭዬት መጣሪያዎች ናቸው ተብለው ይወነጀሉና ችግር ይደርስባቸው ስለነበር እነዚህን ኮሚኒስት ፓርቲዎች ቡርዧዚዎች ከሚያደርሱት ጥቃት ለማዳንና በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የተፈጠረውን ፀረ ፋሺስት ግንባር ለማጠናከር ሲባል በሰኔ ወር 1943 ሦስተኛው ኢንተርናሽናል እንዲፈርስ ተደረገ ።

በሦስተኛው ኢንተርናሽናል አመሠራረትና አመራር ግንባር ቀደም ሚና ከተጫወቱት መካከል ፥— ሌኒን ፥ ስታሊን ፥ ዲሚትሮቭ ፥ ሊብክኔኽትና ሮዛ ሉክሰምበርግ ይገኙባቸዋል ።

## ሦስቱ ጣምራ ጠላቶች
*(The Triad Enemies)*

የሠርቶአደሩ ሕዝብ ቀንደኛ ጠላቶች የሆኑት ፊውዳሊዝም ፥ ኢምፔሪያሊዝምና የነዚህ የሁለቱ ውላጅ የሆነው ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ናቸው ። በተለይ ገና በማደግ ላይ ያሉት ሀገሮች ያሉበት የኅብረተሰብ የዕድገት እርከን በአመዛኙ ከፊል ፊውዳልና ከፊል ካፒታሊስት ነው ። በነዚህ ሀገሮች ያሉ ሠርቶ አደር ሕዝቦች ከሚደርስባቸው ጭቆናና ብዝበዛ ነፃ ለመውጣትና የዕድገት አቅጣጫቸውን በሶሻሊስት ፈር ለመቀየስ ትግል በሚያደርጉበት ጊዜ እነዚህ ሦስት ጠላቶች በአንድ ወገን በመሰለፍ ይዋጓቸዋል ። ስለዚህ ሠርቶ አደሮች ይህን ፀረ ሦስት ማለትም ፀረ ፊውዳል ፥ ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት አቋም በመያዝና እነዚህን የጋራ ጠላቶቻቸውን በአንድነት ሆነው በመታገል ምዝበራና ጭቆና የሌለበትን ሶሻሊስት ኅብረተሰብ ለመመሥረት በቁርጠኝነትና በመሥዋዕትነት ይታገላሉ ።

(ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ይመለከቷል ።)

# ሰ

## ሰላማዊ ሰልፍ
*(Demonstration)*

ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ በአደባባይና በይፋ የሚደረግ ትዕይንተ ሕዝብ ነው ። ሰዎች ደስታቸውንም ሆነ ቅሬታቸውን ለማሳወቅ በጉልህ የተጻፉ መፈክሮችን በመያዝና በቃልም በማሰማት በርካታ ሰዎች በሚገኙባቸው አደባባዮችና ዋና ዋና መንገዶች እየተዘዋወሩ ድጋፍ የሚሰጡበት ወይም ተቃውሞ የሚያሰሙበት ስልት ነው ።

ለምሳሌ በቅድመ አብዮትና በአብዮቱ የመጀመሪያ ወቅት የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ሌሎችም የኅብረተሰብ ክፍሎች አድኃሪውን መንግሥትና ሥርዓት በመቃወም ያደረጓቸው ሰላማዊ ሰልፎች የተቃውሞ ሲሆኑ መሬትን ለሰፊው የገጠር ሕዝብ ያደረገውንና የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት አዋጆችን በመደገፍ በየቦታው የተደረጉት ሰላማዊ ሰልፎች ሰፊው ሕዝብ ከልብ የተሰማውን ደስታ የገለጸባቸውና ሙሉ ድጋፉን ለአብዮቱ የሰጠባቸው ነበሩ ።

## ሰላማዊ ሽግግር
*(Peaceful Transition)*

ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም (ኮሚኒዝም) ለመሸጋገር በሚደረገው ሕዝባዊ ትግል የወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ሲፈቅድ ከፍተኛ አመፅ ፣ የርስ በርስ ጦርነትና ጥፋት ሳያስከትል ሊደረግ የሚችል አንዱ የአብዮታዊ ሽግግር ቅርፅ ነው ። በታሪክ እስከ ዛሬ የዚህ ዓይነቱ አብዮታዊ የሽግግር ዘዴ ብዙም የታየ ባይሆንም ሊኖር እንደሚችል ግን አይካድም ። ይህም የሚሆነው የወዝአደሩ የኃይል ሚዛን አይሎ ሲገኝ ፣ የገዥው መደብም በኃይል ሲዳከምና ፣ በሌሎችም የወቅቱ ተጨባጭ ምክንያቶች በወዛደሩ ላይ ግልጽ የሆነ የማጥቃትና የአፈና ርምጃ ለመውሰድ ሲሳነው ነው ። ይህም ቡርዧዚው አቋሙን አለዝቦ ሲገኝ ትግሉ ለተራማጅና ለአብዮታዊ ኃይሎች ምቹ ይሆናል ። ነገር ግን በነዚህ መለስተኛ ድሎች በመጠቀም ትግሉን ይበልጥ በማፋፋም አድኃሪውን ገዥ መደብ ይበልጥ ለማዳከም ካልተቻለ ሰላማዊ አብዮታዊ ሽግግር ሊከናወን አይችልም ። ሁኔታው ከተቀየረ ትግሉ የመረረና ሕዝባዊ አመፅን የሚያስከትል ሊሆን ይችላል ።

ሰላማዊ ሽግግር ፋብሪካዎችን ፣ ባንኮችንና መሰል የኢኮኖሚ ዘርፎችን ቀስ በቀስ የሕዝብ በማድረግ ፣ የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ፖሊሲ በዲሞክራሲያዊ መንገድ በመቀየስ ፣ በመምራትና በመቆጣጠር ፣ በምርት ዕቅድና አፈጻጸም የሠራተኛውና የመላው ሠርቶ አደር ሕዝብ ተሳትፎ እንዲኖር በማድረግ ፣ በአጠቃላይ የኅብረተሰቡን ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች በዲሞክራሲያዊ መንገድ በመምራት ሊከናወን የሚችል የሥርዓት ለውጥ ነው ። ባለንበት ዘመን የሶሻሊስት ሥርዓት መጠናከር ፣ የቅኝ አገዛዝ መንኮታኮት ፣ በትላልቅ ካፒታሊስት ሀገሮች የተራማጅ ኃይሎች መጠናከርና የአብዮታዊ ንቅናቄው ማኅበራዊ መሠረት እየሰፋ መሄድ ፣ ከዚሁ ጋርም ኮሚኒስቶችና ተራማጅ ኃይሎች በቡርዧው ፓርላማ ውስጥ ገብቶ በመሳተፍና በዲሞክራሲያዊ ተቋሞች በመጠቀም ተደማጭነታቸውን እያሰደጉ መሄድ ለሰላማዊ አብዮታዊ ሽግግር መኖር ሁኔታዎችን የሚያመቻቹ ናቸው ። ይህም ሆኖ ግን በአንድ አብዮት ሂደት ውስጥ በአንድ ደረጃ ላይ አድኃሪ ገዥ መደቦች አብዮታዊውን ንቅናቄ በኃይል ለመምታት ሊነሡ ስለሚችሉ የአብዮቱ ወገኖች አብዮታዊ የትጥቅ ትግል ዘዴን ለመከተል የሚገደዱበት ሁኔታ ሊኖር መቻሉ መዘንጋት የለበትም ።

ሰላማዊ ሽግግር በአዝጋሚ ሂደት ካፒታሊዝምን መለወጥ ይቻላል ከሚለው የማኅበራዊ ዲሞክራቶች አድርባይ አቋም የተለየ ነው ። ሰላማዊ ሽግግር ሂደቱ ዝግ ያለና ሰላማዊ ይምሰል እንጂ አድኃሪው መደብ ሥልጣኑን ካልለቀቀ ወደ አመፃዊ አብዮታዊ ሽግግር የሚያመራ ይሆናል ። የዚህም ሽግግር ዓላማ ወዛደሩን

ሙሉ ሥልጣን ለማስጨበጥ ስለሆነ ከተወሰነ ሂደት በኋላ የገኘሮውን መደብ ዓቅም አሳጥቶ ወዛደሩን ሥልጣን ለመረከብ ወደሚችል በት ደረጃ ያደርሰዋል ።

(አብዮታዊ ሽግግርን ይመለከቷል ።)

## ሰላም አብሮ የመኖር መርህ (በ—)
*(Peaceful Co–existence)*

የተለያዩ ርዕዮተዓለም የሚከተሉ ሀገሮች በመግባባትና በመተባበር በሰላም ለመኖር የሚፈጥሩት ግንኙነት በሰላም አብሮ የመኖር መርህ ይባላል ።

በሰላም አብሮ የመኖር መርህን መቀየስ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘበት ዋና ምክንያት የሶሻሊስት አብዮት እንቅስቃሴ በዓለም ላይ በተመባሳይ ፍጥነት አለማደጉ ነው ። በሩሲያው የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት በሶቭዬት ኅብረት የሶሻሊስት መንግሥት ሲመሠረት በዙሪያው የሚገኙ ሀገሮች የካፒታሊስቱን ሥርዓት የሚከተሉ ነበሩ ። ስለዚህ ቅራኔዎች ተካርረው የመጋፈጥ ሁኔታ ቢፈጠርና ብዙዎች ካፒታሊስት ሀገሮች ቢረባረቡበት ለጋው አብዮት አደጋ ላይ እንደሚወድቅ በመገንዘብ ሌኒን የሶሻሊስት ሶቭዬት ኅብረትን ህልውና ለመጠበቅና ለሶሻሊስት ግንባታ አመች ሁኔታን ለመፍጠር በሰላም አብሮ የመኖርን መርህ መቀየስ ነበረበት ።

በሰላም አብሮ የመኖር መርህ ሦስት የተሳሳቱ ትርጉሞች ተሰጥተውታል ። የመጀመሪያው የተሰነዘረው ከቀኝ ክንፍ ቡርዧዎች ሲሆን ፍሬ ሐሳቡም በሰላም አብሮ የመኖር መርህ አብዮትን በስውር ለማዛመት እንዲያመች ኮሚኒስቶች የፈጠሩት ታክቲክ ወይም ወጥመድ ነው የሚል ነው ። ይሁን እንጂ ኮሚኒስቶች አብዮት የአንድ ሀገር ውስጣዊ ሁኔታ የሚወልደው ነው ብለው ስለሚያምኑ የአብዮትን ከሀገር ሀገር መዛመት ጨርሶ አይቀበሉም ። ሁለተኛው የተሳሳተ ትርጉም ከተራማጅ መሰል (ሊበራል) ቡርዧዚዎች የመነጨው ሲሆን በነዚህ አመለካከት በሰላም አብሮ የመኖር መርህ በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም መካከል የሚካሄደውን የተጧጧፈ ፖለቲካዊና ርዕዮተ ዓለማዊ ትግል ለማዳከምና ለማጥፋት ፣ ብሎም ሁለቱን ሥርዓቶች ለማቀራረብና በመካከላቸው ያለውን ልዩነት አቻችለው እንዲዋሀዱ ለማድረግ የታቀደ ዘዴ ነው የሚል ነው ። ይሁን እንጂ ካፒታሊዝምና ሶሻሊዝም ተፃራሪ ሥርዓተ ማኅበሮች በመሆናቸው በመካከላቸው ያለው ልዩነት ተወግዶ ውህደት ይፈጥራሉ የሚለው አባባል ተቀባይነት አይኖረውም ። ሌላው ሦስተኛው ትርጉም በተለያዩ "የግራ" ክንፍ ቡድኖች የተሰነዘረ ሲሆን ዋናው አቋሙም ይህ መርህ ሶሻሊስት ሀገሮች በዓለም ላይ የሚካሄደውን አብዮታዊ ትግል እንዳይደግፉ ስለሚያደርግ የወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነትን ዓላማ ከመቃወሙም በላይ ፀረ ኢምፔሪያሊዝም እንቅስቃሴ በሰፊው እንዳይካሄድ ዕንቅፋት ይሆናል የሚል ነው ። እነዚህ ግራ አክራሪ ቡድኖች በሰላም አብሮ በመኖር መርህ ፈንታ ውጥረትን ፣ በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም መካከል በየአቅጣጫው የፊት ለፊት ግጭት መፍጠርንና አብዮትን በኃይል ማዛመትን ይመርጣሉ ።

በታሪክ ተደጋግሞ እንደታየው ግን በሰላም አብሮ የመኖር መርህ የዓለምን ሶሻሊስት አብዮት ሂደት ለማፋፋም የሚረዳ እንጂ የሚያዳክም አይደለም ። ሰላም ለሶሻሊስት ኅብረተሰብ ግንባታና ለተፋጠነ ዕድገት አመች ሁኔታን ይፈጥራል ። የተፋጠነ ዕድገት የተጠናከረ ሶሻሊስታዊ ሥርዓትን ለመፍጠር ያስችላል ። የተጠናከረ የሶሻሊስት ሥርዓት ደግሞ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሶሻሊስት አብዮትን ሂደት የማጠናከር ዕድሉ ወይም ችሎታው የበለጠ ይሆናል ።

(ዴታንትን ይመለከቷል ።)

## ሰላም አክራሪነት
*(Pacifism)*

በማንኛውም ዓይነት ጦርነት መካፈልንና መሥዋዕት መሆንን የሚቃወም ፣ በደፈናው የሰላምን ፍላጎት የሚገልጽ የቡርዧ አሳሳችና ለዘብተኛ አዝማሚያ ነው ። ሰላም አክራሪነት ስለጦርነት ባለው ሐሳባዊ ግንዛቤ ትክክለኛ ጦርነትን ትክክለኛ ካልሆነ ጦርነት መለየት ስለሚሳነው በተባበረ የሰፊው ሕዝብ ትግል

ኢምፔሪያሊዝምን መደምሰስና ሶሻሊዝምን
መመሥረት የሰላም ብቸኛ ዋስትና መሆኑን
እይቀበልም ። ቡርዧዎች የራሳቸውን የጦር
ነት ፖሊሲና ዝግጅት በመሸፈን ጭቁን
ሕዝቦች ለሰላም ፣ ለዲሞክራሲ ፣ ለብሔራዊ
ነፃነትና ለሶሻሊዝም የሚያደርጉትን ትግል
ለማጨናገፍ ሕዝቦችን የሚያወናብዱት በዚህ
ሰላማዊነት በሚል ውኸንብር ነው ። ይህ
የተሳሳተ የሰላም ስሜትና ግንዛቤ በተለይ
በአንደኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ የ"ጎሊና
ተቃውሞ" ፣ በጦርነቱ ውስጥ "አለመሳተፍ"
በሚሉ ማንኛውንም ጦርነት እንደ "ኃጢ
አት" በሚቆጥሩ አስተሳሰቦች ሰፊው ሕዝብ
ትክክለኛ አቋም ይዞ በፀረ ኢምፔሪያሊስቱ
ጦርነት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዳያደርግ
ተፅዕኖ አድርጓል ። ስለዚህ ሰላም አክራሪ
ነት የጦርነትን ቁሳዊ መሠረትና መደባዊ
ይዘት ካለመረዳቱም በላይ የተሟላ ሰላም
ከሶሻሊዝም ተነጥሎ ሊታይ የማይችል
መሆኑን ባለመገንዘብ በሰላም ስም በጦር
ነት ላይ ያለው አቋም በእርግጥም ሰላምን
የሚያጠናክር ሳይሆን ጭቁን ሕዝቦች በኢ
ምፔሪያሊዝም ላይ የሚያካሂዱትን ጦርነት
በማዳከም የኢምፔሪያሊስቶችን የጦርነት
ፖሊሲ የሚያጠናክር አዝማሚያ ነው ።

## ሰላም ውል (የ—)

(*Non Aggression Pact or Peace Treaty*)

በጦርነት ላለመፈላለግ ፣ አንዱ በሌላው
ላይ በኃይል ከመጠቀም ለመቆጠብና ልዩነ
ቶችን በውይይትና በዕርቅ ለመፍታት በመን
ግሥታት መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው።
የዚህ ዓይነቱ ስምምነት በሚመለከታቸው
መንግሥታት መካከል እንደተነሣው ችግር
ዓይነትና ጥንካሬ እያንዳንዱ ሀገር (ወይም
ከሁለቱ አንዱ) የወቅቱን የኃይል አሰላለ
ፍና የራሱንም ዐቅም ገምቶ በጊዜያዊነት
የሚያደርገው ወይም ችግሩን ለዘለቄታው
ለመፍታት የሚያስችል ሊሆን ይችላል ።

ለምሳሌ በመጋቢት 1918 አዲሱ የሶ
ቭዬት መንግሥት ገና ባልተጠናከረበት ፣ ወታ
ደራዊ ይዞታው በጣም በተዳከመበት ወቅት
በጀርመን ተፅዕኖ በሁለቱ ሀገሮች መካከል
የተደረገው የብሬስት ሊቶቭስክ የሰላም
ውል ለጊዜው ሩሲያ ከግዛቷ የተወሰኑትን
ክፍሎች ለጀርመን ለመልቀቅ የተገደደ
ችበት ነበር ። ይህ ስምምነት ለሶቭዬት
መንግሥት ጊዜና ፋታ በመስጠቱ የሶቭዬት
መንግሥት አቋሙን ካጠናከረ በኋላ ውሉን
ውድቅ ሊያደርገውና የተወሰዱበትንም ግዛ
ቶች ሊያስመልስ ችሏል ።

## ሰላም ፕሮግራም (የ—)

*(Peace Programme)*

በ1971 በሶቭዬት ኅብረት ኮሚኒስት
ፓርቲ 24ኛ ጉባኤ ለሰላምና ለዓለም አቀፍ
ኅብረት ፣ ለሕዝቦች ብሔራዊ ነፃነትና ማኅ
በራዊ ዕድገት የተነደፈ የትግል ፕሮግራም
ነው ። በዚህ መሠረት የሰላም ፕሮግራም
የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት ፣

—በደቡብ ምሥራቅ እስያ ጦርነቶች
ሊቀስቀሱ የሚችሉባቸውን ሁኔታ
ዎች ማስወገድ ፤ በዚህም ረገድ የተ
ባበሩት መንግሥታት ድርጅት በሚ
ፈጥራቸው አመች ሁኔታዎች ሁሉ
በሚገባ በመጠቀም ማንኛውንም
የወረራ እርምጃ በአፋጣኝ መግታት ፤
በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረትም ችግ
ሮችን በሰላማዊ መንገድ በመፍታት
ፈንታ በኃይል መጠቀምን ማውገዝ ፤
—ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት
(1939—45) በኋላ በአውሮፓ የተደ
ረገውን የሀገሮች ድንበር ለውጥ
በሙሉ ልብ መቀበልና በአውሮፓ
የጋራ ደኅንነትን ማረጋገጥ ፤

—የኑክሊየር ፣ የኬሚካልና የባክቴሪዮሎ
ጂካል የጦር መሣሪያዎች በሥራ ላይ
እንዳይውሉ ማድረግ ፣ የኑክሊየር
ጦር መሣሪያዎች ሙከራ ማንም በየ
ትም ቦታ እንዳያደርግ ለማቆም
መቻል ፣ ከኑክሊየር ጦር መሣሪያ ነፃ
የሆኑ አካባቢዎች እንዲመሠረቱ መታ
ገልና የኑክሊየር ጦር መሣሪያ ባለቤት
የሆኑ መንግሥታት ሁሉ ይህን
ትጥቃቸውን እንዲፈቱ ጥረት ማድ
ረግ ፤

—የጦር መሣሪያን እሽቅድምድም ለማ
ቆም በየሀገሩ የሚገኙት የውጭ የጦር

ሰፈሮች እንዲነሡ ማድረግና በተለይ እንደ መካከለኛው አውሮፓ በመሳሰሉ ወታደራዊ ግጭት ሊነሣ በሚችል ባቸው አካባቢዎች ለጦር ኃይሎችና ለመሣሪያዎች ቅነሳ የሚደረገውን ትግል ማጠናከር ፤ በአጋጣሚና ሆን ተብሎ በሚፈጸም ወታደራዊ ትንኮሳ ጦርነት እንዳይቀስቀስ የሚያስችል ዘዴና መንገድ መፈለግ ፤

—በተባበሩት መንግሥታት ውሳኔዎች መሠረት የቅኝ አገዛዝ ቅሪቶችን ጨርሶ ማጥፋትና ዘረኝነትንና አፓር ታይድን መታገል ፤

—በጋራ ትብብርና ጥቅም አካባቢን ለሕይወት በሚስማማ ሁኔታ በመጠበቅ የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠቀም ፤ የመጓጓዣና የመገናኛ አገልግሎቶችን ማስፋፋትና ማዳበር ፤ እጅግ አሳሳቢ የሆኑትን በሽታዎች ማጥፋት ፤ ወደ ሕዋውና ወደ ውቅያኖሶች በሚደረገው ጉዞ ፣ በጥናት ፣ በምርምርና በሌሎችም መስኮች ለጋራ ደኅንነትና ጥቅም መንግሥታት ተባብረው የሚሠሩበትን ሁኔታ መፍጠር ።

ይህ የሰላም ፕሮግራም በ1976 እና በ1981 በሶቭዬት ኅብረት ኮሚኒስት ፓርቲ 25ኛና 26ኛ ጉባኤዎች ተሻሽሎና ዳብሮ ቀርቧል ።

## ሰሜን አትላንቲክ ቃል ኪዳን ድርጅት

*(North Atlantic Treaty Organization, NATO)*

ሶሻሊስት ሀገሮችን ለመፃረርና ብሔራዊ የእርነት ንቅናቄዎችን ለማፈን የሰሜን አትላንቲክ ካፒታሊስት መንግሥታት ያቋቋሙት ወታደራዊና ፖለቲካዊ ኅብረት ነው ። ኔቶ በአሜሪካ ግፊትና ጉትጎታ በሚያዝያ 1949 በአሜሪካ ፣ በእንግሊዝ ፣ በፈረንሳይ ፣ በቤልጅግ ፣ በሆላንድ ፣ በሉክሰምበርግ ፣ በካናዳ ፣ በኢጣሊያ ፣ በፖርቱጋል ፣ በኖርዌይ ፣ በዴንማርክና በአይስላንድ ዋሽንግተን ውስጥ ተመሠረተ ። በ1952 ግሪክና ቱርክ የኔቶ አባል ሀገሮች ሲሆኑ በ1954 ጀርመን ፌዴራል ሪፐብሊክም የዚሁ ድርጅት አባል ሆናለች ። በታኅሣሥ 1981 የኔቶ አባል ሀገሮች ተወካዮች ስፓኝ የኔቶ አባል ሀገር እንድትሆን የሚያስችላትን ውሳኔ በፊርማቸው አጽድቀዋል።

በዚሁ ወቅት አሜሪካ በሶቭዬት ኅብረትና በዋርሶ ቃል ኪዳን ሶሻሊስት ሀገሮች ላይ የሚሳይሎችና የኑክሊየር ጦር መሣሪያዎች ለማጥመድ የሚያስችላትን ውሳኔ አሳልፏል ። የዚህ ውሳኔ ዓላማ ኔቶ በዋርሶ ቃል ኪዳን ድርጅት ላይ ወታደራዊ የበላይነት እንዲኖረው ማድረግ ነው ። ይሁን እንጂ ይህ ድርጊት የጦር መሣሪያ እሽቅድድምን በማባባሱ ዓለምን በስጋት ላይ እየጣለ ነው ።

ከኔቶ አባል ሀገሮች መካከል ፈረንሳይ ከድርጅቱ ወታደራዊ ኅብረት በ1966 ስትወጣ ግሪክም የፈረንሳይን ፈለግ በመከተል በ1974 ከወታደራዊ ኅብረቱ ራሷን አግልላለች ።

የኔቶ ከፍተኛ ውሳኔ አውጪ አካል የሰሜን አትላንቲክ ምክር ቤት ሲሆን የምክር ቤቱ የዕለት ተዕለት ሥራ የሚከናወነው በአባል ሀገሮች ቋሚ ልዑካን ነው ። የድርጅቱ ጽሕፈት ቤት የሚገኘውም በብራስልስ ነው ።

## ሰርጎገብ

*(Infiltrator)*

በወታደራዊ ሳይንስ በጠላት ሠራዊት መሥመር ውስጥ ሽምቆ በማለፍ በሰተጀርባ አደጋ እየጣለ የጠላትን ኃይል አሰላለፍ የሚበታትን ልዩ ሥልጠና ያለው የሠራዊት አባል ወይም አካል ነው ። በሀገርም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሰላምንና የመረጋጋትን መጠናከር የማይፈልጉ አያሌ ኃይሎች በአሁኑ ወቅት እየተበራከቱ በመምጣታቸው ቃሉ የነሱ ምግባር መግለጫ ጭምር ሆኗል ። በዚህ ትርጉሙ ሰርጎገብ ያንድን ሀገር ፀጥታና መረጋጋት ለማደፍረስ አንድ አድኃሪ መንግሥት ወይም ድርጅት እያሰታጠቀ ወደ ሌላ ሀገር የሚያስማራውና ሽምቆ እየገባ በሕዝብ ላይ የውንብድና ተግባር የሚፈጽም የጥፋት መልክተኛ ነው ።

በአሁኑ ጊዜ ሰርጎገብነት የኢምፔሪያሊዝም ግፊት ዓይነተኛ መሣሪያ ነው ። በመንግሥታት መካከል በሰላም አብሮ የመኖር መርህ እንዲሰፍን ፣ ሉዓላዊነትና ብሔራዊ ዳር ድንበር እንዲከበር ፣ በመካከላቸው የሚነሡ ግጭቶችና አለመግባባቶች በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ የሚያዙት ዓለም አቀፍ ሕጋዊ መመሪያዎች ተፈጻሚነት እንዳያገኙ ኢምፔሪያሊዝም ከሚጠቀምባቸው የጠብ አጫሪነት ዘዴዎች አንዱ ሰርጎገብነት ነው ። ከዚህም በላይ ሰርጎገብ ሀገርንና አብዮትን ለመበታተን በትጥቅ መስክ የሚሰለፍ ብቻ ሳይሆን በረቀቀ ዘዴ በሕዝቡ መካከልና በአብዮቱ ሰፈር ገብቶ በፖለቲካ ውዥንብር ሕዝብን የሚያሸብር ፣ የኢኮኖሚ አሻጥር የሚፈጽምና የሀገርን ነፃነትና አንድነት በከፍተኛ አደጋ ላይ የሚጥል አድኃሪ ተልዕኮ ጭምር ያለው ነው ። በዚህ መልኩ ሰርጎገብ ለሕዝብ ተቆርቋሪና አብዮተኛ መስሎ በረቀቀ ዘዴ በመግባት ከውስጥ አብዮትን የሚቦረቡር አስመሳይ ነው ።

(አስመሳይ ተራማጅን ይመለከቷል ።)

## ሰብነት
*(Personalism)*

ሰብእ ፣—ነፍስና ሥጋ ያለው ፣ ነፍሱ ከሥጋው አንድ የሆነ ፣ ሥጋ ብቻ ወይም ነፍስ ብቻ ያልሆነ

ሰብ ማለት ተፈጥሮ ካስገኛቸው እውነታዎች ሁሉ የተለየ ቦታ ፣ ሚና ፣ ችሎታና ክብር ያለው ፍጡር ነው የሚል በ20ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ የተስፋፋ ሃይማኖታዊና ሐሳባዊ ፍልስፍና ነው ። ይህ የሰብ ልዩ ባሕርይ የፍልስፍና አስተሳሰብ ዋና መመሪያ መሆን አለበት ስለሚል ሰብን የተፈጥሮ ማዕከልና መድረሻ አድርጎ ይወስዳል ። መላው ተፈጥሮ እርስ በርሱ የተሳሰረና የተዋቀረ ሲሆን ሰብ ግን አንድ ነፃና ማዕከላዊ የሆነ የእንቅስቃሴ ፣ የአስተሳሰብ ፣ የፍላጐት ፣ የስሜት ምንጭ አለው ። ሌሎች ነገሮች የሚለዋወጡ ፣ አንዱ በሌላው የሚተካ ሲሆን ሰብ ግን ባለው ግላዊ ባሕርይ የተነሣ በሌላ የማይተካ ነው ።

በሰብነት ፍልስፍና መሠረት የሰውን መንፈሳዊና ሥጋዊ ባሕርያት በአንድነታቸው ማየት ስለሚያስፈልግ ሰው በቁስ አካል ወይም በሐሳብ ብቻ የማይገለጽ ስለሆነ ሰብ የሚያደርገው የሁለቱ ውህደት ነው ። ቁስአካል የሐሳብ ተገዥና ምስል ብቻ ሳይሆን ሰብ እራሱን የሚገልጸውና ችሎታውን ነባራዊ የሚያደርገው በቁስአካል አማካይነት ነው ስለሚል ሰብነት የሐሳባዊ ፍልስፍና ተቃዋሚነቱን ይገልጻል ። በሌላ በኩልም ቁስአካላውያን እንደሚሉት ኅሊና የቁስአካል ነፀብራቅ ሳይሆን የእንቅስቃሴ ምንጭ በመሆኑ የቁስአካል ውጤት ሆኖ ሊቆጠር አይገባም ይላል ። እንደ ሰብነት አባባል ሰብ የቁስ አካል ወይም የሐሳብ ተገዥ ሳይሆን የነፃነቱ መሠረት ሰብ በሥጋዊ አካሉ ከነባራዊ እውነታ ጋር ተግባራዊ ግንኙነት መፍጠሩና በዚህም ጊዜ የሚያሳየው የእንቅስቃሴ ምክንያት ደግሞ ከመንፈሳዊነቱ መመንጨቱ ነው ።

ሰብነት ሰው ሰብ ነው በማለት ለሰው ነፃነትና ክብር የሚከራከር ቢመስልም የሰውን ነፃነትና ክብር ከሰማይ እንደወረደ እንጂ የታሪክ ዕድገትና የሰው የሥራ ችሎታ ውጤት አድርጎ ስለማይቀበል ዓላማውን መልሶ ይሸራል ። የሰብ ክብርና ነፃነት የሚመሠረትበትንና የሚወሰንበትን ማኅበራዊ ግንኙነት መዘንጋቱ የፍልስፍናውን ሐሳባዊነት ያሳያል ። የመብትና የግዴታ ዓይነትም ሆነ ስፋት በምርት ግንኙነቶቹ ዓይነት የሚወሰን በመሆኑ ታሪካዊና ማኅበራዊ ነው ። ሰብ የተፈጥሮ ፀጋ ሳይሆን ማኅበራዊ ፋይዳ በመሆኑ ከመደብ ትግል ሂደት ውጭ የሚታይ አይደለም ።

ሰው በተፈጥሮው ሰብ ነው ማለት ሰው ከማኅበራዊ ሕይወት ሁኔታው ውጭ ነፃነትና ክብር አለው ማለት በመሆኑ ጨቋኝ ሥርዓትን ማድበስበስ የሰብነት ሰውር የመደብ ተልዕኮ መሆኑን ይጠቁማል ። በመደብ በተከፋፈሉ ሥርዓቶች ውስጥ የአምራቹ ዜጋ መብትና ክብር መገፈፍና የዚህም ምክንያት የምርት ግንኙነቶቹ ዓይነት መሆኑን ካለመገለጽ እልፎ እንዲያውም የሰውን ሰብ መሆን በረቂቅ አመለካከት ላይ መመሥረት ማለት የገዥው መደብ ተባባሪ መሆን ማለት ነው ።

## ሰብአዊ መብት
(*Human Rights*)

ሰዎች መሠረታዊ ፍላጐታቸውንና ጥቅማቸውን ለማስከበር በሕግ የሚኖሯቸውን መብቶች ሁሉ የሚያጠቃልል ሰፊ ጽንሰ ሐሳብ ነው ። የመደብ ኅብረተሰብ ታሪክ

እንደሚያመለክተው ለነዚህ መብቶች መረጋገጥ ለዘመናት ከፍተኛ መሥዋዕትነት የተከፈለበት ትግል ሲካሄድ ቆይቶአል ። አያሌ ምሁራንና የፖለቲካ መሪዎችም ስለ ሰብአዊ መብቶች በየበኩላቸው ያሏቸውን አስተሳሰቦች በየወቅቱ ገልጸዋል፤ እየገለጹም ናቸው ።

በታኅሣሥ 10 ፣ 1948 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ መሠረታዊ የሰው ልጅ መብቶች የሚል ሰነድ አውጥቷል ። በዚህ ታሪካዊ ሰነድ ውስጥ የሰፈሩት መርሆች ሁሉ ሕዝቦችና መንግሥታት ሊታገሉላቸው የሚገቡ ናቸው ። በዚህም መሠረት ሰዎች ያላንዳች ተፅዕኖ በእኩልነት ለመኖር ለማኅበራዊ ደኅንነት ፣ ለሰብአዊ ክብርና ለፍትህ ያሏቸው መብቶች ተጠቅሰዋል ። ከዚህም በተጨማሪ ሰዎች ሠርቶ ለመኖር ፣ ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያ ለማግኘት ፣ ሐሳባቸውን በንግግርና በጽሑፍ ለመግለጽ ፣ ለመሰብሰብና ለመደራጀት ፣ ሠርቶ ለማረፍና በአግባቡ ለመደሰት ፣ ለመማርና በኅብረተሰቡ ማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ለመሳተፍ ሊኖሯቸው የሚገቡትን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ይዘረዝራል ። በአጠቃላይ በሰው ልጅ ላይ የሚካሄዱት የቀለም ፣ የዘር ፣ የሃይማኖት ፣ የፆታ ፣ የሀገር ልዩነትና ኢሰብአዊ ድርጊቶች መሠረታዊ መብቱን ስለሚገፉት መወገድ ያለባቸው ናቸው ።

ሰብአዊ መብቶችን ተግባራዊ የማድረግ ሁኔታ እንደየኅብረተሰቡ ተጨባጭ ሁኔታ ፣ ማለትም እንደ ማኅበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሥርዓቱ ይለያያል ። በዚህ መሠረት በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ሰብአዊ መብቶች በሕግ የሚታወቁ ብቻ ሳይሆኑ በተግባርም የተረጋገጡ ናቸው ። ለዚህም የሠርቶ አደሩ ሕዝብ መንግሥት ዋስትና ይሰጣል ። በመሆኑም በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርህ መሠረት ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በመንግሥታዊ አስተዳደርና በማኅበራዊ ጉዳዮች ሰፊ ተሳትፎ የሚያደርግበትን ሁኔታ ይፈጥራል ። የዜጐች ኢኮኖሚያዊ ዋስትናም ብሔራዊ ኢኮኖሚው በሕዝባዊ ይዞታ ሥር መሆኑና የሕዝቡን ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጐቶች ለማርካት በማዕከላዊ ዕቅድ እየተመራ ማደጉ ነው ።

በካፒታሊስት ሀገሮች መብታቸው በተሟላ ሁኔታ የሚከበርላቸው ሀብታሞች ብቻ ናቸው ። ምንም እንኳ የቡርዧ መንግሥታት ለዜጐቻቸው የይስሙላ እኩልነትና ነፃነት ቢለፍፉም እንደእውነቱ ከሆነ ግን መደባዊ አቋማቸው ዛሬ በሀገሮቻቸው ውስጥ የሚታዩትን ሥራ አጥነት ፣ ዘረኝነትና የዘር መድልዎ የመሳሰሉትን አስከፊ ማኅበራዊ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሏቸው አይደሉም ። ይህ እየታወቀ ኢምፔሪያሊስቶች ሕዝቦችን ለማሳመን በየዕለቱ በሚያደርጉት የሀሰት ፕሮፓጋንዳ የሶሻሊስት ሀገሮችን እውነታ በማዛባት በነዚህና በተራማጅ ሀገሮች ሰብአዊ መብት ጨርሶ እንደሌለና በካፒታሊስት ሀገሮች ግን ይበልጥ እያበበ በመሄድ ላይ እንደሚገኝ ይሰብካሉ ። ይህም ሆን ብለው ሕዝቦች ከጭቆናና ከብዝበዛ ለመላቀቅ ከኢምፔሪያሊዝምና ከአድኅሮት ጋር የሚያደርጉትን ትግል ለማለዘብና ከትክክለኛው የትግል ፈር ለማዛነፍ የሚያካሂዱት የርዕዮተዓለም ትግል ነው ። በዚህም ሕዝቦች ለብሔራዊና ለማኅበራዊ ነፃነት የሚያደርጉትን ትግል "እንደሽብር" በመቁጠር ሲወነጅሉ ይገኛሉ ። ሐቁ ግን በሶሻሊስት ሀገሮች ዜጐች ሁሉ የመማር ፣ የመሥራት ፣ የማረፍና የመደሰት መብታቸው ተረጋግጧል ። የዕድገት ጉዳናቸውን በሶሻሊስት የዕድገት ፈር የቀየሱት ሀገሮችም ዓላማ ሕዝቦቻቸውን ከኢምፔሪያሊዝም ብዝበዛና ተፅዕኖ ጨርሶ ነፃ በማውጣት ሰብአዊ መብቶቻቸውን በተጨባጭ ማረጋገጥ ነው ።

(ሰብአዊነትን ፣ ዲሞክራሲን ፣ ነፃነትን ይመለከቷል ።)

## ሰብአዊነት

*(Humanism)*

የሰውን ሀልውናና ክብር በማስመልከት ሰው ራሱን ለመግዛትና እሱነቱን በራሱ ኃይል የበለጠ እውን ለማድረግ የሚችል ፍጡር ነው የሚልና ለዚህም የሰው መብት መከበር አቆማለሁ የሚል የሐሳባዊ ፍልስፍና ዘርፍ ነው ።

ከዘመነ ተሃድሶ ጀምሮ የፍልስፍናን ጥያቄ ከእግዚአብሔር የበላይነት ይልቅ በሰው ሀልውና ምርምር ላይ እንዲያተኩር በማድረጉ ሰብአዊነት ለቡርዧው ሥርዓት መጠናከር ያገለገለ ንድፈ ሐሳብ ነው ። በፊውዳሉ ሥርዓት ውስጥ ፍልስፍና የሃይማኖት አገልጋይ ሆኖ ሥነ መለኮት በበላይነት ይገዛ ስለነበር ዋናው ጥያቄ በእግዚአብሔር ጉዳይ ላይ

ያተኮረ በመሆኑ ለሰው የተሰጠው ቦታና ሚና በጣም ዝቅተኛ ነበር ። በመሆኑም የፊውዳሉ ሥርዓት መውደቅ ፍልስፍናን ከሃይማኖት ቀጥተኛ ተፅዕኖ በማላቀቁ ሰው ከፊውዳሉ ጨለማ ሥርዓት መውጣቱና የራሱን ሕይወት የመወሰን መብት መጨበጡ የሚገለጽበት ዓይነተኛው አስተሳሰብ የሰብአዊነት ፍልስፍና በመሆን ብቅ ለማለት ቻለ ። ሰብአዊነት ሰውን ለሚመለከቱ ጥያቄዎች ቅድሚያ በመስጠት የሰውን ክብር ፣ መብትና ጥቅም በይፋ እያስታወቀ ለሰው ተከራካሪ ሆኖ የተነሣ ፍልስፍና ነው ። በመሆኑም ይህ ፍልስፍና ሃይማኖትን የሚቃወም ባይሆንም በኅብረተሰብ ውስጥ ሰው የሚገባውን ክብርና ቦታ መያዝ እንዳለበት በተለይም የራሱን ኑሮ ያለምንም የውጭ ተፅዕኖ ለመወሰን እንደሚችል በማስተጋባት ሰው የማንም መጫሪያ ሳይሆን ተፈጥሮና ማኅበራዊ ሕይወት የርሱ አገልጋይ መሆን እንዳለባቸው ይሟገታል ።

ይህ ፍልስፍና በእርግጥም ተራማጅ የሆነ አመለካከት ቢታይበትም በውስጡ ግን የሚፋለሱ ሐሳቦችን ያዘለ ነው ፤ ምክንያቱም ሰው ለማንም መጫሪያ መሆን የለበትም ቢልም ፍልስፍናው የተስፋፋበት የካፒታሊስቱ ሥርዓት ግን ሰው የካፒታል አገልጋይና መጫሪያ ሆኖ የሚቆጠርበት ሥርዓት በመሆኑ ነው ። ይህም ሰብአዊነት ስለሰው የሚናገረው በረቂቅ አስተሳሰቦች ክልል ውስጥ ብቻ ተወስኖ እንጂ ከሥርዓቱ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሣት እንዳልሆነ ያሳያል ። ሰብአዊነት ሰው የሚለው ማኅበራዊ ሰውን ሳይሆን ግለሰቡን ብቻ ነው ። ስለሆነም በሰብአዊነት አስተሳሰብ የሰው ክብርና መብት በግል ይዞታ ላይ የተመሠረቱ መሆናቸው ግልጽ ይሆናል ። ካፒታሊዝም ቡርዧዚውን የምርት መጫሪያዎች ባለቤትና የወዛደሩን ጉልበት ደግሞ የግል ሸቀጥ በማድረጉና ይህንን ሁኔታ ሕጋዊ እንዲሆን የግለሰቦች ክብርና መብት የሚለውን አስተያየት መመሪያ አድርጎ መውሰድ በማስፈለጉ ሰብአዊነት ለዚህ ግላዊ አመለካከት አመች መሠረት ሊሆን ችሏል ። በግል ስለሰው እኩልነት ፣ ነፃነትና መብት ማውሳት የካፒታልን ግላዊ ባሕርይ የሰው ልጅ መብት አስከባሪ አድርጎ ማቅረብ መሆኑ ግልጽ ነው ። እዚህ ላይ የተረሳው መሠረታዊ ነጥብ ግን ሰው ማኅበራዊ መሆኑና የሰው መብትም የሚመነጨው ከማኅበራዊ ሥርዓቱ መሆኑ ነው ። ስለዚህም የሰውን መብትና ክብር ማስከበር የሚቻለው ግላዊነት የሰፈነበትን የካፒታሊስት ሥርዓት በማፍረስ የሶሻሊስት ሥርዓትን በመገንባት ይሆናል ። እንዲያ ቡርዧዚ ፣ ሌላውን ደግሞ ወዛደር የሚያደርገው ሥርዓት ግለሰቦችን በመደብ የሚከፋፍል በመሆኑ በዚሁ ሁኔታም ግለሰቦች እኩል ክብርና መብት ሊኖራቸው ስለማይችል በዚህ ሥርዓት ውስጥ የሰውን ክብርና መብት ለማስከበር የሚደረገው ጥረት ከንቱና አሳሳች መሆኑን መገንዘብ እያዳግትም ።

(ሶሻሊስት ሰብአዊነትን ይመለከቷል ።)

## ሰናይና እኩይ
*(The Good and the Evil)*

ሰናይ = መልካም ፣ ውብ ፣ ደግ ፣ በጎ ፣ በመልክም ሆነ በጠባይ ደስ የሚያሰኝ
እኩይ = የከፋ ክፉ ፣ መጥፎ

ሰናይና እኩይ የማኅበራዊ ክስተቶችንና የሰውን ተግባር ግብረገባዊ ብያኔ የሚገልጹ የሥነ ምግባር ፈርጆች ናቸው ። ኅብረተሰቡ ወይም ተራማጁ መደብ ግብረገባዊ አድርጎ በመውሰድ ሰዎች መከተልና ማክበር አለባቸው የሚላቸው ሕጎች ፣ ልምዶች ፣ አስተሳሰቦች ፣ ደንቦች ወዘተ... ሰናይ ሲባሉ ጎጂ በመሆናቸው የተነቀፉና ሰዎች ሊርቋቸው የሚገባቸው ነገሮች እኩይ በመባል ይታወቃሉ ።

በዝባዥ መደቦች በአምላካዊ ትዕዛዝ ወይም በዲበአካላዊ መርሆች ላይ በመመሥረት ሰናይና እኩይ ዘላለማዊና ሁለንታዊ ባሕርይ እንዳላቸው ይናገራሉ ። ይህ አመለካከት የብዝበዛው ሥርዓት ኃላፊ ሆኖ እንዳይታይና ተጠያቂ እንዳይሆን የሚረዳ መሆኑ ግልጽ ነው ።

ሐሳባዊ ፍልስፍና ለሰናይና ለእኩይ የሚሰጠው ፍች መንፈሳዊ ነው ። ግብረ ገብን ከቁሳዊ ሁኔታና ከሰዎች ቁሳዊ ኑሮ በመነጠል ሰናይና እኩይ የሚለዩት ከሚሰጡት ሐሳብ ጥራትና የሐሳብ የበላይነትን ለማስፈጸም ከሚኖራቸው ሚና አንፃር መሆኑን ይናገራል ። ሰናይ ማለት የሐሳብ የበላይነትን

የሚያግዝ ፣ የሚያረጋግጥ ማለት ሲሆን እኩይ ደግሞ ሐሳብን ተገዥ የሚያደርግ ነው ። ለምሳሌ ነፍስ ሥጋን መቆጣጠር ሲችል ነው ሰው ግብረገባዊ ኑሮ የሚኖ ረው ። በአንፃሩም ቁስአካላዊ ፍልስፍና ለሰ ናይና ለእኩይ ምድራዊ ፍች በመስጠት ከደስታ አኳያ መደንገግ እንዳለባቸው ይገል ጻል ። ሰናይ ማለት ደስታን የሚያስገኝ ፣ እኩይ ለደስታ ዕንቅፋት የሆነ ነው የሚል ትርጉም ሰጥቷል ።

በማርክሲዝም ሌኒኒዝም መሠረት ሰናይና እኩይ ዘላለማዊና ግላዊ ሳይሆኑ የታሪክ ሂደት ውጤቶች ናቸው ። የአንድ ኅብረተሰብ ግብረገባዊ አመለካከት የሚመሠረተው ካለው የምርት ግንኙነቶች ሁኔታ በመሆኑ የሰናይና የእኩይ ፍች ታሪካዊና ማኅበራዊ ነው ። ደስታ የሚመነጨው ሰው ከሰው ጋር ባለው ግንኙነት በመሆኑ መሠረቱ ማኅበራዊ ነው ። ኅብረተሰቡን ወደፊት የሚያራምድና የሰዎ ችን ፍላጎት የሚያሟላ ሁሉ ሰናይ ሲሆን እኩይ ለዚህ ሂደት ዕንቅፋት የሚሆን ማንኛውም ነገር ነው ። በተለይም ኀታችና አድኃሪ ጠባይ ያላቸው ድርጊቶች ፣ ሐሳች ፣ አስተሳሰቦች ወዘተ... እኩይ በሚለው ፈርጅ ውስጥ የሚመደቡ ናቸው ። በአንድ ወቅት ተራማጅ በመሆኑ ሰናይ የነበረው በሌላ ወቅት ወደመሰናክልነት ተለውጦ እኩይ መሆኑ የሚያስረዳው በሰናይና በእኩይ መካከል ያለውን ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት ነው ።

(ሥነምግባርን ፣ ላዕላይ መዋቅርን ይመ ለከቷል ።)

## ሰን ሲሞን፣ ክሎድ አንሪ ደ ሩቭሯ

*(Saint Simon, Claude Henri de Rouvroy)*

ከ1760—1825 የኖረ በፈረንሳይ አብ ዮት ወቅት ከጃኩቢኖች ጋር የጠበቀ ግንኙ ነት የነበረው ፣ በአሜሪካም ውስጥ ለነፃነት በተደረገው ጦርነት የተሳተፈ ፈረንሳዊ ተምኔታዊ ሶሻሊስት ነው ። ሰን ሲሞን የፈረ ንሳይ ቁስአካላውያን አመለካከት ተከታይ ሲሆን እምላከኛነትንና ሐሳባዊነትን በተለ ይም የጀርመን ሐሳባዊነትን አጥብቆ የሚ ቃወም ነው ።

ኅብረተሰብን በማሳደግ ረገድ የወሳኛ ዊነት ፍልስፍና ከፍተኛ ሚና አለው ለሚ ለው አመለካከት ሰን ሲሞን ከመቆሙም በላይ ታሪክ የሕግ ተገዥ ነው የሚለውን ሐሳቡን ለማሳመን ከፍተኛ ጥረት አድርጓል ። በሱ እምነት እንደተፈጥሮ ሳይንስ ሁሉ ታሪ ክም ለሰው ልጅ ርምደት አስተዋጽኦ ማድ ረግ ይኖርበታል ።

በሰን ሲሞን አመለካከት እያንዳንዱ ማኅበራዊ ሥርዓት በታሪክ ውስጥ አንድ ርምጃ ነው ። ያም ሆኖ የኅብረተሰብ ዕድገት አንቀሳቃሽ ኃይሎች የሳይንሳዊ ዕውቀት ርምደት ፣ ግብረገብና ሃይማኖት ናቸው ። በዚህ መሠረት ታሪክ ሦስት ደረጃዎችን ያልፋል ። እነሱም የባሪያ አሳዳሪና የፊውዳል ኅብረተሰቦችን የሚሸፍነው የሃይማኖት የበ ላይነት የሰፈነበት የሥነ መለኮት ዘመን ፣ ፊውዳላዊና ሥነ መለኮታዊ ሥርዓት ተቀባ ይነት አጥቶ የተንኮታኮተበት ዲበአካላዊ ዝመን ፣ እንዲሁም መጪው ኅብረተሰብ በሳይንስ ላይ የሚመሠረትበት የተጨባጫ ዊነት ዘመን ናቸው ።

ሰን ሲሞን ለታሪክ ያለው አመለካከት ሐሳባዊ ይሁን እንጂ ማኅበራዊ ርምደት ተጨባጭ ሂደት ነው የሚለውን አመለካከቱን እንዲሁም በኅብረተሰብ ዕድገት ውስጥ ሀብ ትና መደቦች ስለሚጫወቱት ሚና የሰነዘረ ውን የመጠቀ ግምት ሊያፋልስበት አልቻ ለም ። ከሁሉም በላይ በሥነ ኅብረተሰብ ጥናቱ ውስጥ የሰነዘረው ጽንሰ ሐሳብ እያንዳ ንዱ ማኅበራዊ ሥርዓት ከርሱ በፊት የነበ ረው ታሪካዊ ዕድገት ግኝት መሆኑን ለማሳ የት ረድቷል ።

በሰን ሲሞን አመለካከት የወደፊቱ ኅብረተሰብ የሚመሠረተው የግል ሀብትና የመደቦች ህልውና እንደተጠበቀ ሆኖ ሳይን ሳዊ አደረጃጀትና ዕቅድ ባለው ትላልቅ ኢን ዱስትሪ ላይ ይሆናል ። የበላይነቱን ሚና የሚጫወቱት ሳይንስና ኢንዱስትሪ ፣ ሳይን ቲስቶችና ባለኢንዱስትሪዎች ናቸው ። በሁለ ተኛ ደረጃ የሚከተሉትም ሠራተኞች ፣ ነጋዴ ዎችና ባለባንኮች ናቸው ። የኢንዱስትሪው ዕቅድ የሚወጣው የኅብረተሰቡን ብዙኃን አባላት በተለይም የድሆችንና በዝቅተኛ ኑሮ የሚኖሩትን ጥቅም እንዲጠብቅ ተደርጎ

ነው ። ግንኛውም ሰው የመሥራት መብቱ የተጠበቀ ሲሆን የሥራውም ዓይነት በችሎታው መጠን ይሆናል ።

ሰን ሲሞን ስለመጪው ኅብረተሰብ የአስተዳደር ሥርዓት የሰነዘረው አስተያየት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው ። በመጪው ኅብረተሰብ ውስጥ በሰዎች ላይ የሚካሄደው የአገዛዝ ሥርዓት በጉዳዮችና በምርት አስተዳደር ይተካል የሚለው ግምቱ የሚደነቅ ሲሆን የአዲሱ ኅብረተሰብ ገንቢ የመሆን ታሪካዊ ተልዕኮ ያለው ወዝአደሩ መሆኑንና የማኅበራዊ አብዮትን አስፈላጊነት ሊገነዘብ አለመቻሉ ግን ሰን ሲሞንን ተምኔታዊ አሰኝቶታል ።

(ተምኔታዊ ሶሻሊዝምን ይመለከቷል ።)

## ሰው
## (*Man*)

በሥነ ሕይወታዊ አመለካከት ሰው የተፈጥሮ ዕድገት ከፍተኛው ውጤት ነው ። ሰው ከዳበሩ እንስሳዎች የሚለየው በማሰብና በንግግር ችሎታው ነው ። እንስሶች በአካባቢያቸው ላይ ያላቸው ከንዋኔ በደመነፍስ የሚወሰን ሲሆን የሰው ከንዋኔ ግን የሚወሰነው በስሜቶቹ ፣ በፍላጐቶቹና በፈቃዱ እንዲሁም ሰው ስለ ተፈጥሮና ስለኅብረተሰብ ሕግጋት ባለው የዕውቀት ደረጃ ነው ።

ሐሳባውያን እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን የሰው መለያ ነጥቦች ፍጹማዊ በማድረጋቸው ነው የሰው ምንነት ከአመክንዮ ፣ ከኅሊና ፣ ከሃይማኖት ወዘተ... ይገኛል የሚሉት ። ሰውን ከእንስሳ የሚለየው ነጥብ ግን ሰው ተፈጥሮን ለመቀየር ባለው ግብ የማምረቻ መሣሪያዎችን ማምረት መቻሉ ነው ። እንስሶች ከተፈጥሮአዊው ሁኔታ ጋር ተስማምተው የሚኖሩ ሲሆኑ ሰው ግን ባለው የማምረት ችሎታ ተፈጥሮን ለሱ ተስማሚ የሚያደርግ ነው ።

ሰው ከሰዎች ተለይቶ ሊኖር አይችልም ። ሰው በተወሰኑ ማኅበራዊ ሁኔታዎች የሚቀረፅ በመሆኑ ትክክለኛ ትርጉም የምናገኘው ከማኅበራዊ ኑሮ ሳንገነጥለው የማኅበራዊ ግንኙነቶች ድምር ውጤት አድርገን ስንመለከተው ነው ። የሰውን ተግባር የሚያንቀሳቅስና እውንና ነባራዊ ኃይሉን የሚቀርፅ የሰው ቁስአካላዊ ኑሮ ሁኔታ መሆኑን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተማረው ማርክሲዝም ነው ። ምንነቱን የሚገልጹ የሰው መለያ ጠባዮች (ንቃተ ኅሊና ፣ መንፈሳዊ ኑሮ ፣ በማምረቻ መሣሪያዎች የመጠቀም ችሎታው) በሙሉ የማኅበራዊ ሥራ ውጤቶች ናቸው ። ትክክለኛውንና ተጨባጭ ባሕርዩን ልንገነዘብ የምንችለው የሰው ባሕርይ በተወሰነ ታሪካዊ ማኅበራዊ ሥርዓት መወሰኑን ስንቀበል ነው ። በዚህ ጊዜም መመልከት የሚኖርብን ሰው በታሪክ ሂደት ውስጥ የተከማቸውን ባህል የሚወርስ በመሆኑ ሰው እራሱ የሰዎች ትብብር አጠቃላይ ውጤት መሆኑን ነው ።

በመጨረሻም ይህ ያለፈውን ባህል የመውረስ ችሎታው የሚወሰነው ባለው የምርት ባሕርይ ነው ። ተፃራሪ መደቦች ባሉበት ሥርዓት ውስጥ ያለው የሥራ ክፍፍል ሁኔታ የሰውን አካላዊና መንፈሳዊ ችሎታዎች በአንዳኝና ነፃ በሆነ መንገድ ሊያሳድጋቸው አይችልም ። የአእምሮና የጉልበት ሥራ መለያየትና መፃረር የሚገልጸው ሰው የሚያዳብረው አንድ ጐኑን ብቻ መሆኑን ነው ። የብዙኀኑ መበዝበዝና መጨቆን ሰዎች በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዳያደርጉ ያግዳቸዋል ። በሰዎች ታሪክ የተጠራቀመውን ባህላዊ ሀብትም እንዳይወርሱ ያደርጋቸዋል ። ሰው የተሟላ ዕድገት አግኝቶ የግል ስጦታዎቹንና ፍላጐቶቹን ሊያዳብር የሚችለው በኮሚኒስት ሥርዓት ውስጥ ብቻ ነው ።

(ሶሻሊስት ሰብአዊነትን ፣ ንቃተ ኅሊናን ፣ ተግባርን ይመለከቷል ።)

## ሰውኛነት
## (*Anthropomorphism*)

ሕይወት ላላቸውና ለሌላቸው ተፈጥሮአዊ ነገሮችና ክስተቶች ፣ የሰውን ሥነ ልቡናዊ ባሕርያት ፣ አካላዊ ቅርፅ ፣ የሰብአዊነት ገጽታ የሚያጐናፅፍ አመለካከት ነው ። በተለይም በጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት ውስጥ (እስከተወሰነም ደረጃ ቢሆን በአሁኑም ወቅት) የሰው ልጅ ስለዓለም ምንነት በቂ ዕውቀት ባልነበረው ጊዜ ወይም በራሱና

በአካባቢው በሚገኙ ክስተቶች መካከል ያሉትን መሠረታዊ ልዩነቶች ጠንቅቆ ባልተረዳበት ጊዜ ሕይወት የሌላቸውን ነገሮች ሕይወት እንዳላቸው ፣ እንደሚሞቱና ገጠመኝ እንዳላቸው አድርጎ በመውሰድ ሰብአዊ ባሕርይ የሚሰጥ አመለካከት ነው ።

በማኅበራዊ ገጽታው ሰዎች ያላቸውን ባሕርይና ችሎታ ለአንድ ኃይል በማጐናፀፍ ይህንን ኃይል በማምለክ ከሱ በጐ ድርጊትን ሲጠብቁ የሚያንፀባርቁት ሰውኛነትን ነው ።

## ሱቦትኒክ
*(Subbotnik)*

በሩሲያ ቋንቋ ሱቦታ (ቅዳሜ) ከሚለው የመጣ ሲሆን በትርፍ ቀን ያለክፍያ የሚደረግ የነፃ ሥራ አገልግሎትን ያመለክታል ። የሩሲያ ሠራተኛ መደብ የዕድገት ጐዳናውን በሶሻሊዝም ዓላማዎች ላይ ማራመዱን በተያያዘባቸው የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ውስጥ በፈቃደኝነት ተነሣሥቶ የፈጠራ ችሎታውንና የሥራ ጀግንነቱን ያስመሰከረው በኮሚኒስት ሱቦትኒክ ነበር ። ሱቦትኒክ ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በማኅበራዊ ሂደተ ምርት ውስጥ ለሥራ የሚኖረውን ኮሚኒስታዊ አመለካከት የቀረፀበት ትምህርት ቤቱም ነው ።

ኮሚኒስት ሱቦትኒክ ለመጀመሪያ ጊዜ እውን የሆነው በ1919 ሲሆን በወቅቱ ሩሲያ በውጭ ወራሪዎችና በውስጥ ፀረ አብዮተኞች ውጥረት ላይ ነበረች ። መላው ዜጋ በአንድ በኩል የሶሻሊስት እናት ሀገሩን ደኅንነት ለመጠበቅ በግንባር ሲዋደቅ በሌላ በኩል ደግሞ ኢኮኖሚውን ለማሳደግ ብርቱ ጥረት እንዲያደርግ ታሪካዊ ጥሪ የተላለፈበት የፈተና ጊዜ ነበር ። ይህንኑ ዓላማ መሠረት በማድረግ በሞስኮ ካዛን የባቡር ሐዲድ ውስጥ የሚሠሩ ኮሚኒስቶች ሚያዝያ 12 ቀን 1919 ቅዳሜ ዕለት ለአሥር ሰዓት ነፃ አገልግሎት ሰጡ ። ከጥቂት ቀናት በኋላም 205 የባቡር ሐዲድ ሠራተኞች የተሳተፉበት ሕዝባዊ ሱቦትኒክ ተካሄደ ። በዚያው ወራት በሞስኮና በሌሎችም ከተሞች የሚገኙ ሠርቶ አደሮች አርአያነቱን ተከተሉ ። እንቅስቃሴው በወታደራዊ ክፍሎችና በመላ ሀገሪቱም በመስፋፋቱ የሱቦትኒክ ተቀባይነት እያደገ መጣ ።

ይህንኑ በማየት በ1920 የተካሄደው የፓርቲው ዘጠነኛ ጉባኤ "የሜይ ዴይን" በዓል ምክንያት በማድረግ ሱቦትኒክ እንዲዘጋጅ ውሳኔ በማስተላለፉ ሠርቶ አደሮች ሁሉ ዕለቱን በሥራ አሰቡት ። ታላቁ የቦልሼቪክ ፓርቲ መሪ ሌኒንም ክሬምሊን ቤተ መንግሥት ውስጥ በተደረገው የኮሚኒስት ሱቦትኒክ ላይ ተሳትፏል ። ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በሱቦትኒክ አማካይነት ከቀሰመው ልምድና ካስገኘው ውጤት በመነሣት ሌኒን "ታላቅ እጀማመር" በሚለው ጽሑፉ ትንተና አቀረበ ። ጽሑፉ በብዙ ብሔረሰቦች ቋንቋዎች በመዘጋጀቱም የሱቦትኒክ ዓላማና ተግባር በሰፊው ታወቀ ። ብሔራዊ ኢኮኖሚን ለመገንባት ፣ ሀገሪቱን በኢንዱስትሪ ለማበልጸግና የባህል አብዮትን ለማካሄድ በተደረገው ጥረት ሠራተኛው ሕዝብ በኮሚኒስት ሱቦትኒክ አማካይነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

ዛሬም በሶቪዬት ኅብረት ውስጥ የሚከበሩ የተለያዩ ሕዝባዊ በዓላትን ምክንያት በማድረግ ዜጎች ሁሉ የሚሳተፉበት ሱቦትኒክ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅቶ በርካታ ተግባሮች ይከናወናሉ ። የሱቦትኒክ አሠራር ይዘትና ባሕርይ በሶሻሊስት የሥራ ውድድር መርህና ድርጅታዊ መዋቅር ላይ የተመሠረተ ነው ። በሠርቶ አደሩ ሕዝብ ጥቅምና ፍላጎት ላይ ተመሥርቶም በተግባር በመገለጡ እያሌ የፈጠራ ሥራዎችንና አዳዲስ የምርምር ውጤቶችን አስገኝቷል ። የምርት ኃይሎችም በከፍተኛ ደረጃ እያደጉ በመሄዳቸውና ግንኙነቱም ሶሻሊስት ፈር በመያዙ የሥራ ምርታማነት በይበልጥ ሊዳብር ችሏል ።

የሶቪዬት ሠርቶ አደር ሕዝብ በሌኒናዊ ፓርቲው ግንባር ቀደምነት እየተመራ በሱቦትኒክ የጀመረውን የፈቃደኝነት ጥረት ዛሬም በመቀጠል ለኮሚኒዝም ምሥረታ የሚያበቃውን ቴክኒካዊና ቁሳዊ መሠረቱን በማጠናከር ላይ ይገኛል ።

(ሶሻሊስታዊ የሥራ ውድድርን ይመለከቷል።)

## ሲስሞንዲ፣ ሲሞንድ ደ
*(Sismondi, Sismonde de)*

ከ1773 — 1842 የኖረ ፣ ካፒታሊዝም ዘለዓለማዊና ቀውስ አልባ የሆነ ሥርዓት ነው የሚለውን የቅድመ ማርክስ ፖለቲካዊ

ኢኮኖሚ ምሁራን አባባል ስሀተተኛነት ለማ
ሳየት የሞከረና በፈረንሳይ የንዑስ ከበርቴ
ሶሻሊዝም መሥራች የሆነ ግለሰብ ነው ።

የሲስሞንዲ ኢኮኖሚያዊ ንድፈ ሐሳቦች
እንደአዳም ስሚዝና እንደ ዴቪድ ሪካርዶ
አስተሳሰቦች የማርክሳዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ
ምንጭ ናቸው ባይባልም በካፒታሊስት ሥር
ዓት ላይ የሰነዘረው ነቀፋ ግን ለማርክሳዊ
ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መመሥረት የበኩሉን
አስተዋጽኦ ያደረገ ነው ።

በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሳይንስ ዕድገት
ውስጥ ለሲስሞንዲ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው
ከላይ እንደተጠቀሰው ካፒታሊዝም ቀውስ
አልባ ሥርዓት ያለመሆኑን ለመጀመሪያ
ጊዜ ለማሳየት ጥረት ማድረጉ ነው ። እንደ
ሲስሞንዲ አባባል የካፒታሊስቶች ዓላማ
ትርፍ በመሆኑ እስከተቻላቸው ድረስ ወዝ
አደሮችን ይበዘብዛሉ ። በተጨማሪም "በተ
ፈጥሮ እርባታ ሕግ "ምክንያት (የሥራ ኃ
ይል) አቅርቦት ከፍላጐቱ በላይ በመሆኑ ቡር
ዧዚው በወዝአደሩ ገቢ ላይ የበለጠ እንዲ
ጫን አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል ። የወዝአ
ደሩ ገቢም ማነስና በቀን እስከ 14 ሰዓት
ድረስ እየሠራ ከሚያስገኘው ተጨማሪ ምርት
ጋር እኩል አለማደግ በላጥ ምርትን ያስከ
ትላል የሚል ነው ። ሲስሞንዲ ከዚህ አስተ
ሳሰቡ በመነሣት በራሳቸው ጉልበትና የም
ርት ማከናወኛ መሣሪያ የሚያመርቱ አነስ
ተኛ የሸቀጥ አምራቾች እንዲበረከቱ ማድ
ረግን እንደመፍትሔ ያቀርባል ።

የሲስሞንዲ አስተሳሰብ የካፒታሊስት
ክምችት የሚያስከትለውን የሀብት በጥቂቶች
እጅ መከማቸትና የሌላው የኅብረተሰብ ክፍል
ገቢ እያሽቆለቆለ ሄዶ "የበላጥ ምርት" ቀውስ
መከሰትን ለመቋቋም እንደ መፍትሔ ያየው
በታሪክ ሂደት ወደኋላ በመመለስ አነስተኛ
የሸቀጥ አምራቾችን መፍጠርን ነው ።
በመሆኑም የሲስሞንዲ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ
ያዊ አስተሳሰብ በመሠረቱ ከታሪክ አንፃር
ሲታይ አድኃሪ ነው ።

ይህም ማለት ከታሪክና ከፍልስፍና
አንፃር ለንድፈ ሐሳባቸው ያረጁና ያፈጁ
ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓቶችን እንደ
ሞዴል ለሚወስዱ የተሰጠ ትርጉም መሆኑን
ሌኒን ገልጿል ።

## ሲኒየር ፡ ናሳው ዊሊያም
*(Senior, Nassau William)*

ከ1790—1864 የኖረ ፤ በ1811 በእንግ
ሊዝ ሀገር በኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ትምህር
ቱን የፈጸመና ኋላም በ1830 የማስተማር
ተግባሩን አቋርጦ ከፍተኛ የመንግሥት
ባለሥልጣን በመሆን ብዙ የመንግሥት የኢ
ኮኖሚና የፖለቲካ ጉዳዮችን ያብራራ የኢኮ
ኖሚ ሊቅ ነው ።

ሲኒየር ከጻፋቸው የፖለቲካ ኢኮኖሚ
መጻሕፍት ውስጥ "አን አውት ላይን ኦቭ
ዘ ሳይንስ ኦቭ ፖለቲካል ኢኮኖሚ" ፤ "ሌተ
ርስ ኦን ዘ ፋክተሪ አክትስ" የተሰኙት በተ
ለይ የሚጠቀሱ ናቸው ።

ሲኒየር ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን የተፈጥሮ ፤
የምርትና የክፍፍል ሳይንስ አድርጐ ይገል
ጸዋል ። ስለዚህም ጥናቱን የሚጀምረው ሀብ
ትን በመተንተን ሲሆን በርሱ አመለካከት
ሀብት የተወሰኑ ፍላጐቶችን አርኪና ጠቃሚ፣
መጠኑ የተወሰነና ወደሌላ ሰው እጅ ሊተላ
ለፍ የሚችል መሆን አለበት ብሎ ያምናል ።
ሲኒየር ካፒታልንና ሥራን ራሳቸውን የቻሉ
የሀብት ምንጮች የተለያዩና የማይገናኙ የገቢ
ዓይነቶች አድርጐ ይቆጥራቸዋል ። በርሱ
አመለካከት ሠራተኛውም ፤ ካፒታሊስቱም
አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ። ሠራተኛው ጊዜው
ንና ጉልበቱን መሥዋዕት በማድረግ ጠቃሚ
ሀብቶችን ሲያመርት ካፒታሊስቱ ለምርትና
ለልውውጥ ተግባር መሣሪያዎችን ለማቅረብ
ሲል የራሱን የግል ፍጆታ በብዛት መሥዋ
ዕት ያደርጋል ብሎ ያምናል ። ሲኒየር ትር
ፍን የሥራ አስኪያጅ ገቢና የብድር ወለድ
በማለት ከሁለት ይከፍለዋል ። ወለድ የግል
ፍጆታን መሥዋዕት በማድረግ ለተከፈለ
ወጪ የሚከፈል ሲሆን የሥራ አስኪያጅ
ገቢ ደግሞ ለአመራር የሚከፈል ደሞዝ ነው
ብሎ ያምናል ። በዚህም መንገድ ሲኒየር
የተረፈ እሴት ልዩ ልዩ ክፍል የሆኑትን
የሥራ አስኪያጅ ገቢንና የወለድን ውስጣዊ
ይዘትና አንድነት ለመሸፋፈንና አሳስቶ ለማ
ቅረብ ሞክሯል ። ሲኒየር ሞኖፖልን የሚመ
ለከተው ማንም ሊያስቀረው እንደማይችል
የተፈጥሮ ሂደት አድርጐ ነው ። ጠፍ መሬ
ቶችን በማረስ ምክንያት የመሬት ኪራይ ስለ
ሚጨምር ምንዳ ያድጋል ፤ ትርፍ ግን እየቀ
ነሰ ይሄዳል የሚለውን የሪካርዶን አስተሳሰብ
ሲኒየር ይቀበለዋል ። ይህ ደግሞ ለኢንዱስትሪ

ዕድገት አደገኛ በመሆኑ ሲኒየር በኢኮኖሚ ለዘብተኝነት መንፈስ በኢንዱስትሪ የለሙ ሀገሮች ከእርሻ አምራች ሀገሮች ስንዴ ከቀረጥ ነፃ ማስገባት አለባቸው ይላል ። ማርክስ በሲኒየር የተሳሳቱ አስተሳሰቦች ላይ በካፒታል ቅጽ አንድ ውስጥ ኂስ አቅርቧል ።

## ሲንዲካሊዝም
*(Syndicalism)*

ሠራተኛውን ከካፒታል ጭቆና ለማላቀቅና ኅብረተሰቡን በአዲስ መልክ ለማደራጀት ያለው ብቸኛ መሣሪያ የሠራተኛው ማኅበር ነው የሚል በ19ኛው ምዕት ዓመት በሠራተኛው ንቅናቄ ውስጥ ብቅ ያለ አድኃሪ የንዑስ ከበርቴ የፖለቲካ ፈለግ ነው። ሲንዲኬት የሠራተኛ ማኅበር ማለት ሲሆን ሲንዲካሊስቶች ሠራተኛው በሠራተኛ ማኅበራት አማካይነት ጠቅላላ የሥራ ማቆም አድማ በማድረግ ያለ ሕዝባዊ አብዮት የማምረቻ መሣሪያዎችንና ምርትን በቁጥጥር ሥር ማድረግ ይቻላል ብለው ስለሚያምኑ በፖለቲካው ትግል መጠመድ አስፈላጊ እንዳልሆነ ይናገራሉ ። ስለዚህም የሠራተኛውን የፖለቲካ ትግል ባለመቀበላቸው የወዝአደሩን ፓርቲ ግንባር ቀደም ሚናና የወዝአደሩን የበላይ ገዥነት አስፈላጊነት አያምኑም ።

(አናርኮሲንዲካሊዝምን ይመለከቷል ።)

## ሲንዲኬት
*(Syndicate)*

ሲንዲኬት ከካርቴል ይልቅ ከፍ ባለ ደረጃ አንድ ዓይነት ሸቀጥ የሚያመርቱ የካፒታሊስት ድርጅቶች ኅብረት የሚፈጥሩበት የሞኖፖል ቅርፅ ነው ። የሲንዲኬት አባል ድርጅቶች በመካከላቸው በተደረሰው ስምምነት መሠረት የተመደበላቸውን የምርት መጠን በየፊናቸው ከሌሎች የሲንዲኬት አባል ድርጅቶች ነፃ በመሆን ያመርታሉ ። ሆኖም ያመረቱትን ሸቀጥ በየግላቸው ለመሸጥ አይችሉም ።

የሲንዲኬት አባል ድርጅቶች ስምምነት በተደረሰበት ኮታ መሠረት ያመረቱትን ምርት በጋራ ላቋቋሙት የንግድ ተቋም ያስረክባሉ። የንግድ ተቋሙም የተረከበውን ምርት ቀደም ሲል ስምምነት በተደረሰበት የሞኖፖል ዋጋ ሸጦ ከየአባል ድርጅቱ በተረከበው የምርት መጠን መሠረት ገንዘቡን ያከፋፍላል ። በተጨማሪም የንግድ ተቋሙ ለአባል ድርጅቶች አስፈላጊ የሆኑ ጥሬ ዕቃዎችን የሞኖፖል ኃይሉን በመጠቀም በአነስተኛ ዋጋ ገዝቶ እንደ ፍላጎታቸው ያከፋፍላቸዋል ።

(ሞኖፖልን ፣ ካርቴልን ይመለከቷል።)

## ሳርትር ፣ ዣን ፖል
*(Sartre, Jean Paul)*

ከ1905 እስከ 1981 የኖረ ፣ ኢአማኒያዊ ህልውናነትን የመሠረተና ያስፋፋ የፈረንሳይ ሐሳባዊ ፈላስፋ ነው ። "ሌትር ኤለኒያ" ብሎ በደረሰው መጽሐፉ ውስጥ የፍልስፍናውን መሠረታዊ አስተሳሰብና አቋም ጠለቅና ሰፋ ባለ ሁኔታ ገልጿል ።

ሆኖም በ2ኛው የዓለም ጦርነት ማግስት ከማርክሳዊ ፍልስፍና ጋር በመተዋወቁ የፍልስፍናውን ንድፈ ሐሳባዊ ጥልቀትና አብዮታዊ ተግባር ስለተረዳ የማርክሲዝም ፍልስፍና ተከታይ መሆኑን በይፋ አስታውቋል ። ነገር ግን በፊት የነበረውን ፍልስፍና ሙሉ በሙሉ መተው ስላልፈለገ "ክሪቲክ ደ ላ ሬዞ ዲያሌክቲክ" በሚለው መጽሐፉ ውስጥ ማርክሲዝምንና ህልውናነትን ለማስታረቅ ሞክሯል ።

ሳርትር በብዙ የፖለቲካ እንቅስቃሴና ትግል ውስጥ ተካፍሏል ። ሆኖም ያደረጋቸው ትግሎች በራሱ ስም ወይም በተወሰኑ በርሱ ተከታይ ቡድኖች አማካይነት ብቻ ነበር ። በፓርቲ በተቀናጀ ትግል ውስጥ መግባት ባለመፈለጉ የትግሉ ውጤት ውሱን ሆኖ ቀርቷል ።

(ህልውናነትን ይመለከቷል ።)

## ሳንሱር
*(Censorship)*

አንድ ሐሳብ ወይም የሰዎች የፈጠራ ውጤት ለሕዝብ ከመሰራጨቱ በፊት ተገቢነቱንና ጠቃሚነቱን ለማረጋገጥ በሕግ በታወቀ አካል የሚደረግ ቁጥጥር ነው ። በሳንሱር አማካይነት የሚካሄደው ቁጥጥር ዓይነ

ተኛ ዓላማ ኅብረተሰቡን ይጐዳሉ የሚባሉ አስተሳሰቦችን መከላከል ነው ።

ሳንሱር አንድ መንግሥት የቆመለትን ዓላማ ከሚጠብቅባቸው ዘዴዎች አንዱ ነው ። አንድ መንግሥት የሀገርን አንድነት ፣ ነፃነትና ክብር ማስከበር ፣ የሕዝቡን አጠቃላይ ክብረ ኅሊና ወዘተ...መጠበቅ ፣ እነዚህንና ሌሎችንም ለኅብረተሰቡ ጠንቅ ይሆናሉ የሚላቸውን ነገሮች በማንኛውም መንገድ እንዳይሰራጩ ይከላከላል ።

ከዚህም በተጨማሪ አንድ ኅብረተሰብ በዘልማድ የሚጠብቃቸው የሚፈቀዱና የማይፈቀዱ ሁኔታዎች አሉ ። እነዚህም እያንዳንዱ የኅብረተሰብ አባል ከሕፃንነቱ ጀምሮ እንዲቀበላቸው የሚደረጉ ምግባራት ናቸው።

## ሳይንሳዊ ርዕዮተዓለም
*(Scientific Ideology)*

በማርክስና በኤንግልስ የተቀመረውና በሌኒን የዳበረው የወዝአደሩ ርዕዮተዓለም ሳይንሳዊ ርዕዮተዓለም ይባላል ። የሳይንሳዊነቱ መሠረት የወዝአደሩን ጥቅምና የታሪክን እርምጃ ከነባራዊ ማኅበራዊ ግንኙነቶችና ሕግጋት አንፃር ማሳየቱ ነው ።

(ርዕዮተዓለምን ፣ ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ፣ መደባዊ ንጽረትን ይመለከቷል ።)

## ሳይንሳዊ ኮሚኒዝም
*(Scientific Communism)*

ካፒታሊዝምን ለመጣል የሚጠቀሙ ዘዴዎችንና መንገዶችን ፣ አዲሱን የኮሚኒስት ሥርዓት ለመገንባትና ሰውን በሁለንታዊ ዕድገት ለማነጽ መፈጠር ያለባቸውን ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎችን የሚያጠና ሳይንስ ነው ። ሳይንሱ ውስብስብ የሆነውን የኮሚኒስት ሥርዓት ሂደት የሚመረምር በመሆኑ ሰው የኅብረተሰቡን ሂደት ንቁና ግባዊ በሆነ መንገድ እንዲቆጣጠር የሚያስተምር ነው ። ሳይንሳዊ ኮሚኒዝም የማርክሲዝም ሌኒኒዝም አንዱ ክፍል ሲሆን ክፍልስፍናና ከፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የሚለየው የኮሚኒስት ሥርዓት ግንባታን አጠቃላይ ሕግጋት የሚያጠና መሆኑ ነው ።

የኮሚኒስት ሥርዓት ግንባታን የሚመረምር በመሆኑ ሳይንሳዊ ኮሚኒዝም በመጀመሪያ የሚያስተምረው ባለው ነባራዊ ቅራኔ ሳቢያ የካፒታሊዝም ውድቀት አይቀሬ መሆኑንና በሶሻሊስት አብዮት የሚተካው የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ደግሞ እውን ሊሆን የሚችለው በወዝአደሩ የበላይ ገዥ መንግሥት ብቻ መሆኑን ነው ። የኮሚኒስትን ኅብረተሰብ እውን ለማድረግ ልንከተላቸው የሚገቡንን ሕጎችና ዘዴዎች የሚያጠና በመሆኑ የኮሚኒስት ኅብረተሰብ ዋና ጥያቄ የሆነው የሰውን ሁለንታዊ ዕድገት ጥያቄ ተግባራዊ የሚያደርጉትን ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊና መንፈሳዊ ሁኔታዎችን ያስተምራል ። የሰው ቁሳዊና የፈጠራ ችሎታዎች ፣ ፍላጎቶችና አዝማሚያዎች ውስብስብ በሆነው በኮሚኒስት ማኅበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ እንዴት እንደሚገለጹና እንደሚዳብሩ ያጠናል ።

የኅብረተሰብ ዕድገት የሚከናወነው በነባራዊ ሕጎች አማካይነት በመሆኑ ሰዎች የነዚህን ሕጎች ግንዛቤ ማግኘት ግባዊና ድርጅታዊ እንቅስቃሴያቸውን እንዲያሳድጉ ያደርጋቸዋል ። ሳይንሳዊ ኮሚኒዝምም ለኮሚኒዝም ግንባታ አመች የሚያደርገውን የነባራዊ ሕጎችና የኅሊናዊ ሁኔታዎችን መስተጋብር ያስተምረናል ።

በአጠቃላይ ሳይንሳዊ ኮሚኒዝም በኮሚኒስት ግንባታ ሂደት ውስጥ ንቁና ግባዊ የሆኑ የአመራር ፣ የቁጥጥርና የአስተዳደር ስልቶችን የሚያጠና ሳይንስ ነው ።

(ማርክሲዝምን ፣ ሌኒኒዝምን ይመለከቷል ።)

## ሳይንሳዊ ዲያሌክቲክስ
*(Scientific Diàlectics)*

ከሄግል ተወስዶና ከሐሳባዊነት አቋሙ ተላቆ ፣ ተስተካክሎና ትክክለኛው ቁስአካላዊ መሠረት ተሰጥቶት በማርክስ ፣ በኤንግልስና በሌኒን የተቀረፀው ዲያሌክቲክስ ሳይንሳዊ ዲያሌክቲክስ ይባላል ።

ሳይንሳዊ የተባለበትም በሁለት ምክንያቶች ነው ። አንደኛው ከላይ እንደተገለጸው በቁስአካላዊ ይዘቱ ማለትም የሐሳብ የበላይነትን በመሻር ዋነኛው የፍልስፍና አምብርት ሐሳብ እራሱ የሚያንፀባርቀው የቁስአካልን

ወይም የነባራዊ እውነታን እንቅስቃሴና ዕድገት ነው በሚል መርህ ላይ በመመሥረቱ ፣ ይህ ዲያሌክቲክስ የነባራዊ እውነታ ትክክለኛ ግንዛቤ በመሆኑና በየጊዜው እያደገ ፣ እየተጠናከረና እየበለጸገ የሚሄድ በመሆኑ ሳይንሳዊ ነው ። ሁለተኛው እውነታን በትክክል በማንፀባረቅ የሚገኝ ዕውቀት ደግሞ በተግባር ላይ በመዋል ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ ለሰው ልጅ በተለይም ለሠራተኛው መደብ አብዮታዊ እንቅስቃሴና የትግል መመሪያ ንድፈ ሐሳብ ሆኖ ያገለግላል ። ተፈጥሮንና ኅብረተሰብን ለመቀየር ፣ የሠራተኛውን መደብ ታሪካዊ ተልዕኮ እንዲያግዝ ፣ በዚህም ጊዜ ሚናውን እንዲጫወት ለአዲሱ ሥርዓት መከሰትና መጠናከር የሚያስፈልገውን ትግልና አመለካከት ከተጨባጩ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ትክክለኛውን መመሪያ የሚሰጥም በመሆኑ ሳይንሳዊ ዕውቀት ነው ።

(ሐሳባዊ ዲያሌክቲክስን ፣ የዲያሌክቲክስ ሕግን፣ ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነትን ፣ የጀርመን ብሉይ ፍልስፍናን ይመለከቷል ።)

## ሳይንስነት
*(Scientism)*

የሳይንስ በተለይም የተፈጥሮ ሳይንስ ዕውቀት ከፍተኛ የሰው ልጅ የባህል ፋይዳ እንደሆነና ሰውም ስለአካባቢው ለሚኖረው ግንዛቤ በቂ መሠረት ሆኖ የሚያገለግለው ነው የሚል አመለካከት ነው ። ሰው በባህል ዘርፍ ግስጋሴ የሚያደርገው ፣ የህልውና መሠረታዊ የሆኑ ጥያቄዎችን ሊፈታና ብቃት ያላቸውን የተግባር ዕቅዶች ሊያወጣ የሚችለው በሳይንሳዊ ዕውቀት ሲመራ ብቻ ነው ።

ሳይንስነት የተፈጥሮ ሳይንሶችን ፣ የአስተሳሰብ ስልቶችንና አጠቃላይ የአጠናን ዘዴዎችን ፍጹማዊ ባህል አድርጎ የሚወስድ ፣ ከዚህም የተነሣ የስብእዊና የፍልስፍና ጠቀስ ጥያቄዎች ለግንዛቤ ምንም ጠቀሜታ የለውም የሚል ነው ። ይህ አመለካከት በዳበረ መልኩ የተከሰተው በ19ኛው ምዕት ዓመት በቡርዧው ባህል ውስጥ ሲሆን ተቀናቃኞችም ተነሥተውበታል ። ሳይንስ የሰውን ልጅ መሠረታዊ ችግሮች ለመፍታት የማይችል ፣ እንዲያውም ለሰው ልጅ ባዕድና ጠላቱ ከመሆኑም በላይ ለባህል ምንም ዓይነት ጠቀሜታ የማይሰጥ ስለሆነ ሳይንስን ወሰኝ አድርጎ መቁጠር የሰውን ችሎታ በጠባቡ መግታት ነው የሚሉ ፀረ ሳይንስ አመለካከት ያላቸው ተቃዋሚዎች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል ።

እነዚህ አመለካከቶች ሳይንስ በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ያለውን ሚና ዝቅ ስለሚያደርጉ ከሌሎች የማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና መልኮች ጋር ያለውን ግንኙነትና በሰዎች አመለካከት ውስጥ ያለውን ስፍራ ስለማያሳዩ የተዛቡና የተጋነኑ አመለካከቶች በመሆናቸው ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍና ያወግዛቸዋል ። ከዚህም በተጨማሪ ማኅበራዊ ሳይንሶች በማኅበራዊ ዕድገት ውስጥ ያላቸውን ሚና ስለማይቀበሉ ይታገላቸዋል ።

## ሴቶች ቀን (የ—)
*(International Working Women's Day)*

የዓለም ሠርቶ አደር ሴቶች ለሰላም ፣ ለዲሞክራሲና ለሶሻሊዝም በሚያደርጉት ትግል አንድነታቸውን ለማጠናከር በየዓመቱ መጋቢት 28 ወይም 29 (ማርች 8) የሚያከብሩት ቀን ነው ። ይህ ቀን እንዲከበር ውሳኔ የተላለፈው የታወቀችው ጀርመናዊት የዓለም አቀፍ ኮሚኒስት ንቅናቄ መሪ ክላራ ትዜትኪን በ1910 በኮፐንሃገን ለተደረገው ለሁለተኛው ዓለም አቀፍ ሶሻሊስት የሴቶች ጉባኤ ባሳሰበችው መሠረት ነው ። ዓላማውም የፆታ ጭቆና ከመደብ ጭቆና የማይነጠል በመሆኑ በዓለም ያሉ ሠርቶ አደር ሴቶች ከሚደርስባቸው ድርብ ጭቆና ለመላቀቅ ወዝአደሩ ከቡርዧዚው ተፅዕኖ ፣ ጭቆናና ብዝበዛ ነፃ ለመውጣት በሚያደርገው ትግል ተካፋይ እንዲሆኑ ነው። ይህ ቀን የዓለም ሠርቶ አደር ሴቶች ወደትግሉ መስክ ያልገቡትን ጭቁን ሴቶች የሚቀሰቅሱበት ፣ ከኢምፔሪያሊዝም ጋር የሚያደርጉትን ትግል የሚያድሱበትና አንድነታቸውን የሚገልጹበት ነው ። ማርች ስምንት ለመጀመሪያ ጊዜ የተከበረው በ1911 በጀርመን ፣ በኦስትሪያ ፣

በዴንማርክና በስዊዘርላንድ ሲሆን በሩሲያም ለመጀመሪያ ጊዜ በ1913 ተከብሯል ። በሀገራችንም ለመጀመሪያ ጊዜ የተከበረው በኢ.አ. 1968 ነበር ።

(የሴቶች ጥያቄን ይመለከቷል ።)

## ሴቶች ዓለም አቀፍ ዲሞክራቲክ ፌዴሬሽን (የ—)

*(Women's International Democratic Federation)*

ሴቶችን ያለምንም የዘር ፣ የብሔረሰብ ፣ የሃይማኖትና የፖለቲካ እምነት ልዩነት የሚያሰባስብ ዓለም አቀፍ ድርጅት ነው ። ድርጅቱ ሴቶች አብረው እየታገሉ የዜግነት ፣ የእናትነትና የሠራተኛነት መብታቸውን እንዲያስከብሩና ለሕፃናት ደኅንነት መጠበቅ ፣ ለሰላም ፣ ለዲሞክራሲና ለብሔራዊ ነፃነት መረጋገጥ የሚታገል ነው ።

የሴቶች ዓለምአቀፍ ዲሞክራቲክ ፌዴሬሽን በታኅሣሥ 1945 በፓሪስ ከተማ በተካሄደው ዓለም አቀፍ የሴቶች ጉባኤ የተመሠረተ ሲሆን ከመቶ ሀገሮች በላይ የተውጣጡ ከ120 በላይ የሆኑ የሴቶች ድርጅቶችን በአባልነት ያቅፋል ። የአብዮታዊት ኢትዮጵያ የሴቶች ማኅበርም (አኢሴማ) የዚሁ ድርጅት አባል ነው ።

ድርጅቱ ከሌሎች ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በግሉ የሴቶችን ሁኔታ ፣ የሕፃናትን ደኅንነት ፣ የኢምፔሪያሊዝምን ወረራ በመቃወምና ለዓለም ሰላም የሚደረገውን እንቅስቃሴ በመደገፍ በየጊዜው ስብሰባዎች እያካሄደ አቋም እንዲወሰድባቸው ያደርጋል ። በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚካሄዱትን ፀረ አፓርታይድ ፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴዎች ይረዳል ፤ የዓለም ሴቶችም ድጋፍ እንዲሰጡ የተለያዩ ዘመቻዎች እንዲካሄዱ ያስተባብራል ።

የድርጅቱ የበላይ አካል በየአራት ዓመቱ የሚካሄደው ጉባኤ ነው ። ጉባኤው የድርጅቱን ፕሬዚዳንትና በየዓመቱ እየተሰበሰበ ድርጅቱን የሚመራ ምክር ቤት ይመርጣል ። በዓመት ሁለት ጊዜ እየተሰበሰበ አመራር የሚሰጠው ደግሞ ቢሮው ነው ። የድርጅቱ የቀን ተቀን ሥራ በዋና ፀሐፊው እየተመራ በሴክሬታሪያቱ ይከናወናል ። የሴቶች ዓለም አቀፍ ዲሞክራቲክ ፌደሬሽን ዋና ጽሕፈት ቤት በጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ በበርሊን ከተማ ይገኛል ።

## ሴቶች ጥያቄ (የ—)

*(Women's Question)*

ሴቶች በተፃራሪ መደባዊ ሥርዓት ውስጥ ከመደብ ተፅዕኖ ሌላ በፆታቸው ምክንያት ከሚደርስባቸው ውስብስብ ማኅበራዊ ችግሮች ለመላቀቅና መብታቸውንና እኩልነታቸውን ለማስከበር የሚያቀርቡት ጥያቄ ነው ። በወንዶችና በሴቶች መካከል የሚታዩት አንዳንድ ተፈጥሮአዊ ልዩነቶች የሴቶችን የበታችነት የሚያመለክቱ ባይሆኑም በመደብ ኅብረተሰብ ሴቶች በሃይማኖትና በባህል ተፅዕኖ ምክንያት በቤተሰብና በኅብረተሰብ ውስጥ ዝቅተኛ ቦታ ይሰጣቸዋል ። ሴቶች በካፒታሊስት ሥርዓት አነስተኛ ክፍያ እንዲያገኙ መደረጋቸው ፣ በቤተሰቡና በኅብረተሰቡ ውስጥ ዝቅተኛ ቦታ በመሰጠታቸው የተጣለባቸውን ማኅበራዊና ባህላዊ ተፅዕኖ በመቃወም የሚያነሷቸው ጥያቄዎች እንዲካረሩ አድርጓቸዋል ። በዚህም የተነሣ ጥያቄዎቹ የአጠቃላዩ ኅብረተሰብ ጥያቄና በተለይም የሠራተኛው መደብ ጥያቄ አካል ሆነዋል ።

ሌኒን ስለሴቶች ጥያቄ በሰጠው ትንተና ላይ የኅብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆኑት ሴቶች በካፒታሊዝም ድርብ ጭቆና የወደቀባቸውና በጣም ዲሞክራሲያዊ በሆነው ቡርዧ ሪፑብሊክ እንኳ ሴቶች በመጀመሪያ ደረጃ በሕግ ፊት ከወንዶች ጋር ፍጹም እኩልነት የተነፈጋቸው ከመሆኑም በላይ በቤት ውስጥም በመሆን በጣም ኋላቀር ፣ ከባድና አሰልች በሆነ የማድቤት ሥራ ፣ በልጅ አሳዳጊነትና በአጠቃላይ በቤት አገልጋይነት እንዲወሰኑ መደረጋቸውን አብራርቷል ።

በማንኛውም የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ኑሮ ዘርፍ የሴቶች እኩልነት የሚረጋገጠው ሙሉ መብታቸውና ጥቅማቸው ተጠብቆ በትምህርት ፣ በሥራ ፣ በደሞዝ ፣ በጡረታ ... ከወንዶች ጋር ሊኖራቸው የሚገባው እኩልነት በተግባር ሲገለጽ ነው ።

ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ ሴቶች ተደራጅተው መታገል ይኖርባቸዋል ። የሴቶች ጥያቄ የመደብ ትግል አካል እንደ መሆኑ ሌሎች ለመደብ ጭቆና መጥፋት የሚታገሉ መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች ከጐናቸው ቆመው ይታገላሉ ። የሴቶች ጥያቄ የተሟላ መልስ ሊያገኝ የሚችለው ማንኛ ውም ጭቆናና ብዝበዛ በሚወገድበት በሶሻ ሊስት ሥርዓት ብቻ ነው ።

## ሴይ ፡ ዣን ባቲስት
*(Say, Jean Baptiste)*

ከ1767—1832 የኖረ ፣ የፈረንሳይ የኢ ኮኖሚ ተመራማሪና የግልብ ፖለቲካዊ ኢኮ ኖሚ ዋነኛ አራማጅ የነበረ ነው ።

ሴይ መንግሥት በኢኮኖሚ ውስጥ የሚያ ደርገውን ተሳትፎ የሚቃወምና ለነፃ ንግድ የቆመ ነበር ። ከ1819 ጀምሮ ሴይ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መምህር ነበር ። ስለፖለቲካዊ ኢኮ ኖሚ ያለውን አመለካከት ከገለጸባቸው ጽሁ ፎቹ መካከል ዋንኛውን ቦታ ይዞ የሚገኘው "ኧ ትሪቲስ ኦን ፖሊቲካል ኢኮኖሚ" በሚል ርዕስ በ1803 የጻፈው መጽሐፍ ነው ።

ሴይ ምንም እንኳ በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አመለካከት የአዳም ስሚዝ ተከታይና ደቀ መዝሙር ነኝ ቢልም ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን ወደ ግልብ፡ነት የቀየረ ሰው ነው። ሴይ የካፒታሊስትን ምርት የሚመሩት ሕጐች ዘላለማዊነት ያላቸው ናቸው ብሎ ያምናል ። በሱ አመለካከት እሴት የሚወሰነው በሥራ ኃይል ሳይሆን በጠቀሜታ ፣ በምርት ወጭ ፣ በአቅርቦትና በፍላጐት መሠ ረት ነው ። ከአዳም ስሚዝ የኢኮኖሚ አስተ ምህሮም አንዳንድ ክፍሎችን በመውሰድ "ለምርት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች" የተሰኘውን ጽንሰ ሐሳብ ፈጠረ ። በዚህም መሠረት ሴይ እሴት በመፍጠር ረገድ ሥራ ፣ ካፒታልና ተፈጥሮ እኩል ሚና እንደሚጫወቱ አድርጐ አቀረበ ። በመሆኑም ሴይ የካፒታሊስት ምርት በብዝበዛ ላይ ያልተመሠረተ ለማስመሰል ሞክሯል ።

ሴይ ካፒታሊዝምን እንደዘለዓለማዊ ሥር ዓት አድርጐ ስለሚመለከት በዚህ ሥርዓት የሚኖረው ቀውስ አንዳንድ ሸቀጦችን በሚ መለከት ረገድ በከፊል የሚከሰት የበላጥ ምርት ቀውስ እንጂ አጠቃላይ የሆነ የበላጥ ምርት ቀውስ አይኖርም ብሎ ነበር ። ሴይ "አቅርቦት የራሱን ፍላጐት ይፈጥራል" የተሰኘውን የገበያ ሕግ ቀምሯል ። በዚህም ጽንሰ ሐሳብ መሠረት በአጠቃላይ የተመረ ተው ምርት በገበያ ውስጥ ወዲያውኑ በገዥና በሻያጭ (በአቅርቦትና በፍላጐት መካከል) እኩልነት ያገኛል ።

ሴይ የሸቀጥ ምርት ዕድገት በራሱ በል ውውጥ እሴትና በጠቀሜታ እሴት መካከል ቅራኔ እንደሚፈጥር ፣ ይህም ገንዘብ እንደ ተለየ ሁለንታዊ ሸቀጥ ሆኖ እንዲከሰት እንደሚያደርግና በሻያጭና በገዥ መካከል እኩልነት ወዲያውኑ ሊገኝ እንደማይችል ሊገ ነዘብ አልቻለም ።

(ግልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን ይመለከቷል ።)

## ስልተ ምርት
*(Mode of Production)*

ሰዎች ፍላጐታቸውን ለማርካት እንዴ ትና በምን እንደሚያመርቱ ፣ ያመረቱትን እንዴት እንደሚከፋፈሉ ፣ በምርትና በልው ውጥ ሂደት በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙ ነት የሚያጠቃልለው የምርት ኃይሎችና የም ርት ግንኙነቶች ቅንብር ስልተ ምርት ይባ ላል ። ስልተምርት በምርት ኃይሎችና በም ርት ግንኙነቶች ዲያሌክቲካዊ ቅንጅት የተዋ ቀረ ነው ። የምርት ኃይሎች የዕድገት ደረጃ ሰዎች በተፈጥሮ ላይ ያላቸውን የበላይነትና ቁጥጥር ሲያመለክት የምርት ግንኙነቶች ደግሞ ሰዎች በማምረት ሂደት ውስጥ እርስ በርሳቸው ያላቸውን የኢኮኖሚ ግንኙነት ያሳያል ።

በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል ያለው መስተጋብር በአንድነትና በቅራኔ ላይ የተመሠረተ ነው ። የምርት ኃይ ሎች ከደረሱበት የዕድገት ደረጃ ጋር የሚጣ ጣምና የዕድገት ደረጃቸውን የሚያግዝ የም ርት ግንኙነት ካለ የምርት ኃይሎችን ዕድገት ያፋጥናል ። ይህ ከሌለ ግን በምርት ግንኙነ

ቱና በምርት ኃይሎቹ መሀከል የሚካሄደው ትግል ከተካረረ ደረጃ ላይ በመድረስ የምርት ግንኙነቱ የሚለወጥበትን ሁኔታ ይፈጥራል ። በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መሀከል የሚፈጠረው የተካረረ ቅራኔ የሚፈታው በማኅበራዊ አብዮት ነው ። በዚህም ምክንያት ከምርት ኃይሎች ሁኔታ ጋር የሚጣጣም የምርት ግንኙነት ይከሰታል ። የአዲስ ምርት ግንኙነት መከሰት የአዲስ ስልተ ምርትን መከሰት ያስከትላል ።

እስከዛሬ ድረስ ባለው የሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ አምስት ስልተ ምርቶች ተከስተዋል። እነዚህም የጥንታዊ ጋርዮሽ ስልተ ምርት ፣ የባሪያ አሳዳሪ ስልተ ምርት፣ የፊውዳል ስልተ ምርት ፣ የካፒታሊስት ስልተ ምርትና የኮሚኒስት ስልተ ምርት ናቸው ። የባሪያ አሳዳሪው፣ የፊውዳሉና የካፒታሊስቱ ስልተ ምርቶች ብዝበዛ የሚካሄድባቸው ስልተ ምርቶች ሲሆኑ ብዝበዛ የሚያከትመው በኮሚኒስት ስልተ ምርት ውስጥ ነው ።

የስልተ ምርቶች ታሪካዊ መከታተልና አንዱ ስልተ ምርት የፊተኛውን ስልተ ምርት የሚተካው በምርት ግንኙነትና በምርት ኃይሎች መሀከል ባለው የተቃርኖና የመጣጣም ሕግ መሠረት ነው።የኮሚኒስት ስልተ ምርት በማኅበራዊ የባለቤትነት ይዞታ ላይ በተገነባ የምርት ግንኙነት የተዋቀረ በመሆኑ በምርት ግንኙነትና በምርት ኃይሎች መካከል የሚከሰቱ የማይፃረሩ ቅራኔዎች በዕቅድ በተቀነባበረ ዘዴ እየተፈቱ ስለሚሄዱ ዕድገታቸው ሳያቋርጥ ይቀጥላል ።

(የምርት ግንኙነትን ፣ የምርት ኃይሎችን ፣ የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች ዲያሌክቲክስን ፣ ሶሻሊዝምን ይመለከቷል ።)

## ስሚዝ ፣ አዳም
*(Smith, Adam)*

ከ1723—1790 የኖረ የስኮትላንድ ተወላጅና የ18ኛው ምዕት ዓመት የብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ግምባር ቀደም ምሁር ነው ።

አዳም ስሚዝ ገና በ14 ዓመቱ ግላስጎ ዩኒቨርሲቲ በመግባት የሥነ ምግባር ፍልስፍና በኋላም ወደ ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ተዛውሮ ለስድስት ዓመታት ሒሳብና ሥነ ፈለክ (አስትሮኖሚ) አጥንቷል ። ከ1751 ጀምሮ እስከ 1763 በግላስጎ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር የነበረ ሲሆን ፣ በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታትም በፈረንሳይ ውስጥ በመኖር ታዋቂ ከነበሩት ፊዚዮክራቶች እንደነኪኔና እንደነቱርጐ እንዲሁም እንደነሄልቬትዮስ ከመሳሰሉት ፈላስፎች ጋር በቅርብ ለመገናኘትና ከአስተሳሰባቸውም ጋር በቅርብ ለመተዋወቅ ዕድል አግኝቷል። እሴት የሚፈጠረው እንደፊዚዮክራቶች አባባል በእርሻ መስክ በተሰማራው ጉልበት ብቻ ያለመሆኑን ቢያሳይም በአጠቃላይ ፊዚዮክራቶችን "በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ለእውነት የተቃረቡ እነርሱ ናቸው" በማለት ገልጿል ። ከ1778 ጀምሮ ለአሥር ዓመታት በኤደንብራ የጉምሩክ ኮሚሽነር ሆኖ ሲሠራ ከ1787 እስከ ዕለተሞቱ ድረስ በግላስጎ ዩኒቨርሲቲ በዲሬክተርነት አገልግሏል ።

አዳም ስሚዝ በቅድሚያ ያሳተመው ጽሑፍ "ዘ ቲየሪ ኦቭ ሞራል ሴንቲሜንትስ" የተሰኘ ሲሆን በዚህ ሥራውም የሰው ልጅ በተፈጥሮው እኩል ስለሆነ የሥነ ምግባር መርሆችም በዚህ እኩልነት ግንዛቤ ላይ የተመሠረቱ መሆን እለባቸው ብሏል ። የዚህ ሥራው ጉልህነት የአዳም ስሚዝን የፍልስፍናና የኢኮኖሚ አስተሳሰብ አመሠራረትና ዕድገት የሚያሳይ ነው ።

ሁለተኛውና ዋንኛው የአዳም ስሚዝ ጽሁፍ "አን ኢንኳየሪ ኢንቱ ዘ ኔቸር ኤንድ ኮዝ ኦቭ ዌልዝ ኦቭ ዘ ኔሽን" የተሰኘው መጽሐፉ ነው ። በዚህም መጽሐፉ ውስጥ አዳም ስሚዝ የሜርካንቲሊስቶችን ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብና የካፒታሊዝምን ዕድገት ያጨናግፉ የነበሩትን የፊውዳሊዝም ቅሪት አስተሳሰቦችን በጽኑ ተዋግቷል ። በወቅቱ ተራማጅ የነበረውን የኢንዱስትሪ ቡርዧዚውን ጥቅም ሙሉ በሙሉ በማንፀባረቅ መንግሥት በኢኮኖሚ ውስጥ የሚያደርገውን ጣልቃገብነት በመፃረር ለ"ሌሴፌር" የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተሟግቷል ።

አዳም ስሚዝ የኢኮኖሚ አስተሳሰቡ መሠረት የሆኑትን መንደርደሪያ ሐሳቦች እንደሚከተለው ያስቀምጣቸዋል ። ከሰው ልጅ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በስተጀርባ ያለው

መሠረታዊ ዓላማ ጥቅም ነው ፤ ይህን የግል ጥቅሙን ፍላጎት ለማርካት ግን የሰው ልጅ ሥራውንና የሥራውን ውጤት ከሌሎች ጋር እንዲለዋወጥ ይገደዳል ፤ ሁሉም ለየራሱ ጥቅም የሚለዋወጥ ቢሆንም ይህ ድርጊት ምንም ዓይነት ተፅዕኖ ካልተደረገበት የሥራ ክፍፍልን የሚያዳብርና ኅብረተሰቡን ባጠቃላይ ለማበልጸግ የሚችል የራሱን "የተፈጥሮ ሥርዓት" የሚፈጥር ስውር እጅ ነው ።

የሰውን ከአንድ አካባቢ ወደሌላ መንቀሳቀስ የሚገቱ ሕጎች እንዲሻሩ የተሟገተው፣ መሬት መሸጥ መለወጥ አለበት የሚለውን አቋም አጥብቆ ያራመደው ፣ ነፃ የውጭ ንግድ ፖሊሲ እንዲኖር ማናቸውም በኢንዱስትሪ መስክ የወጡ የመንግሥት አዋጆች እንዲሻሩ የጠየቀውና በአጠቃላይም ለ"ሌሴ ፌር" የኢኮኖሚ ፖሊሲ አጥብቆ የተሟገተው ከእነዚሁ መንደርደሪያ ሐሳቦች በመነሣት ነው።

አዳም ስሚዝ የሰው ልጅ በኢኮኖሚ መስክ የሚኖረውን ተሳትፎ የሚመለከተው እንደተለያየ የረዥም ጊዜ የኅብረተሰብ ዕድገት ታሪክ ውጤት ሳይሆን እንደዘለ ዓለማዊና ተፈጥሮአዊ የሰውልጅ ባሕርይ ውጤት አድርጎ ነው። በመሆኑም የሰውን ልጅ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ባለበት ኅብረተሰብ ክልል ውስጥ ከማጥናት ይልቅ ብቻውን "የኢኮኖሚ ሰው" (በገበያ ሁኔታ የሚመራ ሰው) ከሚል ተነሥቶ ለማጥናት ያደረገው ሙከራ የኢኮኖሚ ሕጎችን ማኅበራዊ ባሕርይ እንዳይረዳና የተፈጥሮ ሕጎች ናቸው የሚል የተሳሳተ አቋም እንዲወስድ አድርጉታል ።

አዳም ስሚዝ የማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜን ጽንሰ ሐሳብ በማብራራት የእቤት ሥራ ንድፈ ሐሳብን ያዳበረ ቢሆንም በሥራና በሥራ ኃይል መካከል ያለውን ልዩነት ባለመረዳቱና የቡርዧዚውን የትርፍ ምንጭ በዚህ ንድፈ ሐሳብ ክልል ውስጥ መግለጽ ባለመቻሉ ይህ ንድፈ ሐሳብ በካፒታሊዝም ውስጥ አይሠራም ወደሚል የተሳሳተ መደምደሚያ ደርሷል ። በአዳም ስሚዝ አስተሳሰብ በካፒታሊዝም ውስጥ የሸቀጦች እሴት የወጪዎች ድምር ማለትም ትርፍ፣ የወዝአደሩ ምንዳና የመሬት ኪራይ ነው ።

በአዳም ስሚዝ አባባል በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሳይንስ ዕድገት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የሚያስጠው የካፒታል ክምችት የአንድ ሀገር የሀብት ምንጭ መሆኑን በማስመልከት ያደረገው ትንተና ነው ። ስሚዝ የአንድ ሀገር ሀብት በሁለት መንገዶች የሚያድግ መሆኑን አጥብቆ አስተምሯል ። አንደኛው በሥራ ክፍፍል መስፋፋት የሚገኘው የሥራ ምርታማነት ዕድገት ሲሆን ሌላው ደግሞ የእምራች ሕዝብ ቁጥር ማደግ ውጤት ነው ይላል ። አዳም ስሚዝ በጥናቱ ውስጥ ለሥራ ክፍፍል ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶታል ።

ሁለተኛው ለአንድ ሀገር ሀብት ዕድገት አስተዋፅኦ ያደርጋል ብሎ ያመነበት በምርት መስክ የሚሰለፈው ሕዝብ ቁጥር ኢእምራች ከሆነው ቁጥር ጋር ሲነፃፀር እያደገ መሄዱ ነው ። ከዚህም አስተሳሰብ በመነሣት አዳም ስሚዝ በጊዜው የቡርዧውንም ሆነ የወዝአደሩን መደቦች ጥቅም የሚያንፀባርቅ ነቀፋ ኢእምራች በሆነው የፊውዳሉ መደብ ላይ ሰንዝሯል ። ይህ አቋሙም ከታሪክ አንፃር ሲታይ ከፍተኛ ጉልህነት ያለውና ተራማጅ ነበር ።

አዳም ስሚዝ የካፒታሊስት ክምችት በአንድ ሀገር የሀብት ዕድገት ውስጥ ያለውን ቦታ በትክክል ቢያስቀምጥም የካፒታሊስት ክምችትን ውስጣዊ ባሕርይና ታሪካዊ ዝንባሌም በትክክል ሊረዳ ባለመቻሉ ካፒታሊዝም ዘለዓለማዊ ሥርዓት ነው ከሚል የተሳሳተ መደምደሚያ ላይ ደርሷል ።

ባጠቃላይ የአዳም ስሚዝ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ጥናት በሳይንስ ዕድገት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠውና የማርክሲዝም አንዱ ምንጭ የሆነው የብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መሠረት ነው ።

(ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን ፣ ሌሴፌርን ይመለከቷል ።)

## ስማዊ ምንዳ
*(Nominal Wages)*

ወዝአደሩ በገንዘብ መልክ የሚቀበለው ምንዳ ነው ። ወዝአደሩ መሠረታዊ ፍላጎቱን የሚያረኩ ሸቀጦችን የሚገዛውና ሌሎች ወጪዎችን የሚያወጣው ከዚሁ ምንዳ ነው ።

በካፒታሊስቱ ሥርዓት የዚህ ዓይነቱ ምንዳ መሠረታዊ ትራኔ ለወዝአደሩ ከሚያስፈልጉ ሸቀጦች ዋጋ ጋር በቀጥታ

ያልተዛመደ መሆኑና የወዝአደሩን እውን የኑሮ ደረጃ ለማሳየት አለመቻሉ ነው ። ለምሳሌ በ1970 ብር 100 የነበረው የአንድ ወዝአደር ምንዳ በ1975 ወደ ብር 110 ዐድጐ በዚሁ ጊዜ ውስጥ የወዝአደሩን መሠረታዊ ፍላጐት የሚያረኩ ሸቀጦች ዋጋ በ30% ከፍ ቢል የወዝአደሩ የይስሙላ ምንዳ ያደገው 10% ብቻ በመሆኑ ከሸቀጦች ዋጋ ጋር አልተዛመደም ማለት ነው ። በዚህ ሁኔታ የገንዘቡ የመግዛት ኃይል መቀነስ የወዝአደሩን የኑሮ ደረጃ ዝቅ ያደርገዋል ።

የምርት መገልገያዎች በጥቂቱ የኅብረተሰብ ክፍል በተያዙበት ፣ የምርት መሠረታዊ ዓላማ ትርፍ በሆነበትና ምርት በዕቅድ ሳይሆን ሥርዓት አልባ በሆነ መንገድ በሚመረትበት ፣ የሸቀጦች ዋጋ ውጣ ውረድና የገንዘብ ቀውስ በሰፈነበት በካፒታሊስት ስልተ ምርት ውስጥ ስማዊ ምንዳና እውን ምንዳ ምንጊዜም እኩል ሊሆኑ አይችሉም ።

በሶሻሊዝም ውስጥ ግን የብሔራዊ ገቢ ስርጭትና የሸቀጦች ዋጋ በማዕከላዊ ዕቅድ የሚመሩ በመሆናቸው "ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ፣ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው" በሚለው የሶሻሊስት ክፍፍል መርህ መሠረት እያንዳንዱ ሠራተኛ የሚያገኘው የገንዘብ ምንዳና የመግዛት ዓቅሙ የተጣጣሙ ናቸው ።

(እውን ምንዳን ይመለከቷል ።)

## ስማዊነት

*(Nominalism)*

ጽንሰ ሐሳቦች ነባራዊና ሁለንታዊ እውነታን የማይገልጹና የእያንዳንዱ ነገር መጠሪያ ስም ብቻ እንደሆኑ አድርጎ የሚመለከት በመካከለኛው ዘመን የተከሰተ ፍልስፍናዊ አዝማሚያ ነው ።

በስማዊነት አስተምህሮ መሠረት ህልውና ያላቸው ግላዊ ነገሮችና ግላዊ ጠባዮቻቸው ብቻ ናቸው ። እነዚህን አስመልክቶ በሐሳባችን ውስጥ የምንቀርፃቸው አጠቃላይ ጽንሰ ሐሳቦች የነዚህን ነገሮች ሁኔታ አያንፀባርቁም፤ በራሳቸውም የሚኖሩ አይደሉም ። ስማዊነት ባንድ በኩል የሚገልጸው የነገሮችን ቀዳማዊነትና የጽንሰ ሐሳቦችን ደኃራዊነት በመሆኑ ቁስአካላዊ አዝማሚያ አለው ። በሌላ በኩል ግን ስማውያን ጽንሰ ሐሳቦች የሚገልጹት ነባራዊ ባሕርያትን መሆኑንና ግላዊነት ከሁለንታዊነት ተነጥሎ እንደማይታይ አለመገንዘባቸው ዓይነተኛ ድክመታቸው ነው ። ይህም በመሆኑ ነው በርክሌይንና ሂዩምን የመሳሰሉት ኀሊናዊ ሐሳባውያን ነባራዊ እውነታን ለመካድ በስማዊነት የተጠቀሙት ።

(እውነትን ፣ ኀሊናዊ ሐሳባዊነትን ይመለከቷል ።)

## ስታሊን ፣ ጆሴፍ ቪሳሪዮኖቪች ጁጋሽቪሊ

*(Stalin, Joseph Vissarionovich Dzhugashvili)*

ከ1879—1953 የኖረው የጆርጅያ ተወላጅ የሆነው ስታሊን አብዮታዊ ተግባራቱን የጀመረው ገና ቴፍሊስ በተባለው ስፍራ በአንድ መንፈሳዊ ኮሌጅ ውስጥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በመከታተል ላይ ሳለ ነበር። በሩሲያው ሶሻል ዲሞክራቲክ ሌበር ፓርቲ በኅቡእ የጥናት ቡድን ውስጥ በአባልነት የተመዘገበውም በ1898 ገና ተማሪ ሳለ ነበር ። በዚህም ተሳትፎው ምክንያት ከትምህርት ቤቱ በመባረሩ ከዚያን ጊዜ አንሥቶ ሙሉ ጊዜውን ለትግልና ለተግባራዊ ተሳትፎ አውሏል ። በዚህም ወቅት የትራንስ ኮኬሽያንን የወዝአደር ትግል በመሪነት በማደራጀትና አርአያም በመሆን ትግሉን በቦልሼቪኮች መሥመር ለማሳደግ ችሏል ።

ከ1904 ጀምሮ ደግሞ የቦልሼቪኮች አባል በመሆን በተለያዩ ኅቡእ አብዮታዊ ትግሎች ውስጥ ከመሳተፉም በላይ በተለይም ከሜንሼቪኮች ጋር በተደረገው ክርክርና ትግል በቆራጥነት ታግሏል ። ስታሊን ከሌኒን ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኘው በ1905 ፊንላንድ ውስጥ በተደረገው የፓርቲው ጠቅላላ ስብሰባ ላይ ነበር ። በዚህና በተከታዩም ዓመት ስቶክሆልምና ለንደን ውስጥ በተደረጉት ጉባኤዎች ውሳኔ መሠረት ወዝአደሮች በተከማቹበት በባኩ ከተማ ወዝአደሩን በቦልሼቪኮች መሥመር በማደራጀት ረገድ ጠንካራ አመራር ሰጥቷል ። ሆኖም የአድኃሪው መንግሥት ፀጥታ አስከባሪዎች ስላሳደዱት በ1911 ወደ ፔትሮግራድ ተዛውሮ እንዲሠራ ተደርጓል ። በ1912 ቦልሼቪኮች ፕራግ ውስጥ ባደረጉት ስብሰባ ስታሊንን በሌለበት የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል እንዲሆን መርጠው ከፍተኛ

ኃላፊነት የሚጠይቀውን የቦልሼቪክ ፓርቲን ሥራ በፔትሮግራድ እንዲያካሂድ አድርገዋል ።

በ1919 አዲስ የተቋቋመው የፓርቲው ፖሊቲካ ቢሮና የሠራተኛውና የገበሬው ቁጥጥር "ኦርግቢሮ" አባል እንዲሆን ሲመረጥ የተሳትፎውና የኃላፊነቱም ደረጃ ከፍ ብሏል ። በ1922 ስታሊን የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ አንደኛ ዋና ፀሐፊ ሆኖ ይህንኑ ሥራ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ አከናውኗል ።

ሌኒን በ1924 ከሞተ በኋላ ስታሊን የመሪነቱን ቦታ ይዞ ከቀኝ ጎታቾችም ሆነ ከግራ ተስፈንጣሪዎች ያጋጠሙትን ዕንቅፋቶች እየተቋቋመና በተለይም የትሮትስኪንና የተከታዮቹን መሰሪ የውስጥ ቅስቀሳና ፈተና በቆራጥነት ድል በመምታት ፓርቲውን በትክክለኛ መሥመር አራምዷል ። ሀገሪቱን ከሁለተኛው የኢምፔሪያሊስቶች ወረራ መከላከል ብቻ ሳይሆን ፋሺዝምን ለመግታትና በምሥራቅ አውሮፓ ሶሻሊዝምን ለማስፋፋት በተደረገው ሕዝባዊ ትግል ውስጥ ቆራጥና ውጤታማ አመራር ሰጥቷል ። ሶቭዬት ኅብረት በኢንዱስትሪ የበለጸገችና በዘመናዊ ዕድገት የመጠቀች ሀገር እንድትሆን የማይናወጥ መሠረት የጣለላት ስታሊን ነው ። የወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት ግዴታውንም በማያወላውል መንገድ በመወጣትና ይልቁንም ከቅኝ አገዛዝና ከኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ነፃ ለመውጣት የሚታገሉ ሕዝቦችን በመደገፍ ረገድ ሶቭዬት ኅብረት ግንባር ቀደም ድርሻ እንድታበረክት ያደረገው ጆሴፍ ስታሊን ነው ። በዚህ ረገድ ከምሥራቅ አውሮፓ ክፍሎች በተጨማሪ እንደሕዝባዊት ቻይና ፣ ሕዝባዊት አልባኒያ ፣ ዲሞክራቲክ ኮሪያና ቪዬትናም የመሳሰሉትን ሀገሮች ማውሳት በቂ ይሆናል ።

ስታሊን ከወጣትነት ጊዜው ጀምሮ እስከሞተበት ጊዜ ድረስ ለሠራተኛው መደብ ዓላማዎች መራራ ትግል ሲያካሂድ ከፍተኛ መሥዋዕትነት የከፈለ፣ሶቭዬት ኅብረትንና የዓለም ኮሚኒስት ንቅናቄን በፈተና ወቅቶች ሁሉ በመምራት ለድል ያበቃ ፣ በንድፈ ሐሳብ አስተዋጽኦው በተለይ በለብሔር ጥያቄ ባደረገው ጥናትና ትንተና ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ያዳበረና በተግባራዊ ተሳትፎውም ግንባር ቀደም ኮሚኒስትነቱን ያረጋገጠ ነበር ።

## ስታኻኖቪዝም
*(Stakhanovism)*

በሶቭዬት ኅብረት አሌክሲ ስታኻኖቭ የተባለ የማዕድን ሠራተኛ ነሐሴ 30 ፣ 1935 በአንድ የሥራ ፈረቃ ከሚጠበቅበት በላይ ከፍተኛ የከሰል ምርት በማምረቱ በዚህ ሰው ስም የተሰየመ የምርት ውጤት ማሳደግ እንቅስቃሴ ነው ። በዚህን ጊዜ ስታኻኖቭ አዲስ የሥራ ቅንጅትና የተሻሻሉ መሣሪያዎችን ፈጥሮ 102 ቶን ከሰል በአንድ ፈረቃ እንዲመረት በማድረጉ ምርቱ ከተመደበው ድርሻ በአሥራ አራት እጅ በልጦ ተገኝቷል ። በዚህ መሠረት የምርት ድርሻ ክብረወሰን በመስበር ረገድ ባበረከተው አስተዋጽኦ በርሱ ስም መጠራት የጀመረው የስታኻኖቫይት እንቅስቃሴ በመላ ሀገሪቱ ተዳረሰ ።

የስታኻኖቫይትን እንቅስቃሴ ምሳሌ በማድረግ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እንዲገኙ ፣ ሥራ በአዲስ መልክ እንዲደራጅ ፣ ሂደተ ምርቱና ክፍፍሉም በሥርዓት እንዲመራ ፣ ምርታማነት ከፍ እንዲልና የሠራተኛውም ሕዝብ የኑሮ ደረጃ እንዲሻሻል አመች ሁኔታዎች ተፈጠሩ ። ከየብሔረሰቡ የተገኙ አያሌ ሳይንቲስቶችና መሐንዲሶች በዚህ ውስጥ በንቃት በመሳተፋቸውም ከጊዜ ወደ ጊዜ በርካታ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ውጤቶች ተገኝተዋል ። በዚህ ዓይነት የስታኻኖቫይት እንቅስቃሴ ለሶሻሊስት የሥራ ውድድር ይበልጥ መስፋፋትና መደርጀት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

(ሶሻሊስታዊ የሥራ ውድድርን ይመለከቷል።)

## ስትራቴጂና ታክቲክ
*(Strategy and Tactic)*

ስትራቴጂ በአንድ በተወሰነ የትግል ደረጃ አንድ አጠቃላይ ግብ ለመምታት የሚደረግ የዕቅድና የተግባር ቅንብር ሲሆን ታክቲክ ደግሞ ያንን አጠቃላይ ግብ ለመምታት በቅርብ ከሚደረጉ የዕቅድና የተግባር ቅንብሮች

አንዱ ነው ። ግሳዲን «የዓለም ኮሚኒስት ንቅናቄ ፤ የስትራቴጂና የታክቲክ ንድፈ ሐሳብ» በሚለው መጽሐፉ የስትራቴጂንና የታክቲክን ልዩነት ሲያብራራ ስትራቴጂ በአጠቃላይ በአንድ ጦርነት ላይ ለማሸነፍ የሚደረግ የሐሳብና የተግባራት ቅንብር ሲሆን ፤ ታክቲክ ደግሞ በጦርነቱ በአጠቃላይ ለማሸነፍ ከሚደረጉ ብዙ ውጊያዎች በተለይ እያንዳንዱን ለማሸነፍ የሚደረግ የቅርብ ትግል ቅንብር መሆኑን ገልጿል ።

ስትራቴጂና ታክቲክ የአንድ ትግል ሁለት ገጽታዎች ቢሆኑም የተለያየ ይዘት አላቸው ። ለምሳሌ የስትራቴጂ ይዘት በአጠቃላይ የወቅቱን የኃይሎች አሰላለፍ ለይቶ ማወቅ ፣ የጠላትን አቋም በሚመለከት የወገን ኃይል የሚያተኩርበትን የትግል አቅጣጫ መወሰን ፣ እንዲሁም አንድ የስትራቴጂ ወቅት ሲከናወን ሁኔታዎችን እንደገና በመገምገም አዲስ ስትራቴጂ መቀየስ ነው ።

ታክቲክ የወቅቱን ተግባራት በቅርብ ለማከናወን የሚያስችል ስልት በመሆኑ የቅርብ ሁኔታዎች ሲለዋወጡ ከስትራቴጂ ይበልጥ እንደአስፈላጊነቱ ይለዋወጣል ።

ሌሎች የኮሚኒስቶች ስትራቴጂና ታክቲክ ገጽታዎች ከልምድ የመማርና የማስተማር ፣ ከሕዝብ ጋር የመሥራትና አመራር የመስጠት ፣ በአንድ የትግል ሂደት ውስጥ ላለው ሁናቴ ትክክለኛውን የትግል ስልት የመቀየስ ፣ የጠላትን ስትራቴጂና ታክቲክ ጠንቅቆ የማወቅ ችሎታዎች ናቸው ።

## ስትራቴጂያዊ የጦር መሣሪያ ቅነሳ ድርድር

*(Strategic Arms Limitation Talks)*

የስትራቴጂያዊ ጦር መሣሪያዎች ቅነሳ ድርድር ፣ (ሶልት—Salt) የጠቅላላው የጦር መሣሪያ ቅነሳና የዴታንት ሂደት አንድ ክፍል ሲሆን ኃያላን መንግሥታት በተለይም አሜሪካና ሶቭዬት ኅብረት ያሏቸውንና የሚሠሩዋቸውን እጅግ ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ግምት የሚሰጣቸውን የጦር መሣሪያዎች መጠን ለመወሰን ወይም ለመቀነስ የሚያካሂዱዋቸውን ድርድሮችና የሚያደርጉዋቸውን ውሎች ይመለከታል ። ሶልት ወይም የስትራቴጂያዊ ጦር መሣሪያዎች ቅነሳ ድርድር ውይይት እንደሚደረግባቸው ዘርፎች ዓይነት ሶልት አንድ ፣ ሶልት ሁለት ፣ ሶልት ሦስት እየተባሉ በደረጃ ተመድበዋል። ሆኖም የስትራቴጂያዊ ጦር መሣሪያዎች ቅነሳ ድርድር በዓለም ወታደራዊ የበላይነትን ለመያዝ በሚጥረው በአሜሪካ መንግሥት እብሪተኛነትና እምቢተኛነት ምክንያት ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም ።

(የጦር መሣሪያ ቅነሳን ፣ ዴታንትን ይመለከቷል ።)

## ስቶይሲዝም

*(Staicism)*

በቆጵሮሱ ተወላጅ በዜና የተመሠረተ ፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ2ኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ በመስፋፋት ተከታዮችን ያፈራ የቁስአካልነት አዝማሚያ የነበረው ፍልስፍና ነው ። ይህ ስም ዜኖ ያስተምርበት ከነበረው ስቶይኮስ በመባል በአቴንስ ውስጥ ከታወቀው ቦታ የመጣ ነው ።

የስቶይሲዝም ሥነ ዕውቀት የተገነባው በከረረ ሕውስታዊነት ላይ ነው ። በዚህ ሕውስታዊነት የተነሣ ስቶይኮች ሁለንታዊነት ነባራዊነት የለውም በማለት ከተከታታይ ልባዌ የሚመነጭ የሐሳብ ውጤት ነው ሲሉ ተናግረዋል ። በስቶይኮች አስተሳሰብ የዕውቀት ብቸኛ ምንጭ ሕውስታ ነው ። ይህም ሕውስታዊነት በሥነ ኑባሬ አመለካከታቸው እውንነት ያለው ቁስአካል ብቻ ነው ብሎ ለመናገር ገፋፍቷቸዋል ። እውን ማለት አካል ያለው ነገር ብቻ ነው በማለት ተቃራኒ በሆነ አስተሳሰብ እግዚአብሔር ፣ ነፍስ ፣ ስናይና እኩይ የሚባሉትም አካል አላቸው ብለው ያምኑ ነበር ።

ስቶይሲዝምን በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ ታዋቂ ያደረገው ግን የሥነ ምግባር ንድፈ ሐሳብ ነው ። በስቶይሲዝም አመለካከት ስናይነት የሚገኘው ማንኛውም ነገር ከራሱ ተፈ

ጥሮ ጋር ተስማምቶ ሲኖር ብቻ ነው። ተፈጥሮ ወሳኝ ኃይል ሲሆን የሚያሳየውም ሥርዓት ምክኑያዊ ነው ። ስለሆነም ፋይዳዎች ተፈጥሮአዊ መሠረት አላቸው ፤ የሚገልጹትም ደንብንና ትክክለኝነትን ነው ። አንድ ዛፍ ትክክለኛ መልኩን ሳይዝ ሲቀር እንደሚጠላ ሁሉ የሰው አድራጐትና ተቋሞችም ከትክክለኛ ባሕርያቸው ሲርቁ ይነቀፋሉ ።

ይህ ለሁሉ ነገር የራሱ ደንብና ሥርዓት አለው የሚለው አስተሳሰብ ስቶይኮችን ኮስሞፖሊታን አመለካከት እንዲኖራቸው አድርጓቸዋል ። ሰዎች በዘር ወይም በተፈጥሮ አንድ በመሆናቸው ሁሉም የአንድ ሁለንታዊ ኅብረተሰብ አባል ናቸው ። ይህም አስተሳሰብ የሚያንፀባርቀው በጥንታዊት ግሪክ በከተማ አካባቢ ተመሥርቶ የነበረው ማኅበራዊና ፖለቲካዊ አንድነት እየፈረሰ መሄዱን ነው ። አመለካከቱም ለሮማ ግዛተ አጼ አመች ሆኖ በመገኘቱ ስቶይሲዝም በሮማውያን ዘንድ ተቀባይነት ሊያገኝ ችሏል ።

በስቶይኮች አስተሳሰብ ሰው ምንነቱን የሚጨብጠው ግዳጁን ሲወጣ ነው ። ግዳጅ ማለት የራስ ጥቅምን መፈለግ አይደለም ። ደስታም የሚገኘው ስሜቶችን በመቀስቀስ ሳይሆን በመጨቆን ˜ ነው ። ምክንያቱም ጭቆና የአእምሮ ዕረፍት ይሰጣል ። ሰው ለምንም ነገር ግድ እንዳይኖረው መጣር አለበት ። ግድ ሳይኖረው ሲቀር ነው ዓለምን እንዳለ የሚቀበለውና ከራሱ ተፈጥሮ ጋር ተስማምቶ ሲኖር የሚችለው ። ቁም ነገሩ ጌታ ወይም ደሀ ፣ ነፃ ወይም ባሪያ ወዘተ... መሆኑ አይደለም ፤ ምክንያቱም ወሳኙ በነዚህ ነገሮች ላይ ያለን ውስጣዊ አመለካከት ወይም ግዴለሽነት ነው ። በመሆኑም የረጋና ትክክለኛ ኑሮ የሚገኘው ስሜቶችን በአጠቃላይ በማስወገድ በግዴለሽነት ላይ የተመሠረተ ኑሮ በመኖር ነው ።

ስቶይሲዝም በጐ ጐኖች አሉት ። በተለይም ሰዎች በተፈጥሮ አንድ በመሆናቸው በእኩልና በሁለንታዊ ሕጐች ሥር መተዳደር አለባቸው የሚለው አመለካከት የባሪያ አሳዳሪውን ሥርዓት የሚነቅፍ ነበር ። ጠባብ የጐጣ ስሜቶችን በመዋጋት ዓለምአቀፍ አመለካከቶችን ማራመዱ ሌላው የስቶይሲዝም ጥሩ አዝማሚያ ነው ። ሆኖም ስቶይሲዝም ስለሥነ ዕውቀት ሆነ ስለኑባሬ የነበረው አመለካከት የተዛባና ጥልቀት የሌለው ነው ። በተለይም አካላዊና ኢአካላዊ(ነፀብራቆች) ክስተቶችን መለየት አለመቻሉ ቁስአካላዊነቱን ግልብ አድርጐታል ። በሌላ በኩል የባሪያ አሳዳሪውን ሥርዓት የነቀፈ ቢሆንም ሊታገለውና ሊያወድመው አልፈለገም ። እንዲያውም ግዴለሽነትን በማስፋፋት ሰዎች ሥርዓቱን እንዲቀበሉት የሚገፋፋ ሆኗል ። በአጠቃላይ ስቶይሲዝም የሚያራምደው የራስና የስሜት ጭቆና ሥነ ምግባር የሚያንፀባርቀው የባሪያ አሳዳሪውን ሥርዓት ነው ።

## ስፍራና ጊዜ

*(Space and Time)*

ስፍራ በቅስቃሴ ላይ ያለ የቁስአካል ነባራዊ ሁኔታ ነው ። ስፍራ የሚለው ጽንሰ ሐሳብ የነገሮችን ጣምራ ህልውናና መለያየት እንዲሁም አንዱ ከሌላው ጋር ያለውን ግንኙነት (በርቀትና በቅርበት ፣ በአቅጣጫ ወይም በአኳያ) ይገልጻል ። አጭር ይሁን ረጅም ፣ ጠባብ ይሁን ሰፊ ፣ ከፍተኛም ይሁን ዝቅተኛ ማንኛውም ነገር መጠን አለው ። ነገሮች ሁሉ እንደየባሕርያቸው የራሳቸው የሆነ ወርድ ፣ ቁመትና ይዘት ስለአላቸው በተወሰነ ቦታ ላይ መገኘትና የተወሰነ ስፍራ መያዝ ዓይነተኛ ጠባያቸው ነው ። ይሁን እንጂ በአንድ በተወሰነ ስፍራ ረግተው የሚኖሩ አይደሉም ። ያለማቋረጥ ይንቀሳቀሳሉ ፤ እርስበርስ ቦታ ይለዋወጣሉ ፤ ይዘዋወራሉ ። በዓለም ውስጥ በቅስቃሴ ላይ ያልሆነ ነገር የለም ፣ በቅስቃሴ ላይ ያለው ቁስአካል ደግሞ ከስፍራና ከጊዜ ውጭ ሊንቀሳቀስ አይችልም ።

ጊዜ እንደ ስፍራ በንቅስቃሴ ላይ ያለ የቁስአካል ነባራዊ ሁኔታ ነው ። ጊዜ የቁስአካላዊ ሂደቶችን የዕድገት ደረጃ ተከታታይነት ፣ የደረጃዎችን ፍርርቅ ፣ ለመቆየት መቻልንና በዚህም በደረጃዎቹ የማደግን ዓይነተኛ ጠባይ ያመለክታል ። ስፍራና ጊዜ የጋራ ጠባያቸው ነባራዊ ፣ ዘለዓለማዊ ፣ ወሰንየለሽ ፣ መጀመሪያና መጨረሻ የለሽ መሆናቸው ነው ። የስፍራ ወሰንየለሽነት ሲባል በፈለግነው አቅጣጫ ተነሥተን ብንጓዝ የስፍራ ወሰን የሚሉት አያጋጥመንም ፣ ጭራሽ ወሰን የለውም ማለት ነው ። ስፍራና ጊዜ የቁስአካል

ህልውና ቅርፆች ቢሆኑም የተለያዩ ናቸው ። ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም ልዩነት አላቸው ። ስፍራ ባለሦስት ጐን (ወርድ ፣ ቁመትና ከፍታ) ሲሆን ጊዜ ደግሞ ባለአንድ አቅጣጫ ጐንና የማይቀለበስ ሆኖ ከኃላፊ ወደ አሁኑ ፣ ከአሁኑ ወደ መጪው የሚጓዝ ነው ። ለምሳሌ በስፍራ ውስጥ አንድ ሰው አካሉን ከቀኝ ወደ ግራ ፣ ወይም ከግራ ወደ ቀኝ ሊያንቀሳቅስ ወይም ወደ ላይ ሊዘል ወይም ወደታች ሊያጐነብስ ወዘተ... ሲችል ከጊዜ አንፃር ግን የትናንቱን ወደ ዛሬ ፣ የዛሬውን ወደትናንቱ ሊያዛውር አይችልም ። ስፍራና ጊዜ ከቁስአካል የማይገነጠሉ በመሆናቸው ነባራዊ ናቸው ። ይሁን እንጂ የነርሱ ነባራዊነት ከቁስአካል ውጭ ትርጉም የለውም ።

## ስፒኖዛ ፣ ባሩክ

*(Spinoza, Baruch)*

ከ1632—1677 የኖረ ፣ ወደሆላንድ ከተሰደዱ የፖርቱጋል አይሁድ ቤተሰብ የተወለደ ፈላስፋ ነው ። የፍልስፍናው ይዘት ይሁዳዊነትን ይፃረራል ተብሎም በይፋ ተወግዟል ። ስፒኖዛ ክብርና ሀብት አልፈልግም በማለት እንዲሁም የአስተሳሰብ ነፃነቱን ለመጠበቅ ሲል የፍልስፍና አስተማሪ እንዲሆን ከሀይድልበርግ ዩኒቨርሲቲ የተላከለትን ጥሪ ባለመቀበል የመነጽር መስታወት በመቅረፅ የኖረና ሁልአምላክነትን ያዳበረ ፈላስፋ ነው ።

ስፒኖዛን በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ በይበልጥ ታዋቂ ያደረገው ተፈጥሮንና እግዚአብሔርን አዋህዶ አንድ ናቸው ብሎ መናገሩ ነው ። በዚህም አመለካከቱ ቁስአካላዊ ነው ተብሎ ይገመት ነበር ። የደረሰው ዋናው ጽሑፍ “ኤቲክስ” የሚለው ሲሆን በዚሁ ጽሑፍ ውስጥ ስለእግዚአብሔር መንፈሳዊነት ብቻ እስካሁን የተነገረው ትክክል እንዳልሆነና እግዚአብሔር ፍጹም የማያልቅና የማይወሰን ኃይል በመሆኑ ተፈጥሮን ከሱ ነጥሎ ማየት እንደማይቻል ተናግሮአል ። ተፈጥሮ ከእግዚአብሔር ውጭ ከሆነ እግዚአብሔር የእሱ ባልሆነ ነገር ታግዶ ፣ ተወስኖ ማለት ከመሆኑም በላይ አንድን ነባራዊ የሆነ ጠባይ ከሱ መቀነስ ነው ።

እንደ ስፒኖዛ አባባል ከእግዚአብሔር ጠባዮች እኛ የምናውቃቸው ሐሳብና ዝርጋታ (extension) ወይም ቁስአካል ናቸው ። እነዚህን የኑባሬ ጠባዮች አንዱን ፈጣሪ ፣ ሌላውን ተፈጣሪ ፣ አንዱን መንሥኤ ፣ ሌላውን ተገብሮት አድርገን ማየት የለብንም ፤ ይልቁኑ የሐሳብ ሥርዓትና ቁስአካላዊ ሥርዓት አንድ እንደሆኑ ማወቅ ይኖርብናል ። ሁለቱም የሚገልጹት ያው የእግዚአብሔርን አንድነት በመሆኑ ሐሳብ ከቁስአካል ውጭ ያለ ሳይሆን የቁስአካል ሌላው መልክ ወይም ውስጣዊ ገጽታ ነው ። ለምሳሌ እንቅስቃሴን ብንወስድ በውጫዊነቱ በሥጋዊ ክስተት ፣ በውስጣዊነቱ ደግሞ በስሜት ይገለጻል ።

እንደ ስፒኖዛ አመለካከት እግዚአብሔር የተፈጥሮ ክስተቶች አንድነት ፣ የአመጣጣቸውና የአኗኗናቸው መሠረታዊ አንቀሳቃሽ ሕግ ነው ። ከዚህም የተነሣ ማንኛውም ነገር የሚመነጨው ከግዴታ ብቻ ነው ። እግዚአብሔርን በሰው ምስል የሚገለጽ እንደሰው ፍላጐት ፣ ምኞትና ዕቅድ ያለው ነገር አድርገን ማሰብ የለብንም ። ፍላጐትና ምኞት የሚገልጹት ውሱንነትን በመሆኑ ለእግዚአብሔር ተመጣጣኝ የሚሆነው ከራሱ ውስጣዊ ሕግጋትና ምንነት በሚመነጭና ሊቀር በማይችል ሁኔታ እራሱን ሲገልጽ ነው ። ዓለም በፍጹማዊ ግዴታ የማይገዛ የሚመስለን ነገሮችን በተናጠል ስለምናያቸው ነው ። ይህም ስለ ነገሮች ምክኑያዊ የሆነ ዕውቀት እንደሌለንና ሕውስታዊ አመለካከት ብቻ እንዳለን ያስረዳል። ዓለምን በአንድነቱ ስንመለከተው ማንኛውም ነገር መንሥኤ ያለው ማለትም በግዴታ የሚገዛ መሆኑን እንረዳለን ።

በስፒኖዛ አስተሳሰብ የዕውቀት ሚና ሰውን ከተገዥነት ወደነፃነት መውሰድ ነው ። ነፃነት ማለት ከግዴታ መውጣት ሳይሆን ግዴታን ተረድቶ በዚያው መሠረት መኖር ነው ። የሰው ተገዥነት የሚመነጨው ከዕውቀት ማነስ ማለትም ከምክኑያዊ ዕውቀት ደረጃ አለመድረስ ነው ። ተገዥ መሆን በስሜት መራራት ነው ፤ ምክንያቱም ስሜት የሚመነጨው ነገሮች በተናጠል በኛ ላይ ባላቸው ተፅዕኖ ነው ። በምክንያት ካለመረዳታችን የተነሣ የሚደርስብን ነገር ሁሉ ለኛ እንግዳ ስለሚሆንብን ሐዘን፣ ቅሬታ ፣ ብስጭት ወዘተ... የመሳሰሉትን ስሜቶች ይፈጥርብናል ። ነገር ግን ምክንያቱን ማለትም ግዴታ

ዊነቱን ከተረዳን የራሳችንን ተሳትፎ እንድ ናክልበት ስለሚገፋፉን ተገዥ ሳንሆን በቀ ጥታ ተሳታፊ ሆነን ፍላጐታችንን ከእግዚአ ብሔር ጋር በማዋሀድ የሱን ዘለዓለማዊ ደስታ እንድንቀምስ ያደርገናል ።

በፖለቲካ መስከም ስፒኖዛ ተመሳሳይ አመለካከት ነበረው ። ፖለቲካ ውስጥ ስሜት መጨመር የለብንም ። ሁሉ ነገር በግዴታ ስለሚገዛ ሰናይ ሆነ እኩይ የሚባል ነገር እንደሌለ ሁሉ የመንግሥት ምንነት የሚገለ ጸው ከግዴታ አንፃር ነው ። የኅብረተሰብ አመሠራረት የሚያስረዳን ማንኛውም ግለ ሰብ የራሱ የሆነ ጠባይና ኃይል ቢኖረውም ብቻውን ሆኖ ተፈጥሮን ለመቋቋም እንደ ማይችል ነው ። በዚህም የተነሣ ሰው ኅብረት ለመፍጠር ይገደዳል ። መንግሥት የምንለው የዚህ ኅብረት የተደራጀ መልክ ነው ። ማን ኛውም ግለሰብ የራሱን ማለትም የግሉን ኃይል ለመንግሥት ያስረክባል ፤ በሌሎችም ትብብር ኃይሉ ያንኑ ያህል ያድጋል ። ይህም ማለት አንድ መንግሥት በይበልጥ ኃይለኛ የሚሆ ነው ግለሰቦች ያላቸውን ኃይል በብዛት ወደሱ ሲያዛውሩ ነው ። ለመንግሥት የሚሰጠው ሥልጣን የግለሰቦች ነፃነት መሠረት ማለትም መብት ሆኖ ሲመለስ መንግሥት ኃይለኛና ቋሚ ይሆናል ። በዚህ ግንዛቤ ንጉሣዊና ፍጹማዊ አገዛዝን በጥብቅ በመቃወም የመ ንግሥት ሚና የግለሰቦችን ምክኑያዊ ነፃነት መጠበቅና ማክበር ነው ሲል ተናግሯል ።

የስፒኖዛ ፍልስፍና የግዴታን ጽንሰ ሐሳብ እስከመጨረሻው ድረስ ስናጤን የምን ደርስበት አመለካከት ነው ። ለዕድል ፣ ለአ ጋጣሚ ወይም ደግሞ ለኀሊናዊ ምርጫ ቦታ አለመስጠቱ ቁስአካላዊ ያደረገው ቢመ ስልም ሁሉን ነገር በግዴታ ብቻ ለማስረ ዳት በመሞከሩ ተፈጥሮን ከእግዚአብሔር ጋር አዋህዶ ለማሰብ ተገዷል ። ግዴታ ወደ አጋጣሚ ፣ አጋጣሚ ወደግዴታ የሚቀየር መሆኑን ተረድቶ ቢሆን ኖሮ የእግዚአብሔ ርን ኃይል መጥቀስ ባላስፈለገውም ነበር ። ደግ ሞም ሁሉ ነገር ከግዴታ ብቻ የሚመነጭ ከሆነ ጊዜና ታሪክ ፍች ያጣሉ ፤ በዚህ ሁኔታ ግዴታ ማለት የተወሰነ ፣ ያለቀለት ማለት በመሆኑ ወደዘለዓለማዊ አስተሳሰብ ስለሚመራ አዲስ ሁኔታዎችን መፈጠርና የዕድገት እን ቅስቃሴዎችን መገንዘብ አዳጋች ይሆናል ።

ለምሳሌ ስፒኖዛ ራሱ እንደሚለው ሐሳብ ዘለዓለማዊና የቁስአካል ሌላው ገጽታ አይደለም ፤ ሐሳብ የተገኘው ከተፈጥሮ ዕድገት ነው ። በመሆኑም የሐሳብ ወይም የዕውቀት ሚና ግዴታን ተገንዝቦ ለእሱ ብቻ ተገዥ መሆን አይደለም ። የዕውቀት ትክክለኛው አስተዋጽኦ ሰው የሚገኝበትን ተጨባጭ ሁኔታ ለመቀየር ለሚያደርገው ተግባራዊ እንቅስቃሴ አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት ነው ። ግዴታን ብቻ በመገንዘብ የሚኖረን ነፃነት ኀሊናዊነት እንጂ ነባራዊነት የለውም ። ነፃነት ነባራዊ የሚሆነው ግዴታን ተገንዝቦ በተግባራዊ እንቅስቃሴ የተሻለ ሁኔታ ለማስ ገኘት ጥረት ሲደረግ ነው ።

በሌላ በኩል ግላዊ የሆነ ነፃነት ማለትም ከኅብረተሰቡ ሁኔታ ውጭ የሆነ ነፃነት ሊኖር አይችልም ። በዚህ አኳያ ስለነፃነትና ስለኅብረተሰብ ስፒኖዛ የነበረው አቋም የቡርዧ መሆኑ ግልጽ ነው ። መንግሥት የተ ቋቋመው ግለሰቦች በተናጠል የነበራቸውን ኃይል በውክልና በመስጠታቸው ነው የሚ ለው አባባል ለዚህ በቂ ማስረጃ ነው ። መን ግሥት በውል ፣ በስምምነት የሚመሠረት እንዳልሆነና ጨቋኝነቱ የሚመነጨው በውል (ኮንትራት) አለማክበር እንዳልሆነ ለመገን ዘብ በቅድሚያ የመደብ አገዛዝ መሣሪያ መሆኑን መረዳት ያሻል ።

ስፒኖዛ እራሱን ለማዳንና ነፃ ለማው ጣት በግል የሚያደርገው ጥረት የራሱን አስተሳሰብ ማለትም የተፈጥሮን አንድነት የሚቃረን ነው ። ሁሉ ነገር አንድ ከሆነ ነፃነት የወል እንጂ የግል ሊሆን አይችልም ። ትክክለኛው አስተሳሰብ አንድ ሰው ለኅብ ረተሰቡ በግል ያለውን ኃይል ማስረከብ ሳይሆን በግል ያለው ኃይል እንደ ኅብረተ ሰቡ ሁኔታ በድርሻ የሚያገኘው መሆኑ ነው ። ይህም ማለት በተፈጥሮ ፣ ከማኅበራዊ ኑሮ ውጭ ፣ ግለሰቡ አንድ ቀን እንኳን የሚያኖ ረው ኃይል የለውም ። ከዚህ የምንረዳው ስፒኖዛ በግላዊነቱ የተነሣ የነበረውን ቁስ አካላዊ አዝማሚያ ከግቡ ለማድረስ አለመ ቻሉን ነው ።

(ሁልአምላክነትን ይመለከቷል ።)

## ስፓርታኪስት (ስፓርታሲስት)

(*Spartakist – German*) (*Spartacist – English*)

ካርል ሊብክኔኽት የተባለ ማርክሳዊ ጀር መናዊ ከ1918—1919 በጀርመን ውስጥ ከሮዛ

ሉክሰምበርግና ከሌሎችም ጋር በመሆን በአጽጽመው ስፓርታኩስ ቡድን (የስፓርታኩስ ኅብረት) በተባለ ኀቡእ ማርክሳዊ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ አባል ሆኖ የሚታገል ሰው የሚጠራበት ስም ነው ። ስፓርታኩስ ከ1918 እስከ 1919 በነበረው ጊዜ ውስጥ የካርል ሊብክኔኽት የብዕር ስሙ ስለነበር ስፓርታሲስት ማለት የስፓርታኩስ ፣ ማለትም የካርል ሊብክኔኽት ተከታይ ማለት ነው ። ቢታሪከም ይህ ስያሜ በደቡብ ኢጣሊያ የባሮችን አመፅ ከመራው ማለትም ከስፓርታኩስ ስም ጋር የተያያዘ ነው ።

የካርል ሊብክኔኽት ትግል በሦስት ዓላማዎች ላይ ያተኮረ ነበር ። እነዚህ ም ፣ አንደኛ ከ1848 ጀምሮ በጀርመን እያደገ የመጣውን የወዝአደሩን ትግል ማጠናከር ፣ ማቀነባበርና መምራት ፤ ሁለተኛ በጀርመን ማርክሲዝም ተግባራዊ እንዲሆንና የወዝአደሩም የትግል መመሪያ ይኸው ፍልስፍና ሆኖ ወዛደራዊ ዓለምአቀፋዊነት እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ ፣ ሦስተኛ ጦረኝነትን መዋጋት ናቸው ።

የሊብክኔኽት ዋና ዓላማ በሩሲያ የተካሄደውን የጥቅምት 1917 አብዮት ዓይነት በጀርመንም ማካሄድ ነበር ። ለዚህም ዓላማው መሳካት መላውን የጀርመን ሕዝብ በተለይም ወጣቱን ለመቀስቀስ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል ። በኋላም በጀርመን ኮሚኒስት ፓርቲ እንዲቋቋም ወሳኝ ሚና ተጫውቷል ። ይህ ኮሚኒስት ፓርቲ በጊዜው የነበሩ ተራማጆችን ለማስባሰብ ሞክሮ ሳይሳካለት ቀርቷል ። በመጨረሻም በፓርቲውና በጊዜው በነበረው መንግሥት መካከል ግጭቶች ተፈጥረው ብዙ ደም መፉሰስን አስከተሉ ። በዚህ ጊዜ ሊብክኔኽትም ሆነ አባላቱ አጥብቀው ይቃወሙት የነበረው ታክቲክ ማለትም በመሣሪያ ኃይል መጠቀም በመጀመሩ ተቃዋሚ ፀረ አብዮት ቡድኖችን ቀሰቀስ ። በመጨረሻም ጥር 15 ቀን 1919 ሊብክኔኽትና ሮዛ ሉክሰምበርግ በቅጥር ነፍስ ገዳዮች ተገደሉ ።

## ስፔንሰር ፣ ሄርበርት

*(Spencer, Herbert)*

ከ1820 — 1903 የኖረ የእንግሊዝ ሐሳባዊ ፈላስፋ ነው ።

ስፔንሰር የተጨባጫዊነት ፍልስፍና ተከታይ ሲሆን ፍልስፍናው የተመሠረተው በተፈጥሮ አዝጋሚ ለውጥ ንድፈ ሐሳብ ላይ ነው ። በደረሳቸው መጻሕፍት ውስጥ (ለምሳሌ ፕሪንስፕል ኦቭ ኒው ሲስተም ኦቭ ፊሎሶፊ ፣ ዘ ክላሲፊኬሽን ኦቭ ዘ ሳይንስ ፣ ፕሪንስፕል ኦቭ ሞራሊቲ). ይህንኑ የአዝጋሚ ለውጥ ንድፈ ሐሳብ ለማብራራትና የነገሮችን ምንነት ለመረዳት ንድፈ ሐሳቡ ጠቃሚና ወሳኝ እንደሆነ ለማሳየት ሞክሮ አል ።

በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ ይበልጥ የታወቀው የአዝጋሚ ለውጥ ንድፈ ሐሳብን ለኅብረተሰብ ጥናት መጠቀሚያ ማድረጉ ነው ። ኅብረተሰብ ለውጥና ዕድገት እንደሚያሳይና ይህም ዕድገት ኅብረተሰብን ወደ ውስብስብ አደረጃጀት እንደሚወስደው ለማስረዳት ጥሮ አል ። ሆኖም አመለካከቱ የጠራ ስላልነበረ የተፈጥሮንና የኅብረተሰብን ልዩነት ለመገንዘብ አልቻለም ። ስፔንሰር በአቋሙም ግለሰብኛና ፀረ ሶሻሊስት በመሆኑ የመደብ ትግልን ሁኔታና ሕግጋት ሊረዳና ሊቀበል አልፈቀደም ።

(ተጨባጫዊነትን ይመለከቷል ።)

## ሶሻሊስታዊ የሥራ ውድድር

*(Socialist_Emulation)*

የሶሻሊስት ምርት ግንኙነት ገጽታ የሚገለጽበት ፣ የተወሰነን ዕቅድ በወቅቱ ለማሟላት ወይም ከዕቅድ በላይ ለማከናወን ፣ በአጠቃላይ ወጪን በመቀነስ ምርትን ከፍ ለማድረግ በሠራተኛው መካከል የሚደረግ ጓዳዊ ውድድር ነው ። በሶሻሊስት ሥርዓት ሠራተኛው ሕዝብ ሥራ የሚሠራው ፍላጐቱን ለማሟላት፣ ከብዝበዛ ነፃ በሆነ ሁኔታ ለራሱና ለኅብረተሰቡ ጥቅም አስተዋጽኦ ለማድረግ ነው ።

ሶሻሊስታዊ የሥራ ውድድር በካፒታሊዝም ሥር እንዳለው ውድድር በሠራተኞች ዘንድ መመቀኛኘትን አያስከትልም ። ሠራተኛው ሥራውን የማጣት ሥጋት ስለሌለበት ነገም ን እሆናለሁ አይልም ። ኑሮውና ደኅንነቱ የሚወሰነው በጋራ ጥረት መሆኑን ይገነዘባል ። ስለዚህም የእያንዳንዱ ግለሰብ የሥራ ውጤት ማደግ የኅብረተሰቡን ጥቅም ያሳድ

ጋል ። ይህም የጋራ ዓላማ የጋራ ጥረትን ይጠይቃል ፤ የሶሻሊስት ማንቃቂያ መሠረት የሆነውን ጓዳዊ ትብብር ያጠናክራል ።

ሠራተኛው ሕዝብ ሥራ የሚሠራው ለራሱና ለኅብረተሰቡ ጥቅም በመሆኑ እያንዳንዱ ሠራተኛ ምርትን በብዛትና በጥራት ለማምረት ፣ ምርታማነትን ለመጨመር ፣ ምርትን የሚያሳድግ አሠራር ለመፍጠር ባለው ችሎታ ሁሉ ይጠቀማል ።

ሶሻሊስታዊ የሥራ ውድድር ጥራትን ለማሻሻል፣ ወጪን ለመቀነስ ፣ የማምረቻ መሣሪያን በጥንቃቄ ሥራ ላይ ለማዋልና ጥሬ ዕቃን በቁጠባ ለመያዝ ይረዳል ።

ሶሻሊስታዊ የሥራ ውድድር ቁሳዊና የሞራል ማበረታቻን ያጠቃልላል ። ይህም ሠራተኛው የሥራ ውጤቱን በብዛትና በጥራት እንዲያሳድግ ያደርገዋል ። የበለጠ ውጤት የሚያስገኘው ከፍተኛ ቁሳዊ ማበረታቻ ያገኛል ፤ የክብር የምስክር ወረቀትና ሜዳሊያ ይሰጠዋል ። ስሙ በክብር መዝገብ ላይ ይሰፍራል ። ውጤቱም በዜና ማሰራጫዎች በሰፊው ይገለጻል ። በሥራ እንቅስቃሴአቸው ከፍተኛ ውጤት ያገኙ ግለሰቦችና ድርጅቶች እንደምሳሌ ሆነው ይቀርባሉ ። በአርአያነት መቅረባቸው ሌሎችን ለሥራ ይጋብዛል ። አርአያ የሆኑ ግለሰቦችና ድርጅቶች ያስገኙት የሥራ ውጤት ፣ ለውጤቱ ምክንያት የሆኑት ነጥቦችና የተጠቀሙባቸው የአሠራር ዘዴዎች በዝርዝር ለሠራተኛው ሕዝብ ይገለጻሉ ። የሙያ ማኅበሮችና ሕዝባዊ ድርጅቶች ሶሻሊስታዊ የሥራ ውድድርን የማካሄድ ዓቢይ ሚና አላቸው ።

ሶሻሊስታዊ የሥራ ውድድር በተለያየ መልክ ይካሄዳል ። ለምሳሌ በ1919 በሶቭዬት ኅብረት የተጀመረው የሱቦትኒክ ንቅናቄ ለኅብረተሰቡ ጥቅም ከሥራ ሰዓት ውጭ በፈቃደኝነት የመሥራት እንቅስቃሴ በታሪክ ምሳሌነት ያለው ሶሻሊስታዊ የሥራ ውድድር ዓይነት ነው ። በሀገራችንም ይኸው በትርፍ ሰዓት በነፃ የመሥራትና ኮከብ አምራቾችን የመሸለምና የማስተዋወቅ ልምድ እየተስፋፋ በመሄድ ላይ ይገኛል ።

## ሶሻሊስት የሸቀጥ ምርት
*(Socialist Commodity Production)*

ከሶሻሊስት አብዮት በኋላ የሚከሰት ፣ በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ምርት ለገበያ የሚመረትበት ሂደት ነው ። ሶሻሊስት የሸቀጥ ምርት የሚመለከተው የሠራተኛውንና የኅብረት አራሹን መደቦች ምርት ነው ። በሶሻሊስት የሸቀጥ ምርት ወቅት አምራቹ መደብ የምርት መገልገያዎች ባለቤት በመሆኑ የምርት ማኅበራዊ ጠባይ የተሟላ ይሆናል ።

በሶሻሊስት ሥርዓት የምርት መገልገያ መሣሪያዎች የሕዝብ ከመሆናቸውና የሰው የሥራ ኃይል ሸቀጥ መሆኑ ከማክተሙ ጋር ሁለት የይዞታ መልኮች ማለትም የመንግሥትና የኅብረት ይዞታዎች በመኖራቸው የሸቀጥ ምርት በምርት መገልገያዎች የጋራ ባለቤትነት ላይ የተመሠረተ ነው ።

በሶሻሊስት የሸቀጥ ምርት ወቅት በተለይ ለፍጆታ የሚያገለግሉ ዕቃዎች እንደ ካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት ለትርፍ ብቻ ሳይሆን በቅድሚያ የተጠቃሚውን ሕዝብ ፍላጎት ለማርካት የሚመረቱ ቢሆኑም ለተጠቃሚው ሕዝብ የሚደርሱት በገበያ ውስጥ በሸቀጥ—ገንዘብ ልውውጥ አማካይነት ነው ። እንደ ትርፍና ብድር የመሳሰሉ የኢኮኖሚ ፈርጆች በሶሻሊስት ሸቀጥ ምርት ወቅት ይኖራሉ ። ባሕርያቸው ግን በካፒታሊዝም ውስጥ ካለው የተለየ ነው ። በሶሻሊስት የሸቀጥ ምርት ወቅት እንደ መሬት ፣ እንደ ዋና ዋና የምርት መገልገያዎችና እንደ ሥራ ኃይል ያሉት የሚሸጡ የሚለወጡ ባለመሆናቸው የሸቀጥ ምርት ተገብሮች ከመሆን የተገለሉ ናቸው ።

በሶሻሊዝም ውስጥ የሸቀጥ ምርት እንዲኖር ያስፈለገበት ምክንያት ሁለት የተለያዩ የሶሻሊስት ይዞታዎች ማለትም የመንግሥትና የኅብረት ይዞታዎች በመኖራቸውና በነዚህም በሁለቱ ይዞታዎች መካከል ያለው ማናቸውም ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት በሸቀጥ ገንዘብ ግንኙነት ፣ በገንዘብና በልውውጥ አማካይነት እንዲከናወን ሁኔታዎች ስለሚያስገድዱ ነው ። ከኮሚኒዝም የዕድገት ደረጃ እስከሚደረስና ምርትን ከፍላጐት በላይ ለማምረት እስከ

ሚቻልበት ጊዜ ድረስ ምርትን ለሠራተኛው ሆነ ለኅብረት አራሹ መደብ ለማዳረስ የሚቻለው "ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያንዳንዱ እንደሥራው" በሚለው የሶሻሊስት የምርት ውጤት ክፍፍል መርህ በመሆኑና ይህንንም መርህ ተግባራዊ ለማድረግ የሚቻለው በሸቀጥ—ገንዘብ ግንኙነት አማካይነት ብቻ በመሆኑ ነው ። በሶሻሊስት የዕድገት ደረጃ የሸቀጥ ገንዘብ ግንኙነት የሚኖረው በመንግሥት ይዞታውና በኅብረት ይዞታው ብቻ ሳይሆን በመንግሥት ይዞታው ውስጥ ባሉ የተለያዩ የማምረቻ ፣ የማከፋፈያና የገንዘብ ተቋሞች ነው ።

ሶሻሊስት የሸቀጥ ምርት በምርት መገልገያዎች የጋራ ባለቤትነት ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ዕድገቱ በዕቅድ የሚመራ ነው ። በካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት ወቅት እንዳለው ሳይሆን በሶሻሊስት የሸቀጥ ምርት ወቅት አምራቹ ከምርት መገልገያዎች ባለቤትነት የተገለለ አይደለም ። በሶሻሊስት የሸቀጥ ምርት የሠራተኛው የሥራ ኃይል ሸቀጥ ባለመሆኑ በገበያ ውስጥ ለሽያጭና ለግዥ አይቀርብም ። በሶሻሊስት የሸቀጥ ምርት ወቅት የምንዳ ባርነት ባለመኖሩ የሠራተኛው መደብ የሥራ ኃይሉን የመደቡ የጋራ ሀብት ከሆኑ የምርት መገልገያዎች ጋር በማቀናጀት የሚሠራው ለኑሮው ደረጃ መሻሻልና ለሀገር ብልጽግና ነው ።

ሶሻሊዝም እየዳበረ ሄዶ በገጠርና በከተማ መካከል ያለው ልዩነት ሲጠፋ ፣ በሶሻሊዝም የዕድገት ደረጃ ያሉት ሁለቱ ይዞታዎች ሲጠቃለሉና መደቦች ሲያከትሙ ፣ የምርት ኃይሎችን ከፍተኛ ዕድገት በማስገኘት ምርትን ከፍላጐት በላይ በማምረት "ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያንዳንዱ እንደፍላጐቱ" የሚለውን የኮሚኒስት የክፍፍል መርህ ተግባራዊ ለማድረግ ሲቻል የሶሻሊስት የሸቀጥ ምርት ይከስማል ።

(ካፒታሊስታዊ የሸቀጥ ምርትን ይመለከቷል።)

## ሶሻሊስት የአኗኗር ዘይቤ
*(Socialist Way of Life)*

የሶሻሊስት ሀገሮች ሠርቶ አደሮች የኑሮ ሁኔታ ዋና ዋና ገጽታዎች ድምር ውጤት ነው ። እነዚህም ገጽታዎች የሰው በሰው መበዝበዝ መወገድ ፣ የክፍፍል በሥራ ጥራትና መጠን መወሰን ፣ እውነተኛው የሠርቶ አደሩ ሕዝብ የፖለቲካ ነፃነት መረጋገጥና የመብቱና የሰብአዊ ክብሩ ዋስትና ማግኘት ፣ በሕዝቦች መካከል ጠንካራ የወንድማማችነትና የኅብረት መንፈስ መኖር፣ የእድላዊነት መጥፋት ፣ ምርትን የማሳደግ ጥረት ከሕዝቡ ፍላጐት ጋር መጣጣም ፣ የሶሻሊስት ሥነ ምግባር መስፈን ፣ በሁሉም ሀገሮች ሠርቶ አደሮች መሀከል ዓለምአቀፋዊ አንድነት መፈጠርና ለዓለም ሰላም ሳያሰልሱ መታገል ናቸው ። ሶሻሊስት የአኗኗር ዘይቤ የሚረጋገጠውም በማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ የሚመራው ሠራተኛው መደብ የፖለቲካ ሥልጣን ሲይዝና የምርት መገልገያዎች በማኅበራዊ ይዞታ ሥር ሲውሉ ነው ።

## ሶሻሊስት ሰብአዊነት
*(Socialist Humanism)*

ሶሻሊስት ሰብአዊነት ከቡርዧው ሰብአዊነት በይዘትም በዓይነትም የተለየ ነው ። የሰው ክብር ሆነ ነፃነት በግላዊ ሥርዓት ውስጥ ሊከበሩ አይችሉም የሚለው አመለካከት የሶሻሊስት ሰብአዊነት መንሥኤ ሐሳብ ነው ። ሰው ማኅበራዊ ፍጡር በመሆኑ ነፃነቱና ክብሩ በተጨባጭ ሊረጋገጥለት የሚችለው ማኅበራዊ ኑሮ ከመደባዊ ሥርዓት ሲላቀቅ ብቻ ነው ። ገዥና ተገዥ ፣ በዝባዥና ተበዝባዥ ባሉበት ሥርዓት ውስጥ ሰው ክብርና ነፃነት ሊኖረው ይችላል ብሎ ማሰብ ከንቱና አሳሳች አመለካከት ነው ። ሶሻሊስት ሥርዓት ብቻ ነው ለሰብአዊነት መረጋገጥ ተጨባጭ መሠረት ሊሰጥ የሚችለው ።

በመሆኑም ሶሻሊስት ሰብአዊነት እንደ ቡርዧው በግላዊ ጥቅም ላይ የተመሠረተ አይደለም ። የሰውን የማይነጣጠሉ ሁለት ባሕርያት ማለትም ግላዊነትንና ማኅበራዊነትን የሚያዛምድ አስተሳሰብ ነው ። ሰብአዊነት የሚመለከተው ግለሰቡን ሳይሆን ማኅበራዊ ግለሰቡን ነው ። ማኅበራዊ ግለሰብ ማለት የሱ ጥቅም የሁሉም ጥቅም የሆነ ፣ የሁሉም ጥቅም የግለሰቡ የሆነ ፣ በሙሉ ትብብር ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ውጤት ነው ። ኅብረተሰቡ ለግለሰቡ ነፃነት ፣ ክብር ፣ መብት ወዘተ... መከበር አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል ፤ ግለሰቡ ደግሞ በበኩሉ ለኅብረተሰቡ ደኅንነት አስተዋጽኦ ያደርጋል ።

የሶሻሊስት ሰብአዊነት ዋናው ፍላጐት የግለሰቡን የተሟላ ኑሮ ማለትም ሁለንታዊ

ነቱን ማረጋገጥ ነው ። ይህም ሁለንታዊነት የሚገለጸው በግለሰቡ ማኅበራዊ እንቅስቃሴ ነው ። የሰውን ሁለንታዊ ችሎታ በሥራ ለመ ተርጐም በመጀመሪያ ደረጃ በአእምሮና በጉ ልበት ሥራ መካከል ያለውን ልዩነት በሂደት ለማስቀረት ይጥራል ። በኅብረተሰቡ ውስጥ አብዛኛው ሰው በጉልበት ሥራ ብቻ ከተወ ሰነ ሰብአዊነት, ሊረጋገጥ አይችልም ። ሰው የማሰብ ፣ የመወሰን ፣ የማቀድ ፣ የመፍጠር ችሎታውን ካልተጠቀመበት በግማሽ አካሉ ብቻ እንደሚኖር እሙን ነው ። ይህን ሁኔታ ለማለፍ የሚቻለው የማምረቻ መሣሪያዎች እንዲሁም ማኅበራዊ ሥርዓቱ የግል ጥቅም ማስከበሪያ መሆናቸው ሲቀር ነው። የማምረቻ መሣሪያዎች በማኅበራዊ ባለቤትነት ሥር ሲተዳደሩ ነው ለኅብረተሰቡ አገልጋይና ለግለ ሰቡ ሁለንታዊነት መከሰት መሠረት የሚ ሆኑት ።

ከዚህ መረዳት የሚቻለው ሶሻሊስት ሰብአዊነት ለግለሰቡ ከፍተኛ ደረጃና ሚና የሚሰጥ መሆኑን ነው ። ግለሰብ በተወሰነ የመደብ ጥቅም መታሰሩ በመቅረቱ ችሎ ታው ሰፋ ያለ ማኅበራዊ ግብ ያገኛል ፤ ከዚ ህም የተነሣ ከመቼውም ይበልጥ ዕድገት ይኖረዋል ። አንድ ግለሰብ ለሌላው ተቃራኒው መሆኑ ቀርቶ ረዳቱ በመሆኑ ማለትም በአጠ ቃላይ አነጋገር ኅብረተሰቡ የግለሰቡ አካልና ምርኩዝ በመሆኑ ችሎታውና ኃይሉ በዚያው መጠን ይስፋፋለታል ። ብቻውን ተገንጥሎ ለራሱ ኑሮ የሚሯሯጥ ግለሰብ መሆኑ አብቅቶ ለሰው ዘር አጠቃላይ ዕድገት አንቀሳቃሽ ኃይል ይሆናል ። እኔ ፣ እሱ የሚለውን አልፎ እኛ ሲል ግላዊነትን ወደ ማኅበራዊ ግለሰብነት ደረጃ መቀየሩን የሚያረጋግጥ ይሆናል ።

(ሰብአዊነትን ይመለከቷል ።)

## ሶሻሊስት ንብረት
*(Socialist Property)*

የሶሻሊስት ኅብረተሰብ አባል የሆኑ ሠርቶ አደሮች የሥራ ተገብሮችንና የማምረቻ መሣ ሪያዎችን በጋራ የያዙበት የንብረት ዓይነት ሶሻሊስት ንብረት ይባላል ። በጥንታዊ የጋር ዮሽ ሥርዓት የወል ንብረት ቢኖርም ኋላ ቀር ሲሆን በአንፃሩ ግን የሶሻሊስት ንብረት የሚ ከሰተው ቴክኖሎጂና ባህል በዳበሩበት ወቅት ነው ። ሶሻሊስት ንብረት በሁለት ይከፈላል ። እነዚህም የኅብረት ሥራ ማኅበር ንብረትና የመንግሥት ንብረት ናቸው ።

የኅብረት ሥራ ማኅበር ንብረት የማኅ በሩ አባሎች በወል የያዙት ንብረት ነው ። ይህ የንብረት ዓይነት በአንድ በተወሰነ ወቅት ባለው የምርት ግንኙነት ላይ ይመሠረታል ። የኅብረት ሥራ ማኅበር ከካፒታሊስት ሥርዓት ዕድገት ጋር የተከሰተ ሲሆን በዚህ ሥርዓት ውስጥ የኅብረት ሥራ ማኅበር ንብረት በመሠ ረቱ የግል ንብረት ነው ። በሶሻሊስት ሥር ዓት የኅብረት ሥራ ማኅበር ንብረት አንድ ዓይነት የሶሻሊስት ንብረት ሲሆን የማምረቻ መሣሪያዎች በወል የተያዙበት ፣ አንዱ በሌ ላው የማይበዘበዝበትና ምርት ዕቅድ ባለው ሁኔታ የሚመረትበት ነው ።

የኅብረት ሥራ ማኅበር ንብረት የገበሬ ዎች አምራቾች ፣ የእደጥበብ ባለሙያዎችና የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራትን ንብረት ያጠቃልላል ። በአብዛኛዎቹ የሶሻሊስት ሀገ ሮች ውስጥ የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅ በራት በጣም ጠቃሚ የሆኑ የማምረቻ መሣሪ ያዎችንና የሥራ ተገብሮችን (ማሽኖችን ፣ ሕንፃ ዎችን ፣ ከብቶችን ወዘተ ...) በጋራ ሀብትነት ይይዛሉ ። ይህ የሚያመለክተው የነዚህ የማ ምረቻ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች የባለቤትነት ይዞታ የመላው ኅብረተሰብ ሳይሆን የአንድ ወይም ቁጥራቸው የተወሰነ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ንብረት መሆኑን ነው ። የኅብረት ሥራ ማኅበራት ንብረት የወል ንብረት ፣ የአንድ ወይም ቁጥራቸው የተወሰነ ማኅበራት ንብረት ከመ ሆን አልፎ ቀስ በቀስ የመላው ሕዝብ ንብረት ወደ መሆን ይሸጋገራል ። ይህ ሊሆን የሚ ችለው በኅብረት ሥራ ማኅበራት ውህደት ብሎም በመንግሥት ይዞታ ሥር በመታቀፍ ነው ። በሌኒናዊ መርህ ላይ የተመሠረቱ የኅብረት ሥራ ማኅበራት በኢትዮጵያም ውስጥ በማበብ ላይ ይገኛሉ ።

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ሌላው የን ብረት ዓይነት የመንግሥት ንብረት ነው ። የሶሻሊስት ሀገሮች የምርት መገልገያዎችና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች በይበልጥ የተ ያዙት በመንግሥት ነው ። እነዚህም ፋብሪ ካዎች ፣ የትራንስፖርት ተቋሞች ፣ ባንኮች የንግድ ተቋሞች ፣ የባህል ማዕከሎች ፣ ትም ህርት ቤቶችና የመሳሰሉት ናቸው ። እያንዳ

ንዱ የኅብረተሰብ አባል በእነዚህ የምርት መገልገያዎች አማካይነት ለመሥራት ይችላል ። በሥራውም መጠን ክፍያ የማግኘት መብት ይኖረዋል ። ስለሆነም ሠራተኛው ሕዝብ ከመንግሥት ንብረት ጋር ያለው ግንኙነት በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ነው ። በኢትዮጵያም ሰፋፊ እርሻዎችና ኢንዱስትሪዎች በመንግሥት ይዞታ ሥር መዋል የመንግሥት ንብረት እንዲመሠረት አድርጓል ።

## ሶሻሊስት አብዮታውያን
*(Socialist Revolutionaries)*

በ1901 መጨረሻና በ1902 መጀመሪያ ላይ የተለያዩ ናሮዲያዊ ቡድኖችንና ክበቦችን በማጣመር በሩሲያ የተመሠረተ የንዑስ ከበርቴ ፓርቲ ነው ። ሶሻሊስት አብዮታውያን የገበሬውን ጥያቄ በሚመለከት ባወጡት ፕሮግራማቸው የካፒታሊስቱ ሥርዓት እንዳለ ሆኖ እያንዳንዱ የገበሬ ቤተሰብ ለማረስ በሚችለው መጠን መሬት እንዲሰጠው ጠይቀዋል ። ሶሻሊስት አብዮታውያን ገበሬውን እንደአብዮቱ ዋና ኃይል በመቁጠር በአብዮቱ ውስጥ የሠራተኛውን መደብ ግንባር ቀደም ሚና የካዱ ፣ ማርክሲዝምን የተዋጉና በግለሰብ ሽብር የዘውድ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝን ለመጣል የተነሡ ናቸው ።

ከመጀመሪያው የሩሲያ ቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ሽንፈት በኋላ ብዙዎቹ የሶሻሊስት አብዮታውያን ተከታዮችና በአመራር ላይ የነበሩት ግለሰቦች የቡርዧዚውን ለዘብተኛ አቋም በመያዛቸው ፓርቲው መዳከም ጀመረ ። በ1906 ቀኙ ክንፍ ከዋናው ፓርቲ በመገንጠል በቄሳሩ መንግሥት በሕግ ታውቆ "ሕዝባዊ የሠራተኛ ሶሻሊስት ፓርቲ" በሚል ስያሜ ተቋቋመ ። ይህ ፓርቲ ማንኛውንም አብዮታዊ ጥያቄ ወደጐን በመተው ባካሄደው ፀረ አብዮት እንቅስቃሴ ከካዴቶች ፓርቲ እምብዛም የሚለይ አልነበረም ።

በስቶልፒን የአድኅሮት ዓመታት (በ1907—10) ቀንደኞቹ የሶሻሊስት አብዮታውያን መሪዎች ወደለዘብተኝነት አዘቀጡ ። በየካቲቱ የቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ወቅትም ሶሻሊስት አብዮታውያን የጊዜያዊው ቡርዧ መንግሥት ደጋፊ በመሆን ከሜንሼቪኮችና ከካዴቶች ፣ ከቡርዧዚዎችና ከፊውዳሎች ጋር አብረው ለሶሻሊዝም የሚደረገውን የሠራተኛውን አብዮታዊ ትግል በግልጽ ተዋግተዋል ። የፓርቲው መሪዎችም በአድኃሪው የቡርዧ መንግሥት መዋቅር ውስጥ ቁልፍ ቦታዎችን በመያዝ በየገጠሩ አምፀው ከፊውዳሎች በመንጠቅ መሬት የያዙትን ገበሬዎች በኃይል በማስለቀቅ የገበሬውን ፀረ ፊውዳል ትግል ተፃርረዋል ። ከ1917 የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት በኋላም ሶሻሊስት አብዮታውያን ለኢምፔሪያሊስቶች ጣልቃ ገብነት ፣ ለነጩ ሠራዊት ጠንካራ ድጋፍ በመስጠትና በፀረ አብዮት ድርጊት በመሰማራት በሶቭዬት ባለሥልጣኖችና በኮሚኒስት ፓርቲው መሪዎች ላይ ከፍተኛ የሽብር ዘመቻ አካሂደዋል ።

## ሶሻሊስት አብዮት
*(Socialist Revolution)*

የበዝባዥ መደቦችን የበላይነት ለማስወገድና የወዝአደሩን መደብ የበላይ ገዥነት ለማስፈን የሚካሄድ ሕዝባዊ አመፅ ሶሻሊስት አብዮት ይባላል ። ሶሻሊስት አብዮት በቅድሚያ ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል ዋንኛው ፣ በግንባር ቀደሙ ፓርቲ መሪነት ከበዝባዥ ገዥ መደብ ሥልጣን መንጠቅ ነው ። ከዚህም በኋላ የወዝአደሩ መደብ ይህን ሥልጣኑን እያስፋፋና እያዳበረ ከመሄዱ ጋር የግል ይዞታን በወል ይዞታ በመተካት የሰውን በሰው መበዝበዝ እያስወገደ መደብ አልባ ኅብረተሰብ የሚመሠረትበትን መንገድ ይጠርጋል ።

ሰፊውን ሠርቶ አደር ሕዝብ ዳር እስከ ዳር የሚያቅፈው የሶሻሊስት አብዮት ተግባር በውስብስብነቱና በጥልቀቱ ከአለፉት አብዮቶች ሁሉ የላቀና የተለየ ነው ። የዚህ አብዮት ውጤት የሚሆነው የአዲስ ኅብረተሰብ ግንባታም በተለያዩ ደረጃዎች ውስጥ ያልፋል። የዚህ ግንባታ የመጀመሪያው ደረጃ ሶሻሊዝም ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ኮሚኒዝም ነው ።

ሶሻሊስት አብዮት እንዲሳካ በማርክሳዊ ሌኒናዊ ንድፈ ሐሳብ የሚመራ የሠርቶ አደሩ ግንባር ቀደም ድርጅት አመራር ፣ የወዝአደሩና የአርሶ አደሩ መደቦች ትብብርና የሰፊው ሕዝብ አብዮታዊ ተሳትፎ አስፈላጊ ናቸው ።

የሶቭዬት ኅብረትና የሌሎችም ሀገሮች የሶሻሊስት ግንባታ ልምድ እንዳሳየው ፥ የአብዮቱ በሠራተኛው መደብ መመራትና የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት መመሥረት የቡርዧዚውን መንግሥታዊ መዋቅር ሰባብሮ አዲስ የሆነ መንግሥታዊ መዋቅር መዘርጋት ፥ የሠራተኛውና የገበሬው መደቦች መተባበር ፥ የካፒታሊስት ይዞታ መወገድና እርሻን ወደ ሶሻሊስታዊ ይዞት መለወጥ ፥ የኢኮኖሚ ዕድገት በዕቅድ መመራት ፥ የባህል አብዮት መካሄድ ፥ የብሔረሰቦችና የብሔሮች ጭቆና መወገድ ፥ የሶሻሊስት ድሎች መጠበቅና የወዝአደራዊ ዓለማቀፋዊነት መጠናከር የሶሻሊስት አብዮት ዋና ዋና ተግባራት ናቸው ። የምርት ኃይሎች የዕድገት ደረጃ ፥ የሕዝቡ ጠቅላላ የባህል ደረጃ ፥ በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው የኃይሎች አሰላለፍ ፥ እነዚህና ሌሎችም ጉዳዮች ደግሞ አንድ ሀገር የሚያካሂደውን ሶሻሊስት አብዮት ወይም አንድ ሀገር ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም ሽግግር የሚያደርግበትን ልዩ መልክ የሚወስኑ ይሆናሉ ። አብዮቱን የሚመራው ግንባር ቀደም የፖለቲካ ድርጅት ስልቱን የሚቀይሰውም እነዚህን ልዩ ባሕርያት መሠረት በማድረግ ነው ።

ሌኒን የካፒታሊዝምን ኢምፔሪያሊስታዊ ደረጃ በመተንተንና አዳዲስ መሠረተ ሐሳቦችን በማመንጨት የሶሻሊስት አብዮት ንድፈ ሐሳብን የበለጠ አዳብሯል ። ሌኒን ካቀረባቸው ሐሳቦች መካከልም ወዝአደሩ መጀመሪያ በአንድ ሀገር ወይም በብዙ ሀገሮች አብዮት አካሂዶ ድልን ሊቀዳጅ የሚችል መሆኑ ፥ ይህ ደግሞ የተለያየ የማኅበራዊ ኢኮኖሚና ፖለቲካ ሥርዓት ያላቸው ሀገሮች ጐን ለጐን መኖርን እንደሚያስከትል ፥ የቡርዧው ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት በወዝአደሩ የበላይ ገዥነት አማካይነት ወደ ሶሻሊስት አብዮት እንደሚሸጋገር ፥ የካፒታሊስት ሀገሮች ሠርቶ አደሮች ትግልና የብሔራዊ አርነት ንቅናቄዎች የተሳሰሩ ስለመሆናቸው ፥ አብዮታዊ ሁኔታ ነባራዊና ኅሊናዊ ሁኔታዎችን ስለማጣመሩ የሚሉት ይገኙበታል ። በዚህ ሂደት ግን የግንባር ቀደሙ የፖለቲካ ድርጅት ጠንካራ አመራር ወሳኝ ነው ።

(ፓርቲን ፥ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ይመለከቷል ።)

## ሶሻሊስት ኢንተርናሽናል
*(Socialist International)*

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት "የሠራተኛና ሶሻሊስት ኢንተርናሽናል" ይባል የነበረውን ድርጅት የተካውና አሁን ሶሻል ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎች የተሰበሰቡበት ዓለም አቀፍ ድርጅት ነው ። የተቋቋመው በምዕራብ ጀርመን በፍራንክፈርት (እም ማይን) ከተማ ውስጥ በ1951 ነው ። የድርጅቱ መሠረታዊ ዓላማ "ዲሞክራሲያዊ ሶሻሊዝምን" እውን ማድረግ ሲሆን ይህም ማለት በአዝጋሚ ሂደት ያለመደብ ትግልና ያለሶሻሊስት አብዮት ካፒታሊዝምን ቀስ በቀስ ወደ ሶሻሊዝም መለወጥና የግል ይዞታ ባለበት ሁኔታ ወዝአደሩ ሥልጣን እንዲይዝ ማድረግ ነው ስለሚል የማርክሲዝምን ንድፈ ሐሳብ መሠረታዊ ሕግጋት አይቀበልም ።

የሶሻሊስት ኢንተርናሽናል ተከታዮች በተለይ በታሪካቸው መጀመሪያ ወቅት ላይ ላዩን ለሰላም የቆሙ ቢመስሉም በተግባር ግን የኔቶን አቋም በመደገፍ የፀረ ሶሻሊስት ሀገሮችን አቋም በመውሰድና የካፒታሊስት ሀገሮችን የጦረኝነት አቋም በማጠናከር ቀዝቃዛው ጦርነትና በዚህም የዓለም ውጥረት እንዲባባስ አድርገዋል ። ይህ ድርጅት በመሠረቱ ፀረ ኮሚኒስት አቋም ያለው ቢሆንም አልፎ አልፎ አንዳንድ ጤናማ አዝማሚያዎች ይታዩበታል ። ቀደም ሲል ሁለት ተቃራኒ አቋሞች ነበሩት ። በአንድ በኩል ለኔቶ ታማኝነቱን ሲገልጽ በሌላ በኩል ደግሞ የዓለም ሠርቶአደሮች ለዓለም ሰላም የሚያደርጉትን ትግል ይደግፍ ነበር ። በኋላ ግን የኃይል ሚዛን ወደ ሶሻሊዝምና ወደ ዓለም ሰላም እያመዘነ ሲመጣ ሶሻሊስት ኢንተርናሽናል አቋሙን ከዚህ ሁኔታ ጋር ለማገናዘብና ከዚህም የተነሣ በሰላም አብሮ የመኖር መርሆችን ፥ የሶቭዬት ኅብረት የሰላም ፖሊሲን ፥ የአፍሪካ ፥ የእስያና የላቲን አሜሪካ ሕዝቦች የነፃነት ትግሎችን ለመደገፍ ተገደደ ። ሶሻሊስት ኢንተርናሽናል በ1960ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት ላይ አሜሪካ በቬትናምና በሌሎች የኢንዶቻይና ሕዝቦች ላይ ያካሄደችውን ወረራ ደግፎ ነበር ። በ1960ዎቹ የመጨረሻና በ1970ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት ግን ወረራውን አውግዞታል ።

የሶሻሊስት ኢንተርናሽናል መሪዎች ድርጅቱ ከኮሚኒስት ፓርቲዎችና ከሌሎች ተራማጅ ኃይሎች ጋር መቀራረብ እንዳይፈጥር ብርቱ ጥረት ቢያደርጉም ብዙዎቹ አባል ፓርቲዎች በየግላቸው ከብዙ የኮሚኒስት ፓርቲዎች ጋር የጋራ ስምምነቶችን መሥርተዋል ። ድርጅቱ ከኮሚኒስቶች ጋር ያለውን ግንኙነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻሻለ ቢመጣም አሁንም ቢሆን እንደመሪዎቹ አቋምና እንደጊዜው ሁኔታ የርሱም አቋም ይለዋወጣል ።

ሶሻሊስት ኢንተርናሽናል በ1978 በተደረገው ጥናት 57 ፓርቲዎችን ያጠቃለለ ነበር ። ከነዚህም 42ቱ ሙሉ አባላት ሲሆኑ 15ቱ ተመልካች አባላት ነበሩ ።

ከዚያም ወዲህ ድርጅቱ ለአፍሪካ አህጉር የተለየ ትኩረት በመስጠት በ1981 በቱኒስ ባደረገው ጉባኤ የሶሻሊስት ኢንተርናሽናል የአፍሪካ ቅርንጫፍን አቋቁሟል ። ሶሻሊስት ኢንተርናሽናል ይህን የአፍሪካ ቅርንጫፍ የመሠረተው ለሁለት ዓበይት ዓላማዎች ነው ። አንደኛው ማርክሲዝም ሌኒኒዝም በአፍሪካ እንዳይስፋፋ መከላከል ሲሆን ፣ ሁለተኛው ደግሞ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሶቭዬት ኅብረት በአፍሪካ ተቀባይነት እንዳይኖራት ማድረግ ነው ።

የድርጅቱን መዋቅር በሚመለከት ከፍተኛው የሥልጣን አካል ጉባኤ ሲሆን ይህም በየሁለት ዓመቱ ይሰበሰባል ። ከጉባኤ ቀጥሎ ያለው አካል "ቢሮ" ሲሆን ይህም እንደ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሆኖ የሚሠራ የሙሉ አባል ፓርቲዎች ተወካዮች የሚገኙበት ነው። ሌላው አካል ሴክሬታሪያት ሲሆን ይህም የድርጅቱን የዕለት ተዕለት ተግባር የሚያከናውን ነው ። ሶሻሊስት ኢንተርናሽናል "ሶሻሊስት አፌርስ" የሚል መጽሔት አለው ።

(ማኅበራዊ ዲሞክራሲን ይመለከቷል ።)

## ሶሻሊስት ኢኮኖሚ ዕቅድ (የ—)
*(Socialist Economic Planning)*

የኢኮኖሚ ዕቅድ ከተጨባጩ ሁኔታ በመነሣት የተወሰነን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚከናወን ሥራ መቼ? የት? እንዴትና በማን? እንደሚሠራ በቅድሚያ ለመወሰን የሚያስችል የአሠራር ስልት ሲሆን በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉት ልዩ ልዩ ክፍላተ ኢኮኖሚ ተደጋጋፊ ሆነው ለማደግ እንዲችሉ የሚረዳ አሠራር ነው ።

የሶሻሊስት ዕቅድ ዋና ዓላማ በአጠቃላይ የኅብረተሰቡንና የግለሰቦችን ቁሳዊና ባህላዊ ፍላጐት ማሟላት ነው ። ሶሻሊስት ኢኮኖሚ እንደ ካፒታሊስት ኢኮኖሚ በትርፍ ላይ የተመሠረተና በዘፈቀደ የሚመራ አይደለም ። ዓላማው በአጠቃላይ የኅብረተሰቡንና የግለሰቦችን ቁሳዊና ባህላዊ ዕድገት በከፍተኛ ደረጃ ማዳበር እንደመሆኑ የኢኮኖሚ ውሳኔዎች የሚመሠረቱት በሚያስገኙት ትርፍ ሳይሆን የኅብረተሰቡን መሠረታዊ ፍላጐት ለማርካት ከማስቻላቸው አንፃር ነው ።

ሶሻሊስት ዕቅድ ባለው ሀብት የኅብረተሰቡን ፍላጐቶች ማሟላትን ፤ የኅብረተሰቡን ቁሳዊ ሃብት ፣ ጉልበትና ገንዘብ ምደባና አጠቃቀም በአጭርና በረዥም ጊዜ መወሰንን ፤ ክምችትና ፍጆታ በተፈለገው ሁኔታ ቅንጅቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት የሚገኝበትን መንገድ መተለምን ፣ በልዩ ልዩ የኢኮኖሚ መስኮች መካከል ሚዛናዊና የተስተካከለ የዕድገት ግንኙነት እንዲኖር ማድረግንና ዕቅዱን ለመፈጸም የሚረዱ ተፈላጊ የቴክኒክ ፣ የፋይናንስ ፣ የሰው ኃይልና የመሳሰሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥንና የዕቅዱን አፈጻጸም መቆጣጠርን ያጠቃልላል ።

የምርት መገልገያዎች በመንግሥትና በሕዝብ ይዞታ ሥር መዋልና የሠራተኛው መደብ የፖለቲካ ሥልጣን መጨበጥ በኅብረተሰቡ ፍላጐት ላይ የተመሠረተ ዕድገት ለማስገኘት መሠረት ይጥላል ። በዚህ መሠረት የምርት ኃይሎችን በከፍተኛ ደረጃ ለማዳበር የሚያስፈልገው ክምችት መጠንና የክምችቱም ስርጭት የሚወሰነው እንደ ገበያው ሁኔታ ሳይሆን የኅብረተሰቡን የአጭርና የረዥም ጊዜ ፍላጐት በማመዛዘን ሰፊው ሕዝብ በአወሳሰኑ በየደረጃው በሚሳተፍበት ዕቅድ አማካይነት ነው ። ስለዚህ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ዕድገት ከማናቸውም ዓይነት ቀውስና ዝበት ነፃ በመሆን በከፍተኛ ደረጃ እየዳበረ የሚሄድ ኢኮኖሚ ነው ።

የምርት መገልገያዎች በማኅበራዊ ይዞታ ሥር መሆንና ምርት በማኅበራዊ ሁኔታ መከናወኑ የግድ የኢኮኖሚን ዕቅድ አስፈላጊነት ይጠይቃል ። የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ዕቅድ የኅብረተሰብን ዕድገት ሕጐች በተለይ የሶሻሊዝም ኢኮኖሚን ሕጐች በትክክል ዐውቆ በመጠቀም ላይ የተመሠረተ ነው ። ሶሻሊስት ዕቅድ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን የተከተለና ዕቅዱም ከጸደቀ በኋላ እንደ ሕግ ተፈጻሚነት የሚኖረው ነው ።

ሶሻሊስት ዕቅድ በማምረቻ መሣሪያዎችና በፍጆታ ዕቃዎች ፣ በኢንዱስትሪና በእርሻ ዕቃዎች አቅርቦትና በሕዝቡ ገቢ ፣ በምርትና በፍጆታ ፣ በምርትና በክምችት መካከል ያለው ግንኙነት ሚዛናዊና የተመጣጠነ መሆኑን ያረጋግጣል ። እንዲሁም የምርት ኃይሎችን ስርጭትና ከሌሎች ሶሻሊስት ሀገሮች ጋር መኖር የሚገባውን የሥራ ክፍፍል ይተልማል ። ስለሆነም የሶሻሊስት ዕቅድ መላ ኢኮኖሚውን የሚያጠቃልልና ዓላማውም ለኮሚኒዝም ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት መጣል ነው ።

በካፒታሊስት ሥርዓት የምርት መገልገያዎች በግል በመያዛቸውና እያንዳንዱ ካፒታሊስት የኅብረተሰቡን ፍላጐት ለማርካት ሳይሆን ዓላማው ለራሱ ብቻ ትርፍን ማካበት በመሆኑ በመሠረቱ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ በማኅበራዊ ዕቅድ የሚመራ አይደለም ። ቅይጥ የኢኮኖሚ ይዞታዎች ባሉበት በሽግግር ወቅት መንግሥታዊና ማኅበራዊ የኢኮኖሚ ይዞታዎች ደረጃ በደረጃ እየሰፉ በሄዱ መጠን የሶሻሊስቱን ዕቅድ የሚያቅፈው የኢኮኖሚ ክፍል በዚያው መጠን እየሰፋ ይሄዳል ። የሽግግር ወቅቱም በሚገባደድበት ጊዜ ሶሻሊስት ዕቅድ የተሟላ መልኩን ይይዛል ።

## ሶሻሊስት ኢኮኖሚ ጥምረት (የ—)
*(Socialist Economic Integration)*

የሶሻሊስት ዓለምአቀፍ የሥራ ክፍፍልን መሠረት በማድረግ በሶሻሊስት ሀገሮች መካከል የሕዝቦችን ቁሳዊና ባህላዊ ፍላጐቶች ለማሟላትና ከፍ ለማድረግ ፣ ቀስ በቀስ የተስተካከለ የኢኮኖሚ ዕድገት በአባል ሀገሮች መካከል ለማስገኘት የሚደረግ የኢኮኖሚ ትብብር የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ጥምረት ይባላል ። ዛሬ ይህን ተግባር የሚያስተባብረው ሶሻሊስት ሀገሮች አባል የሆኑበት የጋራ ኢኮኖሚ ተራድኦ ምክር ቤት እየተባለ የሚጠራው ዓለም አቀፍ ድርጅት ነው ።

የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ጥምረት ዓላማዎች የአባል ሀገሮችን የምርት ኃይሎች ማሳደግ ፣ የምርት ግንኙነቶቹን ማዳበር ፣ ከፍተኛ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ውጤት ማስገኘት ፣ ማኅበራዊ ምርትን ከከፍተኛ ደረጃ ላይ ማድረስ ፣ ንግድ እንዲስፋፋና እንዲጠናከር ማድረግ ናቸው ። ከዚህም በላይ ሶሻሊዝም በካፒታሊዝም ላይ የኢኮኖሚ የበላይነት እንዲጐናፀፍ ማድረግ ነው ።

የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ጥምረት በዕቅድ የሚመራ ፣ በፈቃደኝነትና በዓለምአቀፍ ወዝአደራዊነት መርሆች ላይ የተመሠረተ ሲሆን የአባል ሶሻሊስት ሀገሮችን በኢኮኖሚ ፣ በባህል ፣ በፖለቲካ ፣ በርዕዮተዓለምና በወታደራዊ ጉዳዮች ላይ መተባበርን ይጠይቃል ።

በሶሻሊስት ሀገሮች መካከል የሚደረጉ የኢኮኖሚ ትብብሮች የብሔራዊ ኢኮኖሚ ዕቅዶችንና የውጭ ንግድ ማቀናጀትን ፣ ብድር መስጠትን ፣ የሳይንስና የቴክኖሎጂ እርዳታ ማድረግን ፣ የኢኮኖሚ ግንባታ ልምዶች መለዋወጥን ፣ የሰው ኃይል ማሠልጠንንና የመሳሰሉትን ያጠቃልላሉ ። ስለዚህም በሶሻሊዝም ዕድገት ውስጥ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ጥምረት የግድ አስፈላጊ ነው ።

ዛሬ በጋራ ኢኮኖሚ ተራድኦ ምክር ቤት አማካይነት አባል በሆኑ ሶሻሊስት ሀገሮች መካከል በልዩ ልዩ የኢኮኖሚ መስኮች በተለይም በምርት ተግባር የጠበቀ ግንኙነት እየተፈጠረ ነው ። የአንዱ ሀገር ብሔራዊ ዕቅድ ከሌሎች ሀገሮች ዕቅዶች ጋር በይበልጥ እየተቀናጀና እየተገናዘበ ነው ። ልዩ ልዩ ዓይነት ምርምሮችና የንግድ ሥራዎችም እንደዚሁ እየተቀናጁ ናቸው ። ኢንዱስትሪዎች በኅብረት በመቋቋም ላይ ይገኛሉ ።

(ዓለም አቀፍ የሥራ ክፍፍልን ይመለከቷል።)

## ሶሻሊስት እውንነት
*(Socialist realism)*

እውነታን በአብዮታዊ አመለካከት በማየት ታሪካዊ ሁኔታን በተጨባጭነቱ የሚያንፀባርቅ የሥነ ውበት ግንዛቤ ነው ። ይህ አመለካከት የተጸነሰው በወዝአደሩ ትግል

መፋፋምና በሩሲያ የሶሻሊስት ሂደት አብዮት ውስጥ ነው ። ይህ ሥነ ውበታዊ አመለካከት ለመጀመሪያ ጊዜ በኪነ ጥበብ ሥራዎች ውስጥ ለወዝአደሮች የጀግንነት ቦታና ግዕረግ ሊሰጥ ችሏል ። ሶሻሊስት እውንነት የተመሠረተው ምንጊዜም ለሕይወት ታማኝ በመሆን ላይ ሲሆን ይህም ታማኝነት ኮሚኒስታዊ አመለካከት ባዘሉ የኪነ ጥበብ ሥራዎች ይገለጻል ። ለኮሚኒስት ርዕዮተዓለም ታማኝ ፣ ለሕዝብ ወገናዊና አገልጋይ መሆን ፣ ሶሻሊስት ሰብአዊነትንና ዓለም አቀፋዊነትን ማራመድ ፣ ቅርፃዊነትንና ኀሊናዊነትን መቃወምና ምንጊዜም ባለሙሉ ተስፋ ሆኖ መገኘት የሶሻሊስት እውንነት መሪ አስተሳሰቦች ናቸው ።

ሶሻሊስት እውንነትን ተግባራዊ ለማድረግ ስለሰው ኑሮ ፣ ስለሰው አስተሳሰቦችና ስሜቶች ጥልቀት ያለው ዕውቀት ከማስፈለጉም በላይ ማንኛውንም አዲስ የኑሮ ሁኔታን መቀበልና በጥሩ ኪነ ጥበባዊ ምስል መቅረፅ መቻል አስፈላጊ ይሆናል ። ይህ ሲሆን ብቻ ነው ሶሻሊስት እውንነት ሰፊውን ሕዝብ ለማስተማር ተወዳዳሪ የሌለው መሣሪያ ሊሆን የሚችለው ።

(ሥነ ውበትን ፣ ኪነ ጥበብን ይመለከቷል።)

## ሶሻሊስት ክምችት

*(Socialist Accumulation)*

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ከሚፈጠረው ብሔራዊ ገቢ ውስጥ የሕዝቡን ንብረት ለማበልጸጊያ ፣ በተለይም ለምርት ሥራ ማስፋፊያና ለሕዝቡ የኑሮ ደረጃ የማያቋርጥ ዕድገት ቁሳዊ ቅድመ ሁኔታዎችን ለመፍጠሪያ የሚውል ሀብት ነው ። የሶሻሊስት ክምችት ምንጭ ምርት እንደመሆኑ ሁሉ የሚውለውም የሶሻሊስት ኢኮኖሚን የተስፋፋ እርባታ ሂደት ለማጠናከር ነው ።

የሶሻሊስት ክምችት ሂደት የሚጀምረው ሠራተኛው ሕዝብ ሥልጣን ከያዘበት ወቅት እንሥቶ ነው ። በዚህ ረገድ በመጀመሪያ ትላልቅና ዘመናዊ የኢንዱስትሪ ተቋሞችን በመንግሥት ይዞታ ሥር በማዋል አንድ ዋና የሶሻሊስት ክምችት ምንጭ ይፈጠራል ። የሶሻሊስትን ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስፈልጉትን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሁኔታዎች ለማሟላት በሚደረገው ረዥም የሽግግር ወቅትም በልዩ ልዩ ዘዴዎች አማካይነት የሶሻሊስትን ክምችት የማጠናቀሩ ሂደት ይከናወናል ።

ክምችት በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ በተቀነባበረና ሥርዓት ባለው መንገድ በተረፈ ምርት በሚገባ መጠቀምን የሚጠይቅ ነው ። የሶሻሊስት ክምችት ማደግ በመሠረቱ ከሥራ ምርታማነት ማደግና ተጨማሪ አምራች ሠራተኞችን በኢኮኖሚው ውስጥ ከማሰማራት ይመነጫል ። የዚህም የሶሻሊስት ክምችት ወይንም የማምረት ችሎታ መስፋፋትና በኢኮኖሚው ልዩ ልዩ ክፍሎች ውስጥ የሚኖረው የስርጭት ሁኔታ በማዕከላዊ ዕቅድ አማካይነት ተቀናጅቶ የሚካሄድ ነው።

ሶሻሊስት ኢኮኖሚ በማዕከላዊ ዕቅድ እየተመራ የሚያሳየው የማያቋርጥ ዕድገት ከሶሻሊስት ክምችትም ማደግ ጋር የተያያዘ ነው ። ከሶሻሊስት ኢኮኖሚ ባሕርያት አንዱ የክምችት ዕድገት መጠን በኢኮኖሚው ውስጥ ከሚሰማራው የሰው ኃይል ዕድገት መጠን የበለጠ መሆኑ ነው ። ይህም ለሥራ የደረሰውን ዜጋ በሙሉ በሥራ መስክ ለማሰማራት ያስችላል ።

ለክምችት የሚውለው ሀብት መጠንና ለሕዝቡ ፍጆታ የሚውለው ሀብት መጠን በየጊዜው በተገቢው መንገድ በብሔራዊው ዕቅድ ይወሰናል ። ለምሳሌ ባሁኑ ጊዜ በዳበሩት የሶሻሊስት ሀገሮች ውስጥ ከብሔራዊ ገቢ ውስጥ በአማካይ ከ20 — 30% ለክምችት ሲውል ቀሪው ለሕዝቡ ፍጆታ ይውላል ። ይህም የኢኮኖሚውን ያለማቋረጥ ማደግና የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ያለማቋረጥ መሻሻል በተግባር ለማረጋገጥ የሚያስችል ነው ።

በሶሻሊስት ክምችት ዕድገት ላይ ተፅዕኖ ከሚያደርጉ ሁኔታዎች ውስጥ የሥራ ምርታማነት ፣ በምርት ሥራ የተሰማራው የሰው ኃይል መጠን ዕድገት ፣ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለው ለምርት ተግባር የሚውል ሀብት ዕድገት ፣ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕድገት ፣ ለምርት ተግባር የሚውለውን ሀብት ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ የመጠቀም ችሎታ ናቸው ።

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ለክምችት የሚውለው ሀብትና ለሕዝቡ ፍጆታ

የሚውለው ሀብት ማኅበራዊ ባሕርይ አንድ ነው ። በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የሚካሄደው የተስፋፋ እርባታ ተጨማሪ የማምረቻ መሣሪያዎችንና የፍጆታ ሸቀጦችን ለማግኘት ያስችላል ፤ የተገኘው ተጨማሪ የማምረቻ መሣሪያ ደግሞ ለአዳዲስ የምርት ሥራዎች ሲውል የክምችት መጠን ብቻ ሳይሆን የፍጆታ ዕቃዎችም ምርት ያድጋል ። በዚህ አኳኋን የሶሻሊስት ኢኮኖሚ የተስፋፋ እርባታና ክምችት በየጊዜው እያደገ የሚሄደውን የኅብረተሰቡን ፍላጎት ማርኪያ መሣሪያ በመሆን ያገለግላሉ ።

ወደ ሶሻሊዝም በሚደረግ የሽግግር ወቅት በተለይ መንግሥታዊና የኅብረት ይዞታዎችን በማስፋፋትና በማጠናከር እንዲሁም በእነዚሁ ይዞታዎች ውስጥ ምርታማነትን በማሳደግ ክምችትን ማዳበር እጅግ አስፈላጊ ነው ። በሽግግር ወቅት መንግሥት ከግል ይዞታ ልዩ ልዩ ዘርፎች በታክስና በሌሎችም ዘዴዎች አማካይነት የሚያገኘውም ሀብት እንደሌላ የክምችት ምንጭ ሆኖ ለሶሻሊስት ኅብረተሰብ ግንባታ ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት ለመጣል ማገልገል ይኖርበታል ።

## ሶሻሊስት ክፍፍል መርህ (የ—)

*(Principle of Socialist Distribution)*

የሶሻሊስት ክፍፍል መርህ "ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው" የሚል ነው ።

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ አንድ ሰው በኅብረተሰብ ውስጥ የሚኖረውን ቦታና የኑሮ ሁኔታ የሚወስነው የሥራ ውጤት ብቻ ነው ። እያንዳንዱ የኅብረተሰብ አባል ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን ዕቃዎች የሚያገኘው በሥራው አሰተዋጽኦ መጠንና ጥራት መሠረት ይሆናል ፤ ይህም የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ሕግ ነው ። በሶሻሊዝም ያለው የሀብት ክፍፍል "ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያንዳንዱ እንደሥራው" በሚለው መርህ ላይ የተመሠረተበት ምክንያት የምርት ኃይሎች በሚፈለገው ደረጃ ያልዳበሩ በመሆናቸው በገጠርና በከተማ ፣ በአእምሮና በጉልበት ሥራ ፣ በሠለጠነና ባልሠለጠነ ጉልበት መካከል ያለው ልዩነት ባለመወገዱ ነው ።

ይህ መርህ ሳይሠሩ ይኖሩ ለነበሩት ቦታ የማይሰጥ ፣ ብዙ ለማግኘት የበለጠ ለመሥራት ፍላጎት የሚያሳድር ፣ የሠራተኛውን ችሎታ የሚያሻሽልና የነፍስ ወከፍ ምርት እንዲጨምር የሚያበረታታ ፣ የአሠራርን ቴክኒክ የሚያሻሽልና የሶሻሊስትን የሥራ ዲሲፕሊን የሚያስተምር ነው ።

ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያ በሚለው የሶሻሊስት የክፍፍል መርህ ላይ የፆታ ፣ የዕድሜ ፣ የዘርና የብሔረሰብ ልዩነት ምንም ዓይነት ተፅዕኖ አይኖረውም ፣ ክፍፍል እንደ ሥራ መጠን ቢሆንም የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ዕድገት እንዲንቀሳቀስና እንዲበለጽግ የኅብረተሰቡ አባላት የተመረተውን ምርት ሙሉ በሙሉ አይከፋፈሉም ። እያንዳንዱ በሥራው መጠን የሚከፈለው ከሚገኘው ጠቅላላ ምርት ውስጥ የኅብረተሰቡን ፍላጎት ለማሟላት ለሚያስፈልጉ ጉዳዮች ለምሳሌ ተጨማሪ ምርትን ለማስፋፋት ፣ የምርት መሣሪያዎችን ለመጠገን ፣ ለመጠባበቂያ ፣ ትምህርት ቤቶችን ፣ ሆስፒታሎችን ወዘተ... ለማካሄድና ለማስተዳደር ፣ መሥራት የማይችሉትን ሰዎች ለመደገፍና ኅብረተሰቡን ከጠላት ለመከላከል የሚያስፈልጉ ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ ነው ።

## ሶሻሊዝም

*(Socialism)*

የኮሚኒስት ሥርዓት የመጀመሪያው ምዕራፍ የሆነና የወዝአደሩ መደብ ፖለቲካዊ ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ የበላይነት የሚረጋገጥበት ሥርዓት ነው ። በመሆኑም ሶሻሊዝም ክፍተኛ የሆነ የመደብ ትግል የሚካሄድበት ምዕራፍ ነው ።

ሶሻሊዝም ከሌሎች ሥርዓቶች የሚለየው በካፒታሊዝም ውስጥ የበታችና ተበዝባዥ የነበረው የወዝአደር መደብ ገዥ መደብ መሆኑ ነው ። በሕዝባዊ አመፅ የሚመጣና ለመጀመሪያ ጊዜ ለሠራተኛው ሕዝብ ጥቅምና ነፃ መውጣት የቆመ ሥርዓት በመሆኑ በወዝአደሩ መሪነት ብዙኀኑን የሚያቅፍ ነው። በዚህ ባሕርዩ ሶሻሊዝም አዲስ የሆነ የመንግሥት ፣ የማኅበራዊ ኑሮና የኢኮኖሚ አደረጃጀቶችን እንዲሁም መንፈሳዊ አመለካከቶችን ያዘለ ነው ።

በፖለቲካዊ አደረጃጀት የሶሻሊዝም ዓይነተኛ ባሕርይ ዲሞክራሲ በቡርዧ ሥር ዓት ውስጥ ከነበረው ቅርፃዊነት ተላቆ ሠራ ተኛው የበላይነቱን የሚያረጋግጥበት መሣሪያ መሆኑ ነው ። ዲሞክራሲ ሠራተኛው ሕዝብ ከጭቆናና ከብዝበዛ የሚላቀቅበት ማለትም በበዝባዥ መደቦች ላይ የበላይነት ኖሮት እነ ሱን የሚደመስስበት የፖለቲካ መሣሪያ ነው። ይህ ዲሞክራሲ በዓላማውም ሆነ በአሠራሩ የሚያረጋግጠው መንግሥት የብዙኀኑ መሆኑን ነው ። መንግሥት ለጥቂቶች የሚቆም ኃይል መሆኑ መቅረቱ አዲስ ባሕርይ ፣ አደረጃጀ ትና ተልዕኮ ይሰጠዋል ።ፀረ ሕዝብ ኃይሎ ችን የሚዋጋና የሚጨቁን በመሆኑ መንግሥት ነው ፤ ለብዙኀኑ የቆመ በመሆኑ ደግሞ በመ ክሰም ሂደት ውስጥ ያለ መንግሥት ነው ። ይህም ባሕርይ በትክክል የሚገለጸው መን ግሥት ያለውን ሥልጣን ደረጃ በደረጃ ወደ ሕዝባዊ ድርጅቶች በማስተላለፉ ሂደት ነው። በቡርዧው መንግሥት ውስጥ የአስፈጻሚ ፣ የሕግ አውጪና የሕግ አስከባሪ ሥልጣኖች የተከፋፈሉና ጠቅላላ አሠራራቸው ከላይ ወደ ታች የሚሄድ በመሆኑ ከሕዝብ ቁጥጥር ውጭ ናቸው ። በሶሻሊዝም ውስጥ የፖለ ቲካ ሥልጣን የሚመሠረተው በሕዝብ ቀጥ ተኛ ተሳትፎ በመሆኑ በየደረጃው የሦስቱ ሥልጣኖች ውህደት ይታያል ። ይህም የሚ ያሳየው መታዘዝና ተገዥ መሆን በራስ አስ ተዳደር ሂደት እየተተካ መምጣቱን ነው ። የሶሻሊስት መንግሥት ዓይነተኛ ጠባይ ሥልጣን ወደ ራስ አስተዳደር መለወጥ በመሆኑ የቢሮክራሲን ቀስ በቀስ የመጥፋት ሁኔታ ያመቻቻል ። ሥልጣንም ስለማይከ ፋፈል በየደረጃ በምርጫ የተመሠረቱት የአ መራር ክፍሎች በሕዝብ ቁጥጥር በየጊዜው የሚለኩ ናቸው ። በየደረጃው የሚገኙ መን ግሥታዊና ሕዝባዊ የአመራር ሥርዓቶች የሚመሩት በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ነው። ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት የሚያረጋግጠው የሶሻሊዝምን መርህ ማለትም የጥቂቱ ለብዙኀኑ ውሳኔ ተገዥ መሆንን ሲሆን ብዙኀኑ በፀረ ሕዝብ ኃይሎች እንዳይከፋፈሉ የሚያደርግና በዲሲፕሊን ላይ የተመሠረተን አንድነት የሚ ያጐለብት የአሠራር ስልት ነው ። በዚህ ፖለቲ ካዊ አደረጃጀት ውስጥ የወዝአደሩ ፓርቲ ቦታና ኃላፊነት በታሪካዊው ሚና አንፃር ይወሰናሉ ። ፓርቲውም የመደቡን ግንባር ቀደም ኃይሎች የሚያቅፍ በመሆኑ የወዝአደሩን መደብ ታሪ ካዊ ሚና ማለትም የመደብ አልባ ኅብረተ ሰብን አመሠራረት ከግብ ለማድረስ የሚ ያስፈልጉትን ንድፈ ሐሳባዊ መመሪያዎችን የሚሰጥና ስትራቴጅንና ታክቲኮችን የሚቀይስ ነው ። ፓርቲው በመንግሥት ሕጋዊና አስ ተዳደራዊ መዋቅሮች በመጠቀም የሠራተ ኛው ሕዝብ ዘላቂ ግብ እውን እንዲሆን አመራር ይሰጣል ማለት ነው ።

በኢኮኖሚያዊ አደረጃጀቱ ሶሻሊዝም የሚሻው ሠርቶ አደሩን ከጭቆና በማላቀቅ ኢኮኖሚያዊ ነፃነትን ማጐናፀፍ ነው ። ይህ ዓላማ በሁለት ዓበይት እርምጃዎች ይከናወ ናል ። እነሱም የማምረቻ መሣሪያዎችን ከግል ወደ መንግሥት ይዞታ በመለወጥ ለአጠቃላዩ ኅብረተሰብ ዕድገት የሚረዱ የምርት ግንኙነቶች መመሥረትና የምርት ኃይሎችን በአፋጣኝ በማሳደግ ወደ ኮሚኒ ዝም ለመሸጋገር የሚያስችል አስፈላጊ ቁሳ ዊና ቴክኒካዊ መሠረት መጣል ናቸው ።

የማምረቻ መሣሪያዎችን በመንግሥት ይዞታ ሥር ማድረጉ በአንድ በኩል የቡር ዧዚውን የኢኮኖሚ ሥልጣን ለመስበር የሚ ጠቅም ሲሆን በሌላ በኩል በሚፈጥረው የማሰባሰብና የቁጥጥር ችሎታ ምርት በማ ዕከላዊ ዕቅድ እንዲመራና ዕቅዱም ከሕዝብ ፍላጎት አንፃር እንዲነደፍ ያደርጋል ። የኅ ብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊ ኑሮ በገበያ ሕግ መገዛቱ ያቆማል ማለት ነው ። የማምረቻ መሣሪያዎችን ከግልና ግቡ ትርፍ ከሆነ ይዞታ ማላቀቁ በተራድኦ የሚመሩ የምርት ግንኙነቶችን ለመመሥረት ያስችላል ። ወዝአ ደሩ ለግል ጥቅምና ለትርፍ መሥራቱ ስለሚ ያበቃ የሥራ ኃይሉን ሻጭ መሆኑም አብሮ ይቀራል ። ከዚህም ጋር የብዝበዛው ሁኔታ ያከትማል ። ወዝአደሩ የኅብረተሰቡ ሙሉ አካልና የሚሠራውም ለአጠቃላይ የኅብረ ተሰቡ ብልጽግና በመሆኑ በሚያደርገው አስ ተዋጽኦ መጠን ድርሻውን ያገኛል ። ይህ ድርሻ በፍጆታ ብቻ ሳይሆን በአገልግሎ ትም (ነፃ ሕክምና ፣ ነፃ ትምህርት ወዘተ...) የሚተረጎም ነው ።

በሶሻሊዝም የምርት ኃይሎችን በአፋ ጣኝ የማሳደጉ ሁኔታ እውን ሊሆን የሚ ችልበት ዋናው ምክንያት የምርት ኃይሎ

ችና የምርት ግንኙነቶች ተፃራሪ መሆና ቸው ቀርቶ ተራድኦአዊ ግንኙነት ሁለቱን ተደጋጋፊ ኃይል ስለሚያደርጋቸው ነው ። የምርት ግንኙነቶች ከብዝበዛ በመላቀቃ ቸው ፣ ሠራተኛው ለራሱ ጥቅም እንዲያመርት በማድረጋቸውና በአሠራራቸው ሰዎችን የሚያሰባስቡና የወል ኃይል የሚፈጥሩ በመሆናቸው የምርት ኃይሎችን የማሳደግ ሚና አላቸው ። የምርት ኃይሎችን የሚያንቀሳቅሰው የግለሰብ ጥቅም ሳይሆን አጠቃላይ የኀብረተሰቡ ፍላጎት በመሆኑ የዕድገት ግፊት ያንኑ ያህል የሚያይል ነው። በመንግሥት ይዞታ አማካይነት ምርት በአጠቃላይና በማዕከላዊ ዕቅድ መመራት መቻሉ ሳይንሳዊ የሆነ የአሠራር ዘዴ ስለሚቀይስ ለአፋጣኝ ዕድገት ሌላው መንሥኤ ነው ።

በመንፈሳዊ ኑሮ ረገድ ሶሻሊዝም የሚመራው በአንድ ዓቢይ ጉዳይ ነው። ይህም ብዙኃኑ ራሱን በራሱ ለማስተዳደር የሚችልበትን አመለካከት መስጠት ማለትም የሕዝቡን ንቃተ ኅሊናና ባህል ከፍተኛ ደረጃ ላይ ማድረስ ነው ። የተራድኦ ግንኙነት በሚፈቅደው መሠረት የጉልበትና የአእምሮ ሥራ በይበልጥ እንዲቀራረቡ ማድረግ መቻሉ የሠራተኛውን ሕዝብ ዕውቀትና ባህል ለማሳደግ አመች ሁኔታ ይፈጥራል ። የጉልበት ሥራንና ዕውቀትን በምርት ከንዋኔ ውስጥ ለማዋሃድ የሚደረገው ጥረት ትምህርት የጥቂቶች የተለየ መብት እንዳይሆን ያደርጋል ። ይህ ትምህርት በአጠቃላይ የሚመሠረተው በማርክሲዝም ሌኒኒዝም አመለካከት ላይ ሲሆን የባህል ማሳደጉ ሁኔታ እውን የሚሆነው የሰው ልጅ እስካሁን በሥነ ጽሑፍ ፣ በኪንጥበብ ፣ በሳይንስ ፣ በፍልስፍና ወዘተ… ካከማቻቸው ምርጥ ሥራዎች ጋር ሕዝቡ ትውውቅ ሲኖረው በመሆኑ ትምህርቱ ሁለንታዊ ቅርፅና ይዘት ይኖረዋል ። የዚህ ባህል ቁም ነገር ሰው ፣ ተገዥና ግላዊ ከሚያደርጉት ልምዶችና አመለካከቶች ተላቆና ግዴታውንና መብቱን በትክክል አገናዝቦ የራሱ አስተዳዳሪ ሊሆን የሚችል ማኅበራዊ ግለሰብን መፍጠር ነው ። ለዚህ ባህል መሠረት የሆነው ተራድኦአዊ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ትምህርት ለሁሉ እንዲዳረስ የሥራ ጊዜን የመቀነስ ሁኔታን ደረጃ በደረጃ እውን ያደርገዋል ።

## ሶቅራጥስ
*(Socrates)*

ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ469—399 የኖረ ጥንታዊ ሐሳባዊ የግሪክ ፈላስፋ ነው ። ሶቅራጥስ ፍልስፍናውን በጽሑፍ አስፍሮት ባይገኝም እንደነአፍላጦንና እንደነአርስጣጣሊስ ያሉትን ብዙዎቹን ጥንታዊ የግሪክ ፈላስፎች ስላስተማረ ፍልስፍናው በእነዚሁ ፈላስፎች አማካይነት ሊታወቅ ችሏል

ሶቅራጥስ ከታወቀባቸው ዓበይት ጉዳዮች አንደኛው የፍልስፍና ዋና ነጥብ ተፈጥሮን ማጥናት ሳይሆን ስለሰው ማወቅ ነው የሚለው ሲሆን ፣ ሁለተኛው ደግሞ "እኔ የማውቀው አለማወቄን ነው" በማለት ስለሁሉ ነገር መጠየቅን የፍልስፍናው መሠረት ማድረጉ ነው ።

የዕውቀት ዓላማ ንድፈ ሐሳባዊ ሳይሆን ተግባራዊ ነው ፤ ለበጎ ተግባር ምንጩ ሰው ራሱን ማወቁ ነው ብሏል ። ይህ ዓይነቱ የመጠየቅ አዝማሚያ የፍልስፍናን የአጠናን ዘዴ ወደ ጥያቄና መልስ ማለትም ወደ ውይይት እንዲያመራ አድርጎታል ። በውይይትም ወቅት ቅራኔዎች ይገለጣሉ ፤ ስህተቶችም ይወገዳሉ ፤ እርግጠኛ አለመሆንና አለመርካት የሐቀኛ እውነት ፍለጋ መሠረት ነው የሚል አጠቃላይ አስተሳሰብ ነበረው ።

ሰዎች በራሳቸው ከፉ አይደሉም ፤ ምክንያቱም ክፋት የሚመነጨው ከድንቁርና በመሆኑ ክፋት በዕውቀት ሊጠፋ ይችላል የሚል አመለካከት ነበረው ።

ሶቅራጥስ የጥያቄ አቀራረቡና አመለካከቱ ቀኖናዊ አስተሳሰቦችን የሚተችና ልማዳዊ አስተሳሰቦችን የሚያፋልስ በመሆኑ በነበሩት ባለሥልጣናት የሞት ፍርድ ተፈርዶበታል ። ሆኖም በወቅቱ የነበረውን ሐሳባዊ አመለካከት የሚቃወም አልነበረም ። እንዲያውም በእግዚአብሔርና በነፍስ ዘለዓለማዊነት የሚያምን ስለነበር ሐሳባዊ ፍልስፍናን አጠናክሯል ።

(አፍላጦንን ይመለከቷል ።)

## ሶቪዬት
*(Soviet)*

ሶቪዬት ማለት በሩሲያኛ ትርጉሙ ምክር ቤት እንደማለት ነው ። ይህ ቃል በፖለቲካ ይዘቱ ተግባራዊ መሆን የጀመረው

በ1905ቱ የሩሲያ አብዮት ወቅት ሲሆን አጠቃቀሙም በአብዮቱ ሂደት የሠራተኛው ንቅናቄ እየተስፋፋ ይህንኑ ንቅናቄ የሚያስተባብሩ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች በተፈጠሩበትና እነዚህም ቀስ በቀስ ወደ ሠራተኞች ምክር ቤቶች እያደጉ በመጡበት ወቅት ነው ።

ይህ ሁኔታ በ1917ቱ የየካቲት አብዮት ይበልጥ የተደራጀ መልክ በመያዝ አዳዲስ የሠራተኛውና የመለዮ ለባሾች ምክር ቤቶች ተወካዮች ተመርጠው በኋላም እነዚህ በበኩላቸው የመላ ሩሲያን ጉባኤ ሊጠሩ ችለዋል ። ይህም ጉባኤ "ሥልጣን ሁሉ ለሶቭዬቶች" የሚለውን የቦልሼቪኮች መፈክር በማጽደቅ የአዲሱን ሥልጣን መሠረት ጣሏል ።

አዲሱ የሶሻሊስት መንግሥት ሲመሠረት ደግሞ እነዚህ ሶቭዬቶች ከታችኛው የአስተዳደር እርከን እስከላይኛው በሚዘልቀውና እንደፒራሚድ በሚዋቀረው የመንግሥቱ አመራር የሥልጣን አካላት ውስጥ የምርጫ ኃላፊነት በመያዝ ፣ በአጠቃላይም የሠራተኛውን መደብዊ አደረጃጀት ወደ መንግሥታዊ አደረጃጀት በማሸጋገር የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት መግለጫ ዋና መዋቅር ሆነዋል።

በ1917 የቄሳሩ መንግሥት ከተገረሰሰ በኋላ እስከ ጥቅምት ወር ድረስ ጊዜያዊ የቡርዧ መንግሥት ቢቋቋምም በሌላ በኩል ሶቭዬቶች በመጠናከር ሥልጣኑን በጋራ ይዘው ቆይተዋል ። በመጀመሪያ ደረጃ ላይ በሶቭዬቶች ውስጥ በብዛት የነበሩ ሜንሼቪኮችና ሶሻሊስት አብዮታውያን ሶቭዬቶች ጊዜያዊውን መንግሥት ለመቆጣጠር የሚረዱ ዲሞክራሲያዊ መድረኮች ብቻ እንደሆኑ አድርገው በመቆጣጠር ሥልጣን እንዳይወስዱ ይከላከሉ ነበር ። በሰኔ ወር የመጀመሪያው የመላ ሩሲያ ሠራተኞችና መለዮ ለባሾች ሶቭዬቶች ጉባኤ ተካሄደ በኋላ ግን ሁኔታው ተለወጠ ። በሌኒን የሚመራው የቦልሼቪክ ፓርቲ "ሥልጣን ሁሉ ለሶቭዬቶች" የሚለውን አቋም በማጠናከሩና ይህም በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነትን በማግኘቱ በኅዳር ወር መጀመሪያ ላይ የተደረገው ሁለተኛው የመላው ሩሲያ ሶቭዬቶች ጉባኤ የሕዝባዊ ኮሚሳሮች ምክር ቤት የመንግሥቱን ሥልጣን እንዲይዝ ሲያደርግ ፣ ሌኒንንም የዚሁ ምክር ቤት ሊቀመንበር አድርጎ መረጠው ። ከዚህ በኋላ የቀጣናና የአካባቢ ሶቭዬቶችም ይዘት ተለውጦ የመንግሥቱ ሥልጣን መዋቅር ዘርፎች ሆኑ ።

ሌኒን በአንድ ወቅት ስለሶቭዬቶች እንዳመለከተው ሶቭዬቶች የመንግሥቱ ተግባራት መምሪያና ማስፈጸሚያ አዲስ መሣሪያዎች ናቸው ። ሶቭዬቶች ግንባር ቀደሙ ድርጅት ቀድሞ ከፖለቲካ ሕይወትና ከታሪክ ተገልለው የቆዩትን ጭቁን መደቦችን ለማነሣሣት ፣ ለማሠልጠን ፣ ለማስተማርና ለመምራት የሚችልባቸው መሣሪያዎች ሲሆኑ ፣ በውስጣቸው የሚያገለግሉትም ሠራተኞች በሕዝቡ የተመረጡ ፣ ሲያስፈልግም ያለምንም ቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረድ በሕዝቡ ፈቃድ የሚሻሩ ስለሆነ ፣ ይህ አሠራር ቀድሞ ከነበሩት ሁሉ ዲሞክራሲያዊ ነው ።

በነዚህ የአብዮቱ ዓመታት በሌሎችም የአውሮፓ ሀገሮች አብዮታዊ እንቅስቃሴዎች ተስፋፍተው ስለነበር የሶቭዬቶችም አሠራር በተለያዩ ገጽታዎች ተንፀባርቋል ። በተለይም በጀርመን ፣ በኦስትሪያ ፣ በሀንጋሪ ፣ በመጠኑም በእንግሊዝ ሶቭዬቶችን በማቋቋም ልዩ ልዩ የኅብረተሰቡን ክፍሎች ለአብዮታዊ ትግል ለማደራጀት ተሞክሯል ። ሆኖም በእነዚህ ሀገሮች የሶቭዬት አደረጃጀት ከዳር ሊደርስ አልቻለም ። በቻይናም በሕዝባዊው አብዮት ሂደት ውስጥ የሩሲያው የሶቭዬቶች ልምድ በሰፊው ጥቅም ላይ ውሏል ።

ዛሬ በሶቭዬት ኅብረት ውስጥ ሶቭዬቶች እንደፒራሚድ ከታች እስከላይ በተዋቀረ አደረጃጀታቸው የመንግሥት ሥልጣን ዋነኛ መዋቅር ናቸው ። ይህም መዋቅር ከመሠረታዊ መንደሮች ተነሥቶ በከተሞች ፣ በወረዳዎች ፣ በአውራጃዎች ፣ በቀጣናዎች ፣ በሪፑብሊኮች ከዚያም በብሔራዊ ደረጃ እስከ መላ ሶቭዬት ኅብረት ሶቭዬቶች ጉባኤ ድረስ ይዘልቃል ። በያንዳንዱ ደረጃ የሶቭዬቶቹ ጉባኤ ደረጃውን ጠብቆ ሙሉ የሕግ አውጪነትና አስፈጻሚነት ሥልጣን አለው ። ይህንንም ሥልጣን በአጠቃላይ ጉባኤዎች መካከል ባለው ጊዜ ተግባራዊ የሚያደርጉት በጉባኤው የሚመረጡት አስፈጻሚ አካላት ናቸው ።

(ዲሞክራሲን ፣ መንግሥትን ፣ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን ይመለከቷል ።)

## ሶቭዬት ኅብረት ኮ. ፓርቲ (የ—)
*(Communist Party of the Soviet Union)*

የሶቭዬት ኅብረት የሠራተኛው መደብና የመላው ሶቭዬት ሕዝብ ከፍተኛው የፖለቲካ ድርጅት ነው ። የሶቭዬት ኅብረት ኮሚኒስት ፓርቲ (ሶ. ኅ. ኮ. ፓ) የሶቭዬት ኅብረት ርዕዮተዓለማዊና ፖለቲካዊ ግንባር ቀደም መሪና አንቀሳቃሽ ኃይል ፣ የኅብረተሰቡ የፖለቲካ ሥርዓት ማዕከል ፣ የሁሉም መንግሥታዊና ሕዝባዊ አካሎች እምብርት ነው። ሶ.ኅ.ኮ.ፓ. በፈቃደኝነት ላይ በተመሠረተ ሁኔታ ከሠራተኛው መደብ ፣ ከኅብረት አርሻ አርሶ አደሮች ፣ ከምሁራንና ከተቀሩትም ሠርቶ አደር ክፍሎች በፖለቲካ ንቃታቸውና በሙያ ብቃታቸው የታወቁትንና ለኮሚኒዝም ዓላማ ጽኑ አቋም ያላቸውን ሠርቶ አደሮች በማሰባሰብ ለአንድ ዓላማ የሚያታግል ነው ።

ሶ. ኅ. ኮ. ፓ. የተመሠረተውና የተደራጀው በሌኒን ነበር ። በ1898 የመጀመሪያው ጉባኤ ከተካሄደ በኋላ የሩሲያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ሌበር ፓርቲ በሚለው ስም ሲጠራ ቆይቶ በሁለተኛው ጉባኤ ላይ በቦልሼቪኮችና በሜንሼቪኮች መካከል በተከሰተው ልዩነት ምክንያት ቦልሼቪኮች ከአድርባዮቹ ሜንሼቪኮች ራሳቸውን ለመለየት ፓርቲውን የሩሲያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ሌበር ፓርቲ (ቦልሼቪክ) ብለውት ነበር ። ኋላም የሩሲያ ኮሚኒስት ፓርቲ (ቦልሼቪክ) የመላ ኅብረት የቦልሼቪኮች ኮሚኒስት ፓርቲ ተብሏል ። በዚህ ዓይነት ስያሜውን ከአብዮቱ ዕድገት ጋር በማጣጣም መጥቶ የዛሬ ስሙን ያገኘው በ1952 በተደረገው የፓርቲው 19ኛ ጉባኤ ላይ ነበር ።

በሁለተኛዉ ጉባኤ 1903 ላይ የጸደቀው የፓርቲው የመጀመሪያ ፕሮግራም ዓላማ አድርጎ የተነሣው በሩሲያ ሶሻሊስት አብዮትን ማካሄድና የወዝአደሩን የበላይ ገዥነት መመሥረት ነበር ። ከ1917ቱ ታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት በኋላም በ8ኛው ጉባኤ (1919) የሶሻሊስት ግንባታ ፕሮግራም ፣ ከዚያም በ22ኛው ጉባኤ (1961) ለሶቭዬት ኅብረት የኮሚኒዝም ግንባታ ፕሮግራም በማውጣት ተግባራዊ አድርጓል ።

በ1981 የተካሄደው 26ኛው የፓርቲ ጉባኤም አሁን በሥራ ላይ ያለው ፕሮግራም ተሻሽሎ በውስጥ በሀገሪቱ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሕይወት ላይ የታዩትን ለውጦች ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃም በሰላም አብሮ የመኖር ፖሊሲ ሂደት ውስጥ ያጋጠሙትን ችግሮች እንዲሁም ከዚህ አንፃር የፓርቲውን የረጅም ጊዜ ተግባሮች የሚጠቁም አዲስ የፕሮግራም ረቂቅ እንዲዘጋጅ ወስኗል ።

ሶ.ኅ.ኮ.ፓ. የሩሲያን ወዝአደሮችና ደሃ ገበሬዎች በቄሳሩ የዘውድ አገዛዝና በካፒታሊስቶች ላይ አነሣሥቷል ። ይህም ትግል በጥቅምቱ ሶሻሊስት አብዮት ድል ማድረግ ግቡን መትቷል ። በፓርቲው መሪነት የሶቭዬት ሠራተኛ መደብ አጋር በሆነው በአርሶ አደሩ በመታገዝ በውስጥ ፀረ አብዮተኞችና በኢምፔሪያሊስቶች ከተቀነባበረው ወረራና የአብዮት ቅልበሳ ሴራ በአሸናፊነት ሊወጣ ችሏል ። በሰጠውም አብዮታዊ አመራር የሰው በሰው መበዝበዝ በሀገሪቱ ውስጥ አክትሟል ፤ ሶሻሊስት ኢንዱስትሪና የኅብረት እርሻዎች ሊስፋፉና ሊደራጁ ችለዋል። በተካሄደው የባህል አብዮትም የሶቭዬት ሕዝብ ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊና ርዕዮተዓለማዊ አንድነት በጠንካራ መሠረት ላይ ተገንብቷል። በዚህ ኃይሉም ሶሻሊዝምን ለማጥፋት የተነሣውን ፋሺዝምን ለመምታት ችሏል ። የሶቭዬት ሕዝብ የዳበረ ሶሻሊዝም ከገነባ በኋላ በአሁኑ ጊዜ ለኮሚኒዝም ግንባታ ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት በመጣል ላይ ይገኛል ።

በተግባራዊ እንቅስቃሴው ሶ. ኅ. ኮ. ፓ በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ይመራል ። ሥራውንም በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርህ ያከናውናል ። መሠረታዊ ዓላማውም ለሶቭዬት ሕዝብ የተሟላ ዕድገት ማስገኘትና እያደገ የሚሄደውን ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቱን ማርካት ነው ።

ሶ. ኅ. ኮ. ፓ. አመራር የሚሰጠው ከሳይንሳዊ ማኅበራዊ ዕድገት ሕግጋት አንፃር ሕዝቡን በአብዮታዊ አስተሳሰብ በማነፅ ፣ በማደራጀትና በኮሚኒስት ግንባታው በንቃት እንዲሳተፍ በማድረግ እንዲሁም በአባላቱ አማካይነት ሁሉንም መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች አሳምና ፖሊሲውንና ውሳኔዎቹን በማስፈጸም ነው ። ሀገሪቱ የምትመራበት ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲ ሁሉ በፓርቲው አመራር ይወጣል ።

ፓርቲው በማንኛውም ተግባራዊ እን ቅስቃሴው በፕሮግራሙና በደንቡ ይመራል። ከፍተኛ የአመራር አካሉም በየአምስቱ ዓመት የሚሰበሰበው ጉባኤ ሲሆን በጉባኤዎች መካከል አመራር የሚሰጠው ደግሞ ማዕከ ላዊ ኮሚቴው ነው ። ሶ. ኅ. ኮ. ፓ. ወደ 18 ሚሊዮን የሚጠጉ አባላት አሉት ። ከነ ዚህም ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ሠራ ተኞችና አርሶ አደሮች ናቸው ።

ሶ. ኅ. ኮ. ፓ. የዓለም አቀፍ ኮሚኒስት ንቅናቄ አካልና ትልቁ ኃይል እንደመሆኑ ለንቅናቄው መስፋትና መጐልበት ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል ። በውጭ ግንኙነቱ ከእህት ሶሻሊስት ሀገሮች ጋር ያለውን ወዳጅነትና ኅብረት ፣ ከታዳጊ ሀገሮች ጋር ያለውን ትብብር ይበ ልጥ ለማጠናከር እንዲሁም ከካፒታሊስት ሀገ ሮች ጋር በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ ለተ መሠረተ ግንኙነት ግደግ ይታገላል ። ይህም ለዓለም ሰላም ፣ ለሕዝቦች ብሔራዊና ማኅበራዊ ነፃነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ።

(ቦልሼቪክን ፣ ሌኒኒዝምን ይመለከቷል ።)

# ረ

## ረቂቅ ሥራ
*(Abstract Labour)*

በማናቸውም የሸቀጥ ምርት ሂደተ ሥራ ውስጥ የሚፈስው ወይም የሚውለው የሰው የሥራ ኃይል በዓይነት ሳይለይ ረቂቅ ሥራ ይባላል ።

እያንዳንዳቸው የተለያየ ተጨባጭ ሥራ ውጤቶች የሆኑ ሸቀጦች የተለያየ ባሕርይ ቢኖራቸውም ሸቀጦች ሁሉ የወል ባሕርይም አላቸው ። ሸቀጦች ሁሉ በጥቅል የሰው የሥራ ኃይል ማለትም የሰው ልጅ የአእምሮ ፣ የአካልና የሕዋሳት ኃይል ውጤቶች ናቸው ።

ዕቃዎች ሁሉ በጥቅላቸው የሰው የሥራ ኃይል ውጤት በመሆናቸውም ፣ በእያንዳንዱ ዕቃ ወይም ሸቀጥ ውስጥ መጠኑ ይለያይ እንጂ ዓይነቱ አንድ የሆነ ረቂቅ ሥራ አለ ። ይህ በሸቀጦች ውስጥ በዓይነቱ ተመሳሳይ የሆነ የሰው የሥራ ኃይል መገኘት ሸቀጦች ሊለዋወጡ የሚችሉበትን ሁኔታ ይፈጥራል ። ስለሆነም የሸቀጦች የልውውጥ እሴት መሠረት ረቂቅ ሥራ ነው ።

በኅብረተሰብ የዕድገት ታሪክ ውስጥ ረቂቅ ሥራ ህልውናውን ያገኘው ከሸቀጦች ምርት መስፈን ጋር ነው ። በተፈጥሮአዊ ኢኮኖሚ ወቅት የምርት መገልገያዎች በወል በመያዛቸው ፣ አምራቾችም የሥራቸውን ውጤት የሚከፋፈሉት በእኩልነት በመሆኑ የምርታቸውን የልውውጥ እሴት መጠን መተመን አስፈላጊ አልነበረም ። በመሆኑም በዚያን ወቅት ረቂቅ ሥራ እንደ አንድ ፈርጅ ሆኖ ሊከሰት አልቻለም ። ረቂቅ ሥራ ከሸቀጥ ምርት ጋር የተከሰተ እንደ መሆኑ የሸቀጥ ምርት በሚያከትምበት በኮሚኒዝም የዕድገት ደረጃ የሚጠፋ ታሪካዊ ፈርጅ ነው ።

(ተጨባጭ ሥራን ፣ ማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜን ይመለከቷል ።)

## ሩሶ ፣ ዣን ዣክ
*(Rousseau, Jean–Jacques)*

ከ1712 — 1778 የኖረ ፣ ከፈረንሳይ ዘመነ አብርሆት ምሁራን መካከል የግራ ዝንባሌ የነበረው ታዋቂ ሐሳባዊ ፈላስፋ ነው ። ሩሶ በኅብረተሰብ ጥናት ፣ በኪነ ጥበብና በትምህርት መስክ ስፉ የንድፈ ሐሳብ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

በፍልስፍና እምነቱ ቁስአካልና መንፈስ በየራሳቸው ዝንተ ዓለም የሚኖሩ ናቸው ብሎ በማስተማር ሁለታዊነትን አራምዷል። አንዳንድ ግብረገባዊ አስተሳሰቦች በተፈጥሮ ያሉ ቢሆንም ዋናው ዕውቀት በሕዋሳት አማካይነት የሚገኘው ነው ብሏል ።

ኅብረተሰብን በሚመለከት ሩሶ በወቅቱ ተራማጅ አመለካከት ነበረው ። የፊውዳል መደባዊ ግንኙነትንና ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝን አጥብቆ በመቃወም ለቡርዧው ዲሞክራሲ ተከራክሯል ። በተፈጥሮ ሰው ለሰው አጥፊው አይደለም ፤ ሰዎች ሁሉ ሲወለዱ እኩልና ነፃ ናቸው በሚለው አመለካከቱ በሰዎች መካከል ጠብንና መበላለጥን ያስከተለው የግል ሀብት መፈጠር መሆኑን አስተምሯል ። በተጨማሪም በ1762 በጻፈው "ለ ኮንትራ ሶሲያል" በተሰኘው መጽሐፉ የኅብረተሰብ መሠረት ማኅበራዊ ስምምነት መሆኑን ሲያስተምር የግል ሀብት መከማቸት ይህን ስምምነት ወደ ግጭት እንደቀየረው አስረድቷል ፤ ለዚህ ግጭት መፍትሔም የአጠቃላዩን ሕዝብ ፍላጐት የሚያሟላ ከሁሉ በላይ የሆነ መንግሥት ሲቋቋም እንደሆነ ገልጿል ። ሩሶ አሮጌውን የፊውዳል ሥርዓተ ትምህርት በመቃወም ትምህርት ለሥራ ከበሬታ ያለውን ንቁ ዜጋ ማሠልጠን አለበት ብሎ ተከራክሯል ።

ሩሶ በአስተሳሰቡ የሐሳባዊነትንና የንዑስ ከበርቴ ንድፈ ሐሳቦችን አንፀባርቋል ። የኅብረተሰብ ስምምነት መፋለስ ምክንያት የግል ሀብት መሆኑን ቢያምንም የግል ሀብት ሙሉ በሙሉ እንዲጠፋ ሳይሆን በእ

ነስተኛ ይዞታ ብቻ እንዲወሰን በመፈለጉ ከሁሉም ማለትም ከመደብ በላይ የሆነ መንግሥት ሊኖር ይችላል ብሎ በማመኑ ፣ ኅብረተሰብ ተፈጥሮአዊ ሳይሆን በስምምነት እንደሚገኝ አድርጎ በመቁጠሩ ግላዊና የቡርዧ አመለካከቱን አንፀባርቋል ። ቢሆንም በወቅቱ በተጫወተው ተራማጅ ሚና የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መሥራቾች አድንቀውታል ።

## ሪካርዶ ፣ ዴቪድ
*(Ricardo, David)*

ከ1772—1823 የኖረ የብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ዕውቅ ምሁርና በኢንዱስትሪ አብዮት ወቅት በእንግሊዝ የመሬት ከበርቴውን መደብ በመቃወም የቡርዧውን መደብ ጥቅም ያስተጋባ ግምባር ቀደም የቡርዧ ርዕዮተ ዓለም አራማጅ ነው ።

ሪካርዶ ከሀብታም የነጋዴ ቤተሰብ የተወለደ ሲሆን እርሱም ቢሆን ከ1793 እስከ 1812 ድረስ በንግድ ዓለም በተለይም በአክሲዮን ሽያጭና ግዥ መስከ ተሰማርቶ በመቆየት ከሀብታም የእንግሊዝ ነጋዴዎች አንዱ ለመሆን የበቃ ነበር ። ከ1812 ጀምሮ እስከ ዕለተሞቱ ድረስ ግን ስሜቱ ወደፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ጥናት እያዘነበለ በመምጣቱ ጊዜውን በአብዛኛው ለምርምር በማዋል ለማርክሲዝም አንዱ ምንጭ ለሆነው የእንግሊዝ ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ዕውቅ ምሁር ሊሆን በቅቷል ።

የሪካርዶ ዋንኛ ጽሑፍ በ1817 የታተመው "ዘ ፕሪንሲፕልስ ኦቭ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ኤንድ ታክሴሽን" በሚል ርዕስ ያዘጋጀው መጽሐፍ ነው ። የሪካርዶን ሥራ በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሳይንስ ዕድገት ውስጥ ጉልህ ስፍራ የሚያስጠውና ልዩም የሚያደርገው በካፒታሊዝም ውስጥ ያለውን የኢኮኖሚ ግንኙነት የእሴት የሥራ ንድፈ ሐሳብ መሠረትነት ለመመርመር ጥረት ማድረጉና በካፒታሊዝም ውስጥ ያሉ መሠረታዊ መደቦች የሚጋጭ ወይም ተፃራሪ የኢኮኖሚ ጥቅም ያላቸው መሆኑን ለማሳየት መሞከሩ ነው ።

ምንም እንኳን ከላይ እንደተጠቀሰው ሪካርዶ ጥናቱን በእሴት የሥራ ንድፈ ሐሳብ ላይ መመሥረቱ ከአዳም ስሚዝ የሚለየው ቢሆንም ንድፈ ሐሳቡን በሚመለከት አዳም ስሚዝም ገጥመውት የነበሩትን ችግሮች በመፍታት ረገድ ሪካርዶም ያደረገው ወይም ያበረከተው የተለየ አስተዋጽኦ አልነበረም። በተለይም እንደአዳም ስሚዝ ሁሉ ዴቪድ ሪካርዶም ወዝአደሩ ለቡርዧዚው የሚሸጠው ሥራውን ነው ከሚለው የተሳሳተ መንደርደሪያ ሐሳብ የሚነሣ በመሆኑ የቡርዧዚውን የትርፍ ምንጭ በዚህ ንድፈ ሐሳብ ክልል ውስጥ ለመግለጽ አልቻለም ። በተጨማሪም በነፃ ውድድር ካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የካፒታሊስቶች የትርፍ መጠን ከወጣው ካፒታል ጋር በቀጥታ መዛመዱን ከእሴት የሥራ ንድፈ ሐሳብ ጋር ለማጣጣም ሳይችል ቀርቷል ። ከላይ የተጠቀሱትን በንድፈ ሐሳቡ ውስጥ የነበሩትን ተቃርኖች ለመጀመሪያ ጊዜ ያሳየው ካርል ማርክስ ነው ።

ካርል ማርክስ ወዝአደሩ ለቡርዧዚው የሚሸጠው ሥራውን ሳይሆን የሥራ ኃይሉን መሆኑንና ይህም የሥራ ኃይል ሽያጭና ግዥ የሚከናወንበትን ታሪካዊ ሁኔታ በማብራራት በተረፈ እሴት ንድፈ ሐሳቡ ሁኔታውን ግልጽ አድርጎታል ። ቡርዧዚውም የሚያገኘውን የትርፍ መጠን ካወጣው ካፒታል ጋር የማመጣጠኑን ሁኔታ በአማካይ ትርፍና በማምረቻ ዋጋ ንድፈ ሐሳቦቹ ላይ በመመርኮዝ አብራርቶታል ።

ሪካርዶ በውጭ ንግድ ረገድም በእንግሊዝ የኢንዱስትሪ አብዮት ወቅት የኖረ ግለሰብ ስለሆነ እንደአዳም ስሚዝ ሁሉ ለነፃ የውጭ ንግድ ፖሊሲ አጥብቆ ተሟግቷል ። ይህንኑ አቋሙን ለማጠናከርም በውጭ ንግድ ከንዋኔ ውስጥ ከፍፁማዊ ኢኮኖሚ ጥቅም በተጨማሪም በተለያዩ ለውጭ ንግድ በሚቀርቡ ሸቀጦች ምርት ላይ በመሠልጠንም አንፃራዊ የኢኮኖሚ ጥቅም መገኘት መቻሉን በአህዝ በመደገፍ ለማብራራት ሞክሮአል ። ይህንን አንፃራዊ የኢኮኖሚ ጥቅም ንድፈ ሐሳብ ካርል ማርክስ በመርህ ደረጃ ትክክል መሆኑን ጠቁሞአል ።

የገንዘብ ንድፈ ሐሳብንም በሚመለከት ሪካርዶ በጊዜው ከነበሩት የቡርዧ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ምሁራን በላቀ ሁኔታ አብራርቷል ። ወርቅና ብር እንደ ማንኛውም ሸቀጥ ሁሉ እሴታቸው በምርት መስከ እነርሱን ለማምረት በፈሰሰው ማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ

ጊዜ የሚወሰን መሆኑንም አጥብቆ አስገንዝቧል ። ነገር ግን በዝውውር መስክ ያለው የወርቅ ወይም የብር መጠን ከፍ ሲል የሸቀጦች ዋጋ አብሮ ከፍ እንደሚልና አቅርቦታቸው ዝቅ ሲል ደግሞ የሸቀጦችም ዋጋ አብሮ የሚያንስ ነው በማለት እንደነዴቪድ ሂዩም ሁሉ የገንዘብ መጠን ንድፈ ሐሳብን አስተጋብቷል ። በዚህ ረገድ የሪካርዶ መሠረታዊ ስህተት የገንዘብን ተግባር እንደዝውውር መሣሪያነት ብቻ ከመመልከት የመነጨ ነው ።

ሪካርዶ እንደሌሎች የብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ቀደምት ምሁራን ሁሉ ካፒታሊዝም ዘለዓለማዊ የሆነና የራሱ ውስጣዊ መመጣጠን ያለው ቀውስ አልባ ሥርዓት ነው የሚል እምነት ነበረው ። የዚህ እምነት መሠረት ራሱ ካፒታሊዝም ገና በማበብ ላይ የነበረ ሥርዓት እንጂ በስሎ በውስጡ ያቀፋቸውን ቅራኔዎች በገሃድ ማውጣት የጀመረበት ጊዜ አለመሆኑና ለቡርዧው መደብ የነበረው አጠቃላይ ድጋፍ በጥናቱ ላይ ተፅዕኖ ያሳደረበት መሆኑ ይገመታል ። ካርል ማርክስ በካፒታሊስት ክምችትና በእርባታ ሕጐች ላይ በመመርኮዝ ካፒታሊዝም አላፊና ጠፊ እንዲሁም በቀውስም የተወጠረ ሥርዓት መሆኑን አስተምሯል ።ታሪክም ይህንኑ ሐቅ ገሃድ አውጥቶታል ።

## ሪፐብሊክ

*(Republic)*

የአንድ ሀገር መንግሥት ከፍተኛዎቹ የሥልጣን ቦታዎች በምርጫ የሚያዙበት የመንግሥት አወቃቀር ቅርፅ ነው ። ይህም በሁለት መልክ ማለትም በፓርላማ ወይም በፕሬዚዳንት ሥርዓት ይዋቀራል ።

በፕሬዚዳንት ሥርዓት የሚዋቀረው ሪፐብሊክ ፣ ለምሳሌ እንደዩናይትድ ስቴትስ ፣ እንደ አርጀንቲናና እንደ ፈረንሳይ የርዕሰ ብሔርነቱና የርዕሱ መንግሥትነቱ ሥልጣን ተጣምሮ በሕዝብ በተመረጠ ፕሬዚዳንት ይያዛል ። የዚህ ዓይነቱ የመንግሥት አመራር አንዳንድ ጉልህ ባሕርያት አሉት ፤ ለምሳሌ ከፓርላማ ምርጫ በተለየ ሥነ ሥርዓት ፕሬዚዳንቱን የመምረጥና የመንግሥቱን አመራር የማቋቋም ፣ መንግሥቱ ለፓርላማ ያለውን ተጠሪነት የመወሰን እንዲሁም ፕሬዚዳንቱ የፓርላማው የሥራ ጊዜ ከመፈጸሙ በፊት የፓርላማውን አባላት የማሰናበት ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑ ጥቂቶቹ ናቸው ።

በፓርላማ ሥርዓት የሚዋቀረው ሪፐብሊክ ዋነኛ መርህ የመንግሥት ከፍተኛ ሥልጣን የፓርላማው ሆኖ የመንግሥቱ አመራር በጋራ ለፓርላማው ተጠሪ መሆኑ ነው ። በዚህ ሥርዓት የመንግሥት አመራር በሥልጣን ላይ የሚቆየው የፓርላማው አብዛኛው ድምፅ ድጋፍ እስከኖረው ድረስ ብቻ ነው ። ይህን ድጋፍ ሲያጣ የመንግሥቱ አመራር ሥራውን ይለቃል ፤ ወይም በርዕሰ መንግሥቱ አማካይነት ፓርላማውን አሰናብቶ አዲስ የፓርላማ ምርጫ እንዲካሄድ ያስደርጋል ። በፓርላማዊ ሪፐብሊክ መንግሥታዊ አመራሩ የሚመሠረተው በፓርላማ ምርጫ ሥነ ሥርዓት ውስጥ ብቻ ነው ። ይህም ማለት የመንግሥቱ አመራር የሚገኘው በፓርላማ ምርጫው አሸንፈው ከወጡት የሕዝብ እንደራሴዎች መካከል የሚያስፈልጉት ሚኒስትሮች ተወጣጥተው በሚመሠርቱት አካል ነው ። በዚህ መልክ በሚውጣጣው አካል ውስጥ አብዛኛውን ቦታ የሚይዘው መሪው ፓርቲ ወይም ጥምር መንግሥት ነው ። በፓርላማዊ ሪፐብሊክ የጠቅላይ ሚኒስትርነትን ቦታ የሚይዘው ከፍተኛ ድምፅ ያለው ፓርቲ መሪ ነው ። ለዚህም ምሳሌ እንደ እንግሊዝና እንደኢጣሊያ ያሉትን መጥቀስ ይቻላል ።

የሶሻሊስት መንግሥታት በቅርፅ የተለያዩ ስያሜዎች ቢኖሩአቸውም (ለምሳሌ ሶቭዬት ሪፐብሊክ ፣ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ ፣ ሕዝባዊ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ) ሁሉም በሶሻሊስት መርህ የሚመሩና ሕዝባዊ ተሳትፎን በምርጫ ሥርዓት ተግባራዊ የሚያደርጉ ናቸው ። ለምሳሌ በሶቭዬት ኅብረት ሥልጣን የሕዝቡ በመሆኑ ሕዝቡ ይህንኑ ሥልጣን ተግባራዊ የሚያደርገው ከመሀሉ መርጦ በሚልካቸው የሕዝብ ተወካዮች (ሶቭዬቶች) ነው ። እነዚህም ተወካዮች የሶቭዬት ኅብረት ሶሻሊስት ሪፐብሊክን ፖለቲካዊ መሠረት የሚያዋቅሩ ናቸው ። ሌሎች መንግሥታዊና ሕዝባዊ አካሎች ሁሉ በሕዝቡ ተወካዮች ሥር ሲሆኑ ተጠሪነታቸውም ለነሱ ነው ።

## ራስንቃተ ኅሊና
*(Self–Consciousness)*

ሰው ራሱን ከነባራዊው ዓለም ነጥሎ በማየት ስለራሱ ስብእና ፥ ክንዋኔዎች ፥ ስሜቶች ፥ ሐሳቦች ፥ ፍላጐቶችና ጥቅሞች የሚናረውን አስተውሎት ፥ በአጠቃላይ እኔ ማለት መቻሉን የሚገልጽ ጽንሰ ሐሳብ ነው ።

እንስሳ ከእንቅስቃሴውና ከክንዋኔው ጋር አንድ ነው ፤ ከተፈጥሮ ጋርም የሚገናኘው የተፈጥሮ አንድ አካል በመሆን ብቻ ነው ። ሰው ግን ከተፈጥሮ ጋር የሚገናኘው በማኅበራዊ ተግባራዊ ክንዋኔ አማካይነት ነው ። ማለትም እንደእንስሳ ተፈጥሮን በቀጥታ የሚፈጅ ሳይሆን አምራች በመሆን በተወሰነ የሥራ ዓይነት ውስጥ በመመደብ ፥ በማምረቻ መሣሪያዎች በመጠቀም ፥ በምርቱ ውጤት ለውውጥ በማድረግ የሚኖር በመሆኑ ንቃተ ኅሊናው እኔነትንና አስተዋይነትን ያጠቃልላል ። ሰው የሥራ ችሎታ ስላለው ከተፈጥሮአዊ መስተጋብር እራሱን ሊለይ ይችላል ። ምክንያቱም ሥራ ማለት ሰው በራሱ ፍላጐትና ችሎታ አንፃር ተፈጥሮን መቀየር ማለት ነው ። ተፈጥሮንም ሲለውጥ የሚያገኘው ተጨማሪ ኃይል እራሱን ይለውጠዋል። በራሱ የሥራ ኃይል በፈጠራው ነባራዊ ውጤት ውስጥም የራሱን ምንነት በነባራዊ ኑቱ ይመለከታል ።

ሥራ ማኅበራዊ ተግባር በመሆኑ ሰው ስለራሱ የሚኖረው ንቃተ ኅሊና የሚጀምረው እራሱን የአንድ ኅብረተሰብ አካል አድርጐ በመቁጠሩ ነው ። የአንድ ማኅበር አባል አድርጐ እራሱን በማየቱ ነው ሌላውን የሱ ተመሳሳይ በማድረግ እንደሌላ ሰው የሚቆጥረው ። ይህ ራስንቃተ ኅሊና ሊከሰትና ሊዳብር የቻለው በቋንቋ አማካይነት ነው ። ቋንቋ ሰዎችን ሊያገናኝ የሚችለው በመሠረቱ አንድ ሰው የሚኖረው ለሰውና በሰው በመሆኑ ነው ።

ራስንቃተ ኅሊና ከንቃተ ኅሊና የመነጨና የሱም ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ነው ። በመጀመሪያ ሰው እራሱን በአድራጊነት ከተደራጊ ይለያል ። በዚህ ጊዜ ንቃተ ኅሊናው የሚያንፀባርቀው ጋርዮሻዊ አመለካከትን ይሆናል ። በዚህ ደረጃ እኔ ማለት የአንድ ቡድን ወይም ጐሣ አባል ነኝ ማለት ነው ። ሥልጣኔ እያደገ ሲሄድ እኔ የሚለው ግለሰብነትን እየያዘ ወደ ስብእና እየተለወጠ ይመጣል ።

ሐሳባዊ ፈላስፎች ለራስንቃተ ኅሊና ከፍተኛ ግምት በመስጠት ዋና አንቀሳቃሽ ኃይልና የመንፈስ መለያ ጠባይ አድርገው ተመልክተውታል ። የዘነጉት ነገር ቢኖር ራስንቃተ ኅሊና የሰው ልጅ የዕድገት ታሪካዊ ውጤትና የመነጨውም ከሰው ማኅበራዊ ባሕርይ መሆኑን ነው ።

(ንቃተ ኅሊናን ፥ ብይትውርናን ይመለከቷል።)

## ራሳዊነት
*(Solipsism)*

ሰውና ኅሊናው ብቻ ይኖራሉ ፤ ነባራዊው ዓለም ሕዝቡም ጭምር መኖራቸው የሚከሰተው በየግለሰቡ አእምሮ ወይም ኅሊና ውስጥ ብቻ እንጂ ከዚያ ውጭ በራሳቸው ህልውና የላቸውም የሚል የኅሊናዊ ሐሳባዊነት ንድፈ ሐሳብ ራሳዊነት ይባላል ። ለምሳሌ ከእኔ በስተቀር ወይም ከእኔ ኅሊና ወይም አእምሮ ውጭ አንዳችም በውን የሚኖር ነገር የለም በማለት የሌሎችን ነገሮች ህልውና ይክዳል። እንደነበርክሌይ ፥ እንደነፊሽተ የመሳሰሉት ኅሊናዊ ሐሳባውያን ራሳውያን ይባላሉ ።

ራሳዊነት ከእኔ ውጭ ነባራዊው ዓለም ህልውና የለውም በማለት ለሳይንስና ለምርምር እንደዚሁም ለሰው ዕውቀት የዕድገት በር ዘጊ በመሆኑ ኅሊናዊ ሐሳባዊ ፈላስፎች ዲበ ግለሰብ ፥ አጠቃላይና መለኮታዊ ህልውና እንደአለ አድርገው ይቀበላሉ ። በሌላ አባባል አንድ ከሁሉም በላይ የሆነ መለኮታዊ ኃይል አለ ወደሚለው የሐሳባውያን ማጠቃለያ ያመራሉ ።

(ኅሊናዊነትን ፥ ኅሊናዊ ሐሳባዊነትን ፥ በርክሌይን ይመለከቷል ።)

## ራስን መቻል
*(Self–reliance)*

አንድ ሀገር ለህልውናውና ለዕድገቱ በሌላው ላይ ሳይተማመን ፥ ወይም የሌላው

ጥገኛ ሳይሆን ራሱን ችሎ መገኘት ማለት ነው ። ራስን መቻል በተለይ ታዳጊ ሀገሮች በፖለቲካም ሆነ በኢኮኖሚ የሌሎች ያደጉ ሀገሮች ቅጥያ ሳይሆኑ እራሳቸው ለማኅበራዊ ኑሮ መሻሻል የሚያስፈልጋቸውን የግንባታ ስልት በመቀየስ እንደ ሕዝባቸው ጥረት ፣ እንደሀብትና ማዕድናቸው ክምችት በአጠቃላይም በልማትም እንደደረሱበት ተጨባጭ ሁኔታ ዕድገታቸውን ማራመድ አለባቸው የሚል አስተሳሰብን ያዘለ ነው ።

ሆኖም አንድ ሀገር ራስን መቻል በሚለው መርህ ሲመራ ሙሉ በሙሉ ከሌሎች ሀገሮች ተነጥሎ ፣ በማንኛውም መስክ ፍጹም ብቁነት ኖሮትና ቁሳዊም ሆነ መንፈሳዊ ፍላጎቶችን በራሱ ብቻ እሟልቶ ይገኛል ወይም መገኘት አለበት ማለት አይደለም። አንድ ሀገር ለሕዝቡ የሚጠቅመውን የማኅበራዊ ዕድገት ጉዳና ከቀየሰ በኋላ ለዚህ የሚያስፈልጉትን ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊም ሆኑ ሌሎች ግንኙነቶች ከሌሎች ሀገሮች ጋር ሲያካሂድ ፣ ከዓለም አቀፍ የሥራ ክፍፍል በመነጨ መስተጋብር በእኩልነት ፣ በመከባበርና በመደጋገፍ ለተመጣጣኝ የጋራ ጥቅም በሚበጅ መልክ ሊመራ ይገባል ማለት ነው ። ለዚህ ዓይነቱ የጋራ ጥቅም ማስገኛ ትብብር መስፈን ደግሞ ቀደም ሲል በቅኝ አገዛዝ ዘመን በሀገሮች መካከል የተዘረጉት የበዝባዥና የተበዝባዥ ወይም የበላይና የበታች ግንኙነቶችም የመንግሥታትን የሥልጣን ክብር በማይነካ መንገድ በሚካሄዱ ግንኙነቶች መተካት አለባቸው።

ራስን መቻል ከሁሉ በፊት ትኩረቱ በሀገር ቁሳዊና ቴክኒካዊ ሀብት በተለይም በሕዝቡ የጉልበትና የፈጠራ ኃይል መተማመንና ቁልፍና መሠረታዊ በሆኑ የህልውና ማስከበሪያ ተግባራት ረገድ በጥገኝነት ወይም በተቀጥላነት በሌሎች ላይ ከመንተራስ መላቀቅን ይጠይቃል ።

ይህም ሆኖ ዛሬ ዓለም በደረሰችበት የኢኮኖሚ ፣ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ደረጃ የተሟላ ባለቤት ሆኖ መገኘት ስለሚያዳግት በተለይም ታዳጊ ሀገሮች ለዕድገት ብዙ ነገሮች ስለሚያስፈልጓቸው ከላይ የተመለከተው ብሔራዊ መብታቸው ሳይነካ በዓለም አቀፍ ደረጃ የዓላማ አንድነት ካላቸውና ለሕዝቦች የጋራ ብልጽግና ከቆሙ ሀገሮች ጋር መረዳዳትና መተባበር ይኖርባቸዋል ። ይህ ዓይነቱ ትብብርም በኢኮኖሚ ፣ በሳይንስ ፣ በቴክኖሎጂ ፣ በንግድና በመሳሰሉት መስኮች ተጨባጭ ጥቅም ከማስገኘቱም ሌላ ለሕዝቦች መቀራረብ ፣ ለግጭቶች መወገድና ለዓለም ሰላም መከበር ዋስትና ይሆናል ።

## ራስገዝነት
*(Autonomy)*

አውቶኖሚን ይመለከቷል ።

## ርምደት
*(Progress)*

ርምደት—ተራመደ ከሚለው ግሥ የተወሰደ ነው ።

የኅብረተሰብ ኑሮ ጠቅላላ ዘርፎች የሚያሳዩት ታሪካዊና ከፍተኛ የመዳበር ደረጃ ማለት ነው ።

ርምደት የፍልስፍና ፈርጅ ለመሆን የበቃው የቡርዧው ሥርዓት ተጠናክሮ የራሱ የሆነ ስልተ ምርት ከስፈነ ፣ የምርት ማኅበራዊነት ከተረጋገጠና የምርት ግንኙነት አዲስ ቅርፅ ካገኘ በኋላ ነው ። ርምደት የኅብረተሰብን ኢኮኖሚያዊ ፣ መንፈሳዊና ባህላዊ ዕድገትን የሚያጠቃልል ነው ።

በቡርዧው ፍልስፍና ውስጥ ስለ ርምደት የተለያዩ አመለካከቶች ተሰንዝረዋል ። አንዳንዶቹ ርምደት የፍልስፍና ፈርጅነቱን የሚያጠናክሩለት ሳይንሳዊ መመዘኛዎች ስለሌሉት ራሱን ችሎ ሊጸና የማይችል የኅሊናዊ አስተሳሰቦች ጥንቅር ነው ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ ርምደትን ማኅበራዊ ለውጥ በሚል በተድበሰበሰ ስያሜ ሊተኩት ይሻሉ ። እንዲሁም ደግሞ አንዳንዶቹ ምንም እንኳ የርምደትን ሳይንሳዊነት ባይክዱም በነሱ አገማመት ርምደት በኅብረተሰብ ነጠላ ዘርፎች በተለይም በሳይንስና በቴክኖሎጂ አማካይነት የሚከሰትና ይህም ክስተት በካፒታሊስትም ሆነ በሶሻሊስት ምርት ግንኙነቶች የሚደርስ ስለሆነ ዞሮ ዞሮ ወደ ሁለቱ ሥርዓቶች መወራረስ የሚያመራ ነው ይላሉ ።

በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ርምደት ተጨባጭና ሕግን የተከተለ ሂደት ውጤት ነው ። ርምደት የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች፣የመሠረትና የላዕላይ መዋቅሮች መስተጋብር ውጤት ነው ። ለዚህ ነው ማርክስ

ርምጃት እንደወትሮው በተናጠል መታየት የሌለበት መሆኑን ያስተማረው ።

የርምጃት ሳይንሳዊ መለኪያዎች የሥራ ምርታማነት ፣ የሠራተኛው ሕዝብ የዕውቀት አድማስ መስፋት ፣ የቁሳዊ ፍላጎት መጠን መበርከት ፣ ተፈጥሮን ከቁጥጥር ሥር የማዋል ብልሃት መዳበር ፣ ባጭሩ የምርት ኃይሎች ዕድገት ነው ። የምርት ኃይሎች በተስተካከለ ሁኔታ ሊያድጉ የሚችሉት ብዝበዛና ጭቆና ፣ የግል ሀብት ወዘተ... በሌለበት የምርት ግንኙነት ውስጥ ነው ።

## ርዕዮተዓለማዊ ትግል
*(Ideological Struggle)*

ርዕዮተዓለማዊ ትግል የመደብ ትግል አንድ ገጽታ ነው ፤ በአንድ ወቅት ሰፍኖ የሚገኘው የምርት ግንኙነት እንዲቆይ በሚፈልጉና ይህ የምርት ግንኙነትና በርሱም ላይ ተገንብቶ የሚገኘው ሥርዓት እንዲለወጥ ፣ በሌላ እንዲተካ በሚሹ መደቦች መሀከል የሚካሄደው የአስተሳሰብ (ፖለቲካዊ ፣ ሕጋዊ ፣ ፍልስፍናዊ) ልዩነት ግጭት ርዕዮተ ዓለማዊ ትግል ይባላል ። ርዕዮተዓለማዊ ትግል በመደቦች መካከል የሚደረገውን ግብግብ የሚገልጽ በመሆኑ ወደ አመፅና ወደ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ይለወጣል ።

በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የቁሳዊ ምርት ማከናወኛዎች ባለቤትነት ያለው መደብ የኅሊናዊ ምርት ማፍሪያና ማሰራጫ መሣሪያዎች (ትምህርት ቤት ፣ ጋዜጣ ፣ ሬዲዮ) ባለቤት በመሆኑ ርዕዮተዓለሙን ለማሰራጨትና የበላይነቱን ለማስጠበቅ በነዚህ መሣሪያዎች ይጠቀማል ። ለምሳሌ ቡርዧዚው የካፒታሊስቱ ሥርዓት ዘላለማዊ እንደሆነና ከሰው ተፈጥሮ እንደሚመነጭ ፣ ከዚህ የተሻለ ኅብረተሰብ ሊኖር እንደማይችል አስመስሎ በልዩ ልዩ መንገድና ዘዴ አድኃሪውን ርዕዮተዓለም ያሰራጫል ። በዚህ አንፃር ወዝአደሩ የካፒታሊስቱ ስልተ ምርት የጭቆናና የብዝበዛ ሥርዓት እንደሆነ ፣ ፍትህ ፣ እኩልነት ፣ ወንድማማችነት ፣ ነፃነትና ብልጽግና የሰፈነበት ኅብረተሰብ የሶሻሊስት ብሎም የኮሚኒስት ኅብረተሰብ መሆኑንና ይህም የሚመጣው ወይም ተግባራዊ የሚሆነው የወዝአደሩ መደብ በግንባር ቀደሙ አዝማች ፓርቲው እየተመራ የቡርዧውን ሥርዓት ገርስሶ ሲጥልና ግንባታውን ከግቡ ሲያደርስ መሆኑን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚተነትነውንና የሚያብራራውን ማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተዓለሙን ይዞ ይሰለፋል ።

የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ምሁራንና የወዝአደሩ ፓርቲ የማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ሳይንስ ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ የወዝአደሩንና የሰፊውን ሠርቶ አደር ሕዝብ ንቃተኅሊና ያዳብራሉ ፤ ሰው በሰው የማይበዘበዝበት ፣ ብልጽግና የሰፈነበት አዲስ ኅብረተሰብ ለመገንባት በሚደረገው ትግል ውስጥ ወዝአደሩ ከፍተኛ ሚና የመጫወት ታሪካዊ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በማስተማርና በማሳመን ርዕዮተዓለማዊ ትግል ያፋፍማሉ ።

የወዝአደሩ ፓርቲ ውስብስቡን ርዕዮተዓለማዊ ትግል የሚያካሂደው ፊት ለፊት ከሚጋፈጠውና ከሚቋቋመው ከቡርዧው አድኃሪ ርዕዮተዓለም ጋር ብቻ አይደለም ። የወዝአደሩ ፓርቲ የፖለቲካ ሥልጣን ከጨበጠ በኋላም ከ"ግራ" ና ከቀኝ የማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ካባ አጥልቀው ከሚመጡት ቀኖናውያን ፣ አፈንጋጮችና አድርባዮችም ጋር ውስብስብና መራራ ትግል ያካሂዳል ፤ በረዥሙና በመራራው የግንባታ ምዕራፍም ርዕዮተዓለማዊውን ትግል ይቀጥላል ። ርዝራዥ አድኃሪ ርዕዮተዓለሞችንና ባህልን ይታገላል ።

ርዕዮተዓለም የመደብ ትግሉ አካል እንደመሆኑ በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ቅራኔ ይፋ ለማውጣትና ከዚህም ቅራኔ መፈታት ጋር የሚመጣውን ከፍተኛና የተሻለ ሥርዓት በማሳየት የመደቦች የኃይል አሰላለፍ እንዲቀየርና ትግሉ እንዲፋፋም ስለሚያደርግ የርዕዮተዓለም ትግል በታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ሚና አለው ። በሌላ በኩል ርዕዮተዓለማዊ ትግል የመደብ ትግል አካል በመሆኑ ከመደቦች ጋር አብሮ ይከስማል ።

(ርዕዮተዓለምን ፣ ፍልስፍናን ፣ የመደብ ትግልን ፣ አብዮትን ይመለከቷል ።)

## ርዕዮተዓለም
*(Ideology)*

ርዕዮተዓለም ሰፊና ጠባብ ትርጉም አለው ። ሰፋ ባለው ትርጉሙ ርዕዮተዓለም ማለት ማኅበራዊ ሕይወትን ከመደብ ጥቅም

እንፃር የሚመለከት ንድፈ ሐሳባዊ ግንዛቤ ማለት ነው ። በዚህ አገባቡ ሰዎች ስለማኅበራዊ ሕይወት ያላቸውን አመለካከት ሥርዓት ባለውና አጠቃላይ በሆነ መልክ ቅርፅ የሚያስይዝ ነው ።

ጠበብ ባለው ትርጉሙ ደግሞ ርዕዮተዓለም የማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና ዘርፎችን (ሥነ ምግባር ፣ ኪነትና ፍልስፍና) የመደብ ገጽታ የሚያመለክት ጽንሰ ሐሳብ ነው ። ርዕዮተዓለም በዚህ ፍችው የሚሰጠው አገልግሎት ማኅበራዊ ግንኙነቶችንና ክስተቶችን ከተወሰነ መደብ ጥቅም አንፃር መግለጽ ነው ። በዚህም አገልግሎቱ በመደብ ኅብረተሰቦች ውስጥ መደቦች የተለያዩ ብቻ ሳይሆኑ ተፃራሪም የሆኑ ማኅበራዊ ጥቅሞች ፣ ዓላማዎችና ተግባሮች እንዳሏቸው በመግለጽ የተለያዩ መደቦች በግዴታ የተለያዩ ርዕዮተዓለሞችን እንደሚያንፀባርቁ ያመለክታል ።

ሆኖም የተለያዩ ርዕዮተዓለሞች ይኑሩ እንጂ የበላይነት የሚኖረው የገዥው መደብ ርዕዮተዓለም ነው ። በስፋትና በይፋ የመሰራጨትም ዕድል ያለው ይኸው ርዕዮተዓለም ነው ። ጭቁን መደቦች በተለይም የወዝአደሩ መደብ የራሱን ጥቅም በራሱ ማስከበር ከሚችልበት ደረጃ እስከሚደርስ ድረስ በካፒታሊስቱ ርዕዮተዓለም ሊወናበድ ፣ የራሱንም ጥቅም ሊፃረር ይችላል ። ነገር ግን ወዝአደሩ ታሪካዊ ተልዕኮውን ተገንዝቦ ለዚህም ተልዕኮው መታገል ሲጀምር ከካፒታሊስቱ ርዕዮተዓለም ተፅዕኖ በመላቀቅ በማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተዓለም መሪያነት የካፒታሊስቱን ርዕዮተዓለም ማጋለጥና መታገል ይጀምራል ።

ርዕዮተዓለም የፖለቲካ ፣ የሕግ ፣ የሃይማኖት ፣ የፍልስፍና ወዘተ... አስተሳሰቦች ሥርዓት እንደመሆኑ የላዕላይ መዋቅሩ አካል ነው ። ከዚህም የተነሣ የኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች ነፀብራቅ ይሆናል ። በመሆኑም የርዕዮተዓለም ትግል በመደቦች መካከል የሚደረገው ትግል ነፀብራቅና የመደብ ትግሉ አንዱ መሣሪያ ነው ።

ርዕዮተዓለም ሳይንሳዊ ወይም ኢሳይንሳዊ ሊሆን ይችላል ። የኢሳይንሳዊነት ባሕርዩ የሚመነጨው የምርት ኃይሎችን ዕድገት የሚያፍኑ ፣ የሳይንሳዊ ዕውቀት መስፋፋትን የሚጠሉ ፣ የሃይማኖትንና የአምልኮን መጠናከር የሚሹ አድኃሪ መደቦችን ጥቅም ከማንፀባረቁ ሲሆን ለማኅበራዊ ሥርዓት ለውጥ ፣ ለምርት ኃይሎች ዕድገትና ለሳይንሳዊ ዕውቀት መስፋፋት የሚታገሉ የሠራተኛ መደቦችንና የማኅበራዊ ኃይሎችን ጥቅም ሲያንፀባርቅ ደግሞ ሳይንሳዊ ይሆናል ። ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ለሠራተኛው መደብ መሠረታዊ ጥቅምና ታሪካዊ ተልዕኮ እንዲሁም ለማኅበራዊ ነፃነትና እርምጃ የሚታገል በመሆኑ ሳይንሳዊ ርዕዮተዓለም ነው ።

ርዕዮተዓለም እንደሌሎቹ የላዕላይ መዋቅራዊ ክፍሎች ሁሉ ከኢኮኖሚው ወሳኝነት አኳያ ሲታይ አንፃራዊ ነፃነት አለው ። የርዕዮተዓለም ይዘትና ለውጥ በኢኮኖሚያዊው ሁኔታ በቀጥታ ስለማይገለጽና በርዕዮተዓለምና በኢኮኖሚያዊው ሁኔታ መካከል ያልተመጣጠነ የዕድገት ደረጃ በመኖሩ ለአንፃራዊ ነፃነት ምክንያት ይሆናል ። በተጨማሪም ርዕዮተዓለም በኢኮኖሚው ሁኔታ የማይገለጹ የራሱ የዕድገት ሕግጋት ያሉት ክስተት በመሆኑም ነው አንፃራዊ ነፃነት የሚኖረው ።

(ላዕላይ መዋቅርን ፣ ማኅበራዊ ንቃተ ኅሊናን ይመለከቷል ።)

# ሸ

## ሸማቾች ኅብረት ሥራማኅበር(የ—)
*(Consumers' Co-operatives)*

ሸማቾች ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን ምርቶች ከብዝበዛ ነፃ በሆነ መንገድ ለማግኘት እንዲችሉና እንዲሁም ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ምርቶችን እንደየሁኔታው እያመረቱ ለአባሎችና እንዲሁም በአጠቃላይ ለኅብረተሰቡ ለማቅረብ በፈቃደኝነት የሚመሠርቱት ድርጅት ነው ።

ለሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት አጀማመር መንሥኤ ወዝአደሩ ቡርዧዚው ከሚያደርስበት ፣ አትራፊ ነጋዴዎችም ከሚፈጽሙበት ብዝበዛ ለመዳን ያደረገው ጥረት ሲሆን ለኑሮ የሚያስፈልጉትን ሸቀጣ ሸቀጦች በተመጣጣኝ ዋጋ ለማግኘት እንዲችል ገንዘብ በማዋጣት የሚመሠርታቸው የጋራ ዕድገት መደጋገፊያ ማኅበራት ናቸው ።

የመጀመሪያዎቹ የሠራተኛው እንዲሁም የገበሬው የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት በ18ኛው ምዕት ዓመት ማብቂያና በ19ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ላይ በቅድሚያ በእንግሊዝ ፣ ከዚያም በፈረንሳይ፣ በጀርመን ፣ በኢጣልያና በሌሎች የአውሮፓ ሀገሮች ተስፋፉ ። የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት መጀመሪያ በፋብሪካ ውስጥ በሚሠሩ ወዝአደሮች ቢጀመሩም በሌሎች ማለትም በእርሶ አደሩ ፣ አነስተኛ ገቢ ባላቸው የቢሮ ሠራተኞች ወዘተ... እየተቋቋሙ መስፋፋት ቻሉ ።

የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት አጀማመር ከሌሎች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ቀደምትነት ያለውና በአውሮፓ ተጀምሮ በሌሎችም ሀገሮች እየተስፋፋ የመጣ ሲሆን ዛሬ በሶሻሊስት ሀገሮችና በአብዛኛው በካፒታሊስት እንዲሁም በታዳጊ ሀገሮች የቁጥሩ ብዛትና ይዘት ይለያይ እንጂ በስፋት ተቋቁሞ የሚገኝ ሕዝባዊ ድርጅት ነው ።

የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት በመጀመሪያ በንግዱ ተግባር ላይ ያተኩሩ ቢሆንም እንደየጥንካሬያቸው የሥራ ዘርፋቸውን በማስፋፋት የመዝናኛና የሆቴል ድርጅቶችን በመክፈትና አልፎ አልፎም በእርሻና በአነስተኛ ኢንዱስትሪ የማምረት ተግባር ለምሳሌ ዳቦ በመጋገር ፣ የታሸገ ምግብ በመሥራትና በመሳሰሉት ላይ ይሰማራሉ ።

ዛሬ በአንዳንድ ሀገሮች የሸማቾች የኅብረት ሥራ ማኅበር ተግባር በገበያ የኅብረት ሥራ ማኅበርና በገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማኅበር ተጠቃሎ ሲሠራ ይታያል ። በእኛም ሀገር ቢሆን በገጠሩ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር ተግባር በመጀመሪያ ደረጃ ባሕርዩ በገበሬዎች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበር ተጠቃሎ ይሠራል ። በከተሞች ደግሞ የሕዝብ ሱቆች የዚሁ ጥንስስነት ያላቸው ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ ።

የምርት መገልገያዎች በግል ይዞታ ሥር በሆኑበት በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የሚቋቋሙት የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት በመጠኑም ቢሆን አባላቱን ከመሀል አትራፊዎች ብዝበዛ የሚያድኑና አንዳንድ አገልግሎቶች የሚሰጡ ቢሆንም የአባሎችን የዘለቄታ ጥቅም ለማስከበር የሚችሉ አይደሉም ። ምክንያቱም በካፒታልና በጉልበት መካከል ያለው ቅራኔ ባለመወገዱና የንግዱም ሁኔታ በዚህ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ነው ።

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ግን ንግድ በአብዛኛው የሚካሄደው በመንግሥታዊና በሕዝባዊ ድርጅቶች አማካይነት ሲሆን ግለሰቦች በንግዱ ዘርፍ የሚኖራቸው ሚና እየመነመነ የሚሄድ ነው ። የመንግሥታዊና የሕዝባዊ ድርጅቶች ዓላማ ሶሻሊስት የሆነ ኢኮኖሚን በማጠናከር የሕዝቡን ፍላጐት ማሟላት ስለሆነ በነዚህ ተቋሞች የሚካሄደው ንግድ ትርፍን የማካበት ዓላማ የለውም ። ከነዚህ ድርጅቶች የሚገኘው ትርፍ መልሶ የኅብረተሰቡን የጋራ ኑሮ ለማሻሻል የጋራ ክምችት የሚያስገኝ እንጂ የተወሰኑ ግለሰቦችን ጥቅም የሚያዳብር አይሆንም ።

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ንግድ በገጠርና በከተማ ፣ በእርሻና በኢንዱስትሪ

መካከል መኖር የሚገባው ትክክለኛ የኢኮኖሚ ግንኙነት መጠበቁን የሚያረጋግጥ ነው። ሶሻሊዝምን በገነቡ ሀገሮች የንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚ በዚሁ ሶሻሊስት መርህ እንዲመራ ለማድረግ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉና በማድረግም ላይ የሚገኙ ናቸው ። ለዚህም ድርሻቸው መሟላት የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ሀገር አቀፍ ደረጃ በራሳቸው መዋቅር ተደራጅተው በማዕከላዊ አመራር ማኅበራዊ የምርት ስርጭት ያካሂዳሉ ።

በሀገራችንም በአሁኑ ደረጃ በገጠር የተቋቋሙት የገበሬዎች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራትና በከተማም የከተማ ቀበሌ ነዋሪዎች የሕዝብ ሱቆች ለሸማቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ጥንስስ ለመሆን በሚቻልበት ሁኔታ በማገልገል ላይ ናቸው ።

## ሸቀጥ

*(Commodity)*

ለራስ ፍጆታ ሳይሆን ለሽያጭ ወይም ለገበያ ተብሎ የሚመረትና የሰዎችን የተለያዩ ፍላጐት ለማርካት የሚችል የሰዎች የሥራ ኃይል ውጤት የሆነ ዕቃ ፣ ነገር ወዘተ... ሁሉ ሸቀጥ ይባላል ።

ማናቸውም ሸቀጥ ሁለት ጠባዮች አሉት ። እነሱም የጠቀሜታ እሴትና የልውውጥ እሴት ናቸው ።

በኅብረተሰብ ዕድገት ሂደት ውስጥ ዕቃዎችን ለልውውጥ ማምረት የተጀመረው ጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር መፈራረስ ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ ነው ። በጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር የመጨረሻ ደረጃ ወቅት የተፈጥሮ ኢኮኖሚ እየፈራረሰ ሲሄድ ቀደም ሲል እርሻ በኋላም የእደጥበብ ሥራ ተከሰተ ። የተለያዩ የሥራ ዘርፎች መከሰት ለትርፍ ምርት መገኘት አመች ሁኔታን ፈጠረ ። በመሆኑም ለሸቀጥ ምርት መከሰት ምክንያት የሆነው የማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል መዳበር ነው ። የባሪያ አሳዳሪውና የፊውዳሉ ሥርዓቶች ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል በመዳበር ላይ የሚገኙባቸው ሥርዓተ ማኅበሮች እንደመሆናቸው የሸቀጥ ምርት ይመረትባቸዋል ። ይሁንና የሸቀጥ ምርት በከፍተኛ ደረጃ ዳብሮና ተስፋፍቶ የሚገኘው በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ነው ። በዚህ ሥርዓተ ማኅበር ለልውውጥ የሚመረተው የማምረቻ መሣሪያና የፍጆታ ዕቃ ብቻ አይደለም ። የሰው የአእምሮ ውጤቶችም ለምሳሌ ምርምራዊ ሥራዎች ፣ ሥዕል ፣ ሥነ ጽሑፍ ወዘተ... እንደ ሸቀጥ የሚለወጡ ሲሆኑ ፣ በዚህ ሥርዓተ ማኅበር የሰው የሥራ ኃይል ሳይቀር ሸቀጥ ነው ።

የሸቀጥ ምርት በሦስት የተከፈለ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ። እነሱም ቀላል የሸቀጥ ምርት ፣ ካፒታሊስት የሸቀጥ ምርትና ሶሻሊስት የሸቀጥ ምርት ናቸው ።

የሸቀጥ ምርት የሚጠፋው ሶሻሊዝም ወደ ከፍተኛው የኮሚኒዝም የዕድገት ደረጃ ደርሶ በገጠርና በከተማ ፣ በአእምሮና በጉልበት ሥራ መካከል ያለው ልዩነት ከመጥፋቱ ጋር የሸቀጥና የገንዘብ ግንኙነት ሲያከትም ነው ።

(ቀላል የሸቀጥ ምርትን ፣ ካፒታሊስታዊ የሸቀጥ ምርትን ፣ ሶሻሊስታዊ የሸቀጥ ምርትን ፣ የጠቀሜታ እሴትን ፣ የልውውጥ እሴትን ይመለከቷል ።)

## ሸቀጥ በሸቀጥ ለውጥ (የ—)

*(Barter)*

የሸቀጥ በሸቀጥ ለውጥ ጥንታዊ የሆነ የሸቀጥ ልውውጥ መልክ ነው ። ኅብረተሰብ በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ በነበረበት ጊዜ የሸቀጥ ልውውጥ ሥርዓት የያዘ አልነበረም ። አንድ ሸቀጥ በሌላ ሸቀጥ ፣ አንድ ዕቃ በሌላ ዕቃ በአጋጣሚ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ይለወጥ ነበር ። ለምሳሌ አንድ በሬ በሁለት እንቅብ እህል ፣ አንድ ጦር በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ ሞፈር ወዘተ... ይለወጣል። በዚህ መሠረት አንድ ዕቃ የራሱን እሴት በሚለውጠው ዕቃ እሴት ይገለጽ ነበር ። ይህ ሸቀጥን በሸቀጥ በቀጥታ የመለወጡ ሁኔታ ከሥራ ክፍፍል መስፋፋትና ለገበያ ከሚቀርበው ሸቀጥ መጠን መብዛት ጋር ቀስ በቀስ እየከሰመ በአንድ ሁለንታዊ አኩያ ወይም ገንዘብ አማካይነት ለሚካሄድ ልውውጥ ቦታውን እንዲለቅ ተገዷል ።

በሸቀጥና በገንዘብ መካከል ግንኙነት ባለበት ኢኮኖሚ ሁሉ የሸቀጥ ልውውጥ የሚከናወነው በመሠረቱ በገንዘብ አማካይነት ነው ። የሸቀጥና የገንዘብ ግንኙነት የሚጠቀው በኮሚኒስት ስልተ ምርት ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ሲሆን በገንዘብ አማካይነት የሚካሄድ የሸቀጦች ልውውጥ ደረጃ በደረጃ መክስም የሚጀምረው ግን በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ነው ። ይህን ሂደት ከሚያፋጥኑ ሁኔታዎች አንዱ የማኅበራዊ ፍጆታ መጠን እያደገ መሄድ ነው ።

በሶሻሊዝም ውስጥ ገንዘብ ያለው ሚና በካፒታሊዝም ሥር ካለው የተለየ ነው ። በካፒታሊስት ሥርዓት ሥር ገንዘብ እንደ ካፒታል በመሆን የሥራ ኃይልን ለመበዝበዝ ይውላል ። በሶሻሊዝም ሥር ግን የማምረቻ መሣሪያዎችን በግል በመያዝ ሠራተኛን ቀጥሮ መበዝበዝ ስለማይቻል ገንዘብ በካፒታል መልክ ሊያገለግል አይችልም ። ይልቁኑ ገንዘብ በዕቅድ ላይ የተመሠረተ ሶሻሊስት ኢኮኖሚን ለማራመድ ይጠቅማል ። በዚህም መሠረት በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ገንዘብ እንደ እሴት መለኪያ ፣ እንደ ዝውውር አማካይ ፣ እንደ ክፍያ መሣሪያና እንደ ሶሻሊስት ክምችት መሣሪያ በመሆን ያገለግላል ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የገንዘብን ሁለንታዊ እኩያ ተግባር የሚያሟላው ወርቅ ቢሆንም ከሀገሮች ጋር በሚደረግ ንግድ ወርቅ እምብዛም ለክፍያ አይውልም ። ንግዱ የሚካሄደው ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸውን ሸቀጦች በመለዋወጥ ነው ።

## ሼሊንግ ፣ ፍሪድሪሽ ቪልሄልም
*(Schelling, Friedrich Wilhelm)*

ከ1775 እስከ 1854 የኖረ ፣ ከጀርመን ዕውቅ ብሉይ ሐሳባዊ ፈላስፎች ውስጥ አንዱ ሲሆን በየና ፣ በኤርላንግንና በበርሊን ፕሮፌሰር ሆኖ የሠራና በሚዩኒክ የሳይንስ አካዳሚ አባል የነበረ ፈላስፋ ነው። በተፈጥሮ ፍልስፍና ላይ በርካታ ጽሑፎችን ከማዘጋጀቱም ሌላ ስለተፈጥሮ የተስነዘሩትን የካንትን አመለካከትና የላይብኒትዝን አስተምህሮ በመጠቀምና በማቀናጀት በተፈጥሮ ውስጥ ዕድገት መኖሩን የሚያሳዩ ሐሳቦችን ሰንዝሯል ። በሌላም በኩል የፊኽተን ኅሊናዊ ሐሳባዊነት ከራሱ ነባራዊ ሐሳባዊነት አስተሳሰብ ጋር በማዋሀድ ሁለቱንም የሚያጣምር "የትራንስዴንታል ሐሳባዊነት ሥርዓት" ቀምሯል ።

በሼሊንግ አስተሳሰብ ማናቸውም ፍልስፍና ለሁለት ጥያቄዎች መልስ መስጠት አለበት ። እነርሱም ፣ አንደኛው ጥያቄ ንቁ ያልሆነው ተፈጥሮ (ቁስአካል) በዕድገቱ ሂደት እንዴት ኅሊናን ይወልዳል ? የሚለውና ሁለተኛው ደግሞ እራሱ አድራጊ የሆነው ንቁ ኅሊና እንዴት ወደ ተደራጊ ይለወጣል ? የሚሉት ናቸው ። በእርሱ አመለካከት የመጀመሪያው "ጥያቄ" በተፈጥሮ ፍልስፍና የሚመለስ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ "በትራንስዴንታል ሐሳባዊነት" አስተምህሮ የሚመለስ ነው ።

ሼሊንግ ከፊኽተ ኅሊናዊ ሐሳባዊነት የተወሰኑ አስተሳሰቦችን ቢወስድም ኅሊናዊ ሐሳባዊነትን የተረዳው የግለሰቦች ንቃተ ኅሊና እንደሆነ አድርጎ ሳይሆን የሰው አእምሮ ስለተገብሮ ያለው ቀጥተኛ ነጽሮት ወይም "አእምሮአዊ ጭልታ" እንደሆነና ይህም "ጭልታ" ማናቸውንም የአስተሳሰብ ደረጃ እንደሚሸፍን አድርጎ ነው ። ይህም "አእምሮአዊ ጭልታ" የብዙኃኑ ችሎታ ሳይሆን የጥቂት ምርጥ ሰዎች ተስጥኦ ነው ይላል ። ኅሊና የራሱን ግብታዊነት ሲገነዘብ ነፃነቱንና የግዴታ ተገዥነቱን ይረዳል ። የመንፈስና የተፈጥሮ ፣ የአድራጊና የተደራጊ ፣ የነፃነትና የግዴታ ቅንጅት የሚገለጸው በግለሰቡ ነፃ ክንዋኔ ይሆናል ። ሆኖም ይህ ቅንጅትና የግለሰቡ ነፃ ክንዋኔ ከምክኑያዊ ዕውቀት በላይ በመሆኑ ሊገለጽ የሚችለው በእምነት ብቻ ነው ፤ ስለዚህም የታሪክና የሥነ ምግባር ዕድገት ዋስትና እግዚአብሔር ነው ይላል ።

የሼሊንግ አስተምህሮ በታሪክ ውስጥ የነፃነትንና የግዴታን ዲያሌክቲክስ ለማሳየት ጥረት ቢያደርግም በሐሳባዊነትና በተማልሎአዊነት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የታሪክን የዕድገት ጐዳና ለመተንበይ የማያስችልና በቀቢጸ ተስፋ ውስጥ የሚጥል ነው ።

ሼሊንግ በተለያዩ ወቅቶች ከአንድ የሐሳባዊ ፍልስፍና አቋም ወደ ሌላው በመሸ

ጋገርና በመቀየጥ የተለያዩ አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን ለመፍጠር ሞክሯል ። ሆኖም ኤንግልስ በወቅቱ ለነበሩ አቻዎቹ የሼሊንግን ፍልስፍና አድኃሪነት አጋልጧል ።

## ሽምቅ ውጊያ

(*Guerrilla Warfare*)

ጠላትን እያዳከሙ በረዥም ጊዜ ውስጥ ለማሸነፍ ወይም ጠላት ተዳክሞ ሰላማዊ ድርድር እንዲጠይቅ ፊት ለፊት በመግጠም ሳይሆን ድንገተኛ አደጋ በመጣል የሚካሄድ የትግል ስልት ነው ። ይህ የትግል ዓይነት ፖለቲካዊ ፥ ማኅበራዊ ፥ ኢኮኖሚያዊና ሥነ ልቡናዊ ጠባዮች አሉት ። በዚህ ዓይነት ዘዴ የሚካሄድ ትግል ግቡን የሚመታው አብዛኛውን ጊዜ ከረዥም ትግል በኋላ ነው ። የተዋጊው ኃይል በሰውም ሆነ በትጥቅ በኩል ከተቃራኒው ወገን ጋር ሲነፃፀር አብዛኛውን ጊዜ መጠኑ አነስተኛ ነው ።

ተዋጊዎቹ በአሰባበሳቸው እንደመደበኛ ጦር ተመሳሳይ ያልሆኑ ፥ ባገኙት የጦር መሣሪያ የሚጠቀሙ ፥ ቋሚ የሆነ ሰፈር የሌላቸው ፥ በአብዛኛው አድፍጠ ጠላትን በማጥቃት ብቻ ሳይሆን የጠላትን ሞራልና የኢኮኖሚ ጥንካሬ ለማዳከም ልዩ ልዩ ስልቶችንም የሚጠቀሙ ናቸው ።

ሽምቅ ውጊያ በአጠቃላይ የተቃውሞ መግለጫ ነው ። ነገር ግን ተቃውሞው በሕዝቡ ላይ የተጫነውን የጭቆና ቀንበር ለማስወገድና ፍትህና እኩልነት የሰፈነበትን ማኅበራዊ ሥርዓት ለመመሥረት እንዲቻል የውስጥ አድኃሪ መንግሥትን ለመጣል ወይም ከባዕድ አገዛዝ ለመላቀቅ የሚካሄድ ፥ ወይም ጥቂት ወገኖች ለራሳቸው አድኃሪ ዓላማ በዚህ ስልት ተጠቅመው ያለውን ተራማጅና ሕዝባዊ ሥርዓት ለመጣል የሚያካሂዱት የትጥቅ ትግል ሊሆን ይችላል ። ስለዚህ ሽምቅ ውጊያ እንደማንኛውም የትጥቅ ትግል ስልት ተራማጅ ወይም አድኃሪ ዓላማና ገጽታ አለው ።

ሽምቅ ውጊያ ራሱን የቻለ የውጊያ ስልት ሆኖ ሊያገለግልም ይችላል ። በተለይ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ሽምቅ ውጊያ የሕዝባዊና የብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴ ጦርነቶች ዓይነተኛ ቅርፅ ሆኗል ። በቻይና ፥ በአልጄሪያ ፥ በኩባ ፥ በቬትናም ፥ በአንጎላ ፥ በሞዛምቢክ ፥ በጊኒ ቢሳውና በዚምባብዌ የተካሄዱት ሽምቅ ውጊያዎች ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌ ናቸው ። ብዙውን ጊዜ ጦርነቶች በሽምቅ ውጊያነት ተነሥተው ወደመደበኛ ጦርነት እያደጉ ይሄዳሉ ።

## ሽረት ሽረት ሕግ (የ—)

(*Law of Negation of the Negation*)

የዚህን ሕግ መንፈስና አሠራር ለመረዳት በቅድሚያ የሽረትን ትክክለኛ ሚና ማወቅ አስፈላጊ ነው ። ዲበአካላውያን እንደሚሉት ከሆነ ሽረት ማውረድ ፥ መደምሰስ ማለት በመሆኑ ሽረት የዕድገት ተቃራኒ እንጂ የሱ አራማጅ ሊሆን አይችልም ። በተጨማሪም እንደእነሱ አባባል ሻረውን ነገር መልሶ መሻር የሚያመለክተው ዕድገትን ሳይሆን በፊት ወደነበረው ሁኔታ መመለስን ነው ። ይህ የሽረት ሽረት ሕግን አስመልክተው ዲበአካላውያን የሚሰጡት ትርጉም መታረም አለበት ።

ዕድገት ካለሽረት ሊፈጸም አይችልም ፤ ምክንያቱም አዲስ ነገር ሊከሰትና የበላይነት ሊይዝ የሚችለው ከአሮጌው ጋር በመታገልና እሱን በመደምሰስ ነው ። ዲበአካላውያን መሠረታዊ ለውጥን ስለማይቀበሉ ነው አዲሱን የአሮጌው ቅጥያ አድርገው የሚተረጉሙት ። በሌላ በኩል ሌላውን የሻረ ነገር መልሶ ሲሻር ወደኋላ መመለስ የማይሆንበት ምክንያት የመጀመሪያው ሽረት አዲስ ሁኔታ ያስከተለ በመሆኑ ነው ። አዲሱ ሚናውን ካጠናቀቀ በኋላ ወደአሮጌነት ስለሚቀየር በተራው መሻር ይኖርበታል ። ይህ ማለት የሽረት ሽረት ሕግ በነገሩ ውስጥ የሚፈጸመውን የዕድገት ተከታታይነት የሚያሳይ ነው ። ማለትም በአዲሱና በአሮጌው ተከታታይነት ኖሮ ነገሩ በሂደት ውስጥ ያገኛቸውን የዕድገት ውጤቶች እንዲያጠቃልል የሚያስችለው የሽረት ሽረት ሕግ ነው ። ማጠቃለሉም ሊፈጸም የሚችለው ነገሩ አዲስ መልክ በመያዝ ወደከፍተኛ ደረጃ ሲሸጋገር ነው ።

ለምሳሌ ካፒታሊዝም ፊውዳሊዝምን ይሽራል ፤ የግል ንብረት ኖሯቸው የግል አምራች የነበሩትን ወደ ወዝአደርነት በመቀየር

ንብረት አልባ ያደርጋቸዋል ። ካፒታሊዝም እያደገ በሄደ ቁጥር የግል ንብረት በኅብረተ ሰቡ ውስጥ እየመነመነና በጥቂት ሰዎች እጅ ብቻ እየተጠራቀመ ይመጣል ። ይህ ሁኔታ በሶሻሊዝም ሲሻር ኅብረተሰቡ በፊት ወደነበረበት የግል ንብረት ሁኔታ ይመለሳል ማለት አይደለም ። ሶሻሊዝም በተመሠረተበት ማኅበራዊ የምርት ስልትና የማኅበራዊ ንብረት ይዞታ አንፃር አምራቹ በአስተዋጽኦው መጠን ድርሻውን በግል ንብረትነት ይጠቀምበታል ማለት ነው ። እንዲሁም ሐሳባዊ ፍልስፍና ጥንታዊ ቁስ አካልነትን ሲሽርና መልሶ በቁስ አካልነት ሲሻር ፍልስፍና ወደጥንታዊ ቁስአካልነት ይመለሳል ማለት አይደለም ። ከሽረት ሽረቱ የሚገኘው የዳበረ ማለትም ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት በመሆኑ ሻሪው የበላይ ለመሆን የሚበቃው ሐሳባዊነት የበላይ በነበረበት ጊዜ ያጠራቀመውን የሰውን ልጅ የዕውቀት ታሪክ የሚያጠቃልል በመሆኑ ነው ።

የሽረት ሽረት ሕግ የሚያሳየን የዕድገት አቅጣጫን ነው ። ሽረት ለተሻለ ፣ ለበለጠ ነገር በመሆኑ የአንድን ነገር ታሪካዊ ሂደት የሚመራ ነው ። የአንድን ነገር የቀድሞውንና የመጪውን ሁኔታ ማለትም መነሻውንና መድረሻውን የሚያመለክት በመሆኑ የሽረት ሽረት ሕግ የዕድገት አጠቃላይ ሕግ ነው ።

(የዲያሌክቲክስ ሕጐችን ፣ ጥምጥማዊ ዕድገትን ይመለከቷል ።)

## ሽብር

*(Terror)*

በመደብ ትግል ውስጥ ሽብር በተፃራሪ መደቦች መካከል የሚደረገው ሰላማዊ የትግል ስልት ሊሠራ ከማይችልበት ደረጃ ሲደርስ አንዱ ሌላውን ለማንበርከክና የበላይነቱን ለማረጋገጥ የሚያካሂደው የትጥቅ ትግል ነው ። ይሁንና አድኃሪ ኃይሎች በአብዮት ሰፈር የሚያካሂዱት ሽብርና የአብዮቱ ወገኖች በአድኃሪው ሰፈር ላይ የሚያደርጉት የትጥቅ እመፅ በይዘትም ሆነ በዓላማ ፍጹም የተለያዩ ናቸው ።

ነጭ ሽብር አድኃሪ ገዥ መደቦች ሥርዓታቸው እንዳይለወጥ ወይም የተነጠቁትን ሥልጣን በኃይል ለመመለስና ብዝበዛቸውን እንደገና ለማካሄድ በአብዮተኞችና በአብዮቱ ደጋፊዎች ፣ በአጠቃላይ በአብዮቱ ላይ የሚያካሂዱት አሰቃቂ የሆነ የግፍና የጭካኔ ተግባር ነው ። ነጭ ጦር የሚባሉትም በሩሲያ ውስጥ ከ1918—21 በተካሄደው የርስ በርስ ጦርነት በኢምፔሪያሊስቶች ቀጥተኛ ርዳታ በመደገፍ ቀዩን ጦርና ቦልሼቪኮችን ይዋጉ የነበሩ የፀረ አብዮት ወታደሮች ናቸው ። ኋላ በሶቭዬት ኅብረት እንደታየው ትሮትስካይቶችም በነጭ ሽብራቸው የታወቁ ናቸው ። በጀርመንም በ1933 ሂትለር ሥልጣን ከጨበጠ በኋላ በኮሚኒስቶችና በተራማጅ ኃይሎች ላይ ተመሳሳይ ሽብር አካሂዷል ። በሀገራችንም ከ1969 መጀመሪያ እስከ 1970 አጋማሽ ድረስ በተለይ በከተሞች በ "ኢ.ሕ. አ. ፓ." የተካሄደው ነጭ ሽብር በአብዮቱ ላይ አደጋ አድርሶ ነበር ።

ቀይ ሽብር አብዮት በፀረ አብዮት ኃይላት የውጥር በሚያዝበትና የዘላቂነት ተስፋው እጅግ በጣም በሚያጠራጥርበት ወቅት አብዮቱን ከቅልበሳ ለማዳን ሌላ አማራጭ ዘዴ ሲጠፋ የአብዮቱ ወገኖች የመጨረሻ የፖለቲካ ውሳኔ በማድረግ በፀረ አብዮተኞች ላይ በይፋ የሚወስዱት የትጥቅ እርምጃ ወይም ቅጣት ነው ።

ተራማጅ ኃይሎች በፀረ አብዮትና በአድኃሮት ሰፈር የሚያደርሱት ሽብር አድኃሪውን ሥርዓት በመደምሰስ ብዝበዛንና ጭቆናን ለማጥፋት በመሆኑ በይዘቱ ተራማጅና ሕዝባዊ ነው ። ፀረ አብዮትና የአድኅሮት ኃይላት በአብዮቱ ሰፈር የሚፈጥሩት ሽብር ግን ሕዝቦች ለነፃነት ፣ ለሰላምና ለማኅበራዊ ዕድገት የሚያካሂዱትን የትጥቅ አመፅ በጦር ኃይል ፣ በፖለቲካና በኢኮኖሚ ተፅዕኖ በመግታት የአሮጌውን ሥርዓት ዕድሜ ለማራዘምና ብዝበዛና ጭቆና እንዲቀጥል ለማድረግ ስለሆነ አድኃሪና ፀረ ሕዝብ ነው ።

## ሽግግር ወቅት (የ—)

*(Transition Period)*

የሠራተኛው መደብ የፖለቲካ ሥልጣን ከጨበጠበት ጊዜ አንሥቶ ኅብረተሰቡ ለሶሻ

ሊስት ግንባታ አስፈላጊውን ቴክኒካዊ ፣ ቁሳዊና ባህላዊ መሠረት እስከሚጥል ድረስ የሚወስድበት ጊዜ የሽግግር ወቅት ይባላል ። በሌላ በኩል ከረዥሙ የኮሚኒስት ሥርዓተ ማኅበርን ከማስፈን ግብ አኳያ ሲታይ የዚሁ ሥርዓተ ማኅበር የመጀመሪያ ደረጃ የሆነው ሶሻሊዝም ራሱ እንደ ሽግግር ወቅት ይቆጠራል ።

በመጀመሪያው ትርጉም መሠረት ማንኛውም ኅብረተሰብ ከካፒታሊስት ወይም ከቅድመ ካፒታሊስት ስልተ ምርት ወደ ሶሻሊዝም ከመድረሱ በፊት በሽግግር ወቅት ውስጥ ማለፍ ይኖርበታል ። ምክንያቱም ከቅድመ ካፒታሊዝም ወደ ካፒታሊዝም በተደረገው ዕድገት የግል ባለንብረትነት ሳይጠፋ አንድ ዓይነት ብዝበዛ በሌላ ዓይነት ተተካ እንጂ መሠረታዊ የሆነ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ አልተደረገም ። በአንፃሩ ግን ካፒታሊዝም ተሸሮ የማምረቻ መሣሪያዎች በኅብረትና በመንግሥት ይዞታ ሥር የሆኑበት ሶሻሊስት የምርት ግንኙነት የግል ባለንብረትነት በሰፈነበት ሥርዓት ውስጥ ሊያድግ አይችልም ። ሶሻሊዝም ይህን ዕድገት ሊያገኝ የሚችለው የፖለቲካ ሥልጣን በሠራተኛውና በአጋር መደቦች በተያዘበትና የማምረቻ መሣሪያዎች ከግል ባለቤትነት ተላቀው በምትኩ ንብረት የጠቅላላው ሕዝብ ማኅበራዊ ይዞታ በሚሆንበት ደረጃ ነው ። የዚህ የሽግግር ወቅት ማጠር ወይንም መርዘም እንደየሀገሩ ተጨባጭ ሁኔታ በተለይም የምርት ኃይሎች በደረሱበት የዕድገት ደረጃ ይወሰናል ። በኢንዱስትሪ እጅግ ወደፊት በተራመዱና የአመራረቱም ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ማኅበራዊ በሆነባቸው ሀገሮች የሽግግሩ ወቅት አጠር ያለ ሲሆን የኢኮኖሚ ደረጃቸው ዝቅተኛ የሆነ ሀገሮች ረዘም ባለ የሽግግር ወቅት ውስጥ ለማለፍ ይገደዳሉ ።

የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ሶሻሊዝምን የመገንባት ዓላማ ከመቅጽበት የሚሟላ ሳይሆን የረዥም ጊዜ ትግልን የሚጠይቅ ነው ። ምክንያቱም የሠራተኛው መደብ የግንባር ቀደም ፓርቲውን አመራር በመቀዳጀትና አጋር መደቦችን በአንድነት አሰልፎ በሚይዘው የፖለቲካ ሥልጣን ጠላቶቹን ሁሉ በቁጥጥሩ ሥር እያዋለ የበላይነቱን ለማረጋገጥ ፣ ከዚያም ባሻገር በታቀደ የግንባታ ትግል ማንኛውንም ብዝበዛ በማስወገድ የጋራ ብልጽግናውን የሚያዳብርበትን መሠረት ለማጠናከር ሰፊ ትግል ማካሄድ ስለሚያስፈልገው ነው ።

ሶሻሊዝምን ለመገንባት በሽግግር ወቅት ውስጥ የሚገኙ ሀገሮች ሁሉ ተግባራዊ ሊያደርጓቸው የሚገቡ ሕግጋት አሉ ። ከእነዚህም ሕግጋት መካከል ጭቁን ሕዝቦች በሠራተኛው መደብ ግንባር ቀደም ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ መሪነት የበላይነታቸውን ማረጋገጥን ፣ ለዚህም የሠራተኛውንና የገበሬውን አጋርነት ማጠናከርን ፣ የምርት ማከናወኛዎችን የጠቅላላው ሕዝብ ማኅበራዊ ይዞታ እያደረጉ ካፒታሊስት ግንኙነትን ማጥፋትን ፣ በዚህ ረገድ በገጠር ደረጃ በደረጃ የመንግሥት እርሻዎችንና የገበሬዎች አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማስፋፋትን፣ ማንኛውንም የመደብ ፣ የብሔረሰቦችና ሌሎችንም ጭቆናዎች ለማስወገድ መሠረታዊ ለውጦች ማድረግን የመሳሰሉት ዋንኛውን ቦታ የሚይዙ ናቸው ። ደረጃ በደረጃ በባህል መስኮች አብዮት ማካሄድ ፣ በወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት በመመራት ከሶሻሊስትና ከተራማጅ ኅብረተሰቦች ጋር ትብብርን ማስፋፋትም በዚሁ ትግል ውስጥ ይጠቃለላሉ ።

የሽግግር ወቅት ኢኮኖሚ ቀደም ያሉት የምርት ግንኙነቶች ሙሉ በሙሉ የማይወገዱበትና አዲሱም ገና ያልተስፋፋበት በመሆኑ ቅይጥ ይዞታ የሚታይበት ነው ። እነዚህም ዋና ዋናዎቹ ይዞታዎች የሶሻሊስት ፣ የአነስተኛ ሸቀጥ አምራችና የካፒታሊስት ይዞታዎች ናቸው ። የሶሻሊስት ይዞታ ገና በማደግ ላይ ቢሆንም የመንግሥትና የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ንብረቶች የሚያጠቃልልና ለዕድገትም ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ክፍል በመሆኑ በሽግግር ወቅትም ቢሆን መሪ ሚና ይጫወታል ። በአነስተኛ የሸቀጥ አምራችነት የሚከሰሉት ደግሞ አብዛኛውን የገበሬውን ክፍል ፣ የእደ ጥበብ ባለሙያዎችንና የአነስተኛ ነጋዴዎችን ፣ የሰዎችን ጉልበት በመበዝበዝ ሳይሆን በራስ ጥረት የሚጠቀሙ የጐጆ ኢንዱስትሪዎችን በመሳሰሉት ሥራዎች የተሰማሩትን ይይዛሉ ። ሦስተኛው በዚህ ደረጃ ጨርሶ ያልተወገደውና በዲሞክራሲያዊ አብዮት መመሪያ ገደብ የሚሠራው የካፒታሊስት ይዞታ በገጠርና በከተማ የሚገኙትን ከፍተኛ ባለንብረ

ቶች (ቡርዧዚዎች) ያቀፈ ነው ። ይህም በከተሞች ውስጥ የግል ባለኢንዱስትሪዎችን ፥ ትላልቅና መካከለኛ ነጋዴዎችን ፥ በገጠር ደግሞ ቀጥረው የሚያሳርሱ ሀብታም ገበሬዎችን ያጠቃልላል ። ከነዚህ ዋነኛ ይዞታዎች በተጨማሪ በሽግግር ላይ ባሉ በአንዳንድ ሀገሮች እጅግ ኋላ ቀር የሆነ (አባዊ) የኢኮኖሚ ግንኙነት ሊኖር ይችላል ። ይህም ከገበያ ጋር ምንም ዓይነት ወይም በጣም ዝቅተኛ የሆነ ግንኙነት ያላቸውን የገጠር ነዋሪዎች ያቀፈ ነው ። ይበልጡንም ይህን የመሰለው ኢኮኖሚ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚታየው ዘላኖችንና አንዳንድ አናሳ ብሔረሰቦችን ይመለከታል ።

በዚህ የሽግግር ደረጃ የመደብ አሰላለፍና የኃይል ሚዛን እንደዚሁም የመደብ ትግሉ ዓይነት ይለያይ እንጂ ተፃራሪ መደቦች ይኖራሉ ። የሽግግር ወቅት መሠረታዊ ቅራኔ በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም ማለትም በቡርዧዚውና በወዝአደሩ መካከል ያለው ቅራኔ ነው ። በሌላ በኩል እጅግ ወደፊት በተራመደው የፖለቲካ መዋቅርና ገና ኋላቀር በሆነው ኢኮኖሚ መካከል መሠረታዊ ያልሆኑ ቅራኔዎች ይኖራሉ ። እንደዚሁም ሰፋፊ የመንግሥት እርሻዎችና ዘመናዊ የኢንዱስትሪ ይዞታዎችና የተበታተኑ የአነስተኛ ገበሬዎች እመራረት በአንድነት መታየታቸውም ሌላ የዚሁ ዓይነት ቅራኔ የሚታይበት መስክ ነው ።

ቅድመ ካፒታሊስት የምርት ግንኙነት የሰፈነባቸው ሀገሮች ሶሻሊዝምን ዘላቂ ግባቸው አድርገው ከታገሉና ለዚህም በሠርቶ አደሩ ሕዝብ የበላይነት የምርት ኃይሎችን የሚያሳድጉና ከብዝበዛ ነፃ የሆነ የምርት ግንኙነት የሚያሰፍኑ ሥር ነቀል ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦችን በማድረግ ዕድገታቸውን እያቀዱ እስከተራመዱ ድረስ ካፒታሊዝምን ዘልለው ወደ ሶሻሊዝም ሊሸጋገሩ እንደሚችሉ ማርክሲዝም ሌኒኒዝም በተግባር አረጋግጧል ። ቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ በአብዛኛው የፊውዳል ምርት ግንኙነት ሰፍኖባት የነበረች ሀገር ስትሆን ዛሬ የዘውድ አገዛዝ ተገርስሶ ለሠራተኛው መደብ ሥልጣን መያዝ አመች ሁኔታ የተፈጠረባት ፥ መሬት ለአራሹ የሆነባት ፥ ባንኮችና ኢንዱስትሪዎች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የዋሉባት ፥ ሕዝባዊ ድርጅቶች የተቋቋሙባት ፥ በአጠቃላይ ሥር ነቀል ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አብዮት ያካሄደችና የካፒታሊስት የዕድገት ጐዳናን ሳትከተል ደረጃ በደረጃ ለሶሻሊዝም ግንባታ ሁለንታዊ መሠረት በምትጥልበት በሽግግር ሂደት ውስጥ የምትገኝ ሀገር ናት ።

(ለውጥን ፥ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ፥ ሶሻሊስት አብዮትን ፥ የወዝአደሩ የበላይ ገዥነትን ይመለከቷል ።)

## ሽፍን ተረፈ ሕዝብ
*(Latent Surplus Population)*

የአንፃራዊ ተረፈ ሕዝብ መልክ ሲሆን የሚያመለክተው ከውጭ ሲታይ ሙሉ በሙሉ በሥራ ላይ ያሉ የሚመስሉትንና ዳሩ ግን ለተሰማሩበት የሥራ መስክ ከሚያስፈልገው የሰው ኃይል ቁጥር በላይ በመሆናቸው ከዓቅም በታች እንዲያመርቱ የሚገደዱትን ነው ። ይህ የአንፃራዊ ተረፈ ሕዝብ መልክ ጐልቶ የሚታየው በገጠር አካባቢ በእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥ በመሆኑ አንዳንድ ጊዜ የእርሻ ተረፈ ሕዝብ በመባል ይታወቃል።

ሽፍን ተረፈ ሕዝብ የሚፈጠረው ካፒታሊዝም ወደ እርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ እየገባ ሲሄድ ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎችም ሥራ ላይ መዋል ስለሚጀምሩ ፥ ይህ ሁኔታ በእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ፍጹማዊና አንፃራዊ በሆነ መንገድ ለሥራ ኃይል ያለው ፍላጐት እየቀነሰ እንዲሄድ ስለሚያደርግ ነው ። በተጨማሪም ይህ የአንፃራዊ ተረፈ ሕዝብ መልክ አነስተኛ መሬት ስላላቸው ሊያመርቱ ከሚችሉት በታች እንዲያመርቱ የሚገደዱ ገበሬዎችንና የእደ ጥበብ ባለሙያዎችን ያጠቃልላል ።

የዚህ ዓይነቱ አንፃራዊ ተረፈ ሕዝብ ሽፍን የሚባልበት ዋናው ምክንያት ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ሳቢያ ትርፍ የሥራ ኃይል በእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ቢፈጠርና ገበሬዎቹ ወደ ሥራ አጥነት ደረጃ እንዲወርዱ ቢገደዱም በትናንሽ መሬቶች ላይ ሰፍረው በቂ ሥራ ያላቸው በመምሰል ስለሚቆዩ ነው ። ሽፍን ተረፈ ሕዝብ ከካፒታሊስት ስልተ ምርት ማቆጥቆጥ ጋር የሚከሰት በመሆኑ እንደ ዋነኛ የሥራ አጥነት መልክ ጐልቶ የሚታየው በኋላቀር ሀገሮች ውስጥ ነው ።

## ሾፐንሀወር ፥ አርተር
*(Schopenhauer, Arthur)*

ከ1788 — 1860 የኖረ ፥ በበርሊንና በፍራንክፈርት ያስተማረ ሐሳባዊ የጀርመን ፈላስፋ ነው ። ዕውቅ ጽሑፉም "ዲ ቬልት አልስ ቪለ ኡንት ፎርሽቴሉንግ" የሚባለው ነው ። ሾፐንሀወር መታወቅ የጀመረው ከ1848 አብዮት በኋላ ቡርዧዚው የሕዝቡን አብዮታዊ እንቅስቃሴ በመፍራት ወደ አድኅሮት ከተለወጠበት ወቅት አንሥቶ ነው ። ከዚህም የተነሣ አስተሳሰቡ ተፅዕኖ ማሳደር የጀመረው በኢምፔሪያሊዝም ወቅት ነው ። የቁስአካልነትና የዲያሌክቲክስ ተቃዋሚ በመሆኑ በዲበአካላዊ ሐሳባዊነት ሳይንሳዊውን የዓለም ግንዛቤ ይታገል የነበረ ነው ። የዓለም ውጫዊ ገጽታ የንቃተ ኅሊና ክስተት ነው የሚለውን የካንትን አመለካከት የተቀበለ ነገር ግን "ነገር በውስጡ" የሚለውን ጽንስ ሐሳብ በመተው የዓለም ፍሬ ነገር በጭፍንና በኢምክኑያዊ ፍላጎት የሚገዛ ነው የሚል እምነትም ነበረው ። ዓለምን የሚገዛው ፍላጎት ኢምክኑያዊ በመሆኑ ስለተፈጥሮና ስለ ኅብረተሰብ ሳይንሳዊ ግንዛቤ ሊኖር አይችልም ስለሚል የኢታዋቂነት ዝንባሌ ይታይበታል ። ስለሆነም የታሪክ ግስጋሴን መካድ፥ ለአብዮትና ለሕዝብ ካለው ጥላቻ የተነሣም ንጽረተ ዓለሙ በቀቢጸ ተስፋ ሥር መውደቅ የሾፐንሀወር አመለካከት ዓይነተኛ ባሕርያት ናቸው ። ኑሮን ፍች የሌለው አድርጎ ስለሚረዳም የአፍራሽነት ወይም የአውዳሚነት ስሜትና አስተሳሰብ አለው ።

ስለውበትም ያለው አመለካከት ተራማጁን ኪነት የታገለና በምትኩም እውነታን የሚያንቋሽሽበትንና ለሕዝቡ መሠረታዊ ጥቅም ያልቆመውን የሥነ ውበት መሥመር የሚያራምድ ነበር ።

(ፈቃዳዊነትን ፥ ኢምክኑያዊነትን ይመለከቷል ።)

# ቀ

## ቀላል ሥራ
(*Simple or Unskilled Labour*)

ቀላል ሥራ ለአንድ የተወሰነ የሥራ
ዘርፍ የተወሰነ ሥልጠናና ልምድ የማይጠ
ይቅ ሥራ ነው ። ጉድጓድ መቆፈር ፣ ዕቃ መሸ
ከም ፣ መላላክ ወዘተ...ልምድንና ሥልጠናን
የማይጠይቁ ሥራዎች በመሆናቸው የቀላል
ሥራ ምሳሌዎች ናቸው ። ቀላል ሥራ ሥል
ጠናንና ልምድን የማይጠይቅ ሥራ ነው በሚ
ባልበት ጊዜ የተወሰነ የምርት ኃይሎች ዕድ
ገትን መሠረት በማድረግ ነው ። የምርት
ኃይሎች እያደጉና የኅብረተሰቡ ባህል እየ
ዳበረ ሲሄድ ፣ ቀደም ሲል ልምድንና መጠ
ነኛ ሥልጠናን ይጠይቁ የነበሩ አንዳንድ
ሥራዎች ወደቀላል ሥራነት ሊለወጡ ይች
ላሉ ።

(ውስብስብ ሥራን ይመለከቷል ።)

## ቀላል የሸቀጥ ምርት
(*Simple Commodity Production)*

ቀላል የሸቀጥ ምርት ከጥንታዊ የጋር
ዮሽ ሥርዓተ ማኅበር ማክተሚያ ጀምሮ
የተከሰተ ፣ በጥቂት የምርት መገልገያዎች የግል
ባለቤትነትና በራስ ወይም በቤተሰብ ጉልበት
ላይ የተመሠረተ ነው ።

ቀላል የሸቀጥ ምርት በቅድመ ካፒታ
ሊስት ሥርዓተ ማኅበሮች ብቻ ሳይሆን በካ
ፒታሊዝምና ሶሻሊዝምን ለመገንባት ቅድመ
ሁኔታ በሆነው በሽግግርም ወቅት ውስጥ
ይቀጥላል ። ይሁንና በሽግግር ወቅትም ሆነ
በማናቸውም ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ቀላል
የሸቀጥ ምርት የኅብረተሰብን ዕድገት የሚ
መራና የሚወስን አይሆንም ።

ቀላል የሸቀጥ ምርት የገበሬውንና የእደ
ጥበብ ባለሙያውን ምርት የሚመለከት
ሲሆን የአነስተኛ ነጋዴውም ህልውና የሚከ
ስተው በዚሁ የሸቀጥ ምርት ወቅት ነው ።

ቀላል የሸቀጥ ምርት በባሪያ አሳዳሪ
ውና በፊውዳሉ ስልተ ምርቶች ውስጥ
ዓይነተኛ መለያ ባይሆንም በነዚህ ስልተ ምር
ቶች ውስጥ በዛ ያሉ አነስተኛ አምራቾች
በመኖራቸው ተስፋፍቶ ይገኛል ።

በካፒታሊስት ሥርዓት ቀላል የሸቀጥ
ምርት በጣም የቆረቆዘና አነስተኛ የሆነውን
የኅብረተሰብ ክፍል ያቀፈ ነው ። በጣም በዛ
ያለውን የኅብረተሰብ ክፍል በሚያቅፍበትም
ወቅት (ለምሳሌ ከቅድመ ካፒታሊዝም ወደ
ሶሻሊዝም በሚደረገው የሽግግር ወቅትና
በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዳለው
ሁኔታ ማለትም ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ
አብዮት እስከሚገባደድበት ጊዜ ድረስ)
ቀላል የሸቀጥ ምርት በአጠቃላይ ኢኮኖሚ
ውስጥ የመሪነትና የወሳኝነት ሚና አይኖረ
ውም ። ይህ የሚሆንበትም ምክንያት ቀላል
የሸቀጥ ምርት ለማደግ የሚያደርገው ጥረት
እራሱን የሚያቆረቁዘውና ከነአካቴውም ህል
ውናውን የሚያሳጣው በመሆኑ ነው ።

በቀላል የሸቀጥ ምርት ወቅት እያንዳ
ንዱ አምራች የሥራው ውጤት ባለቤት ከመ
ሆኑም በላይ ልውውጥ የሚካሄደው በመ
ሠረቱ ለትርፍ ሳይሆን ፍላጎትን ለማርካት
ነው ። ከዚህ በተጨማሪ በቀላል የሸቀጥ ምርት
ወቅት የሚመረተውም ምርት ኋላቀር በሆኑ
የምርት መሣሪያዎች በመሆኑ የሚገኘውም
ምርት ይህን ያህል አጥጋቢ አይሆንም ።
በቀላል የሸቀጥ ምርት ወቅት ቅጥር የሥራ
ኃይል ስለሌለ የሰው በሰው መበዝበዝ የተ
ለመደ አይደለም ።

(ካፒሊስታዊ የሸቀጥ ምርትን ፣ ሶሻሊስታዊ
የሸቀጥ ምርትን ይመለከቷል።)

## ቀላል እርባታ
(*Simple Reproduction)*

እርባታ ሳይስፋፋ ቀደም ሲል በነበረ
በት መጠን እንደገና የመታደሱ ሂደት ቀላል
እርባታ ይባላል ።

በካፒታሊዝም ክልል ውስጥ የቀላል
እርባታ ጽንስ ሐሳብ የሚያመለክተው የተ

መረተውን ተረፈ እሴት ቡርዧዚው ሙሉ በሙሉ ለኢምርታዊ ፍጆታ የሚያውለው መሆኑን ነው ። ይህም ማለት ለምሳሌ ቡርዧዚው በዓመቱ መጨረሻ ላይ ያገኘው ተረፈ እሴት በትርፍ መልክ ብር 10,000 ሆኖ በዚህ ብር ተጨማሪ የምርት መሣሪያዎች ሳይገዛበት ወይንም ተጨማሪ ወዝአደር ሳይቀጥርበት ሙሉ በሙሉ ለራሱና ለቤተሰቦቹ ልብስ ፣ የቤት ዕቃና የመሳሰሉትን ለኢምርታዊ ፍጆታ የሚውሉ ሸቀጦችን የገዛበት እንደሆነ ነው ። ይሁንና ቡርዧዚው በመጀመሪያው ዓመት ያወጣው ካፒታል መጠን ብር 50,000 ከሆነና በአምስት ዓመታት በየዓመቱ ያገኘውን ብር 10,000 ትርፍ ለኢምርታዊ ፍጆታ በማዋል የምርቱ ተግባር ቀደም ሲል በነበረበት ደረጃ እንዲቀጥል ቢያደርግ ዋናውን በ5 ዓመት ጊዜ ውስጥ ይመልሳል ።

ቀላል እርባታ በካፒታሊዝም ውስጥ በእያንዳንዱ የካፒታሊስት የምርት ተቋም ወይንም አልፎ አልፎ ለአጭር ጊዜ በመላው የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ሊታይ ቢችልም በመሠረቱ በካፒታሊዝም ውስጥ የሚገኘው የእርባታ ዓይነት የተስፋፋ እርባታ ነው ። ካርል ማርክስ የተስፋፋ እርባታ የሚካሄድበትን ሁኔታ ለመመርመር ከቀላል እርባታ ትንታኔ የጀመረውም ለዚህ ነው ።

የሸቀጥ ምርት ዋንኛውን የምርት መልክ በያዘበት በካፒታሊዝም ውስጥ እርባታ በምርትና በዝውውር ሂደት ጥምረት የሚገለጽ ነው ። በዚሁ መሠረት ካርል ማርክስ በካፒታሊስት የተስፋፋ እርባታ ሥር የምርቱና የዝውውሩ ሂደት ጥምረት ምን እንደሚመስል ለማሳየት ትንታኔውን የጀመረው ቀላል እርባታ እንደጠቅላላው የካፒታሊስት የእርባታ ባሕርይ እንደሆነ ፣ በካፒታሊዝም ውስጥ ሁለት መሠረታዊ መደቦች ብቻ እንዳሉና የተመረተው ሸቀጥ የሚዘዋወረው ባንድ ሀገር ክልል ውስጥ ብቻ እንደሆነ በመገመት ነው ። ይህንኑ ትንታኔ በትክክል ማስተዋል ይቻል ዘንድ ጠቅላላው ማኅበራዊ ምርት በቁሳዊ መልኩ ሲታይ በምርት ማከናወኛ መሣሪያዎች (ክፍል አንድ) የምርት ዘርፍና በፍጆታ ዕቃዎች(ክፍል ሁለት) የምርት ዘርፍ የሚከፈል መሆኑን በቅድሚያ ማጤኑ ጠቃሚ ይሆናል ።

ክፍል አንድ ፤*

$4{,}000\ \text{ቋካ}^{1}+1{,}000\ \text{ተካ}^{1}+1{,}000\ \text{ተእ}^{1}=6{,}000\ \text{ጠም}^{1}$

ክፍል ሁለት ፤

$2{,}000\ \text{ቋካ}^{2}+500\ \text{ተካ}^{2}+500\ \text{ተእ}^{2}=3{,}000\ \text{ጠም}^{2}$

በዚህ አኀዛዊ ምሳሌ መሠረት በኅብረተሰቡ ውስጥ ጠቅላላ እሴታቸው 9,000 የሆኑ ሸቀጦች ሲመረቱ ከዚህ ውስጥ እሴታቸው 3,000 የሆነው ለኢምርታዊ ፍጆታ የሚውሉ ሸቀጦችና እሴታቸው 6,000 የሚሆነው ደግሞ ጥሬ ዕቃዎች ፣ የማምረቻ መሣሪያዎችና የኃይል ማመንጫዎች የመሳሰሉት ለምርት የሚያገለግሉ ሸቀጦች ናቸው ። ጠቅላላው ምርት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የተመረተውን ሸቀጥ መጠን የሚያሳይ ነው ብንል በዚያ አንድ ዓመት ውስጥ በወጣው የሥራ ጊዜ የተመረተው አዲስ እሴት በሁለቱ የኢኮኖሚ ክፍሎች የተሰማሩ ወዝአደሮችና ቡርዧዚዎች በምንዳና በትርፍ መልክ የወሰዱት 3,000 ያህል ሲሆን የተቀረው 6,000 ግን ቀደም ባለው ጊዜ የተመረተው በሁለቱ የኢኮኖሚ ክፍሎች በቋሚ ካፒታል መልክ የነበረውና እሴቱን በምርቱ ሂደት ውስጥ በሥራ ኃይል አማካይነት አዲስ ወደተመረቱት ሸቀጦች ያስተላለፈው ነው ።

ቀደም ሲል በካፒታሊዝም ውስጥ ያለው ቀላል እርባታ ቡርዧዚው የተመረተውን ተረፈ እሴት በሙሉ ለኢምርታዊ ፍጆታ ሲያውለው ነው ባልነው መሠረት የተመረተው ሸቀጥ ገበያ አግኝቶ ምርቱም ቀደም ሲል በነበረበት ደረጃ መታደስ የሚችለው የሚከተሉት ሦስት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ነው ።

ሀ/ በክፍል ሁለት የተመረተው ለኢምርታዊ ፍጆታ የሚውለው ሸቀጥ መጠን በሁለቱ የኢኮኖሚ ክፍሎች ከተሰማሩ ቡርዧዚዎችና ወዝአደሮች ጠቅላላ ገቢ ጋር እኩል ሲሆን (ቡርዧዚው ያገኘውን ትርፍ ሙሉ በሙሉ ለኢምርታዊ ፍጆታ ያዋለው በመሆኑና የወዝአደሩም ገቢ

---

*ቋካ = ቋሚ ካፒታል
ተካ = ተለዋዋጭ ካፒታል
ተእ = ተረፈ እሴት
ጠም = ጠቅላላ ምርት

ከመሠረታዊ ፍላጐቱ እርካታ በላይ ሆኖ ለክምችት የሚውል ባለመሆኑ ፤ (በምሳሌያችን መሠረት ፤ ክፍል ሁለት) ጠቅላላ ምርት (3,000)= ክፍል አንድ 1,000 ተካ+ 1,000ተእ+ ክፍል ሁለት 500ተካ+ 500 ተእ

ለ/ በክፍል አንድ የተሰማሩ ቡርዧዚዎችና ወዝአደሮች ባገኙት ገቢ ከክፍል ሁለት የሚገዟቸው የፍጆታ ዕቃዎች እሴትና ምርቱን ቀደም ሲል በነበረበት ደረጃ እንዲታደስ ለማድረግ ክፍል ሁለት ከክፍል አንድ መግዛት ከሚያስፈልገው የምርት መገልገያ መሣሪያ ዎች እሴት እኩል ሲሆን ፤ ለምሳሌ ፦ ክፍል አንድ(1,000ተካ +1,000 ተእ)= ክፍል ሁለት (2,000ቋካ)

ሐ/ የክፍል አንድ ጠቅላላ ምርት መጠን የሁለቱ ኢኮኖሚ ክፍሎችን የቋሚ ካፒታል (መሣሪያዎች ፣ ጥሬ ዕቃዎች ወዘተ...) ፍላጐት ቀደም ሲል በነበረ በት ደረጃ ማሟላት ሲቻል ነው ።

ለምሳሌ ፦
ክፍል አንድ ጠቅላላ ምርት (6,000)= ክፍል አንድ (4,000ቋካ) + ክፍል ሁለት (2,000ቋካ)

ይሁንና በካፒታሊዝም ውስጥ የምርት መሠረታዊ ዓላማ ትርፍን ማጋበስ ስለሆነና በተለያዩ የኢኮኖሚ ክፍሎች መካከል ቅንጅት ባለመኖሩ በእነዚህ ከላይ በጠቀስናቸው ሦስት ሁኔታዎች መካከል ተመጣጣኝነት ሊኖር አይችልም ። ይህም በካፒታሊዝም ውስጥ ለሚከሰተው ቀውስ አንድ ዓይነተኛ ምክንያት ነው ።

(እርባታን ፣ የተስፋፋ እርባታን ይመለከቷል ።)

## ቀላል የካፒታሊስት ትብብር
*(Simple Capitalist Co-operation)*

በኢንዱስትሪ ዘርፍ ካፒታሊዝም ማቆጥቆጥ የጀመረበት የአመራረት ስልት ሲሆን በአንድ ወይም በተያያዘ የምርት እንቅስቃሴ ሂደት በዛ ያሉ ሰዎች በአንድ ላይ ተሰብስበው የሚሠሩበት የሥራ አደረጃጀት ነው ።

ቀላል የካፒታሊስት ትብብር ከቀላል የሸቀጥ አመራረት ያደገ ሲሆን ከቀላል የሸቀጥ አመራረት የሚለይበትም በአንድ በተወሰነ የምርት እንቅስቃሴ ውስጥ በአንድ ቦታ ተሰብስበው በአንድ ካፒታሊስት ይዞታና በሱም ቁጥጥር ሥራ በሚሠሩት ሰዎች ብዛት ነው ። በቀላል የካፒታሊስት ትብብር የአመራረት ደረጃ የምርት መገልገያ ዎች ባለቤት የሆነው ካፒታሊስቱ ከፍተኛ ትርፍ ይሰበስባል ።

በዚህ ደረጃ የሥራ ክፍፍል የለም ፤ ሁሉም ሠራተኞች ተመሳሳይ ሥራ ይሠራሉ ። ሆኖም ግን ከእደ ጥበብ ምርት ይልቅ ቀላል የካፒታሊስት ትብብር ከፍተኛ ዕድገት አሳይቷል ። በአነስተኛ የሸቀጥ ምርት ወቀት ጐልቶ ይታይ የነበረው በግልና ማኅበራዊ ተቀባይነት ባለው የሥራ ጊዜ መካከል የነበረው ልዩነት በቀላል የካፒታሊስት ትብብር ወቅት እየጠበበ ከመሄዱም በላይ የምርት መገልገያዎች በቁጠባ ሥራ ላይ እንዲውሉ አመች ሁኔታን ፈጠረ ። ለምሳሌ ሃያ ሰዎች ሊያሠራ የሚችል አንድ የሥራ ቦታ ማቋቋም ሁለት ሰዎች ሊያሠሩ የሚችሉ አሥር የተለያዩ የሥራ ቦታዎች ከማቋቋም ይቀላል ።

ቀላል የካፒታሊስት ትብብር ላልተቋረጠ የሥራ እንቅስቃሴ አመች ከመሆኑም በላይ ይህ ዓይነት አመራረት ከዚያ በፊት ከነበረው አመራረት የሥራ ምርታማነት በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምር አድርጓል ። በዚህም ሂደት የሥራ ኃይሉን እሴት በመቀነስ የእንፃራዊ ተረፈ እሴት መጠን እንዲጨምር አድርጓል ። በዚህ ደረጃ ካፒታሊስቶች ለተጨማሪ ተረፈ እሴት ያደረጉት ውድድርና ይኸው ውድድር ያስከተለው የምርት ኃይሎች ዕድገት ቀላል የካፒታሊስት ትብብርን ወደ መፈብረክ ደረጃ አሸጋግሯል ።

(ቀላል የሸቀጥ ምርትን ፣ መፈብረክን ይመለከቷል ።)

## ቀኖናዊነት
*(Dogmatism)*

በፍልስፍናና በሳይንስ ሁኔታዎችንና ነገሮችን ከስፍራና ከጊዜ ውጭ በመውሰድ እንደማይለወጡ ፣ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንደተሰጡ አድርጐ የሚወስድ ፣ የእውነትን ተጨባጭነት የሚክድ ፣ ጊዜ ባለፈባ

ቸው አስተሳሰቦች የሚመራ አመለካከት ወይም አስተሳሰብ ቀኖናዊነት ይባላል ። ቀኖናዊነት መጠየቅንና መመራመርን ከሚፃረረው ከጭፍን አምልኮትና ከእምነት (ሃይማኖት) ጋር በቅርብ የተዛመደ ነው ። በዘመናችን ቀኖናዊነት ዓለም ፣ ኅብረተሰብ ፣ እውነታ ይለወጣሉ ፣ ያድጋሉ የሚለውን ማርክሳዊ ትምህርት የሚቃረን የቡርዧ አስተሳሰብ ነው ። በወዝአደር እንቅስቃሴ ውስጥ ቀኖናዊነት የሚከሰተው ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ከጊዜና ከስፍራ ውጭ ቀድሞ እንደነበረ ወይም በሌላ ስፍራና ሀገር በሥራ ላይ እንደዋለ ልክ በዚያው ሁኔታ ሥራ ላይ አውለዋለሁ ወይም እንደነበረ እጠብቀዋለሁ የሚል የተሳሳተ ግትር አስተሳሰብና አቋም ነው ። ቀኖናዊነት እንደበራዥነትና እንደከላሽነት ለዓለም አቀፋዊው የወዝአደር መደብ እንቅስቃሴ አንድነትና ጥንካሬ ጠንቅ ነው ። ቀኖናዊነት ቡድናዊነትንና ጠባብነትን በማበረታታትና በማስፋፋት የዓለምን ሠራተኛ እንቅስቃሴ ይከፋፍላል ። ቀኖናውያን ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ከተጨባጭና ከተንቀሳቃሽ ሁኔታ ጋር እንዳልተያያዘ አድርገው በመመልከት ወደ ሐሳባዊነት ፣ ወደ ፀረ ዲያሌክቲካዊነት ወይም ወደ ዲበአካላዊነት ይለውጡታል ። በአለንበት ወቅት በሶሻሊስት ሀገሮች ተጨባጭ ሁኔታና በዓለም አቀፍ ክስተቶች ላይ ትኩረት ከማድረግና እነዚህን ነባራዊ ሁኔታዎች ተንትና በመገንዘብ ትክክለኛና ሳይንሳዊ አቋም ከመውሰድ ይልቅ ቀኖናውያን በሰላም አብሮ መኖር ፣ ሰላማዊ ውድድር ፣ ሰላማዊ የሽግግር ወቅት የተሰኙትንና የመሳሰሉትን የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መመሪያዎች ያንቋሽሻሉ፤ ይጥሳሉ ። በዚህም ድርጊታቸው ምዝብሮችና ጭቁኖች ከኢምፔሪያሊዝምና ከአድኅሮት ጋር የሚያካሂዱትን ትግል ያዳክማሉ ።

(አድርባይነትን፣ሐሳበ ግትርን ይመለከቷል ።)

## ቀውስ

*(Crisis)*

በመጨመርና በመከማቸት ላይ ባለው የምርት መጠንና ውሱን በሆነው የሠራተኛው የመግዛት ኃይል መካከል ያለመጣጣም በመፈጠሩ ገበያ ያጡ ሸቀጦች ምርት እንዲቀንስ ወይም ጨርሶ እንዳይመረት የሚደረግበት ፤ ከዚህም የተነሣ ሠራተኛው በገፍ ከሥራ ገበታው የሚባረርበትና የኑሮ ደረጃውም ከወትሮው የሚያሽቆለቁልበት የኢንዱስትሪ ዑደት የመጀመሪያ ደረጃ ቀውስ ይባላል ።

በማደግ ላይ ባለው የምርት መጠንና ውሱን በሆነው የሠራተኛው ሕዝብ ሸቀጣሸቀጦችን የመግዛት ኃይል መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርስ ቀውስ ይፈጠራል ። ካፒታሊስቶች ትርፍ ሊያስገኙ የሚችሉ ሸቀጦቻቸውን መሸጥ ሲያቅታቸው የሸቀጦች ክምችት መጠን ያድጋል ። ካፒታሊስቶችም ምርታቸውን ለመሸጥ በመካከላቸው በሚያደርጉት ከፍተኛ ውድድር ምክንያት የሸቀጦች ዋጋ ያሽቆለቁላል ። በዚህም የተነሣ የሚያስመርቱትን ሸቀጥ መጠኑን ይቀንሳሉ ወይንም ማስመረቱን ከነጭራሹ ያቆማሉ ።

በገበያ መቀዛቀዝና በሚመረተው ሸቀጥ መጠን መቀነስ ምክንያት የካፒታሊስት ድርጅቶች ከባንኮችና ከሌሎች ድርጅቶች የተበደሩትን ብድር መክፈል ያቅታቸዋል ። ይህም የባንኮችን ክስረት ሊያስከትል ይችላል የሚል ፍርሀት ስለሚፈጥር በባንኮች ተቀማጭ ገንዘብ ያላቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች ገንዘባቸውን ከባንክ እንዲያወጡ ይገፋፋቸዋል ። በአንድ በኩል የንግድና የባንክ ብድር መጠን እየቀነሰ ሲሄድ በሌላ በኩል ደግሞ የብድር ፍላጎት እያደገ ስለሚሄድ የብድር ወለድ መጣኔ ከፍተኛ ዕድገት ያሳያል ። በዚህ አኳኋን ቀውሱ በንግድና በኢንዱስትሪ ብቻ ሳይወሰን የገንዘብና የብድር ሥርዓቶችንም ይነካል ። በአጠቃላይ በቀውስ ጊዜ ማኅበራዊ የማምረት ሥርዓት ዝውውርና ልውውጥ ይናጋል ።

በቀውስ ጊዜ በተለይም አነስተኛና መካከለኛ መጠን ያላቸው ብዙ አምራች ድርጅቶች ፣ የንግድ ድርጅቶችና ባንኮች ከስረው ይዘጋሉ ። ቁጥራቸው እጅግ ከፍተኛ የሆኑ ወዝአደሮች ከሥራ ይባረራሉ ። የሥራ አጡ ቁጥር በይበልጥ ይጨምራል ። የሠራተኛውም ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ ያሽቆለቁላል ። ይህ ሁሉ የሠራተኛውን ሕዝብ የመግዛት ችሎታ የበለጠ ስለሚቀንሰው ካፒታሊስቶች አስመርተው በየመጋዘኑ ያከማቹትን ሸቀጥ በመሸጥ ረገድ ያለባቸውን ችግር ያባብሰዋል ።

በዚህን ጊዜ ካፒታሊስቶች የዋጋን ማሽቆልቆል ለመግታት ሲሉ አስመርተው በየመጋዘኑ ያከማቹትን ሸቀጣ ሸቀጥ በከፊል እስከማቃጠልና እስከማውደም ይደርሳሉ ። ሠራተኛው ሕዝብ ከባድ ችግር ላይ የወደቀ መሆኑን በመገንዘብ ካፒታሊስቶች ብዝበዛቸውን ያባብሱታል ። የሥራ ቦታም በበለጠ እስከፊና በበለጠ ለጤና ጠንቅ እንዲሆን ያደርጋሉ ። ካሽቆለቆለው የሠራተኛው ሕዝብ የመግዛት ኃይል ጋር በሚጣጣም መጠን የምርት ሂደትም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ቀስ በቀስ ይወድቃል ። በዚህ ደረጃ የሚመረተው የምርት መጠን ማሽቆልቆሉን ያበቃና የኢኮኖሚ ቀውስ ሁለተኛው ደረጃ የሆነው ዝቅጠት ይጀምራል ።

(የካፒታሊዝም የኢኮኖሚ ቀውስን ፣ ዝቅጠትን ይመለከቷል ።)

## ቀዝቃዛ ጦርነት
*(Cold War)*

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት (1939—1945) በኋላ በሶቭዬት ኅብረትና በሌሎች ሶሻሊስት ሀገሮች ላይ ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች የሚያካሂዱት አድኃሪ የማጥቃት ፖሊሲ ነው ። የቀዝቃዛ ጦርነት ዋና ዋና ፖሊሲዎች የተለያየ ማኅበራዊ ሥርዓት ባላቸው ሀገሮች መካከል በሰላም አብሮ የመኖር መርህ እንዳይኖር መቃወም ፣ ዓለምአቀፍ ውጥረት ይበልጥ እንዲባባስ ማድረግ፣ የተፋፋመ ፀረ ሶቭዬት ወታደራዊ ጉራ መመሥረት ፣ የመሣሪያ እሽቅድድምን ማጧጧፍ ፣ በሌሎች መንግሥታት ግዛቶች ውስጥ ወታደራዊ ሰፈርን መመሥረት ፣ ከፍተኛ ጥፋት በሚያስከትሉ የጦር መሣሪያዎች በመጠቀም ጦርነት ለመቀስቀስ መዛትና የዓለምን ኢኮኖሚ ግንኙነት በማደፍረስ በሌሎች ሀገሮች ላይ ደባ መፈጸምና በነርሱ ቁጥጥር ሥር እንዲሆኑ መሞከር ናቸው ። በዓለም መድረክ ላይ የፖለቲካ ሚዛን ወደ ሶሻሊዝም ማጋደሉ ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች የቀዝቃዛ ጦርነት ዓላማቸው የማይሳካ መሆኑን እንዲገነዘቡ አድርጓቸዋል ። በሶቭዬት ኅብረትና በሌሎች ሶሻሊስት ሀገሮች አነሣሽነት በ1970ዎቹ ጥቂት ስምምነቶችን ለማድረግም ተገደዋል ። ይህም ከቀዝቃዛው ጦርነት ወደ ዴታንት ፖሊሲ የማዘንበልን ምዕራፍ ከፍቷል ። ኢምፔሪያሊስቶች ወደ ቀዝቃዛው ጦርነት ለመመለስ ሙከራ ቢያደርጉም ሶሻሊስት ሀገሮችና ሌሎች ሰላም ወዳድ ኃይሎች ዴታንት ይበልጥ እንዲጠናከር ትግል በማካሄድ ላይ ይገኛሉ ።

(ዴታንትን ፣ በሰላም አብሮ የመኖር መርህን ይመለከቷል ።)

## ቀያጭነት
*(Eclecticism)*

ሊዛመዱ የማይችሉ ልዩ ልዩ ፍልስፍናዎችን ርዕዮተዓለሞችን ፣ እስተሳሰቦችንና መመሪያዎችን መራርጦ ለማስታረቅ የሚሞክር የፍልስፍና አመለካከት ነው ። ለምሳሌ ቁስአካልነትን ከሐሳባዊነት ፣ ማርክሲዝምን ከቡርዧ ርዕዮተዓለም ለማዛመድ ይሞክራል ። የቀያጭነት ዋና የአመለካከት ስህተት አንዱ ቁስአካል ወይም ክስተት በአንድ በተወሰነ ጊዜ ከአካባቢው ጋር ያለውን መሠረታዊ ግንኙነት ለይቶ ለማወቅ አለመቻሉ ነው ፤ ከዚህም የተነሣ የሁኔታዎችን ስንስስታዊ ግንኙነት ለማጤን ስለሚያዳግተው በአንድ ታሪካዊ ወቅት ለሚከሰቱ ችግሮች ተገቢ መፍትሔዎችን ለማግኘት ይሳነዋል ።

## ቀይ ጦር
*(Red Army)*

በመደብ ትግል ውስጥ ተፈትኖ ያለፈ ፣ በወዛደሩ ርዕዮተዓለም የታጠቀ ከሠራተኛው ፣ ከገበሬውና ከተቀሩትም ሠርቶ አደሮች ክፍሎች የተውጣጣ፣ በንቃቱና በውጊያ ችሎታውም ሆነ በሞራሉ ወደር የሌለው ፣ ለጭኑ ሕዝባዊ ዓላማ የቆመ ጥራትና ብቃት ያለው የሶሻሊስት ጦር ኃይል ነው ። ቀዩ ጦር በታሪክ የተከሰተው የሩሲያ ታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት ድል ባደረገ ማግስት ነበር ።

ቀዩ ጦር ለመጀመሪያ ጊዜ የራሱን መንግሥት በትግሉ የመሠረተውን የሩሲያን የሠራተኛና የገበሬ መደቦች ጥቅም የሚጠብቅ ሕዝባዊ ኃይል ሆኖ በኮሚኒስት ፓርቲው አመራር በሶቭዬት መንግሥት ተቋቋመ ። ቀዩ ጦር አዲሱን የሠራተኛውንና የገበሬውን መንግሥት ለመገልበጥ ያሴሩና ይፈታተኑ የነበሩትን የውስጥ ፀረ አብዮት ኃይሎችን

የደመሰሰና እንዲሁም የዚህን መንግሥት መቋቋምና መጠናከር አጥብቀው ይፃረሩ የነበሩትን የኢምፔሪያሊስት ጣልቃ ገብ ወራሪ ኃይሎች በመመከት የአብዮታዊት እናት ሀገሩን አንድነትና ነፃነት የመጠበቅ ታሪካዊ ኃላፊነቱን የተወጣ አብዮታዊ ኃይል ነበር ። ለዚህ ጦር መመሥረት ፓርቲውና መንግሥቱ ትኩረት በመስጠት ከሠራተኛው ፣ ከገበሬውና ከቀድሞው ሠራዊት መካከል ለአብዮቱ ዓላማ የቆሙትን ወገኖች በማደራጀት ቀዩን ጦር ለማቋቋም አዋጆች አወጡ ።

የቀዩ ጦር ዋና ዓላማ በመደብዊ ንቃት ላይ ተመሥርቶ ለሠራተኛው ሕዝብ ልዕልና እስከ መጨረሻው በመሥዋዕትነት መታገል ነበር ። ይህም ሠራዊት ከቡርዧው ነጭ አድኃሪ ሠራዊት በዓላማው ፣ በይዘቱና በአመለካከቱ ፍጹም የተለየ ፣ ብሔራዊና ዓለምአቀፋዊ ግዴታን በትክክል አጣምሮ የያዘ እንዲሁም የሰውን ልጅ ከብዝበዛና ከጭቆና ጨርሶ ነፃ ለሚያወጣው የኮሚኒስት ኅብረተሰብ ግንባታ የቆመ ኃይል ነበር ።

ይህም በሶቭዬት ኅብረት የመጀመሪያ የአብዮት እፍላ ዓመታት የተቋቋመው ቀይ ጦር በዚህ መጠሪያው እስከ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ድረስ ሊቆይ ችሏል ። ዛሬ በታሪክ ዕድገትና በሁኔታዎች መለወጥ ምክንያት ከጊዜው ጋር በሚስማማ መልክ ልቆ መደራጀቱ የግድ አስፈላጊ በመሆኑ ዓላማው፣ ይዘቱና ተልዕኮው ከቀድሞው የተለየ ባይሆንም የሶቭዬት ቀይ ጦር ዛሬ የሶቭዬት ጦር ኃይሎች በመባል ይታወቃል ። በሌሎች ሶሻሊስት ሀገሮችም ስያሜያቸው ይለያይ እንጂ በይዘትና በዓላማ ተመሳሳይ የሆኑና ይህንኑ ፈለግ የተከተሉ ጠንካራ የሶሻሊስት መከላከያ ኃይሎች ተደራጅተው ይገኛሉ ።

(አብዮታዊ ጦርን ይመለከቷል ።)

## ቁስአካል

*(Matter)*

ከኅሊና ውጭ የሚኖር ነገር ግን በኅሊና ውስጥ የሚንፀባረቅ ፣ ነባራዊ እውነታን የሚገልጽ የፍልስፍና ፈርጅ ነው ። ቁስአካል አላቂነት የሌላቸው የተለያዩ ነባራዊ ክስተቶችን ፣ ተገብሮችንና ሥርዓቶችን የሚያጠቃልል ሲሆን ለተለያዩ ግንኙነቶች ፣ መስተጋብሮችና ሁኔታዎች እንዲሁም ለእንቅስቃሴ የተለያዩ ቅርፆች መሠረት ነው ። ቁስአካልን ከተጨባጭ መልኩ ለይቶ ቅስቃሴ የሌለውና ልሙጥ የሆነ ነገር አድርጎ ማየት ስህተት ይሆናል ። ምክንያቱም ህልውናው የሚገለጸው በመዋቅራዊ አደረጃጀት ውስጥ በሚከሰቱ የተለያዩ ጭብጥ ቅርፆች በመሆኑ እነዚህ ቅርፆች የተለያየ ጠባይ ፣ ግንኙነትና የመዋቅር ውስብስብነት የሚያሳዩና የሌላም ከፍተኛ ሥርዓት አካል ናቸው ።

የቁስአካል ውስጣዊ ምንነቱ በተለያዩ ባሕርያቱና ግንኙነቶቹ የሚገለጽ በመሆኑ እነዚህን ባሕርያትና ግንኙነቶች ማወቅ ቁስአካልን ማወቅ ነው ። የቁስአካል የውስብስብነት ደረጃ ለባሕርያቱና ለግንኙነቶቹ መስፋፋትና መብዛት ምክንያት ነው ። ከውስብስብነቱ መጨረሻ ጫፍ ማለትም የማሰብ ችሎታ ካለው ሰውን ከመሰለ ፍጡር ላይ ሲደርስ የኅሊናዊ ክስተት ሁኔታ የተለየ ጠባይ ስለሚያሳይ ከቁስአካል ጋር ግንኙነት ያለው አይመስልም ። የኅሊናንና የቁስአካልን ግንኙነት ማጤን ስለተሳናቸው በሁለቱ መካከል የሚታየውን ልዩነት ፍጹማዊ በማድረግ የተለያዩ ሐሳባዊና ሁለንታዊ አስተምህሮዎች ሊከሰቱ ችለዋል ። በዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት አመለካከት በኅሊናና በቁስአካል መካከል ያለው ልዩነት አንፃራዊና ከሁኔታ የመነጨ ነው ። ልዩነቱ ፍች የሚኖረው ከፍልስፍና መሠረታዊ ጥያቄ አንፃር ሲታይ ነው ። ከዚህ ጥያቄ ከመነሣትና መልስ ከማግኘት ውጭ ልዩነቱ የራሱ የሆነ ፍች የለውም ።

በፍልስፍና የተረጋገጠው የቁስአካል ነባራዊነት በሳይንስ የተለያዩ ግኝቶች ተጨባጭነትና ተጨማሪ መረጃ አግኝቷል ። ሆኖም የፍልስፍና ፈርጁን ተፈጥሮአዊ ሳይንስ ከሚደርስባቸው የተለያዩ የቁስአካል መዋቅራዊ ህልውናዎች ጋር ማዋሀዱ ትክክል አይሆንም። ምክንያቱም የሳይንስ አዳዲስ ግኝቶች ስለ ቁስአካል ያለንን ዕውቀት በየጊዜው እየቀያየሩና ግንዛቤያችንን እያዳበሩ የሚሄዱ ሲሆን ፍልስፍናዊ ፍችው ግን ምንም ጊዜ የማይለወጥ ነው ። ቁስአካልን በሆነ የጭብጥ ቅርፅ (አቶም፣ ሞለኪዩል...) ወይም በሆነ ባሕርይ (ኃይል ፣ ቅስቃሴ...) መወሰን የማይቻል ነው ። ምክንያቱም ማንኛውም ነገር ወይም ክስተት ቁስአካላዊ ማለትም የቁስአካል አንዱ ገጽታ ከመሆን በስተቀር አጠቃሎ ቁስአካልን ሊወክል አይችልም ።

የዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት አመለካከት ዲበአካል ስለቁስአካል ከሚሰጠው ግንዛቤም የተለየ ነው ። የዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት አመለካከት ቁስአካል ነባራዊ ፣ ዘላለማዊና ከሰው ኅሊና ነፃ መሆኑን በመግለጽ ብቻ የሚወሰን አይደለም ። ቁስአካል ከቅስቃሴ ፣ ከቦታና ከጊዜ ውጭ እንደማይኖር እራሱን በራሱ ለማሳደግ የሚችልና በቁጥርም ሆነ በዓይነት አላቂነት የሌለው መሆኑን ጭምር ያስረዳል ።

ቁስአካላውያን ለቁስአካል የሚሰጡት ፍልስፍናዊ ፍች ቁም ነገር ያዘለ ነው ። በነሱ አመለካከት የዕውቀት ምንጭ ቁስአካል ነው ። ይህም ማለት በኅሊናችን ውስጥ የሚቀረፀው ማንኛውም ሐሳብ ሁሉ የሚያመለክተው ከኛ ውጭ የሚገኘውን እውነታ ነው ። የቁስአካል ነባራዊነት ነው ዕውቀትን ነባራዊ የሚያደርገው ። የዕውቀትም ሳይንሳዊነት የሚመነጨው ከቁስአካል ነው ። ምክንያቱም ከአምልኮ ፣ ከሐሳባዊና ከሃይማኖታዊ አመለካከት ለመላቀቅ የምንችለውና ዕውቀታችንም ሙሉ ተግባራዊነት የሚኖረው የእውነታን ቁሳዊነት ስንቀበል ነው ። በተለይም አንድ ነገር አለ ለማለት የሚቻለው ለሕዋሳት ሲገለጽ ብቻ በመሆኑ ቁሳዊነት ሳይኖራቸው ነገር ግን አሉ ፣ ይኖራሉ ለሚባሉት ነገሮች የቁስአካል ብቸኛ ነባራዊነት ቦታ አይሰጣቸውም ፤ ስለዚህ የቁስአካል ጽንሰ ሐሳብ ከእምነት የሚያላቅቀን ነው ። ቁስአካል እንደመንፈስ የራሱ ፍላጐት ፣ ምኞትና ውሳኔ ኖሮት ሰውን የሚያዝ ባለመሆኑና በነባራዊነቱ ብቻ የቆመ በመሆኑ ሰው በራሱ ፍላጐት የሚኖር ፣ የራሱ ገዥና የዕድሉ ወሳኝ መሆኑን የሚያረጋግጥ የሰው ነፃነት መሠረት ነው ።

(ፍልስፍናን ፣ ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነትን ፣ ዲበአካልን ፣ ነባራዊ እውነታን ይመለከቷል።)

## ቁስአካልነት
*(Materialism)*

የቁስአካልነት አጠቃላይ ፍቺና ሚና የሚገለጸው ከሐሳባዊነት ጋር ካለው ልዩነትና ትግል አንፃር ነው ። ማንኛውም የአስተሳሰብ ሆነ የተግባር ጥያቄ ተቃራኒ በሆኑ ሐሳባዊና ቁስአካላዊ መልሶች ይተረጐማል ። በመሆኑም የቁስአካልነት ምንነት የሚገለጸው ከሐሳባዊነት በሚለዩት ጠባዮች ነው ።

ቁስአካልነት የተመሠረተው ዓለም ቁሳዊ ባሕርይ ያለውና ቁስአካልም ያልተፈጠረና ዘላለማዊ የሆነ ኑባሬ ነው በሚለው አስተምህሮ ላይ ነው ። ማንኛውም ነገር ቁስአካላዊ ሆነ መንፈሳዊ የሚመነጨውና የሚያድገው ከቁስአካልና እሱን ከሚገዙ ሕጎች ነው ። ነገሮች ሁሉ የቁስአካል የተለያዩ መልኮች ናቸው ። ቁስአካል ነባራዊ እውነታ ነው ፤ ከሐሳብ ፍላጎት ውጭ የሆነ ነፃ ህልውና ያለው ነው ። የቁስአካል ነባራዊነት የሰውን ልጅ ዕውቀት ነባራዊ ያደርገዋል ። ዓለምና ዓለምን የሚገዙ ሕጎች በሰው ሊታወቁ ይችላሉ ።

ቁስአካልነት ሰዎች በአጠቃላይ ሳይንሳዊ አመለካከት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ነው ። ማለትም ከሐሳቦች ውስጥ ሰዎች ተጨባጭ የሆኑትንና በተግባር ሊረጋገጡ የሚችሉትን ሐሳቦች እንዲመርጡ ያደርጋቸዋል ። ቁስአካልነት መንፈሳዊ ዓለም የሚባል የለም የሚል በመሆኑ ሰዎች ሙሉ ትኩረት ለምድራዊ ኑሮ ብቻ እንዲሰጡ ያደርጋል ፤ እሱንም እንዲያሻሽሉና እንዲለውጡ ይገፋፋቸዋል ። ማለትም ሰዎች ተራማጅ የሆኑ አስተሳሰቦች እንዲኖራቸው ያደርጋል ።

ቁስአካልነት ለማንኛውም ነገር ቁሳዊ መሠረት ስለሚሰጥ ነገሮችን በተግባር ለመለወጥ ያለንን ችሎታ ያስገነዝበናል ፤ በራሳችንም ኃይል እንድንተማመን ያደርገናል ። ለሁሉ ነገር ቁሳዊ ምክንያት ስለሚሰጥና ዓለምን ታዋቂ ስለሚያደርግ የሐሳባውያንን ምሥጢራዊነትና ተማልሎአዊነት ያስወግዳል። መንፈሳዊ ምክንያቶችን በማስወገድ ሰዎችን ከአምልኮት ፣ ከጭፍን ተቀባይነትና ከፍርሃት ያላቅቃል ። አብዮታዊ አመለካከት ኖሯቸው ታጋይ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል ። ቁስአካልነት የሰዎችን ነፃነት ፣ ክብርና ደስታ የምናየውና የምንገመግመው ከተጨባጩ ብቻ ተነሥተን መሆኑን ያስተምረናል ። ምክንያቱም ቁም ነገሩ ሰው በሐሳቡ ስለራሱ ያለው አስተያየት ሳይሆን በቁሳዊነቱ ማለትም በእውን የሚገኝበት ሁኔታ ነው ።

ከላይ የተጠቀሱትን የቁስአካልነት ጠባዮች ስንመለከት ይህ ፍልስፍና ለሠራተኛ መደብ ነፃ መውጣት አስፈላጊና አመች አመለካከት እንደሚሰጥ በቀላሉ እንረዳለን ።

(ቁስአካልን ፣ ሐሳባዊነትን ይመለከቷል ።)

## ቁርጥ ሥራ ምንዳ (የ—)
*(Piece–Wages)*

በተወሰነ ሥራ ውጤት መሠረት ለወዝ አደሩ ክፍያ የሚደረግበት አንድ ዓይነት የምንዳ መልክ ነው ። ለምሳሌ ክፍያው በተ መረተ ጥንድ ጫማ ቁጥር ፣ በታሸገ ፓኮ ቁጥር ፣ በጣቃ ጨርቅ ብዛት ፣ በተጫነ ዕቃ ክብደትና በመሳሰሉት መሠረት ይደረጋል ።

የቁርጥ ሥራ ምንዳ የጊዜ ምንዳ የተለ ወጠ መልክ ነው ። ምክንያቱም ቡርዧዚው ክፍያውን ከጊዜ ምንዳ ወደ ቁርጥ ሥራ ምንዳ ከመለወጡ በፊት በጣም ጠንካራ የሆኑ ወዝአደሮች በቀን የሚያመርቱትን ምርት መጠን የሥራ ጊዜን መሠረት በማ ድረግ ከሚከፍለው ምንዳ ጋር አነፃፅሮ መጣኔውን የሚያወጣ ስለሆነ ነው ።

ለምሳሌ አንድ የጫማ ፋብሪካ ያለው ቡርዧዚ አከፋፈሉን ከጊዜ ወደ ቁርጥ ሥራ ምንዳ ለመለወጥ ፈለገ እንበል ። ይህን ለማ ድረግ ግን ለአንድ ጥንድ ጫማ ስፌት ፣ ለቆዳ መቁረጥ ፣ ለአንድ ጥንድ ጫማ ማሸግ ስንት እንደሚከፍል መወሰን አለ በት ። ከላይ ባነሣነው መንገድ ቡርዧዚው ለነዚህ ሥራዎች መጣኔ የሚያወጣው ቀደም ሲል በየክፍሉ ከነበሩት ወዝአደሮች መካከል ጠንካሮቹ በቀን ምን ያህል እንደሚያመር ቱና ለዚያ ምን ያህል ይከፈላቸው እንደ ነበር አስልቶ ነው ። በስፌት ክፍል ያለ ጠንካራ ወዝአደር በቀን አራት ጥንድ ጫማዎች የሚሰፋ ከሆነና በወር የሚያገ ኘው ምንዳ በየቀኑ ከሚያመርተው ምርት መጠን ጋር ሲነፃፀር ለእያንዳንዱ ጥንድ ጫማ ብር 0.50 ሲከፈለው የነበረ ከሆነ ቡርዧዚው ይህንን የአዲሱ ክፍያው |መጣኔ ያደርገዋል ማለት ነው ።

የቁርጥ ሥራ ምንዳ እንደአንድ የምንዳ መልክ ጉልቶ የታየው ቡርዧዚው የወዝ አደሩን የቀን ሥራ ሰዓት እንደፈለገው ማራ ዘምና ማሳጠር ባልቻለበት ፣ በወዝአደሩና በቡርዧዚው መካከል የሚደረገው የመደብ ትግል እየተፋፋመ በመጣበት በካፒታሊስት ዕድገት ደረጃ ላይ ነው ። የቁርጥ ሥራ ምንዳ ከጊዜ ምንዳ ይልቅ የወዝአደሩን መበዝበዝ ይሸፍናል ። ምክንያቱም ክፍያው የተወሰነ ሥራ መጠን ሲፈጸም የሚደረግ በመሆኑ ወዝአደሩ ለደከመበት ሁሉ የሚከፈለው ስለሚያስመስል ነው ።

(የጊዜ ምንዳን ይመለከቷል ።)

## ቅስቀሳ
*(Agitation)*

አንድ ወይም ብዙ ሐሳቦችን ስሜት በሚነካ ሁኔታ በማቅረብ የአድማጭንና የተመልካችን መንፈስ በማነሣሣትና በማነ ቃቃት ለእርምጃ ወይም ለተግባር መጋበዝ ቅስቀሳ ይባላል ። ቀስቃሹ የሚያቀርበው ሐሳብ በአድማጩ ዘንድ ይበልታና ተቀባ ይነት የሚያገኘው በአብዛኛው ከሕዝቡ የቅርብ የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚ ፣ የማኅበራዊ ኑሮ ወዘተ... ነክ ጉዳዮች ጋር የተያያዘ ሲሆን ነው ።

የፖለቲካ ቅስቀሳ ምንጊዜም የመደብ ባሕርይ አለው ። የኮሚኒስት ቅስቀሳ በመደ ቦችና በፓርቲዎች መካከል በሚደረገው ትግል ሰፊውን ሕዝብ ለማነቃቃት እንደ መሣሪያ ሆኖ የሚያገለግል ነው ። ኮሚ ኒስት ፓርቲ በቅስቀሳ የሚጠቀመው ሠርቶ አደሩን ሕዝብ ከጐኑ በማሰለፍ የተወሰኑ ተግባራትን ለማከናወን ፣ ወቅታዊ ችግሮችን ለማብራራት ፣ ሕዝቡን በማንቀሳቀስና በማ ደራጀት ፓርቲውና ሕዝቡ ያጋጠሟቸውን ችግሮች ለመፍታት ነው ። የኮሚኒስት የፖለ ቲካ ቅስቀሳ ሕዝቡን በሰፊውና በተቀነባበረ መንገድ ስለሀገሩ የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚና የባህል ፣ እንዲሁም ስለዓለም አቀፍ ሁኔታ በትክክል እንዲያውቅ የማድረግ ዓላማ አለው ።

ቅስቀሳ በተለያዩ ዘዴዎች ይካሄዳል ። ቅስቀሳ በአንድ ለአንድ ወይም በቡድን ፣ እንዲሁም በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች የሚካ ሄድ ነው ። በዚህም መሠረት በትምህርታዊ መግለጫዎች ፣ በሕዝብ ስብሰባዎች ላይ በሚ ደረጉ ንግግሮች ፣ በሬዲዮ ፣ በቴሌቪዥን ፣ በጋዜጣ ፣ በመጽሔቶች ፣ በተለያዩ ሥዕላዊ መግለጫዎች ፣ በፖስተሮች ፣ በፊልምና በተ ውኔት በሌሎችም ዘዴዎች ይካሄዳል ። ፓር ቲው የባህልና የትምህርት ተቋሞችን ለቅስ ቀሳ ዓላማም ይገለገልባቸዋል ።

ቅስቀሳ ለሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች በአንድ መልክና ይዘት የሚቀርብ ሳይሆን ኅብረተሰቡ የመደብ አቋም ፣ የባህል ፣ የትምህርትና የንቃት ደረጃ እንዲሁም የሥራ መስክ አኳያ የሚቀርብ ነው ። ቅስቀሳ በትዕግሥት ማስተማርንና በግልጽ ቋንቋ ማቅረብን ይጠይቃል ። ከዚህም በስተቀር በቅስቀሳ የሚተላለፉ ሐሳቦች ክሰፊው ሕዝብ ድጋፍና ተቀባይነት የሚያገኙት ፍላጐቱንና ጥቅሙን የሚያንፀባርቁ ሲሆኑ ነው ።

ቅስቀሳ ከፕሮፓጋንዳ ጋር በቅርብ የተያያዘ ነው ። ፕሮፓጋንዳ ዘላቂነት ባለው ዓላማ ላይ የተመሠረተ ሆኖ ሐሳቦችን ለሰዎች ጥልቀት ባለው ሁኔታ የማስተላለፍ ዘዴ ነው።

(ፕሮፓጋንዳን ይመለከቷል ።)

## ቅስቃሴ
*(Motion)*

በጊዜና በቦታ ክልል ውስጥ የሚደረግ ማናቸውም የቁስአካል ለውጥ ነው ። የቅስቃሴ መንሥኤ ፣ ምንጭ ወይም ሞተር በማናቸውም ነገር ፣ ክስተት ፣ ሂደት ወዘተ... ውስጥ የሚገኙ የተቃራኒዎች ትግል እንደመሆኑ ቅስቃሴና ቁስአካል ተለያይተው ሊኖሩ ወይም ሊታዩ አይችሉም ። ቅስቃሴ ያለቁስአካል ፣ ቁስአካልም ያለቅስቃሴ ህልውና የላቸውም ። በመሆኑም እንደጊዜና እንደ ቦታ ፣ ቅስቃሴም የቁስ አካል የህልውና ሌላው ገጽታ እንደ ሆነ እንገነዘባለን ።

ቅስቃሴ ማናቸውም የተፈጥሮ ክፍል (ልዩ ልዩ ቁስአካላዊ ቅርፆችና ገጽታዎች) ኅብረተሰብና የሰው አስተሳሰብም ጭምር በማያቋርጥ ሂደትና ለውጥ ላይ መሆናቸውን ያመለክታል ። ከቅስቃሴ ውጭ የሆነ ወይም ፍጹም የማይንቀሳቀስ ነገር ወይም ክስተት የለም ፤ አይኖርምም። ለምሳሌ ስንዴ ይበቅላል ፤ ያድጋል ፤ ያብባል ፤ ያፈራል። ከዚያ ይታጨድና ይወቃል ፤ ግማሹ ዳቦ ሆኖ ሲበላ ከፊሉ ደግሞ እንደገና ይዘራና ይበቅላል ። ማናቸውም ተክል ወይም ዘር እንደዚሁ ነው ፤ እንስሳም ሰውም እንደዚሁ ። ማናቸውም ሕያው የሆነ ነገር ይወለዳል፤ ያድጋል ፤ ራሱን ይተካል ፤ ያረጃል ፤ ይሞታል ፤ ፈራርሶ ወደ ሌላ ነገር ይለወጣል ። የማይንቀሳቀሱ ወይም በዘላለማዊ ዕረፍት ላይ ያሉ መስለው የሚታዩን እንደ ድንጋይ ያሉት ግዑዝ ነገሮች እንኳን ከመሬት ፣ ከፀሐይ እንደዚሁም ከሌሎች የተፈጥሮ አካላት ጋር በልዩ ልዩ ደረጃ ይንቀሳቀሳሉ ፤ ቀስ በቀስ ፈራርሰውም ወደ ሌላ ነገር ይለወጣሉ ። እንግዲህ ቅስቃሴ ስንል ይህንን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው ። ቅስቃሴ እንደ ቁስአካል ዘለዓለማዊ ሲሆን ፣ የተለያዩና አያሌ ገጽታዎች ፣ ቅርፆችና ደረጃዎች አሉት ።

የቅስቃሴ መልኮች አያሌና የተለያዩ ቢሆኑም ከዓይነተኛ ገጽታቸውና ከአጠቃላይ ሕግጋታቸው አንፃር 1/ የግዑዝ ነገሮች ቅስቃሴዎች፤ 2/ የሕያው ነገሮች ቅስቃሴዎች፤ 3/ የኅብረተሰብ ቅስቃሴዎች ብሎ በሦስት ዓበይት ክፍሎች ለመመደብ ይቻላል ። በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ ቅስቃሴዎች ተናክአታዊ (በመነካካት ፣ በመገፋፋት ፣ በመጓተት ወዘተ... የሚከናወን) ፣ አካላዊ (አንድ ነገር ካንድ ስፍራ ወደ ሌላ ስፍራ ሲዘዋወር የሚከናወን) ኬሚካላዊ (ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ንጥረ ነገሮች ባንድነት ተዋህደው አዲስ ዓይነት ነገር ሲፈጥሩ ወይም ሲሆኑ ወይም በብዙ ንጥረ ነገሮች የተገነባ አንድ ውሁድ ተበታትኖ ወደ ቀድሞ ንጥረ ነገሮቹ ሲመለስ የሚከናወን)፣ ሥነ ሕይወታዊ (አንድ ሕያው ነገር ሌሎች ነገሮችን ከራሱ ጋር ሲያዋህድና የማይፈልጋቸውን አውጥቶ ሲያስወግድ የሚከናወን) ፣ ማኅበራዊ (ኅብረተሰብ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ፣ ከቀላል ወደ ውስብስብ ሲለወጥ የሚከናወን) በመባል ይታወቃሉ ።

የተለያዩ የቅስቃሴ መልኮች እርስ በርሳቸው የተያያዙና የተወሳሰቡ ሲሆኑ የቁስአካልን የዕድገት ደረጃዎች ያመለክታሉ ። ከፍተኛውንና ውስብስቡን የዕድገት ደረጃ የሚያመለክተውን ቅስቃሴ ወደ ዝቅተኞቹ ለመለወጥ ባይቻልም ከፍተኛው ዝቅተኛውን ያጣመረና በላዩ ላይ የተገነባ ነው ። ለምሳሌ የሕያዋን ዓይነተኛ የቅስቃሴ መልክ የሆነው ሥነ ሕይወታዊ ቅስቃሴ በውስጡ ሌሎቹንም ያቀፈ ሲሆን ይህንን የቅስቃሴ መልክ የግዑዛን ዋነኛ ባሕርይ ወደ ሆኑት የቅስቃሴ መልኮች ማለትም ወደ ተናክአታዊ ወይም ኬሚካላዊ የቅስቃሴ መልኮች ለመለወጥ

አይቻልም ። በሌላ በኩል ስንመለከተው ልዩ ልዩዎቹ የቅስቃሴ መልኮች ከቁስአካል አወቃቀሮች ጋር ተያይዘውና ተወሳስበው እናገኛቸዋለን ። አንድ ዓይነት የቁስአካል ቅስቃሴ ለሱ ተስማሚ የሆነ የአወቃቀርና የዕድገት ደረጃ አለው ። ቁስአካል ካንድ ቅርፅ ወደ ሌላ ፣ ካንድ ሁኔታ ወደ ተለየ ሁኔታ ሲለወጥ የቅስቃሴው መልክና አወቃቀሩም አብረው ይለወጣሉ ። የቁስአካል ለውጥና ዕድገት የልዩ ልዩዎቹ የቅስቃሴ መልኮች መከሰቻዎች ናቸው ።

(ቁስአካልን ፣ ቅራኔዎችን ፣ ለውጥን ይመለከቷል ።)

## ቅስቃሴ ቅርፆች (የ—)

*(Forms of Motion)*

የነገሮችን ግንኙነቶችና የቅስቃሴአቸውን የተለያዩ መልኮች የሚገልጽ ጽንሰ ሐሳብ ነው ። በተፈጥሮ ውስጥ በዓይነት የተለያዩ ቁሳዊ ሥርዓቶች ከመታየታቸውም በላይ እያንዳንዱ ሥርዓት የሚገለጽበት የተለየ የቅስቃሴ ቅርፅ አለው ። ይህ ሁኔታ የወል ጠባይ ያላቸውንና ተመሳሳይ በሆኑ አጠቃላይ ሕጎች የሚገዙትን ቅስቃሴዎች በደረጃ ለመመደብ ያስችላል ። የቅስቃሴ ቅርፆች ከቀላል ወደ ውስብስብ የሚሄዱ በመሆናቸው አመዳደባቸው የሚገልጸው የተፈጥሮን የተለያዩ የዕድገት ደረጃዎችን ነው ።

ከቅስቃሴ ቅርፆች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ፦— 1/ ተናክአታዊ ቅስቃሴ ፣ ይህ ቅስቃሴ ከቦታ ቦታ መዘዋወርን የሚመለከት ሲሆን ሙቀትን ፣ ብርሃንን ፣ ኤሌክትሪክን ወዘተ . . . ያጠቃልላል ። 2/ ኬሚካላዊ ቅስቃሴ ፣ በመሠረቱ ቅስቃሴው የሚገልጸው የአቶሞችን የእርስ በእርስ ግንኙነቶች ነው ። 3/ ሥነ ሕይወታዊ ቅስቃሴ ፣ ቅስቃሴው የሕይወትን አመጣጥ ፣ አሠራርና ዕድገት ያጠቃልላል ። 4/ ማኅበራዊ ቅስቃሴ፣ የኅብረተሰብንና የሐሳብን ቅስቃሴ የሚመለከት ነው ።

የነዚህ ቅስቃሴዎች በተዋረድ መያያዝ የሚገልጸው ውስብስቡ ከቀላሉ መመንጨቱን በመሆኑ የተፈጥሮን ቁሳዊ አንድነት የሚያረጋግጥ ነው ። ኅብረተሰብ የቁስአካል ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ በመሆኑ ማኅበራዊ ክስተቶች ከሌሎች ይበልጥ ውስብስብነት አላቸው ። የዲያሌክቲክስ ሕግ እንደሚያስተምረውም ውስብስቡ ቅስቃሴ የበታቾቹን ያጠቃልላል ። ለምሳሌ ሰው አካላዊ ፣ ኬሚካላዊና ሥነ ሕይወታዊ የቅስቃሴ ቅርፆችን ያጠቃልላል ።

ተናክአታዊ ቁስአካልነት የተሳሳተ አመለካከት የፈጠረው የተለያዩ የቅስቃሴ ቅርፆችን ደረጃ ሳይጠብቅ የበላዮቹን በተናክአታዊ ቅስቃሴ ብቻ አስረዳለሁ ማለቱ ነው ። ሐሳባዊነት ደግሞ የበላዩ ማለት የሐሳብ ቅስቃሴ የበታቾቹ ቅስቃሴዎች ፈጣሪ ነው የሚል የዕድገትን ውጤት ወደ ምክንያት የሚቀይር የተገላቢጦሽ አመለካከት ነው ። ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ቀላሉ ወደ ውስብስብ እንዴት እንደሚሸጋገር በማሳየት የዕድገትን ትክክለኛ ሂደት የሚያንፀባርቅ ንድፈ ሐሳብ ነው።

(ተናክአታዊ ቁስአካልነትን ፣ የዲያሌክቲክስ ሕጎችን ይመለከቷል ።)

## ቅራኔ

*(Contradiction)*

የማንኛውም ክስተት ፣ ቅስቃሴና ዕድገት መሠረት የሆነ የዲያሌክቲክስ ፈርጅ ነው ። በቁስአካል ፣ በሐሳብና በኅብረተሰብ ያለ ማንኛውንም ክስተት ፣ ውልደት ፣ዕድገትና ክስመት ብሎም በአዲስ ነገር መተካትን በሚመለከት ሁለት የፍልስፍና አመለካከቶች አሉ ። የሐሳባውያን አጠናን ወይም አመለካከት ዘይቤ የሆነው ዲበአካል እንደሚለው ማንኛውም ነገር የመጠን መጨመር ወይም መቀነስ እያሳየ የተለወጠ ከሚመስል በቀር የዓይነት ለውጥ አያደርግም ። ስአንዴና ለዘለዓለም "የተፈጠረ" ነው ። ለመጠን መጨመርና መቀነስ ምክንያት የሚሆነው በራሱ በክስተቱ ውስጥ ያለ ነገር ሳይሆን ውጫዊ ኃይል ነው ። ለምሳሌ ለኅብረተሰብ ማደግ ወይም ወደኋላ መጐተት የአየር ንብረትን ፣ የሕዝብ መብዛትንና ማነስን ፣ የተፈጥሮ ሀብት መኖርንና አለመኖርን የዲበአካላዊ አመለካከት ተከታዮች እንደዋና ምክንያት አድርገው ያቀርባሉ ።

የቁስአካላዊ ዲያሌክቲክስ አመለካከት ግን ከዚህ የተለየ ነው ። ዲያሌክቲክስ በቁስ

አካል ፣ በሐሳብና ፣ በኅብረተሰብ ያለ ማንኛውም ክስተት ፣ በውልደት ፣ በዕድገትና በክስመት ሂደት በሚኖረው ቅስቃሴ አንዱን ክስተት ከሌላው ጋር የተሳሰረና መስተጋብር ያለው አድርጐ ይመለከታል ። ለክስተቶች መጸነስ ፣ ማደግ ፣ መክሰምና በሌላ አዲስ ነገር መተካት ዋናው ምክንያት ውጫዊ ኃይል ሳይሆን በራሱ በክስተቱ ውስጥ ያለው ተቃራኒነት ነው ። የኅብረተሰብ ዕድገት ምንጭም በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል ያለው ቅራኔ ነው ። በአካባቢያችን ያለ ማንኛውም ክስተት የተቃራኒዎች አንድነትና ትግል ውሁድ ነው ። የተቃራኒዎች በአንድነት መኖር የክስተቱ ህልውና መግለጫ ሲሆን በተቃራኒ ባሕርያቱ መካከል የሚደረገው የማያቋርጥ ትግል የቁስአካል ፣ የአስተሳሰብና የኅብረተሰብ የዕድገት ምንጭ ነው። ቅራኔዎች የዲያሌክቲክስ መሠረት ናቸው ። የቅራኔዎች እየዳበሩ መምጣትና መፈታትም ለአዳዲስ ክስተቶች መወለድ ምክንያት ይሆናል ።

ቅራኔዎች ዐድገው አመርቃ የሚያሳዩበት ሂደት ሁለት ደረጃዎች አሉት ። የመጀመሪያው የቅራኔዎች መጸነስና ማደግ ሲሆን ሁለተኛው እነዚህ ቅራኔዎች ዳብረው መፍትሔ የሚያገኙበትና አዲሱ በአሮጌው የሚተካበት ሂደት ነው ። ቅራኔዎች ሁለንታዊና ልዩ ባሕርይ አላቸው ። በማንኛውም ነገር ወይንም ክስተት ውስጥ ቅራኔዎች ይጸነሳሉ ፣ በሂደትም ይከስማሉ ። በክስተቶች ውስጥ የቅራኔዎች መጸነስና መክሰም መኖር ፣ ለዕድገትም ይህ ሂደት ወሳኝ መሆኑ የቅራኔዎች ሁለንታዊ ባሕርይ ነው ። ይሁንና በአንድ ክስተት ውስጥ ቅራኔዎች የሚጸነሱበት፣ የሚወለዱበት ፣ የሚያድጉበትና የሚፈቱበት ሁኔታ በሌላው ክስተት ውስጥ ካለው ሂደት ይለያል ። ይህ የቅራኔዎች ልዩ ባህርይ ነው ። ይህ ባይሆን ኖሮ የተለያዩ ክስተቶች ባልኖሩና አንዱ ከሌላው የተለየ ባልሆነ ነበር ።

የቅራኔዎች ጠባይ ፣ የዕድገት ቅርፃቸውና አቅጣጫ ሕይወት ባላቸውና በሌላቸው ፣ በተፈጥሮና በኅብረተሰብ ውስጥ የተለያየ ነው ። ይህም በሂደተ ለውጥ ውስጥ ካለው ክስተት ልዩ ባሕርይ የሚመነጭ ነው ። ሕይወት ባላቸው ነገሮች ውስጥ የሚካሄደው ለውጥ ከዘር የተወረሱ ባሕርያትና ከውልደት በኋላ ከአካባቢ ጋር ራሱን ለማስማማት የሚደረገው ትግል ውጤት እንደመሆኑ በጣም አዝጋሚና ረጅም ጊዜ የሚጠይቅ ነው ። ለምሳሌ ሰው "አንትሮፖይድ" ከተባለው የዝንጀሮ ዘር ተገንጥሎ አሁን ያለውን ቅርፅና ይዘት ለማግኘት ብዙ ሚሊዮን ዓመታት ወስዶበታል ። የኅብረተሰብ ለውጥ ከዚህ ጋር ሲነፃፀር በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል ያለው ቅራኔ በማኅበራዊ አብዮት አማካይነት የሚፈታበት አጭር በሆነ ጊዜ የሚከናወን ሂደት ነው ።

በቁስአካል ፣ በሐሳብና ፣ በኅብረተሰብ ውስጥ ቁጥር ስፍር የሌላቸው ክስተቶች አሉ ። እያንዳንዱ ክስተት ከሌላው ጋር ግንኙነትና መስተጋብር ስላለውም ክስተቶች ሁሉ አንድነትና ልዩነት አላቸው ። ይህም ልዩ ልዩ ዓይነት ቅራኔዎች እንዲኖሩ ምክንያት ይሆናል ። በዚህም የተነሣ እንደ ክስተቶች ሁሉ ልዩ ልዩ ዓይነት ለምሳሌ ተፃራሪና ኢተፃራሪ ፣ ውስጣዊና ውጫዊ ፣ መሠረታዊና ኢመሠረታዊ ወዘተ... ቅራኔዎች አሉ ። የክስተቶችን አጠቃላይና ልዩ ባሕርያት ፣ በመካከላቸው ያለውን ግንኙነትና መስተጋብር ፣ የቅራኔዎቻቸውን ዓይነትና ደረጃ መለየት አስፈላጊ ነው ። በአንድ አብዮታዊ ሂደት ውስጥ የቅራኔዎችን ጠባይና ደረጃ መገንዘብ የአብዮቱን ትክክለኛ ስትራቴጂና ታክቲክ ለመንደፍ ወሳኝነት አለው ።

(ዲያሌክቲክስን ፣ ዲበአካልን ፣ የተቃራኒዎች አንድነትና ትግል ሕግን ይመለከቷል ።)

## ቅራኔ ሕግ (የ—)

*(Law of Contradiction)*

በነገሮች ውስጥ ያለውን የተቃራኒዎችን አንድነትና ትግል እንዲሁም ከዚህ የተነሣ የሚፈጠረውን እንቅስቃሴ የሚመለከት ሕግ ነው ። ይህም እንቅስቃሴ የማንኛውም ህልውና ዕድገትና ለውጥ መሠረት በመሆኑ የቁስአካላዊ ዲያሌክቲክስ መሠረት ወይም የዕድገት መሠረታዊ ሕግ ነው ለማለት ይቻላል ። በዚህ ሕግ የሚገዛ ግንኙነት በዘፈቀደ የሚከሰት ሳይሆን ከነገሮች ውስጣዊ ባሕርይ ጋር የተገናዘበ ፣ አስፈላጊ ፣ ረግቶ ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ ፣ የመለወጥ ችሎታ ያለውና በተደጋጋሚ ተከስቶ ሊታይና ሊጠና የሚ

ችል መሆን አለበት ። የቅራኔ ሕግ ሁለንታዊ ግንኙነቶችን የሚያሳይና የህልውናና የዕድገትም ሕግጋት መሠረት ነው ። ይህ ሕግ እንቅስቃሴዎችን በመምራት በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ የዕድገታቸውን መሠረታዊ ባሕርያት የሚወስን ነው ።

በዚህ የዲያሌክቲካዊ ቁስአካላውያን ፍልስፍና መሠረት የዕድገት ወይም የለውጥ ዋነኛ መንሥኤ በነገሮች በራሳቸው ውስጥ ያለው ቅራኔ የሚፈጥረው እንቅስቃሴ ነው። በነገሮች ላይ ከውጭ የሚያደርሱባቸው ተፅዕኖዎች ለለውጡ መከሰት በመንሥኤነት የሚያበረክቱት ድርሻ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ነው ። በተለይም የአንድን ነገር ዕድገትና የዓይነት ለውጥ ምክንያት ለማግኘት በመጀመሪያ በውስጡ ያሉ ቅራኔዎችን ይዘትና ግንኙነት ማጤን ያስፈልጋል ። ከውጭ አካላትና ሁኔታዎች ጋር ያለውን ግንኙነት ማየት ከዚያ ቀጥሎ የሚመጣ ነው ።

ለዲያሌክቲክስ ሕግጋት መሠረት የሆኑትና በቅራኔ ሕግም ውስጥ ዋናዎቹ ዘርፎች የሚከተሉት ናቸው ።

— የቅራኔዎች ሁለንታዊነት ፣ የቅራኔዎች ልዩ ባሕርይና አንፃራዊነት ፣ የመጠን ወደ ዓይነት እንዲሁም በተገላቢጦሽ የዓይነት ወደ መጠን ለወጥ ሕግና ፣ የሽረት ሽረት ሕግ ናቸው ።

## ቅራኔዎች ልዩነትና ሁለንታዊነት(የ-)

*(Particularity and Universality of Contradictions)*

ሂደቶች በሙሉ በቅራኔ ላይ የተመሠረቱ በመሆናቸው ቅራኔ ሁለንታዊ ነው ። ሆኖም ቅራኔ አንድ ዓይነት ብቻ አይደለም ። የተለያዩ ቅራኔዎች አሉ ። ቅስቃሴ በተለያዩ ቅርፆች የሚከፈልና ተፈጥሮም በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ ቅራኔ የተለያዩ ጠባዮችን ያሳያል ።

ለምሳሌ የበድን ማለትም የኢድርጅታዊ ቁስአካል ቅራኔዎች ሕይወት ካላቸው ማለትም ከድርጅታዊ ቁስአካል ቅራኔዎች የተለዩ ናቸው ። የሕይወት ቅራኔ የተመሠረተው ከአካባቢው ጋር በመስማማት ሂደት ውስጥ ሲሆን የኅብረተሰብ ቅራኔ የሚካሄደው በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል ነው ። ይህ የቅራኔ ልዩነት የሚያስረዳው የቅራኔ አፈታት አንድ ዓይነት ሊሆን እንደማይችል ነው ።

እንዲሁም በአንድ ሂደት ውስጥ የተለያዩ ቅራኔዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ ። ለምሳሌ ኅብረተሰብ በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች (ባሪያ አሳዳሪ ፣ ፊውዳሊዝም ፣ ካፒታሊዝም ወዘተ ...) ማለፉ የሚያሳየው የተለያዩ ቅራኔዎች ውጤት መሆኑን ነው ። ውጤቶቹም እንደ ቅራኔዎቹ ልዩነት የተለያዩ ናቸው ። የፊውዳሊዝም ቅራኔ ያመራው ወደካፒታሊዝም ሲሆን የካፒታሊዝም ቅራኔ ግን የሚያመራው ወደ ኮሚኒዝም ማለትም ወደመደብ አልባ ሥርዓት ነው ። የቅራኔዎችን ልዩ ጠባይ ማወቅ ለተግባር ወሳኝ ነው ። ምክንያቱም የቅራኔዎችን ሂደት ለማፋጠን ሆነ ተስማሚውን ምላሽ ለመስጠት ልዩነታቸውን መገንዘብ አስፈላጊ ነውና ።

(ቅራኔን ይመለከቷል ።)

## ቅርፃዊ ሥነ አመክንዮ

*(Formal Logic)*

የአስተሳሰብን አወቃቀር ወይም ቅርፅ የሚያጠና ሳይንስ ነው ። ማለትም የአስተሳሰብን ተጨባጭ ይዘት አንጥሮ በመተው የቅርፁን ክፍሎች የሚያቆራኙትን አጠቃላይ ሁኔታዎች ብቻ መርጦ በማሰባሰብ የሚያጠና ሳይንስ ነው ። ዓይነተኛ ጥረቱም በምንጩታዊ ዘዴ በመጠቀም ዕውቀትን ለመገብየት በሚደረገው ሙከራ ውስጥ ጠቃሚ የሆኑትን ሕግጋትና መርሆች መቀመር ነው።

የቅርፃዊ ሥነ አመክንዮ መሠረት የተጣለው በአርስጣጣሊስ ሲሆን ጥንታዊ ስቶይኮችና በኋላም የመካከለኛው ዘመን ተምህሮ አውያን ለዕድገቱ የሚረዳ ጠቃሚ አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

ቅርፃዊ ሥነ አመክንዮ ለቅርፅ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥ ነው ። ነገሮችን ወይም ክስተቶችን በተናጠል የሚያይ በመሆኑ ትክክለኛውን ጣምራ ህልውናቸውንና ግንኙነታቸውን ሊገነዘብ አይችልም ። አንድ ነገር በአንድ ወቅት ራሱን እንጂ ሌላ ነገር ሊሆን አይችልም ፤ ቅራኔ በሰዎች አስተሳሰብ ውስጥ

እንጂ በእውነታ ውስጥ የለም የሚል ነው ። ስለዚህም ነው የነገሮችን ምንነት በተናጠል ሲገልጽ የቅራኔ አልባነትን ወይም የአንድ ነትን መርህ የሚጠቀመው ። ለምሳሌ አን ድን የአቀበት ጉዳና ሲገልጽ ፣ ጉዳናው በአ ንድ ጊዜ አቀበትና ቁልቁለት ሊሆን ስለማ ይችል ወደ ላይ ስንሄድ አቀበት ይሆናል ፤ ስንመለስ ደግሞ ቁልቁለት ይሆናል በማለት አቀበትን ከቁልቁለት ፣ ቁልቁለትን ደግሞ ከአ ቀበት ነጥሎ ለመረዳት ይሞክራል ። በአንድ ነገር ውስጥ ቅራኔ መኖሩን ቢክድም ቅርፃዊ ሥነ አመክንዮ አሁንም ቢሆን በተወሰነ ደረጃ ተቀባይነት አለው ።

(ዲያሌክቲካዊ ሥነ አመክንዮን ይመለከቷል።)

## ቅርፃዊነት
(*Formalism*)

በቡርዧው ኅብረተሰብ ውስጥ የተከ ሰተ የሥነ ውበት ንድፈ ሐሳብ ነው ። በቅ ርፃዊነት አባባል የሥነ ውበት ሚና እውነ ታን ማንፀባረቅ ሳይሆን አዳዲስና ማራኪ የሆኑ ምናባዊ ቅርፆችን በመፍጠር ለሰው ነፃ የሆነ ደስታን ማስገኘት ነው ። ይህ በኪነ ጥበብ ውስጥ ይዘትን ወደጎን ትቶ ለቅ ርፅ ብቻ ቅድሚያ የመስጠት ዝንባሌ ኪነ ጥበብ የመደብ ይዘት የሌለውና በማኅበራዊ ጥቅሞችና አመለካከቶች የሚወሰን መሆኑን ለመካድ የሚደረግ ጥረት ነው ። ኪነ ጥበብን ከቁሳዊ ኑሮ ነጥሎ በአእምሮአዊ ደስታ ብቻ እንዲወሰን መሻት ስውር በሆነ መንገድ የሚያንፀባርቀው የቡርዧዚውን ርዕዮተዓለም ነው ።

(ሶሻሊስት እውነነትን ይመለከቷል።)

## ቅኝ አገዛዝ
(*Colonialism*)

ካፒታሊስት መንግሥታት በኃይል የወረ ሯቸውን ሀገሮች ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ነፃ ነት የገፈፉበትና በተገዥነት ቀንበር ሥር እን ዲውሉ የተጠቀሙበት ሥርዓትና ፖሊሲ ነው።

በ20ኛው ምዕት ዓመት መባቻ ላይ ዋና ዋናዎቹ ቅኝ ገዥ ኃይላት (እንግሊዝ ፣ ፈረንሳይ ፣ ጀርመን ፣ አሜሪካ ፣ ኢጣሊያ ፣ ጃፓን ፣ ሆላንድ ፣ እስፓኝ ፣ ፖርቱጋልና ሌሎች) ዓለምን በመካከላቸው ተከፋፍለዋት ነበር ። ይህ ከፍፍል ጥሬ ዕቃንና የሰው ጉልበትን በርካሽ ለመበዝበዝ ፣ ወደቅኝ ተገዥ ሀገሮች ሸቀጥና ሙአለ ንዋይ ለማስገባት አስችሏ ቸዋል ። በመሆኑም በቅኝ ግዛቶች ላይ የተካሄ ደው ብዝበዛ ለኢምፔሪያሊስቶች ከፍተኛ ትርፍ አስገኝቶላቸዋል ።

ከ2ኛው የዓለም ጦርነት በኋላ (1939-1945) በቅኝ ተገዥ ሀገሮች ውስጥ የሚገ ኙት ሕዝቦች በዓለም ሶሻሊዝም በተለይም በሶቭዬት ኅብረት ድጋፍና እርዳታ ላይ በመ ተማመን ባካሔዱት የብሔራዊ አርነት እን ቅስቃሴ የቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ምሽግ ሲፈ ራርስ በቅቷል ። ከ120 በላይ የሚሆኑ ከቅኝ አገዛዝ የብዝበዛና የጭቆና ቀንበር የተላቀቁ ታዳጊ ሀገሮች የቅኝ አገዛዝን ቅሪት ለማው ደምና እውነተኛ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ነፃ ነት ለመቀዳጀት ከንዳቸውን እንሥተዋል ፤ ስለሆነም ዛሬ አሮጌው የቅኝ አገዛዝ ሥር ዓት በመፈራረሱ ቅኝ ገዥዎች ነፃ በወጡት ታዳጊ ሀገሮች ውስጥ የበላይነታቸውን ለማ ረጋገጥ በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ዘዴ ለመ ጠቀም ጥረት እያደረጉ ናቸው ።

(የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን ይመለከቷል ።)

## ቅኝ ግዛት
(*Colony*)

በሌላ መንግሥት አገዛዝ ሥር የወደቀ ሀገር ቅኝ ግዛት ይባላል ። በቅኝ ገዥ ሀገ ሮች ብዝበዛና ጭቆና ቀንበር ሥር ከወ ደቁት ሀገሮች መካከል አብዛኞዎቹ ሙሉ ቅኝ ግዛቶች ሲሆኑ ፣ ጥቂቶቹ ደግሞ ከፊል ቅኝ ግዛቶች ናቸው ። በተጨማሪም ጥገኛ ሀገሮችና ጥብቅ ሀገሮች በመባል የሚታወቁ የፖለቲካ ተፅዕኖ ያለባቸው ሀገሮችም አሉ።

ሕዝቡ ለነፃነቱ በሚያደርገው ትግል የፖ ለቲካ ብስለቱ እያደገ ስለሚሄድ ቅኝ ገዥዎች ይህን በመፍራት የትግሉንም ሂደት ለማቀዝ ቀዝ የበላይነታቸውን ሳያስነኩ እስከተወሰነ ደረጃ የራስ አስተዳደር መብት ይሰጣሉ ። አንዳ ንድ ጊዜም የይስሙላ የሕግ ምክር ቤት በማቋ ቋም የቅኝ ግዛት ሕዝብ የሚተዳደርበት ሕግ ራሱ እንደሚያፈልቀውና በዚህም መብቱ ሙሉ በሙሉ እንደተከበረለት አድርገው ለማቅ ረብ ይሞክራሉ ። ይህን የሚያደርጉት ግን ስሕ

ዝቡ መብት ፣ ደኅንነትና ዕድገት ተቆርቁረው ሳይሆን በረቀቀ ዘዴ ሕዝቡን ለመሸንገል ፣ የትግል ስሜቱን ለማብረድና የብዝበዛና የጭቆና ጊዜያቸውን ለማራዘም ነው ።

(ቅኝ አገዛዝን ይመለከቷል ።)

## ቋሚ ካፒታል

*(Constant Capital)*

የምርት ማከናወኛ መሣሪያዎችን ማለትም ማሽኖችን ፣ ጥሬ ዕቃዎችን ፣ ነዳጅን ፣ ሕንፃዎችንና የመሳሰሉትን የሚያጠቃልል አንዱ የካፒታል ክፍል ነው ። ይህንን የካፒታል ክፍል ዓይነተኛ የሚያደርገው በምርት ክንዋኔ ውስጥ እሴቱ በመጠን የማይለወጥ መሆኑ ነው ። ካርል ማርክስ ይህን የካፒታል ክፍል ቋሚ ያለበትም ምክንያት እሴቱን ደረጃ በደረጃ ወይንም ባንድ ጊዜ አዲስ ወደሚመረተው ሸቀጥ በሥራ ኃይል አማካይነት የሚያስተላልፍ እንጂ በመጠን የማይለወጥ መሆኑን ለማመልከት ነው ።

ለምሳሌ በአንድ የማምረቻ ተቋም ውስጥ የተወሰነ ሸቀጥ ለማምረት የተለያዩ ማሽኖች ፣ ለሚመረተው ሸቀጥ የሚያገለግሉ ጥሬ ዕቃዎችና ወዝአደሮች ሊኖሩ ይገባል ። ከነዚህ ልዩ ልዩ ነገሮች ውስጥ ለወዝአደሮች ምንዳ ከሚከፈለው በስተቀር ለሌሎች የምርት መገልገያዎች መግዣ የሚወጣው የካፒታል ክፍል በጥቅሉ ቋሚ ካፒታል ይባላል ።

ካፒታልን በቋሚና በተለዋዋጭ ለመጀመሪያ ጊዜ ክፍሎ የተመለከተው ካርል ማርክስ ሲሆን የዚህም ዓይነት የካፒታል አከፋፈል ተረፈ እሴት የሚፈጠረው በሁሉም የካፒታል ክፍሎች ሳይሆን በተለዋዋጭ ካፒታሉ ክፍል ብቻ ማለትም ለሥራ ኃይል መግዣ በወጣው የካፒታል ክፍል ብቻ መሆኑን በማሳየት በቡርዧዚውና በወዝአደሩ መካከል በብዝበዛ ላይ የተመሠረተውን ግንኙነት በግልጽ አሳይቷል ።

(ተለዋዋጭ ካፒታልን ይመለከቷል ።)

## ቋንቋ

*(Language)*

የሰዎችን ግንኙነትና የዕውቀት ተግባር በምልክት ፣ መልክና ሥርዓት ባለው ሁኔታ የሚያስፈጽምና የሚገልጽ ነው ። በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ ቋንቋ ሁለት መሠረታዊ ጥያቄዎችን አሥነሥቷል ። አንደኛው ቃል ማለትም ስያሜ ተፈጥሮአዊ ወይም ነባራዊ መሠረት አለው ወይም ከስምምነት ብቻ የሚመነጭ ነው የሚለው ሲሆን ፣ ሁለተኛው ደግሞ አሳቦት ካለቋንቋ ፣ ቋንቋ ካለአሳቦት የማይገኝ በመሆኑ የተለያየ ህልውና አላቸው ወይንስ አንድ ናቸው የሚል ነው ።

በነባራዊ ሐሳባውያን አመለካከት ቃላት የሚገልጹት ሐሳብን ሲሆን ሐሳብ ደግሞ የነገሮች ውስጠ ምንነት በመሆኑ ቃላት ሰው ሠራሽ አይደሉም ። ሆኖም አሳቦትና ቋንቋ የተለያዩ ናቸው ፤ ቋንቋ የአሳቦት ውጫዊ ገጽታ በመሆኑ ነፍስ ከሥጋ እንደሚለይ ሐሳብም ከቋንቋ ይለያል ። በኅሊናዊ ሐሳባውያን አስተሳሰብ ግን ቋንቋ አስፈላጊ ሲሆን ከነባራዊ ነገሮች ምንነት የሚመነጭና እነሱን የሚገልጽ አይደለም ። የቃላት ምንጭ ስምምነት ነው ፤ ሰው ስንል ለነገሩ በስምምነት የምንሰጠው ስም እንጂ ምንነቱን የሚገልጽ አይደለም ። ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው አሁንም ቢሆን ከተስማማን በሌላ ቃል ልንጠቀም የምንችል መሆናችን ነው ይላሉ ።

በእርግጥ በቋንቋ ውስጥ ስምምነት አንዳለ ሊካድ አይችልም ። ሆኖም ስምምነት ሲባል በግለሰብ ደረጃ የሚፈጸም ወይም የሚፈጠር አለመሆኑ በትክክል የሚያስረዳን ቋንቋ ማኅበራዊ መሠረት እንዳለው ነው ። ንቃተ ኅሊና ከቋንቋ ውጭ ሊኖርና ሊዳብር አይችልም ። ምክንያቱም ቋንቋ ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፈውን ዕውቀት የሚያጠራቅም በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ካለሱ አሳቦት ከረቂቅ ሐሳቦች ላይ ለመድረስ ስለማይቻለው ነው ። ማንኛውም ቃል (ወንበር፣ሰው ወዘተ...) አጠቃላይ ነው ። ማለት ነባራዊ ሐሳባውያን እንደሚሉት ቋንቋ የሐሳብ መግለጫ ብቻ አይደለም ፤ የአሳቦት አስፈላጊ መሣሪያ እንጂ ። ይህም ሲባል ግን ሁለቱ አንድ ናቸው ማለት አይደለም ። ቋንቋ የራሱ ሕጎች ያሉት መሆኑ ብቻ ሳይሆን ሁለቱን አንድ ማድረግ የነባራዊውንና የኅሊናዊውን ልዩነት መሰረዝ ይሆናል ። ቋንቋ ቁሳዊ ሲሆን ሐሳብ ነፀብራቅ ነው ። የቋንቋ ዓይነተኛ ተግባር የሰውን ንቃተ ኅሊና ማኅበራዊ ማድረግ ነው ። የሰዎችን እንቅስቃሴና አስተሳሰብ የሚያገናኝና የሚያቀናጅ በመሆኑ ቋንቋ የማኅበራዊ ኑሮ ዋንኛው አካል ነው ።

(ጽንሰ ሐሳብን ፣ ንድፈ ሐሳብን ይመለከቷል ።)

# በ

## በርክሌይ ፡ ጆርጅ

*(Berkeley, George)*

ከ1685—1753 የኖረ ፡ የዳሳሽነት ፍልስፍና አራማጅና የቤተክርስቲያን ጳጳስ የነበረ እንግሊዛዊ ፈላስፋ ነው ። በርክሌይ በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ ታዋቂ የሆነው ቁስአካል የሚባል ነገር ጨርሶ የለም ፤ አይኖርምም በማለት ኢቁስአካላዊ የሆነ ፍልስፍና በመቀመሩ ነው ። ይህን ፍልስፍና "አ ትሪቲ ኮንሰርኒንግ ሂዩማን አንደርስታንዲንግ" ፡ "ኤ ኒው ቲየሪ ኦቭ ቪዥን"፡ "ስሪ ዲያሎግ ቢትዊን ሂለን ኤንድ ፊሎነስ" በሚባሉት ጽሑፎች ውስጥ አብራርቷል ።

በርክሌይ ከኢቁሳካላዊ ፍልስፍና ላይ የደረሰው የኅሊናዊ ሐሳባዊ መርህን እስከ መጨረሻው በመከተል መሆኑን ይናገራል ። ኅሊና ሊገናኝ የሚችለው እራሱ ውስጥ ከሚገኙ ሐሳቦችና ሕውስቶች ጋር ብቻ ነው ። ለኅሊና የሚቀርበው ማንኛውም ነገር ታዋቂ ሊሆን የሚችለው ሐሳብ ሲሆን ብቻ ነው ፤ ምክንያቱም ከሐሳብ ውጭ የሆነ ነገር ለኅሊና ሊገለጽ አይችልምና ። በመሆኑም ከሐሳብ ውጭ የሆነ ወይም የተለየ ነገር ልናውቅና ልንረዳ አንችልም ። ቁስአካል የሚባለው ነገር ከሐሳብ ውጭና የተለየ ነገር በመሆኑ ስለርሱ ምንም ዓይነት ግንዛቤ ሊኖረን አይችልም ። ስለዚህም ቁስአካል አለ ብሎ መናገሩ እራሱን የቻለ ፈጠራ ነው። አንድ ነገር አለ ፤ ይኖራል ለማለት የምንችለው ስንለብወው ማለትም በኅሊናችን ውስጥ በሐሳብነት ሲኖር ብቻ ነው ። ህልውና ማለት ልንሰብወው የምንችል ነገር ማለት በመሆኑ ቁስአካልም ከሐሳብ የተለየና ልንሰብወው የማንችል በመሆኑ ህልውና የለውም ። በሌላ በኩልም ቁስአካል ለሕዋሳት ተገላጭ ሆኖ ቅርፅ ፤ ቀለምና ክብደት ፤ ስፋት ፤ ወዘተ... አለው ብለን ስንናገር እራሳችንን መቃረን ይሆናል ። ምክንያቱም የተዘረዘሩት ነገሮች ሕውስታዎች መሆናቸውን እያወቅን መልሰን እነዚሁ ነገሮች የቁስአካል ማለትም ስሜት የሌለው ነገር ጠባዮች ናቸው ብለን መናገር ትክክል አይሆንም ። ሐሳብ ነክ የሆነን ነገር ለቁስአካል መስጠቱ ትክክል ካልሆነ ፤ እኛም ደግሞ ከሐሳብ ውጭ የምናውቀው ነገር ከሌለ ለቁስአካል የምንሰጠው ምንም መለያ ነገር አይኖረንም ። በመሆኑም እንደ በርክሌይ አባባል ቁስአካል ለኛ ዝም ብሎ ባዶ የሆነ ነገር ነው ።

በበርክሌይ አስተሳሰብ ትክክለኛው አቋም ሕውስታና ሐሳብ ከቁስአካል ይመነጫሉ የሚለው ሳይሆን የባሕርይ ተመሳሳይነት በመከተል ሐሳብና ሕውስታ ሊመነጩ የሚችሉት ከመንፈስ ወይም ከመንፈሳዊ ባሕርያት ነው የሚለው ነው ። ስለዚህም ሐሳቦች ሊመነጩ የሚችሉት ከሰው ወይም ከእግዚአብሔር ብቻ ነው ። በተለይም ሰው ሳይፈቅዳቸው የሚሰሙ ሕውስታዎች ሁሉ ምክንያታቸው እግዚአብሔር ነው ። የእነዚህን ሕውስቶች የውስብስብነት ሁኔታ ፡ የአመጣጥ ሥርዓትና የእርስ በርስ መስማማት ስንመለከት በጉ ፈላጊና ጥበበኛ ከሆነ ፈጣሪ እንደሚመነጩ እንረዳለን ። ዕውቀት ማለት ከልምድ በመነሣት የነዚህን ሐሳቦች አመጣጥ ፡ ሥርዓትና አወቃቀር ለተግባር እንደሚጠቅም አድርጎ መረዳት ነው። ዓለም የእግዚአብሔር ቋንቋ እንደመሆኑ የዕውቀት ሚና የዚህን የሚነገረንን ቋንቋ የተለያዩ ፍችዎች መገንዘብ ነው ።

የበርክሌይ ፍልስፍና——የሐሳባዊነትን ውስጠ ምሥጢር በይፋ ያወጣ ነው ። እራሱም እንደተናገረው ሐሳባዊነት በእምነቱ የጸና ከሆነ ለቁስአካል ቦታ ሊኖረው አይችልም ። በሁለታዊነት በመመራት ለቁስአካል የሁለተኛ ደረጃ ህልውና ለመስጠት መሞከር ለሐሳባዊነት ተቃርኖ ነው ። ምክንያቱም ሐሳብ ራሱን ችሎ የሚኖርና ባለሙሉ ሥልጣን እስከ ሆነ ድረስ የቁስአካል መኖርና ከሱ ጋር መቀናጀት አስፈላጊ አይደለም ። ይህ ኢቁስአካላዊነት የሐሳባውያንን ሁለታዊነት ቅራኔ በማጋለጡ ነው በርክሌይ በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ ታዋቂነት ያገኘው ። ሆኖም የራሱ ፍልስፍና ከቅራኔ ነፃ አይደለም ። ህልውና ያለው የምንሰብወው ነገር ብቻ ነው ብሎ ከደነገገ በኋላ ከፍቃዱ ውጭ ለሚሰሙት

ሕውሰታዎች ውጫዊ ምክንያት ማግኘት የማድ ስለሆነበት ስሕዋሳት ጨርሶ ሊገለጥ የማይ ቻለውን ምናባዊ የሆነውን ፍጡር እግዚአ ብሔርን አለ ብሎ መናገሩ እራሱ አንድ መሠረታዊ ቅራኔ ነው ። እንደመነሻው ከሆነ ፍልስፍናው ማምራት የነበረበት ወደ ጠርጣሪነት ነበር ፤ የማውቀው ሐሳቤን ብቻ ነው ካለ ፣ ከኔ ውጭ ስላለው ነገር የማውቀው ነገር የለም ቢል የተሻለ አመለካከት በሆነ ነበር ። ፍልስፍናው ከራሳዊነትም ሊወጣ አይችልም ። በርክሌይ አንድ ነገር አለ የሚለው ለሱ ሐሳብ ሲሆን ብቻ ከሆነ ይህ አባባል በራሳቸው የሚኖሩና የራሳቸው ህልውና ያላቸውን ግለሰቦች መኖርን የማይቀበል ሊሆን ነው ። ከኔ ሐሳብ ውጭ የማውቀው ነገር የለኝም ማለት ከኔ ውጭ ስለሌሎች ሰዎች በነባራዊነት መኖር አላውቅም ማለት ነው ። ከዚህ የምንረዳው ቁስአካልን ወይም የሱን ነፃ ህልውና መካድ የሌሎችን ሰዎች መኖር መካድ እንደሚሆን ነው ፤ ምክንያቱም ሰዎች ከኔ ሐሳብ ውጭ አሉ ለማለት የምችለው ቁሳዊነት ሲኖራቸው ብቻ ነው ። የራሳዊነት ማኅበራዊ ፍችም ግልጽ ነው ። ከራሴ ሐሳብ ውጭ የማውቀው ነገር የለም ለማለት የሚቻለው የተደላደለና ትግል የማይጠይቅ ኑሮ ውስጥ የምንገኝ ከሆነ ነው። ሁሉ ነገር ተሳክቶ ማየት ዓለምን የሐሳብ መልክ ይሰጠዋል ። እንደተባለውም በርክሌይ ጳጳስ ስለነበረ ሁሉ ነገር ተዘጋጅቶ የሚቀር ብለት በመሆኑ የቁስአካልን መኖር ሊክድ ችሏል ። አባባሉ የሚገልጸው ከምርት ነፃ የሆነውን በሐሳብ ደረጃ ብቻ ከነገሮችና ከሰዎች ጋር የሚገናኘውን ሁሉ ነገር ለሱ ድሎት የተፈጠረ የሚመስለውን የገዥው መደብ ሁኔታ ነው ።

(ራሳዊነትን፣ ዳሳሽነትን፣ ኀሊናዊ ሐሳባዊነትን ይመለከቷል ።)

## በርግሰን ፣ አንሪ
*(Bergson, Henri)*

ከ1859—1941 የኖረ ፣ የጭልታዊነትና የሕይወታዊነት ፍልስፍና አራማጅ የሆነ የፈረንሳይ ሐሳባዊ ፈላስፋ ነው ። "ማቲዬር ኤ ሜሟር" ፣ "ሌቮሊሲዮን ክሪአትሪስ" ፣ "ሌ ደሱርስ ደላ ሞራል ኤ ደላ ረሊዢዮን" በተባሉት ዐበይት ጽሑፎች ውስጥ የሕይወትን ምንነት በቁስአካላዊ ምክንያት ልንረዳ የማንችል መሆናችንንና ሕይወት ያለው ጠባይ መንፈሳዊ ኃይልና ባሕርይ የሚያሳይ ነው የሚል መሪ ሐሳቡን አብራርቷል ።

በበርግሰን አስተሳሰብ ቁስአካል የራሱ ህልውና ያለውና በራሱ ሕግጋት የሚገዛ ሲሆን ሕይወት ደግሞ የተለየ ኑባሬ ነው ። ፍልስፍና ይህን የዓለም ሁለታዊነት መቀበል ይኖርበታል ። ሁለት ዓይነት እውነታም በመኖሩ ዕውቀት በሁለት መደቦች የሚከፈል ይሆናል ። ቁስአካል የሚገዛው በተናክአታዊ ሕጐች በመሆኑ ለሱ ተስማሚ የሆነው የዕውቀት ዓይነት በማቲማቲካዊ ሥነ አምክንዮ የሚመራው ሳይንስ ተብሎ የሚታወቀው ነው ። ይህ ሳይንስ መንፈሳዊ ምክንያቶችን ሳይጨምር ቁስአካላዊ ክስተቶችን ያጠናል ፤ በሚያገኘውም ዕውቀት ሰው ተፈጥሮን መቆጣጠር እንዲችል ቴክኖሎጂያዊ ግኝቶችን ያዳብራል ።

ሕይወት ግን በተናክአታዊ ሕግ ስለማይገዛ የተለየ ግንዛቤ ይጠይቃል ። የሕይወት ዋናው ጠባይ እራስን በማሳደግ የተለያዩ ችሎታዎችን ማካበት ነው ። ይህም ዕድገት የሚገኘው መጠን በመጨመር ሳይሆን ፈጠራ በሚጠይቅ ሁኔታ የዓይነት ለውጥ በማድረግ ነው ። የሕይወት አዝጋሚ ለውጥ የሚያሳየን ሕይወት እንዴት ፈጠራ በተሞላበት ሁኔታ ከአነስተኛ ችሎታ ተነሥቶ ሰውን የሚያክል አሳቢ ፍጡር እንዳስገኘ ነው ። እንደ በርግሰን አባባል ይህን የዓይነት ለውጥና የፈጠራ ችሎታ ለመገንዘብ አዲስ የአስተሳሰብ ዘዴ መንደፍ ይኖርብናል ። ይህን ዘዴ ጭልታ ብሎ ሰይሞታል ። ሳይንስ ነገሮችን የሚያጠናው ከቦታ አኳያ ነው ፤ ማለትም ተናክአታዊ ክንዋኔን በመከተል ነገሮችን በምክንያትና በተግብሮት አንፃር ይረዳል። ጭልታ ግን ነገሮችን የሚመለከተው ከጊዜ አኳያ ነው ። የሚያየው የነገሮችን መነካካት ሳይሆን ውስጣቸው በመግባት እንዴት ሕይወታዊ ነገሮች እራሳቸውን በራሳቸው በመፍጠር እንደሚያድጉ ነው ። የለውጡ መንሥኤ ተናክአት ሳይሆን የአንድ አደራጅ የሆነ ሕይወታዊ ግፊት ውጤት እንደሆነ ይረዳል ። ይህ ግፊት አንደኛ ውስጣዊ በመሆኑ ፣ ሁለተኛ ነገሮችን የሚደረድር ሳይሆን ክስተቶችን በማደራጀት ጨምቆ አዲስ ነገር የሚያወጣ በመሆኑ የሚገለጸው በጭልታ ብቻ ነው ።

የኅብረተሰብንም ሂደት የሚመራው ይኸው ሕይወታዊ ግፊት ነው የሚል እምነት በርግሰን ነበረው ። በሱ አባባል ኅብረተሰብ በሁለት ተቃራኒ አዝማሚያዎች የተወጠረ ነው ። አንደኛው ሰዎችን በቤተሰብ ፣ በጐሣ ፣ በብሔረሰብ የሚከፋፍል ነው ። ሁለተኛው ሰዎችን በማሰባሰብ አንድ የሆነ የሰው ልጅ ኅብረተሰብ ለመመሥረት የሚጥር ነው ። የመጀመሪያው አዝማሚያው በሚጠይቀው መሠረት የሰዎች ግብረገብና ማኅበራዊ ፋይዳዎች ይቀረፃሉ ። ግዴታዎችም በትዕዛዝ መልክ ይነደፋሉ ፤ የሚገልጹትም ግለሰቡ የማኅበሩ አባል ለመሆን የሚጠበቅበትን አመለካከትና ድርጊት ነው ። ሁለተኛው አዝማሚያ ከሕይወታዊ ግፊት የሚመነጨው ሲሆን ሁለንታዊ ግንዛቤዎችንና መብቶችን በማፍለቅ የተዘጋውን ኅብረተሰብ ለመክፈት ይጥራል ። ይህ አዝማሚያ የሚራመደው በአንዳንድ ምርጥ በሆኑና ኅብረተሰቡን የመምራት ችሎታ ባላቸው ታላላቅ ታሪካዊ ግለሰቦች ነው ። ለምሳሌ የክርስትና ሃይማኖትና የፈረንሳይ አብዮት ጐሣዊና ብሔራዊ ከሆኑ አመለካከቶች ባሻገር ሁለንታዊ ፍችና ተልዕኮ ያሳዩ ናቸው ።

የበርግሰንን ፍልስፍና ውስጠ ምሥጢር የምንረዳው ሳይንስን በመወሰን ሕይወትና መንፈሳዊ ነገሮችን ከሳይንሳዊ ዕውቀት በላይ ለማድረግ ካለው ፍላጐት አንፃር ስንመለከተው ነው ። የዚህም ፍላጐት ዋናው ምክንያት የሐሳባዊ ፍልስፍና መሠረታዊ እምነቶችን መጠጊያ በመስጠት ከቁስአካላዊ ፍልስፍና የሚሰነዘርባቸውን ጥቃት ለማከሸፍ ነው ። ሕይወትን ከቁሳዊ ፍች ማራቅና ምሥጢራዊ ማድረግ ኅብረተሰቡ በታላላቅ ነገር ግን ባዶ በሆኑ ወይም ለተግባራዊነታቸው ቁሳዊ ኃይል ባልተሰጣቸው ስሜቶች ውስጥ እንዲዝናናና እራሱን እንዲያታልል ማድረግ ነው ። የሰው ዘር አንድነት ፣ የሰው እኩልነት ፣ የፈጠራ ደስታ ፣ የቅራኔዎች መወገድ፣ የሰላም መስፈን ፣ ዕድገት ፣ ነፃነትና የመሳሰሉትን ሐሳቦች ከቁሳዊ መሠረታቸው በመነጠልና ወደ አደንዛዥ ስሜት በመለወጥ ሰዎችን በባዶ ለመደለል የሚጥር ፍልስፍና መደባዊ ፍችው ግልጽ ነው ። በእርግጥ በርግሰን ለሕይወት ተናከአታዊ ትርጉም በቂ አለመሆኑን መመልከቱ ጥሩ ሲሆን ትክክለኛ መልሱ ግን የሚገኘው ወደ መንፈሳዊ ምክንያት በማዘንበል አልነበረም ። የዕድገት ፍልስፍና እራምዳለሁ ከተባለም ተገቢ የነበረው ቁስአካል ከቀላል ወደ ውስብስብ እንዴት እንደሚሻገር ማሳየቱ ነበር ። በቅድሚያ ለሕይወት መንፈሳዊ ባሕርይ ከተሰጠው ዕድገቱን እንዳልነበረ ማድረግ ነው ። በተጨማሪም እውነታ የሚገኘው በዕድገት ላይ ነው ከተባለ ፍጹም የሆነ አምላክ አለ ብሎ በቅድሚያ ማስቀመጡ ዕድገቱን ምናባዊ ማድረግ ነው። በመሆኑም በርግሰን ሐሳባዊነትንና የአዝጋሚ ለውጥ ንድፈሐሳብን ለማስማማት ያደረገው ጥረት የተሳካ አይደለም ። በሌላ በኩል ጭልታ በዕውቀት ውስጥ ያለውን ሚና ማሳየቱ የሚደገፍ ሲሆን ወደ ሌላው ጫፍ በመሄድ ራሱን የቻለና ከሥነ አመክንዮ ሕጐች በላይ እንደሆነ አድርጐ ማቅረቡ ዕውቀት እራሱን ለዐዋቂው ምሥጢራዊ የሚያደርግ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ። ዕውቀት እራሱ ምሥጢራዊ ከሆነ እንዲያስረዳን የሰጠነውን ዓለም መልሶ ምሥጢራዊ ከማድረግ በስተቀር ሌላ ውጤት ሊኖረው አይችልምና ።

(ጭልታዊነትን ፣ አዝጋሚ ለውጥን ፣ ሁለታዊነትን ይመለከቷል ።)

## ቡርዧዚ

*(Bourgeoisie)*

ቡር (ከተማ) ከሚለው የፈረንሳይኛ ቃል የመጣ ሲሆን ፍችው ከተሜ ማለት ነበር ። ከዚያም ቀስ በቀስ በፊውዳሊዝም ሥርዓት መጨረሻ ላይ የገንዘብ ሀብት ያለውና መሳፍንትን የሚቃወመው የኅብረተሰብ ክፍል መጠሪያ ሆነ ። አሁን ባለው አገባቡ የሚያመለክተው የምርት መሣሪያ ባለቤት የሆነውንና በምንዳ ሠራተኞችን ቀጥሮ የሚያሠራውን ዘመናዊውን የካፒታሊስቶች መደብን ነው ። ቡርዧዚ የካፒታሊዝም መሠረታዊ መደብና የወዝአደሩ ተፃራሪ ነው ።

ለቡርዧዚው መጸነስና ማደግ ምክንያት የሆነው ታሪካዊ ሁኔታ የአሜሪካ ግኝትና የህንድና የቻይና ገበያዎች መከፈት ነው ። ይህ ሁኔታ ንግድንና ኢንዱስትሪን በጣም ያስፋፋ በመሆኑ በመውደቅ ላይ ባለው የፊውዳል ኅብረተሰብ ውስጥ ለነበረው አብዮ

ታዊ ክፍል ፈጣን ዕድገት ሰጥቷል ። ከዚያም በማሽን የማምረቻ መሣሪያዎች በመጠቀምና ብዙ ሀብት በማከማቸት መካከለኛ መደብ የነበረው የቡርዧ ክፍል ዘመናዊና እጅግ ሀብታም ወደ ሆነው የካፒታሊስቶች መደብ ተቀየረ ። የቡርዧዚው ኢኮኖሚያዊ ኃይል ባደገ ቁጥር የፖለቲካ ኃይሉም እየጨመረ በመሄዱ በመጨረሻም የመንግሥትን ሥልጣን ሙሉ በሙሉ መጨበጥ ችሏል ።

በታሪክ ሂደት ውስጥ ቡርዧዚው ከፍተኛ የሆነ አብዮታዊ ሚና ተጫውቷል ። የበላይነት ባገኘባቸው ሀገሮች ሁሉ የፊውዳልን ግንኙነቶችንና የነበራቸውን መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ፍች ውድቅ በማድረግ በገንዘብ ግንኙነቶች ተክቷቸዋል ። የቡርዧዚ የማይረካ የትርፍ ፍላጎትና የማያቋርጥ የእርስ በእርስ ውድድር የማምረቻ መሣሪያዎች በየጊዜው እንዲያድጉና ኅብረተሰቡም በማያቋርጥ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲጓዝ አድርጓል ። የገበያ ፍላጎት የካፒታሊዝም ግንኙነት በዓለም እንዲዘረጋና ኋላቀር ሀገሮችም የካፒታል ተገዥ በመሆን ዘመናዊነትን እንዲቀምሱ አድርጓል ። የከተማን ነዋሪ በማብዛት ብዙ ሕዝብ ከኋላቀር የገጠር ኑሮ ሊላቀቅ ችሏል ። ቡርዧዚ ሕዝብን በማሰባሰብ የምርት መሣሪያዎችን በማዕከል እንዲሠሩና የጥቂት ሰዎች ንብረት እንዲሆኑ በማድረግ ፖለቲካዊ ማዕከልነትን አጠናክሯል ። የተለያዩ ክፍሎች በአንድ ብሔር ሥር እንዲሰባሰቡ በማድረጉ የአንድ መንግሥት ፣ የአንድ ሕግ ፣ የአንድ ብሔራዊ መደብ ጥቅም ተገዥ ሊሆኑ ችለዋል ።

ሆኖም ይህ ቡርዧዚ የፈጠረው ከፍተኛ የማምረት ኃይልና የሀብት ክምችት ከቡርዧው የምርት ግንኙነቶች ጋር የሚጣጣም አልነበረም ። በአንድ በኩል ሀብት ሲከማች በሌላ በኩል ግን በየጊዜው ቁጥሩ እያደገ የሚሄደው የወዝአደሩ መደብ መበዝበዝና ለኢኮኖሚ ቀውስ በየጊዜው መጋለጥ ለቡርዧ ኅብረተሰብ የተረጋጋ ሥልጣንና የዕድገት ሂደት ሊሰጠው አልቻለም ። ሀብቱ ብዙ ፣ ተጠቃሚዎቹ ግን ጥቂት መሆናቸው ቡርዧዚ ሊፈታው ከማይችለው ቅራኔ ውስጥ ኅብረተሰቡን ከቶታል ። ዘመናዊ የምርት መሣሪያዎች የሚፈጥሩት ማኅበራዊ የአመራረት ዘዴ ከቡርዧዚ የግል ንብረትና የሥልጣን ተዋረድ ጋር የማይጣጣም ከመሆኑም በላይ እራሱ ቡርዧዚውን የሚያጠፉ ፣ የምርት ኃይሎች የሚጠይቁትን ተስማሚ የምርት ግንኙነት ሊመሠርት የሚችል አብዮታዊ የወዝአደር መደብ በካፒታሊዝም ውስጥ ማደግ ፣ መደራጀትና የራሱን አመለካከት መያዝ የቡርዧዚን ውድቀት አይቀሬ አድርጎታል ።

(ካፒታሊዝምን ፣ ወዝአደርን፣ የቡርዧ አብዮትን ይመለከቷል። )

## ቡርዧ አብዮት (የ—)

*(Bourgeois Revolution)*

በአዲሶቹ የምርት ኃይሎችና በአሮጌዎቹ የፊውዳል የምርት ግንኙነቶች (በተለይ በፊውዳል የምርት ግንኙነቶች ላይ ተዋቅሮ በሚገኘው ፖለቲካዊ ሥርዓት) መሀከል ያለውን ቅራኔ የፈታ ፣ በቡርዧ መደብ ተመርቶ ገበሬውንና ወዝአደሩን አሰልፎ የፊውዳሉን ሥርዓት ያፈረሰና ካፒታሊዝምን የገነባ ፣ በቡርዧዚው የተመራ ነገር ግን ቡርዧዚው ከመሳፍንቱና ከመኳንንቱ ጋር ተመሳጥሮ ወዝአደሩንና ገበሬውን የአብዮት ድል ተቋዳሽ እንዳይሆኑ ያደረገበት አብዮት የቡርዧ አብዮት ይባላል ። ይህ ፈርጅ በቅኝ ግዛቶችና በጥገኛ ሀገሮች ውስጥ የሚካሄደውን ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ፊውዳል አብዮት ያጠቃልላል ። የዚህ ዓይነት አብዮቶች ፀረ ካፒታሊስት የሆኑ አንዳንድ እርምጃዎችን የመውሰድ ባሕርይ ቢታይባቸውም የካፒታሊስት ሥርዓት መሠረት የሆነውን የማምረቻ መሣሪያዎችን የግል ባለቤትነት ስለማይደመስሱ በአጠቃላይ ባሕርያቸው ከቀድሞዎቹ የሚለዩ አይደሉም ። የቡርዧ አብዮት በታሪክ በተለያዩ ሀገሮች ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት የተከሰተ ቢሆንም ጉልቶ የታየው በ16ኛው ምዕት ዓመት ነው ።

በ16ኛው ምዕት ዓመት የተጀመረው ፊውዳሊዝምን የማፍረስ ሂደት እንደየሁኔታው በዓለምአቀፍ ደረጃ አልፎ አልፎ ሲካሄድ ይታያል ። በቅኝ ግዛትና በጥገኝነት በሚገኙ የአፍሪካ ፣ የእስያና የላቲን አሜሪካ ሀገሮች የሚካሄዱት የቡርዧ አብዮቶች የዚህ ማሰረጃ ናቸው ። ይህም የቡ

ርዧውን አብዮት የተለያዩ መደቦች ሊመሩትና ሊሳተፉበት እንደሚችሉ የሚያሳየን ነው ። በቅድመ ሞኖፖል ካፒታሊዝም የዕድገት ደረጃ ላይ የቡርዧው አብዮት ብቸኛ መሪ ቡርዧዚው ሲሆን በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም ግን በአብዮቱ የዕድገት አቅጣጫና ውጤት ላይ የወዝአደሩ መደብ ተፅዕኖ ከፍተኛ እየሆነ ከመምጣት አልፎ እንዲያውም በ1905 የሩሲያ አብዮት እንደታየው በአንዳንድ ሀገሮች ውስጥ በወዝአደሩ ተመርቷል።

የቡርዧ አብዮቶች ለአብዮቱ እንደሚያሰልፏቸው መደቦችና እንደሚያስገኙዋቸው ውጤቶች ፣ የቡርዧ አብዮትና የቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮቶች ተብለው ይከፈላሉ ። የቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የሚባለው በቡርዧዚው ተመርቶ ወዝአደሩና ገበሬው የተሳተፉበት ፣ ገበሬው ለመሬት ስሪት ለውጥ ከሚያደርገው ትግል ጋር የተዛመደበት ፣ ሕዝባዊው ጥያቄ ከቡርዧዚው ጥያቄ ቢለይም ሰፊው ሕዝብ የሚሳተፍበት አብዮት ነው ። በታሪክ ውስጥ ከነበራቸው ሚናና ከአንቀሳቃሽ ኃይሎቻቸው አንፃር ሲታዩ እርስ በርሳቸው የሚለያዩ በርካታ የቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮቶች ተካሂደዋል ።

የቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ዲሞክራሲያዊ ገጽታ አለው የሚባለው እስከ ተወሰነ ደረጃ ቢሆንም ለገበሬው ዲሞክራሲያዊ ጥያቄ መልስ ስለሚሰጥ ነው ። ከ1789—94 የተካሄደው የፈረንሳዩ የቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮት አንድ በቂ ምሳሌ ነው። በቡርዧዚው የተመራው አብዮት ፀረ ፊውዳል የነበረና ለቡርዧዚው የኢኮኖሚና የፖለቲካ የበላይነትን ያጐናፀፈ አብዮት ነው ። በወቅቱ ፀረ ፊውዳል የነበረ አብዮት የሚያመራው ወደ ካፒታሊዝም በመሆኑ አብዮቱ በቡርዧዚው መመራት ነበረበት ።

ሌላው ደግሞ በኢምፔሪያሊዝም የመጀመሪያ ወቅትና በካፒታሊዝም የመጀመሪያ አጠቃላይ ቀውስ ጊዜ የተካሄደው የቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ነው ። በዚህ የኅብረተሰብ የዕድገት ደረጃ ላይ ካፒታሊዝም ወደ ኢምፔሪያሊዝም ደረጃ በመሸጋገሩ ቡርዧዚው ካፒታሊዝምን የመገንባቱን የታሪክ ኃላፊነትና አብዮታዊነት ጨርሶ ወደ አድኃሪነት ፣ ወደ ፅድገት ጐታችነት የተሸጋገረበት ወቅት በመሆኑ በፀረ ፊውዳል አብዮት ውስጥ ለመሳተፍና አመራር ለመስጠት አልቻለም ። ይልቁንም ከመሳፍንቱና ከመኳንንቱ ጋር አጋርነት ይፈጥራል ። በዚህ ጊዜ የሚካሄደው አብዮት የወዝአደሩ መደብ ከገበሬው ጋር በሚፈጥረው አጋርነት የሚመራና ወደ ሶሻሊስት አብዮት ሊያመራና ሊያድግ የሚያስችል ሁኔታ የሚፈጥርበት ነው ። የ1917 የካቲት አብዮት ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌ ነው ።

በመጨረሻም በቅኝ ግዛትና በጥገኛ ሀገሮች ውስጥ በሁለተኛው የካፒታሊዝም የቀውስ ደረጃ ላይ የተካሄደው ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ፊውዳል የቡርዧው ዲሞክራሲያዊ አብዮት ነው ።

ቀደምሲል እንደተገለጸው ወዝአደሩና ገበሬው የተሳተፉባቸው ከውጤታቸውም ተጠቃሚ የሆኑባቸውና በቡርዧዚው የተመሩት የቡርዧው ዲሞክራሲያዊ አብዮት መልኮች ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ የወዝአደሩና የገበሬው ተሳትፎ በጣም "ያልጐላባቸው" እምብዛም ጥቅም ያላገኙባቸው የቡርዧ አብዮቶች ተካሂደዋል ። ለምሳሌ የ1848 የጀርመን ቡርዧዚ የወዝአደሩን የትግል አጋርነት ቢፈልግም የኃይሉን መጠናከር ስለፈራ ከመሳፍንቱና ከመኳንንቱ ጋር አጋር በመሆን የመሬት ጥያቄን ለገበሬው በሚጠቅም ሳይሆን ለመሳፍንቱ በሚበጅ መንገድ መፍትሔ ሰጥቷል ። እንዲሁም የእንግሊዝ ቡርዧዚ በአብዮቱ ውስጥ ገበሬውንና ወዝአደሩን በመክዳት የመሬትን ጥያቄ ለመሳፍንት በሚጠቅም ሁኔታ ከመፍታቱም በላይ ገበሬው ያለውን መሬት ከነጭራሹ በመንጠቁ ከ19ኛው ምዕት ዓመት መጨረሻ እንሥቶ ገበሬው እንደ መደብ መኖሩ አከተመ ።

(አብዮትን ፣ ኢምፔሪያሊዝምን ፣ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ይመለከቷል ።)

## ቡንድ

*(Bund)*

ቡንድ የሚለው ቃል በይዲሽ ቋንቋ ኅብረት ማለት ሲሆን በ1897 በቪልና ከተማና በምዕራብ ሩሲያ ግዛቶች ውስጥ የሚኖሩ የአይሁድ እደጥበብ ባለሙያዎች የመሠረቱት ኅብረት ነው ። ትክክለኛ መጠሪያው

"በሊቱዌንያ ፣ በፖላንድና በሩሲያ የሚገኙ የአይሁድ ሠራተኞች ጠቅላላ ኅብረት" ነበር ።

ድርጅቱ በመጀመሪያ የሶሻሊዝምን ፈር የተከተለና ይህንኑም ሐሳብ የሚያራምድ ነበር ። በመሆኑም የአይሁድ ወዝአደሮችን በሚያስመለክት ጉዳይ ላይ ብቻ ነፃነቱ እንደ ተጠበቀ ቆይቶ በሌሎች ጉዳዮች ረገድ ከሩሲያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ሌበር ፓርቲ (ሩ.ሶ.ዲ.ሌ.ፓ.)ጋር ለመተባበር ራስገዝነት ያለው አባል ሆኖ ኅብረት ፈጠረ ። ነገር ግን ቡንዱ የአይሁዶችን የጠባብነት መሥመር እያፋፋመ በመምጣቱ ኅብረቱ ከ1901 ጀምሮ ውጥረት ላይ ወድቆ ዓቢይ የሆነ የመሥመር ልዩነት በውስጡ ተከሰተ ። ከዚያ ወቅት ጀምሮ ቡንዱ ከሜንሼቪኮች ጋር ተደምሮ በግል ልሳኖቹ እማካይነት ቦልሼቪኮችን በግልጽ ከመቃወም ባሻገር ሩ.ሶ.ዲ.ሌ.ፓ. አንድ ወጥና ብሔር አቀፍ ፓርቲ በመሆን ፈንታ በብሔረሰብ መሥመር በአዲስ እንዲዋቀር ጥያቄ አቀረበ ። ጥያቄው ተቀባይነት ማጣቱ እንደታወቀ ቡንዱ ከፓርቲው ተነጥሎ ከጽዮናዊነት እንቅስቃሴ ጋር ኅብረት ፈጠረ ።

የቦልሼቪክ አብዮት መፋፋም ግልጽ እየሆነ ሲሄድ ማለትም በ1906 ቡንዱ እንደ ገና ከሩ.ሶ.ዲ.ሌ.ፓ. ጋር በድጋሚ ኅብረት ፈጠረ ። እሁንም ቢሆን ቡንዱ ከጠባብ ብሔረተኝነት መሥመሩ ምንም እልፍ እላለም ። በተለይም "ብሔሮች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው ለመወሰን ያላቸውን መብት" በማስመልከት ፓርቲው ያቀረበውን ጥያቄ መሠረታዊ ይዘት በፍጹም ሊቀበል ባለመቻሉ የሁለቱ ድርጅቶች "ኅብረት" ትርጉም አልባ መሆኑ በመታወቁ በ1912 በፕራግ ላይ በተደረገው የመላው ሩ. ሶ. ዲ. ሌ.ፓ. ጉባኤ ላይ ቡንዱ ከኅብረቱ ተወገደ ። ከ1914 ጀምሮ የጥቅምቱ አብዮት ድል አድርጐ የሶቭዬት መንግሥት እስከ ተቋቋመበት ጊዜ ድረስ ቡንዱ በቦልሼቪኮች ላይ ያልተቆጠበና ያላሰለሰ ዘመቻ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ሀገር በማፋፋም ላይ ነበር ። ነገር ግን የቡንድ መሪዎች የሚያካሂዱትን የጠባብነት ዘመቻ የተረዱት የቡንዱ ሰፊ አባላት ድርጅታዊ ህልውናቸውን ስርዘው በ1921 የሩሲያ ኮሚኒስት ፓርቲ (ቦልሼቪክ) አባላት ሆነዋል ።

## ቡዋጊልቤር ፣ ፒዬር

*(Boisguillebert, Pierre)*

ከ1646 - 1714 የኖረ ፈረንሳዊ ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚስት ነው።ቡዋጊልቤር የኢኮኖሚ ጥናቱን የጀመረው በ1670ዎቹ ነው ። ማርክስ «ኮንትሪቢዩሽን ቱ ዘ ክሪቲክ ኦቭ ፖለቲካል ኢኮኖሚ» በተባለው ጹሑፍ ውስጥ ለመቶ አምሳ ዓመታት ያህል ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በእንግሊዝ በዊልያም ፔቲና በፈረንሳይ በቡዋጊልቤር ተጀምሮ በእንግሊዝ በሪካርዶና በፈረንሳይ በሲስሞንዲ አበቃ በማለት አድናቆቱን ገልጿል ።

ቡዋጊልቤር በፈረንሳይ የብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መሥራች የሚል ግምት ሊሰጠው የቻለው በተለይ የእሴት የሥራ ንድፈ ሐሳብን በሚመለከት ባቀረበው ጥናታዊ አስተያየት የተነሣ ነው ። በዚህ አስተያየቱ የገበያ ዋጋንና እውን እሴትን ለይቶ ከማቅረቡም ሌላ አንድ ሸቀጥ ለማምረት የሚፈጀውን ጊዜ እውን እሴት ብሎ ጠርቶታል ። ቡዋጊልቤር በጥናቶቹ ውስጥ "የተሟላ የዋጋ አመሠራረት" የሚል ጽንሰ ሐሳብ በማስተዋወቅ ይህም ዋጋ ፣ ወጪንና ትርፍን እንደሚይዝና በነፃ ንግድ ውስጥም እንደሚሠራ በመግለጽ ጽፎአል ።

የቡዋጊልቤር ሌሎቹ የኢኮኖሚ ጥናቶች ያተኮሩት በሦስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ነበር። እነዚህም ፦

1. በወቅቱ በፈረንሳይ ውስጥ ሰፊ የታክስ መሻሻል ስለማስፈለጉ ፣ ይህም በወቅቱ ልሁላኑ ፣ መሳፍንቱና መኳንንቱ ከፍተኛ ገቢ ኖሯቸው ምንም ታክስ ስለማይከፍሉ ታክስ ይከፈሉ፣
2. ለሀገር ውስጥ ንግድ መዳበር መሰናክል የነበሩት የከፍላተ ሀገር የጉምሩክ ቀረጦች ይነሡ ፤
3. ለእህል ንግድ የነፃ ገበያ ይከፈት የሚሉ ናቸው ።

ከነዚህም ሌላ ቡዋጊልቤር በወቅቱ ስለ ነበረው የተመሳቀለ የፈረንሳይ የኢኮኖሚ ሁኔታና ስለፈረንሳይ የገጠር ሕዝብ የሥቃ

ይና የድህነት ኑሮ በስፊው ጽፎአል ። በዚህ ጽሑፉ ውስጥ የነዚህ ሁሉ ችግሮች መሠረታዊ ምክንያቶች የፈረንሳይ መኳንንት ፣ መሳፍንትና ልዑላን እንደነበሩና የኢኮኖሚውም ሥርዓት ገበሬውን ከማሠቃየቱም ሌላ ገበሬው መሬቱን እንዳያለማና ምርቱን እንዳያበዛዛ ማነቆ እንደሆነበት ገልጿል ። በዚህ ጽሑፉም በግልጽ የንጉሥ ሉዊ አሥራ አራተኛን ፖሊሲ ተቃውሟል ።

ቡዋጊልቤር ገንዘብን የማንኛውም ብሔራዊ ችግር መንሥኤ አድርጎ ይገምት ስለነበር እንደ መጥፎ ነገር አድርጎ ቆጥሮታል ። ሸቀጦች በውስጣቸው ባለው የተጨባጭና የረቂቅ ሥራ ቅራኔ መሠረት የሸቀጦች የገንዘብ መልክ አስፈላጊ መሆኑን አለመረዳቱ ዋናው ድክመቱ ሲሆን የካፒታልን የገንዘብ መልክ አለመገንዘቡ ሌላው ሊጠቀስ የሚችል ድክመቱ ነው ።

## ቢሮክራሲ

*(Bureaucracy)*

ቢሮክራሲ ከግሪክ የመጣ ቃል ሲሆን ትርጉሙም ፤
ቢሮ—መሥሪያ ቤት
ክራሲ—ኃይል

ቢሮክራሲ የሚያመለክተው ሰዎች በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና በአንዳንድ ከፍተኛ ድርጅቶች ውስጥ በሚይዙት ቦታ የሚሰጣቸውን ኃላፊነትና ሥልጣን ሲሆን ከዚሁ ጋር የሚፈጠረውን የአስተዳደር መዋቅርና የአሠራር ዘይቤንም የሚያቅፍ ነው ። በመሆኑም ቢሮክራሲ በመሠረቱ የፖለቲካ ጽንሰ ሐሳብ ነው ።

ቢሮክራሲ ከካፒታሊዝም ዕድገትና በተለይም ከፍተኛ የሥራ ክፍፍል ያለባቸውን የመዋቅር አውታሮችን ከያዙ ትላልቅ ድርጅቶች አሠራር ጋር የተያያዘ ነው ። የቢሮክራሲ አሠራር የሥልጣን እርከኖችና የደብዳቤ ልውውጥ የበዙበት፣ጉዳዮች በቀላሉ ውሳኔ የማያገኙበትና በኃላፊነት መንዛዛት ምክንያት የአፈጻጸም ውስብስብነት የጐላበት ፣ አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎችንና የሥራ ማሻሻያ ዘዴዎችን እየተጠቀሙ ሥራን ከማቀላጠፍ ይልቅ ወግ አጥባቂነትና ለዘብተኝነት የሰፈነበት ነው ። በአጠቃላይ ሥርዓት ፣ ጥራትና ቅልጥፍና ካለውና ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ ጠቃሚ ከሆነው አሠራር አንፃር ሲታይ በጥልፍልፍና በዝርዝር የአስተዳደር ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር የአሠራር ልምድ ነው ።

እንደማክስ ቬበር ያሉ ቡርዧ ምሁራን ቢሮክራሲን እንደአጠቃላይ የዕድገት ውጤትና እንዲያውም ለትላልቅ ድርጅቶች ሥራ መቀላጠፍ የሚያግዝ አሠራር አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ ። እውነቱ ግን ቢሮክራሲያዊ አሠራር ቡርዧዚዎች መደባዊ ጥቅማቸውን ለማራመድ የሚጠቀሙበት ስልት ነው ።

በመሆኑም ይህ የቢሮ ወይም የአስተዳደር አደረጃጀት የካፒታሊስቱ ሥርዓት ያስከተለው እንደመሆኑ ሥርዓተ ማኅበሩ በሚለወጥበት ጊዜ አስተዳደራዊ መዋቅሮችና የአሠራር ግንኙነቶችም በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርህ መሠረት እየተለወጡ ለሠርቶ አደሩ ንቁ ተሳትፎ በሚያመችና የሕዝቡን ጥቅም በሚያራምዱ አሠራሮች መተካት ግዴታ ነው ። ከዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርህ ሌላም እንደሶቭዬት ባሉትና በሌሎች የሶሻሊስት ሀገሮች መንግሥታዊ መዋቅሮች፣ በሕዝባዊ ድርጅቶችና በመሳሰሉት አደረጃጀቶች ውስጥ ቢሮክራሲያዊ አስተዳደር እንዳይሰፍን መከላከያው ሶሻሊስት ስልት የምርጫ ፣ የደመወዝ ክፍያና እንዲሁም የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት በአዲስ መልክ መዘርጋት ነው ። በዚህ መርህ መሠረት ፣

—ምርጫ ሲባል በአንድ ድርጅት ወይም ሌላ መዋቅር የሚገኝ መሪው አካል በአመራር ወይም በተለያዩ ዘርፎች የሚያገለግሉ አካላትን የመምረጥ ብቻ ሳይሆን እነዚሁ የተወሰኑላቸውን የጊዜ ገደብ ሲጨርሱ የመለወጥ ወይም የተጣለባቸውን ኃላፊነት በትክክል መወጣት ሲያቅታቸው በአግባቡ የመሻርና የመለወጥ መብት አለው ።

—ምንም እንኳ በየደረጃው እንደሚፈለገው ሙያ ከፍተኛነትና እንደ ኃላፊነቱም ክብደት የሰዎች ደሞዝ (ክፍያ) ቢለያይም በተቻለ መጠን በአንድ ንቁና ታታሪ ሠራተኛ ደመወዝና በሚመረጡ አካላት መካከል

ያለው የክፍያ ልዩነት በኑሮም ረገድ ስፊ ልዩነት እንዳያስከትል ጥንቃቄ ይደረጋል ።

—እነዚህና ሌሎችም አሠራሮች በሥርዓት መከናወናቸውንና በሶሻሊዝም ዓላማዎች የኅብረተሰቡን የጋራ ጥቅም የማይፃረሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓትን ማስፈን ደግሞ ዋነኛ መተማመኛ ነው ። ይህ የአሠራር መርህ ተግባራዊ የሚሆነው ግን እንደየሀገሩ ተጨባጭ ሁኔታና የአብዮቱ ዕድገትና የግንባታው ውጤት እንደሚደርስበት ደረጃ እየታየ በመሆኑ በአፈጻጸሙ ረገድ ብዙ ልዩነቶች ሊከሰቱ ይችላሉ ።

(ሶቪዬትን ፣ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን ፣ ሕዝባዊ ቁጥጥርን ይመለከቷል ።)

## ባህላዊ ብሔራዊ ራስገዝነት

*(Cultural National Autonomy)*

በ1890ዎቹ ዓመታት የኦስትሪያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ መሪዎች በብሔር ጥያቄ ላይ ያራምዱት የነበረው አድርባይ አቋም ነው ። ይህ አቋም የአንድ ብሔር ወይም ብሔረሰብ አባላት የትም ይኑሩ የት ባሉበት ሀገር ውስጥ ብሔራዊ መለያቸውን የመጠበቅ መብት በክልል የማይወሰን በመሆኑ የእያንዳንዱን ብሔር ወይም ብሔረሰብ ትምህርታዊና ባህላዊ እንቅስቃሴዎች ለመቆጣጠር ሙሉ መብት ባለው አንድ ነፃ ብሔራዊ ማኅበር ወይም ድርጅት እንዲሰባሰቡ ይጠይቃል ። በዚህ መሠረት የሚቋቋመው ብሔራዊ ተቋም የሚፈቅደው መብት ሲታይ ደግሞ መሠረታዊ የሆነውን የኢኮኖሚ ባለቤትነትና የፖለቲካ ሥልጣን መጐናፀፍ ሳይሆን ባህሉን ብቻ "መጠበቅና ማዳበር" ነው ። ይህም መብት ተግባራዊነት የሌለው ከመሆኑም ሌላ ሕዝቦችን የሚያስልፋቸው በመደብ እንፃር ሳይሆን በብሔር ነው ። በመሆኑም የወዝአደሩን የመደብ አንድነትና ዓለም አቀፋዊነትን የሚያዳክም ፣ የሠራተኛውን ኃይል የሚበታትን ብሔረተኝነትን የሚያስፋፋ ነው ።

ባህላዊ ብሔራዊ ራስገዝነት ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ ኦቶ ባወርና ካርል ሬነር ያሉ የኦስትሪያ ማኅበራዊ ዲሞክራቶች በ1899 በብሩን ከተማ ባደረጉት ጉባኤ ላይ ለብሔሮች ጥያቄ መፍትሔ አድርገው አቅርበውት ነበር ። በሩሲያም የቡርዧ አፈቀላጤዎች የነበሩ ደምሳሾች ፣ ቡንዲስቶችና ሌሎችም አድኃሪ ኃይሎች ይሙሁለት የነበረ መፈክር ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ ሌኒን በኦስትሪያ ማኅበራዊ ዲሞክራቶች የወጣው የባህላዊ ብሔራዊ አውቶኖሚ ፕሮግራም ፍጹም ቡርዧዊና በተሳሳተ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ፣ ሕዝቦችን በልዩ መንግሥታዊ ተቋም ለመነጣጠል የታቀደ መሆኑን በተለያዩ ጽሑፎች ገልጿል ።

(የብሔር ጥያቄን ይመለከቷል ።)

## ባህል

*(Culture)*

ኅብረተሰቡ በታሪካዊ ሂደት ውስጥ የፈጠራቸው ቁሳዊና መንፈሳዊ ፋይዳዎች ፣ እነሱንም ለማዳበርና ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች ጥምር ባህል ይባላሉ ። ቁሳዊ ባህልን (ቁሳዊ ሀብት፣ የማምረቻ መሣሪያዎች ወዘተ . . .) ከመንፈሳዊ ባህል (ሳይንስ፣ ኪነጥበብ፣ ፍልስፍና ወዘተ...) ለይቶ ማየት የተለመደ ቢሆንም ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መንፈሳዊ ባህል የኅብረተሰቡ ምርጥ ክፍል ፈጠራ ነው የሚለውን ሐሳባዊ አስተሳሰብ በመቃወም ቁሳዊ ምርት የባህል መሠረት መሆኑን አስገንዝቧል ። ባህል ታሪካዊ ክስተት በመሆኑ ዕድገቱ የሚወሰነው በኅብረተሰቡ ሥርዓት ዕድገት ነው ። ታሪካዊነቱ የሚያረጋግጠውም የብዙኅኑ ክንዋኔ ውጤት መሆኑን ነው ።

መንፈሳዊ ባህል በቁሳዊ ሁኔታዎች የሚወሰን ቢሆንም አንፃራዊ ነፃነት ስላለው የራሱ የሆኑ የዕድገት ሕግጋት አሉት ። በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ በተግባራዊ ግቦቹም ሆነ በርዕዮተዓለማዊ ይዘቱ ባህል የመደብ ጠባይ አለው ። ይህም የኅብረተሰቡን አመለካከት በገዥና በተገዥ አመለካከቶች መክፈሉ ነው ። በካፒታሊስት ሥርዓት

ውስጥ ሁለት የተለያዩ ባህሎች ይታያሉ ፤ አንዱ የቡርዧውን ገዥነት የሚያንፀባርቅ ሲሆን ሌላው ከዲሞክራሲያዊ ኃይሎችና ከተ ጨቆነው ሠራተኛ የሚመነጭ ሶሻሊስታዊ ባህል ነው ።

የሶሻሊስት ባህል ከቀድሞዎቹ ባህሎች ውስጥ ተራማጅና ጠቃሚ የሆኑትን አመለ ካከቶች የሚያጠቃልል ከመሆኑም በላይ የኮ ሚኒስት ርዕዮተዓለምን ፣ ሶሻሊስት ሰብአዊ ነትን ፣ ሳይንሳዊ ንጽረተ ዓለምን ፣ ተራድኦ አዊ ግንኙነትን ፣ ዓለም አቀፋዊነትን ወዘተ... የሚያራምድ ነው ። የዚህ ባህል ዋና ዓላማ ሕዝቡን ከተገዥነት መንፈስ በማ ላቀቅ ራሱን በራሱ ለማስተዳደር ብቁ ማድ ረግ በመሆኑ ከቡርዧው ባህል በዓይነት የሚ ለይ ነው ። በተጨማሪም የተለያዩ ብሔራዊ ባህሎች ያላቸውን ሀብት በመለዋወጥና ወደ ከፍተኛ ደረጃ በማሸጋገር በይዘቱና በቅርፁ ዉይበልጥ ዓለም አቀፋዊ የሆነ ባህል እንዲያ ፈልቁ የሚገፋፋ ባህል ነው ፤ ማለትም የሶ ሻሊስት ባህል የመደብ አልባ ኅብረተሰብ ባህል ወደሆነው የሰው ልጅ ባህል የሚያሸ ጋግር ነው ።

(የባህል አብዮትን ፣ ሶሻሊዝምን ይመለከቷል ።)

## ባህል አብዮት (የ—)

*(Cultural Revolution)*

የሶሻሊስት አብዮት ዓቢይ ክፍል ሲሆን የትምህርትን ሥርዓት በመለወጥ ሰፊውን ሕዝብ ዕውቀ ከሆኑ ባህላዊ ሥራ ዎች ጋር በማስተዋወቅና በአጭር ጊዜ ውስጥ ንቃተ ኅሊናውን ከፍ በማድረግ በኢኮኖሚያዊ ፣ በማኅበራዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆንና የራስ በራስ ማስተዳደር ችሎታውን እንዲያዳብር በአንፃሩም በሶሻሊስታዊ ባህል እንዲታነፅ የሚያደርግ ሂደት ነው ።

የባህል አብዮት ግብ በቡርዧው ባህል ምትክ ሳይንሳዊ ባህል መፍጠር ቢሆንም ሠራተኛው ሕዝብ የቡርዧውን ባህል አሽ ቀንጥሮ የሚጥልበት ወቅት አይደለም ። የሰው ታሪክ ያፈራቸውን ምርጥ ሥራዎችንና አመለካከቶችን በመውረስና አስፈላጊውን ጊስና እርማት በማድረግ የዕድገት ሕግ በሚጠይቀው መሠረት የተወረሰውን ባህል ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚያደርስበት አብዮ ታዊ ሂደት ነው ።

የባህል አብዮት ሚና ሕዝባዊ የሆነ ባህል ማስገኘት በመሆኑ በፊት የገዥ መደ ቦች ንብረት የነበሩትን መንፈሳዊ ፋይዳ ዎችን ፣ የሳይንስና የኪነ ጥበብ ክንዋኔዎችን የሕዝብ ንብረት እንዲሆኑ ያደርጋል ። የሕ ዝቡን የትምህርት ደረጃ ከፍ በማድረግ ሳይንሳዊ አመለካከቶች እንዲኖሩትና የፈ ጠራ ችሎታዎቹንም እንዲያዳብር አመች ሁኔታ ይፈጥራል ። በመሆኑም የባህል አብ ዮት ከመቅጽበት የሚከናወን ሳይሆን ሰፋ ያለ ጊዜና ትግል የሚጠይቅ ሂደት ነው።

የባህል አብዮት ቅድሚያ የሚሰጠው ሰፊውን ሕዝብ ለኮሚኒስታዊ ሥርዓት ታ ማኝ እንዲሆን ማድረግን ነው ። ለዚህም የሥራና የወል ንብረት ከቡርነትን አስመ ልክቶ አስፈላጊው ግብረገባዊ አመለካከት እንዲኖረው ያደርጋል ። ከካፒታሊዝም የተ ወረሱት የጨቋኝ ባህል ቅሪቶችን እንዲያስ ወግድ ፣ የግለሰቡና የኅብረተሰቡ ሁለንታዊ ዕድገት ተደጋጋፊ መሆኑን እንዲረዳ ተገቢውን አመለካከት ይቀርፃል ። የነዚህ ኮሚኒስታዊ አመለካከቶች - መሰራጨትና ሥር መስደድ የሕዝቡን ተሳትፎ ከፍ ስለሚያደርጉና የራስ በራስ አስተዳደርንና ዲሞክራሲያዊ መርሆችን ስለሚያጎለብቱ ለምርት ኃይሎ ችና ለምርት አደረጃጀት ዕድገት አመች ሁኔ ታን ይፈጥራል ።

(ባህልን ይመለከቷል ።)

## ባሕርዮት

*(Substance)*

ባሕርዮት ባሕርይ ከሚለው ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙም የነገር ሁሉ ሥረ መሠ ረት ፣ ምንጭ ህላዌ ማለት ነው ።

ባሕርዮት የሚለው ጽንሰ ሐሳብ የሚ ገልጸው የከሰተቶችን እንቅስቃሴና ለውጥ ፣ ከቋሚ እውነታ ጋር ያሏቸውን ግንኙ ነቶች ነው ። አንድ ነገር በሰፋት ፣ በቅርፅ፣ በቀለምና በቦታ ወዘተ...የሚገለጽ ቢሆንም እነዚህን ከሰተቶች የሚሸከመው ነገር ወይም ሥረ መሠረታቸው ባሕርዮት ይባላል ። ሰፋትና

ቅርፅ የአንድ ነገር ገጽታዎች በመሆናቸው በራ ሳቸው ብቻ ሊኖሩ የሚችሉ አይደሉም። የሚመ ኙና የሚፈልግ ሁሴም ቢሆን የሚያስብ ነገር ነውና ምኞትና ፍላጐትም ብቻቸውን አይገኙም።

የእነዚህ ሁሉ አቃፊ የሆነው ባሕርዮት ነው ። የሚያቅፋቸው ክስተቶች ተንቀሳቃሽና ተለዋዋጭ ሲሆኑ ባሕርዮት ግን ቋሚና የማይለ ወጥ ነው ። ለምሳሌ አንድ ሰው እኔ ሲል በዕድሜና በኑሮ ከሚደርሱበት ለውጦች ባሻ ገር እነዚህን ለውጦች የሚያዝለውና የርሱ መሆናቸውን የሚገልጸው እኔ የሚለው ባሕ ርዮት ይሆናል ። ቁሳዊ ክስተቶች ቢለዋወ ጡም ቁስአካል ግን አይቀየርም ፣ አያንስም ፣ አይበዛምም ።

ባሕርዮት የሚለው ጽንሰ ሐሳብ በፍል ስፍና ታሪክ ውስጥ በርካታ ክርክሮችን አስ ነሥቷል ። ሁለታዊ ሐሳባዊ ፍልስፍና ቁስአ ካላዊና መንፈሳዊ ባሕርዮትን ለይቶ የሚያይ ሲሆን አንዳዊ ሐሳባዊነት ግን የሚቀበለው የመንፈሳዊ ባሕርዮትን መኖር ብቻ ነው ። የክ ርክሩ ዋና ነጥብ የባሕርዮትንና የክስተቶቹን ልዩነት ከማወቁ ላይ ነበር ። የአንድን ነገር ስፋቱን ፣ ቅርፁንና ቀለሙን ባንድ ቃል ተጨ ባጭ የሚያደርጉትን ባሕርያት ካነሣን ምን ይቀራል ? ባሕርዮት ተብሎስ የሚጠራው ምንድነው ? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ለመ ስጠት ችግር በመፈጠሩ ከነጭራሹ ባሕር ዮት የሚባል ነገር የለም የሚሉ ፈላስፎች ብቅ ሊሉ ችለዋል ። ከዚህም የተነሣ የተለ ያዩ ገጽታዎች ያሏቸው ሐሳባዊ የባሕርዮት ትርጉሞች ተፈጠሩ ።

ማርክሳዊ ፍልስፍና ለጥያቄው የተለ የና ትክክለኛ መልስ በመስጠት ፣ ቁስአካል ሁሌም በእንቅስቃሴ ላይ የሚገኝ ነውና ቋሚ ወይም ግትር ቁስአካል የለም ። እንቅስቃሴ የክስተቶች ምክንያት በመሆኑ ከእንቅስቃሴ ውጭ ቁስአካል ከቶውንም ሊታሰብ እንደ ማይችል አሳየ ። ነገር ግን የክስተቶች ውስጣዊ ግንኙነት ነገሮችን ስለሚቀርፅ የነርሱ አንድነትና አደረጃጀት መባል ያለ በት ባሕርዮት ሳይሆን መዋቅር ነው በማለት መዋቅር ከክስተቶች ውስጣዊ መስተ ጋብር የሚገኝ መሆኑን አረጋገጠ ። መዋቅር የማይታወቅ ወይም ምሥጢራዊ ነገር ሳይ ሆን የክስተቶች አንድነትና ውስጣዊ ሥር ዓት ነው ።

(ሥርዓትን ይመለከቷል ።)

## ባለሞግዚት ግዛቶች
*(Trusteeship Territories)*

ቀደም ሲል በቅኝ ገዥዎች ቁጥጥር ሥር ከነበሩት ሀገሮች መካከል "እራሳቸውን ለማስተዳደር የማይችሉ" ተብለው በተባበ ሩት መንግሥታት ፈቃድ ለአንዳንድ ሀገሮች በአደራ መልክ የተሰጡ ወይም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የበላይ ተመልካችነት ሥር እንዲቆዩ የተደረጉ ሀገሮች ናቸው ። በዚህ መልክ እነዚህ በሞግዚት የሚተዳደሩ ሀገሮች ነፃ እስካልወጡ ድረስ ሕዝቦቹ ራሳ ቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር እስኪችሉ በሚል ሰበብ በባለአደራዎቹ መንግሥታት ሙሉ የአስተዳደር ሥልጣን ሥር ይቆያሉ ።

እያንዳንዱ ሞግዚት ሀገር በተባበሩት መንግሥታትና በሞግዚትነት በሚያስተዳድ ረው ሀገር መካከል በሚደረገው ስምምነት መሠረት ይተዳደራል። በዚህም በሞግዚትነት እንዲያስተዳድር አደራ የተሰጠው ሀገርም በባለሞግዚቱ ሀገር ውስጥ መሠረታዊ የሰው ልጅ መብቶችንና ነፃነቶችን የማስከበር ፣ ሕዝቡም ራሱን በራሱ እንዲያስተዳድር የማ ስቻልና በመጨረሻም ለሙሉ ነፃነቱ እንዲ በቃ የማዘጋጀት ኃላፊነት ሲኖርበት በዚህም መሠረት በየዓመቱ ለተባበሩት መንግሥ ታት ሪፖርት ማቅረብ ይጠበቅበታል ።

የተባበሩት መንግሥታትም የባለሞግ ዚት ሀገሮችን ሁኔታ በቅርብ ለመከታተል እንዲችል በየወቅቱ መልዕክተኞችን በመ ላክ ሁኔታዎችን እንዲመለከቱ ከማድረግም በላይ የባለሞግዚት ሀገሮችን ጉዳይ በሚከ ታተለው ምክር ቤቱ አማካይነት ይቆጣ ጠራል ።

ባለሞግዚት ሀገሮች ራሳቸውን ለማስተዳ ደር እስከሚችሉ ወይም ነፃ እስከሚወጡ ድረስ ባለአደራዎቹ መንግሥታት ሕግ የማውጣ ትና የማስተዳደር ሙሉ ሥልጣን አላቸው።

(ቅኝ ግዛትን ይመለከቷል ።)

## ቫልራ ፣ ሌዮ
*(Walras, Leon)*

ከ1834—1910 የኖረ ፣ የስዊዘርላንድ ተወላጅ ሲሆን በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ጥናት ውስጥ የማቲማቲክስ ዘዴን በስፋት መጠ ቀም ከጀመሩት ቡርዧ ኢኮኖሚስቶች

መካከል በግንባርቀደምትነት የሚጠቀስ ነው ። ቫልራ በሉዛን ዩኒቨርሲቲ ከ1870—90 በፕሮፌሰርነት ሠርቷል ።

ቫልራ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ተማዝኖ የተሰኘውን ማቴማቲካዊ የኢኮኖሚ ሞዴል የመሠረተ ነው ። የቫልራ ሞዴል በአንድ ኢኮኖሚ ባጠቃላይ በመንዕስ ወጪ ፣ መልዕል ውጤት የሚገኝባቸውን ሁኔታዎች የሚሻ ነው ።

ሆኖም ቫልራ የመሠረተው አጠቃላይ የኢኮኖሚ ተማዝኖ ሞዴል ኢሳይንሳዊ በሆነው በእርካታ የእሴት ንድፈ ሐሳብ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ በማቴማቲክስ አገላለጽ ዘዴ የተሸፈነ የቡርዧው ርዕዮተዓለም አንፀባራቂ ሞዴል ከመሆን አላመለጠም ። ቫልራ የካፒታሊስት ምርት በዕድገት ሂደቱ የሚያሳየውን ውስጣዊ ጠባይ ሊረዳ ካለመቻሉም በላይ የዚህንም ስልተ ምርት መሠረታዊ ቅራኔዎች አላጤነም ።

## ባበፍ ፣ ግራኩስ

(*Babeuf, Gracchus*)

ከ1760—1797 የኖረ ፣ ፈረንሳዊ አብዮተኛና የተምኔታዊ ሶሻሊዝም አራማጅ ነው ። የባበፍ አቋም ከሌሎች ተምኔታዊ ሶሻሊስቶች የሚለየው ካፒታሊዝምን ለመጣል በኃይል መጠቀም ማስፈለጉን ማመኑ ነው ። ሆኖም ተምኔታዊ በመሆኑ በሱ አስተሳሰብ ጥቃቱ መፈጸም ያለበት ብዝበዛንና ሀብትን በፍጹም የሚጠሉ ጀብደኞችና ሴረኞች የሆኑ ግለሰቦች በሚያቋቁሙት ሥውር ቡድን ነው ።

ባበፍና ተከታዮቹ በታላቁ የፈረንሳይ አብዮት የተሳተፉ ሲሆን አብዮቱ የብዝበዛን ቅርፅ የቀየረ እንጂ ብዝበዛን ያላጠፋ መሆኑን ወዲያው ለመገንዘብ ችለዋል ። ይህ የቡርዧ አብዮት ሕዝቡ በአብዮታዊ የበላይ ገዥነት ሥልጣን ይዞ ደሀም ጌታም የሌለበት ፣ የግል ንብረት የሚጠፋበት ፣ ሁሉም ለጋራ ጥቅም የሚሠራበት "የእኩሎች ኅብረተሰብ" አብዮትን ያስከትላል ብለው ያምኑ ነበር ።

የባበፍ መሪ ሐሳብ የእኩልነት ጥያቄ ሲሆን እኩልነትን ከሁሉ በላይ በማድረጉ ሥልጣኔ ፣ ትምህርት ፣ ኪነጥበብና ሳይንስ እኩልነትን ያፋልሳሉ በማለት እስከ መንቀፍ ደርሷል ። ከሚኒዝምንም የተመለከተው በከፍተኛ ደረጃ በማዕከላዊነት የተደራጀና በጋራ ንብረትና በብሔራዊ አንድነት ላይ እንደተመሠረተ ኅብረተሰብ አድርጎ ነው ።

ባበፍና ተከታዮቹ የታዳጊውን የፈረንሳይ ወዝአደር ጥቅም ያንፀባረቁ ቢሆንም የወዝአደሩ አሰመበራበትና አሰመደራጀት ስለመጪው ኅብረተሰብና ተግባራዊ ስለሚሆንበት መንገድ የሰነዘሩት ጥሬ ሐሳብ የሁኔታውን አለመብሰል የሚገልጽ ነበር። የመረጡት የስውር ደባ የትግል ታክቲክ ከሕዝቡ እንዲርቁና እንዲሸነፉም አድርጓቸዋል ። ተከታዮቹ በእሥር ቤት የማቀቁ ሲሆን ባበፍ ግን በፍርድ በሞት ተቀጥቷል ።

(ተምኔታዊ ሶሻሊዝምን ይመለከቷል ።)

## ባንክ

(*Bank*)

የገንዘብ አቅርቦትን የሚፈጥርና የሚቆጣጠር ዓቢይ ተቋም ነው ።

ዘመናዊ ባንኮች በአውሮፓ መከሰት የጀመሩት በ16ኛውና በ17ኛው ምዕተ ዓመቶች ውስጥ ነበር ። በወቅቱም የነዚሁ ባንኮች ዋነኛ ተበዳሪዎች መንግሥታትና ትላልቅ የሥራ አከሲዮን ማኅበሮች ነበሩ ። ከኢንዱስትሪ አብዮት በኋላ ግን ዘመናዊ ባንኮች በቁጥር ከማደጋቸውም በላይ ተግባራቸውም እየሰፋ ሊመጣ ችሏል ።

በካፒታሊስት ሀገሮች ባንኮች በአበዳሪ ካፒታሊስቶችና በተበዳሪ ካፒታሊስቶች መካከል ሆነው የብድር ካፒታልን በማንቀሳቀስ የሚሠሩ የካፒታሊስት ተቋሞች ናቸው ። የካፒታሊስት ባንኮች በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ለጊዜው ነፃ ሆኖ የተቀመጠውን የካፒታሊስቶች ገንዘብ ፣ የባለመሬቶችን የመሬት ኪራይ ፣ የመንግሥት በጀት ፣ የጡረታ ገንዘብ ፣ የሕዝባዊ ድርጅቶች ገንዘብና የሌሎች ካፒታሊስት ኅብረተሰብ አባሎችን የቁጠባ ገንዘብ በመሰብሰብ ፣ በማከማቸትና ወደብድር ካፒታል በመቀየር ለካፒታሊስቶች

በአጭርና በረዥም ጊዜ የብድር ስልቶች
አማካይነት የሚያስተላልፉ ድርጅቶች ናቸው።
ባንኮች ንብረቶችንና ገንዘብን ከአስቀማ
ጮች ተቀብሎ ከማስቀመጥና ብድርንም
በልዩ ልዩ መያዣ ዋስትና መሠረት ከመስ
ጠት በላይ በካፒታሊስት ደምበኞቻቸው
መካከል የሚካሄዱ የእርስ በርስ የገንዘብ
ክፍያዎች ማከናወንን ፣ ገንዘቦች መለወጥን ፣
ገንዘብ ማስተላለፍንና ከነዚሁ ጋር የተያያዙ
ሌሎች ተግባሮችንም ያካሂዳሉ ። በባንክ
ውስጥ አስቀማጮች ከሚያስቀምጡት ገን
ዘብ የተወሰነው በአስቀማጮች የቅድሚያ
የማውጣት ጥያቄ ሊወጣ ሲችል ሌላው
ደግሞ ያለቅድሚያ የማውጣት ጥያቄ
በአስቀማጮች ሊወጣ የሚችል ነው ።
ባንኩ ለአስቀማጮች ወለድ የሚከፍል
ሲሆን ከተበዳሪዎችም ይቀበላል ። ሆኖም
ባንኩ ከተበዳሪዎች የሚቀበለው የወለድ
መጣኔ ለአስቀማጮች ከሚሰጠው የወለድ
መጣኔ ይበልጣል ።

በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የተለያዩ
የሥራ ዘርፎችን የሚያካሂዱ የተለያዩ ባን
ኮች ይገኛሉ ። ከነዚህም መሀከል የማዕከላዊ
ባንክና የንግድ ባንክ ከፍተኛ ስፍራን
ይይዛሉ ። ማዕከላዊ ባንክ ብሔራዊ ገንዘብን ፣
የባንክ ኖቶችን የሚያትምና የሚያሰራጭ ፣
የገንዘብ ፖሊሲ የሚነድፍ ፣ የመንግሥት
ገንዘብ የሚያስቀምጥና ለመንግሥት የሚ
ያበድር ፣ ለሌሎችም ባንኮች ብድር የሚሰጥ
የባንኮች ባንክ ነው ። የንግድ ባንክ ደግሞ
በልዩ ልዩ ሥራዎች ለተሰማሩ ካፒታሊስቶች
የረዥምና የአጭር ጊዜ ብድር በመስጠትና
የአስቀማጮችን ንብረትና ገንዘብ በማስቀ
መጥ የሚሠራ ባንክ ነው ።

በኢምፔሪያሊዝም ደረጃ የሞኖፖል
ባንኮችና የኢንዱስትሪ ሞኖፖሎች በሚያደር
ጉት መስተጋብር የፋይናንስ ካፒታል ይመ
ሠረታል ። በዚህም ሂደት ከፍተኛ ዓለም
አቀፍ የሞኖፖል ባንኮች በመመሥረት ልዩ
ልዩ የምርት ፣ የአገልግሎትና የንግድ ድርጅ
ቶችን በልዩ ልዩ መንገዶች በቁጥጥራቸው
ሥር በማዋል ከፍተኛ የሞኖፖል ትርፍ ያገ
ኛሉ ። በተጨማሪም ከፍተኛ የወለድ መጣኔ
በማውጣትና ሥራ ላይ በማዋል ከልዩ ልዩ
ሀገሮች ሀብት ወደ ሞኖፖል ባንኮች እንዲ
ዛወር ያደርጋሉ ።

በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ባንኮች
የመንግሥት ይዞታዎች ሲሆኑ ለማዕከላዊ
የኢኮኖሚ አመራር አካል የሚያስፈልገውን
ልዩ ልዩ ዝርዝር የሒሳብ መረጃዎች አጠናቅ
ረው የሚይዙ ፣ የተለያዩ የሶሻሊስት ኢኮኖ
ሚው ዘርፎችና ድርጅቶች በማዕከላዊው
ዕቅድ መሠረት ሥራቸውን ማከናወናቸውን
የሚቆጣጠሩና ስልዩ ልዩ ከፍላተ ኢኮኖሚ
ዎችም በዕቅዱ መሠረት ብድር የሚሰጡ
ድርጅቶች ናቸው ። የሶሻሊስት ባንኮች ከህ
ገሪቱ ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ክፍሎች ፣ ድር
ጅቶችና ግለሰቦች ላይ ገንዘብ በአደራ መልክ
ተቀብለው ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋሉ ።
የሶሻሊስት ባንኮች የወለድ መጣኔ በማዕከ
ላዊው ዕቅድ መሠረት ተቀናብሮ የሚወሰን
ነው ።

## ባንክ ትርፍ (የ—)
*(Banker's Profit)*

ባንክ ለአስቀማጮች ከሚሰጠው ወለ
ድና ከተበዳሪዎች ከሚቀበለው ወለድ የሚ
ያገኘው ልዩነት የባንክ ትርፍ ይባላል ።

የካፒታሊስት ባንክ ብድር ሲሰጥ
ከተበዳሪዎች የሚቀበለው የወለድ መጣኔ
ባንኩ ለአስቀማጮች ከሚሰጠው የወለድ
መጣኔ እጅግ ከፍ ያለ ነው ። የካፒታሊ
ስት ባንክ በቅድሚያ የራሱን ካፒታል
በመያዝና የሌሎችን ካፒታል በአስቀማ
ጭነት በመሰብሰብ ሥራውን ያንቀሳቅሳል።
አስቀማጮች ያስቀመጡትን ካፒታልና የራ
ሱን ካፒታል ለተበዳሪዎች በመስጠት
ለዚህ አገልግሎትም ወለድ በመጠየቅ
ገንዘብ በመሸጥ ከፍተኛ ገቢ ያገኛል ።
የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱ ከባንኩ የተበ
ደረውን ካፒታል በምርታማ ሥራ ላይ
በማዋል ወዝአደሮችን በመበዝበዝ ከሚያገ
ኘው ትርፍ ውስጥ የተወሰነውን ለአበዳሪው
ባንክ በወለድ መልክ ይከፍላል ። የባንክ
ትርፍ የተረፈ እሴት አንድ ክፍል ነው ፤
የባንኩ ትርፍ በኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ
ውስጥ ከሚገኝ አማካይ ትርፍ መጣኔ የሚያንስ
አይደለም ። የባንክ ትርፍ ምንጭ ወዝአደ
ሩን በመበዝበዝ የሚገኘው ተረፈ እሴት ነው።

የካፒታሊስት ባንክ ትርፍ ለአስቀ
ማጮች ከሚከፍለው ወለድና ከተበዳሪ
ዎች ከሚቀበለው የወለድ መጠን ልዩነት
የሚገኝ ቢሆንም በተጨማሪ ባንኩ የገን
ዘብ ዝውውር ለደንበኞቹ በማድረግ ፣

በካፒታሊስቶች መካከል የድለላ ሥራዎች በማከናወንና በመሳሰሉት ከሚሠራቸውም ተጨማሪ ገቢ ያገኛል ። የካፒታሊስት ባንኮች ብድር ለካፒታሊስቶች ብቻ ሳይሆን የፍጆታ ሸቀጦች ለሚገዙ ሠርቶ አደሮችም የአጭር ጊዜ ብድር በመስጠት ከነርሱም ወለድ ያገኛሉ ። በተጨማሪም የካፒታሊስት ባንኮች ለካፒታሊስት መንግሥት በማበደር ከፍተኛ ትርፍ ይሰበስባሉ ።

በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የባንክ ብድር ፣ ካፒታል ከአንድ ክፍለ ኢኮኖሚ ወደሌላ ክፍለ ኢኮኖሚ በፍጥነት እንዲሸጋገርና አማካይ ትርፍ እንዲገኝ ያስችላል ። የካፒታሊስት ብድር የካፒታልን የዝውውር ጊዜ በማሳጠርና የዝውውር ወጪዎችን በመቀነስ ተረፈ እሴት እንዲጨምር ይረዳል ። በተጨማሪም ብድር የካፒታልን መማከልና መሰባሰብ በማስከተል አነስተኛ ካፒታሊስቶች በከፍተኛ ካፒታሊስቶች የሚዋጡበትን ሂደት ያፋጥናል ። በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የባንክ ሞኖፖሎች በመከሰታቸውና የኢንዱስትሪ ካፒታልና የብድር ካፒታል ተዋህደው ፋይናንስ ካፒታልን በመፍጠራቸው ምክንያት የትርፍ ማግኛ መስኮቻቸው ሊሰፉ ችለዋል ።

በሶሻሊስት ሥርዓት ባንክ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በመሆኑና መንግሥቱም ለኅብረተሰቡ ጥቅም የቆመ ስለሆነ የሚያስከፍለው የወለድ መጣኔ መጠነኛ ነው ። ከዚህም በላይ አንዳንድ ለኅብረተሰቡ ጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶች ሥራቸውን ለማስፋፋት ከባንክ ሲበደሩ የሚከፍሉት ወለድ አነስተኛ ሲሆን ለኅብረተሰቡ ጥቅም ለማይሰጡ ድርጅቶች ሥራ ማስፋፊያ የሚሰጠው ብድር መጣኔው ከፍተኛ ይሆናል ። ይህም እንዲህ ዓይነቶቹን ድርጅቶች ለመግታት የሚደረግ ነው ።

ከባንክ ወለድ የሚገኘው ትርፍ መልሶ ለሀገሪቱ ጥቅምና ለኅብረተሰቡ የኑሮ ማሻሻያ ይውላል ።

(የብድር ካፒታልን ይመለከቷል ።)

## ባንክ ኖት (የ—)

*(Bank Note)*

ባንክ ለግለሰቦች ወይም ለድርጅቶች የሚሰጠው እንደ ገንዘብ በመሆን የሚያገለግል የመተማመኛ የብድር ሰነድ ነው ። ባንኩ በማንኛውም ጊዜ የባንክ ኖቱን ለሚያቀርብ ግለሰብ ወይም ድርጅት በባንክ ኖቱ ላይ የተጠቀሰውን የገንዘብ መጠን እንደሚከፍል ቃል ይገባል ። በዚህም የተነሣ የባንክ ኖት እንደ ገንዘብ የሚያገለግል ሕጋዊ የሆነ የገንዘብ መክፈያ ሰነድ ነው ።

በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ታሪክ የመጀመሪያ ወቅት የሽርፍራፊ ገንዘቦች በሁለንታዊ የዝውውር ማዕከልነት ሲያገለግሉ ቆይተዋል ። በዚሁ ወቅት ደግሞ በካፒታሊስቶች መካከል በሽርፍራፊ ገንዘብ ምትክ የካፒታሊስቶች የመተማመኛ የብድር ሰነዶች ተተክተው በሥራ ላይ ውለዋል ። ከነዚህ በኋላ የተከሰተው ደግሞ የባንክ ኖት ነው ። በብዙ የካፒታሊስት ሀገሮችም ውስጥ ቀስ በቀስ የባንክ ኖት ብሔራዊ ገንዘብ በመሆን ሥራ ላይ ውሏል ።

በሶሻሊስት ሀገሮች የባንክ ኖት የመንግሥት የብድር ገንዘብ ነው ። በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የባንክ ኖቶች መጠንና ስርጭት በማዕከላዊው ዕቅድ ተቀናብሮ የሚካሄድ ነው ። የሶሻሊስት የባንክ ኖቶች የመተማመኛ መሠረትም በሶሻሊስት መንግሥት ይዞታ ሥር የሚመረተው ምርት ነው።

## ቤከን ፣ ፍራንሲስ

*(Bacon, Francis)*

ከ1561—1626 የኖረ ፣ የሙከራዊ ሳይንስና የዘመናዊ ቁስአካላዊ ፍልስፍና መሥራች የሆነ እንግሊዛዊ ፈላስፋ ነው ። ‘‘ኖቮም ኦርጋነም’’ በተባለው ዓቢይ ጽሑፉ ውስጥ ስለሳይንስ ተግባሮችና ስለሳይንሳዊ መስተጋብእ መሠረት የደረሰበትን አዲስ ግንዛቤ አብራርቷል ።

የዕውቀት ዓላማ የሰውን ኃይል ማሳደግ ነው ከሚለው ሐሳብ በመነሣት ቤከን ስለነገሮች ትክክለኛ ዕውቀት የሚኖረን የነሱን እውነተኛ ምክንያት ስናጤን ነው ሲል ተናግሯል ። እንደ ቤከን አባባል በወቅቱ የነበረው የእጠናን ዘዴ ሁለት ዓይነት ድክመቶች ነበሩት ። ጨርሶ ቀኖናዊ በመሆን ለልምድና ለሙከራ ቦታ ሳይሰጥ ሁሉን ነገር ከሐሳብ ብቻ ለማፍለቅ መሻቱ ወይም ደግሞ የከረረ የዳሳሽነትን አዝማሚያ በመከተል የተለያዩ

መረጃዎችን በመዘርዘርና በመመዝገብ ብቻ መወሰኑ ነው ። ትክክለኛውና ዕውቀት የሚያስገኘው ዘዴ ከነዚህ ድክመቶች የተላቀቀው ነው ።

በመጀመሪያ ደረጃ አመለካከት እራሱ ከአንዳንድ መሠረተ ቢስ እምነቶችና አሳሳች የአስተሳሰብ ልምዶች መላቀቅ ይኖርበታል ። ከዚያም ልምድን ምክኑያዊ በሆነ መንገድ መገንዘብ ያስፈልጋል ። ይህ ዘዴ ሙከራዊ ሳይንስ የሚባለው ሲሆን የእሱም መሪ ሐሳብ መረጃዎችን በሥርዓት በማገናዘብና በማጠቃለል ማለትም ከጭብጥ በመነሣት በመስተጋብአዊ ሥነ አመክንዮ በመጠቀም ወደንድፈ ሐሳብ መተላለፍ ነው ።

በሥነ ኑባሬ አመለካከቱ ቤከን ቁስ አካላዊ አቋም በመያዝና የሐሳባዊነትን ስህተቶች በማጋለጥ ነባራዊው ቁስአካል ብቻ እንደሆነ ተናግሯል ። ቁስአካል የብናኞች ግጥምጥሞሽ እንደሆነና ተፈጥሮም ብዙ ጠባይ ያሏቸው የአካሎች ግጥምጥሞሽ ውጤት እንደሆነ ገልጿል ። እንቅስቃሴ የቁስአካል ምንነታዊ ጠባይ መሆኑንም ጠቁሟል ። እንቅስቃሴ ተናክእታዊ ብቻ እንዳልሆነ ለማስረዳት 19 ዓይነት የእንቅስቃሴ ቅርፆች አሉ ሲል ተናግሯል ።

ቤከን የነበረበት ወቅት በእንግሊዝ መጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት ይካሄድ የነበረበት ወቅት ስለነበር ፍልስፍናው የሚያንፀባርቀው ተስማሚ የሆነውን የዕውቀት አቅጣጫ ነው ። ቤከንን ታዋቂ ያደረገው በተምህሮነት የበላይነት ሥር ሰፍኖ የነበረውን የዕውቀትን እውጠንጣኝነት በመንቀፍ ለተግባር ጠቃሚ የሚሆነውን የዕውቀት ስልት መቀየሱ ነው ። ሆኖም ቤከን በቁስአካልነት አቋሙ የጸና አልነበረም ። በተለይም በፖለቲካዊ አስተምህሮው ፍጹም ተምኔታዊ ከሆነ አመለካከት ላይ በመውደቅ የተገዥና የገዥ ልዩነት ሳይጠፋ በሳይንስና በቴክኖሎጂ እማካይነት ብቻ ትክክለኛ ኅብረተሰብ ለመመሥረት ይቻላል ሲል ተናግሯል ።

## ብሔረሰብ
(*Nationality*)

በይበልጥ የባሪያ አሳዳሪና የፊውዳል ሥርዓት ዓይነተኛ ገጽታ የሆነ የሰዎች ታሪካዊ ማኅበረሰብ ነው ። ብሔረሰብ ከደም አንድነት ይልቅ የተመሠረተው በክልል ፣ በቋንቋና በባህል አንድነት ላይ ነው ። ብሔረሰብ የነገድ ከፍተኛ ደረጃ የሆነ የብዙ ነገዶች ውህደት ውጤት ነው ።

ይህ የክልል ፣ የቋንቋና የባህል አንድነት የተወሰነ ቁሳዊ መሠረት አለው ። ዋናው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የተመሠረተው በግብርና ላይ ሲሆን በመጠኑም ቢሆን እደጥበባዊ ኢኮኖሚን አስፋፍቷል ። ሆኖም ብሔረሰብ ዘላቂ ዕድሜ ያለው ማኅበረሰብ አልነበረም ። ምክንያቱም በባሪያ አሳዳሪ ሥርዓትና በፊውዳሊዝም ውስጥ ቋሚና ሰፊ ያላቸው ግንኙነቶችን ለማዳበር ባለመቻሉ ብሔረሰብ ለዕድገት ግፊት ተስማሚ አልነበረም ። በሁለቱም ሥርዓቶች ውስጥ የሸቀጥ ልውውጥ ቢኖርም ልውውጡ ዳብሮ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ልዩነቶችን ሊያሸንፍ አልቻለም። የዕድገት ሂደት ከሚጠይቀው አንፃር ሰፋ ያሉ የኢኮኖሚ ግንኙነቶችን በመፍጠር እነዚህን ልዩነቶች የሚያስቀር የብሔረሰብ ከፍተኛ ደረጃ ብሔር ነው ።

(ብሔርን ይመለከቷል ።)

## ብሔረተኝነት
*(Nationalism)*

ሕዝቦችን በብሔር የሚከፋፍል የአንዱ ብሔር ሕዝብ የሌሎች ብሔሮችን ሕዝቦች በጥላቻ ፣ በጥርጣሬና በጠላትነት እንዲመለከት የሚገፋፋ የቡርዧው ርዕዮተዓለም አድኃሪ አዝማሚያ ነው ። ብሔረተኝነት ከካፒታሊዝም የሚመነጭና በብሔሮች መካከል ያለውን የተዛባ ግንኙነት የሚያንፀባርቅ ሲሆን በሁለት መሠረታዊ መልኮች ይከሰታል ። የመጀመሪያው በአንድ ወቅት በፖለቲካና በኢኮኖሚ የበላይነትን የያዘው ብሔር ወይም ብሔረሰብ ገዥ መደብ በሚያሳየው ትምክህተኝነት ሲንፀባረቅ ፣ ሁለተኛው ደግሞ ከዚሁ በመነጨ ሁኔታ በጭቁን ብሔሮች ወይም ብሔረሰቦች በዝባዥ መደቦች አካባቢ በሚታይ የጠባብ ብሔረተኝነት አዝማሚያ ይገለጻል ። የብሔር ትምክህተኝነትም ሆነ ጠባብ ብሔረተኝነት የበዝባዥ መደቦችን ፍላጐትና ዓላማ የሚያንፀባርቁ ፣ የልዩ ልዩ ብሔሮች ወይም ብሔረሰቦች

ጭቁን መደቦችን የዓላማና የትግል አንድነት የሚፃረሩ የአንድ ከስተት ገጽታዎች ናቸው ።

ብሔረተኝነት በብሔሮች ምሥረታ ታሪካዊ ሂደት ውስጥ የተወለደና እያደገም የመጣ ክስተት እንደመሆኑ ከብሔር ቋንቋዎች ፣ ባህሎች ፣ ሥነ ልቦናዊ አመለካከቶችና እምነቶች ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ነው ። በመሠረቱ የቡርዧው ብሔረተኝነት በየአካባቢው የተበታተኑ የፊውዳል ግዛቶችን በአንድ የቡርዧ ማዕከላዊ መንግሥት ጥላ ሥር የማሰባሰብ ዓላማ ስለነበረው ንቅናቄው የተራማጅነት ገጽታ ነበረው ። በኋላ ግን ከካፒታሊዝም ዕድገት ጋር ቡርዧዚው ተራማጅነቱን ጨርሶ የጭቁን ሕዝቦችን ትግል የሚገታ ኃይል ሆኖ ሲወጣ ከተራማጅ ይልቅ አድኃሪ ገጽታው እያየለ መጥቷል ።

ብሔረተኝነት የገዥ መደብን ጥቅም የሁሉም መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች የጋራ ጥቅም አስመስሎ ያቀርባል ። በጣም በደረጁ ካፒታሊስት ሀገሮች ብሔረተኝነት ሰፊው ሕዝብ የሞኖፖል ቡርዧዚው ተገዥ እንዲሆን መገፋፊያ ፣ ሠራተኛው መደብ ለአብዮታዊ ለውጥ እንዳይታገል ማፈኛና ከዓላማውም ውጭ በሌሎች ሕዝቦች ላይ እንዲዘምት የሥነ ልቡናዊ ትጥቅ መስጫ መሣሪያ ነው ። ኢምፔሪያሊዝም ብሔረተኝነትን በማፋፋም ሶሻሊዝምን ለመዋጊያ ዋነኛ መሣሪያው ያደርገዋል ። ብሔረተኝነት የሶሻሊስት ሀገሮችንና የኮሚኒስት ንቅናቄን አንድነት አጥብቆ የሚፃረር እንቅስቃሴ ነው ።

ሠራተኛው መደብ በወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት መርህ ስለሚመራ ብሔረተኝነትን አይቀበልም ። ይሁን እንጂ ጭቁን ሕዝቦች ከኢምፔሪያሊዝምና ከውስጥ አድኃሪ ኃይሎች ጋር የሚያደርጉት የብሔራዊ አርነት ትግል አጠቃላይ ዲሞክራሲያዊ ይዘት ያለው በመሆኑ ይደግፈዋል ። በአጠቃላይ ብሔረተኝነት ከሠራተኛው መደብ ፣ ከሶሻሊስትና ከብሔራዊ አርነት ኃይሎች ፣ ለብሔራዊ ነፃነት ፣ አንድነትና ክብር ካላቸው ከፍተኛ የሶሻሊስት አርበኝነትና የሀገር ፍቅር ስሜት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም ።

(አርበኝነትን ይመለከቷል ።)

## ብሔራዊ ሶሻሊዝም
*(National Socialism)*

ከ1933 እስከ 1945 በጀርመን ውስጥ በሂትለር መሪነት ተቋቁሞ የነበረውና የሁለተኛው ዓለም ጦርነት መንሥኤ የሆነው ፋሺጭ ቆራጭ መንግሥት ይከተል የነበረው ርዕዮተዓለማዊና ፖለቲካዊ ሥርዓት ነው ። ብሔራዊ ሶሻሊዝም አዲስ የዓለም አመለካከት አለኝ የሚል ሲሆን የአመለካከቱ መሠረት የጀርመን ዘር ከሁሉ በላይ በመሆኑ ዓለምን መግዛት አለበት ፤ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የጀርመን ዘር በሙሉ ፍጹማዊ በሆነና በሂትለር የበላይ አለቅነት በሚመራ መንግሥት ሥር መሰባሰብ አለበት የሚለው ነው ። የዚህ ሥርዓት ግንባር ቀደም ኃይል ብሔራዊ ሶሻሊስት ፓርቲ ሲሆን ፓርቲው የሌሎች ፓርቲዎችን መኖር የማይቀበል ፣ በይፋ ፀረ ዲሞክራሲ ፣ ፀረ እኩልነት ፣ ፀረ ፓርላማና ፣ ፀረ ኮሚኒስት ነው ። ዋና ተግባሩም ኅብረተሰቡን መቆጣጠርና ርዕዮተዓለሙን ማስራጨት ነው ።

የዚህ በዘረኝነት ላይ የተመሠረተ ፋሺስታዊ መንግሥት አስከፊነት የተረጋገጠው የሁለተኛው ዓለም ጦርነት መንሥኤ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን የጀርመንን ዘር ጥራት እጠብቃለሁ በሚል ሰበብ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ አይሁዶችን መጨፍጨፉ ነው ። በአንደኛው የዓለም ጦርነት የጀርመን መሸነፍ ፈጥሮት የነበረው የብሔር ትምክህተኝነት ፣ በአውሮፓ ውስጥ ከ1929 ጀምሮ የተነሣው የካፒታሊዝም ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ቀውስ ያስከተለው የተስፋ መቁረጥ ስሜትና የአስተሳሰብ ውዥንብር ለብሔራዊ ሶሻሊዝም መጸነስና ተደማጭነት ማግኘት አመቺ ሁኔታ ፈጥሯል ። በአንፃሩም ሠራተኛው ሕዝብ በደረሰበት ከፍተኛ ውድቀት ተነሣሥቶ ካፒታሊዝምን በመዋጋት ለሶሻሊስት ሥርዓት እንዳይታገል ማለትም የመደብ ትግሉን እንዲዘነጋና የራሱን ድርጅቶች እንዲያፈራርስ በብሔር ትምክህተኝነትና በዘረኝነት በመደለል ለካፒታል ፍጹም ተገዥ ሆኖ የቀውሱን ጊዜ ካስተቀናቃኝ ለማለፍ እንዲችል የፋይናንስ ካፒታል የወጠነው አስከፊና አደገኛ ሥርዓት ነበር ።

(ዘረኝነትን ፣ ፋሺዝምን ይመለከቷል ።)

## ብሔራዊ ነፍስ ወከፍ ገቢ ፥ *(National per Capita Income)*

የአንድን ሀገር ብሔራዊ ገቢ መጠን በሕዝቡ ጠቅላላ ቁጥር በማካፈል የሚገኝ የገቢ መጠን ብሔራዊ ነፍስ ወከፍ ገቢ ይባላል ። ለምሳሌ የአንድ ሀገር የአንድ የተወሰነ ዓመት ጠቅላላ ብሔራዊ ምርት መጠን አሥር ቢሊዮን (10,000,000,000) ብር ነው እንበል ። በዚያው ዓመት የዚህ ሀገር ሕዝብ ጠቅላላ ቁጥር ደግሞ አሥር ሚሊዮን (10,000,000) ነው እንበል ። ስለዚህ በዚያ ዓመት የዚሁ ሀገር ብሔራዊ ነፍስ ወከፍ ገቢ

$$\frac{10,000,000,000}{10,000,000} = 1,000 \text{ ብር ይሆናል ።}$$

ይህም ማለት በዚያ ዓመት የዚሁ ሀገር አማካይ የዓመት ገቢ አንድ ሺህ (1,000) ብር ነበር ማለት ነው ።

ብሔራዊ ነፍስ ወከፍ ገቢ የአንድን ሀገር የኑሮ ደረጃ ለመለካት በሥራ ላይ ከሚውሉት መመዘኛዎች አንዱ ነው ። ከዳበሩት ካፒታሊስት ሀገሮች መካከል ከፍተኛ ብሔራዊ ነፍስ ወከፍ ገቢ ያላት ስዊትዘርላንድ ስትሆን ከዷም በተከታታይ ከፍተኛ ብሔራዊ ነፍስ ወከፍ ገቢ ካላቸው ሌሎች ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች መካከል ስዊድን ፣ ጀርመን ፌደራል ሪፐብሊክ ፣ ፈረንሳይ፣ አሜሪካ ፣ ጃፓንና እንግሊዝ ይገኛሉ ።

ከሶሻሊስት ሀገሮች መካከል ከፍተኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ ያላቸው የጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ፣ ቼኮዝሎቫኪያ እና ሶቭዬት ኅብረት ይገኛሉ ።

ከአፍሪካ ሀገሮች መካከል ከፍተኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ ያላቸው ሊቢያ ቱኒዝያና አይቮሪ ኮስት ናቸው ።

በብሔራዊ ነፍስ ወከፍ ገቢ አማካይነት የአንድን ሀገር የኑሮ ደረጃ መለካት የተለመደ ቢሆንም ይህ አሠራር መሠረታዊ ችግር ያለው መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው ። ይህንንም ሀብታም ከሆኑት ከአረብና ከአፍሪካ ዘይት አምራች ሀገሮች የገቢ መጠንና የዕድገት ደረጃ ለማየት ይቻላል ። ብሔራዊ ነፍስ ወከፍ ገቢ የሕዝብ አማካይ ገቢ እንደመሆኑ መጠን የአንድ ሀገር ብሔራዊ ገቢ በሕዝቡ መካከል እንዴት እንደሚከፋፈል አያመለክትም ፤ በኢምፔሪያሊስት ሀገሮችና ኋላ ቀር በሆኑ የካፒታሊዝምን የዕድገት ፈለግ በሚከተሉ ሀገሮች ውስጥ ቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑ ግለሰቦች የምርት መገልገያዎችን በግል ንብረትነት በመያዝ በየዓመቱ ከሚፈጠረው ብሔራዊ ገቢ ከፍተኛውን ክፍል ይወስዳሉ ። በአንፃሩ በሰፊው ሕዝብ መካከል የሚከፋፈለው የብሔራዊ ገቢ ክፍል አነስተኛ ሆኖ ይገኛል ። ስለዚህ እንደ አሜሪካ ባሉ ከፍተኛ ብሔራዊ ነፍስ ወከፍ ገቢ ባላቸው ሀገሮች ውስጥ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ገቢያቸው እጅግ አነስተኛ በመሆኑ ሥራ አጥም በመሆናቸው በድህነት ሲቆራመዱ ይታያሉ ። በሰዎች መካከል የገቢ ልዩነት በጠበበባቸውና ይበልጥም እየጠበበ በመሄድ ላይ በሚገኙባቸው በሶሻሊስት ሀገሮች ግን ብሔራዊ ነፍስ ወከፍ ገቢ የኅብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ በተሻለ ሁኔታ ለማሳየት ይችላል ።

ብሔራዊ ነፍስ ወከፍ ገቢን የሚወስኑ የብሔራዊ ገቢ መጠንና የሕዝብ ጠቅላላ ቁጥር እንደመሆናቸው የዕድገቱ መጣኔም የሚወሰነው በብሔራዊ ገቢ የዕድገት መጣኔና በጠቅላላ የሕዝብ ቁጥር የዕድገት መጣኔ ነው ። ስለሆነም የብሔራዊ ነፍስ ወከፍ ገቢ ዕድገት ሊያሳይ የሚችለው የብሔራዊ ገቢ ዕድገት መጣኔ ከጠቅላላ የሕዝብ ቁጥር የዕድገት መጣኔ በልጦ ሲገኝ ብቻ ነው ። ለምሳሌ ብሔራዊ ገቢ በ2.5% ቢያድግና የሕዝቡ ቁጥርም እንደዚሁ በ2.5% ቢያድግ የብሔራዊ ነፍስ ወከፍ ገቢ መጠን ምንም ለውጥ ሊያሳይ አይችልም። ነገር ግን የሕዝቡ ቁጥር በዚያው በ2.5% ዕድጐ ብሔራዊ ገቢ በ6% ቢያድግ ብሔራዊ ነፍስ ወከፍ ገቢ በ3.5% ያድጋል ። በአንፃሩም የሕዝቡ ቁጥር መጣኔ ጨምሮ የብሔራዊ ገቢው መጣኔ ግን ካነስ የነፍስ ወከፍ ገቢው ያንሳል ።

(ብሔራዊ ገቢን ይመለከቷል ።)

## ብሔራዊ የአርነት ንቅናቄ
*(National Liberation Movement)*

አንድን በቅኝ ገዥነት ወይም በሌላ መልክ በተፈጠረ ሁኔታ በባዕድ አገዛዝ ሥር የምትገኝ ሀገር ከባዕድ ኃይል መዳፍ ተላቅቃ ብሔራዊ ህልውናዋን ፣ በሙሉ ነፃነትና መብት እራሷን እንድትመራ ለማድረግ የሚታገል ኃይል ነው ።

ብዙውን ጊዜ የዚህ ዓይነቱ ንቅናቄ ነፃ ለመውጣት ከምትታገለው ሀገር ዜጎች መካከል በትምህርትና በንቃታቸው ላቅና በኢኮኖሚ አቋማቸው ጠንከር ባሉ ፣ በአብዛኛው ከተሜ በሆኑ ክፍሎች ይጀመራል ። በመጀመሪያው ደረጃ ላይ አመራሩን የሚይዙትም እነዚሁ ወገኖች ናቸው ።

ነገር ግን በሀገሪቱ ውስጥ ካፒታሊዝም እያደገ ሲሄድና በከተሞች ፣ በኢንዱስትሪ ማዕከሎች ፣ በወደቦችና በመሳሰሉት አካባቢዎች የኢምፔሪያሊዝም እንቅስቃሴ ሲስፋፋ የሠራተኛው መደብም ያድጋል ። ይህ መደብ በቁጥር እየበዛና እየተደራጀ በመጣ መጠን ደግሞ በንቅናቄው ውስጥ የሚያደርገው ተሳትፎ ይጨምራል ። የዚህ ሂደት ይበልጥ መጠናከር ደግሞ የሠራተኛው መደብ አባላትና ደጋፊዎች የንቅናቄውን አመራር ጭምር እንዲይዙ አመች ሁኔታዎችን ይፈጥራል ። ይልቁንም በንቅናቄው የትግል ሂደት ላይ ተራማጅ ኃይሎች እየተደራጁ ፣ በተለይም ግንባር ቀደም ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲን ከመሠረቱ የንቅናቄውን ዓላማና የትግል መሥመር በጠራ ርዕዮተዓለም በመምራት ከባዕድ አገዛዝ ወጥቶ የፖለቲካ ነፃነት ከማግኘት ባሻገር ንቅናቄው እኩልነትና ዲሞክራሲ ለሰፈነበት ኅብረተሰብ መገንባትም እንዲታገል ሰፊ ስልት ይቀይሱለታል ።

ንቅናቄው በዚህ መልክ እየተጠናከረና በዓላማውም የዓይነት ለውጥ እያሳየ በሄደ መጠን በመጀመሪያው ደረጃ የነበረው የኃይል አሰላለፍ ይለወጣል ። ትግሉም ከባዕድ ቅኝ ገዥዎችና ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር ብቻ መሆኑ ቀርቶ የነሱ የመደብ ጥቅም ተባባሪ በመሆን አብረዋቸው ከሚሰለፉ የውስጥ አድኃሪዎች ፣ አምስተኛ ረድፈኞችና ከሌሎችም አጋሮቻቸው ጋር ይሆናል ። ከዚህም የተነሣ ንቅናቄው በአንድ በኩል እየተጠናከረና ድሎችን እየተጐናፀፈ ሲሄድ በሌላ በኩል ትግሉ ውስብስብና የረቀቀ እየሆነ ይመጣል ። ይህ ዓይነቱ ለብሔራዊ እርነትና ለማኅበራዊ ነፃነት የሚደረግ ትግል በድል ለመውጣትም ንቅናቄው ከሶሻሊስትና ተራማጅ ሀገሮች ጋር የትግል አንድነት በመመሥረት ድጋፍ ማግኘቱ ወሳኝ ነው ። እስካሁንም ያለው ሁኔታ ሲታይ በተለይ የሶቭዬት ኅብረት በሶሻሊዝም ግንባታ ከፍተኛ ደረጃ መድረሷና ከሁለተኛው የኢምፔሪያሊስቶች ጦርነት ወዲህ በበርካታ ሀገሮች ውስጥ ሶሻሊዝም እየተስፋፋ መምጣቱ በአፍሪካ ፣ በእስያና በላቲን አሜሪካ ውስጥ በሚገኙ በርካታ ሀገሮች የብሔራዊ ነፃነት ንቅናቄዎች በድል እንዲወጡና ብዙዎቹም በነፃ ማኅበራዊ ዕድገት እንዲራመዱ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

(ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ፣ ቅኝ አገዛዝን ፣ ዓለምአቀፋዊነትን ይመለከቷል ።)

## ብሔራዊ ዕዳ
*(National Debt)*

ብሔራዊ ዕዳ የሚባለው የአንድ ሀገር መንግሥት ያለበት ያልተከፈለ የብድርና የወለድ ዕዳ ነው ። ብሔራዊ ዕዳ የሀገር ውስጥና የውጭ ተብሎ በሁለት ሊከፈል ይችላል ።

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ብሔራዊ ዕዳ ለቡርዧው መንግሥት ህልውና አስፈላጊ ነው ። ስለዚህም የካፒታሊስት ሀገሮች ብሔራዊ ዕዳ እጅግ ከፍተኛ የሆነና እያደገ በመሄድ ላይ የሚገኝ ነው ። ለምሳሌ በ1981 የዩናይትድ ስቴትስ ፌደራል መንግሥት ዕዳ 998 ቢሊዮን ዶላር ነበር ። በብዙ ካፒታሊስት ሀገሮች ብሔራዊ ዕዳ ከብሔራዊ ገቢ ይበልጥ እያደገ ሄዷል ። በዚህ አኳኋን በብሔራዊ ዕዳና በብሔራዊ ገቢ መካከል ያለው ጥምርታ በማደግ ላይ ይገኛል ። ለምሳሌ በዩናይትድ ስቴትስ በ1914 ብሔራዊ ዕዳ የብሔራዊ ገቢውን 3.3% ያህል ነበር ይህ ቁጥር በ1969 ወደ 63% ከፍ ብሏል ። በዚያው ጊዜ በእንግሊዝ ሀገርም ከ31.2% ወደ 126.1% ሊያድግ ችሎ ነበር ። የዚህም መሠረታዊ ምክንያት ኢምፔሪያሊስት

ሀገሮች ለጦር መሣሪያ እሽቅድድምና ለሌሎችም ተግባሮች በሚያወጡት ወጪ ከፍተኛነትና ዕድገት የተነሣ የበጀት ተዛቦት እያደገ መሄድ ነው ። የቡርዧው መንግሥት በያመቱ የሚያደርገው የዕዳ ክፍያም በበኩሉ ከበጀት ተዛቦት ዕድገት ጋር በቅርብ የተያያዘ ነው ።

በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮች ብሔራዊ ዕዳ በአብዛኛው የውጭ ዕዳ ነው ። የእነዚህ ሀገሮች የውጭ ዕዳ ከፍተኛነትና በአፋጣኝ እያደገ መምጣት በኢኮኖሚ ዕድገታቸው ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ በማሳደር ላይ ይገኛል። ለምሳሌ በመልማት ላይ ያሉት ሀገሮች የውጭ ዕዳ በ1975 179 ቢሊዮን ዶላር የነበረው በ1982 ወደ 626 ቢሊዮን ዶላር ከፍ ብሏል ። በ1982 ነዳጅ አምራች ያልሆኑ በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮች የውጭ ዕዳ ከገቢ ንግዳቸው ካገኙት ገቢ 37% ያህሉን ለብድርና ለወለድ ክፍያ ለማዋል ተገድደው ነበር ። አሁንም እነዚሁ ሀገሮች በ1981 ያደረጉት የብድርና የወለድ ክፍያ በዚያው ዓመት ካገኙት የውጭ ብድር 85% ያህል እንደነበር ለማወቅ ተችሏል ።

በዚህ አኳኋን በመልማት ላይ ያሉ ፣ በተለይም ነዳጅ አምራች ያልሆኑት ሀገሮች ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ ልከውም ሆነ ከውጭ ተበድረው ከሚያገኙት ከፍተኛ የሆነውንና በማደግ ላይ የሚገኘውን ከፍል ለብድርና ለወለድ ክፍያ ለማዋል ተገድደዋል ። ይህም ለኢኮኖሚ ዕድገት ሊውል የሚገባውን ክምችት እንዲመነምን ያደርጋል ።

ብሔራዊ ዕዳ በሶሻሊስት ሀገሮችም ውስጥ የሚገኝ ነው ፤ ሆኖም በዕቅድ በሚመራው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴያቸው ውስጥ ወሳኝነት የለውም ። የሶሻሊስት ሀገሮች መንግሥታት ብሔራዊ ዕዳን በተለይ በየሀገሮቻቸው ውስጥ የሚገኘውን ለጊዜው በጥቅም ላይ ያልዋለን ገንዘብ እንደመሳቢያ ዘዴ ይገለገሉበታል ። ከሕዝቡ የሚገኘውንም ብድር ለሶሻሊስት ሙአለ ንዋይና የሕዝቡን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ያውሉታል ።

## ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት
*(National Democratic Revolution)*

በአብዮታዊ ሂደት ውስጥ በተወሰነ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚከሰት የኅብረተሰብ ፖለቲካዊ አደረጃጀት ቅርፅ ነው ። ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ነፃነት ለማግኘት ኢምፔሪያሊዝምንና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን ሳያወላውሉ መዋጋት ፣ የውስጥ የአድህሮት ኃይሎችን በመደምሰስ ኅብረተሰቡን በዕድገት ጎዳና ማራመድ ፣ በሰፊው የተዘረጉ ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች መደንገግና ተግባራዊ ማድረግ ፣ በመንግሥት ፖሊሲ አቀያየስ ውስጥ የሕዝቡ ተሳትፎ ወሳኝነት ማግኘት ፣ እንደ መሬት ፣ እንደፋብሪካዎች ያሉትን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ማድረግ የመሰሉ አብዮታዊ ማኅበራዊ ለውጦችን ማካሄድ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ዋና ዋና ድርጊቶች ናቸው ።

የሂደቱን ብሔራዊነት የሚያረጋግጠው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ነፃነትን እውን ለማድረግ ከኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ጋር የሚያደርገው ቀራጥ ትግል ሲሆን ይህ ትግል ደግሞ የሚከናወነው በሕዝብ ኃይልና ቀጥተኛ ተሳትፎ መሆኑ አብዮቱ ሰፊ ዲሞክራሲያዊ መሠረት እንዳለው ያስረዳል ። ሰፊውን ሕዝብ ለትግል የሚያደራጅና የሚያስተምር መሆኑ ፣ ከብዝበዛና ከጭቆና ነፃ የሆኑና ለዕድገት አፋጣኝ የሆኑ የምርት ግንኙነቶችን መመሥረቱ ሂደቱን አብዮታዊ ያደርገዋል ።

የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፖለቲካዊ ባሕርይ ተራማጅ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችና ሀገር ወዳድ የሆኑ ኃይሎች ኢምፔሪያሊዝምንና ፊውዳሊዝምን ለመዋጋት በሚፈጥሩት የጋራ ግንባር ላይ የተመሠረተ ነው ። የግንባሩ መመሥረት አብዮታዊ የሆነው የሠራተኛ መደብ ቀጥተኛ ተሳትፎና ግፊት ውጤት ነው ። በመሆኑም በግንባሩ ውስጥ የሠራተኛው መደብ ኃይል እያደገ መምጣት ፣ በኅብረተሰብ ውስጥ የማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተዓለም መሠራጨት ፣ ሰፊው የገበሬ መደብና ሌሎች ሠርቶ አደር ክፍሎች በሠራተኛው መደብ መሪነት መሰባሰብ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የካፒታሊዝምን የዕድገት ጎዳና ጨርሶ በመተው ወደ ሶሻሊስት የዕድገት ጎዳና እንዲያመራ የሚያደርግ ወሳኝ ሁኔታ ነው።

(ኢምፔሪያሊዝምን ፣ ብሔራዊ የአርነት ንቅናቄን ይመለከቷል ።)

## ብሔራዊ ገቢ
*(National Income)*

በአንድ ሀገር ወይም ኅብረተሰብ በአንድ በተወሰነ ጊዜ ማለትም በአንድ ዓመት ውስጥ አዲስ የተፈጠረ አጠቃላይ የእሴት መጠን ነው ። ጠቅላላ ማኅበራዊ ምርት በአንድ ኅብረተሰብ በአንድ ዓመት ውስጥ የሚመረተው ጠቅላላ ቁሳዊ ምርት መጠን ሲሆን ከዚህ ከጠቅላላ ማኅበራዊ ምርት በምርቱ ሂደት ውስጥ በሥራ ላይ ከዋሉት የምርት መገልገያዎች አዲስ ወደ ተመረቱት ቁሳዊ ምርቶች የተላለፈው እሴት ሲቀነስ የሚገኘው ብሔራዊ ገቢ ወይንም ብሔራዊ ምርት ይባላል ። በሌላ አነጋገር በአንድ ዓመት ጊዜ በአንድ ኅብረተሰብ የምርት ሂደት ውስጥ አስፈላጊ ለሆኑ ቁሳዊ ነገሮች የወጣውን ወጪ ከጠቅላላ ማኅበራዊ ምርት ስንቀንስ ብሔራዊ ገቢን ወይም ብሔራዊ ምርትን እናገኛለን ።

ብሔራዊ ገቢ በቁሳዊ መልኩ ሲታይ በአንድ ኅብረተሰብ በአንድ ዓመት ውስጥ አዲስ የተመረቱትን የፍጆታ ዕቃዎችንና የምርት መገልገያዎችን ያጠቃልላል ።

ከማርክስ በፊት ስለብሔራዊ ገቢ ልዩ ልዩ አስተሳሰቦች የተሰነዘሩ ቢሆንም ሳይንሳዊነት ይጐድላቸው ነበር ። ለመጀመሪያ ጊዜ ብሔራዊ ገቢን ለመተመን ሙከራ ያደረገው በ17ኛው ምዕት ዓመት የነበረው ዊልያም ፔቲ የተባለው እንግሊዛዊ ኢኮኖሚስት ፣ "ፖለቲካል አሪትሜቲክ" በተባለው መጽሐፉ ነበር ። በኋላም ፊዚዮክራቶች ለብሔራዊ ገቢ ንድፈ ሐሳብ መዳበር አስተዋጽኦ አድርገዋል ። ከእነሱም መካከል ዋነኛው ፍራንሷ ኬኔ የተባለው ፈረንሳዊ ነው ። ኬኔ በ1758 ባዘጋጀው የኢኮኖሚ ሠንጠረዥ የማኅበራዊ ምርትን ሂደት ለማሳየት የመጀመሪያውን ሙከራ አድርጐ ነበር ። ሆኖም ፊዚዮክራቶች እርሻን እንደብቸኛ ምርታዊ መስክ የመውሰድ ስህተት በመፈጸማቸው ስለ ማኅበራዊ ምርት እርባታ የተሟላ አስተሳሰብ ለመሰንዘር አልቻሉም ። ብሉይ ቡርዧ ኢኮኖሚስቶቹ ስሚዝና ሪካርዶም ስለ ብሔራዊ ገቢ ሐሳብ ቢሰነዝሩም የማኅበራዊ ምርት እርባታን በትክክል ሊገነዘቡ አልቻሉም ነበር ።

ቡርዧ ኢኮኖሚስቶች ስለብሔራዊ ገቢ ያላቸውን አመለካከት የሚመሠርቱት በካፒታሊስቱ ሥርዓት ብዝበዛ የለም በሚል አስተሳሰብ ላይ ሆኖ የትርፍ ምንጩ ካፒታል ፣ እንዲሁም የመሬት ኪራይ ምንጩ መሬት ነው በሚልና ለሠራተኛው የሥራ ውጤቱ ሙሉ በሙሉ በምንዳ መልክ ይከፈለዋል በሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ ላይ ነው ። በዚህ ዓይነት ቡርዧ ኢኮኖሚስቶች የብሔራዊ ገቢ ብቸኛ ምንጭ ሠራተኛው መሆኑን በመካድ በካፒታሊስቱ ስልተ ምርት ውስጥ የሚካሄደውን ብዝበዛ ለመሸፈን ሞክረዋል ።

በእነዚሁ ቡርዧ ኢኮኖሚስቶች አስተሳሰብ ቁሳዊ ምርትን በማምረት የተሰማሩትና ሌሎቹም በአጠቃላይ በአንድ ዓመት ውስጥ የሚያገኟቸው ገቢዎች ድምር ብሔራዊ ገቢ ይባላል ። ሆኖም የዚህ ዓይነቱ የብሔራዊ ገቢ አተማመን አንድ ጊዜ በሠራተኛው የተፈጠረው ገቢ ወይንም ምርት ከአንድ ጊዜ በላይ ተመን ውስጥ እንዲገባ ስለሚያደርግ የአንድን ሀገር ብሔራዊ ገቢ ትክክለኛ መጠን በአማካይ ከ20—30% ያለአግባብ ከፍ ያደርገዋል ።

ለስብሔራዊ ገቢ አስተሳሰብ ሳይንሳዊ መሠረት የሰጠው ማርክስ ነው ። በማርክሳዊ ሌኒናዊ አስተሳሰብ ብሔራዊ ገቢ የሚፈጠረው ምርታዊ በሆኑ የኢኮኖሚ መስኮች ማለትም በኢንዱስትሪ ፣ በእርሻ ፣ በሕንፃ ሥራና በመሳሰሉ ቁሳዊ ምርት በሚመረትባቸው መስኮች ነው ። እንደ ትምህርት ፣ እንደ ጤና ፣ እንደ መንግሥት አስተዳደር ፣ እንደ መከላከያ ወዘተ... ያሉ መስኮች ምርታዊ ባለመሆናቸው ለብሔራዊ ገቢ መፈጠር ቀጥተኛ የሆነ አስተዋጽኦ አያደርጉም ። እነዚህን ምርታዊ ያልሆኑ መስኮች ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልገው ወጪ የሚገኘው በብሔራዊ ገቢ ዳግም ክፍፍል ጊዜ በተለይም በመንግሥት በጀት አማካይነት ነው ። ሆኖም ምርታዊ ባልሆኑ መስኮች በተለይም ማኅበራዊ አስፈላጊነትና ጠቃሚነት ባለው ተግባር ላይ የተሰማሩ ሠራተኞች ብሔራዊ ገቢን በመፍጠር ቀጥተኛ ተሳትፎ ባያደርጉም በተዘዋዋሪ መንገድ ለብሔራዊ ገቢ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆኑን መጥቀስ ተገቢ ነው ።

ብሔራዊ ገቢ ሊያድግ የሚችለው ምርታዊ በሆኑ መስኮች የተሰማሩ ሠራተኞች

ቁጥር ሲጨምርና በእነዚሁ መስኮች ውስጥ የተሰማሩ ሠራተኞች ምርታማነት ሲያድግ ነው ። ሆኖም የብሔራዊ ገቢ ማደግ የአንድን ኅብረተሰብ የኑሮ ደረጃ የሚጠበቀውን ያህል ሊያሳድግ የሚችለው ሰፊው ሕዝብ የሥራው ውጤት ተጠቃሚ ለመሆን ሲችል ነው ። በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ መደቦችና ክፍሎች የኑሮ ደረጃ ፣ የዓመታዊ ገቢያቸው መጠንና ከብሔራዊ ገቢው የሚያገኙት ድርሻ የሚወሰነው በብሔራዊ ገቢ መጠንና የዕድገት መጣኔ ብቻ ሳይሆን ገቢው በሚከፋፈልበት መርህና ገቢው በሚውልበት ጥቅም ዓይነት ጭምርም መሆኑን መገንዘብ ይጠቅማል ።

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ከብሔራዊ ገቢ ውስጥ በዛ ያለ መጠን ለቡርዧው መደብና ለተባባሪዎቹ የቅንጦት ፍጆታ ይውላል ። በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚካሄደው ክምችትም የቡርዧዚውን ትርፍ ለማዳበር እንጂ የሕዝቡን ፍላጎት ለማርካት ታቅዶ የሚከናወን አይደለም ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ብሔራዊ ገቢ ለኅብረተሰቡ ጥቅም እንዲውል ይደረጋል ። የሕዝቡን ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎት ለማርካት እንዲሁም ሶሻሊስት ምርትን ለማሳደግ ተግባር ይውላል ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ክምችት የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ በፍጆታና በክምችት መካከል ሚዛናዊ የሆነ ቅንጅት አለ ።

በካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ የሚገኙት የምርት ግንኙነቶች ከምርት ኃይሎች ዕድገት ደረጃ ጋር የተጣጣሙ ባለመሆናቸው የብሔራዊ ገቢ ዕድገታቸው መጣኔ ውሱን ነው ። በሶሻሊስት ሀገሮች ውስጥ የሚገኙት የምርት ግንኙነቶች ግን ለምርት ኃይሎች ዕድገት አመቺ በመሆናቸው የሶሻሊስት ሀገሮች ብሔራዊ ገቢ የዕድገት መጣኔ ከኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ጋር ሲነፃፀር ፈጣን ዕድገት በማሳየት ላይ ይገኛል ።

(ጠቅላላ ማኅበራዊ ምርትን ይመለከቷል ።)

## ብሔራዊ ገቢ ክፍፍልና ዳግም ክፍፍል (የ—)

*(Distribution and Re–distribution of National Income)*

ብሔራዊ ገቢ በኅብረተሰቡ ልዩ ልዩ መደቦችና ማኅበራዊ ክፍሎች መካከል ያለው የክፍፍል ደረጃ ነው ። የብሔራዊ ገቢ ክፍፍልና ዳግም ክፍፍል መደባዊ ጠባይ አለው ። በካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የብሔራዊ ገቢ ክፍፍልና ዳግም ክፍፍል በቅድሚያ የበዝባዥ መደቦችን ጥቅም ለማስከበርና ለማዳበር ይውላል ።

በካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ወዝ አደሩ የሚፈጥረው ብሔራዊ ገቢ በመጀመሪያ ሙሉ በሙሉ ምርታዊ በሆኑ መስኮች ላይ በተሰማሩ ካፒታሊስቶች እጅ ይገባል ። ከዚያም ብሔራዊ ገቢው በመጀመሪያ በእነዚሁ ካፒታሊስቶችና ቁሳዊ ምርትን በማምረት ተግባር ላይ በተሰማሩ ወዝአደሮች መካከል ይከፋፈላል ። በዚህ ዓይነት ወዝአደሮቹ ምንዳ ሲወስዱ ካፒታሊስቶች ተረፈ እሴት ያገኛሉ ። የብሔራዊ ገቢ አንድ ክፍል የሆነው ተረፈ እሴትም በኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶች ፣ በንግድ ካፒታሊስቶች ፣ በእርሻ ካፒታሊስቶችና በካፒታሊስት ባለመሬቶች መካከል ይከፋፈላል ።

ብሔራዊ ገቢ በዚህ ዓይነት በካፒታሊስቱ ኅብረተሰብ ሦስት መሠረታዊ መደቦች ማለትም በወዝአደሩ ፣ በካፒታሊስቱና በካፒታሊስት ባለመሬቶች መካከል በመጀመሪያ ከተከፋፈለ በኋላ ዳግም ክፍፍል ይከናወናል ። በዳግም ክፍፍል አማካይነት ገቢ የሚያገኙት ምርታዊ ባልሆኑ ማለትም ቁሳዊ የሆኑ ዕቃዎች በማይመረቱባቸው መስኮች የተሠማሩ ካፒታሊስቶችና ሠራተኞች ናቸው። ካፒታሊስቶችና የቡርዧው መንግሥት ምርታዊ ባልሆኑ መስኮች ካፒታላቸውን በሥራ ላይ ሲያውሉም ትርፍ ያገኛሉ ። የእነዚህ ክፍያዎችና ገቢዎች ምንጭም ምርታዊ በሆኑ መስኮች ብቻ የሚፈጠረው ብሔራዊ ገቢ ነው ። እንደትምህርት ቤት ፣ እንደ ሆስፒታል ያሉ ምርታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመጀመሪያ ብሔራዊ ገቢውን በመካከላቸው ለተከፋፈሉት ካፒታሊስቶች ፣ ባለመሬቶችና ለወዝ አደሩ መደብ አባላት አገልግሎት በሚያበ

[illegible]ቱበት ወቅት ክፍያ ያገኛሉ ። ይህም ክፍያ ምርታዊ ባልሆኑ መስኮች የተሰማሩ ድርጅቶችን ለማካሄድ ፣ በእነዚሁ ድርጅቶች ውስጥ ለሚሠሩ ሠራተኞች ደመወዝ ለመክፈልና በድርጅቶቹ ውስጥ ካፒታላቸውን ሥራ ላይ ላዋሉ ካፒታሊስቶች ትርፍ ለማስገኘት ያስችላል ። በበጀት አማካይነትም የቡርዧው መንግሥት የወዝአደሩንና የሌሎቹንም መሠረታዊ መደቦች ገቢ በከፊል በቀረጥ መልክ በመሰብሰብ በተለይ የገዥ መደብ አባላትን ጥቅም ለማዳበርና ለማስከበር የሚረዳ መልክ ምርታዊ ያልሆኑ መስኮችን ለማካሄድ ይጠቀምበታል ።

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የብሔራዊ ገቢ ክፍፍል የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ያለማቋረጥ ለማሳደግና የሶሻሊስት እርባታን ለማዳበር ሲባል በዕቅድ የሚካሄድ ነው ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የሚፈጠረው ብሔራዊ ገቢ ሁለት ክፍሎች አሉት ። አንደኛው ክፉል አስፈላጊ ምርት ሲሆን ይኸውም ቁሳዊ ምርት በማምረት ተግባር የተሰማሩ ሠራተኞች እንደየሥራቸው መጠንና ችሎታ የሚያገኙት ነው ። ሁለተኛው ክፍል ተረፈ ምርት ሲሆን ይህም የኅብረተሰቡን የማምረት ችሎታ ለማዳበርና የኅብረተሰቡን ልዩ ልዩ አጠቃላይ ፍላጐቶች ለማርካት ይውላል ። የሶሻሊስቱ መንግሥት በተለይ በበጀት አማካይነት የብሔራዊ ገቢ ዳግም ክፍፍል እንዲካሄድ ያደርጋል ። በዚህ በዳግም ክፍፍል አማካይነትም ምርታዊ ባልሆኑ መስኮች የተሰማሩ ሠራተኞች ደመወዝ እንዲከፈላቸውና በአጠቃላይም የኅብረተሰቡን ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጐቶች በዕቅድ በበለጠ ለማሟላት ያስችላል ።

(ብሔራዊ ምርትን ይመለከቷል ።)

## ብሔር
*(Nation)*

በታሪክ ሂደት ውስጥ የተከሰተ የሰዎች ማኅበረሰብ ነው ። አንድ ብሔር በመጀመሪያ ደረጃ የሚለየው ባሉት የወል ቁሳዊ የኑሮ ሁኔታዎች ነው ። በአንድ መልክአምድራዊ ክልል ውስጥ መኖር ፣ በኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች መተሳሰር ፣ በአንድ ቋንቋ መጠቀም ፣ በጋራ ታሪካዊ ሂደት ውስጥ የወል ሥን ልቡናዊ ገጽታዎችና ባህላዊ አመለካከቶች መከሰት የብሔር መሠረቶች ናቸው ።

ብሔር ሰፋትና ቋሚነት ያለው በካፒታሊዝም ሂደት ውስጥ የተገኘ የሰዎች ከፍተኛ ማኅበረሰብ ነው ። የፊውዳሊዝም ክፍፍል መወገድና ግዛቶች በኢኮኖሚያዊ ሰንሰለት ተያይዘው አንድ ብሔራዊ ገበያ መፍጠራቸው ለብሔር ጠንካራ መሠረት ሰጥቶታል። ብሔር እንዲከሰት ለሂደቱ መሪ የሆነው የቡርዧው መደብ ነው ።

ሆኖም ብሔሮች እየተጠናከሩ ሲሄዱ በውስጣቸው የመደቦች ልዩነትና ግጭትም እየጐላ ይመጣል ። የውስጡን ቅራኔ ለማቀዝቀዝ ቡርዧዚው ብሔረተኛነትን በማራመድ በብሔሮች መካከል ጠብና ግጭት እንዲነግሥ አድርጓል ። ይህ ሁኔታ ወዝአደሩን በመከፋፈል የእርስ በርስ ግጭት በመፍጠሩና የወዝደሩን መደብ ታሪካዊ ሚናና የዓላማ አንድነት በማፋለሱ ወዝአደሮችን ሊያዋህድ የሚችል የዓለም አቀፋዊነት መርህ የመደቡ መሪ ሐሳብ ሆኗል ።

የካፒታሊዝም ውድቀት አዲስ የሆነ ሶሻሊስታዊ ሀገር ወዳድነት እንዲከሰት አድርጓል ። ይህ ሀገር ወዳድነት የተመሠረተው የመደብ ልዩነትና ግጭት በሌለበት ኅብረተሰብ ውስጥ በመሆኑ የሚሻው የብሔሮችን እህትማማችነት ነው ። ሶሻሊስታዊ ሀገር ወዳድነት ብሔሮችን በይበልጥ በማቀራረብና በማስማማት ከፍተኛ የሆነና ሰዎችን የአንድ ቤተሰብ አካል የሚያደርግ የኮሚኒስት ማኅበረሰብ እንዲፈጠር የሚገፋፋ አመለካከት ነው ።

(ብሔረተኛነትን ፣ ወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነትን ይመለከቷል ።)

## ብሔር ትምክህተኛነት (የ—)
*(National Chauvinism)*

ብሔረተኛነት የከረረ አቋም ይዞ የሚገኝበት ሁኔታ የብሔር ትምክህተኛነት ይባላል ። የብሔር ትምክህተኛነት የአንድን ብሔር ጥቅም ከሁሉ በላይ የሚያደርግ ብቻ ሳይሆን ሌሎችን ብሔሮች በጥላቻና በበታችነት የሚያይና አስከፊ ለሆነ ብዝበዛና

ጭቆና የሚያዘጋጅ ፣ አንዳንዴም ጨርሶ ለመጨፍጨፍ የሚነሣሣ ነው ። የብሔር ትምክህተኝነት አንዱ አዝማሚያ ዘረኝነት ነው ። የብሔር ትምክህተኝነት መደባዊ ምንጭ እንዳለው የሚያጠያይቅ አይደለም ። ብሔሮችን በበላይና በበታች ፣ በገዥና በተገዥ የሚከፋፍል አመለካከት በመሆኑ የከፋ ብዝበዛንና ጭቆናን ለመፈጸም የሚጠቅም ነው ።

(ፀረ አይሁድነትን ፣ ዘረኝነትን ፣ ፋሽዝምን ፣ አፓርታይድን ይመለከቷል ።)

## ብሔር ጥያቄ (የ—)

*(National Question)*

የብሔሮችን ነፃ መሆንና ነፃ ዕድገት ማግኘታቸውን የሚመለከት ጥያቄ ነው ። የብሔር ጥያቄ ይዘትና አስፈላጊነት እንደየሁኔታው የሚለዋወጥ በመሆኑ ታሪካዊ አመለካከት የሚያስፈልገው ነው ። በብሔሮች መከሰት ዘመን የብሔር ጥያቄ ያተኮረው ፊውዳሊዝምንና የውጭ ኃይል ጨቋኝ አገዛዝን በመታገሉ ላይ ነበር ። በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የብሔር ጥያቄ ወደ መንግሥት ጥያቄ በመቀየር በጨቋኝ አገዛዝ ሥር የሚገኙ ሕዝቦችን ነፃ ከማውጣት አጠቃላይ ጥያቄ ጋር በመተሳሰር ወደ አርነት ትግል አድጓል ። በአርነት ትግል ውስጥ በአመዛኙ ተካፋይ የነበረው የገበሬው ክፍል በመሆኑ የብሔር ጥያቄ ከገበሬው ጋር ሊያያዝ ችሏል ። የሶሻሊዝም የብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴዎች ዘመን ማለትም የቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ውድቀት ዘመን በሩሲያ አብዮት ተጀምሯል ። ባለንበት ዘመን ዓለምን ለመግዛት በመፈለግ እንደናዚ ጀርመንና በኋላም እንደ አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ያሉት መነሣሣታቸው በዳበሩ የካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ የብሔር ጥያቄ እንደገና እንዲያንሰራራ አድርጓል ።

የሠራተኛው መደብና የኮሚኒስት ፓርቲዎች የኢምፔሪያሊስቶችን የብዝበዛ ዕቅድ ለማክሸፍ በዛ ባሉ ሀገሮች ውስጥ የብሔራዊ ነፃነት እንቅስቃሴን በመደገፍና ዲሞክራሲያዊና ሀገር ወዳድ ኃይሎችን ከነሱ ጎን በማሰለፍ የእንቅስቃሴውን አመራር ይዘው ታሪካዊ ኃላፊነታቸውን የመወጣት ግዴታቸውን አስመስክረዋል ። የኢምፔሪያሊዝም ርዕዮተዓለማውያን የብሔር ጥያቄ ሊፈታ የሚችለው ብሔሮችን በመለያየት ነው የሚል አቋም መያዛቸው የሚገልጸው በብሔሮች መካከል አለመጣጣምን በመፍጠር አንዱን ለሌላው ተገዥ ለማድረግ ያላቸውን ፍላጎት ነው ። ሆኖም የሶሻሊስት አመለካከት ለዚህ ጥያቄ ሌላ አብዮታዊ መልስ ሰጥቷል ። ይኸውም ካፒታሊዝምንና ብሔራዊ ጭቆናን ጨርሶ በማጥፋት በሕዝቦች መካከል ወንድማማችነትን መፍጠር ነው። ይህም ተግባራዊ የሚሆነው ከበፊቱ ሥርዓት የተወረሰውን የኢኮኖሚና የባህል ደረጃ ልዩነት በአጭር ጊዜ ውስጥ በማጥፋት የብሔሮች እኩልነት ሲረጋገጥ ነው። በብሔሮች መካከል ትብብርና ተራድኦ በመፍጠር በተመጣጠነ ሁኔታ ዘመናዊ ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም ፣ የሠለጠኑ ሠራተኞችንና ምሁሮችን በማፍራት በቅርፁ ብሔራዊ በይዘቱ ሶሻሊስታዊ የሆነ ባህል መመሥረት ነው ። የኮሚኒስት ሥርዓት ማንባታ የመደብ ልዩነትን የሚያጠፋና ኮሚኒስታዊና ማኅበራዊ ግንኙነቶች በባህል ፣ በሥነ ምግባር ፣ በአኗኗር የጋራ አመለካከቶችን የሚያጎለብቱ በመሆናቸው ሥርዓቱ የብሔሮችን አንድነት በይበልጥ የሚያጠናክር ነው ።

(ብሔርን ፣ ብሔረሰብን ፣ ብሔራዊ የአርነት ንቅናቄን ፣ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ይመለከቷል ።)

## ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ

*(Classical Political Economy)*

ብሉይ ጥንታዊ ፣ ቀዳማዊ ማለት ነው ።

የካፒታሊስት ስልተ ምርት ሰጋ በነበረበት ፣ የወዝአደሩ መደብ የሚያካሂደው የመደብ ትግል እየተጠናከረ መምጣት ከመጀመሩ በፊት በ18 ኛው ምዕት ዓመት የተከሰተ የቡርዧ ኢኮኖሚ አስተምህሮና አመለካከት ነው ።

በካፒታሊስት ምርት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀናጀና ሥርዓት የተከተለ ምርምር ያካ

ሄዱት የብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሊቃውንት እንደመሆናቸው ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሳይንሳዊ አዝማሚያ ሊይዝ የቻለው በነሱ ሥራ አማካይነት ነው ።

ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ካፒታሊዝምን የሚመለከተው እንደ ዘለዓለማዊ ፈርጅ አድርጐ ነው ። ይህ የኢኮኖሚ አመለካከት ካፒታሊዝም "ከሰው ተፈጥሮ" ጋር የተጣጣመ ፤ (ከቡርዧው መደብ ጥቅም ጋር ማለት ነው) አመክንዮአዊ በሆነ ራስ ወዳድነት መርህ የሚመራ ሥርዓት እንደሆነ አድርጐ ያቀርበዋል ። ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የፊውዳሉን መደብ ጥገኝነት በጽኑ የተቃወመ ሲሆን የንግድ ካፒታሊስቱ ጥቅም አራማጆችና ርዕዮተዓለማውያን የነበሩት የሚርካንቲሊስቶችን አመለካከት ውድቅ አድርጎታል ።

ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ "የኢኮኖሚ ነፃነት" (ሌሴፌር) በሚለው መፈክሩ አማካይነት የካፒታሊስት መንግሥት በቡርዧው መደብ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ጣልቃ እንዳይገባ አስጠንቅቋል ።

ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ከቡርዧው አመለካከት ክልል ውስጥ የተወሰነ የኢኮኖሚ አመለካከት ቢሆንም በኢኮኖሚው ዘርፍ ያካሄደው ምርምር የቡርዧው ኅብረተሰብ የኢኮኖሚ ሕይወት ተጨባጭ በሆኑ "የተፈጥሮ" ሕጎች እንደሚመራና በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ሂደት እነዚህን ሕጎች አለመከተልም ወደ ከፍተኛ ቀውስ እንደሚያመራ አስረድቷል ።

ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በእንግሊዝና በፈረንሳይ ውስጥ ሰፍኖ የነበረ የኢኮኖሚ አመለካከት ሲሆን ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ ሊደርስ የቻለው ግን በእንግሊዝ ነው ። ከዋናዎቹ የእንግሊዝ ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚስቶች መካከል የእሴት የሥራን ንድፈ ሐሳብ በማመንጨትና ስለ ምንዳና ስለኪራይ በማጥናት የመጀመሪያ የሆኑት ዊልያም ፔቲ ፣ አዳም ስሚዝና የዚህ ምርምር አሳራጊ የሆነው ዴቪድ ሪካርዶ ይገኙበታል ። በፈረንሳይ የብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አስተምህሮን ያራመዱት በፈረንሳይ የዚሁ አስተምህሮ መሥራች የነበረው ቡዋጊልቤር ፣ ፊዝዮክራቶቹ ፍራንሷ ኪኒ ፣ ቱርጎና በፈረንሳይ ለብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አስተምህሮ የመጨረሻ ቅርፁን የሰጠው ሲስሞንዲ ነበሩ ።

ብሉያውያኑ የኢኮኖሚ ሊቃውንት ለፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ምርምር የሚጠቅም ሳይንሳዊ ዘዴ ቢቀይሱም አመለካከታቸው ግን ዲበአካልነትና ኢታሪካዊነት ያጠቃው ነበር ። የካፒታሊዝምን የኢኮኖሚ ፈርጆች የተመለከቷቸው የመጠን ለውጥ በማሳየት ብቻ እንደሚቀጥሉ ዘለዓለማዊ ፈርጅ በመቁጠር ነው ። ማኅበራዊ የምርት ግንኙነትን የሚገልጹ የኢኮኖሚ ፈርጆች ከታሪክ አንፃር ኃላፊ ጠፊ መሆናቸውን አልተገነዘቡም ።

በሌላ በኩል ብሉያውያኑ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚስቶች የእሴት የሥራ ንድፈ ሐሳብን በመቀመራቸውና የተረፈ እሴትን የተለያዩ ቅርፆች ለመጀመሪያ ጊዜ ለማመልከት በመቻላቸው በኢኮኖሚ ሳይንስ ምርምር ውስጥ ተገቢ የሆነ ከፍተኛ ቦታ ይሰጣቸዋል ። ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የማናቸውም ሸቀጥ እሴት ሸቀጡን ለመሥራት በዋለው ሥራ መጠን እንደሚወሰን አሳየ ። በዚህ ውስጥ የስሚዝ አስተዋጽኦ በተለያዩ የምርት መስኮች የሥራ ማኅበራዊ ክፍፍል የእሴት ምንጭ መሆኑን ማስገንዘቡ ነው ። ሪካርዶ የካፒታሊስትን ስልተ ምርትና በዚህ ስልተ ምርት ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና የኢኮኖሚ ፈርጆች ለመገምገም ከእሴት የሥራ ንድፈ ሐሳብ መነሣት እንደሚያስፈልግ አስገንዝቧል ። አዳም ስሚዝና ዴቪድ ሪካርዶ በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ጥናት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የያዘውን የሸቀጥ ባሕርይ በማስመልከት በጠቀሜታ እሴትና በልውውጥ እሴት መካከል ልዩነት እንዳለ አስገንዝበዋል ።

ይሁንና ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በግልና በማኅበራዊ ሥራ ፣ በተጨባጭና በረቂቅ ሥራ መካከል ያለውን ቅራኔ ፣ የቅራኔውንም መንሥኤ ሊገነዘብ አልቻለም ። እሴት በአኅዝ መልክ ሊተመን የሚችልበትን ዘዴ ከመግለጽ ሌላ በእሴት አማካይነት የሚንፀባረቀውን የምርት ግንኙነት በሚገባ ለመረዳት አልቻለም ። ስሚዝና ሪካርዶ እሴት በግል ሥራ አንፃር ሊወሰን እንደማይችል ቢገነዘቡም ማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ የእሴት መሠረት የመሆኑን ጽንሰ ሐሳብ ሊጨብጡ አልበቁም ። የእሴት የሥራ ንድፈ

ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ

ሐሳብን በማብራራቱ ረገድ ሪካርዶ ከስሚዝ ብዙ ገፍቶ ሄዷል ። ማርክስ ይህን በማስመልከት አዳም ስሚዝ ሳይሆን ዴቪድ ሪካርዶ የሸቀጦች እሴት በሥራ ኃይል እንደሚወስን በግልጽ ያብራራ ከመሆኑም በላይ ይህ ሕግ ቀደም ሲል የተገለጸውን ሁኔታ የሚፃረር የሚመስለውን የቡርዧ የምርት ግንኙነትም ጭምር እንደሚገዛ አብራርቷል በማለት ገልጿል ። ‘‘ፍጹማዊ’’ እሴትን ከ‘‘አንፃራዊ’’ እሴት በመለየት ሪካርዶ እሴት በሸቀጦች ውስጥ የተጠራቀመ ሥራ እንደሆነ ፣ ይህም እሴት የተወሰኑ ሸቀጦችን እሴት ከሌሎች ጋር ለማነፃፀር ከሚያገለግለው የልውውጥ እሴት የተለየ እንደሆነ አስገንዝቧል ። በዚህ አንፃር የሪካርዶ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ቢሆንም የልውውጥ እሴት የእሴት መልክ እንደሆነ ሊያሳይ አልቻለም ። ማርክስ እንዳለው የብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ዋንኛው ድክመት ስለሸቀጦች በተለይም ደግሞ ስለእሴታቸው ባካሄደው ምርምር ውስጥ እሴት የልውውጥ እሴት ሊሆን የሚችልበትን ሁኔታ ከቶውንም ለማግኘት አለመቻሉ ነው ። በተጨማሪም ማርክስ የዚህ አስተምህሮ (ብሉይ ፖለቲካ ኢኮኖሚ) ዋንኛ ተወካይ የሆኑት አዳም ስሚዝና ዴቪድ ሪካርዶ እንኳ የእሴት መልክ ምንም ጠቀሜታ (አስፈላጊነት) እንዲሁም ከሸቀጦች ውስጣዊ ባሕርይ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው አድርገው እንደሚመለከቱት ጽፏል ። የእሴትን መልክ የተለያዩ ገጽታዎች ለመገንዘብ ባለመቻላቸው ብሉያውያኑ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚስቶች (ሪካርዶም ጭምር) ስለ ገንዘብ ባሕርይና ተግባርም ሆነ ስለካፒታል ምንነት ትክክለኛ ግንዛቤ ሊኖራቸው አልቻለም ።

የብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ጠበብቶች ሥራ የእሴት ብቸኛ ምንጭ ነው ከሚለው መነሻ በመነሣት ትርፍ ፣ ወለድና ኪራይም ከሥራ እንደሚመነጩ አመልክተው ምንዳና ትርፍ የእሴት ሁለት ክፍሎች እንደሆኑ በመቁጠር ተረፈ እሴት በሙሉ በትርፍ እንደሚጠቃለል አድርገው ነው የተገነዘቡት ። በኢኮኖሚ ንድፈ ሐሳብ ታሪክ በምንዳና በትርፍ እንዲሁም በትርፍና በኪራይ መካከል ያለውን ግንኙነት ተቃራኒ የሆነ ግንኙነት እንደሆነ የተገነዘቡት የብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ጠበብቶች ናቸው ። ብሉያውያኑ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚስቶች የኢኮኖሚን ጥቅም በሚመለከት በቡርዧው ኅብረተሰብ ውስጥ ቅራኔ እንዳለ ቢገነዘቡም ፣ ቅራኔው በሸቀጦች የዝውውር ሂደት ውስጥ ብቻ እንደሚከሰት በመገመት የተሳሳተ አስተያየት አራምደዋል ። በሥራ ኃይልና በሥራ መካከል ያለውን ልዩነት ካለመገንዘባቸው የተነሣ ሥራን እንደሸቀጥ ፣ ምንዳን እንደ ሥራ እሴት በመመልከት ራሳቸው ከቀመሩት የእሴት ሥራ ንድፈ ሐሳብ ጋር ቅራኔ ውስጥ ለመግባት ተገደዋል ። በእሴት ሕግ በመጠቀም የካፒታሊስቱ መደብ ትርፍ እንዴት እንደሚሰበስብ ለመግለጽ አልቻሉም ።

የብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ጥናት የተረፈ እሴት የተለያዩ ገጽታዎች በሆኑት በትርፍ ፣ በወለድና በኪራይ ላይ ያተኮረ በመሆኑ የተረፈ እሴትን ይዘት ሊገነዘብ አልቻለም ። በመሆኑም የካፒታሊስት ብዝበዛን ይዘትም ሆነ የብዝበዛውን የተለየ ገጽታ አልተገነዘበም ። ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በእርሻው ዘርፍ ከመሬት ምርታማነት እያነሰ መሄድ የተነሣ የልዩነት ኪራይ ይኖራል ቢልም በእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ የፍጹማዊ ኪራይ መኖርን አይቀበልም ።

የማኅበራዊ ምርት እርባታን በሚመለከት ረገድ ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በተለይም የፈረንሳይ ፊዚዮክራቶች መሠረት ጥለዋል ። በዚህ ረገድ ምርታዊ የሆነው ክፍለ ኢኮኖሚ የእርሻው ዘርፍ ብቻ ነው በማለት ጠባብና የተሳሳተ አመለካከት ቢያራምዱም ማርክስ በወቅቱ ለኪኔ የኢኮኖሚ ሠንጠረዥ ከፍተኛ ግምት ሰጥቶት ነበር ።

ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚስቶች በተለይም ስሚዝና ሪካርዶ ካፒታልን ከቁሳዊ ገጽታው አንፃር ብቻ (ማለትም እንደ ምርት መገልገያ ፣ ገንዘብ ፣ ሸቀጥ ወዘተ..) በመመልከት ካፒታል በዝውውር ቁሳዊ ገጽታውን የሚለዋወጥ ማኅበራዊ የምርት ግንኙነት መሆኑን አልተገነዘቡም ። ካፒታልንም የከፈሉት በነባርና በተዘዋዋሪ ካፒታል ብቻ ነው ። በካፒታሊዝም ስለ ተረፈ እሴት ምርት የተረዱት ነገር ባለመኖሩ ካፒታልን በቋሚና በተለዋዋጭ የመከፈሉን አስፈላጊነት ሊገነዘቡ አልቻሉም ። ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ማኅበራዊ ምርት በሞላ ወደ ትርፍ ፣ ወደምንዳ ፣ ወደወለድና ወደኪራይ ይከፈላል የሚል የተዛባ አመለካከት ስለነበ

ረሙም በካፒታሊዝም ስለማኅበራዊ ምርት
ክርባታ ትክክለኛ ግንዛቤ ሊኖረው አልቻ
ለም ።

ሪካርዶ በካፒታሊዝም ውስጥ የመደብ
ቅራኔ እንዳለ አመልክቷል ። ይሁንና ሪካርዶ
በካፒታሊስት ሥርዓት የወዝአደሩን መደብና
የሌሎች ሠርቶ አደሮችን ድህነት የተመለከ
ተው ከተፈጥሮ ሕግ ጋር የተያያዘ እንደሆነ
አድርጎ ነው ። ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ
የካፒታሊስት ሥርዓት በውስጡ “ ተፈጥ
ሯዊ መመጣጠን ” ያለበት ሥርዓት ነው ብሎ
ስለሚያምን ፣ በካፒታሊስት ኢኮኖሚ የሚነ
ግሠው ቀውስ በዚያው በሥርዓቱ ውስጥ ሊፈታ
ይችላል የሚል አቋም አለው ። በሌላ በኩል
ሲስሞንዲ ስለካፒታሊዝም ቅራኔ ቢያትትም
በካፒታሊዝም ላይ ያካሄደው ኂስ ከንዑስ ከበር
ቴው መደብ አመለካከት አንፃር ነው ። ለዚ
ህም ነው ወደኋላ ተመልሶ የአነስተኛ ሸቀጥ
ምርት ደጋፊ የሆነው ።

የቡርዧ መደብ የፖለቲካ ሥልጣኑን
እያደላደለ ሲሄድና በአንፃሩም ወዝአደሩ
የሚያካሂደው የመደብ ትግል እየተፋፋመ
ሲመጣ በቡርዧ ኢኮኖሚስቶች አማካይነት
እንዳንዶቹ የብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ
ክንስ ሐሳቦች ወደ ግልብነት እንዲለወጡና
ለካፒታሊስቱ መደብ ጥቅም እንዲከራከሩ
ተደርጎ ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚም ቦታ
ውን ለግልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መልቀቅ
ጀመረ ። ይሁንና አሁን በያዝነው ዘመንም
እንዳንድ የብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ
አመለካከቶች የአዲሱ ብሉይ ኢኮኖሚ አስ
ተምህሮ ተከታዮች በሆኑ የቡርዧ ኢኮኖሚ
ስቶች ሥራ ውስጥ ሲንፀባረቁ ይታያሉ ።

ከብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በመነ
ሣትና በዚህ አስተምህሮ ውስጥ የነበሩትን
ድክመቶች በማረም ማርክስ ፣ ፖለቲካዊ ኢኮ
ኖሚን ለወዝአደሩ መደብ ጥቅም ሊያገለግል
የሚችልበት አኳኋን ሙሉ በሙሉ ሳይንሳዊ
ፈር እንዲከተል አድርጎታል ።

(ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን ፣ ግልብ ፖለቲካዊ
ኢኮኖሚን ይመለከቷል ።)

## ብላንኪ ፣ ሉዊ አጊዩስት
*(Blanqui, Louis Auguste)*

ከ1805 - 81 የኖረ ፣ ፈረንሳዊ ተምኔ
ታዊ ኮሚኒስት ነው ። ብላንኪ በ1830 እና
በ1848 በተካሔዱት አብዮቶች ተሳታፊ የነ
በረና ግማሽ ዕድሜውን በእስር ቤት ያሳ
ለፈ ፣ ሁለት ጊዜ የሞት ፍርድ የተፈረደበት
ሰው ነበር ።

የብላንኪ አመለካከት በተናክአታዊ ቁስ
አካልነት ፣ በኢአማኒነትና በተምኔታዊ ሶሻ
ሊዝም ላይ የተመሠረተ ነው ። አጠቃላይ
ፍልስፍናዊ አመለካከቱ ቁስአካላዊ ቢሆንም
ስለታሪካዊ ዕድገት የሰጠው ትንታኔ ሐሳ
ባዊ ነበር ።

ብላንኪ የነደፋቸው የሴራ ታክቲኮች
የተሳሳቱ ከመሆናቸው የተነሣ የሱ ተከታ
ዮች ለወሰዷቸው እርምጃዎች መከሸፍ ምክ
ንያት ሆነዋል ።

አንድ አብዮት በተሳካ ሁኔታ ሊከ
ናወን የሚችለው በአብዮታዊ ፓርቲ በሚ
መራ ሠርቶ አደር ሕዝብ ሲካሄድ መሆ
ኑን ብላንኪ ሊገነዘብ አልቻለም ። ብላንኪ
ባበረከታቸው አብዮታዊ ተግባራት በማር
ክሲዝም ሌኒኒዝም መሥራቾች ዘንድ ተደ
ናቂነትን ቢያተርፍም በነደፋቸው ታክቲኮች
ነቀፋ ደርሶበታል ። ዓቢይ ሥራውም “ክሪ
ቲክ ሶሲያል” በሚል ርዕስ በ1885 የወ
ጣው ጽሑፉ ነው ።

(ብላንኪዝምን ይመለከቷል ።)

## ብላንኪዝም
*(Blanquism)*

በአብዮታዊ ትግል ወቅት የብላንኪ
ንና የእሱን ተከታዮች የታክቲክ መርሆች
የሚከተልና የሴራ ታክቲክ አራማጆችን አመ
ለካከት የሚያንፀባርቅ በፈረንሳይ የተከሰተ
ፖለቲካዊ ፈለግ ነው ።

ያለውን አገዛዝ በድንገተኛ የትጥቅ
አመፅ ለመገርሰስ ኅቡእና ተዋረድ ያለው
ድርጅት መመሥረት አስፈላጊ እንደሆነ
ብላንኪስቶች ያምናሉ ። ለሰፊው ሕዝብ
የሚደረገውም ፕሮፓጋንዳ ኅቡኡን ድርጅት
የሚያጋልጥ ነው በማለት ያወግዛሉ ።
ተጨባጭ ሁኔታዎችን ችላ ከማለታቸውም
በላይ የአብዮታዊ ሁኔታዎችን መኖርና አለ
መኖር ከቁጥር አያስገቡም ። ለግባቸው መሳ

ካት የሚያደርጉት ትኩረት በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ሳይጠረጥር ድንገት ማጥቃት በሚለው ታክቲክ ላይ የተመረኮዘ ነው ።

የተራመደውን መደብ ሳይዝና ሕዝቡን ለአብዮታዊ እንቅስቃሴ ሳያነሣሣ በሴራና በፓርቲ ብቻ የትጥቅ አመፅ ማካሄድን ዓላማ አድርጐ የተነሣው ብላንኪዝም በሌሎችም ሀገሮች አብዮታዊ እንቅስቃሴ ላይ ተፅዕኖ የነበረው ሲሆን በተለይ በሩሲያ ለተከሰተው ናሮዲዝም ግፊት ሰጥቷል ።

በማቆጥቆጥ ላይ የነበረው ወዝአደራዊ እንቅስቃሴ ከቡርዧው ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ ራሱን ገና ባልለየበት ወቅት ብቅ ያለው የብላንኪስቶች ታክቲክ የሰፊው ወዝአደር እንቅስቃሴ እያደገ ሲመጣና ማርክሳዊ ፓርቲዎች እያበቡ ሲሄዱ ውድቅ እየሆነ መጥቷል ። ይሁንና ወዝአደራዊ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎች በእነዚህ ታክቲኮች አልፎ አልፎ ሲጠቀሙ ታይተዋል ።

(ብላንኪን ፣ ፑቮይዝምን ፣ ናሮዲዝምን ይመለከቷል ።)

## ብዝበዛ

*(Exploitation)*

የምርት መገልገያዎች በግል በተያዙበት በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የምርት መገልገያዎች ባለቤት የሆነው መደብ የሠራተኛውን ሕዝብ የሥራ ውጤት የሚገፍበት ሂደት ብዝበዛ ይባላል ። በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት የባሪያው አሳዳሪ መደብ የባሪያውን ፣ በፊውዳሉ ሥርዓት ፊውዳሉ የገባሩን ፣ በካፒታሊስት ሥርዓት ካፒታሊስቱ የወዝአደሩን የሥራ ፍሬ ይበዘብዛሉ ።

በባሪያውና በገባሩ ላይ የሚካሄደው ብዝበዛ ገዥ መደቦች በሃይማኖትና በፖለቲካ ሽፋን ለማድበስበስ ቢሞክሩም ብዝበዛው በግልጽ የሚታይ ነው ። በካፒታሊስቱ ሥርዓት ግን ይህ የሃይማኖትና የፖለቲካ ሽፋን ተወግዶ በምትኩ በወዝአደሩ ላይ የሚፈጸመው ብዝበዛ በሥራ ኃይል ሽያጭና ግዥ በነፃ ገበያ ሽፋን በምንዳ ክፍያ መልክ የቀረበ ቢሆንም ብዝበዛው የከፋ ነው ።

የመደብ ብዝበዛ ሊጠፋ የሚችለው በኢኮኖሚው መስክ የግል ሀብትን በማጥፋት ፣ የምርት መገልገያዎችን ወደ ወል ይዞታ በመለወጥ ፣ የምርት ኃይሎችን በማዳበር በፖለቲካው መስክ በሠራተኛው መደብ የበላይ ገዥነት አማካይነት የሶሻሊስት ብሎም የኮሚኒስት ኅብረተሰብ ለመገንባት ሲቻል ነው ።

(ተረፈ እሴትን ፣ ወዝአደርን ይመለከቷል ።

## ብያኔ

*(Judgement)*

በነባራዊነት ትክክል ወይም ስህተት ሊሆን የሚችል ስለነገሮች የምንሰጠውን ማረጋገጫ የሚገልጽ ሐሳብ ነው ። ለምሳሌ አካባዊ ነገሮች በሙሉ ስፋት አላቸው ፤ ሰው የተፈጥሮ ዕድገት ውጤት ነው ፤ ሐሳብ እራሱን የቻለ ኑባሬ ነው ። ከነዚህ ከተለያዩ ብያኔዎች ውስጥ የመጀመሪያውና ሁለተኛው ትክክል ሲሆኑ የመጨረሻው ግን ስህተት ነው ። ትክክል ወይም ስህተት ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ ሊነገርባቸው የማይቻሉ ሐሳቦች ለምሳሌ ጥያቄ ፣ ትእዛዝ ፣ ወዘተ.. ብያኔ አይደሉም ። ብያኔዎች ቀላል ወይም ውስብስብ ሊሆኑ ይችላሉ ። ውስብስብ ብያኔዎች ቀላል ብያኔዎችን የሚያቅፉ ናቸው ። ሳይንሳዊ ሕጎች የብያኔ ውጤት ሲሆኑ ሙሉ ማረጋገጫ ያገኙ ናቸው ።

ብያኔ በዕውቀት ሂደት ውስጥ ካለው ከፍተኛ ሚና የተነሣ በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ አከራካሪ የሆኑ ፍችዎች ተሰጥተውታል ። በሐሳባውያን አመለካከት የውጭው ዓለም ዕውቀት የሚገኘው በብያኔ መሆኑ የሚያስረዳው ብያኔ ሰጪው ማለትም ሐሳብ የበላይ ገዥ እንደሆነ ነው ። የቁስአካላዊ ሥርዓቶች ትክክለኛ ምንነታቸው የሚገለጸው በሐሳብ ብያኔ በመሆኑ የዕውቀት ምንጭ ሐሳብ ነው ከሚለው ድምዳሜ ላይም ደርሰዋል ። በዚህ አባባል የተዘነጋ ነገር ቢኖር ብያኔ ከመሰጠቱ በፊት መረጃዎችና ልምዶች መኖር እንዳለባቸው ነው ። ከልባዊ በፊት ብያኔ መስጠት አለመቻሉ የሚያስረዳው ሕውስታዊ መረጃዎች የብያኔ መነሻ መሆናቸውንና ብያኔውም የሚያንፀባርቀው ነባራዊ እውነታን መሆኑን ነው ።

(ዕውቀትን ፣ ነፀብራቅን ይመለከቷል ።)

## ብይትውርና
*(Alienation)*

በተወሰነ ታሪካዊ ሁኔታ ውስጥ ሰዎች በራሳቸው እንቅስቃሴና ጥረት ያገኟቸውን ውጤቶችና (የሥራ ውጤቶች ፣ ማኅበራዊ ግንኙነቶች ወዘተ...) ያዳበሯቸውን ጠባዮችና ችሎታዎች ከነሱ በላይና ውጭ ከሆነ ኃይል የሚመነጩና የተሰጡ አድርገው መተርጐማቸውን የሚገልጽ ጽንሰ ሐሳብ ነው ። በተጨማሪም ጽንሰ ሐሳቡ የአንዳንድ ክስተቶችና ግንኙነቶችን ከደንብ ውጭ መሆንና እንዲሁም ሰዎች በሐሳባቸው ውስጥ የእርስ በርስ ግንኙነታቸውን በተዛባ ሁኔታ ማንጸባረቃቸውን ይገልጻል ።

ጽንሰ ሐሳቡ የግል ንብረትና ጥቅም የበላይ በሆነበት ሥርዓት ውስጥ ሰዎች በራሳቸው እንቅስቃሴ ላፈሯቸው ነገሮች እንግዳ መሆንን ፣ በነሱም መገዛትንና የውጤቱ ተካፋይ አለመሆንን ለመግለጽ የተነደፈ ሲሆን ሐሳባውያን ለጽንሰ ሐሳቡ ትክክለኛውን ፍች አልሰጡትም ነበር ። በተለይም ሄግል ለፍጹማዊ ሐሳብ ፍች በመስጠት ነባራዊውን ዓለም ባይተዋር የሆነ መንፈስ አድርጐ በመውሰድ የዕድገት ዓላማ ይህን ሁኔታ በዕውቀት አማካይነት ማረም መሆኑን ተናግሯል ። ማለትም ሐሳብ ወደ ተፈጥሮ ሲቀየር ለራሱ ባይተዋር ስለሚሆን ምንነቱን መልሶ የሚጐናፀፈው ስለ ራሱ በሚያገኘው ዕውቀት ነው ። ይህን ዕውቀት የሚቀርፁት ሰዎች ግን በተግባር ወይም በቁሳዊነታቸው ከብይትውርና አይላቀቁም ። ፎየርባኽ በበኩሉ ሃይማኖት የሰው ምንነት ፣ ሐሳባዊነትም የአመክንዮ ብይትውርናዎች ናቸው ሲል ተናግሯል ። እሱም ቢሆን ብይትውርናን ኅሊናዊ ሁኔታ ብቻ አድርጐ በመተርጐም የሚወገድበትን ተግባራዊ መንገድ ሊቀይስ አልቻለም ።

ማርክስ ስለብይትውርና ባደረገው ትንተና የኅብረተሰብ የዕድገት ሂደት የሚያስከትለው ቅራኔ ውጤት መሆኑን አስረድቷል ። ብይትውርና የሚመጣው ከግል ንብረትና ከተቃራኒ የሥራ ክፍፍል መሆኑንም በግልጽ አሳይቷል ። የሥራ ክፍፍል ሰዎችን በቡድንና በመደብ የሚከፋፍል ፣ በጥቅምም አኳያ የሚያጣላና አንዱን ሰው የሌላው ጠላት የሚያደርግ በመሆኑ ይህ ሰው ከሰው የመጋጨቱ ሁኔታ ሰው ለራሱ እንግዳ እንዲሆን ያደርገዋል ። በዚህም የተነሣ የሚሠራው ነገርም ሆነ የሚያገኘው ውጤት ከሰው ጋር ያለው ማኅበራዊ ግንኙነት ጭምር ከሱ ውጭ በሆነ ኃይል የሚደነገግ ይመስለዋል ። የወዝአደሩ መደብ አምራች ካልሆነው ነገር ግን የምርት መሣሪያ ባለቤት ከሆነው ከቡርዧዚው ጋር ያለው መተሳሰር ፣ ወዝአደሩ ከሥራው ጋርና ከሥራው ውጤት ጋር ያለው ግንኙነት ፣ የማኅበራዊ ግንኙነት ቁሳዊ ጠባይ መያዝ ፣ በኅብረተሰብ ውስጥ ኢሰብአዊ ኃይሎች የበላይ መሆን ፣ በአምራቹ ላይ የሚደርሰው አካላዊና ግብረገባዊ ውድቀት ወዘተ... በሥራ ላይ የሚደርሱ የተለያዩ የብይትውርና መልኮች መሆናቸውን ማርክስ አስረድቷል ። በተጨማሪም የመንግሥት የበላይነትና የሰዎች በሃይማኖታዊና በሐሳባዊ አስተሳሰቦች መገዛት የሥራ ብይትውርና ውጤት መሆናቸውን አሳይቷል ። ሰዎችን የሚገዙ ሕጐች ፣ አስተሳሰቦችና ፖለቲካዊ ሥርዓቶች ከሰው የመነጩ ቢሆኑም በሰዎች የእርስ በእርስ ቅራኔ የተነሣ እነዚህ ነገሮች ከነሱ ቁጥጥር ውጭ እንዴት እንደሚሆኑ አብራርቷል ።

ማርክስ የሥራ ብይትውርና ለሁሉ ዓይነት ብይትውርና (ርዕዮተዓለማዊ ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ) መሠረት መሆኑን በመገንዘቡ ነው በተግባር የሚወገድበትን መንገድ ለመቀየስ የቻለው ። የግል ንብረት ተወግዶ በሶሻሊስት ሥርዓት መተካት ሰውን ከሰው ጋር የሚያስታርቅ በመሆኑ ሰው የራሱ ሥራ ፍሬ ባለቤት እየሆነ ሲመጣ ከብይትውርናም ነፃ ይሆናል ።

## ብድር ካፒታል (የ—)
(*Loan Capital*)

ወለድ የሚያስገኝ የገንዘብ ካፒታል የብድር ካፒታል ይባላል ። በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የብድር ካፒታል አቅራቢዎች የገንዘብ ካፒታሊስቶች ሲሆኑ ፣ የብድር ካፒታል ተቀባዮች ደግሞ የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶችና የንግድ ካፒታሊስቶች ናቸው ። ብድሩም የአጭርና የረዥም ጊዜ ሊሆን ይችላል ።

የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ዕድገት የሚያሳይበትና የተስፋፋ እርባታም የሚከናወንበት ሁኔታ ሲፈጠር ለብድር ካፒታል ተፈላጊነት አመች ሁኔታ ይፈጠራል ። በዚህን ጊዜ ለጊዜው በሥራ ላይ ያልዋለ የገንዘብ ካፒታል ብድር ለሚፈልጉ ካፒታሊስቶች ይተላለፋል ። ይህ የሚሆነውም በጊዜው ካላቸው የፋይናንስ ዓቅም በላይ የምርትና የንግድ እንቅስቃሴዎቻቸውን ለመጀመርም ሆነ ለማስፋፋት ፍላጐት ያላቸው የኢንዱስትሪና የንግድ ካፒታሊስቶች ስለሚኖሩ ነው ።

ለጊዜው ሥራ ላይ ያልዋለ የገንዘብ ካፒታል የሚገኘውም በካፒታሊስት እርባታ ሂደት ውስጥ ለነባር ካፒታል ታስቦ በየጊዜው ከሚቀመጠው ገንዘብ ፣ አስፈላጊ ለሆኑት ለተዘዋዋሪ ካፒታል አካሎች (ለምሳሌ አላቂ ዕቃዎች ፣ ነዳጅ ወዘተ...) መግዣ እንዲሆን ከሚመደበው ተቀማጭ ገንዘብ ፣ለምንዳ ወጪ ሆኖ ምንዳው እስከሚከፈልበት ጊዜ ተቀማጭ ከሆነው ገንዘብ ፣ ለካፒታል ክምችት ተብሎ ከተያዘውና የተስፋፋ የካፒታል እርባታ እስከሚጀመርበት ጊዜ ድረስ ተቀማጭ ከሚሆነው ገንዘብ ላይ ነው ። በተጨማሪም በባንክ ውስጥ የሚገኝ የግለሰቦችና የሌሎች ድርጅቶች ተቀማጭ ገንዘብ በካፒታሊስቱ ሥርዓት እንደብድር ካፒታል ያገለግላል ። ይህንን ለጊዜው ሥራ ላይ ያልዋለ ገንዘብ በብድር ካፒታል መልክ ለካፒታሊስቶች ማበደር ወለድ ያስገኛል ። ገንዘቡን የተበደሩት ካፒታሊስቶች ሠራተኛውን በመበዝበዝ ተረፈ እሴት ያገኙበታል ፤ ካገኙት ተረፈ እሴት ውስጥም የተወሰነውን መጠን በወለድ መልክ ለብድር ካፒታሊስቱ ከዋናው ጋር ይመልሱለታል ።

በሞኖፖል ካፒታሊዝም የብድር ካፒታል በጥቂት ትላልቅ የሞኖፖል ባንኮችና በሌሎች ዓለም አቀፍ የብድርና የፋይናንስ ድርጅቶች ቁጥጥር ሥር ይሆናል ። አብዛኛው የብድር ካፒታል በጥቅም ላይ የሚውለው በሞኖፖሊስቶች ነው ።

(ባንክን ፣ የወለድ መጣኔን ፣ የንግድ ካፒታልን ይመለከቷል ።)

## ቦልሼቪክ
(*Bolshevik*)

በሁለተኛው የሩሲያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ሌበር ፓርቲ ጉባኤ 1903 በማዕከላዊ አካሎች ምርጫ ላይ የአብዛኛውን የድጋፍ ድምፅ በማግኘት የፖለቲካ መሥመሩ በአሸናፊነት የወጣውና በሌኒን የተመራው አብዮታዊ ክንፍ ቦልሼቪክ ይባላል ።

በቀድሞዋ ሩሲያ አንድ ጠንካራ ብሔራዊ ማርክሳዊ ፓርቲ ለመመሥረት የመጀመሪያው ሙከራ የተደረገው በ1898 ሌኒን ሳይቤሪያ ውስጥ በእሥር ላይ በነበረበት ወቅት በሚንስክ ከተማ ዘጠኝ የፖለቲካ ማኅበራት ተወካዮች በተገኙበት አነስተኛ ጉባኤ ነበር ። ይህ ሦስት ቀናት የፈጀ ጉባኤ ማዕከላዊ ኮሚቴ ከመምረጡም በላይ አንድ የፓርቲ ጋዜጣ ለማውጣትም ወስኖ ነበር ። ሆኖም በወቅቱ ጉባኤው የሩሲያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ሌበር ፓርቲን መመሥረት ቢያሳውቅም በጊዜው የነበረው የፈላጭ ቆራጩ የቄሳር ጭቆናና አፈና እጅግ የከፋ ስለነበር የማዕከላዊ ኮሚቴው አባላት ሁሉ ተይዘው ታስረዋል ። ከዚህም በላይ በወቅቱ በፓርቲው የተቀነባበረ ፕሮግራምና ደንብ እንዲሁም ትክክለኛ የትግል ስትራቴጂና ታክቲክ አልነበረውም ። ርዕዮተዓለማዊም ሆነ ድርጅታዊ አንድነቱ የላላና ጠንካራ አመራርም የጎደለው ነበር ።

የቦልሼቪክ ፓርቲን የመሠረተው ጉባኤ ለንደን ላይ ሲካሄድ ከ1901—03ቱ የኢንዱስትሪ ቀውስ የተነሣ በከተሞች ሠራተኛውና ተማሪው ፣ በገጠሩም ገበሬው በከፍተኛ እንቅስቃሴ ላይ ነበር ። ሌኒንም ለዚህ ፓርቲ መመሥረት ጥርጊያ ጐዳናውን ሲያመቻች ቆይቷል ። በተለይም የ“ኢስክራ” ጋዜጣና (1900—03) “ምን መደረግ አለበት” የሚሰው ታዋቂ ጽሑፉ በተለያዩ ቡድኖች ውስጥ ይሳተፉ የነበሩትን ማርክሳውያን በማሰባሰብ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

በለንደን ጉባኤ ላይ ሃያ ስድስት የተለያዩ ቡድኖችን የሚወክሉ አርባ ሦስት መልእክተኞች የተገኙ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የኢስክራ ፕሮግራም ደጋፊዎች ሃያ አራት ብቻ ነበሩ ። የነሌኒን ተቃዋሚዎች በፕሮግራሙ

ውስጥ የተነሡትን የወዝአደሩን የበላይ ገዥነት ፣ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ፣ የገበሬውን ጥያቄና የመሳሰሉትን ዓበይት ጉዳዮች በተመለከተ የቀረቡትን መሠረታዊ ሐሳቦች አልተቀበሉም ። በሌኒን የቀረበውን የፓርቲውን ደንብም በሚመለከት በነማርቶቭ የሚመራው የሜንሼቪክ ቡድን የፓርቲ አባላትን ተግባራዊ ተሳትፎ ወደጐን በመተው ፕሮግራሙን የተቀበለና በገንዘብ የሚረዳ ሁሉ አባል መሆን አለበት በማለት ደካማና ዲሲፕሊን ለሌለው አድርባይ ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ ቆሟል ። በመጨረሻ ግን ማዕከላዊ ኮሚቴው ሲመሠረትና የኢስክራ አዘጋጆች ሲመረጡ የነሌኒን መሥመር ደጋፊዎች አብዛኛዎቹ በመሆናቸው ቦልሼቪክ (ብዙሃን) ሲባሉ የነርሱን አቋም የተቃወሙት ደግሞ ሜንሼቪክ (ንዑሳን) ተብለዋል ።

የቦልሼቪክ ቡድን መጀመሪያ የሩስያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ሌበር ፓርቲ (ቦልሼቪክ) ፣ ከዚያም የሩሲያ ኮሚኒስቶች ፓርቲ (ቦልሼቪክ) ፣ ቀጥሎም የመላ ኅብረት የቦልሼቪኮች ኮሚኒስት ፓርቲ በመባል ሲጠራ ቆይቶ በ1952 ዛሬ የሚጠራበትን የሶቭዬት ኅብረት ኮሚኒስት ፓርቲ የሚለውን ስያሜ አግኝቷል ። በአሁኑ ጊዜ በየትም ቦታ ቦልሼቪክ የሚለው ስም የቦልሼቪኮችን ጠንካራ አብዮታዊ አቋም ፣ የትግል ወኔና ስራ ልምድ የሚያመለክት ነው ።

(ሜንሼቪክን ፣ ሌኒኒዝምን ይመለከቷል።)

## ቦም - ባዌርክ ፣ አይገን
*(Bohm-Bawerk, Eugen)*

ከ1851—1914 የኖረ በቪየና ፣ በሃይድልበርግ ፣ በላይፕሲግና በዬና ዩኒቨርሲቲዎች እየተዘዋወረ ከተማረ በኋላ ፕሮፌሰርና የመንግሥት ባለሥልጣን በመሆን የሠራ ኦስትሪያዊ ኢኮኖሚስት ነው ። በቪየናና በኢንዝብሩክ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ፕሮፌሰር በመሆን ከመሥራቱም በላይ የኦስትሪያ የገንዘብ ሚኒስትር በመሆን በተለያዩ ጊዜያት ሠርቷል ። ኋላም የኦስትሪያ የሳይንስ አካዳሚ ፕሬዝዳንት ሆኖ አገልግሏል ።

ቦም-ባዌርክ በቡርዧ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ ውስጥ " የኦስትሪያ አስተምህሮ" የተባለውን ከመሠረቱት ኦስትሪያዊ ኢኮኖሚስቶች መካከል አንዱ ነው ። ሁለት ሌሎች የዚህ አስተምህሮ መሥራቾች ካርል ሜንገር (1840—1921) እና ፍሬደሪሽ ፎን ቪዘር (1851—1926) ናቸው ። እነዚህ ቡርዧ ኢኮኖሚስቶች የእሴት መሠረት ሥራ ሳይሆን እርካታ ነው በተሰኘ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተውን ኅሊናዊ የእሴት ንድፈ ሐሳብ በመቀመር ማርክሳዊውን የተረፈ እሴት ንድፈ ሐሳብ ለመፈታተን ሙከራ ካደረጉት መካከል ዋንኞቹ ናቸው ።

ቦም-ባዌርክ በተለይ ስለ ካፒታልና ስለወለድ በርካታ መጽሐፎችን የደረሰ ሲሆን ዋና ዓላማውም ከፍተኛ ተቀባይነት በማግኘት ላይ የነበረውን ማርክሲዝምን ለመግታት እንደነበር ይነገራል ። እንደ ቦምባዌርክ አስተሳሰብ ወደፊት ይገኛል ተብሎ ከሚጠታመን ሸቀጥ ወይንም ነገር ይልቅ አሁን በእጅ ላይ ላለ ሸቀጥ ወይንም ነገር የበለጠ ግምት እንዲሰጡ ሰዎች ልቡናቸው ይመራቸዋል ። ስለሆነም የአንድ ሸቀጥ ወይንም ነገር ባለቤት የሆነ ሰው ይህ ሸቀጥ ወይንም ነገር አሁን ሲሰጠው የሚችለውን እርካታ ለወደፊት ሲል መሥዋዕት ካደረገ ጊዜው ሲደርስ ተጨማሪ ነገር ወይንም ካሣ ማግኘት ይኖርበታል ። በዚሁ መሠረት ገንዘቡ ለምርትም ሆነ ለሌላ ተግባር እንዲውል የፈቀደ መሥዋዕትነት ከፍሏልና ወለድ ይገባዋል በማለት ወለድ ሠራተኛውን ከመበዝበዝ የሚገኝ ገቢ አለመሆኑን ለማሳመን ሙከራ አድርጓል ።

ቦም-ባዌርክ ፀረማርክሳዊ አቋሙን በግልጽና በቀጥታ የገለጸበት ጽሑፉ ፣ "ካርል ማርክስ ኤንድ ዘ ክሎዝ ኦቭ ሂዝ ሲስተም" የተሰኘው በ1898 የታተመው ነው ። በዚህ ጽሑፉ ውስጥ ማርክሲዝም በቅርቡ ያበቃለታል ፣ ለወደፊትም ዕድል የለውም በማለት የተናገረውን ታሪክ ውድቅ አድርጎታል ።

# ተ

## ተለዋዋጭ ካፒታል
*(Variable Capital)*

ተለዋዋጭ ካፒታል የሚባለው ቡርዧዚው የሥራ ኃይል ለመግዛት የሚያወጣው የካፒታል ክፍል ወይም ቡርዧዚው ለወዝአደሩ የሚከፍለው ምንዳ ነው ማለት ነው ። ይህን የካፒታል ክፍል ተለዋዋጭ የሚያሰኘውና ዓይነተኛም የሚያደርገው በምርት ክንዋኔ ውስጥ ባልተከፈለበት የወዝአደሩ የሥራ ጊዜ በሚፈጠረው ተረፈ እሴት በመጠን የሚያድግ ወይንም የሚለወጥ መሆኑ ነው ።

ይህም የሚሆንበት ዋናው ምክንያት በምርት እንቅስቃሴ ውስጥ ከራሱ እሴት በላይ ተረፈ እሴት መፍጠር የሚችለው የሰው የሥራ ኃይል ብቻ በመሆኑ ነው ። ወዝአደሩ በሚያፈሰሰው የሥራ ኃይል ከሚፈጥረው አዲስ እሴት ውስጥ ከራሱ የሥራ ኃይል እሴት ጋር የሚመጣጠነው በምንዳ መልክ ሲከፈለው ፣ ከራሱ የሥራ ኃይል እሴት በላይ የሆነው ተረፈ እሴት ግን በትርፍ መልክ ወደቡርዧዚው ኪስ የሚገባ ነው ። የሥራ ኃይል ከላይ እንደተጠቀሰው በምርት ክንዋኔ ወቅት በምርት ማከናወኛ መሣሪያዎች ውስጥ የተጠናቀረውን እሴት አዲስ ወደሚመረተው ሸቀጥ ማስተላለፍ ብቻ ሳይሆን ተጨማሪ እሴትም የሚፈጥር ሸቀጥ በመሆኑ በመጠን የሚለወጠው ካፒታል ለሥራ ኃይል መግዣ የወጣው የካፒታል ክፍል ብቻ ነው ።

ካፒታልን ለመጀመሪያ ጊዜ በቋሚና በተለዋዋጭ ክፍሉ የተመለከተው ካርል ማርክስ ሲሆን በዚህም ዓይነት አከፋፈል ተረፈ እሴት የሚፈጠረው በሁሉም የካፒታል ክፍሎች ሳይሆን በተለዋዋጭ ካፒታል ብቻ መሆኑን በማሳየት በቡርዧዚውና በወዝአደሩ መካከል በብዝበዛ ላይ የተመሠረተውን ግንኙነት በግልጽ አሳይቷል ።

(ተረፈ እሴትን ፣ ቋሚ ካፒታልን ይመለከቷል ።)

## ተማልሎአዊነት
*(Mysticism)*

ተማለለ ከሚለው ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙ ተማጸና ማለት ነው ።

ተማልሎአዊነት በፍልስፍና አገባቡ ሃይማኖታዊና ሐሳባዊ የሆነ ንጽረተ ዓለምና አስተሳሰብ ነው ። ይህ ፍልስፍና ከጥንታዊ የሃይማኖት ማኅበረሰቦች ሥርዓተ አምልኮ የመጣ ነው ። የዚህ አስተሳሰብ ዓይነተኛ ባሕርይ ጸሎት በሚደረግበትና መሥዋዕት በሚቀርብበት ወቅት ሰው ከእግዚአብሔር ወይም ከአንድ ከሁሉም በላይ ከሆነ ኃይል ጋር ሊገናኝ ይችላል የሚለው ሐሳብ ነው ። እንደ ኮንፊሺያኒዝምና እንደ አፍላጦናዊነት የመሳሰሉት ጥንታዊ የሃይማኖት ፍልስፍና አስተምህሮች ተማልሎአዊነትን የሚያንፀባርቁ ናቸው ።

ሰው ዓለምን ለመግለጽ በሚያደርገው ሙከራው አንድ ነጥብ ላይ ሲደርስ ምክኑያዊ የዕውቀት ችሎታው ይገታል ። ከዚህ በኋላ ግን ስለዓለም ምንም ለማወቅ ስለማይችል ፣ ማለትም ነገሮች ሁሉ ምሥጢር ስለሚሆኑበት ከምክኑያዊ ዕውቀቱና ጥረቱ ተገትቶ በመንፈስና በራዕይ ዲበኩሉ ከሆነው ኃይል ጋር ለመገናኘት ይሞክራል የሚል አስተሳሰብ ነው ። ስለሆነም ከሃይማኖት ጋር የሚዛመድና የኢታዋቂነት ባሕርይ ያለው ነው ።

(ሃይማኖትን ፣ እምነትን ፣ ሐሳባዊነትን ፣ ኢታዋቂነትን ይመለከቷል ።)

## ተምህሮነት
*(Scholasticism)*

ተምህር ማለት በቃል ፣ በጽሑፍ ማጥናት መቀጸል ማለት ሲሆን ተምህሮነትም ከዚህ የወጣ ነው ።

ተምህሮነት በመካከለኛው ዘመን ለሃይማኖታዊ ንጽረተ ዓለም ንድፈሐሳባዊ መሠረት ለመስጠት ይጥር ለነበረው ሐሳባዊ ፍልስፍና የተሰጠ ስያሜ ነው ። ዋንኛ ዓላማውም የአፍላጦንንና የአርስጣጣሊስን ፍልስፍናዎች

ከሥነ መለኮት ጋር በማጣጣምና በማዋሀድ ለሃይማኖት ምክኑያዊ መሠረት መስጠት ነው። ሆኖም የሁለንታዊን ምንነት አስመልክቶ በእፍላጦንና በአርስጣጣሊስ መካከል የነበረው አለመግባባት በተምህሮትም ውስጥ በመንፀባረቁ መከፋፈልን አስከትሏል ። ተምህሮነት በሦስት ዘመኖች የተከፈለ ሲሆን ከ9ኛው እስከ 13ኛው ምዕት ዓመት የነበረው ተምህሮነት የመጀመሪያው ነበር ፥ ይህም ዘመን በአዲሱ አፍላጦናዊነት የበላይነት ይመራ ነበር ። ከ14ኛው እስከ 15ኛው ምዕት ዓመት ደግሞ የብሉይ ዘመን ሲሆን ይህም ዘመን በአርስጣጣሊሳውያን ክርስቲያኖች ይመራ ነበር ። ይህንንም ፍልስፍና የቀመረው ቶማስ አኩዊናስ ነበር ። ከ15ኛው እስከ 16ኛው ምዕት ዓመት የነበረው ዘመን ኋላ መጥ ተምህሮነት ሲሆን በዚህም ወቅት ዋና ጉዳይ የነበረው በካቶሊክና በፕሮቴስታንት ሥነ መለኮታውያን ይካሄድ የነበረው ክርክር ነው ። በ19ኛው ምዕት ዓመት የነበረው አዲስ ተምህሮነት ሲሆን የካቶሊክ ፍልስፍናን የተለያዩ አመለካከቶች ( ቶሚዝምን ፥ አውገስጢኖሳዊነትን ፥ ፍራንሲስካዊነትን ወዘተ...) ለማዋሀድ ጥረት የተደረገበት ነው ። ፍልስፍናን ተጨባጭነት ከሌለው ከሥነ መለኮት ጋር ለማጣጣም የተደረገው ጥረት አውጠንጥኖትን ፥ ጭቅጭቅን ወዘተ ... ከማስከተሉ በቀር ሌላ ውጤት ሊያስገኝ ባለመቻሉ ተምህሮነት እያደር የቃላት ሰንጠቃ ፥ ጭቅጭቅ ፥ ንትርክ ፥ ኢተግባራዊ ዕውቀት የሚል ትርጉም እየያዘ መጥቷል ።

(ንጽረተ ዓለምን ፤ ሃይማኖትን ፤ ቶሚዝምን ይመለከቷል ።)

## ተምኔታዊ ሶሻሊዝም
*(Utopian Socialism)*

በተለያዩ ጊዜያት የወል ንብረትን አስፈላጊነት ፥ ለሁሉም የኅብረተሰብ አባል የሥራና የምርት ውጤቶችን በእኩል የማከፋፈልን ግዴታ ያስተማሩ ነገር ግን መርሆቻቸው ምናባዊ ከመሆናቸው የተነሣ በተግባር ሊተረጎሙ ያልቻሉ አስተምህሮችን የሚያጠቃልል የወል መጠሪያ ነው ። ተምኔታዊ ሶሻሊስቶች የግል ንብረትን በማውገዛቸው ፥ የመጪውን ኅብረተሰብ አምሳላዊ ቅርፅ በመንደፋቸው ፥ የወል ንብረትን አስፈላጊነት በንድፈ ሐሳባዊ ግንዛቤ በመደገፋቸውና ሌላም ብዙ ጠቃሚ ሐሳቦችን በመሰንዘራቸው የማርክሲዝም አንዱ ምንጭ ሊሆኑ ችለዋል ። ከተምኔታዊ ሶሻሊዝም አራማጆች ውስጥ በይበልጥ የታወቁቱ ቶማስ ሞር ፥ ቶማስ ካምፓኔላ ፥ ባበፍ ፥ ሰንሲሞን ፥ ፉርየና ሮበርት አውን ናቸው ።

የተምኔታዊ ሶሻሊዝም አመለካከት በጥንት የግሪክና የሮማ ምሁሮች የተሰነዘረ ቢሆንም ዕድገት አግኝቶ እራሱን ለመቻልና ተከታዮች ለማፍራት የበቃው በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ነው ። የካፒታሊዝም ቅራኔ እያደገ መምጣት ማለትም በውስጡ ተቃራኒ የሆኑ የሀብት ክምችት ማደግና የድህነት መባባስ ፥ ቅራኔውንም የቡርዧ የጥገና ለውጥ ሊፈታው አለመቻሉ ተምኔታዊ ሶሻሊዝም የግል ንብረትን ለማውገዝና የካፒታሊዝምን አስከፊ ሁኔታ ለማጋለጥ አመች ሁኔታ ፈጥሯል ።

ተምኔታዊ ሶሻሊዝም የተለያዩ አዝማሚያዎችን ያቀፈ ቢሆንም በመሠረታዊ የጋራ አመለካከቶች ላይ የተገነባ ነው ። እነሱም ፥ የካፒታሊዝም አስከፊ ገጽታዎችን በማሳየት በሱ ፋንታ በእኩልነትና በወንድማማችነት ላይ የተመሠረተ ኅብረተሰብን መገንባት ፥ የብዝበዛው መንሥኤ የግል ይዞታ ንብረት መሆኑን በማስረዳት የወል ንብረትን አስፈላጊነት ማሳመን ፥ በሰብአዊ ፍላጎት በመነሣሣት የሰውን ሙሉ ዕድገትና ደስታ መሻትና ይህንንም እውን ለማድረግ የኅብረተሰቡ መለወጥ ወሳኝ መሆኑን ማስገንዘብ ፥ በገጠርና በከተማ ፥ በአእምሮና በጉልበት ሥራ መካከል ያለውን ልዩነት በማጥፋት ሁሉም እንዲሠራና ከፍፍልም በሥራና በፍላጎት መጠን እንዲሆን ማድረግ ፥ ለሰው ጠቃሚ እንዲሆን ኅብረተሰቡን ንቁና ግባዊ በሆነ መንገድ መምራት ማስፈለጉን ማስተማር ናቸው።

ተምኔታዊ ሶሻሊዝም የካፒታሊዝምን ውድቀት ቢፈልግም የትኛው ኃይል ይጥለዋል ? በምን ሁኔታ ይወድቃል ! በምንስ ይተካል ? ለሚሉት ጥያቄዎች ግልጽና ተግባራዊ የሆነ መልስ አላዘጋጀም ። በተለይም የካፒታሊዝምን መጥፎ ጎን አሳየ እንጂ በጎ ጎኑንና ታሪካዊ ሚናውን አልተረዳም ። እንዲያውም የሰውን እኩልነት ሊመሠርት የፈለገው በሀብት ላይ ሳይሆን ወደ ኋላ በመመለስ ለሁሉም እኩል ድህነትን በመሻት ነው። ካፒ

ታሊዝም በፈጠረው ከፍተኛ የማምረት ችሎታ በመጠቀም ምርትን በይበልጥ ለማሳደግ አስመሻት የሚያንፀባርቀው ተምኔታዊ ሶሻሊዝም የኅብረተሰብን ነባራዊ የዕድገት ሕግጋት አለመገንዘቡን ነው ።

ተምኔታዊ ሶሻሊስቶች ኅብረተሰቡን ሊለውጥ የሚችለውን ቁሳዊ ኃይል ባለማጤናቸው ከመደብ ትግልና ከአብዮት ግንዛቤ ላይ ሊደርሱ አልቻሉም ። እንዲያውም ብዙዎቹ እራሳቸውን ከኅብረተሰቡ በማግለል ከተጨባጭ ሁኔታ ውጭ አዲሱን ማኅበረሰብ ለመመሥረት ሞክረዋል። ይህ የሚያስረዳው ለውጥ የመደብ ትግል ውጤት ሳይሆን ከአመለካከት መቀየር ፣ ከትምህርትና ከአብርሆት የሚገኝ ይመስላቸው እንደነበር ነው ።

የተምኔታዊ ሶሻሊዝም ጥሬነት የሚያንፀባርቀው የማኅበራዊ ግንኙነቶችን አስመኅልበትና በተለይም የወዝአደሩ መደብ ገና በማደግ ላይ መሆኑንና የራሱን ታሪካዊ ሚና አለመገንዘቡን ነው ። የካፒታሊዝም ማደግ የወዝአደሩን ቁጥር እየጨመረ እንዲሄድና እንዲደራጅ ማድረጉ ይህን ሥርዓት የሚተካውና ኃያሉ መደብ የወዝአደሩ መደብ መሆኑን አረጋግጧል ። በመሆኑም የታሪካዊ ቁስአካልነትን ንድፈ ሐሳብ በመቀመርና ለበላይ ገዥነቱ የወዝአደሩ መደብ መደራጀትና የራሱን ርዕዮተዓለም ማቀናጀት ወሳኝ መሆኑን በማስተማር ማርክስና ኤንግልስ ሶሻሊዝምን ከተምኔታዊነት ወደ ሳይንሳዊነት እንዲያድግ አድርገውታል ።

(ታሪካዊ ቁስአካልነትን ፣ የወዝአደሩ የበላይ ገዥነትን ይመለከቷል ።)

## ተስፋፋ የእሴት መልክ (የ—)

(*Extended form of Value*)

ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል እየተስፋፋ ሲሄድ የሸቀጥ ምርትና ልውውጥ እየዳበረና እያደገ ይመጣል ። በተለያዩ የሥራ ዘርፎች የተሰማሩ አምራቾች የምርት ውጤቶቻቸውን በአጋጣሚ መሆኑ ቀርቶ ቀስ በቀስ በቋሚነት መለዋወጥ ይጀምራሉ ። በዚህ የሸቀጥ ልውውጥ ደረጃም አንድ የተወሰነ ሸቀጥ በአካባቢው በብዛት በመመረቱ ወይም በመገኘቱ ታዋቂነቱና ተቀባይነቱ እየጐላ ይመጣል ። በዚህ ጊዜ ይህ ሸቀጥ በዝቅተኛ የልውውጥ ደረጃ እንደታየው በሌላ አንድ ሸቀጥ ተመጣጣኝ የሆነ የእሴት መልክ ብቻ መገለጹ ቀርቶ በዛ ያሉ ሸቀጦችን ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ መለወጥ ይጀምራል ። ለምሳሌ ሸቀጡን በግ ብንለው አንድ በግ አራት ቁና ገብስ ወይም ሁለት መጥረቢያ ወይም አንድ ጋቢ ወይም ሦስት እንሥራ ይለውጣል ብንል ፣ የበጉ እሴት በእነዚህ ሸቀጦች መልክ ይገለጻል ማለት ነው ። በዚህ ምሳሌ ላይ እንደተገለጸው በግ ሌሎችን ሸቀጦች የሚለውጠው ወይም ሌሎች ሰዎች ዕቃቸውን በበግ የሚለውጡት በጉ እራሱ በሚሰጠው የጠቀሜታ እሴት ለመጠቀም ነው ። በሌላ አገላለጽ አንድ በግ ሌሎችን ሸቀጦች በተወሰነ መጠን ይለውጣል ማለት ነው ። ይህ ዓይነቱ የሸቀጦች ልውውጥ የተስፋፋ የእሴት መልክ ይባላል።

## ተስፋፋ እርባታ (የ—)

(*Extended Reproduction*)

በማያቋርጥ አኳኋን የሚካሄደው የማምረት ተግባር ቀደም ሲል ከነበረበት ደረጃ በላይ በማደግ የሚታደስበት ሂደት ነው ። የተስፋፋ እርባታ በካፒታሊዝምም በሶሻሊዝምም ውስጥ የሚታይ ዋንኛው የእርባታ መልክ ነው ።

በካፒታሊዝም ውስጥ ያለው እርባታ በቁሳዊ ምርት መራባት የሚወሰን ሳይሆን የካፒታልና የምርት ተግባር መሠረታዊ ዓላማ የሆነውን የትረፈ እሴትን መራባት የሚያጠቃልል ነው ። ቡርዧዚዎች ይህን ትርፍ ለማግኘት ያላቸው ፍላጎትና በመካከላቸውም ያለው ውድድር በየጊዜው ካፒታል እንዲያከማቹ ወይንም የተስፋፋ እርባታ እንዲያካሂዱ ይገፋፋቸዋል ። በካፒታሊዝም ውስጥ የአምራች ኃይል እርባታ የሚይዘው መልክ ወዝአደሮች መሠረታዊ ፍላጎታቸውን በማርካት ለመሥራት ያላቸውን ችሎታ እያደሱ የሥራ ኃይላቸውን ለቡርዧዚው ለመሸጥ በየጊዜው ዝግጁ ሆነው መገኘታቸው ነው ። ባንድ በኩል ቡርዧዚው በካፒታሉ የሥራ ኃይል ገዝቶ ትረፈ እሴት የማግኘቱ ሂደት በየጊዜው ሲታደስ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ወዝአደሩ በሚያገኘው ምንዳ መሠረታዊ

ፍላጎቱን እያረካ የሥራ ኃይሉን በየጊዜው ለቡርዧዚው የመሸጡ ሂደት ሲቀጥል የካፒታሊስታዊ የምርት ግንኙነት መታደስን ወይም መራባትን ያመለክታል ።

የሸቀጥ ምርት ዋንኛ የምርት መልክ ብሆንበት ሥርዓት ውስጥ እርባታ የምርትና የዝውውር ሂደቶችን በጥምር የሚያመለክት ነው ።

ካርል ማርክስ በካፒታሊዝም ውስጥ የነዚህ ጥምረት የሚናጋበት ሁኔታ ምን እንደ ሆነ ለማሳየት የቻለውና ሥርዓቱም በቀውስ የተወጠረ መሆኑን ለማመልከት የበቃው የማምረት ተግባር ባደገ ደረጃ ታድሶ በምርትና በዝውውር ሂደት መከከል አለመጣጣም ሳይፈጠር የእርባታው ተግባር ሊከናወን የሚችለው ምን ምን ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ እንደሆነ በማሳየት ነው ። በዚሁ መሠረት የሚከተሉት ሦስት ሁኔታዎች መሟላት እንዳለባቸው ጠቁሟል ። እነኝህን ሁኔታዎችም ከሌሎች ወሳኝ ካልሆኑ ሁኔታዎች ነጥሎ ለማየት ይቻል ዘንድ በካፒታሊዝም ውስጥ ሁለት መሠረታዊ መደቦች ብቻ እንዳሉ ፣ የቁሳዊ ሀብት ምርት የሚካሄድበት ቅድመ ካፒታሊስት ግንኙነት እንደሌለ ፣ ክምችቱ የሚካሄደው በቀድሞው ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር መሠረት እንደሆነና የተመረተው ሸቀጥ የሚዘዋወረው ባንድ ሀገር ክልል ውስጥ ብቻ እንደሆነ እድርጎ በሚገምት መላምት ላይ የተመሠረተ ነው ። ይህንኑ ትንታኔ በትክክል ማስተዋል ይቻል ዘንድ ጠቅላላ ማኅበራዊ ምርት በቁሳዊ መልኩ ሲታይ በምርት መገልገያዎች (ክፍል እንድ) የምርት ዘርፍና በፍጆታ ዕቃዎች (ክፍል ሁለት) የምርት ዘርፍ የሚከፈል መሆኑን በቅድሚያ ማጤኑ ጠቃሚ ይሆናል ።

ለምሳሌ ያህል በ1974 በክፍል እንድና (የምርት መገልገያ መሣሪያዎች ብቻ የሚመረቱበት) በክፍል ሁለት (የፍጆታ ዕቃዎች ብቻ የሚመረቱበት) የካፒታል አከፋፈል እንደሚከተለው ነበር እንበል ።

የክፍል እንድ ቡርዧዚዎች ብር 5,000 ወጪ ቢያደርጉና ከዚህ ውስጥ 4,000 ለቋሚ ካፒታል (ቋካ)፤ ብር 1,000 ደግሞ ለተለዋዋጭ ካፒታል (ተካ) ቢያውሉ ፣ (የተረፈ እሴት መጣኔ 100% ነው ብለን ብንገምት) በዓመቱ መጨረሻ ላይ በክፍል እንድ የሚከተለውን የምርት ሁኔታ እናገኛለን ።

<u>ክፍል እንድ</u> ፤

4,000ቋካ$^1$ + 1,000ተካ$^1$ + 1,000ተእ$^1$ = 6,000ጠም$^1$

በተመሳሳይ መንገድ የክፍል ሁለት ቡርዧዚዎች 1500 ለቋሚ ካፒታል ፣ 750 ደግሞ ለተለዋዋጭ ካፒታል ቢያውሉና የተረፈ እሴት መጣኔው ያው 100% ነው ብንል 750 ተረፈ እሴት (ተእ) ያገኛሉ ። ዝርዝሩም እንደሚከተለው ይሆናል ።

<u>ክፍል ሁለት</u> ፤

1,500ቋካ$^2$ + 750ተካ$^2$ + 750ተእ$^2$ = 3,000 ጠም$^2$

ከላይ እንደጠቀስነው በክፍል እንድ ውስጥ የማምረቻ መሣሪያ ብቻ ስለሚመረት በዚያ ክፍል ያሉ ወዝአደሮችና ቡርዧዚዎች የሚፈልጉትን የፍጆታ ዕቃ የግዴታ ከክፍል ሁለት ማግኘት ይኖርባቸዋል ። በክፍል ሁለት ውስጥ ደግሞ የፍጆታ ዕቃ ብቻ ስለሚመረት በዚህ ክፍል ያሉ ቡርዧዚዎች ለሚቀጥለው ጊዜ ምርት ለማምረት እስካሰቡ ድረስ የምርት መሣሪያ የግዴታ ከክፍል እንድ እግኝተው ያለቀውን መተካት ይኖርባቸዋል ። በዚህ ዓይነት የምርቱ ሁኔታ ሊቀጥል የሚችለው በሁለቱ ክፍሎች መሀከል ልውውጥ ሲካሄድ ብቻ መሆኑ ግልጽ ነው ። ይሁንና የማምረቱ ተግባር ሳይቃወስ በተስፋፋ ደረጃ ሊቀጥል የሚችለው ልውውጡ በምን ዓይነት ሁኔታ ሲካሄድ ሲችል ነው? እስቲ ቀረብ ብለን እንመልከተው ።

የክፍል እንድ ቡርዧዚዎች በክፍላቸው ከተመረተው 6,000 ከሚያወጣ የምርት መሣሪያ ውስጥ ለሚቀጥለው ጊዜ ምርት ለመቀጠል የሚያስችላቸውን (ያለቀውን የሚተካላቸውን) 4,000 ቋሚ ካፒታል(ቋካ) አስቀድመው ይቀንሳሉ ። በቋሚ ካፒታል መልክ 2,000 ያህል የሚቀረው ሲሆን 1,000 የሚሆነው ለወዝአደሩ ፍጆታ ፣ የሚቀረው 1,000 ለቡርዧዚዎች ፍጆታ ይውሳል ። ይሁንና በተስፋፋ እርባታ ውስጥ ቡርዧዚው ጠቅላላውን ተረፈ እሴት ለራሱ ፍጆታ ስለማያውለው የተወሰነውን ያህል ምርቱን ለማስፋት (ለክምችት) ካዋለ በኋላ የተቀረውን ለፍጆታ ያውለዋል ። 50% ለፍጆታ ፣ 50% ለክምችት ያውላል ብንል ከ1000 ውስጥ 500 ለቡርዧዚው ፍጆታ (ቡፍ$^1$) 500 ደግሞ ለክምችት ይውላል ማለት ነው ። ለክምችት የሚውለው 500 በቋሚ ካፒታልና በተለዋዋጭ ካፒታል

መካከል መከፋፈል ይኖርበታል ። ፊት እንደ ጠቀስነው ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር ስለ ማይለወጥ ለዚህ ክፍፍል ፊት የነበረውን ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር (4፡1) ብንጠቀም ከ500 ውስጥ አራት እጅ ለተጨማሪ ቋሚ ካፒታል (ተቋካ$_1$) አንድ እጅ ደግሞ ለተጨማሪ ተለዋዋጭ ካፒታል (ተተካ$^1$) ሆኖ እናገኛለን ። በዚህም መሠረት 400 ለተጨማሪ ቋሚ ካፒታል (ተቋካ$^1$) · 100 ደግሞ ተጨማሪ ወዝአደሮች ለመቅጠር (ተተካ$^1$) ይውላል ። የክፍል አንድ ስሌታችንን አጠቃለን ስናየው የሚከተለውን እናገኛለን ።

ክፍል አንድ ፤ 4,000ቋካ$^1$ + 400ተቋካ$^1$
+1,000ተካ$^1$ +100ተተካ$^1$ +500ቡፍ$^1$
= 6,000 ጠም$^1$

እንግዲህ በክፍል አንድ ውስጥ ከተመረተው 6,000 ቋካ ውስጥ 4,400 ቋካ (4,400 ቋካ$^1$ + 400ተቋካ$^1$) በዚያው ክፍል ውስጥ ሲቀር 1,600 ቋካ ደግሞ ወደ ክፍል ሁለት በመሄድ ለክፍል አንድ ወዝአደሮችና ቡርዧዚዎች ፍጆታ የሚሆን (1,000ተካ$^1$ + 100 ተተካ$^1$ +500ቡፍ$^1$) የፍጆታ ዕቃ መምጣት አለበት ።

ክፍል ሁለት ለምርት የተጠቀመው 1,500 ቋሚ ካፒታል ሲሆን አሁን 1,600 ቋሚ ካፒታል ከክፍል አንድ በፍጆታ ዕቃ ልዋጭ ካገኘ 1,500ውን አሮጌውን ቋሚ ካፒታል ለመተካት 100ውን ደግሞ ምርቱን ለማስፋፋት ይጠቀማል ማለት ነው ። ይሁንና ቋሚ ካፒታል ከተጨመረ እሱን የሚያንቀሳቅስ ተጨማሪ ወዝአደር መቅጠር አስፈላጊ ይሆናል ። ቀደም ሲል በነበረው የክፍል ሁለት ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር መሠረት ከሄድን ለሁለት እጅ ቋካ አንድ እጅ ተካ ያስፈልጋል (2፡1) ይህ ከሆነ ለ100 ተጨማሪ ቋሚ ካፒታል (ተቋካ$^2$) 50 ተጨማሪ ተለዋዋጭ ካፒታል (ተተካ$^2$) ያስፈልጋል ማለት ነው ። እንግዲህ አሁን የቀረን የክፍል ሁለት ቡርዧዚ ፍጆታን (ቡፍ$^2$) ማስላት ነው ። ስክፍል ሁለት ከተመረተው 3,000 ጠቅላላ ምርት (ጠም$^2$) ላይ የወጣውን ሁሉ ብንቀንስ (1,500ቋካ$^2$ + 100ተቋካ$^2$ +750ተካ$^2$ +50ተተካ$^2$) የቡርዧውን ፍጆታ ማለትም 600 ቡፍ$^2$ እናገኛለን ። አሁን ሁለቱን ክፍሎች ባንድ ላይ ብናስቀምጥ የሚከተለውን እናገኛለን ።

ክፍል አንድ ፤ 4,000ቋካ$^1$ + 400ተቋካ$^1$
+ 1,000ተካ$^1$ + 100ተተካ$^1$ +500 ቡፍ$^1$
= 6,000 ጠም$^1$

ክፍል ሁለት ፤ 1,500ቋካ$^2$
+100ቋካ$^2$ + 750ተካ$^2$
+50ተተካ$^2$ + 600 ቡፍ$^2$ = 3,000 ጠም$^2$
9,000 ጠም

በሁለቱ ክፍሎች መሀከል የተደረገውን ለውውጥ በቀስቶቹ ከተመለከተው ማየት እንችላለን ። ለውውጡ በዚህ ሁኔታ ከተከናወነ በኋላ ሁኔታው ለሚቀጥለው የምርት ደረጃ ዝግጁ ይሆናል ። አዲሱ ዓመት 1975 ነው ብንል በዚህ ዓመት ክፍል አንድ 4,400 ቋካ ፤ 1,100ተካ ፤ ክፍል ሁለት ደግሞ 1,600ቋካ ፣ 800ተካ ይዘው ይነሣሉ ። በሁለቱም ክፍል የተረፈ እሴት መጣኔ ያው 100% ነው ብንል የ1975 የምርት ሁኔታ የሚከተለውን ይሰጠናል ።

ክፍል አንድ ፤ 4,400ቋካ$^1$ +1,100ተካ$^1$
+1,100ተእ$^1$ = 6,600 ጠም$^1$

ክፍል ሁለት ፤ 1,600ቋካ$^2$
+800ተካ$^2$ +800ተእ$^2$ = 3,200 ጠም$_2$

የኢኮኖሚው ጠም (6,600+3,200) = 9,800

እንግዲህ እንደምናየው ጠቅላላ የኢኮኖሚው ምርት በ1974 ከነበረው 9,000 አሁን ወደ 9800 ከፍ ብሎ እናገኛለን ። የቋሚ ካፒታል ፣ የተለዋዋጭ ካፒታልና የተረፈ እሴቱም መጠን እየጨመረ ሲሄድ እናያለን ። ቀደም ሲል የ1974ን ምርት ለክፍፍል እዘጋጅተን የ1975 ምርት እንደተካሄደ ሁሉ አሁንም የ1975ን በተመሳሳይ መንገድ አዘጋጅተን የ1976 ምርት የሚካሄድበትን የቋካ ፣ የተካ ፣ የተእ እንዲሁም የጠቅላላ ምርቱን መጠን ማሳየትና ቀደም ካለው ዓመት ጋር ማነፃፀር እንችላለን ። ሆኖም ይህን ለአንባቢው እንተዋለን ።

በሁለቱ የኢኮኖሚ ክፍሎች መካከል ለውውጥ ተካሂዶ ሸቀጦች ሁሉ ገበያ አግኝተው አለመናጋት ሳይፈጠር በሚቀጥለው የምርት ደረጃ የማምረቱ ተግባር በተስፋፋ ደረጃ ሲቀጥል የሚችለው ለምሳሌ ቀጥሎ በምንመለከተው ዓይነት ለውውጥ የተካሄደ እንደሆነ ብቻ ነው ። ለመመልከት እንዲቀለን የ1974 የምርት ክፍፍልን ዝርዝር እንደገና እናቀርባለን ።

$$\text{ክፍል አንድ ፤ } 4{,}000\text{ቋካ}^1 + 400\text{ተቋካ}^2 + 1{,}000\text{ተካ}^2 + 100\text{ተተካ}^2 + 500\text{ቡፍ}^1 = 6{,}000\text{ ጠም}^1$$

$$\text{ክፍል ሁለት ፤ } 1{,}500\text{ቋካ}^2 + 100\text{ተቋካ}^2 + 750\text{ተካ}^2 + 50\text{ተተካ}^2 + 600\text{ ቡፍ}^2 = 3{,}000\text{ ጠም}^2$$

ሀ/ በክፍል ሁለት የተመረተው ምርት ጠቅላላ እሴት በሁለቱ ክፍሎች የተሰማሩ ወዝአደሮች ጠቅላላ ገቢና በሁለቱ ክፍል ያሉ ቡርዧዚዎች ለኢምርታዊ ፍጆታ ከሚያውሉት ጋር እኩል መምጣት አለበት ።

$$3{,}000\text{ ጠም}^2 = 1{,}000\text{ተካ}^1 + 100\text{ተተካ}^2 + 500\text{ ቡፍ}^1 + 750\text{ተካ}^2 + 50\text{ተተካ}^2 + 600\text{ ቡፍ}^2$$

ለ/ በክፍል አንድ የተሰማሩ ወዝአደሮችና የዚሁ ክፍል ቡርዧዚዎች ለፍጆታ ከክፍል ሁለት የሚገዟቸው ሸቀጦች ዋጋ የክፍል ሁለት ቡርዧዚዎች የቀድሞ ቋሚ ካፒታልን ለመተካት ፣ እንዲሁም ተጨማሪ ቋሚ ካፒታል ለመግዛት ከሚያውሉት ጋር እኩል መሆን አለበት ።

$$1{,}000\text{ተካ}^1 + 100\text{ተተካ}^1 + 500\text{ቡፍ}^1 = 1{,}500\text{ቋካ}^2 + 100\text{ተቋካ}^2$$

ሐ/ የክፍል አንድ ጠቅላላ ምርት መጠን ሁለቱም ክፍሎች በተስፋፋ ደረጃ ለማምረት ከሚጠቀሙበት ቋሚ ካፒታል ድምር ጋር እኩል መሆን አለበት ።

$$6{,}000\text{ጠም}^1 = 4{,}000\text{ቋካ}^1 + 400\text{ተቋካ}^1 + 1{,}500\text{ቋካ}^2 + 100\text{ተቋካ}^2$$

እነዚህ ከላይ ያነሣናቸው ሁኔታዎች ሲሟሉ የተስፋፋ እርባታ ሳይናጋ ይቀጥላል ። ይሁንና በካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ይህ ሚዛን አይጠበቅም ። ይልቁኑ ከዚህ ሚዛን መፋለስና ከሚፈጠረው አለመጣጣም የተነሣ በርካታ የሰው ጉልበትና ቁሳዊ ሀብት ሲባክን ይታያል።

በካፒታሊዝም ውስጥ ለካፒታል ክምችት የሚውለው ተረፈ እሴት ዕድገት የገበያው መሠረት ከሆነው የወዝአደሩ ገቢ ማነስ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ሁለቱ በአንድ ላይ ማደግ ስለማይችሉ የእርባታው ሂደት የሚናጋበት ሁኔታ ይፈጠራል ። በካፒታሊዝም ውስጥ ያለው መሠረታዊ ቅራኔ ማለትም በማኅበራዊ የአመራረት ሁኔታና በግለሰባዊ የምርት ውጤት ክፍፍል መካከል ያለው የማይታረቅ ቅራኔ ከእርባታ ጋር በተያያዘ መንገድ የሚከሰተውም በዚህ ሁኔታ ነው ።

የካፒታሊስት ሀገሮች ከሀገራቸው ውጭ ገበያ ለማግኘትና አስተማማኝ የጥሬ ዕቃ ምንጭ እንዲኖራቸው የሚያደርጉት ሩጫ የሚመነጨውም ከዚሁ ነው ።

የካፒታሊስት የተስፋፋ እርባታ ዋንኛው ሕግ በቴክኖሎጂ ዕድገት ሳቢያ በውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር ውስጥ የቋሚ ካፒታል ድርሻ ከተለዋዋጭ ካፒታል በበለጠ ፍጥነት የሚያድግ መሆኑ የምርት ማከናወኛ መሣሪያዎች የምርት ዘርፍ ከኢምርታዊ ፍጆታ ዕቃዎች የምርት ዘርፍ በበለጠ ፍጥነት የሚያድግ መሆኑ ነው ።

በሶሻሊዝም ያለው የተስፋፋ እርባታ በዕቅድ ላይ የተመሠረተና ቁሳዊ ሀብት ቀደም ሲል ከነበረበት መጠን ባደገ ሁኔታ መታደሱን ወይም መራባትን የሚያመለክት ነው ። ይህ መራባት በጋራ ንብረትነት ሥር የምርት መገልገያዎችን ፣ ከብዝበዛ የተላቀቀውን አምራች ኃይል ፣ ጠቅላላ ማኅበራዊ ምርትን ፣ የሶሻሊስት የምርት ግንኙነትን የሚያጠቃልል ነው ።

የሶሻሊስት የተስፋፋ እርባታ በዕቅድ የሚመራና በጋራ የምርት መገልገያዎች ባለቤትነት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ በካፒታሊስት የተስፋፋ እርባታ ውስጥ ከሚታየው በኢኮኖሚ ክፍሎች መካከል ካለው ግንኙነት መፋለስ ፣ ከንብረት መባከንና ባጠቃላይም ከኢኮኖሚ ቀውስ ነፃ የሆነ ነው ። በመሆኑም የሶሻሊስት የተስፋፋ እርባታ የተስተካከለ የሀብት አጠቃቀም እንዲሁም የተሟላ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት የሚያስገኝ ነው ።

(እርባታን ፣ ቀላል እርባታን ይመለከቷል ።)

## ትረፈ ምርት
*(Surplus Product)*

በቁሳዊ ሀብት ምርት መስክ በተሰማሩ ሠራተኞች ከሚፈጠረው ማኅበራዊ ምርት ውስጥ አስፈላጊው ምርት ሲነሣ የሚቀረው ክፍል ነው ። ትረፈ ምርትን ለማምረት የሚውለው ጊዜ ትርፍ የሥራ ጊዜ ሲባል ፣ በዚህ ጊዜ ውስጥ ሠራተኞች የሚሠሩት ሥራም ትረፈ ሥራ ይባላል ።

በእያንዳንዱ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ትረፈ ምርት የተለየ መልክ አለው ። የአመ

ራረቱና የክፍፍሉ ሁኔታም እንዲሁ በየሥርዓተ ማኅበሩ ውስጥ ባለው የንብረት ይዞታ ዓይነት የሚወሰን ነው ። በጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር የሥራ ምርታማነት እጅግ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ስለነበር ተረፈ ምርት አልፎ አልፎ በአጋጣሚ እንጂ በቋሚነት ሊገኝ አይችልም ነበር። በኅብረተሰብ የዕድገት ታሪክ ውስጥ ተረፈ ምርት በቋሚነት ሊገኝ የቻለው የምርት ኃይሎች ዕድገት የተወሰነ ደረጃ ላይ ደርሶ አንድ ሠራተኛ ለሱና ለቤተሰቡ ከሚያስፈልገው በላይ ማምረት በጀመረበት ጊዜ ነው።

የተረፈ ምርት መከሰት ለግል ሀብት መፈጠርና ለኅብረተሰብ በመደብ መከፋፈል ቁሳዊ መሠረት በመሆን ለሰው በሰው መበዝበዝ አመቺ ሁኔታ ከመፍጠሩም በላይ በጉልበትና በአእምሮ ሥራ መካከል ልዩነት እንዲከሰት ምክንያት ሆኗል ። ብዝበዛ በሰፈነባቸው ሥርዓተ ማኅበሮች ሁሉ ተረፈ ምርት ያለምንም ከፍያ በገዥ መደቦች ተወስዶ በተቀባቢነት ኑሮአቸውን ለሚያካብቱት የሀብት መሠረት በመሆን ያገለግላል ።

በካፒታሊዝም የሥርዓቱ መሠረታዊ ዓላማና ዋንኛውም አንቀሳቃሽ ኃይል የተረፈ እሴት መፈጠርና መካበት እንደመሆኑ ተረፈ ምርት የተረፈ እሴትን ቁሳዊ መልክ በመውሰድ በወዝአደሩና በገዥ መደቦች መካከል ያለውን ተፃራሪ ቅራኔ ያመለክታል ። በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ተረፈ ምርት (ተረፈ እሴት) ወደተለያዩ ንዑሳን ክፍሎች ሲከፋፈል ፣ የኢንዱስትሪን ትርፍ ፣ የንግድን ትርፍ ፣ የባንክ ወለድንና የመሬት ኪራይን መልክ ይይዛል ። ካፒታሊስቶችና የመሬት ከበርቴዎች ተረፈ ምርትን ለግል ፍጆታና ለካፒታል ክምችት ይጠቀሙበታል። ካፒታሊዝም እያደገ በሄደ መጠን ከአጠቃላይ ማኅበራዊ ምርት ውስጥ የተረፈ ምርት ድርሻ ከፍ ይላል ። ይህም በወዝአደሩ መደብ ላይ የሚካሄደው ብዝበዛ እየከፋ መሄዱን ያመለክታል ።

በሶሻሊዝም የምርት መገልገያዎች የጋራ ሀብት በመሆናቸውና ብሔራዊ ኢኮኖሚውም በዕቅድ የሚመራ በመሆኑ ተረፈ ምርት ለበዝባዥ መደቦች ሳይሆን ለሠርቶ አደር ሕዝቦችና ለነሱ ብቻ የሚውል ነው ። በሶሻሊዝም በተረፈ ምርትና በአስፈላጊ ምርት መካከል ያለው ተፃራሪ ቅራኔ ስለሚጠፋ የተረፈ ምርት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ባሕርይ የዓይነት ለውጥ ያሳያል ። በሶሻሊዝም ተረፈ ምርት የአምራቾችን ማኅበራዊ ፍላጎት የሚያረካ ከመሆኑም በላይ የሶሻሊስት ክምችት ምንጭ በመሆንም ያገለግላል ። በሶሻሊዝም ተረፈ ምርት የሀገር መከላከያ ወጪን ፣ የመንግሥት አስተዳደር ወጪንና በኢኮኖሚው ውስጥ ኢምርታዊ የሆነውን ክፍል ወጪ የሚሸፍን ከመሆኑም በላይ የማኅበራዊ ፍጆታ ምድብም የተወሰነ ክፍል ከዚሁ ተረፈ ምርት የሚወሰድ ነው ።

በሶሻሊዝም የተረፈ ምርት መመረትና ጥቅም ላይ መዋል የሶሻሊስት ምርት መሠረታዊ ዓላማ ከሆነው የሠራተኛ ሕዝቦችን ፍላጎት ከማርካት ጋር የተቆራኘ በመሆኑ ሠራተኞች ተረፈ ምርትን የሚያመርቱት የራሳቸውንና የኅብረተሰቡን ፍላጎት ለማርካት ካላቸው ፍላጎት በመነሣት ነው ። ተረፈ ምርት በሚከፋፈልበት ጊዜ የተወሰነው ክፍል በትርፍ መልክ ለመንግሥት የኢኮኖሚ ተቋሞችና በተጣራ ገቢ መልክ ደግሞ ለአገልግሎትና ለኅብረት ሥራ ማኅበራት ይዳረሳል ። ቀሪው ደግሞ የተጣራ ማኅበራዊ ገቢ ሆኖ በማዕከላዊ ደረጃ ለኅብረተሰቡ ግልጋሎት ይውላል ።

(አስፈላጊ ምርትን ይመለከቷል።)

## ተረፈ ሥራ
*(Surplus Labour)*

በቁሳዊ ምርት ተግባር ላይ የተሰማራ ሠራተኛ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በሥራ ላይ ከሚያውለው ጉልበቱ መካከል ለራሱ የሥራ ኃይል መታደስና ለሱና ለቤተሰቡ ኑሮ የሚያስፈልገውን ለማግኘት ከሚሠራው ሥራ በተጨማሪ የሚያከናውነው ነው ።

በአስፈላጊ ሥራና በተረፈ ሥራ መካከል ልዩነት የተፈጠረው የምርት ኃይሎች ዕድገት የተወሰነ ደረጃ ላይ ደርሶ አንድ ሠራተኛ ለራሱና ለቤተሰቡ ፍላጎት ማሟያ ከሚሆነው በላይ ለማምረት በቻለበት ጊዜ ነው ። በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት የባሪያው ተረፈ ሥራ ፣ በፊውዳሉ ሥርዓት የጭሰኛው ተረፈ ሥራ ለባሪያ አሳዳሪውና ለፊውዳሉ ተረፈ ምርት አስገኝተዋል ።

በካፒታሊስት ሥርዓት ወዝአደሩ በተረፈ ሥራ ጊዜ የሚያከናውነው ሥራ ለካፒታሊስቱ ተረፈ እሴት ያስገኛል ። ወዝአደሩ በተረፈ ሥራው የሚፈጥረውን ተረፈ እሴት ካፒታሊስቱ ለራሱ ሊያደርገው የቻለበትም ምክንያት ካፒታሊስቱ የምርት መገልገያዎቹ ባለቤት በመሆኑ ነው ።

በካፒታሊስት ሥርዓት በተረፈ ሥራና በአስፈላጊ ሥራ መካከል ያለው ልዩነት በምንዳ ሥርዓት አማካይነት ይሸፈናል ። ካፒታሊስቱ ለወዝአደሩ የሚሰጠው ምንዳ ወዝአደሩ በአስፈላጊ የሥራ ጊዜው ያከናወነውን አስፈላጊ ሥራ የሚሸፍን ሲሆን ባለው የምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት በመጠቀም የወዝአደሩ ተረፈ ሥራ ያስገኘውን ተረፈ እሴት ያለምንም ክፍያ ይወስዳል ።

የካፒታሊስት ምርት መሠረታዊ ዓላማ ትርፍን መሰብሰብ እንደመሆኑ ይህን ለማድረግ ካፒታሊስቶች የሥራ ቀን ሰዓትን በማራዘም ፣ የሥራ ዕምቀትን በመጨመርና አስፈላጊ የሥራ ጊዜን በመቀነስ ተረፈ እሴት የሚያገኙበትን የተረፈ ሥራ ጊዜ ይጨምራሉ ። በዚህ መንገድ የተረፈ እሴትን መጣኔም ሆነ የተረፈ እሴትን እከብ በመጨመር ብዝበዛን ያጠናክራሉ ።

የተረፈ ሥራ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ይዘት በሶሻሊዝም የዓይነት ለውጥ ያሳያል። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ተረፈ ሥራ የሠራተኞች ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጐት የሚሟላበት ፣ የሶሻሊስት ኅብረተሰብ አባላት በሙላ የተሟላ ዕድገት የሚያገኙበት ዓይነተኛ መሣሪያ ነው ። በሶሻሊዝም በተረፈ ሥራ አማካይነት የሚመረተው ተረፈ ምርት ማኅበራዊ ፍጆታን ለመሸፈን የሚያገለግል ከመሆኑም በላይ ተጨማሪ የምርት መገልገያዎችንና የፍጆታ ዕቃዎችን በማምረት ለተስፋፋ የሶሻሊስት እርባታ ቁሳዊ መሠረት ሆኖ የሚያገለግል ነው ። ስለዚህ በሶሻሊዝም ተረፈ ሥራ እንደ ካፒታሊዝም ለጥቂት ግለሰቦች ሳይሆን ለሙላ ሠራተኞች ጥቅም የሚውል ነው ።

(አስፈላጊ ምርትን ፣ ተረፈ እሴትን ይመለከቷል ።)

## ተረፈ እሴት
*(Surplus Value)*

ወዝአደሩ በካፒታሊስት ሂደተ ምርት ውስጥ የሥራ ኃይሉን ከምርት መገልገያዎች ጋር በማቀናጀት ከራሱ የሥራ ኃይል እሴት (ምንዳ) በላይ የሚፈጥረው እሴት ተረፈ እሴት ይባላል ። ካፒታሊስቱ ካፒታሉን በየጊዜው እያደለበ የሚሄደው ወዝአደሩን በሕይወት ለማቆየትና ለመሥራት የሚያስችለውን ያህል ኃይል እንዲያገኝ ምንዳ በመክፈል ወዝአደሩ የሚፈጥረውን ተረፈ እሴት በማካበት ነው ።

በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የወዝአደሩ የሥራ ጊዜ በሁለት ይከፈላል ። አንደኛው አስፈላጊ የሥራ ጊዜ ይባላል ። በዚህ የሥራ ጊዜ ወዝአደሩ የራሱን የሥራ ኃይል እሴት ይፈጥራል ፤ ማለትም ለራሱና ለቤተሰቡ ሕይወት አስፈላጊ የሆኑትን ቁሳቁሶች ወይም ነገሮች ለመግዛት የሚያስችለውን ምንዳ ለማፍራት ያውለዋል ። ስለዚህ ምንዳ የሚከፈለው ለዚህ የሥራ ጊዜ ነው ።

ሁለተኛው ትርፍ የሥራ ጊዜ የሚባለው ሲሆን በዚህ የሥራ ጊዜ ውስጥ ወዝአደሩ ለካፒታሊስቱ ተረፈ እሴትን ይፈጥራል ።

በዚህ የሥራ ጊዜ ውስጥ ለሚያከናውነው ሥራ ወዝአደሩ ምንም ክፍያ አያገኝም፤ ካፒታሊስቱ የወዝአደሩን የሥራ ኃይል የሚበዘብዘው በዚህ ትርፍ የሥራ ጊዜ ውስጥ ተረፈ እሴትን በማስፈጠር ነው ።

ተረፈ እሴት በሂደተ ምርት ውስጥ በወዝአደሩ የሚፈጠር ቢሆንም የሚከሰተው ወይም ተጨባጭ ገጽታ የሚይዘው ግን በሸቀጦች ዝውውር ወቅት ማለትም በልውውጥ ሂደት ውስጥ ነው ።

(እሴትን ፣ ብዝበዛን ፣ ወዝአደርን ይመለከቷል ።)

## ተረፈ እሴት መጣኔ (የ—)
*(Rate of Surplus Value)*

በሂደተ ምርት ውስጥ ወዝአደሩ አዲስ የፈጠረውን እሴት በእርሱና በካፒታሊስቱ መካከል እንዴት እንደሚከፋፈል ፣ ተረፈ እሴት በተሰዋዋጭ ካፒታሉ ማለትም ከምንዳ

በመቶኛ (%) ሲነፃፀር ምን ያህል ተዛምዶ እንዳለው የሚያመለክት ነው ። ስለዚህም የተረፈ እሴት መጣኔ የብዝበዛውን ደረጃ ማለትም ምዝበራው እስከምን ድረስ እንደሆነ የሚያሳይ አኀዛዊ መግለጫ ነው ።

የተረፈ እሴት መጣኔ ስሌት በሁለት ዓይነት መንገድ ሊገለጽ ይችላል ። ለምሳሌ አንድ ወዝአደር በቀን ስምንት ሰዓት ቢሠራና ከዚህ ውስጥ ሦስቱን ሰዓት የሥራ ኃይሉን እሴት ማለትም ለራሱና ለቤተሰቡ ሕይወት አስፈላጊ ነገሮች ለማግኘት መሥራት ያለበት ቢሆንና የቀረውን 5 ሰዓት ደግሞ ለቡርዧዚው ተረፈ እሴትን ቢፈጥርበት መጣኔው $\frac{5}{3} \times 100 = 167\%$ ወይም ከአንድ ተኩል በላይ የሥራ ኃይሉን ይበዘበዛል ማለት ነው ። በዚህ ምሳሌ መሠረት ወዝአደሩ 167% ወይም 5:3 ጊዜ ያህል የሥራ ኃይሉን ይበዘበዛል ማለት ነው ።

## ተረፈ እሴት እክብ (የ—)
*(Mass of Surplus Value)*

የተረፈ እሴት እክብ የምንለው ፍጹማዊ የሆነውን አኀዛዊ የተረፈ እሴት መጠን ነው ። የተረፈ እሴትን መጠን ፍጹማዊና አንፃራዊ በሆነ መንገድ ለመለካት ይቻላል ። አንድ ካፒታሊስት በአንድ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሚያገኘው የተረፈ እሴት እክብ ከጠቅላላው የምርት ውጤት ውስጥ ለምንዳ የሚከፈለው ተቀንሶ የሚገኘው መጠን ነው ። ለምሳሌ አንድ ካፒታሊስት በአንድ በተወሰነ ጊዜ ያገኘው ተጨማሪ እሴት ብር 450 ቢሆንና በዚህ ጊዜ ውስጥ ለወዝአደሮች ምንዳ ብር 150 ቢያወጣ የተረፈ እሴቱ እክብ መጠን ብር 300 ይሆናል ። ስለዚህ የተረፈ እሴት እክብ ካፒታሊስቶች በአንድ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ቅጥር ሠራተኛን በመበዝበዝ የሚያገኙት የተረፈ እሴት አኀዛዊ መግለጫ ነው ።

(የተረፈ እሴት መጣኔን ይመለከቷል።)

## ተራማጅ
*(Progressive)*

የርምጃትን ዲያሌክቲካዊ ሕግ የሚከተል ፣ የጋራ ብልጽግናን ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ፍትህን የሚደግፍና ለዚህም እስተዋጽኦ የሚያደርግ ነው። ለዕድገት የሚሰለፉ መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች በዚሁ የሚጠቃለሉ ናቸው።

(ርምጃትን ይመለከቷል።)

## ተቃራኒዎች አንድነትና ትግል ሕግ (የ—)
*(Law of the Unity and Struggle of Opposites)*

ይህ ሕግ የዲያሌክቲክስ መሠረታዊና ዋናው ሕግ ነው ። ዲበአካል ስለቅራኔ ያለውን አስተሳሰብ ስንመለከት የምንረዳው ቅራኔ ነባራዊ ሳይሆን ከሰው ልጅ አስተሳሰብ ስህተት የሚመነጭ እንደሆነ ነው ። አንድ ነገር በዚያው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እራሱንና ሌላ ነገር ሊሆን አይችልም በማለት ዲበአካል ነገሮች ከቅራኔ ነፃ እንደሆኑ ለማሳመን ይጥራል ። ለምሳሌ ሕይወትንና ሞትን ብንወስድ ከተቃራኒነታቸው የተነሣ ሁለቱ በአንድ ነገር ውስጥ በአንድነት ሊኖሩ አይችሉም ። በሕይወት ያለ ነገር ከሞት ውጭ ነው ፤ የሞተ ደግሞ ሕይወት ያለው አይደለም ። ሕይወት ሞትን ፣ ሞት ሕይወትን ስለሚቃረንና አንዱ ሌላውን ስለሚሽር በአንድነት ሊታሰቡ አይችሉም ። በሕይወት ያለ ነገር በዚያው ጊዜ ከሞት ነፃ ከመሆኑም በላይ ሁኔታው ፈጽሞ የተለየ በመሆኑ ሁለቱን በአንድነት ማሰብ ፍች የሌለው አነጋገር ይሆናል ። ወይ በሕይወት አለ ወይ ሞቷል እንጂ በዚያው ጊዜ አንድ ነገር ሁለቱንም ሊሆን አይችልም ይላል ።

ከልምድ የተነሣ ይህ አባባል ትክክል ቢመስለንም ጠለቅ ብለን ስንመረምረው ያልተሟላና አሳሳች ሆኖ እናገኘዋለን ። ሕይወትና ሞት በዚህ ሁኔታ የተለያዩ ከሆኑ እንዴት አንዱ ወደሌላው ይቀየራል? በሕይወት ያለ መሞት ባልተገባው ፣ የሞተው ደግሞ በመጀመሪያ በሕይወት ባልኖረ ነበር ። በሕይወት ያለ ነገር ሁሉ እያደገና እየተለዋወጠ እንደሚሄድ እናያለን ። ይህ እራሱ የሚያስረዳን አዲሱ በአሮጌው እየተተካ መሆኑን ስለሆነ አሮጌው እየሞተ በአዲሱ ሲተካ የሕይወትና የሞት አንድነት መረጋገጡ አይደለምን?

ይህ የሚያሳየው ማንኛውም ተንቀሳቃሽና በሕይወት ያለ ነገር ሁሉ የተወሰነ ቋሚ ባሕርይ እንደሌለውና አንድ ሁኔታ ወደሌላ ሁኔታ እንደሚቀየር ነው ። መቀያየር ፣ መለዋወጥ ማለት ደግሞ ቅራኔ ማሳየት ነው ። አንድ ነገር ተቀየረ ስንል ምንነቱ ተለወጠ ማለታችን በመሆኑ የመለወጡ ሁኔታ የሚያሳየን ነገሩ እራሱን ሽሮ ሌላ መልክ እንደያዘና ከዚህም የተነሣ እራሱን እንደተቃረነ ነው ። የቅራኔዎች አንድነት የተባለውም የቅራኔው ባለቤትና ምንጭ እራሱ ነገሩ በመሆኑ ነው ።

ቅራኔዎች አንድነት አላቸው ስንል ሊኖራቸው የሚችለው ግንኙነት የትግል መሆኑ ግልጽ ነው ። አዝማሚያዎች አንድ ወይም የማይነጣጠሉ ሆነው ሲቃረኑ የመሻኮት ፣ የመጋፋት ፣ የመታገል ሁኔታን ያስከትላሉ ። ከዚህም የተነሣ በነገሩ ውስጥ የመንቀሳቀስና የመለወጥ ኃይል ያመነጫሉ ። ሆኖም በአንድነታቸው የተነሣ አንዱ ሌላውን አጥፍቶ ብቻውን ሊኖር አይችልም ። በመሆኑም የእርስ በርስ ትግላቸው አንዱ ሌላውን በመግዛትና የበላይነት በመቀዳጀት ይገለጻል ። በሞትና በሕይወት መሀል ትግል አለ ሲባል ሕይወት ከሞት ነፃ ይሆናል ማለት ሳይሆን በሕይወት ያለው እንዳይሞት ወይም የበላይነቱን ጠብቆ ለመኖር ይታገላል ማለት ነው ። ሆኖም ይህ የበላይነት ዘለዓለማዊ ሊሆን አይችልም ። ምክንያቱም እንዳይሞት የሚያደርገው ትግል በየጊዜው ለውጥ ስለሚያስከትል ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ወደድክመት ማለትም ወደእርጅና ይለወጣል ። ጥረቱ ሁሉ የሚያመራው ወደ ራሱ ተቃራኒ ማለትም ወደሞት ነው ። ድክመቱ ለተቃራኒው አመች ሁኔታ በመፍጠሩ በተራው ደግሞ የተቃራኒው የበላይነት ቀስ በቀስ ይከሰታል ።

የተቃራኒዎች አንድነትና ትግል ሕግ በትክክል የሚያስረዳን እንቅስቃሴና ዕድገት የሚመነጩት ከነገሮች ውስጣዊ ሁኔታ መሆኑን ነው ። ነገሮች የሚንቀሳቀሱት ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ኃይል ሳይሆን በራሳቸው ውስጣዊ ቅራኔ በመሆኑ ይህ የእንቅስቃሴ ሕግ ለቁስአካላዊ ፍልስፍና መሠረታዊ ድጋፍና መረጃ ስጥቶታል ። የዓለምን ምንነትና ሁኔታ ለመረዳት መንፈሳዊ ምክንያት መፈለግ አያሻም ፤ ዓለም እራስዋን በራስዋ ታስረዳለችና ። ይህ ሕግ ዕድገት የተቃራኒዎች ትግል ውጤት መሆኑን ስለሚያስረዳን የመለዋወጥ ፣ የአሮጌውን መሞትና በአዲሱ የመተካት ሁኔታዎችን ትክክለኛ ግንዛቤ ይሰጠናል ።

ለምሳሌ የወዝአደሩንና የቡርዧዚውን ግንኙነት ብናይ ወዝአደር ካለቡርዧዚ፤ ቡርዧዚ ካለወዝአደር ሊኖር አይችልም ። አንዱ የሥራ ኃይል የሚሸጥ ሌላው ደግሞ የሥራ ኃይል የሚገዛ በመሆኑ ሁለቱ አይነጣጠሉም ። ይህ አንድነትም በቅራኔ ላይ የተመሠረተ ነው። ምክንያቱም የወዝአደሩ መኖር ለቡርዧዚው የግል ትርፍ ማግኛው ሲሆን ይህ ትርፍ ደግሞ የሚገኘው ወዝአደሩን በመበዝበዝ ነው ። የቡርዧዚው በብዛት የግል ትርፍ የማከማቸት ፍላጎት የወዝአደሩን ቁጥር ከማብዛትም በላይ በዘመናዊ መሣሪያ ማለትም በፋብሪካ ሥራ ውስጥ የወዝአደሩን መደራጀት ያስከትላል ። በዚህ ፋብሪካ ሥራ በአንድ በኩል አዲስ ግንኙነት ማለትም የስልተ ምርት በይበልጥ ማኅበራዊ መሆን ሲከሰት በሌላ በኩል ደግሞ የሚመረተው ሀብት እፍኝ ለማይሞሉ ቡርዧዚዎች ጥቅም ይውላል ። ከሥር የበቀለው የምርት ማኅበራዊ አሠራርና ከላይ ያለው የግል ጥቅም የበላይነት አለመጣጣም እየከረረ ስለሚሄድ የራሱ የካፒታሊስት ሥርዓት እያደገ መሄድ ለሶሻሊስት ሥርዓት መምጣት አመች ሁኔታ ይፈጥራል ። ሶሻሊዝም የትግሉ ዓይነተኛ መፍትሄ መሆኑ የሚያስረዳን የተቃራኒዎች አንድነትና ትግል ሕግ ነገሮች ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንዲሸጋገሩ የሚያደርግ መሆኑን ነው ።

የተቃራኒዎች አንድነትና ትግል የተፈጥሮ መሠረታዊ ሕግ ነው ። ማንኛውም ነገር በውስጡ ቅራኔ ያዘለ በመሆኑ ምንነቱን የምናስበው በዚህ በቅራኔው አማካይነት ነው ። ትልቅ ስንል ትንሽን ፣ ላይ ስንል ታችን ፣ ቀኝ ስንል ግራን ፣ ቀን ስንል ሌሊትን ወዘተ... እናስባለን ። ይህ ለማነፃፀር ብቻ የምናደርገው ሳይሆን የነገሩ ባሕርይ የሚወሰነው በውስጡ ባዘለው ቅራኔ በመሆኑ ነው ። የነገሮች ምንነት የእርስ በእርስ ግንኙነታቸው ውጤት በመሆኑ ማንኛውም ነገር እራሱን ብቻ ሳይሆን ሌላም ነገር ነው ። 10 ስንል ይህ ቁጥር ከ2 ይበልጣል ከ20 ደግሞ ያንሳል ፤ ትንሽም ትልቅም ነው ። 10 ቁጥር በዚሁ ባለው ባሕርይ የተወሰነ ስፍራ ይይዛል ። የተቃራኒዎች አንድነት ሁኔታዊ ፣ ጊዜያዊ ፣ ኃላፊና አንፃራዊ ሲሆን ትግላቸው ግን

ፍጹማዊ ነው ። የቅራኔዎች አንድነት የሚከሰተው በዘፈቀደ ወይም በአጋጣሚ ሳይሆን በሁኔታዎች ላይ ተመሥርቶ ነው ። ይህም ሲባል ተቃራኒዎች ለዘለዓለም ተጣብቀው የሚቀሩ አይደሉም ። ወደአዲስ ክስተት የሚለወጡ በመሆናቸው አንድነታቸው ጊዜያዊና ኃላፊ ነው ። ፍጹማዊ ነገር ቢኖር ትግሉ ነው ። ማለትም ተቃራኒዎች ከተከሰቱ በኋላ ትግል ያካሂዳሉ ፤ ይህም ትግል ወደማይቀረው መፍትሔ ማለትም ወደ አዲስ ሁኔታ እንዲሸጋገሩ ያደርጋቸዋል ።

(የዲያሌክቲክስ ሕጎችን፣ ዕድገትን ፣ ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነትን ፣ ዲበአካልን ይመለከቷል ። )

## ተቃርኖ

*(Antithesis)*

የአንድ ነገር ፣ ክስተት ወይም ሐሳብ ሁለት የተያያዙ ፣ የማይነጣጠሉና የሚወራረሱ ነገር ግን ተቃራኒ ወይም ተቃዋሚ የሆኑ ክፍሎችን (ለምሳሌ የኤሌክትሪክ ፖስቲቭና ኔጌቲቭ ክፍሎችን ፣ የአእምሮና የጉልበት ሥራ ፣ የገጠርና የከተማ ልዩነቶችን ወዘተ...) የሚያመለክት ጽንሰ ሐሳብ ነው።

በሁለት ተቃራኒ ነገር ግን ውህደት ባላቸው ክፍሎች መሀከል ትግል ይደረጋልና ትግሉ በሚጠይቀው ሁኔታ መሠረት አዲስ ነገር ይፈጠራል ። አዲሱም እንዲሁ የራሱ የሆነ ሁለት ተቃራኒዎችን ያቀፈ ቢሆንም ተከቶት ከመጣው አንፃር ሲታይ ግን በከፍተኛና በተሻሻለ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው ። ይህም ተቃርኖ ነው ።

(የተቃራኒዎች አንድነትና ትግል ሕግን ይመለከቷል ።)

## ተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (የ—)

*(United Nations Organization)*

የዓለምን ሰላምና ፀጥታ ለመጠበቅና ለማጠናከር እንዲሁም በሀገሮች መካከል ኅብረት እንዲፈጠር ለማድረግ የተቋቋመ ዓለም አቀፍ ድርጅት ነው። የድርጅቱ የተግባር መርሀና መዋቅር የተዘጋጀው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ሲሆን ተሳታፊዎቹም በፀረ ሂትለር ኅብረት ውስጥ ዓቢይ ሚና ይጫወቱ የነበሩት ሀገሮች ናቸው። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እንዲመሠረት ያበቁት የሶቭዬት ኅብረት ፣ የአሜሪካና የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች የተሳተፉበት በ1943 የተካሄደው የሞስኮ ጉባኤ ፣ እንዲሁም በ1944 በዱምባርቶን ኦክስ ፣ በ1945 በያልታ ፣ በ1945 በሳን ፍራንሲስኮ የተካሄዱት ጉባኤዎች ናቸው ። በሰኔ 26/1945 በሳን ፍራንሲስኮ በተደረገው ጉባኤ 50 መንግሥታት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ቻርተር በመፈረም የድርጅቱ መሥራች አባላት ሆኑ ። ይህን ቻርተር ሶቭዬት ኅብረት ፣ አሜሪካ ፣ እንግሊዝ ፣ ፈረንሳይ ፣ ቻይናና ሌሎችም ሀገሮች ካጸደቁት በኋላ ጥቅምት 24 ፣ 1945 በሥራ ላይ ዋለ ።

በቻርተሩ ውስጥ እንደተጠቀሰው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ዓላማ ዓለም አቀፍ ሰላምንና ፀጥታን ማስጠበቅ ፣ የራስን ዕድል በራስ በመወሰንና በእኩልነት በተመሠረተ መርሀ ላይ በመመርኮዝ በሀገሮች መካከል የእህትማማችነት ግንኙነቶች ማዳበር ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊ ፣ ባህላዊ ወይም ሰብአዊ ችግሮችን በዓለም አቀፍ ትብብር ለመወጣት ጥረት ማድረግና እነዚህ የጋራ ዓላማዎች ግባቸውን እንዲመቱ ሀገሮችን ለማስተባበር በማዕከልነት ማገልገል ፣ አባል ሀገሮችን ሁሉ በእኩልነት ደረጃ መመልከት፣ በሀገሮች ...ከል የሚነሡ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ወዘተ... ናቸው ።

ድርጅቱ በቻርተሩ መሠረት የሚወስዳቸውን እርምጃዎች ከማስፈጸም በቀር በማንኛውም ሀገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አይገባም ። የዓለምን ሰላምና ፀጥታ ለማስከበር በሚያደርገው ጥረት አባል ሀገሮች ብቻ ሳይሆኑ አባል ያልሆኑ ሀገሮችም የመተባበርና ደንቡን የማክበር ግዴታ አለባቸው ።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በ50 መሥራች ሀገሮች ቢቋቋምም በፀጥታው ምክር ቤት ድጋፍ የተሰጣቸውና በጠቅላላው ስብሰባ ሁለት ሦስተኛ ድምፅ ያገኙ ሀገሮች በአባልነት ሊመዘገቡ መቻላቸው በቻርተሩ ውስጥ ስለተጠቀሰ የአባላቱ ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ መጥቷል ።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስድስት ዓበይት አካላት አሉት ፤ እነርሱም ጠቅላላ ስብሰባ ፣ የፀጥታ ምክር ቤት ፣ የኢኮኖሚያዊና የማኅበራዊ ጉዳይ ምክር ቤት ፣ የሞግዚት አስተዳደር ምክር ቤት ፣ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤትና የድርጅቱ ጽሕፈት ቤት ናቸው ።

በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር መሠረት በኢኮኖሚያዊ ፣ በማኅበራዊ ፣ በባህላዊ ፣ በትምህርት ፣ በጤናና ከእነዚህ ጋር በተያያዙ መስኮች የሚሠሩ እንደዩኔስኮ ፣ እንደ ዩኒሲኤፍ ያሉ በርካታ ድርጅቶች ተቋቁመዋል ።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከተመሠረተ ጀምሮ በኢኮኖሚያዊና በማኅበራዊ መስኮች ብዙ እርምጃዎችን ወስዷል ። ቅኝ አገዛዝን ፣ ዘረኝነትንና የብሔር ጭቆናን በመቃወም ጠቅላላ ስብሰባው ያሳለፋቸው ውሳኔዎች ተጨባጭ ጠቀሜታ ሰጥተዋል ። የጦር መሣሪያ ቅነሳንና የዓለምን ፀጥታ በሚመለከት ረገድ ብዙ ጠቃሚ ውሳኔዎችን አሳልፏል ።

የዴታንት ተቃዋሚዎች የዓለምን ሰላምና ፀጥታ ለማጠናከር የወጡት ደንቦች እንዳይጸድቁ ከፍተኛ ተፅዕኖ አድርገዋል ። እስከ 1950ዎቹ አጋማሽ ድረስ የምዕራብ ሀገሮች የነሱ ጥገኞች በሆኑ ሀገሮች ድምፅ በመተማመን ሶቭዬት ኅብረት የአቶሚክ መሣሪያዎች እንዲታገዱና የጦር መሣሪያ ቅነሳ እንዲደረግ ያቀረበቻቸውን ሐሳቦች ውድቅ ለማድረግ ችለዋል ። ኢምፔሪያሊስታዊ ፖሊሲያቸውንም የሚያራምዱ ውሳኔዎች በማሳለፍ በኩል ሊሳካላቸው ችሏል ። አሜሪካ በ1950 ኮሪያን ወርራ በነበረችበት ወቅት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሰንደቅ ዓላማ እንዲውለበለብ መደረጉ ለዚህ ምሳሌ ነው ።

ይሁን እንጂ የዓለም የኃይል ሚዛን ወደ ሶሻሊዝም ማጋደሉ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውስጥ ተጨባጭ ለውጦችን አስከትሏል ። በዚህም ምክንያት በ1955 ሶሻሊስት ሀገሮች የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል እንዳይሆኑ የምዕራብ ሀገሮች ያቀረቡት ተቃውሞ ውድቅ ሊሆን ችሏል ። በተጨማሪም በ1950ዎቹ መገባደጃና በ1960ዎቹ መጀመሪያ ላይ ብዙ የአፍሪካና የእስያ ሀገሮች አባል ለመሆን በመብቃታቸው የዓለምን ሰላምና ፀጥታ በሚመለከት የሚተላለፉ ውሳኔዎችን ደግፈዋል ። የምዕራብ ሀገሮች ግን በእነዚህ ዓመታት ውስጥ በድርጅቱ በመጠቀም ሶሻሊስት ሀገሮችን የሚፃረሩና የነሱን የቅኝ ገዥነት ዓላማ የሚያራምዱ ፖሊሲዎችን ለማስተላለፍ ብዙ ሙከራ አድርገዋል ።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ድክመቶች ቢኖሩበትም በቻርተሩ የተጠቀሱትን መርሆችና ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ብዙ ጥሯል ። ዓለም አቀፍ ሰላምና ፀጥታ እንዲጠበቅና አደገኛ የነበሩ ዓለም አቀፍ ውጥረቶች እንዲፈቱ አስተዋጽኦ አድርጓል ። የሶሻሊስት ሀገሮችና ሰላም ወዳድ የሆኑ ኃይሎችም የዓለምን ሰላምና ፀጥታ ለማስከበር ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጎን ይቆማሉ ።

(የተባበሩት መንግሥታት ፀጥታ ምክር ቤትን ይመለከቷል ።)

## ተባበሩት መንግሥታት ፀጥታ ምክር ቤት (የ—)

*(U. N. Security Council)*

በመንግሥታት መካከል ሊነሡ የሚችሉትን ዓለም አቀፍ አለመግባባቶችና ወረራዎች ለማስወገድ ፣ የዓለምን ሰላምና ደኅንነት ለመጠበቅ የተቋቋመ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅታዊ አካል ነው ። ምክር ቤቱ አምስት ቋሚ አባላት (ሶቭዬት ኅብረት ፣ ቻይና ፣ አሜሪካ ፣ እንግሊዝና ፈረንሳይ) እንዲሁም ሌሎች በየሁለት ዓመቱ የሚመረጡ አሥር ሀገሮች በጠቅላላው አሥራ አምስት አባላት አሉት። ምክር ቤቱ የሚያሳልፋቸውን ውሳኔዎች ለመቀበልና በሥራ ለመተርጎም አባል ሀገሮች የስምምነት ውል መግባታቸው በተባበሩት መንግሥታት 'ድርጅት ቻርተር ላይ ተጠቅሷል ።

በሥነ ሥርዓት ጉዳዮች ላይ የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔዎች በዘጠኝ አባላት የሚጸድቁ ሲሆን ፣ ከበድ ባሉ ጉዳዮች ላይ ግን ከዘጠኙ ውስጥ የአምስቱም ቋሚ አባላት ስምምነት መኖር አለበት። ይህም ድምፅን በድምፅ የመሻር ሥልጣን በመባል የሚታወቀውና ሶቭዬት ኅብረት ፣ አሜሪካና እንግሊዝ በ19

45ቱ የያልታ ስምምነት የተቀበሉት ነው ። አንድ አከራካሪ ጉዳይ በሰላማዊ መንገድ እንዲያልቅ ውይይት በሚደረግበት ወቅት ጉዳዩ የሚመለከተው ሀገር ድምፅ የመስጠት መብት አይኖረውም ።

ፀጥታው ምክር ቤት ሰላምን የሚያደፈርስ ሁኔታ መኖሩን ሲያረጋግጥ ዓለም አቀፍ ሰላምና ደኅንነት የሚረጋጋበትን ሐሳብ ያቀርባል ወይም አስፈላጊ የሆነውን እርምጃ ይወስዳል ። በዚህም መሠረት አባል ሀገሮች ከኃይል እርምጃ በመለስ ለምሳሌ የኢኮኖሚና የመገናኛ ግንኙነታቸውን እንዲያቋርጡ ወይም ጥቃትና ወረራ ከተፈጸመበት ሀገር ጎን በመቆም ወታደራዊ ድጋፍ እንዲሰጡ ያደርጋል ። ፀጥታው ምክር ቤት እርምጃ እስከሚወስድ አባልሀገሮች በተናጠል ወይም በጋራ ራሳቸውን ከጠላት ሊከላከሉ ይችላሉ ። ፀጥታው ምክር ቤት ሥራዎቹን እንዳስፈላጊነቱ ልዩ ልዩ ኮሚሽኖችንና ኮሚቴዎችን በማቋቋም ያከናውናል ።

በአጠቃላይ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በተቋቋመበት ዓላማ መሠረት በተለይ ለዓለም ሰላምና መረጋጋት አደገኛ የሆኑ ውጥረቶችን በማቀዝቀዝና ከተቻለም በማስወገድ ረገድ የፀጥታው ምክር ቤት ጠቃሚ አስተዋጽኦ ያለው ቢሆንም በተለይ አብዛኛዎቹ የምክር ቤቱ ቋሚ አባላት የምዕራብ ኃያላን መንግሥት መሆንና እነዚህም ድምፅን በድምፅ በመሻር መብታቸው ተጠቅመው ተፅዕኖ ስለሚያደርጉ ሁኔታው የምክር ቤቱን ዐቅም ውሱን አድርጎታል ። በዚህ ምክንያት ምክር ቤቱ የሚጠቀምበትን ያህል ለማከናወን ባለመቻሉ በተለይ ድምፅን በድምፅ የመሻር ሥልጣን ይዞታን በሚመለከት በተለያዩ ጊዜያት ሐሳቦች ቀርበዋል።

## ተናሥአት
*(Uprising)*

> ተንሥአ ከሚለው ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙም መነሣሣት ማመፅ ፣ ማለት ነው ።

የተወሰኑ ማኅበራዊ ክፍሎች ወይም መደቦች ያለውን የፖለቲካ ሥልጣን በመቃወም ለመብታቸው መከበር የሚያካሂዱት እንቅስቃሴ ነው ። ተናሥአት ከትጥቅ ትግል ጋር ሲቀናጅ ወደ አመፅነት የሚሸጋገርና የተጠናከረም ይሆናል ። የተደራጀ ተናሥአት ሕዝባዊነት ያለውና ከምላ ጉደልም አብዮታዊ ዓላማዎች ያሉት ቢሆንም ግልጽ የሆነ ግብና የተደራጀ አመራር ሳይኖረው በግብታዊነትና በተበታተነ ሁኔታ የሚካሄድ ተናሥአትም አለ ። የግብታዊ ተናሥአት ጠቀሜታ በሚያጋጥመው ቅዋሜና በሂደትም በሚያገኘው አመራር የሚወሰን ቢሆንም በአመዛኙ ውጤታማነቱ አጠራጣሪ ነው ።

ማርክሳውያን የተናሥአትን ይዘትና ጠቀሜታ የሚያዩት የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ ከሚደረገው አጠቃላይ የፖለቲካ ትግል ጋር በተያያዘ ሁኔታ ነው ። አድኃሪ መደቦች ሥልጣን ላይ ለመቆየት በኃይል ሲጠቀሙና አብዮታዊ ኃይሎችን በጉልበት ለማፈን ሲሞክሩ ሕዝባዊ ተናሥአት በትጥቅ ትግል ጭምር ተጠናክሮ መካሄድ እንደሚያስፈልገውና ሥልጣን በአመፅ እንዲያዝ መታገሉም ግዴታ እንደሚሆን ማርክሳውያን ያምናሉ ። ይህ ዓይነቱ ሕዝባዊ ተናሥአት ለታለመለት ግብ እንዲበቃ ለማድረግ ግን በተደራጀ መልክ መካሄድና በአብዮታዊ ኃይሎች መመራት አለበት ።

(አመፅን ፣ አብዮትን ይመለከቷል ።)

## ተናክአታዊ ቁስአካልነት
*(Mechanical Materialism)*

> ተናክአ ከሚለው የግዕዝ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም መነካካት ማለት ነው ።

ዓለም የተሠራው ቁሳዊ ከሆኑ ብናኞችና ግንኙነቶች ነው የሚል ፍልስፍና ነው ። ብናኞች ራሳቸውን ችለው የሚኖሩ ሲሆን በአጠቃላይ ግንኙነታቸውና ውስብስብ አወቃቀራቸው ዓለምን ይመሠርታሉ ። ግንኙነቶቹ የሚመነጩት ከተናክአታዊ እንቅስቃሴ ነው ፤ ማለትም የብናኞቹ ግንኙነት የሚፈጸመው በውጫዊ ንክኪት ነው ። እንቅስቃሴው ተናክአታዊ ወይም ከንክኪት የሚመጣ መሆኑ ዓለም ከሐሳብ ወይም ንቁ ከሆነ ፈጣሪ እንዳልመነጨ የሚጠቁም የተናክአታዊ ቁስአካልነት መሪ ሐሳብ ነው ። በዚህ ፍልስፍና መሠረት ዓለም በአጠቃላይ ውስብስብ የሆነ ማሽን ነው ።

በተናክአታዊ ቁስአካልነት አመለካከት አንድን ነገር መረዳት ማለት እንዴት እንደሚሠራ ማወቅ ማለት ነው ። እንዴት እንደሚሠራ ለማወቅ የምንችለው ውስጡ ባሉት ብናኞችና ክፍሎች መካከል ያለውን ግጥም

ጥምሸና የእርስ በርስ ንክኪት በማየት ነው። የሰዓትን አሠራር ማወቅ የምንችለው የተለያዩ ዕቃዎች በመነካካት እንዴት እንደሚንቀሳቀሱ ስናይ ነው ። ዓለምን የምናውቀው የቁሳዊ ብናኞችን ግጥምጥምሸና ንክኪት በማጤን ነው ። በተጨማሪም አንድ ነገር እንዴት እንደሚሠራ ካወቅን ልንጠግነው ፣ ልናሻሽለውና ልንለውጠው በለምንችል ያለን ተናክእታዊ ዕውቀት ለተግባራዊ እንቅበቃሴአችን ጠቃሚ ነው ።

ተናክእታዊ ቁስአካልነት በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ የተጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው ። በአንድ በኩል በአመለካከቱ የሳይንስን በተለይ የተናክእትን ሳይንስና ዕድገት ያገዘና ያበረታታ ሲሆን በሌላ በኩል ሐሳባዊ ፍልስፍናን በመዋጋት ቁስአካልነትን እራም ዷል ። በሐሳባዊ ፍልስፍና አመለካከት አመጣጥ ፣ ምንነትና ለውጥ የሚያንፀባርቁት የሐሳብን ፍላጎት ወይም ግብ ነው ። የተናክእታዊ ቁስአካልነት ታላቁ አስተዋጽኦ ማንኛውንም ነገርና ክስተት ከቁስአካል ሁኔታና ሕግ አንፃር ብቻ ለመረዳት መሞከሩ ነው ። ቁስ አካል እራሱን በራሱ ያስረዳል የሚለውን መርህ በመያዝ መንፈሳዊ ምክንያቶችን ለማስወገድ ጥሯል ።

ይህ ፍልስፍና የተስፋፋው በ17ኛውና በ18ኛው ምዕት ዓመት መሆኑ የሚያስረዳው በጊዜው ተራማጅ የነበረውን የቡርዧርዕዮተዓለምና ጥቅም የሚያንፀባርቅ መሆኑን ነው ። በሐሳባዊነት በተለይም በሃይማኖት የበላይነት ላይ ተመሥርቶ የነበረውን የፊውዳል ርዕዮተዓለም ለመገርሰስ ተናክእታዊ ቁስአካልነት አስፈላጊ አመለካከት ነበር ። ኅብረተሰብን በሚመለከት ረገድ በጊዜው ተራማጅ የነበሩ ሐሳቦችን አፍልቋል ። ተናክእታዊ ቁስአካላውያን ሰዎችን እራሳቸውን እንደቻሉ አቶሞች አድርጎ በመውሰድ ፣ በትክክል ሊሠራ የሚችል ኅብረተሰብ ሊመሠረት የሚችለው በምን ዓይነት ግንኙነትና መዋቅር ነው የሚለውን ጥያቄ በማንሣት የኅብረተሰብን ለውጥ አስፈላጊነት ከማስተማራቸውም በላይ አንዳንዶቹ የተምኔታዊ ሶሻሊዝም መሥራች ለመሆን በቅተዋል ።

ሆኖም ተናክእታዊ ቁስአካልነት ዓይነተኛና መሠረታዊ ድክመቶች ነበሩት ። ዓለምን የነገሮች ጥርቅም አድርገው በመመልከታቸው ተናክእታዊ ቁስአካላውያን የዓለምን ሞና ጠባይ ማለትም የዕድገትን የማያቋርጥ ሂደት እውንነት ሊመለከቱ አልቻሉም ። በእነሱ አመለካከት የአዲስ ነገሮች መፈጠር የዕድገት ሂደት ውጤት ሳይሆን ከዕድል ወይም ከአጋጣሚ የሚገኝ የግጥምጥምሽ ውጤት ነው ። የእንቅስቃሴን የተለያዩ ቅርፆች (ኬሚካላዊ ፣ ሥነ ሕይወታዊ ወዘተ...) አለማጤናቸውና እንቅስቃሴን በአጠቃላይ ተናክእታዊ ብቻ አድርገው መውሰዳቸው ሌላው ድክመታቸው ነው ። ዓለም ውስብስብ ማሽን ነው የሚለው አመለካከታቸው እንኳን ይህን ማሽን ማን ፈጠረው የሚል ጥያቄ ከማስነሣቱም በላይ የዓለም ማሽንነት የሐሳብን ፈጣሪነት ይጠይቃል ወደሚል ሐሳባዊ ድምደማ የሚወስድ ነው ። ውስብስብ የሆኑትን የኅብረተሰብንና የሐሳብን እንቅስቃሴዎች በተናክእታዊ ዘዴ እንረዳለን ማለታቸው ተጨባጭ ያልሆኑና የተሳሳቱ የሥነ ዕውቀትና የፖለቲካ አስተሳሰቦች እንዲኖራቸው አድርጓቸዋል ።

(ሥነ ግብን ፣ ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነትን ፣ አቶሚዝምን ፣ ቁስአካልነትን ይመለከቷል ።)

## ተንገዋላይ ትረፈ ሕዝብ
*(Floating Surplus Population)*

በካፒታሊስት ሀገሮች አንዴ በምርት ተግባር ውስጥ በመሳተፍ ፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ ከምርት ተግባር ውጭ የሚገኙትን ሰዎች የሚያመለክት የአንፃራዊ ትረፈ ሕዝብ አንዱ መልክ ነው ። የተንገዋላይ ትረፈ ሕዝብ ዓይነተኛ ጠባይ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ በግንባታና በድራት ደረጃ ላይ በሚገኝበት ጊዜ ቁጥሩ የመቀነስ አዝማሚያ ሲኖረው ኢኮኖሚው በቀውስና በዝቅጠት ደረጃ ላይ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ የማደግ አዝማሚያ ያሳያል ።

ተንገዋላይ ትረፈ ሕዝብ ጎልቶ የሚታየው በኢንዱስትሪም ሆነ በሌሎች የሥራ መስኮች የተሰማሩ ሠራተኞች በሚገኙባቸው በከተሞችና በኢንዱስትሪዎች አካባቢዎች ሲሆን የምንዳ ደረጃ (አንፃራዊ በሆነ መንገድ) እንዲያቆለቁል ያደርጋል ።

ምንም እንኳን ተንገዋላይ ተፈፈ ሕዝብ ከላይ እንደተጠቀሰው አንዴ በምርት መስክ ውስጥ የሚገኙትን በሌላ ጊዜ ደግሞ ከምርት መስክ ውጭ የሚሆኑትን ሥራ አጦች

የሚያመለክት ቢሆንም ከምርት መስክ ውጭ በሚቆዩበት ወቅት በሚፈጠሩት የቴክኖሎጂ ዕድገትና የምርት አደረጃጀት ለውጦች ምክንያት አንዳንዶቹ በቀድሞ ሙያቸው ሊሰማሩ የሚችሉበት የምርት መስክም እየጠፋ ስለሚሄድ ሙያየለሽ ይሆናሉ ።

## ተዘዋዋሪ ካፒታል
*(Circulating Capital)*

ባንድ የምርት ሂደት ውስጥ እሴቱን በከፊል ሳይሆን ሙሉ በሙሉ አዲስ ወደሚመረተው ሸቀጥ በማስተላለፍ ሸቀጡ ከተሸጠ በኋላ በገንዘብ መልክ ወደ ቡርዧዚው የሚመለሰው የምርታዊ ካፒታል ክፍል ነው ።

ይህም እንደጥሬ ዕቃዎችና እንደ ነዳጅ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል ። ምንም እንኳን የሥራ ኃይል በምርት እንቅስቃሴ ውስጥ እሴቱን እንደጥሬ ዕቃዎች ወደ አዲሱ ሸቀጥ ማስተላለፍ ሳይሆን አዲስ እሴት የሚፈጥር ቢሆንም የተለያዩ የምርታዊ ካፒታል ክፍሎች በካፒታል የመገለባበጥ ፍጥነት ውስጥ ባላቸው አጠቃላይ ባሕርይ አንፃር ሲታይ በተዘዋዋሪ ካፒታል ሥር ካሉት እምብዛም ልዩነት የሌለው በመሆኑ በተዘዋዋሪ ካፒታል ሥር ይመደባል ።

ምርታዊ ካፒታልን በተዘዋዋሪና በነባር ካፒታል መከፈሉ በካፒታል የመገለባበጥ ፍጥነት ውስጥ የተለያዩ የምርታዊ ካፒታል ክፍሎች ያሏቸውን የተለያዩ ባሕርያት ለመገንዘብ ሲረዳ ፣ ቀደም ሲል በጠቀስነው የጋራ ባሕርይ ምክንያት ጥሬ ዕቃንና የሥራ ኃይልን አንድ ላይ ለማስቀመጥ መወሰን ግን የቡርዧዚው ትርፍ ምንጭ የተበዘበዘው የወዝአደሩ የሥራ ጊዜ መሆኑን ስለሚሸፍን አሳሳች ነው ።

(ቋሚ ካፒታልን ፣ ተለዋዋጭ ካፒታልን ፣ ነባር ካፒታልን ይመለከቷል ።)

## ተግባር
*(Practice)*

ሰዎች የህልውናቸው መሠረት የሆነውን ቁሳዊ ሀብት የሚያመርቱበትን ነባራዊ ሂደት ፣ መደቦች የሚያከናውኑትን አብዮታዊ ትግልና ዓለምን ለመለወጥ የሚፈጽሟቸውን ማኅበራዊ ክንዋኔዎች ፣ ሳይንሳዊ ምርምርንና ጥናትን የሚያመለክት የፍልስፍና ፈርጅ ነው ። ተግባር ሥራን (ምርትን) ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ክንዋኔዎችን እንዲሁም ሳይንሳዊ ምርምርንና ጥናትን ያቀፈ ሲሆን መሠረቱ ግን ሥራ ነው ።

ተግባር እያንዳንዱ ግለሰብ በስሜት አነሣሽነት የሚፈጽማቸውን ክንዋኔዎችና እንቅስቃሴዎች የሚያመለክት ሳይሆን ሰዎች ባህላቸውንና ዕውቀታቸውን የሚፈጥሩበትን አጠቃላይና ዓላማ ያለው ማኅበራዊ እንቅስቃሴን የሚያሳይ ጽንሰ ሐሳብ ነው ። ተግባር ማኅበራዊ በመሆኑ አድራጊው ኅብረተሰብ ነውና በተግባር አማካይነት የሚገኘውም ዕውቀት ማኅበራዊ ነው ።

ተግባር ፣ ሰዎች ተፈጥሮንና ኅብረተሰብን የሚለውጡበት ሂደት በመሆኑ ዕውቀትን ይገበያሉ ፤ ልምዳቸውን ያዳብራሉ ፤ ችሎታቸውንም ያሻሽላሉ ። በዚህም ጊዜ እራሳቸውን ይለውጣሉ ። የዕውቀት መሠረት ፣ የዕውቀት ዓላማና የዕውቀት ትክክለኛነት የሚረጋገጠው በተግባር ነውና ተግባር የእውነት መለኪያም ነው ።

ንድፈ ሐሳብ ከተግባር የሚመነጭ ፣ መልሶም የተግባር መመሪያ በመሆን የሚያገለግል በመሆኑ ሁለቱም የማይነጣጠሉ ናቸው ።

(ሥራን ፣ ንድፈ ሐሳብን ይመለከቷል ።)

## ተጣራ የማዟዟሪያ ወጪ (የ—)
*(Net or Genuine Cost of Circulation)*

በካፒታሊስት ኢኮኖሚ የንግድ ዘርፍ ውስጥ የንግድ ካፒታሊስቱ የገዛቸውን ሸቀጦች ወደገንዘብ ለመለወጥ እንዲችል የሚያወጣው ወጪ የተጣራ የማዟዟሪያ ወጪ ይባላል ።

የተጣራ የማዟዟሪያ ወጪ የሒሳብ መዝገብ ለመያዝ ፣ ሸቀጦችን ለማሻሻጥና ለማስተዋወቅ ወዘተ... የሚወጣ የንግድ ካፒታሊስቱ ወጪ ነው ። የንግድ ካፒታሊስቱ በዚህ ዓይነት የሥራ እንቅስቃሴ እንዲሰማሩ

የሚቀጥራቸው ሠራተኞች የሥራ ባሕርይ በመሠረቱ ኢምርታዊ ነው ። ስለሆነም ለእነዚህ ሠራተኞች የሚደረገው ክፍያ የሚገኘው በምርታዊው መስክ ከተገኘው ተረፈ እሴት ነው ። ካፒታሊዝም አሁን በደረሰበት ደረጃ በተለይ በማሻሻጥ ሥራ ላይ ያሰማራቸው ሠራተኞች ቁጥር እጅግ ከፍተኛ ነው ፤ እንዲሁም ለማሻሻጫና ለማስተዋወቂያ የሚያወጣው ወጪ መጠን በተመሳሳይ እጅግ ከፍ ያለ ነው ። ይህንን ሁሉ ወጪ ደግሞ የንግድ ካፒታሊስቱ ሸቀጦችን በሚገዙት ተገልጋይ ሕዝቦች ላይ በመጫን ለራሱ ከፍተኛ ትርፍ ያገኛል ።

(የማዚዚሪያ ወጪን ፣ ተጨማሪ የማዚዚሪያ ወጪን ይመለከቷል ።)

## ተጨማሪ የማዚዚሪያ ወጪ
*(Additional Cost of Circulation)*

የንግድ ካፒታሊስቱ ለተገልጋዮች የሚያቀርበው ሸቀጥ ለፍጆታ ብቁ እንዲሆን መዝአደሮች ቀጥሮ ሸቀጡን በማጓጓዝ ፣ በማሸግ ወዘተ... ተጨማሪ ተረፈ እሴት ለማከል የሚያወጣው ወጪ ተጨማሪ የማዚዚሪያ ወጪ ይባላል ።

ተጨማሪ የማዚዚሪያ ወጪ የሚፈጥሩት ምርታዊ ሥራዎች ናቸው ። እነዚህም ለምሳሌ እንዱን ሸቀጥ በወረቀት ፣ በማጥን ፣ በጠርሙስ ወዘተ... አሽጎ የማቅረብ ሥራ ፣ ሸቀጦችን በመጋዘን ውስጥ የማስቀመጥ ሥራ ፣ ሸቀጦችን ከተመረቱበት ስፍራ ወደሚሸጡበት ስፍራ የማድረስ ሥራ ወዘተ ... ምርታዊ ሥራዎች ሲሆኑ በዚህ የሥራ ዘርፍ ተሰማርተው የሚሠሩት ወዝአደሮች በምርታዊ ሥራቸው ሸቀጡ ላይ አዲስ እሴት ይጨምሩበታል ። በዚህ አዲስ እሴት ዝውውርን በሚመለከት ሸቀጦችን በመጨረሻ መልካቸው ለፍጆታ አመቻችተው ያቀርባሉ ። ተጨማሪ የማዚዚሪያ ወጪ የሚባለውም የንግድ ካፒታሊስቱ ለዚህ ዓይነቱ ሥራ የሚያወጣው ወጪ ነው ።

(የማዚዚሪያ ወጪን ፣ የተጣራ የማዚዚሪያ ወጪን ይመለከቷል ።)

## ተጨማሪ ተረፈ እሴት
*(Extra Surplus Value)*

የተወሰኑ ካፒታሊስቶች ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ሊያገኙት የሚችሉ የአንፃራዊ ተረፈ እሴት ዓይነት ነው። በተለይ በነፃ ውድድር ካፒታሊዝም ዘመን እያንዳንዱ ካፒታሊስት ከፍተኛ ትርፍ ለማጋበስ ባለው ፍላጎት አዳዲስ መሣሪያዎችን በመሥራት ወይም በመግዛት ድርጅቱን ይበልጥ ዘመናዊና ምርታማ ለማድረግ ይሽቀዳደማል ። በዚህ መንገድ አንዳንድ ካፒታሊስቶች ከሌሎች ካፒታሊስቶች ቀድመው አዳዲስ መሣሪያዎችንና የአሠራር ዘዴዎችን በማምረት ተግባር ላይ በማዋል የሥራን ምርታማነት ያሳድጋሉ ። እነዚህ ካፒታሊስቶች የሚያስመርቱት የእያንዳንዱ ሸቀጥ እሴትም ሌሎች ካፒታሊስቶች ከሚያስመርቷቸው ተመሳሳይ ሸቀጦች እሴት ዝቅ ያለ ይሆናል ። የሸቀጦች ዋጋም የሚወሰነው ባለው አማካይ የአመራረት ሁኔታ እንደመሆኑ ቁጥራቸው የተወሰነ ካፒታሊስቶች ሸቀጦቹን ካላቸው እሴት በላይ በሆነ ዋጋ ይሸጧቸዋል ። ሸቀጦቹ በተሸጡበት ማኅበራዊ እሴትና ባላቸው እሴት መካከል ያለው ልዩነት ተጨማሪ ተረፈ እሴት ይባላል።

የተሻሻለው የማምረት ቴክኒክ በሌሎች ካፒታሊስቶች ታውቆ በሥራ ላይ ሲውል ተጨማሪ ተረፈ እሴት ማግኘቱ ያከትማል። ለተጨማሪ ተረፈ እሴት የሚደረገው እሽቅድምድም ግን ያለማቋረጥ ይካሄዳል ። ይህ እሽቅድምድም የቴክኖሎጂ ዕድገት ቢያስገኝም በካፒታሊስቶች መካከል ያለውን ቅራኔ እያባባሰ የብዙዎችን መዳቀቅና የጥቂቶችን መበልጸግ ብሎም የሞኖፖሎችን መፈጠር ያስከትላል ። በሌላም በኩል የተሻሻሉ የማምረቻ መሣሪያዎችንና የአመራረት ዘዴዎችን ለመጀመሪያ ጊዜ በሥራ ላይ ያዋሉ ካፒታሊስቶች ተጨማሪ ተረፈ እሴት የማግኛ ጊዜያቸውን ለማራዘም በምሥጢር ስለሚይዙ ለቴክኖሎጂ ዕድገት መስፋፋት ዕንቅፋት መሆኑ ግልጽ ነው ።

(አንፃራዊ ተረፈ እሴትን ይመለከቷል።)

## ተጨባጫዊነት

*(Positivism)*

ሰውን ከሥነ መለኮት ፣ ከዲበአካልና ከመሳሰሉት በጣም ረቂቅ ፣ ጠቃሚ ያልሆኑና ትክክለኝነታቸው በተግባርና በተጨባጭ ከማይረጋገጥ አስተሳሰቦች ማላቀቅ ያስፈልጋል የሚል የሐሳባዊ ፍልስፍና አንድ አዝማሚያ ነው ። ተጨባጫውያን እንደሚሉት ዕውቀት ትክክለኛና ጠቃሚ እንዲሆን ከተፈለገ መከተል ያለብን ሕግ ፣ የአስተሳሰብና የአቀራረብ ዘዴ በተፈጥሮ ሳይንስ ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት ።

ሳይንስ የሚያጠናውና በጥናቱም የሚገነዘበው ተጨባጭ ነገሮችን በመሆኑ ፣ ሐሳብም ከተጨባጭ ነገሮች ሳይገነጠል ከልባዊና ከልምድ በሚገኙ መረጃዎች በተቀነባበረ መንገድ ሲገለገል ሳይንሳዊ መርህ ይሆናል ይላሉ ። በተጨባጫውያን አመለካከት ዕውቀት ጠቃሚ ፣ ትክክለኛና ተግባራዊም ግልጋሎት የሚሰጠው መነሾው ተጨባጩ እውነታ ሲሆንና የሰው ልጅ ረቂቅና ከዐቅሙ በላይ የሆኑ ጥያቄዎችን ትቶ ግንዛቤውን በተጨባጭ እውነታ ላይ ብቻ ሲወስን ነው ።

በእነሱ ሐሳብ ዕውቀት ሦስት ደረጃዎችን የሚያልፍ ነው ፤ የመጀመሪያው ደረጃ ነገሮችን በመንፈሳዊ ኃይሎች አማካይነት የምንገነዘብበት በመሆኑ የሥነ መለኮት ደረጃ ይባላል ። ሁለተኛው ከመንፈሳዊው ወደ ረቂቁ የምንተላለፍበት የዲበአካል ደረጃ ነው ። ሦስተኛው የትክክለኛና የብስለት ደረጃ ማለትም የተጨባጫዊነት ደረጃ ሲሆን የዚህም ደረጃ ባሕርይ መንፈሳዊና ረቂቅ አስተሳሰቦችን በመተው ነገሮችን ከተጨባጭ ግንኙነታቸው አንፃር ለመረዳት የምንነሣበት ደረጃ ነው ።

ተጨባጫዊነት ከዳሳሽነት የሚለይበት ነጥብ ለዳሳሾች የዕውቀት ምንጭ ልምድ ሲሆን ተጨባጫዊነት ግን ይህንን አባባል በሙሉ ሳይቃወም ልምድ ሲባል ግን በአጋጣሚ የሚገኘው ሳይሆን ለዕውቀት አመች በሚሆን መንገድ አበጅተን ፣ አቀነባብረንና አስተካክለን የምንቀይሰው ነው ይላል ። ዕውቀትን ለማግኘት ነገሮችን እንዳሉ መቀበል ሳይሆን ተጨባጭ በሆነ መንገድ መመልከት ያስፈልጋል ። ተጨባጫዊ የምንሆነው ነገሮችን እንድንጠቀምባቸው የሚረዳንን ዘዴ ቀይሰንና በርሱም እማካይነት ለዕውቀት ብቁ ወይም አመች ስናደርጋቸው ነው ።

በተጨባጫዊነት ውስጥ ተጨባጭ የሚለው ጽንሰ ሐሳብ ሲታይ ባንድ በኩል ተጨባጩ ነባራዊነት ያለው አይመስልም ። ምክንያቱም ተጨባጩ ሆን ተብሎ በኛው የተቀነባበረ ፣ የተስተካከለና በርሱም ብቻ አንድን ወሰን የሚጠይቅ በመሆኑ ነው ። በሌላም በኩል ከተጨባጩ ሁኔታ ባሻገር ከዐቅማችን በላይ የሆነ እውነታ እንዳለ አድርጎ የሚገምትም በመሆኑ ተጨባጫዊነት ወደ ኢታዋቂነት ያመራል ።

ተጨባጩ ነባራዊ ክስተት ነውና የምንረዳው በተናጠል ሳይሆን በክስተቶች ሥርዓትነቱ ነው ። እነዚህ ክስተቶች ደግሞ እኛ የምናበጃቸው ሳይሆኑ ከነባራዊ እውነታ የሚፈልቁና የርሱንም ምንነት የሚገልጹ ናቸው። ለምሳሌ የመንግሥትን አመጣጥ ፣ አስፈላጊነትና ሚና የምንረዳው ከሌሎች ማኅበራዊ ክስተቶች ነጥለን ሳይሆን ከሚፈጠርበት ስልተ ምርት ጋር በማገናዘብ ነው ። ከነባራዊ ክስተቶች ውጭ ምንም ነገር ሊኖር ባለመቻሉና የክስተቶች ምንነት የሚገለጸው በሥርዓት አማካይነት በመሆኑ ፣ ይህንን ሥርዓት የሚያንፀባርቅ ንድፈ ሐሳብ እንደ እመችነቱ የሚነደፍ ሳይሆን የነባራዊ ክስተቶችን ውስጣዊ ሕግጋት የሚያንፀባርቅ ነው ። ነባራዊውን እውነታ ከሰው ዐቅም ውጭ አድርጎ መረዳት ሰው በነባራዊ ሕግጋት የሚገዛ ሳይሆን ለራሱ በሚያመቸውና በሚቀናው ሕግ የሚመራ ነው ማለት ስለሚሆን የእውነትን ፍች ማዛባት ፣ የሕግንም የነባራዊ እውነታ ነፀብራቅነት አለመቀበል ይሆናል ። እንደተጨባጫውያን እውነት ማለት ጠቃሚና አመች የሆነ ነገር ማለት ነው ፤ ለምሳሌ የኅብረተሰብን በመደብ መከፋፈል ከጠቃሚነት አንፃር የሚተረጉሙ ስለሆነ አመለካከታቸው የገዥ መደብ ደጋፊዎች መሆናቸውን ያረጋግጣል ።

(ዳሳሽነትን ፣ ኢታዋቂነትን ፣ እውነትን ፣ ነባራዊ እውነታን ይመለከቷል ።)

## ተጨባጭ ሥራ
*(Concrete Labour)*

ማናቸውንም የተወሰነ ምርት ወይም ግልጋሎት ለማስገኘት ታስቦ ጥቅም ላይ የሚውል የሰው የሥራ ኃይል ተጨባጭ ሥራ ይባላል ።

የሰው ልጅ የሥራ ኃይሉን የሚያፈስባቸው ተግባሮች ሁሉ በተወሰኑ የምርት ተግባሮችና የምርት መሣሪያዎች በመጠቀም የተለያዩ የአሠራር ዘዴዎችን በመቀየስ የተወሰኑ ውጤቶችን ለማስገኘት የሚታቀዱ ናቸው ። ግብርና ፥ ሸክላ ሥራ ፥ አናጢነት ፥ ግንበኝነት ወዘተ ... የተለያዩ ውጤቶችን ለማስገኘት የሚታቀዱ ፥ በተለያዩ የምርት መገልገያዎች የሚከናወኑ ሥራዎች ናቸው ። ለምሳሌ ግንበኝነት ፥ ልብስ ሰፊነት ፥ አንጥረኝነት ፥ ሸክላ ሠሪነት ወዘተ ... እያንዳንዳቸው የተለያዩ ተጨባጭ ሥራዎች ናቸው ። ዋናው ተጨባጭ ሥራ የሚባለው አንድ የተወሰነ የጠቀሜታ እሴት ለማስገኘት ወይም የተወሰነ ግልጋሎት ለመስጠት የሚውል የሰው ሥራ ነው ።

ሥራ ሁልጊዜም ቢሆን የተወሰነ ግብ ያለውና ለኅብረተሰብ ህልውና አስፈላጊ የሆኑ የጠቀሜታ እሴት ያላቸውን ዕቃዎች ለማምረት የሚውል ስለሆነ ተጨባጭነት ያለው ነገር ነው ። ተጨባጭ ሥራ ኅብረተሰብ በሥራ አማካይነት መሠረታዊ ፍላጎቶቹን ለማሟላት ማምረት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ የነበረ ታሪካዊ ፈርጅ እንደመሆኑ ከተለያዩ ሥርዓተ ማኅበራት ባሕርያት ጋር ያልተያያዘ የኅብረተሰብ ህልውና መሠረት የሆነ ዘላቂነት ያለው ፈርጅ ነው ።

(ረቂቅ ሥራን ይመለከቷል ።)

## ተፃራሪና ኢ-ተፃራሪ ቅራኔዎች
*(Antagonistic and Nonantagonistic Contradictions)*

ተፃራሪ ቅራኔ የሚገልጸው ጥቅማቸው ጨርሶ ሊጣጣም በማይችል በሁለት መደቦች መካከል ያለውን የግንኙነት ዓይነት ነው ። ተፃራሪ የተባለበትም ዋና ምክንያት ቅራኔው [illegible]ያው ባለው ማኅበራዊ ሥርዓት ውስጥ ሊፈታ የማይችል በመሆኑ አይቀሬ የሥርዓት ለውጥ ስለሚያስከትል ነው ። የተፃራሪ ቅራኔ ዓይነተኛ ጠባይ ቅራኔው በየጊዜው እየሰፋና እየከረረ መሄዱና በተወሰነ ደረጃ ላይ ከፍተኛ ግጭትና አመፅ በማስከተል ወደ አብዮታዊ ሁኔታ ማምራቱ ነው ።

ኢ-ተፃራሪ ቅራኔዎች የሚገልጹት በሁለት መደቦች ወይም የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል ያለውን መሠረታዊ ያልሆነ ቅራኔ ሲሆን ግጭታቸውም ወደ ኅብረተሰብ ለውጥ የማይወስድ ነው ። ማለትም ቅራኔው ቀስ በቀስ የሚፈታ እንጂ አብዮትን የሚጠይቅ አይደለም ። በወዝአደሩና በአርሶ አደሩ መካከል ያለው ቅራኔ እንደምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል ። ወዝአደሩና አርሶአደሩ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ የሚገኙ በመሆናቸው በተለይም በገበያ አካባቢ በሁለቱ መደቦች መካከል ቅራኔ ይታያል ። ሆኖም ቅራኔው ሁለቱም ከሚገኙበት ትክክለኛ ሁኔታ አንፃር ማለትም ሁለቱም ተበዝባዥ መደቦች ከመሆናቸው አንፃር ሲታይ መሠረታዊ አይደለም ። መሠረታዊ ባለመሆኑ ነው የጋራ ጠላታቸውን በአንድነት ለመዋጋት ከስምምነት ላይ መድረስ የሚችሉት ።

(መሠረታዊና ኢ-መሠረታዊ ቅራኔን ይመለከቷል ።)

## ተፈጥሮ ሕግጋት (የ—)
*(Natural Laws)*

በተፈጥሮ ውስጥ በሚገኙ ክስተቶችና ሂደቶች መሀከል የሚታዩ ግንኙነቶችን የሚገልጹ ሕግጋት የተፈጥሮ ሕግጋት ይባላሉ ። እነዚህ ክስተቶችና ሂደቶች ከሰው ፍላጎትና ኅሊና ውጭ ነፃ ህልውና ያላቸው በመሆናቸው ነባራዊ ናቸው ። ስለዚህ በነዚህ ነባራዊ ነገሮች መሀከል ያሉትን ግንኙነቶች የሚገልጹት ሕግጋትም ነባራዊ ናቸው ።

የተፈጥሮ ሕግጋት ሦስት መሠረታዊ ባሕርያት አሏቸው ። በመጀመሪያ በተፈጥሮ ውስጥ የሚታዩ ድርጊቶች ተፈጥሮአዊ ምክንያት አላቸው ። እነዚህ ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች ደግሞ የጭፍንነትና የግብታዊነት ባሕርይ ይታይባቸዋል ። ለምሳሌ ዝናብ ሲዘንብ መሬቱ ይርሳል ፤ ወንዞች ይሞላሉ ፤

ነፋስ ሲነፍስ አቧራ ያስነሣል ፤ ዛፎችን ያወዛውዛል ፤ ደመናን ያጓጉዛል ። በዚህ መልክ ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች ተመሳሳይ ባሕርይ ያላቸው ውጤቶችን በማያቋርጥ ሁኔታ ያስገኛሉ ። እነዚህ ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች ሊገለጹ ፣ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ሊተነተኑ ይችላሉ ። ያም ሆኖ ግን ማንኛቸውም ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች በግብ የሚከናወን እንቅስቃሴ ውጤቶች አይደሉም ።

ሁለተኛው ባሕርያቸው ደግሞ የተፈጥሮ ክስተቶች ሳይለዋወጡ እንዳሉ የሚደጋገሙ መሆናቸው ነው ። ፀሐይ ጠዋት ጠዋት በምሥራቅ ትወጣለች ፤ ማታ ማታ ደግሞ በምዕራብ ትጠልቃለች ። ሰዎች ይወለዳሉ ፤ ያድጋሉ ፤ ይሞታሉ ። ብረት ሙቀት ሲያገኝ ይለጠጣል ። በተፈጥሮ ውስጥ ፍጹማዊ ድግግሞሽ ባይኖርም ፣ በተለያዩ ተፈጥሮአዊ ክስተቶችና ሂደቶች ውስጥ የሚታየውን ድግግሞሽ በቀላሉ ለማየት ይቻላል ። ይህም የተፈጥሮ ክስተቶች ድግግሞሽ ስለክስተቶች ለማጥናትና ሕግጋታቸውን ለማወቅ ያስችላል።

በመጨረሻም የተፈጥሮ ክስተቶች ፣ በነርሱም መሀከል ያሉትን ግንኙነቶች የሚገልጹት ሕግጋት የማንንም መደብ ጥቅም ስለማያንፀባርቁ የመደብ ጠባይ የላቸውም ።

(ሕግን ፣ ማኅበራዊ ሕግጋትን ይመለከቷል ።)

## ተፈጥሮአዊነት
*(Naturalism)*

የኅብረተሰብን ዕድገት መሠረታዊ መንሥኤዎች በአየር ንብረት ሁኔታዎች ፣ በመልክአ ምድር አካባቢዎች ፣ በሥነ ፍጥረትና በሰው ልጆች መካከል ባሉ የቀለም ወይም የዘር ልዩነቶችና በመሳሰሉት ላይ በተመሠረቱ ተፈጥሮአዊ ሕጎች አማካይነት ለመግለጽ የሚጥር ፍልስፍና ነው ። ከዚህም የተነሣ ተፈጥሮአዊነት ከአጠቃላይ የተፈጥሮ ሕጎች ሌላ የማኅበራዊ ሕይወትን ዕድገት የሚገዙ የተለዩ ሕጎችን መኖር ይክዳል ።

በእርግጥ ተፈጥሮአዊነት ሁሉም ነገር የሚገዛው በተፈጥሮ ሕጎች ነው ብሎ መናገሩ መንፈሳዊነትን ለመዋጋት የጠቀመ ቢሆንም የኋላ ኋላ ግን አድኃሪና ሐሳባዊ አቋሙ እየጐላ መጥቷል ። በተለይም ይህ ፍልስፍና ከ19ኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ የተንፀባረቀው በሥነ ውበት አመለካከት ውስጥ ነው ። ይህ አስተምህሮ ሥነ ውበትና የኪነት ውጤቶች ፣ የክስተቶችና የሁኔታዎች ቀጥተኛ ግልባጭ ውጤቶች ከፖለቲካና ከግብረገብ ውጭ እንደሆኑ ለማሳመን ጥሯል ። በተለይ በአሁኑ ዘመን በሕይወት አካላዊ ገጽታና በተፈጥሮአዊ ስሜቶች እርካታ ላይ በማተኮር በስለላ ታሪኮች ፣ በቀማኞች ፊልሞች ፣ በወሲባዊ ስሜት ቀስቃሽ ሥዕሎች ወዘተ... አማካይነት ስሜትን ለመቀስቀስ ይሞክራል ። ባጠቃላይ በአሁኑ ጊዜ ከማኅበራዊ ትግል መሸሽ ፣ ለሕዝቡ ደስታና ሥቃይ ደንታቢስ መሆን ፣ ብልሹ በሆኑ የሕይወት ገጽታዎች ላይ ማተኮር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በተፈጥሮአውያን የሚሰበኩ ሐሳቦች ናቸው ።

በሥነ ምግባር ረገድ ተፈጥሮአዊነት ግብረገባዊ ፋይዳዎች የሚመነጩት ከተፈጥሮአዊ ማለትም ከደስታ ፍላጎት ፣ ሥነ ሕይወታዊ ዝግመተ ለውጥ ከሚያስከትለው የኃይልና የበላይነት ፍላጎት ወዘተ... ነው የሚል ንድፈ ሐሳብ ነው ። ሆኖም በ1940ዎቹና በ1950ዎቹ ውስጥ በተወሰኑ ተፈጥሮአውያን አማካይነት ሥነ ምግባርን አስመልክቶ አንዳንድ ሳይንሳዊ መርሆች ተሰንዝረዋል ። እነሱም አንደኛ ፣ ሰናይ የሚለው የግብረገብነት ፋይዳ ነባራዊ ነው ፤ ምክንያቱም ከማኅበራዊ ሥርዓት ፣ ከሰዎች ጥቅምና ፍላጎት ጋር የተያያዘ ነው ። ሁለተኛ ፣ ሰናይ የሚለው ጽንሰ ሐሳብ ይዘት ሊወሰንና የተለያዩ ግብረገባዊ ደረጃዎቹም በነባራዊነት ሊረጋገጡ ይችላሉ ፤ ሦስተኛ ፣ ግብረገባዊ ብያኔዎች ነባራዊ ጠቀሜታ አላቸው ፤ ይህም ሊገለጽና ሊረጋገጥ ይችላል ። አራተኛ ፣ በሌሎች ማኅበራዊ ሳይንሳዊ መረጃዎች ላይ ከተመሠረቱ የሥነ ምግባርና የግብረገብ መርሆች ሳይንሳዊ ሊሆኑ ይችላሉ የሚሉ ናቸው ።

ሐሳባውያን ስለሥነ ምግባር ያላቸውን አቋም አስመልክተው ተፈጥሮአውያን የሰነዘሩት ትችትና በንድፈ ሐሳቦቻቸውም ውስጥ ያራመዷቸው ሐሳቦች ቁስአካላዊ ሐሳቦችን ያንፀባርቁ በመሆናቸው ተራማጅ ገጽታ አሳይተዋል ። ይሁን እንጂ በተፈጥሮአዊነት

ውስጥ አንዳንድ ቁስአካላዊ አስተሳሰቦች የታቀፉ ቢሆንም ማርክሲዝም እንዳስረዳው ከተፈጥሮአዊ አቋሞች በመነሣት ለሥነ ጥበብም ሆነ ለኅብረተሰብ ፈርጆች ዘላቂ የሆነ ሳይንሳዊ ትንተና ለማድረግ አይቻልም ።

(ዳርዊኒዝምን ይመለከቷል ።)

## ተፈጥሮአዊ ኢኮኖሚ
*(Natural Economy)*

ተፈጥሮአዊ ኢኮኖሚ እምራቹ ግለ ሰብ ለመሸጥና ለመለወጥ ሳይሆን በቀጥታ የራሱን ፍጆታ ብቻ ለማርካት የሚያካሂደው የማምረት ተግባር ነው ። በዚህ ዓይነቱ ሂደተ ምርት ውስጥ አምራቹ የማምረቻ መሣሪያዎችን ከማምረት እንሥቶ ለፍ ጆታ ብቁ የሆኑ የምርት ውጤቶችን እስ ከማምረት ድረስ ሁሉ ባለው ሂደተ ሥራ በመሳተፍ ፍላጎቶቹን ያረካል ።

ተፈጥሮአዊ ኢኮኖሚ የማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል ፥ የማኅበራዊ ልውውጥና የግል ሀብት ይዞታ ባልነበረበት የኅብረተ ሰብ ዕድገት ደረጃ የተከሰተ ሲሆን በባሪያ፣ አሳዳሪውና በፊውዳሉ ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ ምንም እንኳን የሸቀጦች ልውውጥና የሸቀጦችና የገንዘብ ግንኙ ነት ይካሄዱ የነበረ ቢሆንም በነዚህ ሥር ዓቶች ውስጥም ተፈጥሮአዊ ኢኮኖሚ ዋንኛው ክፍል ሆኖ ቆይቷል ።

በተፈጥሮአዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለው የምርት ሥራ እንቅስቃሴ ጥንታዊና ልማ ዳዊ የአሠራር ዘዴዎች የሚታዩበት ፥ የምርት ሥራ ቅልጥፍና እጅግ በዝቅተኛ ደረጃ የሚጓዝበትና በአጠቃላይ ኋላቀር የምርት ሥራ አደረጃጀት የሰፈነበት ነው ። በብዙ የኋላቀር ሀገሮች ውስጥ ዛሬ ገበሬዎች በእርሻና በከብት ርባታ ሥራ ከመሰማራታቸው ሌላ በየቤታቸው ውስጥ ቆዳ በማልፋት ፥ ገመድ በመግመድ ፥ ቅርጫት በመሥራት ፥ እንጨት በመጥረብና ጨርቅና ሸክላ በመሥራት ይጠቀማሉ ። ይህ ሁኔታ በጉልህ የተፈጥሮአዊ ኢኮኖ ሚን የሥራ ባሕርይ ያሳያል ።

## ቱርጎ ፥ ሮቤር ዣክ
*(Turgot, Robert Jacques)*

ከ1727—1781 የኖረና ፊዝዮክራቶች በመ ባል ከሚታወቁት የፈረንሳይ ብሉይ ኢኮኖ ሚስቶች አንዱ ነበር ። ቱርጎ በሃያ ሦስት ዓመቱ ከፈረንሳይ ዝነኛ ከፍተኛ ኮሌጅ ከሶ ርቦን በከፍተኛ ማዕረግ በዲግሪ ተመረቀ ። ቱርጎ በሃያ ሁለት ዓመቱ "ስለወረቀት ገን ዘብ" ጥናታዊ ጽሑፍ አቀረበ ። ሆኖም ከፍ ተኛው የቱርጎ የኢኮኖሚ የምርምር ጽሑፍ በ1776 ያቀረበው "ሬፍሌክሲዮን ሲዩር ላ ፎርማሲዮን ኤ ላ ዲስቲሪቢዩሲዮን ዴ ሪሼስ" የተባለው ዝነኛው ጽሑፉ ነው ። ቱርጎ በዚህ የምርምር ጽሑፉ በጥልቀት ካብራራቸውና ካቀረባቸው ጽንሰ ሐሳቦች ውስጥ "የተጣራ ምርት" የሚለው ዋንኛው ነው ። ይህ የቱርጎ ሐሳብ በተዘዋዋሪ መንገድ "ትረፈ እሴት" ከሚለው ጽንሰ ሐሳብ የተጠጋ ነው ። በተ ጨማሪም ቱርጎ በተለያዩ ጥናታዊ ጽሑፎች ውስጥ ስለ እሴት ፥ ስለ ዋጋና ስለገንዘብ በር ካታ ትንተናዎችን አቅርቧል ።

ቱርጎ "የተጣራ ምርት" ወይም "የተ ጣራ ገቢ" ምንጭ አድርጎ የወሰደው የእር ሻን ሥራ ብቻ ነው ። ይህ ሐሳብ መሠረታዊ የሆነው የፊዝዮክራቶች አስተያየት ዋና ድክ መት ነው። ቱርጎ ከእርሻ ክፍለኢኮኖሚ ውጭ የኢንዱስትሪ ፥ የንግድ ፥ የብድርና የሌሎች የካ ፒታል መልኮችን አፈጣጠር በሚመለከት የተ ወሰኑ ጥናቶችን አድርጓል ። ከእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ውጭ ካፒታል የሚመነ ጨውና የሚ ስፋፋው ሰዎች በሚያደርጉት ቁጠባ ፥ የኢኮ ኖሚ ቁጥጥርና ሌሎች ጥረቶች ነው በማለት ጽፏል ።

የሸቀጦችን ዋጋ በሚመለከት ቱርጎ አንድ ሸቀጥ ለተገልጋዩ በሚሰጠው እርካታ ፥ ሸቀጡ በቀላሉ ሊገኝ በመቻሉና ባለመቻሉ ፥ በሸቀጡ እጥረት ሁኔታና በሻጩና በገዥው መካከል ባሉት የፍላጎቶች ዕምቀት ይወሰናል በማለት አቅርቧል ።

ፊዝዮክራቶች በጥናታቸው ውስጥ በጊ ዜያቸው የነበረውን ኅብረተሰብ በሦስት በመ ከፈል "የምርታማ መደብ" (ገበሬዎችን) ፥ የባለንብረት መደብ (የመሬት ባለቤቶችን) እና ሌሎቹን በጥቅሉ መካን መደብ ብለው በመሰየም ከፋፍለዋቸው ነበር ። ቱርጎ ባደረ

ገው ጥናት ደግሞ በጥቅሉ በአንድ መደብ ውስጥ ተሰይመው የተቀመጡትን እነዚህን ከምርታዊና ከባለንብረት መደቦች የተለዩትን በሁለት በመከፈል አቀረበ ። አንደኛውን የኢንዱስትሪ ካፒታሊስትና የኢንዱስትሪ ወዝአደር ሲል ሌላኛውን ደግሞ የእርሻ ካፒታሊስትና የእርሻ ወዝአደር በማለት መድቧቸዋል ።

ቱርጎ በፈረንሳይ ውስጥ የንጉሥ ሉዊ አሥራ ስድስተኛ የገንዘብ ሚኒስትር በመሆን ከ1774 እስከ 1776 ሠርቷል ። በሥልጣን ላይ በነበረበት ወቅት የፈረንሳይን መንግሥት የፋይናንስ ሁኔታና የታክስ ሥርዓት ለማቃለል መመሪያዎችን ነድፎ በተግባር ለማዋል ጥረት አድርጎ ነበር ። ካደረጋቸው ጥረቶች ውስጥ በንግድና በኢንዱስትሪ ላይ የነበረውን የታክስ ጫናና የመንግሥት ወጪ መቀነስ ፣ በእህልና በዱቄት ንግድ ውስጥ የነፃ ንግድ ፖሊሲ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ፣ ገበሬዎች በግዳጅ ለመንግሥት ይሰጡት የነበረውን የጉልበት ሥራ ግብር ማስቀረትና የጉልበት ሥራውን በተቀጠሩ ሠራተኞች ማካሄድ ወዘተ... ይገኙበታል ። ቱርጎ በሥልጣን ላይ በነበረበት ወቅት በወሰዳቸው የፖሊሲ እርምጃዎች የተነሣ የቤተመንግሥቱ ታላላቅ ሹማምንትና ፊውዳሎች በተቀነባበረ መንገድ ባካሄዱበት አሻጥር ሥራውን በያዘ በሁለት ዓመቱ ከሥልጣን እንዲወርድ ተደርጓል ።

(ፊዚዮክራሲን ይመለከቷል ።)

## ቱጃሮች ምስፍና (የ—)

*(Oligarchy)*

በኢኮኖሚ አቋማቸው የበላይነት ያላቸው ጥቂት ሰዎች የመንግሥት ሥልጣን የሚይዙበት የአገዛዝ ቅርፅ ነው ።

የቱጃሮች ምስፍና የሚሰው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው በጥንታዊት ግሪክ ጽሑፎች ውስጥ ነው ። ከነዚህም ጽሑፎች መካከል "ፖለቲክስ" (መጽሐፍ 4) በሚል ርዕስ የወጣው የአርስጣጣሊስ ጽሑፍ በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው ።

በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የኢንዱስትሪና የባንክ ካፒታል ከመዋሃዳቸው የተነሣ ሌላ ዓይነት የቱጃሮች ምስፍና ማለትም የፋይናንስ ምስፍና ሊከሰት ችሏል ።

## ታህታይ መዋቅር

*(Basis)*

(መሠረትን ይመለከቷል ።)

## ታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት

*(The Great October Socialist Revolution)*

በሌኒን በሚመራው ኮሚኒስት ፓርቲ አማካይነት የሩሲያ ሠራተኛ መደብ ከደሃ አርሶ አደሮች ጋር በመተባበር ጥቅምት 25 ቀን (በአዲሱ አቆጣጠር ኅዳር 7) 1917 ያካሄደው በታሪክ የመጀመሪያው ድል አድራጊ ሶሻሊስት አብዮት ነው ።

ታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት በሩሲያ ተንሰራፍቶ የነበረውን የቡርዧዚና የመሬት ከበርቴ ሥልጣን ገርስሶ የወዝአደሩን የበላይ ገዥነት የመሠረተና የሶቪዬት መንግሥትን ያቋቋመ ፣ ሩሲያ በኢንዱስትሪ እንድትበለጽግና በእርሻም ሶሻሊስታዊ ለውጥ እንዲደረግ መሠረት የጣለ ፣ ሕዝቡ በኑሮው ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንዲደርስና ባህሉንም እንዲያዳብር ያደረገ ፣ የብሔሮችንና የብሔረሰቦችን ጥያቄዎች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በመፍታት ብዙ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ተባብረውና ተጋግዘው ለመኖር መቻላቸውን ያስመሰከረ ታላቅ አብዮት ነው ።

ታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት የዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝምን ቅስም በመስበር የማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ትክክለኛነት ፣ የካፒታሊዝምን ውድቀት አይቀሬነትና የሶሻሊዝምን ድል አድራጊነት ያረጋገጠ ፣ ዓለምን በሁለት ማለትም በሶሻሊዝምና በካፒታሊዝም ጐራ የከፈለና በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ የከፈተ ነው ።

የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሐሳቦች በዓለም ዙሪያ እንዲሰራጩ በማድረግ የዓለምን ታሪካዊ ሂደት በማፋጠን ፣ ጭቁኖች ለነፃነታቸውና ለመብታቸው በጨቋኞች ላይ እንዲነሡ በመቀስቀስ በዓለም ላይ የብሩህ ተስፋ ጨረር እንዲፈነጥቅ አድርጓል።

የብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴዎችን ፣ የወዝአደሩንና የሌሎችንም አብዮታዊ ኃይሎች ትግል በማስተባበር ለዓለም አብዮታዊ ሽግግር አስተማማኝ መሠረት ጥሏል ።

በጥቅምቱ ሶሻሊስት አብዮት መሠረቱ የተጣለው የሶሻሊስት ሥርዓት በዘመናችን ከፍተኛ የፖለቲካ ኃይል ለሆነው ለዓለም አቀፍ የኮሚኒስት እንቅስቃሴ ምንጭና ለዓለም አቀፍ ሶሻሊስት ሥርዓት መሠረት የሆነ ዓቢይ ኃይል ነው ።

(ሶቭዬትን ፣ ቮልሼቪክን ይመለከቷል ።)

## ታሪካዊ ቁስአካልነት

*(Historical Materialism)*

የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ፍልስፍና አንዱ ክፍል ሲሆን የሚያጠናው መስከ የኅብረተሰብ ዕድገት ሕግጋትንና የማኅበራዊ ክስተቶችን ሥርዓት ነው ።

ሰዎች ፍላጎታቸውን ለማሟላት የሚያከናውኑት የሥራ እንቅስቃሴ ፣ የሚፈጥሯቸው ማኅበራዊ ግንኙነቶች የታሪካቸው ምንጭናቸው ፤ የሰው ልጅ ታሪክ ከምርት ተግባር የተለየ አይደለም ፤ የሰዎች ማኅበራዊ ኑባሬ በቁሳዊ ምርት ላይ የተገነባ ነው ፤ የሰዎች ሀልውና በቁሳዊ ምርት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ማኅበራዊ ኅሊናቸውም በምርት ሂደት ይወሰናል ።

ታሪካዊ ቁስአካልነት አጠቃላይ የኅብረተሰብ ሳይንስ በመሆኑ ማኅበራዊ ኑባሬን ፣ ማኅበራዊ ንቃተ ኅሊናን ፣ ሥርዓተ ማኅበርን፣ ስልተ ምርትን ፣ ማኅበራዊ አብዮትንና የመሳስሉትን ዓበይት ፈርጆች የሚያቅፍ ነው ። የእነርሱንም የዕድገትና የለውጥ አጠቃላይ ሕግጋት ያጠናል ፤ ይመረምራል ፤ ያቀነባብራል ። ሰዎች የሚያመርቱት ቁሳዊ ሀብት ብቻ ሳይሆን አስተሳሰባቸውን ፣ ዕውቀታቸውን ፣ በአንድ ቃል ንቃተ ኅሊናቸውንም ጭምር በመሆኑ ታሪካዊ ቁስአካልነት በመሠረትና በላዕላይ መዋቅር መካከል ያለውን ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት ያጠናል ።

ታሪካዊ ቁስአካልነት ከታሪክ ሳይንስ የተለየ ነው ። የታሪክ ሳይንስ በተናጠል የሀገሮችን፣ የሕዝቦችን ፣ የግለሰቦችን ወዘተ... ታሪክ የሚያጠና ነው ። ታሪካዊ ቁስአካልነት ግን አጠቃላይ የኅብረተሰብን የዕድገትና የለውጥ ሕግጋት ፣ የሥርዓተ ማኅበሮችን ፍርርቅ የሚያጠና ነው ። አንድ ኅብረተሰብ በምን የዕድገት ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ፣ ወዴትስ እንደሚያመራ ፣ የኅብረተሰቡ መሠረታዊ መደቦችና ቅራኔዎች ምን እንደሆኑ ፣ እንዴትስ ሊፈቱ እንደሚችሉ ለማወቅና ለመገንዘብ በዚህም ግንዛቤ መሠረት አንዱ ሥርዓት በሌላው እንዴት እንደሚተካ የሚያሳይ ነው።

(ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነትን ፣ መሠረትና ላዕላይ መዋቅርን ይመለከቷል ።)

## ታሪክነት

*(Historicism)*

የነገሮችንና የክስተቶችን አነሣሥ ፣ ዕድገትና ባሕርያቸውን ከሚወስኑት ታሪካዊ ሁኔታዎች ጋር በማዛመድ የሚያጠና የግንዛቤ መርህ ነው ።

ማናቸውም ነገር ፣ ሰውና አስተሳሰቡም ጭምር የተወሰነ የታሪክ ወቅት ውጤት እንደሆነና ዓይነተኛ ባሕርዩም በዚህ ሂደት ውስጥ የሚወሰን ፣ የሚለዋወጥና ወደኋላ ወይም ወደቀድሞው ሁኔታም የማይመለስ መሆኑንም ያስረዳል ። ለምሳሌ ሰው ከእንስሳ የመጣ ሲሆን ነገር ግን እንደገና ወደ እንስሳነት ሊመለስ አይችልም ። ተሰውጦና ተሻሽሎ የሚመጣው ዓይነት ወደ ቀድሞው ዝቅተኛ የዓይነት ደረጃ ሊመለስ አለመቻሉን መቀበል የዚህ መርህ ዓይነተኛ ባሕርይ ነው።

ታሪክነት ተፈጥሮና ሰው እንደዚሁም አሳቦት በእንቅስቃሴ ፣ በለውጥና በዕድገት ላይ እንደተመሠረቱና ይዘታቸውና ቅርፃቸው በደረሱበት የታሪክ ወቅት እንደሚወሰን ስለሚያስረዳ የመደብን ፣ የመንግሥትን ፣ የመሳሰሉትንና የማናቸውንም ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ምንነትና ባሕርይ ለመገንዘብ ያስችላል ። በዚህም ፣ ታሪክነት የዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት አንድ ክፍል እንደሆነ እንገነዘባለን ።

ታሪክነት ለተፈጥሮ እንቅስቃሴ አጠቃላይ ሳይንሳዊ አመለካከት የሚሰጥ ፣ ይህንን እንቅስቃሴና ለውጥ የሚገዙትን ሕግጋት የሚ

ያመለክት እንደመሆኑ ዳርዊኒዝምን ከመሳሰሉ የአዝጋሚ ለውጥ ልዩ ልዩ አመለካከቶች ጋር ግንኙነት አለው ።

(ዳርዊኒዝምን ፣ አዝጋሚ ለውጥን ፣ ይመለከቷል)

## ታሪክ ፍልስፍና (የ—)
*(Philosophy of Hisotry)*

የታሪክን ፍች ፣ ሕጐችና የዕድገት አዝማሚያዎች የሚያጠና የፍልስፍና ክፍል ነው። የታሪክ ፍልስፍና ትኩረት ተሰጥቶት ሊዳብር የቻለው በአብራሀያን ፈላስፎች ነው ። አብራሀያን በታሪክ ግንዛቤያቸው ውስጥ ምክንያታዊ ግንኙነቶችን በማስገባት የርምደት ንድፈ ሐሳብን ቀምረዋል ፤ የአካባቢውን ተፅዕኖ በማስገንዘብም ታሪክን ከነበረው ሥነ መለኮታዊ ትርጉም ለማላቀቅ ጥረዋል ። የሄግል አመለካከት ከመሠረቱ የተዛባ ቢሆንም ታሪክ በዲያሌክቲካዊ ሕጐች የሚገዛ መሆኑን ገልጿል ። ይሁን እንጂ ታሪክ በነባራዊ ሕጐች ላይ ተመሥርቶ ትክክለኛውን ግንዛቤ ያገኘው በማርክስና በኤንግልስ በተቀመረው ታሪካዊ ቁስአካልነት ንድፈ ሐሳብ ነው ።

(ታሪካዊ ቁስአካልነትን ይመለከቷል ።)

## ቴክኒካዊ የካፒታል ጥንቅር
*(Technical Composition of Capital)*

ምን ያህል የምርት መገልገያዎች (ሕንፃዎች ፣ ጥሬ ዕቃዎች ፣ ነዳጅ ፣ ኬሚካሎችና የመሳሰሉት) ከምን ያህል መጠን የሥራ ኃይል ጋር እንደተቀናጁ ወይንም ባሉት የምርት ማከናወኛ መሣሪያዎችና እነዚህኑ ጥቅም ላይ ለማዋል በሚያስፈልገው የሥራ ኃይል መጠን መካከል ያለውን ጥምርታ የሚያመለክት ነው ።

ካፒታል እየተከማቸ በሄደ መጠን ቴክኒካዊ የካፒታል ጥንቅሩም እያደገ ይሄዳል ። ማለትም በቴክኒካዊ የካፒታል ጥንቅሩ ውስጥ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት ሳቢያ የተሻሻሉ የምርት መገልገያዎች ሥራ ላይ የሚውሉበት ፍጥነት የምርት መገልገያዎቹን ለማንቀሳቀስ ከሚያስፈልገው ሥራ ኃይል መጠን ይበልጥ እያደገ ይሄዳል ። ይህም ዕድገት ወዝ አደሩ በነፍስ ወከፍ በሚገለገልባቸው የምርት መገልገያዎች መጠን ይመዘናል ።

ቴክኒካዊ የካፒታል ጥንቅሩ የእሴት መልክ ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር ይባላል ። በካፒታሊስት ሥርዓት በረዥም ጊዜ እንፃር ሲታይ በቴክኒካዊ የካፒታል ጥንቅሩ ዕድገት ሳቢያ ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅሩም እያደገ የሚሄድ በመሆኑ ጥቅም ላይ የሚውለው የሥራ ኃይል መጠን ዕድገት ከጠቅላላ ማኅበራዊ ካፒታሉ ዕድገት አኳያ እየቀነሰ ይሄዳል ። ይህም ለተጠባባቂ የሥራ እጥ ሠራዊት መበራከት ምክንያት ይሆናል ።

(ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅርን ይመለከቷል ።

## ቴክኖሎጂ አብዮት (የ—)
*(Technological Revolution)*

በዘመናዊ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝቶች በመጠቀም የምርት ኃይሎችን ዕድገት የማፋጠን ሂደት የቴክኖሎጂ አብዮት በመባል ይታወቃል ። የቴክኖሎጂ አብዮት የምርት ኃይሎች የተፋጠነ ዕድገት እንዲኖራቸው በማያቋርጥ ሁኔታ ቴክኖሎጂ ሳይንሳዊ የአሠራር ስልቶችን በመጠቀም ኢንዱስትሪዎችን በተለይም ከባድ ኢንዱስትሪዎችን የመገንባትና እንደዚሁም በከፍተኛ ምህንድስና በመጠቀም ጠቅላላውን ኢኮኖሚ የመለወጥ ሂደት ነው ።

ለሳይንስና ለቴክኖሎጂ አብዮት መሠረት የጣለው ካፒታሊዝም ነው ። ዘመናዊ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ባስገኛቸው አዳዲስ የማምረቻ መሣሪያዎች በመጠቀም ምርት ከምን ጊዜውም የበለጠ በብዛትና በጥራት እንዲመረት አስችሏል ። ካፒታሊዝም የቴክኖሎጂ አብዮትን በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች አይጠቀምበትም ። የቴክኖሎጂ አብዮትን የሚጠቀምበት ከፍተኛ ትርፍ በሚያስገኙለት የኢኮኖሚ ዘርፎች ብቻ ነው ። ምክንያቱም ከትርፍ አንፃር ስለሚመለከተው ነው ።

በካፒታሊዝም የቴክኖሎጂና የሳይንስ ዕድገት ሥር የሰደደ ቅራኔ ያዘለ ነው ። የቴክኖሎጂና የሳይንስ ዕድገት ምርት በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ የማድረግ አዝማሚያ ሲያሳይ በሌላ በኩል ደግሞ የሕዝቡ የመግዛት ዐቅም ውሱን እየሆነ እንዲሄድ የማድረግ ዝንባሌ አለው ። የገበያ መጣበብ የምርት መጠን ዕድገትን ሲገታ የሰው ኃይልን በሚቀንሱ ማለትም ዘመናዊ በሆኑ የማም

ረቻ መሣሪያዎች በመጠቀም በብዙ ሠራተኞች ይሠራ የነበረውን ሥራ በጥቂት ሠራተኞች በማሠራት የበለጠ ማምረት ስለሚያስችል አያሌ ወዝአደሮች ከሥራቸው እንዲፈናቀሉና ለሥራ አጥነት እንዲዳረጉ ይገፋፋል ።

የሳይንስና የቴክኖሎጂ አብዮት ኢኮኖሚ ማኅበራዊ እንዲሆን ያደርጋል ። የሞኖፖል የበላይነት በሰፈነበት ሥርዓት ተፃራሪ ቅራኔዎች በሰፋትና በተካረረ ሁኔታ እንዲባባሱ ወደሚያደርግ ሁኔታ ያመራል ፤ ይህ አብዮት ቀደም ብለው የነበሩትን ቅራኔዎች ማባባስ ብቻ ሳይሆን ሌሎች አዳዲስ ቅራኔዎችም እንዲፈጠሩ ያደርጋል ። ካፒታሊዝም የዘመናዊ ሳይንስና የቴክኖሎጂ ግኝቶችንና የሀብት ምንጮችን በአብዛኛው ለጦር መሣሪያ በማዋል የኅብረተሰቡን ብሔራዊ ሀብት ያባክናል ።

የሳይንስና የቴክኖሎጂ አብዮት የኅብረተሰቡን ችግር በተፋጠነ መንገድ የሚፈታው በኅብረተሰቡ መካከል ልዩነት የሚፈጥረው የግል ሀብት ሲጠፋ ብቻ ነው ። ይህ ደግሞ የሚሆነው በሶሻሊዝም ነው ።

የቴክኖሎጂ አብዮት በካፒታሊዝምም ሆነ በሶሻሊዝም በሥራ ላይ ውሏል ። ሆኖም የካፒታሊዝምና የሶሻሊዝም ማኅበራዊ ዕድገት የተለየ እንደመሆኑ ሁሉ የቴክኖሎጂ አብዮትም ዓላማ የተለየ ነው ። በካፒታሊዝም የቴክኖሎጂ አብዮት እያንዳንዱ ካፒታሊስት በተስማራበት የኢኮኖሚ ዘርፍ ሀብቱን ይበልጥ ለማድለብና ብዝበዛውን ይበልጥ ለማጧጧፍ ሲጠቀምበት በሶሻሊዝም ግን ምርት በጥራትና በብዛት በየትኛውም የኢኮኖሚ ዘርፍ እንዲመረት ፣ የሰው ልጅ የኑሮ ሁኔታ እንዲሻሻል ፣ የዕውቀት አድማሱ እንዲሰፋ ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ዕድገቱ እንዲፋጠን ለማድረግ ነው ።

በሶሻሊዝም የቴክኖሎጂ አብዮት በተናጀ ዕቅድ የሚመራ ነው ። በመሆኑም ማኅበራዊ ምርት የኅብረተሰቡን መሠረታዊ ፍላጎቶች እንዲያሟላ የኅብረተሰቡ አባላት ሁሉ ሁለገብ የሆነ ዕድገት እንዲኖራቸው ፣ ምርት በተትረፈረፈ እኳኋን ለማምረት ብቻ ሳይሆን የሰውን ልጅ ደኅንነት ለመጠበቅ ፣ ጤንነታን ለመከላከልና የኅብረተሰቡን ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎት ለማርካት እንዲቻል በቂ የዕረፍትና የመዝናኛ ጊዜ እንዲኖር ፣ የፈጠራ ችሎታውን እንዲያዳብር የሚረዳ ነው ።

የሶሻሊስት አብዮት አካል የሆነው ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት በሚካሄድበት በሽግግር ወቅት በተለይም ኢኮኖሚያቸውን በእርሻ ላይ በመሠረቱ ሀገሮች ውስጥ የቴክኖሎጂ አብዮት ዝቅተኛ የአመራረትን ዘይቤ አስወግዶ ወደ ከባድ ኢንዱስትሪ ግንባታ ወይም ወደ ከፍተኛ የምርት አደረጃጀት የሚያሸጋግር ፣ ሠራተኛው በተሻሻለ መሣሪያ እንዲጠቀም የሚያደርግ ፣ የሰው ልጅ በተፈጥሮ ላይ ያለውን ቁጥጥር የሚያጠናክር ፣ እነስተኛ የሽቀጥ አመራረትን የሚያስወግድና የሥራ ምርታማነትን በከፍተኛ ደረጃ የሚያሳድግ ነው ።

(የኢንዱስትሪ አብዮትን ይመለከቷል ።)

## ቴይለሪዝም
*(Taylorism)*

በ20ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ላይ በአሜሪካ የማምረቻ ተቋሞች ውስጥ በሥራ ላይ መዋል የጀመረ የምርት አደረጃጀትና የክፍያ ዘዴ ነው ። ይህን ዘዴ ለመጀመሪያ ጊዜ አጥንቶ ያቀረበው አሜሪካዊው መሃንዲስ ፍሬደሪክ ዊንስሎ ቴለር በመሆኑ ዘዴው ቴይለሪዝም የተሰኘ መጠሪያ ሊያገኝ ችሏል ።

በዚህ የምርት አደረጃጀትና የክፍያ ዘዴ መሠረት የብርቱና የፈጣን ወዝአደሮች የሥራ እንቅስቃሴና አንድን ሥራ ለማከናወን የሚወስድባቸውን ጊዜ ለተወሰነ ወቅት በመመዝገብና በማጥናት የአደረጃጀትና የአከፋፈል ደረጃ ይወሰናል ። ከዚህ በኋላ ወዝአደሮቹ ይህን በአዲስ የተወሰነውን ደረጃ መሠረት በማድረግ እንዲያመርቱ ይደረጋል ። በዚሁ ደረጃ ለማምረት ያልቻሉት የክፍያቸው መጣኔ ዝቅ እንዲል ይደረጋል ።

ቴይለሪዝም በካፒታሊስት ስልተ ምርት ውስጥ ወዝአደሩን ለመበዝበዝ የሚያስችል ዓይነተኛ መሣሪያ ይሁን እንጂ ሳይንሳዊነት ያለው የሥራ አደረጃጀትና የምርታማነት ማሳደጊያ ዘዴም በመሆኑ በሶሻሊዝም ውስጥ ከሠራተኛው እንክብካቤ ጋር በተገናዘበ ሁኔታ የሕዝቡን ፍላጎት ለማርካት ያገለግላል ።

## ትላልቅ ኢንዱስትሪዎችና ትናንሽ ኢንዱስትሪዎች
*(Large-Scale Industries and Small-Scale Industries)*

ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ቁጥራቸው በርካታ የሆነ ሠራተኞች ባሏቸው በአብዛኛው ዘመናዊ በሆኑ የማምረቻ መሣሪያዎችና የአመራረት ዘዴዎች የሚጠቀሙ የምርት መገልገያዎችንም ሆነ የፍጆታ ዕቃዎችን የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች ናቸው ።

ትናንሽ ኢንዱስትሪዎች የሚባሉት ደግሞ ቁጥራቸው አነስተኛ የሆነ ሠራተኞች ያሏቸው ፣ በአብዛኛው ዘመናዊ ባልሆኑ የማምረቻ መሣሪያዎችና የማምረት ዘዴዎች የሚጠቀሙ ፣ የምርት መገልገያዎችንና የፍጆታ ዕቃዎችን የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች ናቸው ።

በትላልቅ ኢንዱስትሪዎችና በትናንሽ ኢንዱስትሪዎች መካከል ያለው ልዩነት በግልጽና በማያሻማ አኳኋን የተቀመጠ አይደለም ። ለምሳሌ አንዳንድ ሀገሮች ቁጥራቸው ከ10 በላይ ያልሆነ ሠራተኞች ያሏቸውን የኢንዱስትሪ ድርጅቶች ትናንሽ ኢንዱስትሪዎች ይሏቸዋል ። ሌሎች ሀገሮች ደግሞ ትናንሽ ኢንዱስትሪዎች የሚሏቸው በሞተር የሚንቀሳቀሱ ሆነው ከ10 የማይበልጡ ሠራተኞች ያሏቸውን ወይም በሞተር የማይንቀሳቀሱ ሆነው ከ20 የማይበልጡ ሠራተኞች ያሏቸውን የኢንዱስትሪ ድርጅቶች ነው ።

ካፒታሊስታዊ የዕድገት ፈርን በሚከተሉ በመልማት ላይ ባሉ ሀገሮች ውስጥና በአጠቃላይ በካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ በትላልቅ ኢንዱስትሪዎችና በትናንሽ ኢንዱስትሪዎች መካከል የከረረ ቅራኔ ይታያል ። ካፒታልን የበለጠ በማማከልና በማሰባሰብ ሂደት ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ተመሳሳይ ሸቀጦችን በርካሽና በብዛት በማምረት ትናንሽ ኢንዱስትሪዎችን ከውድድር ውጭ አድርገው ይውጧቸዋል ፤ እንዲከስሩና እንዲዘጉም ያደርጓቸዋል ። የሶሻሊስትን የዕድገት ፈር በሚከተሉ በመልማት ላይ ባሉ ሀገሮች ውስጥ ግን ትናንሽ ኢንዱስትሪዎች አስፈላጊው ድጋፍ እየተደረገላቸውና በኅብረት እየተደራጁ ከትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ጎን ለጎን በመሰፋፋትና በመጠናከር የከምችት ምንጭና ተፈላጊ የሆኑ የፍጆታ ዕቃዎች አምራች ለመሆን ኋላም ወደ ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ለመሸጋገር የሚያስችላቸው ሁኔታ አለ ።

## ትረስት
*(Trust)*

ተመሳሳይ ሸቀጦች የሚያመርቱ ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ በመዋሃድ የሚፈጥሩት የሞኖፖል ቅርፅ ትረስት ይባላል ።

ተመሳሳይ ሸቀጥ የሚያመርቱ የካፒታሊስት አምራች ድርጅቶች ለሚያመርቱት ሸቀጥ ያለውን ገበያ በመከፋፈል ፣ የዋጋ ተመን በማውጣት ፣ የሚመረተውን ምርት መጠን በመወሰንና በመሳሰሉት ስምምነቶች መሠረት በመካከላቸው የሚካሄደውን ውድድር ለማስቀረት በመጀመሪያ እንደየሁኔታው ጥረት ያደርጋሉ ፤ ሆኖም ድርጅቱ በተለይ የኢኮኖሚው ሁኔታ ለትርፍ ማካበት በማያመችበት ጊዜ የተዋዋሉትን ስምምነት በማፍረስ ቀደም ሲል በመካከላቸው ይካሄድ የነበረውን ከፍተኛ ውድድር እንደገና ይጀምራሉ ። ድርጅቶቹ ይህ ሁኔታ እንዳይፈጠር በማለት ሙሉ በሙሉ በመዋሃድ ትረስትን ይመሠርታሉ ።

አምራች ድርጅቶች ትረስትን በመመሥረት ምርትንም ሆነ ሽያጭና ግዥን በሚመለከት በየግላቸው የነበራቸውን መብት ያጡና አንድ የሞኖፖል ድርጅት ይፈጥራሉ ። ድርጅቶቹን በግል ባለቤትነት ይዘው የነበሩ ካፒታሊስቶችም አዲስ በተፈጠረው ሞኖፖል ውስጥ ባለአክሲዮን ይሆናሉ ።

(ካፒታሊስት ሞኖፖሎችን ይመለከቷል።)

## ትርፍ
*(Profit)*

በካፒታሊዝም ውስጥ ትርፍ የሚለው የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ፈርጅ የተረፈ እሴት የተለወጠ መልክ ወይንም በቡርዧው መደብ ምንም ዓይነት ክፍያ ሳይደረግበት የተበዘበዘው የወዝአደሩ ትርፍ የሥራ ጊዜ ነው ። ትርፍ የተረፈ እሴት የተለወጠ መልክ ነው የሚባልበት ዋናው ምክንያት የተበዘበዘው

የወዝ አደሩ የሥራ ጊዜ ወይንም ተረፈ እሴት በተመረተው ሸቀጥ ዋጋና በቡርዧዚው የካፒታል ወጪዎች መካከል እንዳለ ልዩነት ሆኖ ስለሚታይ ነው ። የሸቀጥ ዋጋ የምርት ወጪ ዋጋና የትርፍ ድምር ነው ። የዚህ ዓይነት አቀራረብ ትርፍ ከሥራ ኃይል ጋር ያለውን ግንኙነት ይሸፍናል ። የምርት ወጪ ዋጋ እንደ ጠቅላላ ካፒታል ወጪ ሲታይ ትርፍ ደግሞ ባልተከፈለ ወይንም በተበዘበዘ የወዝአደሩ የሥራ ጊዜ የሚፈጠር ነው ። ትርፍ የሚከተሉት መልኮች ይኖሩታል ፥ እነሱም የኢንዱስትሪና የንግድ ትርፍ ፣ ወለድና ኪራይ ናቸው ። የዚህ ሁሉ ምንጩ በኢንዱስትሪ ካፒታል እንቅስቃሴ ውስጥ የሚፈጠረው ተረፈ እሴት ነው ።

በሞኖፖል ካፒታሊዝም ደረጃ ከፍተኛ የሞኖፖል ትርፍ የማግኘት ዓላማ የካፒታሊስት ሥርዓት ዕድገት መሠረትና ዋነኛው እንቀሳቃሽ ኃይል ነው ። ይህ ከፍተኛ ትርፍን የማግኘት ቋሚ ዓላማም በካፒታሊዝም ውስጥ ያለው መሠረታዊ ቅራኔ እንዲባባስ ያደርጋል ።

በሶሻሊዝም ትርፍ አዲስና በዓይነት የተለየ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ትርጉም ያገኛል ። በዚህም መሠረት በሶሻሊዝም ውስጥ ያለው ትርፍ በካፒታሊዝም ውስጥ ካለው ትርፍ በአመራረቱ ፥ በማኅበራዊ እርባታ ላይ በሚኖረው ተፅዕኖና በአጠቃቀሙ ይለያል ። በሶሻሊዝም ውስጥ ትርፍን ከካፒታሊስት ሥርዓት የተለየ የሚያደርጉ አራት ዓበይት ባሕርያት አሉ ። እነርሱም ፥

1ኛ/ ትርፍ በሶሻሊዝም በእኩልነትና በመተባበር ላይ የተመሠረተ የሶሻሊስት ምርት ግንኙነት መግለጫ ነው ።

2ኛ/ በሶሻሊዝም ውስጥ ትርፍ የሚመረተው ከብዝበዛ ነፃ በሆነ አምራች ኃይል በዕቅድ አማካይነት ነው ፤

3ኛ/ በሶሻሊዝም ውስጥ ትርፍ ወደ ጥቂቶች ኪስ የሚገባ ሳይሆን ለሰፊው ሕዝብ የጋራ ዕድገትና ብልጽግና የሚውል ነው ፥

4ኛ/ ትርፍ በሶሻሊዝም ውስጥ በዕቅድ የሚመራ የኢኮኖሚ አስተዳደር መሣሪያና የኢኮኖሚ ቅልጥፍና መለኪያ ነው ።

## ትርፍ መጣኔ (የ—)
*(Rate of Profit)*

የትርፍ መጣኔ ተረፈ እሴት ከጠቅላላው የካፒታል ወጪ ጋር ያለው ጥምርታ ከመቶ ሲሰላ የሚገኘው ውጤት ነው ። ይህም ሁኔታ በቀመር ሲገለጽ የሚከተለውን ይመስላል ።

$$\text{የትርፍ መጣኔ} = \frac{\text{ተረፈ እሴት} \times 100}{\text{ቋሚ ካፒታል} + \text{ተለዋዋጭ ካፒታል}}$$

የትርፍ መጣኔ ቡርዧዚው ያገኘው ትርፍ መጀመሪያ ካወጣው ጠቅላላ የካፒታል ወጪ ጋር የሚነፃፀርበት ፈርጅ በመሆኑ ካፒታል ራሱን የሚያስፋፋበት ወይንም የሚያሳድግበት ደረጃ የሚለካበት ነው ።

የትርፍ መጣኔው የተረፈ እሴት መጣኔ የተለወጠ መልክ ነው ። ምክንያቱም በትርፍ መጣኔው ተረፈ እሴት ከጠቅላላ የካፒታል ወጪ ጋር ሲነፃፀር የተረፈ እሴት መጣኔ ደግሞ ያው ተረፈ እሴት ለምንዳ ክፍያ ከዋለው ተለዋዋጭ ካፒታል ጋር ብቻ ስለሚነፃፀር ነው ። የትርፍ መጣኔው ከጠቅላላ የካፒታል ወጪ ጋር የሚነፃፀር በመሆኑና ቡርዧዚው ያገኘው ትርፍ ከተለዋዋጭ ካፒታሉ ብቻ የመነጨ ሳይሆን በጠቅላላ ካፒታል ወጪው አማካይነት ያገኘው ስለሚያስመስል በካፒታሊዝም ውስጥ ያለውን ብዝበዛ ይሸፍናል ።

የትርፍ መጣኔን ደረጃ ከሚወስኑት ሁኔታዎች መካከል የብዝበዛው ደረጃ (መጣኔ) አንዱ ነው ። ሌሎች ሁኔታዎች እንዳሉ ሆነው የተረፈ እሴት መጣኔው ካደገ የትርፍ መጣኔውም ያድጋል ። የተረፈ እሴት መጣኔው ካነሰም የትርፍ መጣኔውም ያንሳል ። በተጨማሪም የትርፍ መጣኔው ደረጃ በውስጣዊ የካፒታል ጥንቅሩ ይወሰናል ። ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅሩ አነስተኛ ከሆነ የተረፈ እሴት ምንጭ የሆነው ተለዋዋጭ ካፒታል ከፍተኛ ስለሚሆን የትርፍ መጣኔውም እንዲሁ ከፍተኛ ይሆናል ። ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅሩ ከፍተኛ ከሆነ ግን የቋሚ ካፒታል ድርሻ ከፍ ብሎ የተለዋዋጭ ካፒታል ድርሻ ማነስን ስለሚያመለክት የትርፍ መጣኔው ዝቅተኛ ይሆናል ። የካፒታል መገለባበጥ ፍጥነትና በቋሚ ካፒታል ወጪ ላይ የሚደረግ ቁጠ

ባም በትርፍ መጣኔው ደረጃ ላይ ተፅዕኖ አለው ።

በካፒታሊዝም ውስጥ ቡርዧዚው ከፍተኛ ትርፍ ለማግኘት ያለው ጉጉት በየጊዜው የተሻሻሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ሥራ ላይ በማዋል የሥራ ምርታማነትን ለማሳደግ ያስችለዋል ። ይህም በተራው በውስጣዊ የካፒታል ጥንቅሩ ውስጥ አንፃራዊ በሆነ መንገድ የተለዋዋጭ ካፒታል ድርሻ እያነሰ እንዲሄድ ያደርጋል ። የተረፈ እሴት ምንጭ ተለዋዋጭ ካፒታል የመሆኑን ያህልም የተለዋዋጭ ካፒታልም እያነሰ መሄድ የትርፍ መጣኔን እያቆለቆለ መሄድ ያስከትላል ። ይህም የትርፍ መጣኔ የማቆልቆል ዝንባሌ ማርክስ ያገኘው አንዱ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ሕግ ነው። ይሁንና ቡርዧዚዎች ይህንን የማቆልቆል ዝንባሌ የሚቋቋሙባቸው ሁኔታዎች የብዝበዛውን ደረጃ ከፍ ማድረግ ፣ ምንዳን ከሥራ ኃይል እሴት በታች ማውረድ ፣ የቋሚ ካፒታል ዕቃዎችን እሴት ዝቅ ማድረግ ፣ ሸቀጦችን ኋላቀር ወደሆኑ ሀገሮች መላክና ማስመጣት ናቸው ።

የትርፍ መጣኔ እያቆለቆለ የመሄድ ሕግ በካፒታሊስት ምርት ዓላማና ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ በሚጠቀሙበት ዘዴ መካከል ያለውን ቅራኔ በገሀድ ያሳያል ። ዋንኛው የካፒታሊስት ምርት ዓላማ ተረፈ እሴትን ማምረትና ትርፍን ማሳደግ ነው ። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ቡርዧዚዎች በየጊዜው የምርት ኃይሎችን እንዲያሳድጉ ይገደዳሉ ። የዚህ ውጤት ግን በተቃራኒው ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅርን በማሳደግ የትርፍ ምንጭ የሆነውን የተለዋዋጭ ካፒታል ድርሻ ስለሚያሳንስ የትርፍ መጣኔው እያቆለቆለ የመሄድ ዝንባሌ እንዲኖረው ያደርጋል ።

(ትርፍን ይመለከቷል ።)

## ትርፍ ክፍያ

*(Profit Sharing)*

ካፒታሊስቶች ለወዝአደሩ የሚከፍሉት አንድ ዓይነት የክፍያ መልክ ነው ። በዚህ የክፍያ መልክ መሠረት ለወዝአደሩ የሚከፈለው ምንዳ ሁለት ክፍል ይኖረዋል። አንዱ ክፍል በጊዜ ወይም በቁርጥ ሥራ መሠረትነት የሚከፈል መደበኛ ምንዳ ነው ። ሌላው ክፍል ደግሞ ካፒታሊስቱ በዓመቱ መጨረሻ ላይ ከተገኘው ትርፍ ለወዝአደሩ "ይገባዋል" በማለት የሚያደርገው ክፍያ ነው ።

በመሠረቱ የዚህ ዓይነት የክፍያ መልክ ሥራ ላይ የሚውለው የወዝአደሩን ምንዳ ቀደም ሲል በዝቅተኛ ደረጃ ላይ በመወሰን በመሆኑ በዓመቱ መጨረሻ ላይ ወዝአደሩ በትርፍ ክፍያ መልክ የሚቀበለው የራሱን ምንዳ ቀሪ ክፍል ነው ።

የዚህ ዓይነቱ አሠራር መሠረታዊ ዓላማ ሠራተኞች የድርጅቱ ትርፍ ተካፋይ የሆኑ መስሏቸው ከፍተኛ ምርት ለማስገኘት እንዲጥሩና ከመደብ ትግሉም እንዲዘናጉ ማድረግ ነው ።

## ትሮትስኪዝም

*(Trotskyism)*

በስውር ፀረ አብዮተኝነቱ ከታወቀው ከሊዮን ትሮትስኪ ጋር በስም የተያያዘ በሁለት የተሳሳቱ ሐሳቦች ላይ የተገነባ ፀረ አብዮት አቋም ነው ።

አንደኛው ሐሳብ በአንድ ሀገር ውስጥ ብቻ የሚካሄድ የወዝአደሩ አብዮት አይሰምርም የሚል ነው ። ይህም ማለት በአንድ ሀገር የወዝአደሩ አብዮት ድል ለማድረግ የሚችለው በዓለም ውስጥ ተመሳሳይ አብዮቶች ሲካሄዱና እነዚህም አብዮቶች እርስ በርስ ለመደጋገፍ ሲችሉ ብቻ ነው የሚል ነው ።

ሁለተኛው የተሳሳተ ሐሳብ በአንድ ሀገር ውስጥ እንደአጋጣሚ የወዝአደሩ አብዮት ቢካሄድም ከውጭ ተመሳሳይ አብዮቶች ድጋፍ ካላገኘ ሶሻሊስት ግንባታ ሊካሄድ አይችልም የሚል ነው ። ሆኖም እነዚህን የትሮትስኪዝም ሐሳቦች ታሪክ በተጨባጭ ማስረጃ ሽሮአቸዋል ። በታሪክ የመጀመሪያው የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት ድልና ከዚህም በኋላ በሶቭዬት ኅብረት ውስጥ ከፍተኛ የሶሻሊስት ግንባታ መካሄድ ትሮትስኪዝም ለተመሠረተባቸው ነጥቦች አፍራሽ ማስረጃዎች ናቸው ።

ትሮትስኪዝም ከላይ ከተጠቀሱት የተሳሳቱ ሐሳቦች በመነሣት የሚያንፀባርቃቸው ሌሎች ገጽታዎች አሉት ። እነዚህም የወዝአደሩን የአመራር ሚና አሳንሶ ማየቱ ፣ ገበሬው የወዝአደሩ ዋና አጋር መሆኑን ባለመቀበል አብዮታዊ ሚናውን መካዱና የሶቭዬትን መንግሥትና የኮሚኒስት ፓርቲውን አቋም በመፃረር መቆሙ ናቸው ። ትሮትስኪዝም የአንድን ሶሻሊስት ሀገር ለን[illegible]ና ብቸኛ የኮሚኒስት ፓርቲ መመራት ይቃወማል ። ከዚህ ይልቅ የተለያየ አመለካከትና ራሱን የቻለ ውስጣዊ ድርጅት ያላቸው ንዑሳን ቡድኖች በፓርቲው ውስጥ እንዲኖሩ ይደግፋል ። በዚህም በፓርቲውም ሆነ በዓለም ኮሚኒስት ንቅናቄ ውስጥ የከፋፋይነት ሚና ይጫወታል ። ከዚህም በላይ መሪው ፓርቲ የሚከተለውን ጠንካራ ዲሲፕሊን ፣ እንዲሁም በፓርቲው መሪዎችና በአባል ጓዶች መካከል የሚታየውን መተማመንና መከባበር ጭፍንነት ነው በማለት እንደድክመት ይቆጥረዋል ።

የትሮትስኪዝምን አደገኛነት ከሁለት አቅጣጫ ማየት ይቻላል ። አንደኛው የፀረ አብዮተኛነት አቋሙን በማርክሲዝም ቃላት ሸፍኖ ለሚያቀርብ ንቃተ ኅሊናቸው ያልዳበረ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ሊያሳስት መቻሉ ነው ። ሁለተኛው ለወዝአደሩ አብዮት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ለማድረግ የሚችሉ ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎችን ከአብዮቱ እንዲርቁ ፣ አብዮቱን እንዲቃወሙ ፣ አለበለዚያም በፍርሀት ተውጠው በገለልተኝነት እንዲወሰኑና የበኩላቸውን አብዮታዊ አስተዋጽኦ እንዳያደርጉ ግፊት ማድረጉ ነው ።

## ትንታኔ
## (*Analysis*)

በምርምር ውስጥ የሚገኝ አንድ ነገር የተገነባባቸውን አካሎች በመበታተን የማጥኛና ስለነገሩ ዕውቀት የማግኛ ዘዴ ነው ። አንድን ነገር እንዳለ በደፈናው በማጥናት ስለነገሩ አጠቃላይና ትክክለኛ ዕውቀት ለማግኘት ያዳግታል ። ስለሆነም ስለተለያዩ ነገሮች አጠቃላይና ትክክለኛ ፣ የማይፋለሱና ሥርዓት የተዋቀሩ ሐሳቦችን ለመቅረፅ በነገሩ ውስጥ የሚገኙትን አካሎች ባሕርያቸውን ፣ አወቃቀራቸውን ፣ ግንኙነታቸውንና የእንቅስቃሴ ሕግጋታቸውን ማጥናት ያስፈልጋል ። ለማጥናት ሲባል አንድን ነገር ወደ ተገነባባቸው ክፍሎች መበታተን የዚህን ነገር አወቃቀር ለመመልከት ይረዳል ። ውስብስብን ክስተት ወደ ቀላል አካሎች በመከፋፈል አስፈላጊውን ከማያስፈልገው ክፍል ለይቶ ለማጥናትና ውስብስቡንም ነገር በቀላሉ ለመገንዘብ ይረዳል ። በዕድገት ላይ የሚገኝን ሂደት በተለያዩ ደረጃዎቹና በተቃራኒ አዝማሚያዎቹ አንፃር ለመረዳት ያስችላል ።

የትንታኔ ዓላማ የአንድን ውስብስብ ክስተት ሥርዓት አካላትን በመውሰድ በነዚህ አካላት መሀከል ያሉትን ግንኙነቶች ፣ ባሕርያትና እንቅስቃሴ በማወቅ የአጠቃላዩን (አቅፎአቸው የሚገኘውን) ሥርዓት የዕድገት ሕግጋት መረዳት ነው ። ይህም በመሆኑ ትንታኔ ከአስተፃምሮ ጋር ተደጋጋፊ ነው ። ሐሳባችን የተደራጊ ውጤት ስለሆነ ትንታኔ በሐሳብ ውስጥ ብቻ የሚደረግ ክንውን ሳይሆን ከልምድና ከእውነታ ጋር የተዛመደ ነው ።

ለምሳሌ ስልተ ምርትን ጠንቅቆ ለማወቅ ሁለቱን ክፍሎች ማለትም የምርት ኃይልንና የምርት ግንኙነቶችን ማወቅ እንደሚያስፈልግ ፣ የምርት ኃይል ሲባልም የሥራ ማከናወኛን ፣ የሥራ ተገብሮንና ሥራን እንደሚያጠቃልል ፣ እነዚህ ደግሞ በተራቸው ምን እንደሆኑ ፣ እርስ በርሳቸው ያላቸውን ግንኙነት ፣ ሦስቱም የምርት ኃይል ክፍል ቢሆኑም የትኛው ዋንኛ (ወሳኝ) እንደሆነ መለየት ያስፈልጋል ። ከነዚህ ነጥቦች በመነሣት ስለምርት ኃይሎች አንድ አጠቃላይ ሐሳብ ይመሠረታል ።

በሌላም በኩል የምርት ግንኙነቶች ምን እንደሆኑ ፣ በኅብረት ይዞታው ዓይነት እንደሚወሰኑ ፣ በምርት ፣ በፍጆታ ፣ በልውውጥና በክፍፍል መስከ ያሉትን ግንኙነቶች ስለሚያጠቃልል እነኝህንም ማጥናት ያስፈልጋል ። በዚህም ጊዜ የሚገኙትን ሐሳቦች አንድ ላይ በማምጣት ስለምርት ግንኙነቶች ጠቅለል ያለ ትክክለኛ ሐሳብ ለመመሥረት ይቻላል ። በመጨረሻም ስለምርት ኃይሎችና ስለምርት ግንኙነቶች በጥናት የተገኙትን አጠቃላይ ሐሳቦች አንድ ላይ በመሰብሰብ ስለ ስልተ ምርት ምንነት ለማወቅ ይቻላል ።

(አስተፃምሮን ይመለከቷል ።)

## ትንኮሳ
*(Provocation)*

ግለሰቦችን ፣ ቡድኖችን ወይም ድርጅቶችን በተለያዩ መንገዶች በማነሣሣትና በመገፋፋት የማይፈለጉ ውጤቶችን ወደሚያስከትል ፣ እንዲያውም ከፍተኛ አደጋ ላይ ሊጥል ወደሚችል ሁኔታ ለመምራት ተንኮለኞች የሚጠቀሙበት መሠሪ ዘዴ ነው ። የዚህ ዓይነቱን ተንኮል የሚፈጽሙ የአድኃሪ መሣሪያዎች የትንኮሳ ወኪሎች (*Agents Provocateurs*) ይባላሉ ።

ተራማጅ ኃይሎች ኅቡእ ትግል ሲያካሂዱ አድኃሪ የገዥ መደቦች ከውስጥና ከውጭ ሰላዮችን በልዩ ልዩ ሽፋን በታጋዮች ውስጥ አሰርገው በማስገባት መረጃ ከሚያገኙበትና አልፎ ተርፎም በኃይል ጭምር ከሚያጠቁበት ስልት አንዱ በተንኳሽነት መጠቀም ነው ። እነዚህ ተንኳሾች በታጋይ ድርጅቶች ውስጥ ሰርገው ከገቡ በኋላ ተናግረው በማናገር ወይም እየተነኮሱ ነገሮችን በማውጣጣት ሐቀኛ ታጋዮችን ያጋፍጣሉ ። ከዚህም አልፎ ሲሆንላቸው ከትክክለኛ ታክቲክ ውጭ ግብታዊና ጀብደኛ እርምጃ እንዲወሰድ በመገፋፋት ፣ በሚደርሰውም ውድቀት ሕዝቡ እንዲማረር ፣ አብዮታዊ ድርጅቶች እንዲወገዙ ፣ በዚህም ሳቢያ የአብዮቱ ወገኖች በጠላቶቻቸው በቀላሉ እንዲመቱ ሁኔታዎችን የሚያመቻቹ ናቸው ።

አብዮተኞች ምንጊዜም ቢሆን በተለይም ከፍተኛ ምሥጢራዊ ተግባራት በሚያከናውኑባቸው ወቅቶች ከነዚህ ዓይነቶቹ "አፈ ቅቤና ልበ ጩቤ" አስመሳዮች መጠንቀቅ የሁልጊዜ ትኩረታቸው ሊሆን ይገባል ።

(ሰርጎ ገብን ፣ አስመሳይ ተራማጅን ይመለከቷል ።)

## ትግል
*(Struggle)*

ተቃራኒ ኃይሎች አንዱ በአንዱ ላይ የበላይነትን ለመቀዳጀት የሚያደርጉት ጥረት ትግል ይባላል ። ትግል ከዲያሌክቲክስ ሕግጋት አንዱ በመሆን በተፈጥሮ ውስጥ በተለያዩ መልኮች ይከሰታል ። ለምሳሌ ጎጂ ተሕዋሲያን በሰውነታችን ውስጥ ሲገቡ የሰውነታችን ተከላካይ ሕዋሳት ከእነዚህ ጎጂ ተሕዋስያን ጋር የሞትና የሽረት ትግል ያካሂዳሉ ። ተከላካይ ሕዋሳት ከአሸነፉ ሰውነታችን ከበሽታው ይድናል ፤ ከተሸነፉ ግን በበሽታው ይጠቃል ።

የሰው ልጅ በግለሰብም ሆነ በቤተሰብ ፣ እንዲሁም በማኅበረሰብ ደረጃ ኑሮውን ለማሸነፍና ሕይወቱን ለማሻሻል ይታገላል ። የዕውቀት አድማሱን ለማስፋትና ተፈጥሮን የመቆጣጠር ችሎታውን ከፍ ለማድረግ ይጥራል። በዓለም አቀፍ ደረጃም ሕዝቦች ለሰላም ፣ ለፍትህ ፣ ለብሔራዊና ለማኅበራዊ ነፃነት እነዚህን ከሚፃረሩ ኃይሎች ጋር ይታገላሉ ።

ኅብረተሰብም የዲያሌክቲክስ ሕግጋት ተገዥ እንደመሆኑ የገንቢና የአፍራሽ ኃይሎች ትግል የሚካሄድበት መድረክ ነው ። ኅብረተሰብ በመደብ መከፋፈል ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ ተጨቋኝ መደብ ከጨቋኙ መደብ ጋር ለነፃነት ፣ ለእኩልነትና ለፍትህ ያላቋረጠ ትግል አካሂዷል ። በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት የጀመረው የመደብ ትግል እስከ ካፒታሊስቱ ሥርዓት ድረስ እየከረረ መጥቷል ። ወዝአደሩ ለብዙ ዘመናት በአካበተው የትግል ልምድ በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ በሚያደርገው ትግል የበላይነቱን ተቀዳጅቶ ወደ ሶሻሊስት ሥርዓት እንዲሸጋገር ያደርገዋል ።

የሰው ልጅ ወደ ኮሚኒስት ሥርዓት ሲሸጋገር የመደብ ቅራኔ ስለማይኖር መደባዊ ትግልም አይኖርም ። ሆኖም የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር የሚያደርገው ትግል ይቀጥላል ።

(የመደብ ትግልን ፣ የዲያሌክቲክስ ሕግን ፤ ዕድገትን ይመለከቷል ።)

## ቶሚዝም
*(Thomism)*

የካቶሊክ ፍልስፍና ግንባር ቀደም አዝማሚያ ሲሆን ጽንሰ ሐሳቡ የተመሠረተው የካቶሊክ እምነት ተከታይና ሐዋርያ በነበረው በቶማስ አኩዊናስ ነው ።

የፍልስፍናው መሠረተ ሐሳብ የአመክንዮና የራዕይ ምንጩ እግዚአብሔር ነው ፤ ስለሆነም አመክንዮና ራዕይ እርስ በርሳቸው የሚስማሙና የሚዋሀዱ ናቸው የሚል ነው ። የአመክንዮንና የራዕይን ምንነት ፣ መነሻና መድረሻ ለማረጋገጥ መሞከሩ እነሱን መልሶ ማጥፋት እንደሆነ አድርጎ የሚያቀርብ ፍልስፍና ነው ።

የቶሚዝም ፍልስፍና አዝማሚያ ዋና ዓላማ ፣ የዘመናዊ ሳይንስን ንድፈ ሐሳብ መሠረት ማዳከም ነው ።

(ቶማስ አኩዊናስን ይመለከቷል።)

# ቻ

## ቻርቲስት እንቅስቃሴ (የ—)

(*The Chartist Movement*)

በለንደን ሠራተኞች በ1836 ተመሥርቶ እስከ 1850 የቆየ የመጀመሪያው ሰፊ የሠራተኛው መደብ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ነው ። ቻርቲዝም ሠራተኛው ብቻ ሳይሆን ብዙ የንዑስ ከበርቴው መደብ አብዮታዊ ዲሞክራቶችና የሙያ ትምህርት ያላቸው ሠራተኞች ግንባር ቀደም ሚና የተጫወቱበት እንቅስቃሴ ነበር ።

የቻርቲስት እንቅስቃሴ ዝነኞቹ ስድስት ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው ። እነሱም ፤ ድምፅ ሲሰጥ በምሥጢር እንዲሆን ፣ በየአካባቢውና በየምርጫ ጣቢያው እኩል የምርጫ መብት እንዲሰጥ ፣ ዓመታዊ የፓርላማ ምርጫ እንዲደረግ ፣ ለፓርላማ ተወካዮች ደሞዝ እንዲከፈል ፣ ንብረት የመመረጥ መመዘኛ መሆኑ እንዲቀርና የምርጫ መብት ለሁሉም እንዲሆን የሚሉት ናቸው። እነዚህም ስድስት ነጥቦች በ1837 በአቤቱታ መልክ ለፓርላማ በቀረቡበት ወቅት በእንግሊዝ ለመምረጥ ከሚችለው ከስድስት ሚሊዮን ሕዝብ ውስጥ የመምረጥ መብቱ የተከበረለት 850,000 የሚሆነው ብቻ ነበር ።

በቻርቲስት እንቅስቃሴ ውስጥ የተለያዩ ኃይሎች ስለነበሩ የተለያዩ አዝማሚያዎች ቢንፀባረቁበትም ኋላ በቡርዧዚው አድኃሪ እርምጃዎች በመደናገጥ አብዛኞቹ ንዑስ ከበርቴዎች ራሳቸውን ከእንቅስቃሴው አገለለዋል ። በተለይ ሐምሌ 24 ፣ 1840 በተቋቋመው "ብሔራዊው የቻርተር ማኅበር" አማካይነት የቻርቲስቱ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ዕድገት አሳየ ። ብሔራዊ የቻርተር ማኅበር በየዓመቱ የሚመረጥ አጠቃላይ ምክር ቤትና የሥራ አስፈጻሚ አካል የነበረው ቻርቲስቶችን የሚያስተባብር አካል ነበር ። አባላቱ የአባልነት መዋጮ የሚከፍሉ ሲሆን የአባልነት መታወቂያም ነበራቸው ። የብሔራዊ የቻርተር ማኅበር ድርጅቶች ወይም አካሎች 400 ሲደርሱ በ1842 የአባላቱ ቁጥር ወደ 40,000 አድጓል ። የአባላቱም ተቀዳሚ ዓላማ ስድስቱን ነጥቦች ተግባራዊ ማድረግ ነበር ። በዚህ ጊዜ የቻርቲስት እንቅስቃሴ በግልጽ ወዝአደራዊና መደባዊ ባሕርይ የሚታይበትና ሠራተኛውን ወደ ፖለቲካ ትግሉ ለመሳብ በነበረው ዓላማ መሠረት በተለይ ከሠራተኛው ማኅበራት ጋር የቀረበ ግንኙነት ነበረው ። በ1842 ላይ የሕዝብ ጥያቄዎች ለተባሉት ስድስት ነጥቦች ከመታገልም አልፈው "የሞኖፖሎችንና" ባጠቃላይም የቡርዧዚውን ልዩ መብትና በሕዝቡም ላይ የሚሰነዘረው ጭቆና እንዲጠፋ መጠየቃቸው ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነበር ።

ለጥያቄዎቻቸው ሕዝባዊ ድጋፍ ለማግኘት ቻርቲስቶች ባካሄዱት ከፍተኛ የቅስቀሳ ተግባር በአንዳንድ ስብሰባዎች ላይ ቁጥሩ እስከ 350,000 የሚደርስ ሕዝብ ይገኝ ነበር ። ለፓርላማው የቀረቡት አቤቱታዎች የሕዝቡ መሆናቸውን ለማሳመን ከጥያቄዎቹ ጋር የደጋፊዎችን ፊርማ አብረው ያቀርቡ ነበር ። የቡርዧው ፓርላማ ለጥያቄዎቹ ተገቢውን መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግና በአመፅ ለማስፈጸም ይታገሉ ነበር ። ለምሳሌ በ1842 ከሦስት ሚሊዮን በላይ የድጋፍ ፊርማ በመያዝ ዓላማቸው ተግባራዊ እንዲሆን ጥረዋል ። በቻርቲስቶችና በፓርላማው መካከል ከፍተኛ ግጭት የተደረገውም በዚህን ጊዜ ነበር ። ዳሩ ግን እንቅስቃሴው የዊሊንግተኑ መስፍን ባሰለፈበት 250,000 የቡርዧ ጨካኝ አድኃሪ ጦር ሠራዊት ክፉኛ በመመታቱ ወደ 1,500 የሚደርሱ የእንቅስቃሴው መሪዎችና አባላት ታሠሩ ። በዚህም እንቅስቃሴው ክፉኛ ተዳከመ ። ቆይቶም በ1848 በምዕራብ አውሮፓ በነበረው አብዮታዊ ሁኔታ አጋጣሚ እንደገና ለማንሰራራት ሞክሮ አልተሳካለትም ። በመጨረሻም በውስጡ በተሰገሰጉ ንዑስ ከበርቴዎች ሴራና በቡርዧዚው ተፅዕኖ እየተዳከመ ሄዶ በ1850 ላይ ህልውናው ጨርሶ አከተመ ።

## ችርቻሮ ንግድ (የ—)
*(Retail Trade)*

የአንድ ሀገር የውስጥ ንግድ አንድ አካል ሲሆን ሸቀጦችን በቀጥታ ለሸማቹ ክፍል የሚያቀርብ የንግድ ክፍል ነው ። በችርቻሮ ንግድ የተለያዩ የፍጆታ ሸቀጦች ለሸማቾች ይቀርባሉ ። የችርቻሮ ንግድ በሸቀጦች የዝውውር ሂደት ውስጥ የሸቀጦች ዝውውር የመጨረሻ ደረጃ ነው ። ይህም በመሠረቱ በገንዘብ አማካይነት የሚከናወን ይሆናል ።

በችርቻሮ ንግድ የሚቀርቡት ሸቀጦች አጠቃሳይ የኢንዱስትሪና የምግብ ውጤቶች ሊሆኑ ይችላሉ ።

በአሁኑ ጊዜ በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የንግድ ሞኖፖሊስቶች የችርቻሮ ንግድ የስርጭት አውታሮችን በሰፊው በመዘርጋት በልዩ ልዩ ሱቆች ፣ በትላልቅ የገበያ አዳራሾች ወዘተ . . . መልክ ተደራጅተው ትርፍ ይሰበስቡበታል ።

በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የችርቻሮ ንግድ በመንግሥትና በኀብረተሰብ የንግድ ድርጅቶች የተያዘ ሲሆን የኀብረት ይዞታውም በቀጥታ የሸማቾች ኀብረት ሥራ ማኀበር ነው ። ዓላማቸውም የሶሻሊስት የምርት ግንኙነቶችን ማጠናከርና ለሕዝቡም የፍጆታ ዕቃዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ ነው ።

በሽግግር ወቅት የችርቻሮ ንግድ ድርጅቶች በአብዛኛው በግል ነጋዴዎች ይዞታ ሥር ስለሚገኙ ሰው ሠራሽ እጥረቶችን በመፍጠር ፣ ወይም ደግሞ ሸቀጦችን ሕገወጥ በሆነ መንገድ በማስራጨት በሕዝቡ ላይ የኑሮ ውድነትን ያስከትላሉ ። ስለዚህም በሽግግር ወቅት የግል ችርቻሮ ንግድ አውታሮችን በከፍተኛ ደረጃ መቆጣጠርና በምትካቸውም መንግሥታዊና የኀብረት ችርቻሮ ንግድ አውታሮችን ማጠናከር እጅግ አስፈላጊ ይሆናል ።

# ነ

## ነባራዊ
*(Objective)*

ከሰው ንቃተ ኅሊና ውጭ ያለ ፣ ለሀልውናው የሰዎችን ኅሊና የማይሻ ፣ በራሱ ሕግጋት የሚገዛ ፣ ለሰው የዕውቀት ምንጭ የሆነ ማናቸውም ነገር ነባራዊ ይባላል ። ጽንሰ ሐሳቡ የጭብጥ ነገሮች ባሕርይና ግንኙነት ከሰው ንቃተ ኅሊና ውጭ የሚኖሩ መሆኑን ያመለክታል ።

የሰው ሐሳብና ሰው ስለነገሮች ያለው ዕውቀትና አመለካከት የሚመነጨው ሰው ከነባራዊው ወይም ከቁሳዊው ክስተት ጋር በሚያደርገው የተግባር ግንኙነት ነው ። በዚህም ምክንያት ሰው ስለነገሮች ያለው ዕውቀት የሚረጋገጠው በተግባር ላይ እያዋለው ሲሄድና ዕውቀቱም ተጨባጩን ነገር መለወጥ ሲችል ነው ። በዚህም ሂደት ነባራዊ እውነት ይመሠረታል ። ነባራዊ እውነት መኖሩን መቀበልና ማረጋገጥ ደግሞ የቁስአካላዊ ዕውቀት ንድፈ ሐሳብ መሠረት ነው ።

(ነባራዊ እውነትን ፣ እውነታን ይመለከቷል ።)

## ነባራዊ ሁኔታ
*(Objective Condition)*

ነባራዊ ሲባል ነገሮች ፣ ባሕርያቸውና ግንኙነታቸው ከሰው ኅሊናና ፍላጎት ውጭ ነፃ ህልውና ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ ጽንሰ ሐሳብ ነው ። ሁኔታ ደግሞ አንድ ነገር ወይም ክስተት በአካባቢው ከሚገኙ ነገሮች ጋር ያለውን ግንኙነትና ከዚህም ግንኙነት ውጭ ሊኖር አለመቻሉን ፣ ነገሮችና ክስተቶች ህልውና የሚያገኙበትና ማደግ የሚጀምሩበት አካባቢ መሆኑን የሚያመለክት የፍልስፍና ፈርጅ ነው ።

ነባራዊ ሁኔታ ለማኅበራዊ ዕድገት ከሚያስፈልጉት ሁለት ሁኔታዎች አንዱ ነው ። ለቁሳዊ ፣ ለፖለቲካዊና ለአእምሮአዊ የተፋጠነ ዕድገት ታሪክ አጣዳፊ ምላሽ እንደሚያስፈልጋቸው አድርጎ የሚያቀርባቸው ተግባሮች ፣ እርምጃዎች ፣ ግዴታዎችና ሁኔታዎች እንዲሁም የተፈጥሮ አካባቢዎች ለነባራዊ ሁኔታ በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ ።

የማኅበራዊ አብዮት ነባራዊ ሁኔታዎች ስንል ለአብዮት መፈጠርና ማደግ የሚያስፈልጉና ከሰዎች ኅሊና ውጭ የሚገኙ ሁኔታዎች ማለት ነው ። እነዚህም በአሮጌው ሥርዓት ውስጥ የቀውስ መፈጠርን ፣ የመደብ ቅራኔዎች ማደግንና ከፍተኛ ደረጃ ላይ በመድረስ መፍትሔ የሚያስፈልጋቸው ሆኖ መገኘትን ፣ የአብዮታዊ ሁኔታዎች ተሟልተውና በስለው መገኘትን ፣ የነዚሁም ሁሉ መሠረት የሆነውን በአዲሶቹ የምርት ኃይሎችና በአሮጌዎቹ የምርት ግንኙነቶች መሃከል ያለውን መሠረታዊ አለመጣጣምና ቅራኔን ይይዛሉ ።

ነባራዊ ሁኔታ ጭቁን መደቦች ስለፈለጉት የሚመጣ ወይም ገዥ መደቦች ስለጠሉት የሚቀር ሳይሆን በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች አለመጣጣም መንሥኤነት የሚፈጠር ተጨባጭ የዕድገት ሁኔታ ነው ።

የማኅበራዊ አብዮት ነባራዊ ሁኔታዎች አሮጌውን ማኅበራዊ ሥርዓት ከውስጥ ሆነው ቢያናጉትም ብቻቸውን ግን የአሮጌውን ሥርዓት መፍረስና የአዲሱን ሥርዓት መተካት አያስከትሉም ። ምክንያቱም የአሮጌው መፍረስና የአዲሱ መገንባት የሰዎች ንቁና ዓላማ ያለው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውጤት በመሆኑ ነው ። ስለሆነም ነባራዊ ሁኔታዎች የማኅበራዊ አብዮት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሆኑ አብዮቱን እውን ለማድረግ ግን የተፈላጊዎቹ ኅሊናዊ ሁኔታዎች መሟላት ግዴታ ነው ።

(አብዮትን ፣ ኅሊናዊ ሁኔታን ፣ ተግባርን ይመለከቷል ።)

## ነባራዊ ሐሳባዊነት
*(Objective Idealism)*

ራሱን ጠብቆ በነባራዊነት በመኖር የዓለምን ህልውናና ጠቅላላ ዕድገት የሚገዛ ሐሳብ አለ የሚል የሐሳባዊነት ፍልስፍና ዘርፍ ነው ።

ይህ ፍልስፍና ከጥንት ጀምሮ የነበረና ዛሬም ያለ ሲሆን ከሐሳባዊነትም ፍልስፍና ሁለት ዋና ዋና ዘርፎች መካከል አንደኛው ነው ። ይህን ዘርፍ በማራመድ ከታወቁት ታላላቅ ፈላስፎች መካከል ቀደም ሲል አፍላጦን ፣ በኋላም ደግሞ ሄግል ይገኙበታል ። በተለይ ሄግል ይህን የሐሳባዊነት ፍልስፍና ዘርፍ ብሉያዊ ቅርፁን ሊያስይዘው ችሏል ።

ሐሳባዊነት በአጠቃላይ ከኅሊና ቀዳማይነት በመነሣት ቁስአካል የኅሊና ነፀብራቅ ነው የሚል የፍልስፍና ዘርፍ ነው ። ነባራዊ ሐሳባዊነት በዚህ የሐሳባዊነት አስተምህሮ ላይ በመመርኮዝ ነባራዊውን ዓለም የፈጠረው ኅሊና በአፍላጦን "ፍጹማዊ መንፈስ" በሄግል ደግሞ "ፍጹማዊ ሐሳብ" በመባል የተሰየመ ፣ የዕውቀትም ሆነ የእውነታ የመጀመሪያ መንሥኤ የሆነውና ፍጹማዊ ጠባይ ያለው ነባራዊ ኅሊና ነው ከሚል መሠረተ ሐሳብ ይነሣል ። ከዚህ መሠረተ ሐሳብ በመነሣትም በዓለም ውስጥ ያሉ ነገሮችንና ክስተቶችን በሙሉ የዚህ "ፍጹማዊ ሐሳብ" ውጤቶች ወይም ፍጥረቶች እንደሆኑ አድርጎ ይወስዳቸዋል ። ቁስአካል ራሱን ችሎ በነባራዊነት የሚገኝ የሐሳብ ዕድገት ውጤት ነው በማለት ማንኛውንም ተፈጥሮአዊ ሆነ ማኅበራዊ ነገርና ክስተት ከዚሁ አንፃር ለመተንተንና ለመተርጎም ይሞክራል ። ህልውናቸውም ሆነ ዕድገታቸው በዚሁ ፍጹማዊ ሐሳብ የሚገዛ እንደሆነ ለማሳመን ይጥራል። ይህ ሐሳባዊነት ነባራዊ የተባለበትም ምክንያት የማንኛውም እውነታ ምንጭ የሆነው ሐሳብ ከሰዎች ኅሊና ውጭ የሆነና የራሱ ነፃ ህልውና ያለው ነው ብሎ ስለሚያምን ነው ።

ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት እውነታ ነባራዊ እንደሆነና ለህልውናው ሆነ ለዕድገቱ መንሥኤው በነገሮችና በክስተቶች ውስጥ የሚገኘው ቅራኔ እንደሆነ በመግለጽ ከቁስአካል የተነጠለ ኅሊና ሊኖር እንደማይችል ይልቁንም ኅሊና እራሱ የነባራዊው እውነታ ሂደት ውጤት እንደሆነ በማሳየት የነባራዊ ሐሳባዊነትን መነሻ መሠረተ ሐሳብ ከንቱነት አረጋግጧል ። በተጨማሪም ነባራዊ ሐሳባዊነት በመጨረሻ ትንታኔ ላይ ይህችን ዓለም የፈጠረ አንድ መለኮታዊ ኃይል አለ ወደሚለው አስተሳሰብ በመቃረብ ከሥነ መለኮት ጋር እንደሚሄድና የሃይማኖትን ፍልስፍናዊ መሠረት እንደሚያደላድል አሳይቷል ።

(ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነትን ፣ ኅሊናዊ ሐሳባዊነትን ፣ ሄግሊያኒዝምን ፣ አፍላጦንን ይመለከቷል ።)

## ነባራዊነት
*(Objectivism)*

ነባራዊነት የሰው ልጅ ትክክለኛ ዕውቀት ለማግኘት በሚያደርገው ጥረት በማኅበራዊና በፖለቲካዊ ጥያቄዎች ላይ ወገናዊ የሆነ አቋም መውሰድ የለበትም የሚል የሐሳባዊ ፍልስፍና አንድ ገጽታ ነው ። በነባራዊነት አመለካከት ወገናዊነትና ሳይንሳዊነት አብረው አይሄዱም ። ስለሆነም ማንኛውም የኅብረተሰቡንና የተፈጥሮን እንዲሁም በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት በሚመለከት የሚደረገው ጥናት ወገናዊነትን ካሳየ ሳይንሳዊነት የለውም ማለት ነው ።

የነባራዊነት ዓይነተኛ ባሕርይ ሁኔታዎችን ወይም ንድፈ ሐሳባዊ አመለካከትን ከመደብ ወይም ከፓርቲ አመለካከት አንፃር አለማየቱ ነው ። ነባራዊነት ከወገናዊ አመለካከት ውጭ የሆነ እውነት አለ ከሚል አቋም ተነሥቶ በሳይንሳዊ ዕውቀት ላይ የታሪክ ሂደት ተፅዕኖ አያደርግበትም ፣ ሳይንስ ለነገሮች ወገናዊ የሆኑ መደምደሚያዎች ሊሰጥ አይችልም ይላል ። በነባራዊነት ላይ የተመሠረተ የማኅበራዊ ሳይንስ አመለካከት የመደቦችና የመደብ ትግል ፣ የአድኃሪና የተራማጅ ርዕዮተዓለም ትግል መኖሩን አይቀበልም ። አድኃሪና ተራማጅ ማኅበራዊ ኃይሎች የሚያደርጉት ትግል ለማኅበራዊ ችግሮችና ቅራኔዎች መፍቻ መሆኑን አያምንም ።

ከርዕዮተዓለም ትግል አንፃር ነባራዊነት የመደብ መሣሪያ የሆነውን መንግሥት ከመደቦች በላይ እንደሆነና "ሀገርን" በመወከል ቅራኔዎችን አቻችሎ የሚኖር

 ነባራዊ እውነት

ማኅበራዊ ኃይል አድርጎ ይወስደዋል ። ኪነታዊ ሥራዎችንም በሚመለከት “ኪነት ለኪነት ብቻ” የሚለውን እመለካከት በማራመድ ኪነታዊ ሥራዎች የማኅበራዊ ቅራኔዎችና የኅብረተሰብ ግብረገባዊ ችግሮች ማንፀባረቂያ መሆናቸውን ይክዳል።

የነባራዊነት እመለካከት ከመደብና ከወገናዊነት ውጭ ነገሮችን ስለሚያይ ገዥ መደቦች የመደብ ትግሉን ለማፈን ፣ ኋላቀርና አድኃሪ ማኅበራዊ ሥርዓቶችን እንዳሉ ለማቆየት ፣ ኢሳይንሳዊ እመለካከቶች እንዳይጋለጡ ለማድረግ የሚያራምዱት የአድኃሪ ፍልስፍና ጽንሰ ሐሳብ ነው ። በዚህም ምክንያት ምንም እንኳን ነባራዊነት ገለልተኛነትን የሚያራምድ መስሎ ቢቀርብም ራሱ ለቡርዧው ርዕዮተዓለም ወገናዊ ነው ። ነባራዊነት በተጨባጩ ዓለም ከሚታዩ ሁኔታዎች የራቀ እመስካከት በመሆኑም ኢሳይንሳዊ ነው ፤ ምክንያቱም ኅብረተሰብንና ተፈጥሮን ለማወቅ በሰውና በተፈጥሮ እንዲሁም በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመተርጐም የሚደረግ ጥናት ሁሉ ወገናዊ የሆነ ፍልስፍናዊ መደምደሚያ ከመስጠት የማያልፍ ነው ።

በማርክሳዊ ሌኒናዊ እመለካከት በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ በተለይ ማኅበራዊ እውነታን ለማወቅና ለመተርጐም የሚደረግ ሳይንሳዊ ጥናት በመጨረሻ ወገናዊ የሆነ መደምደሚያ ይሰጣል ። ማርክሲዝም ሌኒኒዝም የማንኛውም ማኅበራዊ ኃይል ድርጊት ከመደብ እንፃር መታየት እንዳለበትና በሂደቶች ውስጥ ዋናው ተዋናይ ማን እንደሆነ ፣ ሚናውስ እስከምን ድረስ እንደሆነ እስካልታወቀ ድረስ የነገሮች ትክክለኛ ግንዛቤ እንደማይኖር ያስተምራል ። በመሆኑም ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ወገናዊ የሆነ ሳይንስ ነው ።

(ኀሊናዊነትን ፣ ወገናዊነትን ፣ የቅራኔዎች አንድነትና ትግል ሕግን ይመለከቷል ።)

## ነባራዊ እውነት
*(Objective Truth)*

እውነታን በትክክል የሚያንፀባርቅ ዕውቀት ፣ ከእውነታ ጋር የሚጣጣምና የሚስማማ አስተሳሰብ ማለት ነው ። የሰው እመለካከት የነባራዊ እውነታ ነፀብራቅ በመሆኑ ትክክል ወይም ስሕተት ሊሆን ይችላል ። እውነት ግን ትክክለኛ ዕውቀት ማለት ነው ። የዕውቀት እውነትነት ይዘቱ በነባራዊ እውነታ የሚወሰንና ዓለምን በተግባር በምንለውጥበት ሂደት ውስጥ እውነታን በማንፀባረቅ የምናገኘው ነው ። እንድን ሐሳብ እውነት የምንለው ስለ አንድ ነገር ወይም ስለ እውነታ በአእምሮአችን ውስጥ ያለን ግንዛቤ ከዚሁ ነገር ወይም እውነታ ጋር ስምምነትና ተመሳሳይነት ሲኖረው ነው ። በዚህም ጊዜ ያገኘነው እውነት ነባራዊ ነው የሚባለው ስለእርሱ ያለን ግንዛቤ የስሜት ፣ የምኞት ወይም የፈጠራ ሳይሆን በእርግጥም ከሐሳባችን ውጭ ስለሚገኘው ነባራዊ እውነታ ምንነት የሚያስረዳን በመሆኑ ነው ። ይህም አባባል እውነት ነባራዊ መሆን እንዳለበት ያሳያል ። ነባራዊው ዓለም እውነት ወይም ውሸት ሊሆን አይችልም ፤ እውነት ወይም ውሸት ሊሆን የሚችለው እኛ ስለነባራዊው ዓለም ያለን አስተሳሰብ ነው ።

ሐሳባዊ ፈላስፎች ሐሳብ እራሱን የቻለ ነባራዊነት እንዳለው አድርገው በመቁጠራቸው የነባራዊ እውነት ዋነኛ መመዘኛ ነጥብ ሐሳብ ከሐሳብ ጋር መስማማቱ ነው ብለው ያምናሉ ። ማለትም ሐሳብ ከሐሳብ ጋር ከተቃረነ ሐሳቡ ራሱን የሚያፈርስ ይሆናልና ሐሳቡ ነባራዊነት ሊኖረው አይችልም ይላሉ። ለምሳሌ ትንሽ ከትልቅ ይበልጣል ብንል አባባሉ ራሱን የሚቃረን በመሆኑ የሚያመለክተው ነባራዊ ነገር ወይም ሁኔታ አይኖርም ። ትንሹ ትልቁን በልጦ ሊኖር የማይችለው ከአስተሳሰብ ሕግጋት ጋር ስለማይጣጣም ነው በማለት ሐሳባዊ ፈላስፎች የእውነትን ነባራዊነት መመዘኛ የሚያደርጉት አስተሳሰብ ከሐሳብ ቅራኔ የመጽዳቱን ነጥብ ነው ።

በማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍና የእውነት ነባራዊነት የሚወስነው ሐሳብ ከሐሳብ ጋር በመስማማቱ ብቻ አይደለም ። ቁምነገሩ የእውነት ነባራዊነት ምንጩ ከሐሳብ ውጭ ስለሚገኘው ነገር ትክክለኛ ግንዛቤ መሆኑ ነው ። ማንኛውም ሐሳብ ከቅራኔ የጸዳ በመሆኑ ብቻ ነባራዊ እውነት ነው ማለት አይደለም ። የፈጠራ ሐሳብ ወይም ምኞት ከቅራኔ የጸዳ ቢሆንም እንደ እውነት አይወሰድም ። ነባራዊ

እውነት የሚያመለክተው የሐሳቡን ይዘት ብቻ ሳይሆን ሐሳቡ የእውነት ትክክለኛ ግንዛቤ መሆኑንም ጭምር ነው ። ሐሳባችን የእውነታ ትክክለኛ ግንዛቤ የመሆኑ ጉዳይ የሚረጋገጠው በተግባር በመሆኑ ማርክሲዝም ተግባርን የዕውቀት መሠረት ፣ ዓላማና የእውነት መመዘኛ አድርጎ ይወስዳል ። ስለ አንድ ሰው ማንነት ትክክለኛ መረጃ የምናገኘው ሰውዬው ስለ ራሱ በሚነግረንና ስለ ራሱም ካለው አስተሳሰብ ሳይሆን በተግባሩ እማካይነት እንደመሆኑ የዕውቀትም እውነትነት የሚወሰነው በሐሳብ ሳይሆን በነባራዊነቱ ነው ። ይህም ነባራዊነቱ በተግባር የሚገለጽና የሚረጋገጥ ነው ።

(ዕውቀትን ፣ ተግባርን ይመለከቷል ።)

## ነባራዊ ዕውቀት
*(Objective Knowledge)*

ይዘቱ በነባራዊ እውነታ የሚወሰን ፣ ነባራዊ እውነታን በትክክል የሚያንፀባርቅ ስለሆነም በማኅበራዊ ተግባር ላይ የሚመሠረትና ዓላማውም የተግባር መመሪያ ሆኖ የሚያገለግል ዕውቀት ማለት ነው ። ይህም በመሆኑ ይዘቱ በዐዋቂው ግለሰብ የማይወሰን ዕውቀት ነው ። ነባራዊ ዕውቀት ተጨባጩን ሁኔታ የሚያስረዳ ፣ ምሥጢሩንም በትክክል ለመመርመር የሚጥር ሲሆን ዓይነተኛ ጠባዩም ነገሮችንና ክስተቶችን ከዕድገትና ከእንቅስቃሴያቸው ሕግጋት አንፃር መገንዘቡ ነው። የዕውቀትን ነባራዊነት ለመረዳት የሚቻለው ከሰው ሐሳብና ፍላጐት ውጭ የሚገኙ ክስተቶችንና ነገሮችን የሚመለከት በመሆኑ ነው ። በእውነታ ውስጥ የሚገኙ ነገሮች በፍላጐታችን እንደማይመሩ ሁሉ ስለነሱ ትክክለኛ ግንዛቤ ሊኖረን የሚችለውም ከፍላጐታችን አንፃር ስንመለከታቸው ሳይሆን በሚገዙበት ሕግጋት አንፃር ስናጤናቸው ብቻ ነው ። ነባራዊ ዕውቀት የነባራዊ እውነታ ግንዛቤ በመሆኑ ረቂቅ ይዘት ቢኖረውም ከሕዋሳት መረጃዎች ጋር የተያያዘና ከነርሱም የሚጀምር ነው ።

ዕውቀት ኅሊናዊ (ኅሊናን ብቻ የሚመለከት) ነው የሚሉ ፈላስፎች ከተከሰቱ ጀምሮ ትክክለኛ ዕውቀት ነባራዊ መሆኑን ማሳየት አስፈልጓል ። ምክንያቱም ዕውቀት እውነት የሚሆነው ለተግባርም የሚያገለግለው በነባራዊነቱ ነው ። ዕውቀት ኅሊናዊ ነው ባዮቹ ፈላስፎች ስለዕውቀት ኅሊናዊነት ሲያስረዱ ነገሮችን የምንለያቸው በቀለም ፣ በክብደት ፣ በሽታ ፣ በቅርፅ ወዘተ... ሲሆን እነዚህ የነገሮች ባሕርያት ደግሞ ሐሳብ ወይም ሕውስታ ናቸው ፤ በሐሳባችን ውስጥ ያሉ እንጂ ከኅሊናችን ውጭ ቀለም ፣ ክብደት ፣ ሽታ ወዘተ... በነባራዊነት የሚገኙ አይደሉም ። ስለዚህም ዕውቀት የነዚህ ኅሊናዊ ክስተቶች ግንዛቤ እንጂ የነባራዊ እውነታ ግንዛቤ አይደለም ይላሉ ። አባባሉ ነባራዊ እውነታ ከንቃተ ኅሊናችን ውጭ የማይገኝና ሊታወቅ የማይቻል ፣ የምናውቀውም በሐሳባችን ውስጥ ያሉትን ሁኔታዎች በመሆኑ ዕውቀት ነባራዊነት ሊኖረው አይችልም ከማለት የሚዘል አይደለም ።

በማርክሳዊ የዕውቀት ንድፈ ሐሳብ አንፃር ዕውቀትን ወደ ሐሳብ ብቻ አዙሮ የኅሊና ግንዛቤ ማድረግ የዕውቀትን ምንነት መዘንጋት ነው ። ስለ እውነታ ያለን አመለካከት በሐሳባችን ውስጥ የሚገኝ ቢሆንም ቁምነገሩ ግን ሐሳቦች እራሳቸውን የቻሉ ሁኔታዎች እንዳለመሆናቸውና የሚያመለክቱትም እራሳቸውን ሳይሆን ከእነርሱ ውጭ የሚገኘውን እውነታ እንደሆነ መረዳቱ ነው ። ለምሳሌ ወንበር ስንል ይህ ሐሳብ ነው ፤ ሆኖም በሐሳብነቱ ብቻ የራሱ ህልውና ያለው ሳይሆን ከሐሳባችን ውጭ ያለውን ወንበር የሚያመለክት ነው ። ይህም የሚያስረዳን ሐሳብ የሚገልጸው የራሱን የሐሳብ ክስተቶችን ሳይሆን የነዚህ የሐሳብ ክስተቶች ምንጭ ነባራዊው እውነታ መሆኑን ነው ። ሐሳብ የነባራዊ እውነታ ነፀብራቅ በመሆኑ የምናውቀው የሐሳብ ሁኔታዎችን ሳይሆን የነባራዊውን እውነታ ምንነት ነው ። የዕውቀት ነባራዊነት መሠረቱ የእውነታ ነፀብራቅነቱ ነው። ለምሳሌ ደመና የዝናብ መንሥኤ ነው ስንል ለኅሊናዊ ፈላስፎች ይህ ነባራዊ ዕውቀት አይደለም ። በእነርሱ አባባል መንሥኤ ስንል ደመና ወደ ዝናብ እንዴት እንደሚቀየር ሳይሆን ከልምድ የተነሣ የደመናና የዝናብ ሐሳብ በአንጎላችን ውስጥ መያያዛቸውን መግለጻችን ብቻ ነው ፤ መንሥኤ ያልነው ነባራዊ ግንኙነትን ሳይሆን በሐሳባችን ውስጥ

ያለውን ግንኙነት ነው ። የዚህ አባባል መሠረታዊ ስህተት ሐሳቡ በእውነታ ውስጥ የሚገኙ ሁኔታዎችና ሕጎች ነፀብራቅ መሆኑና ምክንያት ሲባል የሁለት ሐሳቦች መያያዝ ከሆነ የሐሳቦች መያያዝ ምክንያት ደግሞ በእውነታ ውስጥ የሚገኙ ክስተቶች መያያዝ ነው ። ነባራዊ ዕውቀት የተባለውም የሐሳቦች ግንኙነቶች ከነባራዊው ሁኔታ የሚመነጩ በመሆኑ ነው ።

(አንፃራዊና ፍጹማዊ ዕውነትን ፣ ኅሊናዊ ሐሳባዊነትን ይመለከቷል ።)

## ነባር ካፒታል

*(Fixed Capital)*

በአንድ ሂደት ምርት ውስጥ እሴቱን ሙሉ በሙሉ ሳይሆን በከፊል ወደሚመረተው ሸቀጥ በማስተላለፍ ሸቀጡ ከተሸጠ በኋላ በገንዘብ መልክ ወደ ቡርዧዚው የሚመለሰው የምርታዊ ካፒታል ክፍል ነው ።

በነባር ካፒታል ውስጥ የሚጠቃለሉት እንደ ሕንፃዎች ፣ እንደ ልዩ ልዩ ማሽኖች ፣ እንደ ማጓጓዣ ዕቃዎችና የመሳሰሉት ነገሮች ናቸው ። እነዚህ ነገሮች አንድ ጊዜ ከተገዙ ወይንም ከተሠሩ በኋላ ከሞላ ጐደል ረዘም ላለ ጊዜ በምርት ክንዋኔ ውስጥ የሚቆዩ በመሆናቸው እሴታቸውን ሙሉ በሙሉ አስተላልፈው የሚጨርሱት ባንድ የምርት ሂደት ውስጥ ሳይሆን ከዚያ በላይ በሆኑ የምርት ሂደቶች ውስጥ ነው ።

ለምሳሌ አንድ ለሃያ ዓመት ጊዜ የሚያገለግል ማሽን ብንገዛ ይህ ማሽን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ አዲሱ ሸቀጥ የሚያስተላልፈው የእሴት መጠን በአማካይ 1/20ኛ ወይንም አምስት ከመቶ ያህሉን ብቻ ነው ማለት ነው ።

ካፒታልን በነባርና በተዘዋዋሪ ካፒታል ከፍሎ መመልከቱ የሚጠቅመው በካፒታል መገለባበጥ ፍጥነት ላይ የተለያዩ የምርታዊ ካፒታል ክፍሎች ያላቸውን የተለያየ ሚና በቅጡ ለማጤን የሚያስችል በመሆኑ ነው ።

ለምሳሌ ከላይ የጠቀስነው ማሽን እሴት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አምስት ከመቶ ያህሉ ብቻ ወደአዲሱ ሸቀጥ ሲተላለፍና ሙሉ በሙሉ እሴቱን ለማስተላለፍ የ20 ዓመት ጊዜ ሲፈጅበት ጥሬ ዕቃዎች ግን በአንድ የምርት ሁደት ውስጥ እሴታቸውን ሙሉ በሙሉ ወደአዲሱ ሸቀጥ ስለሚያስተላልፉ በካፒታሉ የመገለባበጥ ፍጥነት ውስጥ ተመሳሳይ ቦታ ሊሰጣቸው አይችልም ።

በመሆኑም በማርክሳዊ ሌኒናዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የዚህ ዓይነቱ የካፒታል አከፋፈል መሠረት የምርታዊ ካፒታሉ የተለያዩ ክፍሎች እሴታቸውን አዲስ ወደተመረተው ሸቀጥ የሚያስተላልፉበት የተለያየ ባሕርይ ያላቸው መሆኑ ሲሆን ፣ ካፒታልን በቋሚና በተለዋዋጭ ካፒታል የመከፈሉ መሠረት ደግሞ የተለያዩ የካፒታል ክፍሎች በእሴትና በትረፊ እሴት አመራረት ረገድ ያላቸው የተለያየ ሚና ነው ።

የቡርዧ ኢኮኖሚስቶች ግን ካፒታልን በነባርና በተዘዋዋሪ ካፒታል ብቻ የሚከፍሉበት መሠረታዊ ምክንያት የቡርዧዚው ትርፍ ምንጭ ያልተከፈለ የወዝአደሩ የሥራ ጊዜ መሆኑን ለመሸፈን ነው ።

(ተዘዋዋሪ ካፒታልን ይመለከቷል ።)

## ነገድ

*(Tribe)*

የጥንታዊ ጋርዮሽ ሥርዓት ዓይነተኛ ባሕርይ የሆነ የማኅበረሰብ ቅርፅ ነው ። በዚህ ወቅት በሰዎች መሀከል በወል ሠርቶ የመከፋፈልና የእኩልነት ግንኙነት ቢኖርም እያንዳንዱ ነገድ ከሌላው ነገድ በሚኖርበት አካባቢ ፣ በባህሉና በቋንቋው የሚለይ ነበር ። አንድ ሰው የአንድ ነገድ አባል መሆኑ ብቻ ከቀሩት የነገዱ አባላት ጋር እኩል የባለቤትነት ፣ ከምርቱ የመካፈልና በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ የመሳተፍ መብት ነበረው ። የወል ግንኙነት በሸቀጥ ግንኙነት መተካቱ ነገዶች ፈርሰው ወደ ብሔረሰብነት እንዲለወጡ አድርጓቸዋል ።

የነገድ አባላት እንደጐሳ አባላት በደምና በሥጋ ዝምድና ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ያላቸው ሳይሆን ግንኙነታቸው በኢኮኖሚያዊ ፣ በባህላዊና በአካባቢያዊ አንድነት ላይ የተገነባ ነው ። ስለሆነም ነገድ የጐሳ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ነው ። ነገድ የጥንታዊ ጋር

የሽ ሥርዓት ዓይነተኛ ባሕርይ ቢሆንም
አሁን ባለንበት ዘመን በአንዳንድ ኋላ ቀር
ሀገሮች ውስጥ የሚታይ ክስተት ነው ።

(ጕሳን ፡ ብሔረሰብን ፡ ብሔርን ይመለከ
ቷል ።)

## ነጭ ዋርድዮች
*(White Guards)*

በ1906 በፊላንድ ውስጥ ይካሄድ የነ
በረውን አብዮታዊ እንቅስቃሴ ለማፈንና
ለማክሸፍ ሲባል የተፈጠረ የቡርዧ
ፖሊስ ሠራዊት ነው ። አባላቱ ነጭ
ዋርድዮች የተባሉበትም ምክንያት መለያ
ቸው በክንዳቸው ላይ የሚያደርጉት ነጭ
ጨርቅ ስለነበር ነው ። በልማድ ነጭ የወግ
አጥባቂነትና የፀረ አብዮት ምልክት ሲሆን
ቀይ ደግሞ በአንፃሩ የአብዮትና የአብዮተ
ኞች ምልክት ነው ።

ከጊዜ በኋላ ግን ነጭ ዋርድዮች የሚ
ለው ስያሜ ከነዚያ የፊላንድ ፀረ አብዮት
ፖሊሶች አልፎ በአጠቃላይ አብዮት ለመቀ
ልበስ የተቋቋሙ ብሔረተኛ ወታደራዊ ድር
ጅቶች ከዚያም አልፎ የማንኛውም ፀረ አብ
ዮተኛ ወይም ግለሰብ መጠሪያ እየሆነ ሄደ ።

ለምሳሌ በ1918 እና በ1919 በሶቪዬት
ኅብረት በተካሔደው የእርስ በርስ ጦር
ነት ፡ በአድኃሪ የውጭ መንግሥታት እየተ
ረዱ አብዮቱን ለመቀልበስና የቡርዧዚውንና
የመሬት ከበርቴውን ሥርዓት ለመመለስ
ከፍተኛ የትጥቅ ትግል ያካሄዱት ነጭ
ዋርድዮች ናቸው ። በዚህም ትግላቸው
በብዙ ቦታዎች ጊዜያዊ ድሎችን በማግኘት
ከፍተኛ ሽብር ቢያካሂዱም የሶቪዬትን ሥል
ጣን ለመጣል አልቻሉም ። የሩሲያ ሠራተኛ
ሕዝብ በሌኒን በተመራው ኮሚኒስት ፓርቲ
ግንባር ቀደም መሪነት ታላቅ መሥዋዕትነት
የጠየቀ ተጋድሎ በማድረግ ነጭ ዋርድዮ
ችን ድል በመምታትና ከሀገር በማስወጣት
ሕዝባዊውን አብዮት ከቅልበሳ አደጋ አድ
ኗል ።

(አብዮታዊ ጦርን ፡ ሕዝባዊ ሠራዊትን ይመ
ለከቷል ።)

## ነጽሮት
*(Contemplation)*

አተኩሮ ማየት ፡ ማስተዋል ፡ መመርመር ፡
መመልከት ፡

በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ ነጽሮት የሰው
ልጅ ዕውቀት የሚደርስበት ከፍተኛ ደረጃ
ሆኖ ታይቷል ። ሐሳብ ከፍጹማዊ እውነት
ላይ ሲደርስ ከዕውቀት ተደራጊ ጋር ሊኖረው
የሚችለው ግንኙነት የነጽሮት ግንኙነት ብቻ
ነው ማለት የዕውቀት ግብ ተግባር እንዳል
ሆነ ማመልከት ነው ። በዚህ አመለካከት
እውነትን ማየት ለሰው ልጅ ተገቢ የሆነና
እራሱን የቻለ ፋይዳ ነው ። ንድፈ ሐሳብንና
ተግባርን የሚለያይ በመሆኑ አቋሙ ከሥረ
መሠረቱ ሐሳባዊ ነው ።

ይህን አቋም ማርክሲዝም በጥብቅ ተዋግ
ቶታል ። ቅድመ ማርክሳዊ ቁሳአካላውያን
ጭምር የዕውቀት ግብ የእውነት ነጽሮት ነው
ብለው ያምኑ ስለነበር በአጠቃላይ ለተግባር
የነበራቸውን ንቀት የሚያንፀባርቅ ነው ።
አቋሙም የሚገልጸው የተሳሳተ ሥነ ዕውቀ
ትን ነበር ። ሰው የሚኖርበትን ዓለም የሚ
ፈጥር ፡ የዕውቀትን ተደራጊዎች የሚቀርፅ ፡
እራሱ ተግባር መሆኑን ባለመረዳት በዕውቀ
ትና በተግባር መካከል ያለውን የቅርብ ግን
ኙነት ለመመልከት አልቻሉም ። ማወቅ
ማለት እውነትን መመልከት ሳይሆን በተግ
ባር እውነታን በመለወጥ ውስጣዊ ሕጎችን
ይፋ ማውጣት መሆኑን በማሳየቱ ነው ማር
ክሲዝም በሥነ ዕውቀት ውስጥ አዲስ አመ
ለካከትን ሊያመነጭ የቻለው ።

(ሥነ ዕውቀትን ፡ ተግባርን ይመለከቷል ።)

## ነፀብራቅ
*(Reflection)*

የዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ሥነ ዕው
ቀት መሠረታዊ ጽንሰ ሐሳብ ነው ። የነፀብ
ራቅ ልቡናዊ ፍች ከማንኛውም ቁስአካላዊ
የማንፀባረቅ ሁኔታ የተለየ ነው ። ልቡናዊ
ነፀብራቅ የሚለየው በእንስሳትና በሰው አንፀ
ባራቂ ሕዋሳት ላይ ነገሮች የሚፈጥሩት ተፅ
ዕኖ በአንጎል ውስጥ ወደነገሮች ምስል
በመቀየር የነገሮችን ኅሊናዊ ቅጂ በመቅ
ረፅ ነው ። እነዚሀ ምስሎች የሰውንና የእን

ስሳን እንቅስቃሴ በመምራት አካባቢውን ንቁ በሆነ መንገድ እንዲዳስሱ ይረዷቸዋል ። የልባዌ ነፀብራቅ ዋናው መለያ ጠባይ ያለው ነባራዊ ፍች ወይም መልእክት ነው ። በአንጎላችን ውስጥ የሚቀረፀው የነገሮች ምስል የነገሮች ኅሊናዊ ግልባጭ በመሆኑ ነባራዊነት የለውም ። ነባራዊነት ስለሌለውም ነው ከሱ ውጭ ስላለው ነገር የማመልከት ፣ የመግለጽ ሚና ሊጫወት የሚችለው ። ዋና ውን ማለትም ምንጩን አመልካች የሚሆን ውም የሐሳብ ግልባጭ በመሆኑ ነው ።

የነፀብራቅን ንድፈ ሐሳብ መሠረታዊ የሚያደርገው የዕውቀትንና የኑባሬን ምንነት መግለጹና የሐሳባውያንን አጠቃላይ አመለካከት ማረሙ ነው። ነባራዊ ሐሳባውያን ሐሳብ ራሱን ችሎ በነባራዊነት ይኖራል ለማለት የበቁት የሐሳብን ነፀብራቅነት በመካድ ነው ። ምክንያቱም ነፀብራቅ ማለት በሐሳብ ውስጥ የተቀረፀ ቅጅ ማለት በመሆኑ ቅጅው ዋናነት እንደሌለው ፣ ነገሮችም ከሱ ውጭ በነባራዊ ነት እንዳሉ የሚገልጽ ነው ። ስለዚህም የነ ፀብራቅ ንድፈ ሐሳብ የቁስአካልን ነባራዊነትና የዕውቀትን ምንጭነት ያረጋግጣል ። ኅሊናዊ ሐሳባውያን በበኩላቸው ሐሳብን ኅሊናዊ ብቻ በማድረግ ከውጭ ዓለም ጋር ሊመሳሰል አይችልም ያሉት የሐሳብን ነፀብራቅነት በመካድ ነው ። ነፀብራቅ ቅጅ(ኮፒ) እስከሆነ ድረስ ከዋናው ጋር ተመሳሳይነት ይኖረዋል ። የተንፀባራቂውና የአንፀባራቂው መመሳሰል የዕውቀትን ነባራዊነት ያረጋግጣል ። እንዲሁም ዕውቀት ፍጹማዊ ወይም አንፃራዊ ነው ለሚለው ጥያቄ የነፀብራቅ ንድፈ ሐሳብ ዲያሌክቲካዊ መልስ ይሰጣል ። የሚንፀባረቅ ነገር ሁሉ ከፊላዊ ነው ፤ ሆኖም ከፊል አካል ማለት በመሆኑ የተንፀባረቀው የነባራዊው አካልና በዚህም የተነሣ ነባራዊነት ያለው ነው ። በከፊልነቱም ሊባዛ ፣ ሊዳመር ይችላል ። በመሆኑም ትክክለኛው መልስ ዕውቀት ፍጹማዊ ወይም አንፃራዊ ነው የሚለው ሳይሆን ዕውቀት በየጊዜው የሚያድግ ታሪካዊ ባሕርይ ያለው መሆኑን የሚያስረዳው ነው ።

(አንፃራዊና ፍጹማዊ እውነትን ፣ ነባራዊ ሐሳባዊነትን ፣ ኅሊናዊ ሐሳባዊነትን ፣ ቁስአካልን ፣ ተግባርን ፣ እርቅቀትን ይመለከቷል ።)

## ነፃነት
*(Freedom)*

የሰው ልጅ ከተፈጥሮአዊና ከማኅበራዊ ሕግጋት በመነሣት ፍላጎቱንና ዓላማውን ለማሟላት አስፈላጊውን ርምጃ የመውሰድ ችሎታው ነፃነት ይባላል ። ነፃነት ፍጹማዊ ሳይሆን አንፃራዊ ፣ ረቂቅ ወይም ሐሳባዊ ሳይ ሆን ተጨባጭ ነው ። በአንድ ታሪካዊ ወቅት ሰዎች የሚኖራቸው ነፃነት በምርት ኃይሎች ዕድገትና ሰዎች ስለተፈጥሮአዊና ማኅበራዊ ተጨባጭ ሕግጋት ባላቸው ግንዛቤ ደረጃ እንዲሁም ባሉበት ኅብረተሰብ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ይዘት ይወሰናል ። በሌላ በኩል ነፃነት አንድ ሀገር የግዛት አን ድነቱና ብሔራዊ ክብሩ በሌላ ኃይል ተፅዕኖ ሥር ሳይወድቅ ህልውናውን አስከብሮ ራሱን በራሱ መምራቱን ያመለክታል ።

ነፃነት የሰውን ልጅ ከዲያሌክቲካዊ ሕግጋት ተገዥነት አያድነውም ። ሆኖም የእ ነዚህን ተጨባጭ ሕግጋት ውስጣዊ ምሥ ጢር በትክክል በመረዳት ለርሱ ህልውና ፣ ደኅንነትና ዕድገት በሚበጅ መንገድ ለመ ጠቀም ሁኔታው በሚፈቅደው መሠረት ሊወስዱ ከሚችሉት ርምጃዎች የመምረጥ ነፃነት ይኖረዋል ።

በመሠረቱ የግለሰቡ ነፃነት የማኅበረ ሰቡን ነፃነት ያመለክታል ። አንድ ግለሰብ ለብቻው ተነጥሎ ማኅበረሰቡ የሌለው ነፃ ነት ሊኖረው አይችልም ። በተፃራሪ መደ ቦች በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ግን ገዥው መደብ ተገዥውን መደብ ነፃነት በመንሣትና ለፍላጎቱ ተገዥ በማድረግ ለራሱ ነፃነት ይጠቀምበታል ። የጭቁኖች ትግል ዓላማ በዝ ባዥ መደቦች ከሚያደርሱባቸው ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ተፅዕኖ ነፃ መው ጣትና በአጠቃላይም ለሰው ልጅ ደኅንነት የሚበጅ ሥርዓት መመሥረት ነው ።

የሰው ልጅ ከጭቆና ተላቅቆ ሙሉ ነፃነቱን የሚያገኘው ተቃራኒ መደቦች ሲጠፉ ፣ መሠረታዊ ፍላጎቶቹ ሁሉ ሲሟሉና ኅብ ረተሰቡ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ ደርሶ በሳይንሳዊ ሕግጋት ሲመራ ነው ።

## ነፃነትና ግዴታ
(*Freedom and Necessity*)

በሰዎች እንቅስቃሴ ፣ በተፈጥሮና በኅብረተሰብ ነባራዊ ሕጎች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገልጹ የፍልስፍና ፈርጆችናቸው ። በሐሳባውያን አመለካከት ነፃነትና ግዴታ ተቃራኒ በመሆናቸው የተለያዩ ነገሮችናቸው ። ነፃነት የመንፈስን እራሱን በራሱ የመወሰን ችሎታን የሚገልጽ ሲሆን በተለይም የሚያስገነዝበው የሰው ፈቃድ በውጭ ሁኔታዎች ሳይወሰን ነፃ በሆነ መንገድ እራሱን እንደሚመራ ነው ። እንደሐሳባውያን አባባል የወሳኛዊነት አመለካከት ሰውንና ድርጊቱን ተወሳኝና ተደራጊ ስለሚያደርጋቸው ሰው ለሚሠራው ነገር ሁሉ ኃላፊና ተጠያቂ አይደለም ። በመሆኑም በሐሳባውያን አመለካከት ሰው ኃላፊና ግብረገባዊ ፍጡር ሊሆን የሚችለው ሙሉና ፍጹማዊ ነፃነት ሲኖረው ብቻ ነው ።

ተናከአታዊ ቁስአካላውያን የሰጡት አስተያየት የሐሳባውያንን አመለካከት የሚቃረን ነው ። በነሱ አባባል ሰው የተፈጥሮ አካል በመሆኑ ከተፈጥሮ ሕጎች ውጭ ሊሆን ስለማይችል ድርጊቶቹ በሙሉ የሚወሰኑት በውጫዊ ሁኔታዎች ነው ። በእርግጥም ይህ የተናከአታዊ ቁስአካላውያን አመለካከት የሰውን ድርጊቶች ከሱ ውጭ በሆኑ ኃይሎች የሚወሰኑ ማድረጉ ሰውን ተገብሮትና ተደራጊ ከማድረግ አላለፈም ነበር ።

የነፃነትና የግዴታ ግንኙነት ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ሊያገኝ የሚችለው በዲያሌክቲካዊ አመለካከት ነው ። ስፒኖዛ ነፃነት ማለት የታወቀ ግዴታ ነው በማለት ለመጀመሪያ ጊዜ የሁለቱን ግንኙነት ለመግለጽ ሞክሯል ። በትክክልም መልሱ ማምራት ያለበት ወደነባራዊ ግዴታ ቀዳሚነትና ወደሰው ፈቃድ ተከታይነት ወይም ሁለተኛነት ነው ። ግዴታ በተፈጥሮና በኅብረተሰብ ውስጥ በነባራዊ ሕግ መልክ ይገኛል ። የዚህ ሕግ ዕውቀት ሳይኖረን ሲቀር ግዴታ ጭፍን ሆና ይታየናል ። ለምሳሌ የሰውን ታሪክ መነሻ ስናይ ሰዎች የተፈጥሮአዊ ሕጎች ግንዛቤ ስላልነበራቸው ለግዴታ ተገዥ በመሆናቸው ነፃ አልነበሩም ። ሆኖም የሰዎች የሥራ ኃይልና የዕውቀት ደረጃ እየዳበረ ሲሄድ ድርጊቶቻቸው በይበልጥ ንቁና ነፃ እየሆኑ መጥተዋል ።

በሌላ በኩል የሰው ነፃነት የሚወሰነው በተፈጥሮ ብቻ አይደለም ፤ በማኅበራዊ ኃይሎችም የሚገዛ ነው ። በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ ማኅበራዊ ግንኙነቶች ከሰው በላይ በመሆን ሰዎችን ይገዛሉ ። ይህ ሁኔታ ሊቀር የሚችለው ማኅበራዊ ጭቆናን የሚያስወግደው ሶሻሊስት ሥርዓት ሲመሠረት ነው ። የምርት መሣሪያዎች ማኅበራዊ ይዞት ማግኘት በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የሚታየውን የምርት ምስቅልቅልነት ያስወግዳል ፤ በምትኩም ዕቅድ ያለውና ግባዊ የሆነ ሥርዓት ይመሠርታል ። ይህም በመሆኑ የሰው የኑሮ ሁኔታ ለሰዎች ባይተዋርና ግብታዊ መሆኑ ቀርቶ በነሱ ቁጥጥር ሥር ይውላል ። የሰዎች የምርት ኃይልና የዕውቀት ደረጃ እያደገ ሲሄድ የሰዎች ነፃነት እየሰፋ መምጣቱ የሚያስረዳው ነፃነት ታሪካዊና ማኅበራዊ ክስተት መሆኑን ነው ።

(ወሳኛዊነትን ፣ ፈቃዳዊነትን ይመለከቷል ።)

## ነፃዊነት
(*Liberalism*)

የተጣጣመ ማኅበራዊ ሕይወትንና የሰው ልጅ ዕድገትን ለመቀዳጀት የሚቻለው ንብረት በግል ሲያዝና ግለሰቦች በኢኮኖሚያዊና በሌሎች የሕይወት ዘርፎች ውስጥ ለሚያከናውኑት ተግባር በቂ ነፃነትና ዋስትና ሲያገኙ ብቻ ነው የሚል የቡርዧ ርዕዮተዓለማዊ ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ነው ።

የነፃዊነት አራማጆች የቡርዧውን ፓርላማዊ ሥርዓት ፣ የቡርዧውን የነፃነትና የነፃ ካፒታሊስታዊ ውድድርን ሐሳብ የሚደግፉ ፣ ነፃ ውድድር የሥርዓቱ መሠረት መሆኑንና መንግሥት በኢኮኖሚው ዘርፍ ጣልቃ መግባቱ ቀውስ የሚያስከትል ነው የሚሉ ናቸው ። የነፃዊነት አስተሳሰብ የሚያንፀባርቀው የቡርዧዚውን ግላዊነት ነው ። ከዚህም በመነሣት የኅብረተሰቡ አጠቃላይ ደኅንነትና ምቾት የሚገኘው በግለሰቡ ዓላማና እንቅስቃሴ ነው ፤ ግለሰቦች በነፃ ውድድርና እንቅስቃሴ አማካይነት የሚቀዳጁት ድልና የሚያገኙት ውጤት በኅብረተሰብ ደረጃ ሲታይ የጠቅላላው ኅብረተሰብ ዕድገትና ደኅንነት መሠረት ሆኖ ይገኛል የሚል ነው ።

ሆኖም ካፒታሊዝም እያደገ በሄደ ቁጥር የነፃዊነትም ይዘት በዚያው መጠን እየተለወጠና በርካታ መልኮች እየያዘ መጥቷል ።

ነፃዊነት በተከሰተበት የመጀመሪያ ወቅት ተራማጅ ቡርዧዚና ወደ ቡርዧዚነት የተለወጠው የመሬት ከበርቴ ትግል ያተኮረው በፊውዳሊዝምና በሃይማኖት ሳቢያ በሚፈጸመው ጭቆና ላይ ነበር ። በዚህም ጊዜ ነፃዊነት በፊውዳሊዝም ላይ ለሚካሄደው ሁለንታዊ ትግል (ለዕድገት ፣ ለሰላም ፣ ለነፃነት ፣ ለእኩልነት) አጋዥ ነበር ። የነፃዊነት አንጋፋ አራማጆች ተብለው የሚጠሩት የአብርሆት ርዕዮተዓለማውያን በተለይም ወግ አጥባቂ ያልሆነው ክንፍ አባላት የነበሩት ሎክ ፣ ሞንተስኪየ ፣ ቮልቴርና የቡርዧ ብሎይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መሥራች የነበሩት አዳም ስሚዝና ዴቪድ ሪካርዶ ነበሩ ።

ሆኖም በ1830ዎቹ ውስጥ በቡርዧዚውና በሠራተኛው መደብ መካከል ያለው ቅራኔ በመባባሱ ፣ ከፈረንሳይ የ1830 አብዮት በኋላና በተለይም በታላቋ ብሪታንያ በ1832 ከተካሄደው የፓርላማ ጥገናዊ ለውጥ በኋላ የቡርዧዚው ፀረ ወዝአደርነት አዝማሚያ እያደገና ሥር እየሰደደ መጣ ። ነፃዊው ቡርዧዚ በወቅቱ በሚያካሂደው ጥገናዊ ለውጥ አማካይነት የሠርቶአደሩን ሕዝብ የትግል ውጤቶች ከንጉሣዊ የአድኅሮት ኃይሎች ጋር ለመደራደር ፣ ካፒታሊስታዊ ብዝበዛን ለማድበስበስና ለመሸፈን ነፃዊነትን ተጠቅሞበታል ። ይህ የነፃዊ ቡርዧዚ አዝማሚያ የቻርቲስት ንቅናቄን ፣ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎችንና ወዝአደራዊ ንቅናቄዎችን ለማፈን ባደረገው ጥረት ሊከሰት ቻለ ። በዚህም ጊዜ ነፃዊነት በተወሰኑ የንዑስ ከበርቴና የሠራተኛ ማኅበራት አባል ሠራተኞች ላይ ከፍተኛ ርዕዮተዓለማዊና ፖለቲካዊ ተፅዕኖ ለማሳደር ችሏል ። ከዚህም የተነሣ የቡርዧዚውን የፓርላማና የነፃ ውድድር ስሜት በማጠናከር ነፃዊነት በአሁኑ ወቅትም ቢሆን የተለያዩ መልኮችን በመያዝ የቡርዧዚውን ማኅበራዊና ፖለቲካዊ አስተሳሰቦች እንደ ሁኔታው በማራመድ ላይ ይገኛል ።

## ነፃ ውድድር
(*Free Competition*)

በምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት ላይ የተመሠረተ በካፒታሊዝም ዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ወቅት ሰፍኖ የሚገኝ የሸቀጥ ምርት ሥርዓት ነው ።

ነፃ ውድድር በግል አምራቾች መካከል ለምርትና ለገበያ የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠር የተካረረ ትግል የሚካሄድበት ሁኔታ ነው ። በዚህ የካፒታሊስት ዕድገት ደረጃ ፣ ካፒታሊስቶች ከፍተኛ ትርፍን ለማግኘት በመካከላቸው ከፍተኛ ውድድር ከማካሄዳቸውም በላይ የምርት ሥርዓት አልባነት ሰፍኖ ይታያል ።

ነፃ ውድድር የምርት መገልገያ መሣሪያዎች በግል ካፒታል ሥር ከመዋላቸው የመነጨ ሲሆን ማኅበራዊ ምርትን ግብታዊ በሆነ መንገድ የመቆጣጠሪያም ስልት ነው ። ነፃ ውድድር አንዳንድ አምራቾች እንዲከስሩና ሌሎች እንዲከብሩ የሚያደርግ በመሆኑ በካፒታሊስቶች መካከል የሀብት ልዩነት በመፍጠር ለካፒታሊስት የምርት ግንኙነት መዳበር ሁኔታዎችን የሚያመቻች ነው ።

በቅድመ ሞኖፖል ካፒታሊዝም ወቅት ሰፍኖ ይገኝ በነበረው የነፃ ውድድር ደረጃ ውድድሩ በተለይም ዋጋን በሚመለከት በዋጋ ቅነሳ መልክ ይካሄድ ነበር ። ይህ ውድድር የዋጋ ቅነሳው የምርት ወጪውን ሊሸፍን ያልቻለ አምራች ሁሉ እንዲከስርና ከገበያ እንዲወጣ የሚያደርግ ነው ።

በዚህ የካፒታሊዝም ዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ሁለት ዋና ዋና የውድድር ቅርፆች ነበሩ ። የመጀመሪያው ዓይነት ውድድር ተመሳሳይ ሸቀጥ በሚያመርቱ መካከል አንዱ ባንዱ ላይ የበላይነትን ለማረጋገጥ የሚካሄድ ሲሆን ፣ ሁለተኛው ዓይነት ውድድር ደግሞ ካፒታልን አነስተኛ ትርፍ ከሚገኝበት ከፍተኛ ትርፍ ወደሚገኝበት መስክ በማሸጋገር ከፍተኛ ትርፍ የሚያስገኘውን መስክ ለመያዝ የሚያደርገው ውድድር ነው ።

በመሆኑም ውድድር በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ለምርት ኃይሎች ዕድገት ዓይነተኛ ምክንያት ነው ። ማናቸውም ካፒታሊስት የምርት ወጪውን በመቀነስ ተፎካካሪውን ከገበያ ለማስወጣት በሚያ

ደርገው ጥረት ዘመናዊ የምርት መሣሪያ ዎችንና ቴክኖሎጂን ለማስተዋወቅና አዳ ዲስ የአመራረት ዘዴዎችን ሥራ ላይ ለማ ዋል ይገደዳል ። በዚህ ሁኔታም የምርት ኃይሎች ሊያድጉ ይችላሉ ።

ውድድር ለምርት መሰባሰብ ዓይነተ ኛና ዋነኛ መንሥኤ በመሆኑ በሂደቱ ሞኖ ፖሎችን በመመሥረት ካፒታሊዝም ከነፃ ውድድር ደረጃ ወደ ኢምፔሪያሊዝም ደረጃ እንዲያድግ የሚያደርግ ነው ። በሞኖፖል ደረጃም ቢሆን ውድድር መልኩን ለውጦ ይቀርባል እንጂ አይጠፋም ።

(ሌሴፌርን ፣ ሞኖፖል ካፒታሊዝምን ይመለ ከቷል ።)

## ነፍሳዊነት
## (*Animism*)

ነፍስና መንፈስ የሰዎችንና የእንስሳትን ኑሮ ይወስናሉ ፤ በነገሮችና በክስተቶች ላይም ተፅዕኖ አላቸው የሚል እምነት ነው ። ይህ አስተሳሰብ የመነጨው በጥንታዊ ኅብረተሰብ ውስጥ ነው ። በጊዜው ሰዎች እንስሳት ፣ እት ክልቶችና ነገሮች ነፍስ አላቸው ብለው ያምኑ ነበር ። የዚህ አስተሳሰብ ምክንያት የምርት ኃይሎች በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆና ቸውና የሰውም ዕውቀት በዚሁ ደረጃ የተወ ሰነ መሆኑ ነበር ። ሰዎች ከተፈጥሮ ኃይሎች ጋር ለመታገል በቂ ኃይል ሳይኖራቸው ሲቀር እነዚህ ኃይሎች ባዕድና ምሥጢራዊ ይሆኑባቸዋል ። በተወሰነ የዕድገት ደረጃ ላይም ነፍሳዊነት ለነዚህ ኃይሎች ሰብአዊ መልክ በመስጠት ከሰው ጋር ሊያመሳስላቸው የሚ ችል አስተሳሰብ ሆኖ ተከስቷል ። የነፍሳዊ ነት ጽንሰ ሐሳቦች ለሃይማኖቶች ጠቃሚ መሠረት ሆነዋል ።

## ኑባሬ
## (*Being*)

በፍልስፍና ፍቺው ኑባሬ የሚገልጸው የመ ኖርን አጠቃላይ ግንዛቤ ነው ። ህልውና የሚ ገለጸው በሚያሳያቸው ክስተቶች (ቁመት ፣ ቀለም ፣ ጠባይ ወዘተ..) ሲሆን እነዚህ ክስ ተቶች ተለዋዋጭ ፣ ኃላፊና ግሳዊ ናቸው ። መኖር ግን እራሱን የቻለ ሁለንታዊ ሁኔታ በመሆኑ ኑባሬ የሚለው ጽንሰ ሐሳብ የሚገ ልጸው ኑባሬን በራስነቱ ብቻ ለመገንዘብ የሚደረገውን ጥረት ነው ። በዚህ አገባቡ ከክስተቶች ባሻገር የዓለም መሠረት ምንድ ነው ከሚለው ጥያቄ ጋር ይያያዛል ።

በመሆኑም የኑባሬ ንድፈ ሐሳብ በቁስ አካላዊና በሐሳባዊ አቀራረቦች የተከፈለ ነው። ለሐሳባውያን ሐሳብ የዓለም መሠረት በመ ሆኑ ቁስአካልና ክስተቶቹ ከሱ የተፈጠሩና የሱን ዝቅተኛ ደረጃ የሚገልጹ ናቸው ። ለሁሉ ነገር ምንጭና መሠረት በመሆን ሐሳብ ኑባሬን በኑባሬነቱ የሚገልጽ ነው ። በቁስአካላውያን አመለካከት ከሐሳብ ውጭ በመሆን ኑባሬነት ያለው ቁስአካል ብቻ ነው ። ቁስአካል በተለያዩ ክስተቶች የሚገ ለጽ ሲሆን ያልተፈጠረ ፣ ዘለዓለማዊ ፣ የሐሳብና የነገሮች ሁሉ ምንጭና መሠረት በመሆኑ ብቸኛ ኑባሬ ነው ።

ይህ የኑባሬ ፍች ራሱን ችሎ ያለና የራሱ ምክንያት የሆነ የዓለምን አጠቃላይ ግንዛቤ የሚመለከት በመሆኑ የዕውቀት የመጨረሻ ግብ ሆኖ ታይቷል ። የኑባሬን ምንነት አስመልክቶ በቁስአካላውያን መካ ከል የሚኒሣው ክርክር የፍልስፍናን መሠ ረታዊ ጥያቄ የሚመለከት ነው ። ቅድመ ማርክሳዊ ቁስአካላውያን ሐሳብ የራሱ ህል ውና የሌለው የኑባሬ ነፀብራቅ መሆኑን የገ ለጹ ቢሆንም በሐሳብና በኑባሬ (ቁስአካል) መካከል ያለውን ዲያሌክቲካዊ መስተጋብር አልተረዱም ነበር ። በተለይም ሐሳብ ተወ ሳኝ ተገብሮት ብቻ አለመሆኑንና እምሳላዊ ነፀብራቅ በተግባር ወደ ኑባሬ ሊቀየር ወይ ንም ሊለወጥ እንደሚችል ማስገንዘቡ አስ ፈልጎ ነበር ። ለኑባሬ ቅድሚያ በመስጠት ነገር ግን ሰው በንቁ እንቅስቃሴው የራሱ ታሪክ ሠሪ መሆኑን በማሳየት ስለሐሳብና ስለኑባሬ ግንኙነት ትክክለኛውን ግንዛቤ ያስ ተማረ ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ነው ።

(ሥነ ኑባሬን ይመለከቷል ።)

## ኒቼ ፣ ፍሪድሪሽ ቪልሄልም
## (*Nietzsche, Friedrich Wilhelm*)

ከ1844—1900 የኖረ የፋሺዝም ንድፈ ሐሳብ ቀዳማይ አመቻች የሆነ ፣ በባሰል (ስዊዘርላንድ)

የፊሎሎጂ ፕሮፌሰር የነበረ ፣ ጀርመናዊ ሐሳባዊ ፈላስፋ ነው ። ከዕውቅ ሥራዎቹ ውስጥ "ዘስ ስፔክ ዛራቱስትራ" ፣ "ቢዮንድ ጉድ ኤንድ ኢቭል" ፣ "ዘ ዊል ቱ ፓወር" የተባሉት ይገኙበታል ። ኒቼ የነበረበት ወቅት ካፒታሊዝም በዕድገቱ ወደ ኢምፔሪያሊዝም ደረጃ የተሸጋገረበት በመሆኑ ንጽረተ ዓለሙ በአብዮትና በሕዝብ ጥላቻ በጣም የተበከለ ነበር ። ብዝበዛ "ከማናቸውም ሕይወት ካለው ነገር ጋር የተቆራኘ ነው" በማለት የብዝበዛን ትርጉምና መሠረት ለማድበስበስ ይሞክራል። ጠቅላላ ሐሳቡ የታሪክ ዕድገት ውጤት የሆነውን የአብዮት ማዕበል ለማገተት የሚጥር ነው ። ከዚህም አስተሳሰብ በመነሣት የለዘብተኛውን ቡርጂ ርዕዮተዓለማዊ መርሆችና መለኪያዎች ለመቀየር በማሰብ ምክኑያዊ ፍልስፍናን ፣ ልማዳዊ ሥነ ምግባርንና የክርስቲያን ሃይማኖትን ካጠና በኋላ እነዚህ ሁሉ የትግልን መንፈስ ቢያዳክሙም እያደገ የሚሄደውን አብዮታዊ እንቅስቃሴ ለመግታት የማይችሉ በመሆናቸው በምትካቸው ኢሰብአዊ በሆኑና ዲሞክራሲያዊ ባሕርይ በሌላቸው መርሆች መጠቀም እንደሚያስፈልግ ሐሳብ አቅርቧል ።

በሠራተኛው ሕዝብ ውስጥ የታዛዥነትና የበታችነት መንፈስ እንዲኖር ለማድረግ የባሪያ ሞራሊቲ ፣ ገዥዎችን ለማሠልጠን የገዥዎች ሞራሊቲ በማለት የሚጠራቸውን የርዕዮተዓለም መልኮች ማስራጨት አስፈላጊ ነው ይላል ። ለሁለተኛው የርዕዮተዓለም መልክ መሠረቱ አድርጐ የሚወስደው የማያወላውል የሕግና የግብረገብነት ግላዊነት ነው ይላል ።

ኒቼ ፍላጎትን ከአመንክዮ ጋር ስለሚያቃርን ፍልስፍናው ፈቃዳዊ ነው ። የዕድገት ሁለንታዊ እንቀሳቃሽ ኃይል የኃይል ፍላጎት ነው ብሎ ያምናል ። ሕይወት ለኃይል የሚደረግ ትግል ከሆነ አስፈላጊው ነገር የበላይነትን መጐናፀፍ ነው ። ጥሩና እውነት ማለት የበላይነትን ለማስጠበቅ የሚረዳ ደንብና ሥርዓት ነው ። ስለዚህ የተፈጥሮ የአዝጋሚ ለውጥ ሕግ የሚሻው (የሚፈጥረው) ጥቂት ብርቱዎችንና አሸናፊዎችን ለማስገኘት ነው የሚል የሕይወት ፍች ስላለው የኒቼን ንድፈ ሐሳብ የፋሺዝምን ንድፈ ሐሳብ ለመቀመር ሌሎች ተጠቅመውበታል ።

(ፈቃዳዊነትን ይመለከቷል ።)

## ኒውተን ፣ ይስሐቅ
*(Newton, Isaac)*

ከ1642—1727 የኖረ እንግሊዛዊ የፊዚክስ ሊቅና የብሉይ ተናከአት መሥራች ነበር ። የስበትን ሁለንታዊ ሕግ የደነገገና በተናከአታዊ ቁስአካልነት ዕድገት ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ ነበር ። ኒውተን በ1669 የካምብሪጅ ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር በመሆን ያገለገለ ሲሆን ፣ ዋና ጽሑፉ "ፊሎሶፊያ ናቱራሊ ፕሪንሲፕያ ማቴማቲካ" (1687) የሚባለው ነበር ። በዚህም የቅስቃሴ ሕጎችን( የዘላቂነት ሕግ ፣ የፍጥነትና የኃይል ምጥነት ሕግና እንዲሁም የአድራጊና ተደራጊ እኩልነት ሕግጋት) አጥንቶ ከአያሌ መደምደሚያዎች ላይ ደርሷል ። ስምሳሌ የብሉይ ተናከአትንና የብሉይ ፊዝክስን መሠረት የጣለ ኒውተን ነው ። ፍጹማዊ ቅስቃሴ ከቁስአካላዊ አካሎች ጋር ዝምድና የሌለው ነገር ግን በባዶው ፍጹም ስፍራና ጊዜ ያለው መሆኑን በመርሁ አረጋግጧል ። እንዲሁም በተጨማሪ ኒውተን አካሎች በመካከላቸው ያለው የእርስ በርስ ስበት ካላቸው ክብደትና በአንፃሩም በመካከላቸው ካለው ርቀት መጠን ጋር የተመጣጠነ መሆኑን ተገንዝቧል ። በመርሁ ውስጥ የኬፕለርን የጠፈር ዓለማትን ቅስቃሴ ሕግጋት ተቀብሎታል ። በጠቅላላው ዩኒቨርስ ውስጥ ባሉ ነገሮች ላይ ሳይንሳዊ ትንታኔ በመስጠት የስበትን ሁለንታዊ ሕግጋት መሠረት አስይዟል ።

ከዚህም ሌላ ኒውተን የአካላዊና የኬሚካላዊ ነገሮችን ግንዛቤ በማቀነባበር የዓለምን አካላዊ አንድነት ለማረጋገጥ ችሏል ።

ይሁን እንጂ የኒውተን የስበት ንድፈ ሐሳብ ተቃውሞ ደርሶበት ነበር ። ምክንያቱም የስበት ንድፈ ሐሳቡ አንዱ አካል በሌላው አካል ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩን ያሳያል እንጂ በመካከላቸው ያሉት የሌሎች አካሎች ስበት ተፅዕኖ እንደሚያደርግ አልተገነዘበምና ነው ።

ኒውተን ስለብርሃንና ስለማቴማቲክስም የተገነዘባቸው አዳዲስ ነጥቦች ነበሩት ። በፍልስፍናው ረገድ የነባራዊውን እውነታ መኖር በመቀበልና ዓለም ሊታወቅ ይችላል በሚለው አቋም ጸንቶ ነበር ። ሆኖም ይህን ተናከአታዊ አመለካከቱን ከሃይማኖት ጋር እንደማይቃረን አድርጐ ቆጥሮታል ።

በኒውተን አስተሳሰብ ኃይልና ስበት የጠፍር አካሎችን ተደጋጋሚና መጨረሻ የሌለው ክባዊ እንቅስቃሴ ይገልጻሉ ። ይሁን እንጂ በዚህም "ለመጀመሪያው ግፊት" እግዚአብሔር ምክንያት ነው ይላል ።

ኒውተን ሥነ መለኮታዊ አመለካከት ቢኖረውም እንዲሁም የክስተቶችን ውስጣዊ ምክንያት ለመተንተን ባይፈቅድም አስተሳሰቡ ለቁስአካልነት ዕድገት አስተዋጽኦ አድርጓል ።

## ናሮዲዝም
(*Narodism*)

በ1860ዎቹ ዓመታት መጨረሻ ላይ በሩሲያ አብዮታዊ ንቅናቄ ውስጥ የተከሰተ የንዑስ ከበርቴ አድኃሪ እንቅስቃሴ ሲሆን ዓላማው ቁሳራዊ ፊላጭ ቆራጭ አገዛዝን ማጥፋትና መሬትን ለገበሬዎች እኩል ማደላደል ነበር ። ይህ የናሮዲያውያን አቋም በወቅቱ በሩሲያ ውስጥ በብዛት የሚገኘውን ገበሬ ፍላጎት የሚያንፀባርቅ ነበር ። ናሮዲያውያን በዚህ አቋማቸው ራሳቸውን እንደ ሶሻሊስቶች ይቆጥሩ ነበር ። ነገር ግን የነርሱ ሶሻሊዝም በኅብረተሰብ ዕድገት ነባራዊ ሕጎች ላይ ያልተመሠረተ በመሆኑና የገጠር ኮምዩኖችን የሶሻሊዝም ጥንስሶች አድርገው ስለሚቆጥሩ ከንዑስ ከበርቴ ተምኔታውያን አልተለዩም ።

ናሮዲያውያን መሬትን ለገበሬው እኩል በማከፋፈል በገጠሩ የሶሻሊስት የምርት ግንኙነትን ለመመሥረት ጥረት አድርገዋል ። ኖሮዲያውያን በሩሲያ አብዛኛው ሕዝብ ገበሬ ስለነበር ሶሻሊዝም ሊመሠረት የሚችለው በገጠር ብቻ እንደሆነና የዚህ አብዮትም ዋና ኃይል ሠራተኛው ሳይሆን ገበሬው ነው ይሉ ነበር ። ከዚህ የተሳሳተ አመለካከት የተነሡ በመሆናቸው ሰፊውን ሕዝብ በመተው የታጠቁ ጥቂት ግለሰቦች የዘውድ አገዛዝን ሊገረስሱና ፍትህና እኩልነት የሰፈነበትን ኅብረተሰብ ሊገነቡ ይችላሉ ብለው ነበር ። በዚህም ገበሬውን በቁሳሩ የዘውድ አገዛዝ ላይ በማነሣሣት ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ ወደ ገጠር ገቡ ። ነገር ግን በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ማጣታቸውንና ሐሳባቸው ውድቅ መሆኑን ሲረዱ "የሕዝብ ፈቃድ" በተሰኘ የሤራ ቡድን አማካይነት በአድኃሪው መንግሥት ላይ ሽብር ማካሄድ ጀመሩ ። በዚህ የሽብር ዘመቻቸው በ1881 ቁሳሩን ዳግማዊ እስክንድርን ገድለዋል ።

ናሮዲዝም የተለያዩ ደረጃዎችን በማለፍ ከዲሞክራሲያዊ ንቅናቄነት ወደ ቡርዧ ለዘበኝነት አዝቅጧል ። የኋላ ኋላም ከቁሳሩ መንግሥት ጋር የዕርቅ ፖሊሲ በማውጣት የሀብታም ገበሬዎችን አቋም ይዞ ማርክሲዝምን ተዋግቷል ። በመጨረሻም ባለንበት ምዕት ዓመት መግቢያ ላይ የናሮዲዝም አቋም ሕዝባዊ ሶሻሊስቶችና ሶሻሊስት አብዮታውያን በተሰኙ ቡድኖችና በሌሎች የንዑስ ከበርቴ ፀረ አብዮት ወገኖች ቢስተጋባም አድኃሪ ዓላማው ሊሳካ አልቻለም ።

## ንቁ
(*Conscious*)

ንቁ ሲባል ማናቸውንም ዓላማ ያለውን እንቅስቃሴ የሚመለከት ሲሆን በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ግንዛቤው ሁኔታዎችን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚገነዘብና ከታሪክ ሂደት ሕግጋት አንፃር እንዲለወጡ ተሳትፎ የሚያደርግ ማለት ነው ። በዚህ ሁኔታ የተከናወነ ድርጊትም ንቁ ይባላል ። ለምሳሌ ንቁ ተሳትፎ ።

(ንቃተ ኅሊናን ይመለከቷል ።)

## ንቃተ ኅሊና
(*Consciousness*)

ሰው ብቻ ሊደርስበት የሚችል ነባራዊ ዓለምን የማንፀባረቅ ከፍተኛ ደረጃ ነው ። ንቃተ ኅሊና ፣ ሰው ስለነባራዊው ዓለምና ስለ ራሱ ሰብእና ግንዛቤ ለማግኘት የሚያስፈልጉትን አእምሮአዊ ሂደቶች በሙሉ ያጠቃልላል ። የሰው የሥራ ችሎታ ፣ ማኅበራዊ የምርት እንቅስቃሴና ቋንቋ የንቃተ ኅሊና አጠቃላይ ምንጮች ናቸው ። በሂደተ ሥራ ውስጥ በሚፈጠሩት ማኅበራዊ ግንኙነቶች አማካይነት ነው ሰው ስለአካባቢው ፣ ስለ ነገሮች ፣ ስለራሱ ምንነት ግንዛቤ የሚያገኘውና በፍላጎትና በዕቅድ በመመራት ተፈጥሮን የሚቀይረው ። ስለሆነም ንቃተ ኅሊና የማኅበራዊ ኑሮ ዕድገት ውጤት ነው ፤ ከኅብ

ረተሰብ ውጭ ሊከሰት ወይም ሊኖር አይች
ልም ።

ንቃተ ኅሊና የማንፀባረቅ ከፍተኛ ደረጃ
ነው የሚባለው ውጭውን ዓለም በሕውስታ
በማንፀባረቅ ብቻ ሳይወሰን ከዕውቀት ደረጃ
ላይ በመድረስ በሕውስታ የሚደርሱንን ምልክ
ቶች ፍች ፣ ሚናና ምንነት ስለሚረዳ ነው ።
ንቃተ ኅሊና ዕውቀት የሚያስገኛቸው የተለያዩ
አስተሳሰቦችን ከሰው ፍላጎትና ስሜት ጋር
በማጣመር የሚገኝ የኅሊና ዓይነት ነው። ሰው
በረቂቅ ሐሳብ ችሎታ ብቻ የማይወሰንና ፍላጎ
ቶችና ስሜቶችም ያሉት በመሆኑ በግንዛቤው
ውስጥ አመክንዮአዊ አስተሳሰቡ ከስሜቶችና
ከፍላጎቶች ጋር የተዋሀደ ነው ። ንቃተ ኅሊና
ልቡናዊ ብቻም አይደለም ። ንቁ ያልሆኑ ስሜ
ቶች ስላሉ ከልቡና ጋር ሙሉ በሙሉ ማዋሀዱ
ትክክል አይሆንም ።

(ልቡናን ፣ ራስንቃተ ኅሊናን ፣ ፍሮይድን
ይመለከቷል።)

## ንዑስ ከበርቴ
(*Petty Bourgeoisie*)

በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ መሠረ
ታዊ መደብ ያልሆነ ነገር ግን የማይናቅ ፖለ
ቲካዊ ሚና ያለው ፣ ገበሬዎችን ፣ የእደጥበባት
ባለሙያዎችን ፣ ትናንሽ ነጋዴዎችን ፣ ትናንሽ
ባለግል ንብረቶችን የሚያቅፍ የኅብረተሰብ
ክፍል ነው ። ይህ መደብ በኢኮኖሚያዊ
አቋሙ በቡርዧዚውና በወዝአደሩ መካከል
የሚገኝ ነው ። የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ
ከቡርዧዚው የሚያቀራርበው ሲሆን እራሱ
ሠራተኛና የካፒታል ጭቆና የሚፈጸምበት
መሆኑ ደግሞ ከወዝአደሩ ጋር ያመሳስለዋል ።
ይህ ማኅበራዊ ቦታው መደቡን ብዙውን
ጊዜ ወላዋይ የሆነ የፖለቲካ አቋም እንዲኖ
ረው ያደርገዋል ።

የንዑስ ከበርቴ ማኅበራዊ ኑሮ ዓይነተኛ
ጠባይ ቋሚነትና እርጋታ ማጣቱ ነው ። የካ
ፒታሊዝም እንቅስቃሴና ዕድገት ይህን
መደብ በየጊዜው እንዲመሰቃቀል ያደርጋል።
የመደቡ አነስተኛው ክፍል ሀብቱን ከፍ በማ
ድረግ ከካፒታሊስቱ ጋር ሲቀላቀል ፣ አመ
ዛኙ ደግሞ በመክሰሩ ወደ ወዝአደርነት ወይም
ወደ ጥገኛ ባለንብረትነት ይለወጣል ። አነ
ስተኛ የምርት ክንውን ከሰፋፊ የምርት ክን
ውን ጋር መፎካከር ባለመቻሉ የካፒታሊዝም
ነፃ ፉክክር ሂደት በሚጠይቀው መሠረት
የንዑስ ከበርቴው መደብ በየጊዜው የመፍ
ረክረክ ዕድል ይገጥመዋል ።

ይህ ማለት ግን ካፒታሊዝም የንዑስ
ከበርቴውን መደብ ጨርሶ ያጠፋዋል ማለት
አይደለም ። በአንድ በኩል መደቡን ማጥፋት
ለሱ ጠቃሚ አይደለም ። ምክንያቱም በመካከል
ያለ መደብ በመሆኑ ቡርዧዚውና ወዝአደሩ
በቀጥታ እንዳይፋጠጡ የሚረዳ ነው ። በሌላ
በኩል የካፒታሊዝም ዕድገት ሁሌም የተዛ
ባና ያልተመጣጠነ በመሆኑ የአንዳንድ የም
ርት ክፍሎች ወደ ኋላ መቅረት ለንዑስ
ከበርቴ መደብ መቆየት ምክንያት የሚሆን
ነው ።

(መሠረታዊና ኢመሠረታዊ መደቦችን ይመ
ለከቷል ።)

## ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀት
(*Theoretical Knowledge*)

ዕውቀት ዐድጐ ምንነቱ ተሟልቶ
የምንደርስበት ደረጃ ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀት
ይባላል ። የዚህ ዕውቀት መነሻው ዳሰሳዊ
ዕውቀት ቢሆንም የተጨባጩን ግንዛቤ ለማ
ግኘት በተለያዩ ዘዴዎችና ሥነ አመክንዮዎች
ይጠቀማል ። ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ ረቂቅ
አስተሳሰብና በሥነ አመክንዮአዊ ሕጎች
በመመራት ማገናዘብና ማዋቀር ናቸው ።
ረቂቅ ሐሳብ የሚገኘው በሕዋሳት የሚደር
ሱንን መረጃዎች በመለያየት በመልካቸውና
በባሕርያቸው ከፋፍለን ስናስቀምጣቸው
ነው ። ለምሳሌ አንድን ወንበር ብንወስድ
ሕዋሳት የሚያሳዩን በአንድ ጥቅል መልኩ
ነው ። ሆኖም በሐሳባችን የወንበሩን መልክ
በዓይነት በመከፋፈል ስፋት ፣ ቁመት ፣
ቦታ ፣ ቀለም ወዘተ...የሚሉ ጽንስ ሐሳቦችን
እናገኛለን ። ለስፋት ረቂቅ ትርጉም የሚሰ
ጠው የምናስበው የአንድ ወንበር ስፋት ሳይ
ሆን ሁሉን ወይም ማንኛውንም ወንበር
የሚመለከት በመሆኑ ነው ። ይህም ማለት
ስፋት ካለቁመት ፣ ካለቦታና ካለቀለም የሚ
ታይ ባይሆንም ሐሳብ ስፋት የሚለውን ገን
ጥሎ ብቻውን ለማሰብ እንደሚችል ነው ።
የዚህ አስተሳሰብ ዋና ፍሬ ነገር ከስተቶችን

በመልካቸውና በባሕርያቸው ማስቀመጣችን ሲሆን የምንደርስበት ግንዛቤ ረቂቅ ዕውቀት ተብሎ ይጠራል ።

ሆኖም ልናውቀው የምንፈልገው ተጨባጩን ስለሆነ በረቂቁ ሳንወሰን ወደ ተጨባጩ መመለስ ይኖርብናል ። ስለሆነም እነዚህ በባሕርይና በተመሳሳይነታቸው ያስቀመጥናቸው ረቂቅ ሐሳቦች በተጨባጩ መልክ በመመራት እንዴት እንደሚገናዘቡና እንደሚገናኙ ስናመቻች የተጨባጩን ውስጣዊ ምንነት ግንዛቤ እናገኛለን ። በረቂቆቹ መሃል የሚኖረው መዋቅር የተጨባጩ ውስጣዊ ፍሬ ነገር ወይንም ሕግ ሆኖ ይከሰታል ። ከተጨባጩ ወደ ረቂቁ ስንሄድ እንከፋፍላለን ፤ እናጠቃልላለን ፤ ከረቂቁ ወደ ተጨባጩ ስንወርድ እንዳጠቃለልን እናገኛለን ማለትም በሐሳባችን ውስጥ የተጨባጩን ምንነት በሕግ አንፃር እንረዳለን ።

ለምሳሌ በኅብረተሰብ ውስጥ በኑሮ ደረጃ የተለያዩ ደሃና ጌታ የሆኑ ግለሰቦችን እናያለን ። ግለሰቦቹን ወደ ጐን በመተው ተመሳሳይ የሆኑትን ባሕርያቸውን እናስቀምጣለን ። ከበርቴው ቀጥታ አያመርትም ፤ አምራች ደሀው ነው ። የማያመርተው በትርፍ ሲተዳደር በጉልበቱ የሚያመርተው ደግሞ በምንዳ እንደሚተዳደር እንረዳለን ። ከዚህ ላይ የሚያመርት ፣ የማያመርት ፣ ትርፍና ምንዳ የሚባሉ አጠቃላይ ጽንሰ ሐሳቦች እናገኛለን ። እነዚህን ሐሳቦች ሊያገናኝ የሚችለው ምንድነው? የማምረቻ መሣሪያዎች ባለቤት መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ መሆኑን እንገነዘባለን ። በዚህም የምርት ግንኙነት የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ አገኘን ማለት ነው ። ከዚህ ሐሳብ ወደ ተጨባጩ ስንወርድ የምርት ግንኙነት የሚያስከትለው የክፍፍል ልዩነት ወይም የብዝበዛ ሁኔታ እንዴት አንዱን ጌታ ሌላውን ደሃ እንዳደረገው እንረዳለን ። ይህ ዕውቀት ንድፈ ሐሳብ ያቀፈ ለመሆኑ የምናየው ባለው የማስረዳትና የማብራራት ችሎታ ነው ። ክስተቶችን መመልከት ብቻ ሳይሆን ለምንና እንዴት ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል ። አንድን ሰዓት ስንመለከት ቆጣሪዎቹ ሲንቀሳቀሱ እናያለን ። ለምንና እንዴት ብለን ስንጠይቅ መልሱን ለማግኘት ሰዓቱን ከፍተን ውስጥ ያሉትን ዕቃዎች ለያይተን እንደገና መግጠም እንዳለብን ሁሉ ተጨባጩን በመገነጣጠልና መልሶም በመግጠም ዕውቀት ስለነገሮች ፍሬ ነገር ወይም ውስጣዊ ባሕርይ ይረዳል ።

(ጭብጥን ፣ ጽንሰ ሐሳብን ፣ ዳሰሳዊ ዕውቀትን ይመለከቷል ።)

## ንድፈ ሐሳብ
### (*Theory*)

የእውነታን የተለያዩ ክፍሎች ሥርዓት ባለውና በተጠቃለለ ሁኔታ የሚገልጽ ዕውቀት ንድፈ ሐሳብ ይባላል ። ሥርዓቱ የሚገልጸው የንድፈ ሐሳብን ሥነ አመክንዮአዊ ባሕርይ ሲሆን የተለያዩ ነገሮችንና ክስተቶችን የሚያገናዝብ በመሆኑ ደግሞ የማጠቃለል ጠባይ አለው ። ለምሳሌ ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ንድፈ ሐሳብ ነው ስንል ነገሮችን ከጠቅላላ ሕጎቻቸው አንፃር የሚመለከትና የተፈጥሮን ፣ የኅብረተሰብንና የዕውቀትን አመጣጥና ምንነት የሚያጠና በመሆኑ ያጠቃልላል ማለታችን ሲሆን የሚመራበት ዲያሌክቲካዊ ሥነ አመክንዮ ደግሞ የሥርዓቱ መሠረት ነው ። ንድፈ ሐሳብ ከጽንሰ ሐሳብ የሚለየው የተለያዩ ነገሮችን የማገናዘብና የማጠቃለል ባሕርይ ስላለው ነው ። ጽንሰ ሐሳብ በተወሰኑ ነገሮች መካከል ያለውን የወል ጠባይ የሚገልጽ ሲሆን ንድፈ ሐሳብ ደግሞ የተለያዩ ጽንሰ ሐሳቦችን የሚያቅፍና የሚያዋቅር ነው ።

በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ ስለንድፈ ሐሳብ የተለያዩ አስተሳሰቦች ተሰንዝረዋል ።ነባራዊ ሐሳባውያን ንድፈ ሐሳብ የእውነታ አፈጣጠርና አቀራረፅ ቀዳሚና መሪ ሐሳብ ነው በማለት ከሐሳብ ብቻ እንደሚመነጭና የአድራጊነት ተልዕኮም እንዳለው ተናግረዋል ። በኅሊናዊ ሐሳባውያን አመለካከት የንድፈ ሐሳብ የማጠቃለል ችሎታ ከልምድ የመጣ ቢሆንም በረቂቅነቱ ከተጨባጩ የመራቅ አዝማሚያ ስላለው ከተግባር ጋር ብዙውን ጊዜ የማይዛመድ ነው የሚል ነው ። እንደ ነባራዊ ሐሳባውያን አስተሳሰብ ንድፈ ሐሳብ ፍጹም አድራጊ ሲሆን እንደ ኅሊናዊ ሐሳባውያን ኢተግባራዊ አዝማሚያ ያለው ነው ።

ይህ አለመስማማት የሚመነጨው ንድፈ ሐሳብን የእውነታ ነፀብራቅ አድርገው ሁለቱም ባለመመልከታቸው ነው ። ንድፈ

ሐሳብ ፍጹም አድራጊ ሊሆን የማይችልበት ዋናው ምክንያት ነገሮች ከሱ ቀድመው የነበሩ በመሆኑ ሲሆን ተግባራዊ ተልዕኮ የሚኖረውም በእነሱ ላይ ሰው ቁጥጥር እንዲኖረው ስለሚያደርግ ነው ። ይህ የዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት አቋም የሚመነጨው ንድፈ ሐሳብና ተግባር (የሰው ተፈጥሮንና ኅብረተሰብን የመቀየር ማኅበራዊና ታሪካዊ ሂደት) የማይነጣጠሉ መንፈሳዊና ቁሳዊ ገጽታዎች ናቸው ከሚለው አመለካከት ነው ። ንድፈ ሐሳብ በዘፈቀደ የሚጸነስ ሳይሆን ከሰዎች ተግባራዊ እንቅስቃሴ ጋር የተሳሰረ በመሆኑ በታሪካዊ ሁኔታ በምርት ኃይሎች ዕድገት ደረጃ ፣ በሰዎች ፍላጎትና በኅብረተሰቡ ማኅበራዊ ሥርዓት የሚወሰን ነው ። ንድፈ ሐሳብ በተግባር ግፊት የሚቀረፅ ብቻ ሳይሆን እውነትነቱም የሚለካውና የሚረጋገጠው በተግባር ነው ። ተግባር ያረጋገጠው ዕውቀት በመሆኑ ደግሞ ሰዎች በነገሮች ላይ አጠቃላይ የቁጥጥር ችሎታ እንዲኖራቸው ስለሚያደርግ ተግባርን ወደ ንቁና ብልህ ለዋጭ ኃይል ይለውጠዋል ።

(ተግባርን ፣ ዕውቀትን ፣ ግንዛቤን ይመለከቷል ።)

## ንጉሣዊ አገዛዝ

*(Monarchy)*

ይህ ስያሜ የሚመለከተው የትውልድ ሐረግ እየመዘዙና ዝርያቸው ከንጉሣዊ ቤተሰብ በመሆኑ ብቻ የሥርወ መንግሥት ባለቤት በመሆን የጥቂት ቤተሰብ ወገኖች የአንድን ሀገር ርዕሰ ብሔርነትና ርዕሰ መንግሥትነት የሚይዙበትን አገዛዝ ነው ። ንጉሣዊ አገዛዝ በባሪያ አሳዳሪውና በፊውዳሉ ሥርዓተ ማኅበሮች የጎላ ቢሆንም በአንዳንድ ካፒታሊስት ሀገሮችም ውስጥ በተለያዩ ገጽታዎችና ለየት ባለ ይዘት ይገኛል ።

በሁለቱ ቀደምት ሥርዓቶች ማለትም በባሪያ አሳዳሪውና በፊውዳሉ ውስጥ ንጉሣዊ አገዛዝ ፈላጭ ቆራጭነት ፣ ፍጹም አምባገነንነትና አስቃቂ ጭቆና የሰፈነበት ነው ። ነገር ግን ከካፒታሊዝም ዕድገትና ከዚሁ ጋር ከሚዳብሩት የቡርዧ ዲሞክራሲያዊ ባሕርያት መስፋፋት ጋር ንጉሣዊ አገዛዝ ለውጥ እያሳየ ማለትም ወደ ሕገ መንግሥታዊ ንጉሣዊ አገዛዝ እየተቀየረ መጥቷል ።

እስከ ሃያኛው ምዕት ዓመት መግቢያ ድረስ በርካታ ሀገሮች በንጉሣዊ አገዛዝ ሥር ነበሩ ። ነገር ግን ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ወዲህ የንጉሣዊ አገዛዝ ይዞታዎች እየመነመኑ መጥተዋል ። ለዚህም ዋናው ምክንያት የረዥምም ዘመን ሂደትና የሰፊ ይዞታ ባለቤት የነበሩት የሩስያ ፣ የኦስትሮ ሃንጋሪ ፣ የጀርመን ፣ የኦቶማንና የመሳሰሉት ንጉሣዊ አገዛዞች መገርሰስ ነው ።

ከዚያ ወዲህ በዓለም ላይ ጥቂት እጅግ ኋላቀርና ጨቋኝ የሆኑ ፍጹማዊ የንጉሣዊ አገዛዝ ሥርዓቶች በተወሰኑ ሀገሮች ቆይተዋል። ከነዚህም አንዱ ከሰለሞን ዘር ተገኘ በመባል ለዘመናት ተንሰራፍቶ የቆየውና እ. ኢ.ት. አ. በ1966 ሕዝባዊ አብዮት የተደመሰሰው የኢትዮጵያ ንጉሣዊ አገዛዝ ነበር ።

በዳበሩት የምዕራብ አውሮፓ ሀገሮች የቀሩት ንጉሣዊ ይዞታዎች ግን የፍጹማዊነትና የአምባገነንነት ሥልጣን የሌላቸው ፣ በአመዛኙም ለብሔራዊ አንድነት ፣ ለአርማነትና ለወግ ምልክትነት (ሲምቦል ኦፍ ትራዲሽን ኤንድ ዩኒቲ) በርዕሰ ብሔርነት የሚቀመጡ ሲሆኑ የመንግሥቱን አመራር የሚይዙት ግን በፓርላማዊ ዲሞክራሲ አሠራር መሠረት በምርጫ የሚሾሙ ጠቅላይ ሚኒስትሮች ናቸው ።

(ሥርወ መንግሥትን ፣ ሕገ መንግሥትን ፣ ሪፑብሊክን ይመለከቷል ።)

## ንግድ ሚዛን (የ—)

*(Balance af Trade)*

ባንድ በተወሰነ ወቅት ባብዛኛው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከአንድ ሀገር ወደ ውጭ በተላኩት ሸቀጦች ጠቅላላ ዋጋና ወደ አንድ ሀገር ከውጭ በገቡት ሸቀጦች ጠቅላላ ዋጋ መካከል ያለው ንጽጽር የንግድ ሚዛን ይባላል ። የዕቃዎች ንግድ ሚዛን በተወሰነ ወቅት ከአንድ ሀገር ወደ ውጭ በእጅ በእጅ ክፍያና በብድር የተሸጡበትን ፣ የሸቀጦች ዋጋ እንዲሁም ወደ አንድ ሀገር ከውጭ በእጅ በእጅ ክፍያና በብድር ተገዝተው የገቡትን ሸቀጦች ዋጋ ይመለከታል ። ስለዚህ የዕቃዎች የንግድ ሚዛን ሁለት መልኮች አሉት ። እነዚህም የወጪ ንግድና የገቢ ንግድ ናቸው ።

የእያንዳንዱ ሀገር የዕቃዎች ንግድ በጠቅላላ የዓለም አቀፍ የዕቃዎችን ንግድ ይፈጥራል ። የዓስም አቀፍ የዕቃዎች ንግድ መሠረት በሀገሮች መካከል ያለው የሥራ ክፍፍል ነው ።

የአንድ ሀገር የንግድ ሚዛን አቋም ሀገራቷ በዓስም አቀፍ ገበያ ያላትን የኢኮኖሚ አንድ ገጽታ ያመለክታል ። የሸቀጦች የገቢ ዋጋና የወጪ ዋጋ በመሠረቱ ሸቀጦችን ከወሰኖችና ከወደቦች የማድረሻ ፣ የማጓጓዣና የመድን ወጪዎችንና ለማምረት የወጣባቸውን ወጪዎች ይይዛል ። በተጨማሪም ሸቀጡ የወጪ ንግድ ታክስንና ሌሎች ተመሳሳይ የደንብ ክፍያ ወጪዎችን ያጠቃልላል ።

የካፒታሊስት ሀገሮች የንግድ ሚዛን ሁኔታዎች ግብታዊ የሆኑና የዋጋ ንረትና የገንዘብ ቀውስ በየወቅቱ የሚታይባቸው ናቸው ። የካፒታሊዝም ያልተመጣጠነ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ዕድገት በካፒታሊስት ኃይሎች መካከል ያለውን የገበያ ሽሚያና የእርስ በርስ ፉክክር ከማካረሩም በላይ በዓለም አቀፍ ደረጃም እንዲሁ የንግድ ሚዛን ሁኔታዎችን መመሰቀል ያስከትላል። ምናም እያንዳንዱ ካፒታሊስት ሀገር የራሱን የዕቃዎች ንግድ ሁኔታ የተሻለ ለማድረግ ልዩ ልዩ ዘዴዎችን ሥራ ላይ ያውላል ። ዘዴዎቹ ዋና ዋናዎቹ በገቢ ሸቀጦች ላይ ቀረጥ መጣል ፣ የገቢ ኮታ መወሰን ፣ ለሀገር ውስጥ አቅራቢዎች ማበረታቻ የቀረጥ ቅናሽ ማድረግ ፣ ለሀገር ውስጥ አቅራቢዎችና ወደ ውጭ ለሚልኩ ልዩ ልዩ ድጎማዎች መስጠትና አመች የብድር ደንብ መፍጠር ናቸው ።

በዳበሩ የካፒታሊስት ሀገሮችና የካፒታሊስቱ ዓለም ጥገኛ በሆኑ ኋላቀር ሀገሮች መካከል ያለው የዕቃዎች ንግድ ግንኙነት የተመሠረተው የዳበሩት የካፒታሊስት ሀገሮች ልዩ ልዩ የኢንዱስትሪ ውጤቶችን በማቅረብና ኋላቀር ሀገሮች ደግሞ ጥሬ ዕቃዎችንና ሌሎች የእርሻ ውጤቶችን በመላክ ላይ ነው ። ይህ ግንኙነት የዳበሩ ካፒታሊስት ሀገሮችን የበለጠ ሀብታም የሚያደርግና ኋላቀር ሀገሮችን በድህነት የሚያቆይ ነው ። ይህ ሁኔታ ኋላቀር ሀገሮችን የተሟላ የኢንዱስትሪ ልማት ለማካናወን አያስችላቸውም ። በአንፃሩ በሶሻሊስት ሀገሮች ኢኮኖሚው በማዕከላዊ ዕቅድ ስለሚመራ የወጪና የገቢ ንግድ የዚህ ዕቅድ አካል ሆኖ ይንቀሳቀሳል ።

(የገንዘብ ክፍያ ሚዛንን ይመለከቷል*።)

## ንግድ ትርፍ (የ—)

*(Commercial Profit)*

ነጋዴ ሸቀጦችን ከገዛበት ዋጋ በላይ አድርጎ በመሸጡ የሚገኝ ትርፍ ነው ። የንግድ ትርፍ በካፒታሊስት ኢኮኖሚ የሸቀጥ ምርት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚገኘው የጠቅላላ ተረፈ እሴት አንድ አካል ነው ። ጠቅላላው ተረፈ እሴት የሚፈጠረው ደግሞ በምርት ሥራ በተሰማሩ ወዝአደሮች ነው ። ከዚህም ጠቅላላ ተረፈ እሴት ውስጥ የተወሰነውን የሚወስደው በንግድ ሥራ የተሰማራው ካፒታሊስት ነው ። ይህ ካፒታሊስት የሚወስደው የጠቅላላ ተረፈ እሴት አካል የንግድ ትርፍ ይባላል ።

የንግድ ትርፍን አነሣሥ በደንብ ያልመረመሩ ሁሉ የንግድ ትርፍ ሸቀጦችን ከእሴታቸው በላይ በመሸጥ ብቻ የተገኘ ገቢ አድርገው ይወስዱታል ። ይህ ስህተት ነው ። በካፒታሊስት ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሸቀጥ ዝውውር መስከ ከጠቅላላው የሸቀጥ ሂደተ ምርት ጋር የተያያዘ ነው ። የሸቀጥ የዝውውር ሂደት የሸቀጥ ካፒታል ወደ ገንዘብ ካፒታል የሚለወጥበት ሂደት ነው ።

በኢኮኖሚ ውስጥ የተገኘው ተረፈ እሴት በኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶችና በንግድ ካፒታሊስቶች መካከል በአማካይ ትርፍ ሕግ መሠረት ሲከፋፈል የንግድ ትርፍ በመከሰት ለንግድ ካፒታሊስቶች ገቢ ይሆናል ። ሁኔታውን በመጠኑም ቢሆን ዘርዘር አድርገን ብንመለከት ጉዳዩ የበለጠ ግልጽ ሊሆን ይችላል ። የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶች ያስመረቷቸውን ሸቀጦች ለንግድ ካፒታሊስቶች ከማኅበራዊ የማምረቻ ዋጋ በታች ይሸጡላቸዋል ። የንግድ ካፒታሊስቶቹ ደግሞ ለተገልጋዮች ሸቀጦችን በማምረቻ ዋጋቸው ይሸጣሉ ። የሁለቱ የመሸጫ ዋጋ ልዩነት የንግድ ካፒታልን ትርፍ ያስገኛል ። የንግድ ትርፍ ባጠቃ

ላይ በኢኮኖሚው ውስጥ ካለው ማኅበራዊ ካፒታል አንፃር በአማካይ ትርፍ ስሌት መሠረት በመገናዘብ የሚገኝ ትርፍ ነው ። ይህንን ሁኔታ በስሌት ለማብራራት ይቻላል ። ለምሳሌ በካፒታሊስት ኢንዱስትሪ የምርት መስክ ብር 900 ካፒታል ወጪ ቢደረግና ይህም ለቋሚ ካፒታል ብር 720 ፣ ለሠራተኛ ብር 180 ወጪ ቢሆን በ100% የብዝበዛ መጠን የሚገኘው ተረፈ እሴት ብር 180 የሚያወጣ ይሆናል ። በዚህ ካፒታል ወጪ የአማካይ ትርፍ መጠኑ ከመቶ ፤

$$\frac{\text{ተረፈ እሴት}}{\text{ጠቅላላ ካፒታል ወጪ}} = \frac{180 \times 100}{900} = 20\%$$

ስለዚህ በዚህ ሁኔታ የመቶ ብር ካፒታል ወጪ ብር 20 ትርፍ ሊያስገኝ ይችል ነበር ማለት ነው ። ሆኖም የተመረተውን ሸቀጥ ለመሸጥና ወደ ገንዘብ ካፒታል ለመቀየር ተጨማሪ የካፒታል ወጪ ይጠይቃል ፤ ይህ ተጨማሪ የካፒታል ወጪ የንግድ ካፒታል ይባላል ። ለምሳሌ በዚህ ሁኔታ የንግድ ካፒታሉ ወጪ ብር 100 ቢሆን ለኢንዱስትሪ ምርት ሥራ ከወጣው ካፒታል ጋር ሲዳመር በጠቅላላ የወጣው ካፒታል ብር 1,000 ይሆናል ። ሆኖም በንግድ ካፒታል የሥራ መስክ ውስጥ የሚመረት ተጨማሪ ተረፈ እሴት ባለመኖሩ የተረፈ እሴት መጠን ያው በምርት ሥራ መስክ የተገኘው ብር 180 ነው ። ስለዚህ ሁኔታ የአማካይ ትርፍ መጠን ከመቶ ፣

$$\frac{180 \times 100}{1,000} = 18\% \text{ ይሆናል}$$

ስለዚህ የመቶ ብር የካፒታል ወጪ የሚያስገኘው አማካይ ትርፍ ብር 18 ይሆናል ። በዚህ ምሳሌያችን የንግድ ካፒታሊስቱ ያወጣው ካፒታል ብር 100 በመሆኑ የሚያገኘው ትርፍ ብር 18 ይሆናል ። ይህ የንግድ ካፒታሊስቱ ትርፍ የንግድ ትርፍ ይባላል ።

የንግድ ካፒታሊስቶች የፍጆታ ሸቀጦችን የመሸጫ ዋጋ በጣም ከፍ በማድረግና ከእሴታቸው በላይ አድርገው በመሸጥም ከፍተኛ ትርፍ ያገኛሉ ። በተለይም ከአነስተኛ አምራቾች ላይ ሸቀጦችን እጅግ ባነሰ ዋጋ በመግዛትና ሲሸጡ ደግሞ ዋጋውን እጅግ ከፍ በማድረግ የሚያገኙት ትርፍ ስፌ ነው ። በሞኖፖል ካፒታሊዝም ወቅት ደግሞ የንግድ ሞኖፖሊስቶች የሚሸጡትን ሸቀጥና የሚገዙትን ሸቀጥ በሞኖፖል ዋጋዎች በመሸጥ ከፍተኛ የሞኖፖል ትርፍ ይሰበስባሉ ።

በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የሶሻሊስት የንግድ ድርጅቶች በማዕከላዊው ዕቅድ ላይ በተመሠረተ አኳኋን የንግድ ሥራን ለማዳበርና በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩትን ሠራተኞች ክፍያ ለመሸፈን በሚያስችል ሚዛናዊ በሆነ የመሸጫ ዋጋ ሸቀጦቻቸውን በማቅረብ የተጠቃሚዎቹን ፍላጎት ያሟላሉ ።

(የንግድ ካፒታልን ፣ የኢንዱስትሪ ካፒታልን ይመለከቷል ።)

## ንግድ ካፒታል (የ—)
### (*Commercial Capital*)

በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ሸቀጦችን በግዥና በሽያጭ መልክ ለማንቀሳቀስ የሚውል ካፒታል ነው ። የንግድ ካፒታል የማኅበራዊ ካፒታል አንድ ክፍልና የሸቀጥ ካፒታልን ወደ ገንዘብ ለመለወጥ የሚያስችል ካፒታል ነው ። የንግድ ካፒታል እንቅስቃሴ በቀመር መልክ ሲቀርብ ገ—ሸ—ገ$^{1}$ ይሆናል። ይህ ሲዘረዘር ገ—ገንዘብ ፣ ሸ—ሸቀጥ ፣ ገ$^{1}$ —ትርፍ የታከለበት ገንዘብ ማለት ነው ። ይህ ቀመር የሚገልጸው የንግድ ካፒታሊስቱ በመጀመሪያ ሸቀጦችን ለመግዛት የተወሰነ ገንዘብ ማውጣቱን ፣ ከዚያም በኋላ የገዛውን ሸቀጥ ለተገልጋዮች በትርፍ መሸጡን ነው ።

የሸቀጥ ካፒታል ወደ ገንዘብ ካፒታል እንዲለወጥ መሠረት የሆነው የኢንዱስትሪ ካፒታል እንቅስቃሴ ነው ። የኢንዱስትሪ ካፒታል እንቅስቃሴ በተለያዩ የተግባር መስኮች ሲከናወን ማኅበራዊ ካፒታሉ የተወሰነው ካፒታል ያለማቋረጥ በሸቀጥ ዝውውር መስክ ሸቀጦችን ለሽያጭ በመግዛትና ሸቀጦቹንም መልሶ ለተገልጋዩ በመሸጥ ይንቀሳቀሳል ። ይህ የንግድ ካፒታል ነው ። ይህንንም ብቻ የሚያከናውኑ የካፒታሊስት ቡድኖች የንግድ ካፒታሊስቶች ናቸው ። በንግድ ካፒታል እንቅስቃሴ በቀጥታ ተረፈ እሴት አይፈጠርም ። ምክንያቱም እሴት የሚፈጠረው በምርታዊ ሥራ መስክ ብቻ ስለሆነ ነው ። ይሁንና

የንግድ ካፒታሊስቶች በልዩ ልዩ የሽያጭ ስልቶች በመጠቀም ፣ የሸቀጥ ካፒታል ወደ ገንዘብ ካፒታል የሚለወጥበትን ጊዜ በማፋጠን የትርፍ መጣኔ እንዲያድግና የተረፈ እሴት ዕድገትም እንዲኖር ያግዛሉ ። ይህም በአጠቃላይ ለካፒታል ክምችትና መጣከል አመች ሁኔታን ይፈጥራል ።

በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ባለው የአመራረት ሥርዓት አልበኝነት ምክንያት በምርትና በፍጆታ መካከል ቅራኔ ይፈጠራል ። በዚህ ሁኔታም የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶች ያመረቱትን ለንግድ ካፒታሊስቶች በማቅረብ የተመረተው ለተገልጋዮች ተሸጦ ሳያልቅ እንደገና አዲስ ያመርታሉ ። የንግድ ካፒታሊስቶች ሸቀጦችን በዱቤና በብድር ለተገልጋዮች በመሸጥ የሸቀጦችን ያለመሸጥ ችግር ሊቆጣጠሩ ይሞክራሉ ። ይህ ለተወሰነ አጭር ጊዜ ለችግሩ መፍትሔ ቢመስልም ችግሩን ከመደበቅ በቀር ዘላቂነት የለውም ። የንግድ ካፒታሊስቶች በዱቤና በብድር ለተገልጋዮች ሸቀጦችን በመሸጥ ሀሰተኛ ፍላጎት በገበያው ላይ ይፈጥራሉ ። በሞኖፖል ካፒታሊዝም ደረጃ የንግድ ካፒታል ሞኖፖሎች ይከሰታሉ ። እነዚህም ሰፊ የገበያ ሸቀጦችን በቁጥጥራቸው ሥር በማድረግ የተለያዩ የንግድ ካፒታል የገበያ ማቅረቢያ መዋቅሮችን ይፈጥራሉ ። በሚሸጡዋቸው ሸቀጦች ላይም የመሸጫ ዋጋዎችን በሞኖፖል ዋጋ በማቅረብ ከፍተኛ የሞኖፖል ትርፍ በቀላሉ ያገኛሉ ። በዚህ ሁኔታም በንግድ ሞኖፖል ካፒታሊስቶችና በኢንዱስትሪ ሞኖፖል ካፒታሊስቶች መካከል መቀራረብና መተሳሰር ይፈጠራል ።

(የኢንዱስትሪ ካፒታልን ይመለከቷል።)

## ንጽረተ ዓለም
## (*World Outlook*)

ሰዎች ስለሚያከብባቸው ዓለም ያላቸው የአመለካከት ሥርዓት ፣ አስተያየትና ጽንሰ ሐሳብ ንጽረተ ዓለም ይባላል ።

ንጽረተ ዓለም ሰፋ ባለ ትርጉሙ ሲታይ ሰው ስለሚያከብበው ዓለም ያለውን የአመለካከቶች ድምር ማለትም ፍልስፍናዊ፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ ፣ ሥነ ውበታዊ፣ ሳይንሳዊ ወዘተ... አመለካከቶችን ይይዛል ፤ ሆኖም ጠበብ ባለ አገባቡ ሲታይ ግን ንጽረተ ዓለም በፍልስፍና አመለካከቶች ይወሰናል ። ስለዚህም የንጽረተ ዓለም መሠረታዊና ዋነኛው ጥያቄ የፍልስፍና መሠረታዊ ጥያቄ ይሆናል ። በዚህም ጥያቄ መፍትሔ ላይ በመመሥረት ፍልስፍና በሁለት ዋነኛ ንጽረተ ዓለሞች ማለትም በቁስ አካላዊና በሐሳባዊ ንጽረተ ዓለሞች ይከፈላል ። ይኸውም ነገሮችንና ክስተቶችን ቀዳማይ ፣ ሐሳብን ደኃራይ አድርጐ የሚነሣው ንጽረተ ዓለም ቁስአካላዊ ንጽረተ ዓለም ሲሆን ሐሳብን ቀዳማይ አድርጎ የሚነሣው ንጽረተ ዓለም ደግሞ ሐሳባዊ ንጽረተ ዓለም ነው ።

በአጠቃላይ ንጽረተ ዓለም የሰዎችን የዕውቀት ዘርፎች ሁሉ የሚያጠቃልል በመሆኑ እጅግ ሰፊ ጽንሰ ሐሳብ ነው ። ለምሳሌ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ንጽረተ ዓለም ፍልስፍናን ፣ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚንና ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን አጠቃሎ የያዘ ሰፊ ጽንሰ ሐሳብ ነው ። ሐሳባዊ ንጽረተ ዓለም የዚያኑ ያህል ሰፋት ያለው ነው። ንጽረተ ዓለም አጠቃላይ አመለካከት ቢሆንም የማኅበራዊ ኑባሬ ነፀብራቅ በመሆኑ ነው በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ ዞሮ ዞሮ ከቁሳዊ ወይንም ከሐሳባዊ ጐራ መውደቁ የማይቀረው ።

ንጽረተ ዓለም ሳይንሳዊ ወይንም ኢሳይንሳዊ ሊሆን ይችላል ። ኢሳይንሳዊ ንጽረተ ዓለም በውስጡ ያቀፋቸው አመለካከቶችና ሐሳቦች የሚመሠረቱት ነገሮችንና ክስተቶችን ከማጥናትና ከመመርመር በመነሣት ሳይሆን በጭፍን ቀኖናዊ እምነት ወይም ከተፈጥሮ ውጭና በላይ በሆነ ኃይል እውነታን ለማስረዳት በሚደረግ ሙከራ ላይ ነው ። ሳይንሳዊ ንጽረተ ዓለም ግን የሚመሠረተው ነገሮችንና ክስተቶችን በመመርመርና በማጥናት በመሆኑ ተፈጥሮንም የሚያስረዳው ከመለኮታዊ ኃይል ጋር ሳያያይዝ ነው ።

ንጽረተ ዓለም ሰዎች ስለሚያከብባቸው እውነታ ያላቸውን አስተሳሰብ የሚገልጽና ለተግባር መመሪያ የሚያገለግል በመሆኑ ተግባራዊ ጠቀሜታ አለው ። ንጽረተ ዓለም የማኅበራዊ ኑባሬ ነፀብራቅ በመሆኑ በአንድ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት የሰው ልጅ ዕውቀት በደረሰበት ደረጃና ባለው ማኅበራዊ ሥርዓት ላይ ይመሠረታል ። በየሥርዓት

ማኅበሩም ውስጥ የገኘው መደብ ንጽረተ ዓለም የበላይነቱን ስፍራ ይዞ ይገኛል ። ንጽረተ ዓለም በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የመደብ ጠባይ አለው ። ኢሳይንሳዊ ንጽረተ ዓለም የአድኃሪ መደቦችን ጥቅም የሚጠብቅና ሠራተኞች ለአርነታቸው የሚያደርጉትን ትግል አቅጣጫ በማሳት ማኅበራዊ ዕድገትን ለማገድ የሚጥር ነው ። በአንፃሩም ሳይንሳዊ ንጽረተ ዓለም የተራማጅ ኃይሎችን ጥቅም የሚገልጽና አጠቃላይ ማኅበራዊ እርምጃን ለማፋጠን የሚያግዝ ነው ።

ሳይንሳዊ ንጽረተ ዓለም ማርክሳዊ ሌኒናዊ ንጽረተ ዓለም ነው። ይህም ንጽረተ ዓለም ከማኅበራዊ ዕድገት ነባራዊ ሕግጋት ጋር የሚገጣጠምና የወዝአደሩንና የተቀረውን ሠርቶ አደር ሕዝብ ጥቅም የሚገልጽ ነው ።

(ርዕዮተዓለምን ፡ ፍልስፍናን ፡ መደባዊ ንጽረትን ይመለከቷል ።)

# አ

## አመክንዮ
*(Reason)*

አመክነየ ምክንያት ሰጠ ፣ ምክንያት አቀረበ ከሚለው የግዕዝ ቃል የመጣ ነው ።

በፍልስፍና በተለይም በጥንታዊ የግሪክ ፍልስፍና ውስጥ የነበረው አመለካከት ሰውን ከእንስሳት የሚለየው የማሰብ ችሎታው ማለትም ክፉና ደጉን፣እውነቱንና ስህተቱን ለይቶ ለማወቅና በዚህም ዕውቀት በመመራት ተግባሩን ለጥሩና ለጠቃሚ ነገር የማዋል ችሎታው የሚመነጨው ከስሜት ግፊት ሳይሆን ከአመክንዮ ነው የሚል ነበር ።

የሰው ልጅ ዕውቀትና ምርምር እያደገና እየሰፋ በሄደ ቁጥር በተለይም ሐሳባዊ ፍልስፍና እየተጠናከረ ሲመጣ አመክንዮ እውነቱንና ደጉን የመለያ ችሎታ ብቻ መሆኑ ቀርቶ ራሱን እንደቻለ ፣ ነባራዊ ህልውና እንዳለው ረቂቅ ነገር ሆኖ ከመታየት አልፎ ከሰው ውጭና የበላይነት ያለው በመሆኑ ከራሱ የሚፈልቁ የሐሳብ ሕግጋትን እንዳቀፈና ነባራዊነት እንዳለው የግንዛቤ ኃይል ተደርጎ ተቆጠረ ። ይህም ሐሳባዊ ፍልስፍና ዞሮ ዞሮ "ከአንድ ኃይል" ወይም ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚገናኝ ያሳየናል ። አንድ ዕቃ የራሱ የሆኑ ባሕርያት ማለትም ቁመት ፣ መልክ ፣ ክብደት ፣ ስፋት እንዳለው ሁሉ አመክንዮም ከራሱ የሚፈልቁና ምንነቱን የሚገልጹ ሐሳቦች ይኖሩታል ። እነዚህም ሐሳቦች መመሪያዎች በመሆናቸው በጊዜና በቦታ የማይለወጡ ፣ ሁለንታዊና ዘለዓለማዊ ናቸው ይላል ። ለምሳሌ ለሁሉም ነገር ምክንያት ያለው መሆኑን ስለምናውቅ ነው ለማንኛውም ነገር ምክንያት የምንፈልግለት ።

በሐሳባውያን አመለካከት ተፈጥሮን የሚገዙ ሕጎችን በማስተዋል ፣ በልምድና በተግባር የምናገኛቸው ሳይሆን አብረውን የተወለዱ መንፈሳዊ ምክንያት ያላቸው ናቸው ። ይህም የሚያስረዳን የሰው ልጅ የማሰብ ችሎታው ለሕይወት አስፈላጊ ፣ በተግባር ላይ የተመሠረተና በዕድገት የተገኘ መሆኑን ሐሳባውያን እንደማይቀበሉት ነው ። ዕውቀት በሰው ልጅ ጥረት የሚገኝ መሆኑ ቀርቶ ከአንድ ኃይል የሚገኝ ስጦታ ተደርጎ በመወሰዱ ሰው በራሱ ጥረትና ተግባር ያፈራውን የዕውቀት ባለቤትነት ይክዳል ። ነገር ግን በተግባር እንደሚታየው ሐቁ ዕውቀት ከሰው ተግባር የሚገኝና ከተግባርም ጋር የሚያድግ መሆኑነው።

(ተግባርን ፣ ዕውቀትን ፣ ምክኑያዊነትን ይመለከቷል ።)

## አማተርነት
*(Amateurishness)*

አንድን ሥራ በትርፍ ጊዜ ማከናወንን የሚያመለክት ሲሆን እንዲሁም ሥራውን በሙሉ ልብ ካለመያዝ የተነሣ በቂ ልምድና ችሎታ አለማግኘትን ይጠቁማል ። በአብዮታዊ ተግባርም አማተርነት በጠባብ አመለካከት ውስጥ መገኘትን ፣ በዚህም ላይ በተመረኮዘ የአሠራር ዘዴም ጠንካራ አብዮታዊ ድርጅት ለመመሥረት የማይቻል መሆኑን ባለመገንዘብ ይህንኑ ውሱን አስተሳሰብ ወደ ንድፈ ሐሳብ ደረጃ አሳድጎ የግል ፍላጐት ተገዥ መሆንን ያጠቃልላል ።

(አብዮተኛን ይመለከቷል ።)

## አማኒነት
*(Theism)*

እግዚአብሔር ሰብአዊ ባሕርይ ያለውና በአመክንዮና በፈቃድ ችሎታው የዓለምን ቁሳዊና መንፈሳዊ ኑሮ ሂደት የሚገዛ ነው የሚል ሃይማኖታዊ ፍልስፍና ነው ። በአማኒነት አስተሳሰብ በዓለም ውስጥ የሚከሰተው ማንኛውም ነገር የሚመነጨው በአምላክ ፈቃድ ነው ፤ የተፈጥሮ ሕግ ብለን የምንጠራውም ሁሉ የሚገልጸው የአምላክን ፈቃድ ነው ። ይህ ፈቃድ መለኮታዊ በመሆኑ ባለሙሉ ሥልጣን ፣ ቋሚና በጐም ነው ። በፈቃዱም በጐነት ምክንያት በዓለም ውስጥ ያለ ሰናይ ኃይል በእኩያን ላይ በመጨረሻ አሸናፊነትን እንደሚቀዳጅ ሙሉ ተስፋ ያሳድርብናል ይላል ።

አማኒነት የሥነ መለኮትና የእምነታዊነት መሠረታዊ አስተሳሰብ ነው ። ዓለም የተፈጠ

ረውና የሚገዛው በዲበተፈጥሮአዊ ፈቃድ ነው የሚለው አመለካከቱ ከሳይንሳዊ አመለካከት ጋር የሚፃረር ነው ። በመሆኑም አማኒነት ለሳይንስ ዕድገትና በኅብረተሰቡ ውስጥ ለሳይንሳዊ አመለካከቶች መስራጨት ዕንቅፋት የሚሆን ነው ። ሁሉ ነገር የሚወሰነው በአምላክ ነው የሚለው አስተሳሰቡ ሰዎች በራሳቸው በመተማመን ታግለው ነገሮችን እንዳይለውጡና ያለውንም ሁኔታ እንዲቀበሉ የሚያደርግ በመሆኑ ለመደብ አገዛዝ ጠቃሚ ነው ።

(ኢአማኒነትን ፣ ሁልአምላክነትን ይመለከቷል ።)

## አማዕከሎሰብነት

*(Anthropocentrism)*

ሰው የዓለም ማዕከል ፣ የተፈጥሮ የመጨረሻ ዓላማና ግብ ነው የሚል ሃይማኖታዊና ሐሳባዊ አስተሳሰብ ነው ። አማዕከሎሰብነት ከሥነ ግብ ጋር የቅርብ ግንኙነት አለው ። ኮፐርኒከስ በሳይንሳዊ ጥናት መሬት እንደ ሌሎቹ ፕላኔቶች ፀሐይን የምትዞር መሆኗን ማስረዳቱና ዳርዊንም ሰው ከእንስሳ የመጣ መሆኑን ማስገንዘቡ ይህን አስተሳሰብ መሠረተ ቢስ አድርጐታል ።

(ዳርዊኒዝምን ፣ ሥነ ግብን ይመለከቷል ።)

## አማካይ ትርፍ

*(Average Profit)*

በተለያዩ የኢንዱስትሪ መስኮች በተሰለፉ ቡርዧዚዎች መካከል የሚደረግ ውድድር የተለያዩ ካፒታሊስቶችን የትርፍ መጣኔ ወደ አንድ አማካይ መጣኔ ያስተካክለዋል ። በዚህ አማካይ መጣኔ ስሌት መሠረት የሚገኘው ጠቅላላ ትርፍ አማካይ ትርፍ ይባላል ።

በተለያዩ የኢንዱስትሪ መስኮች ውስጥ ያለው ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር የመለያየቱን ያህል ሌሎች ሁኔታዎች እንዳሉ ሆነው በተመሳሳይ የብዝበዛ ደረጃ በየመስኩ የሚናረው የትርፍ መጣኔ መበላለጡ የግድ ነው ። በካፒታሊዝም ውስጥ የትኛውም ቡርዧዚ የሚሰማራበትን የምርት መስክ የሚወስነው አገኛለሁ ብሎ በሚገምተው የትርፍ ደረጃ ሁኔታ ብቻ በመሆኑ የሁሉም ቡርዧዚዎች ዓላማ ዝቅተኛ የትርፍ መጣኔ ካለበት የኢንዱስትሪ መስክ ወጥቶ ከፍተኛ የትርፍ መጣኔ ወዳለበት መስክ መሰማራት ነው ። በዚሁ ሳቢያ ግብታዊ በሆነ መንገድ ካፒታል ካንዱ መስክ ወደ ሌላው መስክ የሚዘዋወርበትና በዚሁ ዝውውር የተነሣ በረጅም ጊዜ ሲታይ ቡርዧዚዎች በየመስኩ ያለውን የትርፍ መጣኔ መለያየት በማስወገድ እኩል በሆነ የካፒታል ወጪ ላይ እኩል የሆነ ትርፍ የሚያገኙበት ሁኔታ ይፈጠራል ። ይህም ተመጣጣኝ ትርፍ ከላይ እንደተጠቀሰው አማካይ ትርፍ ይባላል ።

## አምላክኛነት

*(Deism)*

ሰብአዊ ስሜት የሌለው ፣ በሥነ አመክንዮ እውነታነት ገጽታው ብቻ የሚኖር ፣ እግዚአብሔር የማናቸውም ነገርና ክስተት መንሥኤና ምንጭ ነው የሚል እምነት ነው ። ሰዓት አንድ ጊዜ ከተሞላ በኋላ በራሱ እንደሚንቀሳቀስ ሁሉ ዓለምም አንዴ ከተፈጠረ በኋላ በራሱ ሕግጋት ይንቀሳቀሳል ፤ እግዚአብሔርም በዚህ ውስጥ ጣልቃ አይገባም የሚል ለመጀመሪያ ጊዜ በእንግሊዝ የተከሰተ አስተሳሰብ ነው ። ይህ አስተሳሰብ ሃይማኖት ገንና በነበረበት በፊውዳሊዝም ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ ቁስአካላውያን እምነትን ለመታገል ጥረት በሚያደርጉበት ወቅት የኢአማኒነታቸው ሽፋን በመሆን አገልግሏል ። እንደ ቮልቴር ፣ እንደ ኒውተን ፣ እንደ ሎክ ፣ እንደ ሩሶ ወዘተ... ያሉት ተራማጅ ቡርዧ ፈላስፎች በአምላክኛነት ካባ ሃይማኖታዊ አስተሳሰቦችንና ቤተክርስቲያንን ለመታገል ችለዋል ። ይሁንና በዛሬው ዘመን አምላክኛነት ኢአማኒነትን ለመቃወም መጠለያ በመሆን ያገለግላል ።

## አምልኮተ ሸቀጥ

*(Fetishism of Commodities)*

የግል አምራቾች ለሽያጭ ወይም ለልውውጥ በሚያመርቱበት ጊዜ በአምራቾች መካከል ያለው ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ግንኙነት በሰዎች መካከል ሳይሆን በምርት ውጤቶቻቸው መካከል ያለ ግንኙነት ሆኖ

ይቀርባል ። ከዚህም የተነሣ ሸቀጦች በሰው አእምሮ ውስጥ የተመላኪነት ባሕርይ ይይዛሉ ። ይህን ሁኔታ የሚያንፀባርቀው ግንኙነት እምልኮተ ሸቀጥ ይባላል ።

በአምራቾች መካከል የሚኖረው የተሳሰረ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት የሚገለጸው የሸቀጦች ልውውጥ በሚከናወንበት ገበያ ውስጥ ነው።በሸቀጥ አምራቾች የተሠራው ዕቃ ገበያ ውስጥ ከገባ በኋላ ከአምራቾች ቁጥጥር ውጭ ይሆናል ። በካፒታሊስት ስልተ ምርት የሸቀጦች ልውውጥ በዕቅድ ላይ ተመሥርቶ የሚከናወን ሳይሆን በዘፈቀደ ወይም በግብታዊነት የሚፈጸም በመሆኑ የሸቀጥ አምራቾች ህልውናም እንዲሁ በሸቀጦች የገበያ ሁኔታ ላይ የሚመሠረት ይሆናል ። በመሆኑም የሸቀጥ አምራቾች ሕይወት ሙሉ በሙሉ በሸቀጦች ዋጋ ውጣ ውረድና በገበያ ሁኔታ ላይ የሚመሠረትና በዚህም የሚመራ ነው ። ከዚህም የተነሣ በካፒታሊስት ስልተ ምርት ውስጥ ሸቀጦች በተፈጥሮ የተለየ ኃይል ያላቸው ይመስላል ።

በካፒታሊስት ሥርዓት አምራቾች ሊያገኙዋቸው ለማይችሏቸው ሸቀጦች ማጎብደዳቸው ፣ የአምራቾች ህልውና በገበያ ኃይል ላይ መቆሙንና ሸቀጥ በሰዎች ላይ ያለውን "መለኮታዊ" ተፅዕኖ የሚያመለክት ነው። ሸቀጦች ሰዎችን የመቆጣጠራቸው ሁኔታ ወይም ይህ በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ያለ የሸቀጦች ባሕርይ ለገበያ ብቻ ሲባል ከሚመረቱ ሸቀጦች የሚመነጭ ውስጣዊ ባሕርያቸው ነው ።

አምራቾች በገበያ ላይ ያላቸው ጥገኝነት እያደገ በሚሄድበት በካፒታሊስት ስልተ ምርት ውስጥ ይኸው እምልኮተ ሸቀጥ እየተስፋፋ የሚሄድ ሲሆን የግል ሀብት በሚጠፋበትና የአምራቾች ህልውና በገበያ ላይ በማይመሠረትበት በሶሻሊዝም ግን እምልኮተ ሸቀጥ ይጠፋል ።

## እምሳል
(*Ideal*)

የሰው ንቃተ ኅሊና ከቁስአካል ጋር ያለውን ሥነ ዕውቀታዊ ልዩነት የሚገልጽ ጽንሰ ሐሳብ ነው ። ንቃተ ኅሊና (አእምሮ) ቁስአካላዊ ዓለምን በምስል ፣ በሐሳብና በጽንሰ ሐሳብ የሚያንፀባርቅ በመሆኑ እምሳል ነው ። እምሳል የሚባለው ይህ የማንፀባረቁ ሁኔታ ነው ። እውነታን ለማንፀባረቅ ቁሳዊ መንሥኤዎችና ዘዴዎች (እንጐል ፣ ሕዋሳት ፣ ቋንቋ ፣ ተግባር ወዘተ...) አስፈላጊ ቢሆኑም ነፀብራቁ (ማለትም ሐሳብ ፣ ስሜት ፣ ሕውስት) ቁሳዊ አይደለም ። በአእምሮ ውስጥ የሚገኙት ነገሮች እራሳቸው ሳይሆኑ የነሱ እምሳሎች ናቸው ። ለምሳሌ የወንበርን ሐሳብ ብንወስድ አእምሮ ውስጥ ያለው ወንበሩ ሳይሆን የሱ እምሳል ማለትም ሐሳቡ ነው ።

እሳቦት እምሳል በመሆኑ ነው የነገሮችን ምንነት በማንፀባረቅ ነባራዊ ሕጎችን ለማጥናትና አዳዲስ ዕቅዶችንም ለማመንጨት የሚችለው ። ሆኖም አእምሮ እውነታን በትክክል ባለማንፀባረቁ ምትሀታዊ የሆኑ ሐሳቦችንና አመለካከቶችን ሊያፈልቅ ይችላል ። ይህን ሁኔታ በማስወገድ ሳይንሳዊ የሆነ ዕውቀት ሊኖረን የሚችለው እሳቦትን በተግባር በየጊዜው ስንፈትን ነው ።

እምሳል ከሥነ ዕውቀታዊ ፍቺው ጋር የተያያዙ ማኅበራዊ፣ ሥነ ምግባራዊና ሥነ ውበታዊ ፍቾችም አሉት ። በዚህም ጊዜ ጽንሰ ሐሳቡ የሚገልጸው የነገሮችን ፍጹማዊና የመጨረሻ ሞዴል ወይም ዓይነት በሐሳብ ውስጥ መቀረፅን ነው ። ለምሳሌ ፍጹማዊ የሆነ የኅብረተሰብ ሥርዓት በአእምሮአችን ውስጥ ማሰብ እምሳልን ማቀድ ነው ። ምክንያቱም ሐሳቡ የሚገልጸው አንድ መደብ ፍጹም በሆነ መንገድ ይስማማኛል ብሎ የሚመኘውን ሥርዓት ነው ። ሐሳባዊነት እውንንና እምሳልን ተፃራሪ ነገሮች አድርጎ በማቅረብ እምሳል ከምድራዊና ከቁሳዊ ኑሮ ውጭና የበላይ እንደሆነ ለማሳመን ይጥራል ። ይህ ምድራዊ ኑሮን ለማንቋሸሽ የሚረዳ ከመሆኑም በላይ እምሳልን አርቆ በማስቀመጥ ሰዎች በእምነት እንዲታለሉና እንዲጽናኑ የሚጠቅም ነው ።

ማኅበራዊ እምሳል ከነባራዊው ሁኔታና ከዕድገቱ ሕግጋት አቅጣጫ ከተቀረፀ እውን ወይም ተግባራዊ ሊሆን ይችላል ። ተምኔታዊ የሚሆነው ምድራዊው ዓለም የተረገመ በመሆኑ ሳይሆን ትክክለኛ ቁሳዊ መሠረቱን ሳያገኝ ሲቀር ነው ። ኮሚኒዝም ከቁሳዊ ዓለም ነባራዊ ሕጎች አንፃር የተቀየሰ በመሆኑ እውን የሚሆን የወዝአደሩ መደብ እምሳል ነው ።

እንዲሁም ሥነ ምግባራዊ አምሳል የሚገልጸው ግብረገባዊ ፍጹማዊነትን ነው ። አምሳሉ የሚያንፀባርቀው ግዴታን በትክክል ለመፈጸምና ስናይነትን እውን ለማድረግ መከናወን ያለባቸውን ምርጥ ነጥቦች ነው ። በተመሳሳይ ሁኔታ ሥነ ውበታዊ አምሳል የሚገልጸው የአንድን መደብ ወይም የኅብረተሰቡን የውበት ከፍተኛ አመለካከት ነው ።

(ነፀብራቅን ይመለከቷል ።)

## አምስተኛ ረድፍ

*(The Fifth Column)*

የውስጥ ጠላቶችና አስመሳዮች የስፌውን ሕዝብ ካባ ደርበው በአብዮታዊ ሐረጐች ሽፋንነት አብዮትንና ሕዝቡን ለመውጋት የሚሰለፉበት ፀረ አብዮት የምሥጢር ድርጅት ነው ።

አምስተኛ ረድፍ የሚለው ቃል ከ1936 እስከ 1939 በተካሄደው የስፓኝ የርስበርስ ጦርነት ጊዜ ማድሪድ ስትከበብ ፣ ፋሺስቱ ጄኔራል ሞላ በውስጥ አርበኝነት ስለሚያገለግሉት ደጋፊዎቹ ሲናገር “እኛ ማድሪድን በአራት ረድፍ እያጠቃናት ነው ፤ በከተማይቱ መሀል ደግሞ አምስተኛ ረድፍ አለን ” በማለት ከገለጸው የተወሰደ ነው ። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ አምስተኛ ረድፈኞች የፋሺስቱ የጦር ቃል ኪዳን አባል ባልሆኑ ሀገሮች ውስጥ የጀርመን ፣ የኢጣሊያና የጃፓን ወኪሎች በመሆን ሠርተዋል ። በስፓኝ በአንድሬኒን የሚመራው “የማርክሳዊ አንድነት የሠራተኞች ፓርቲ” የተሰኘው የትሮትስካይቶች ድርጅትም የአድኅሮት ኃይላት ማዕከል በመሆን አገልግሏል ።

አምስተኛ ረድፈኞች ከሚፈጽሟቸው ደባዎች ጥቂቶቹ ሕዝቡን በልዩ ልዩ ምክንያት በመከፋፈል ማበጣበጥ ፣ የግድያ ተግባር መፈጸም ፣ ንብረት ማውደም ፣ ለጠላት ስለላ ማካሄድ ፣ አድኅሮትን መደገፍና ጠላት መግቢያ በር እንዲያገኝ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ናቸው ።

## አምነስቲ ኢንተርናሽናል

*(Amnesty International)*

በ1961 በእንግሊዝ ውስጥ በለንደን ከተማ የተቋቋመ ድርጅት ነው ። ከድርጅቱ ሰነዶች ለመረዳት እንደሚቻለው ዓላማው አድርጎ የተነሣው በየሀገሩ በተለይ በፖለቲካና በሃይማኖት ልዩነቶች ሳቢያ በመንግሥታት ቁጥጥር ሥር የዋሉትን ሰዎች መብት በማስከበር ረገድ እነዚህ ሰዎች እንዲለቀቁ ወይም ደኅንነታቸው እንዲጠበቅ ማድረግ ፣ ሁኔታውን ለዓለም ሕዝብ በማሳወቅ ሕዝቦች ወይም መንግሥታት ግፊት እንዲያደርጉ መቀስቀስ ፣ ኢሰብአዊ ድርጊቶች እንዳይፈጸምባቸውና መብታቸው ተጠብቆና ጉዳያቸው ታይቶ በአፋጣኝ ለፍርድ ቀርበው ውሳኔ እንዲያገኙ ማድረግ የሚሉ ይገኙበታል ።

አምነስቲ ኢንተርናሽናል ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ በተለያየ መንገድ የሚረዱትና የሚተባበሩት መቶ ሺህ አባላት ሲኖሩት በብዙ ሀገሮች ውስጥ ቅርንጫፍ አካሎችና ሰባት መቶ የሚደርሱ የአካባቢ ቡድኖች አሉት ። በጥናት ክፍሉ አማካይነት በየሀገሩ የሚገኙትን የፖለቲካ እስረኞች ምዝገባና ግምገማ ያካሂዳል ። በተጨማሪም ድርጅቱ በየወሩ የሚታተም “ኒውስ ሌተር” የተባለ ጋዜጣና በየዓመቱ በተለያዩ ሀገሮች ስላሉት የፖለቲካ እስረኞች ሁኔታ የሚያስረዳ “አኑዋል ሪፖርት” የተሰኘውን ጽሑፍ ያወጣል ። በአሁኑ ጊዜ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ዋና ጽሕፈት ቤት በለንደን ይገኛል ። አምነስቲ ኢንተርናሽናል ምንም እንኳ ከማንኛውም ተፅዕኖ ውጭ ለሰብአዊ መብት እታገላለሁ ቢልም በተግባር ሲታይ ግን የቡርዧዚዎችን አመለካከትና ዓላማ የሚያራምድ ፣ የአብዮታዊና የተራማጅ መንግሥታትን ስም በማጉደፍ የቡርዧ ዲሞክራሲ አፈቀላጤነቱን ያረጋገጠ ድርጅት መሆኑን ከዕለት ተዕለት ተግባሮቹ ለመገንዘብ ይቻላል ።

## አሣቂ

*(Comic)*

ማኅበራዊ ክስተት፣የሰው ተግባር ከንዋኔ፣ ግብረገባዊና ባህላዊ አመለካከቶች ከነባራዊ የዕድገት ደረጃ ጋር አግባብ ማጣታቸውን በአንፃሩም ተራማጅ የሆኑ ማኅበራዊ አሴተሳሰቦችን የሚገልጽ በታሪክ የሚወሰን የሥነ ውበት ፈርጅ ነው ። አሣቂ ብዙ ዓይነት መልኮች አሉት ። በአሮጌውና በአዲሱ ፣ በቅርፅና በይዘት ፣ በግብና በአፈጻጸም ፣ በተግ

ባርና በሁኔታ ፣ በሰው እውን ጠባይና ሰው ሰለራሱ ባለው አስተሳሰብ መካከል ያለውን አለመጣጣም ሊገልጽ ይችላል ።

አሣቂ ጠባዮችና ሁኔታዎች ሣቅን ፣ ፌዝንና ተቃውሞን ይቀሰቅሳሉ ። አሣቂ የሚመነጨው ከተቃራኒ ማኅበራዊ ኑሮ በመሆኑ አመጣጡ ፣ ባሕርዩና ተግባሩ ማኅበራዊነቱን ያረጋግጣሉ ። ፌዝ ፣ ቀልድ ወዘተ ... የኂስና የእርምት ፍች መያዛቸው የሚገልጸው የሣቅን ማኅበራዊ ሚና ነው ።

ማርክስ ሣቅ ጠፊና ኋላቀር የሆኑ ነገሮችን ለመዋጋት የሚጠቅም መሣሪያ መሆኑን ተናግሯል ። በኮሚኒስት ኅብረተሰብ ግንባታ ውስጥም ሣቅና ፌዝ የተለያዩ ቅሪቶችን ፣ አድርባይነትን ፣ ቢሮክራቲዝምን ፣ ወዘተ... ለማንቋሸሽና ለማዋረድ ይጠቅማሉ።

(ሥነ ውበትን ይመለከቷል ።)

## አስመሳይ አብዮተኛ
*(Pseudo–revolutionary)*

ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን በማነብነብ ታጋይ የሚመስል ፣ በአብዮት ስም የሚምልና የሚገዘት ፣ ነገር ግን ለራሱ ጥቅም እንጂ ለሰፊው ሕዝብ ጥቅም ደንታ የሌለው የፖለቲካ ቁማርተኛ ነው ። አስመሳይ አብዮተኛ በደኅና ጊዜ ከማንም ይበልጥ አብዮተኛ መስሎ ቢቀርብም በችግር ወቅት አብዮቱን አጋፍጦ ከጠላት ጎን የሚሰለፍና ሕዝባዊውን አብዮት መልሶም የሚወጋ ነው ።

(ሰርጎ ገብን ፣ ጽናት አልበኝነትን ይመለከቷል ።)

## አስተምህሮ
*(Doctrine)*

አንድ የተወሰነ የዕውቀት ዘርፍ በውስጡ የያዛቸውን መሠረታዊ ሐሳቦች ወይም ትምህርታዊ ይዘቶች ባጭሩ የሚገልጽ ማለትም የመርህ ወይም የእምነት ሥርዓት ወይም ቀኖናን የሚገልጽ ጽንሰ ሐሳብ ነው ። በፍልስፍና ፣ በሃይማኖት ፣ በፖለቲካ ወዘተ...የዕውቀት ዘርፎች ውስጥ ያሉት ቀኖናዎች ወይም ጭብጥ ሐሳቦች አስተምህሮ ይባላሉ ። ለምሳሌ "በመጀመሪያ ቃል ነበረ ፤ ቃል ሥጋ ሆነ" የሚለው ቀኖና ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ነው ። በሰላም አብሮ መኖር የሚለው ፖሊሲም የአብዮታዊት ኢትዮጵያ የውጭ ፖሊሲ አስተምህሮ ነው ።

በየዕውቀት ዘርፉ የታቀፉት አስተምህሮዎች ሳይንሳዊ ወይም ኢሳይንሳዊ ሊሆኑ ይችላሉ ። ኢሳይንሳዊ አስተምህሮ ከሁኔታዎችና ከተግባር ጋር መዛመድ ስለማይችል ቀኖናዊ ነው ። ሳይንሳዊ አስተምህሮ ግን ንድፈ ሐሳብን ከተግባር ጋር ያቀናጀ በመሆኑ ነባራዊ ሁኔታን በትክክል ያንፀባርቃል ።

(ንድፈ ሐሳብን ፣ ቀኖናዊነትን ይመለከቷል ።)

## አስተፃምሮ
*(Synthesis)*

ተቃርኖ አንብሮን ሽሮ በተራው ሲሻርና ከሁለቱ የተገኙት ውጤቶች በአንድነት ተጠቃለው ከፍተኛ የሆነ ሐሳብ ወይም ክስተት ሲፈጥሩ አስተፃምሮ ይባላል ። ይህ ማለት ግን አስተፃምሮ የአንብሮና የተቃርኖ ድምር ወይም ስምምነት ነው ማለት አይደለም ። የሁለቱን ጠቃሚ ጠባዮች የሚያቅፍ በመሆኑ የነሱ የበሳይና ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ነው ። ለምሳሌ ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት የሐሳባዊነትና የቁስአካልነት አስተፃምሮ ነው ሲባል የሁለቱ ቅልቅል ነው ማለት አይደለም ፤ የሁለቱ ቅራኔ የወለደው ልዩና ከፍተኛ ውጤታቸው እንጂ ።

(አንብሮን ፣ ተቃርኖን ፣ የሽረት ሽረት ሕግን ይመለከቷል ።)

## አስታራቂነት
*(Conciliationism)*

በኮሚኒስት ፓርቲ ውስጥ ለፓርቲው ሐቀኛ ፖሊሲ ተቃዋሚነታቸውን በግልጽ ካሳዩ አባላት ጋር ስምምነትና መቻቻል እንዲኖር የሚከራከር ፣ ፀረ ማርክሳዊ አመለካከታቸውንም በቆራጥነት ከመታገል የሚያፈገፍግ አቋም ነው ። የአስታራቂነት አስተሳሰብ የፓርቲ አንድነት እንዲጠበቅ በሚል ሽፋን አፈንጋጮች ፣ አንጃኞችና አድርባዮች ለሚያደርጉት ፀረ ማርክሳዊ እንቅስቃሴ ዕድል ሊሰጥ የሚችል በመሆኑ በጣም አደገኛና በእንጭጩ ሊቀጭ የሚገባው ነው ።

(ለዘብተኝነትን ይመለከቷል ።)

# አስፈላጊ ምርት
*(Necessary Product)*

በቁሳዊ ምርት መስክ የተሰማሩ ሠራተኞች ከሚያመርቱት አጠቃላይ ማኅበራዊ ምርት ውስጥ ለራሳቸውና ለቤተሰባቸው ቁሳዊና ባህላዊ ፍላጐት መታደስ የሚያውሉት የምርት ክፍል አስፈላጊ ምርት ይባላል ። አስፈላጊ ምርትን ለማምረት የሚውለው ጊዜ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ ሲባል በዚህ ጊዜ ውስጥ ሠራተኞች የሚሠሩት ሥራ አስፈላጊ ሥራ ይባላል ። አስፈላጊ ምርትን ከአጠቃላይ ማኅበራዊ ምርት ወይም ከተረፈ ምርት ጋር ካለው መጠናዊ ተዛምዶ ወይም ጥምርታ አንፃር መለካት ይቻላል ።

በጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት ውስጥ የምርት ኃይሎች ጨርሰው ያልዳበሩ ስለነበሩ ተረፈ ሥራ የሚባል ነገር አልነበረም ። ስለዚህም የሚመረተው ምርት በጠቅላላ የአስፈላጊ ምርትን መልክ የሚይዝ ነበር ። የምርት ኃይሎች መሻሻልና መዳበር የተረፈ ምርትን መገኘት አስከተለ ። ይህም አንዱ መደብ ሌላውን ለመበዝበዝ እንዲችል ነባራዊ ሁኔታን ፈጠረ ።

ተፃራሪ መደቦች ባሉባቸው ማኅበራዊ ሥርዓቶች ሁሉ በአስፈላጊ ምርትና በተረፈ ምርት መካከል ያለው ግንኙነት ከብዝበዛ ጋር የተቆራኘ ነው ። በዝባዥ መደቦች የሚያገኙት ተረፈ ምርት በምርት መስክ ከመሰማራት የመነጨ ሳይሆን የምርት መገልገያዎችን በግል ባለቤትነት በመያዛቸው ነው ። በባሪያ አሳዳሪውና በፊውዳሉ ሥርዓቶች ውስጥ የአስፈላጊ ምርት መጠን በእነዚህ ሥርዓቶች ውስጥ ባለው ዝቅተኛ በሆነ የሥራ ምርታማነትና የብዝበዛ ግንኙነት የሚወሰን ነው ።

የካፒታሊስት ምርት ዓይነተኛ ጠባይ ተረፈ እሴትን ማጋበስ እንደሆነ ይታወቃል ። ይህን ለማድረግ ደግሞ ካፒታሊስቶች በአብዛኛው የአስፈላጊ ምርትን ድርሻ በመቀነስ የተረፈ ምርትን ድርሻ ለማሳደግ ይጣጣራሉ። በካፒታሊዝም የዕድገት ሂደት ውስጥ ማኅበራዊ ሥራ በሚያሳየው የምርታማነት ዕድገት የተነሣ የአስፈላጊ ምርት ከአጠቃላይ ማኅበራዊ ምርት ድርሻ አንፃራዊ በሆነ መንገድ ይቀንሳል ። ይህ ሁኔታ በተለይ የሚመለከተው የፍጆታ ዕቃዎችንና እነዚህን ዕቃዎች ሠርቶ የሚያወጣውን ክፍለ ኢኮኖሚ ነው ።

ከላይ እንደተጠቀሰው በካፒታሊዝም ከአጠቃላይ ማኅበራዊ ምርት የአስፈላጊ ምርት ድርሻ አንፃራዊ ቅነሳ ቢያሳይም በዚሁ ሥርዓት ውስጥ ይህንን አዝማሚያ የሚከላከሉ ሌሎች ሁኔታዎችም አሉ ። ከነሱም መካከል በካፒታሊስት ሀገሮች የወዝአደሩ መደብ ለምንዳ ጭማሪና ለማኅበራዊ መብቱ መስፋፋት የሚያደርገው ትግል ዋንኛው ነው ። በካፒታሊስት ሥርዓት የሥራ ዕምቀት መጨመርና ይህም የሚያስከትለውን የአካል ድክመትና የአእምሮ ጭንቀት ለማካካስ ካፒታሊስቶች የተወሰነ ወጪ እንዲያደርጉ ያስገድዳቸዋል ። ከዚህም በተጨማሪ አሁን ካለው የሳይንስና የቴክኖሎጂ አብዮት አንፃር የሠራተኛውን መደብ የትምህርትና የሙያ ደረጃ ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ እነዚህ ሁኔታዎች ተጠራቅመው ከአጠቃላይ ማኅበራዊ ምርት የአስፈላጊ ምርት ድርሻ እንዳያቆለቁል ለማድረግ ይረዳሉ ።

በሶሻሊዝም የምርት መገልገያዎች በጋራ የተያዙና ማኅበራዊ ምርትም በዕቅድ የሚመረት በመሆኑ በአስፈላጊ ምርትና በተረፈ ምርት መካከል ያለው ቅራኔ ይወገዳል ። በሶሻሊዝም የአስፈላጊ ምርት መጠን የሚወስነው የሠራተኛውን መሠረታዊ ፍላጐት ለማሟላት በመቻል ብቻ ሳይሆን የሠራተኞችን የተሟላ አካላዊና ባህላዊ ዕድገት ከማስገኘት አንፃር ነው ።

በሶሻሊዝም ከአስፈላጊ ምርት ውስጥ የተወሰነው ክፍል ከእያንዳንዱ እንደ ችሎታው ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው በሚለው መርህ መሠረት የሚከፋፈል ሲሆን የተቀረው ክፍል ደግሞ በማኅበራዊ ፍጆታ ምድብ በኩል በተጨማሪ ክፍያዎችና አገልግሎቶች መልክ ይከፋፈላል ። ስለሆነም በሶሻሊዝም አስፈላጊ ምርት በምግብ ፣ በልብስና በመሳሰሉት መልክ ለግል ፍጆታ ሲውል በሌላ በኩል ደግሞ በትምህርት ቤት ፣ በመጻሕፍት ቤት ፣ በሕክምና ተቋሞችና በሌሎች አገልግሎት ሰጭ ተቋሞች መልክ ለወል ፍጆታ ይውላል ።

(ተረፈ ምርትን ይመለከቷል ።)

## አስፈላጊ ሥራ
(*Necessary Labour*)

በቁሳዊ ምርት ተግባር ላይ የተሰማራ ሠራተኛ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በሥራ ላይ ከሚያውለው ጉልበቱ መካከል ለራሱ የሥራ ኃይል መታደስና ለሱና ለቤተሰቡ ኑሮ የሚያስፈልገውን ለማግኘት የሚሠራው ሥራ ነው ። ይህ ለሱና ለቤተሰቡ ኑሮ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ለማግኘት የሚሠራው አስፈላጊ ሥራ የሚወስደው ጊዜ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ በመባል ይታወቃል ።

በአንድ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ውስጥ የአስፈላጊ ሥራ ዓይነተኛ ጠባዮች የሚወሰኑት በምርት ኃይሎችና በማኅበራዊ ምርት የዕድገት ደረጃ ነው ። ለምሳሌ በጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት ዘመን የሥራ ምርታማነት እጅግ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ስለነበር የሚሠራው ሥራ ሙሉ አስፈላጊ ሥራ ነበር ። ማለትም በዚያን ወቅት ተረፈ ምርት የሚባል ነገር ስለአልነበረና የሚመረተውም ምርት ከፍላጎት በላይ ስላልሆን ተረፈ ሥራ የሚባል ፈርጅ አልተከሰተም ነበር ።

የምርት ኃይሎች ዕድገት ባሳዩበትና በተሰይም ተፃራሪ መደቦች በተከሰቱበት ሁኔታ ግን አስፈላጊ ሥራ ከሥራ ጊዜ የተወሰነውን ድርሻ ሊይዝ በቃ ። ቀሪው ደግሞ ተረፈ ሥራ የሚባለው ሲሆን የዚህም ውጤት ተፃራሪ መደቦች ባሉበት ሁኔታ ለበዝባዥ መደቦች ግልጋሎት የሚውል ነው ። በአስፈላጊ ሥራና በተረፈ ሥራ መካከል ያለው መጣኔ የብዝበዛውን መጠን ይገልጻል ። በዝባዥ መደቦች ባሉበት ሁኔታ በዝባዦች ከተመደበው የሥራ ቀን ውስጥ የአስፈላጊ ሥራን ድርሻ በመቀነስና የተረፈ ሥራን ድርሻ በመጨመር ፣ በዚህም የሠርቶ አደር ሕዝቦች የኑሮ ደረጃ እንዲያቆለቁል በማድረግ የነሱን ገቢ ያሳድጋሉ ።

በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት የባሪያው ሥራ በአስፈላጊና በተረፈ ሥራ የተከፋፈለ ቢሆንም ባሪያው ያመረተው ምርት በሙሉ ለባሪያ አሳዳሪው ስለሚወሰድ ይህ ክፍፍል ይደበቅና ባሪያው የሚሠራው ሥራ ሁሉ ተረፈ ሥራ መስሎ ይታያል ።

በፊውዳል ሥርዓት ግን የጭሰኛው አስፈላጊ ሥራና ተረፈ ሥራ በግልጽ የተከፋፈለ ነው ። የገበሬው ተረፈ ሥራ የገንዘብና የዓይነት ክፍያ መልክንም የሚገልጽ ነው ። ጭሰኛው በአስፈላጊ የሥራ ጊዜው በራሱ ማሣ ላይ በማረስ ለራሱና ለቤተሰቡ የሚያስፈልገውን ሲያመርት በሳምንት ውስጥ ባለው ቀሪ ጊዜ ደግሞ በተረፈ ሥራ መልክ በፊውዳሉ ማሣ ላይ ለፊውዳሉ በነፃ ይሠራል ።

በአንፃሩ በካፒታሊስት ሥርዓት የሥራ ኃይሉን ሸጦ በሚተዳደረው ወዝአደር አስፈላጊ ሥራና ተረፈ ሥራ መካከል ያለው ክፍፍል ድብቅ ነው ። ምክንያቱም በካፒታሊዝም ውስጥ ያለው የምንዳ ሥርዓት ለወዝአደሩ የሚከፈለው ምንዳ ለአስፈላጊ ሥራው ብቻ ሳይሆን ለተረፈ ሥራው ጭምር የሚከፈል መስሎ ስለሚታይ ነው ። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን በካፒታሊዝም ምንዳ የሚሸፍነው አስፈላጊ ሥራን እንጂ ተረፈ ሥራን አይደለም ፤ ሊሆንም አይችልም ።

በሶሻሊዝም ሥራ በአስፈላጊና በተረፈ ሥራ መከፈሉ ይቀጥላል ። ይሁንና የሶሻሊስት ምርት ዓላማ የግል ትርፍ ማሰባሰብን የሚፃረር በመሆኑ በማኅበራዊ ምርትና በማኅበራዊ ክፍፍል መካከል መጣጣም ይኖራል ። ስለሆነም በአስፈላጊ ሥራና በተረፈ ሥራ መካከል ያለው ቅራኔ ይወገዳል ። የሶሻሊዝም መሠረታዊ የኢኮኖሚ ሕግ እያደገ የሚሄደውን የሕዝቡን ፍላጐት ማርካት እንደ መሆኑ በአስፈላጊ ሥራ አማካይነት የሚገኘውና በየጊዜው እያደገ የሚሄደው አስፈላጊ ምርት ለአመረተው ሠራተኛ የግል ፍጆታ ከመዋሉም በላይ በተረፈ ሥራ የሚገኘው ምርትም የሶሻሊስት መንግሥት ለማኅበራዊ አገልግሎትና ለሕዝቡ የኑሮ መሻሻያ ያውለዋል ።

(አስፈላጊ ምርትን ፣ ምንዳን ይመለከቷል ።)

## አረብ ሊግ
(*Arab League*)

በአረብ ሀገሮች መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር ፣ ፖሊሲያቸውንና ተግባራዊ እርምጃዎቻቸውን ለማቀናጀትና ለጋራ ጥቅም ለማዋል እንዲቻል ታስቦ በነፃ የአረብ ሀገሮች መካከል በመጋቢት 1945 የተመሠረተ

ድርጅት ነው ። በዚህም መሠረት ዛሬ የአረብ ሊግ በሰሜንና በምሥራቅ አፍሪካ ፣ እንዲሁም በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኙ 21 ሀገሮችን (የፍልስጥኤም ነፃ አውጭ ድርጅትን ጨምሮ) በአባልነት ያቀፈ ነው ። የድርጅቱ ጽሕፈት ቤት ቱኒስ ውስጥ ሲሆን ፣ ድርጅቱ ስሥራው እንዲያመቸው በአንዳንድ ሀገሮች ጽሕፈት ቤቶችና የመረጃ ማዕከሎች አሉት ።

የአረብ ሊግ ከተመሠረተበት ወቅት ጀምሮ በቅኝ አገዛዝ ሥር የነበሩ የአረብ ሀገሮች ነፃ እንዲወጡና በአረብ ሀገሮች የኢምፔሪያሊዝምን የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ በመቃወምና አባላቱን በፀረ ኢምፔሪያሊስት ዓላማ በማስተባበር አስተዋጽኦ አድርጓል ። ከአባል ሀገሮቹ ዝርዝር ለመረዳት እንደሚቻለው የአረብ ሊግ ተራማጅና አድኃሪ መንግሥታትን በአንድ መድረክ ያሰባሰበ በመሆኑ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ጥያቄዎች ላይ ተመሳሳይ አቋም እንዳይይዝ አድርጎታል ። ለምሳሌ በሳዳት የሚመራው የግብጽ መንግሥት በአሜሪካ ግፊት ከእስራኤል ጋር በተናጠል የካምፕ ዴቪድ ስምምነት ከተፈራረመ ወዲህ በድርጅቱ ውስጥ የታየው መከፋፈል የዚሁ ነፀብራቅ ነው ። አድኃሪ የአረብ መንግሥታት በተለያዩ አካባቢዎች በሃይማኖት ስም የሚካሄዱትን ፀረ ሕዝብ እንቅስቃሴዎች እንዲረዳ ድርጅቱን ሲገፋፉ ፣ ተራማጅ የሆኑት ደግሞ የሕዝባዊ እንቅስቃሴዎችን ፀረ ኢምፔሪያሊስት ይዘት ለማጠናከር ትግል ያካሂዳሉ ።

## አረብ ሶሻሊዝም
*(Arab Socialism)*

ከመደብ አንድነት ይልቅ በአረቦች ወንድማማችነት ላይ የተመሠረተ ሶሻሊስታዊ ይዘት አለኝ የሚል እንቅስቃሴ ነው ። ይህ እንቅስቃሴ የተመራው የአውሮፓን ትምህርት በቀመሱ አረብ ምሁራንና ወጣት መኮንኖች ሲሆን ዓላማውም የመደብ ትግል አካሂዶ የሠራተኛውን መደብ ለሥልጣን ማብቃት ሳይሆን መላውን አረብ ከሥልጣኔ ጋር ማስተዋወቅና ጠንካራ የሆነ የአረብ ወንድማማችነትን መመሥረት ነው ።

የአረብ ሶሻሊዝም ግንባር ቀደም መሪ የአረብ ሶሻሊስት ፓርቲ ወይም በአዝ ፓርቲ በመባል የሚታወቀው ነው ።

የአረብ ሶሻሊዝም ዓላማ ላይ ላዩን ሲታይ የአረብን ዓለም ወንድማማችነት ማስፈን እንደሆነ ቢስፋፍለትም ለመደብ ትግል ያልቆመ በመሆኑ ሶሻሊስታዊነቱን በተግባር ሊተረጉም አልቻለም ።

## አረቦን
*(Bond)*

በተወሰነ ገንዘብ የሚገዛ ፣ የተወሰነና ቋሚ የሆነ ገቢ ለተወሰነ ጊዜ በወለድ መልክ ለማስገኘትና ዋናውን ከተወሰነው ጊዜ በኋላ መልሶ ለማግኘት የሚያስችል ሕጋዊ የምስክር ወረቀት አረቦን ይባላል ። አረቦን በጋራ አክሲዮን ኩባንያ ወይም በካፒታሊስት መንግሥት አማካይነት ለሽያጭ ይቀርባል ። ኩባንያዎች ወይም ካፒታሊስት መንግሥታት አረቦን በመሸጥ ካፒታል ይሰበስባሉ ።

አረቦን ሕጋዊ የምስክር ወረቀት በመሆኑ አረቦኑን የሸጠው አካል ስገዛው ወገን ዋናውን ከነወለዱ በተወሰነ ጊዜ እንዲመልስ ሕጋዊ ስምምነት ያደረገ መሆኑን ያረጋግጣል ።

አረቦን ለተወሰነ ጊዜ ቋሚ የሆነ ገቢ ለያዡው የሚያስገኝ እንደመሆኑ ሁሉ የተወሰነው ጊዜ ሲያልቅም አረቦኑን የሸጠው ኩባንያ መልሶ ይገዛዋል ።

በአረቦን ገዥዎችና ሻጮች መካከል ያለው ግንኙነት የአበዳሪና የተበዳሪ መልክ አለው ። ስለዚህ አረቦን ገዥዎች የኩባንያው የጋራ ባለቤቶች ሳይሆኑ የኩባንያው አበዳሪዎች ናቸው ። የሶሻሊስት መንግሥት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በአረቦን ሽያጭ አማካይነት ከሕዝብ ገንዘብ ተበድሮ ተጨማሪ ገንዘብ በማግኘት የሰፊውን ሕዝብ ጥቅም ያዳብራል ።

(አክሲዮንን ፣ የጋራ አክሲዮን ኩባንያን ይመለከቷል ።)

# አርስጣጣሊስ

*(Aristotle)*

ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ384—322 የኖረ በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የያዘ ፣ አስተምህሮውም ሁለንታዊና ሥር ስደድ የሆነ ፣ የቅርፃዊ ሥነ አመክንዮ ሕጎችን የቀመረ ፣ በአጠቃላይ የተሟላና በታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ሚና የተጫወተ ፍልስፍናን የመሠረተ ዕውቅ የግሪክ ሐሳባዊ ፈላስፋ ነው ። ለብዙ ጊዜ የአፍላጦን ተማሪ የነበረና ከዚያም የትልቁ አስክንድር አስተማሪ በመሆን ያገለገለ ሲሆን ከደረሳቸው ጽሑፎች ውስጥ "ሜታፊዚክስ" ፣ "እርጋነን" ፣ "ፖለቲክስ" ፣ "ኤቲክስ" የተባሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው ።

ለአርስጣጣሊስ ፍልስፍና መነሻ የሆነው አርስጣጣሊስ በአፍላጦን ፍልስፍና ላይ ያቀረበው ኂስ ነው ። በተለይም አፍላጦን ሁለንታዊና ግላዊ ባሕርያትን ለይቶ በተለያዩ ሁለት ዓለሞች ውስጥ ይገኛሉ ብሎ የሰነዘረውን አመለካከት አጥብቆ ተቃውሟል። እንደአርስጣጣሊስ አባባል እውነታነት ያለው ተጨባጭና ግላዊ ነው። ሁለንታዊ የሆነው ቤት ወይም ሰው በራሱ እንደማይኖር ሁሉ ማንኛውም ሁለንታዊ የሆነ ነገር ከግላዊ ውጭ የራሱ ህልውና የለውም ። ሁለንታዊነት ያላቸው ግንዛቤዎች ናቸው ፤ እነርሱንም የምንቀርፀው ከግላዊ ባሕርያት ተነሥተን በወል ያላቸውን ጠባይ በማጤን ነው ። ይህም ዘዴ አርቅቆት ይባላል። ስለዚህም ዕውቀት የሚነሣው ከሕዋሳት በመሆኑ የሁለንታዊ ግንዛቤዎች መሠረት የተጨባጩ ዓለም ሥርዓትና ከሱም የምናገኘው ልምድ ነው በማለት አርስጣጣሊስ ተናግሯል ።

እንዲሁም አርስጣጣሊስ አፍላጦን ስለ ቅስቃሴ ተለዋዋጭ ጠባይ የሰጠውን አስተያየት ለማረም ሞክሯል ። በአርስጣጣሊስ አመለካከት አንድ ነገር ተለዋዋጭ ስለሆነ ታዋቂነት የለውም ማለት አይደለም ። መለዋወጥ ራሱ በሕግ የሚገዛ በመሆኑ አንድ ነገር ተለወጠ ማለት እራሱን ከዳ ፣ ደመሰሰ ማለት ሳይሆን አደገ ፣ በውስጡ በጽንስ ደረጃ የነበረው እውን ሆነ ማለት ነው ። ይህ የቅስቃሴ ሕግ የሚያሳየን አንድ ነገር የሚለወጠው ወይም ሌላ ነገር የሚያፈልቀው የራሱን ሕይወት ከጨረሰ በኋላ የሚተካው ነገር የሱ ተቃራኒ ሳይሆን ቅጥያው መሆኑን ነው ። ከዚህ በመነሣት አንድ ነገር ለተወሰነ ጊዜ የሆነ መልክ ይኖረዋል ፣ በተወሰነ ጊዜ ውስጥም ይለወጣል በማለት አርስጣጣሊስ የቅርፃዊ ሥነ አመክንዮን መሠረታዊ አስተሳሰብ ማለትም የራስነትን ወይም የቅራኔ አልባነትን መርህ ቀምሯል ። አንድን ነገር በትክክል የምንረዳው ተቃርኖ ሳንጨምርበት እንደሂደቱ አመጣጥ በሥርዓት ስንገልጸው ነው ። አንድ ነገር ከትንሽ ወደ ትልቅ ሲቀየር በአንድ ጊዜ ሁለቱንም ነው ብሎ መናገሩ ተቃርኖ ሲሆን ትክክለኛው አነጋገር ግን ለተወሰነ ጊዜ ትንሽ እንደነበርና ከዚያም ወደትልቅነት እንደተሸጋገረ ማለትም ሁለቱን ጠባዮች በጊዜና በቦታ ለይቶ የሚገልጸው ነው ።

አርስጣጣሊስ በፖለቲካና በሥነ ምግባር አስተሳሰብም የአፍላጦንን አስተምህሮ አልተቀበለም ነበር ። በተለይም ኅብረተሰብንና ሰውን በትክክል ልናጠና የምንችለው መሆን ካለበት ተነሥተን አይደለም ። ምን ጊዜም ቢሆን መነሻችን ተጨባጭ ሁኔታ መሆን አለበት ። በመሆኑም የሥነ ምግባር ዓላማ ስሜትን መጨቆን አይደለም ። የሰው ፍላጎት ደስታን ማግኘት መሆኑን በቅድሚያ ተረድተን የሥነ ምግባር ዓላማ ይህን ደስታ ቋሚ ለማድረግ የሚያስፈልጉትን መንሥኤዎችና ጥበብ ማስተማር ይሆናል ። ደስታ ወጣ ገባ ሳይሆን ቋሚነት የሚኖረው ስሜታችን ፣ ከንዋኔያችንና ፍላጐታችን ከልክ ሳያልፍና ከጉድለት የተጠበቀ ማለትም መካከለኛ ወይም ሚዛናዊ ሲሆን ነው ። ለምሳሌ ከብኩንነትና ከስግብግብነት የሚመረጠው በቁጠባ መኖር ነው ። ከትእቢትና ራስን ከማንቋሸሽ ጥሩው ትሁት መሆን ነው ። ከፍርሃትና ከድፍረት ሚዛናዊው መልካም ጉብዝና ነው ። እንደ አርስጣጣሊስ አባባል የውበትም ዋና ሚና በውስጥ መጣጣምና በቅርፅ ጥራት ኃይለኛ ግፊት ያላቸውን ተፈጥሮአዊ ስሜቶቻችንን ማቀዝቀዝና ዲሲፕሊን ማስተማር ነው ።

ይህ የደስታ ኑሮ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው አመች በሆነ ማኅበራዊ ሥርዓት ውስጥ ነው ። ሰው በተፈጥሮ ማኅበራዊ በመሆኑ ከማኅበር ውጭ ሊኖር ወይም ሊደሰት አይችልም ። አመች ወይም ትክክለኛው ማኅበራዊ ሥርዓት ሲባል መንግሥት መሆን ከነበረበት አንፃር መናገር ሳይሆን ከተከሰቱት

የመንግሥት ዓይነቶች የሚሻለውን በመም ረጥ እሱኑ ማሻሻል ማለት ነው ። ለምሳሌ እንደ አርስጣጣሊስ አባባል ባርነትን ለማስ ቀረት መሞከር ፍጹም ተምኔታዊ የሆነ አመ ለካከት ነው ። በሰው መካከል ያለውን ተፈ ጥሮአዊ ልዩነት ስናይ ፣ ያግሞም ከብዙው ውስጥ ጥቂቶቹ ጥበብንና ዕውቀትን ለማሳ ደግና ሚዛናዊና የደስታ ኑሮ እንዲኖራቸው ለማድረግ ከጉልበት ሥራ ነፃ መሆን እንዳ ለባቸው ስንመለከት ባሪያ አስፈላጊ መሣሪያ መሆኑን እንረዳለን ። በመሆኑም ቁም ነገሩ የማኅበራዊ ሥርዓትን ፍጹም ጥሩነት መመ ኘት ሳይሆን ሚዛናዊ ማድረጉ ነው ። ለአር ስጣጣሊስ ብዙው የበላይ ገዥ ከሚሆንበት (ዲሞክራሲ) ትንሹ የበላይ ገዥ ከሚሆንበት (ኦሊጋርኪ) ከሁለቱ መጥፎ ገጽታዎች ለመ ራቅ የሚሻለው የመካከለኛው መደብ አገ ዛዝ ሥርዓት ነው ።

አርስጣጣሊስ የአፍላጦንን ተምኔታዊ ነት በመቃወም ከተጨባጩና ከልምድ በመ ነሣት ስለ ኑባሬ ፣ ስለዕውቀት ፣ ስለ ግብረገብና ስለ ማኅበራዊ ሥርዓት ከተቀነባበረ ዕው ቀት ላይ ለመድረስ ሞክሯል ። ነገር ግን ይህ ሳይንሳዊ አዝማሚያ አርስጣጣሊስ በነ በረው መሳፍንታዊ አቋም በመበከሉ የወላ ዋይነት ጠባይ ይዞአል ። በነበረው ቁስአካ ላዊ እዝማሚያ እስከ መጨረሻው ሳይገፋ በት ፣ የቅስቃሴ ምንጭ እግዚአብሔር ነው ብሎ መናገሩ ፣ ስለደስታ ዓለማዊነት ከገለጸ በኋላ የደስታ መጨረሻ አእምሮአዊ ደስታ ነው ብሎ ማሰቡ ፣ ተጨባጩ ለማንኛውም ነገር መነሻና ማመዛዘኛ ነው ካለ በኋላ ስለ ጉልበት ሥራ ያሳየው ጥላቻና ስለ ባርነት የሰጠው የተዛባ አመለካከት ለወላዋይነቱ ብቁ ማስረጃዎች ናቸው ። ከዚህም የምንረ ዳው የነበረበት የመደብ ተፅዕኖ ቁስአካላዊ አስተሳሰቡን በማደፍረስ ወደሐሳባዊነት እን ዲያደላና ተቃራኒ አመለካከት እንዲኖረው ማድረጉን ነው ። አርስጣጣሊስ የቅርፃዊ ሥነ አመክንዮ ሕጎችን መቀመሩ እጅግ የሚያ ስመሰግነው ቢሆንም ይህንን ሥነ አመክንዮ ግን ፍጹማዊ አድርጎ መውሰዱ ፣ በተለይም የቅራኔን ነባራዊነት በመካድ ቅራኔ ከአስተ ሳሰብ ስህተት የሚመነጭ ነው ብሎ መና ገሩና ማስተማሩ ለዲያሌክቲካዊ አስተሳሰብ መወለድና ማደግ ከፍተኛ መሰናክል ሆኗል ።

አርስጣጣሊስ በተፈጥሮም ሆነ በማኅ በራዊ ሳይንስ መስኮች ብዙ ምርምሮችን ያካሄደ እንደመሆኑ በኢኮኖሚ ሳይንስ ዘርፍም አንዳንድ ምርምሮችን አድርጓል ። የኢኮኖሚ አመለካከቱም የተመሠረተው የባሪያ አሳዳ ሪውን ሥርዓት የሸቀጥ ምርት እንደ ዘለዓለማ ዊና እንደተፈጥሮ ክስተት አድርጎ በመውሰድ ነው ።

ሀብትን በሚመለከት አርስጣጣሊስ በሁ ለት ከፋፍሎ አቅርቦት ነበር ። ይኸውም አንደኛው የአጠቃላይ የፍጆታ ዕቃዎች እሴት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የገንዘብ ወይም የል ውውጥ እሴት ጥርቅም ነው ። እንደ አርስጣጣ ሊስ አመለካከት የመጀመሪያው ዓይነት ሀብት የሚመነጨው ከእርሻና ከእደጥበብ ሲሆን ይህንንም ዓይነት ምርት ፣ ከምርታዊ ሥራ የሚመነጭና የሰውንም ፍላጎት ለማርካት የሚያገለግል በመሆኑ የተፈጥሮ ምርት በማለት ሰይሞት ነበር ። ሁለተኛው ዓይነት ሀብት ከዝውውር የሚመነጭና ለቀጥተኛ ፍጆታ የሚውል ባለመሆኑ ኢተፈጥሮአዊ በማለት ሰይሞታል ።

አርስጣጣሊስ በሀብት ላይ የሚደረገውን ጥናት ኢኮኖሚክስና ክሬማቲስቲክስ በማለት በሁለት ከፍሎታል ። እንደርሱ አመለካከት ኢኮኖሚክስ ማለት ከተፈጥሮ ክስተት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ስለፍጆታ ዕቃዎች እሴት ምርት የሚደረግ ጥናት ነው ። አነስተኛ ደረጃ ንግድ ብዙም ትርፍ ስለማያስገኝ ፣ ይህንኑ አስመልክቶ የሚደረገው ጥናት በኢኮ ኖሚክስ ጥናት ውስጥ ሊጠቃለል እንደሚ ችል ጽፏል ። በሌላ በኩል ክሬማቲስቲክስ የሚለውን የጥናት ዘርፍ የተመለከተው ገንዘ ብን ከማከማቸት ጋር የተያያዘውንና ኢተፈ ጥሮአዊ ክስተት የሚለውን እንደሚመለከት አድርጎ ነው ።

ኢኮኖሚክስንና ክሬማቲስቲክስን የማነፃ ፀሩ ሁኔታ አርስጣጣሊስን ስለሸቀጦችና ስለ ሸቀጦች ልውውጥ ውስጣዊ ይዘት እንዲመ ራመር አድርጎት ነበር ። በኢኮኖሚ ሳይንስ ታሪክ ውስጥ በጠቀሜታ እሴትና በልውውጥ እሴት መካከል ያለውን ልዩነት በመገንዘብ ረገድ የመጀመሪያው ሰው ነው ። ለዚህም ነው በብዙ የኢኮኖሚ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ አርስጣጣሊስ የኢኮኖሚ ሳይንስ አባት በመ ባል የሚታወቀው ።

አርስጣጣሊስ ስለ ልውውጥ እሴት ይዘትና መንሥኤ በመመራመር አንዳንድ አስተሳሰቦች ቢሰነዝርም ፣ የሰው የሥራ ኃይል የዕቃዎች እሴት ፈጣሪ መሆኑን በሚገባ ሊገነዘብ አልቻለም ።

በማርክስ አመለካከት አርስጣጣሊስ የሸቀጦችን ልውውጥ በሚመለከት ያበረከተው አስተዋጽኦ የዕቃዎችን እሴት በሚገልጽበት ጊዜ በዕቃዎቹ ውስጥ ያለውን እኩያዊ ግንኙነት ማግኘቱ ነው ።

ስለገንዘብ አመጣጥና በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል ከሚደረገው የንግድ ልውውጥ አንፃር አንድ የተወሰነ ሸቀጥ የግዴታ የገንዘቡን ሚና እንዲጫወት ስለማስፈለጉ አርስጣጣሊስ ያደረገውን ገለፃ ማርክስ ከፍተኛ ግምት ሰጥቶታል ።

ይሁንና አርስጣጣሊስ የገንዘብን ታሪካዊ አመጣጥና አስፈላጊነት በሚመለከት ትክክለኛ ግንዛቤ ስላልነበረው ፣ ገንዘብ ሁለንታዊ የልውውጥ አማካይ ሊሆን የቻለው በመንግሥታት ወይም በሰዎች ስምምነት እንደሆነ አድርጎ ይመለከታል ። አርስጣጣሊስ የገንዘብን ተግባር ሲገልጽ ገንዘብ እንደ ዝውውር አማካይ ፣ እንደ እሴት መለኪያና እንደተከማቸ ሀብት የሚያገለግል መሆኑን አብራርቷል ።

(አፍላጦንን ፣ ይመለከቷል ።)

## አርሶ አደር

(*Peasantry*)

(ገበሬን ይመለከቷል ።)

## አርቅቆት

*(Abstraction)*

የአንድን ነገር ጠባዮች ወይንም የነሱን የእርስ በርስ ግንኙነቶች በሐሳብ የሚለያይ የዕውቀት ስልት ነው ። ይህ የመለያየት ሁኔታ ከውሱንና ግላዊ ከሆኑ ክስተቶች ሐሳቦችን አላቆ ወደ አጠቃላይ ግንዛቤዎች እንዲያመሩ ያደርጋል ። ቁስአካል ፣ እንቅስቃሴ ፣ ፋይዳ ፣ ሕይወት ወዘተ ... የምንላቸው አጠቃላይ ጽንስ ሐሳቦች የሚገኙት ከነገሮች ግላዊነት ባሻገር አጠቃላይ ሁኔታዎችን በማጤን ነው ።

ማንኛውም ዕውቀት በአርቅቆት ላይ የተመሠረተ ነው ። ምክንያቱም ከረቂቅ ሐሳቦች ላይ ካልደረስን የአንድን ነገር ባሕርያት ወይም ውስጣዊ ምንነት ልንረዳ አንችልም ። አንድ ነገር ካልተፈታታና ምንነታዊ መልኮቹ ተለያይተው ካልተጤኑ ውስጠ ምሥጢሩ ሊታወቅ አይችልም ። የአርቅቆቱ ዓይነት በተለይም ምን ከምን እንደሚለይ የሚወሰ ነው በስዎች ተግባራዊ ፍላጐት ፣ በግንዛቤ ሂደትና በሚጠናው ነገር ባሕርይ ነው ።

ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ስለ አርቅቆት ያለው አመለካከት ሳይንሳዊ ነው ። በተለይም የሐሳባውያን አስተሳሰብ የተመሠረተው የአርቅቆትን ውጤቶች ወደ ባሕርዮት በመለወጥ ማለትም ሐሳብን ነባራዊ በማድረግ መሆኑን ያስረዳል ። ይህን የተሳሳተ አመለካከት በማረም ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ረቂቅ ሐሳቦች በነባራዊነት ያሉ ሳይሆኑ ሰው የነባራዊውን ዓለም ግንዛቤ ለማግኘት ከሚያደርገው ጥረት የሚመነጩና ተጨባጩን የሚያንፀባርቁ መሆናቸውን ያስረዳል ።

(ጭብጥን ፣ ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀትን ፣ ነባራዊ ሐሳባዊነትን ይመለከቷል።)

## አርበኝነት

*(Patriotism)*

አንድ ሰው ለሀገሩ ብልጽግና ፣ ደኅንነት ፣ ነፃነት ወዘተ... ያለው ጥልቅ የፍቅር ስሜትና ቀናኢነት ፤ ይህንንም ለማስከበር ያለው የቆራጥነትና የዝግጁነት መንፈስ ነው ። አርበኝነት ከአንድ ከተወሰነ ኅብረተሰብ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች የሚመነጭ ቁሳዊ መሠረት ያለው ነው ።

አርበኝነት በተለያዩ ወቅቶች የተለያየ ይዘት ያለው ክስተት ነው ። አርበኝነት የማኅበራዊ ንቃት ውጤት እንደመሆኑ በተለይ በካፒታሊዝም መባቻ ወቅት ላይ ከብሔሮችና ከብሔራዊ መንግሥታት መከሰትና መጠናከር ጋር እያደገ የመጣ ነው ። ካፒታሊስት ኅብረተሰብ በመደቦች የተከፋፈለ በመሆኑ ቡርዧዚው የሕዝቡን የአርበኝነት ስሜት ለግ

ለቲካ የበላይነቱና ለኢኮኖሚ ጥቅሙ አውሎታል ።

ሶሻሊስት አርበኝነት ግን የሚያስከብረው የሰፊውን ሕዝብ የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት በመሆኑ ከዚሀ እጅግ የላቀና የተለየ ነው ። ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ሶሻሊስት አርበኝነትን የሚጐናፀፈው በወዝአደሩ መሪነት ከአድኃሪ ሥርዓት ምዝበራና ጭቆና ጨርሶ ለመላቀቅና እውነተኛ መብቱን ለመጐናፀፍ በሚያደርገው ረዥምና ውስብስብ የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ግንባታ ሂደት ውስጥ ነው ። ሶሻሊስት አብዮት እየተጠናከረ ሲሄድ ሠርቶ አደሩ ለሠራተኛው መደብ መንግሥትና ለአዲሱ ሥርዓተ ማኅበር ያለው የአርበኝነት ስሜትም እየዳበረ ይሄዳል ።

ሶሻሊስት አርበኝነት ከወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት ጋር በቅርብ የተሳሰረ ፣ የብሔረተኝነትና የኮስሞፖሊታኒዝም ተፃራሪ የሆነ ነው ።

(ብሔረተኝነትን ፣ ኮስሞፖሊታኒዝምን ይመለከቷል ።)

## አሻንጉሊት
(*Puppet*)

በውጭ ኃይል ወይም ተፅዕኖ ቁጥጥር ሥር የዋለ ግለሰብ ፣ ቡድን ፣ ወይም አስተዳደር አሻንጉሊት ይባላል ። በተለይ የሀገራቸውን ነፃነትና የሕዝባቸውን መብት በማስከበር ፈንታ የኢምፔሪያሊዝም መሣሪያ ለሆኑ መሪዎችና የፖለቲካ ሰዎች እንዲሁም መንግሥት አሻንጉሊት የሚለውን ቅጽል መስጠት የተለመደ ነው ።

## አሻጥር
(*Sabotage*)

በማኅበራዊ ግንኙነት ውስጥ ግለሰቦች ፣ ቡድኖች ወይም ድርጅቶች ባላቸው ቅሬታ ወይም ጥቅማቸውንና ፍላጐታቸውን ለማሟላት ሲሉ በተለያየና ስውር በሆነ መንገድ ሌሎችን ለመጉዳት ወይም ለማጥፋት የሚፈጽሙት ድርጊት አሻጥር ይባላል ። ለምሳሌ በአንድ የማምረቻ ድርጅት ውስጥ የምርትን ሂደት ማደናቀፍ (በስውር የማምረቻ መሣሪያ መስበር ፣ ሰነዶችን ማጥፋት ወዘተ...) አሻጥር ነው ። የተወሰነን ክፍል ወይም መደብ በተለይም የለውጥና የዕድገት ተፃራሪ ወገኖችን ጥቅምና ፍላጐት በመመርኮዝ ተመክሮበትና ተዘክሮበት ሆን ተብሎ የተራማጅ ኃይሎችን አቋምና ተግባር ለማደናቀፍ በአንድ ሀገር የውስጥና የውጭ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የሚፈጸም የሴራ ተግባር ነው ።

በዚሀ መሠረት ፀረ አብዮት ኃይሎች የኢኮኖሚና የማኅበራዊ አገልግሎት ድርጅቶችንና የመገናኛ አውታሮችን በማፈራረስ ፣ ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ምርቱንና የሥራ ውጤቱን ከፍ እንዳያደርግ ፣ የተመረተውም በወቅቱ ተሰብስቦና በአግባቡ ተጠብቆ ለተጠቃሚው ሕዝብ እንዳይደርስ በመቀስቀስ ለአድኃሪ ዓላማቸው መሳካት በአንድ ሀገር ውስጥ ችግር እንዲባባስ ፣ በፖለቲካውም የተረጋጋ ሁኔታ እንዳይኖርና የመንግሥታዊና የሕዝባዊ ድርጅቶችን አቋምና የሥራ ቅልጥፍና በማዳከም አብዮትን ለመቀልበስ የሚፈጽሚቸው ፀረ ሕዝብ አፍራሽ ተግባሮች አሻጥር ናቸው ።

## አቅርቦትና ፍላጎት
(*Supply and Demand*)

አቅርቦትና ፍላጎት የሸቀጥ ምርት የኢኮኖሚ ፈርጆች ናቸው ። አቅርቦት ማለት ለገበያ ቀርቦ ፍላጎትን ሊያሟላ የሚችል የሸቀጦችና የአገልግሎቶች ክምችት ማለት ነው ። አቅርቦት በምርት መጠንና በመጓጓኛ ዘዴዎች መሟላት ይወሰናል ።

ፍላጐት በመግዛት ኃይል ክልል የሚወሰን ማኅበራዊ ፍላጐት ሲሆን ፣ ሸማቹ ሕዝብ ዕቃና አገልግሎት ሲፈልግ አምራች ድርጅቶች ደግሞ የማምረቻ መሥሪያዎችን ፣ ጥሬ ዕቃዎችንና የሥራ ኃይልን ይፈልጋሉ።

አቅርቦትና ፍላጎት ውስብስብ በሆነ ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት ተሳስረው በገበያ ላይ የኢኮኖሚ ግንኙነቶች ነፀብራቅ በመሆን በምርትና በፍጆታ መካከል ያለውን ተዛምዶ ይወስናሉ ። የአቅርቦትና የፍላጐት ተፅዕኖ ሸቀጦች በሚሸጡበትና በሚገዙበት ጊዜ የሚከሰት ነው ።

በአቅርቦትና በፍላጎት መካከል ያለው ግንኙነትና የእያንዳንዳቸው ጠባይ የሚወሰነው በየሥርዓቱ ማኅበሩ ተጨባጭ የኢኮኖሚ ሕጎች ነው ። በካፒታሊስት ሥርዓት በአቅርቦትና በፍላጎት መካከል ተፃራሪ የሆነ ቅራኔ አለ ። ይኸውም፣ ቅራኔ የሚመነጨው በሥርዓቱ ውስጥ በማኅበራዊ አመራረትና በግል የሃብት ክፍፍል መካከል ካለው ቅራኔ ነው ። ይህ ሁኔታ የዋጋ ውጣ ውረድን በማስከተል በምርት መጠን ላይ ተፅዕኖ ያደርጋል። እንደ አቅርቦትና እንደ ፍላጎት ወቅታዊ ግንኙነትም የሸቀጦች ዋጋ ከሸቀጦቹ እሴት ወይም (በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ እንደሚሰራው) ከምርት ዋጋ በላይ ሌላ ጊዜ ደግሞ በታች ይሆናል ። በዚህ ሁኔታ የእሴት ሕግ ግብታዊ በሆነ መንገድ የካፒታሊስት ምርትን ይቆጣጠራል ። በገበያ ውስጥ የአቅርቦትና የፍላጎት ተመጣጣኝነት የሚገኘው በዋጋ ሥርዓት አማካይነት ካፒታልና የሥራ ኃይል ከአንድ ኢኮኖሚ ዘርፍ ወደ ሌላው ብዙ ጊዜ ከዋዠቀ በኋላ ነው ።

ይሁንና በአጠቃላይ ሲታይ በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ባለው የዋጋ ንረት ፣ በሥራ አጥነትና በመግዛት ኃይል ዐቅም ማነስ አንፃር አቅርቦት በአብዛኛው ጊዜ ከፍላጎት በላይ ይሆናል ። ይህም አለመመጣጠን በየወቅቱ የሚነሣውን "የበላጥ ምርት" ቀውስ ያስከትላል ።

ሶሻሊዝም የምርት መገልገያዎች የጋራ ባለቤትነት የሰፈነበት በመሆኑ ፣ በምርትና በፍጆታ ፣ በአቅርቦትና በፍላጎት መካከል ያለውን ተመጣጣኝነት በዕቅድ ለመጠበቅ ይቻላል ። ይህ ማለት ግን አቅርቦትና ፍላጎት ተመጣጣኝ ናቸው ማለት አይደለም ። በሶሻሊዝም ውስጥ ካሉት የኢኮኖሚ ሕጎች መካከል የሰፊውን ሕዝብ እያደገ የሚሄድ ፍላጎት ማሟላት አንዱ ነው ። ከፍላጎትና ከሕዝብ ቁጥር በየጊዜው መጨመር አንፃር የአቅርቦት ጭማሪ አስፈላጊ ሲሆን የሕዝቡ የኑሮ ሁኔታ መሻሻል ደግሞ አዲስ ፍላጎትን ይፈጥራል ።

ይሁንና ይህ በዕቅድ ውስጥ ተገናዝቦ በመንግሥት የኢኮኖሚ ፖሊሲ አማካይነት በአቅርቦትና በፍላጎት መካከል ተመጣጣኝነት እንዲኖር ይደረጋል ። በሶሻሊስቱ ኢኮኖሚ የማምረት ኃይልና በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ፍላጎት መካከል ባለው አለመመጣጠን የተነሣ በአቅርቦትና በፍላጎት መካከል አለመጣጣም ሊኖር ቢችልም ይህ ሁኔታ በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ እንዳለው ወደሚፃረር ቅራኔ የሚያመራ ሳይሆን በምርት ኃይሎች ዕድገትና የሕዝቡንም ፍላጎት ከዐቅም ጋር በማስተካከል የሚፈታ ነው ።

## አቋም
*(Stand)*

አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን አምኖና ተቀብሎ የሚዋጋለት ወይም ባለመቀበል የሚቃወመው መሥመር የዚያ ግለሰብ ወይም ቡድን አቋም ይባላል ።

ሚና መለየት ፣ የተወሰነ የፖለቲካ መሥመር መያዝ ወይም መከተል ፖለቲካዊ ፣ ማኅበራዊና ወታደራዊ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አጥጋቢ የሆነ ውይይት ከተካሄደ በኋላ በብዙኀን ድምፅ አሸናፊነት ከአንድ ውሳኔ ላይ መድረስና ውሳኔውን መመሪያ አድርጎ መቀበል አቋም መውሰድ ይባላል ።

## አባዊ ሥርዓት
*(Patriarchate)*

በኢኮኖሚያዊ ፣ በማኅበራዊና በቤተሰብ ኑሮ ረገድ የወንድ የበላይነት የሰፈነበት የጥንት ማኅበረሰብ ሥርዓት ነው ።

አባዊ ሥርዓትን ያሰፈነው የጥንት ማኅበረሰብ ኢኮኖሚ እየዳበረ መምጣቱና ምርታማነቱን ከፍ ማድረጉ ነው ። ወትሮ ሴቶች ተሰማርተውባቸው የነበሩትን ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ማለትም ከብት ርባታን ፣ እጣ እሥግርትን ፣ እርሻን ፣ አደንን ወዘተ... ወንዶች እየተረከቡ ሲሄዱ ሴቶች በማጀት ተወሰኑ ። ውርስ የአባትን ዝርያ መሥመር እየቀጠለ ይሄድ ጀመር ። ሴቶች በባሎቻቸው ቤት ወይም በወንድ እማቶቻቸው አባወራነት ሥር ይኖሩ ነበር ። የጐሣው መሪ ወንድ ነበር። አንድ ወንድ ለአንድ ሴት የሚሰው የጋብቻ

መርህ ለመጀመሪያ ጊዜ ተግባራዊ የሆነው በዚህ ሥርዓት ነበር ።

በኅብረተሰብ ታሪክ ውስጥ ከመጀመሪያው እንሥቶ ሰፍኖ የቆየው ሥርዓት አባዊነት ነው እንጂ ሌላ] ዓይነት ሥርዓት ሊኖር አይችልም በማለት የሚያምኑ ብዙ ምሁራንና ፈላስፎች ነበሩ ፤ ዛሬም አሉ ። ከነዚህም ውስጥ የጥንት የግሪክ ፈላስፎች አፍላጦንና አርጣጣሊስ ነበሩ ። ነገር ግን ይህ አስተሳሰብ የተሳሳተ መሆኑን በሞርጋን ጽሑፍ ላይ ተመሥርቶ ፍሬደሪክ ኤንግልስ በትክክል አስረድቷል ።

(እማዊ ሥርዓትን ፣ የሴቶች ጥያቄን ይመለከቷል ።)

## አብርሆት
*(Enlightenment)*

አብርሀ ከሚለው ፣ የግዕዝ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም ማሳወቅ ማስረዳት ማለት ነው ።

የሳይንስን ዕውቀት ፣ የግብረገብንና የፍትህን ሐሳቦች በማሰራጨት የኅብረተሰብን ድክመቶች ለማረም የአስተሳሰብን ፣ የኑሮ ዘዴን ፣ የፖለቲካ አመለካከትን ለመቀየር ይቻላል የሚል ማኅበራዊ ፖለቲካዊ አመለካከት ነው ። የአብርሆት መሠረታዊ እምነት በኅብረተሰብ ዕድገት ውስጥ ኀሊና ወሳኝ ሚና ሊጫወት ይችላል የሚል ሐሳባዊ አመለካከት በመሆኑ ማኅበራዊ ችግሮች ከሰዎች ድንቁርናና ከዕውቀት ማነስ እንደሚመነጩ አድርጎ የሚገምት ነው ። አብራሀያን ችግሮችን ሊያስወግድ የሚችል ትምህርት ብቻ ነው የሚል አመለካከት ስለአላቸው የኢኮኖሚን ወሳኝነትና ኅብረተሰብን የሚገዙ ነባራዊ ሕጎችን ለመገንዘብ አልቻሉም ።

ፍልስፍናው የተስፋፋው በቡርዧ አብዮት ፍንዳታ አጥቢያ ሲሆን ቮልቴር ፣ ሩሶ ፣ ሞንተስኪዩ ፣ ሄርደር ፣ ቪለር ፣ ጎቴ ወዘተ ... የታወቁ የፍልስፍናው አራማጆች ነበሩ ። አብራሀያን የፊውዳልን ርዕዮተዓለም ያዳከሙ ከመሆናቸውም በላይ በቀጥታ ቤተክርስቲያንን ፣ ሃይማኖታዊ ቀኖናዎችንና ተምህሮአዊ አስተሳሰቦችን ተዋግተዋል ። ይህ ርዕዮተዓለም በአሁኑም ወቅት ማርክሳዊ ያልሆነው የምሁራን ክፍል አመለካከት ነው ።

## አብዮተኛ
*(Revlutionary)*

ለሥር ነቀል ለውጥ የቆመ ፣ መመሪያውን ማርክሲዝም ሌኒኒዝም አድርጎ ጭቆናንና ብዝበዛን በመቃወም የሠርቶ አደሩን አብዮት በቆራጥነት የሚያራምድ ፣ ራሱን ለሠርቶ አደሩ ጥቅምና ደኅንነት የሰጠ ፣ በተሰለፈበት ቦታ ሁሉ ለሠርቶ አደሩ ጥቅም የቆመ ሐቀኛ ታጋይ የሆነ ሰው አብዮተኛ ይባላል ።

(ኮሚኒስትን ይመለከቷል ።)

## አብዮታዊ ሁኔታ
*(Revolutionary Conditions)*

ለማኅበራዊ አብዮት መምጣት ወሳኝ ሊሆን የሚችል በኢኮኖሚና በፖለቲካ ቀውስ የሚገለጽ የአንድ ሥርዓተ ማኅበር አጠቃላይ ሁኔታ ነው ። ሌኒን እንዳመለከተው አብዮታዊ ሁኔታ የሚታወቅባቸው ዋና ዋና ምልክቶች የገዥ መደቦች እንደቀድሞው የበላይነታቸውን እንደያዙ መቆየት አለመቻልና ተጨቋኝ መደቦች በጥንቱ ሁኔታ ለመኖር አሻፈረኝ ማለት ናቸው ።

አብዮታዊ ሁኔታ ነባራዊና ኅሊናዊ ሁኔታዎችን ያቀፈ ነው ። ነባራዊ ሁኔታ በኢኮኖሚያዊና በማኅበራዊ ቀውስ የሚገለጽ ሲሆን የኅሊናዊ ሁኔታዎችም መሟላት ለአብዮታዊ ሁኔታ መሳካት አስፈላጊ ነው ። ማለትም አንድ አብዮት ግቡን ሊመታ የሚችለው ሁለቱም ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ነው ። ኅሊናዊ ሁኔታ በአጠቃላይ ሲታይ የሚከተሉትን ሁለት ቁምነገሮች ይይዛል ። አንደኛው ሰፊው ሕዝብ በቂ የመደብ ንቃት በማግኘት የአብዮትን አስፈላጊነት የተገነዘበና ለአብዮቱም አስፈላጊውን መሥዋዕት ለመክፈል የቆረጠና የተዘጋጀ ሆኖ መገኘት ነው ። ሁለተኛው ፖለቲካዊ ፣ ርዕዮተዓለማዊና ድርጅታዊ አመራር በመስጠት

ሰፊውን ሕዝብና አብዮታዊ ኃይሎችን አሰባስቦ በአንድነት እንዲታገሉ ለማድረግ የሚችል ፣ አስተማማኝ በሆነ ታክቲክና ስትራቴጂ በመጠቀም ዕቅዱን በተግባር የሚተረጉም የፖለቲካ ድርጅት መኖር ነው ።

(ነባራዊ ሁኔታን ፤ ኅሊናዊ ሁኔታን ይመለከቷል ።)

## አብዮታዊ ሽግግር
(*Revolutionary Transition*)

ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም (ኮሚኒዝም) ለማለፍ በሕዝባዊ አመፅና በትጥቅ ትግል የሚካሄድ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ነው ። አብዮታዊ ሽግግር ማፍረስንና መገንባትን ያጣመረ ሂደት ሲሆን ዋና ዋና ገጽታዎቹም ሠርቶ አደሩ በኃይል የፖለቲካ ሥልጣን ከያዘ በኋላ የቀድሞውን ጨቋኝ መንግሥት አውታር ማፈራረስ ፣ የማምረቻ መሣሪያዎችን የሕዝብ ማድረግ ፣ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ተግባራትን በዕቅድ ለመምራት የሚያስችል መዋቅር መዘርጋት ፣ የመደብና የብሔረሰብ ጭቆናዎችን እንዲሁም የሰው በሰው ብዝበዛን ጨርሶ ማስወገድ ፣ ሶሻሊስት ዲሞክራሲን መመሥረትና የባህል አብዮትን ማካሄድ ናቸው ።

የአብዮታዊ ሽግግር መነሻው በካፒታሊስቱና በወዝአደሩ መካከል እየከረረ የሚመጣው ተፃራሪ ቅራኔ ነው ። የካፒታሊስቱ ሥርዓት ራሱን አጠናክሮ ዕድሜውን ለማራዘም እንዲሁም የወዝአደሩን የትግል እንቅስቃሴ ለማፈን ስለሚጥር ወዝአደሩም መላውን ሰፊ ሕዝብ አስተባብሮ የካፒታሊስቱን ሥርዓት ለመገርሰስና ሶሻሊስት ኅብረተሰብ ለመገንባት በፓርቲው አማካይነት በኃይል ለመጠቀም ይገደዳል ። የአመፁ የመክረር ደረጃ የሚወሰነው የካፒታሊስቱ መደብ በሚወስደው የተቃውሞ አቋምና በሚጠቀምባቸው ታክቲኮች ዓይነት ፣ በወቅቱ ባለው የኃይል አሰላለፍ እንዲሁም በወቅቱ አጠቃላይ ተጨባጭ ሁኔታዎች ነው ። በዚህ አብዮታዊ የሽግግር ወቅት ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን መመሪያው ያደረገ የግንባር ቀደም ፓርቲ አመራር ወሳኝ ነው ።

(ሕዝባዊ አመፅን ፣ ተናሥኦትን ፣ አብዮትን ፣ ሰላማዊ ሽግግርን ይመለከቷል ።)

## አብዮታዊ ዲሞክራሲ
(*Revolutionary Democracy*)

በሠራተኛው መደብ የትግል ታሪክ የመጀመሪያው ወቅት ፣ ይህ ጽንሰ ሐሳብ ከከተማው ንዑስ ከበርቴ ፣ ከገበሬውና ከተራማጁ ምሁራን መካከል የፖለቲካ ንቃትያላቸውን ፀረ ፊውዳልና ፀረ ካፒታሊስት የሆነውን ትግል የሚደግፉትን ፣ ለዚህም የሚታገሉ ክፍሎችንና እንዲሁም የነዚሁኑ ፍላጐትና ጥቅም የሚያራምዱ ፓርቲዎችን ፣ ድርጅቶችንና ቡድኖችን የሚያጠቃልል ነበር ። በአሁኑ ታሪካዊ ወቅት ደግሞ በዕድገት ወደ ኋላ በቀሩና ካፒታሊዝም እምብዛም ባልተስፋፋባቸውና ባልተጠናከረባቸው ሀገሮች ለብሔራዊና ለማኅበራዊ አርነት የሚታገሉ ኃይሎችን በዚህም ውስጥ ገና ለጋ የሆነውንና በማደግ ላይ የሚገኘውን የሠራተኛ መደብ እንቅስቃሴም የሚያጠቃልል ነው ።

አብዮታዊ ዲሞክራሲ በረጅሙ ፀረ ፊውዳልና ፀረ ካፒታሊስት ትግል ውስጥ ለዲሞክራሲና ለማኅበራዊ ለውጥ ስፊ የትግል ታሪክና ሚና አለው ። በዚህም መሠረት በእንግሊዝ ፣ በአሜሪካ ፣ በፈረንሳይ ፣ በጀርመንና በሩሲያ ውስጥ በሠራተኛው እንቅስቃሴና በተለይም በነዚህ ሀገሮች ቡርዧ አብዮቶች ወቅት አብዮታዊ ዲሞክራቶች በራሳቸው የፖለቲካ ድርጅቶች በመሰባሰብ ጭምር ከሠርቶ አደሩ ሕዝብ ጎን ቆመው መሥዋዕትነት የተመላው ትግል አካሂደዋል ። በተለይ በሩሲያ በ19ኛው ምዕትዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ላይ እንደነ ቪ.ጂ. በሊንስኪ ፣ ቸርኒሼቭስኪ፣ ኤን. ኤ. ዶብሮሉቦቭ ፣ ኤ.አይ. ሄርዘንና ኤን.ፒ. ኦጋሬቭ የመሳሰሉት የታወቁ አብዮታዊ ዲሞክራቶች ሲሆኑ አመለካከታቸውም የገበሬ አብዮትና የተምኔታዊ ሶሻሊዝም አስተሳሰቦች ቅይጥ ነበር ። በዚህም አስተሳሰባቸው ሩሲያ ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም የምትሸጋገረው በገበሬው አብዮት አማካይነት ገባርነትን በማጥፋትና የገበሬ ኮምዩኖችን በመመሥረት እንደሚሆን ይሰብኩ ነበር ። ለዚህም "መሬትና ነፃነት" ፣ "የሕዝብ ፈቃድ" ወዘተ... የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶችን በማቋቋም ታግ

ለዋል ። ቭ. ኢ. ሌኒን እነዚህ አብዮታዊ
ዲሞክራቶች በወቅቱ ላደረጉት ትግል ከፍተኛ
ግምት በመስጠት ለሩሲያ ማኅበራዊ ዲሞክ
ራቶች ጥርጊያ ጉዳና እንዳዘጋጁ ተናግሯል።
ይህ አስተሳሰባቸውም ለማኅበራዊ ሳይንሶች፣
ለሥነ ጽሑፍና ለኪነት መዳበር አስተዋ
ጽኦ ቢያደርግም በአብዮታዊ ንድፈ ሐሳብ
ትጥቅ ጉድለትና በጠንካራ ግንባር ቀደም
ፓርቲ አመራር እጦት ምክንያት በተቀናጀ
ስትራቴጂና ታክቲክ ሕዝባዊውን ትግል አስ
ተባብረው ሊመሩና ከግብ ሊያደርሱ አልቻ
ሉም ።

ባለንበት ታሪካዊ ወቅት አያሌ የአፍሪካ፣
የእስያና የላቲን አሜሪካ ሕዝቦች ራሳቸውን
ከኢምፔሪያሊዝም ግልጽና ስውር ብዝበዛና
ጭቆና ነፃ ለማውጣት ከፍተኛ ትግል በማ
ድረግ ላይ ናቸው ። ምንም እንኳ በእነዚህ
ሀገሮች አብዛኛዎቹ ከዘመናት የኢምፔሪያ
ሊዝም ቀጥተኛ ቅኝ አገዛዝ ተላቀው የፖ
ለቲካ ነፃነታቸውን የተጐናፀፉ ቢሆንም
ከዓለም አቀፍ የካፒታሊስቱ የኢኮኖሚ ሥር
ዓት ተፅዕኖ ገና ያልተላቀቁ በመሆናቸው
ነፃነታቸው የተሟላ ሊሆን አልቻለም ። በመ
ሆኑም እነዚህ ሀገሮች ከብሔራዊ ነፃነት
ባሻገር ለማኅበራዊ ነፃነታቸው መታገል ግድ
ሆኖባቸዋል ። በዚህ መሠረት ብዙ የአፍ
ሪካ ፣ የእስያና የላቲን አሜሪካ ሀገሮች ባገኙት
የፖለቲካ ነፃነት ብቻ ሳይወሰኑ ሕዝቦቻቸውን
ከውስጥ በዝባዥ መደቦችና ዋና ተገናቸው
ከሆነው ከዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም
ምዝበራና ጭቆና አላቀው ፍትህ ፣ ነፃነት ፣
እኩልነት ፣ ሰላምና ብልጽግና ወደሰፈነበት
ኅብረተሰብ ለማሸጋገር የሞት ሽረት ትግል
በማድረግ ላይ ይገኛሉ ። ሆኖም እነዚህ ሀገ
ሮች በዕድገት እጅግ ኋላ ቀር በመሆናቸው
ሠራተኛው በፖለቲካ ንቃቱና በተደራጀ
የትግል ልምዱ ገና ተጠናክሮ ያልወጣ እንደ
መሆኑ የፖለቲካ ባህል ደረጃው እጅግ ዝቅ
ተኛ ሆኖ ይገኛል ። በዚህም ምክንያት ሠራ
ተኛው በፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግሉ እንደ ገበ
ሬው ፣ እንደተራማጅ ምሁራኑና እንደ ንዑስ
ከበርቴው ከመሳሰሉት ተራማጅና ፀረ ኢም
ፔሪያሊስት ኃይሎች ጋር በመሆን ለብሔራዊ
ነፃነት በተደረገው ፍልሚያ የበኩሉን አስተ
ዋጽኦ ቢያደርግም ቀድሞ ነቅቶና ተደራጅቶ
ታሪካዊ ሚናውን በመገንዘብ ትግሉን በግም
ባር ቀደምነት ለመምራት አልቻለም ።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ትግሉን በማስተባ
በርና በማደራጀት ግንባር ቀደም አመራር
የሰጡት በአብዛኛው ከተለያዩ መደቦችና
የኅብረተሰብ ክፍሎች የወጡት ተራማጅ ምሁ
ራን ሊሆኑ ችለዋል ። የብሔራዊ አርነት
ትግሉ በድል ካበቃና ብሔራዊ ነፃነት ከተገ
ኘም በኋላ በብዙ ሀገሮች ከነዚህ ግንባር
ቀደም አመራር ከሰጡት ኃይሎች መካከል
ትግሉን በዚሁ ለመወሰንና ከቀድሞዎቹ
ቅኝ ገዥዎች ጋር በመመሳጠር በሥልጣን
ላይ ተኮፍሰው የግል ጥቅማቸውን ብቻ ለማ
ሳደድ የተነሡና ተግባራዊ ያደረጉ ሲኖሩ ፣
በተቀሩት ሀገሮች ደግሞ አብዮታዊ ኃይሎች
የበላይነትን በመያዝ ሕዝባዊውን ትግል
ከብሔራዊ አርነት ደረጃም አልፎ በሶሻሊስት
የዕድገት ፈለግ ለማኅበራዊ ነፃነት ወደሚ
ደረግ የላቀ ትግል ለማሸጋገር ችለዋል ። በዚ
ህም ሽግግር የፖለቲካ ሥልጣን በመጨበጥ
ግንባር ቀደም ሚና የተጫወቱትና በመጫወ
ትም ላይ ያሉት ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን
ተቀብለው ተግባራዊ መመሪያቸው ያደረጉ
ቁርጠኛ ኮሚኒስቶችና አብዮታዊ ዲሞክራ
ቶች ናቸው ።

በዚህ ዓይነት በዘመናችን አብዮታዊ
ዲሞክራሲ ከፊል ካፒታሊስትና በአብዛኛው
በቅድመ ካፒታሊስት የዕድገት ደረጃ ላይ
በሚገኙ ሀገሮች ሥልጣን በመጨበጥ ፀረ
ፊውዳል ፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ካፒታ
ሊስት የሆነውን ትግል በማርክሳዊ ሌኒናዊ
ድርጅት ግንባር ቀደም መሪነት የሚያራምድ
ኃይል ነው ። ይህ ኃይል የፖለቲካ ሥልጣኑን
የሠርቶ አደሩ ሕዝብ መሣሪያ በማድረግ መሬ
ትንና ቁልፍ የማምረቻ ፣ የማከፋፈያና አገል
ግሎት ሰጪ ድርጅቶች በመንግሥት ቁጥጥር
ሥር ሆነው ለሕዝብ ጥቅም እንዲውሉ ያደር
ጋል ። በገጠርና በከተማ የአምራቾች ኅብረት
ሥራ ማኅበራትን በማስፋፋትና በማጠናከር
ለሶሻሊስት የምርት ግንኙነት መሰረት
ይታገላል ። በየደረጃው በሚወስዳቸው እርም
ጃዎችም የቀድሞውን አድኃሪ መንግሥታዊ
ቢሮክራሲ በማዳከም ለአዲስ የፖለቲካ ሥር
ዓት ግንባታ ይታገላል ። የቀድሞውን ሠራ
ዊት በአዲስ መልክ በማደራጀት ለአብዮቱ
ዓላማና ለሰፊው ሕዝብ ጥቅምና ልዕልና
የታጠቀ ሕዝባዊ መከላከያ ኃይል ይገነባል ።
በማርክሲዝም ሌኒኒዝም መርሆች ላይ በመ
መርኮዝ ሠርቶ አደሩን ሕዝብ በተራማጅና

በአብዮታዊ አስተሳሰቦች እያነፀና እያደራጀ
በትግሉ ውስጥ በንቃት በማሳተፍ ለዲሞክ
ራሲያዊ መብቱ መረጋገጥና ለአዲስ ባህል
መገንባት ሁኔታዎችን ያመቻቻል ። እንዲሁም
የብሔራዊ አርነት ንቅናቄዎች የዓለም አብዮት
ሂደት የማይነጣጠሉ አካሎች እንደመሆናቸው
ትግሉ በወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት መርህ
መሠረት የዘመናችን አብዮታዊ እንቅስቃሴ
ዎች መሪ ኃይል ከሆነው ከሶሻሊስት ሥርዓት
ጋር የቀረበና የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖረው
ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋል ። በዚህ ዓይነት
የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ሥልጣን በጠንካራ
ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ አመራር ከኅብረተ
ሰቡ አጠቃላይ ዕድገትና በዚህም ውስጥ ከሠ
ራተኛው መደብ አመራር ሚና ማደግ ጋር
ወደ ወዝአደሩ የበላይ ገዥነት በማደግ አብዮ
ቱን ቀስ በቀስ ወደ ሶሻሊስት ደረጃ ለማሸ
ጋገርና ሰው በሰው የማይበዘበዝበትን ኅብረ
ተሰብ ለመመሥረት የሚያስችል የሠርቶ አደሩ
ሕዝብ የበላይነት ማረጋገጫ መሣሪያ ይሆናል።

(ኢካፒታሊስታዊ የዕድገት ፈለግን ፥ ብሔ
ራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ፥ የብሔራዊ
አርነት እንቅስቃሴን ይመለከቷል ።)

## አብዮታዊ ጦር

*(Revolutionary Army)*

በማርክሲዝም ሌኒኒዝም አስተምህሮ
የታነፀ ፥ ለወዝአደሩ ዓላማና ተልዕኮ ፍጹም
ተገዥ የሆነ ከሠርቶ አደሩ የተውጣጣ ሠራ
ዊት ነው ።

አብዮታዊ ጦር የሀገርን ህልውናና ነፃ
ነት እንዲሁም ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በትግል
የተቀዳጃቸውን ድሎች ለመጠበቅና ለመን
ከባከብ የቆመ አብዮታዊ ኃይል ነው ። ይህ
ሠራዊት ከብዝበዛና ከጭቆና ነፃ የሆነውን
ሶሻሊስት ሥርዓት ለመገንባት የሚያስችለ
ውን ዲሞክራሲና ሰላም የሰፈነበትን ሁኔታ
ለመፍጠር ማናቸውንም መሥዋዕት ለመ
ክፈል የቆመ ነው ።

የዚህ ጦር አባላት እናት ሀገርንና አብ
ዮትን ከውስጥም ሆነ ከውጭ ጥቃት መከላ
ከል ብቻ ሳይሆን በሀገራቸው በሚካሄደው
አዲስ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ግንባታ ውስጥ
ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ ። ለዚህም ብቁ
የሚያደርጋቸው የግንባር ቀደም ፓርቲ
ወሳኝ አመራር ነው ። ፓርቲውም የሠራዊቱን
አባላት በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ርዕዮተዓ
ለም በማነፅና በዘመናዊ ወታደራዊ ሳይንስና
መሣሪያ በማስታጠቅ ለቆመለት ዓላማ ግብ
መምታት ጥራትና ብቃት ያለው ሕዝባዊ
ኃይል መሆኑን ያረጋግጣል ።

(ሕዝባዊ ሠራዊትን ይመለከቷል ።)

## አብዮት

*(Revolution)*

አበየ ከሚለው የግዕዝ ቃል የመጣ ሲሆን
ትርጉሙም አሻፈረኝ አለ ፥ እምቢ አለ
ማለት ነው ።

በአንድ ነገር ፥ ክስተት ወይም ሂደት
ውስጥ ያሉ ቅራኔዎች ተካረው ከፍተኛ
ደረጃ ላይ ሲደርሱ የሚፈጠር መሠረታዊ
ለውጥ ፥ አዲስ ከፍተኛና የተሻለ ነገር ፥ ክስ
ተትና ሂደት ወይም አስተሳሰብና ዕውቀት
የሚከሰትበት የዓይነት ለውጥ አብዮት ይባ
ላል ። አብዮት ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚደረግ
የዓይነት ለውጥ እንደመሆኑ በአንድ በተወ
ሰነ ክስተት ወይም ሂደት ውስጥ ብቻ ሊታይ
ይችላል ። ለምሳሌ የኢንዱስትሪ አብዮት ፥
የፍልስፍና አብዮት ፥ የባህል አብዮት ፥ የፖለ
ቲካ አብዮት በማለት በተጠቀሱት ዘርፎች
የታዩትን መሠረታዊ ለውጦች ለመለየት
ይቻላል ። ሆኖም እነዚህ ለውጦች በሌሎች
ዘርፎች ላይ ተፅዕኖ እንደሚያደርጉ ቢታወ
ቅም የተሟላ ውጤት ለማስገኘት የሚችሉት
ግን በኅብረተሰቡ ውስጥ ጠቅላላና መሠረታዊ
ለውጥ ሲኖር ብቻ ነው ።

ስለሆነም በአንድ ኅብረተሰብ ፖለቲካዊ፥
ኢኮኖሚያዊ ፥ ማኅበራዊ ፥ ባህላዊ ወዘተ...
ዘርፎች ውስጥ የሚታየው መሠረታዊ ለውጥ
የኅብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ግን
ኙነቶችና የመደቦችን ዓይነት የሚለውጥ
በመሆኑ ማኅበራዊ አብዮት ይባላል ።

አብዮት መሠረታዊ የዓይነት ለውጥ
እንደመሆኑ አዲሱ በአሮጌው ውስጥ ተጸንሶ

አሮጌውንም በማፈራረስ ከርሱም እንዳንድ ደጎና ጎኖችን ወርሶ ለዕድገቱ እንደሚያመቻቸው አድርጐ አሻሽሎ ፣ አደራጅቶና አቀናጅቶ የራሱ በማድረግ ይጠቀምባቸዋል ። ይህም የቡርዧ ምሁራን እንደሚሉት አብዮት የዕድገት ሂደት የሚቋረጥበት ፣ በሰላም ፈንታ ረብሻና ሁካታ የሚሰፍንበት ሳይሆን ዕድገት በአሮጌው ላይ ተመሥርቶ ይበልጥ የሚሻሻልበት ፣ ሂደቱም የሚቀጥልበትና የሚፋጠንበት እንደሆነ ያሳያል ። አብዮት ይመጣ ዘንድ የተወሰኑ ሁኔታዎች መሟላት ያለባቸው መሆኑ ደግሞ አብዮት በሕግ የሚገዛ እንጂ በዘፈቀደ የሚፈጠር ክስተት እንዳልሆነ የሚያሳይ ነው ።

(የዓይነት ለውጥን ፣ ፖለቲካዊ አብዮትን ፣ የባህል አብዮትን ፣ ነባራዊ ሁኔታን ፣ ኅሊናዊ ሁኔታን ይመለከቷል ።)

## አቶሚዝም
*(Atomism)*

የአቶሚዝም ታሪክ ከቁስአካላዊ ፍልስፍና ታሪክ ጋር በቅርብ የተሳሰረ ነው ። ምክንያቱም ቅድመ ማርክሳዊ ቁስአካላውያን ንጽረተዓለማቸውን የመሠረቱት በአቶሚዝም ላይ ነው ። አቶም ከግሪክ የመጣ ቃል ሲሆን ፍችውም የማይሰነጠቅ ፣ የማይከፋፈል ማለት ነው ። በአቶማውያን አመለካከት አቶም የቁስ አካል ጥንተ ነገር ነው ። በመሆኑም አቶሞች የማይከፋፈሉና አነስተኛ ከመሆናቸው የተነሣ ለሕዋሳት የማይገለጹ ነባራዊ ጥንተ ነገሮች ናቸው ። የሁሉ ነገር ጥንተ ነገር በመሆናቸው አቶሞች እርስ በርሳቸው በዓይነት አይለዩም ። በሕዋሳት ልንደርስባቸው የምንችላቸው ግዙፍ ነገሮች ሁሉ የአቶሞች ግጥምጥሞሽ ውጤት ናቸው ። ነገሮች ሁሉ ከአቶም የተሠሩ በመሆናቸው ዓለም አንድ ነው ።

ነገሮች በዓይነት የሚለዩት ማለት የተለያዩ ሕውስታዎች የሚሰጡንና በጠባይና በባሕርይ የሚለያዩት በሚያቅፏቸው አቶሞች ብዛትና አደረጃጀት ነው ። ይህም ማለት በአቶማውያን አመለካከት የዓይነት ልዩነት የሚያንፀባርቀው የመጠንን ልዩነት ነው ። እንደአቶማውያን አስተሳሰብ ባዶ እንደአቶም በነባራዊነት የሚኖር ነው ። ይህን ለማለት ያበቃቸው የእንቅስቃሴ ጉዳይ ነው ። አቶሞች ሊለያዩ ወይም ሊዋሀዱ የሚችሉት መንቀሳቀስ ሲችሉ ነው ። እንቅስቃሴያቸው ደግሞ ሊደረግ የሚችለው ባዶ በነባራዊነት ሲኖር ብቻ ነው ።

ለአቶማውያን ነባራዊው ወይም እውን የሆነው ዓለም የአቶሞች ዓለም በመሆኑ በሕውስታ የምናስተውለው ዓይነታዊ ዓለም ኅሊናዊ ነው ። ይህ ማለት ዓለም ታዋቂ አይደለችም ማለት ሳይሆን ነባራዊና ትክክለኛ ዕውቀት ሊኖረን የሚችለው ከሕውስታዊ ዕውቀት አልፈን ክምክኑያዊ ግንዛቤ ማለት ከአቶሞች ግንዛቤ ላይ ስንደርስ ነው ።

አቶማውያን ከጥንት ጀምሮ ያዘነበሉት ወደ ተናክአታዊ አመለካከት ነው ። ቁስአካላውያን እንደመሆናቸው ፣ ተናክአታዊ አመለካከት በመያዝ ዓለም በሐሳብና በሥነ ግባዊ አሠራር ተፈጠረች የሚለውን የሐሳባውያን አቋም ለመዋጋት ሞክረዋል ። አቶሞች የሚገናኙትና የተለያዩ ነገሮችን የሚፈጥሩት በግብ በመመራት ሳይሆን በተናክአታዊ ኃይል ብቻ ነው ፤ በመሆኑም ማንኛውም ነገር የሚከሰተው በፈቃድ ሳይሆን በግዴታ ነው በሚለው አመለካከታቸው አቶማውያን እምልክትን ፣ ሃይማኖትንና ሐሳባዊነትን ተዋግተዋል ።

ተናክአታዊ አመለካከታቸው ቁስአካላዊነታቸውን ያረጋገጠ ቢሆንም የድክመታቸው ዋናው ምንጭም ነበር ። በተለይም ተናክአታዊ እንቅስቃሴ ጭፍን ሂደት በመሆኑ የውስብስብ ነገሮችን አመጣጥ ለማስረዳት ባለመቻሉ ከአጋጣሚ የሚገኝ እንደሆነ አድርገው ለማቅረብ ተገደዋል ። በተጨማሪም የማይከፈል ነው ብለው ያቀረቡት አቶም በሳይንሳዊ ምርምር እራሱ ብዙ ነገሮችን (ፕሮቶን ፣ ኤሌክትሮን ወዘተ...) ያቀፈ ሆኖ መገኘቱ ከቁስአካል ጥንተ ነገር ላይ ደረስን የሚለው አመለካከታቸው ውድቅ ሆኗል ።

(ተናክአታዊ ቁስአካልነትን ፣ ሥነ ግብን ፣ ዲሞቅሪጦስን ይመለከቷል ።)

## አናርኮ ሲንዲካሊዝም
*(Anarcho-syndicalism)*

በአጠቃላይ የፖለቲካ ትግልን የማይቀበል ፣ በሠራተኞች ንቅናቄ ውስጥ የሠራተኛ ማኅበርን እንደብቸኛ ድርጅት አድርጐ የሚመለከት ፣ የሥራ ማቆም አድማን ለሠራተኛው የሚበጅ ብቸኛ የትግል ስልት አድ

ርጕ የሚቆጥር ፥ ከወዝአደሩ የበላይገዥነትና ከኮሚኒዝም ጋር ተፃራሪ የሆነ የቡርዧ ፈለግ ነው ። አናርኮ ሲንዲካሊስቶች ሠራተኛው ሥልጣን ሳይዝ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚሠራባቸውን ፋብሪካዎች ከነቅ ርንጫፎቻቸው የራሱ በማድረግ አካባቢውን መምራት አለበት ብለው የሚሟገቱና ለሶሻ ሊዝም ግንባታ የግንባር ቀደም ፓርቲ አመ ራር እንደማያስፈልግ የሚሰብኩ ናቸው ።

አናርኮ ሲንዲካሊስቶች የፐሩዶኒዝምና የበኩኒኒዝም አመለካከት ያላቸውና በተለይም በፈረንሳይ፥በስፓኝ፥በኢጣሊያ፥በፖርቱጋልና ኋላም እንደ ቺሊ ፥ እንደ አርጀንቲናና እንደ ሜክሲኮ በመሰሰሉት ሀገሮች በሠራተኛው ውስጥ ከፍተኛ ተደማጭነት ለማግኘት የበቁ ናቸው ። በነዚህ ሀገሮች ለአናርኮ ሲንዲካሊ ዝም መጠናከርና መስፋፋት ምክንያት ከሆኑት ሁኔታዎች መካከል የኢንዱስትሪ ኋላቀርነትና የትናንሽ የእጅ ጥበብ ሥራዎች በብዛት መገ ኘት ፥ የመምረጥና የመመረጥ መብት እጅግ ውሱን መሆን ፥ በሥልጣን መባለግ ፥ የማኅ በራዊ ዲሞክራሲ እድርባይነት እንዲሁም የካቶሊክ ቤተክህነትና የፊውዳሊዝም የተቀነ ባበረ አፈናና ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ዋነኞቹ ናቸው ።

አናርኮ ሲንዲካሊስቶች የአዲሱ ኅብረተ ሰብ እንቀሳቃሽ ፥ አምራችና አከፋፋይ ኃይል የሠራተኛው ማኅበራት ናቸው የሚለውን ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ በቆራጥነት ታግለዋል ። ነገር ግን በዚህ ፈለግ በማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ አመራር ለሚገነባ ሶሻሊስት ኅብረተሰብ ቀርቶ ለቡርዧው ዲሞክራሲ የሚካሄደውን የተቀነባበረ ትግል እንኳ ለመቀበል ዝግጁ አልነበሩም ። የታወቀው ፈረንሳዊ አናርኮ ሲንዲካሊስት ፈርናንድ ፐሎቲየር የፈረንሳይ ሠራተኞች ኮንፌደሬ ሽን በሚል አጠቃላይ የሠራተኞች ማኅበር አማካይነት ይህንኑ ዓላማ ተግባራዊ ለማድ ረግ ተነሥቶ ሳይሳካለት ቀርቷል ። በኢጣሊ ያና በስፓኝ የአናርኮ ሲንዲካሊዝም አዝማ ሚያ ይህንኑ ፈለግ የተከተለ ነበር ።

ማርክስ የአናርኮ ሲንዲካሊስቶችን ቆራጥ ባሕርይና የትግል ስሜት ቢያደን ቅም ከፊታቸው ያለውን ትንሹን ሥራ ሳያ ከናውኑ ትልቁን የሚያልሙ ግብዞች ናቸው በማለት ነቅፎአቸዋል ።

## አናክሲማንደር (የማሌቱሱ)

*(Anaximander of Miletus)*

ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ610 — 546 የነበረ ጥንታዊ የግሪክ ቁስአካላዊና የግብ ታዊ ዲያሌክቲክስ አራማጅ ነው ።

ተፈጥሮን በሚመለከት ያዘጋጀው ጽሑፍ በግሪክ የመጀመሪያው የፍልስፍና ሥራ ሲሆን ዓለሞች ፥ ነገሮች ወዘተ... ሁሉ የመጡት ወይም የተገኙት ወሰንና ባሕርይ አልባ ከሆነ ከአንድ አፔሮን ከሚባል ነገር ነው ። ከዚህ ከአፔሮን የሚመነጩት ነገሮች በእንቅስቃሴ አማካይነት ከሱ በመነጠል ለተወሰነ ጊዜ ግላዊ ባሕርይና ውሱን ህል ውና ያገኛሉ ፤ እንደገናም ተመልሰው ወደ አፔሮኑ ይጠቃለላሉ ። ይህም ዑደት ዐቢይ የተፈጥሮ ሕግ ነው ይላል ።

መሬት የዩኒቨርስ እምብርት ናት ፤ የፀ ሐይ ፥ የጨረቃና የከዋክብት ቀለበቶች ከበ ዋታል የሚል የሥነ ህዋ (ኮስሞሎጂ) ንድፈ ሐሳብ አቀነባብሯል ።

ሰው እንደማናቸውም እንስሳ ከአሣ የመጣ ነው የሚለውን የእዝጋሚ ለውጥ ንድፈ ሐሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ ያመነጨውም ይኸው ፈላስፋ ነው ።

አናክሲማንደር ቁስአካላዊ ፈላስፋ ነው ቢባልም ዓለምን ወሰንና ባሕርይ ከሌለው ማለትም ሊታወቅ ከማይችል ነገር ትመነጫ ለች ማለቱ የዓለምን ምንጭ ምሥጢራዊ ስለሚያደርግ የሐሳባዊነት አዝማሚያ ይታይ በታል ።

## አናክሲሚኒስ (የማሌቱሱ)

*(Anaximenes of Miletus)*

ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ588 — 525 የኖረ ጥንታዊ የግሪክ ቁስአካላዊ ፈላስፋና የግብታዊ ዲያሌክቲክስ አራማጅ ነው ።

ነገሮች ሁሉ የመጀመሪያ ከሆነው ከአ የር ይገኛሉ ፥ እንደገናም ወደዚያው ይመለ ሳሉ ፥ አየር ከ—እስከ የሌለው ዘለዓለማዊና ተንቀሳቃሽ ነው ፤ በአንድነት ሲከማችና ሲሰበ ሰብ በመጀመሪያ ደመና ይሆናል ፤ ከዚያ

ወደ ውሃ ይለወጣል ፣ በመጨረሻም ወደ አፈርና ድንጋይ ይቀየራል ፣ ሲረቅ ደግሞ እሳት ይሆናል ። ከዋክብት እሳት ናቸው ፣ ይሁን እንጂ እሩቅ ስለሆኑ ሙቀታቸው አይሰማንም ። አየር የዓለማት ሁሉ ነፍስና መሠረተ ነገር ነው የሚል አጠቃላይ ንድፈ ሐሳብ ቀምሯል ። ይህ ንድፈ ሐሳብ የቁስአካልን ቀዳማዊነትና ቁስአካልም በማያቋርጥ ዕድገትና ቅስቃሴ ላይ ያለ ስለመሆኑ አናክሲሜነስ እንደተቀበለ ያሳያል ።

የዓለም ምንጭ አየር ነው በማለት ሊታወቅ ከሚችል ነገር መነሣቱ ቁስአካላዊ ያስኘዋል ፣ ሆኖም የመጀመሪያው ቁስአካል አየር ነው ማለቱ ስለቁስአካል የነበረው ግንዛቤ ጮርቃ መሆኑን ያመለክታል ፣ ምክን ያቱም አየር ራሱ የተወሰነ የቁስአካል ውጤት እንጂ የመጀመሪያው የዓለም ምንጭ አይደለምና ።

## አንብሮ
(*Thesis*)

አንድ ሰው ለሰዎች በማቅረብ በክርክር የሚደግፈው ሐሳብ አንብሮ ይባላል ። አንብሮ ክርክር የሚያስነሣ በመሆኑ የመነሻነት ፍች አለው ። ክርክር መፍጠሩ የሚኖረው ውጤት የመነሻው ሐሳብ መሻሩና በተቃርኖው መተካቱ ነው ። አንብሮ ይህን ከላይ የተጠቀሰውን ፍች ያገኘው በተለይ በዲያሌክቲካዊ አስተሳሰብ ውስጥ ነው ። በዲያሌክቲካዊ አመለካከት አንብሮ የዕድገት መነሻ ማለት ሲሆን የዕድገት ሕግ በሚጠይቀው መሠረት አንብሮ ተሽሮ ወደ ተቃርኖው ይለወጣል ። ለምሳሌ ጥንታዊ ቁስአካልነት አንብሮ ሲሆን የዕድገት ሕግን በመከተል በሐሳባዊነት ይሻራል ማለትም ወደተቃርኖው ይለወጣል ።

(ተቃርኖን ፣ አስተፃምሮን ፣ የዲያሌክቲክስ ሕግን ይመለከቷል ።)

## እንደበተኛነት
(*Sophism*)

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ5ኛው ምዕት ዓመት በጥንታዊት ግሪክ ውስጥ እራሳቸውን ጥበበኛ ፣ ዐዋቂ በማለት የሚጠሩ ፣ ከተማ ለከተማ በመዘዋወር የሀብታም ቤተሰብ ወጣት ልጆችን ጥበብ እናስተምራችሁ እያሉ ክፍያ የሚጠይቁ ፣ የተዘዋዋሪ አስተማሪዎችን መከሰትና የነሱንም አጠቃላይ አቋምና አመለካከት የሚገልጽ ጽንሰ ሐሳብ ነው ። ከእንደበታውያን መካከል ስማቸው የገነነው ፕሮታጐረስ ፣ ጎርጂየስ ፣ ትራዚማክስ በመባል የታወቁት ነበሩ ።

የእንደበታውያን ፍልስፍና በአጠቃላይ መንፈሱ የሚያንፀባርቀው ጠርጣሪነትንና አንፃራዊነትን ነበር ። እንደበታውያን በዚህ ፍልስፍና በተለይ የሚጠቀሙት ልማዳዊ እምነቶችን ፣ አመለካከቶችንና ፋይዳዎችን ለማንቋሸሽ ነበር ። የሚሰጡት ትምህርት ጠቃሚ ነው የሚሉትም ሰዎችን ከልማዳዊና ኋላቀር ከሆኑ አስተሳሰቦች ነፃ ያደርጋል በማለት ነበር ። በአንፃራዊነታቸውም ሁለንታዊ ወይም ነባራዊ የሆነ እውነት የለም በማለት ያስተምሩ ነበር ። በነሱ አባባል እውነት ፣ ሰናይ ፣ ትክክል ስንል ለግለሰቡ ይጠቅማል ከማለት በስተቀር ሌላ ሁለንታዊ ፍች ልንሰጥ አይገባንም ። በአንፃሩም ስሕተት ፣ ጥፋት የምንላቸው ለግለሰቡ ጎጂ የሆኑትን ነገሮች ነው ። በራሱ ሰናይ ፣ እውነት ፣ ትክክል የሆነ ነገር ባለመኖሩ ጥበብ ማለት የራስን ጥቅም ለይቶ በማወቅ ሰዎችን በማሳመንና በነሱም በመጠቀም በኅብረተሰቡ ውስጥ አሸናፊና የበላይ እንዲሆን ማድረግ መቻል ማለት ነው ። ለዚህም ዓላማ ዋናው መሣሪያ የአንደበተርቱዕነትና የክርክር ዘዴ ችሎታ ነው ። ማራኪ የሆነ የአነጋገር ስልት በማወቅና በክርክር ውስጥ በቃላት በመጫወት ወይም ተከራካሪውን ቅራኔ ውስጥ በመክተት ወይም ደግሞ ፍች የሌለው ነገር ግን ውስብስብ የሆነ ረጅም ገለጻ በመስጠት የራስን ጉዳይና ጥቅም አሸናፊ ማድረግ የእንደበታውያን ትምህርት ዋና ግብ ነበር ። የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝና በፍርድ ቤት አሸናፊ ለመሆን ትምህርቱ ተወዳዳሪ የለውም በማለት እራሳቸውን ያዋድዱም ነበር ።

የእንደበተኛነትን መከሰት ምክንያት ለመረዳት የምንችለው የነበረውን ማኅበራዊ ሁኔታ ስንመለከት ነው ። ጊዜው የሚያሳየው የግሪክ ጥንታዊ የመኳንንት ዘር ኃይል መዳከምንና በንግድ አማካይነት ሀብት ያከማቹና ሥልጣን በመያዝ አዲስ መኳንንት ለመሆን የሚታገል ክፍል መነሣቱን ነበር ። ይህ የሥር

ዓት ቀውስ ያስከተለው የሥልጣን ሽሚያና የአመለካከት ግጭት ለአንደበታውያን መከሰት አመቺ ሆኗል ። በተለይም የመኳንንቱ ፍጹማዊ አገዛዝ መዳከምና በግሪክ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መተካት የፖለቲካ አመራር በምርጫ እንዲሰየም በማድረጉ መራጩን ሕዝብ ለመማረክ የአንደበት ችሎታ ተፈላጊ ሊሆን ችሏል ። በሌላ በኩል በንግድ የበለጸገውና ለሥልጣን የሚፎካከረው አዲሱ ክፍል የጥንት መኳንንትን ርዕዮተ ዓለማዊ የበላይነት ለመስበር የነሱን አመለካከትና ማኅበራዊ ፋይዳዎችን ማንቋሸሽ ስለ ነበረበት የአንደበታውያን አንፃራዊነትና ጠርጣሪነት ለዚህ ዓላማ ጠቃሚ ሆኖ ተገኝቷል ።

## አንደኛው ኢንተርናሽናል
(*First International*)

የወዝአደሮች ዓለም አቀፋዊ የትግል ድርጅት መጠሪያ ነው ። አንደኛው ኢንተርናሽናል በመስከረም 1864 ለንደን ከተማ ተመሠረተ ። መሥራቾቹ በካርል ማርክስና በፍሬደሪክ ኤንግልስ አነሣሽነትና መሪነት የእንግሊዝ ፣ የፈረንሳይ ፣ የጀርመን ፣ የፖላንድ ፣ የኢጣልያና የሌሎችም ሀገሮች የወዝአደር መሪዎችና ታጋይ ኮሚኒስቶች ናቸው ።

የዚህ ዓለም አቀፋዊ የወዝአደር ድርጅት ዋና ዓላማ ጭቆናንና ብዝበዛን አጥፍቶ በእኩልነት ፣ በነፃነትና በብልጽግና ላይ የተመሠረተ ዓለም አቀፋዊ መደብ አልባ ኅብረተሰብ መመሥረት ነው ።

የአንደኛው ኢንተርናሽናል ዋና ጽሕፈት ቤት ለንደን ሆኖ በአውሮፓና በሌሎችም ሀገሮች ከተሞች ቅርንጫፎችና ንዑስ ማዕከሎች ነበሩት ።

በየሀገሩና በየስፍራው የሚካሄደውን የወዝአደሩን ትግል ከዋና ጽሕፈት ቤቱ ሆኖ ስትራቴጂና ታክቲክ በመቀየስ አስተባብሮና አቀነባብሮ የሚመራው የኢንተርናሽናሉ ጠቅላይ ምክር ቤት (ጄኔራል ካውንስል) ሲሆን በየጊዜውና በየቦታው ለሚቀጣጠሉት ትግሎች መመሪያ ፣ ምክር ፣ ቁሳዊ ዕርዳታና የሞራል ድጋፍ ይሰጥና ያሰባስብ ነበር ።

በኢንተርናሽናሉ መሪነት የወዝአደሩ ትግል ከማናቸውም ጊዜ የበለጠ ተጠናክሮ ነበር ። የሥራ ሰዓትን በማስቀነስ ፣ ምንዳን በማሻሻልና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን በማስከበር አያሌ ድሎች ተገኝተዋል።

አንደኛው ኢንተርናሽናል አንደ አንድ ግንባር ሆኖ ከቡርዧውና ከአድኃሪ መደቦች ጋር ካደረገው መራራ ትግል ባሻገር በሶሻሊዝምና በፀረ ቡርዧ ካባ ውስጥ ተሰግስገው ከነበሩት ሥርዓት አልበኞች (ፕሩዶኒስቶች ፣ ብላንኪስቶች፣ ባኩኒኒስቶች) ከቀኝና ከ"ግራ" አድርባዮችና ከጀብደኞች ጋር ውስብስብ የርዕዮተዓለም ትግል አካሂዷል ። ከዚህም ትግል ውስጥ ማርክሲዝም ተጠናክሮ በአሸናፊነት ወጥቶአል ።

ኢንተርናሽናሉ ያካሄደው መራራ ትግል በፓሪስ ኮሚዩን በ1871 ከፍተኛ ደረጃ ላይ በመድረስ ተከስቷል ። ከኮሚዩኑ ሽንፈት በኋላ የአውሮፓ አድኃሪ ገዥ መደቦች በኢንተርናሽናሉ ላይ ከባድ ጦርነት አውጀው በአባላቱ ላይ ስደት ፣ እሥራትና ግድያ በማፋፋማቸው ፣ በዚህም አውሮፓ ውስጥ ተግባሩን ሊያከናውን ባለመቻሉ ከ1872 በኋላ ዋና ጽሕፈት ቤቱን ወደ ኒውዮርክ አዛውሮ እስከ 1876 ከቆየ በኋላ በገጠመው የአድኅሮት ትግል ፈርሷል ።

## አንደኛ ደረጃ ቅራኔ
(*Primary Contradiction*)

ቅራኔዎች በዓይነትና በደረጃ የሚለያዩ እንደመሆናቸው በአንድ ወቅት አንደኛው ቀዳሚ ሆኖና ተካርሮ ሲገኝ ሌላው በሁለተኛ ደረጃ ቀዝቀዝ ብሎና ለጊዜውም ቢሆን ተቻችሎ ሊገኝ ይችላል ። በዚህ መሠረት አንደኛ ወይም ዋንኛ ቅራኔ የሚባለው የዚሁ ቅራኔ መኖርና የዕድገቱም ሂደት ሌሎች ቅራኔዎች የሚገኙበትን ሁኔታ ፣ ግንኙነታቸውንና ዕድገታቸውን የሚወስን ሆኖ መሪ ሚና ሲጫወት ነው ። በትግል ሂደት ውስጥ በአንድ ወቅት ይህን ዓይነቱን ወሳኝ ሚና ለመጫወት የሚችለው ቅራኔ አንደኛ ደረጃ ቅራኔ ይባላል ።

## አንዳዊነት
(*Monism*)

የማንኛውም ነገር ምንጭ አንድ ነው የሚል የፍልስፍና ትምህርት ነው ። በዚህ የፍልስፍና ትምህርት ቁስአካላውያን ሆኑ ሐሳባውያን የየራሳቸው የአንዳዊነት አቋም አላቸው ። ከዚህ የተነሣ ቁስአካላውያን ቁስአካልን የዓለም መሠረት ነው ሲሉ ሐሳባውያን ደግሞ በበኩላቸው መንፈስን ወይም ሐሳብን የዓለም መሠረት ያደርጋሉ ። ይሁንና ሳይንሳዊ የሆነው የአንዳዊነት ፍልስፍና ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ነው ። ይህም ፍልስፍና ዓለም በተፈጥሮዋ ቁስአካል እንደሆነችና ማንኛውም በዓለም ውስጥ የሚገኝ ክስተት ሁሉ ተንቀሳቃሽ እንዲሁም ልዩ ልዩ የቁስአካል እንቅስቃሴ ቅርፅ እንደሆነ አድርጐ የሚወስድ ፍልስፍና ነው ።

(ሁለታዊነትን ይመለከቷል ።)

## አንዱና ብዙው
*(The One and the Multiple)*

የዓለም ምንጭና በዓለም ውስጥ ያሉ ነገሮች ከምንጩ ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚገልጹ ማለትም የዓለምን አንድነትና ልዩነት የሚያንፀባርቁ የፍልስፍና ፈርጆች ናቸው።

ነገሮች በሙሉ የወል ከሆነ አንድ ምንጭ የተገኙ ናቸው የሚለው አመለካከት ከፍልስፍና ጋር አብሮ የተጸነሰ ነው ። ለልባዊ ነገሮች በሙሉ በቅርፅ ፣ በዓይነት ፣ በቁመት ፣ በጠባይ ወዘተ . . . የተለያዩ ቢመስሉም ዓለም የሚለው ጽንስ ሐሳብ ፍቾ የሚኖረው የነገሮች ምንጭ አንድ ሲሆን ነው ። አንዱ ብዙውን እንዴት አመነጨ ወይም ወደ ብዙ እንዴት ተቀየረ የሚለው ጥያቄ የሚወስደን ወደ ቅስቃሴ ነው ። አንዱ ብዙ ሆነ ስንል ተራባ ፣ ልዩ ልዩ ሜልኮች ያዘ ማለታችን በመሆኑ ይህ ሊሆን የሚችለው በቅስቃሴና በለውጥ አማካይነት ነው ።

ሐሳባውያን ስለ አንዱና ስለብዙው ግንኙነት ሲናገሩ ከሚፋለስ አመለካከት ላይ ይወድቃሉ ። ምክንያቱም ለነሱ የሁሉ ነገር ምንጭ ሐሳብ በመሆኑና ቁስአካልም ከሐሳብ የተለየ ነው ስለሚሉ በዚህ በሁለታዊነት አቋማቸው የተነሣ የዓለምን አንድነት በትክክል ሊገነዘቡ አይችሉም ። ለጥያቄው የሚሰጡት መልስ የዓለምን መፈጠር በመሆኑ ፈጣሪውንና ተፈጣሪውን በሁለት በተለያዩ ማለትም ተፈጥሮአዊና ዲበ ተፈጥሮአዊ በሆኑ ዓለሞች ውስጥ ለማስቀመጥ ተገደዋል ።

የሁለቱን ግንኙነት በትክክል ሊያጤን የሚችለው የዕድገትን እውንነት የተቀበለው ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ነው ። በዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት አመለካከት የሁሉም ነገር ምንጭ ቁስአካል ሲሆን ቁስአካልም በማያቋርጥ ቅስቃሴ ውስጥ ይገኛል ። ይህም ማለት አንዱ በማያቋርጥ ሁኔታ ወደ ብዙነትና ወደ ልዩነት ይቀየራል ማለት ነው ። የዓለም ቁሳዊ መሆን የአንድነቱ መሠረት ነው ። የቁስአካል የዕድገት ቅስቃሴ ብዙነትን ያስከትላል ፤ ብዙነትም በደረጃ ወደ ልዩነት ይቀየራል ። አንዱ ነገር ከሌላው ነገር ዕድገት የመነጨ በመሆኑ ዓለምና በውስጡ ያሉ ነገሮች የተፈጠሩ አይደሉም ። በነገሮች መካከል ያለው ይህ የዕድገት ሰንሰለት የአንድነታቸውና የልዩነታቸው መሠረት ነው ። የዓይነት ልዩነት የሚገልጸው ነገሮች በዕድገት ደረጃ ውስጥ የያዙትን ቦታ ሲሆን ይህም ቁስአካል በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች አንፃር መዋቀሩን የሚያስረዳ ነው።

(የቅስቃሴ ቅርፆችን ይመለከቷል ።)

## አንጃ
(*Faction*)

በአንድ ማዕከል ከሚመራ አካል ውስጥ አንድነትን ለማናጋት ራሱን የሚለይ ቡድን አንጃ ይባላል ። አንጃ በኮሚኒስት ፓርቲው ውስጥ የመሥመር ልዩነት ሲከሰት የሚፈጠር የአፈንጋጮች ወይም የከፋፋዮች ቡድን ሲሆን ህልውናውም ለፓርቲው አንድነት አደገኛ ነው ። የአንጃ መኖር ማለት በፓርቲው ውስጥ ከአንድ በላይ ማዕከል እንዲኖር ትግል የሚካሄድ መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን ይህ ደግሞ በፓርቲው ውስጥ የጋራ ዓላማና አንድነት አለመኖርን ያሳያል ። በፓርቲው ውስጥ የጋራ ማዕከልና የዓላማ አንድነት መታጣት ርዕዮተዓለማዊና ድርጅታዊ አንድነትን የሚያፋልስና የፓርቲውን ህልውና የሚነካ ነው ።

በፓርቲው ውስጥ የጋራ ማዕከልና የዓላማ አንድነት መኖር ማለት የሐሳብን ግጭት ያስቀራል ማለት አይደለም ። እንዲያውም ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርሀ የሚካሄድ ጊዜና የሐሳብ ፍጭት ለፓርቲው ጥራትንና ጥንካሬን የሚያስገኝ መሆኑ ይታመንበታል ። ይህም ሲሆን ሐሳቦች ተፋጭተው ውሳኔ ላይ ከተደረሰ በኋላ ግን የፓርቲው አንድነትና ጠንካራ ዲሲፕሊን መጠበቅ የሚያጠያይቅ በመሆኑ የፓርቲው አባላት በዓላማና በድርጊት አንድነት ይተሳሰራሉ ። የተላለፈውንም ውሳኔ በሙሉ ልባቸውና ኃይላቸው ከሥራ ላይ ያውላሉ ። በጋራ የተደረሰበትን ውሳኔ ተግባራዊ አለማድረግና ተቃዋሚ ቡድኖችን መፍጠር ግን አንጃኝነት ነው ።

(ፓርቲን ፣ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን ይመለከቷል ።)

## እንገብጋቢ ጥያቄ
*(Burning Issue)*

በአንድ ወቅት ደጋፊዎቹንና ተቃዋሚዎቹን እጅግ የሚያከራክር ከፍተኛ ወቅታዊነትና ወሳኝነት ያለው ጉዳይ ነው ። ጥያቄው ኢኮኖሚያዊ ፣ በሀላዊ ፣ ፖለቲካዊ ወይም ማኅበራዊ ሊሆን ይችላል ። ጥያቄውን እንገብጋቢ ሊያደርገው የሚችለው ወቅታዊነቱ ብቻ ሳይሆን የልዩ ልዩ መደቦችንና የኅብረተሰብ ክፍሎችን ስሜት ለመጥቀምም ሆነ ለመጉዳት የሚችል በመሆኑም ጭምር ነው ። ለምሳሌ ለአንድ አብዮት በአንድ ወቅት የፖለቲካ ሥልጣን ፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ የመሬት ፣ የመከላከያና የደኅንነት ወዘተ… ጉዳዮች ወቅታዊና ወሳኝ ሊሆኑ ይችላሉ ። እንደ ወቅቱ የመደብ ትግልና አጠቃላይ ሁኔታ እያንዳንዱ ጉዳይ ለአብዮቱ ወደፊት መራመድ ፣ መጐተት ወይም መቀልበስ ምክንያት ሊሆን ወይም አስተዋጽኦ ሊያደርግ ስለሚችል ወሳኝነት ይኖረዋል ።

## አንፃራዊ ትረፈ እሴት
**(*Relative Surplus Value*)**

የወዝአደሩ የቀን የሥራ ሰዓት እንዳለ ሆኖ አስፈላጊ የሥራ ጊዜን በመቀነስ የሚፈጠር ትረፈ እሴት ነው ። የወዝአደሩ የትምህርትና የሙያ ደረጃ ሲያድግና ቴክኖሎጂም ሲዳብር ምርታማነቱም ያድጋል ። የሠራተኛው ምርታማነት ማደግም አስፈላጊ የሥራ ጊዜ እንዲቀንስ ያደርጋል ። ለምሳሌ የቀኑ የሥራ ሰዓት ስምንት ሰዓት ሆኖ የመጀመሪያው 4 ሰዓት አስፈላጊ የሥራ ጊዜ ፣ ቀሪው 4 ሰዓት ደግሞ ትርፍ የሥራ ጊዜ ነበር እንበል ፤ ኋላ ግን የሥራ ምርታማነት በማደጉ ምክንያት አስፈላጊ የሥራ ጊዜ ከ4 ወደ 3 ሰዓት ቢቀነስ ቀሪው 5 ሰዓት ሠራተኛው በነፃ የሚሠራበት ትርፍ የሥራ ጊዜ ይሆናል ። በዚህም

ምክንያት $\frac{4}{4} \times 100 = 100\%$ የነበረው

የትረፈ እሴት መጣኔ ወደ $\frac{5}{3} \times 100 = 167\%$

ከፍ ይላል ። የወዝአደሩ የመደብ ትግል እየጨመረ መጥቶ የሥራ ሰዓትን ማራዘም ሲያዳግተው ካፒታሊስቱ አንፃራዊ ትረፈ እሴትን በማሳደግ ብዝበዛውን ያጠናክራል ።

የሥራ ምርታማነት ሲያድግ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ ሊቀንስ የሚችልበት ምክንያት ሠራተኛው ለራሱና ለቤተሰቡ ህልውና የሚያስፈልጉና በምንዳው ሊገዛቸው የሚችላቸው የፍጆታ ዕቃዎች ከበፊቱ ጋር ሲነፃፀሩ አጠር ባለ ጊዜ ውስጥ ሊመረቱ በመቻላቸው ነው ። ሌላው አንፃራዊ ትረፈ እሴት ማግኛ በሥራ ዕምቀት አስፈላጊ የሥራ ጊዜን አሳጥሮ የትረፈ እሴት መፍጠሪያ ጊዜን ከፍ ማድረግ ነው ።

(ፍጹማዊ ትረፈ እሴትን ፣ ተጨማሪ ትረፈ እሴትን ይመለከቷል ።)

## አንፃራዊነት
*(Relativism)*

የነገሮችንና የክስተቶችን አንፃራዊ ባሕርይ ፍጹማዊ አድርጐ የሚያቀርብ ፣ ማንኛውም ዕውቀት አንፃራዊ ብቻ ነው የሚል ሐሳባዊ አስተምህሮ ነው ። ከተፈጥሮ ውስብስብነት ፣ ከዕውቀት በጊዜና በቦታ መወሰን የተነሣ የሰው ልጅ ግንዛቤ ምንጊዜም ቢሆን ከአንፃራዊነት ሊያልፍ አይችልም የሚል አመለካከት ነው ።

አንፃራዊነት በአንድ በኩል ፍጹማዊ አመለካከትን የሚዋጋ በመሆኑ ቀኖናዊነትን የመታገል ጠንካራ ጎን ያለው ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉም ነገር አንፃራዊ ነው በማለት እራሱን ቀኖና አድርጐ ስለሚያቀርብ ድክመት ይታይበታል ። ባጭሩ አንፃራዊነት የሰውን ልጅ ዕውቀት አንፃራዊና ኅሊናዊ ስለሚያደርግ የኢታዋቂነትና የኅሊናዊ ሐሳባዊነት አንዱ ገጽታ ነው ።

በመሠረቱ ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ባጠቃላይ በማያቋርጠው እንቅስቃሴ ውስጥ የግንዛቤን አንፃራዊ መሆን ይቀበላል ።አቀባበሉ ግን ነባራዊ እውነትን በመካድ ሳይሆን ማናቸውም ዕውቀት በአንድ ታሪካዊ ወቅት የምርት ኃይሎችና ሳይንስ በደረሱበት የዕድገት ደረጃ እንደሚወሰን አድርጎ ነው ። አንፃራዊነት የዕውቀትን ታሪካዊ ባሕርይ ባለመገንዘብ ዕውቀት እየተሟላና እየዳበረ የሚሄድ መሆኑን አይቀበልም ።

(ኅሊናዊ ሐሳባዊነትን ፣ ኢታዋቂነትን ፣እውነትን ፣ ፍጹማዊና አንፃራዊ እውነትን ይመለከቷል ።)

## አንፃራዊ ነፃነት
*(Relative Independence)*

በታሪካዊ ቁስአካልነት ንድፈ ሐሳብ ውስጥ የመሠረትንና የላዕላይ መዋቅርን ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት የሚገልጽ ጽንሰ ሐሳብ ነው ። ላዕላይ መዋቅር የሚመነጨውና የሚወሰነው በመሠረቱ ሲሆን አንፃራዊ ነፃነት አለው የሚባለው በበኩሉ በመሠረቱ ላይ ተፅዕኖ ስለሚያደርግ ነው ።

በሐሳባዊ ፍልስፍና መሠረት ታሪክን የሚያንቀሳቅሰውና ግብም የሚሰጠው ኃይል ሐሳብና የእርሱ ዕድገት ነው ። በሐሳባውያን አባባል የላዕላይ መዋቅር ክፍሎች (መንግሥት ፣ ሕግ ፣ ባህል ፣ ርዕዮተዓለም ወዘተ... በዕውቀት ዕድገት አማካይነት ጥራትና ትክክለኛነት እያገኙ መሄድ የሰው ልጅ ታሪክ እንዲንቀሳቀስና ወደተሻለ ሁኔታ እንዲያመራ ያደርጉታል ። ለምሳሌ የፍትህ ጽንሰ ሐሳብ ጥራት ማግኘት ኅብረተሰብን ወደተሻለ የፍትህ ደረጃ ያራምደዋል ። ማርክሲዝም በመጀመሪያ ደረጃ የተቃወመው ይህን የሐሳብ መሪነት ነው ። የታሪክ አንቀሳቃሽ ኃይል በቁሳዊ መሠረቱ ውስጥ እንደሚገኝ በማስገንዘብ ላዕላይ መዋቅሩ ከሱ የሚመነጭና በእሱም የሚወሰን መሆኑንም አስተምሯል ።

ሆኖም ይህ አመለካከት ከአንዳንድ ግርክሳዊ ነን ከሚሉ ተከታዮች የተሳሳተ ትርጉም ሊያገኝ ችሏል ። እሱም ወደተናክአታዊ አመለካከት በማዘንበል ላዕላይ መዋቅሩ ምንም ሚና እንደማይጫወትና የራሱ እንቅስቃሴ የሌለው ግትር የመሠረት ተገብሮት አድርጎ የመውሰድ አዝማሚያ ነው ። ይህን አመለካከት ማርክሲዝም ሌኒኒዝም በጥብቅ የሚዋጋው ነው ፤ ምክንያቱም ታሪካዊ ቁስአካልነትን ከተጨባጭ ሁኔታ የሚያርቅና የሚያዛባ ነው ። የአንፃራዊ ነፃነት ጽንሰ ሐሳብም የተቀመረው ይህን የተሳሳተ ትርጉም ለማረም እንዲያመች ነው ።

የመሠረት ዋናው ክፍል ማለትም የኢኮኖሚ ግንኙነቶች የታሪክ የመጨረሻ ወሳኝ እንጂ ብቸኛ ወሳኝ ኃይል አይደሉም ። ታሪክ የብዙ ሁኔታዎችና ኃይሎች (አካባቢ ፣ ተፈጥሮ ፣ ሃብት ፣ የጉርብትናና የዓለም አቀፍ ሁኔታ ፣ የመደቦች ሁኔታና አሰላለፍ ፣ ባህል ወዘተ...) ውጤት ሲሆን የኢኮኖሚ ግንኙነቶች የላቀና የመጨረሻ ወሳኝ ሚና አላቸው ። ነገር ግን ዲያሌክቲክስ እንደሚያስተምረው ወሳኙ ኃይል ከሚወሰነው ኃይል ጋር መስተጋብር ስለሚፈጥር መንሥኤው ከራሱ ተገብሮት በተገላቢጦሽ ተፅዕኖ ይደርስበታል ።

እያንዳንዱ የላዕላይ መዋቅር ክፍል (መንግሥት ፣ ሕግ ፣ ወዘተ...) የሚከተላቸው የራሱ ሥነ አመክንዮአዊ አንፃራዊ ሕጎች ያሉት መሆኑና ክፍሎቹም በእርስ በርስ ውስብስብ ግንኙነቶች እኳያ የተዋቀሩ መሆናቸው የአንፃራዊ ነፃነታቸው አንዱ መንሥኤ ነው ። ለምሳሌ ሕግን ብንወስድ ከመሠረቱ የተለየ የዕድገት ሕግ ያለው ከመሆኑም በላይ ከመንግሥት ጋር የተጣመረ ግንኙነት አለው ። እንዲሁም ባህልን ስንመለከት የመሠረት መቀየር የባህልን ለውጥ ወዲያው የሚያስከትል አይደለም ። የላዕላይ መዋቅር ሁኔታ ለመሠረቱ ዕድገት መፋጠን ወይም መጓተት ምክንያት ሊሆን ይችላል ። በተጨማሪም ታሪካዊ ሂደት ምንጊዜም ቢሆን ግላዊ መልክ ያለው የአንድ ሀገር ታሪክ ነው ። ሁለንታዊ

ነቱ የሚረጋገጠው በኢኮኖሚው ሂደት ወሳኝነት ሲሆን ግላዊነቱ ደግሞ የሚመነጨው የተለያዩ ሁኔታዎች አጠቃላይ ውጤት በመሆኑ ስለሆነ ሁለንታዊነትና ግላዊነት የሚገኘው ከመሠረትና ከላዕላይ መዋቅር ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት ነው ።

መንግሥትን እንደ ምሳሌ እንውሰድ ። የመደብ ትግል ውጤት መሆኑ ግልጽ ሆኖ ሳለ ግላዊ ቅርፅ የሚኖረው የተለየ ተፅዕኖ ከኢኮኖሚው ሁኔታ በቀጥታ ለማመንጨት የማይቻል ነው ። መሠረቱ ካፒታሊስታዊ ሆኖ መንግሥቱ ሪፐብሊክ ወይም ንጉሣዊ አገዛዝ ወይም ደግሞ ሕገ መንግሥታዊ ንጉሣዊ አገዛዝ ሊሆን ይችላል ። ይህን ሁኔታ ለመረዳት የምንችለው ከመንግሥቱ አንፃራዊ ነፃነት የታሪክ ሕግና ሂደት ነው ። ሌላው ሊጠቀስ የሚችለው መንግሥት ኢኮኖሚያዊ የበላይነት ያለውን የመደብ ጥቅም የሚያስከብር ሆኖ ሳለ ይህን ተግባር ለማከናወን ሲል ከገዥው መደብ ለየት ያለ ጥቅም ያለውን የቢሮክራቱን ክፍል መፍጠሩ የመደብ ትግልን ሁኔታ በዚያው አንፃር ውስብስብ እንዳደረገው ነው ። በሌላ በኩል መንግሥት የሚያወጣቸው ዕቅዶችና ሕጎች ፣ ያለው የአሠራር ዘዴ በቀጥታ በኅብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ የማፋጠን ወይም የመትተት ተገብሮት አላቸው ። በተጨማሪም ለአንድ አብዮታዊ መደብ የመንግሥት ሥልጣን ጥያቄ ወሳኝ የሚሆነው በመንግሥት ሥልጣን አማካይነት የኢኮኖሚ ግንኙነቶችን ለመለወጥ በመቻሉ ስለሆነ ይህ የሚያረጋግጠው መንግሥት የማይናቅ ሚና ሊጫወት እንደሚችል ነው ።

ሆኖም መታወቅ ያለበት መንግሥት አቅጣጫን ከማሳየት ባሻገር የኢኮኖሚ ሁኔታ የሚፈቅደው ውጭ አዲስ ክስተት ወይም ሂደት ሊያመነጭ የማይችል መሆኑ ነው ። መንግሥት አንፃራዊ ነፃነት ወደሙሉ ነፃነት ሊለወጥ አይችልም ። በመሠረትና በመንግሥት መካከል ያለው ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት የሚመራው መንግሥት በአንፃራዊ ነፃነቱ ግፊት የሚያደርገው እንቅስቃሴ ዞሮ ዞሮ የኢኮኖሚውን ወሳኝነት እንዲያጠናክር ለማድረግ ነው ። የመንግሥት ፖሊሲ ዕድገትን የሚገትት ከሆነ የመሠረቱን ቅራኔ ያባብሳል ፤ አብዮትን ያመቻቻል ፤ ዕድገትን የሚያፋጥን ከሆነ የኢኮኖሚን ሂደት ወሳኝነት ተቀብሎ እሱኑ ያራምዳል ማለት ነው ። እንዲሁም ለምሳሌ የማርክሳዊ ሌኒናዊ አመለካከት በኅብረተሰቡ ውስጥ መስራጨት በሚፈጥረው የንቃተ ኅሊና ደረጃና የድርጅታዊ ሥራ ዝንባሌ ለኢኮኖሚ ዕድገት ዓይነተኛ መጣሪያ ነው ፤ በአንፃሩም ኋላቀር አስተሳሰቦችና ልምዶች ለዕድገት ዕንቅፋት በመሆናቸው የሚያስወግዳቸውን ኃይል እየጋበዙና እያጠናከሩ ነው ።

በመሆኑም የአንፃራዊ ነፃነት ዲያሌክቲካዊ ትርጉም በአጠቃላይ እንደሚከተለው ነው ። የመሠረት ወሳኝ ሚና በሚፈጥረው ተገብሮት ተፅዕኖ ይደርስበታል ። ተፅዕኖው የታሪካዊ ሂደቱን ዓይነተኛ ቅርፅ ወይም መልክ ይፈጥራል ። ቅርፁ ከሚኖረው ባሕርይ አኳያ የይዘቱን ማለትም የኢኮኖሚ ግንኙነቱን ወሳኝነት ያመቻቻል ፤ ያጠናክራል ፣ ልዩ ሁኔታዎችንም ይፈጥራል ። ይህ ታሪካዊ ሂደት የላዕላይ መዋቅርና የመሠረት ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት ውጤት እንጂ ተናክአታዊ ተገብሮት እንዳልሆነ ያስረዳናል ማለት ነው ።

(ታሪካዊ ቁስአካልነትን ፣ መሠረትን፣ ላዕላይ መዋቅርን ይመለከቷል ።)

## አንፃራዊ የኑሮ ሁኔታ ቁርቁዝና (*Relative Impoverishment*)

አንፃራዊ የኑሮ ሁኔታ ቁርቁዝና የሚባለው በካፒታል ክምችት ሳቢያ በወዝአደሩና በቡርዧው መደብ ገቢ መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ መሄዱን ወይንም የወዝአደሩ መደብ የኑሮ ሁኔታ ከቡርዧው መደብ የኑሮ ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር እያቆለቆለ መምጣቱን የሚያመለክት ነው ።

ለምሳሌ በእንግሊዝ ሀገር በ1891 42.7% የነበረው የወዝአደሩ መደብ የብሔራዊ ገቢ ድርሻ በ1963 ወደ 26% ዝቅ ሲል ፣ በአሜሪካ በ1909 39.3% የነበረው የወዝአደሩ መደብ የብሔራዊ ገቢ ድርሻ በ1965 ወደ 24.4% አሽቆልቁሏል ። ከዚህም በላይ ከ1960 እስከ 1968 ባለው ጊዜ ውስጥ የአሜሪካ ሞኖፖል ድርጅቶች የተጣራ ትርፍ የ92% ዕድገት ሲያሳይ በዚህ ጊዜ

ውስጥ የወዝ አደሩ መደብ ምንዳ ያደገው በ11% ብቻ መሆኑ እየሰፋ በመሄድ ላይ ያለውን የገቢ ልዩነት በገሀድ የሚያሳይ ነው ።

በካፒታሊስት ሥርዓት አንፃራዊ ቁርቁዝና ከአንድ የካፒታሊስት ሀገር ጠቅላላ ብሔራዊ ሀብት ውስጥ የወዝአደሩ መደብ ድርሻ እያነሰ በመሄዱም ጭምር ይገለጻል ። ለምሳሌ በአሜሪካ ውስጥ 3% ያህል የሚሆኑት የቡርዧው መደብ አባላት 57% የሚሆነው የሀገሪቱ ሀብት ባለቤቶች ሲሆኑ በእንግሊዝ ሀገርም እንዲሁ 3% የሚሆኑት ቡርዧዎች 61% የሚሆነው የሀገሪቱ ሀብት ባለቤቶች መሆናቸው በሁለቱ መደቦች መካከል እየሰፋ በመሄድ ላይ ሳለው የኑሮ ልዩነት ዓይነተኛ ማስረጃ ነው ።

የካፒታሊስት ክምችት እያደገ በሄደ መጠን የወዝአደሩ መደብ የኑሮና የሥራ ሁኔታ ማሽቆልቆል ከሚከሰትባቸው መልኮች መካከል አንዱ አንፃራዊ ቁርቁዝና ነው ። የዚህ ሁኔታ መፈጠር ደግሞ የወዝአደሩ መደብ እያቆለቆለ የሚሄደውን የኑሮም ሆነ የሥራ ሁኔታ ለማሻሻል ትግል እንዲያደርግ ስለሚገፋፋው በብዝበዛ ላይ የተመሠረተውን የካፒታሊስት የምርት ግንኙነት በሶሻሊዝም ለመተካት የሚያስችል ነባራዊና ኅሊናዊ ሁኔታ ለመፍጠር ይረዳል።

## አንፃራዊ የእሴት መልክ

(*Relative Form of Value*)

አንድ ሸቀጥ በተወሰነ መጠናዊ ተዛምዶ ወይም ጥምርታ በሌላ ሸቀጥ ሲለወጥ በተነፃፃሪነት ከፊት ለፊቱ የቆመ ሌላ ሸቀጥ መኖሩን የሚያሳይ የእሴት መልክ አንፃራዊ የእሴት መልክ ይበባል ። ለምሳሌ አንድ በግ በአሥር ቁና ገብስ ይለወጣል እንበል ። እዚህ ላይ በጉ የራሱን እሴት በሌላው ሸቀጥ ማለትም በገብሱ ስለሚገልጽ አንፃራዊ የእሴት መልክ አለው እንላለን ። የገብሱ ጠቀሜታ እሴት ደግሞ የበጉን እሴት ለመግለጽ ስለሚውል ገብሱ በእኩያዊ የእሴት መልክነት ይቀርባል ።

በመሠረቱ እነዚህን ሁለት የተለያዩ ሸቀጦች (በግና ገብስ) በተመጣጣኝነት አስቀምጦ በልውውጥ ሂደት ውስጥ ማስገባት የተቻለው ሁለቱም እሴትን የሚወክሉና ረቂቅ የሰው ሥራን ያዘሉ በመሆናቸው ነው ። በመሆኑም አንፃራዊ የእሴት መልክ በመልዋወጥ ላይ ያሉ ሸቀጦችን አሀዛዊ ተመጣጣኝነት ያሳያል ። አንፃራዊ የእሴት መልክ በሁለት ሸቀጦች መካከል ያለውን የወል ባሕርይ ማለትም ማኅበራዊ ሥራን ያመለክታል ። በተጨማሪም በመወዳደር ላይ ባሉት ሸቀጦች መካከል ሊኖር የሚችለውን የልውውጥ መጠን ማለትም ልውውጡ ስንት በስንት መሆን እንዳለበትም ይወስናል ።

(እኩያዊ የእሴት መልክን ፣ የእሴት ጥንት መልክን ይመለከቷል ።)

## አንፃራዊና ፍጹማዊ እውነት

(*Relative and Absolute Truth*)

የሰው ልጅ ዕውቀት እውነትነት አንፃራዊ ወይስ ፍጹማዊ ነው የሚለውን ጥያቄ የሚመለከት የሥነ ዕውቀት ፈርጅ ነው ። ኅሊናዊ ፈላስፎች ዕውቀት የተወሰነ በመሆኑ ስለ ነባራዊ እውነታ ጥልቀት ያለው ትክክለኛ ወይም ፍጹማዊ የሆነ ግንዛቤ ሊገኝ አይቻልም ይላሉ ። በነሱ አባባል ዓለምን የምናውቀው በነባራዊነቱ ባለመሆኑ የምናገኘው ዕውቀት በአጠቃላይ አንፃራዊ ነው ። አንፃራዊ ማለት ነገሮችን የምናውቃቸው ሕዋሳት በሚሰጡን ሕውስታዊ መረጃዎች አማካይነትና እነዚህም ሕውስታዎች በኛ ውስጥ ብቻ የሚገኙ በመሆናቸው የምንደርስበት ዕውቀት ከእኛ ተነጥሎ የማይታይና በኛ የተፈጥሮ አመለካከትና አቀያየስ የተወሰነ ነው ማለት ነው ። ለምሳሌ ቦታ የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ ብንወስድ ግራ ፣ ቀኝ ፣ ታች ፣ ላይ ስንል እነዚህ አቅጣጫዎች ከእኛ አቀማመጥ አንፃር የሚሰየሙ በመሆናቸውና ቦታ ነባራዊ ሳይሆን ነገሮችን ከእኛ አቅጣጫ የምናስቀምጥበት አንፃራዊ አመለካከት ይሆናል ማለት ነው ።

ሌሎች ፈላስፎች ደግሞ የሰው ልጅ ዕውቀት ፍጹምነት ያለው መሆኑን ለማሳየት ጥረዋል ። ፍጹማዊ እውነት ማለት በማያጠራጥር ሁኔታ የነባራዊውን እውነታ ምንነት በሐሳባችን ውስጥ ሙሉ በሙሉ ለመቅረፅ እንደምንችልና ማንኛውም ጥያቄ ረቂቅ ሆኖ

ሕውስታዊ ትክክለኛ መልስ የሚገኝለትና ዕውቀታችንም የተረጋገጠ ይዘት ያለው መሆኑን የሚያሳይ ነው ። በእነዚህ ፈላስፎች እመለካከት የሰው የማሰብ ችሎታ ገደብ የሌለው ስለሆነ ትክክለኛ የምርምር ዘዴ ከተቀየሰ በዓለም ውስጥ ከሰው ሐሳብ የተሰወረ ምንም ነገር ሊኖር አይችልም ። ምክንያቱም ለእነሱ ሐሳብ የዓለም ፈጣሪ እንደመሆኑ ከሐሳብ የተፈጠረ ከሐሳብ በላይ እንደማይሆንና ሙሉ በሙሉ ሊታወቅ እንደሚችል የሚያምኑ በመሆናቸው ነው ። ለምሳሌ አንድ መሐንዲስ የሠራውን ድልድይ ሙሉ በሙሉ እንደሚያውቀው ሁሉ እንዲሁም ራሱ ሐሳብ የፈጠረውን ነገር ፍጹማዊ በሆነ ሁኔታ ያውቀነዋል ።

በማርክሳዊ አመለካከት ይህ የቀረበው ምርጫ ማለትም እውነት ፍጹማዊ ነው ወይስ አንፃራዊ የሚለው ተቀባይነት የለውም ። እውነት አንፃራዊም ፍጹማዊም ነው ። አንፃራዊነቱ የሚመነጨው ከድከመት ወይም ከብልሽት ሳይሆን ታሪካዊና ማኅበራዊ በመሆኑ ነው ። ስለ ዓለም ያለን ግንዛቤ በአንድ ታሪካዊ ወቅት የተወሰነ በመሆኑ እውነትንም ባለን መሠረታዊ ፍላጐትና የተግባር ዓይነት ማለትም በምንገኝበት ስልተ ምርት ይዘት አንፃር እንገነዘባለን ። ሆኖም እውነት አንፃራዊ ቢሆንም ፍጹማዊነትም አለው ። ምክንያቱም በተወሰነ ጊዜ የምናውቀው እውነት ኅሊናዊ ብቻ ሳይሆን በእርግጥም ነባራዊ ሁኔታን የሚመለከት ነው ። ነባራዊን በአንፃራዊነቱ ማወቁ የነባራዊን አንድ ገጽታ መረዳታችን መሆኑ ግልጽ ነው። የምናውቀው በከፊል ቢሆንም ይህ ክፍል ብቻ አንጐል ውስጥ ያለ ብቻ ሳይሆን የራሱ የነባራዊው ክፍል በመሆኑ ግንዛቤአችንን ፍጹማዊ እውነት ያደርገዋል ። እውነት አንፃራዊና ፍጹማዊ ነው ሲባል እዳገ. መሆኑን መግለጽ ይሆናል ። የምርት ኃይሎች ባደጉ ቁጥር ዕውቀት እየሰፋና ጥልቀት እያገኘ ይሄዳል ። በአንድ ወቅት ፍጹማዊ የመሰለን እውነት በዕድገት ምክንያት አንፃራዊ ሆኖ እናገኘዋለን ። አንፃራዊ እውነት ሙተት ወይም የሚጣል እውነት ሳይሆን ኪሱ በመነሣት አዲስ ዕውቀት ወይም ከፍና ሰፋ ያለ እውነት እንዳገኘንና በድሮው ላይ በመደመር ዕውቀት እያከማቸን እንደምንሄድ የሚያስረዳ ነው ። እውነት አንፃራዊና ፍጹማዊ ነው ማለት የዲያሌክቲክስ ሕግ እንደሚያመለከተው ዕውቀት ከትንሽ ወደ ትልቅ ከጠባብ ወደ ሰፊ ፣ ከክስተት ወደ ምንነት ይጓዛል ማለት ነው ። ይህ ማለት ግን ትንሽ በትንሽ ፍጹማዊ ከሆነ ዕውቀት ላይ እንደርሳለን ማለት አይደለም ። ምክንያቱም ፍጹማዊ ከሆነ ዕድገትን የጨረሰ ስለሚሆን ዕድገት ደግሞ ሁሉን የሚገዛ ሕግ በመሆኑ ይህ አባባል ስህተት ከመሆኑም በላይ ፍች የሌለው እነጋገር ይሆናል ። ምንም ጊዜ ወሳኝ የሆነው ታሪካዊ ሂደት በመሆኑ ዕውቀት እያደገና ጥልቀት እያገኘ ይሄዳል እንጂ የሚቆምበት ወቅት ከቶ ሊኖርና ሊታሰብ አይችልም ። የሰው ፍላጐትና ኃይል እያደገ በሄደ ቁጥር ከዓለም ጋር ያለው ግንኙነት ስለሚለዋወጥ እውነትም በዚሁ በማያቋርጥ ሂደት ውስጥ እንደሚገኝ መረዳት ይኖርብናል ።

(እውነትን ፣ ዕውቀትን ይመለከቷል ።)

## አኩዊናስ ፣ ቶማስ
*(Aquinas, Thomas)*

ከ1225—1274 የኖረ የካቶሊክ ሥነ መለኮት ምሁርና የዶሚኒካን መነኩሴ የነበረ ኢጣሊያዊ ሐሳባዊ ፈላስፋ ነው ። ቶማስ እኩዊናስ የአርስጣጣሊስን አስተሳሰብ የክርስትና ሃይማኖት መማሪያ አድርጐ ለመጠቀም በነበረው ፍላጐት የተሳሳተ ትርጉም ሰጥቶ ወደነባራዊ ሐሳባዊነት ቀይሮታል ። ከዚህም የተነሣ በአርስጣጣሊስ ፍልስፍና ውስጥ የነበሩትን ቁስአካላዊ አመለካከቶች ወደጐን በመተው ሐሳባዊ የሆኑትን ብቻ አስቀርቷል ፤ ለምሳሌ የዓለም እንቅስቃሴ የሚመነጨው "ከማይንቀሳቀሰው የመጀመሪያ እንቀሳቃሽ" ነው የሚለውን የአርስጣጣሊስን አመለካከት አጉልቶ ለማሳየት ሞክሯል ።

የቶማስ እኩዊናስ አስተሳሰብ መርህ ሃይማኖትንና አመክንዮን ለማጣጣም መሞከር ነው ። በእኩዊናስ አባባል የእግዚአብሔር መኖር በአመክንዮ ይረጋገጣል ። ማንኛውም ነገር እግዚአብሔር በፈጠረው ተዋረዳዊ ሥርዓት ውስጥ ቦታ አለው ይላል ። ለዚህ አባባሉ ግን ማረጋገጫና ምክንያት አይሰጥም ። ይህ የቶማስ እኩዊናስ የተዋረድ አስተምህሮ የሚያንፀባርቀው የፊውዳል ዘመን ቤተ ክርስቲያናችን ውስጣዊ አደረጃጀት ነው ።

የቶማስ አኩዊናስ አስተሳሰብ አዲሱ ቶሚዝም (ኒዮቶሚዝም) በመባል የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ፍልስፍና መርህ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል ። አኩዊናስ አስተሳሰቦቹን "ሱማ ኮንትራ ጀንትል" ፣ "ሱማ ቲዮሎጂካ" በተባሉት ድርሰቶቹ ላይ አስፍሯል ።

(ቶሚዝምን ይመለከቷል ።)

## አክሲዮን
(*Share*)

አክሲዮን በአንድ በተወሰነ የካፒታሊስት ኩባንያ ውስጥ ለኩባንያው የሥራ እንቅስቃሴ አንድ ሰው የተወሰነ ካፒታል ማዋጣቱን የሚገልጽ ሕጋዊ ሰነድ ነው ። ባለአክሲዮኑ ከኩባንያ ካገኘው ትርፍ ውስጥ የተወሰነ ድርሻ በአክሲዮን ክፍያ መልክ የማግኘት መብት አለው ። ማንኛውም የኩባንያውን አክሲዮን የገዛ ሰው ከሌሎች የኩባንያው ባለቤቶች ጋር የጋራ ባለቤት ሆኖ ይቆጠራል ፤ በድርጅቱም የባለ አክሲዮኖች ጠቅላላ ስብሰባ ላይ የመካፈል መብት አለው ።

አክሲዮኖች የሚሸጡትና የሚገዙት በአክሲዮን ገበያ ወይም በባንክ አማካይነት ነው ። አክሲዮኖች በጋራ አክሲዮን ኩባንያ ፣ በግለሰብ ወይም በካፒታሊስት መንግሥታዊ ኩባንያዎች ሊሸጡ ይችላሉ ። የአክሲዮን ባለቤቶች ኩባንያው ሲፈርስ ዕዳው ተከፍሎ የቀረውን ካፒታል በአክሲዮናቸው መጠን ይከፋፈላሉ ። ባሁኑ ጊዜ ባለው አሠራር መሠረት የኩባንያውን ዕጣ የገዙ ግለሰቦች ለኩባንያው ዕዳ ያለባቸው ተጠያቂነት በገዙት ዕጣ መጠን የተወሰነ ነው ፤ ስለዚህም እንዲህ ያለው ኩባንያ ኃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ ይባላል ።

(የጋራ አክሲዮን ኩባንያን ይመለከቷል።)

## አክሲዮን ክፍያ (የ—)
(*Dividend*)

እያንዳንዱ የአክሲዮን ባለቤት አክሲዮን በመግዛት ኩባንያው ከሚያገኘው ዓመታዊ ትርፍ ውስጥ የሚያገኘው ገቢ የአክሲዮን ክፍያ ይባላል ።

ለምሳሌ የኩባንያው አንድ አክሲዮን ተመን ብር መቶ ቢሆንና ይህም አክሲዮን በዓመቱ መጨረሻ ላይ ብር 7.00 ቢያስገኝ ፤ ይህ ብር 7.00 የአክሲዮን ክፍያ በመባል ይታወቃል ።

የአክሲዮን ክፍያ መጠን በመሠረቱ በኩባንያው አመራር አካል የሚወሰን ሆኖ ኩባንያው ከሚያገኘው የትርፍ መጣኔ ያነስና የካፒታሊስት ባንኮች ከሚሰጡት የወለድ መጣኔ ደግሞ በመጠኑ ከፍ ያለ ነው ። ኩባንያው ካገኘው ትርፍ ውስጥ ለአክሲዮን ባለቤቶች በአክሲዮን ክፍያ መልክ እንደ አክሲዮን ይዞታቸው ከከፋፈለ በኋላ የሚቀረውን ትርፍ ለድርጅቱ ማስፋፊያ ያደርገዋል ።

(የጋራ አክሲዮን ኩባንያን ይመለከቷል ።)

## አክሲዮን ገበያ (የ—)
(*Stock Exchange*)

በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ አክሲዮኖችና አረቦኖች የሚሸጡበትና የሚገዙበት የንግድ ድርጅት የአክሲዮን ገበያ ይባላል ። አክሲዮኖችንና አረቦኖችን ለመግዛትና ለመሸጥ የሚያገለግሉት የንግድ ተቋሞች ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች ናቸው ። የአክሲዮን ገበያ አክሲዮንና አረቦን የሚሸጡትንና የሚገዙትን ሰዎች በማገናኘት አገልግሎት ይሰጣል ። አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስችለውን የድርጅት መዋቅር በመዘርጋትና በደላሎችም አማካይነት በመሥራት ሻጮችንና ገዥዎችን ያገናኛል ።

በዘመናዊ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የአክሲዮን ገበያዎች ከመከሰታቸው በፊት ካፒታሊስቶች በታወቁ የገበያ ቦታዎች በመገናኘት የአክሲዮንና የአረቦን ግዥና ሽያጭ ያከናውኑ ነበር ። ዛሬ በማንኛውም ካፒታሊስት ሀገር ውስጥ ቢያንስ አንድ የታወቀ ትልቅ የአክሲዮን ገበያ አለ ። በካፒታሊስት ሀገሮችም መካከል በዓለም አቀፍ ደረጃ በአክሲዮን ገበያቸው ከታወቁ ከተሞች መካከል ኒውዮርክ ፣ ለንደን ፣ ፓሪስና አምስተርዳም ይገኛሉ ። በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የአክሲዮን ገበያ ከፍተኛ የካፒታል መሰብሰቢያ ፣ ማከማቻና ማማከያ ስልት ሲሆን በዚህ አማካይነት ሰፊ የሙአለ ንዋይ ተግባ

ራትን ለማከናወን ይቻላል ። የአክሲዮን ገበያ በካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ከፋይናንስ ድርጅቶች ጋር የተሳሰረ ነው ። የካፒታሊስት ኩባንያዎች አክሲዮኖችና አረቦኖች ሲሸጡና ሲገዙ ፣ የካፒታሊስት መንግሥታት ደግሞ በተለይ አረቦኖችን በመሸጥ የበጀት እጥረታቸውን ይወጣሉ ።

የአክሲዮኖችና የአረቦኖች የመሸጫ ዋጋ መጣኔ በአክሲዮን ገበያ ላይ ይወሰናል ። የካፒታሊስት ኢኮኖሚ አጠቃላይ ቀውስ በሚገጥመው ወቅት ዋጋው ዝቅ ይላል ፤ በተቃራኒው ደግሞ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ በአጠቃላይ በሚስፋፋበትና በሚደራጅበት ወቅት ዋጋው ከፍ ይላል ። ሞኖፖሊስቶችና የፋይናንስ ካፒታሊስቶች እንደ ኢኮኖሚው ሁኔታና አዝማሚያ አክሲዮኖችንና አረቦኖችን በመግዛትና በመሸጥ ከፍተኛ ትርፍ ያገኛሉ ።

በአክሲዮን ገበያ ላይ በካፒታሊስቶች መካከል በሚኖረው ፉክክር የሚያሸንፉት ከፍተኛ የፋይናንስ ካፒታሊስቶች ሲሆኑ አነስተኛ ካፒታሊስቶች ግን ውድድሩን ስለማይችሉት ከገበያው ለመውጣት ይገደዳሉ ። በአሁኑ የሞኖፖል ካፒታሊዝም ወቅት ከፍተኛ የአክሲዮኖችና የአረቦኖች ሽያጭና ግዥ የሚከናወነው በሞኖፖል ባንኮች አማካይነት ነው ።

## አውሮፓ ኢኮኖሚ ማኅበር (የ—)

*(European Economic Community–EEC)*

የተወሰኑ የምዕራብ አውሮፓ ካፒታሊስት ሀገሮች መንግሥታዊ ድርጅት ነው።የተመሠረተውም በ1957 በፈረንሳይ ፣ በፌደራል ጀርመን ፣ በኢጣልያ ፣ በቤልጅግ ፣ በኔዘርላንድና ሉክሰምበርግ አባልነት ነበር ። ማኅበሩን ሕጋዊ ያደረገው ስምምነት በሮም ከተማ ከተፈረመ በኋላ ድርጅቱ ይፋ እንቅስቃሴውን በሚቀጥለው ዓመት ጀመረ ። በወቅቱ የማኅበሩ መመሥረት ካፒታሊዝም ከደረሰበት የመንግሥታዊ ሞኖፖል ደረጃ ፣ ከካፒታል በከፍተኛ ደረጃ መሰባሰብ እንዲሁም ከአካባቢው የሞኖፖል ቡርዧዚዎች የተጠናከረ መተሳሰር ጋር የተያያዘ ነው ።

ማኅበሩ በተመሠረተበት ወቅት ዓላማዎቹ በአባል ሀገሮች መካከል ንግድን ፣ ካፒታልንና የሰው ኃይልን በሚመለከት ከቁጥጥር ነፃ የሆነ ንቅናቄ እንዲኖር ማድረግ ፣ ከሌሎች ሀገሮች ጋር በሚደረግ ንግድ የጋራ የወጪና የገቢ ንግድ ፖሊሲ መከተል ፣ በአባል ሀገሮች ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች መካከል ያለውን የሥራ ክፍፍል ማቀናበር ፣ በተለይም የጋራ የእርሻ ፖሊሲ በመቀየስ በካፒታሊስት አውሮፓ ውስጥ በቂ የምግብ ምርትና ለአውሮፓ የእርሻ ካፒታሊስቶች አስተማማኝ ገቢ ማስገኘትና የመሳሰሉት መሆናቸው ተገልጾ ነበር ። ይሁንና የሶሻሊስቱን ዓለም ፣ በካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ ያሉ ዲሞክራሲያዊ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግሎችንና ፀረ ኢምፔሪያሊስት የብሔራዊ አርነት ንቅናቄዎችን በተቀነባበረ መንገድ መዋጋት ፣ የኢምፔሪያሊዝምን ዕድሜ ማራዘም ከማኅበሩ ዋና ዋና ዓላማዎች መካከል ጥቂቶቹ መሆናቸው የሚያጠራጥር አይደለም ።

የማኅበሩ አባል ሀገሮች ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ በመሄድ ላይ ነው ። በ1973 እንግሊዝ ፣ ዴንማርክና አየርላንድ አባል ሆነዋል ። ከዚያም ወዲህ ግሪክ የማኅበሩ 10ኛ አባል ሆናለች ። ፖርቱጋልና ስፓኝም የአባልነት ጥያቄ አቅርበው በቅርቡ የማኅበሩ አባላት እንዲሆኑ ተወስኗል ።

የማኅበሩ የአመራር አካላት የማኅበሩ ካውንስል ፣ የማኅበሩ ኮሚሽን ፣ የማኅበሩ ጉባኤ (የአውሮፓ ፓርላማ) እና የማኅበሩ የፍርድ አካል ናቸው ። ከዚህም ሌላ ማኅበሩ የአውሮፓ የሙአለ ንዋይ ባንክና የአውሮፓ ልማት ፈንድ የተባሉ ተቋሞች አሉት ። የማኅበሩ ጽሕፈት ቤት የሚገኘው በብሩሴልስ ከተማ ነው ።

በማኅበሩ ውስጥ አባል በሆኑት የሞኖፖል ካፒታሊስት ሀገሮች መካከል ጉልህ ቅራኔዎች በገሀድ ይታያሉ ። ለምሳሌ የእርሻ ውጤቶችን አምርታ በብዛት በምታቀርበው በፈረንሳይና የእርሻ ውጤቶች ሸማች በሆነችው በፌደራል ጀርመን መካከል ሥር የሰደደ ቅራኔ ይታያል ። ይህ ቅራኔ በጋራ የእርሻ ፖሊሲ አነዳደፍ ፣ በተለይም በእርሻ ምርት ዋጋ ድጎማ ላይ ጉልህ ችግር በማስከተል ተከስቷል ። የዚህ ዓይነቱ ችግር በመሠረቱ እያንዳንዱ አባል ሀገር ከሚገኝበት የተለያየ

የእርሻ ኢኮኖሚ ዕድገት ደረጃ ሊመነጭ የሚችል ነው ። በማኅበሩ ውስጥ በጣም አወዛጋቢ የሆነ አንድ ሌላ ጉዳይ የአባላት መዋጮ ጉዳይና ከዚሁ ጋር የተያያዘው የበጀት አጥረት ችግር ነው ።

በዓለም አቀፍ የካፒታሊስት ገበያ ላይ የማኅበሩ ዋና ተፎካካሪዎች አሜሪካና ጃፓን ናቸው ። እነዚህ ሦስት ኢምፔሪያሊስት ኃይሎችና ሌሎችም ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ባንድ በኩል በመካከላቸው የተካረረ ትግል ሲካሄድ በሌላ በኩል ደግሞ በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ አማካይነት በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮችን በጋራ በመበዝበዝ ላይ ይገኛሉ ። የአውሮፓ ኢኮኖሚ ማኅበር የአባል ሀገሮች የሞኖፖል ካፒታሊስቶች ኢኮኖሚያዊ ጥቅምና ፍላጐት መጠበቂያ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ጥቅማቸውና ፍላጐታቸው ማስከበሪያና ማስፋፊያም ጭምር ነው ። በመሠረቱ ማኅበሩ የምዕራብ አውሮፓ ኢምፔሪያሊዝም የጋራ ማንባርና የኔቶ አንድ ዋና የኢኮኖሚ መሠረት ነው ።

## አውቶኖሚ (ራስ ገዝነት)

*(Autonomy)*

በአንድ ክልል ውስጥ ለሚገኝና በኢኮኖሚና በባህል ለተሳሰረ ሕዝብ በሕግ የሚረጋገጥ የራስ በራስ አስተዳደር መብት ነው ። አውቶኖሚ እስከ ተወሰነ ደረጃ የሥልጣን ማከፋፈል ስልት ሲሆን ከብሔር ጥያቄ መፍቻ ዘዴዎችም አንዱ ነው ።

አውቶኖሚ የተለያየ መልክ አለው ። ይህም መልኩ የሚወሰነው፡ መብቱ የሚረጋገጥለት ሕዝብ በደረሰበት የዕድገት ደረጃ ነው ። ለምሳሌ በሶቭዬት ኅብረት ውስጥ ሁለት ዓይነት የአውቶኖሚ ቅርፆች ማለትም ፖለቲካዊ አውቶኖሚና አስተዳደራዊ አውቶኖሚ አሉ ። ፖለቲካዊ አውቶኖሚ የሚያስገኘው መብት ሰፋ ያለ ነው ። ፖለቲካዊ አውቶኖሚ ያለው ክልል ራሱን የቻለ ብሔረ መንግሥት ሆኖ የራሱ ሕገ መንግሥት ፣ የአስተዳደር ፣ ሕግ አውጭና አስፈጻሚ አካሎች እንዲሁም የራሱ የሆነ የዜግነት ደንብ ይኖሩታል ። አስተዳደራዊ አውቶኖሚ የዚህ ዓይነቱ ደረጃና ሥልጣን ባይኖረውም ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብት ያለው ሆኖ ከባድ ጉዳዮች ግን በበላይ ክልል አካል የሚወሰኑ ይሆናሉ ።

የአውቶኖሚ ሥርዓት አጠቃቀም እንደየሀገሩ ታሪክና እንደጊዜው ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ ባህላዊ ወዘተ... ተጨባጭ ሁኔታዎች ሊለያይ ይችላል ። ሆኖም የአውቶኖሚ ሥርዓት በመሠረቱ በአንድ ክልል ውስጥ የሚኖር ሕዝብ የፍትህና የእኩልነት መብቱ ተጠብቆለት ዕድገቱን ጠብቆ ከአንድ የአውቶኖሚ ደረጃ ወደሚቀጥለው እንዲያድግ የሚያስችለውን አመች ሁኔታ የሚፈጥርለት መሆን አለበት ። በሶሻሊዝም አውቶኖሚን ዓይነተኛ የብሔር ጥያቄ መፍቻ ስልት የሚያደርገው ይኸው ዲሞክራሲያዊና የሠርቶ አደሩን ሕዝብ የዓላማ አንድነት የማረጋገጥ መደባዊ ይዘቱ ነው ።

(ፌደሬሽንን ፣ ኮንፌደሬሽንን ፣ መገንጠልን ፣ የብሔር ጥያቄን ይመለከቷል ። )

## አውዳሚነት

*(Nihilism)*

ያለፈውንና አሮጌውን ፣ አሁንም ያለውን ሁሉ በጥቅሉ የሚቃወም ኢዲያሌክቲካዊና ሐሳባዊ አዝማሚያ ነው ። በዚህ አመለካከት መሠረት የሰው ልጅ በዕድገት ሂደቱ ያካበተው ሥልጣኔና ባህል ሁሉ ፋይዳ የለውም ። ይህ አመለካከት በአብዮታዊ ለውጥ ስም ኅብረተሰብ በዘመናት ሂደት ያካበተውን የርዕዮተዓለም ፣ የሥነ ምግባርና የባሕርይ መለኪያ በጥቅሉ ይቃወማል ። አውዳሚነት የሩሲያ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ከሳይንሳዊ ንድፈ ሐሳብ ጋር ባልተገናዘበበት በ1860ዎቹ "በአብዮታዊ ምሁራን" ዙሪያ የተከሰተ ፣ በወቅቱ የነበረውን ማናቸውንም ነገር የሚቃወም አዝማሚያ ነው ።

በሌላ በኩል ለውጥ ፈላጊ ዲሞክራቶችና አብዮታውያን ጭቆናንና ብዝበዛን ለማጥፋት የሚያደርጉት ትግል የሰውን ልጅ ባህልና ሥልጣኔ የሚያወድም ነው በማለትና በዚህም አብዮታውያንን "የጥፋት መልእክተኞች" እንደሆኑ አድርጉ በማቅረብ አድኃርያን አብዮታውያንን ለማጥላላት ይሞክራሉ ።

ለውጥ አሮጌውን የሚያጠፋ ቢሆንም ካለፈው ለአዲሱ ሥርዓት ጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉትን ይወስዳል ። በአሮጌውና በአዲሱ መካከል ተከታታይነትና ግንኙነት ያለ በመሆኑ የአሮጌውን በጐ ጐኖች ከኋላቀሩና ከማይጠቅመው በጥንቃቄ በመለየት ፣ የሰው ልጅ በዕድገት ሂደቱ ያካበተውን በጐ ባህል ለአዲሱ ጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል ። የለውጥ የአፍራሽነት ገጽታ በዚህ መልኩ ካልታየ ጎጂ ነው ። ለምሳሌ ካፒታሊዝምን መቃወም ማለት በሥርዓቱ ውስጥ ያሉትን የባህል ክምችቶች በሙሉ መደምሰስ ማለት አይደለም ። እንዲያውም ሥርዓቱ ያዳበረውን የምርት ኃይል ፣ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ውጤት ለአዲሱ ሥርዓት መጠቀሚያ ማድረግ ያስፈልጋል ።

## አውጠንጣኝ ፍልስፍና
(*Speculative Philosophy*)

በአእምሮ ውስጥ ሐሳቦችን በማውጣትና በማውረድ ብቻ የዓለምን ዕውቀት እመነጫለሁ የሚል ፍልስፍና ነው ። ግንዛቤው የተመሠረተው በልባዊና በልምድ ላይ አይደለም ። ይህ ፍልስፍና በይዘትም ሆነ በቅርፅ ሐሳባዊ ነው ፤ ምክንያቱም የዓለምን ዕውቀት ከሐሳብ ብቻ እመነጫለሁ ማለቱ የሚገልጸው እውነት በሐሳብ ሕግጋት እንደሚገዛ ማመኑን ነው ። የነባራዊውን ዓለም ነፃ ህልውና ሂደት የማይቀበል በመሆኑ የሚደርስበት ዕውቀት ለተግባር አገልግሎት የሚሰጥ አይደለም ። የእውነታን ምንነት የሚያፈልቀው ከሐሳብ በመሆኑ አውጠንጣኝ ፍልስፍና የሚጠቀመው በምንጨታዊ ሥነ አመክንዮ ነው ። ማርክስ በተለይ የጀርመን ብሉይ ፍልስፍናን አውጠንጣኝ ፍልስፍና ብሎ ሰይሞታል ።

## አዝጋሚ ለውጥ
*(Evolution)*

የአንድ ነገር ወይም ክስተት ዓይነት ሳይለወጥ ፣ እርሱነቱን የሚያመለክቱት ባሕርያቱ ሳይጠፉ ፣ የሰው አእምሮ በቀላሉ ሊገነዘባቸው የማይችል ፣ በአሮጌው ነገርና ክስተት ጠባዮች ክልል ውስጥ ቀስ በቀስ የሚካሄድ የመጠን ለውጥ አዝጋሚ ለውጥ ይባላል ። ይህ ለረጅም ጊዜ በዝግታ የሚካሄድ ለውጥ አሮጌው እየተረሳና እየተለወጠ በምትኩም የአዲሱ መምጣት ቅድመ ሁኔታዎች የሚዘጋጁበት ሂደት ነው ። አሮጌው በዓይነቱ ገና ሳይለወጥ በውስጡ ግን አንዳንድ ለውጦች የሚታዩበት ነውና አዝጋሚ ለውጥ መቀጠልን ፣ አለማቋረጥን የሚያሳይ ነው ።

(አመርታን ፣ አብዮትን ፣ የመጠን ለውጥን ይመለከቷል ።)

## አዲሱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ
*(New Economic Policy—N.E.P)*

ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም ሽግግር ባደረጉበት በአንድ ወቅት የሶቭዬት ኅብረት ኮሚኒስት ፓርቲና መንግሥት ያራመዱት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ነው ። "አዲስ" የተባለበት ምክንያት ከ1918 እስከ 1920 በተካሄደው የእርስ በርስ ጦርነት ወቅት የሶቭዬት ኅብረት ኮሚኒስት ፓርቲና መንግሥት ይከተሉት ከነበረው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ልዩ መሆኑን ለማሳየት ነው ።

አዲሱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ መሆን የጀመረው በ1921 10ኛው የኮሚኒስት ፓርቲ ጉባኤ ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት ሲሆን ዓላማውም በወቅቱ አጋጥሞ የነበረውን የኢኮኖሚ ቀውስ ማስወገድ ፣ በኢኮኖሚው መስክ የሠራተኛውን መደብና የገበሬውን ኅብረት ማጠናከር ፣ የሸቀጥና የገንዘብ ግንኙነት በደራበት በቁርጥራጭ መሬት አስተራረስ ላይ በተመሠረተው የአርሻ ክፍለ ኢኮኖሚና በሶሻሊስት ኢንዱስትሪ መካከል ተጣጣሚ ግንኙነት መመሥረት ፣ ገበሬዎችን ለሶሻሊስት ግንባታ እንዲሰለፉ ማድረግ ፣ የምርት ኃይሎችን እንዲሁም የሠራተኞችንና የገበሬዎችን የኑሮ ሁኔታ ማሻሻል ነው ።

የከረረ የመደብ ትግል ይካሄድ በነበረበት በዚህ ወቅት ለጊዜው ካፒታሊዝም (በአብዛኛው በንግዱና በትናንሽ የማምረቻ መስኮች) እንዲያንሰራራ አመቺ ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር ፤ ይሁን እንጂ የካፒታሊዝም ማንሰራራት ከገደቡ እንዳያልፍ ለማድረግ

የሶሻሊስቱ መንግሥት ቁጥጥር ከወትሮው ይበልጥ ጠበቅ እንዲል ተደርጎ ነበር ።

በ1929 በሶቭዬት ኅብረት ውስጥ የተ ጀመረው አርሻን በአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር ሥር የማድረግ ሂደት በገጠሩ ይገኙ የነበሩትን የካፒታሊስት ኃይሎችን መደምሰስ አስከትሏል ። በብዝበዛ ላይ የተሰማሩ ከተሜ በዝባዦችም እንዳልነበሩ ሆነዋል ። በመሆኑም አዲሱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በ1930 አጋማሽ ላይ በሶሻሊዝም ድላማነት ሊደመደም ችሏል ።

ማርክሳውያን ሌኒናውያን አዲሱ የኢ. ኮኖሚ ፖሊሲ ሶቭዬት ኅብረት ከ1918—1920 የነበረችበት ልዩ ሁኔታ የፈጠረው ሁኔታ እንደሆነ ከመቀበላቸውም በላይ ለወቅቱ ተስማሚ የሆነ ርምጃ መሆኑንም ያረጋግጣሉ ።

## አዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት

*(The New International Economic Order)*

ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነትንና የየሀገሮችን ግንኙነት በእኩልነት መርህ ላይ በአዲስ መልክ ለማዋቀር የቀረበ ፕሮግራም ነው ።

ለአዲሱ ዓለምአቀፍ ሥርዓት የተደረገው ጥሪ በተቀናጀ ፕሮግራም መልክ በተባበሩት መንግሥታት ሸንጎ ላይ የቀረበው በ1974 ነው ። በዚሁ ዓመት የተሰበሰበው ስድስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ልዩ ጠቅላላ ጉባኤ ባስተላለፋቸው ውሳኔዎች በቁጥር 3201ና 3202 አማካይነት አዲስ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ሊመሠረት የሚችልበት መግለጫና የድርጊት ፕሮግራም ተነደፈ ። በዚሁ ዓመት የተሰበሰበው 29ኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ የመንግሥታትን የኢኮኖሚ መብቶችና ግዴታዎች ቻርተር አጸደቀ ።

የአዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት የድርጊት ፕሮግራም በመንግሥታት መካከል መኖር የሚገባውን የኢኮኖሚ ግንኙነት በሚመለከት ሦስት ዘርፎችን የያዘ ነው ። እነሱም ፣ 1ኛ/ በአሁኑ ወቅት በዳበሩ ካፒታሊስት ሀገሮችና በኋላቀር ሀገሮች መካከል ያለው የንግድ ፣ የገንዘብና የፋይናንስ ግንኙነት የተዛባና የዳበሩ ካፒታሊስት ሀገሮችን ጥቅም ብቻ የሚያስከብር በመሆኑ ይኸን ሁኔታ መለወጥ አስፈላጊ መሆኑን ፣ 2ኛ/ የኋላቀር ሀገሮችን የኢኮኖሚ ዕድገት ያፋጥናል ተብሎ ሲሰጥ የቆየው "እርዳታ" የእነዚህን ሀገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት ማፋጠን ቀርቶ ጨርሶ በመግታቱ እርዳታው በእርግጥ ለኢኮኖሚ ዕድገት ሊውል የሚችል በትን መንገድ መቀየስ ማስፈለጉንና 3ኛ/ ነፃ መንግሥታት ያለምንም ተፅዕኖ በክልላቸው ሥር ያለውን ማናቸውንም የተፈጥሮ ሀብት ለራሳቸው ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት በሚያመች መንገድ ሊጠቀሙበት የመቻል መብታቸው እንዲረጋገጥ የሚጠይቁ ናቸው ።

አዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት አጠቃላይ ፕሮግራም በጥሬ ዕቃና በኢንዱስትሪ ውጤቶች መካከል ያለው የተራራቀ የዋጋ ልዩነት ሲስተካከልና ሥርዓት ሲይዝ የሚችልበት የውጭ የኢኮኖሚ ግንኙነት ፣ ግንኙነቱም ለሚመለከታቸው ሀገሮች የጋራ ጥቅም ሊውል የሚችልበትን ፣ ለውጭ ንግድ የሚቀርቡ ጥሬ ዕቃዎች መጠባበቂያ ክምችት (Buffer Stock) የሚያዝበትንና ይህንንም ክምችት ለመያዝና ወጪውን ለመሸፈን የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋትን የሚያጠቃልል ነው ።

በአጠቃላይ አዲሱን ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት በሚመለከት በብዙ ዓለምአቀፍ ጉባኤዎች ላይ የተላለፉ ውሳኔዎችና ከዚህም አንፃር ሲካሄድ የቆየው ትግል አሁን ያለው ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ለኋላቀር ሀገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት ፣ ኢኮኖሚያቸውን ለዕድገት አመች በሆነ መንገድ በአዲስ ለማዋቀር እስቸኳይ መፍትሔ የሚሻ ነው ። ረሀብን ፣ ድህነትንና ሌሎች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮችን ለመፍታት አመች ሆኖ ባለመገኘቱ ይህን ሁኔታ መለወጥ አስፈላጊ መሆኑን የሚያመለክት ፕሮግራም ነው ።

የአዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ፕሮግራም መሠረታዊ ድክመት ይህንኑ ጉዳይ በሚመለከት የሚካሄደው ትግል

በዓለምአቀፍ ደረጃ ብቻ እንጂ ከእያንዳንዱ ኋላቀር ሀገር ውስጣዊ ሁኔታ ጋር ማለትም በእያንዳንዱ ኋላቀር ሀገር ውስጥ መከናወን ካለበት ዲሞክራሲያዊና ተራማጅ ለውጥ ጋር መቀናጀት እንደሚገባው አለመገንዘቡ ነው ። ፕሮግራሙ በኋላቀር ሀገሮች ውስጥ ያሉትን የችግሮቹን መንሥኤዎች በሚገባ አላገናዘበም ፤ ስለዚህም በእያንዳንዱ ኋላቀር ሀገር ውስጥ ለማኀበራዊ ዕድገት አስፈላጊ የሆነው መሠረታዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ተገቢ ትኩረት አልተሰጠውም ።

ባጠቃላይ እኩልነትና ፍትህ የሰፈነበት አዲስ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ለመመሥረት የሚደረግ ዓለምአቀፍዊ ጥረት በብሔራዊ ደረጃ እኩልነት የሰፈነበት ማኀበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ለመመሥረት ከሚደረግ ትግል ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃም የሁሉንም ሀገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት በመጐተት ረገድ ከፍተኛ ሚና የሚጫወተው የጦር መሣሪያ አሽቅድምድምንና የጦርነት ዝግጅትን በጥብቅ ከመቃወም ፣ ለሰላምና ለማኀበራዊ ዕድገት ለመታገል ከቆመ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል ተነጥሎ ሊታይ አይችልም ።

## አድኃሪ
*(Reactionary)*

ምንጩ አድኀረ የሚለው የግዕዝ ቃል ነው ። ትርጓሜውም አቆየ ፣ አስቆየ ፣ አዘገየ ማለት ነው ። ድኀረ ሲል ኋለኛ ፣ የኋላ ፣ የመጨረሻ ፣ ድኅር ሲል ደግሞ መቆየት ፣ መዘግየት፣ ማፈግፈግ ፣ ኋላ መቅረት ፣ በማናቸውም ነገር የመጨረሻ መሆን ማለት ይሆናል ። ከዚህም የወጣው አድኃሪ የሚለው ቃል በነጠላ ትርጉሙ ፣ ኋላቀር ፣ ጐታች ማለት ነው ።

ሰፋ ባለ ትርጉሙ አድኃሪ በኅብረተሰቡ የዕድገት ሂደት ውስጥ ለውጥን የማይሻ ወይም የሚቃወም ለጨቋኝ ፣ ለበዝባዥና ለአሮጌ ሥርዓት ሀልውና የሚሟገት ፣ የጊዜው ሁኔታ ዕድገትን ፣ እርምጃንና ለውጥን ሲጠይቅ ይህን የታሪክ ሂደት በአቋምና በድርጊት ለማቆምና ለመግታት የሚጥር ግለሰብ ፣ ቡድን ፣ ድርጅት ወይም የፍልስፍና ዘርፍ ማለት ነው። አንድ ሥርዓተ ማኀበር ወደተሻለውና ከፍ ወደአለው ሥርዓተ ማኀበር በሚደረገው ሽግግር ለአረጀውና ለአፈጀው ሥርዓተ ማኀበር የሚቆም ነው ፤ ለምሳሌ የካፒታሊዝም ሥርዓተ ማኀበር የዕድገት ሂደት በአከተመበት በአሁኑ ዘመን ለእኩልነት ፣ ለነፃነትና ከብዝበዛ የተላቀቀ ኅብረተሰብ ለመመሥረት አስፈላጊነቱና ተግባራዊነቱ የተረጋገጠለትን ሶሻሊዝምን የሚቃወም ኃይል አድኃሪ ነው ።

ከመደብ አንፃር አድኃሪ አቋም ፣ ተግባርና አስተሳሰብ የበዝባዦችን ጥቅምና የበላይነት ከመጠበቅ ፍላጐት የሚመነጭ ሲሆን በግለሰብ ደረጃ ደግሞ ከንቃት ዝቅተኝነትና ከትክክለኛ ግንዛቤ ጉድለት ሊመጣ ይችላል ፤ ለምሳሌ አንድ ጭቁን ግለሰብ በዝባዥ የገዥ መደብ ባሰረፀበት አጉል ርዕዮተዓለም ለእርሱ የሚበጀውን ለውጥ ባለማጤን አድኃሪ አመለካከት ሊኖረው ወይም አድኃሪ አቋም ሊወስድና በተቃዋሚነት ሊቆም ይችላል ማለት ነው ።

(ተራማጅን ይመለከቷል ።)

## አድራጊ—ተደራጊ
*(Subject - Object)*

አድራጊ በፍልስፍና ትርጉሙ የዕውቀት ማረፊያ ወይም ባለቤት ማለት ሲሆን ተደራጊ ደግሞ ከፊት ለፊት ያለ ለሐሳብ ፣ ለዕውቀት የቀረበ ማለት ነው ።

ጽንሰ ሐሳቦቹ የሚገልጹት የዕውቀትን የማይነጣጠሉ ሁለት ክፍሎች ነው ። ያለ ታዋቂው አዋቂው ፣ ያለአዋቂው ታዋቂው ሊኖር እንደማይችል ሁሉ የአድራጊና የተደራጊ ግንኙነት የዕውቀት መከሰቻ አስፈላጊ ግንኙነት ነው ።

ሁለቱም ክፍሎች የተያያዙና የማይነጣጠሉ ቢሆኑም የተለያየ ጠባይ አላቸው ። አድራጊ ከርሱ ውጭ ያለውን ሁኔታ በኅሊናው ውስጥ ለራሱ የሚያቀርብና የሚቀርፅ ፣ እኔ የሚልና ኅሊናዊ ነው ። ከራሱ ውጭ ለመውጣት የማይችል ፣ ከነገሮች ጋር በቀጥታ የማይዋሀድ ነገር ግን የነርሱን ምስል በውስጡ የሚቀርፅና ወደሐሳብ የሚለውጥ ነው ። ተደራጊ ግን ከአድራጊ ውጭ የሚገኝ ፣ በውጫዊ አቀማመጡ ለግንዛቤ የቀረ

በና የግንዛቤም መነሻ ምክንያት የሆነ ነው ። ስለርሱ የሚቀረፅ ግንዛቤ እርሱን የሚያመለክት እንጂ እርሱን የሚተካ ወይም ህልውናውን የሚያሳጣ አይደለም ። ለምሳሌ ሰው (አድራጊው) ወንበርን (ተደራጊውን) የሚያውቀው የወንበሩን ምስል በአእምሮው ውስጥ በመቅረፅ እንጂ ከወንበሩ ጋር በመዋሃድ አይደለም ። ወንበሩ ደግሞ ከሰው ውጭ የሚገኝ ፣ ሊታወቅ የሚችል ፣ ስለርሱም ለሚቀረፀው ዕውቀት መነሻ ምክንያት ሲሆን በሰዎች አእምሮ ውስጥ የርሱ ምስል መቀረፁ ግን ህልውናውን የሚያሳጣው አይደለም ።

ተደራጊው ከሐሳብ ውጭ የራሱን ህልውና መጠበቁና ነፃ መሆኑ እንዲያውም አድራጊው በተደራጊው ሕግጋት (ዕውቀት) መገዛቱ ፣ ማናቸውም ነገር ከሐሳብ የመነጨና በሐሳብ የሚገዛ ነው ከሚለው ሐሳባዊ አቋም ጋር ይጋጫል ። በመሆኑም ሐሳባዊ ፍልስፍና በተለያዩ ዘዴዎችና አቀራረቦች በመጠቀም ተደራጊውን የአድራጊው ውጫዊ ነፀብራቅ አድርጎ ለማቅረብ ይሞክራል ። የዕውቀትም ተልዕኮ የተደራጊውን የይስሙላ ውጫዊ ህልውና ማለፍ ወይም መሰረዝ ይሆናል ። ተደራጊው ታወቀ ማለት በሐሳብ ሕግጋት እንፃር ተጣርቶ ወደሐሳብ ተመላሽ ሆነ ፤ ወደ ሐሳብ ተለወጠ ፤ ትክክለኛ ወይም እውነተኛ መልኩን አገኘ ማለት ነው ።

በማርክሳዊ ፍልስፍና መሠረት ዕውቀት የተደራጊውን ነፃ ህልውና ከመጠበቁም በላይ ዕውቀት የተደራጊው ነፀብራቅና በርሱም የሚገዛ መሆኑን ይቀበላል ። ተደራጊው ከአድራጊው ጋር የሚዛመደው በዕውቀት ኃይል ሳይሆን በሰው የሥራ ኃይል ነው ። የሥራ ቁሳዊ ኃይል ተደራጊውን ለሰው ፍላጐት ተስማሚ በሆነ መንገድ ይቀርፃል ። ስለዚህም የአድራጊና የተደራጊ ግንኙነት በዕውቀት ላይ ብቻ የተመሠረተ ሳይሆን ግንኙነቱ በመጀመሪያ ደረጃ ላይ የተግባር ግንኙነት ነው ።

በሁለቱም መካከል ያለው ግንኙነት ዲያሌክቲካዊ በመሆኑ አድራጊው በተደራጊው ላይ የበላይነት የለውም ። የተደራጊው ከአድራጊው ውጭ መኖር አድራጊው ተደራጊውን ፈላጊ ያደርገዋል ። ከዚህም ፍላጐት እንፃር ሲታይ ነው ነገሮች ለአድራጊው ተደራጊ የሚሆኑት ። አድራጊው በሥራ ኃይል በመጠቀምና በዕውቀት በመረዳት ፍላጐቱን ለማርካት ተስማሚ በሆነ መንገድ ተደራጊውን ይቀይራል ።

አድራጊው ተደራጊውን በዕቅዱ መሠረት እንደሚቀይረው ሁሉ ፣ የዕቅድ በሥራ መተርጐም አድራጊውን የነባራዊ እውነታ ባሕርይ ይሰጠዋል ። ለምሳሌ አንድ አናጢ ወንበር ሲሠራ በአንድ በኩል የወንበሩ ተፈላጊነት የአድራጊውን ውስጣዊ ፍላጐት የሚገልጽ ሲሆን በሌላ በኩል የሚያስፈልጉትን ጥሬ ዕቃዎች አቅርቦ በሥራ አማካይነት በዕውቀት እየተረዳ ጥሬ ዕቃዎቹን ወደ ወንበርነት ሲቀይር ፍላጐቱን ነባራዊ ያደርገዋል ።

(ዕውቀትን ፣ ተግባርን ፣ ነባራዊ ሐሳባዊነትን ፣ ኅሊናዊ ሐሳባዊነትን ይመለከቷል ።)

## አድራጎታ ዊነት
(*Behaviourism*)

የሰውንና የእንስሳን ድርጊት ተናክአታዊ በሆነ መንገድ የሚገነዘብ ማለትም ድርጊት የውጭ ግፊቶች በአካሎቻቸው ላይ የሚያሳርፉት ተፅዕኖ አጸፋ ነው ብሎ የሚተረጉም በገቢርነት ላይ የተመሠረተ የዘመኑ ሥነ ልቡና አዝማሚያ ነው ። የሰዎች አድራጎትና ሥነ ልቡናዊ ክስተቶች የሚወሰኑት በአካሉ ልዩ ልዩ ክፍሎች እንቅስቃሴ ነው ይላል ።

የአነሣሡም ምክንያት በ20ኛው ምዕት ዓመት በእንስሳት ሥነ ልቡና ተመራማሪዎች ላይ የምርምርና የሙከራ ጥናት ያሳደረው ከፍተኛ ግፊት ነው ። እንስሳትን ለማጥናት ፓቭሎቭ የተጠቀመበት ዘዴና ያገኘው ጥናታዊ ውጤት የሰዎችን ሥነ ልቡና ለማጥናት ያገለግላል በማለት አድራጎታውያን ኅሊናንና አድራጎትን አንድ በማድረግ ተናክአታዊ የሆነ አተረጓጐም ሰጥተዋል ። ይህም ማለት ማንኛውም አድራጐት ሳይታሰብና በውጭ ተፅዕና የሚከናወን ተደርጎ በመወሰዱ የሰው አንጐል ያለውን የማሰላሰል ሚና ዝቅ ያደርገዋል ።

## አድርባይነት
(*Opportunism*)

በሠራተኛው መደብ እንቅስቃሴ ውስጥ በንድፈ ሐሳብና በተግባር የሠርቶ አደሩን መሠረታዊ ፍላጐት በጥቂት ጊዜያዊ ጥቅሞች ለቡርዧዚው አሳልፎ የመሸጥና በመራራ ትግል ለሚከፈል መሥዋዕትነት ዝግጁ ያለመሆን አድኃሪ አዝማሚያ አድርባይነት ይባላል ።

አድርባይነት እርስ በርሳቸው የተያያዙ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ምንጮች ያሉት ከስተት ነው ። ኢኮኖሚያዊ ምንጩ ከካፒታሊዝም ዕድገት ጋር የተያያዘ ሲሆን ካፒታሊዝም ወደ ሞኖፖል ካፒታሊዝም ወይም ወደ ኢምፔሪያሊዝም ደረጃ በሚያድግበት ጊዜ ከቅኝ ግዛቶች በሚያጋብሰው ከፍተኛ የሞኖፖል ትርፍ የሠራተኛውን መደብ መሪዎች በገንዘብ በመደለል በአኗኗራቸው፣ በገቢያቸውና በአመለካከታቸው ከሠራተኛው የተነጠሉ "የወዝአደር መሳፍንት" በመፍጠር የጥቅሙ ማስከበሪያና የብዝበዛው መሣሪያ ያደርጋቸዋል ።

የአድርባይነት ማኅበራዊ መሠረቱ ሌኒን እንዳለው የሠራተኛው መደብ እንቅስቃሴ በየጊዜው እየሰፋ መሄድ ከተለያዩ መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች በሠራተኛው ድርጅቶች ውስጥ የንዑስ ከበርቴውን ሥነ ልቡናዊ አመለካከቶች ማለትም የወላዋይነት ፣ የትዕግሥት የለሽነትና ለድርጅታዊ ዲሲፕሊን ተገዥ የአለመሆን ባሕርዮችን ይዞ መምጣት ነው ።

ከፖለቲካው አኳያ በሥልጣን ላይ ያለው አድኃሪ መንግሥት የሚወስደው አቋም ለአድርባይነት ሌላው መንሥኤ ነው ። ቡርዧዚዎች የአገዛዛቸውን ሥርዓት በመጠጋገን የካፒታሊዝምን ዕድሜ ለማራዘም በሚያደርጉት ጥረት የቡርዧው መንግሥት መደባዊ ይዘት የሌለውና ከመደቦች በላይ በመሆን ለመላ ኅብረተሰብ የጋራ ጥቅምና ደኅንነት እንደቆመ አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ ። ይህም ሁኔታ በሕዝቡ ዘንድ ካፒታሊዝም መልኩን እየለወጠ ቀስ በቀስ ወደ ሶሻሊዝም የሚሸጋገር የሚያስመስል በመሆኑ ለአድርባይነት መነሻ ይሆናል ።

አድርባይነት በጥቅሉ ፀረ ወዝአደር አቋም ያለው አድኃሪ መሥመር ሲሆን በሁለት መልኮች ይንፀባረቃል ። እነዚህም የቀኝና "የግራ" አድርባይነት ናቸው ። የቀኝ አድርባይነት በቡርዧዚዎች እግር ለመተካት የሚፈልገው የንዑስ ከበርቴው መደብና የሞኖፖል ቡርዧ ቡችሎች የሆኑ ከሃዲ "የወዝአደር መሳፍንት" የሠራተኛውን አብዮታዊ ትግል በአንዳንድ ጥገናዊ ለውጦች ለመግታትና የቡርዧው ፍላጐት ተገዥ እንዲሆን ለማድረግ የሚጥሩበት የአድርባይነት አንዱ ገጽታ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ "የግራ" አድርባይነት ሠራተኛው በእያንዳንዱና በተለየ ታሪካዊ ወቅት መውሰድ ያለበትን ተግባራዊ እርምጃ በሚገባ ሳያጤን በማንኛውም ሁኔታ ቀጥተኛና አስቸኳይ እርምጃ እንዲወስድ ይጋብዛል ። የ"ግራ" አድርባይነት ለረዥም፣ ውስብስብና መሥዋዕትነት ለሚጠይቅ ትግል ዝግጁ ባለመሆን ፣ ለዚህም ትግል ሰፊውን ሕዝብ ለማንቃትና ለማደራጀት ትዕግሥት በማጣት፣ ሁሉን ነገር ተጨባጭ ሁኔታው ከሚፈቅደው ውጭ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማከናወን በስሜት ብቻ ይነሣል ። አብዮታዊ ተግባርንም ግራ ለበስ ሐረጐችን ብቻ በማነብነብ አድርባይነትን እንታገላለን በሚል ከንቱ ቅዠት ፣ በማንኛውም ሁኔታ በሕጋዊ መድረክ ባለመካፈልና ምንም ዓይነት ድርድር ባለመቀበል አመፅን ፣ ያውም የጥቂት ግለሰቦችን ወይም ቡድኖችን ሴራ እንደብቸኛ የትግል ዘዴ በመውሰድ አብዮታዊውን ፓርቲ ከሕዝቡ የሚነጥል ጀብደኛ አቋም ነው ።

የቀኝም ሆነ የ"ግራ" አድርባይነት በስምና በቅርፅ የሚለያዩ ቢሆንም አንድ ዝርያ የሆኑና ለአንድ ሕዝባዊ አብዮት ካላቸው አደገኛነት አንፃር አንዱ ከሌላው ይሻላል የማይባሉ ናቸው ። ሁለቱም የመደብ ትግልንና የሶሻሊስት አብዮትን አስፈላጊነት ፣ የሠራተኛውን መደብ የመሪነት ሚና ፣ የማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲን ርዕዮተዓለማዊና ድርጅታዊ መርሆች የሚክዱና በወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት ቦታ የቡርዧ ብሔረተኝነትን የሚቀበሉ የካፒታሊስቱን ሥርዓት የብዝበዛና የጭቆና ዕድሜ የሚያራዝሙ ናቸው ።

## አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበር (የ—)
*(Service Cooperatives)*

በግብርና ሙያ ለተሰማሩ አርሶ አደሮችና የእደ ጥበብ ባለሙያዎች ለኑሮና ለምርት

ማስፋፊያ የሚያስፈልጓቸውን ዕቃዎች ፣ ሽቀጣ ሽቀጦች እንዲሁም የገበያ ፣ የብድርና የቁጠባ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚቋቋም ሁለገብ የኅብረት ሥራ ማኅበር ነው ።

በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የተቋቋሙት የአገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ዓይነ ቶች ሁለት ሲሆኑ እነሱም የገበሬዎችና የእደ ጥበብ ባለሙያዎች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ናቸው ።

የገበሬዎች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበር ቁጥራቸው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የቀበሌ ገበሬ ማኅበራት በውስጣቸው ለሚገኙ ገበሬዎች ለኑሮና ለሥራ የሚያስፈ ልጉ አገልግሎቶችን ለማበርከት የሚያቋቁሙት ድርጅት ነው ። የአገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበር አባል የሚሆኑትም የቀበሌ ገበሬ ማኅበራት ናቸው ።

የገበሬዎች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበር በተሻሻለ ዘርና ማዳበሪያ ለመጠቀም፣ ልማዳዊ የግብርና አሠራር አዲስ መልክ ይዞ በዘመናዊ መንገድ እንዲራመድ ለማድ ረግ ፣ ለኑሮ ማሻሻያና ለእርሻ ሥራ ማስፋ ፊያ ብድር ለማግኘት ፣ ምርትን በተሻሻሉ ጐተራዎች አከማችቶ ለገበያ ለማቅረብ ፣ ለዕለት ኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን ሸቀጣ ሸቀ ጦችና አገልግሎቶች ከብዝበዛ ነፃ በሆነ መን ገድ ለማግኘት ፣ ገበሬዎች የመቆጠብ ልምድ እንዲኖራቸውና ከሚያገኙት ገቢ ለማጠራ ቀም እንዲችሉ ለመርዳት የሚያቋቁሙት ድርጅት ነው ። ማኅበሩ ከሥራው እንቅስቃሴ ከሚያገኘው ገቢ በአባል ገበሬ ማኅበር ውስጥ የሚቋቋሙ የገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት እየተጠናከሩ የሥራ ይዞታ ቸው እንዲስፋፋና የአባሎች ቁጥርም እየ ጨመረ እንዲሄድ የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ በመስጠት ፣ አባል የሆኑ የገበሬ ማኅበራትም ወደ አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲ ለወጡ በማገዝ ክፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክ ታል ።

የእደ ጥበብ ባለሙያዎች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበር ደግሞ የእደ ጥበባት ባለሙያዎች የጥሬ ዕቃ ፣ የማምረቻ መሣሪያ ፣ የገበያ ፣ የብድርና የመሳሰሉትን አገልግሎቶች ከብዝበዛ ነፃ በሆነ መንገድ ለማግኘት እንዲ ችሉ የሚያቋቁሙት ድርጅት ነው ። የእደ ጥበባት ባለሙያዎች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበር ለአባሎቹ ትምህርት በመስጠ ትና በማኅበር የመሥራትን ጥቅም በማሳ ወቅ አባላቱ ወደ እደ ጥበባት ባለሙያዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲሸ ጋገሩ ይረዳል ።

(የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ይመለከቷል ።)

## አንዳኝነት

*(Parallelism)*

ነፍስና ሥጋ ጐን ለጐን ግን በቀጥታ ሳይገናኙ በእኩልነት ይኖራሉ የሚል የሐ ሳባዊ ፍልስፍና አመለካከት ነው ። ካርቴዥያኒዝም ሐሳብንና ቁስአካልን ለይቶ ካስቀመጠ በኋላ በሁለቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ሳይወስን መተዉ ለአንዳኝነት መከሰት ምክንያት እንደሆነ ይታመናል ። ነፍስና ሥጋ በአንድ በኩል የተለያዩ ሲሆኑ በሌላ በኩል ግን በአንዱ ላይ የሚደርሰው ሁኔታ በሌላው ላይ ይንፀባረቃል ። ችግሩ ሁለቱ የተለያዩ በመሆናቸው በመንሥኤና በተገብሮት ግንዛቤ ይህንን ሁኔታ በቀጥታ ለመግለጽ ያለመቻሉ ነው ።

አንዳኝነት የነፍስንና የሥጋን ልዩነት በመቀበል በሁለቱ መካከል ምክንያታዊ ግን ኙነት የለም ይላል ። በእርግጥ በነፍስ ላይ የሚደርሰው ማንኛውም ሁኔታ በሥጋ እን ቅስቃሴ ይተረጐማል ፤ ሆኖም ሁኔታው የሚ ገኘው አንዱ በሌላው ላይ ባለው ቀጥተኛ ግንኙነት ወይም ንክኪት ሳይሆን ሁለቱም በተናጠል ነገር ግን በተቀነባበረ ሁኔታና በፕሮግራም ስለሚሠሩ ነው ። ሁለት የተለ ያዩ ሰዓቶች በእኩል ሰዓት ላይ ከተሞሉ ሳይነካኩ የሚያሳዩት ያው ተመሳሳይ ጊዜ እንደሚሆን ሁሉ ነፍስና ሥጋም እንዲሁ በአ ንድ ዓይነት አሠራር የሚንቀሳቀሱ ናቸው ይላል ። ሥጋ ሲታመም ነፍስ ይሠቃያል ፤ ነፍስ ሲደነግጥ ሥጋ ይንቀጠቀጣል ። እንደ አንዳኝነት አባባል ይህ የሚያሳየን ሁለቱ ሳይነካኩ ያንኑ ሁኔታ ካላቸው ጠባይ እንፃር እንደሚገልጹ ነው ።

ከላይ በተገለጸው አመለካከት መሠረት አንዳኝነት እንድ ዲበኩሉ ኃይል ወይም ፈጣሪ መጠየቁ አልቀረም ። ምክንያቱም ነፍስና

ሥጋ ሳይነካኩ በፕሮግራም እንዲሠሩ ሊያደርግ የሚችለው አንድ የሆነ ኃይል አቀነባብሮ ማስቀመጥ ስለሚኖርበት አንዳኝነት በቀጥታ የሐሳባዊነቱን ባሕርይ ይገልጻል ። አስተሳ ሰቡም የተዛባ መሆኑ በቀላሉ የሚታይ ነው ። በአንድ በኩል ሥጋን ቀጥተኛ የነፍስ ተገዥ ባለማድረጉ የሥጋን ነፃ ህልውና ሲቀበል በሌላ በኩል ነፍስም የራሱ ነፃ ህልውና እንዳለው ተደርጐ ሲወሰድ ሁለቱም ተመጣጣኝና እኩል ስለሚሆኑ ዋናው ወይም ወሳኙ የትኛው እንደሆነ ለመለየት አይሞክርም ። በመሆኑም አንዳኝነት የሰውን ማለትም የነፍስንና የሥጋን አንድነት ማሰብ ይሳነዋል ። ደግሞም ነፍስና ሥጋ የሚገልጹት ያው አንድ ነገር ከሆነና አንዱ ከሌላው የሚጨምረው ነገር ከሌለ ጠቃሚነት የሌለው ድግግሞሽ ይሆናል ።

ይህ ድክመት የሚያሳየው በአንዳኝነት ውስጥ የዲያሌክቲካዊ አመለካከት አለመኖርን ነው ። የሥጋ ወሳኝነት በተለይም ነፍስ ውስጥ የሚቀረፁ ሐሳቦችና ስሜቶች የሥጋና የቁሳዊ ኑሮ ሁኔታ ነፀብራቅ መሆናቸውን ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ያስተምራል ። ከዚህ ተነሥቶ ነፍስ በሐሳብ መልክ የሚገልጸው ሁኔታ በንቁነቱ ለተግባራዊ እንቅስቃሴ ዓይነተኛ ድጋፍ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል ። ነፍስና ሥጋ ባይነካኩ የሚጓዙ ሳይሆን ነፍስ ወይም ኅሊና የሥጋችን ክፍል የሆነው የአንጐላችን እንቅስቃሴ ውጤት መሆኑንና ሥጋም ወሳኝነት እንዳለው እንገነዘባለን ። ነፍስ ደግሞ ሁኔታዎችን በማንፀባረቅ ዕውቀትን በመፍጠር ለተግባር ንቃተ ኅሊና ይሰጣል ፣ ለዋጭ ኃይልም ያደርገዋል ።

(መንፈሳዊነትን ፣ ሁለታዊነትን ፣ ሐሳብን ፣ ተግባርን ፣ ንቃተ ኅሊናን ይመለከቷል ።)

## አጠቃላይ ማኅበራዊ ምርትን የማጣራት ችግር

*(Problems of Realization of Gross Social Product)*

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ካፒታሊስቶች የምርት መገልገያዎችን ገዝተውና ሠራተኞችን ቀጥረው ምርት እንዲመረት ያደርጋሉ ። ከዚህ በኋላ የተመረተው አጠቃላይ ማኅበራዊ ምርት ለልዩ ልዩ ክፍሎች ተሸጦ ጥቅም ላይ መዋል አለበት ። ካፒታሊስቶቹ የማምረት ተግባር እንዲቀጥል ለማድረግ ችሎታና ፍላጐት የሚኖራቸውም ቀደም ሲል ያስመረቱትን ሸቀጥ ወደ ገንዘብ ሊለውጡ ሲችሉ ብቻ ነው ። ይህ የአጠቃላይ ማኅበራዊ ምርት ልዩ ልዩ ክፍሎች በእሴትና በቁሳዊ መልክ የሚተኩበትን ዘዴ ከመሸቱ ማለትም ገዥ አግኝተው ለምርት መገልገያ ዎችና ለፍጆታ ዕቃዎች ያለውን ፍላጐት ከማሟላታቸውና በአጠቃላይ የማኅበራዊ ምርት እርባታ መካሄዱን ከማረጋገጡ ጋር የተያያዘው ጉዳይ አጠቃላይ ማኅበራዊ ምርትን የማጣራት ችግር ይባላል ።

በካፒታሊስት ሥርዓት አጠቃላይ ማኅበራዊ ምርት ሙሉ በሙሉ ገዥ አግኝቶ በጥቅም ላይ እንዳይውል የሚያደርጉ ችግሮችና ከእነዚህም ጋር የተያያዙ ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች በየጊዜው ይደርሳሉ ። በካፒታሊስቱ ሥርዓት እያንዳንዱ ካፒታሊስት ምን መመረት እንዳለበትና በምን ያህልስ መጠን መመረት እንዳለበት የሚወስነው በዚህ ረገድ ሌሎች ካፒታሊስቶች የወሰኑትን ሳያውቅ ትርፍ ለማግኘት በብሔራዊ ደረጃ ቅንጅት በሌለው ዓላማ በመነሣሣት ብቻ ነው ። በካፒታሊስት ሥርዓት በብሔራዊ ደረጃ በዕቅድ የሚመራ የምርት አደረጃጀት ባለመኖሩ የኢኮኖሚው እንቅስቃሴ በአጠቃላይ ሥርዓት አልባ ይሆንና የሚመረተው ሸቀጥ መጠን ከኅብረተሰቡ ፍላጐት ጋር የማይጣጣም ይሆናል ። ይህም አለመጣጣም በተለይ በሚባባስበት ጊዜ የሚመረቱት ሸቀጦች በወቅቱ ተሸጠው የማምረት ተግባር በተፈለገው ደረጃ እንዳይቀጥል ዕንቅፋት በመሆን የኢኮኖሚ ቀውስ ያስከትላል ።

የምርት መገልገያዎች በሕዝብ በተያዙበትና የማምረት ዓላማ የሰፊው ሕዝብ ፍላጐት እርካታ በሆነበት በሶሻሊስቱ ሥርዓት የኢኮኖሚው ልዩ ልዩ ክፍሎች እንቅስቃሴ በብሔራዊ ደረጃ ከሚወጣ ዕቅድ ጋር ተገናዝቦ ስለሚካሄድ በመሠረቱ አጠቃላይ ማኅበራዊ ምርትን የማጣራት ችግር አይኖርም ።

## አጠቃላይ (ሁለንታዊ) የእሴት መልክ

(*General or Universal Form of Value*)

ቀላል የሸቀጥ ምርት እየተስፋፋ ሲሄድ በልውውጥ ውስጥ የሚገቡ ሸቀጦች እየበዙ ይሄዱና አንድን ሸቀጥ በቀጥታ በሌላ ሸቀጥ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሸቀጦችን በመሰወጥ ሂደት ውስጥ መሰናከል መፈጠር ይጀምራል ። ለምሳሌ በተስፋፋ የእሴት መልክ ወቅት አንድ በግ በተወሰነ ጥምርታ መጥረቢያን ፣ ጋቢን ፣ እንስራን ፣ ገብስን ወዘተ... ሊለውጥ ይችል ነበር ። ይህ ዓይነቱ ልውውጥ ሊከናወን የሚችለው ግን የገብሱም ፣ የመጥረቢያውም ፣ የጋቢውም ፣ የእንስራውም ባለቤቶች በግ ይፈልጋሉ በሚል መነሻ ነው ። ይሁንና መጥረቢያ ያለው ሰው የሚፈልገው ገብሱን ወይም ጋቢውን እንጂ በጉን ካል ሆነ ፣ ባለጋቢው የሚፈልገው እንስራውን ወይም ገብሱን እንጂ በጉን ካልሆነ ወዘተ... ልውውጡ ሊከናወን አይችልም ማለት ነው። ወደገበያ የሚገቡ ሸቀጦች ቁጥር እየጨመረ በሄደ መጠን ሸቀጥን በሸቀጥ የመለወጡ ሁኔታ አስቸጋሪ እየሆነ ይመጣል ።

ሸቀጥ አምራቾች የሚያመርቱትን ሸቀጥ በገበያ ውስጥ በተፈለገው መጠንና በማንኛውም ጊዜ በሚገኝ ሸቀጥ ለመለወጥ ይገደዳሉ ። ከጊዜ በኋላ ይህ ዓይነት ሸቀጥ የሚመረተው በራሱ የሰውን የተወሰነ ፍላጐት ለማርካት ሳይሆን አንድ የጋራ መገበያያ ሆኖ ለማገልገል ይሆናል ። እንደዚህ ዓይነት ሸቀጥ ቀስ በቀስ የሌሎችን ሸቀጦች እሴት መግለጽ ይጀምራል ። ይህም የብዙ ሸቀጦችን እሴት የሚገልጽ መገበያያ አጠቃላይ የእሴት መልክ ይባላል ።

የጋራ መገበያያ በመሆን የሚያገለግሉ ሸቀጦች በቀድሞ ጊዜ ከቦታ ቦታ የተለያዩ ነበሩ ። እንዳንድ ቦታ የቀንድ ከብቶች ይህንን ሚና ሲጫወቱ ሌላ ስፍራ ደግሞ እህል ፣ አሣ ፣ ከፀጉር የሚሠራ ልብስ በሀገራችንም አሞሌ ጨው ወዘተ... በተለያዩ ጊዜያት እንደ ሁለንታዊ የመገበያያ ሸቀጥ ወይም የእሴት መልክ ሆነው አገልግለዋል ። ለምሳሌ አንድ አሞሌ ጨው አንድ ጋቢ ወይም ሁለት እንስራ ወይም አንድ በግ ይለውጣል ማለት ነው ።

አጠቃላይ የእሴት መልክ ቀደም ሲል የተጠቀሰውን የተስፋፋ የእሴት መልክ መተካት በጀመረበት ጊዜ ሸቀጥን በሸቀጥ የመለወጥ ዘዴ አብቅቶ የሸቀጥ ዝውውር አማካይ ሆኖ በሚያገለግል ሸቀጥ አማካይነት ሁሉንም ሸቀጥ ለመግዛትና ለመሸጥ መቻል ይሆናል ።

## አፍላጦን

*(Plato)*

ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ427—347 የኖረ ፣ የምዕራባዊ ሐሳባዊ ፍልስፍና መሥራች በመሆን የታወቀ ታላቅ የግሪክ ፈላስፋ ነው ። ፍልስፍናው በይዘቱ የተሟላ ከመሆኑም በላይ አፍላጦን በነበረው የጽሑፍና የአቀራረብ ስጦታ በመጠቀም ለፍልስፍናው ማራኪ የሆነ መልክ ሰጥቶታል ። የደረሳቸው መጻሕፍት አብዛኛዎቹ በውይይት መልክ የቀረቡ ሲሆን ባቀራረባቸው የቴያትር መልክ የያዙ አሥቂኝ ወይም አስደናቂ(ድራማቲክ) ናቸው። ከነዚህ ውስጥም "ሪፐብሊክ"፣ "ጎርጂየስ"፣ "ፓርሚኒደዝ"፣ "ሶፊስት"፣ "ቴይቴይተስ" የተባሉት ይገኙበታል ።

አፍላጦንን ወደፍልስፍና እንዲያዘነብል ፣ ፍልስፍናንም ተረድቶ ታላቅ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ የገፋፋው ሶቅራጥስ ነው ። የሶቅራጥስ አስተምህሮ ሊማርከው የቻለው በጊዜው ከነበረው አስተሳሰብ ለየት ባለ ሁኔታ ዕውቀት የአነጋገር ስልትና የማታለል ዘዴ (እንደበተኛነት) ሳይሆን ለሰው ልጅ ደኅንነትና እውነተኛ ደስታ የሚጠቅም መጣሪያ ሊሆን ይችላል የሚል እምነት ስለነበረው ነው ። ሶቅራጥስ የጀመረውን የምርምር ዘዴና የቀየሰውን አዲስ የዕውቀት አቅጣጫ ከግብ ለማድረስ ሲል አፍላጦን ሊነሣሣ ችሏል ። በተለይም እውነት የግል ነው ፤ እውነት ማለት ለራስ የሚጠቅመውን አመዛዝኖና ለይቶ ሌሎችን በማሳመን በመንግሥት ሥልጣን አማካይነት ማስፈጸም ነው የሚለውን የአንደበታውያንን አስተምህሮ በመቃወም የእውነትን ሁለንታዊ ባሕርይ ለማሳወቅ ጥሯል ። በሌላ በኩል ከሱ በፊት የነበሩት ፈላስፎች የእውነታን መሠረትና የዓለምን ታዋቂነት አስመልክቶ የደረሱባቸውን አከራካሪ ሐሳቦች "በማረም" የነገሮችን ምንጭ ቁሳዊ ከሆን አካል ይልቅ ሐሳባዊ ከሆነ

አካል ዘንድ መፈለጉ ለዓለም ታዋቂነት ትክክለኛ መሠረት ይሰጠዋል በማለት የሐሳባዊነቱን አቅጣጫ አሳይቷል ።

አፍላጦንን ዝነኛ ያደረገው አንዱ አእምሮአዊ ፣ ሌላው ቁሳዊ የሆኑ በጠባይ የተለያዩ ሁለት ዓለሞች አሉ ብሎ መናገሩ ነው ። አእምሮአዊው ዓለም የማይለወጥ ፣ ረቂቅ ፣ ዘለዓለማዊና ሁለንታዊ ሲሆን ቁስአካላዊው ዓለም ግን ተለዋዋጭ ፣ አላቂ ፣ ግላዊና በሕዋሳት ደረጃ ብቻ የሚገለጽ ነው ። አፍላጦን ይህን ለማለት የበቃው የእውነትን ትክክለኛ ጠባይና መሠረት ለመግለጽ መሆኑን ይናገራል ። አንድ ነገር አላፊ ፣ ተለዋዋጭና ግላዊ ከሆነ እውነትነት ሊኖረው አይችልም ። ምክንያቱም እውነት ለሁሉም አንድና ከጊዜና ከቦታ ነፃ የሆነ የማይቀየር ጠባይ ያለው በመሆኑ ነው ። እንደአፍላጦን አባባል በእውነት ማመን አላቂና ተለዋዋጭ ከሆነው ከቁስአካላዊው ዓለም ውጭ ዘለዓለማዊና ቋሚ የሆነ ዓለም አለ ማለት ነው ። የዚህም ዓለም ታዋቂነት ሊረጋገጥ የሚችለው ግላዊ በሆኑ ቁስአካላዊ ነገሮች የተሠራ ሳይሆን ግንዛቤ በቀጥታ ሊግባባቸው በሚችል ሁለንታዊ ሐሳቦች የተገነባ ሲሆን ነው ። ቁስአካላዊው ዓለም እውን በመምሰል ቢያሳስትም ትክክለኛው ሁኔታ ግን የዘለዓለማዊው ዓለም የተለያየ ነፀብራቅ ወይም የተዛባ ግልባጭ መሆኑ ነው ። ለምሳሌ ሰው ስንል በሕዋሳት አማካይነት የምናየውን በቁመት ፣ በመልክና በሁኔታ የተለያዩ ግለሰቦችን ብቻ ማለታችን አይደለም ። ሰው እከሌ ሳይሆን ሁለንታዊ የሆነ ፣ ሊዳሰስ የማይችል ፣ ግለሰቦች ከሚያሳዩት ተለዋዋጭና ግላዊ ጠባይ የተላቀቀ ፣ የሰውን ዘለዓለማዊ ቅርፅ በሚገልጽ አእምሮአዊ ዓለም ውስጥ የሚመደብ ነባራዊ ሐሳብ ነው ።

እንደ አፍላጦን የዕውቀት ምንጭ ሐሳብ ሲሆን በሱ አባባል አእምሮአዊውን ዓለም በቀጥታ ለማወቅ የሚቻለን የሰው ነፍስ ሥጋ ከመልበሱ በፊት ይህን ዓለም የተመለከተ በመሆኑ ነው ፤ ነፍስ ሥጋ ሲለብስ ያየውን ስለሚረሳ ዕውቀት ማለት ማስታወስ ነው ሲልም ተናግሯል ። ስለዚህ ማስታወስ ዓይነተኛ ሥነ ምግባር ያስፈልገዋል ። ሥጋዊና አላፊ ለሆኑ ነገሮች ዋጋ አለመስጠት ከግላዊ ስሜት ወደ ሁለንታዊ አስተሳሰብ ለመሸጋገር የሚረዳን በመሆኑ ዲሲፕሊን ፣ ትክክለኝነትና መልካም ጠባይ ለዕውቀት መገኘት አስፈላጊ ናቸው ። ዕውቀትም መልሶ የሚያጠናክረው እነሱኑ ነው ። በፖለቲካ መስኩም ለአፍላጦን ትክክለኛ ወይም እውነት የሆነ መንግሥት ከግላዊ ጥቅም ነፃ በመሆን ለማንም ሳያዳላ በሕግ አማካይነት የኅብረተሰቡን ሁለንታዊ ጥቅም የሚያስከብረው ነው ። ይህም መንግሥት በምድር ሊከሰት የሚችለው ሥልጣንን ለትክክለኛ የመንግሥት ዓላማ ሊያውሉ የሚችሉ ፣ ከግል ጥቅም የተላቀቁ ፣ ለሁለንታዊው ብቻ ቅድሚያ የሚሰጡ ፈላስፎች ገዥ ሲሆኑ ነው በማለት ተናግሯል ።

አፍላጦን የኖረበት ጊዜ የግሪክ የባሪያ አሳዳሪ ሥርዓት ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ የገባበት ወቅት በመሆኑ ለዚህ ኅብረተሰብ ችግር መፍትሔ ለማግኘት ለአስመሳዮችና ለአታላዮች ሥልጣን መያዝ መሣሪያ የሆነውን የግሪክን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በማስወገድ በምትኩ ፍጹማዊ የሆነ ነገር ግን በዕውቀት ላይ የተመሠረተ በሁለንታዊነት የሚገዛ ትክክለኛ መንግሥት መመሥረት ነው በማለት ደጋግሞ ተናግሯል ። ይህ መንግሥት በኅብረተሰቡ ተቀባይነት አግኝቶ እውን እንዲሆን ዋናው መሣሪያ ትምህርት ነው በማለት ለመጀመሪያ ጊዜ የትምህርት ይዘት አሰጣጥና ቁጥጥር የመንግሥት ዋናው ጉዳይ መሆኑን ጠቁሟል ።

ሆኖም ይህ መንግሥት የሚመሠረተው በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ሳይሆን በግለሰቦች ተፈጥሮአዊ ችሎታ ላይ መሆኑና በአፍላጦንም አስተሳሰብ ሰዎች በተፈጥሮ በገዥና በተገዥ የተከፋፈሉ መሆናቸው የፍልስፍናውን መደባዊ ይዘት ያንፀባርቃል ። በሥነ ዕውቀት አመለካከቱ ከተጨባጩ ይልቅ ረቂቁ እውነትነት አለው ብሎ መናገሩ ፣ ስሜታዊና ሥጋዊ ጥያቄዎችን በዝቅተኛ ደረጃ መመልከቱ ፣ የሰውን ህልውናና ክብር በሐሳብ ውስጥ ብቻ ማስቀመጡ በአጠቃላይ ሲታይ ከጭቆና ሥርዓት የመነጨ አስተሳሰብ መሆኑ ግልጽ ነው ። በአንፃሩም የአፍላጦን አስተሳሰብ ቁስአካላዊ ዓለምን አስመሳይ ዓለም ማድረጉና ለቁስአካላዊ ጥያቄዎች ዝቅተኛ ግምት መስጠቱ ፣ የአእምሮ ሥራ የምርት ሥራ የበላይና ገዥ መሆኑን የሚያደ

ግፍ በመሆኑ ለመደባዊ አገዛዝ አመች አመለካከት የሚሰጥ ነው ።

(ሶቅራጥስን ፣ እንደበተኛነትን ፣ አርስጣጣሊስን ይመለከቷል ።)

## አፍሪካ ሶሻሊዝም (የ—)

*(African Socialism)*

በአህጉራዊነት ላይ የሚያተኩር በአፍሪካ ልምድ ፣ በጋርዮሽ ይዞታ ፣ በጐሳ ወይም በነገድ ኅብረተሰብ ላይ ተመሥርቶ ሶሻሊዝምን ለመገንባት የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው ።

ለዚህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ ዋናው ምክንያት የነጭ ወይም የቅኝ ገዥዎች ጥላቻ ነው ። ከነፃነት በኋላ ብዙ የአፍሪካ ሀገሮች መሪዎች በቅኝ ገዥዎች ላይ አድሮባቸው በነበረው ጥላቻ በመገፋፋት የካፒታሊስቱን ፈለግ ከመከተል ይልቅ ሶሻሊስት መሆንን መርጠዋል ። ለየሀገሮቻቸውም ተስማሚ መስሎ በታያቸው መንገድ ሶሻሊዝምን የዕድገት ፈለግ አድርገዋል ። በብዙ የአህጉሩ ክፍሎች ሶሻሊዝም የዕድገት ፈለግ ተደርጎ ቢወሰድም ዓላማው በተጨባጭ ግቡን ሊመታ አልቻለም ።

ለዚህ አለመሳካት የሚጠቀሱት ምክንያቶች እያሌ ቢሆኑም ሕዝቡን የሚመራ ፓርቲ አለመኖሩ ፣ ሕዝቡ ከማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተዓለም ጋር እንዲተዋወቅ ከማድረግ ይልቅ የሃይማኖትና የጎሳ እምነት እንዲከተል መደረጉ ፣ በአመራር ላይ ያሉት ግለሰቦች ለሶሻሊዝም ያላቸው ታማኝነት አፍአዊ ሆኖ መቅረቱ ናቸው ።

ሶሻሊዝም በይዘቱ ዓለም አቀፋዊ ሲሆን ንድፈ ሐሳባዊ መመሪያውም ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ነው ። ከዚህ ውጭ የሚገነባ ሶሻሊዝም በተግባር የማይገለጽ የይስሙላ ሶሻሊዝም ነው ። በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ላይ ያልተመሠረቱት እንደአፍሪካ ሶሻሊዝም ዓይነቶቹ ግባቸውን መምታት የተሳናቸውም ይህ ሳይንሳዊነት ስለሚጎድላቸው ነው ።

## አፍሪካ አንድነት ድርጅት (የ—)

*(Organization of African Unity)*

በግንቦት 1963 በአዲስ አበባ ከተማ በተካሄደው ነፃ የአፍሪካ ሀገሮች ስብሰባ የተቋቋመ አህጉራዊ ድርጅት ነው ። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በአሁኑ ጊዜ 51 አባል ሀገሮች ያሉት ሲሆን በአፍሪካ ውስጥ ያሉ የብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴዎችም በተመልካችነት በሥራው እንቅስቃሴ ይሳተፋሉ ።

የድርጅቱ ዋና ዓላማዎች የአፍሪካን ሀገሮች አንድነትና ትግል ማጠናከር ፣ ተግባሮቻቸውን በማስተባበር በመካከላቸው ያለውን ትብብር ማዳበር ፣ የእያንዳንዱን አባል ሀገር ብሔራዊ ልዕልናና የግዛት አንድነት ማስከበርና ነፃነቱን ማስጠበቅ ፣ በመላው አፍሪካ የቅኝ ግዛትነት ሥርዓትን መደምሰስና በአባል ሀገሮች መካከል ዓለምአቀፍ ትብብር እንዲጠናከር ማድረግ ናቸው ። ለነዚህ ዓላማዎች ግብ መምታትም የድርጅቱ አባል ሀገሮች በውጭ ፖሊሲ ፣ በኢኮኖሚ ፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ፣ በመከላከያና በደኅንነት ፣ በትምህርት ፣ በባህልና በጤና ጥበቃ እንቅስቃሴዎቻቸውን ለማስተባበር ተስማምተዋል ።

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በአባል ሀገሮች መካከል የእኩልነት መረጋጋትን ፣ በአባል ሀገሮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባትን ፣ የግዛት አንድነትና ነፃነት ማክበርን ፣ ቅራኔዎችን ሰላማዊ በሆነ ውይይት መፍታትን ፣ በአፍሪካ የሚገኙትን የብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴዎች መርዳትንና የገለልተኝነትን መርህ ማራመድን ያበረታታል ።

ድርጅቱ ለነፃነታቸው የሚዋጉትን የአፍሪካ ሕዝቦች ለመርዳት በአቋቋመው የነፃነት ኮሚቴ አማካይነት ብዙ አስተዋጽኦ ከማድረጉም በላይ አባል ሀገሮች ከበጀታቸው አንድ በመቶውን ለዚሁ ጉዳይ ለማዋል ቃል ገብተዋል ። በአፍሪካ ሀገሮች መካከል የኢኮኖሚ ትብብር ለማጠናከርም በድርጅቱ እርዳታ የአፍሪካ ልማት ባንክና የኢኮኖሚ ዕድገትና ፕላን ተቋም ተመሥርቷል ። ድርጅቱ በአባል ሀገሮች መካከል የሚነሡትን ግጭቶችና ቅራኔዎች ለመፍታት

የተለዩ አስታራቂ ኮሚቴዎችን በማቋቋም ብዙ የተሳኩ ድርጊቶችን አከናውኗል ። ድርጅቱ ለነፃነታቸው ይታገሉ የነበሩትን የፖርቱጋል ቅኝ ግዛቶችንና የዚምባብዌ ታጋዮችን በመርዳትም ነፃነታቸውን እንዲቀዳጁ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ። በአሁኑ ጊዜም የናሚቢያ የነፃነት እንቅስቃሴና የደቡብ አፍሪካ ሕዝብ በዘረኝነት ላይ የሚያካሂዱትን ትግል እየረዳ ነው ።

የድርጅቱ ከፍተኛው የአመራር አካል በየዓመቱ የሚሰበሰበው የአባል ሀገሮች መሪዎች ስብስባ ነው ። እያንዳንዱ አባል ሀገር አንድ ድምፅ ያለው ሲሆን ውሳኔዎች በሁለት ሦስተኛው ከተደገፉ ይጸድቃሉ ። በመሪዎች ስብስባ መካከል ባለው ጊዜ የድርጅቱ የበላይ አመራር አካል ሆኖ የሚሠራው በዓመት ሁለት ጊዜ የሚሰበሰበው የአባል ሀገሮች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባ ነው ። የመሪዎች ስብስባ የድርጅቱን ዋና ፀሐፊ ይመርጣል ። ዋና ፀሐፊውም የድርጅቱን የቀን ተቀን የሥራ እንቅስቃሴ የሚያካሂደውን ሴክሬታሪያቱን ይመራል ። በተጨማሪም ድርጅቱ በኢኮኖሚ ፥ በማኅበራዊ ጉዳዮች ፥ በትምህርት ፥ በሳይንስ ፥ በባህል ፥ በጤና ጥበቃና በመከላከያ የተለያዩ ኮሚሽኖች አሉት ። የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይገኛል ።

ድርጅቱ እስከ አሁን ብዙ ጠቃሚ ሥራዎች የሠራ ቢሆንም በሥራው ግን በየጊዜው ብዙ እክሎች አጋጥመውታል ። ችግሮቹ የሚመነጩትም አባል ሀገሮች የሚከተሉት ርዕዮተዓለም የተለያየና የኢምፔሪያሊዝምም ጣልቃገብነት ከፍተኛ በመሆኑ በተለያዩ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ችግሮች ላይ ተፃራሪ አቋሞች ስለሚይዙ በአንዳንድ ችግሮች መፍትሔ ፍለጋ ላይ አለመግባባት ይፈጠራል ።

## አፍሪካና የእስያ ሕዝቦች አንድነት ድርጅት (የ—)

*(Afro-Asian Peoples' Solidarity Organifation)*

የአፍሪካና የእስያ ሕዝቦች ፀረ ኢምፔሪያሊስት የትግል ኅብረት ነው ። ይህ አንድነት የአፍሪካንና የእስያን ሕዝቦች ፀረ ቅኝ አገዛዝና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል በማስተባበር የብሔራዊ አርነት ንቅናቄዎችን ለማጠናከር በነበረው ዓላማ መሠረት በህንድ ፥ በስሪላንካ ፥ በኢንዶኔዥያ ፥ በፓኪስታንና በበርማ አሳሳቢነት በ1955 በባንዱንግ የተደረገው ሃያ ዘጠኝ የአፍሪካና የእስያ ሀገሮች ተወካዮች በተገኙበት ስብስባ ውሳኔ መሠረት በ1957 በካይሮ ተመሠረተ ። በወቅቱ ነፃነታቸውን ያልተቀዳጁት የአፍሪካና የእስያ ሕዝቦችም በብሔራዊ አርነት ንቅናቄዎቻቸው አማካይነት በስብሰባው ሊካፈሉ ችለዋል ።

የባንዱንግ ስብስባ ተካፋዮች ቅኝ አገዛዝን ፥ የዘር መድልዎንና የኢምፔሪያሊስቶችን ፀረ ሰላም ፖሊሲ በማውገዝ ቅኝ አገዛዝን ከአህጉሮቻቸውና በአጠቃላይም ከዓለም ለማጥፋት ለሚደረገው ትግል ቆርጠው መነሣታቸውን በአንድ ድምፅ ገለጹ ። በሀገሮች መካከልም ከተፅዕኖ ነፃ የሆነ በእኩልነትና በመደጋገፍ ላይ የተመሠረተ ግንኙነት እንዲኖር ጠየቁ ።

ይህንኑ ዓላማ ለማጠናከር ሁለተኛው የአፍሪካና የእስያ ሕዝቦች አንድነት ስብስባ በ1963 በኮናክሪ ተደረገ ። መተዳደሪያ ደንቡንም በመቅረፅ የተቀነባበረ ድርጅታዊ ህልውና ያገኘው በዚህ ወቅት በመሆኑ የኮናክሪው ስብሰባ ለድርጅቱ ጥንካሬ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ። በ1965 በአልጀሪያ የተደረገውም ስብሰባ ይህንኑ ፀረ ቅኝ አገዛዝና በተለይም የአፍሪካና የእስያ ሕዝቦች የኢኮኖሚ ችግሮቻቸውን ለማቃለል የሚያደርጉትን የጋራ ትግል አጠናከሯል ። ከዚህም በላይ በ1966 በሀቫና የተደረገው ስብሰባ ከአፍሪካና ከእስያም አልፎ የላቲን አሜሪካን ሕዝቦች ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል በአንድ መድረክ ለማሰባሰብ ችሏል ።

የአፍሪካና የእስያ ሕዝቦች አንድነት ድርጅት ከተመሠረተ ወዲህ በተለያዩ የዓለም አካባቢዎች የኢምፔሪያሊዝምን ቀጥተኛና ስውር ቅኝ አገዛዝን ፥ ዘረኝነትንና ጽዮናዊነትን ለማጥፋትና በሕዝቦች መካከል በእኩልነትና በመደጋገፍ ላይ የተመሠረቱ የባህልና የኢኮኖሚ ግንኙነቶች እንዲጠናከሩ በሚደረገው ጥረት ያልተቆጠበ የሞራልና የቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ የትግል አጋርነቱን ገልጿል ። ከዚህም በላይ በዓለም ሰላምና ዲሞክራሲያዊ ለሆነ አዲስ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት

መመሥረት ከፍተኛ ዓለምአቀፍ ስብሰባዎችን፣ ሴሚናሮችን ፣ ሲምፖዚየሞችን አካሂዷል ። ከነዚህም ውስጥ ከሚያዝያ 21—23፣1974 "በድንበር ዘለል ዓለምአቀፍ ኩባንያዎች ሚናና በኢኮኖሚ ዕድገት ስትራቴጂ" ላይ በአዲስ አበባ የተካሄደው ዓለምአቀፍ ስብሰባ አንዱ ነው ።

## አፓርታይድ
*(Apartheid)*

የዘር መድልዎንና የነጮችን የበላይነት በመቀበል ነጮን "ከፍተኛ" ፣ "ምርጥ"ና "ንጹሕ" ፣ ጥቁሩን የበታችና ተዋራጅ አድርጐ የሚቆጥር በደቡብ አፍሪካ በተግባር ላይ ያለ የለየለት የዘረኝነት ፖሊሲ ነው ። የአፓርታይድ ፖሊሲ የተከሰተው አውሮፓውያን አካባቢውን በቅኝ ግዛትነት ከያዙበት ከ17ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ አንሥቶ ቢሆንም የዘረኛው መንግሥት ዋና ፖሊሲ የሆነው ግን በዶክተር ማላን የሚመራው ብሔራዊ ፓርቲ ከታወጀ በኋላ ማለትም ከ1948 አንሥቶ ነው ።

አፓርታይድ የነጮች የበላይነት ማስጠበቂያ መሣሪያ ሲሆን ለጥቁሮች ግን ሰብአዊነታቸው ተገፎ ማኅበራዊ ኑሮአቸው እንዲቆረቁዝና ህልውናቸው ከፍተኛ አደጋ ላይ እንዲወድቅ የሚደረግበት የለየለት አድኃሪ ፖሊሲ ነው ። የአፓርታይድ ፖሊሲ የነጮችን የበላይነት ለማስጠበቅ የሚከተሉትን ዓላማዎች ተግባራዊ ያደርጋል ፣

1. ነጮችንና ጥቁሮችን ለያይቶ ማኖር፣
2. የጥቁሮችን ከስፍራ ወደስፍራ መዘዋወር መቆጣጠር ፣
3. የጥቁሮች የተለየ የልማት ስፍራ እየተባለ በሚታወቀው ዕቅዳቸው ጥቁሮችን በተወሰኑ ለምነት በሌላቸው (ባንቱስታን) ክፍሎች ማስፈር።

በዚህ ፖሊሲ ተግባራዊ መሆን 87% የሚሆነው ለምና ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት ክምችት ያለው መሬት አራት ሚሊዮን ተኩል ለሚሆኑት ነጭች ሲሰጥ ፣ ቁጥራቸው ከ18 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት ጥቁሮች ግን በተቀረው 13% በሆነው ፣ ለምነት በሌለውና ለኑሮ አደገኛ በሆነው አካባቢ ተወስነው ለችግርና ለእልቂት ተዳርገዋል ።

ዘረኛውና ፋሺስቱ የደቡብ አፍሪካ መንግሥት በጥቁሮች ላይ ኢሰብአዊ ጭፍጨፋና በደል የሚፈጽመው በዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም እየታገዘ ነው ። የተለያዩ ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች በተለይም የአሜሪካ ፣ የእንግሊዝ ፣ የፈረንሳይ ፣ የምዕራብ ጀርመን ፣ የጃፓን ፣ የእስራኤልና የመሳሰሉት ሀገሮች ሞኖፖል ኩባንያዎች ከደቡብ አፍሪካ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ትርፍ የሚያጋብሱ በመሆናቸው የደቡብ አፍሪካን መንግሥት እቅፈው ደግፈው መያዛቸው ብቻ ሳይሆን የኑክሊየር ጦር መሣሪያ ባለቤት እንዲሆን ወደ ማብቃትም ደርሰዋል ።

በ1957 የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ የአፓርታይድን ኢሰብአዊነትና ለዓለም ሰላም ያለውን ጠንቀኛነት በመገንዘብ ዘረኛው መንግሥት ይህን ፖሊሲውን እንዲተው ፣ የሚደግፉትም መንግሥታት ከዚህ ተግባራቸው እንዲቆጠቡ ጠይቋል ። ይሁን እንጂ ደቡብ አፍሪካ የተባበሩት መንግሥታትን ውሳኔዎችም ሆነ የዓለም ተራማጅ ኃይሎችን ተደጋጋሚ ውግዘት ከምንም ባለመቁጠር በፋሺስታዊና ዘረኛ ፖሊሲዋ ገፍታበታለች ። በዚህም የአፍሪካን ደኅንነት ብቻ ሳይሆን የዓለምን ሰላም ከፍተኛ አደጋ ላይ ጥላለች ።

የደቡብ አፍሪካ ሕዝብ ከአፓርታይድ የጭቆና ሥርዓት ለመላቀቅና የመብቱ ባለቤት ለመሆን በአፍሪካን ናሽናል ኮንግሬስ አመራር ቀራጥ ትግል እያካሄደ ነው ። ይህንንም ትግል የዓለም ተራማጅ ኃይሎች ከልብ በመደገፍ ወደዘላቂ ድል እንዲያመራ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛሉ ።

(ዘረኝነትን ፣ ጽዮናዊነትን ይመለከቷል ።)

## ኢመሠረታዊ ቅራኔዎች
*(Non-Basic Contradictions)*

ኢመሠረታዊ ቅራኔዎች የሚባሉት በክስተቶች ቅስቃሴና ዕድገት ውስጥ የወሳኝነት ሚና የሌላቸው ብዙውን ጊዜ ሁለተኛ ደረጃ በመባል የሚታወቁት ቅራኔዎች ናቸው ። ሕይወት ባላቸውና በሌላቸው ነገሮች ውስጥ

ከክስተቱ ውስጣዊ ተቃራኒ ሂደቶች ውጭ ክስተቱ በአካባቢው ካሉ ሌሎች ክስተቶች ጋር የሚኖረው መስተጋብርና ከዚህም የሚመነጭ ቅራኔ አለ ። ይህ ውጫዊ ቅራኔ ግን ተፅዕኖ ከሚኖረው በቀር ለክስተቱ መኖር ወይም አለመኖር ወሳኝ አይደለም ። በኅብረተሰብ ዕድገትም ውስጥ እንዲሁ ወሳኝነት የሌላቸው ከመሠረታዊው ቅራኔ የሚመነጩ ቅራኔዎች አሉ ። እነዚህም በመሠረታዊ ፍላጎታቸው ግጭት በሌላቸው መደቦች መካከል ያሉ ወይንም ከዕድገት ልዩነት የተነሣ በአንድ መደብ ውስጥ ባሉ ማኅበራዊ ክፍሎች መካከል ሊኖሩ የሚችሉ ቅራኔዎች ናቸው ።

በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓተ ማኅበር ከባሪያ አሳዳሪውና ከባሪያው ሌላ "ነፃ" ሰዎች ነበሩ ። እነዚህ ነፃ ሰዎች መጠነኛም ቢሆን ከባሪያው ጋር ቅራኔ ነበራቸው ። በፊውዳሉም ሥርዓት ከመሬት ከበርቴውና ከገባሩ ጎን የራሳቸው መሬት ኖሯቸው የራሳቸው ጉልበት ተጠቃሚ የሆኑ አራሾች አሉ ። የጠቅላላው ሥርዓት ጫና ያለባቸው ቢሆንም ከገባሩ የተሻሉ በመሆናቸው ገባሩ በበጐ ዓይን አይመለከታቸውም ። በካፒታሊስቱ ሥርዓት በተለይ በመጀመሪያ የዕድገት ደረጃው እንዲሁ ከካፒታሊስቱና ከወዝአደሩ ጐን የራሳቸው የማምረቻ መሣሪያ ባለቤቶችና የጉልበታቸው ተጠቃሚ የሆኑ ንዑስ ከበርቴዎች አሉ ። ካፒታሊዝም እያደገ በሄደ መጠን በአብዛኛው እየተደቀሱ የሚሄዱ ቢሆንም የግል ንብረት ባለቤቶች በመሆናቸው ከወዝአደሩ ጋር ቅራኔ አላቸው ። በዳበረ የካፒታሊስት ኅብረተሰብም እንዲሁ ከዕድገቱ አለመመጣጠን የተነሣ የሚፈጠሩ መለስተኛ ቅራኔዎች አሉ ። ለምሳሌ በገጠርና በከተማ ፣ በወዝአደርና በገበሬ ፣ በአእምሮና በጉልበት ሥራ ወዘተ ... ። እነዚህ መሠረታዊ ያልሆኑ ቅራኔዎች መሠረታዊው ቅራኔ ከተፈታ በኋላ እንኳን ለረጅም ጊዜ የሚኖሩ ቢሆን የሚፈቱበት መንገድ ከመሠረታዊ ቅራኔ የተለየ ነው ። እነዚህ ኢመሠረታዊ ቅራኔዎች በጠቅላላው ሕዝብ ትግልና ግንባር ቀደሙ ፓርቲ በሚያደርገው ጥረት መሠረታዊ ጥቅማቸው በማይጋጭ ማኅበራዊ ክፍሎች መካከል በሚካሄድ ኂስና ግለኂስ አማካይነት ይፈታሉ ። መሠረታዊ ቅራኔዎችን ከመፍታት በፊት በነዚህ መለስተኛና ጥቃቅን ቅራኔዎች ላይ ማትኮርና ለመፍታትም መሞከር ግን "ከፈረሱ በፊት ጋሪውን ማስቀደም" ይሆናል ።

(ቅራኔን ፣ መሠረታዊ ቅራኔን ይመለከቷል ።)

## ኢመደባዊ ፍልስፍና

*(Non–Class Philosophy)*

ኢመደባዊ ፍልስፍና የመደብ ጥቅምን የማያንፀባርቅ ፣ መደቦች በሌሉበት ማለትም በኮሚኒስት ሥርዓት ውስጥ ሊኖር የሚችልና ስለተፈጥሮ ፣ ስለኅብረተሰብ ፣ ስለሰው አስተሳሰብና የዕውቀት ሂደት አጠቃላይ ጥያቄዎችን የሚመለከት ፍልስፍና ነው ። ሆኖም በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የመደቦችን ጥቅም የማያንፀባርቅ የፍልስፍና ፈርጅ ሊኖር አይችልም ።

የሐሳባዊ ፍልስፍና ልዩ ልዩ ዘርፎች ኢመደባዊ መስለው ለመታየት ይሞክራሉ፤ ሐሳባውያን ፈላስፎች የፍልስፍና አስተሳሰቦች ከመደብ ጥቅም ጋር እንደማይዛመዱ ፣ መንግሥትና ፍልስፍና ከመደብ በላይ እንደሆኑ አስመስለው ያቀርባሉ ። ዳሩ ግን በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ በፍልስፍና የሚታቀፉ አስተሳሰቦች የመደብን ጥቅም የሚያንፀባርቁና መንግሥት በገዥው መደብ ጥቅም የሚመራ በመሆኑ መንግሥትና ፍልስፍና ቀጥተኛና የቅርብ ዝምድና አላቸው ። በመደብ ኅብረተሰብ ውስጥ የዕውቀት (የፍልስፍና) ሰርጭት ፣ ይዘትና ተግባራዊነት ከገዥው መደብ ጥቅም ጋር የተያያዘ በመሆኑ ከመንግሥት ቁጥጥር ውጭ ሊሆን አይችልም ።

(መደባዊ ፍልስፍናን ፣ የፍልስፍና መሠረታዊ ጥያቄን ፣ የፓርቲ ፍልስፍናን ይመለከቷል ።)

## ኢምርታዊ ሥራ

*(Non–Productive Labour)*

በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ በቀጥታ ቁሳዊ ሀብትን ለማምረት ያልዋለ ሥራ ኢምርታዊ ሥራ ይባላል ። ኢምርታዊ ሥራ በሕክምና ፣ በአስተዳደር ፣ በሀገር ደኅንነትና በመ

ከላከያ ፣ በባህል ፣ በመምህርነት ፣ በንግድ ፣ በባንክ አገልግሎት ፣ በሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋሞችና በመሳሰሉት መስኮች ይከናወናል ። ሆኖም በተወሰኑ የአገልግሎትና የኢኮኖሚ ዘርፎች ለምሳሌ በሆቴሎች ኢንዱስትሪ ውስጥ ምግብ በማዘጋጀት የተሰማሩት ሠራተኞችና የምርት ውጤቶችን ከምርት ቦታ ወደ ገበያ ቦታ በማጓጓዝ የተሰማሩ የትራንስፖርት ሠራተኞች በምርታዊ ሥራ ላይ የተሰማሩ ናቸው ። ኢምርታዊ ሥራ ቁሳዊ ሀብት የማይፈጥር የሥራ ዓይነት ቢሆንም እንደየሥርዓተ ማኅበሩ ሁኔታ ለምርት ሥራ መሳካት የሚሰጠው አገልግሎት ጠቃሚነቱና አስፈላጊነቱ የጎላ ነው ። በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ከሚኖረው የሥራ ክፍፍል አንፃር የተወሰኑ የኅብረተሰቡ አባሎች በምርታዊ ሥራ ላይ ሲሰማሩ ሌሎች ደግሞ በኢምርታዊ ሥራዎች ላይ ይሰማራሉ።

በኢምርታዊ ሥራ ላይ የተሰማሩት ሠራተኞች የሚያገኙት ገቢ የሚመነጨው በምርታዊ ሥራ ከተፈጠረው ብሔራዊ ገቢ ነው ። ጠቃሚ ኢምርታዊ ሥራ ለተሟላ የኢኮኖሚ ዕድገት አስፈላጊ የሆነና ለምርታዊ ሥራ ጠቃሚ የመሠረት ድጋፍ የሚሰጥ የሥራ ዓይነት ነው ። በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ለኅብረተሰቡ ጠቃሚ ያልሆኑ ኢምርታዊ የሥራ ዓይነቶች አሉ ። ለምሳሌ የተንዛዛ የሸቀጥ ማስታወቂያ ሥራ ኢምርታዊ ሥራ ነው ።

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ኢምርታዊ ሥራ በማዕከላዊ ደረጃ የሚደራጅና ለምርታዊ ሥራ ተገቢና ጠቃሚ አገልግሎት የሚሰጥ ነው ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ጠቃሚ ያልሆኑ ኢምርታዊ ሥራዎች ሊከሰቱ የሚችሉበት ቁሳዊ መሠረት የለም ።

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ቴክኖሎጂ ባልዳበረባቸው ሀገሮች በኢምርታዊ ሥራዎች ላይ የተሰማሩት ሠራተኞች ቁጥር መብዛትና በአንፃሩ በምርታዊ ሥራ ላይ የተሰማሩት ሠራተኞች ቁጥር ማነስ የሚመረተውን ቁሳዊ ሀብት ዝቅ ያደርገዋል ። ሆኖም የኅብረተሰቡ የዕድገት ደረጃና የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕድገት እጅግ ከፍተኛ ከሆነና የሥራ ምርታማነትም በዚሁ መጠን ከደገ ቁጥራቸው አነስተኛ በሆኑ በምርታዊ ሥራ ላይ በተሰማሩ ሠራተኞችም እጅግ ከፍተኛ ቁሳዊ ሀብት ሊመረት ይችላል ።

(ምርታዊ ሥራን ይመለከቷል ።)

## ኢምክኑያዊነት

*(Irrationalism)*

በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ ዓለም ምክኑያዊ ባልሆነና በቀጥታ ሊታወቅ በማይችል ኃይል ይገዛል የሚል አዝማሚያ ኢምክኑያዊነት ይባላል ። ቁስአካልነትና ሐሳባዊነት ዓለም በምክኑያዊ ሕግ እንደሚገዛ የሚቀበሉ በመሆናቸው ኢምክኑያዊነት የሚቃወመው ሁለቱንም ነው ። ኢምክኑያዊነት ሕግን በደመነፍሳዊ ወይም ፍጹም ስሜታዊ በሆነ ኃይል ወይም ንቁ ባልሆነ ፈቃድ ወይም ደግሞ በዘር ልዩነትና የበላይነት ወዘተ... በመተካት ሕይወትን አሳዛኝ ወይም ፋይዳቢስ አድርጎ ለማቅረብ ይሞክራል ። የዕውቀትን ምክኑያዊ ባሕርይ በመካድም ዕውቀትን በጭልታ ፣ በስርፀት ፣ በተማልሎአዊነተ ወዘተ... የሚገኝ በማድረግ ምሥጢራዊ የሆነ ሥነ ዕውቀትን ያራምዳል ። ኢምክኑያዊ ፍልስፍና የሚመነጨው ኅብረተሰብ በቀውስ ወይም በጦርነት ውስጥ በሚገኝበት ጊዜ ነው ።

(ህልውናነትን ፣ በርግሰንን ፣ ሾፐንሀወርን ፣ ፋሺዝምን ፣ ኒቸን ይመለከቷል ።)

## ኢምፔሪያሊዝም

*(Imperialism)*

ኢምፔሪያሊዝም ሞኖፖል ካፒታሊዝም ማለት ነው ። ኢምፔሪያሊዝም የካፒታሊዝም ከፍተኛውና የመጨረሻው ደረጃ እንዲሁም የሶሻሊስት አብዮት ዋዜማ ነው ። በነፃ ውድድር ደረጃ ይገኝ የነበረው ካፒታሊዝም ከ1870ዎቹ በኋላ ቀስ በቀስ ወደ ሞኖፖል ደረጃ እያደገ ሄዶ በ19ኛው ምዕት ዓመት መጨረሻና በ20ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ላይ ወደ ኢምፔሪያሊዝም ደረጃ ተሸጋገረ ።

ታላቁ አብዮታዊ ምሁር ሌኒን በማርክስና በኤንግልስ ሥራዎች ላይ በመመሥረ

ትና የዘመኑን የካፒታሊስት ሀገሮች ተጨባጭ ሁኔታዎች በማጤን ኢምፔሪያሊዝም፣ የካፒታሊዝም ከፍተኛ ደረጃ በተሰኘው እጅግ በታወቀው ጽሑፉ ስለኢምፔሪያሊዝም ሳይንሳዊ ንድፈ ሐሳብ አበረከተ ። ሌኒን እንዳመለከተው ኢምፔሪያሊዝም አምስት መሠረታዊ የሆኑ ኢኮኖሚያዊ ገጽታዎች አሉት ። እነሱም ፥

1. የምርትና የካፒታል መሰባሰብ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ማደጉ በኢኮኖሚው ውስጥ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ የሞኖፖል ድርጅቶች እንዲፈጠሩ ማድረግ ፤

2. የባንክ ካፒታል ሞኖፖል ከኢንዱስትሪ ካፒታል ሞኖፖል ጋር መዋሃድና በዚሁ የፋይናንስ ካፒታል ላይ የተመሠረተ የፋይናንስ አገዛዝ መፈጠር ፤

3. የካፒታል ከብሔራዊ ድንበሩ አልፎ ወደሌሎች ሀገሮች መዝመት ፥

4. ዓለምን በመካከላቸው የሚከፋፈሉ ዓለም አቀፍ የሞኖፖል ድርጅቶች ኅብረት መከሰት፤

5. ታላላቅ ካፒታሊስት ሀገሮች ዓለምን በመካከላቸው የመቀራመቱን ተግባር መፈጸም ፥ ናቸው ።

ኢምፔሪያሊዝም የካፒታሊዝም ሞኖፖል ደረጃ ነው የሚባለው በዚህ የካፒታሊዝም የዕድገት ደረጃ ኢኮኖሚው በሞኖፖል ድርጅቶች ቁጥጥር ሥር ስለሚወድቅ ነው ። በካፒታሊዝም የነፃ ውድድር ደረጃ ተመሳሳይ ሸቀጥ የሚያመርቱ ቁጥራቸው በርካታ የሆኑና እንቅስቃሴያቸው ያልተቀናጀ ትናንሽ አምራች ድርጅቶች በተለያዩ የግል ካፒታሊስቶች ባለቤትነት የተያዙ ነበሩ ። በመካከላቸው ይካሄድ የነበረው ውድድርም አንፃራዊ እኩልነት ነበረው ። በኢምፔሪያሊዝም የዕድገት ደረጃ የምርትና የካፒታል መሰባሰብ የሞኖፖሎችን መፈጠር በማስከተሉ ሞኖፖሎችም በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉትን ወሳኝ የሆኑ የኅብረተሰቡን የምርት መገልገያዎች የራሳቸው በማድረግ የኢኮኖሚና የፖለቲካ የበላይነት አገኙ ፤ ይህንንም ጥቂታ በማድረግ የወዝአደሩ መበዝበዝ እንዲባባስ አደረጉት ። ትናንሽና መካከለኛ ሸቀጥ አምራቾችን በቁጥጥራቸው ሥር በማዋል ከፍተኛ ሀብት ማሰባሰብ ጀመሩ ።

በቅድመ ሞኖፖል ካፒታሊዝም ደረጃ የኢንዱስትሪ ካፒታል ዋንኛውን ቦታ ይዞ ይገኝ ነበር ። በዚያን ጊዜ ባንክ እንደአቀባይ በማገልገል ነበር ከኅብረተሰቡ ገንዘብ በመሰብሰብ በአምራችነትና በንግድ መስክ ለተሰማሩ ካፒታሊስቶች የብድርና የመሳሰሉ ግልጋሎቶችን ይሰጥ የነበረው ። በኢምፔሪያሊዝም ደረጃ ግን ትላልቅ ባንኮች በኢንዱስትሪዎች ውስጥ አክሲዮን በመግዛት ሥልጣናቸውን እያስፋፉ ሄዱ ፤ አምራች ድርጅቶችም አክሲዮኖችን በመግዛት በባንኮች ውስጥ ሰርገው ገቡ ። የዚህም ውጤት የባንክ ካፒታልና የኢንዱስትሪ ካፒታል መዋሃድና የፋይናንስ ካፒታልና የፋይናንስ አገዛዝ መፈጠር ነው ። የኢምፔሪያሊዝም ዋና መግለጫ ጠባይም የኢንዱስትሪ ካፒታል ሳይሆን የፋይናንስ ካፒታል ነው ። ይህንንም የፋይናንስ ካፒታል በቁጥጥራቸው ሥር ያዋሉ ጥቂት ካፒታሊስቶች የፋይናንስ አገዛዝን መሠረቱ ። በዚሁ መሠረት ኢኮኖሚውን በቁጥጥራቸው ሥር ከማድረግ አልፈው የፖለቲካ ሥልጣንም ያዙ ። ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖችንና ሕግ አውጪዎችን የነሱ አፈቀላጤዎች በማድረግ የመንግሥቱን መዋቅር መቆጣጠር ጀመሩ ። አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙትም እራሳቸው በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ ቁልፍና` መሪ ቦታዎችን ይይዙ ጀመር ።

በኢምፔሪያሊዝም የዕድገት ደረጃ የካፒታል ወደ ውጭ ልከት ከፍተኛ ቦታ ማግኘት የፋይናንስ አገዛዝን ከመመሥረት ጋር አብሮ የሚታይ ነው ። ካፒታልን ወደ ውጭ መላክ በቅድመ ሞኖፖል ደረጃ የነበረ ቢሆንም ዋነኛዎቹ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነቶች ይካሄዱ የነበሩት በሸቀጣ ሸቀጥ ልውውጥ አማካይነት ነበር ። በሞኖፖል ካፒታሊዝም ደረጃ ግን ምንም እንኳን የውጭ ንግድ ቢደራም ካፒታልን ወደ ውጭ መላክ በዓለምአቀፍ ግንኙነት ከፍተኛውን ቦታ ያዘ ። ካፒታሊዝም እየዳበረ ሲሄድ በዳበሩ ካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ "የተትረፈረፈ" ካፒታል እየተከሰተ ይሄዳል ። በእነዚህ ሀገሮች ውስጥ "የተትረፈረፈ" ካፒታል የሚፈጠርበት ምክንያት የካፒታ

ሊዝም ዕድገት ራሱ በእነዚህ ሀገሮች ውስጥ ካፒታሊስቶች ካፒታላቸውን በሥራ ላይ በማዋል ትርፍ የሚሰበስቡባቸው የኢኮኖሚ መስኮች እየጠበቡና የትርፍ መጣኔም እየቀነሰ መሄዱ ነው ። "የተትረፈረፈው" ካፒታልም ስሌሎች ካፒታሊስት ሀገሮች መንግሥታትና ካፒታሊስቶች በወለድ ብድር ይሰጣል ወይንም በእነዚሁ ሀገሮች ውስጥ በቀጥታ በሙአለ ንዋይ መልክ በሥራ ላይ ውሎ ከፍተኛ ትርፍ እንዲያስገኝ ይደረጋል ። "የተትረፈረፈ" ካፒታል በተለይ የሚላከውም የካፒታል እጥረት ወደሚታይባቸው ፣ ምንዳ ዝቅተኛ ወደሆነባቸው ፣ የተፈጥሮ ሀብትና ጥሬ ዕቃዎች ርካሽ ወደሆኑባቸውና ከፍተኛ ትርፍ ሊገኝባቸው ወደሚችሉ ኋላ ቀር ሀገሮች ነው ።

ሞኖፖል ድርጅቶች ከፍተኛ ትርፍ ለመሰብሰብ የሚጠቀሙበት መሠረታዊ ዘዴ በሞኖፖል አቋማቸው በመጠቀም ዋጋን በከፍተኛ ደረጃ ወስኖ የምርትን መጠን በማታት መሆኑ የታወቀ ነው ። ስለዚህ ትላልቅ አምራች ድርጅቶች በአንድ በኩል የሀገራቸውን ገበያ በስምምነት በመካከላቸው ይከፋፈላሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ ሞኖፖል ካፒታሊዝም እየዳበረ ሲሄድ ትላልቅ ሞኖፖል ካፒታሊስቶች የዓለምን ገበያዎች በዚሁ አኳኋን በመካከላቸው ይቀራመቷቸዋል ። በእነዚህ ካፒታሊስቶች ግፊትም የካፒታሊስቱ ዓለም ኃያላን መንግሥታት ዓለምን በቅኝ ግዛትነት በመካከላቸው ተከፋፈሉ ። ለምሳሌ በ1876 ፣ ከአፍሪካ አህጉር ጠቅላላ የመሬት መጠን 10.8% ብቻ ነበር በቅኝ አገዛዝ ሥር የነበረው ። ይህ ቁጥር በ1900 ወደ 90.4% ሊመጥቅ ቻለ ። የካፒታሊስቱ ዓለም ኃያላን መንግሥታት ዓለምን በመካከላቸው የተከፋፈሉበት ምክንያት ካፒታላቸውን በሥራ ላይ የሚያውሉበት የኢኮኖሚ መስክ ፣ የጥሬ ዕቃዎች ምንጭ ፣ የሸቀጣ ሸቀጦቻቸው ማራገፊያ ገበያ ፣ ርካሽ የሥራ ኃይልና ሌሎች ጥቅሞችንም ለማግኘት ነው ።

የካፒታሊስቱ ዓለም ኃያላን ሀገሮች በያዝነው ምዕት ዓመት መባቻ ላይ ዓለምን በመካከላቸው ተከፋፍለው ካበቁ በኋላ ከሚያካሂዱት ብዝበዛ አልተገቱም ፤ ሊገቱም አይችሉም ። ካፒታሊዝም በይበልጥ እየዳበረ ሲሄድና ልዩ ልዩ የካፒታሊስት ሀገሮች ኢኮኖሚ በተለያየ ደረጃ እያደገ ፣ በመካከላቸው የነበረው የኃይል ሚዛን እየተቀየረ አንፃራዊ ዕድገት ያሳዩት ሀገሮች ዓለምን ዳግም ለመከፋፈል ያላቸው ፍላጐት እያደገ ሄደ ። በኢምፔሪያሊስት ሀገሮች መካከል የተከሰተው የተካረረ ቅራኔ ሁለት የዓለም ጦርነቶች አስነሥቶ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር የሰው ሕይወትና ከፍተኛ የንብረት ጥፋት አስከትሏል ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በቅኝ ግዛቶች ውስጥ የተካሄዱ የአርነት ንቅናቄዎች የኢምፔሪያሊዝምን መሠረት አናጉት ። ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆነ ቅኝ ግዛቶች የፖለቲካ ነፃነታቸውን በትግላቸው ተጐናፀፉ ። በ1960ዎቹ መጨረሻ ላይ በጥቂት የዓለም ክፍሎች ከሚገኙት በስተቀር የዓለም ሕዝቦች የፖለቲካ ነፃነታቸውን ተቀዳጁ ። የቅኝ አገዛዝ ሥርዓትም በዚህ አኳኋን ሊፍረከረክ ቻለ ።

ሆኖም ከቅኝ አገዛዝ የተላቀቁት ሕዝቦች ስማዊ የሆነ የፖለቲካ ነፃነት ቢያገኙም የተሟላ ነፃነት ሊጐናፀፉ አልቻሉም ። የኢምፔሪያሊዝም አንዱ ጠባይ የሆነው እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ቀጥታ ቅኝ አገዛዝን በመተካት ቅኝ ግዛት የነበሩትን ወደ እጅ አዙር ቅኝ ግዛትነት እንዲለወጡ አደረገ ።

የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ የሚከሰተው በኢኮኖሚ ፣ በፖለቲካ ፣ በርዕዮተዓለም ፣ በወታደራዊና በመሳሰሉት መስኮች ሲሆን በመሠረቱ ከቅኝ አገዛዝ ጋር አንድ ነው ። ልዩነቱ የእጅ አዙር ቅኝ ግዛቶች የራሳቸው ባንዲራ ፣ ስማዊ መንግሥትና ስማዊ የፖለቲካ ነፃነት ያላቸው መሆናቸው ብቻ ነው ።

ታላቁ አብዮታዊ ምሁር ሌኒን ኢምፔሪያሊዝም በታሪክ ውስጥ ያለውን ስፍራ ሲገልጽ ኢምፔሪያሊዝም ሞኖፖል ካፒታሊዝም ፣ ወይንም በመፈራረስ ላይ ያለ ካፒታሊዝም ፣ በመሞት ላይ ያለ ካፒታሊዝም ነው ብሏል ። ኢምፔሪያሊዝም እየፈራረሰ በመሄድ ላይ ያለ ካፒታሊዝም መሆኑን የሚገልጹት የምርት ግንኙነቶች የምርት ኃይሎችን ዕድገት አፍነው ከሚይዙበት ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ያስረዳል። ኢምፔሪያሊዝም በመሞት ላይ ያለ ካፒታሊዝምና የሶሻሊስት አብዮት ዋዜማ ነው ። በኢምፔሪያሊዝም የዕድገት ደረጃ ውስጥ የሶሻሊስት አብዮት ነባራዊና ኅሊናዊ ሁኔታዎች

ይሟላሉ ። ኢምፔሪያሊዝም የሚሞት ካፒታሊዝም ነው ቢባልም በፈቃዱ የታሪክን መድረክ ለቆ የሚጠፋ አይደለም ። ኢምፔሪያሊስቶች የብዝበዛን ሥርዓት ለማቆየት እስከመጨረሻው ከባድ ትግል ያካሂዳሉ ። በአሁኑ ጊዜ እንኳ በዓለም ላይ ታይቶ የማይታወቅ የጦር መሣሪያ ክምችት በማድረግ ዓለም በከፍተኛ የጦርነት ሥጋት ላይ እንድትወድቅ አድርገዋል ። ስለዚህ ኢምፔሪያሊዝም ሊደመሰስ የሚችለው የዓለም ሠርቶ አደር ሕዝብ በሚያደርገው አብዮታዊ ትግል ብቻ ነው ። የሶሻሊስቱ ዓለም እየተጠናከረ መሄድም ለዚሁ ትግል ፍሬያማነት አንድ ዋና አስተማማኝ ሁኔታ መሆኑ ይታወቃል ።

ኢምፔሪያሊዝም ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ ሀገራችን ኢትዮጵያን በተፈጥሮ ሀብቷ ፣ በስፋቷና በሕዝቧ ብዛት እንዲሁም በስትራቴጂያዊ አቀማመጧ ምክንያት ትኩረት አድርጎባት ቆይቷል ። ኢጣሊያ ፣ ፈረንሳይ ፣ እንግሊዝና አሜሪካ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛትነትም ሆነ በእጅ አዙር ቅኝ ግዛትነት በቁጥጥራቸው ሥር ለማዋል በልዩ ልዩ ጊዜያት ያደረጓቸው ጥረቶች ይህንኑ በጉልህ የሚያሳዩ ናቸው ።

ከኢምፔሪያሊዝም ጋር በደረገው የረጅም ጊዜ ትግል የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ከባድ መስዋዕትነትን በመክፈል ታላላቅ ድሎችን ለመጐናፀፍ ችሏል ። በዚህ አንፃር ከአብዮታችን ፍንዳታ በፊት ከተካሄዱ መራራ ትግሎች መካከል ከኢጣሊያ ጋር እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1888 የተካሄደውን የአድዋን ጦርነትና የማያወላውል ሽንፈት የደረሰባት ከአርባ ዓመታት በኋላም ያካሄደችብንን ፋሺስታዊ ወረራ መጥቀስ ይበቃል ።

ፋሺስት ኢጣሊያ ከሀገራችን ከተባረረችበት በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከ1933 በኋላም እንግሊዝና አሜሪካ ከንጉሣዊ አገዛዙ ጋር ትብብረት በመመሥረት በየተራ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን በሀገራችን ውስጥ በቀንደኛነት ሲያካሂዱ ቆይተዋል ። ይሁንና የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ከብዝበዛና ከጭቆና ሙሉ በሙሉ ለመላቀቅ ባደረገው ትግል እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በየካቲት 1966 አብዮታችን ሊፈነዳ በቅቷል ።

አብዮታችን ፀረ ፊውዳል ብቻ ሳይሆን ፀረ ኢምፔሪያሊስት ጭምር በመሆኑ ኢምፔሪያሊዝም በተለይም የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የውስጥ ፀረ አብዮተኞችንና የውጭ ወራሪዎችን በማስተባበርና በመርዳት ለጋውን አብዮታችንን በአጭር ለመቅጨት ከፍተኛ ሙከራ አድርጓል ። ከኢምፔሪያሊዝም ጋር የሚደረገው ትግል ወደፊትም የሚቀጥል በመሆኑ ነቅቶ መጠበቅና ከሶሻሊስቱ ዓለምና በአጠቃላይም ከተራማጅ ኃይሎች ጋር ያለንን ግንኙነት ይበልጥ እያጠበቅን ለሶሻሊስት ኅብረተሰብ ምሥረታ የምናደርገውን ጥረት ማጠናከር አማራጭ የማይገኝለት አቋም ነው ።

## ኢሰብአዊ ጭፍጨፋ
*(Genocide)*

ኢምፔሪያሊስቶችና የአድኅሮት ኃይሎች የኢኮኖሚ ጥቅማቸውንና የፖለቲካ የበላይነታቸውን ለመጠበቅ ሲሉ የአንድን ብሔር ፣ ዘር ፣ ሕዝብ ወይም የሃይማኖት ተከታዮች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የሚያጠፉበት ድርጊት ነው ። የዚህ ዓይነቱን ወደር የሌለው ኢሰብአዊ ድርጊትና አስከፊ ወንጀል የጀርመን ፋሺስቶች በሁለተኛው የዓለም ጦርነት (1939—45) ወቅት በኃይል በያዟቸው ግዛቶች ሕዝቦች ላይ ፈጽመዋል ። የካምፑቺያ የፖልፖት መንግሥትም በሚሊዮን በሚቆጠሩት የራሱ ዜጎች ላይ በወሰደው እርምጃ በግልጽ ታይቷል ። በአሁኑ ጊዜም የዚህ ዓይነቱ ድርጊት የደቡብ አፍሪካ ፋሺስትና ዘረኛ መንግሥት የሀገሬውን ጥቁር ሕዝቦች በሚመለከት የሚያራምደው ፖሊሲ ነው ። ጽዮናዊት እሥራኤልም በፍልስጤም አረብ ሕዝቦች ላይ የምታካሂደው የወረራና የማሳደድ ተግባር ይህንኑ የአድኅሮት ኃይላትን ኢሰብአዊ ተግባር የሚያመለክት ነው ።

## ኢስክራ
*(Iskra)*

በ1900 ታትሞ የወጣ የሩሲያ ማርክሳውያን የመጀመሪያ ኅቡእ ጋዜጣ ነው ። ይህም ጋዜጣ ማርክሳዊ ርዕዮተዓለምን ለማስፋፋት ፣ የሠራተኛውን መደብ ትግል ለማ

ፋፋምና በሩሲያ አብዮታዊ ፓርቲን ለመመ ሥረት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ። የሩ ሲያ ማኅበራዊ ዲሞክራሲያዊ ሌበር ፓርቲም በሁለተኛው ጉባኤው የፓርቲው ልሳን እንዲሆን ወስኖ ነበር ።

ጋዜጣው ሲጀምር ዓላማው በዚያን ጊዜ በሩሲያ ሰሻል ዲሞክራቶች ላይ ይታይ የነ በረውን ርዕዮተዓለማዊ ውዥንብርን ፣ ድርጅ ታዊ መከፋፈልንና የፖለቲካ አለመብሰልን ማስወገድ ፤ የሩሲያ ማኅበራዊ ዲሞክራቶችን አቋም በጊዜው ከነበሩ አድርባይ ቡድ ኖች (ለምሳሌ እንደ ኢኮኖሚስቶች ያሉ) ለይቶ ማሳወቅ ፤ በሀገሪቱ ውስጥ ለሚካሄደው የወዝአደሮች ግብታዊ እንቅስቃሴ የተቀነባ በረ አመራር መስጠት ፤ የአካባቢውን ማኅበራዊ ዲሞክራቶች በማርከሳዊ መርሆች ሥር ማሰ ባሰብ ነበር ።

የመጀመሪያዎቹ የኢ.ስክራ አዘጋጆችም ሌኒን ፣ ፕሌኻኖቭ ፣ ማርቶቭ ፣ አክስልሮድ ፣ ዛሱሊችና ፖትሬሶቭ ነበሩ ። እነዚህ አዘጋጆች ጽሕፈት ቤታቸውን በሚዩኒክ በማድረግ የመጀመሪያውን የኢ.ስክራ እትም በታኅሣሥ 1900 አወጡ ። ጋዜጣው ከ1901 አጋማሽ ጀምሮ በወር አንድ ጊዜ ፣ ከ1902 ጀምሮ ደግሞ በወር ሁለት ጊዜ ይታተም ነበር ።

የቄሣሩ የውጭ ሀገር ሰላዮች ስለጋዜ ጣው መታተም ደርሰውበት ክትትል ሲያደ ርጉ አዘጋጆቹ ከሀገር ሀገር መሰደድ ተገ ደው ነበር ። ለምሳሌ በሚያዝያ ወር 1902 ከሚዩኒክ ወደለንደን ፣ ከዚያም በ1903 ወደ ጄኔቭ ተዘዋውረዋል ።

ከጊዜ በኋላ በሩሲያ ውስጥ በሞስኮና በሌሎችም ከተሞች ማዕከሎች ተቋቁመው ጋዜጣው ይሰራጭ ጀመር ። የእነዚህ ማዕከ ሎች ተጨማሪ ተግባር ኢ.ስክራን ብቻ ሳይ ሆን ሌሎች የፖለቲካ ጽሑፎችን ከውጭ ተቀ ብሎ ማሰራጨት ፣ ለኢ.ስክራ ማዘጋጃ የሚ ረዳ ገንዘብ መሰብሰብ ፣ በሩሲያ ውስጥ ስለአ ለው ሁናቴ ሪፖርት ማጠናቀር ፣ ምሥጢራዊ የስብሰባ ቦታዎችን ማዘጋጀትና ከየአንዳንዱ የአካባቢው ማኅበራዊ ዲሞክራትና ወዝአደር ጋር ግንኙነት ማድረግ ነበር ።

ኢ.ስክራ ከ53ኛው እትም በኋላ በፕሌ ኻኖቭ አቀነባባሪነት ቀስ በቀስ የሚንሼቪ ኮች አቋም ማንፀባረቂያ እየሆነ መጣ ። ሌኒን ይህን ሂደት በመቃወም ከአዘጋጅነቱ በፈ ቃዱ እስከመሰናበት ደርሷል ። በመጨረሻም 112ኛው እትም ከወጣ በኋላ በ1905 የኢ.ስ ክራ መታተም አቆመ ።

# ኢ.ታዋቂነት

*(Agnosticism)*

የሰው ልጅ ነባራዊ እውነታን ለመ ገንዘብ ያለውን ችሎታ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ፣ በጠቅላላ ወይም በከፊል የሚክድ ወይም የሚገድብ ፍልስፍናዊ አቋም ነው ። ኢ.ታዋቂነት ስለነባራዊው ዓለም ሊታመን የሚችል ዕውቀት ለማግኘት አይ ቻልም ይላል ።

ኢ.ታዋቂነት የዕውቀትን ትክክለኛነትና እውነትነት በማስመልከት የሰው ልጅ ዕው ቀት ውሱን እንደሆነና ከኅሊናችን ውጭ ስለሚገኘው ነባራዊ እውነታ ትክክለኛ ግን ዛቤ ሊኖረን እንደማይችል ለማስረዳት ይጥ ራል ። የሰው ሐሳብ ከነባራዊ እውነታ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ስለሌለውና ቢኖረ ውም እንኳን ግንኙነቱ የሚፈጠረው ነባራዊ እውነታ በኅሊናችን ውስጥ በሚፈጥራቸው ሕውስታዎች አማካይነት ብቻ ነው ። በመሆኑም ዓለም ለእኛ ምን እንደምትመስል እንጂ በእርግጥ በነባራዊነቷ ምን እንደሆነች ለማወቅ አይቻልም ይላል ።

ኢ.ታዋቂነት ሰዎች የሚያውቁት ነባራዊ እውነታን ሳይሆን እውነታ የሚፈጥረውን ሕው ስታ ብቻ ነው ይላል ። ይህ በአእምሮአችን ውስጥ የሚገኝ ሕውስታችን ደግሞ ሕውስታ ብቻ በመሆኑ ከነባራዊ እውነታ የተለየ ስለ ሆነም ከሕውስታችን ውጭ ስለሚገኙ ነገ ሮች ዕውቀት ምንም ለመናገር ስለማይችል ከነባራዊ እውነታ ጋር ሊዋሀድ አይችልም ይላል ። ለምሳሌ አንድ ዕቃ ከባድ ነው ስንል ከብደቱ ሕውስታ በመሆኑና ሕውስታም ከኅሊና ውጭ ሊኖር ስለማይችል ክብደት የዕቃ ውን ነባራዊ ጠባይ የሚገልጽ አይደለም ።

በኢ.ታዋቂነት አመለካከት መሠረት የሰው ልጅ ይህን የመሰለ አንስተኛ ጉዳይ በትክክል ለመገንዘብ ካልቻለ ስለዓለም መጠንና ወሰን ፣ ስለዓለም መነሻና መድረሻ ፣

ስለነባራዊ እውነታ ምንነትና ስለመሳሰሉት ረቂቅና አጠቃላይ ጥያቄዎች አስተማማኝ መልስ ለመስጠት ችሎታው እንደሌለው ግልጽ ነው ።

ኢታዋቂነት በሐሳባዊነትና በቁስአካልነት መካከል የነበረውንና ያለውን ተቃራኒነትና ትግል ከንቱ በማድረግ እራሱን እንደ ሦስተኛ አማራጭ በማቅረብ በአሸናፊነት ብቅ ለማለት ይጥራል ። ኢታዋቂነት የሐሳባዊነትን ፍልስፍና መሠረታዊ ሐሳብ የሚቀናቀን ቢመስልም በወላዋይ አቋሙ ለእምነት በር ስለሚከፍት በሐሳባዊነት ውስጥ ይመደባል ።

ኢታዋቂነት እውነታን ለማወቅ አይቻልም ስለሚል የሳይንስን ዕድገት የሚገታ ፣ ሰው ስለእውነታ ከማይፋለስ አስተሳሰብ ላይ አይደርስም ስለሚልም ሰዎች የተፈጥሮንና የኅብረተሰብን ዕድገትና እንቅስቃሴ የሚገዙትን ሕግጋት እንዳይረዱ የሚጋርድ ነው ። ይሁን እንጂ ተግባር፣ሳይንሳዊ ምርምርና የቴክኖሎጂ ዕድገት የኢታዋቂነትን ስህተተኛነት ከጊዜ ወደጊዜ እያጋለጡ መጥተዋል ። ሰዎች ነገሮችንና ክስተቶችን ዓላማ ባለው ንቁ እንቅስቃሴያቸው ሊረዱ ፣ ሊለውጡና ሊያራቡ ከቻሉ "ነገሮች ሊታወቁ አይችሉም" ለሚል አስተሳሰብ ምንም ቦታ አይኖርም ።

(ኅሊናዊ ሐሳባዊነትን ፣ ጠርጣሪነትን ይመለከቷል ።)

## ኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን (ኢሠፓአኮ) (የ–)

*(Commission for Organizing the Party of the Working People of Ethiopia –COPWE)*

በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ውስጥ ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ይበልጥ እንዲሰርፅና እንዲሰራጭ ፣ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ እንዲመሠረት አስፈላጊውን ድርጅታዊና ርዕዮተዓለማዊ ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርግ፣ በዚሁም ጊዜ ፓርቲ አከል ተግባር እንዲያከናውን እንደ ኢት. አ. ታኅሣሥ 8 ፣ 1972 በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የተቋቋመ የፖለቲካ ድርጅት ነው ።

ኢሠፓአኮ እንደተቋቋመ ለስድስት ወር ጊዜ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ካጠናቀቀ በኋላ በዚያው ዓመት ሰኔ 9 ቀን የመጀመሪያውን ጉባኤ አደረገ ። በዚህ ጉባኤ ላይ የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ተሰየመ ፤ የመተዳደሪያ ደንብና የድርጊት ፕሮግራም ጸደቀ ። ከዚህ በኋላ ኢሠፓአኮ የፓርቲ ማደራጀት ሥራን በሰፊው ተያያዘው ። መዋቅሮቹን በአሥራ አምስቱ ክፍላተ ሀገር (በአዲስ አበባ ጭምር) ከዚያም ባውራጃና በወረዳ ደረጃ ዘረጋ ። በየመሥሪያ ቤቶችና በየፋብሪካዎች መሠረታዊ ድርጅቶች ተቋቋሙ ። ሕዝባዊ ድርጅቶች ማለትም ከነማ ፣ መኢሠማና መኢገማ በአዲስ መዋቅር ተጠናከሩ ። አኢወማና አኢሴማም በሀገር አቀፍ ደረጃ ተደራጁ። ከዚህ በኋላ በታኅሣሥ ወር 1975 የኢሠፓአኮ ሁለተኛ ጉባኤ ተደረገ ።

የኢሠፓአኮ ሁለተኛ ጉባኤ የፓርቲውን መዳረሻ ምዕራፍ አበሰረ። ከዚህ በኋላ የነበረው ጊዜ በፊት የተጀመረውን ድርጅታዊ ሥራ መቀጠልና ማጠናከር ሕዝባዊ ድርጅቶችን ማጠናከር ፣ የፕሮፓጋንዳንና የቅስቀሳውን ሥራ በበለጠ ማፋፋም ፣ የሕዝቡን የባህል ደረጃ ከፍ ማድረግ ፣ የብሔረሰቦችን የተስተካከለ ልማት ለማስገኘት የብሔረሰቦች ኢንስቲትዩትን ማቋቋም ፣ በተለይም የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ሶሻሊስት ፈር ለማስያዝ ፣ ጥረት ማድረግ፣ የአሥር ዓመት መሪ ዕቅድ መንደፍ፣ የእናት ሀገርን ደኅንነት በበለጠ መጠበቅ ወዘተ… ነበር ።

የተመሠረተበትን ተልዕኮ በሙሉ ካከናወነ በኋላ እንደ ኢት. አ. በ1977 መጀመሪያ ኢሠፓ ሲመሠረት ህልውናው አከተመ ።

## ኢንተርናሲዮናል—መዝሙር

*(International—Proletarian hymn)*

በኤዠን ፖቴ በ1871 ተደርሶ በ1887 የታተመ ፣ በዶጊቴ በሙዚቃ የተቀነባበረ ዓለምአቀፍ የወዝአደሮች መዝሙር ነው ።

ለመጀመሪያ ጊዜ ለሕዝብ የቀረበው በሊል ሠራተኞች መዘምራን አማካይነት ሰኔ 23 ፣ 1888 ሲሆን በ1890ዎቹ ዓመታት መጀመሪያ ላይ በሰሜናዊ ፈረንሳይ አጐራባች ሀገሮችና በቤልጅግ ሠራተኛ

መደብ አባላት ዘንድ መሰራጨት ጀመረ ። ፓሪስ ውስጥ የሁለተኛው ኢንተርናሽናል የመጀመሪያው ጉባኤ ከተካሄደ በኋላ ከእ ነዚህ ሀገሮች ክልል አልፎ ለወዝአደሩ አብ ዮታዊ ትግል ዓለምአቀፍ መዝሙር በመ ሆን መሰማት ጀመረ ። ይህን መዝሙር ለማ ሰራጨት የፈረንሳዩ ሶሻሊስት ጉስለ መዝ ሙሩን በ1894 ለሁለተኛ ጊዜ እንዲታተም በማድረጉ በእሥራት እንዲቀጣ ተፈርዶ በታል ።

መዝሙሩ በመጀመሪያ ጊዜ በሌሎች ቋንቋዎች የተተረጐመው በ1890ዎቹ ሲሆን የጥቅምቱ ሶሻሊስት አብዮት መዝሙሩ በመላው ዓለም እንዲታወቅና በዓለም ቋን ቋዎች እንዲተረጐም ረድቷል ።

ሌኒን ይህን መዝሙር በማስመልከት ጥር 13 ፣ 1913 በፕራቭዳ ላይ ባወጣው ጽሑፉ የመዝሙሩን ዓለምአቀፋዊ ታሪካዊ ነት በመጥቀስ የደራሲውን የትግል አስተ ዋጽኦ አድንቋል ።

## ኢንተርፕራይዝ
*(Enterprise)*

ትርፍ ለማግኘት የተቋቋመ ሕጋዊ ሰውነት ያለው የኢኮኖሚ ድርጅት ኢንተር ፕራይዝ ይባላል ። በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ኢንተርፕራይዝ አንድ ካፒታሊስት አቋቁሞ የሚያስተዳድረው ድርጅት ሲሆን የድርጅቱም ዓላማ ለባለቤቱ ትርፍ ማስገኘት ነው ። በተጨማሪም በካፒታሊስት መንግ ሥት ይዞታ ሥር ሆኖ ለትርፍ ማግኛ ሥራ የሚንቀሳቀስ ድርጅትም አለ ።

በሽግግር ወቅት የመንግሥት ኢንተር ፕራይዝ ፣ የኅብረት ሥራ ኢንተርፕራይዝ ፣ የግል ኢንተርፕራይዝ የመንግሥትና የግል ኢንተርፕራይዝ ፣ ይኖራል ። በሶሻሊስት ኢኮ ኖሚ ውስጥ ኢንተርፕራይዝ የኢኮኖሚው መሠረታዊ አካል ነው ።

የሶሻሊስት መንግሥት ኢንተርፕራይዝ በማዕከላዊው ዕቅድ መሠረትነት ዝርዝር የውስጥ አፈጻጸም ፕሮግራም በማውጣት በትርፍና ኪሣራ የኢኮኖሚ አስተዳደር ስልት በመመራት ከመንግሥት የተመደበለትን ገንዘብና ቁሳዊ ሀብት በመጠቀም ይሠራል ። ኢንተርፕራይዙ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴው ውስጥም አንፃራዊ ነፃነት ስላለው በዚህ በመጠቀም በራሱ አነሣሽነት በሕግ ክልሎች ውስጥ የተፈቀዱለትን ርምጃዎች በመውሰድ ይንቀሳቀሳል ። የሶሻሊስት መንግሥት ኢን ተርፕራይዝ ከመንግሥት በተሰጠው ሀብት በመጠቀም የሶሻሊስት ሀብትን ያዳብራል ፤ የሠራተኛውን ገቢም ያሳድጋል ።

ሶሻሊስት ኢንተርፕራይዞች የተለያዩ ምርታዊ ሥራዎችን የሚያከናውኑ ለምሳሌ የጎምረቻ መሣሪያዎችንና የፍጆታ ሸቀጦችን የሚያመርቱ እንዲሁም የንግድ ሥራ የሚያ ካሂዱና ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን የሚሰጡ የኢኮኖሚ ድርጅቶች ናቸው ። ኢንተርፕራይ ዞች የዳበረ የሸቀጥ ምርት ኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች እንደመሆናቸው እርስ በርሳቸ ውም ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች አሏቸው ። የተ ለያዩ ኢንተርፕራይዞችንም በማቀናጀትና በማዋሃድም ጠንካራ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ዎች ሊካሄዱ ይችላሉ ።

በሶሻሊስት ሀገሮችም ውስጥ ለምሳሌ በሶቭዬት ኅብረት የምርት ድርጅቶች በተለ ያዩ ደረጃዎች ይዋቀራሉ ። እንዲህ ያሉ በከ ፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ድርጅቶች ኮምባ ይን ተብለው ይጠራሉ ።

## ኢንተርፕራይዝ ትርፍ (የ—)
*(Enterprise Profit)*

በአንድ የካፒታሊስት የምርት ድርጅት ውስጥ ወዝአደሮችን በመበዝበዝ ከተገኘው ትርፍ የተወሰነው መጠን በወለድ መልክ ለአበዳሪ ካፒታሊስቶች ተከፍሎ የሚቀረው ትርፍ የኢንተርፕራይዝ ትርፍ ይባላል ።

የኢንተርፕራይዝ ትርፍ ከብድር ካፒ ታል እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ ነው ። የኢን ዱስትሪ ካፒታሊስቱ ካፒታሉን ለማስፋፋትና በተወሰነ የገበያ ወቅት የተፈጠረውን ትርፍ ለማግኘት በሚያስችል ሁኔታ ለመጠቀም ተጨማሪ ካፒታል ያስፈልገዋል ። ይህም ቋሚ ካፒታሉን ለማስፋፋት ፣ አዲስና ዘመ ናዊ ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ለማዋልና ለሌ ሎች ተዘዋዋሪ የካፒታል ወጪዎች የሚያስ ፈልገውን ካፒታል ከባንክ በብድር መልክ ለማግኘት ያስችለዋል ። በዚህ አኳኋን የሚገ ኘው ትርፍ ከሁለት ይከፈላል ። እነዚህም

ለኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱ የሚገባው የኢንተርፕራይዝ ትርፍና አበዳሪ ካፒታሊስቱ የሚያገኘው ወለድ ናቸው ።

የቡርዧ አፈቀላጤዎች የኢንተርፕራይዝ ትርፍ ወዝአደሩን በመበዝበዝ የሚገኝ መሆኑን በመደበቅ የካፒታል ባለቤትነት ብቻ በራሱ የሚያስገኘው ትርፍ አድርገው በማቅረብ የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱ ድርሻ የሚል መጠሪያ ይሰጡታል ።

(የብድር ካፒታልን ይመለከቷል ።)

## ኢንዱስትሪ ተጠባባቂ ሠራዊት (የ-)

*(Industrial Reserve Army)*

ካፒታሊስት ክምችት እያደገ በሄደ መጠን በሂደተ ምርት ውስጥ የማምረቻ መሣሪያዎች ድርሻ ከሚያንቀሳቅሰው የሰው ኃይል የበለጠ አንፃራዊ ዕድገት ያሳያል ። በዚህም ሳቢያ ከጠቅላላ ካፒታሉ ዕድገት አኳያ የተለዋዋጭ ካፒታሉ ድርሻ እያነሰ መሄድ የሥራ ኃይልን ተፈላጊነት እንዲቀንስ ስለሚያደርግ በምርት ተግባር ውስጥ ሊሳተፍ ያልቻለ ሥራአጥ የሰው ኃይል የኢንዱስትሪ ተጠባባቂ ሠራዊት ይባላል ።

የኢንዱስትሪ ተጠባባቂ ሠራዊት የካፒታሊስት ክምችት የማይቀር ውጤት የመሆኑን ያህል ለካፒታሊስት ስልተ ምርት ህልውና አስፈላጊ ሁኔታ ነው ። ምክንያቱም የኢንዱስትሪ ተጠባባቂ ሠራዊት መኖር ቡርዧዚው በምርት ተግባር ላይ የተሰማራው ወዝአደር ለምንዳ መሻሻልና ለመሳሰሉት ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች የሚያደርገውን ትግል ለማዳከም እንዲገለገልበት ስለሚያስችለው ነው ። ይህም የምንዳን ደረጃ ዝቅ በማድረግ ቡርዧዚው የሚያገኘው ትርፍ እያደገ እንዲሄድና የተስፋፉ ክምችትም እንዲኖር አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል ።

የኢንዱስትሪ ተጠባባቂ ሠራዊት ቁጥር ከፍና ዝቅ ማለት በካፒታሊስት የኢንዱስትሪ ዑደት ውስጥ ከሚኖሩት የተለያዩ ደረጃዎች ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው ። ይህም ማለት በኢንዱስትሪ ዑደት የመጀመሪያው ሁለት ደረጃዎች ማለትም በቀውስና በዝቅጠት ውስጥ ቁጥሩ ከፍ ሲል በሌሎቹ ሁለቱ ደረጃዎች ማለትም በማገገምና በድራት ደረጃዎች ግን ቁጥሩ ዝቅ ይላል ። ስለዚህ የኢኮኖሚ ሁኔታው በተሻሻለበት ጊዜ የኢንዱስትሪ ተጠባባቂ ሠራዊት ለካፒታሊስቱ አስፈላጊውን ተጨማሪ የሰው ኃይል ለማስገኘት ያስችላል ። የኢንዱስትሪ ተጠባባቂ ሠራዊት መፈጠር የካፒታሊስት ስልተ ምርት ዓይነተኛና ልዩ ባሕርይ ነው ።

## ኢንዱስትሪ አብዮት (የ—)

*(Industrial Revolution)*

የኢንዱስትሪ አብዮት በመባል የሚታወቀው ከማሽኖች መፈጠርና ሥራ ላይ መዋል ጀምሮ ማሽኖችን በሌሎች ማሽኖች ሠርቶ ማውጣት እስከተቻለበት ድረስ ያለው ጊዜ ሲሆን ይኸውም በምዕራብ አውሮፓ ከ18ኛው ምዕት ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ጀምሮ እስከ 19ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ድረስ ያለውን ጊዜ የሚሸፍን ነው ። የኢንዱስትሪ አብዮት በቴክኖሎጂ ዘርፍ የተደረገውን ለውጥ ብቻ ሳይሆን በዚህ ወቅት በኢኮኖሚያዊ ፣ በማኅበራዊና በፖለቲካዊ ዘርፍ ሁሉ የተገኙትን ለውጦች ያጠቃልላል ።

የኢንዱስትሪ አብዮት ከመካሄዱ በፊትና እንዲካሄድም ለማድረግ መጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት መከናወን ነበረበት ። መጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት 1/ ከምርት መገልገያ ባለቤትነታቸው ተፈናቅለው ለመኖር የሥራ ኃይላቸውን ለመሸጥ የሚገደዱ በዛ ያሉ ሥራ አጦችን በመፍጠር ፤ 2/ በተወሰኑ ሰዎች እጅ የሀብት ክምችት እንዲደልብ በማድረግና በዚህም ሀብት በመጠቀም የምርት መገልገያዎችን በግል ባለቤትነት በመያዝ ለሥራ ኃይል ብዝበዛ ሊጠቀሙበት በመቻላቸው ይህ ሁኔታ የካፒታሊስት የምርት ግንኙነትን በማስፋፋት ለኢንዱስትሪ አብዮት መከናወን ረድቷል ። ከዚህም በተጨማሪ በዚሁ ወቅት የዓለም ገበያ በከፍተኛ ደረጃ መስፋፋት ፣ የከሰልና የብረት ሀብት መገኘት ፣ በእንፋሎት የሚሠራ ሞተር መፈጠር ፣ የመገናኛ ዘዴዎች መሻሻል ለዚህ አብዮት መካሄድ ቅድመ ሁኔታዎች ነበሩ ።

የኢንዱስትሪ አብዮት የተጀመረው በእንግሊዝ ሲሆን በኋላም ወደ ሌሎች የአውሮፓ ሀገሮችና ወደ አሜሪካም ተዛምቷል ። የኢንዱስትሪ አብዮት በመሠረቱ የኢንዱስትሪ ልማትን በአጠቃላይ የሚመለከት ሲሆን ትኩረት ያደረገው በከባድ ኢንዱስትሪ ላይ ነው ። በአነስተኛ ኢንዱስትሪ የካፒታል የመገላበጥ ፍጥነት ከፍተኛ በመሆኑ ትርፍ ቶሎ ስለሚያስገኝ የኢንዱስትሪ ልማት የተጀመረው በአነስተኛ ኢንዱስትሪ ነበር ። ካፒታሊስቶች በዚህ ሁኔታ ለረዥም ጊዜ ትርፍ ካካበቱ በኋላ ትርፋቸውን ለከባድ ኢንዱስትሪ ግንባታ ማዋል ጀመሩ ።

በኢንዱስትሪ አብዮት ሂደት ከተነሡት መሠረታዊ ቅራኔዎች መካከል ዋነኛው በአንድ በኩል አዳዲስ የማምረቻ መሣሪያዎችን ለማግኘት ባለው ፍላጐትና የካፒታሊዝም የመፈብረክ ደረጃ እንደነዚህ ያሉ የማምረቻ መሣሪያዎችን ሠርቶ ለማውጣት ባለመቻሉ መካከል የተፈጠረው ቅራኔ ነበር ። ይህ ቅራኔ የማምረቻ መሣሪያዎችን ሠርተው ለማውጣት የሚችሉ ሌሎች የማምረቻ መሣሪያዎች ሲፈጠሩ ሊፈታ ችሏል ።

ከመፈብረክ ደረጃ ወደ ተስፋፋ የማሽን ምርት ደረጃ የተደረገው ሽግግር በቴክኒክ ብቻ ሳይሆን በማኅበራዊ ግንኙነቶችም ላይ ለውጥ አሳይቷል ። በዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች ውስጥ የማሽን ምርት መስፋፋት ለትላልቅ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት አመቺ ሁኔታ ቢፈጥርና የእርሻን ምርታማነት ቢያሳድግም በእርሻና በኢንዱስትሪ መካከል ያለውን የዕድገት ልዩነት ደረጃ ሊያጠበው አልቻለም ።

በኢንዱስትሪ አብዮት አማካይነት ካፒታሊስቱ የተስፋፋ የማሽን ቴክኖሎጂን ለምርት ተግባር ማዋል ሲጀምር የወዝአደሩን ብዝበዛ ከበፊቱ ይበልጥ እንዲጠናከር ከማድረጉም በላይ ሠራተኛው የማሽኑ ጥገኛ እንዲሆን አድርጎታል ። የካፒታሊስት የማሽን ምርት ዕድገት በአእምሮ ሥራና በጉልበት ሥራ ፣ በገጠርና በከተማ መካከል የነበረውን ልዩነት እያሰፋው መጣ ። የተስፋፋ የማሽን ምርት የሥራ እጡ ሠራዊት እንዲጨምር ከማድረጉም በላይ የካፒታሊስት ሥርዓት መሠረታዊ ቅራኔ የሆነውን ማለትም በማኅበራዊ አመራረትና በግል የሀብት ክፍፍል መካከል ያለውን ቅራኔ ገሃድ በማውጣት ሥርዓቱን በዓለምአቀፍ ደረጃ ቀውስ ውስጥ እንዲገባ አስገድዶታል ።

የኢንዱስትሪ አብዮት በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ያሉት ሁለት መሠረታዊ መደቦች ማለትም ወዝአደሩና ቡርዧዚው የተሟላ ቅርፃቸውን ይዘው እንዲከሰቱ ያደረገ ሂደት ሲሆን በሁለቱ መደቦች መካከል ያለው የመደብ ትግል መካረር የጀመረው ከዚሁ ወቅት እንሥቶ ነው ።

ከኢንዱስትሪ አብዮት በኋላ የካፒታሊዝም ቴክኒካዊና ቁሳዊ መሠረቱ በሚገባ በመጠናከሩ በፊውዳሉ ስልተ ምርት ላይ የበላይነቱን ሙሉ በሙሉ ሲያሰፍን ከመቻሉም በላይ የካፒታሊዝም አስከፊ ገጽታዎችም ከዚሁ ወቅት በኋላ በጉልህ ሊታዩ ችለዋል ።

(መፈብረክን ፣ የቴክኖሎጂ አብዮትን ፣ የማሽን ምርትን ይመለከቷል ።)

## ኢንዱስትሪ ካፒታል (የ—)

*(Industrial Capital)*

በካፒታሊስት የምርት ግንኙነት ውስጥ ቁሳዊ ሀብት በማስመረት ተረፈ እሴት ለማስገኘት የሚውል ካፒታል ነው ። የኢንዱስትሪ ካፒታል የወዝአደሩን የሥራ ኃይልና (ወዝአደሩን በመቅጠር) የምርት መገልገያዎችን በምርታዊ ሥራ እንዲቀናበሩ በማድረግ እሴት በወዝአደሩ ያስመርታል ። ይህ የኢንዱስትሪ ካፒታል ተረፈ እሴት የማስገኘት እንቅስቃሴን ያለማቋረጥ ያከናውናል ። የኢንዱስትሪ ካፒታል ያለማቋረጥ በሚያደርገውም እንቅስቃሴ በዚያው ወቅት በሦስት የተለያዩ ቅርፆች ይከሰታል ። እነዚህም የመጀመሪያው የገንዘብ ካፒታል ፣ ሁለተኛው ምርታዊ ካፒታልና ሦስተኛው የሸቀጥ ካፒታል ናቸው ። እነዚህ ሦስት ቅርፆች በተያያዘ መንገድ ያለማቋረጥ ይከናወናሉ ። ይህ የተቀናበረ የኢንዱስትሪ ካፒታል እንቅስቃሴ የተረፈ እሴትን መመረትና መገኘት ያስከትላል ።

የኢንዱስትሪ ካፒታል እንቅስቃሴን በሚከተለው ዓይነት ማመልከት ይቻላል ፤

የሥራ ኃ.
ገ—ሸ ............ የም.ሥ...ሸ$^{1}$—ገ$^{1}$
የም.መ.

ገ=የገንዘብ ካፒታል
ሸ=ሸቀጥ
የሥ.ኃ=የሥራ ኃይል
የም.መ.=የምርት መገልገያ
የም.ሥ=የምርት ሥራ ሂደት (ምርታዊ ካፒታል)

ሸ$^{1}$ =አዲሱ ሸቀጥ (የሸቀጥ ካፒታል)
ገ$^{1}$ =አዲሱ ገንዘብ (የገንዘብ ካፒታል)

ስለዚህም በመጀመሪያው እንቅስቃሴ የገንዘብ ካፒታል ሠራተኛን ለመቅጠርና የምርት መገልገያዎችን ለመግዛት ይውላል ። ከዚህ በኋላ ወዝአደሩ የምርት ሥራ ያካሂዳል። በዚህ ወቅት የምርት መገልገያዎች እሴት ወደ አዲሱ ሸቀጥ ሲሸጋገር ሠራተኛው በተወሰነ የሥራ ኃይሉ የራሱን እሴት ከፈጠረ በኋላ በቀረው ደግሞ ተረፈ እሴት ይፈጥራል ። ይህ ምርታዊ ካፒታል ነው ። አዲሱ ሸቀጥ ለማምረቻ መሣሪያዎች የወጣውን እሴትና ወዝአደሩ ያፈሰሰውን እሴት የያዘ ነው ። ወዝአደሩ ያመረተው እሴት ለርሱ ከተከፈለው ምንዳ በላይ ነው ። በዚህ ሂደት ውስጥ የሚመረተው ሸቀጥ የሸቀጥ ካፒታል ነው ። ሸቀጥ ከተሸጠ በኋላ የሚያስገኘው ገንዘብ የምርት መገልገያዎች ወጪን፣ የምንዳ ወጪንና ትርፍን የያዘ ነው ። ይህ የገንዘብ ካፒታል ይባላል ። ከዚህ በኋላ የኢንዱስትሪ ካፒታል እንቅስቃሴ እንደገና ይቀጥላል ። ይህ ሂደት ያለማቋረጥ የሚቀጥል ሲሆን ሦስቱም የኢንዱስትሪ ካፒታል ቅርፆች ባንድ የምርት ክንውን ወቅት ይከሰታሉ ።

የኢንዱስትሪ ካፒታል ተረፈ እሴት የማግኘት እንቅስቃሴ ሂደት በወዝአደሩና በካፒታሊስቱ መደብ መካከል ያለውን ትግል ይወስናል ። የካፒታሊስት የምርት ግንኙነት እየዳበረ ሲሄድ እያንዳንዱ የኢንዱስትሪ ካፒታል የተግባር መልክ በተለያዩ ካፒታሊስቶች ይከናወናል ። የገንዘብ ካፒታል ወደ ብድር ካፒታልና የሸቀጥ ካፒታል ወደ ንግድ ካፒታል የመለወጡ ተግባር በአበዳሪ ካፒታሊስቶችና በንግድ ካፒታሊስቶች ይከናወናል። ተረፈ እሴት የሚመረትበት ዘርፍ ግን ምርታዊ ካፒታል ነው ። ይህንን የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱ ያደራጃል ።

(የንግድ ካፒታልን ፣ የብድር ካፒታልን ይመለከቷል ።)

## ኢአማኒነት
*(Atheism)*

ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ኃይል ማለትም በአማልክት ፣ በመናፍስትና ከሞት በኋላ ባለ ሕይወት ማመንን የማይቀበል የፍልስፍና አመለካከት ነው ። ኢአማኒነት ሃይማኖት እንዴት እንደመጣና ለምን እንደመጣ ከማስረዳቱም በላይ ዩኒቨርስን በሳይንሳዊ መንገድ ከማጥናት የተነሣ የሃይማኖት ቀኖናዎችን ይነቅፋል ፣ የሃይማኖትን ማኅበራዊ ተግባር በማሳየት ለሰው ልጅ ዕድገት ዕንቅፋት መሆኑንና እንዴትም እንደሚከስም ያስረዳል ።

ኢአማኒነት መከሰት የጀመረው ሳይንሳዊ ዕውቀት እየተስፋፋ በሄደበት ዘመን ነው ። የኢአማኒነት ፍልስፍናዊ መሠረት ቁስአካልነት ነው ። ስለዚህም ኢአማኒነት ከሃይማኖት ጋር የሚያደርገው ትግል ከመደብ ትግል ጋር የቅርብ ግንኙነት አለው ።

ኢአማኒነት ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተው በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት ነው ። በዚህም ጊዜ እንደ ዲሞቅሪጦስ ያሉ ጥንታውያን ፈላስፎች ማንኛውም ክስተት በተፈጥሮ ምክንያት የተገኘ መሆኑን ገልጸዋል ።

በመካከለኛው ዘመን ወይንም ፊውዳሊዝም በተስፋፋበት ዘመን ሃይማኖትና ቤተክህነት ጠንካራ ሥልጣን በነበራቸው ጊዜ ለኢአማኒነት አመች ሁኔታ አልተፈጠረም ነበር ። የቡርዧው ኢአማኒነት ፍልስፍና የሃይማኖትን ምንነትና ሕግጋት ደኅና አድርጎ ለመረዳት ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጓል ። ይሁንና የቡርዧው የኢአማኒነት ፍልስፍና በጥቂት ምሁራን መካከል ከመሰራጨት በስተቀር ወደ ሰፊው ሕዝብ አልደረሰም ነበር ።

ኢአማኒነት የመጨረሻውን የማይለወጥ ቅርፁን የያዘው የማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍና መሠረት በሆኑት በዲያሌክቲካዊና ታሪካዊ ቁስአካልነት ፍልስፍና ነው ። ከዚህም የተነሣ ይህ ፍልስፍና ለመጀመሪያ ጊዜ የሃይማኖትን

ጐታችነትና አዘናጊነት ከማጋለጡም በላይ በርሱም ላይ ፍጹም ድል እንዴት እንደሚገኝ በተጨባጭ ሁናቴ መፍትሔውን አሳይቷል ።

ማርክሳዊ ኢአማኒነት በሃይማኖት ላይ ፍጹም ድል የሚገኘው በኮሚኒዝም ግንባታ ሂደት ውስጥ ፤ሃይማኖት ማኅበራዊ መሠረት እየተደመሰሰ ሲሄድ መሆኑን ያስተምራል ።

በኮሚኒስት ግንባታ ጊዜ ሰው በሳይንሳዊ ትምህርት ይታነፃል ፤ ይህም ሰው ከሃይማኖትና ከአለፈው ትውልድ አጉል እምነት ነፃ የሆነና በኢአማኒነት ርዕዮተዓለም የታነፀ ይሆናል ።

(ሃይማኖትን ይመለከቷል ።)

## ኢእኩያዊ ልውውጥ
*(Unequal Exchange)*

በኢምፔሪያሊስት ሀገሮችና በመልማት ላይ ባሉ ሀገሮች መካከል የሚካሄደው የተዛባ የንግድ ልውውጥ ሂደት ኢእኩያዊ ልውውጥ በመባል ይታወቃል ።

በኢምፔሪያሊስት ሀገሮችና በመልማት ላይ ባሉ ሀገሮች መካከል ያለው የውጭ ንግድ ግንኙነት አንድ ዋና ገጽታ በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮች ለካፒታሊስቱ ዓለም ገበያ ምግብና ሌሎች የእርሻ ምርት የሆኑ ጥሬ ዕቃዎችና ማዕድናት አቅራቢ ፣ ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ደግሞ በመልማት ላይ ላሉ ሀገሮች የኢንዱስትሪ ምርት አቅራቢ ሆነው መገኘታቸው ነው ። ከዚሁ ጋር የተያያዘ የግንኙነቱ አንድ ሌላ ዋና ገጽታ ደግሞ በአጠቃላይ ለረጅሙ ጊዜ በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮች ወደ ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች የሚልኳቸው ጥሬ ዕቃዎች ዋጋ ፣ ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች በመልማት ላይ ወዳሉ ሀገሮች ከሚልኳቸው የኢንዱስትሪ ውጤት ከሆኑ ሸቀጣሸቀጦች ዋጋ ጋር ሲነፃፀር እያሽቆለቆለ መምጣቱ ነው ። ለምሳሌ ከ1978—1981 ባለው ጊዜ ውስጥ ነዳጅ ዘይት ሻጭ ያልሆኑ በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮች ወደ ውጭ የላኳቸው ሸቀጣሸጦች አማካይ ዋጋ ከውጭ ከሚያስገቧቸው ሸቀጣሸቀጦች አማካይ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር በ20% ያህል የቀነሰ መሆኑ ይታወቃል ። ይህ ማለት ለምሳሌ አንድ በመልማት ላይ ያለ ሀገር አንድ የእርሻ መኪና ከኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ለመግዛት በ1978 መቶ ኩንታል ቡና መሸጥ አስፈልጎት እንደሆነ ፣ በ1981 ያንኑ የእርሻ መኪና ለመግዛት መቶ ሃያ ኩንታል ቡና መሸጥ ያስፈልገው ነበር ማለት ነው ።

በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮች ወደ ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች የሚልኳቸው ሸቀጦች ዋጋ ማሽቆልቆልና መዋዠቅ ኢኮኖሚያቸውን ለማዳበር በሚያደርጉት ጥረት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያደርጋል ። የኢኮኖሚ ዕቅድና ፕሮግራም ነድፎ ተከታታይነት ባለው መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ አዳጋች ሁኔታን ይፈጥራል ። የንግድ ሚዛን ተዛቦት (ዴፊሲት) ከዚህም ጋር በተያያዘ መንገድ የውጭ ክፍያ ሚዛን ተዛቦት እንዲያድግ ያደርጋል ። ይህንንም ተዛቦት ለመሸፈን መበደር ስለሚኖርባቸው የውጭ ዕዳቸው በከፍተኛ ደረጃ ንሯል ። የብድርና የወለድ ክፍያም በበኩሉ በኢኮኖሚያቸው ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እያሳደረ ነው ። አብዛኞቹ በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮች በዚህ ሁኔታ ነፃ የሆነና የዳበረ ኢኮኖሚ ለመገንባት በማያስችል በተወሳሰበ የኢምፔሪያሊዝም የብዝበዛ መረብ ውስጥ ተተብትበው ይገኛሉ ።

በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮች በዓለም አቀፍ የንግድ ግንኙነት ውስጥ እኩያዊ የሆነ ልውውጥ ለማስፈን የሚያስችል ፣ በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ አዲስ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲመሠረት በየዓለምአቀፍ መድረክ ከመጠየቅ ቸል አላሉም ። ይህም ሥርዓት የንግድ ግንኙነትን ብቻ ሳይሆን የቴክኖሎጂ ሽግግርን ፣ የገንዘብና የፋይናንስ ሥርዓትንና ሌሎችንም የኢኮኖሚ የውጭ ግንኙነት መስኮችን የሚያቅፍ ነው ። ጥያቄውን ግን ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ግልጽ በሆነ ምክንያት ሳይቀበሉት ቀርተዋል ። በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮች በአንድ በኩል ለረጅሙ ጊዜ ለአዲስ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት እየታገሉ በሌላ በኩል ደግሞ ለአጭሩ ጊዜ የኢኮኖሚ ልማት መርሀ ፕሮግራማቸውን ለማንቀሳቀስ የሚያስችሏቸው አንዳንድ ሁኔታዎች እንዲሟሉላቸው አጥብቀው በመጠየቅ ላይ ይገኛሉ ። ከእነዚህም ሁኔታዎች መካከል ከውጭ ንግድ

የሚያገኙት ገቢ እያሽቆለቆለ በመሄዱ የሚያጡትን ገቢ የሚያካክስ ሁኔታ እንዲፈጠር፣ የኢንዱስትሪ ምርቶቻቸውን ለኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ገበያ አቅርበው ተመጣጣኝ ዋጋ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲኖር ፣ ለካፒታሊስቱ ዓለም ገበያ የሚያቀርቧቸው ጥሬ ዕቃዎች ዋጋ በየጊዜው ከውዥቀት ተላቆ የሚረጋጋበት ዘዴ እንዲቀየስ የሚሉ ይገኙባቸዋል ።

## ኢካፒታሊስታዊ የዕድገት ፈለግ *(Non–Capitalist Way of Development)*

በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም በኋላቀርነት ሆነ በቅኝ አገዛዝ ጭቆና የተነሣ በካፒታሊዝም የዕድገት ፈለግ ዘልቀው ያልተራመዱና ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ የዕድገት ደረጃቸው በቀጥታ ወደ ሶሻሊዝም ሊወስዳቸው የማይችሉ ሀገሮች በአብዮታዊ ሂደት ውስጥ የሚከተሉት ሶሻሊስታዊ ዝንባሌ ያለው የሽግግር ዕድገት ፈለግ ነው ። የሽግግሩ ዓቢይ ሥራ ወደ ሶሻሊዝም ሊያደርሱ የሚችሉትን ቁሳዊና መደባዊ ሁኔታዎችን ማሟላት ነው ።

ኢካፒታሊስታዊ የዕድገት ፈለግ ለኋላ ቀር ሀገሮች አማራጭየለሽ የሚሆንበት ዋናው ምክንያት የኢምፔሪያሊዝም ሞኖፖላዊ አገዛዝ ከሚፈጥረው ሁኔታ ሌላ መውጫ መንገድ ስለሌለ ነው ። ኢምፔሪያሊዝም ኋላቀር ሀገሮችን በጥገኝነት በመያዝ የራሳቸውን ብሔራዊ ኢኮኖሚና ብሔራዊ ገበያ እንዳያዳብሩ ከማድረጉም በላይ አንዳንድ ውሱን የሆኑና ለውጭ ንግድ ብቻ የሚጠቅሙ ዘመናዊ ክፍሎችን በመክፈት በሀገሮቹ ውስጥ ጨርሶ ያልተመጣጠነ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እንዲኖር ያደርጋል ። ይህ ሁኔታ ስንኩል የሆነ የመደብ አሰላለፍን ይፈጥራል ። አብዛኛው ሰው በኋላቀር የግብርና ሥራ የሚተዳደርና ከገጠር ውሱን ኑሮ ያልተላቀቀ ሆኖ ይቀራል ። ለኢምፔሪያሊዝም ለማቅረብ የግብርና ጥሬ ዕቃዎችን (ቡና ፣ ጥጥ ወዘተ...) የሚያመርተው የኢኮኖሚ ክፍል በሸቀጥና በገንዘብ ግንኙነቶች ውስጥ የሚገኝና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያለው የገበሬ ንዑስ ከበርቴ መደብን ይፈጥራል ። በቁጥር አነስተኛ የሆን በማዕድንና በአነስተኛ የፋብሪካ ሥራዎች የተሰማራ ሙሉ በሙሉ ያልተቀረፀ ነገር ግን ከልማዳዊና ከጎሳዊ ግንኙነቶች በመላቀቁ የመደብ ንጽረትን በቁንጽልም ቢሆን የሚያንፀባርቅ የወዝአደር መደብ ይገኛል ። በትርፍ ከመኖር ፍላጎት ላይ ባለመድረሳቸው ከበፊቱ አመለካከት ያልተላቀቁና ከፋብሪካ ሥራዎችና ከትላልቅ የንግድ ማዕከሎች ጋር ለመወዳደር የሚያዳግታቸውና በመጥፋት አደጋ ላይ ያሉ የማምረቻ መሣሪያዎች ባለቤትና እራሳቸውም አምራች የሆኑ እንደ እጅ ጥበብ ባለሙያዎችና እንደ ትናንሽ ነጋዴዎች ያሉትን የሚወክል በሙሉ ንዑስ ከበርቴነት ደረጃ ላይ ያልደረሰ ክፍል ይገኛል ። በይፀልጥ በንግድ ፣ በፋይናንስና በአገልግሎት መስክ የተሰማራ ሙሉ ካፒታሊስት ለመሆንና የፖለቲካ ሥልጣን ፍላጎት ያለው ነገር ግን በራሱ ሊቆም የማይችል ፣ የውጪውን ጥቅም ተገን የሚያደርግ ጥገኛና ደካማ የብሔራዊ ቡርዧ መደብ ሌላው ኃይል ነው ። በአስተዳደር ፣ በፖለቲካና በባህል ሥራ ወዘተ... ውስጥ የሚገኝ በትምህርት ደረጃው ከፍ ያለ አስተማሪዎችን ፣ ተማሪዎችንና አነስተኛ የጦር መኮንኖችን የሚወክል ብሔራዊና ዲሞክራሲያዊ ስሜት ያለው የምሁር ክፍል በአንድ በኩል የተሰለፈ ሲሆን በሌላ በኩል ከመንግሥት መዋቅር ጋር በቅርብ የተያያዙና በከፍተኛ የኃላፊነት ቦታ የሚገኙ የኢምፔሪያሊዝም መሣሪያ የሆኑትን የሚያጠቃልል የቢሮክራሲያዊ ምሁራን ክፍል ይገኛል ።

ይህ የመደብ ሁኔታ በተለይ የሚያሳየው ነፃ ብሔራዊ ኢኮኖሚና ፖለቲካዊ አመራር ለማስገኘት ፣ ካፒታሊዝም ነፃ ውድድርን በሞኖፖላዊ አገዛዝ በተካበት ወቅት ብሔራዊ ቡርዧዚ ከጥገኝነት ተላቆ ሀገሩን አስተማማኝ በሆነ የዕድገት ጎዳና ለመምራት የማይችል መሆኑን ነው ። በመሆኑም የብሔራዊ ነፃነት ወይም ከጥገኝነት የመላቀቅ ጥያቄ ቀጥተኛ ፀረ ካፒታሊስት ይዘት እንዲኖረውና የዕድገት ጎዳናው ካፒታሊዝምን በመተው ሶሻሊስታዊ እንዲሆን ታሪካዊው ሁኔታ አስገድዷል ። ይህን ተግባራዊ የሚያደርግ አንዱ ሁኔታ ዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የሶሺያሊዝም የሽግግር ዘመን በመሆኑ በተለይም የዳበሩ ሶሻሊስት ሀገሮች መኖር ይህን የዕድገት ፈለግ ለሚከተሉት ሀገሮች አስፈላጊ

የሆነውን ቁሳዊና ቴክኒካዊ እርዳታ ማድ
ረግ መቻሉ ነው ።

የዕድገቱ ፈለግ ፖለቲካዊ አመራር የሚ
መሠረተው ተራማጅ የሆኑ የኅብረተሰቡ
ክፍሎች በሚፈጥሩት ፀረ ኢምፔሪያሊስት ፥
ፀረ ፊውዳልና ፀረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም
ግንባር ነው ። ኅብረተሰቡ ኋላቀር በመሆኑና
የጠራ የመደብ ኃይልና አሰላለፍ ስለሌለው
አንድ መደብ ብቻውን የመሪነት ደረጃ
ሊይዝ አይችልም ። ግንባሩ ደሀ ገበሬዎችን ፥
ብሔራዊ ቡርዧዚን ፥ የወዝአደሩን መደብ እን
ዲሁም ሌሎች የሠርቶ አደር ተራማጅ ክፍ
ሎችን የሚወክል ፖለቲካዊ ሥርዓት ነው ።
ሆኖም የዚህ ግንባር ማዕከልና አንቀሳቃሽ
ኃይል የወዝአደሩ መደብ መሆን ይኖርበ
ታል ። ምክንያቱም ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ
አድኅሮት አቋሙ ሊረጋገጥ የሚችለው የሠ
ራተኛው መደብ የሚወክለውን ዘመናዊና
ተራድኦአዊ የምርት ግንኙነት የበላይነት
ሲቀበል ብቻ በመሆኑ አቅጣጫው የሚቀየ
ሰው ፥ ብሔራዊና ሕዝባዊ ይዘትም የሚኖረው
ሠራተኛውን መደብ ተቀዳሚው ኃይል
ሲያደርግ ብቻ ነው ።

የዕድገቱ ፈለግ በኢኮኖሚያዊ ፖሊሲ
ሲተረጎም ሰፋፊ የማምረቻና የፋይናንስ ክፍሎ
ችን ከግል ይዞታ በማላቀቅ በመንግሥት
ቁጥጥር ሥር ማድረግን ይጠይቃል ። ይህ
እርምጃ የሂደቱን ብሔራዊነት የሚያረጋግ
ጥና በዕቅድ የሚመራ ዕድገትን የሚቀይስ
ነው ። ዕቅዱም በሶሻሊስታዊ መርሀ ይክና
ወናል ፤ ማለትም ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ
ዕድገትን አብሮ በማራመድ ተደጋጋፊ ያደር
ጋቸዋል ። ይህ ብዝበዛን የሚያስቀር ብቻ
ሳይሆን በተለይ ሰፊውን የገጠር ሕዝብ
ከድህነት ፥ ከበሽታ ፥ ከማይምነት በቶሎ
የሚያላቅቅ ይሆናል ። የምርት ኃይሎች ዕድ
ገት የሚደገፈው በምርት ግንኙነቶች ከብዝ
በዛ ነፃ መሆን ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ
ሁኔታ ላይ በተመሠረቱ በሳይንሳዊና በቴክኒ
ካዊ ምርምሮችና ግኝቶች ጥምር ነው ።

አብዛኛውን ሕዝብ ያቀፈውን የግብርና
ክፍለ ኢኮኖሚ ሁኔታ የመለወጡ ጉዳይ
የሂደቱ ዓቢይ ጥያቄ ነው ። የወዝአደሩና
የገበሬው አንድነት ሊረጋገጥ ፥ ገበሬውም
ሶሻሊስታዊ አመለካከት ሊኖረው የሚች
ለው ተራድኦአዊ የምርት ግንኙነት በገጠር
ሲመሠረት ነው ። በመሆኑም የሂደቱ አፋጣኝ
ሥራ የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት
እንዲፈጠሩና በቶሎም እንዲዳብሩ በማድረግ
ከግል የሥራ ክንዋኔ አላቆ ገበሬውን ወደ
ሠራተኛነት ደረጃ ማሳደግ ነው ። በግል
ይዞታ የሚንቀሳቀሱ የብሔራዊ ቡርዧዚ
ውና የንዑስ ከበርቴው ኢኮኖሚያዊ ክፍሎች
ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ያላቸውን ቀጥተኛ
ግንኙነት በማቋረጥ ብሔራዊ ገበያና ኢንዱ
ስትሪ እንዲስፋፉ የመንግሥት አጋዥ ኃይል
አድርጎ የሚያሠራቸውን መዋቅር መዘርጋት
ሌላው ዓቢይ ጉዳይ ነው ።

ኢካፒታሊስታዊ የዕድገት ፈለግ ለመን
ግሥት የሚሰጠው ኢኮኖሚያዊ ፥ ማኅበራዊና
ፖለቲካዊ ሚና ከፍ ያለ ነው ። በግል ሥር
ዓት ፈንታ መንግሥት ኢኮኖሚያዊና
ማኅበራዊ ዕድገትን በዕቅድ የሚመራ ብቻ
ሳይሆን ሕዝቡን በማደራጀትና ንቃተ ኅሊ
ናውን በማሳደግ በዲሞክራሲያዊ መርሆች
ላይ በተመሠረተ ኢኮኖሚያዊ ፥ ማኅበራዊና
ፖለቲካዊ ተሳትፎው ተራድኦአዊ ግንኙ
ነትን እንዲያጠናክርና የራስ በራስ አስተዳደር
ልምዶችን እንዲያገኝ ያደርጋል ። ይህ በመን
ግሥትና በሕዝብ መካከል የሚታየው ዲሞክ
ራሲያዊ አሠራር የሚያሰባስበው ሕዝባዊ
ኃይል ለምርት ኃይሎች ፈጣን ዕድገትን
የሚሰጥ ነው ።

ኢካፒታሊስታዊ የዕድገት ፈለግ ወደ
ሶሻሊዝም የሚሸጋገሩትን ቁሳዊ ፥ ድርጅ
ታዊና ኅሊናዊ ሁኔታዎችን የሚያሟላ
ሂደት በመሆኑ በውስጡ ተቃራኒ አዝማሚ
ያዎችን ያቀፈ ነው ። ዘመናዊው ማለትም
የወዝአደሩ ክፍል ሶሻሊስታዊ አዝማሚያ
ሲኖረው ኋላቀሩ ክፍል በተለይም የገጠሩ
ክፍል በኑሮ ደረጃ ዝቅተኛነትና ባለው የግል
የአመራረት ዘዴ የተነሣ ወደ ግላዊነት ማለ
ትም ወደ ካፒታሊስታዊ ግንኙነት የሚያዘነ
ብል ነው ። በመሆኑም ሰፊውን የገበሬ ክፍል
በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ማነፅ ፥ የግል የምርት
አሠራርን በማኅበራዊ አሠራር በአስቸኳይ
መተካትና በአፋጣኝ የኑሮ ደረጃውን ከፍ
ማድረግ አማራጭ የሌለው ፖሊሲ ነው ።
የዕድገቱ ፈለግም የሚጠይቀው ይህንኑ
ኋላቀር የሆነውን ክፍል በዘመናዊ አቅጣጫ
የማራመድን ስልት ነው ።

ሌላው ወሳኝ ጥያቄ በፖለቲካው መዋቅር ውስጥ ማለትም በግንባሩ ውስጥ የሚካሄደው የማያቋርጥ የመደብ ትግል ሁኔታ ነው ። የሀገሩ አጠቃላይ የድህነት ሁኔታ የሸቀጥ ምርት አዝማሚያን በየጊዜው የሚቀሰቅስ በመሆኑ የብሔራዊ ቡርዧዚውና የንዑስ ከበርቴው ክፍሎች የፖለቲካ የበላይነትን ለማግኘት የሚያስመኛቸውና የሚገፋፋቸውም ይኸው ነው ። በመሆኑም እንቅስቃሴያቸውን ለመቆጣጠር ማለትም በአጋዥነታቸው እንዲወሰኑ ለማድረግ የግንባሩ ግራ ክንፍ በተለይም ኮሚኒስታዊ ክፍሉ የማያቋርጥ ፖለቲካዊና ርዕዮተዓለማዊ ትግል ማካሄድ አለበት ። ትግሉ ማስገኘት ያለበት ውጤት ኢንዱስትሪ በማስፋፋት የወዝአደሩን ቁጥር በመጨመር ፣ ንቃተ ኅሊናውንና ድርጅታዊ ሁኔታውን በማዳበር ሰፊውን ሠርቶ አደር ሕዝብ አስባስቦ የመሪነቱን ቦታ እንዲይዝ ማድረግ ነው ። ይህ የሚያመለክተው በግንባሩ ውስጥ የኮሚኒስቱ ክፍል የአመራር ብስለት ምንኛ ወሳኝ እንደሆነ ነው ። የዚህ ክፍል ከስሜታዊነት ፣ ከጀብደኝነትና ከሐሳባዊነት መሰቀቅና በዕቅድና በሳይንሳዊ አመለካከት መመራት የመደብ ትግሉ ወደተፈለገበት ማለትም ወደ አስተማማኝ ሶሻሊስታዊ ሥርዓት እንዲጓዝ የሚያደርግ ወሳኝ ሁኔታ ነው ።

(ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ፣ የሽግግር ወቅትን ፣ ኢምፔሪያሊዝምን ይመለከቷል ።)

## ኢኮኖሚያዊ ሕግ
*(Economic Law)*

በማናቸውም ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች (ምርትን ፣ ልውውጥን ፣ ክፍፍልንና ፍጆታን) የሚወስንና ነባራዊነት ያለው ሕግ ኢኮኖሚያዊ ሕግ ይባላል ። ኢኮኖሚያዊ ሕጐች የማኅበራዊ ሕጐች ዋና አካል ናቸው ። የእያንዳንዱ ሥርዓተ ማኅበር የምርት ግንኙነት በዚያው ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ለሚሠራ ኢኮኖሚ ሕግ መሠረት ነው ።

ኢኮኖሚያዊ ሕግ ነበራዊ ነው በሚባል [illegible]ት ጊዜ ሰው እንደፈለገ የሚፈጥረው ሳይሆን [illegible]ሳይንስና በቴክኖሎጂ ዕድገት ላይ ተመር[illegible] ለራሱ በሚያመች መንገድ የሚገለገል [illegible]ት ነው ማለት ነው ።

ኢኮኖሚያዊ ሕግ በሦስት ይመደባል ፤—

1. በአንድ በተወሰነ ሥርዓተ ማኅበር ብቻ ተግባራዊ የሚሆን ኢኮኖሚያዊ ሕግ ፤
2. ከአንድ በላይ በሆኑ ሥርዓተ ማኅበሮች ተግባራዊ የሚሆን ኢኮኖሚያዊ ሕግ ፤
3. በሁሉም ሥርዓተ ማኅበሮች ተግባራዊ የሚሆን ኢኮኖሚያዊ ሕግ ፤

ለምሳሌ የተረፈ እሴት ሕግ የካፒታሊስቱ ኢኮኖሚ ዋንኛ ኢኮኖሚያዊ ሕግ ስለሆነ በካፒታሊስት ሥርዓት ብቻ የሚኖር ኢኮኖሚያዊ ሕግ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ በየጊዜው እያደገ የሚሄደውን የሠራተኛውን ሕዝብ ፍላጐት የማሟላት ሕግ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ዋንኛው ሕግ ነው ።

በሁለተኛው ተራ ቁጥር ለተጠቀሰው የኢኮኖሚ ሕግ ዓይነት እንደምሳሌ ሊያገለግል የሚችል የእሴት ሕግ ነው ። የእሴት ሕግ የሸቀጥ ምርት ከተጀመረበት ከጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ጀምሮ እስከ ሶሻሊስት ኢኮኖሚ ድረስ ያለና ከአንድ በላይ በሆኑ ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ የሚኖር የኢኮኖሚ ሕግ ነው ።

በሦስተኛው ተራ ቁጥር ለተጠቀሰው ኢኮኖሚያዊ ሕግ እንደ ምሳሌ ሊያገለግሉ ከሚችሉት መካከል የሥራ ምርታማነትን በየጊዜው የማሳደግ ሕግና የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች መጣጣም የተሰኙት ይገኙበታል ። እነዚህ በሁሉም ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ ተፈጻሚነት የሚኖራቸው ሕጐች ናቸው ። በእያንዳንዱ ሥርዓተ ማኅበር ከላይ የተጠቀሱት ሦስቱም የኢኮኖሚያዊ ሕግ ዓይነቶች ሲኖሩ ፣ በሥርዓቱ ውስጥ ያለው ዋንኛው ኢኮኖሚያዊ ሕግ በሌሎች ኢኮኖሚያዊ ሕጎች ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ይኖረዋል ።

የምርት መገልገያዎች በግል ሀብትነት በተያዙበት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ሕግ ቢታወቅም አሠራሩ ግብታዊ ነው ። በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ግን ሰዎች ኢኮኖሚያዊ ሕግን በመገንዘብ ለኅብረተሰቡ ጥቅም በሚሰጥበት መንገድ በዕቅድ ተግባር ላይ በማዋል ያልተቋረጠ ዕድገት ለማግኘት ያስችላቸዋል ።

## ኢኮኖሚያዊ ማዕቀብ
(*Economic Sanction*)

ኢኮኖሚያዊ ማዕቀብ አንድን ሀገር በኢኮኖሚ ብቸኛ ለማድረግ ወይም ከሌሎች ሀገሮች ጋር ያለው የኢኮኖሚ ግንኙነት እንዲቀዘቅዝ መሠረታዊ የሆኑ ጥሬ ዕቃዎችና ሌሎች ምርቶች ለዚህ ሀገር እንዳይደርሱና እንደዚሁም በዚህ ሀገር የተመረቱ ልዩ ልዩ የምርት ውጤቶች የውጭ ገበያ እንዳያገኙ በማድረግ በዚህ ሀገር ላይ የኢኮኖሚ ውድቀት ለማስከተል ሲባል የሚወሰድ እርምጃ ነው ። ኢኮኖሚያዊ ማዕቀብ ተግባራዊ የሚሆነው ማዕቀቡ ከተጣለበት ሀገር ጋር ሌሎች ሀገሮች ያላቸውን የንግድ ፣ የገንዘብ ፣ የብድርና ሌሎች የኢኮኖሚ ግንኙነቶችን በማቋረጥ ነው ። የሚጣለው ማዕቀብ የኢኮኖሚውን ልዩ ልዩ ዘርፎች በሙሉ ወይም በከፊል ብቻ የሚነካ ሊሆን ይችላል ። ብዙውን ጊዜ በአንድ ሀገር ላይ የፖለቲካ ብቸኝነትን ለመፍጠር ፖለቲካዊ ማዕቀብ ፣ ለምሳሌ የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ማቋረጥ ፣ ከኢኮኖሚያዊ ማዕቀብ ጋር እንዲጎዳኝ ይደረጋል ።

አንድ መንግሥት የዓለምአቀፍ ግንኙነት መሠረታዊ መርሆችን በመጣስ ወንጀል ቢፈጽም ማዕቀብ ይጣልበታል ። ማዕቀቡም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አማካይነት በአጥፊው መንግሥት ላይ የንግድ ማዕቀብ ፣ የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ማቋረጥ ፣ ከተባበሩት መንግሥታት አባልነት መሠረዝና ሌሎች ተመሳሳይ እርምጃዎችን መውሰድ ሊሆን ይችላል ። የዓለምን ሰላም ለመጠበቅ በአንድ ሀገር ላይ ማዕቀብ ማድረግ ትክክለኛ እርምጃ መሆኑ በተባበሩት መንግሥታት ደንብ ላይ የሰፈረ ነው ።

ኃያላን ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ሶሻሊዝምን ለመዋጋት የሶሻሊስት ሀገርችና እንደዚሁም ኋላቀር የሆኑ ተራማጅ ሀገሮች የሚከተሉትን የሶሻሊስት መሥመር በግድ እንዲለውጡ ለማድረግ በእነዚህ ሀገሮች ላይ የማዕቀብ እርምጃ ሲወስዱ ቆይተዋል ፤ ዛሬም እየወሰዱ ናቸው ። የአሜሪካ መንግሥት በሶቭዬት ኅብረት ሶሻሊስት ሪፐብሊክ ፣ በሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኮሪያ ሪፐብሊክና በሌሎችም ሀገሮች ላይ የማዕቀብ እርምጃ የወሰደ ሲሆን ይህን ተግባሩን ዛሬም አላቋረጠም ። የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በአብዮታዊት ኩባ ሕዝብና መንግሥት ላይ በጣለው ማዕቀብ የተነሣ የኩባ የምርት ውጤቶች በአሜሪካ ገበያ ላይ እንዳይሸጡ ፣ እንደዚሁም የአሜሪካ የምርት ውጤቶች በተለይም መድኃኒቶችና ልዩ ልዩ መሣሪያዎች ወደ ኩባ እንዳይገቡ አድርጓል ። የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በዚህ ወንጀለኛ እርምጃው ተራማጅ ሀገሮችን ለማግለል ታጥቆ ቢነሣም በተግባር እንደታየው ይህ እርምጃ እንዳሰበው ሊሳካለት አልቻለም ። በአንፃሩም የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝምና ሌሎችም ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በደቡብ አፍሪካ ላይ የጣለውን ማዕቀብ በመጣስ በዘረኝነት ላይ የተመሠረተውን ሽብር ፈጣሪ መንግሥት በመደገፍ ላይ ይገኛሉ ።

## ኢኮኖሚያዊ ትግል
(*Economic Struggle*)

ከወዝአደሩ የዕለት ተዕለት ኑሮና ፍላጎት ጋር የተያያዘውና ከቡርዧዚው ጋርየሚካሄደው የመደብ ትግል የመጀመሪያ ምዕራፍና የትግል ቅርፅ ነው ። ትግሉ የሚያመለክተው ወዝአደሩ የደሞዝ ጭማሪ ፣ የሥራ ሰዓት ቅነሳ ወዘተ... በመጠየቅ የኑሮውንና የሥራውን ሁኔታ ለማሻሻል እንደሚጥር ነው ። ጥያቄው ምላሽ ሳያገኝ ሲቀር የትግሉ ዋና መሣሪያ የሆነውን የሥራ ማቆም አድማ ያካሂዳል ። ትግሉ የሚጠበቀውን ውጤት ሊያስገኝ የሚችለው ወዝአደሮቹ የራሳቸውን ድርጅት የመሠረቱ እንደሆን በመሆኑ ኢኮኖሚያዊ ትግል ለሠራተኛ ማኅበራት መመሥረት ቀጥተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

የኢኮኖሚያዊ ትግል ጠቃሚነት ግልጽ ነው ። ሙሉ በሙሉ ባይሆንም በኢኮኖሚያዊ ትግል የተነሣ ወዝአደሩ የኑሮውን ሁኔታ ለማሻሻል ችሏል ። ዋናው ሚናግን ወዝአደሩን ለትግል የሚያሰባስብና በዚህም ትግል ውስጥ መደባዊ ንቃተ ኅሊና እንዲኖረው አመች ሁኔታ መፍጠሩ ነው ። ሆኖም የኢኮኖሚያዊ ትግል ውሱንነት የማይካድ ነው ። ትግሉ የካፒታሊስት ሥርዓትንና የካፒታሊስት ግንኙነትን ከመሠረቱ የሚያናጋ ባለመሆኑ ለወዝአደሩ መሠረታዊና ዘላቂ መፍትሔ

አያስገኝም ። ወዝአደሩ ለጉልበቱ ዋጋ መጨመር ተከራካሪ እንጂ ጉልበት ሻጭ መሆኑን አልቀበልም አላለም ። በመሆኑም ኢኮኖሚያዊ ትግል ምንነቱን ስቶ ወዝአደሩ በጥገና ለውጥ ፍላጎት ላይ እንዳይወሰን ትግሉ ወደከፍተኛ ደረጃ ማለትም ወደ ርዕዮተዓለማዊና ፖለቲካዊ ትግል መሸጋገር አለበት ።

(የመደብ ትግልን ፣ ፖለቲካዊ ትግልን ፣ ርዕዮተዓለማዊ ትግልን ይመለከቷል ።)

# ኢኮኖሚዝም
*(Economism)*

የወዝአደሩን መደብ ንቅናቄ በኢኮኖሚያዊ የትግል መስክ ብቻ ለመወሰን የሚጥር ፣ ወዝአደሩ የፖለቲካ ትግሉን ለነፃው ቡርዧዚ መተው አለበት የሚል ፣ የወዝአደሩን ፓርቲና አብዮታዊ ንድፈ ሐሳብ ሚና የማይቀበል ፣ በአንፃሩም የወዝአደሩ መደብ ትግል ግብታዊነት የሰፈነበት እንደሆነ አድርጐ ይሰብክ የነበረ ፣ በ19ኛው ምዕት ዓመት መጨረሻና በ20ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ላይ በሩሲያ የተከሰተ የማኅበራዊ ዲሞክራሲ አድርባይ አዝማሚያ ነው ።

ኢኮኖሚዝም የከላሽነት አንድ ገጽታ በመሆኑ የቡርዧዚውን ተፅዕኖ በወዝ አደሩ ላይ ለማስፈን በመጣር የወዝአደሩ ፓርቲ እንዳይፈጠር ከፍተኛ ዕንቅፋት ሆኖ ነበር ።

የወዝ አደሩ መደብ የዕለት ተዕለት ግብታዊ ትግል የወዝአደሩን ንቃተ ኅሊና ወደ መደባዊ የንቃተ ኅሊና ደረጃ ሊያሸጋግረው ይችላል ስለሚል የሶሻሊስት ንድፈ ሐሳብ ከሳይንስ ፣ ከታሪክና ከፍልስፍና መመንጨቱን ይክዳል ። ከዚህም በማለፍ አንቂዎች ንቃታቸውን ወደ ወዝአደሩ መደብ ንቃተ ኅሊና ደረጃ ዝቅ ማድረግ አለባቸው እንጂ ወዝአደሩን ወደ ራሳቸው ንቃተ ኅሊና ደረጃ ከፍ ማድረግ የለባቸውም በማለት የፓርቲውን የማንበር ቀደምትነት ሚና የነቃው የመደብ ክፍል የመሆኑን ባሕርይ ያቃልላል ።

ይህ አመለካከት ለረጅም ጊዜ የቆየ ፣ በአሁኑም ወቅት ያለ ነው ። ማርክሳዊ ንጽረተ ዓለምን በአጠቃላይ ፣ ማርክሳዊ ቁስአካላዊ የታሪክ ግንዛቤን በተለይ ለማጣመም የሚሹ ኃይሎች ማርክሲዝም ለቁሳዊ ሕይወት የሚሰጠውን የቀዳሚነትና የወሳኝነት ሚና በተዛባ መንገድ ይተረጉማሉ ። ኢኮኖሚው ወይም መሠረቱ ብቻ ወሳኝ እንደሆነና ኅሊናዊ ሕይወት ወይም ፖለቲካዊና ርዕዮተዓለማዊው አመለካከት ሚና እንደሌላቸው አድርጐ ማርክሲዝም ይተረጉማል በማለት የተዛባ ፍች በመስጠት ማርክሲዝም ኢኮኖሚዝም እንደሆነ አድርገው ይወስዳሉ ። የኅብረተሰብ ኅሊናዊ ሕይወት መልኮች በኢኮኖሚያዊ መሠረቱ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩና እራሳቸው ግን በመጨረሻው የሚወሰኑት በቁሳዊ ሕይወት ነው የሚለውን ማርክሳዊ አስተሳሰብ በማጣመም ነው ማርክሲዝም ኢኮኖሚዝም ነው የሚሉት ።

(የመደብ ንቃተ ኅሊናን ፣ መሠረትና ላዕላይ መዋቅርን ፣ አንፃራዊ ነፃነትን ይመለከቷል ።)

# ኤንግልስ ፤ ፍሬደሪክ ፤
*(Engels, Frederick)*

ከ1820 እስከ 1895 የኖረና የወዝአደር መሪ የነበረ ፣ ከማርክስ ጋር በመሆን ማርክሳዊ አስተምህሮን ፣ የሳይንሳዊ ኮሚኒዝምንና የዲያሌክቲካዊና የታሪካዊ ቁስአካልነትን ንድፈ ሐሳብ የቀመረ ጀርመናዊ ፈላስፋ ነው ።

ኤንግልስ በወቅቱ የነበረው ማኅበራዊ ግንኙነት እንዲለወጥ በሚደረገው ትግል ውስጥ ለመሳተፍ ከወጣትነት ዕድሜው ጀምሮ ጥረት ያደረገ ነበር ። የወጣት ሄግልያውያን ግራ ክንፍ ቡድን አባል በነበረበት ጊዜ በሼሊንግ አድኃሪ ተማልሎታዊ አመለካከት ላይ ጥልቀት ያለው ኂስ አቅርቧል ። በተጨማሪም ሄግል በቀመረው ሐሳባዊ ዲያሌክቲክስ ውስጥ ሼሊንግ የሰጠው ወግአጥባቂ ማጠቃለያ እርስ በርስ የሚቃረን መሆኑን አስመልክቶ ኂስ ሰንዝሯል ።

እንግሊዝ ውስጥ በነበረበት ወቅት በወዝአደሩ ላይ ስለሚደርሰው የኢኮኖሚ ጭቆናና ወዝአደሩ የፖለቲካ ሥልጣንን ሸለመነፈጉ ሰፊ ጥናት ካደረገና ቡርዧዚው ሥልጣኑን ለወዝአደሩ በፈቃዱ ይለቃል የሚለውን ተምኔታዊ አመለካከት ይዞ የተነሣውን የቻርቲስትን እንቅስቃሴ ድክመት ከመረመረ

በኋላ "ኧ ኮንትሪቢዩሽን ቱ ዘ ክሪቲክ ኦቭ ፖለቲካል ኢኮኖሚ" (1844) እና "ዘ ኮን ዲሽን ኦቭ ዘ ዎርኪንግ ክላስ ኢን ኢንግ ላንድ" (1845) በሚሉ ርዕሶች የወዝአደሩን የወደፊት ብሩህ ገጽታና የሚጫወታቸውንም ታሪካዊ ሚናዎች በግልጽ አሳይቷል ። ወዝ አደሩ የሚጨቆን ብቻ ሳይሆን ለአርነቱ የሚታገል መደብ መሆኑንም ለመጀመሪያ ጊዜ ገሀድ ያወጣው ኤንግልስ ነበር ።

ወደ ፓሪስ ሄዶ ከማርክስ ጋር ከተ ገናኘ በኋላ ወዝአደሩን ከካፒታሊዝም ቀን በር ለማላቀቅ የነበራቸው ሐሳብ ሁለቱንም ያጣመራቸው በመሆኑ "ዘ ሆሊ ፋሚሊ" እና "ዘ ጀርመን አይዲኦሎጂ" የተሰኙትን መጻሕፍት በጋራ ጽፈዋል ። የነዚህም ጽሑ ፎች ዋና ዓላማ በወቅቱ የበላይነት የነበረውን የሄግልን ፣ የፎየርባኽንና የነርሱን ተከታዮች ፍልስፍና የሚገመግምና የሚኄስ ነበር ። በዚህም አጋጣሚ ማርክስና ኤንግልስ የዲያ ሌክቲካዊና የታሪካዊ ቁስአካልነትን መሠረተ ሐሳብ አስፋፍተዋል ። ከዚህም በላይ የኮሚ ኒስት ሊግ እንዲመሠረትና በኋላም ወደ ወዝአደሩ አብዮታዊ ፓርቲ ደረጃ ከፍ እን ዲል ከፍተኛ ተግባር አከናውነዋል ። ኤንግልስ "ፕሪንሲፕልስ ኦቭ ኮሚኒዝም" በሚል ርዕስ በ1847 የሊጉን ፕሮግራም ጽፏል ። ይህን ንም መሠረት በማድረግ ማርክስና ኤንግልስ ከሚኒስት ማኒፌስቶን በ1848 አዘጋጅተዋል ።

ኤንግልስ የተሳተፈበት የ1848—49 የጀርመን አብዮት ከከሸፈ በኋላ "ፒዛንት ዎር ኢን ጀርመኒ" እና "ሪቮሉሽን ኤንድ ካውንተር ሪቮሉሽን ኢን ጀርመኒ" በሚሉ ርዕሶች ገበሬው የወዝአደሩ አጋር በመሆን ስለ ሚጫወተው ሚና ሲዘረዝር የቡርዧዚውንም ክህደት አጋልጧል ።

ሠራተኛው የመጀመሪያውን ኢንተርና ሽናል ለመመሥረት ባደረገው እንቅስቃሴ የንዑስ ከበርቴን አድርባይነትና ሥርዓት አልበኝነት አመለካከት ለመዋጋት ባካሄደው ትግል ውስጥ ኤንግልስ ንቁ ተሳታፊ ነበር ።

ማርክስ ካፒታልን በሚጽፍበት ጊዜ የማርክስ ረዳት ከመሆኑም በላይ ማርክስ በዚህ ሥራ ሙሉ በሙሉ ተጠምዶ በነበረ በት ወቅት ኤንግልስ ዲያሌክቲካዊና ታሪ ካዊ ቁስአካልነትን አዳብሯል ። ማርክስ ከሞ ተም በኋላ የካፒታልን ቅጽ ሁለትና ቅጽ ሦስት በጥንቃቄ መርምሮ አዘጋጅቷል ።

እንደ "ሉድቪግ ፎየርባኽ ኤንድ ዘ ኢንድ ኦቭ ክላሲካል ጀርመን ፊሎሶፊ" ፣ "አንታይ ዱሪንግ" ፤ "ዘ ኦሪጅን ኦቭ ዘ ፋሚሊ ፣ ፕራይቬት ፕሮፐርቲ ኤንድ ዘ ስቴት" ያሉትና የመሳሰሉት የኤንግልስ ሥራዎች ለማርክሳዊ ፍልስፍና ዕድገት የረዱ ዓበይት ክንውኖች ናቸው ።

የዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነትን ሐሳብ ለተፈጥሮ ሳይንስ የተጠቀመበት ኤንግልስ ነበር ፤ ለዚህም "ዲያሌክቲክስ ኦቭ ኔቸር" ፣ "ሉድቪግ ፎየርባኽ" እና "አንታይ ዱሪንግ" የተባሉት ሥራዎቹ በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው ።

ኤንግልስ የፍልስፍናን መሠረታዊ ጥያቄዎች የቀመረ ፣ ፍልስፍናም መደባዊ ይዘት ያለው መሆኑን የገለጸ ፣ የዕውቀትን ንድፈ ሐሳብ ያዳበረና ኢታዋቂነትን ያጋለጠ ነው ።

ኤንግልስ በመሠረትና በላዕላይ መዋቅር መካከል ስላለው ግንኙነትና መስተጋብር የቀረበውን ተናክአታዊ አመለካከት በመዋጋት ኅብረተሰቡ የሚገኝበት ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የሚጫወተው ወሳኝ ሚና ሐሳቦች ወይም ግለሰቦች ሊኖራቸው የሚችለውን ተፅዕኖ ሊቀንስ እንደማይችል ያረጋገጠ ፣ ስለዲያሌ ክቲካዊ ሥነ አመክንዮ በርካታ ጥያቄዎችን ያነሣና አስፋፍቶ የገለጸ ፣ የታሪካዊ ቁስአካ ልነትን መሠረታዊ ጥያቄዎች በሚገልጽበት ወቅት ስለታሪካዊ ቁስአካልነት የቀረበውን ግልብ ግንዛቤ ያጋለጠ ፣ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ በአውሮፓ ውስጥ በነበረው የፖለቲካ ትግል ውስጥ የተሳተፈና ከማርክስ ጋር የወዝአደሩ እንቅስቃሴ መሪ የነበረ ነው ።

## ኤፌቆሮስ
*(Epicurus)*

ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ341 — 270 የኖረ የጥንታዊት ግሪክ ቁስአካላዊና ኢአማኒ ፈላስፋ ነው ።

ኤፌቆሮስ ፣ አማልክት በዚህ ዓለም ጉዳይ አይገቡም ፤ ቁስአካል ዘለዓለማዊና በራሱ የሚንቀሳቀስ ነው ፤ የእንቅስቃሴው

ምንጭ አቶሞች ናቸው ፤ የአቶሞች ግጭት ከግብታዊ እንቅስቃሴያቸው የሚመጣ ነው የሚል አጠቃላይ አስተሳሰብ ነበረው ።

ይህ ፈላስፋ ሕዋሳት ከነባራዊ እውነታ ጋር የተቆራኙ በመሆናቸው በራሳቸው እውንና የዕውቀት ምንጭ ናቸው ፤ ስሕተት የሚመጣው ከሕውስታ የሚገኙትን መረጃዎች ከመተርጐሙ ላይ ነው ፤ በሕዋሳት አማካይነት የሚቀረፁት መረጃዎች መንሥኤ ከነገሮች የሚመነጩ ብናኞች በሰው አካል ላይ ሲያርፉ የሚፈጥሩት የነገሮች ምስል ነው ፤ የዕውቀት ዓላማ ሰውን ከድንቁርና ፣ ከአምልኮትና አምልኮ ከሚያስከትለው ፍርሃት ነፃ ማውጣት ነው የሚል የዕውቀት ንድፈ ሐሳብ ቀምሯል ።

ስቃይ የሌለበትና ፀጥታ የተሞላበት የመንፈስ ደስታ የሰው ሕይወት ከፍተኛ ግብ ነው የሚል የሥነ ምግባር አስተሳሰብም ነበረው ። ኤፊቆሮስ ቁስአካላዊ ቢሆንም አመለካከቱ ተናከአታዊ ከመሆኑም በላይ የግላዊ ደስታ ፍላጐቱ ከማኅበራዊ ኑሮ አርቆታል ።

## እመርታ ፤
## (*Leap*)

አሮጌው ዓይነት ለሚተካው አዲስ ዓይነት ቦታውን ለቆ የሚያልፍበት የመጨረሻ የሽግግር ደረጃ ወይም ቅጽበት እመርታ ይባላል ። በአንድ ነገር ውስጥ የሚካሄደው የማያቋርጥና አዝጋሚ የመጠን ለውጥ ድርጅት ከነበረው ዓይነት ጋር አብሮ ሊሄድና ሊጣጣም ባልቻለበት ወቅት የነበረውን ያረጀና ያፈጀ ዓይነት ሽሮ ወደ አዲሱና ከፍተኛው የዕድገት ደረጃ ይሸጋገራል ። ማንኛውም ነገር ወይም ክስተት ጠባዩና ዕድገቱ የሚከናወንበት ሁኔታ እንደመለያየቱ የእመርታውም ቅርፅ ይለያያል ። እመርታን በጣም አጠቃላይ በሆነ መንገድ ከሁለት ከፍሎ ለማየት ይቻላል ። 1ኛ/ ቅጽበታዊ እመርታ ፣ 2ኛ/ ዝግተኛ እመርታ ።

ቅጽበታዊ እመርታ ፈጣን የሆነና አሮጌው ዓይነት ወደ አዲስ ዓይነት በቶሎ ወይም በአንዴ የሚለወጥበት ሁናቴ ነው ። በቁስአካላዊው ዓለም አንዳንድ ንጥረ ነገሮች በተፈጥሮ ኃይል አስገዳጅነት የነበረ ባሕርያቸው ድንገት ወደ ሌላ ሲለወጥ ቅጽበታዊ እመርታ ያሳያሉ ። ለምሳሌ በተወሰነ የሙቀት ደረጃ የሁለት የኦክስጂን አቶሞች ወደ አንድ የኦዞን አቶም ይለወጣሉ ። በኅብረተሰብም ውስጥ ይኸው እመርታ ይከሰታል። ለምሳሌ በቄሳራዊት ሩሲያ የተካሄደው የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮትና በኢትዮጵያ የፈነዳው የየካቲት 66 (እንደ ኢት. አ.) አብዮት እያንዳንዱን ኅብረተሰብ ከሥረመሠረቱ በማናጋት ለብዙ ጊዜ ተንሰራፍተው የነበሩ ሥርዓቶችን በከፍተኛ ፍጥነት እንዲለወጡ አድርገዋል ።

ቅጽበታዊ እመርታ የማይታረቁ ቅራኔዎች ግጭት ውጤት ነው ። ለምሳሌ በቡርዧዚውና በወዝአደሩ መካከል የማይታረቅ ዓይነተኛ ቅራኔ አለ ። ወዝአደሩ የቡርዧውን መደብ ደምስሶ የበላይነቱን የሚያረጋግጠው በፖለቲካዊ አብዮት ነው ። ይህ አብዮት የሚያስከትለው ቅጽበታዊ እመርታ የሶሻሊስት ሥርዓትን ይወልዳል ።

ዝግተኛ እመርታ የመጠን ለውጥ በመጠራቀምና በመደራጀት ነባሩ ዓይነት በአንድ ጊዜ ሳይሆን ቀስ በቀስ ፣ ደረጃ በደረጃና በከፊል እየተለወጠ በመጨረሻ አዲስ ዓይነት የሚሆንበት ሂደት ነው ። ለምሳሌ በኅብረተሰብ ዕድገት ከቅድመ ካፒታሊስት ወይም ከካፒታሊስት ኅብረተሰብ ወደ ሶሻሊስት ኅብረተሰብ ቅጽበታዊ እመርታ ከተደረገ በኋላ ከሶሻሊዝም ወደ ኮሚኒዝም የሚደረገው ለውጥ በዝግተኛ እመርታ ይከናወናል ።

የሁለቱ እመርታዎች ሁኔታ እንደነገሩ ጠባይና ከሌሎቹ ነገሮች ጋር ባለው ግንኙነት ይለያይ እንጂ አንድ ነገር አርጅቶ ወደ አዲስ ዓይነት ሲለወጥ የግድ እመርታ ይኖራል ። ኅብረተሰብን በሚመለከት "ቅጽበታዊ እመርታ በመደብ በተከፋፈለ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ውስጥ ግዴታ ሲሆን ተፃራሪ መደቦች በሌሉበት ኅብረተሰብ ግን ዝግተኛ እመርታ ዓይነተኛው የለውጥና የዕድገት ሂደት ነው ።

(ለውጥን ፣ የዓይነት ለውጥን ፣ የመጠን ለውጥን ይመለከቷል ።)

## እማዊ ሥርዓት
*(Matriarchate)*

በጥንታዊ የኅብረተሰብ ዕድገት ውስጥ ለተወሰነ ዘመን ጸንቶ የቆየ የሴት የበላይነት የሰፈነበት ሥርዓት ነው ።

የእማዊ ሥርዓት መሠረታዊ ባሕርያት በጐሳ መሰል ሥርዓት ውስጥ የመሪነት ቦታ የሴቶች መሆኑ ፣ ውርስ የናትን ዘረ ሐረግ ተከትሎ የሚሄድና ባሎችም መኖሪያቸውን በሴት አማቶቻቸው ቤት (መንደር) ማድረግ ያለባቸው መሆኑ ነው ። የእማዊነት ሥርዓትን ያሰፉ አንዳንድ ሕዝቦች የነበሩ መሆኑን ለመጀመሪያ ጊዜ ያጠና ባሆፈን የተባለ የጀርመን ሊቅ ነበር ።

(አባዊ ሥርዓትን ይመለከቷል ።)

## እምነታዊነት
*(Fideism)*

ዕውቀትን ወደእምነት የሚለውጥ ወይም ደግሞ ከዕውቀት ይልቅ ለእምነት ከፍተኛ ቦታ የሚሰጥ ማንኛውም አስተምሀሮ እምነታዊነት ይባላል ። ይህ ጽንሰ ሐሳብ በአጠቃላይ የሐሳባዊ ፍልስፍናን ባሕርይ የሚገልጽ ነው ።

ሐሳባዊነት ለሂደተ ዕውቀት መንፈሳዊ ባሕርይና ለተደራጊው ዲበተፈጥሮአዊ ሀልውና ስለሚሰጥ ደረስኩበት የሚለው ዕውቀት ተጨባጭነት የሌለው ፣ በእምነት ላይ የተመሠረተ ነው ። በዚህ ፍልስፍና ውስጥ ለሐሳብ የበላይነትና ለመንፈሳዊ ምክንያቶች የሚሰጠው ሚና በእምነት የተደገፈ እንጂ ከተረጋገጠ ዕውቀት የመነጨ አይደለም ። ዲበተፈጥሮአዊ የሆነ ነገር ሁሉ ለሕዋሳት የማይገለጥ ወይም ደግሞ በተግባር ሊረጋገጥ የማይችል በመሆኑ እምነታዊነት የሰውን የዕውቀት ችሎታ የሚበክል ነው ።

## እሳቤ
*(Conception)*

ማሰብ ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም ተጠንቶ ፣ ተሰላስሎ የታወቀ ወይም የተገኘ ዕውቀት ማለት ነው ።

እሳቤ የአንድን ነገር ተናጠል ባሕርያት ሳይሆን የነገሩን ምንነትና ባሕርያቱን ባንድነት (በውህደት) እንዲሁም ነገሩ ከሌሎች መሰል ነገሮች ጋር ያለውን ግንኙነት የምንረዳበት የዕውቀት ደረጃ ነው ።

እሳቤ የሁኔታዎች ፣ የድርጊቶች ፣ የነገሮችና የክስተቶች ዳር ድንበርና ቅርፅ ነፀብራቅ ነው ። ሕውስታዊ ዕውቀት ከፍና ጠቅለል ያለ ሲሆን ከጽንሰ ሐሳብ አንፃር ሲታይ ግን አጠቃላይነቱ መለስተኛ ነው ።

(ጽንሰ ሐሳብን ፣ ግንዛቤን ይመለከቷል ።)

## እሳቦት
*(Thought)*

የቁስአካል ልዩ ድርጅት፣የአንጐል ከፍተኛው ውጤት የሆነ ነባራዊውን ዓለም በጽንሰ ሐሳብ፣ በንድፈ ሐሳብና በብያኔ ወዘተ... የማንፀባረቅ ችሎታ እሳቦት ይባላል ። እሳቦት የሚመነጨው ከሰዎች ማኅበራዊ የተግባር እንቅስቃሴ ሲሆን እውነታን ከሰው የሚያገናኝና የእውነታን ውስጣዊ ግንኙነቶች የሚገልጽ ነው ። ከአጸናነሱ ፣ ከአሠራሩና ከውጤቱ አንፃር ሲታይ እሳቦት አንጐላዊ ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ ውጤት መሆኑን ለመረዳት ይቻላል ። ምክንያቱም እሳቦት የኅብረተሰብ ማኅበራዊ ኑሮ ልዩ ጠባዮች ከሆኑት ከሥራና ከንግግር ተለይቶ ሊታይ አይችልም ። እርቅቀት ፣ ትንታኔ ፣ አስተፃምሮ ፣ ጽንሰ ሐሳብ ፣ ብያኔ ፣ ንድፈ ሐሳብ ወዘተ... የእሳቦት ዋና ዋና ክንውኖች ናቸው ።

የሐሳባዊነት የማያቋርጥ ጥረት እሳቦትን ከቁስአካል መለየት ነው ። አንጐልና ማኅበራዊ ኑሮ የእሳቦት ምክንያቶች መሆናቸው ቀርቶ የሱ ውጤትና መሣሪያ እንደሆኑ አድርጐ በመተርጐም ሐሳባዊነት ለእሳቦት ኢቁስአካላዊ ምንጭ ለመስጠት ሞክሯል ። ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት በተፈጥሮ ዕድገት ላይ በመመሥረት እሳቦት የቁስአካል ከፍተኛው ውጤት መሆኑን ከማሳየቱም በላይ ማኅበራዊ መንሥኤውንና ይዘቱን በግልጽ አብራርቷል ።

(ተግባርን ፣ ግንዛቤን ፣ ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነትን ይመለከቷል ።)

## እሴት
*(Value)*

በሸቀጥ ውስጥ የሚጠናቀረው ሸቀጥ አምራቾች አንድን ምርት ለማምረት የሚያፈሉት ማኅበራዊ ሥራ እሴት ይባላል ። እሴት ምርት በሚመረትበት ወቅት ሁሉ ያለ ዘለዓለማዊ ፈርጅ አይደለም ። በአንድ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት ማለትም ከሸቀጥ መመረት ጋር ብቅ ያለ ታሪካዊ ክስተት ነው ። እሴት የሚፈጠረው ሸቀጥ በሚመረትበት ሂደት ውስጥ ቢሆንም ይፋ የሚወጣው ግን የተመረተው ሸቀጥ ከሌሎች ሸቀጦች ጋር በሚነፃፀርበት በልውውጥ መስክ ላይ ነው ።

ለልውውጥ የሚቀርቡት ሸቀጦች ከሚሰጡት ጠቀሜታ አንፃር የተለያዩ ናቸው ። ቢሆንም አንድ የሚያደርጋቸው ዓይነተኛ ባሕርይም አላቸው ፤ ይኸውም ሸቀጦች ሁሉ የማኅበራዊ ሥራ ውጤት መሆናቸው ፣ ማኅበራዊ ሥራም እሴታቸው መሆኑ ነው ። ሸቀጥን በሸቀጥ በምንለውጥበት ጊዜ የምናስተያየው ወይም የምንለካው በሸቀጦቹ ውስጥ የተጠናቀረውን ይህን እሴት ነው ።

የአንድ ሸቀጥ እሴት የሚለካው በሸቀጡ ውስጥ በፈሰሰው የሥራ ጊዜ ነው ቢባልም የተለያዩ ሸቀጥ አምራቾች አንድ ወይም ተመሳሳይ ሸቀጥ ለማምረት የተለያየ የሥራ ጊዜ ስለሚወስድባቸው የተመረቱት ሸቀጦች የተለያየ እሴት ይኖራቸዋል ማለት አይደለም ። ምክንያቱም እሴት ማኅበራዊ ሥራን የሚገልጽ በመሆኑ ማኅበራዊ እሴት የግል አምራቾች አንድን ምርት ለማምረት ያፈሰሱትን ሥራ በተናጠል ስለማይመለከት ነው ። እሴት ማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ በመሆኑ የሚሰላው በጊዜው የምርት ኃይሎች በደረሱበት የዕድገት ደረጃና ባለው የአሠራር ልምድ ችሎታ ላይ በመመርኮዝ አንድ ዓይነት ሸቀጥ የሚያመርቱ አምራቾች ያንን ሸቀጥ ለማምረት በአማካይ በሚወስድባቸው ጊዜ አንፃር ነው ።

የሸቀጦች እሴት በሚተመንበት ወቅት በሸቀጡ ውስጥ የፈሰሰው የሥራ ጠባይ እሴቱ አተማመን ላይ ተፅዕኖ ያደርጋል ። ይህም ማለት ውስብስብ ሥራ ከቀላል ሥራ የሚበልጥ በጥቂት ሰዓት ውስጥ የተከናወነው ውስብስብ ሥራ ብዙ ሰዓት የፈጀ ቀላል ሥራ ከሚፈጥረው እሴት ሊበልጥ ይችላል ።

እሴት በውስብስብም ሆነ በቀላል ሥራ አማካይነት ይፈጠራል ቢባልም የእሴቱ መጠን የሚለካው ግን ውስብስቡን ሥራ በቀላል ሥራ በመተመን ነው ።

እሴት ከሸቀጥ ግንኙነት ጋር ብቅ ያለ ታሪካዊ ፈርጅ ስለሆነ የሸቀጥና የገንዘብ መኖር አስፈላጊ በማይሆንበት የኮሚኒስት ሥርዓት ህልውናው ያከትማል ።

(የጠቀሜታ እሴትን ፣ የልውውጥ እሴትን ይመለከቷል ።)

## እሴት ሕግ (የ—)
*(Law of Value)*

የሸቀጥ ምርት ባለበት ሁሉ ሸቀጦች ማኅበራዊ አስፈላጊነት ባለው የሥራ ጊዜ መጠን መለዋወጣቸውን የሚወስን ኢኮኖሚያዊ ሕግ ነው ። የእሴት ሕግ ከልውውጥ መከሰት ጋር አብሮ የመጣ በመሆኑ ልውውጥ ባለበት ሁሉ ይሠራል ። የሕጉ አሠራር ግን እንደየኅብረተሰቡ የምርት ግንኙነት ዓይነት ለውጥ ያሳያል ። የግል ሀብትን መሠረት ባደረገ የሸቀጥ አመራረት ውስጥ የእሴት ሕግ የሚሠራው ከኅብረተሰቡ ቁጥጥር ውጭ በመሆን በግብታዊነት ነው ። በካፒታሊስት አመራረት ምን ምን ዓይነት ሸቀጥ በምን ያህል ብዛት መመረት እንዳለበት የሚመራ ማኅበራዊ ዕቅድ የለም ። እንደ አቅርቦትና እንደ ፍላጐት ሁኔታ ዋጋ ከእሴት ወደ ላይም ሆነ ወደታች ስለሚዋዥቅ ይህ ሁኔታ በአመራረቱ ሂደት ውስጥ ግብታዊነትን ያስከትላል ። ስለዚህም በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ያልተመጣጠነ ዕድገት የሚኖረው የአንዱ ኢንዱስትሪ ዘርፍና የሌላው ፣ ወይም የአምራቹና የገበያው ግንኙነት ሥርዓት የለሽና ግብታዊ በመሆኑ ጠቅላላውም አመራረት በኅብረተሰቡ ሳይሆን በእሴት ሕግ ተገዥ በመሆኑ ነው ። በካፒታሊስት ሥርዓት ይህ ሕግ የሚገለጸው በምርት ዋጋ አማካይነት ነው ።

በሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበርም ውስጥ የእሴት ሕግ ይሠራል ። ሆኖም በካፒታሊዝም ውስጥ ያለው ዓይነት የወሳኝነት ሚና የለ

ውም ። ምክንያቱም በሶሻሊዝም ውስጥ የምርት መገልገያዎች የጋራ ሀብት ፣ የሕዝብ ሀብት ስለሆኑ ከልውውጥ ውጭ በመሆናቸው ነው ።

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ የምርት መገልገያዎችና የሥራ ኃይል አሰረጫጨት በመንግሥቱ ዕቅድ አውጭ አካላት በዕቅድና በብሔራዊ ኢኮኖሚው የተመጣጠነ ዕድገት ሕግ መሠረት የሚካሄድ ነው ። ይሁንና ኅብረተሰብ በዚህ ደረጃ ላይ የፍጆታ ዕቃዎችን በማምረቱና በማከፋፈሉ ረገድ የእሴት ሕግ ተፅዕኖ ይኖረዋል ።

የእሴት ሕግ ከሸቀጥ ምርትና ከልውውጥ ጋር እንደመምጣቱ በኮሚኒስት ኅብረተሰብ የዕድገት ደረጃ ፣ ማለትም የሸቀጥ ምርትና ልውውጥ በሚያከትሙበት ጊዜ አብሮ ያከትማል ።

(የተረፈ እሴት ሕግን ይመለከቷል ።)

## እሴት መልክ (የ—)
*(Form of Value)*

አንድ ሸቀጥ ከሌላ ሸቀጥ ጋር ተነፃፅሮ እሴቱ የሚገለጽበት ሁኔታ የእሴት መልክ ይባላል ። ለምሳሌ አንድ ሸቀጥ በገንዘብ ቢሸጥና ቢገዛ ፣ እሴቱ የተገለጸበት መልክ ገንዘብ ነው ። በየዘመኑ የተለያዩ የሸቀጥ ልውውጥ ዓይነቶች ታይተዋል ። እነዚህም የተለያዩ የሸቀጥ ልውውጥ ዓይነቶች ከሸቀጥ ምርት ዕድገትና መስፋፋት ጋር የተለያየ መልክ እየያዙ መጥተዋል ። በዚህም ሂደት ውስጥ የተለያዩ የእሴት መልኮች ተከስተዋል ። እነዚህም ፡—

1/ የእሴት ጥንተ መልክ ፤ 2. የተስፋፋ የእሴት መልክ ፤ 3/ አጠቃላይ (ሁለንታዊ) የእሴት መልክ ፤ 4/ ገንዘባዊ የእሴት መልክ ናቸው ።

### እሴት ጥንተ መልክ (የ—)
*(Elementary Form of Value)*

የእሴት ጥንተ መልክ በኅብረተሰብ የዕድገት ታሪክ ውስጥ ከትርፍ ምርት መከሰትና ከማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል ማቆጥቆጥ ጋር ተያይዞ የመጣ የመጀመሪያው የሸቀጥ ልውውጥ ያስከተለው የእሴት ዓይነት ነው ። በዚህ የሸቀጥ ልውውጥ ዓይነት የሥራ ክፍፍል እየተስፋፋ ሲሄድ በተለያየ የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ አምራቾች የምርት ውጤቶቻቸውን በአጋጣሚ መለዋወጥ ይጀምራሉ ። በዚህ ሂደት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ ዕቃ በሌላ ዕቃ ያለምንም የልውውጥ አማካይ በቀጥታ ይለወጣል ።

ለምሳሌ አንድ መጥረቢያ ሁለት ቁና ገብስ ከለወጠ የአንድ መጥረቢያ ተመጣጣኝ የሆነው የእሴት መልክ ሁለት ቁና ገብስ ነው ። ማለትም በዚህ ዓይነት የልውውጥ ጥምርታ (ሬሾ) አማካይነት አንድ መጥረቢያ ለመሥራት የፈሰሰው ማኅበራዊ የሥራ ጊዜ ሁለት ቁና ገብስ ለማምረት ከወጣው ማኅበራዊ የሥራ ጊዜ ጋር ተመጣጣኝ ነው ማለት ነው ። በመጥረቢያው ውስጥ የተጠናቀረው እሴት ሊተመን የሚችለው በዚህ ዓይነት መንገድ በሌላ ሸቀጥ ውስጥ ከተጠናቀረው እሴት ጋር ሲነፃፀር ሲችል ብቻ ነው ። በዚህ ዓይነት ሸቀጦች ወይም ዕቃዎች እርስ በርሳቸው ሲለዋወጡ እንዱ የሌላውን እሴት ይገልጣል ።

## እርስ በርስ ጦርነት (የ—)
*(Civil War)*

በጐሳ ፣ በሃይማኖት ፣ በመደብና እንዲሁም በተለያዩ የገዥ መደብ ክፍሎች መካከል የሚካሄድ የትጥቅ ትግል ነው ።

የእርስ በርስ ጦርነት ብዙውን ጊዜ የሚከሰተው አድኃሪ ገዥ መደቦች በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን የመደብ ቅራኔ ለማስታገስ ሲያቅታቸው ወይም "ሕጋዊ" በሆነ መንገድ ሕዝቡን እንደቀድሞው አፍነው በመያዝ መግዛት ሲሳናቸው ነው ። በዚህ ጊዜ በአድኃሪው ሥርዓት ሲበዘበዙና ሲጨቆኑ የነበሩ መደቦች የፖለቲካ ሥልጣን በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ በገዥ መደቦች ላይ የአመፅ እንቅስቃሴ ማካሄድ ይጀምራሉ ። የገዥ መደቦች በፈቃደኝነት የፖለቲካ ሥልጣናቸውን አሳልፈው ስለማይሰጡ የግዴታ የእርስ በርስ ጦርነት ይከተላል ። በታሪክ እንደታየው በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት ማኅበር

ውስጥ የባሮች አመፅ በየጊዜው ተካሂዷል ። በፊውዳሊዝም ውስጥም የገበሬ አመፆች በየ ቦታው ታይተዋል ። በካፒታሊዝም ውስጥ ደግሞ ከቡርዧው መደብ ሥልጣን ለመንጠቅና ሶሻሊዝምን ለመገንባት የተሰያዩ የእርስ በርስ ጦርነቶች ተካሂደዋል ።

ማርክሳውያን ሠርቶ አደሩን ሕዝብ ከጭቆና ነፃ ማውጣት ዓላማቸው አድርገው የሚነሡትን የእርስ በርስ ጦርነቶች ያለማወላወል ይደግፋሉ ። በአንፃሩ ግን የእርስ በርስ ጦርነት በማንኛውም ዓይነት ሁኔታ መካሄድ አለበት የሚሉትን "ግራ" አክራሪዎች በጥብቅ ይቃወማሉ ። ማርክሳውያን ከተቻለ ጭቁን መደቦች የፖለቲካ ሥልጣን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ከገዥ መደቦች መውሰዳቸውን ይመርጣሉ ። ሆኖም አድኃሪ መደቦች ሥልጣናቸው እንዳይወሰድባቸው ስለሚከላከሉና ቀድመውም መሣሪያቸውን በጭቁኖች ላይ ስለሚያነሡ ጭቁን መደቦች ለትጥቅ ትግል የሚያደርጉትን ዝግጅት ይደግፋሉ ። ስለዚህ የትጥቅ ትግልንና የትጥቅ ጥያቄን እንደሁኔታውና እንደየመደብ ትግሉ ደረጃ እንጂ በማንኛውም ጊዜና ቦታ እንደብቸኛና እንደፍጹማዊ የትግል ስልት አድርገው አይመለከቱትም ።

በታሪክ በተደጋጋሚ እንደታየው ከሶሻሊስት አብዮቶችና ከቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮቶች ጋር ተያይዘው የእርስ በእርስ ጦርነቶች ተካሂደዋል ። የቀድሞ አድኃሪ ገዥ መደቦች የፖለቲካ ሥልጣናቸውንና የኢኮኖሚ የበላይነታቸውን እንደገና ለማስመለስ ማኅበራዊው አብዮት ሥልጣኑን በተረከበው መደብ ላይ ጦርነት ይከፍታሉ ። በሥልጣን ላይ ያሉት አብዮታዊ ኃይሎችም የተነ[illegible]ገባቸውን የፀረ አብዮት እንቅስቃሴ ለመ[illegible]ምና ለመምታት የግዴታ በእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ለመግባት ይገደዳሉ ። ከታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት በኋላ በሶቪዬት ኅብረት የተካሄደው የእርስ በርስ ጦርነትና በኢትዮጵያም ከአብዮቱ ፍንዳታ ወዲህ ከፀረ አብዮት ኃይሎች ጋር የተደረገው የትጥቅ ትግል ይህንኑ የሚያረጋግጡ ናቸው ።

## እርባታ
*(Reproduction)*

ማንኛውም ኅብረተሰብ አንድ ጊዜ ባመረተው ምርት ብቻ ፍላጐቱን እያረካ ሊኖር አይችልም ። ስለዚህም ምርት በማያቋርጥ አኳኋን መቀጠል አለበት ። ይህም የምርት ተግባር እንደ ነጠላ ክንዋኔ ሳይሆን እንደማያቋርጥ ተደጋጋሚ ሂደት ሲታይ እርባታ ይባላል ። ይህም የቁሳዊ ምርትን ፣ የአምራች ኃይሉንና የምርት ግንኙነቱን እርባታ የሚያጠቃልል ነው ።

እያንዳንዱ ኅብረተሰብ የሚገኝበት ተጨባጭ ታሪካዊ ሁኔታ እንደሚለያይ ሁሉ የእርባታው ተግባር ሂደትም እንደዚሁ ይለያያል ። የእርባታ ተግባር በመሠረቱ በሁለት ይከፈላል ። አንደኛው ቀላል እርባታ የሚባለው ሲሆን በዚህ ዓይነት እርባታ የምርቱ ሂደት ቀደም ሲል በነበረበት ደረጃ ሳይለወጥ ይካሄዳል ። ሁለተኛው ዓይነት እርባታ ደግሞ የተስፋፋ እርባታ የሚባለው ሲሆን የምርቱ ሂደት ቀደም ሲል ከነበረበት ደረጃ በላይ በማደግ የሚታደስበት ነው ።

ቀላል እርባታ በቅድመ ካፒታሊስት ሥርዓቶች ውስጥ ጐልቶ ሲታይ የተስፋፋ እርባታ ደግሞ በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም ውስጥ ያለው እርባታ ዋንኛ መልክ ነው ።

(ቀላል እርባታን ፣ የተስፋፋ እርባታን ይመለከቷል።)

## እርካታ
*(Complacency)*

የካፒታሊስቶችን ኃይል ዝቅ አድርጎ ከመገመት የተነሣ በሠራተኛው ጥያቄ ውስጥ የሚንፀባረቅ የቸልተኝነት አቋም ነው ። በመደብ ትግል ውስጥ ቅንጣት የሆነ ቸልተኝነት ካፒታሊስቶችን እንደሚጠቅምና እያንዳንዱ የሠራተኛ መደብ የተሳካ እርምጃ የካፒታሊስቶችን የአፀፋ ሙከራ እንደሚያስከትል ካለመገንዘብ የሚመጣ ነው ። የአብዮቱ ኃይል እያደገ ሲሄድ የአብዮቱ ጠላቶች እጃቸውን የሰበሰቡና እንገታቸውንም የደፉ ስለሚመስል ይህን የተሳሳተ ግምት ማስወገድ አስፈላጊ ነው ። በተገኘው ድል ረክቶ

መዝናናትና ለጠላት መግቢያ ቀዳዳ መተው የአብዮታውያን ልምድ ስላልሆነ ምን ጊዜም ቢሆን አብዮቱን ነቅቶ መጠበቅ ዋንኛ ተግባራቸው ነው ።

## እንስታዊነት
*(Feminism)*

ለሴቶች ማኅበራዊና ሕጋዊ እኩልነት የቆመ የሚመስል ፣ በተግባር ግን የንዑስ ከበርቴውንና የቡርዧውን መደብ ሴቶች ጥቅምና ርዕዮተዓለም የሚያንፀባርቅ እንቅስቃሴ እንስታዊነት ይባላል ። ይህ እንቅስቃሴ በሠራተኛው መደብ ሴቶች ዘንድ ተቀባይነት የለውም ።

እንስታዊነት ከካፒታሊዝም መስፋፋት ጋር ከተያያዙ ለዘብተኛ ንቅናቄዎች አንዱ ሲሆን ባላባታዊና ደብተራዊ (ለምሳሌ “የሴት ቦታዋ ማጀቷ”) አመለካከቶችን በመቃወም ጠቃሚ አስተዋጽኦ አድርጓል ። ይሁን እንጂ የመደብ ትግልን ስለማይቀበል ለዘላቂ ድል ለሚደረገው ትግል አደገኛ ነው ። ሴቶች ከድርብ ጭቆና ነፃ ለመውጣት ያላቸው ብቸኛ መንገድ ከተቀሩት ሠርቶ አደሮች ጋር ኃይላቸውን በማስተባበር በአንድነት የሚያደርጉት የተቀነባበረ ትግል ነው ።

እንስታዊነት በአሁኑ ዘመን በካፒታሊስት ሀገሮች የቡርዧውንና የሠራተኛውን መደብ ሴቶች በአንድነት በማጣመርና የሴቶችን ጉዳይ ከአጠቃላይ የመደብ ትግል በመነጠል ይህንን መሠረታዊ ትግል ለማጨናገፍ ይጥራል ። ሴቶችን እንደ አንድ የተለየ መደብ የመቁጠር አዝማሚያ ስህተት ነው ፤ ምክንያቱም ሴቶች በየመደቡ የሚገኙ የኅብረተሰብ አባሎች እንጂ ለብቻ ራሱን ችሎ በወጣ መደብ ውስጥ የሚመደቡ አይደሉም ። ስለዚህ የሴቶች የእኩልነትና የነፃነት ጥያቄ የሚፈታው በአጠቃላዩ የመደብ ትግል ሂደትና በሶሻሊዝም ብቻ ነው ።

## እኩልታነት
(*Equalitarianism*)

በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የሰዎችን በአቻነት ፣ በእኩልነት ሁኔታ ላይ መገኘትን የሚያመለክት ጽንሰ ሐሳብ ነው ። ይሁን እንጂ እኩልታነት በተለያዩ የታሪክ ወቅቶችና በተለያዩ መደቦች የተለያየ ይዘት አለው ። በቡርዧ አስተሳሰብ እኩልታነት በፖለቲካና በኢኮኖሚ ሳይሆን በሕግ ፊት የዜጎች እኩልነት ማለት ነው ። በንዑስ ከበርቴው ንድፈ ሐሳብ ደግሞ እኩልታነት እያንዳንዱ ሰው የግል ባለንብረት የመሆን መብት አለው ከሚል መሠረተ ሐሳብ ይነሣል ። ሁለቱም ጽንሰ ሐሳቦች ለእኩልታነት መሠረት የሆነውን ዋና ጉዳይ ማለትም ከምርት መገልገያዎች ጋር ያለውን ግንኙነት ይዘሉታል ። ስለዚህም የቡርዧው የእኩልታነት ጽንሰ ሐሳብ ለበዝባዥ ገዥ መደቦች ብቻ እንጂ ሠርቶ አደሩን በሚመለከት ረገድ በተግባር ሊውል የማይችል ነው ።

በማርክሳዊ ሌኒናዊ ንድፈ ሐሳብ ግን እኩልታነት በምርት መገልገያዎች የጋራ ይዞታና በበዝባዥ መደቦች መወገድ ላይ የተመሠረተ ነው ። ስለዚህም እውነተኛ እኩልታነት በሶሻሊዝም ድል አድራጊነት የሚመጣ ነው ። በሶሻሊዝምም ቢሆን እኩልታነት በማናቸውም መልኩ ይንፀባረቃል ማለት አይደለም ። ለምሳሌ በዜጎች ሁሉ መካከል ፍጹማዊ የሆነ የደሞዝና የጠቅላላ ኑሮ ደረጃ እኩልነት ይኖራል ማለት አይደለም ። ሶሻሊዝም ከተመሠረተ በኋላ ከአለፈው ሥርዓተ ማኅበር የተወረሰው የእእምሮና የጉልበት ሥራ ልዩነት ስለሚኖር ለጠቅላላው ኅብረተሰብ ጥቅምና ዕድገት አንዳንዶቹ በዓይነትም በመጠንም የበለጠ ድርሻ ስለሚያበረክቱ የበለጠ ደሞዝና ጥቅም ያገኛሉ። ስለዚህም በሶሻሊዝም ግንባታ ወቅት እስከ ተወሰነ ደረጃ ድረስ የደሞዝና የኑሮ ደረጃ ልዩነት ይኖራል ማለት ነው ። የሶሻሊስት ስልተ ምርት ሲዳብር በዚሁ አኳያ በገጠርና በከተማ ፣ በጉልበትና በእእምሮ ሥራ መካከል ያለው ልዩነት እየጠበበ ሲሄድ በመላው ኅብረተሰብ መካከል የገቢ መጠን እየተቀራረበ ወደመስተካከል ያመራል ። ይህ ሂደት ራሱ ከሶሻሊዝም ወደኮሚኒዝም መሸጋገርን ወይም ማደግን የሚያመለክት ነው። በኮሚኒዝም በደሞዝ እኩል መሆንና አለመሆን ወይም መበላለጥ የመሳሰሉት የኢኮኖሚ ፈርጆችና ማኅበራዊ አስተሳሰቦች እየጠፉ ይሄዳሉ ። እያንዳንዱ የሚችለውን ያህል በሚያበረክትበት ፣ እያንዳንዱም የሚፈልገውን ያህል በሚያገኝበት በኮሚኒስት ኅብረተሰብ “ደሞዝ” የሚባል የኢ

ክኖሚ ፈርጅ አይኖርም ። ያን ጊዜ ማኅበራዊ ተመሳሳይነት ፣ ፍጹማዊ እኩልነት ይፈጠራል ።

## እኩያዊ የእሴት መልክ
*(Equivalent Form of Value)*

ለልውውጥ የቀረበ የአንድ ዓይነት ሸቀጥ እሴት የሚገለጥበት ሸቀጥ እኩያዊ የእሴት መልክ ይባላል ። ይህ የእሴት መልክ የሌላ ሸቀጥ እሴት ለመግለጽ የቆመ የእሴት መልክ ነው ማለት ነው ።

ለምሳሌ አንድ በግ አሥር ቁና ገብስ ይለውጣል እንበል ። በዚህ ምሳሌ ውስጥ የበጉ እሴት የተገለጠው በገብሱ እሴት አማካይነት ነው ። የገብሱ ዋና ተግባር የበጉን እሴት ለመግለጥ መቆሙ ነው ። በመሆኑም ገብሱ እኩያዊ የእሴት መልክ በመሆን ያገለግላል ።

ከላይ በተጠቀሰው ምሳሌ የበጉን የጠቀሜታ እሴት የሚገልጠው ሸቀጥ ማለትም ገብሱ በልውውጡ ውስጥ የሌላውን ሸቀጥ እሴት መልክ በመያዝና በማለጥ ከጠቀሜታ እሴትነት ወደ ልውውጥ እሴትነት ይለወጣል ።

እኩያዊ የእሴት መልክ የራሱ የሆኑ ሦስት ልዩ ባሕርያት አሉት ። እነሱም ፣

1ኛ/ በሁለት ሸቀጦች መካከል ልውውጥ እንዲካሄድ ከተፈለገ አንድ ዓይነት የጠቀሜታ እሴት ባላቸው ሸቀጦች መካከል (ለምሳሌም አሥር ቁና ጤፍ ባሥር ቁና ጤፍ) ልውውጥ ሊኖር ስለማይችል በእኩያዊ የእሴት መልክነት የሚያገለግለው ሸቀጥ የተለየ የጠቀሜታ እሴት እንዲኖረው ያስፈልጋል ።

2ኛ/ ይህን የእኩያዊ ሚና በሚጫወተው ሸቀጥ ላይ የተወሰነ ያህል ተጨባጭ የሥራ ኃይል የፈሰሰበት ስለሆነና ልውውጥ በሚካሄድበትም ወቅት ይህ ሸቀጥ የሌላው ሸቀጥ እሴት መግለጫ ሆኖ ስለሚያገለግል ተጨባጭ የሆነው ሥራ የእሱ ተቃራኒ የሆነው ረቂቅ ሥራ የሚከሰትበትን ቅርፅ ይይዛል ።

3ኛ/ ለልውውጥ የቀረበው ሸቀጥ በሌላ ሸቀጥ ይለወጣል ከተባለ ሸቀጡ ለኅብረተሰቡ ጠቃሚ መሆኑ ታውቆ ተፈላጊነት አግኝቷል ማለት ነው ። ይህን ምርት ለማምረት ሥራ ላይ የዋለው የግል ሥራም የማኅበራዊ ሥራ አካል በመሆን ተቀባይነት ያገኛል ማለት ነው ። ስለዚህም የእኩያዊ እሴት መልክ ሦስተኛ ልዩ መልኩ የግለሰቦች ሥራ የተቃራኒውን የማኅበራዊ ሥራ መልክ መያዙ ነው ።

## እውነት
*(Truth)*

የእውነታ ትክክለኛና በተግባር የተፈተነ ነፀብራቅ ማለት ነው ። እውነት በነባራዊው ዓለም ውስጥ የሚገኙ የክስተቶችንና የነገሮችን ዕድገትና ለውጥ ሕግጋት ከአንድ ወይም ከበርካታ ገጽታቸው አንፃር የሚያንፀባርቅ ዕውቀት ነው ። እውነት የሚለካው በተግባር ብቻ ሳይሆን በሥነ አመክንዮአዊ ትክክለኛነቱም ነው ። ዕውቀት በተግባር ተመዝኖ እውነታን በትክክል ማንፀባረቁ ሲረጋገጥ የሰው ልጅ በረጅም ጊዜ ባከማቸው ልምድና ዕውቀት ላይ ተመሥርቶ አጠቃላይ የክስተቶችን የወደፊት ዕድገት አዝማሚያና ባሕርይ በሥነ አመክንዮአዊ ሥርዓት ላይ ሲያዋቅር ፣ ማለትም የሐሳቦች መፋለስ ሳይኖር በዲያሌክቲክስ ሕጋግት ላይ ሲመሠረትና ሲቀረፅ እውነት ይሆናል ።

ዕውቀት የእውነታ (የማኅበራዊና የተፈጥሮአዊ እውነታ) ነፀብራቅ በመሆኑ የእውነት ይዘት በሚያንፀባርቀው ነባራዊ እውነታ ይወሰናል ። በነባራዊ እውነታ ውስጥ የሚገኙ ነገሮችና ክስተቶች ዓይነት ፣ መጠን ፣ ባሕርይና ግንኙነት የዕድገት ሕግጋት ነባራዊ በመሆናቸው የነርሱ ነፀብራቅ የሆነው እውነት ይዘቱ ነባራዊ ነው ። እውነት በሰው የሚፈጠር ሳይሆን ከነባራዊ እውነታ በተግባር የሚገኝና ሳይንሳዊ ዕውቀት እያደገ ሲሄድ የሚበለጽግ ነው ።

ዲበአካላውያን እውነትን ዘለዓለማዊና የማይለዋወጥ ፣ ምንጩም እግዚአብሔር እንደሆነና ከእግዚአብሔርም የሚሰጥ እንደሆነ አድርገው ይመለከቱታል ። እውነት ዘለ

ዓለማዊና የማይለወጥ ተደርጐ ከተወሰደ የዕውቀትን ዕድገት መካድ ከመሆኑም በላይ የትክክለኛነቱ መሠረትና ማረጋገጫ ተግባር መሆኑ ስለሚቀር ምሥጢራዊ ይሆናል ።

ኅሊናዊ ሐሳባውያን ግን ዕውቀት እንፃራዊ እንጂ ፍጹማዊ ሊሆን አይችልም ይላሉ። ለዚህም የሚሰጡት ማስረጃ የሳይንስ ዕድገት በየወቅቱ በርካታ ስህተቶችን ማረሙ እውነት እንፃራዊ እንጂ ነባራዊ ሊሆን እንደማይችል ያሳያል የሚለውን ነጥብ ነው ። ይህ የተሳሳተ የዕውቀት ግንዛቤ የሚመነጨው እንፃራዊና ፍጹማዊ ዲያሌክቲክስን ካለመረዳት ነው ። መጀመሪያውኑ ከእምነት ጋር በመያያዙና ከዚህም የተነሣ ሰፊ ተቀባይነት በማግኘቱ ብቻ እንደእውነት የተቆጠረ ዕውቀት (ለምሳሌ መሬት ጠፍጣፋ ናት ፤ ፀሐይ መሬትን ትዞራለች) በሳይንስና በቴክኖሎጂ የሳይንስ ዕድገት እንደ ዕውቀት ማደግ ተደርጐ ከል ተወሰደ የዕውቀት ማደግ እንደ ስህተት ስለሚቆጠር ሁልጊዜ ጥርጣሬን መጋበዝ ወይም ዕውቀት መታመን እንደሌለበት እድርጐ ማቅረብ ይሆናል ። ቁምነገሩ ግን ዕውቀት እንፃራዊ ወይም ፍጹማዊ ብቻ መሆኑ ሳይሆን በእንፃራዊነት ውስጥ ፍጹማዊነት እንዳለና ይህም የዕውቀት ዕድገት ሕግ መሠረት መሆኑን መረዳቱ ነው ።

(አንፃራዊና ፍጹማዊ እውነትን ፣ ኅሊናዊ ሐሳባዊነትን ፣ ነባራዊ ሐሳባዊነትን ፣ ዕውቀትን ይመለከቷል ።)

## እውን
(*Real*)

የአንድ ነገር ልባዊ የሚገልፀው የነገሩን ዓይነት ብቻ ሳይሆን እውን መሆኑን ማለትም ከኛ ሐሳብ ውጭ እውንነትና ቋሚነት እንዳለው ጭምር ነው ። እውን ምናባዊና ኅሊናዊ ብቻ የሆነውን ፣ በራሱ ሀልውና ካለውና ነባራዊ ከሆነው ለመለየት የሚጠቅም ጽንሰ ሐሳብ ነው ።

በሐሳባውያን አመለካከት እውን የሚለው ሐሳብ አጨቃጫቂ የሆነ ፍች የሚይዝ ነው ። ነባራዊ ሐሳባውያን ሐሳብ እራሱ ነባራዊ ነው ሲሉ ፣ ኅሊናዊ ሐሳባውያን ግን የምናውቀው ነገሮችን ሳይሆን እነሱ በኅሊናችን ውስጥ የሚፈጥሩትን ኅሊናዊ ክስተት ነው ስለሚሉ እውን የሆነውን ምናባዊና ኅሊናዊ ብቻ ከሆነው ለመለየት የሚያስቸግር ነው ።

ሆኖም አንድን ነገር እውን ነው ስንል የምናቀርባቸው ምክንያቶች ወይም መለያ ነጥቦች ባጭሩ የሚከተሉት ናቸው ። 1/ ለተግባር የቀረበና የተግባርን ኃይል የሚጠይቅ መሆኑ ፤ 2/ ሰዎች በነገሩ የሚስማሙበት ማለት ማኅበራዊ ምስክርነትን የሚያገኝ መሆኑ ፤ 3/ ነገሩ በተወሰነ ሥነ አመክንዮአዊ ሥርዓት ውስጥ የሚገለጽና በነባራዊ ሕግጋት የሚገዛ መሆኑ ናቸው ። እነዚህ ነጥቦች የሚያመለክቱት የቁስአካልን ጠባዮች በመሆኑ እውን የሚለው ጽንሰ ሐሳብ በመጀመሪያ ደረጃ የሚገልጸው ቁሳዊነትን መሆኑን በቀላል ለመረዳት ይቻላል ።

(እውነታን ፣ ቁስአካልን ይመለከቷል ።)

## እውን ምንዳ
(*Real Wages*)

ወዝአደሩ በገንዘብ ምንዳው ሊገዛው የሚችለው የሸቀጦችና የግልጋሎት መጠን ነው ። የእውን ምንዳ ደረጃ ወዝአደሩ በሚያገኘው ስማዊ ምንዳ መጠንና ለወዝአደሩ መሠረታዊ ፍላጐት እርካታ በሚውሉ ሸቀጦች ዋጋ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው ።

በካፒታሊዝም ውስጥ በረዥም ጊዜ ክልል ሲታይ እውን ምንዳ ፍጹማዊ በሆነ መንገድ አይሁን እንጂ የመቀነስ አዝማሚያ ያሳያል ። ይህም አዝማሚያ በካፒታሊስቱና በወዝአደሩ መካከል ያለውን የገቢ ልዩነት እያሰፋው ይሄዳል ። የቡርዧው መደብ ምሁራን ግን ይህንን እውነት በመካድ በዘመነ ካፒታሊዝም የሀብት ስርጭት በአጠቃላይ ለኅብረተሰቡ በሚጠቅም መንገድ እየተካሄደ መሆኑን አስመስለው ለማቅረብ ይጥራሉ ።

በሶሻሊስት ሥርዓት የብሔራዊ ገቢ ስርጭት በአጠቃላይና የሸቀጦች ዋጋ በተለይ በተቀናጀ መንገድ በማዕከላዊ ዕቅድ የሚመሩ በመሆናቸው እያንዳንዱ ሠራተኛ የሚያገኘው ምንዳ ከኢኮኖሚው ዕድገት

ጋር በተመጣጠነ መንገድ አብሮ የሚሄድ ነው ። በመሆኑም በሶሻሊስት ሥርዓት በስማዊ ምንዳና በእውን ምንዳ መካከል በመሠረቱ ልዩነት አይኖርም ።

(ስማዊ ምንዳን ይመለከቷል ።)

## እውንነት
*(Realism)*

ሁለንታዊ ንድፈ ሐሳቦች የራሳቸው ህልውና ያላቸውና ከግላዊ ነገሮች በፊት የነበሩ ናቸው የሚል በመካከለኛው ዘመን በአውሮፓ ታሪክ ውስጥ የተከሰተ የተምሀሮነት አዝማሚያ ነው ። ይህ የፍልስፍና አዝማሚያ አፍላጦን ስለንድፈ ሐሳብና ስለነባራዊ ዓለም ፣ ስለሁለንታዊና ስለግላዊ ግንኙነት የሰነዘረውን አመለካከት የሚያራምድ ነበር ። ይህ አመለካከት የሚቃወመው ስማዊነትን ነበር ።

(አፍላጦንን ፣ ስማዊነትን ይመለከቷል ።)

## እደ ጥበብ ባለሙያዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር (የ—)
*(Handicraft Producers' Cooperatives)*

ባለሙያዎች በግል የያዙትን የማምረቻ መሣሪያ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በፈቃደኝነት የወል ንብረት በማድረግና በአንድ መዋቅር ሥር ሆኖ በማምረት የጋራ ጥቅማቸውን የሚያስከብሩበትና የሚያዳብሩበት የኢኮኖሚ ድርጅት ነው ።

የእደ ጥበብ ባለሙያዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው ፤

1. በባለሙያዎች በግል የተያዙትን የማምረቻ መሣሪያዎች ወደ ወል ንብረትነት በመለወጥና ሙያንና ቁሳቁስን በማስተባበር የካፒታሊዝምን ብዝበዛ ማስቀረት ወይም ይህ ሥርዓት እንዳያቆጠቁጥ መከላከል ፤
2. ሙሉ በሙሉ በሰው ኃይል ከሚካሄዱትና ኋላቀር ከሆኑት የአመራረት ዘዴዎች ወደተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች በመሸጋገር ምርትን መጨመርና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት ፤
3. በእደ ጥበባት ባለሙያዎች ላይ የተጣለውን የባህል ተፅዕኖ መዋጋትና የሥራ ክቡርነትን ማረጋገጥ ፤
4. የሶሻሊስት የምርት ግንኙነትን በማዳበር የእደ ጥበብ ባለሙያዎችን ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶች ማስከበር ፤
5. ኢኮኖሚውን በማዕከላዊ ዕቅድ ለመምራት የሚያስችል አመቺ ሁኔታን መፍጠር ፤

በኅብረት ሥራ ማኅበር እንቅስቃሴ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የእደ ጥበብ ባለሙያዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር የተቋቋመው በ1871 በፈረንሳይ ሀገር ተካሂዶ በነበረው በፓሪስ ኮሚዩን ወቅት ነበር ።

በዚሁ በፓሪስ ንቅናቄ ምክንያት አንዳንድ ብሔራዊ ቡርዧዚዎች ፋብሪካዎቻቸውን እየዘጉ በመጥፋታቸው ኮሚዩኑ በእነዚሁ ፋብሪካዎች ውስጥ የሚገኙትን ሠራተኞች በአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር በማደራጀት የምርት እንቅስቃሴ እንዲቀጥል አድርጐ ነበር ። ነገር ግን የኮሚዩኑ ንቅናቄ በአጭር ጊዜ ውስጥ በመቀጨቱ ተቋቁመው የነበሩትም የኅብረት ሥራ ማኅበራት ዕድሜ እንደዚሁ ሊያጥር ችሏል ።

የመጀመሪያው የሶሻሊስት አብዮት በተካሄደባት ሩሲያ ከ1917—1945 ድረስ ጥቂት የኢንዱስትሪ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ተቋቁመው እንደነበር ይታወቃል ።

ከ1945 ወዲህ ግን በምሥራቅ አውሮፓ ሀገሮች የሶሻሊስት ሥርዓት በመስፈኑ የእደ ጥበብ ባለሙያዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት በሶሻሊስት መርህ መሠረት ሊቋቋሙና ሊስፋፉ ችለዋል ።

በሀገራችን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን የእደ ጥበብ ባለሙያዎች ለኅብረተሰቡ አስፈላጊ የሆኑ የቤት ውስጥ መገል

ገያ ቁሳቁሶችን ፥ ልብሶችን ፥ የእርሻና የጦር መሣሪያዎችን እንዲሁም የጌጥ ዕቃዎችን እየሠሩ በማቅረብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያደርጉ ቆይተዋል ። ሆኖም በሀገሪቱ ተንሰራፍቶ የነበረው ከፊል ፊውዳልና ከፊል ካፒታሊስት ሥርዓት በእደ ጥበብ ሙያ ላይ የተሰማሩትን ሁሉ የሚንቅ ፥ የሚያራክስና የሚያንኳስስ ስለነበር በማኅበር እንዲደራጁ ተገቢውን ድጋፍ ሳያደርግላቸው ቆይቷል ። ምንም እንኳን ሥርዓቱ ለይስሙላ የኅብረት ሥራ ማኅበር አዋጅ ቢያወጣም የእደ ጥበብ ባለሙያዎች በማኅበራት እንዲደራጁ ነባራዊው ሁኔታ አልፈቀደላቸውም ። ቁጥራቸው የተመጠነ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ቢቋቋሙም የሥርዓቱ ነፀብራቅ ነበሩና ተጠቃሚዎቹ የእደ ጥበብ ባለሙያዎች ሳይሆኑ ሀብታም ነጋዴዎች ብቻ ነበሩ ። ከአብዮቱ ፍንዳታ ወዲህ ግን የወጡት አዋጆች በተለይም እንደ ኢ.ት. አ በሐምሌ 1971 የወጣው የእደ ጥበባት አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር መመሪያ በቀድሞው ሥርዓት ተንቀውና ተረስተው የነበሩ የእደ ጥበብ ባለሙያዎች ተገቢ ቦታቸውን አግኝተው በየሥራ መስካቸው ዕውቀታቸውን እንዲያዳብሩ ፥ በሀገሪቱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥም ተሳትፎአቸው እንዲያድግ አመች ሁኔታዎችን ፈጥሯል ። በመሆኑም በመመሪያው መሠረት በሽመና ፥ በሸክላ ሥራ ፥ በቆዳ ሥራ ፥ በእንጨት ሥራ ፥ በብረታ ብረትና በሌሎችም መስኮች የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት በመቋቋም ላይ ናቸው ።

የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት የእደ ጥበብ ባለሙያዎች በተሻሻሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በመጠቀም ለምርት ዕድገት እንዲታገሉ አመች ሁኔታን ለመፍጠር ከማስቻላቸውም በላይ ቀስ በቀስ እያደጉ ወደ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች በመለወጥና የሶሻሊስት ኢኮኖሚ መሠረት የሆነውን ከባድ ኢንዱስትሪ ለማቋቋም በሚደረገው ጥረት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ። የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚያደርጉት ፈጣን እርምጃ ለገጠሩና ለከተማው ሕዝብ ሰፊ የሥራ ዕድል ይከፍታል ።

(የኅብረት ሥራ ማኀበራትን ይመለከቷል ።)

## እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ

*(Neo–Colonialism)*

ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች የፖለቲካ ነፃነት ያላቸውን ኋላቀር ሀገሮች የሚበዘብዙበት ኢኮኖሚያዊ ፥ ፖለቲካዊ ፥ ወታደራዊና የመሳሰሉትን በእኩልነት ላይ ያልተመሠረቱ ግንኙነቶችን የሚያጠቃልል ጽንሰ ሐሳብ ነው ። እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ የተከሰተው ቀጥተኛ የሆነው ቅኝ አገዛዝ በእስያ ፥ በአፍሪካና በላቲን አሜሪካ እየተደመሰሰ መሄድ እንደጀመረ ነው ። በቅኝ አገዛዝ ከምላ ጉዶል መደምሰስ ኢምፔሪያሊስቶች በቅኝ ግዛትነት ይዘዋቸው የነበሩትን የዓለም ክፍሎች ቢያጡም በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ አማካይነት ዓለምን በመከከላቸው ከፋፍለው አዲስ ፖለቲካዊ ፥ ኢኮኖሚያዊና ስትራቴጂያዊ የተፅዕኖ ክልሎች ለማግኘት ትግል በማካሄድ ላይ ይገኛሉ ።

የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ማካሄጃ ዋና መሣሪያ የውጭ ሞኖፖል ካፒታል ነው ። ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ቀድሞ ቅኝ ግዛቶቻቸው ወደነበሩትና ወደሌሎችም ኋላቀር ሀገሮች የሚልኩት ካፒታል መጠን በቅኝ አገዛዝ ዘመን ከነበረው የበለጠ ሆኗል ። ይህም ካፒታል ሁለት ዋና ዋና መልኮች የሚይዝ ሲሆን እነርሱም መንግሥታዊና ግላዊ ካፒታል ናቸው ። በተለይ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ መንግሥታዊ ካፒታል በመጠን ከማደጉም በላይ የኢምፔሪያሊስት ሀገሮችን ጥቅም በኋላቀር ሀገሮች ውስጥ በማስከበር ረገድ በሚጫወተው ሚና ከፍተኛውን ስፍራ እየያዘ መጥቷል ።

መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታል ወደ ኋላቀር ሀገሮች የሚገባው በእርዳታና በብድር ስም ነው ። ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ከቀየሱት ዓለምአቀፍ ፖሊሲ አንፃር የእርዳታና የብድር ሚና ኋላቀር ሀገሮችን የካፒታሊስቱ ዓለም ኢኮኖሚ ተቀጥላ አድርጎ ማቆየት ፥ የካፒታሊስቱን የዕድገት ፈለግ እንዲከተሉና በተቻለ መጠን ኢምፔሪያሊዝምን የሚደግፍ አቋም እንዲይዙ ማድረግ ነው ። ብድሩ የሚሰጠው በኢምፔሪያሊስት ሀገሮች መንግሥታት በቀጥታ ወይንም በእነሱ ቁጥጥር ሥር በሚገኙ እንደ ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅትና እንደዓለም ባንክ ባሉ ዓለም

አቀፍ ድርጅቶችና እንደአውሮፓ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ባሉ አህጉር አቀፍ ድርጅቶች አማካይነት ነው ።

ግላዊ ካፒታል ከኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ወደኋላቀር ሀገሮች በሙእለ ንዋይና በንግድ ብድር ስም ይላካል ። ኢምፔሪያሊስት ሞኖፖሎች በየዓመቱ ወደኋላቀር ሀገሮች ከሚልኩት የካፒታል መጠን እጅግ የበለጠ ገንዘብ በትርፍ ፣ በአክሲዮን ክፍያና በወለድ መልክ ከኋላቀር ሀገሮች በመበዝበዝ ያወጣሉ ። በውጭ ብድርም አማካይነት የኢምፔሪያሊስት ፣ የፋይናንስ ሞኖፖሎችና የኢምፔሪያሊስት ሀገሮች መንግሥታት የኋላቀር ሀገሮችን የውጭ ገበያዎችና የጥሬ ዕቃ ምንጮችን በቁጥጥራቸው ሥር ያውላሉ ። ከዚህም በስተቀር ኢምፔሪያሊስት ሞኖፖሎች በሀገራቸው ውስጥ ብዙ ትርፍ የማያስገኙና አካባቢውን ከፉኛ የሚበክሉ ኢንዱስትሪዎችን ወደእስያ ፣ ወደ አፍሪካና ወደ ላቲን አሜሪካ በማዛወር ላይ ይገኛሉ ። በኋላቀር ሀገሮች ውስጥ ለሥራ ኃይል ዝቅተኛ ክፍያ በመክፈል በዳበሩ የካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ ሊያገኙ ከሚችሉት መጠን እጅግ ከፍ ያለ የትርፍ መጣኔ ያገኛሉ ።

ኋላቀር ሀገሮች ያለባቸው የኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ፣ ሞኖፖሎችና ድርጅቶች ብድር በከፍተኛ ደረጃ እያደገ በመሄድ ላይ ነው ። ለምሳሌ በ1982 ኋላቀር ሀገሮች ባጠቃላይ ከ600 ቢሊዮን ዶላር በላይ የሚገመት ብድር እንደነበረባቸውና በዚያው ዓመት ከ110 ቢሊዮን ዶላር በላይ የብድርና የወለድ ክፍያ እንዳደረጉ ታውቋል ። ይህም ከውጭ ንግዳቸው ከሚያገኙት ገቢ ከ20% በላይ ይሆናል ። ብዙ ሀገሮች በየዓመቱ ለመክፈል የተዋዋሉትን ወለድ እንኳ ለመክፈል ተጨማሪ ብድር ለመጠየቅ ስለሚገደዱ የውጭ ብድር ሁኔታ የኋላቀር ሀገሮችን የኢኮኖሚ ዕድገት በማቀጨጭ አንፃር ብቻ ሳይሆን የሚገኙበትን ዝቅተኛ የፍጆታ ደረጃ እንኳ ለመጠበቅ በማይችሉበት አኳኋን እንዲገኙ አድርጓቸዋል ።

ለዚህ ችግር መባባስ ምክንያት ከሆኑት ውስጥ አንደኛው በኢምፔሪያሊስት ሀገሮችና በኋላቀር ሀገሮች መካከል የሚካሄደው ንግድ በእኩልነት ላይ ያልተመሠረተ መሆኑ ፣ ሁለተኛው ደግሞ ኋላቀር ሀገሮች ለኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎችና ከኢምፔሪያሊስት ሀገሮች የኢንዱስትሪ ሸቀጣ ሸቀጥ ሸማቾች መሆናቸው ነው ። ኋላቀር ሀገሮች ከኢምፔሪያሊስት ሀገሮች የሚገዟቸው የኢንዱስትሪ ምርቶች ዋጋ እየናረ ሲሄድ ወደኢምፔሪያሊስት ሀገሮች የሚልኳቸው የእርሻ ውጤቶችና ጥሬ ዕቃዎች (ከነዳጅ ዘይት በስተቀር) ዋጋ እያሽቆለቆለ በመሄድ ላይ ይገኛል ። ይህ ሁኔታ በተለይ ነዳጅ ዘይት ሸማች የሆኑ ኋላቀር ሀገሮችን ከባድ ችግር ላይ ጥሏቸዋል ።

(ኢምፔሪያሊዝምን ይመለከቷል ።)

## እግዚአብሔር
*(God)*

ፍልስፍና ከማኅበራዊ እምነቶች በመነሣት እንዲሁም የሁሉ ነገር መጨረሻ ፣ ምክንያትና ምንጩ ምንድን ነው ለሚለው ዲበአካላዊ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ስለ እግዚአብሔር ህልውናና ምንነት ከተለያዩ አመለካከቶች ላይ ደርሷል ።

ጥንታውያኑ የግሪክ ፈላስፎች እግዚአብሔርን የተመለከቱት የዓለም ሥርዓትና ታዋቂነት መሠረት እንደሆነ አድርገው ነው ። በአፍላጦንና በአርስጣጣሊስ አመለካከት እግዚአብሔር የዓለም ፈጣሪ ከመሆኑ ይልቅ ዓለምን ያደራጀና ዓለምም ከሱ ጋር አብሮ ለሁሌም የሚኖር ነው ። በባሕርዩም እግዚአብሔር መጨረሻ የሌለው ነገር አይደለም ፤ ምክንያቱም ፍጻሜ የሌለው መሆንና እንዲሁም ቋሚ ወሰንና ቅርፅ ማጣት ለእግዚአብሔር ተስማሚ የሆነ ባሕርይ አይደለም ይላሉ ። በተጨማሪም እግዚአብሔር ሰብእናና ግብረገባዊ ጠባዮች ያሉት ኑባሬ አይደለም ፤ በነሱ አመለካከት እግዚአብሔር ስለራሱ እንጂ ስለዓለም ጉጉት የለውም ።

የክርስቲያን ሃይማኖት ከተከሰተ በኋላ በፍልስፍና ውስጥ ስለእግዚአብሔር የነበረው አመለካከት ወደ አማኒነት ተለውጧል ፤ ማለትም እግዚአብሔር መጨረሻ የሌለው የዓለም ቀጥተኛና ንቁ ፈጣሪ ሆኖ ተቆጥሯል ። በአማንያን አመለካከት የአምላክ ዋናው ጠባይ ምሉእ በኩለሄነትና በሁሉም አቅጣጫ ፍጹማዊ መሆን ሲሆን ሰብአዊ ባሕርይም አለው ።

 እግዚአብሔር ህልውና... (የ—)

ሰብአዊነቱም የሚገለጸው በሚያከናውናቸው ግብረገባዊ (ፍትህ ፥ ጥበብ ፥ ደግነት ወዘተ...) ድርጊቶች ነው ።

እማኒነትን የሚቃወመው ሁልእምላክነት ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ አዲስ ሐሳብ ሰንዝሯል ። እንደ ሁልእምላክነት አባባል እግዚአብሔር ንቁና ግባዊ በሆነ ድርጊት ዓለምን ከሱ ውጭ አልፈጠረም ። ዓለምና እግዚአብሔር አንድ ናቸው ፤ በዓለም ውስጥ የሚታየው ማንኛውም ነገር የእግዚአብሔርን ምንነት የሚገልጽ ነው ። በመሆኑም ሁልእምላክነት እግዚአብሔር የሰብአዊነት ባሕርይ የለውም ይላል ።

ከቁስአካላዊ እቋም የሚመነጨው ኢእማኒያዊ አመለካከት ግን ማንኛውንም ዲበተፈጥሮአዊ ህልውና እንደማይቀበል ሁሉ የእግዚአብሔርንም መኖር አይቀበልም ። በኢእማንያውያን አመለካከት ተፈጥሮ ራሱን የቻለና ራሱን የሚገልጽ ኑባሬ ነው ። ሰው ስለ እግዚአብሔርም ያለው እምነት የሚመነጨው ከዕውቀት ሳይሆን ከፍርሃትና ከድንቁርና ነው ። ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ለኢእማኒነት ጠንካራ ድጋፍ ከመስጠቱም በላይ የእምነትን ማኅበራዊና መደባዊ መሠረት በማጤን ለበዝባዥ መደቦች እንደ መሣሪያ የሚያገለግል መሆኑን አሳይቷል ። በመሆኑም ኢእማኒነት ሰዎችን ከሃይማኖት ተፅዕኖ ለማላቀቅና ነፃ ለማድረግ የሚታገል እቋም ሆኗል ። በሃይማኖትም ምትክ ሳይንሳዊ አመለካከቶችን በኅብረተሰቡ ውስጥ ለማስረጨት ይጥራል ።

(እማኒነትን ፥ ሁልእምላክነትን ፥ ኢእማኒነትን ፥ ሃይማኖትን ፥ ይመለከቷል ።)

## እግዚአብሔር ህልውና ማረጋገጫዎች (የ—)

*(Proofs of the Existence of God)*

የእግዚአብሔርን መኖር በእምነት ብቻ የምንቀበለው ሳይሆን ምክኑያዊ ድጋፍ አለው በማለት ሐሳባውያን ያቀነባበሯቸው ማረጋገጫዎች አሉ ። እነሱም በሦስት ዓበይት ክፍሎች ይመደባሉ ።

የመጀመሪያው ሥነ ኑባሬአዊ ማረጋገጫ የተባለው ሲሆን ይህም የሚገልጸው እግዚአብሔር ማለት ፍጹማዊ ኑባሬ ማለት በመሆኑ ህልውና የግድ እንደሚኖረው ነው ፤ ምክንያቱም ህልውና ሳይኖረው ቢቀር ኖሮ ፍጹማዊ ነው ብሎ ማሰብ ባልተቻለም ነበር ። ሁለተኛው አካላዊ ማረጋገጫ ተብሎ የሚታወቀው ነው ። በዚህም ማረጋገጫ መሠረት ዓለምን ስንመለከት ዓለም ውሉንና ጨርሶም ላይኖር ይችል ነበር ። ፍጹማዊ ባለመሆኑ ዓለም የራሱ መንሥኤ አይደለም ። በመሆኑም ህልውና ያገኘው በራሱ በግዴታ ህልውና ካለው ኃይል ማለትም ከእግዚአብሔር መሆን አለበት ። በተጨማሪም ዓለምና በውስጡ ያሉ ነገሮች በግብና በሥርዓት የሚሠሩ በመሆናቸው ጠቢብ የሆነ ኑባሬ የፈጠራቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል የሚል ነው ። ሦስተኛው ግብረገባዊ ማረጋገጫ ተብሎ የሚታወቀው ነው ። ይኸውም በተለይ ግብረገባዊ ግዴታን አስመልክቶ ከሰው በላይ ሆኖ የመጀመሪያ ድንጋጌና የመጨረሻ ፈራጅ ማለትም እግዚአብሔር ከሌለ የሰናይና የእኩይ ልዩነት መሠረተቢስ ይሆናል የሚል ነው ።

እነዚህ ማረጋገጫዎች ተቀባይነት እንደሌላቸውና በሥነ አመክንዮአዊ ስህተት ላይ የተመሠረቱ እንደሆኑ ያስረዳው ካንት የተባለው የጀርመን ሐሳባዊ ፈላስፋ ነው ። ካንት ከምንነት (ፍጹማዊነት) ህልውናን ማመንጨት አይቻልም በማለት ህልውና ከሐሳብ የሚወጣ ሳይሆን ለሕዋሳት ብቻ የሚገለጥና በነሱ ብቻ የሚረጋገጥ ነው ሲል ተናግሯል ። እግዚአብሔር የሚለው ጽንሰ ሐሳብ የሚያመለክተው ዲበአካላዊ ነገር ማለትም ከሕዋሳት ውጭ የሆነን ነገር በመሆኑ መቼም ሊረጋገጥ አይችልም ። በሐሳብ ገንዘብ አለኝ ማለትና በገንዘቡ እውን መሆን መካከል ከፍተኛ ልዩነት ከመኖሩም በላይ እንዱን ሁኔታ ከሌላ ሁኔታ በሐሳብ ኃይል ለማመንጨት እንደማይቻል ሁሉ በሥነ አመክንዮአዊ አስተሳሰብ ብቻም የእግዚአብሔርን ህልውና ለማረጋገጥ አይቻልም ሲል ካንት ተናግሯል ። ካንት በግልጽ ለማስረዳት የሞከረው እግዚአብሔር የእምነት ጉዳይ እንጂ በዕውቀት የሚደረስበት እንዳልሆነ ነው ።

ይህ ካንት የሰጠው የማያዳግም ሒስና እግዚአብሔርንና ዕውቀትን በመለያየቱ

ሰው ስለእግዚአብሔር ህልውናና ምንነት ያለው አስተሳሰብ ሁሉ የሚመነጨው ከእ ምነት ብቻ መሆኑን በግልጽ ማስረዳቱ ለቁስ አካላዊና ለኢእማኒያዊ ፍልስፍና ከፍተኛ ድጋፍ ሰጥቷል ።

(እግዚአብሔርን ፣ ኢእማኒነትን ይመለከቷል ።)

## እግዳት
*(Stagnation)*

እግዳት በካፒታሊስት ኢኮኖሚ አጠቃ ላይ ቀውስ ውስጥ የሙአለ ንዋይ መጠን በዝቅ ተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝበት ፣ በወቅቱ በሙአለ ንዋይ መልክ ሥራ ላይ ማዋል ሳይችል ቀርቶ የገንዘብ ካፒታል ከመጠን በላይ የሚጠራቀምበት ፣ የሠራተኛው ሕዝብ የገቢ መጠን በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኝበትና ከዚሁ ጋር በተገናኘ መንገድ የሥራ አጡ ቁጥር በከፍ ተኛ ደረጃ ጨምሮ የሚገኝበት የኢኮኖሚ ሂደት ነው ።

(ቀውስን ይመለከቷል ።)

## እግድ ተረፈ ሕዝብ
*(Stagnant Surplus Population)*

በካፒታሊዝም ውስጥ የሚፈጠረው አን ፃራዊ የኢንዱስትሪ ተረፈ ሕዝብ አንዱ መልክ ነው ። በዚህ ተረፈ ሕዝብ መልክ ሥር የሚጠቃለሉት ባብዛኛው ቋሚ ባልሆነ ስራታዊ ሥራ ኑሮአቸውን የሚገፉና እጅግ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙት ናቸው ። እነዚህ ሰዎች ባብዛኛው በራሳቸው ቤት ውስጥ ሆነው ለቡርዧዚዎች ጥቃቅን ሥራ ዎችን እንደተገኘ የሚያከናውኑና አብዛኛውን ጊዜ ግን ሥራ ፈትተው የሚኖሩ ናቸው ። እግድ ተረፈ ሕዝብ በዝቅተኛ እርከን የሚገኙት ንና ከምርት መስክ የተገለሉትን ፣ እንደገ ናም ሥራ ለማግኘት ያላቸው ዕድል እጅግ የመነበበ በመሆኑ ይበልጡኑ በምጽዋት እንዲ ኖሩ የተገደዱትንም ያጠቃልላል ።

የዚህ ዓይነቱ አንፃራዊ የኢንዱስትሪ ተረፈ ሕዝብ መልክ ጐልቶ የሚታየው በመለስተኛ የገጠር ከተሞች ውስጥ ነው ።

## እውን ፣ ሮበት
*(Owen, Robert)*

ከ1771—1858 የኖረ እንግሊዛዊ ተም ኔታዊ ሶሻሊስት ነው ። በእጅ ጥበብ ሙያ ይተዳደር ከነበረ አንድ ደሀ ቤተሰብ የተገኘው እውን ራሱን ለመርዳት ገና የአሥር ዓመት ልጅ ሳለ ተቀጥሮ መሥራት ጀመረ ። አሥራ ዘጠኝ ዓመት ሲሆነውም ማንቸስተር ውስጥ የሚገኝ የአንድ ትልቅ ፋብሪካ ሥራ አስኪያጅ ለመሆን በቃ ። ይህ ሁኔታና አጋጣሚ ከሌ ሎች ተምኔታዊ ሶሻሊስቶች በተሻለ ስለካፒ ታሊስት ሥርዓት ምንነት እንዲያውቅ የረ ዳው በመሆኑ የኢንዱስትሪ አብዮት በወዝ አደሩ ላይ ያስከተለውን ሁኔታ እንዲኄስ አስችሎታል ። በሰብአዊ ተግባር ላይ የተሰ ማራው እውን ለፋብሪካ ሕጎች መሻሻል ሽንጡን ገትሮ ከመከራከሩም በላይ በፋብ ሪካ ውስጥ የሥራ ሰዓትን በመቀነስ ፣ ሙአለ ሕፃናትን በማቋቋም የወዝአደሩን ኑሮ ለማሻ ሻል ተግባራዊ ጥረት ያደረገ ነው ።

በእውን በተከታታይ ይሰነዘር የነበረው ኂስ በግል ሀብትና የግል ሀብትን ተገቢ በሚያደርገው ሃይማኖት ፣ እንዲሁም በቡርዧ የጋብቻ ሥርዓት ላይ ያተኮረ ነበር ።

በእውን አመለካከት ማኅበራዊ ሥር ዓት በሰው ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳድራል ፤ የኅብረተሰብ ችግር ምንጩም ድንቁርና ነው ። በመሆኑም “አዲስ ግብረገብ” (ሶሻሊስት ዓለም) ለመፍጠር አንደኛው ከፍተኛ መሣ ሪያ ትምህርት ነው ።

ከዚህም አመለካከት በመነሣት እውን በሥነ ትምህርት ላይ እያሌ ሐሳቦችን ሰንዝ ሯል ። በ1820ም እነዚህን ሐሳቦቹን ሶሻሊ ስት ነው ወደሚለው ሥርዓት ትምህርት ለመቀየር ጥረት ማድረግ ጀምሯል ። የወል ይዞታና የወል ሥራ አንድነት የአእምሮና የጉልበት ሥራ ውህደት ፣ ሁለንታዊ (የተሟላ) የግለሰብ ዕድገት ፣ የተሟላ እኩልነትና መብት የዚህ ሥርዓት ትምህርት መርሆች ናቸው ።

ሶሻሊስት ትምህርቱ የኢንዱስትሪና የእርሻ ሥራን ያጣመረ ሲሆን ይበልጥ የሚያደላውም ለእርሻው ሥራ ዘርፍ ነው ።

አውን መደብ አልባ ኅብረተሰብ የማይቀር መሆኑን ቢቀበልም ይህን ኅብረተሰብ እውን የማድረጉ ተልዕኮ የሠራተኛው መደብ መሆኑንና የማኅበራዊ አብዮትን አስፈላጊነት ሳይገነዘብ ቀርቷል ። ይልቁንም በኅብረተሰብ ውስጥ ለውጥ የሚመጣው አብራህያን በሆኑ በቡርዧ መንግሥታት ነው ከሚል እምነቱ በመነሣት ለዚህ ተልዕኮ ቡርዧዚዎችን ሲማጸን ይታይ ነበር ። አውን የወዝአደሩን ታሪካዊ ሚና ሊገነዘብ ባይችልም ከሠራተኛው መደብ ጋር የጠበቀ ግንኙነት በመመሥረት ፣ በሠራተኛና በኅብረት ሥራ ማኅበራት እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ በማድረግ ያካሄደው ትግል የሚደነቅ ነው ።

(ተምኔታዊ ሶሻሊዝምን ይመለከቷል ።)

# O

## ዓለም ሂደተ አብዮት (የ—)

*(World Revolutionary Process)*

በጊዜያችን የሚካሄዱትን አብዮታዊ እንቅስቃሴዎች ማለትም ሶሻሊስት አብዮቶችን ፣ ብሔራዊ የአርነት እንቅስቃሴዎችን፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ፊውዳል የሆኑ ዲሞክራሲያዊ አብዮቶችን ፣ ፀረፋሺስትና ፀረፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ትግሎችንና በአጠቃላይ ለሰላም ፣ ለዲሞክራሲና ለማኅበራዊ ዕድገት የሚደረጉትን ትግሎች የሚያካትት ሲሆን የዚህ መሪ ኃይል የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት ነው ።

## ዓለም የመልሶ ግንባታና የልማት ባንክ (የ—)

*(International Bank for Reconstruction and Development - IBRD)*

ባጭሩ የዓለም ባንክ በመባል የሚታወቀው የዓለም የመልሶ ግንባታና የልማት ባንክ ዓለም አቀፍ የብድር ድርጅት ነው ። ባንኩ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ልዩ አካላት ከሆኑት አንዱ ቢሆንም በሁለቱ ድርጅቶች መካከል በተፈረመ ውል መሠረት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በዓለም ባንክ እንቅስቃሴ ወይንም ፖሊሲ ውስጥ ጣልቃ አይገባም ።

የዓለም ባንክ በ1944 ማለትም ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ጋር ባንድ ወቅት በአሜሪካ ብሪቶን ውድስ በተባለ ስፍራ በተደረገ ዓለም አቀፍ የገንዘብና የፋይናንስ ጉባኤ ተመሠረተ ። በጉባኤው ላይ 44 ሀገሮች የተሳተፉ ሲሆን የጉባኤውም ዓላማ በኢኮኖሚ ዝቅጠትና በጦርነት ምክንያት ተንኮታኩቶ የነበረውን ዓለም አቀፍ የገንዘብና የፋይናንስ ሥርዓት መልሶ መዘርጋት መሆኑ ተገልጾ ነበር ። አሜሪካና እንግሊዝ በጉባኤው ከተሳተፉ ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ዋናዎቹ ሲሆኑ ሶቭዬት ኅብረት ፣ ፖላንድ ፣ ቼኮዝሎቫኪያና ዩጎዝላቪያ ተሳትፈው ነበር ። ሆኖም ሶቭዬት ኅብረት አባል ላለመሆን ወዲያውኑ ስትወስን ፣ ፖላንድና ቼኮዝሎቫኪያም ከጥቂት ዓመታት በኋላ ከድርጅቱ ወጡ ።

የዓለም ባንክ አባል ለመሆን የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አባል መሆን የሚያሻ ሲሆን ሶሻሊስት ሀገሮች የገንዘብ ድርጅቱም ሆነ የዓለም ባንኩ አባል ላለመሆን ከሚያቀርቧቸው ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል በሁለቱም ድርጅቶች ውስጥ በተለይም ዋና ዋና ውሳኔዎችን በሚመለከት ለአሜሪካ ድምፅን በድምፅ የመሻር መብት የሚሰጥ መሆኑ ፣ አባላት የሚጠየቁትን ማንኛውንም የኢኮኖሚ መረጃ በተለይም ያላቸውን የወርቅና የውጭ ምንዛሪ መጠን በየጊዜው የማቅረብ ግዴታ ያለባቸው መሆኑ ፣ የወርቅና የውጭ ምንዛሪ መዋጮም በአሜሪካ እንዲቀመጥ ግዴታ መኖሩ ፣ እንዲሁም አባል ሀገሮች ከድርጅቶቹ ብድር ለማግኘት ከቡርዧ የኢኮኖሚ አመለካከት የሚመነጩ ግዴታዎችን እንዲያሟሉ መጠየቃቸው ይገኙባቸዋል ። ይሁንና አሁንም ቢሆን ጥቂት የሶሻሊስት ሀገሮች የድርጅቱ አባል ናቸው ።

ከኋላቀር ሀገሮች መካከል 27 በጉባኤው ላይ የተካፈሉ ቢሆንም በኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ተፅዕኖ ሥር ስለነበሩ የጉባኤውን ሂደት ለመወሰን ሙሉ ነፃነት አልነበራቸውም ። ቅኝ ግዛቶች የነበሩት ሌሎች የአፍሪካ ፣ የእስያና የካሪቢያን ሀገሮች ደግሞ በጉባኤው ላይ ጨርሶ ምንም ዓይነት ቦታ አልተሰጣቸውም ነበር ።

የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ የተግባር ክልል በምሥረታቸው ወቅት ተገልጾ ነበር ። በዚያም መሠረት ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የውጭ ምንዛሪ ዋጋንና ክፍያን የሚመለከቱ መመሪያዎች በማውጣትና አባላት መመሪያዎቹን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያገለግላቸውን የአ

ጭር ጊዜ የገንዘብ ብድር በመስጠት የውጭ ምንዛሪ ዋጋ መዋዠቅ እንዲገታና ዓለም አቀፍ ንግድ እንዲስፋፋ ማድረግ መሆኑ ተገልጿል ። የዓለም ባንክ የተግባር ክልል ደግሞ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ምክንያት ኢኮኖሚያቸው ለተንኮታኮተባቸው አባል ሀገሮች ኢኮኖሚ መልሶ ግንባታና ለሌሎችም በተለይ በመልማት ላይ ላሉ አባል ሀገሮች የኢኮኖሚ ልማት የሚያገለግል የረጅም ጊዜ ብድር መስጠትና በአባል ሀገሮች ውስጥ የግል የውጭ ካፒታል በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስችል ዋስትና ማስገኘት መሆኑ ተገልጿል ። ሆኖም የሁለቱም ድርጅቶች መሠረታዊ ተግባር ድርጅቶቹን በቁጥጥራቸው ሥር ባዋሉ የኢምፔሪያሊስት ኃይሎች አመለካከት ካፒታሊዝምን ከውድቀት ማዳን ፣ የካፒታሊስት ይዞታ በየሀገሩ እንደየሁኔታው እንዲያቆጠቁጥና እንዲጠናከር ማድረግ እንዲሁም የሞኖፖል ካፒታል በውጭ ምንዛሪና በውጭ ንግድ ላይ ያለውን የበላይነት ማጠናከር ነው ። የእነዚህ ድርጅቶች የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት በአባላት መዋጮ መጠን ላይ በመመሥረቱ ኢምፔሪያሊስቶች ድርጅቶቹን ለዚሁ ተግባር ለማዋል አልተቸገሩም ። ከዓለም ባንክ ጠቅላላ ድምፅ አሜሪካ 20% ያህሉን ፣ ጥቂት ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ባንድነት ደግሞ አብዛኛውን ድምፅ በመያዛቸው በባንኩ ገዥዎች ቦርድና የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ ውስጥ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን በኢምፔሪያሊስት ሀገሮች እጅ ሊገባ ችሏል ።

በ1945 ተመሥርቶ በሚቀጥለው ዓመት ሥራውን የጀመረው የዓለም ባንክ የአባል ሀገሮች ቁጥር በ1981 ወደ 139 ደርሶ ነበር ። ባንኩ ሲመሠረት አሥር ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የነበረው አሁን ወደ አርባ ቢሊዮን አድጓል ። ባንኩ ለአባላቱ የሚያበድረው ገንዘብ ምንጭ የአባላቱ መዋጮ ብቻ አይደለም ። ከዓለም የገንዘብ ገበያ በተለይም ከኢምፔሪያሊስት ሀገሮች የካፒታሊስት ድርጅቶችና ግለሰቦች በወለድ ተበድሮ መልሶ ያበድራል ። ከእንቅስቃሴው የሚያገኘው ትርፍም አንድ ሌላ ዋና የገንዘብ ምንጩ ነው ።

የዓለም ባንክ ለአባላት ለሚሰጠው ብድር ወለድ ያስከፍላል ። የወለዱም መጣኔ በጊዜው በገበያ ላይ የሚታየው የወለድ መጣኔና ባንኩ በሚያስከፍለው የአገልግሎት ዋጋ ባንድነት ይወሰናል ። ለምሳሌ በ1981 ባንኩ ለአባላት ያበደረው በ9.6% ወለድ ነበር ። የዋናው ብድርም ሆነ የወለድ ክፍያ የሚጀመረው ብድሩ ከተሰጠ ከአምስት ዓመታት በኋላ ሲሆን ብድሩም ተጠናቆ የሚከፈለው እስከ 20 ዓመታት በሚደርስ ረጅም ጊዜ ውስጥ ነው ።

ከዓለም ባንክ ጋር በቅርብ የተቆራኙ ሁለት ዓለም አቀፍ ድርጅቶች አሉ ። እነርሱም ዓለም አቀፍ የልማት ማኅበርና ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ኮርፖሬሽን ናቸው ። ዓለም አቀፍ የልማት ማኅበርና የዓለም ባንክ ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ሲሆኑ ልዩነቱ ዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር እጅግ ኋላቀር ለሆኑ ሀገሮች ብቻ ለተበዳሪዎች የበለጠ አመቺ በሆኑ ሁኔታዎች ብድር የሚሰጥ መሆኑ ነው ። ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ኮርፖሬሽን ደግሞ ዓላማው በመልማት ላይ ባሉ ሀገሮች ውስጥ የሀገር ውስጥና የውጭ ካፒታል የግል የኢኮኖሚ ይዞታን ለማጠናከር እንዲውል መርዳት መሆኑን በይፋ ያሳወቀ ነው ። በእነዚህ በሁለቱ ድርጅቶች ውስጥ አባል ለመሆን በቅድሚያ የዓለም ባንክ አባል መሆን ያሻል ።

በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮች በተለይም ሶሻሊስት የዕድገት ፈርን የሚከተሉት ዲሞክራሲያዊ የሆኑና በወቅቱ የዓለም ኢኮኖሚ ሁኔታዎችና ችግሮች ላይ የተመሠረተ እውነትም ዓለም አቀፍ የሆነ አዲስ ዓለም አቀፍ የገንዘብና የፋይናንስ ሥርዓት ፣ በአጠቃላይም አዲስ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲመሠረት ተደጋጋሚ ጥያቄ ማቅረባቸው አልቀረም ። ሆኖም ያለው ሥርዓት ተቀዳሚ ተጠቃሚ የሆኑት የኢምፔሪያሊስት ሀገሮች እስካሁን ድረስ ጥያቄውን አልተቀበሉትም ።

(ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትን ይመለከቷል ።)

## ዓለም ሠራተኛ ማኅበራት ፌደሬሽን (የ—)

*(World Federation of Trade Unions)*

በ1947 በፓሪስ ውስጥ የተመሠረተ ሲሆን ለአመሠራረቱ አመች ሁኔታን የፈጠረው የዓለም አቀፍ የሠራተኞች ማኅበራት ፌደሬሽን ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲጀመር እንስቃሴውን በማቋረጡ የሠራተኛውን አንድነት ለማጠናከርና ለማሰባሰብ አለመቻሉና ጭልጥ ያለ አድኃሪ መሥመር መያዙ ነው ።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ላይ የተበታተኑትን የሠራተኛውን መደብ ማኅበራት ሊያሰባስብ የሚችል አንድ ዓለም አቀፍ ድርጅት መመሥረት እንደሚያስፈልግ የአሜሪካ ፣ የእንግሊዝና የሶቭዬት ኅብረት የሠራተኛ ማኅበራት ተወካዮች ለንደን ላይ ባደረጉት ስብሰባ ስምምነት ላይ ደረሱ ። በዚሁ መሠረት በለንደን በ1945 የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ የሠራተኛ ማኅበራት ጉባኤ ተካሄደ ። ጉባኤው በአዲስ መንፈስ ለሚቋቋመው የሠራተኛ ማኅበራት ፌደሬሽን ሕገ ማኅበር በማርቀቅ መሠረት ጣለ ። ይኸውም አዲስ ድርጅት ዓለም አቀፍ የሠራተኛ ማኅበራት ፌደሬሽን የሚል ስያሜ ሲሰጠው ዋና መሥሪያ ቤቱም ፕራግ ፣ ቼኮዝሎቫኪያ እንዲሆን ተወሰነ ። የድርጅቱ ግበይት ዓላማዎች ፤

1. የሃይማኖት ፣ የዘርና የፖለቲካ አስተሳሰብ ልዩነቶችን ሳያደርግ የዓለምን ሠራተኛ ማኅበራት ማስተባበር ፣ አንድነታቸውን ማጠናከርና ማበረታታት ፤
2. የዓለም ሠራተኞች ለመብታቸውና ለጥቅማቸው እንዲታገሉ በማድረግ የኑሮና የሥራ ሁኔታዎች እንዲሻሻሉ መታገል ፤
3. ኢምፔሪያሊዝምን ፣ ቅኝ አገዛዝን፣ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝንና የዘር መድልዎን ለማስወገድ ሠራተኛውን በዚህ መሠረት ለትግል ማሰለፍ ፤
4. ለሰላም ፣ ለጦር መሣሪያ ቅነሳ ፣ ለዴሞክራሲና ለዲሞክራሲ በዓለም ላይ መስፈን ለሚደረገው ትግል ሠራተኛውን ማዘጋጀት ናቸው ።

ይህ ድርጅት እነዚህን የመሰሉ ክቡር ዓላማዎች በማንገብ ሥራውን በጀመረበት ጊዜ የአሜሪካና የምዕራብ አውሮፓ አድኃሪ የሠራተኛ ማኅበራት የኮሚኒስቶች ተፅዕኖ ያለበት ድርጅት ነው በማለት አዲስና ሌላ ተቀናቃኝ ድርጅት ቢመሠርቱም ማኅበሩ እያደገና እየተጠናከረ መጣ ። ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት ከ190 ሚሊዮን በላይ አባላት ያሏቸው በ81 ሀገሮች የሚገኙ 90 ማኅበራትን በአባልነት ያቀፈ ታላቅ ድርጅት ለመሆን በቅቷል ። የመላው ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበርም (መኢሠማ) የዚሁ ድርጅት አባል ነው ።

## ዓለም ሰላም ምክር ቤት (የ—)

*(World Peace Council)*

ለፍትሕ ፣ ለብሔራዊ ነፃነት ፣ ለዴሞክራሲ መጠናከርና ለሰላም መስፈን የሚታገል ፣ ለዓለም ሰላም የቆሙ ዓለም አቀፍና ብሔራዊ ድርጅቶች እንዲሁም ንቅናቄዎችና የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮችን ያቀፈ ዓለም አቀፍ አካል ነው ። የዓለም ሰላም ምክር ቤት አባል የሆኑት ብሔራዊ የሰላም ንቅናቄዎች፣ የሙያ ፣ የሃይማኖት ፣ የፖለቲካ ፣ የወጣቶች ፣ የሴቶች ፣ የልዩ ልዩ ማኅበራዊና የባህል ድርጅቶች በአጠቃላይም በመላው ዓለም ያለውን ሕዝባዊ አስተያየት የሚያስተጋቡ ናቸው ። እንደዚሁም ከዓለም ሰላም ምክር ቤት አባላት መካከል የፖለቲካ ፓርቲዎች ፣ የሕዝባዊ ድርጅቶች ፣ የነፃነት ንቅናቄ መሪዎች ፣ የታወቁ የሥነ ጽሑፍ ፣ የባህል ፣ የሳይንስ ፣ የትምህርትና የሥነ ጥበብ ሰዎች ይገኛሉ ።

የዓለም ሰላም ምክር ቤት የተጠነሰሰው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተደምስሳ በነበረችው ሮስሎው በተባለችው የፖላንድ ከተማ በ1948 ነበር ። ዓለምን ሌላ አዲስ ጦርነት ባሰጋበት በዚህ ወቅት ቀራጥ ሴትና ወንድ ምሁራን የዓለም አቀፍ ምሁራን ጉባኤ አድርገው፣ ሕዝቦች ሁሉ ለሰላም እንዲታገሉ

ጥሪ አደረጉ ። ጥሪያቸውም በ1949 በሚያዝያ ወር በፓሪስና በፕራግ ከተሞች የተደረገውን የመጀመሪያውን "የሰላም ጠባቂዎች የዓለም ጉባኤን" አስገኘ ። በዚህ የዓለም ጉባኤ ላይ ከሰባ ሁለት ሀገሮች የመጡ መልዕክተኞች ተካፋይ ሆነው ነበር ።

በዚህ መሠረት የፓሪስንና የፕራግን ስብሰባዎች ተግባር ለመቀጠል ዓለም አቀፍ ኮሚቴ ተቋቋመ ። ዓመቱ ሳያልቅ በሰባ ሀገሮች ብሔራዊ የሰላም ኮሚቴዎች ተመሠረቱ ። በአምስቱም አህጉራት ጉባኤዎች፣ ስብሰባዎችና ትዕይንተ ሕዝቦች ተደረጉ ።

በ1950 ኅዳር ወር የንቅናቄው ጉባኤ በፖላንድ ዋና ከተማ በዋርሶ ተደረገ ። ከዚህም ጉባኤ "የዓለም ሰላም ምክር ቤት" ተወለደ ።

የዓለም ሰላም ምክር ቤት ሰላምን፣ የሰው ደኅንነትንና ብልጽግናን፣ የሀገሮች ነፃነትን በሚመለከት ረገድ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና ከድርጅቱ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ጋር በቅርብ በመተባበር ይሠራል ። እንደዚሁም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ከቅኝ አገዛዝ ፣ ከአፓርታይድና ከዘረኝነት ጋር በሚያደርገው ትግል የዓለም ሰላም ምክር ቤት ከፍተኛ ትብብርና ድጋፍ ያደርጋል ።

## ዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት (የ—)
*(World Socialist System)*

ከካፒታሊዝም ወደሶሻሊዝም ሽግግር በሚደረግበት ባለንበት ታሪካዊ ዘመን ለሰላም ፣ ለዲሞክራሲ ፣ ለብሔራዊ አርነትና ለሶሻሊዝም የቆመ ፣ በአጠቃላይ በዓለም አብዮታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ፀረ ኢምፔሪያሊስትና በፀረ አድኀሮት ትግል ውስጥ የተሰለፉ ሀገሮችን የሚደግፍ ወሳኝ አብዮታዊ ኃይል ነው ።

የዓለም ሠራተኛ መደብና የኮሚኒስት ንቅናቄ ውጤት የሆነው ይህ የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት በታላቁ የሩሲያ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት የተበሰረና በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ውስጥ እያለፈ በመምጣት ዛሬ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ስፍቶና ደርጅቶ የሚገኝ ነው ።

ከሁለተኛው የኢምፔሪያሊስት ጦርነት በኋላ ሶሻሊዝም ከሶቭዬት ኅብረት ክልል አልፎ በደቡብና በመካከለኛው አውሮፓና በእስያ ድልን መቀዳጀቱ የሶሻሊስቱን ሥርዓት ራሱን የቻለ ሥርዓት ሆኖ ለመውጣት አስችሎታል ። ይህም ሁኔታ በጥቅምቱ ሶሻሊስት አብዮት የተጀመረው የካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ እንዲባባስና ሥርዓቱ እንዲፍረከረክ አድርጓል ። በሌላም በኩል የሶሻሊስቱ ሥርዓት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጠናክሮ መውጣት ለብሔራዊ አርነትና ለሌሎች ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴዎች መፋፋም አመች ሁኔታዎችን በመፍጠሩ የዓለም የኃይል አሰላለፍ ሚዛን ወደሶሻሊዝም እንዲያጋድል አድርጓል ።

በ1950ዎቹ መጨረሻና በ1960ዎቹ መጀመሪያ ላይ ሶሻሊዝም አንፃራዊ በሆነ ሰላማዊ ሁኔታ ውስጥ ይበልጥ ሊጠናከር ችሏል ። በዚህ ጊዜ ሕዝቦች ለሰላም ፣ ለዲሞክራሲ ፣ ለማኅበራዊ ዕድገት ፣ ለብሔራዊ ነፃነትና ለሶሻሊዝም የሚያደርጉት ትግል በየቦታው መፋፋሙ ለሶሻሊዝም መጠናከር አመች ሁኔታን ፈጥሯል ። በዚህን ወቅት በአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም አፍንጫ ሥር የተካሄደው የኩባ አብዮት ድልን መጐናፀፉ የሶሻሊስት ሀገሮችንና የዓለም ተራማጅ ኃይሎችን የቅርብ ድጋፍና ትብብር የሚገልጽ ነው ። ሶሻሊስትና ሌሎች ተራማጅ ኃይሎች የሚያራምዱት የሰላም ፖሊሲ ዛሬ ባለንበት ዓለም አቀፍ ሁኔታ የመደብ ትግልን የሚያኮላሽ ሳይሆን እንዲያውም እንዲጠናከር አመች ሁኔታዎችን የሚፈጥርለት መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው ።

በዘመናችን በዓለም አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሂደት ውስጥ የሶሻሊስት ሥርዓት ከፍተኛ ዓለም አቀፋዊ ሚና ይጫወታል ። የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት ባሁኑ ጊዜ የኅብረተሰብን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ የዕድገት አቅጣጫ በትክክል ያመለክታል ። ሶሻሊዝም በየጊዜው በካፒታሊዝም ላይ የሚጐናፀፋቸው ድሎች የዘመኑ ቅራኔ የሚፈታባቸው ደረጃዎች ሲሆኑ የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት ኢምፔሪያሊዝምን በመዋጋት የመጀመሪያውን ኃላፊነት የሚሸከም ነው ።

የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት ለዓለም አብዮታዊ ሂደት መፋጠንና መጠናከር ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ርዕዮተዓለማዊ መሠረ

ረት ነው ። ሶሻሊስት ሀገሮች በኢኮኖሚ ረገድ በአጭር ጊዜ ውስጥ የደረሱበት ከፍተኛ ዕድገት ለሌሎች ሀገሮች አብዮታዊ አር አያነት ያለው ከመሆኑም በላይ ለተለያዩ አብዮታዊ ኃይሎች የሚያደርጉት ቁሳዊና ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎችን የሚያስተባብርና የሚያጠናክር ነው ።

በዓለም አቀፍ ግንኙነትም የሶሻሊስቱ ሥርዓት በመንግሥታት መካከል መልካም ትብብርና ግንኙነት እንዲሰፍን በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና አለው ። በሰላም አብሮ በመኖር ፖሊሲ መሠረት በሁለቱ ማኅበራዊ ሥርዓቶች ማለትም በሶሻሊዝምና በካፒታሊዝም ውስጥ በሚገኙና የተለያዩ የዕድገት ፈለጐችን በሚከተሉ ሀገሮች መካከል በእኩልነት ፣ በወንድማማችነትና በጋራ ጥቅሞች ላይ የተመሠረቱ ግንኙነቶች እንዲጠናከሩ በማንባር ቀደምትነት ይታገላል ።

# ዓለም አቀፍ ሞኖፖል
(*International Monopoly*)

አንድ ወይንም ከአንድ በላይ የሆኑ የዓለም ካፒታሊስት ኢኮኖሚ መስኮችን በቁጥጥሩ ሥር ያዋለ ፣ በውጭ ሀገር ንብረቱን የሚያንቀሳቅስ ድርጅት ወይንም የልዩ ልዩ ሀገሮች ካፒታሊስቶች ይዞታ የሆኑ ድርጅቶች ኅብረት ዓለም አቀፍ ሞኖፖል ወይም እንደ ሌኒን አባባል ልዕለ ሞኖፖል በመባል ይታወቃል ።

ለዓለም አቀፍ ሞኖፖሎች መፈጠርና መስፋፋት ኢኮኖሚያዊ መሠረቱ ካፒታሊስት የማምረት ተግባር በከፍተኛ ደረጃ ማኅበራዊ ፣ የኢኮኖሚ ሕይወት የበለጠ ዓለም አቀፋዊ እየሆነ መምጣት ነው ። የዓለም አቀፍ ሞኖፖሎች መመሥረት የጀመሩት ከ1860ዎቹ እስከ 1880ዎቹ ባለው ጊዜ ቢሆንም የካፒታሊዝም አንድ ዋና ገጽታ ለመሆን የቻሉት በያዝነው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ላይ ነው ፤ ለምሳሌ በ19ኛው ምዕት ዓመት መጨረሻ ላይ የነበሩ ዓለም አቀፍ ሞኖፖሎች 40 ያህል ሲሆኑ በ1910 ቁጥራቸው ወደ 100 ፣ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መገባደያ ላይ ደግሞ ወደ 1000 ከፍ ብሎ ነበር ።

በአሁኑ ጊዜ ዓለም አቀፍ ሞኖፖሎች የሞኖፖል መሪ ኃይል በመሆን ላይ ይገኛሉ ። ዋና ዋናዎቹ 500 ዓለም አቀፍ ሞኖፖሎች ከካፒታሊስት ሀገሮች ጠቅላላ ብሔራዊ ምርት ከሦስት እጅ አንዱን ፣ ከኢንዱስትሪ ምርትም ግማሽ ያህሉን ያመርታሉ ። በተጨማሪም ከካፒታሊስቱ ዓለም ጠቅላላ ንግድ 60% ያህሉን በቀጥታ በቁጥጥራቸው ሥር ሲያውሉ የዳበሩ ካፒታሊስት ሀገሮች ወደውጭ ከሚልኩት ካፒታል አጠቃላይ መጠን ደግሞ 90% ያህሉን ይይዛሉ ። የአንዳንድ ትላልቅ ዓለም አቀፍ ሞኖፖሎችን የዓመት ሽያጭ የበርካታ ሀገሮች ብሔራዊ ገቢ ቢጠቃለል እንኳን የማይመጣጠነው መሆኑ እነዚህ ሞኖፖሎች ምን ያህል የኢኮኖሚና የፖለቲካ ኃይል እንዳላቸው ያስገነዝባል ።

ሁለት ዓይነት ዓለም አቀፍ ሞኖፖሎች አሉ ። አንደኛው ባለብዙ ብሔር ሞኖፖል የሚባለው ሲሆን በልዩ ልዩ ሀገሮች የካፒታል ኅብረት የሚፈጠር ነው ። ሁለተኛው ዓይነት ደግሞ ድንበር ዘለል ሞኖፖል የሚባል ሲሆን በአንድ ሀገር ካፒታሊስቶች ይዞታና ቁጥጥር ሥር የሚገኝ ሆኖ በአንቅስቃሴው ዓለም አቀፍ ይዞታ ያለው ነው ።

ከባለብዙ ብሔር ሞኖፖሎች ዋና ዋና ገጽታዎች መካከል ጥቂቶቹ የአክሲዮን በብዙ ሀገሮች ውስጥ መሰራጨትና ዋና ዋናዎቹ ሥራ አስኪያጆች ከልዩ ልዩ ሀገሮች የተውጣጡ መሆናቸው ነው ። የእንግሊዝ ፣ የኔዘርላንድና የሌሎች ሀገሮች ካፒታል በአንድነት የሚገኝበት የሼል ኩባንያ ለባለ ብዙ ብሔር ሞኖፖሎች እንደ ምሳሌነት ሊጠቀስ ይችላል ። የባለብዙ ብሔር ሞኖፖሎች ቁጥር ከድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ቁጥር ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ አይደለም ። ከምክንያቶቹ መካከል የየሀገሩ ሕጋዊ መዋቅር መለያየት ፣ ለተለያዩ ሀገሮች ቀረጥ የመክፈል ችግርና አንዳንድ መንግሥታት የዚህ ዓይነት ሞኖፖሎችን መቋቋም የሚቃወሙ መሆናቸው ይገኙበታል ።

ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ባሁኑ ጊዜ እጅግ እየዳበሩና እየተስፋፉ በመሄድ ላይ ይገኛሉ ። ኤክሶን ፣ ጀኔራል ሞተርስ ፣ ጀኔራል ኤሌክትሪክ በመባል የሚታወቁት የአሜሪካ ሞኖፖሎች የድንበር ዘለል ሞኖፖሎች

ምሳሌዎች ናቸው ። የአሜሪካ ካፒታሊስቶች ከድንበር ዘለል ሞኖፖሎች መካከል ግማሽ ያህሉን በባለቤትነት ይዘው ይገኛሉ ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የሌሎች ካፒታሊስት ሀገሮች በተለይም የምዕራብ አውሮፖ ሀገሮችና የጃፓን ሞኖፖሎች በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በማጠናከር ላይ ይገኛሉ ።

ዓለም አቀፍ ሞኖፖሎች ከፍተኛ የሞኖፖል ትርፍ ለማግኘት በርካታ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ ። ለምሳሌ ለሚሸጧቸው ሸቀጦች ከፍተኛ የሞኖፖል ዋጋ ፣ ለሚገዟቸው ጥሬ ዕቃዎች ደግሞ ዝቅተኛ ዋጋ ይተምናሉ። የሸቀጦችን ምርትና ሽያጭ መጠንም ይወስናሉ ። የዓለምን ገበያና የጥሬ ዕቃን ምንጮች በመካከላቸው ይከፋፈላሉ ። አዳዲስ መሣሪያዎችንና የአሠራር ዘዴዎችን ስርጭት ይቆጣጠራሉ ። ለመንግሥት የሚከፍሉት ቀረጥ በተቻለ መጠን ዝቅተኛ እንዲሆን ለማድረግ የማይጠቀሙበት ዘዴ የለም ።በዚህ አኳኋን በእነርሱ ሥር ባሉ ድርጅቶች ውስጥ በሚሠሩ እስከ 20 ሚሊዮን በሚገመቱ ሠራተኞች ላይ ብቻ ሳይሆን የሚያስመርቷቸውንና የሚሸጧቸውን ሸቀጦች በሚገዙቱ ከዚህ ቁጥር በብዙ እጥፍ በሚበልጡ ሕዝቦችም ላይ ከፍተኛ ብዝበዛ ያካሂዳሉ ።

የዓለም አቀፍ ሞኖፖሎች ተግባራት በተለይ በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮችን በከፋ አደጋ ላይ የሚጥሉ ናቸው ። ዓለም አቀፍ ሞኖፖሎች በመልማት ላይ ላሉ ሀገሮች የኢኮኖሚ ዕድገትን ከማምጣት ይልቅ ለኢኮኖሚያቸው መቆርቆዝ ዓይነተኛ ምክንያት ሆነዋል ። ለምሳሌ ከ1970–1980 ባለው ጊዜ ውስጥ ከኢምፔሪያሊስት ሀገሮች በመልማት ላይ ወደሚገኙ ሀገሮች ተሸጋግሮ በሥራ ላይ ለዋለ ሙሉ ንዋይ ለእያንዳንዱ የአሜሪካ ዶላር ዓለም አቀፍ ሞኖፖሎች 2.2 የአሜሪካ ዶላር በመልማት ላይ ካሉ ሀገሮች መዝብረው አውጥተዋል ። በዚሁ ጊዜ ውስጥ የአሜሪካ ሞኖፖሎች ለእያንዳንዱ ዶላር ሙሉ ንዋይ 4.25 የአሜሪካ ዶላር በመልማት ላይ ካሉ ሀገሮች አሽሽተዋል ። አሁንም በዚሁ ጊዜ ውስጥ የአሜሪካ ሞኖፖሎች በውጭ ሀገር በሥራ ላይ ካዋሉት 18% ያህሉን ብቻ በመልማት ላይ ባሉ ሀገሮች ውስጥ በሥራ ላይ ያዋሉ ሲሆን ከነዚህ ሀገሮች ያገኙት ከጠቅላላ ትርፍ 36% ነው ። ወደ አሜሪካ ከላኩት ትርፍ 46% ያህሉ የተገኘው በመልማት ላይ ካሉ ሀገሮች ነው። የአሜሪካ ሞኖፖሎች ራሳቸው በ1981 በይፋ እንዳሳወቁት በመልማት ላይ ባሉ ሀገሮች የሚያገኙት የትርፍ መጣኔ 24.1% ሲሆን በዳበሩ ካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ የሚያገኙት ግን 16.6% ነው ። በዚህ አኳኋን ዓለም አቀፍ ሞኖፖሎች በመልማት ላይ ባሉ ሀገሮች ውስጥ በሚያካሂዱት እንቅስቃሴ አማካይነት የኢኮኖሚ ዕድገትን የሚያስገኙት ለእነዚህ ሀገሮች ሳይሆን ለራሳቸው ለኢምፔሪያሊስት ሀገሮች መሆኑን በግልጽ ለማየት ይቻላል።

ዓላማቸው የሞኖፖል ትርፍ ማግኘት የሆነው ዓለም አቀፍ ሞኖፖሎች የሚያደርጉት እንቅስቃሴ በመልማት ላይ ላሉ ሀገሮች የተመጣጠነ ዕድገት ዕንቅፋት ነው ። ዓለም አቀፍ ሞኖፖሎች በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮችን ብሔራዊ ነፃነት አደጋ ላይ እንደሚጥሉ የታወቀ ነው ። በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮችን ሕግጋት በተለይም ሙሉ ንዋይን፣ ቀረጥን ፣ ንግድን ፣ ቅጥርንና የዋጋ ምደባን ላለማክበር በልዩ ልዩ ዘዴዎች ይጠቀማሉ ። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በብሔራዊ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ ይገባሉ ። መንግሥቶቻቸው በመልማት ላይ ባሉ ሀገሮች ላይ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ተፅዕኖአቸውን በማጠናከር ጥቅማቸውን እንዲያዳብሩላቸው ያደርጋሉ ። በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮች የሞኖፖሎችን ድርጅቶች ወደ መንግሥት ንብረትነት ሲያዛውሩ ካሣ ከፍያን በሚመለከት የእነዚህን መንግሥታት ሕግጋት አይቀበሉም ። በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮች የተፈጥሮ ሀብታቸውን ለመቆጣጠርና ለመንከባከብ ለሚያደርጉት ጥረት ዕንቅፋት ይሆናሉ።

በተለይ ከ2ኛው ዓለም ጦርነት በኋላ የዓለም አቀፍ ሞኖፖሎች የኢኮኖሚ ኃይል እየዳበረ የመጣ ቢሆንና ሕዝቦች ለተሟላ ነፃነትና ለሶሻሊዝም የሚያደርጉትን ትግል ለማጨናገፍ የማይሸርቡት ደባ ባይኖርም ፣ ፊት ያደርጉት እንደ ነበረው በዓለም ካፒታሊስት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ እንደ ልባቸው ሊፈነጩ አልቻሉም ። የዚህም ዋና ዋና ምክንያቶች የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት እየዳበረ መምጣት ፣ ዓለም አቀፍ የሠራተኛው መደብ ንቅናቄና የብሔራዊ ነፃነት ትግል

 ዓለም አቀፍ የሥራ ክፍፍል

መጠናከር ናቸው ። ባሁኑ ጊዜ በአብዮታውያን ኃይሎችና በዓለም አቀፍ ሞኖፖሎች መካከል ብቻ ሳይሆን በሞኖፖሎች እንዲሁም በሞኖፖሎቹና በትናንሽ የካፒታሊስት ድርጅቶች መካከል የከረረ ትግል በመካሄድ ላይ ይገኛል።

## ዓለም አቀፍ የሥራ ክፍፍል (በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም)

*International Division of Labour* (*Under Capitalism and Socialism*)

ከአንድ ሀገር ብሔራዊ ድንበር አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ በማምረት ሆነ በልውውጥ ተግባር በተወሰኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ላይ ትኩረት በማድረግ የሚከናወን የሥራ ድርሻ ነው ። ይህም ከምርት ኃይሎች መዳበርና ከኢኮኖሚ ሕይወት ዓለም አቀፋዊ ባሕርይ እያደገ መምጣት ጋር የተያየዘ ነው ።

ዓለም አቀፍ የሥራ ክፍፍል በአነስተኛ ደረጃም ቢሆን በቅድመ ካፒታሊስት ስልተ ምርት በነበሩ ሥርዓተ ማኅበሮች እንደ ነበረ ይታወቃል ። ከካፒታሊስት ስልተ ምርት በፊት በነበሩት ሥርዓተ ማኅበሮች የነበረው ዓለም አቀፍ የሥራ ክፍፍል በተለያዩ ሀገሮች ውስጥ በነበረው ተፈጥሮአዊ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነበር ። ዓለም አቀፍ የሥራ ክፍፍል የዳበረውና የተስፋፋው ከኢንዱስትሪ አብዮት ዘመን ወዲህ ነው ። ኢንዱስትሪ በከፍተኛ ደረጃ እየተስፋፋ ሲመጣ ምርትም በብዛትና በጥራት እያደገ መጣ ፤ ከዚህም በላይ ከራሳቸው ሀገር ድንበር አልፈው በሌሎች ሀገሮች ውስጥ ሥራቸውን የሚያስፋፉ ኩባንያዎች መፈጠርን አስከትሏል ።

በ19ኛው ምዕት ዓመት መጨረሻ የታየው ዓለም አቀፍ የሥራ ክፍፍል ከምዕራብ አውሮፓ ከሚመጡትና በርካሽ ዋጋ ከሚሸጡት ሸቀጦች ጋር መወዳደር ያልቻሉት በኢኮኖሚ ኋላ ቀር የሆኑት የእስያ ፣ የአፍሪካና የላቲን አሜሪካ ሀገሮች አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን መፈራረስ አስከተለ ። ስለዚህም አብዛኛዎቹ በኢኮኖሚ ኋላ ቀር የሆኑ ሀገሮች የእርሻ ምርት ውጤቶችና የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች ፣ በኢንዱስትሪ የበለጸጉ ሀገሮች ደግሞ የኢንዱስትሪ የምርት ውጤቶች አቅራቢ የመሆኑ ሁኔታ እየጎላ መጣ ። ይህ ዓይነቱ የሥራ ክፍፍል ምን ጊዜም ቢሆን የኢምፔሪያሊስት ሀገሮች የበላይነትን ፣ አዳጊ ሀገሮች ደግሞ የበታችነትን ይዘው እንዲቆዩ የሚያደርግ ነው ። ስለሆነም ዛሬ የሚታየው ዓለም አቀፍ የንግድ ልውውጥ በእኩልነት ላይ ያልተመሠረተ ነው ። የበለጸጉ ካፒታሊስት ሀገሮች ጥሬ ዕቃ አቅራቢ በሆኑ ኋላ ቀር ሀገሮች ላይ በተለያዩ ዘዴዎች ተፅዕኖ በማድረግ የራሳቸውን ከባድ ኢንዱስትሪ እንዳያቋቁሙ በማድረግ ጥገኛ አድርገዋቸዋል ።

የሶሻሊዝም ዕድገት ዓለም አቀፍ ሶሻሊስት የሥራ ክፍፍል እንዲኖር አስችሏል ። ዓለም አቀፍ ሶሻሊስት የሥራ ክፍፍል በዕቅድ በመመራት ፣ እርስ በእርስ በመከባበር ፣ የአንድን ሀገር ነፃነት ባለመድፈር በጋራ ጥቅም ላይ በመመሥረት ፣ በሶሻሊስት ዓለም አቀፋዊነት ፣ በወንድማማችነትና በመረዳዳት መርሀ ላይ የተመሠረተ ነው ። በዚህ የሥራ ክፍፍል መሠረት በልዩ ልዩ የሶሻሊስት ሀገሮች ጠቅላላ የኢኮኖሚ ዕድገት እየታየና አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችም እየተተከሉ ናቸው ። እጅግ ኋላ ቀር የነበሩ ሀገሮች ዛሬ በእርሻ ውጤቶች ላይ የተመሠረቱ ብዙ ኢንዱስትሪዎችን አቋቁመዋል ። በማዕድንና ኃይል በማመንጨት ረገድም ብዙ ሠርተዋል ።

ዓለም አቀፍ ሶሻሊስት የሥራ ክፍፍል ኃይልና ሀብትን በመቆጠብ የኢኮኖሚ ዕድገትን በማፋጠን በሶሻሊስት ሀገሮች የሚገኙትን ሕዝቦች የኑሮ ደረጃ በየጊዜው ከፍ የሚያደርግ ነው ። የሥራ ክፍፍሉም በአብዛኛው በቁሳዊ ምርት ፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ መስክ ያተኩራል ።

የዓለም አቀፍ ሶሻሊስት የሥራ ክፍፍል ዋና ዓላማ በሶሻሊስት ሀገሮች መካከል ያለውን የኢኮኖሚ ዕድገት ልዩነት ማጥበብና እያንዳንዱ ሀገር የተስተካከለ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲኖረው ማድረግ ነው ። ዓለም አቀፍ ሶሻሊስት የሥራ ክፍፍል የኢኮኖሚ ጥምረት መሠረት ነው ። የዓለም አቀፍ ሶሻሊስት የሥራ ክፍፍል መሠረታዊ ዓላማ እያንዳንዱ ሀገር በኢንዱስትሪ እንዲበለጽግ ማስቻል ነው ።

ዓለም አቀፍ ሶሻሊስት የሥራ ክፍፍል ሶሻሊስት ሀገሮች በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ከሌሎች ሀገሮች ጋር ማድረጋቸውን አይከለክልም ። ይህም ሁኔታ በሰላም አብሮ የመኖር መርህን ለማጠናከር አስፈላጊ መሆኑ ይታመንበታል ።

(ሶሻሊስት የኢኮኖሚ ጥምረትን ይመለከቷል።)

## ዓለም አቀፍ የተማሪዎች ኅብረት

*(International Union of Students)*

በነሐሴ 1946 በፕራግ ከተማ የተመሠረተ ዓለም አቀፍ የተማሪዎች ማኅበራት ኅብረት ነው ። የድርጅቱ ዓላማዎች የተማሪዎችን መብት ማስከበር ፣ ለሰላምና ለዓለም አቀፍ ደኅንነት መታገል ፣ ኢምፔሪያሊዝምን ፣ ቀጥተኛና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን ፣ አድኅሮትን ፣ ፋሺዝምንና ዘረኝነትን መዋጋት ፤ ለብሔራዊ ነፃነት ፣ ለማኅበራዊ ዕድገትና ለዲሞክራሲያዊ የትምህርት ሥርዓት የሚካሄዱትን እንቅስቃሴዎች ማገዝ ነው ። የዚሁ ዓላማ ደጋፊ የሆነው የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ወጣቶች ማኅበርም (አኢወማ) የድርጅቱ አባል ነው ።

ድርጅቱ የተራማጅ ተማሪዎችን ዓለም አቀፍ የትግል አንድነት በማጠናከር ትልቅ ሚና ተጫውቷል ። በየጊዜው ዓለም አቀፍ የወጣቶችና የተማሪዎች ፌስቲቫሎችን ያዘጋጃል ። ስለወጣቶች ሁኔታ ፣ ለሰላም ስለሚደረገው ትግል ፣ ለብሔራዊ ነፃነት ስለሚካሄዱት ትግሎችና ስለ ትምህርት ፣ በአጠቃላይም ስለ ማኅበራዊና ኢኮኖሚ ጉዳዮች የሚወያዩ ስብሰባዎችን በመጥራት የዓለም ወጣቶች አቋም እንዲወስዱባቸውና የድጋፍና የእርዳታ ዘመቻዎች እንዲያደርጉ ጥረት ያደርጋል ። ድርጅቱ ለተለያዩ የተማሪዎች ማኅበራት የመድኃኒት ፣ የትምህርትና የስፖርት ዕቃዎች ይሰጣል ፤ ለታመሙና ለተቸገሩ ተማሪዎች የሕክምናና የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ የገንዘብና የነፃ ትምህርት እርዳታ ያደርጋል ።

የድርጅቱ ከፍተኛ የአመራር አካል ጉባኤው ነው ። ጉባኤው የድርጅቱን ፕሬዚዳንት ፣ ሴክሬታሪያትና ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይመርጣል ። የድርጅቱ ዋና ጽሕፈት ቤት በቼኮዝሎቫኪያ ውስጥ በፕራግ ከተማ ይገኛል ።

## ዓለም አቀፍ የነፃ ሠራተኛ ማኅበራት ኮንፌደሬሽን

*(World Free Trade Union Confederation)*

የአሜሪካና የእንግሊዝ ቀኝ ክንፍ የሠራተኛ ማኅበራት መሪዎች ከዓለም የሠራተኛ ማኅበራት ፌዴሬሽን በመገንጠል ያቋቋሙት አድኃሪ ዓለም አቀፍ የሠራተኛ ማኅበራት ድርጅት ነው ። ድርጅቱ በ1949 በለንደን ከተማ የተቋቋመ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በ88 ካፒታሊስትና አዳጊ ሀገሮች የሚገኙ ሠራተኛ ማኅበራትን በአባልነት የያዘ ነው ።

የድርጅቱ ዓላማ በማኅበራዊ ዲሞክራሲ አድርባይ መሥመር ላይ የተመሠረተ ሲሆን የሠራተኛው ማኅበራትን አንዳንድ መብቶች መጠበቅ ፣ ለማኅበራዊ ፣ ለኢኮኖሚያዊና ለባህላዊ ጥገናዊ ለውጦች መታገልና ፀረ ኮሚኒስት እንቅስቃሴዎችን ማካሄድ ከተግባራቱ ዋናዎቹ ናቸው ። ድርጅቱ ኔቶን ፣ አሜሪካ በተለያዩ ቦታዎች የምታካሂዳቸውን ወረራዎችና የምዕራብ ኃያላን መንግሥታትን የጦረኝነት ፖሊሲ የሚደግፍ ነው ። ይህ ድርጅት ከአሜሪካው የስለላ ድርጅት ከሲ.አይ.ኤ. ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው ። በሀገራችንም ከአብዮቱ በፊት የሠራተኛውን ማኅበራት እንቅስቃሴ ለማኮላሸት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል ።

ኮንፌደሬሽኑ በአፍሪካ ፣ በእስያ ፣ በአሜሪካና በአውሮፓ ቅርንጫፎች ያሉት ሲሆን ዋናው ጽሕፈት ቤቱ በበልጅግ ዋና ከተማ በብራሰልስ ይገኛል ። ከፍተኛው የአመራር አካሉ ጉባኤው ሲሆን በየሦስቱ ዓመት ይሰበሰባል ። ጉባኤው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውንና ዋና ፀሐፊውን ይመርጣል ። ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውም ፕሬዚዳንቱንና ምክትል ፕሬዚዳንቶችን ይመርጣል ። የኮንፌደሬሽኑ የቀን ተቀን ሥራ በሴክሬታሪያቱ አማካይነት ይከናወናል ።

## ዓለም አቀፍ ኮሚኒስት ንቅናቄ
*(World Communist Movement)*

(አንደኛው ኢንተርናሽናልን ፣ ሁለተኛው ኢንተርናሽናልን ፣ ሦስተኛው ኢንተርናሽናልን ይመለከቷል ።)

## ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት
*(International Monetary Fund IMF)*

ዓለምአቀፍ የገንዘብ ሥርዓትን የማቀነባበር ከፍተኛ ኃላፊነት የተጣለበት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ልዩ አካላት ከሆኑት አንዱ ነው ። ሆኖም በሁለቱ ድርጅቶች መካከል በተፈረመ ውል መሠረት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት እንቅስቃሴ ወይንም ፖሊሲ ውስጥ ጣልቃ ሊገባ አይችልም ።

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት በ1944 ማለትም ከዓለም ባንክ ጋር ባንድ ወቅት በአሜሪካ ብሬቶን ውድስ በተባለ ስፍራ በተደረገ ዓለም አቀፍ የገንዘብና የፋይናንስ ጉባኤ ተመሠረተ ። በጉባኤው ላይ 44 ሀገሮች የተሳተፉ ሲሆን የጉባኤውም ዓላማ በኢኮኖሚ ዝቅጠትና በጦርነት ምክንያት ተንኮታኩቶ የነበረውን የዓለም አቀፍ የገንዘብና የፋይናንስ ሥርዓት መልሶ መዘርጋት መሆኑ ተገልጾ ነበር ። አሜሪካና እንግሊዝ በጉባኤው በግንባር ቀደምትነት ከተሳተፉት ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች መካከል የሚገኙ ሲሆን ሶቪዬት ኅብረት ፣ ፖላንድ ፣ ቼኮዝሎቫኪያና ዩጎዝላቪያም ተሳትፈው ነበር ። ሆኖም ሶቪዬት ኅብረት አባል ላለመሆን ወዲያውኑ ስትወስን ፣ ፖላንድና ቼኮዝሎቫኪያም ከጥቂት ዓመታት በኋላ ከድርጅቱ ወጡ ። ሶሻሊስት ሀገሮች በድርጅቱ ውስጥ ላለመሳተፍ ከሚያቀርቧቸው ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል የድምፅ አሰጣጡ ሥርዓት በተለይ ዋና ዋና ውሳኔዎችን በሚመለከት ለአሜሪካ ድምፅን በድምፅ የመሻር መብት የሚሰጥ መሆኑ ፣ አባላት ማንኛውንም ድርጅቱ የሚጠይቃቸውን የኢኮኖሚ መረጃዎች ፣ በተለይም ያላቸውን የወርቅና የውጭ ምንዛሪ መጠን በየጊዜው የማቅረብ ግዴታ ያለባቸው መሆኑ ፣ የወርቅና የውጭ ምንዛሪ መዋጮም በአሜሪካ እንዲቀመጥ ግዴታ መኖሩ እንዲሁም አባል ሀገሮች ከድርጅቱ ብድር ለማግኘት ከቡርዧ የኢኮኖሚ አመለካከት የሚመነጩ ግዴታዎችን እንዲያሟሉ መጠየቃቸው ናቸው ። በአሁኑ ጊዜ ዩጎዝላቪያ ሩሜንያ ፣ ሀንጋሪ ፣ ቬትናምና ቻይና ሕዝባዊት ሪፐብሊክ ከድርጅቱ አባላት መካከል ይገኛሉ ።

ሃያ ሰባት ኋላቀር ሀገሮች በጉባኤው ላይ የተካፈሉ ቢሆንም በኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ተፅዕኖ ሥር ስለነበሩ የጉባኤውን ሂደት ለመወሰን ሙሉ ነፃነት አልነበራቸውም ። ቅኝ ግዛት የነበሩት ሌሎች የአፍሪካ ፣ የእስያና የካሪቢያን ሀገሮች ደግሞ በጉባኤው ላይ ጨርሶ ምንም ዓይነት ቦታ አልተሰጣቸውም ነበር ።

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት በ1947 ሥራውን ሲጀምር የአባላቱ ቁጥር 49 እንዲሁም የካፒታሉ መጠን ስምንት ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ያህል ነበር ። በ1981 የአባላቱ ቁጥር ወደ 141 ከፍ ሲል ፣ ከእነዚህ በመዋጮ ያገኘው ገንዘብ ብቻ ድርጅቱ ሥራውን ሲጀምር ከነበረው ካፒታል ጋር ሲነፃፀር በአሥር እጅ ያህል ሊያድግ ችሏል ።

ድርጅቱ ሲቋቋም በጸደቀው ስምምነት ውስጥ ከተዘረዘሩት ዋና ዋና ዓላማዎች መካከል ዓለም አቀፍ የገንዘብ ነክ ስምምነትና የአጭር ጊዜ የውጭ ምንዛሪ ክፍያ እንዲኖር ፣ የዓለም አቀፍ ንግድ እንዲስፋፋና የተመጣጠነ ዕድገት እንዲያሳይ ፣ የውጭ ምንዛሪ ዋጋ መዋዠቅ እንዲገታና አባል ሀገሮች የውጭ ምንዛሪ ችግር ሲያጋጥማቸው ችግሩ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ ከማስከተሉ በፊት መፍትሔ እንዲገኝለት ማድረግ የሚሉ ይገኙበታል ። እነዚህን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላሉ በማለትም ድርጅቱ ሁለት ዓበይት ተግባራትን እንደሚያካሂድ ይገልጻል ። የመጀመሪያው ተግባር የውጭ ምንዛሪ ዋጋንና ክፍያን የሚመለከቱ መመሪያዎችን ማውጣትና የወጡትን መመሪያዎችም አባል ሀገሮች በተግባር መተርጐማቸውን መከታተልና መቆጣጠር ሲሆን ፣ ሁለተኛው

ደግሞ አባል ሀገሮች እነዚህን መመሪያዎች ለመከተል ይችሉ ዘንድ የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ ዕርዳታ መስጠት ነው ።

የኮታ(መዋጮ) መጠን በአባል ሀገሮች መካከል ከፍተኛ ልዩነት ያሳያል ። በ1981 የአሜሪካ ኮታ ከጠቅላላው 21.2% ነበር ። የድርጅቱ አባል የሆኑት 25ቱ የበለጸጉ ካፒታሊስት ሀገሮች በአንድነት ከጠቅላላው ኮታ 65% በመካከላቸው ሲከፋፈሉ ፤ የቀሩት 116 አባል ሀገሮች ድርሻ የተረፈው 35% ነበር ። የድርጅቱ አባላት የሆኑት 48 የአፍሪካ ሀገሮች (ደቡብ አፍሪካን ሳይጨምር) በአንድነት የነበራቸው ድርሻ ከጠቅላላው 7% ብቻ ነበር ። የኢትዮጵያ ድርሻ ከጠቅላላው 0.09% ነበር ። እያንዳንዱ አባል ሀገር በድርጅቱ ውስጥ የሚኖረውን የድምፅ ጥንካሬ የሚወስነው የኮታው መጠን በመሆኑ በገንዘብ ድርጅቱ የገዥዎች ቦርድና የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ ውስጥ ውሳኔ የመስጠቱ ሥልጣን በኢምፔሪያሊስት ሀገሮች እጅ እን ዲገባ አድርጓል ። እጅግ ከፍተኛ ውሳኔ ዎችን በሚመለከት ከጠቅላላው 85% ድምፅ ማግኘት ያስፈልጋል ። ከዚህም በላይ ከጠቅ ላላው ድምፅ ከ20% በላይ ያላት አሜሪካ በተናጠል ወሳኝ ጉዳዮችን በሚመለከት ድም ፅን በድምፅ የመሻር መብት ተሰጥቷታል ።

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ለኢኮ ኖሚ ችግሮች መፍትሔ ይሆናሉ በሚል ሳቢያ ተደራዳሪዎችን የሚያስገባቸው ግዴ ታዎች የተመሠረቱት በቡርዧ ኢኮኖሚ ንድፈ ሐሳቦች ላይ ሲሆን በእነዚህ ንድፈ ሐሳቦች መሠረት የሚወሰዱ እርምጃዎች የኋላ ቀር ሀገሮችን ችግሮች ሊያቃልሉ ይቅርና በቅድሚያ ያንፀባርቃሉ የሚባለውን የበለጸጉ ካፒታሊስት ሀገሮች ሁኔታ እንኳን የማያን ፀባርቁና የእነዚህን ሀገሮች ችግሮች ለመረዳ ትና ለችግሮቹም መፍትሔ ለማስገኘት የማ ያስችሉ መሆናቸው በየጊዜው የሚታይ ነው ። ድርጅቱ የሚያቀርባቸው ሐሳቦች ከመንግሥት ቁጥጥር ነፃ የሆነ ገበያ ለችግሮች ሁሉ መፍ ትሔ ሊያስገኝ ይችላል በሚል አስተሳሰብ ላይ የተመሠረቱ ሲሆን የሀገር ውስጥና የውጭ ካፒታሊስቶች በኢኮኖሚው ውስጥ እንደ ልብ እንዲፈነጩ ለማስቻል የታቀዱ ናቸው ። ከዚህም አመለካከት በመነሣት በአንድ ሀገር ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ የመንግሥት ተሳ ትፎ እንዳይዳብርና እንዲመነምን ለማድረግ ሁልጊዜ ይጥራል ። ድርጅቱ በኋላቀር ሀገሮች ለሰፊው ሕዝብ የሚጠቅሙ መሠረታዊ የሆኑ መዋቅራዊ ለውጦችን ለማምጣት የሚደረጉ ብሔራዊ ጥረቶችን በማፈን ካፒታሊስታዊ ግንኙነት እንዲስፋፋ ያልተቆጠበ ጥረት ያደ ርጋል ። ድርጅቱ የራሱን መመሪያዎች በማስ ፈጸምም በኩል በአባል ሀገሮች መካከል ልዩነት ያደርጋል ። ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች የድርጅቱን መሠረታዊ መርሆች ባፈረሱበት ጊዜ እንኳን አይቶ እንዳላየ ማለፉን ከድር ጅቱ ታሪክ ለመረዳት አያዳግትም ። በአን ፃሩ ደግሞ ሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ በሚከ ተሉ ሀገሮች ላይ በተለይ የውጭ ምንዛሬ ችግራቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ሲገኝ እጅግ አስቸጋሪ ግዴታዎችን በመጫን ስውር የፖለቲካና የርዕዮተዓለም ዓላማዎቹን ተግባ ራዊ ከማድረግ አይመለስም ።

ኋላቀር ሀገሮች በተለይም ኢካፒታ ሊስታዊ የዕድገት ፈርን የሚከተሉት ዲሞ ክራሲያዊ የሆነና እውነትም ዓለም አቀፍ የሆነ አዲስ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ሥርዓት ፤ በአጠቃላይም አዲስ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲመሠረት በየጊዜው ጥያቄ ያቀ ርባሉ ። የዓለም ኢኮኖሚ ሁኔታዎችና ችግ ሮች ድርጅቱ ሲቋቋም ከነበሩት ጋር ሲነፃ ፀሩ ከፍተኛ ልዩነት ያላቸው በመሆኑ ዓለም አቀፍ የገንዘብና የፋይናንስ ጉባኤ እንዲጠራና ከነባራዊ ሁኔታው ጋር የሚጣጣም ሥርዓት እንዲፈጠር ተደጋጋሚ ጥያቄ ማቅረባቸው አልቀረም ። ሆኖም ያለው ሥርዓት ተቀዳሚ ተጠቃሚ የሆኑት ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች እስካሁን ድረስ ጥያቄውን አልተቀበሉትም።

## ዓለም ዲሞክራሲያዊ ወጣቶች ፌደሬሽን (የ—)

*(World Federation of Democratic Youth)*

በፖለቲካ ፣ በሃይማኖት ፣ በዘርና በሀገር ልዩነት ሳያደርግ የዓለም ወጣቶችን የሚያ ሰባስብ የዓለም አቀፍ ዲሞክራሲያዊ የወ ጣቶች ድርጅት ነው ።

ድርጅቱ በ1945 በለንደን በተካሄደው የዓለም ወጣቶች ስብሰባ ላይ ተመሠረተ ። የድርጅቱ ዋና ዓላማዎች ለሰላም መታገል ፣

የወጣቶችን መብት ማስከበር ፣ ለሕዝቦች ነፃነት መታገልና ተራማጅ ወጣቶች በፀረ ኢምፔሪያሊስት ፣ በፀረ ቅኝ አገዛዝ ፣ በፀረ ፋሺስትና በፀረ ዘረኝነት አቋም የትግል አንድነት እንዲመሠርቱ ማድረግ ነው ። ድርጅቱ ከመቶ በላይ ከሆኑ ሀገሮች የተውጣጡ ከ200 የሚበልጡ ማኅበራትን በአባልነት ይዟል ። የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ወጣቶች ማኅበርም (አኢወማ) የዚሁ ድርጅት አባል ነው።

የዓለም ዲሞክራሲያዊ ወጣቶች ፌዴሬሽን የወጣቶችን ችግር ፣ የዓለምን ሰላምና የሕዝቦችን የነፃነት ትግሎች በተመለከቱ የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎችን በመጥራት ውይይት እንዲደረግባቸው ያደርጋል ። ወቅታዊ በሆኑ ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ላይም ኮሚቴዎችን በማቋቋም ለአፍሪካ ፣ ለእስያና ለላቲን አሜሪካ ወጣቶች የመድኃኒት ፣ የባህልና የስፖርት ዕቃዎች እርዳታና የነፃ ትምህርት ዕድልም ይሰጣል ።

የዓለም ዲሞክራሲያዊ ወጣቶች ፌዴሬሽን ከፍተኛ የአመራር አካል የአባል ድርጅቶች ጠቅላላ ስብሰባ ነው ። ከዚሁ ውጭ የድርጅቱን የቀን ተቀን የሥራ እንቅስቃሴ የሚያካሂዱት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውና በርሱም የሚመደበው ጽሕፈት ቤት ናቸው ። የድርጅቱ ዋና ጽሕፈት ቤት የሚገኘው በቡዳፔስት ከተማ ነው ።

## ዓይነት ለውጥ (የ—)
*(Qualitative Change)*

አንድ አካል ወይም ክስተት በውስጡ የሚገኙ ተቃራኒ ኃይላት ትግል የተነሣ የመጠን ለውጥ ሲያደርግ ቆይቶ በእመርታና በቅጽበት አጠቃላይ ለውጥ ለማድረግ ወደ አዲስ ነገር መቀየር ፣ መሠረታዊ ለውጥ ማድረግ ማለት ነው ። የእያንዳንዱ የዓይነት ለውጥ ሂደት (የራሱ መዋቅር) ወደ ከፍተኛውና ወደ ውስብስቡ እንዲሁም ወደ ቀላሉና ወደ ዝቅተኛው ሊሆን ይችላል ።

የዓይነት ለውጥ የመጠን ለውጥ ሂደት ውጤት ሲሆን የሚፈጸመው በእመርታ ብቻ ነው ። ማናቸውም ነገር የዓይነትና የመጠን ቅራኔና አንድነት ያለው በመሆኑ ከመጠን ወደ ዓይነት የሚደረገው ሽግግር የዕድገት ሁለንታዊ ባሕርይ ፣ ዕድገትም ከመጠን ወደ ዓይነት የሚደረገው ሽግግር እንደሆነ ያሳያል ። ዕድገት በሕግ የሚገዛ በመሆኑ ከመጠን ወደ ዓይነት የሚደረገውም ሽግግር እንዲሁ በሕግ የሚገዛ ነው ።

አንድ ነገር ወይም ክስተት አንድ ጊዜ ሙሉ በሙሉ የዓይነት ለውጥ ካሳየ ወደ በፊቱ ዓይነትና መጠን ፈጽሞ ሊመለስ ወይም ሊቀለበስ አይችልም ።

የዓይነት ለውጥ በእመርታና በቅጽበት የሚከናወን ቢሆንም የእመርታውና የቅጽበቱ ባሕርይ ግን እንደሚለወጠው ነገር ባሕርይ የተለያየ ነው ። ኬሚካላዊ ለውጦች እጅግ በጣም ቅጽበታዊ ሲሆኑ ማኅበራዊና ሥነ ሕይወታዊ ለውጦች የሚያሳዩት የዓይነት ለውጥ በእመርታ መሆኑ የግድ ቢሆንም እንደ ኬሚካላዊ ለውጦች ቅጽበታዊ አይደለም ።

የዓይነት ለውጥ ከአንድ ዓይነት ወደ ሌላኛው ዓይነት የሚደረገውን የእመርታ ለውጥ የሚያሳይ በመሆኑ ማቋረጡን ፣ ነገሩ ወይም ክስተቱ በዚያ መልክና ዓይነት ያለው ህልውና ማብቃቱን ያሳያል ። የመጠንና የዓይነት ውህደት መፍረሱን ያመለክታል ።

(የዲያሌክቲከስ ሕጎችን ፣ የመጠን ለውጥን ፣ ከመጠን ወደዓይነት ከዓይነት ወደመጠን ለውጥ ሕግን ይመለከቷል ።)

## ዕውቀት
*(Knowledge)*

የሰው ልጅ የሚኖርበትን አካባቢና የዓለምን ምንነት ፣ የክስተቶችን አመጣጥና ምክንያት የሚረዳበት ዘዴና ችሎታ ነው ። ዐወቀ ማለት ተረዳ ፤ ተገነዘበ ፤ ሲገባው ቻለ ማለት ሲሆን ይህን ውጤት ለማግኘት ነገሮችን በቅርብና በጥልቀት መመልከትን ፣ ማሰላሰልንና ማገናዘብን ይጠይቃል ። ዕውቀት የሌለው ለነገሮች እንግዳ የሆነ ፣ ሁኔታው የተዳፈነበት ሲሆን ዕውቀት የጨበጠ ደግሞ ነገሮች ግልጽ የሆኑለት ፣ ጠልቆ በመግባት ምሥጢራቸውን የተረዳ

ነው ፤ ይህም ማለት ዕውቀት ነገሮች እንደሚመስሉ ወይም መስለው እንደሚቀርቡ መቀበል ሳይሆን እውነተኛና ውስጣዊ ምንነታቸውን መገንዘብ ነው ። ለምሳሌ ፀሐይ ከመሬት ስትታይ አነስተኛ ብትመስልም በምርምር እንደተገኘው ትክክለኛው ሁኔታ ግን ከዚህ የተለየ ነው ። ዕውቀት ሁኔታዎችን እንደሚመስሉ መቀበል ሳይሆን በሚገዙበት ሕግጋት አንፃር የመረዳት ፍላጐት በመሆኑ ነገሮች በእውነት ፣ በትክክል ምን እንደሆኑ የሚገለጸውም በሕግጋት አግካይነት ሲቋጩና ሲዋቀሩ ነው ።

እንደሐሳባዊ ፍልስፍና የዕውቀት ምንጭ የማሰብ ችሎታ ወይም ሐሳብ መሆኑ ይነገራል ። የሰው ልጅ በመንፈሳዊ ፍላጐት በመነሣሣት ባለው የማሰብና የማገናዘብ ችሎታ በቀጥታ የነገሮችን ዕውቀት እንደሚጐናፀፍ ተደርጐ ይቀርባል ። የሚያውቀው ሐሳብ በመሆኑ የሚታወቀውም በግድ ሐሳባዊ ባሕርይ ያለው መሆኑን ለማሳመን ይሞክራል። ማለትም ከዐዋቂው ሐሳብ ውጭ ያለው ሐሳብ ካልሆነ የሁለቱ መዛመድ ፣ አንዱ እንዱን ማወቅ የማይታሰብ ይሆናል በማለት ሐሳባዊ ፍልስፍና ዕውቀት ማለት ሐሳብ ሐሳብን ሲያውቅ ነው ይላል ። የነገሮች እውነትነት መስለው እንደሚታዩት ማለትም እንደተጨባጭነታቸው ሳይሆን በውስጣቸው የሚገኘውን ሐሳብ መጨበጥ ነውና ።

ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ግን የዕውቀት ምንጩ ሐሳብ ሳይሆን ቁስአካል ነው በሚለው ይመራል ። ይህም ማለት የሰው ልጅ የማሰብ ችሎታ አስፈላጊ አይደለም ወይም ዝቅተኛ ሚና ይጫወታል ማለት ሳይሆን ዕውቀት እውነት የሚሆነው (ግላዊ ወይም ኀሊናዊ ብቻ የማይሆነው) ከተጨባጭ ነገሮች ሲመነጭ ብቻ ነው ። የዕውቀትን ምክንያትና ሚና በትክክል ለመረዳት የሚቻለውም ምንጩ ተጨባጩ መሆኑን ስናውቅ ነው ። የሰው ልጅ ፍላጐትና ድርጊት ከቁስአካል የሚመነጭና የተያያዘ በመሆኑ ዕውቀት ለሰው ልጅ ጠቃሚ የሚሆነው ሐሳብን በማወቅ ሳይሆን ስለተጨባጩ ሁኔታ ትክክለኛ ግልባጭ በሐሳባችን ውስጥ ሲቀረፅ ነው ። ሐሳብ የዕውቀት ምንጭ አይደለም ፤ የተጨባጩ ውስጣዊ ግንዛቤ እንጂ ። ሐሳብ የሚያስረዳው ሐሳብን ሳይሆን ከሐሳብ ውጭ ያሉትን ተጨባጭ ሁኔታዎችንና ድርጊቶችን ነው ። ይህም ማለት ዕውቀት በመመልከት ብቻ የሚገኝ ወይም ዝም ብሎ ከሰማይ የሚወርድ ሳይሆን የሰውን ልጅ የሐሳብ ችሎታ ማለትም ማመዛዘንን ፣ መተንተንን ፣ መመራመርን የሚጠይቅ ነው ። ምንጩ ቁስአካል ቢሆንም እንደማንኛውም ድርጊት ዕውቀትም መመሪያ አለበት ። ከተጨባጩ ሁኔታ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ዕውቀት ማኅበራዊ ፣ ታሪካዊና አዳጊ ነው ። ሳለው ስልተ ምርት አመችና አስፈላጊ የሆነው ዕውቀት ይመረታል ፤ ለዚሁ ስልተ ምርትም ይኸው ዕውቀት መልሶ ያገለግላል ።

(ገድፈ ሐሳባዊ ዕውቀትን ፣ ዳሰሳዊ ዕውቀትን፣ አንፃራዊና ፍጹማዊ እውነትን ፣ ጭብጥን ፣ ተግባርን ይመለከቷል ።)

## ዕድገት

*(Development)*

ዕድገት የለውጥ ውጤት በተለይም የዓይነት ለውጥ ፣ ከዝቅተኛው ወደ ከፍተኛው ዓይነት የሚደረግ ሽግግር ማለት ነው ። ከዝቅተኛው ፤ ከቀላሉና ካረጀው የመዋቅር ደረጃ ወደ ከፍተኛው ፣ ወደ ውስብስቡና ወደ አዲሱ የመዋቅር ደረጃ የሚደረግ ለውጥ ነው ።

በማንኛውም አካል ወይም ክስተት ውስጥ ባሉት ተቃራኒ ኃይሎች መካከል በሚካሄደው የማያቋርጥ ትግል ምክንያት የአሮጌው መደምሰስና የአዲሱ መከሰት የማይቀር ነው ። ዲያሌክቲክስ እንደሚያስረዳው ማንኛውም አካል ወይም ክስተት በውስጡ በያዛቸው ተቃራኒዎች ትግል ምክንያት እያንዳንዳቸው እንደየራሳቸው ሁኔታ ለውጥና ትስታቤ ያደርጋሉ ። እነዚህ የተቃራኒነትና የአንድነት ባሕርይ ያላቸው ኃይሎች በትግሉ ሂደትና ውጤት ለውጥ ያስገኛሉ ። ይህም

ዕድገት ሲሆን በተቃራኒዎቹ ትግል ምክንያት የአካሉን ወይም የክስተቱን ከደረጃ ወደ ደረጃ የመተላለፍ ፣ የመጐልመስ ፣ የመበልጸግና የተለያዩ ውስብስብ ባሕርያትን ለማሳየት የመቻል ሁኔታን ያመለክታል ። ዲያሌክቲካዊ ዕድገት በሕግ የሚመራ ነው ። የዕድገት አቅጣጫ ወደፊት እንጂ ወደኋላ ባለመሆኑ ሻሪው ክስተት ወይም አካል ከተሻረው (ከቀደምቱ) አካል ወይም ክስተት የተለየ ይሆናል ። ለምሳሌ ካፒታሊዝም እየዳበረ ሲሄድ በውስጡ ባሉት ተቃራኒ ኃይሎች ማለትም በወዝአደሩና በቡርዧዚው መካከል ትግል ይካሄዳል ። ከጊዜ ወደ ጊዜም ትግላቸው ይበልጥ እየከረረ በመሄድ ወዝአደሩ በቆራጥ ትግሉ የካፒታሊስቱን ኅብረተሰብ የምርት ግንኙነት ያፈራርሳል ። በየጊዜው የተደረጉትም የመጠን ለውጦች ተጠራቅመው እመርታ በማምጣት የዓይነት ለውጥ ያስከትላሉ ። የሚመሠረተው አዲሱ(ሻሪው) የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ከተደመሰሰው ከአሮጌው (ከተሻረዉ) የካፒታሊስት ኅብረተሰብ የተለየ በዕድገት ደረጃው ከፍ ያለ ፣ ከካፒታሊስት ኅብረተሰብ ይበልጥ ውስብስብ የሆነ ነው ።

(የዲያሌክቲክስ ሕግን ይመለከቷል ።)

# ከ

## ከላሽነት

*(Revisionism)*

ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ከሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ ማሻሻል ፣ ማጠናከርና ማጻበር ይገባል በሚል ሽፋን የወዝአደሩን ሳይንሳዊ ርዕዮተዓለም በቡርዧው ርዕዮተዓለም ለመተካት የሚሞክር ንድፈ ሐሳብ ነው ።

ከላሽነት የተከሰተው በ19ኛው ምዕት ዓመት ማብቂያ ላይ ነው ። የክስተቱም መነሻ ከፒታሊዝም ወደኢምፔሪያሊዝም እንዲሸጋገር ምክንያት ከሆኑት ከሳይንስና ከፍልስፍና አስተሳሰቦች ጋር ማርክሲዝም መጣጣም አለበት የሚለው ቀኝ ዘመም እንቅስቃሴ ነበር ። በዚህ ረገድ የተደረገው ሙከራ በእርግጥም ማርክሲዝምን ከዘመኑ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም ለማጻበርና ለማበልጸግ ሳይሆን ንድፈ ሐሳባዊ መሠረቱንና አብዮታዊ ትምህርቱን ለዋውጦ በቡርዧው የፍልስፍናና የኢኮኖሚ ንድፈ ሐሳብ ለመተካት ነበር ።

የከላሽነትን አስተሳሰብ የቀመረውና ያጻበረው የጀርመን ማኅበራዊ ዲሞክራሲንና የሁለተኛውን ኢተርናሽናል አድርባይ ክንፍ ይመራ የነበረው በርንስታይን ነው ። በርንስታይን የሦስቱን የማርክሲዝም ዘርፎች ማለትም የፍልስፍናን ፣ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚንና የሳይንሳዊ ኮሚኒዝምን መሠረተ ሐሳቦች ሽሮ በምትካቸው የቡርዧውን አስተሳሰብ አስፋፋ።

በርንስታይን ፍልስፍናን በማስመልከት ቁስአካላዊ አቋምን በመሻር የካንትን አስተሳሰብ አስፋፍቷል ። በዚህም የከላሽነት አስተሳሰቡ የመደቦችን ትግል በማስመልከት የሰነዘረው ጉልቶ ይታያል ። ኢኮኖሚንም በማስመልከት በርንስታይን ካፒታሊዝም ቀስበቀስ በዕቅድ ወደሚመራው የኢኮኖሚ አደረጃጀት ስለሚያመራ በካፒታልና በሠራተኞች መካከል ያለው መሠረታዊ ቅራኔ እየተዳከመ መሄዱ ስለማይቀር የመደብ ቅራኔም እየጠፋ ይሄዳል ብሏል ። ከዚህ በመነሣት የወዝአደሩ የበላይገዥነት የሚባል ነገር ሊነሣ አይችልም ወደሚለው መደምደሚያ ያመራል።

እንዲያውም በበርንስታይን አስተሳሰብ ካፒታሊዝምና ሶሻሊዝም የኋላ ኋላ ከመጣጣምና ከመዋሃድ ደረጃ ላይ ይደርሳሉ ።

በፖለቲካው መስክም በርንስታይን መንግሥት የአንድ መደብ የመጨቆኛ መሣሪያ ሳይሆን መደብ ግዑዝ አካል ነው ፤ ሠራተኛው ትግሉን አፋፍሞ ሥልጣን ለመያዝ የሚችለው በቡርዧው ፓርላማ ውስጥ በሚያደርገው ተሳትፎ የበላይነትን ሲያገኝ ነው ይላል ።

በሃያኛው ምዕት ዓመት በካፒታሊስቱ ዓለም ላይ በኢኮኖሚውም ሆነ በፖለቲካው ዘርፍ የደረሰው ቀውስ የከላሽነትን አስተሳሰብ ክስረት በግልጽ አሳይቷል ። በተለይም የጥቅምቱ ሶሻሊስት አብዮት ድል አድራጊነት የመደቦች ትግል ውጤት እንደመሆኑ የተፃራሪ መደቦች እርቅ ከቶ ሊኖር እንደማይችል አበክሮ አስገንዝቧል ።

በሃያኛው ምዕት ዓመት የተከሰተው ሁኔታ የበርንስታይንን ተከታዮች ከለሳ ፍሬቢስነት በግልጽ አሳይቷል ። ነገር ግን ከለሳም አብሮ ጠፋ ማለት አይደለም ፤ እንዲያውም ባዲስ መልክ እንደገና ተነሥቷል ። የዚህ ከለሳ እንቀሳቃሽና መሪ ካርል ካውትስኪ ነበር ። እነካርል ካውትስኪ በመሠረቱ ማርክሲዝምን የማይክዱ በመምሰል በዘመኑ ማርክሲዝም ማለትም በሌኒኒዝም ላይ ከፍተኛ ቅዋሚ ነበራቸው ። በተለይም የመጀመሪያውን የሶሻሊስት መንግሥት ያቋቋመውንና የመራውን አዲሱን ዓይነት ሌኒናዊ ፓርቲ በመቃወም የዚህ ፓርቲ አደረጃጀትና የትግል መርህ ኋላቀር ለነበረችው ለሩሲያ ብቻ አግባብነት ያለው እንጂ ሁለንታዊነት ስለሌለው "መናኛ ማርክሲዝም" ነው በማለት የስም ማጥፋት ዘመቻ ጀምረው ነበር ። ሆኖም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የሶሻሊስቱ ጎራ እያበበ ፣ የካፒታሊስቱ ጎራ ደግሞ በሦስተኛው ዙር ቀውስ ውስጥ በመግባቱ የነካርል ካውትስኪ ከለሳ ውድቅ ሆኗል ። ከዚያም በኋላ ይህ አሳሳችና አደገኛ አስተሳሰብ በተለያዩ ገጽታዎች የተ

ከሰተ ሲሆን አሁንም ቢሆን ከላሽነት መልኩንና ታክቲኩን እየለዋወጠ መታየቱ አልቀረም ።

## ከባድ ኢንዱስትሪና ቀላል ኢንዱስትሪ

*(Heavy Industry & Light Industry)*

ከባድ ኢንዱስትሪ ለአንድ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ዕድገትና መስፋፋት የቴክኖሎጂ መሠረት የሆኑት የምርት መገልገያዎች የሚመረቱበት የኢንዱስትሪ ክፍል ነው ። ከባድ ኢንዱስትሪ የብረታ ብረትና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪን ፣ የኃይል ማመንጫ ኢንዱስትሪን ፣ የነዳጅ ዘይት ፣ የጋዝና የከሰል ኢንዱስትሪዎችን ፣ የኮንስትራክሽን ሥራ ዕቃዎች አምራች ድርጅቶችን ፣ የኬሚካልና የፔትሮኬሚካል ኢንዱስትሪዎችን ፣ የወረቀትና ሌሎች መገልገያዎችን የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎችን ያጠቃልላል ።

ቀላል ኢንዱስትሪ በቀጥታ ለፍጆታ የሚሆኑ የምርት ዓይነቶች የሚመረቱበት የኢንዱስትሪ ክፍል ነው ። ቀላል ኢንዱስትሪ ጨርቃጨርቅን ፣ ጫማን ፣ ምግብን ፣ መጠጥንና ሌሎችንም የፍጆታ ዕቃዎች የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎችን ያጠቃልላል ።

ከባድ ኢንዱስትሪና ቀላል ኢንዱስትሪ በመካከላቸውና ከሌሎችም ክፍላተ ኢኮኖሚዎች ጋር የጠበቀና የተወሳሰበ ግንኙነት አላቸው ። ለምሳሌ ከባድ ኢንዱስትሪዎች ለቀላል ኢንዱስትሪዎች የማምረቻ መሣሪያዎችንና ልዩ ልዩ ዕቃዎችን ፣ ለእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ የማምረቻ መሣሪያዎችንና ልዩ ልዩ ኬሚካሎችን ፣ ለትራንስፖርት ክፍለ ኢኮኖሚ ልዩ ልዩ ማጓጓዣዎችን ፣ ለኮንስትራክሽን ክፍለ ኢኮኖሚ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችንና የኮንስትራክሽን ሥራ ዕቃዎችን ያመርታሉ ። ቀላል ኢንዱስትሪዎችም በበኩላቸው ለከባድ ኢንዱስትሪዎች ውስጥና በሌሎችም የኢኮኖሚው ልዩ ልዩ ክፍሎች ውስጥ ተቀጥረው ለሚሠሩ ሠራተኞችና በአጠቃላይ ለሕዝቡ ፍጆታ የሚሆኑ ልዩ ልዩ ዕቃዎችን ያመርታሉ ። ቀላል ኢንዱስትሪዎች የፍጆታ ዕቃዎችን ለማምረትም ከከባድ ኢንዱስትሪዎች የምርት መሣሪያዎችንና ልዩ ልዩ ዕቃዎችን ፣ ከእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ በርካታ ጥሬ ዕቃዎችን ፣ ከሌሎች ክፍላተ ኢኮኖሚም ልዩ ልዩ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ያገኛሉ ።

በአንድ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ውስጥ በከባድ ኢንዱስትሪና በቀላል ኢንዱስትሪ መካከል ያለው ሚዛን ከፍተኛ ትኩረት ይሻል ። ምክንያቱም በምርት ፣ በክምችትና በፍጆታ መካከል ያለውን ሚዛን በመወሰን ረገድ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት በመሆኑ በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮች በአብዛኛው የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴያቸው በቀላል ኢንዱስትሪ ላይ ያተኮረ ነው ። ይህ ሁኔታ በመሠረቱ በቅኝ አገዛዝ ዘመን ሥር የሰደደና አሁንም በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ሥር ከሚደርስባቸው ተፅዕኖ የሚመነጭ ነው ።

የሶሻሊስትን የዕድገት ፈር የሚከተሉ በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮች ለሶሻሊስት ኢኮኖሚ ግንባታ መሠረት ለመጣል ይችሉ ዘንድ ለከባድ ኢንዱስትሪ መስፋፋትና መጠናከር ተገቢውን ትኩረት ለመስጠት ያልተቆጠበ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ ። የኅብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታም ደረጃ በደረጃና ተከታታይነት ባለው መንገድ ማሻሻል ያለባቸው መሆኑን ይገነዘባሉ ። ይህንንም ጣምራ ተግባር ለማካሄድ ከኢምፔሪያሊዝም የብዝበዛ ወጥመድ መላቀቅ ፣ ከሶሻሊስቱ ዓለም ጋር ያለውን ግንኙነት ማጠናከርና ያለውን የሰው ኃይልና ቁሳዊ ሀብት ለኢኮኖሚው ግንባታ በአግባቡ ማዋል የሚያስፈልግ መሆኑ አያጠራጥርም ።

## ከፊል ቅኝ ግዛት

*(Semi–Colony)*

የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ ፣ ፖለቲካና የጦር ኃይል በከፊል በሌላ ሀገር ቁጥጥር ሥር ሲውል ከፊል ቅኝ ግዛት ይባላል ።

## ኩላክ

*(Kulak)*

በ1860ዎቹ ዓመታት ውስጥ የሩሲያ ገጠር ኅብረተሰብ በሦስት የተከፈለ ነበር። እነዚህ ሦስት ክፍሎች ደሀው ገበሬ ፣ መለስተኛው የገጠር ቡርዧዚና ከፍተኛው የመሬት

ከበርቴ ነበሩ ። ከእነዚህ ከሦስት ክፍሎች ሁለተኛው ክፍል ማለትም የመለስተኛው የገጠር ከበርቴ አባላት በሩሲኛ ቋንቋ “ኩላክ” ተብለው ይጠሩ ነበር ። ኩላኮች የመደብ ጠባይ ይዘው ይህ ስም የተሰጣቸው በ1890 አካባቢ ነው ። ኩላኮች በባህልና በአኗኗር ዘዴ ከደሃው ገበሬ እምብዛም የሚለዩ አልነበሩም ። ከድሃው ገበሬ የሚለዩበት ነገር ቢኖር በቡርዧ አመለካከታቸውና መጠነኛ ሀብት የነበራቸው መሆናቸው ነው ።

ኩላኮች አብዛኛው ገበሬ በቅድመ ካፒታሊስት ደረጃ በነበረበት ጊዜ የተሻለ የመሬትም ሆነ የሌላ ንብረት ይዞታ የነበራቸውና በገጠሩ በገበሬው መካከል የካፒታሊስት ጠባዮችን ማንፀባረቅ የጀመሩ ናቸው። ኩላኮች የከበሩት አራጣ በማበደር ፣ የእርሻ ሠራተኞችን ቀጥር በማሠራትና ለሌሎችም አሳልፈው በማከራየት ፣ ሰብሎችን በርካሽ ገዝተው በማከማቸትና ውድ በሚሆኑበት ጊዜ አውጥቶ በከፍተኛ ትርፍ በመሸጥ ፣ መሬት በማከራየት ፣ የገጠር ሆቴሎችንና መጠጥ ቤቶችን በመክፈት ፣ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም ፣ የእርሻ ከብቶችንና አነስተኛ የማምረቻ መሣሪያዎችን ለደሀ ገበሬዎች በጉልበት ሥራ በሚከፈል ዋጋ በማከራየት በአጠቃላይ ደሀ ገበሬዎችን በመበዝበዝ ነበር ።

ኩላኮች በመደብ መልክ የተከሰቱት በ1861 ገደማ ሲሆን በ20ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ላይ በሩሲያ ውስጥ ከነበረው የካፒታሊስት መደብ በቁጥር ከፍተኛውን ክፍል ይዘዋል ። በጊዜው በገጠር ይገኝ ከነበረው የእርሻ መሬት ፣ የእርሻ መሣሪያ እንዲሁም የእርሻና የርቢ ከብት አብዛኛው በኩላኮች እጅ ነበር ። ወደ ገበያ ከሚወጣው ጠቅላላ ሰብል 50% ያህል የሚቀርበው በኩላኮች ነበር ። የቄሣሩ መንግሥትም በገጠሩ ተባባሪና ደጋፊ ኃይል እንዲሆኑት ኩላኮችን ለማጠናከር ከፍተኛ ጥረት አድርርጓል ።

ታላቁ የጥቅምት አብዮት በሩሲያ መቀጣጠሉ ጥቅማቸውን ስለነካባቸው ኩላኮች አጥብቀው ተቃውመውታል ። በሌላ በኩል ደግሞ በ1918 የሶቭዬት መንግሥት የመሬት ከበርቴዎችን ብዝበዛ ለማስወገድ ትግል ያደርግ በነበረበት ወቅት ኩላኮች ከሰፊው ደሀ ገበሬ ጋር የቆመ በመምሰል የመኳንንቱን መሬትና ንብረት በመዝረፍ ለጥቅማቸው አውለዋል ። እንዲያውም አንዳንድ ኩላኮች በቀበሌ የሕዝብ ሸንጎዎች ውስጥ እስከመመረጥ ደርሰው ነበር ። ሶሻሊስት አብዮት በገጠርም እየተጠናከረና እየተስፋፋ በመሄዱ ኩላኮች ፀረ አብዮት አቋማቸውን ይፋ በማድረግ በመላ ሀገሪቱ አመፁ ። የገበሬዎችን መደራጀትና የኅብረት እርሻዎችን መስፋፋት ከመቃወም አልፈው የፓርቲውን አንቂና አደራጆች ገድለዋል ። ሆኖም በገጠር የተቋቋሙት የደሀ ገበሬዎች ኮሚቴዎችና የምግብ አደራጅና አከፋፋይ ቡድኖች ባደረጉት መሥዋዕትነት የተሞላበት ትግል አድኀሪ ዓላማቸውን አከሽፈዋል ። በመጨረሻም የአብዮቱ ድል አድራጊነት ተረጋግጦ የኅብረት እርሻ በገጠሩ በመስፋፋቱና በመጠናከሩ የኩላኮች የመደብ አቋም ተደምስሷል ።

## ኪርከጋርድ ፣ ሰረን

*(Kierkegaard, Sören)*

ከ1813 — 1855 የኖረ ክርስቲያናዊ ህልውናነትን የመሠረተ ሐሳባዊ የዴንማርክ ፈላስፋ ነው ። በደረሳቸው መጻሕፍት (ፊሎዞፊካል ፍራግመንትስ ፣ ኮንክሉዲንግ አንሳይንቲፊክ ፖስትስክሪፕተም ፣ አይዘር ኦር ወዘተ...) ውስጥ የጠራ ህልውና ለመኖር የሚያስፈልገውን አመለካከት በመግለጽ ይህ አመለካከት የክርስቶስን የኑሮ አርአያነት ለመገንዘብ የሚያስችል መሆኑን ለማስረዳት ሞክሯል ።

ኪርከጋርድ የተነሣው የሄግልን ፍልስፍና ለማፍረስ ነበር ። ሄግል ህልውናን በሥነ አመክንዮአዊ ሥርዓት ውስጥ በማስገባቱ የተሳሳተ አመለካከት ፈጥሯል በማለት ህልውና በሥነ አመክንዮ የሚመራ ሳይሆን ዋና መሠረቱ እምነት ነው ሲል ተናግሯል ።

ኪርከጋርድ ህልውናን ከሳይንሳዊ ዕውቀት ውጭ በማድረጉ ብዙ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮችን አፍርቷል ፤ ምክንያቱም ከሄግል ጋር ያነሣው ክርክር በተዘዋዋሪ መንገድ ማርክሳዊ ፍልስፍናን የሚቃረን በመሆኑ ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነትን ለመዋጋት የሚጠቅም መሣሪያ ስለሆነ ነው ።

(ህልውናነትን ይመለከቷል ።)

## ኪነ ጥበብ
*(Art)*

የማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና ክፍል የሆነ ፣ እውነታን በምስል የሚያንፀባርቅና ሰዎች ስለ ዓለም ያላቸውን ሥነ ውበታዊ ግንዛቤ የሚገልጽ ነው ። ሐሳባውያን ኪነ ጥበብን ምድራዊ ፍች ማለትም እውነታን የማንፀባረቅ ጠባይ የለውም በማለት መንፈሳዊና ልቡናዊ ፍች በመስጠት የማስደሰትና የማዝናናት ሚና ብቻ እንዳለው ይናገራሉ ።

ሆኖም የጥንታዊ ኅብረተሰብ ሁኔታ በግልጽ እንደሚያሳየው በሰዎች ታሪክ ውስጥ ኪነ ጥበብ ከሥራ ጋር በቅርብ የተያያዘ ነው ። የኅብረተሰብ ዕድገት በሥራና በኪነ ጥበብ መካከል ክፍፍል የፈጠረ ቢሆንም ኪነ ጥበብ ከሰዎች ኑሮ ጋር ያለውን ግንኙነት ምንጊዜም አላቋረጠም ። የኪነ ጥበብ ብሔራዊ ይዘት ለዚህ ዓይነተኛ ማስረጃ ነው ።

ኪነ ጥበብ የማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና አካል በመሆኑ ከሳይንስ ፣ ከግብረገብ ፣ ከርዕዮተዓለም ወዘተ . . .ጋር ተመሳሳይ ጠባዮች አሉት ፤ እንደነሱም በኅብረተሰቡ የመደብ ሁኔታ የሚወሰን ነው። ከነሱ የሚለየውም እውነታን በተለየ መልክ ማንፀባረቁ ነው ። ኪነ ጥበብ እውነታን የሚያንፀባርቀው በኪነ ጥበባዊ ምስሎች ሲሆን ምስሎቹ የሚገልጹት የሕውስታንና የሥነ አመክንዮን ፣ የጭብጥንና የረቂቅን ፣ የግላዊንና የሁለንታዊን ወዘተ . . . ውህደት ነው ። ለምሳሌ ፍልስፍና ነገሮችን በጽንሰ ሐሳብ ና በንድፈ ሐሳብ አግካይነት የሚገልጽ ሲሆን ኪነ ጥበብ የነገሮችን ግንዛቤ ሕውስታዊ በሆነ መንገድ የሚቀርፅ ነው ።

ኪነጥበባዊ ምስሎች ለልባዌ በመቅረባቸው ውበትን እውን በማድረግ በሰዎች ዘንድ ደስታን ይፈጥራሉ ። አእምሮአዊ ዕድገት ከማስከተላቸውም በላይ በኑሮ ውስጥ ውበት እውን እንዲሆን ከፍተኛ ፍላጐት ይቀሰቅሳሉ ። በዚህ በሥነ ውበታዊ ተግባሩ ኪነ ጥበብ ግንዛቤን የሚያሰፋና ከፍተኛ የሆነ ርዕዮተ ዓለማዊና ትምህርታዊ ሚና የሚጫወት ነው ። ሥነ ጽሑፍ ፣ ሥዕል ፣ ቅርፃቅርጽ ፣ ሙዚቃ ፣ ቲያትርና ሲኒማ ከኪነ ጥበብ ዓይነቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው ።

(ሥነ ውበትን ፣ ላዕላይ መዋቅርን ይመለከቷል።)

## ኬኔ ፣ ፍራንሷ
*(Quesnay, François)*

ከ1694 - 1774 የኖረ የፈረንሳይ ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መሥራች ነው ።

ኪኔ በ1718 ሕክምና ለማጥናት የሚያስችለውን ፈተና ካለፈ በኋላ በ1744 በሕክምና የዶክትሬት ዲግሪውን አግኝቶ የሉዊ 15ኛና የንጉሣውያን ቤተሰቦች ሐኪም በመሆን አገልግሏል ።

ኪኔ አብዛኛውን ጊዜውን የሙያ ሥልጠናው መስክ በሆነው በሕክምና ሥራ ላይ ያሳለፈ ሲሆን የኢኮኖሚ ምርምሮችን ማካሄድ የጀመረው 60 ዓመት ከሞላው በኋላ ነው ።

በአጠቃላይ የፊዚዮክራሲያዊ አስተሳሰብ ተከታዮችና በተለይም የኪኔ ትልቁ አስተዋፅኦ የሀብት ምንጭ የልውውጡ መስክ ሳይሆን የምርት መስክ ነው ማለታቸው ነው ። በኪኔ አስተሳሰብ ለክምችት የሚውለው የተጣራ ምርት ምንጭ ከእርሻው ማለትም ከመሬት የሚገኝ የተፈጥሮ ፀጋ ነው ። "የተፈጥሮ ሥልጣን" የሚል ትርጉም ያለው ፊዚዮክራሲ የሚለው የግሪክ ቃል ለኢኮኖሚ አስተሳሰብ መጠሪያ የሆነውም ለዚህ ነው ። ኪኔ ቁሳዊ ምርት ከሚከናወንባቸው መስኮች ሁሉ የእርሻውን ክፍለ ኢኮኖሚ ብቻ የተጣራ ምርት የሚገኝበት አድርጐ ማየቱ የአስተሳሰቡ መሠረታዊ ድክመት ነው ።

በተጨማሪም እንደካርል ማርክስ አባባል ፊዚዮክራቶችን የዘመናዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መሥራቾች የሚያሰኛቸው ሌላው አስተዋፅኦ በቀጥታ "ካፒታል" የሚለውን ቃል ባይጠቀሙም "የዓመት ወጪ" እና "ቋሚ ወጪ" በማለት በቡርዧው ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ክልል ውስጥ ስለካፒታል ትንተና በማድረግ ግምባር ቀደም መሆናቸውም ጭምር ነው ።

የኪኔ ሌላው ትልቁ አስተዋጽኦ በ1758 ያሳተመው "ታብሉ ኢኮኖሚክ" የተሰኘ መጽሐፉ ነው ። በዚህ መጽሐፉ

ውስጥ ኪኒ ከእርሻ የሚገኘው ተረፈ ምርት ወይንም የተጣራ ምርት በተለያዩ የኅብረተሰቡ መደቦች መካከል እንዴት እንደሚሰራጭና ባጠቃላይ የኢኮኖሚ እርባታ ሂደት እንዴት እንደሚከናወን ለመጀመሪያ ጊዜ ለማሳየት ሞክሯል ። በዚህ ጥረቱም ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ኅብረተሰቡን በሦስት መደቦች ከፍሎ አጥንቷል ። እንደኪኒ የመደብ ትንተና የተጣራ ምርት የሚያስገኘው በእርሻ ሥራ የተሰማራው ክፍል በመሆኑ ገበሬውን "አምራች መደብ" ይለዋል ።የኢንዱስትሪው መስክ የተጣራ ምርት ይገኝበታል ብሎ ስለማያምን የእደጥበብ ባለሙያተኞችን ጨምሮ በዚህ ክፍለ ኢኮኖሚ የተሰማሩትን "መካን መደብ" ሲላቸው ፣ የተጣራ ምርት ተቀባይ የሆኑ ባለመሬቶችን ፣ ካህናትንና የመንግሥት ባለሥልጣኖችን "ተቀራማች መደብ" ይላቸዋል ።

የኪኒ የኢኮኖሚ አስተሳሰብ በጊዜው ከነበረው ሁኔታ አንፃር ሲታይ ተራማጅ አስተሳሰብ ነው ። በተለይም በኢኮኖሚ ፖሊሲ ረገድ ታክስ መጣል ያለበት የተጣራ ምርት ተቀባዮች በሆኑት የተቀራማች መደብ አባሎች ላይ መሆን አለበት የሚለው አስተሳሰቡ ኪኒም ሆነ ፊዚዮክራቶች ባጠቃላይ ፀረ ፊውዳል አቋም የነበራቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው ።

## ካምፓኔላ ፣ ቶማሶ

*(Campanella, Tommaso)*

ከ1568—1639 የኖረ ፣ በኢጣሊያ የነፃነት እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ የነበረ የተምኔታዊ ሶሻሊዝም አራማጅ ነው ። "ሲቲ ኦፍ ዘ ሳን" (የፀሐይ ከተማ) ብሎ በሰየመው ኅብረተሰብ ውስጥ የግል ንብረት ባለመኖሩ ሰዎች የካፒታል ተገዥ ሳይሆኑ በእኩልነትና በደስታ የሚኖሩበትን ሁኔታ አሳይቷል ። ሁሉም ሰው የሚሠራ ሲሆን የሥራ ጊዜ በቀን 4 ሰዓት ብቻ ይሆናል ። የዕረፍት ጊዜያቸውን ሰዎች ለአእምሮአዊና ለአካላዊ ዕድገት ያውሉታል ። የሥራ ፍሬአቸውን በጋራ ማከማቻ ውስጥ ያስቀምጣሉ ፤ የሚፈልጉትንም ከዚያው ይወስዳሉ ። የማኅበረሰቡ መሪ ብዙ ልምድና ዕውቀት ያለው ሳይንቲስት መሆን አለበት ሲል ተናግሯል ። ይህ አስተሳሰብ የሚገልጸው ኅብረተሰብን ግባዊ በሆነ መንገድ ለመምራትና ለመቆጣጠር በሳይንስ መጠቀም የሚቻል መሆኑን መገንዘቡ ነው ።

(ተምኔታዊ ሶሻሊዝምን ይመለከቷል ።)

## ካርቴል

*(Cartel)*

ካርቴል አንድ ዓይነት ምርት የሚያመርቱ ካፒታሊስት ድርጅቶች ገበያን በመካከላቸው በመከፋፈል ፣ የዋጋ ተመን በማውጣትና የሚመረተውን ምርት መጠን በመወሰን ረገድ ኅብረት የሚፈጥሩበት አንድ የሞኖፖል ቅርፅ ነው ። በእነዚህ መስኮች ስምምነት ከተደረሰ በኋላ እያንዳንዱ የካርቴል አባል ከሌሎቹ የካርቴል አባሎች ነፃ በመሆን ለብቻው መጠኑ የተወሰነለትን ምርት ያመርታል I ያመረተውንም ምርት በግሉ ለገበያ ያቀርባል ።

የካርቴል አባል ድርጅቶች በሚያመርቱት ሸቀጥ የመሸጫ ሞኖፖል ዋጋ ላይ ከስምምነት ይደርሳሉ ። ገበያውንም በመካከላቸው ይከፋፈላሉ ። እያንዳንዱ የካርቴል አባል ድርጅት በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ምን ያህል ማምረት እንደሚገባውና ምንስ ያህል ለገበያ ማቅረብ እንደሚኖርበት በስምምነት ይወሰናል ። እንዲሁም የካርቴሉ አባል ድርጅቶች የሥራ ኃይል አቀጣጠርን ፣ አዲስ የአሠራር ዘዴዎችንና ሂደቶችን ፣ የመረጃ ልውውጥን ወዘተ... በሚመለከት ከስምምነት ላይ ይደርሳሉ ።

አምራች ድርጅቶች ካርቴል የሚመሠርቱት በመካከላቸው ይካሄድ የነበረው ውድድር መቀጠል ፍሬ ቢስ ሆኖ ሲያገኙትና ውድድሩን በመቀጠል ከሚገኘው ትርፍ ይልቅ በመካከላቸው እላይ በተገለጹት መስኮች ኅብረት መመሥረት የበለጠ ትርፍ ለመሰብሰብ የሚያስችላቸው መሆኑን በመረዳት ነው ።

(ሞኖፖልን ፣ ሲንዲኬትን ይመለከቷል ።)

## ካርቴዥያኒዝም

*(Cartesianism)*

ዴካርት የተባለው ታላቁ የፈረንሳይ ሒሳባዊ ፈላስፋ የቀመረው ፍልስፍና ነው ።

ይህ ፍልስፍና ከ17ኛው ምዕት ዓመት አንሥቶ በአውሮፓ ውስጥ ከፍተኛ ቦታና ተደማጭነት ነበረው ። ፍልስፍናው ሐሳባዊ ቢሆንም በዘመኑ ተራማጅ የሆነ ሚና ተጫውቷል ።

የካርቴዥያኒዝም መሠረታዊ አስተሳሰብ ሰው ያለው የሐሳብ ችሎታ ተግባራዊ ውጤት እንዲኖረው የሚያስችል የአስተሳሰብ ዘዴ መቀየስ ነው ። ሰው ተፈጥሮን ለመቆጣጠር ሳይንሳዊ የሆነ የአስተሳሰብ ዘዴ እንዲኖረው ያስፈልጋል ። ይህን ሳይንስ ለመመሥረትና ለማሳደግ ፍልስፍና ስለ ሐሳብና ስለ ቁስአካል ልዩነትና ግንኙነት ጥራት ካለውና ግልጽ ከሆነ ንድፈ ሐሳብ ላይ መድረስ ይኖርበታል ፤ ምክንያቱም የሁለቱ ልዩነት በግልጽ የታወቀ ሲሆን ነው የተፈጥሮን ነባራዊ ሕግጋት ለመገንዘብና ለማጥናት የሚቻለው ። ሳይንስ ሊገነባ የሚችለው ነባራዊውና ኅሊናዊው በግልጽ የተለዩ ሲሆኑ ብቻ ነው ። ለምሳሌ ይህ ውሃ ሙቅ ነው ስንል በአባባላችን ውስጥ ነባራዊውና ኅሊናዊው ተለይቶ አልተቀመጠም ። ሙቀት ሕውስታ ነው ፤ ምክንያቱም ሙቀትነቱ ውሃው አራሱ የሚሰማው ሳይሆን በኛ ውስጥ የሚፈጠር ሕውስታ ነው ። ነባራዊው ውሃው ውስጥ የሚገኙት ብናኞች ከፍተኛ እንቅስቃሴ ማድረጋቸው ነው ። የነሱ እንቅስቃሴ ነው ለኛ እንደ ሙቀት የሚሰማን ።

በመሆኑም በውስጡ ምንም ስሜት ሳንጨምር ቁስአካልን ተናክአታዊ በሆነ አመለካከት ብቻ ማየት ይኖርብናል ። ቁስአካል ስፋት ፣ ጥልቀት ፣ ትርዕ ያለው ፣ በቦታና በጊዜ የሚወሰን ፣ በሕዋሳት የሚገለጽ ፣ አራሱን ማንቀሳቀስ ባይችልም ከተገፋ የሚንቀሳቀስ ነገር ነው ። ከዚህ ሌላ በቁስአካል ውስጥ ምንም ነገር የለም ። በሌላ በኩል ሐሳብ አለ ። ሐሳብ የሚጠራጠር ፣ የሚመራመር ፣ የሚገባው ፣ የሚመኝ ፣ የሚሰማው ፣ የሚፈልግ ፣ ራሱን የሚመራና እኔ ማለት የሚችል ነገር ነው ። ይህም ማለት ቁሳዊ ተፈጥሮን ከሕውስታና ከሐሳብ አድራጐት ውጭ አድርገን ማጥናት ይኖርብናል ። ቁስአካል የሚለካ እንጂ በሕውስታ መልክ የምንገነዘበው አይደለም ።ስለዚህም ቁስአካልን በማተማቲክስ አመለካከት ብቻ እንዲታይ በማድረጉ ነው ካርቴዥያኒዝም ለተናክአታዊ የሕውስታ ሳይንስ መመሥረት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገው ።

የካርቴዥያኒዝምን አመጣጥ ስንመለከት የተጫወተውን ተራማጅ ሚና እንረዳለን ። ንድፈ ሐሳቡ በነበረው አዲስ አመለካከት በአውሮፓ የፊውዳል ሥርዓት ውስጥ ሰፍኖ የነበረውን የተምህርትን ፍልስፍና ገርስሶ በመጣል እያቆጠቆጠ ለሚገኘው የቡርዧ መደብ ተስማሚ አመለካከት ፈጥሯል ። ካርቴዥያኒዝም ማንኛውም ቁሳዊ ክስተት የተደበቀ ነፍስ የለውም ፤ እንደማንኛውም ሰው ሠራሽ ማሽን ውስጡ ባሉት ዕቃዎች የእርስበርስ ንክኪት የምንፈታው ነው ማለቱና ዓለምን እንደ አንድ ትልቅና ውስብስብ ማሽን አድርጐ መመልከቱ የሚገልጸው የካፒታሊስትን የምርት ግንኙነት የማሽን ፍላጐት ነው ። በመሆኑም የሰው ሐሳብ ወደ ማሽን ፈጠራ እንዲያመራ አስፈላጊውን አመለካከት ከካርቴዥያኒዝም አግኝቷል ።

የሐሳብንና የቁስአካልን ልዩነት በጥራት ለማስቀመጥ መሞከሩ የካርቴዥያኒዝም ጠንካራ ጐን ሲሆን ለይቶ ማገናኘት አለመቻሉ ግን ዋና ድክመቱ ነው ። ለሐሳብ ብቸኛና የተለየ እውነታ በመስጠቱና ቁስአካልን በእግዚአብሔር የተፈጠረ ነገር በማድረጉ የነበረው ሳይንሳዊ ዓላማ ተዛብቶበታል ። እያቆጠቆጠ የሚገኘው የካፒታሊስት ቁሳዊ ጥቅምና የሥልጣን ፍላጐት ለካርቴዥያኒዝም ውሱንነትና ዝበት ዋና ምክንያት ነው ። ይህም ማለት በአንድ በኩል የሳይንስ መስፋፋት የሚያስገኘው የቴክኖሎጂ ውጤት ለካፒታሊስት የምርት ግንኙነት ዕድገት አስፈላጊ ሲሆን በሌላ በኩል የካፒታሊስቱ መደብ ቀጥታ አምራች ሳይሆን በአእምሮ ሥራ ብቻ የተወሰነ በመሆኑ ለብዝበዛ የሚጠቅመው የምርት መሣሪያዎች ባለቤት መሆኑና ፖለቲካዊ ሥልጣን መፈለጉ ሕጋዊ ወይም ተገቢ ሊሆንለት የሚችለው በሐሳብ የበላይነት ሲተረጐም ብቻ ነበር ። ይህ ሁኔታ ካርቴዥያኒዝም ተቃራኒ የሆኑትን ሳይንስንና ሐሳባዊነትን ሮማስታረቅ ሚና እንዲኖረው በማድረጉ ሐሳብንና ቁስአካልን ለይቶ ከማስቀመጥና ቁስአካልን የሐሳብ ተገዥ ከማድረግ በስተቀር ሌላ ምርጫ የሚሰጠው አልነበረም ። ይህን ትራኔ ተገንዝበው የፍልስፍናው ተከታይ ነን የሚሉት የፈረንሳይ ቁስአካላውያን መከሰትና የካርቴዥያኒዝም ሐሳባዊነት ተስርዞ ተናክ

አታዊ አመለካከቱ ብቻ እንዲቀር መደረጉ በእርግጥ የሚያስረዳን ሐሳባዊነትና ሳይንስ አብረው የማይሄዱ መሆናቸውን ነው ።

(ሁለታዊነትን ፣ ተናከአታዊ ቁለአካልነትን ዴካርትን ይመለከቷል ።)

## ካንቲያኒዝም
*(Kantianism)*

ካንት በተባለው ታላቅ የጀርመን ፈላስፋ የተመሠረተ ሐሳባዊ ፍልስፍና ነው ። ለሐሳባዊ ፍልስፍና አዲስና አመች የመከራከሪያ ነጥቦች ያስገኘና ከምላ ጉድል በይዘቱም ሆነ በቅርፁ ሁሉን ነክ ፍልስፍና በመቅረፁ በጊዜውና በአሁኑም ዘመን ብዙ ተከታዮችን ያፈራ ነው ።

ይህን ፍልስፍና ያመነጨው በሳይንስና በእምነት መካከል እየሰፋ የመጣው መራራቅና ግጭት መፍትሔ ማግኘት አለበት ከሚለው ሐሳብ ነው ። እንደማተማቲክስና እንደ ፊዚክስ የመሳሰሉት ሳይንሶች በጠንካራ መሠረት ላይ በመሆናቸው በየጊዜው እያደጉና ተደማጭነት እያገኙ የሄዱ ሲሆን ከእምነት ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለው ዲበአካል ተብሎ የሚጠራው የዕውቀት ክፍል ግን የሚመረምራቸው ጉዳዮች የእግዚአብሔርን መኖር አለመኖር ፣ የዓለምን መጀመሪያና መጨረሻ ፣ የሰውን ልጅ ነፍስ ዘለዓለማዊነትና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ነው ፤ ሆኖም የሚገኘው ዕውቀት ከሁለንታዊ ስምምነት ላይ ሊያደርስ ካለመቻሉም በላይ በእርስ በርስ ንትርክና ቅራኔ የተነካ ሊያድግ አልቻለም ። የጭቅጭቁን ምንጭና የዲበአካላዊ ዕውቀት አለመሳካት ምክንያት ለማወቅ በመፈለጉ ነው ካንት ስለ ሥነ ዕውቀት ፣ ስለ ሥነ ምግባር ፤ ስለ ውበት ከዚህም ባገኘው ውጤት ላይ ተመርኩዞ ስለታሪክ ፣ ስለኅብረተሰብ ወዘተ... ምርምር ያደረገው ።

ዲበአካላዊ ዕውቀትን ለማግኘት የሚቻል መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ የሚወሰነው የሰው ልጅ ከልምድ ውጭ ሊያውቅ ይችላልን በሚለው ጥያቄ መልስ ነው ። ምክንያቱም እግዚአብሔርን ፣ ነፍስን ፣ የዓለምን መጨረሻ ወዘተ... የሚመለከቱ ጥያቄዎች በሕዋሳት የማንረዳቸውና በልምድ ልናስተውላቸው የማንችል በመሆናቸው መልስ ሊያገኙ የሚችሉት የሰው ልጅ ከልምድ ውጭ ለማወቅ ችሎታ ያለው እንደሆነ ነው ። የካንት አቋም የሰው ልጅ ከልምድ ውጭ ግንዛቤ ሊኖረው አይችልም የሚል ሲሆን ለዚሁም የሚከተሉትን ምክንያቶችና መረጃዎች አቅርቧል ።

የዕውቀት መነሻ የሚሆኑን ከኛ ውጭ ያለውን ሁኔታ የሚገልጹ በሕዋሳት አማካይነት የሚደርሱን መረጃዎች ሲሆኑ እነዚህም መነሻ እንጂ መድረሻ ወይ በቂ ሊሆኑ አይችሉም ። እነዚህን መረጃዎች በቦታ፣ በጊዜና በፈርጅ ለይቶ በሕግ አቀነባብሮ ማለትም ለዕውቀት አዘጋጅቶ የሚያቀርብ ኃይል በኛ ውስጥ በቅድሚያ መኖር አለበት ። እነዚህ ልምድን የሚያቀነባብሩ ዕውቀቶችን ካንት ቅድመ ዕውቀቶች ብሎ ሰይሟቸዋል ። የሕውስታ ቅድመ ዕውቀት ቦታና ጊዜ ሲሆን ግንዛቤ ደግሞ 12 ፈርጆች አሉት (መንሥኤ፣ አንድነት ፣ ሁለንታዊነት ፣ ግንኙነት ፤ ግዴታ ወዘተ...)

ለምሳሌ ሕውስታዊ መረጃዎችን ከኛ ውጭ አድርጉ በስፋት ፣ በቁመትና በጥልቀት ሕግ የሚያስቀምጥልን ቦታ ሲሆን እሱም ከልምድ በፊት በኛ ውስጥ ስለሚገኝ የሕዋሳት ነፃ ቅርፅ ነው ፤ ይህም ማለት ቦታ ኀሊናዊነት እንጂ ነባራዊነት የለውም ። እንዲሁም ጊዜ ነገሮችን ባለፈው ፣ በአሁኑና በመጪው ሕግ ለመደርደር የሚያስችል ነው ። በግንዛቤ ደረጃ ደግሞ መንሥኤን ብንወስድ ለምሳሌ እንፋሎት የሙቀት ተገብሮት ነው ስንል ለሕዋሳት በእርግጥ የተገለጠው መጀመሪያ ሙቀት ፣ ቀጥሎ እንፋሎት ሲሆን እነዚህን ክስተቶች በሕግ እያይዞን እንዱ መንሥኤ ሌላው ተገብሮት ነው ለማለት የሚያበቃን ቅድመ መንሥኤ ግንዛቤ በኛ ውስጥ በመገኘቱ ነው ። በመሆኑም መንሥኤ የሰው ልጅ የአስተሳሰብ ሕግ እንጂ ነባራዊነት የለውም ።

እነዚህ ቅድመ ዕውቀቶች ቅርፅነት እንጂ ይዘትነት ስለሌላቸው የዕውቀት መነሻና መጋቢ ልምድ መሆን ይኖርበታል ። እንደ ካንት አባባል ቅድመ ዕውቀቶች ልምድን የማዋቀር ሚና ብቻ ስላላቸው ከልምድ ውጭ ልንጠቀምባቸው አንችልም ። በእርግጥም ዲበአካል እነዚህን ዕውቀቶች ከልምድ ውጭ ለመጠቀም በመሞከሩ ነው ጭቅጭቅና ቅራኔ ውስጥ ደጋግሞ የሚወድቀው ። ለምሳሌ መንሥኤን ብንወስድ ዓለም

መንሥኤ አለው ወይም የለውም የሚለው
ጥያቄ ከልምድ ውጭ የሚወስደን በመሆኑ
መንሥኤ የሚለው ፈርጅ ሁለት ተቃራኒ
መልሶች ይሰጠዋል ። አንዱ ዓለም መንሥኤ
አለው ሲል ሌላው የለውም በማለት ክርክር
ቢገጥሙም የሁለቱም አቋም በልምድ ሊረጋ
ገጥ ስለማይችል ጥያቄው ሳይንሳዊ መልስ
የለውም ። ካንት በእነዚህ ፈርጆች ከልምድ
ውጭ የመጠቀም ሁኔታ የሚያስከትለውን
ቅራኔና ጭቅጭቅ የቃሉን የጥንታዊ የግሪክ
ፍች በመከተል ፣ ዲያሌክቲክስ ብሎ ሰይሞ
ታል ።

ካንት በሥነ ምግባር ሆነ በውበት
ጥያቄ ላይ ይህንኑ ተመሳሳይ አቋም ማለትም
ኀሊናዊ ሐሳባዊነትን አንፀባርቋል ። ሆኖም
የዲበአካል ዕውቀት ከሰው ልጅ ችሎታ
በላይ ነው ቢልም በሥነ ምግባር በኩል ለእ
ምነት ንድፈ ሐሳባዊ ድጋፍ ለመስጠት ሞከ
ሯል ። ይህም ማንኛውም ነፃ ሥነ ምግባራዊ
ድርጊት በስሜት ወይም በግዴታ ተገፋፍ
ተን የማናደርገው በመሆኑ የሰውን ፍላጎት
ነፃነት የሚገልጽ ነው ። ለምሳሌ አንድ ድሀ
የወደቀ ገንዘብ አግኝቶ ለመውሰድ ቢጓጓም
ከፍርሀት ሳይሆን ገንዘቡን ባይነካ ድርጊቱ
ነፃ የሕግ ማክበርን ፍላጎት ስለሚያሳይ
ፍጹም ነፃ የሆነ ነው ። ጥሩ እንድንሠራ የሚ
ያዘን እራሳችን ውስጥ ያለ ሕግ ደግሞ ፍች
የሚኖረው ሁሌም የመሻሻልና ዘለዓለማዊ
ኑሮን የማግኘት ተስፋ ሲጨመርበት ነው። ዘለ
ዓለማዊ ኑሮ በበኩሉ የእግዚአብሔርን መኖር
ይጠይቃል ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ከሌለ
ሥነ ምግባር በሙሉ ፍች የሌለው የቂል ሥራ
ስለሚሆን ነው ። ሆኖም በካንት አመለካከት
በሥነ ምግባር በኩል የምንደርስባቸው ግንዛ
ቤዎች ሳይንሳዊ አይደሉም ለሥነ ምግባር
አስፈላጊ የሆኑ እምነታዊ መነሻዎች እንጂ ።

የካንት ፍልስፍና በአጠቃላይ መልኩ
ሲታይ ፣ እራሱም ካንት እንደገለጠው ዋና
ፍላጎቱ ፣ ዕውቀትን በመወሰን ለእምነት ቦታ
መስጠት ነው ። ዕውቀት በአጠቃላይ የሚ
ገኘው በኛ ውስጥ በሚገኙ ቅድመ ዕውቀ
ቶች በመሆኑና ታዋቂውን የምናዘጋጀው
እኛው በመሆናችን የምናውቀው የነገሮችን
ክስተቶች እንጂ እራሳቸውን ነገሮችን አይ
ደለም በማለት ለእምነት ቦታ ይሰጣል ።
ዕውቀትን ኀሊናዊና በሰው ልጅ ደረጃ ብቻ
ትክክለኛነት እንዳለው በማድረጉ ነው ካንት
የቁስአካልነትን ፍልስፍና የመቃወሚያ ስልት
የቀረፀው ። በካንት አባባል ቁስአካላዊ ፍልስ
ፍና መንፈሳዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ የሚስ
ነዝራቸው አፍራሽ አስተሳሰቦች ሁሉ ከልም
ድና ክክስተት ስለሚያስወጡትና ሳይንሳዊነት
ስለሌላቸው የቁስአካላውያንም አስተሳሰብ
እንደ ሐሳባውያኑ በእምነት ላይ የተመሠረተ
ነው ። ስለዚህም መንፈሳዊ እምነቶች ለሥነ
ምግባር አስፈላጊ በመሆናቸው በይበልጥ
ሊታመንባቸው ይገባል ።

ካንት ሰው ዲበአካላዊ ዕውቀት ላይ
አይደርስም ማለቱ በአንድ በኩል ዲበአካላ
ውያንን ያስደነገጠ ቢመስልም በሌላ በኩል
ግን እምነታቸውን ካለመንካቱም በላይ ሳይ
ንስ እንዳይደርስበት ዋስትና ሰጥቷቸዋል ።
ሆኖም ሐሳባውያን በተለይም ሄግል መን
ፈሳዊ ጉዳዮች ከሳይንስ ውጭ ተደርገው
ለእምነት ብቻ መተዋቸውን ሊቀበሉ አልፈ
ለጉም ። ይህ በመሆኑ ነው ሄግል በመጀመሪያ
ደረጃ በፍልስፍና ውስጥ የሚታየው ቅራኔና
ጭቅጭቅ ራስ በራስ መሻሻር አለመሆኑን
ለማስረዳት የተነሣው ። ዲያሌክቲክስን ጭቅ
ጭቅ ሳይሆን ዕድገት አድርጎ በመመልከቱ
ነው ሄግል የቅራኔው ሕግ የሰውን ልጅ በመ
ጨረሻ ከፍጹማዊ ዕውቀት ላይ ያደርሰዋል ብሎ
የተናገረው ። ይህ ማለት የካንት ኀሊናዊ ሐሳ
ባዊነት መከሰት ለሄግል ሐሳባዊ ነባራዊ ዲያ
ሌክቲክስ መወለድ አንዱ ምክንያት ሆኗል ።

በመሠረቱም በፍልስፍናው አጠቃላይ
መንፈስ ካንት የገለጠው የቡርዧውን ዓለም
ሁኔታ ነበር ። የፈረንሳይ ቡርዧ አብዮት
መፈንዳት እጅግ ያስደሰተው መሆኑን ካንት
ተናግሯል ። የፈረንሳይ አብዮት ስለ ሰው
ልጅ መብትና ክብር የደነገጋቸው ሕጎች
ሰው የራሱን ሕግ አውጪ እንጂ ተገዥ
እንዳልሆነ የሚገልጽ ነው በማለት ካንት
ነገሩን አስፍቶ በማየት የተፈጥሮንና የዕው
ቀትን ሕጎች ከሰው እንደሚመነጩ ለማስገን
ዘብ ሞክሯል ። ሰው የተፈጥሮ ተማሪ ሳይሆን
ዳኛ ነው ብሎ እራሱ ካንት እንደጻፈው የፍ
ልስፍናው መንፈስ የሚገልጠው ተራማጅ
የነበረውን የቡርዧ ጥቅም ፣ እንቅስቃሴ ፣ ሥል
ጣን ድርጅታዊ መርህ ነው ። ማለትም የገ
ዥው መደብ ሐሳቦች ኅብረተሰቡን የሚያ
ደራጁ ናቸውና ነው ።

ነገር ግን በቡርዧዚው የተደራጀው የሕ
ዝብ ኃይል ተፈጥሮን ለመቆጣጠር የሚያ

ፈስሰው ጉልበት ለአምራቹ ተመላሽ ያለመ ሆኑ ሁኔታ ለካንት ግልጽ ሊሆንለት አልቻ ለም ። ሰው እራሱ ያወጣቸው ሕግጋት መልሶ እራሱን የሚገዙ መሆናቸው ተመልክቶ ሳለ ሰው ተፈጥሮን ለመቆጣጠር የሚችለው በመ ጀመሪያ ደረጃ ኅብረተሰቡን መቆጣጠር ሲችል መሆኑን ባለመረዳቱ ሰው የሥራው ፍሬ ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው ከተፈጥሮ ውጭ ነው በማለት ነገሩን ለእምነት ለመተው ተገዷል ። ዓለምን ከውስጥ ልናውቅ አንች ልም ብሎ መናገሩ የቡርዧው ዓለም ሁኔታ ምሥጢራዊ ስለሆነበት ነው ። በአንድ በኩል ቡርዧዚው ስለሰው መብትና ክብር የደነገጋ ቸው ሕግጋት ተግባራዊ ውጤት እንደሚጠ ብቀው ባለመሆኑ ካንት እምነትን እንዲማ ጠን አድርጎታል ። የቡርዧዚው ቅራኔ ትክክ ለኛ ታሪካዊ ፍች ስላልታየው ዲያሌክቲክስን የቅራኔና የጭቅጭቅ ምንጭ ብቻ በማድረግና የዕውቀትን ድንበር በመወሰን ባላጋራዎችን ወይም ተቃራኒዎችን ለማስታረቅ ሞክሯል ። ቅራኔው በራሱ ሕግ ዐድጎ የራሱን መፍትሔ የሚወልድ ሆኖ ስላልታየው ጭቅጭቁ የትም አያደርስም በማለት ነገሮችን ከቅራኔ አግ ልለን እንድናያቸው የመጣሩ ሁኔታ የሚገ ልጠው የቡርዧዚውን ውስጣዊ ቅራኔ ነው ። በተለይ የቡርዧው መንግሥት በምርት ግን ኙነት ቅራኔ አስገዳጅነት የአስማሚና የአስ ታራቂ ሚና እንዲጫወት የመደረጉን ሁኔታ ስንመለከት ካንት በዲያሌክቲክስ ላይ የወሰ ደው አቋም የአስታራቂነትን መንፈስ የሚያ ንፀባርቅ መሆኑን ልንረዳ እንችላለን ።

(ካንትን ይመለከቷል ።)

## ካንት ፣ እማኑኤል

*(Kant, Immanuel)*

ከ1724—1804 የኖረ ፣ በጀርመን ብሉይ ፍልስፍና ውስጥ ጉልህ ስፍራ የነበረው ፣ ታላቅ ጀርመናዊ ሐሳባዊ ፈላስፋ ነበር ። ካንት በወጣትነት ዘመኑ ላፕላስ ከተባለው ሳይንቲስት ጋር ሰለምድርና በፀሐይ ዙሪያ ስለሚሽከረከሩ ሌሎች ፕላኔቶች አመጣጥ ሳይንሳዊ መላምት የተለመ ሳይንቲስት ነው። በኋለኛ ዘመኑም ዛሬ ካንሺያኒዝም በመባል የሚታወቀውን ሐሳባዊ ፍልስፍና ቀምሯል ።

ከጻፋቸው ዋና ዋና መጻሕፍት መካከል "ክሪቲክ ኦቭ ፒዩር ሪዝን" ፣ "ክሪቲክ ኦቭ ፕራክቲካል ሪዝን" ፣ "ክሪቲክ ኦቭ ጃጅሜንት" ይገኙበታል ።

(ካንሺያኒዝምን ይመለከቷል ።)

## ካዴት

*(Cadet)*

በጥቅምት 1905 የተመሠረተው የዘ ውድ ደጋፊ የሆኑት የለዘብተኛ ቡርዧዚዎች ፓርቲ ሕገ መንግሥታዊ ዲሞክራቲክ ፓርቲ አባል ለሆኑ ሕገ መንግሥታዊ ዲሞክራቶች የተጠስ መጠሪያ ነው ። ካዴቶች ሕገ መንግሥ ታዊ የዘውድ አገዛዝን የጠየቁና የወዝአደሩን የበላይ ገዥነት እስከመጨረሻው የተዋጉ ፀረ አብዮት ኃይሎች ናቸው ።

በ1905 የሩሲያ ቡርዧ ዲሞክራቲክ አብዮት ወቅት ካዴቶች ከቄሳሩ መንግሥት ጋር አብረው አብዮቱን ለመቀልበስ የዶሎቱ ናቸው ። በሕዝቡ ፊት ራሳቸውን "የሕዝ ባዊ ነፃነት" ቡድን በሚል ስያሜ እያቀ ረቡ ቆይተው በኋላ ግን በቄሳሩ መንግሥት በተቋቋመው ዱማ (ሸንጎ) ውስጥ ከተቃ ዋሚ ፓርቲዎች አንዱ ቢሆኑም ለሥልጣን በመቋመጥ በዋና ዋና የውስጥና የውጭ ጉዳዮች ላይ ከአድኃሪው መንግሥትና ከፊ ውዳሎች ጋር ተመሳሳይ አቋም ወስደዋል ። የገበሬውን የመሬት ጥያቄ በሚመለከት መሬት በግል ይዞታነት እንዲቆይ ለማድረግ ገበሬ ውን ከጨቋኝ ፊውዳል ባለመሬቶች ጋር የሚያስታርቅና የባለመሬቶችን ጥቅም የሚ ያስከብር ሕግ ለሸንጐው አቅርበዋል ።

በመጀመሪያው የዓለም ኢምፔሪያሊ ስት ጦርነት ጊዜ የካዴት መሪዎች የቄሳ ሩን መንግሥት የውጭ ወረራ ፖሊሲ ደግፈ ዋል ። ከየካቲት 1917 እስከ ጥቅምት 1917 በነበረው የቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ወቅትም ካዴቶች የጊዜያዊው ቡርዧ መን ግሥት ቀንደኛ አባላት በመሆን የወዝአደ ሩንና የአርሶ አደሩን አብዮታዊ ትግል ተቃውመዋል ። ለፊውዳሎችና ለሞኖፖሊ ስቶች ጥቅም በመቆምም ሩሲያ የኢምፔ ሪያሊስቱን ጦርነት እንድትቀጥል በመገፋፋት ከፍተኛ ፀረ ሕዝብና ፀረ አብዮት ተግባር ፈጽመዋል ። ከጥቅምቱ ሶሻሊስት አብዮት ድል በኋላ ደግሞ የአዲሱ የሶቭዬት ሥልጣን ጠንቀኛ ጠላት በመሆን የውስጥና የውጭ ወራ

ሪዎች ባነሡት የፀረ አብዮት የትጥቅ ትግል ውስጥ በመካፈል አብዮቱን ወግተዋል ።

## ካድሬ
*(Cadre)*

በአጠቃላይ ትርጉሙ ካድሬ በአንድ መንግሥታዊ ተቋም ፣ በፓርቲ ፣ በሙያ ማኅበራትና በሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ በተወሰነ የሥራ መስክ የተመደበ ፣ ለተመደበበትም ሥራ የሠለጠነና ብቁ የሆነ ሠራተኛ ነው ። እንደ ዚሁም በአንድ ሀገር ጦር ኃይሎች ውስጥ በቋሚ ሥራ ላይ የሚገኙት መኰንኖችና የበታች ሹማምንትም ካድሬዎች ተብለው ይጠራሉ ።

የሶሻሊስት ኅብረተሰብ በመገንባት ሂደት የሚያጋጥሙት ዋነኞቹ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች መፍትሔ ሊያገኙ የሚችሉት ካድሬዎችን በትክክለኛ ቦታዎች በመመደብና ችሎታቸውን በጥቅም ላይ በማዋል ነው ። ይህ ሲሆን እያንዳንዱ ሠርቶ አደር ትምህርቱ ፣ የሥራ ልምዱና ግላዊ ችሎታው በሚፈቅድለት መሠረት ለሶሻሊስት ግንባታው ከፍተኛ ድርሻ ሊያበረክት ይችላል ። ሌኒን እንዳስገነዘበው ማንኛውም ፖሊሲ በተግባር ሊገለጽ የሚችለው የፓርቲ ኃይሎችን በትክክል በማሰማራትና በመመደብ ነው ። ዋነኞቹ የፓርቲ ኃይሎች ደግሞ ካድሬዎች ናቸው ። ካድሬዎች የሚገመገሙትና የሚደለደሉትም በፖለቲካዊና በተግባራዊ ችሎታቸው እን ዲሁም በጥሩ ሥነ ምግባራዊ አቋማቸው መሠረት ነው ።

አንድ የኮሚኒስት ፓርቲ ካድሬ ከፍተኛ ብቃትና አርአያነት ይጠበቅበታል ። የኮሚኒስት ፓርቲውን አቋም የሚያጠናክር ፣ ሌሎችን በማስተማርና በመምራት ንቃተ ኅሊናቸውን ከፍ የሚያደርግ ፣ በሥራም ኃላፊነት ከፍ ያለ ድርሻ የሚወስድ ፣ የፓርቲውን የርዕዮተዓለም ጥራት የሚጠብቅ ፣ የፓርቲውን አባሎች በርዕዮተዓለም የሚያጠናክር ፣ ፓርቲው በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት እንዲደራጅ ትክክለኛውን የአመራር መሥመር የሚያሳይ ነው ። አንድ ኮሚኒስት ፓርቲ ይህንን በመሰሉ ብቁ ካድሬዎች አማካይነት ያድጋል ፤ ይደረጃል ፣ ይጠናከራል ። በትግል ተፈትነው ከሚወጡት መካከልም አዳዲስ መሪዎች ያገኛል ።

## ካፒታሊስታዊ የመሬት ኪራይ
*(Capitalist Ground Rent)*

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ባለመሬቶች የእርሻ ወዝአደር ከፈጠረው ተረፈ እሴት የሚወስዱት ድርሻ ካፒታሊስታዊ የመሬት ኪራይ ይባላል ። በእዚህ ሥርዓት ውስጥ በእርሻው መስክ ያሉ የምርት ግንኙነቶች በፊውዳሉ ሥርዓት ውስጥ ከሚገኙት የተለዩ ናቸው ። በፊውዳሉ ሥርዓት ውስጥ የሚገኙት መሠረታዊ የሆኑት የምርት ግንኙነቶች በፊውዳል ባለመሬቶችና በገባሮች መካከል ያሉት ሲሆኑ በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ግን እርሻ ትላልቅ ባለመሬቶችን ፣ ከባለመሬቶች ላይ መሬት የሚከራዩ ካፒታሊስቶችንና የእርሻ ወዝአደሮችን ያጠቃልላል ።

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ባለመሬቱ እራሱ በአብዛኛው በእርሻ ተግባር ላይ አይሰማራም ። በእርሻ ተግባር ላይ ገንዘቡን ለማዋል ለፈለገ ካፒታሊስት መሬቱን ያከራየዋል ። ካፒታሊስቱ የእርሻ ወዝአደሮች ቀጥሮ በማሠራት ተረፈ እሴት እንዲፈጠር ያደርጋል ። በዚህ አኳኋን የተፈጠረውን ተረፈ እሴት ካፒታሊስቱ ከሁለት ይከፍለዋል ። አንደኛውን ክፍል ለራሱ አስቀርቶ ሌላውን ክፍል በመሬት ኪራይ ስም ለባለመሬቱ ይሰጣል ። ካፒታሊስቱ የመሬት ባለቤት ከሆነም የመሬት ኪራይ መክፈል ስለሚቀርለት የተፈጠረውን ተረፈ እሴት በአጠቃላይ ለራሱ ይወስዳል ።

## ካፒታሊስታዊ የሸቀጥ ምርት
*(Capitalist Commodity Production)*

ካፒታሊስታዊ የሸቀጥ ምርት እንደ ቀላል የሸቀጥ ምርት በምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት ላይ የተመሠረተ ከመሆኑም በላይ ከፍተኛው የሸቀጥ ምርት ዓይነት ነው ።

ካፒታሊስታዊ የሸቀጥ ምርት በግል ይዞታ ላይ የተመሠረተ በመሆኑም ዕድገቱ ግብታዊ ነው ። ቀላል የሸቀጥ ምርትንና ካፒታሊስታዊ የሸቀጥ ምርትን የሚያመሳስ

ላቸው ጠባይ የመኖሩን ያህል የሚያለያያቸ ውም ዓይነተኛ የሆነ ጠባይ አለ ። በቀላል የሸቀጥ ምርት ወቅት አምራቹ በራሱ ጉል በትና በራሱ የማምረቻ መሣሪያዎች ምርትን ሲያከናውን ፣ በካፒታሊስታዊ የሸቀጥ ምርት ወቅት ግን ምርት የሚከናወነው በቅጥር የሥራ ኃይል ብዝበዛ ላይ ተመርኩዞ ነው ። እንደ ቀላል የሸቀጥ ምርት ሳይሆን በካፒ ታሊስታዊ የሸቀጥ ምርት ወቅት አምራቹ ከም ርት መገልገያ መሣሪያዎች ባለቤትነት የተ ገለለ ነው ። አምራቹና የምርት መገልገያ መሣሪያዎች ሊቀናጁ ያሚችሉት በሽያ ጭና በግዥ በገበያ ውስጥ በካፒታሊስቱ አማካይነት ነው ። በካፒታሊስታዊው የሸቀጥ ምርት ወቅት ወደ ሸቀጥነት የሚለወጠው የወዝአደሩ የሥራ ውጤት ብቻ ሳይሆን እራሱ የወዝአደሩ የሥራ ኃይል ጭምር ነው ። ስለ ሆነም ካፒታሊስታዊ የሸቀጥ ምርት የሰውን የሥራ ኃይል እንደማናቸውም ሸቀጥ በገበያ ውስጥ የሚሸጥና የሚለውጥ የአመራረት ዘይቤ ነው ።

በባሪያ አሳዳሪውና በፊውዳሉ ሥርዓት የገበሬውና የእደ ጥበብ ሠራተኛው ምርት (የሸቀጥ ምርት) ከእጅ ወደ አፍ የነበረው ኢኮኖሚ ጥገኛና በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ሲሆን በካፒታሊስት ሥርዓት ግን የሸቀጥ ምርት የቁሳዊ ሀብት ምርት ሁለንታዊ መልክ ነው ።

የካፒታሊስታዊ የሸቀጥ ምርት መሠረታዊ ዓላማ ትርፍን ማካበት ሲሆን ፣ የአምራቹም የሥራ ውጤት እንደ አነስተኛ የሸቀጥ ምርት ለአምራቹ ወገን ግልጋሎት የሚውል ሳይሆን ለካፒታሊስቱ መደብ ጥቅም የሚ ውል ነው ። በሶሻሊስት አብዮት አማካይነት ማናቸውም የምርት መገልገያዎች ወደ መን ግሥትና ወደ ኅብረት ይዞታዎች ሲሸጋገሩ የሰው የሥራ ኃይል እንደማናቸውም ሸቀጥ መሸጥና መለወጥ ሲያቆም ካፒታሊስታዊ የሸቀጥ ምርት በታውን ለሶሻሊስታዊ የሸቀጥ ምርት ይለቃል ።

(ቀላል የሸቀጥ ምርትን ፣ ሶሻሊስታዊ የሸ ቀጥ ምርትን ይመለከቷል ።)

## ካፒታሊስታዊ ዱቤ
*(Capitalist Credit)*

የብድር ካፒታልን እንቅስቃሴና የኢን ዱስትሪ ካፒታሊስቶችና የንግድ ካፒታሊ ስቶች በመካከላቸው የሚያካሂዱትን የዱቤ ንግድ ያጠቃልላል ። የዱቤ ንግድ በመተማ መኛ ሰነድ አማካይነት የሚከናወን ነው ። በዚህም ሰነድ ላይ ገዥው ለሻጩ የተወሰነ ገንዘብ በተወሰነ የጊዜ ገደብ እንደሚከፍል ውል የገባ መሆኑን ይገልጻል ።

በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ በባን ኮች አማካይነት የብድር ካፒታል ለካፒታሊ ስቶች ከመቅረቡ የተነሣ በምርት ዘርፍ የተ ሰማሩት ካፒታሊስቶች እርባታውን በተስፋፋ ሁኔታ ያለማቋረጥ ለማከናወን ያስችላቸ ዋል ። የንግድ ካፒታሊስቶችም ሸቀጦቹን ባፋጣኝ እንዲያዟዙሩ ያግዛቸዋል ። በአጠቃ ላይም የካፒታሊስት ባንኮች በባንክ የተቀ መጠውን የቁጠባ ገንዘብ በብድር ካፒታል መልክ በማንቀሳቀስ የካፒታል ክምችታቸ ውን ያሳድጋሉ ።

በሞኖፖል ካፒታሊዝም ወቅት ሞኖፖል ካፒታሊስቶች የሚፈልጉት የብድር ካፒታል መጠን እጅግ ከፍተኛ ነው ፤ ምክንያቱም በዚህ ደረጃ ቋሚ ንብረቶችን የማስፋፋቱ ተግባር ከፍተኛ የብድር ካፒታል ስለሚጠይቅ ነው ። ይህንንም የብድር ካፒታል የሚያቀር ቡት ከፍተኛ የሞኖፖል ባንኮች ናቸው ።

(የብድር ካፒታልን ይመለከቷል ።)

## ካፒታሊስት ሞኖፖሎች
*(Capitalist Monopolies)*

በግለሰቦች ፣ በቡድኖች ወይንም በባለ አክሲዮኖች በባለቤትነት የተያዙ ትላልቅ የኢኮኖሚ ኅብረቶች ካፒታሊስት ሞኖፖሎች ይባላሉ ። እነዚህም የሞኖፖል ዋጋ የመመሥ ረትና የሞኖፖል ትርፍ የማግኘት ዓላማን ተግባራዊ ለማድረግ ኢንዱስትሪዎችን ፣ ገበያዎችንና ከዚያም አልፎ ብሔራዊ ኢኮ ኖሚን በጠቅላላ በቁጥጥራቸው ሥር ያውላሉ።

የሞኖፖሎች ታሪካዊ አመጣጥ ከነፃ ውድድር ካፒታሊዝም ወደ ሞኖፖል ካፒ ታሊዝም ከተደረገ ሽግግር ጋር የተያያዘ ነው ። በትናንሽ ካፒታሊስቶች መካከል የተ ካሄደ ውድድር ካፒታልና ምርት በጥቂት ካፒታሊስቶች ባለቤትነት ሥር እንዲሰባሰብ አደረገ ። በ19ኛው ምዕት ዓመት ሁለተኛ አጋማሽና በ20ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ

ላይ የተከናወኑ ሳይንሳዊና ቴክኒካዊ ግኝቶችና ፈጠራዎች ይህንን የምርት መሰባሰብ ሂደት ለማፋጠን ረድተዋል ። ይህ ሁኔታም ካፒታሊስት አምራች ድርጅቶችን በከፍተኛ ደረጃ ማደራጀትን አስከተለ ። በዚያን ጊዜ በተደረሰበት የቴክኖሎጂ ዕድገት ደረጃ አንድን አምራች ድርጅት ለማቋቋምና ለማካሄድ የሚያስፈልገው ዝቅተኛ የካፒታል መጠን አደገ ። ይህም የካፒታል መጠን ትላልቅ ካፒታሊስቶች በግል ካጠራቀሙት ካፒታል የበለጠ ሆኖ ተገኘ ፣ ይህን ችግር ለመወጣት ካፒታሊስቶች ካፒታላቸውን ማሰባሰብ ወይንም የሌሎችን ግለሰቦች ካፒታል መበደር ነበረባቸው ። ይህም የጋራ አክሲዮን ኩባንያዎች በአፋጣኝ እንዲዳብሩ ረዳ ። የጋራ አክሲዮን ኩባንያዎች ከዚያን በፊት የነበሩ ቢሆንም በሰፊው በሥራ ላይ የዋሉትና ከፍተኛ ሚና መጫወት የጀመሩት የምርት ኃይሎች ከፍተኛ ዕድገት ማሳየት ከጀመሩ በኋላ ነው ። ይህም የካፒታልና የምርት መሰባሰብ ጥቂት ትላልቅ ካፒታሊስት ድርጅቶች በዳበሩ ካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ ቁልፍ ቦታ እንዲይዙ አድርጓል ።

ሞኖፖሎች በመካከላቸው በአለው የውህደት ደረጃ ልዩ ልዩ ቅርፆች አሏቸው ። ዋና ዋናዎቹም ካርቴል ፣ ሲንዲኬት ፣ ትረስትና ኮንሰርን በመባል ይታወቃሉ ።

የአንድን የኢኮኖሚ ድርጅት የሞኖፖልነት ደረጃ ከሚወስኑ ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ፤ ድርጅቱ ከአጠቃላይ የኢንዱስትሪው ውጤት ከፍተኛ ክፍሉን የሚያመርት መሆኑ ፣ ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆነ ሠራተኞች ቀጥሮ ማሠራቱና ከፍተኛ መጠን ባላቸው የምርት መሣሪያዎችና ኃይል መጠቀሙ ናቸው ። በ20ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ላይ የነበሩ ሞኖፖሎች በተወሰኑ ኢንዱስትሪዎች ብቻ በአንዳንድ ካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ ቁልፍ ቦታዎችን ይዘው ነበር ። አሁን ግን ማንኛውም የካፒታሊስቱን ዓለም ክፍለ ኢኮኖሚ በቁጥጥራቸው ሥር እንዲውል አድርገዋል ። በዚያው ልክ የሞኖፖሎች መጠን እያደገ መጥቷል ። በ20ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ላይ በጀርመንና በአሜሪካ አንድ ድርጅት 50 ሠራተኞች ካሉት ትልቅ ይባል ነበር ። አሁን ግን ትልቅ ድርጅት የሚባለው ከ10,000 ሰዎች በላይ ቀጥሮ የሚያሠራ ሆኗል ። ካፒታላቸው በቢሊዮን የሚቆጠር ሞኖፖሎች ቁጥራቸው እያደገ ሄዷል ። በያዝነው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ላይ የዚህን ያህል ካፒታል የነበረው የሞኖፖል ድርጅት ዩናይትድ ስቴትስ ስቲል ብቻ ነበር ። በ1950ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት ይህ ቁጥር ወደ አራት ከፍ አለ ። እነዚህም የአሜሪካው ስታንዳርድ ኦይል (ኤክሶን) ፣ ጄኔራል ሞተርስ ፣ ዩናይትድ ስቴትስ ስቲል እና ሼል ነበሩ ። በ1963 ይህ ቁጥር ወደ 57 ከፍ ሲል በ1974 ደግሞ ወደ 344 ሊያድግ ችሏል ። እነዚህ 344ቱ ሞኖፖሎችም የካፒታሊስት ኩባንያዎች በአጠቃላይ ከሚቀጥሯቸው ሠራተኞች ውስጥ ከሦስት ሁለቱን እጅ የሚይዙና ካፒታላቸውና ትርፋቸውም ከመቶ ሰባ ያህል የሚሆን ነው ።

ሞኖፖሎች የሚቆጣጠሩአቸው የኢኮኖሚ መስኮችም እየበዙ ሄደዋል ። ሞኖፖሎች ከከባድ ኢንዱስትሪ አልፈው ወደ ቀላል ኢንዱስትሪ ፣ ወደ መጓጓዣ ፣ ወደ እርሻና ወደ ንግድ መስኮች ተዛምተዋል ። ለምሳሌ ትላልቅ የገበያ አዳራሾችና ሌሎች የንግድ ድርጅቶች በአሜሪካ ፣ በጃፓንና በብዙ የምዕራብ አውሮፓ ሀገሮች በሀገር ውስጥ ንግድ ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው ይገኛሉ ።

በካፒታሊስቱ ሥርዓት የሞኖፖሎች መዳበር በአንድ በኩል እነዚሁ ትላልቅ ሞኖፖሎች በአላቸው በዕቅድ የመሥራት አዝማሚያ ፣ በሌላ በኩል በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ በአጠቃላይ በሚታየው ሥርዓት አልባ አመራረት መካከል ያለው ቅራኔ እንዲከር ያደርገዋል ። ይህም ቅራኔ በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ሊፈታ አይችልም ። የሞኖፖሎች መደብር ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም ለሚደረግ ሽግግር ቁሳዊ መሠረት መጣል ብቻ ሳይሆን ሽግግሩን የሚረዱ የአሠራር ዘዴዎችንና መዋቅሮችንም ያስገኛል ።

## ካፒታሊዝም

*(Capitalism)*

ካፒታሊዝም ፊውዳሊዝምን ሽሮ የመጣና በፊውዳሊዝምና የኮሚኒስቱ ሥርዓተ ማኅበር የመጀመሪያ ደረጃ በሆነው በሶሻሊዝም መካከል የሚገኝ ሥርዓተ ማኅበር ነው ።

የካፒታሊዝም ዋና መለያ በኢኮኖሚ ውስጥ የሸቀጥና የገንዘብ ግንኙነት የበላይ መሆን ፣ የምርት መገልገያዎች በግል ባለቤትነት መያዝ ፣ የማኅበራዊ ሥራ ክፍፍል መዳበር ፣ የምርት ማኅበራዊነት ማደግ ፣ ሁለንታዊ በሆነ መንገድ የሥራ ኃይል ወደ ሸቀጥነት መለወጥና በምንዳ ሥራ ላይ በተመሠረተ ግንኙነት የወዝአደሩ መደብ በካፒታሊስቱ መደብ መበዝበዝ ናቸው ። የካፒታሊስት ምርት ዋነኛ ዓላማም የወዝአደሩን የሥራ ኃይል በመበዝበዝ ተረፈ እሴት ማስገኘት ነው ።

ካፒታሊዝም ሦስት የዕድገት ደረጃዎችን አልፎአል ። እነዚህም ቀላል የካፒታሊስት የኅብረት አሠራር ፣ የመጀመሪያ ደረጃ የፍብረካ ሥራና የኢንዱስትሪ ወይም የማሽን ምርት ደረጃዎች ናቸው ። ቀላል የካፒታሊስት የኅብረት አሠራር የተባለው በአውሮፓ ውስጥ በተለይም በሆላንድና በእንግሊዝ ከአሥራ ስድስተኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ መከናወን የጀመረ ሲሆን በአንድ ካፒታሊስት ቁጥጥር ሥር በተለያዩ ቦታዎች በዛ ያሉ ሰዎች የተለያዩ የምርት ሥራዎችን የሚያከናውኑበት ሂደት ነው ። ይህ ዓይነት የአመራረት ዘዴ የካፒታሊስት አመራረት ‘‘ሀ’’ ብሎ የጀመረበት ነው ። ለመጀመሪያዎቹ ካፒታሊስቶች የርካሽ ጉልበት ምንጭ ሆኗቸው የነበረው ይህ ሂደት በንብረት ይዞታው ላይ ባስከተለው ለውጥ ብዛት ያላቸው የእደ ጥበብ አምራቾችና ገበሬዎች እየከሰሩ ሄዱ ።

የምርት ኃይሎች ዕድገት በተለይም በ16ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ላይ የታየው ዕድገት ቀላል የካፒታሊስት የኅብረት ሥራ ወደ ፍብረካ ደረጃ እንዲሸጋገር ረዳ ። በዚህ ደረጃ ቀደም ሲል በተለያየ ስፍራ ተነጣጥለው የነበሩት ሸቀጥ አምራቾች በአንድ ቦታ ተሰባስበው እንዲያመርቱ በመደረጉ የሸቀጥ ምርትም እየተስፋፋ ሄደ ። ይሁንና በ18ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ላይ የአንዳንድ የአውሮፓ ሀገሮች የካፒታሊዝም የዕድገት ደረጃ በወቅቱ ከነበረው የካፒታሊዝም የፍብረካ ዕድገት ደረጃና እያደገ ከመጣውም ቴክኒካዊ መሠረት ጋር ሊጣጣም አልቻለም ። ስለዚህም የካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት ፍብረካ ደረጃ ወደ ማሽን አመራረት ማደጉ አስፈላጊ ሆነ ። ይህም ሽግግር በ18ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ላይ በተጀመረው በኢንዱስትሪ አብዮት አማካይነት ተከናወነ ።

የፍብረካ ወይም የማሽን የአመራረት ዘዴ መከሰት ለካፒታሊዝም ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት በመጣል የካፒታሊዝም ስልተ ምርት የበላይነት እንዲጐናፀፍ አስቻለው ። የማሽን አመራረት ከተስፋፋበት ደረጃ ላይ ከመደረሱ በፊትና ወደዚህም ደረጃ ለመድረስ ካፒታሊዝም የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችትን ማከናወን ነበረበት ። የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት በይዘቱ አነስተኛ አምራቾች በብዛት ከምርት መገልገያ ባለቤትነታቸው የተነጠሉበትና የሥራ ኃይላቸውን ለካፒታሊስቶች ለመሸጥ የተገደዱበት ፤ በሌላ በኩል ሀብት በጥቂቶች እጅ የተከማቸበት ሂደት ነው ። በተጨማሪም ቅኝ ግዛቶችን በመበዝበዝ ለካፒታሊዝም መነሻ ሀብት የተካበተበትም የካፒታሊስት ብዝበዛ የዚሁ ሂደት አካል ነው ። ይኸው ሂደት የሥራ ኃይል ወደ ሸቀጥነት ፣ የምርት መገልገያዎች ከሥራ ኃይል ጋር ተቀናጅተው ወደ ካፒታል መለወጣቸውንና የካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት አነስተኛ የሸቀጥን ምርት መተካቱን ያሳያል ።

ካፒታሊዝም በዳበረባቸው ሀገሮች ሁሉ መሠረታዊ የሆኑ የካፒታሊዝም የዕድገት ሕግጋት ተመሳሳዮች ሲሆኑ ፣ በእያንዳንዱ ሀገር የካፒታሊስት ስልተ ምርት አጀማመር ግን እንደ ሀገሩ ታሪካዊና ተጨባጭ ሁኔታ የተለያየ ነው ፤ ማለትም ቀደም ሲል የተጠቀሱት ሦስቱ የካፒታሊስት ዕድገት ደረጃዎች የታዩት በእንግሊዝና በሆላንድ ሲሆን በሌሎች የካፒታሊስት ሀገሮች ግን የካፒታሊዝም ዕድገት የተለያዩ ገጽታዎች ነበሩት ።

ካፒታሊዝም በሁለት ወቅቶች የተከፈለ ነው ፤ አንደኛው ዝቅተኛው የነፃ ውድድር ወቅት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሞኖፖል ካፒታሊዝም (የኢምፔሪያሊዝም) ወቅት ነው። የመጀመሪያው ወቅት ከ16ኛው ምዕት ዓመት እስከ 19ኛው ምዕት ዓመት ፣ ሁለተኛው ከ19ኛው ምዕት ዓመት መጨረሻ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያለው ነው ። በነፃ ውድድር ወቅት በካፒታሊስቶች መካከል ያለው ውድድር ሳይንስና ቴክኖሎጂ እንዲያድግና ካፒታልም በተወሰኑ ማዕከሎች እንዲሰባሰብ በማድረጉ ሞኖፖሎች እንዲፈጠሩ ሁኔታዎችን አመቻቸ ። በዚህ መሠረት

የደረጀው ሞኖፖል ካፒታሊዝም የገንዘብ ካፒታልና የዚህ ባለቤት የሆኑት የፋይናንስ መሳፍንት የበላይነት የሰፈነበት ወቅት ነው ።

ኢምፔሪያሊዝም አሁን በደረሰበት ደረጃ የመንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝምን ቅርፅ እየያዘ መጥቷል ። መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም ከፋይናንስ ቡርዧዚው መንግሥታዊ ቢሮክራሲ ከፍተኛው ክፍል ጋር በጥብቅ የሚተሳሰርበትና የሚዋሃድበት ሁኔታ የተፈጠረበት ነው ።

ካፒታሊዝም በተለያዩ ወቅቶች በነፃ ውድድርና በሞኖፖል ካፒታሊዝም የተከፈለ ቢሆንም እነዚህ ሁሉ የካፒታሊስቱ ሥርዓተ ማኅበር የዕድገት ደረጃዎች እንጂ ከካፒታሊስት ሥርዓት ውጭ ያሉ ወቅቶች አይደሉም ። በነዚህ በካፒታሊዝም የተለያዩ የዕድገት ወቅቶች የአመራረቱ ሁኔታና አቋም ፣ ተረፈ እሴት የማጋበሱ ዘዴ ቢለያይም የካፒታሊስቱ ሥርዓት መሠረታዊና ዓይነተኛ ባሕርያት የሆኑት የሸቀጥ ምርት ፣ የምርት መገልገያዎች በግል ባለቤትነት መያዝ ፣ የሥራ ኃይል በካፒታል መበዝበዝ አይቀየሩም ።

ካፒታሊዝም ፊውዳሊዝምን በመገርሰስ የተከሰተ ሥርዓተ ማኅበር እንደመሆኑ በወቅቱ የተራማጅነት ሚና ተጫውቶ ነበር ። ቅድመ ካፒታሊስት የኢኮኖሚ ግንኙነቶችን በመበጣጠስ በምትኩ የገንዘብ ግንኙነት እንዲስፋፋ ፣ ትላልቅና ዘመናዊ ከተሞች እንዲቆረቆሩ ፣ የፊውዳል የግዛት መከፋፈል በማዕከላዊ አስተዳደር እንዲተካና ብሔራዊ መንግሥታት እንዲቋቋሙ ፣ ከዚያ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የምርት ኃይሎች በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድጉና የምርት ከንዋኔም ማኅበራዊ እንዲሆን አድርጓል ።

ይሁን እንጂ ካፒታሊዝም በውስጡ መሠረታዊ የሆኑ ቅራኔዎችን የያዘ ሥርዓተ ማኅበር ነው ። የሥርዓቱም መሠረታዊ ቅራኔ ማኅበራዊ በሆነ የአመራረት ስልት የሚመረተውንና የሠራተኛው መደብ የሥራ ውጤት የሆነውን ሀብት በግል ከማጋበስ የተነሣ የሚመነጭ ቅራኔ ነው ። ይህም ሁኔታ የምርት ሥርዓት አልባነትን ፣ ሥራ አጥነትንና የኢኮኖሚ ቅራኔን ያስከትላል ። ስለሆነም የካፒታሊዝም መሠረታዊ ቅራኔዎች በየጊዜው እየከረሩ መምጣታቸው የካፒታሊዝምን መዳከምና ሟችነት እንዲሁም ታሪካዊ ውሱንነቱንና በሶሻሊዝም መተካቱ የማይቀር መሆኑን ያበስራል ።

## ካፒታሊዝም የአልተመጣጠነ ዕድገት ሕግ (የ—)

*(Law of Uneven Development of Capitalism)*

በካፒታሊስት ድርጅቶች ፣ በኢንዱስትሪዎችና በካፒታሊስት ሀገሮች መካከል የታየውና የሚታየው ያልተመጣጠነ የኢኮኖሚ ዕድገት ነው ። ያልተመጣጠነ የኢኮኖሚ ዕድገት በቅድመ ሞኖፖል ጊዜም ቢሆን የነበረ ነው ። ሆኖም ካፒታሊዝም ከኢምፔሪያሊዝም የዕድገት ደረጃ ላይ ሲደርስ እመርታዊ የዓይነት ለውጥ አሳየ ። የተለያዩ ካፒታሊስት ሀገሮች ባልተጠበቀ ፍጥነት ማደግ ጀመሩ ። ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ባስገኘው ውጤት በመጠቀም አንዳንድ ዘግይተው የካፒታሊስት ዕድገት የተከተሉ ሀገሮች ተወዳዳሪዎቻቸውን ልቀው እንዲገኙ አስቻላቸው ። በዚህ የካፒታሊስት ዕድገት የመሪነቱን ሚና የያዙ ሀገሮች የተቻላቸውን የጥሬ ሀብት ምንጮች ፣ ገበያዎችና ካፒታላቸውን የሚያውሉበት ክልል ለመያዝ ይሯሯጡ ጀመር ። ሆኖም ቀደም ያሉት ካፒታሊስት ሀገሮች ዓለምን ተከፋፍለው ስለነበረ ይህ ሁኔታ በቀላሉ ሊሳካላቸው አልቻለም ። ዓለምን እንደገና መከፋፈል የሚቻለው በወታደራዊ ኃይል ብቻ ነበር ። ስለዚህም በየሀገሩ የታየው ያልተመጣጠነ የኢኮኖሚ ዕድገት የኢምፔሪያሊስት ጦርነቶችንና ዓለምን እንደገና የመከፋፈልን ሁኔታ አስከተለ ።

የተፅዕኖ ክልል ፣ የጥሬ ሀብት ምንጮችና የካፒታል ልከት ይዞታ ከአዲሱ የኃይል ሚዛን ጋር አለመጣጣም በየጊዜው በኢምፔሪያሊስት ሀገሮች መካከል ያለውን የኃይል ሚዛን መለዋወጥን አስከትሏል ።

ሞኖፖል ካፒታሊዝም በሰፈነበት ወቅት በካፒታሊስት ሀገሮች መካከል ያልተመጣጠነ ዕድገት መታየት የኢምፔሪያሊዝም የግንኙነት ሰንሰለት በላላበት አካባቢ ግንኙነቱ እንዲበጠስና የሶሻሊስት አብዮት መጀመሪያ በጥቂት ሀገሮች ወይንም በአንድ ሀገር ድል እንዲጎናፀፍ የሚያደርግ ተጨባጭ መሠረት ነው ።

ያልተመጣጠነ የፖለቲካ ዕድገት ማለት ደግሞ በሁሉም የካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ

የመደብ ቅራኔዎች በአንድ ዓይነት ደረጃ አለመገኘት ፣ የወዝአደሩ ፖለቲካዊ ንቃተ ኅሊና በሁሉም ሀገሮች በተመሳሳይ መንገድ ዳብሮ አለመገኘት ፣ የወዝአደሩ አብዮታዊ ቆራጥነት ፣ ወዝአደሩ ሰፊውን ሠርቶ አደር ሕዝብ በዙሪያው አሰባስቦ የመምራትና ፣ በአብዮታዊ እንቅስቃሴ ወቅት አብዮቱን የሚመራ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ የግንባር ቀደም መሪነቱን ሚና የመጫወት በሁሉም ሀገሮች በአንድ ጊዜ ነባራዊና ኅሊናዊ ሁኔታዎች በአንድ ጊዜ ተሟልተው አለመገኘት ነው።

የቅራኔዎች መካረር ማለትም የወዝአደሩ አብዮታዊ እንቅስቃሴ መጐልበት በካፒታሊስት ዕድገት ላይ ብቻ የተመረኮዘ አይደለም ። በካፒታሊስት ዕድገት ወደፊት ባልገፉ ሀገሮች ውስጥ የመደብ ትግሉ ይበልጥ የዳበረ ሊሆን ይችላል ። በሩሲያና በሌሎች ሶሻሊስት አብዮት ድል በተጐናፀፈባቸው ሀገሮች የታየው ሁኔታ ይኸው ነው ።

ይሁንና ምንም ያህል የካፒታሊዝም የኢኮኖሚ ቅራኔዎች ቢካረሩና ይህ ቅራኔ ወዲያውኑ የሥርዓት ለውጥ ባያስከትልም ካፒታሊዝም ከመውደቅ የማይቀር መሆኑን ያመለክታል ። ካፒታሊዝም እንዲወድቅ በተለያዩ ሀገሮች በተለያዩ ጊዜያት መሟላት ያለባቸው አብዮታዊ ሁኔታዎች አሉ ። ነባራዊና ኅሊናዊ ሁኔታዎች ሲሟሉ የኢምፔሪያሊዝም የግንኙነት ሰንሰለት በላላበት በኩል አብዮቱ ይፈነዳል ።

## ካፒታሊዝም የኢኮኖሚ ቀውስ (የ–)

*(Economic Crisis of Capitalism)*

በካፒታሊስታዊ የማምረት ሥርዓት "በላጥ" ምርት በመመረቱና ለዚሁ ምርት ተመጣጣኝ የሆነ የመግዛት ኃይል ባለመገኘቱ የሚፈጠረው የኢኮኖሚ ሁኔታ የኢኮኖሚ ቀውስ ይባላል ።

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ሊታረቁ የማይችሉ ቅራኔዎች ይገኛሉ ። የሌሎች ቅራኔዎችና የኢኮኖሚ ቀውስ መሠረት የሆነው ቅራኔም በማምረት ተግባር ማኅበራዊነትና በምርት ክፍፍል ግላዊነት መካከል ያለው ቅራኔ ነው ።

ካፒታሊዝም እየዳበረና የምርት ኃይሎች እያደጉ ሲሄዱ የማምረት ተግባር ይበልጥ ማኅበራዊ እየሆነ ይሄዳል ። የትላልቅ አምራች ድርጅቶች መፈጠር የኅብረተሰቡ የምርት ኃይሎች በጥቂቶቹ እጅ እንዲከማቹ ያደርጋል ። የማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል እየዳበረ መሄድ በአምራች ድርጅቶች መካከል ያለውን ግንኙነት ያስፋፋል ፤ ያጠናክራል ። የተበጣጠሱ የኢኮኖሚ ክፍሎችም ወደአንድ ማኅበራዊ የማምረት ሂደት ይጠቃለላሉ ። ካፒታሊዝም እየዳበረ ሲሄድ ምርት ይበልጡን የሚመረተው ለገበያ ይሆናል ። በአንፃሩ ደግሞ የግልን ፍላጐት በቀጥታ ለማርካት የሚመረት ምርት እየጠፋ ፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ንግድ እያደገ ይሄዳል ። የዓለም ገበያ ይስፋፋል ። ሆኖም የካፒታሊስቱ ሥርዓት እስካለ ድረስ የግል ካፒታሊስቶች ምርትን የራሳቸው ንብረት ማድረጋቸውን ይቀጥላሉ ። በካፒታሊስቱ ሥርዓት ለሚፈጠረው ቅራኔ መሠረቱ ይኸው ነው ።

ይህ በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የሚገኝ መሠረታዊ ቅራኔ ለኢኮኖሚ ቀውስ መሠረታዊ ምክንያት ከመሆኑም በላይ ቀውሱን የሚያባብሱ የሌሎች ቅራኔዎች መንሥኤም ነው ። መሠረታዊ ቅራኔው ከሚያስከትላቸው ሌሎች ዋና ዋና ቅራኔዎች መካከል በእያንዳንዱ አምራች ድርጅት የምርት አደረጃጀትና በአጠቃላይ በኅብረተሰቡ ውስጥ ባለው ሥርዓት አልባ የሆነ የማምረት ተግባር መካከል ያለው ቅራኔ ይገኛል ። ካፒታሊስቱ እያንዳንዱን አምራች ድርጅት የሚያደራጀውና የሚያካሂደው ላንድ ለተወሰነ ዓላማ ማለትም ለትርፍ ነው ። በዚህ መሠረት ካፒታሊስቱ በአንድ አምራች ድርጅት ውስጥ ያሉ ክፍሎችን እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ አስተባብሮ ያካሂዳል ። በካፒታሊስቱ ኅብረተሰብ ደረጃ ግን ምንም ዓይነት በዕቅድ የሚመራ የምርት አደረጃጀት የለም ፤ ሊኖርም አይችልም ። በዚህ ምክንያት የኢኮኖሚው እንቅስቃሴ በአጠቃላይ ሥርዓት አልባ ይሆንና የሚመረተው ሸቀጥ ዓይነትና መጠን ከኅብረተሰቡ ፍላጐት ጋር የማይጣጣም ይሆናል ። በአንዳንድ የኢኮኖሚ ክፍሎች ሸማቾች ከሚፈልጉት በላይ ሲመረት በሌሎች የኢኮኖሚ ክፍሎች ደግሞ ሸማቾች የሚፈልጉትን ያህል አይመረትም ። ይህ አለመጣጣም በተለይ በሚባባስበት ጊዜ የሚመረቱት ሸቀጣ ሸቀጦች በወቅቱ ተሸጠው የማምረቱ ተግባር በተፈለገው ደረጃ እንዳይቀጥል ዕንቅፋት በመሆን የኢኮኖሚ ቀውስ ያስከትላል ።

በካፒታሊስቱ ሥርዓት የኢኮኖሚ ቀውስ ከሚያስከትሉ ዋና ዋና ችግሮች መካከል ያለው ሌላ ቅራኔ በምርትና በፍጆታ መካከል ያለው ነው ። ካፒታሊስቱ ትርፍ የማሳደግ ፍላጎቱን ለማርካት ቴክኖሎጂን ያሻሽላል ፤ አዳዲስና ዘመናዊ የማምረቻ መሣሪያዎችን በሥራ ላይ ያውላል ፤ ተጨማሪ ሠራተኞችን ይቀጥራል ፤ ምርትንም ያሳድጋል ። ነገር ግን የካፒታሊስቱ ዓላማ ትርፍ ማካበት በመሆኑ የወዛደሩ ምንዳ እንዳያድግ ፣ ብዝበዛውም እንዲባባስ ያደርጋል ። የብዝበዛው መባባስና የሠራተኞች መደህየት የኅብረተሰቡ ሸቀጦችን የመግዛት ኃይል ይቀንሰዋል ። ካፒታሊስቱም ምርቱን ለመሸጥ የበለጠ ችግር እየገጠመው ይሄዳል ። ይህም “በዛት” ምርት የኢኮኖሚ ቀውስን ያስከትላል ።

በኢኮኖሚ ቀውስ ምክንያት በተለይ ትናንሽ አምራች ድርጅቶች እየተዳከሙና እየተዘጉ ይሄዳሉ ። በአንፃሩ ደግሞ ጥቂት ካፒታሊስቶች እየተጠናከሩና የኅብረተሰቡን ኢኮኖሚ ይበልጥ በቁጥጥራቸው ሥር እያደረጉ ይመጣሉ ። በኢኮኖሚ ቀውስ ምክንያት የማምረቻ መሣሪያዎች ከሥራ ውጭ ይሆናሉ ። ምርት ከኅብረተሰቡ የማምረት ችሎታ እጅግ ባነሰ መጠን ይመረታል ። ሥራ አጥነት ይስፋፋል ፤ የሰፊው ሕዝብ የኑሮ ደረጃም ያሽቆለቁላል ።

በካፒታሊስቱ ዓለም በተለይ በልዩ ልዩ ኢንዱስትሪዎች በማሽን ማምረት ከተስፋፋበት ጊዜ ጀምሮ የኢኮኖሚ ቀውሶች በየጊዜው ሲፈጠሩ ቆይተዋል ። በተለይ በ1847 ፣ ከ1920—21 ፣ ከ1929—33 ፣ ከ1937—38 ፣ ከ1957—58 እና ከ1974—75 ደርሰው የነበሩት የኢኮኖሚ ቀውሶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ጥፋት በማስከተል ረገድ የሚጠቀሱ ናቸው ። በካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ከሞላ ጎደል በየአሥሩ ዓመት አንድ ጊዜ የኢኮኖሚ ቀውስ እንደሚያጋጥም በጥናት ተደርሶበታል ። ይህ የቀውሶች መደጋገም ካፒታሊስታዊ የማምረት ተግባርን ዑደታዊ አድርጎታል ። ይህ የካፒታሊስቱ ኢኮኖሚ ከአንድ ቀውስ ወደሚቀጥለው ቀውስ የሚያደርገው እንቅስቃሴ የኢንዱስትሪ ዑደት በመባል ይታወቃል ። አንድ የኢንዱስትሪ ዑደት አራት ተከታታይ ደረጃዎች ወይንም ምዕራፎች አሉት ። እነርሱም ቀውስ ፣ ዝቅጠት ፣ ማገገም እና ድራት በመባል ይታወቃሉ ።

ምንም እንኳ ቡርዧ ኢኮኖሚስቶች ካፒታሊስታዊ የኢኮኖሚ ቁጥጥር በማድረግ የኢኮኖሚ ቀውሶችን ከካፒታሊስት ኅብረተሰብ ለማስቀረት ይቻላል ብለው ቢለፍፉም ሐቁ ግን ካፒታሊዝም የኢኮኖሚ ቀውስ የተጠናወተው መሆኑን መቀጠሉ ነው ። የካፒታሊስቱን ሥርዓት መሠረታዊ ቅራኔዎች ለመፍታት ፣ በየጊዜው የሚፈጠሩ የኢኮኖሚ ቀውሶች እንዳይፈጠሩ ለማድረግና የኅብረተሰቡን የምርት ኃይሎች ያለገደብ በማሳደግ የሕዝቡን ፍላጎት በአስተማማኝ ለማርካት የሚቻለው በዕቅድ የሚመራ የሶሻሊስት ሥርዓት በመመሥረት መሆኑ ግልጽ ነው ።

(ቀውስን ፣ ማገገምን ፣ ዝቅጠትን ፣ ድራትን ይመልከቱ።)

## ካፒታል
*(Capital)*

የተካበተ ወይም የተጠራቀመ ትርፍ እሴት ወይም እሴትን የሚወልድ እሴት ነው ። በሌላም አገላለጽ ካፒታል ካፒታሊስቶች በቅጥር የሥራ ኃይል ላይ የሚያካሂዱትን ብዝበዛ የሚገልጽ የኢኮኖሚ ፈርጅ ነው ።

ካርል ማርክስ ካፒታል ቁሳዊ ነገር ሳይሆን ይልቁንም በአንድ በተወሰነ የኅብረተሰብ ታሪክ ወቅት የሚከሰት የተወሰነ ማኅበራዊ የምርት ግንኙነት ሲሆን ይህም ግንኙነት የተለየ ማኅበራዊ ባሕርይ በሚሰጠው ቁሳዊ መልክ የሚገለጽ መሆኑን አብራርቷል ።

በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ካፒታል የሚገለጽባቸው ቁሳዊ ገጽታዎች ቅጥር የሥራ ኃይል ፣ የምርት መገልገያዎችና ገንዘብ ናቸው ። እነዚህ ሁሉ በአንድ ወቅት በአንድ ላይ ተሰባስበው እስካልተገኙ ድረስ የቡርዧ ፖለቲካል ኢኮኖሚ እንደሚያቀርበው በተናጠል የካፒታል ቁሳዊ መገለጫ ሆነው ሊያገለግሉ አይችሉም ። እነዚህ ዓይነቶች ተቀናጅ

ተው ሲንቀሳቀሱ ሸቀጥ ይመረታል ። በዚሁ ሂደት ውስጥ የወዝአደሩ የሥራ ኃይል ተረፈ እሴትን ይፈጥራል ።

ካፒታል ህልውና ያገኘው የሸቀጥ ምርት ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ በደረሰበትና የሥራ ኃይል ሸቀጥ በሆነበት ወቅት ነው ። ለካፒታል መከሰት ሁለት መሠረታዊ ነገሮች በቅድሚያ መሟላት ነበረባቸው ። እነሱም 1ኛ/ የምርት መገልገያዎች ተሰበቀሰ በጥቂቶቹ እጅ መከማቸት ፤ 2ኛ/ በዚህም ምክንያት የምርት መገልገያ ባለቤትነታቸውን ያጡ ሰዎች ለመኖር ሲሉ የሥራ ኃይላቸውን ለመሸጥ መገደዳቸው ነበር ። ይህም የሆነው የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት እየተባለ በሚታወቀው ታሪካዊ ወቅት ነበር ።

በካፒታሊስት ሂደተ ምርት ካፒታሊስቱ በገበያ ውስጥ የገዛቸውን የሥራ ኃይልና የምርት መገልገያዎች አቀናጅቶ ምርት እንዲመረት ያደርጋል ። የተመረተውንም አዲስ ሸቀጥ በገበያ ውስጥ ከሸጠ በኋላ ካፒታሊስቱ ሸቀጡን ለማስመረት ካወጣው ሙሉ ንዋይ በላይ ተጨማሪ ገንዘብ በእሴት መልክ ያገኛል ። ይህን በአጠቃላይ የካፒታል ቀመር ማርክስ ገ—ሸ—ገ[1] ብሎታል ። ካፒታሊስቱ መጨረሻ ላይ ያገኘው ገንዘብ ምርቱን ለማስመረት ካወጣው ገንዘብ ከፍ ያለ ነው ። ይህ ካፒታሊስቱ ሸቀጡን ለማስመረት ካወጣው ወጪ በላይ ሸቀጡን ሲሸጥ የሚያገኘው ገንዘብ ተረፈ እሴት በመባል የሚታወቅ ሲሆን ይህም በምርት ሂደት ውስጥ ወዝአደሩ የሥራ ኃይሉን እሴት ከሸፈነ በኋላ ባልተከፈለው የሥራ ጊዜ የሚያስገኘው ነው ። ካፒታሊስቱ ወዝአደሩ የፈጠረውን ተረፈ እሴት ይመዘብራል ፤ ለፍጆታው የሚያስፈልገውን ካነሣ በኋላ የቀረውን በገንዘብ መልክ ያገኘውን ተረፈ እሴት ተጨማሪ የምርት መገልገያዎችን በመግዛትና ተጨማሪ የሥራ ኃይል በመቅጠር ወይም የተሻሻሉ ማሽኖችን ሥራ ላይ በማዋል ወደ ካፒታል ይለውጠዋል ። በመሆኑም ካፒታል የሚያድገውና የሚዳብረው የወዝአደሩ የሥራ ኃይል የሚፈጥረውን ተረፈ እሴት በማካበት ነው ።

ያለወዝአደሩ የሥራ ኃይል ብዝበዛ ካፒታል የሚባል ነገር ሊከሰት አይችልም ። ካፒታል የቅጥር ሥራ መኖርን እንደሚጠይቅ ሁሉ ፤ ቅጥር ሥራም የካፒታልን መኖር ይጠይቃል ። ቅጥር የሥራ ኃይል ደግሞ በሥርዓተ ማኅበራት የዕድገት ታሪክ ሁለንታዊ በሆነ መንገድ ሊሰፍን የቻለው በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ብቻ ነው ።

ተረፈ እሴትን ማስመረትና በግል ማጋበስ የካፒታሊስት ምርት ዋነኛ ዓላማ ሲሆን በኢምፔሪያሊዝም የዕድገት ደረጃ ደግሞ የሞኖፖል ትርፍን ማጋበስ የካፒታሊስት ምርት ዋንኛ አንቀሳቃሽ ኃይል ነው ።

ካፒታሊስቶች ሁልጊዜም ከፍተኛ ትርፍ ለማግኘት ባላቸው ፍላጐት የተወሰነውን የተረፈ እሴት ክፍል ለክምችት ስለሚገደዱ ይህ ሁኔታ ወደ ካፒታል መበባበብና መማከል ማለትም ወደ ካፒታሊስት ሞኖፖሎች መፈጠር ያመራል ። በዚህም ሂደት የነፃ ውድድር ካፒታሊዝም ወደ ሞኖፖል ካፒታሊዝም ያድጋል ።

ማርክስ በካፒታልና በተረፈ እሴት ላይ ያደረገው ትንተና የማርክሳዊ ሌኒናዊ ካፒታሊስት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መሠረት ነው ። ሌኒን ማርክሳዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን በማዳበርና በኢምፔሪያሊዝም ወቅት የካፒታልን እንቅስቃሴ በማጤን ፋይናንስ ካፒታል የተባለውን ታዋቂ የሆነውን የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ፈርጅ ለመጀመሪያ ጊዜ አስተዋውቋል ።

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የምርት መገልገያዎች የሕዝብ ሀብት ስለሆኑ የማምረቻ መሣሪያዎች ፤ ገንዘብም ሆነ የሥራ ኃይል ወደ ካፒታልነት ሊለወጡ አይችሉም።

(ተረፈ እሴትን ፤ ጸሚ ካፒታልን ፤ ተለዋዋጭ ካፒታልን ፤ ነባር ካፒታልን ፤ ተዘዋዋሪ ካፒታልን ይመለከቷል ።)

## ካፒታል መማከል (የ—)
*(Centralization of Capital)*

ቀደም ሲል የነበረውን የግለሰቦች ካፒታል በጥቂት ካፒታሊስቶች እጅ የማካበት ሂደት ነው ። ይህ ሂደት በሁለት መንገዶች

ይከናወናል ። አንደኛው በካፒታሊስቶች መካከል በሚደረግ ውድድር ሳቢያ የአነስተኛ ካፒታሊስቶች መክሰርና የካፒታል በጥቂት ጠንካራ ካፒታሊስቶች እጅ መካበት ሲሆን ፤ ሁለተኛው ደግሞ ቡርዧዚዎች በጋራ አክሲዮን ማኅበር ወይም ኮርፖሬሽን አማካይነት ካፒታላቸውን ማዋሃዳቸው ነው ።

የካፒታል መግከል ቀደም ሲል በርከት ባሉ ቡርዧዚዎች እጅ የነበረው ካፒታል በጥቂቶች እጅ መካበት ስለሆነ ድርጊቱ ወዲያውኑ የማኅበራዊ ካፒታል ዕድገት አያስገኝም ። ይሁንና የካፒታል መግከል የምርት መሰባሰብን ስለሚያስከትልና ይህም ልዩ ልዩ ጥቅሞችን ስለሚያስገኝ የተረፈ እሴትን መጣኔ ከፍ በማድረግ ለካፒታል ክምችት አመች ሁኔታዎችን ይፈጥራል ። በመሆኑም የካፒታል መግከልና የካፒታል መሰባሰብ ሂደቶች በቅርብ የተያያዙና የተደጋገፉ ሲሆኑ በመካከላቸው ያለው ልዩነት የካፒታል መግከል ካፒታል በጥቂቶች እጅ በመካበት የሚፈጠር ሲሆን የካፒታል መሰባሰብ ግን በተረፈ እሴት ክምችት የሚመጣ መሆኑ ነው ።

የካፒታል መግከል ሂደት የምርት መሰባሰብን የሚያስከትል በመሆኑ የማምረት ተግባር በጥቂት ትላልቅ ተቋሞች ውስጥ እየተሰባሰበ ይሄዳል ። የካፒታሊዝም ከፍተኛው የዕድገት ደረጃ የሆነው የኢምፔሪያሊዝም አንዱ የኢኮኖሚ ባሕርይም በካፒታል መሰባሰብና መግከል ሳቢያ ጥቂት ሞኖፖሎች በምርቱም ሆነ በዝውውሩ መስክ የበላይነት ያገኙ መሆናቸው ነው ። የካፒታል መግከል ሂደት አፍኝ የማይሞሉ ትላልቅ ሞኖፖሊስቶች በመላው ወዝአደር ላይ የሚያካሂዱትን ብዝበዛ እያጠናከሩ እንዲሄዱ ስለሚያደርግ በካፒታሊዝም ውስጥ በቡርዧውና በወዝአደሩ መደቦች መካከል ያለው ቅራኔ እንዲባባስና የመደብ ትግሉም እየተካረረ እንዲሄድ ያደርጋል ።

(የካፒታል መሰባሰብን ይመለከቷል ።)

## ካፒታል መሰባሰብ (የ—)
*(Concentration of Capital)*

ግለሰብ ካፒታሊስቶች የበዘበዙትን ተረፈ እሴት በማከማቸት ካፒታላቸውን የሚያጠናክሩበት ሂደት የካፒታል መሰባሰብ ይባላል ። በካፒታል መሰባሰብ ሳቢያ የግለሰቦች ካፒታል እያደገ መሄድ ጠቅላላው ማኅበራዊ ካፒታል እንዲያድግ ያደርጋል ።

ትላልቅ የማምረቻ ድርጅቶች ከትናንሾቹ ጋር ሲነፃፀሩ አመች ሁኔታ ስላላቸው የካፒታል መሰባሰብ የካፒታል ክምችትን ሂደት ያፋጥናል ። የካፒታል መሰባሰብ ፍጥነት መጨመር ደግሞ የትናንሽ የማምረቻ ድርጅት ባለቤቶችን ክስረትና በሌላ መጥፋት እያባባሰው ስለሚሄድ የካፒታል መግከልን ያስከትላል ። እንዲሁም የካፒታል መግከል የካፒታል ክምችት ሂደትን በማፋጠን የካፒታል መሰባሰብን ያስከትላል ። በመሆኑም የካፒታል መሰባሰብና መግከል ሂደቶች እርስ በርሳቸው የተያያዙና የተደጋገፉ ናቸው ።

የካፒታል መሰባሰብ ሂደት በሚከተሉት ሦስት ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ነው ። እነርሱም ፤

1. ባንድ በተወሰነ ወቅት ያለው የቴክኖሎጂ ደረጃና የተረፈ እሴት መጣኔ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚገኘው ጠቅላላ ተረፈ እሴት መጠን የሚወሰነው በካፒታሉ መጠን ላይ መሆኑ ፤
2. በቴክኖሎጂ ዕድገት ሳቢያ የተወሰነ የካፒታሊስት የማምረቻ ተቋምን ለማካሄድ የሚያስፈልገው ዝቅተኛ የካፒታል መጠን እያደገ መምጣቱ ፤
3. በቡርዧዚዎች መካከል ያለው ውድድር እየተባባሰ መሄዱና የትርፍ መጣኔ የማሽቆልቆል ዝንባሌ ስላለው ይህንን ሁኔታ ለማካካስ የካፒታል ክምችትን ማሳደግ ማስፈለጉ ናቸው ።

የካፒታል መሰባሰብ ሂደት ከምርት መሰባሰብ ጋር በቅርብ የተቆራኘ ነው ። የካፒታል መሰባሰብ በተደረገ መጠን የማምረት ተግባር በጥቂት ትላልቅ የማምረቻ

ተቋሞች ውስጥ እየተሰባሰበ ይሄዳል ። የካፒታሊዝም ከፍተኛው የዕድገት ደረጃ የሆነው የኢምፔሪያሊዝም አንደኛው የኢኮኖሚ ባሕርይ በካፒታል መሰባሰብና መማከል ሳቢያ ጥቂት ሞኖፖሎች በምርቱም ሆነ በዝውውሩ መስክ የበላይነት ያገኙ መሆናቸው ነው ።

የካፒታል መሰባሰብ ሂደት እፍኝ የማይሞሉ ትላልቅ ሞኖፖሊስቶች በመላው ወዝአደር ላይ የሚያካሂዱትን ብዝበዛ እየጠነከሩ እንዲሄዱ ስለሚያደርግ በካፒታሊዝም ውስጥ በቡርዧው መደብና በወዝአደሩ መደብ መካከል ያለው ቅራኔ እንዲባባስና የመደብ ትግሉም እየተካረረ እንዲሄድ ያደርጋል ።

(የካፒታል መማከልን ፣ የተስፋፋ እርባታን ይመለከቷል ።)

## ካፒታል መገላበጥ (የ—)
*(Turn-Over of Capital)*

ሥራ ላይ የዋለው ካፒታል ዝውውር እንደ አንድ ነጠላ ክንዋኔ ሳይሆን እንደ ተከታታይ የእድሳትና የድግግሞሽ ሂደት ሲታይ የካፒታል መገላበጥ ይባላል ። በእርባታ ሂደት ካፒታል በምርትና በዝውውር መስኮች ውስጥ ያልፋል ። በዚሁ እንቅስቃሴውም ውስጥ የተለያዩ መልኮች ይኖሩታል ።

በዚህ መሠረት በቅድሚያ ከገንዘብ ካፒታልነት ወደ ምርት ካፒታልነት፣ ከምርት ካፒታልነት ወደ ሸቀጥ ካፒታልነት ፣ በመጨረሻም ወደ ቀድሞ መልኩ ወደ ገንዘብ ካፒታልነት ይለወጣል ። ካፒታል መጀመሪያ ሥራ ላይ ከዋለበት የገንዘብ መልክ ተነሥቶ የተለያዩ መልኮችን ይዞ በኋላ እንደገና ወደ ገንዘብ መልክ ለመመለስ የሚወስድበት ጊዜ የካፒታል መገላበጫ ጊዜ ይባላል ።

የምርትና የዝውውር ሁኔታዎች ከምርት ምርት ስለሚለያዩ የካፒታል መገላበጫ ጊዜ እንደዚሁ የተለያየ ነው ። ለምሳሌ እንደ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ያሉ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን ሠርቶ ካፒታልን በአንድ የመገላበጥ ሂደት ውስጥ ለማሳለፍ በዓመታት ሊቆጠር የሚችል ረጅም ጊዜ የሚወስድ ሲሆን አንዳንድ ቀላልና ትናንሽ ኢንዱስትሪዎችን በሚመለከት ግን የካፒታል መገላበጫ ጊዜ በጥቂት ሳምንታት ወይንም ወራት የሚለካ ይሆናል ።

ልዩ ልዩ የካፒታል ክፍሎችን በመገላበጥ ጊዜ አንፃር ለማወዳደር የአንድ ዓመት ጊዜ ወሰን መጠቀም የተለመደ ነው ። ለምሳሌ አንድ የካፒታል ክፍል አንድን የመገላበጥ ጊዜ በሦስት ወራት ቢያጠናቅቅ በአንድ ዓመት ውስጥ አራት የመገላበጫ ጊዜያትን ያጠናቅቃል ። ሌላ የካፒታል ክፍል ደግሞ አንድን የመገላበጥ ጊዜ በ24 ወራት ቢያጠናቅቅ በአንድ ዓመት ግማሽ የመገላበጥ ጊዜን ያጠናቅቃል ። በዚህ አኳኋን የመጀመሪያው የካፒታል ክፍል ከሁለተኛው የካፒታል ክፍል ጋር ሲነፃፀር በስምንት እጅ በሚበልጥ ፍጥነት ይገላበጣል ።

በካፒታል መገላበጥ ሂደት ውስጥ ሁሉም የምርት ካፒታል ክፍሎች ተመሳሳይ የመገላበጥ ፍጥነት የላቸውም ። በመሆኑም የተለያዩ የካፒታል ክፍሎች በተረፈ እሴት ምርት ውስጥ ባላቸው ሚና ሳይሆን በካፒታል መገላበጥ ሂደት ውስጥ በሚኖራቸው የተለያየ ባሕርይ ነባርና ተዘዋዋሪ ካፒታል ተብለው በሁለት ይከፈላሉ ። በዚሁ መሠረት በነባር ካፒታል ውስጥ እንደ ሕንፃ ፣ እንደ ማሽነሪዎች የመሳሰሉት እሴታቸውን ባንድ ጊዜ ሳይሆን ቀስ በቀስ አዲስ ወደ ተመረቱት ሸቀጦች እንደሚያስተላልፉ ሆነው ሊጠቃለሉ ፣ በተዘዋዋሪ ካፒታል ሥር ደግሞ እንደ ኃይል ፣ እንደ ጥሬ ዕቃ የመሳሰሉት ባንድ ጊዜ ምርት እሴታቸውን ሙሉ በሙሉ አዲስ ወደተመረቱ ሸቀጦች የሚያስተላልፉት ይገኙበታል ።

## ካፒታል ክምችት (የ—)
*(Accumulation of Capital)*

በተስፋፋ የካፒታሊስት እርባታ ወቅት የተረፈ እሴት ወደ ካፒታል መለወጥ የካፒታል ክምችት ይባላል ። የካፒታል ክምችት ቁሳዊ ምርትና ካፒታሊስታዊ የምርት ግንኙነት ባንድ ላይ የሚራቡበት ሂደት ነው ። ከፍተኛ ትርፍ ለማግኘት ካፒታሊስቶች ያላቸው ዓላማና በመካከላቸው የሚ

ካሄደው ውድድር ለካፒታል ክምችት መሠረቶች ናቸው ።

በካፒታሊስት ሥርዓት ከተመረተው ትረፈ እሴት ውስጥ የተወሰነው ክፍል ለካፒታሊስቱ አምርታዊ ፍጆታ ሲውል የቀረው ክፍል ደግሞ በመከማቸት የተስፋፋ እርባታ ይካሄድበታል ። ትረፈ እሴት እንዲከማች ወይንም ወደ ካፒታል እንዲቀየር የካፒታሊስቱ የማከማቸት ፍላጐት መኖር ብቻውን በቂ አይሆንም ። ክምችቱ እውን እንዲሆን በተመረተው ትረፈ ምርት ውስጥ አዲስ የተከማቸውን ካፒታል ሊያስተናግድ የሚችል የምርት መሣሪያዎች ምርትና ለተጨማሪ ሠራተኞች አስፈላጊ የሆኑ የፍጆታ ሸቀጦች ሊኖሩ ይገባል ።

የቡርዧ ኢኮኖሚስቶች የካፒታሊስቱን ትርፍ ከብዝበዛ እንዳልመነጨና ተገቢም እንደሆነ አድርገው ለማቅረብ እያሉ ጉድፈ ሐሳቦችን ሰንዝረዋል ። ከነዚህ ጉድፈ ሐሳቦች ውስጥ ዋነኛው ግልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚስቶች የሚያስተጋቡት ፣ ካፒታሊስቱ ከፍጆታው ቀንሶ ወይንም ራሱን ከተንደላቀቀ ኑሮ በመቆጠብ ለማኅበራዊና ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሊውል የሚችል ሀብት በማከማቸቱ ለጠቅላላው ኅብረተሰብ ባለውለታ ነው የሚለው ነው ። ሐቁ ግን ካፒታሊስቱ እንዲያከማች የሚገፋፋው ወይንም የሚያስገድደው ለኅብረተሰቡ መልካም ኑሮ ወይንም ዕድገት መመኘቱ ሳይሆን መሠረታዊ የካፒታሊስት ኢኮኖሚያዊ ሕግ የሆነውን ትርፍ የማግኘት ዓላማ ነው ። ካፒታሊስቱ ካፒታልን በማከማቸት የሚያገኘውን ትርፍ ከፍ በማድረግ በበለጠ ለማከማቸትና የበለጠ የተንደላቀቀ ኑሮ ለመኖር ይችላል ። ይልቁንም የክምችቱ መጠን ዕድገት የሚወሰነው በቡርዧው መደብ ፍጆታ መቀነስ ሳይሆን የቀኑን የሥራ ሰዓት በማራዘምና አስፈላጊ የሥራ ጊዜን በመቀነስ የብዝበዛውን ደረጃ ከፍ በማድረግ ነው።

የካፒታል ክምችት ካፒታሊስታዊ የምርት ግንኙነትን የሚያራባ ከመሆኑም በላይ ብዝበዛው ከፍ እንዲልና በወዝአደሩና በቡርዧው መደቦች መካከል ያለው የኑሮ ልዩነት እንዲሰፋ ያደርጋል ። ይሁንና የካፒታል ክምችት በአንድ በኩል የምርት ኃይሎችን ዕድገት በማስከተል ብዝበዛ ለሌለበት ሥርዓት ምሥረታ ቁሳዊ ቅድመ ሁኔታ ይፈጥራል ።

የካፒታል ክምችት ሁለት ገጽታዎች አሉት ። አንደኛው የካፒታል መሰባሰብ ሲሆን ሌላው ደግሞ የካፒታል መግከል ነው ። የካፒታል መሰባሰብም ሆነ መግከል ለሥራ ምርታማነት ዕድገት አስተዋጽኦ የሚያደርግ የአመራረት ሁኔታን ይፈጥራሉ ። ይህ ሂደት በአንድ በተወሰነ ደረጃ ለሞኖፖሎች መፈጠር ምክንያት ይሆናል ።

የካፒታልን ክምችት ከሚያፋጥኑት ምክንያቶች መካከል አንዱ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕድገት ነው ። በዚህ ዕድገት ሳቢያ ከፍተኛ ክምችት የሚጠይቁ አዳዲስ የኢኮኖሚ መስኮች መከፈትና የምርት ዓይነቶች መበራከት ተጨማሪ የክምችት መስክ ይፈጥራሉ ።

በካፒታሊዝም ውስጥ የካፒታል ክምችት የሚከናወነው ሥርዓት አልባ በሆነና ባልተመጣጠነ መንገድ በመሆኑ የምርት ዕድገትና የገበያ ስፋት እኩል ሊራመዱ ስለማይችሉ የካፒታሊስት ሂደተ ምርት በቀውስ የተወጠረ ይሆናል ።

የካፒታሊስት ክምችት ሂደት በካፒታሊዝም ውስጥ ያለውን መሠረታዊ ቅራኔ ማለትም በማኅበራዊ አመራረትና ካፒታሊስቱ ምርቱን የግል በማድረግ መካከል ያለውን ቅራኔ እንዲባባስ ያደርጋል ። ምክንያቱም የካፒታል ክምችት ሂደት በቀጠለ መጠን ባንድ በኩል ከፍተኛ ሀብት በቡርዧው መደብ እጅ እንዲከማች በሌላ በኩል የወዝአደሩ መደብ ድርሻ እያቆለቆለ እንዲሄድ ስለሚያደርግ የኑሮ ደረጃ ልዩነት እየሰፋ ይሄዳል ። ይህም በወዝአደሩና በቡርዧው መደቦች መካከል ያለው ቅራኔ እንዲባባስና ብዝበዛ የሰፈነበትን የካፒታሊስት ሥርዓት ማስወገድ የሚያስችሉ ነባራዊና ኅሊናዊ ቅድመ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ ያደርጋል ። "ካፒታሊዝም ዘለዓለማዊ ሥርዓት ነው" በማለት የብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ምሁራን ያስተጋቡትን ጉድፈ ሐሳብ ፍሬቢስነት ካርል ማርክስ ሊያሳይ የቻለውም በዚህ የካፒታሊስት ክምችት ሂደት ታሪካዊ ዝንባሌ ላይ በመመርኮዝ ነው ።

## ካፒታል ዙረት (የ—)
*(Circuit of Capital)*

ካፒታል ተከታታይነት ባለው መንገድ ከአንድ ቅርፅ ወደሌላ ቅርፅ በመቀየር በመነሻው ይዞት የነበረውን ቅርፅ እንደገና የሚይዝበት፣በምርትና በዝውውር መስከ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ነው ። በዚህ እንቅስቃሴ ካፒታል የገንዘብ ካፒታልን ፣ ቀጥሎም የምርታዊ ካፒታልንና የሸቀጥ ካፒታልን ቅርፅ ይይዛል።

የኢንዱስትሪ ካፒታል እንቅስቃሴ የመጀመሪያ ደረጃ የገንዘብ ካፒታል ወደ ምርታዊ ካፒታልነት መለወጥ ነው ። ይህም የሚሆነው ካፒታሊስቱ በገንዘቡ የሥራ ኃይልንና (ወዝአደር በመቅጠሩ) ሌሎች ለምርቱ ተግባር የሚያስፈልጉትን እንደ ማምረቻ መሣሪያዎችና እንደ ጥሬ ዕቃዎች የመሳሰሉትን ሲገዛ ነው ። ይህም የኢንዱስትሪ ካፒታል እንቅስቃሴ የመጀመሪያ ደረጃ በሚከተለው ቀመር ሊገለጽ ይችላል ።

ገ—ሸ { የምርት መገልገያዎች / የሥራ ኃይል

በዚህ ደረጃ ከተገዙት ሸቀጦች ውስጥ አንዱ የሆነው የሥራ ኃይል ተረፈ እሴት ወደሚፈጥር እሴት የመለወጥ ወይንም ቀደም ሲል የነበረውን እሴት በተረፈ እሴት የማሳደግ ልዩ ሚና ይጫወታል ። በመሆኑም የሥራ ኃይል ግዥ ከምርት መገልገያዎች ባለቤትነት በመገለል የሥራ ኃይሉን ሸጦ እንዲኖር በተገደደው የወዝ አደር መደብና የምርት መገልገያዎች ባለቤት በሆነው በቡርዧው መደብ መካከል ያለውን ግንኙነት ያሳያል ።

የኢንዱስትሪ ካፒታል እንቅስቃሴ ሁለተኛው ደረጃ የምርታዊ ካፒታል በሂደተ ምርት አማካይነት ወደ ሸቀጥ ካፒታልነት መለወጥ ነው ። ቀደም ሲል የነበረው የእሴት መጠን የሚያድገው በዚህ ደረጃ ነው ። ይህን ሁለተኛ የኢንዱስትሪ ካፒታል እንቅስቃሴ ደረጃ በሚከተለው ቀመር መግለጽ ይቻላል ።

...ም...ሸ[1]

በምርቱ ሂደት ሠራተኛው የምርት መገልገያውን እሴት አዲስ ወደ ተመረተው እሴት ማዛወር ብቻ ሳይሆን አዲስ እሴትም ይፈጥራል ። ይህ አዲስ እሴት ለሥራ ኃይል እርባታ የሚሆነውንና ተረፈ እሴትን የሚያጠቃልል ነው ። ስለዚህ አዲስ የተመረተው ሸቀጥ እሴት ቀደም ሲል በካፒታሊስቱ ከተገዙት ሸቀጦች እሴት አዲስ በተፈጠረው ተረፈ እሴት መጠን ይበልጣል ።ስለዚህ ነው ከዚህ በላይ በተገለጸው ቀመር ውስጥ በሸ ምትክ ሸ[1] የሰፈረው ።

ሦስተኛው ደረጃ የሚከተለው የሸቀጥ ካፒታልን በዝውውር መስክ ወደ ገንዘብ ካፒታልነት መለወጥ ነው ። በዚህ ደረጃ የሸቀጥ ካፒታሉ እሴት መጠን በሁለተኛዉ ደረጃ ተረፈ እሴት የተፈጠረ በመሆኑ በአንደኛው የካፒታል እንቅስቃሴ ደረጃ ከነበረው የገንዘብ መጠን የበለጠ ነው ። ሦስተኛው የእንቅስቃሴ ደረጃ እንደሚከተለው በቀመር ይገለጻል ።

ሸ[1] —ገ[1]

ሦስት ገቢራዊ መልኮችን በመውሰድ ካፒታል በሦስት ደረጃዎች ውስጥ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ወይንም ባጭሩ የካፒታልን ዙረት በተጠቃለለ መንገድ በሚከተለው ቀመር መግለጽ ይቻላል ።

ገ—ሸ { የምርት መገልገያዎች / የሥራ ኃይል } ...ም... ሸ[1] —ገ[1]

የካፒታል ዙረት በአንድ ዑደት የሚያቆም ሳይሆን በተከታታይ የሚታደስና የሚደጋገም ሂደት ነው ። ይህ የካፒታል ዙረት ተከታታይ እድሳትና የድግግሞሽ ሂደት የካፒታል መገላበጥ ይባላል ። የድግግሞሽ ሂደቱ መኖርም ለማያቋርጥ የተረፈ እሴት መፈጠር አስፈላጊ ነው ።

የኢንዱስትሪን ካፒታል እንቅስቃሴ ደረጃ ባለው ጥምረት አኳያ ለመጀመሪያ ጊዜ የተነተነው ካርል ማርክስ ሲሆን ይህም ትንታኔው ለካፒታሊዝም ቀውስ ምክንያት የሆኑ ሁኔታዎችን በግልጽ ለማብራራት አስችሎታል ። እነዚህም ሁኔታዎች የኢንዱስትሪ ካፒታል በእንቅሲቃሴው ሂደት ውስጥ የሚያልፍባቸው ሦስት ደረጃ

ዎችና የሚወስዳቸው የተለያዩ ቅርፆች የተለያዩ ተግባራትን የሚያከናውኑ ከመሆናቸው በላይ የእነዚህ ደረጃዎች መነጣጠልና ለየብቻ መከናወን ሂደቱን እንዲወሳሰብና ቅራኔውም እንዲባባስ ያደርጉታል ።

## ኬይንስ ፡ ጆን ሜይናርድ

*(Keynes, John Maynard)*

ኬይንስ ከ1883 እስከ 1946 የኖረ፣ "ኬይንሲዝም" የተሰኘውን የቡርዧ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ የመሠረተ እንግሊዛዊ የኢኮኖሚክስ ሊቅ ነው ።

ኬይንስ በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ የሒሳብና የኢኮኖሚክስ ትምህርት ከተከታተለ በኋላ በዚያው ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በፕሮፌሰርነት እንዲሁም ከ1915 እስከ 1919 ድረስ በእንግሊዝ መንግሥት ጠቅላይ ግምጃ ቤት ውስጥ በከፍተኛ የኃላፊነት ቦታ የሠራና ከአንደኛው ዓለም ጦርነት በኋላ በፓሪስ ውስጥ በተደረገው የሰላም ጉባኤ ላይ በዚሁ ሥራው የእንግሊዝን መንግሥት ወክሎ የተሳተፈ ነው ። በፓሪስ የተደረገውን የሰላም ጉባኤ ተሳትፎ ከተመለሰ በኋላ በጻፈው "ዘ ኢኮኖሚክ ኮንሲኩንስ ኦቭ ዘ ፒስ" በ ተሰኘው መጽሐፉ በጦርነቱ አሸናፊ የሆኑ ወገኖች የተከተሉትን የኢኮኖሚ ፖሊሲ በጦርነቱ ከደረሰው ጉዳት የማገገሙን ሂደት የሚያጨናግፍና ለሌላ ጦርነት መቀስቀስ ሁኔታዎችን የሚያመቻች ነው በማለት መንቀፉ በዓለም ደረጃ ታዋቂነትን እንዲያገኝ ካስቻሉት ሥራዎቹ መካከል አንዱ ነው ። ኬይንስ በ1944 በብሪቶን ውድስ፣ በአሜሪካ በተካሄደው ዓለም አቀፍ የገንዘብና የፋይናንስ ጉባኤ ላይ የተካፈሉት የእንግሊዝ ልዑካን መሪ በመሆን ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ አሁን ያላቸውን ጠባይ ይዘው እንዲመሠረቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ። በተጨማሪም ከ1912 እስከ ዕለተሞቱ ድረስ "ኢኮኖሚክ ጆርናል" የተሰኘው መጽሔት አዘጋጅ በመሆንም ሠርቷል ።

ኬይንስ ከጦርነቱ በኋላ በአውሮፓ የካፒታሊዝምን ዕድሜ ማራዘም የሚቻለው በአጠቃላይ የካፒታሊስት ሀገሮችን ኢኮኖሚ ማረጋጋት ሲቻል ብቻ ነው የሚል እምነት ስለነበረው በዚሁ ጭብጥ ሐሳብ ላይ የተመሠረቱ አያሌ ጽሑፎችን በተከታታይ አቅርቧል ። ይሁንና ኬይንስን በዓለም ደረጃ ታዋቂ ያደረገው ዋና ሥራው "ዘ ጀነራል ቲየሪ ኦቭ ኢምፕሎይሜንት ኢንተረስት ኤንድ መኒ" በሚል ርዕስ በ1936 ያወጣው መጽሐፉ ነው ።

"ኬይንሲዝም" የተሰኘው ዘመናዊ የቡርዧ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ መሠረታዊ መርሆችም የተነደፉት በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ነው ። በ1930 ስለዓለም የኢኮኖሚ ቀውስ መነሻ በጻፈው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ኬይንስ የካፒታሊስት መንግሥታት ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ለካፒታሊዝም ዕድሜ መራዘም እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አስተጋብቷል። አጠቃላይ የካፒታሊስት ኢኮኖሚን እርባታ ሂደት ቀደም ካሉ ቡርዧ ኢኮኖሚስቶች በተለየ መንገድ በጥቅሉ ለማየት ከመሞከሩም በላይ ቀውስን ለማስወገድ ያስችላሉ ብሎ በሚያምንባቸው አጠቃላይ ፖሊሲዎች ላይ ያተኮረ ጥናት ኬይንስ "አቅርቦት የራሱን ፍላጐት ይፈጥራል"፤ "ጤናማ" ያልሆነ የኢኮኖሚ ሁኔታ በራሱ "ይስተካከላል" የሚለውን የብሉይ ፖለቲካ ኢኮኖሚ መሠረተ ሐሳብ በመቃወም ቀውስ በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የሚፈጠር ክስተት መሆኑን ገልጿል። በኬይንስ አባባል ቀውስ የሚፈጠረው በጠቅላላ ፍላጐትና በጠቅላላ አቅርቦት መካከል በሚፈጠር አለመጣጣም ሲሆን ይህም ሁኔታ በአብዛኛው ከሰዎች ሥነ ልቡናዊ ዝንባሌ ይመነጫል ።

ኬይንስ ለሥራአጥነት መፈጠርም ይህኑን ሥነ ልቡናዊ ምክንያት ይሰጣል ። በእርሱ አስተሳሰብ ሥራ እየተፈጠረ ሲሄድ ብሔራዊ ገቢ እየጨመረ ይሄዳል ። ይህም የሰዎችን ፍጆታ ይጨምራል ። ይሁንና የፍጆታው ዕድገት ከገቢው ዕድገት ጋር እኩል ስለማይራመድ ተመጣጣኝ የፍላጐት ዕድገት አይኖርም ። ይህ ደግሞ በተራው የምርት መቀነስን ስለሚያስከትል የምርት መቀነስ በተራው ሥራ አጥነት እንዲባባስ ያደርጋል ብሏል ።

እንደኬይንስ አስተሳሰብ የፍጆታ ዕቃዎችንና የምርት መገልገያዎችን አጠቃላይ ፍላጐት በማሳደግ ከአቅርቦት ጋር እንዲመጣጠንና ሥራ አጥነት ተባብሶ የካፒታሊስቱ ሥርዓት እስኪ ደረጃ ላይ እንዳ

ይደርስ ለማድረግ መንግሥት በኢኮኖሚው ውስጥ በቀጥታ ጣልቃ በመግባት ለልዩ ልዩ የሥራ መስኮች ወጪ በመመደብ ማንቀሳቀስና ለግል ሙሉ ንዋይ መስፋፋት አመች ሁኔታዎችን መፍጠር ይኖርበታል ። ለዚህም በተለይ የመንግሥት በጀትንና የወለድ መጣኔን መንግሥት በመግሪያነት እንዲገለገልባቸው ኬይንስ አሳስቧል ።

በአጠቃላይ የኬይንስ ፀረ ቀውስ ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች በአንድ ወቅት የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ያጋጠመውን ችግር ለማቃለል ያስቻሉ ቢመስሉም በነባራዊ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ሕጐች ትክክለኛ ግንዛቤ ላይ ያልተመሠረቱ በመሆናቸው የቡርዧ ኢኮኖሚስቶች እንደገመቱት የካፒታሊስት ኢኮኖሚን ለዘለቄታው ከቀውስ ሊያድነው አልቻለም ። ከዚህም የተነሣ ዛሬ የኬይንስ የኢኮኖሚ አስተሳሰብ በካፒታሊስቱም ዓለም ተቀባይነቱ ከጊዜ ወደጊዜ እየቀነሰ በመሄድ ላይ ይገኛል ።

## ክላሎታዊነት

*(Protectionism)*

ከለለ=ከለከለ ፣ ጋረደ ፣ አጠረ ፣ ከበበ፣ ማለት ነው።

የነፃ ንግድ ፖሊሲን የሚቃወም ፣ በአንድ ሀገር የኢኮኖሚ ሕይወት ውስጥ የመንግሥትን ጠንካራ ቁጥጥር ማድረግ የሚደግፍና የሚያበረታታ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ክላሎታዊነት ይባላል ። ይህ የኢኮኖሚ ንድፈ ሐሳብ የጠበቀ የውጭ ንግድ ቁጥጥርን የሚደግፍና መንግሥት ለካፒታሊስት ኢንዱስትሪ ማደግ አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ያለበት መሆኑን የሚገልጽ ነው ።

ክላሎታዊ የኢኮኖሚ ፖሊሲን ይከተሉ በነበሩ ሀገሮች ውስጥ ክላሎታዊነት ብሔራዊ ቡርዧዚው ከውጭ የሚገጥመውን ውድድር በመከላከል ለብሔራዊ ካፒታሊዝም መዳበር ረድቷል ። በተለይም በ19ኛው ምዕት ዓመት መገባደጃ ላይ ክላሎታዊነት በአብዛኛዎቹ የአውሮፓ ሀገሮችና በአሜሪካ ውስጥ በተግባር ላይ ውሎ ነበር ።

ከካፒታሊዝም መባቻ ጀምሮ እስከአሁን ድረስ ባልተመጣጠነ ዕድገት ሳቢያ በካፒታሊስት ሀገሮች መካከል ውድድር ሲካሄድ ቆይቷል ። ይህ ውድድር እያንዳንዱ ካፒታሊስት ሀገር ለካፒታሊስቱ መደብ አመች ሆኖ ሲያገኘው በተለይ ወደ ሀገር ውስጥ በሚያስገባቸው የውጭ ዕቃዎች ላይ ከፍተኛ የቀረጥና የታሪፍ ደንብ በማውጣት በብሔር አቀፍ ደረጃ ለካፒታሊዝም መስፋፋት አመች ሁኔታ ፈጥሮ ነበር። ካርል ማርክስ ክላሎታዊነት ባለፋብሪካዎችን ሰው ሠራሽ በሆነ መንገድ የሚፈጥር ፣ ከመካከለኛው (ፊውዳል) ወደ ዘመናዊ ካፒታሊስት ስልተ ምርት ያለውን ሽግግር በኃይል የሚያፋጥን ነው ብሎ ነበር ።

የክላሎታዊነት ታሪካዊ አመጣጥ ከላይ የተጠቀሰውን ቢመስልም ዛሬም ቢሆን ግልጋሎቱ ያቆመ የኢኮኖሚ መመሪያ አይደለም ። በተለያዩ ካፒታሊስት ሀገሮችና ካፒታሊስት ቡድኖች መካከል ለምሳሌ በአውሮፓ የኢኮኖሚ ማኅበር ፣ በጃፓንና በአሜሪካ መካከል በሚካሄደው ውድድር የንግድ ሚዛን አለመመጣጠን በሚኖርበት ጊዜ አንዱ ሀገር ወይም ቡድን በሌላው ላይ የንግድ ቁጥጥሩን ያጠብቃል ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የአሜሪካ የኢኮኖሚ ኃይል ከአውሮፓ ካፒታሊስት ሀገሮችና ከጃፓን ጋር ሲነፃፀር በጣም ከፍተኛ በነበረበት ወቅት በነፃ ንግድ ፖሊሲ ከፍተኛ ጥቅም ያገኝ ስለነበር ሌሎቹ በጦርነቱ ምክንያት ተዳክመው የነበሩት የካፒታሊስት ሀገሮች የነፃ ንግድ ፖሊሲን እንዲከተሉ በተለያየ ተፅዕኖ አማካይነት ያስገድድ ነበር ።

በአሁኑ ጊዜ ግን የጃፓን የኢኮኖሚ ዕድገት ከአሜሪካና ከአውሮፓ የጋራ ገበያ ሀገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ መሆንና በአጠቃላይ በኢምፔሪያሊስት ሀገሮች መካከል ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት አለመመጣጠን የክላሎታዊነትን ፖሊሲ እንዲስፋፋ እያደረገው ነው ።

በሌላ በኩል በአሁኑ ወቅት በዳበሩ ካፒታሊስት ሀገሮችና በኋላቀር ሀገሮች መካከል ያለው ግንኙነት ሲገመገም ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ባላቸው የፋይናንስና የቴክኖሎጂ የበላይነት በመጠቀም የኢንዱስትሪ ውጤቶቻቸውን በገፍ ወደ ኋላቀር ሀገሮች ሲያስገቡ ፣ የኋላቀር ሀገሮች የኢንዱስትሪ

ውጤቶች ወደ ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ገበያ እንዳይገቡ የተለያየ ገደብ ሲጣልባቸው ይታያል ። ኢምፔሪያሊስቶች ኋላቀር ሀገሮች ኢኮኖሚያቸውን ለማዳበር የሚያደርጉትን ጥረት የፋይናንስ ፣ የቴክኖሎጂና ዘመናዊ አሠራር ስልትን ስርጭት በማፈን ከሚፈጥሩባቸው መሰናክሎችም በተጨማሪ የከላሎታዊነት ፖሊሲን በመከተል የኋላቀር ሀገሮች የኢንዱስትሪ ውጤቶች ወደዳበሩ ካፒታሊስት ሀገሮች እንዳይገቡ በማድረግ በዕድገት ወደ ኋላ በቀሩ ሀገሮች ውስጥ የኢንዱስትሪው ክፍል ኢኮኖሚ እንዳያድግ በማድረግ ላይ ይገኛሉ ። ስለዚህ አዲሱን የኢኮኖሚ ሥርዓት ለመመሥረት በሚካሄደው ትግል ኋላቀር ሀገሮች የኢንዱስትሪ ውጤቶቻቸውን እለ ምንም መሰናክል ወደዳበሩ ካፒታሊስት ሀገ ሮች ገበያዎች ውስጥ ለማስገባት የሚችሉ በት ሁኔታ ይፈጠር የሚለው ጥያቄ አንዱ ነው ።

በአንድ አዳጊ ሀገር ውስጥ የቀላል ኢን ዱስትሪና የእደ ጥበብ ሥራ ውጤቶችን ለማዳ በር ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ ተመ ሳሳይ ዕቃዎች ላይ መንግሥት ታሪፍ ቢጥል፣ በሀገር ውስጥ ለቀላል ኢንዱስትሪ ማደግ አመች ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል ።

## ክላርክ ፣ ጆን ቤይትስ
*(Clark, John Bates)*

ከ1847—1938 የኖረ አሜሪካዊ የኢኮ ኖሚክስ ሊቅ ነው ። ክላርክ በ1872 በዚያው ሀገር ከሚገኘው ከአምኸርስት ኮሌጅ ከተመ ረቀ በኋላ ትምህርቱን በሃይድልበርግና በዙ ሪክ ዩኒቨርሲቲዎች ቀጠለ ። ከ1877 ጀምሮ በብዙ የአሜሪካ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ያስተማረ ሲሆን በተለይ ከ1895—1923 በኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ በፕሮፌሰርነት ሠር ቷል ። ከ1893—1895 ባለው ጊዜም የአሜ ሪካ የኢኮኖሚክስ ማኅበር ፕሬዚዳንት ሆኖ አገልግሏል ።

ክላርክ የቡርዧው ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ዋና ዋና ቀኖናዎች ከሆኑት መካከል አንዱ የሆነውን የተጨማሪ ምርታማነትን ንድፈ ሐሳብ የቀመረ ነው ።

ክላርክ አንድን እሴት ለመፍጠር የሥራ ኃይልና ካፒታል እኩል አስተዋጽኦ ያደር ጋሉ በማለትና ካፒታሊስቱ የሚያገኘው ትርፍ የአስተዋጽኦው ውጤት በመሆኑ ተገቢ ነው በማለት የቡርዧዚውን ጥቅም አራም ዷል ። የተጨማሪ ምርታማነት ንድፈ ሐሳብ ሠራተኛውና ካፒታሊስቱ ባለመሬት ከብሔ ራዊ ገቢ ውስጥ የሚደርሳቸው ድርሻ እንደ አስተዋጽኦዋቸው ነው በማለት ከተጨባጭ ሁኔታው እጅግ የራቀና በካፒታሊስቱ ኅብረተ ሰብ ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ መደቦች ጥቅ ማቸው የማይጋጭና ቅራኔም በመካከላቸው እንደሌለ አድርጐ ለማቅረብ የሚሞክር አስ ተሳሰብ ነው ።

## ክስተታዊነት
*(Phenomenalism)*

የዕውቀት ቀጥተኛ ተደራጊዎች ሕውስታዎች ብቻ ናቸው የሚል ሐሳባዊ ሥነ ዕውቀት ነው። ይህ አመለካከት በአጠቃላይ የሚያደላው ወደ ኅሊናዊ ሐሳባዊነት ነው። ሕውስታዎችን አልፈን የነሱን ነባራዊ ምንጮች ለመገንዘብ እንችልም የሚል በመሆኑም በኢታዋቂነት ውስጥ የሚ መደብ ነው ። በአጠቃላይ ክስተታዊነት ዕው ቀትንና እውነታን የሚለያይ በመሆኑ ተቀባይ ነት የለውም ።

(ኅሊናዊ ሐሳባዊነትን ፣ ኢታዋቂነትን ፣ ሕው ስታዊነትን ይመለከቷል ።)

## ክስተት
*(Phenomenon)*

በሰው ሕዋሳት በኀሀድ ሊዳሰስ ፣ ሊሸ ተት ፣ ሊሰማ ወይም ሊታይ የሚችል በዚ ሀም ጊዜ በአእምሮአችን ውስጥ የሚፈጠረ ውን ምስል የሚያመለክት ነው ። ስለሆነም ክስተት ቁሳዊ ወይም ኅሊናዊ ሊሆን ይች ላል ። ኅብረተሰብ ፣ ቤት ፣ ሸቀጥ ፣ ወዘተ... ቁሳዊ ክስተቶች ሲሆኑ የተለያዩት የማኅበ ራዊ ንቃተ ኅሊና መልኮች ፍልስፍና ፣ ርዕ ዮተዓለም ወዘተ... ደግሞ ኅሊናዊ ክስተቶች ናቸው ።

## ክርስቲያን ሶሻሊዝም
*(Christian Socialism)*

የክርስትናን ሃይማኖት በሶሻሊዝም ቀለም ለመቀባትና ክርስትናን የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ጥቅም አስከባሪ አድርጎ ለማቅረብ እንዲሁም በኅብረተሰብ ውስጥ ከሚገጥም አደጋ ሊያድን የሚችል ብቸኛ መንገድ ክር ስትና ብቻ ነው ብሎ ለመስበክ የሚጥር አስተምህሮ ነው ። የክርስቲያን ሶሻሊዝም በታሪክ የተከሰተው በ1800 ዎቹና በ1840ዎቹ ሲሆን ዓላማውም አብዮታዊ እንቅስቃሴን መዋጋትና ማክሸፍ ፣ በአንፃሩም ተፃራሪ መደቦችን ማስማማት ነው ።

ክርስቲያን ሶሻሊዝም በአሁኑ ጊዜ ራሱን ከካፒታሊዝምና ከኮሚኒዝም የተለየ አድርጎ ለመቁጠር ይከጅለዋል ፤ ይሁን እንጂ ቆሜለታለሁ የሚለው "ክርስቲያን ዲሞ ክራሲ" ከቡርዧ ማኅበራዊ ግንኙነቶች ውጭ ሊሆን አልቻለም ። ክርስቲያን ሶሻሊ ዝም ከጠጋኝነት ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያለው ሲሆን ዛሬም ለሠራተኛው መደብ አመራር መከፋፈል አጥብቆ ሲታገል ይታ ያል ።

## ክፍያ ሚዛን (የ—)
*(Balance of Payments)*

አንድ ሀገር በአንድ በተወሰነ የጊዜ ክልል ውስጥ ለምሳሌ በዓመት ከሀገር ውጭ የሚ ያገኘው ገቢ በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ ከሀገር ውጭ ከሚያደርገው ክፍያ ጋር ሲነፃፀር የሚያሳይ ሚዛን ነው ።

አንድ ሀገር ፣ አንድ ድርጅት ወይም አንድ ግለሰብ ወደ ሌላ ሀገር ለግለሰብ ወይም ለድርጅት ሸቀጦችን ፣ አገልግሎቶች ንና ገንዘብ ሲያስተላልፍ የዚህ ዓይነቱ የመ ቀበልና የመስጠት ሁኔታ ይመዘገባል ። እነ ዚህም ገቢዎችና ክፍያዎች ተብለው በሒ ሳብ ሠንጠረዥ የሚሰፍሩ ናቸው ። በዚህ ሠንጠረዥ ውስጥ የሚሰፍሩ የገቢና የወጪ ርዕሶች ንግድን፣መጓጓዣን፣የመጓጓዣ መድንን፣ ጉዞን ፣ የግለሰብ ወይም የድርጅት ሃብት ዝው ውሮችን ፣ የሙአለንዋይ ትርፎችን ፣ የአክሲ ዮን ክፍያዎችን ፣ በመንግሥታት የዲፕሎማ ቲክ ግንኙነት አማካይነት የሚደረጉ የሀብት ዝውውሮችን ፣ የብድርና የወለድ ክፍያዎችን ወዘተ... ያጠቃልላሉ ።

በክፍያዎች ሚዛን ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ ይዞ የሚገኘው የንግድ ሚዛን ሲሆን ይኸውም በክፍያ ሚዛን አንድ ሀገር በዓለም ንግድ ውስጥ ያለውን ቦታና የተሳትፎ ሁኔታ የሚያሳይ መሥፈርት ነው ። አንድ ሀገር በአንድ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ከውጭ የሚ ያገኘው ገቢ በጠቅላላ ወደውጭ ከሚያደ ርገው ክፍያ በልጦ ሲገኝ የክፍያው ሚዛን ትርፍ አሳየ ወይም ጤናማ ሆነ ይባላል ። በአንፃሩ ይህ ሀገር በአንድ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሚያደርገው ክፍያ መጠን ከውጭ ከሚያገኘው መጠን በልጦ ሲገኝ የክፍያ ዎች ሚዛን ተዛበት (ዴፊሲት) አሳየ ይባ ላል ።

ኋላቀር ሀገሮች በመሠረቱ ካፒታል ተቀባዮች እንደመሆናቸው ሁሉ ከውጭ የሚመጣው ካፒታል ምንም እንኳን በመጠ ኑም ቢሆን በምርታዊ ሥራ ላይ በመዋል ተጨባጭ ጥቅም ሊያስገኝ ቢችልም የዚህ ካፒታል ላኪ ሀገሮች የሚያገኙትን ከፍተኛ ትርፍ መልሰው በማውጣት በኋላ ቀር ሀገሮች ላይ የውጭ ምንዛሪ እጥረትን በመፍጠር ከፍተኛ የኢኮኖሚ ችግር ያስከ ትላሉ ። ይህ ሁኔታ የኋላቀር ሀገሮች የክፍያ ሚዛንን በተዛበት ችግር ውስጥ እንዲወድቅ ከሚያደርጉ ዋና ምክንያቶች አንዱ ነው ። የክፍያዎች ሚዛን በየጊዜው ተዛበት የሚያ ሳይ ከሆነ ሀገሪቷ ወደ ክፍያ ሚዛን ቀውስ ታመራለች ማለት ነው ።

አንድ ሀገር በመሠረቱ ያለው የውጭ ምንዛሪ ተከበት ይዞታ የስድስት ወር ያህል የገቢ ንግድ ክፍያ ሊሸፍን የሚችል ከሆነ የሀገሪቱ የክፍያ ሚዛን አቋም በጎ ነው ማለት ይቻላል ። ይህ ካልሆነና በተለይም የክፍያ ሚዛናቸው ተዛበት እየተባባሰ ከሄደ በገንዘብና በፋይናንስ ሞኖፖል ድርጅቶች ቁጥጥር ሥር ለመውደቅ በር ይከፍታል ።

(የንግድ ሚዛንን ፣ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትን ይመለከቷል ።)

## ኮመንዌልዝ
*(Commonwealth)*

ይህ ጽንሰሐሳብ ከነሣሡ ያንድ ሀገር ዜጎች በእኩልነት የሚሳተፉበት መንግሥትና

መስተዳድር ወይም ሪፐብሊክ እንደሆን ተደርጎ ተወሰዷል ። ኮመንዌልዝ የሚለው ቃል *"Common Weal"* (የጋራ ደህንነት ፣ ብልጽግና ወይም አስተዳደር) ከሚለው የተወረሰ ነው። ይህን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመበት የእንግሊዙ ፈላጭ ቆራጭ ገዥ ኦሊቨር ክሮምዌል ሲሆን የሱ አስተዳደር (ከ1649—1660) ዲሞክራሲያዊ እንጂ ፈላጭቆራጫዊ አለመሆኑን ለማስገንዘብ የሀገሪቱን አስተዳደር "ኮመንዌልዝ" ብሎት ነበር ።

ባሁኑ ወቅት ኮመንዌልዝ ቀድሞ በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ሥር የነበሩ ሀገሮች በእኩልነትና በፈቃደኝነት የሚሳተፉበት ዓለም አቀፍ ድርጅት ነው ። ኮመንዌልዝ ዘመናዊ ቅርፁን ያገኘው በ1947 ህንድ ፣ ፓኪስታንና ስሪላንካ ነፃነታቸውን ከተቀዳጁ በኋላ ነው ። ሦስቱም ሀገሮች (አሁን ፓኪስታን ወጥታለች) ባንድነት በፈቃደኝነት የኮመንዌልዝ አባል ሆኑ ። ከዚያ በኋላ ከቀጥተኛ ቀኝ አገዛዝ ነፃ የወጡ ሀገሮች ሁሉ (ከበርማ በስተቀር) የድርጅቱ አባላት ሆኑ ። የኮመንዌልዝ አባልነት እንደወትሮው የእንግሊዝን ንጉሥ ወይም ንግሥት የአባል ሀገሩ የክብር መሪ አድርጎ መቀበልን የግዴታ አይጠይቅም ። የቀድሞዎቹ (ነጮች) አባል ሀገሮች ግን ማለትም ካናዳ ፣ አውስትራሊያና ኒውዚላንድ የእንግሊዝን ንግሥት እስካሁን ድረስ የሀገራቸው ንግሥት አድርገው ይቀበላሉ ። የእንግሊዝ ንግሥት የኮመንዌልዝ መሪ ናት ።

የኮመንዌልዝ ዓላማ በአባል ሀገሮች መካከል የጋራ ትብብርን ማጠናከር ፣ ለታዳጊ አባል ሀገሮች የቴክኒክ እርዳታን መስጠት ፣ ለዓለም ሰላምና ብልጽግና በጋራ መሥራት የሚል ነው ። ኮመንዌልዝን በአሠራሩ ከሌሎች ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የተለየ የሚያደርገው ውሳኔን ሲያሳልፍ በድምፅ ብልጫ ሳይሆን በጋራ ስምምነት ነው ። በየሁለቱ ዓመት በመሪዎች ደረጃ ከሚደረገው ስብሰባ በኋላ የሚወጣው ሰነድ እንደሌሎች ድርጅቶች ውሳኔ ሳይሆን የጋራ መግለጫ ነው ። የኮመንዌልዝ ዋና ጽሕፈት ቤት በለንደን ከተማ የሚገኝ ሲሆን ድርጅቱም የሚመራው በዋና ጸሐፊ ነው ። ኮመንዌልዝ በዕድገት ደረጃቸውና በብሔራዊ ጥቅማቸው የተለያዩ ሀገሮችን የሚያቅፍ በመሆኑ ውስጣዊ ቅራኔው ለሰላምና ለጋራ ብልጽግና ቆሚለታለሁ የሚለውን ዓላማ አደብዝዞታል ።

## ኮሚሳር
*(Commissar)*

በተለያዩ የሥራ ዘርፎች በከፍተኛ የኃላፊነት ቦታ ተመድበው አመራር የሚሰጡ የመንግሥት ባለሥልጣኖች መጠሪያ ነው ። በአብዛኛው ጥቅም ላይ የዋለውም በሶቭዬት ኅብረት ነው ።

ሕዝባዊ ኮሚሳርያት በመባል የሚታወቀው በሶቭዬት ኅብረት ከፍተኛው የመንግሥት አመራር አካል የተቋቋመው ጥቅምት 26 (በአዲሱ አቆጣጠር ታህሣሥ 8) ፣ 1917 በተካሄደው ሁለተኛው የመላው ሩሲያ ጉባዔ ሲሆን ፣ ምክር ቤቱ በሌኒን መሪነት የተቋቋመ የመጀመሪያው የሶቭዬት መንግሥት ነበር ከ1917 እስከ 1946 በሶቭዬት ኅብረት ፣ በኅብረት ሪፐብሊኮችና በራስ ገዝ (አውቶኖመስ) ሪፐብሊኮች ጭምር ከፍተኛው የመንግሥት አካል የኮሚሳርያት ምክር ቤት ነበር

በመጋቢት 1946 የሶቭዬት ኅብረት የሕዝባዊ ኮሚሳርያት ምክር ቤት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ተብሎ ሲደራጅ ፣ የኅብረት ሪፐብሊኮችና የራስገዝ ሪፐብሊኮችም ምክር ቤቶች በዚሁ መልክ ተደራጁ ።

## ኮሚሽን
*(Commission)*

አንድ የተወሰነ ተግባር ለማከናወን የተቋቋመ መንግሥታዊ ፣ ዓለምዓቀፋዊ ወይም የሁለትና ከሁለት የሚበልጡ መንግሥታት ተወካይ የሆነ አካል ነው ። መንግሥታዊ አካል የሆነ ኮሚሽን ተግባርና ሥልጣን እንደየሀገሩ መንግሥታዊ መዋቅር ይለያያል። ጊዜያዊም ቋሚም ሊሆን ይችላል ።

በአንዳንድ ሀገሮች የሚቋቋሙ ኮሚሽኖች እንደሌሎች ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ዓይነት ሆነው ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊና ንግዳዊ ወዘተ… ተግባር የሚያከናውኑ ናቸው። በሀገራችንም በዚህ ዓይነት የተቋቋሙ በርከት ያሉ የኮሚሽን መሥሪያ ቤቶች ይገኛሉ።

በሌሎች ሀገሮች ኮሚሽኖች በተለይ የመንግሥት ደንቦች አፈጻጸምን የሚቆጣጠሩ ፣ የመንግሥታዊ አካሎችን አሠራር በቋሚነት ወይም በዘላቂነት የሚመረምሩና የሚያጣሩ ናቸው ። በሀገራችን በፊውዶቡርዧው

አገዛዝ ዘመን በሥልጣን የባለጉትን ፣ በተለ
ይም በወሎው የረሃብ ዕልቂት ተጠያቂ የሆ
ኑትን ባለሥልጣኖች ጉዳይ ለማጣራት ተቋ
ቁሞ የነበረው መርማሪ ኮሚሽን ለዚህ ዓይነት
ኮሚሽን አንድ ምሳሌ ነው ።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለይ የተባበ
ሩት መንግሥታት ድርጅት ለተወሰኑ የሥራ
ዘርፎች የተቋቋሙ ኮሚሽኖች ያሉት (ለም
ሳሌ የተባበሩት መንግሥታት ዓለም አቀፍ
የሕግ ኮሚሽን) ሲሆን በየጊዜው ለሚ
ፈጠሩ ጉዳዮች ጠቅላላው ጉባኤ በሚሰጠው
ውክልና ጊዜያዊም ሆነ ቋሚ ኮሚሽኖችን
ሊያቋቁም ይችላል ።

እንደዚሁም ሁለትና ከሁለት የሚበልጡ
ሀገሮች በቋሚነትም ሆነ በጊዜያዊነት የጋራ
ጉዳያቸውን በሚመለከት ረገድ የሚያቋቁ
ሙት ኮሚሽን የጋራ ኮሚሽን ይባላል ። ኢት
ዮጵያ ከጐረቤትና ከሌሎችም ወዳጅ ሀገ
ሮች ጋር የጋራ ኮሚሽን አቋቁማለች ።

## ኮሚኒስት

*(Communist)*

ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን የትግል መሣ
ሪያውና መመሪያው በማድረግ ማንኛውንም
ዓይነት ጭቆናና ብዝበዛ እንዲሁም ፀረ
ማርክሳዊ ርዕዮት በመቃወም ፣ ሰው በሰው
የማይበዘበዝበትን መደብ አልባ የኮሚኒስት
ሥርዓተ ማኅበር ለመመሥረት በቆራጥነት
የሚታገል አብዮተኛ ነው ። ፍጹማዊ እኩልነ
ትና ነፃነት የሰፈነበት አዲስ ሥርዓተ ማኅበር
ለመመሥረት በሚደረገው ትግል አንድ
ኮሚኒስት በፓርቲው መሪነት ሰፊውን ሕዝብ
በማንቃት ፣ በማደራጀትና ኃይሉን አሰባስቦና
አቀናጅቶ በመምራት በግንባር ቀደምትነት
የሚዋጋ ፣ ሕዝቡን እያስተማረ ከሕዝቡ የሚ
ማር ፣ ምንጊዜም ለሠራተኛው ሕዝብ
መብት ፣ ነፃነትና እኩልነት እንዲሁም ሰሰ
ላም የቆመና ለዚህም ሁሉ በሚደረገው ትግል
ራሱን ለመሥዋዕትነት ያቀረበ ነው ። ኮሚኒ
ስት ለእናት ሀገሩ ነፃነትና አንድነት በግን
ባር ቀደምትነት የተሰለፈ አርበኛ የመሆኑን
ያህል በዓላማው በሀገር ድንበር ሳይወሰን
ለመላው ሠራተኛ ሕዝብ አርነት የቆመ ዓለም
አቀፍ ታጋይ ነው ።

(ኮሚኒዝምን ፣ ፓርቲን ይመለከቷል ።)

## ኮሚኒስት ሊግ

*(Communist League)*

በ1847 በካርል ማርክስና በፍሬደሪክ
ኤንግልስ መሪነት በለንደን ከተማ ከተለያዩ
ሀገሮች ተሰደው በመጡ ታጋይ ምሁራንና
ሠራተኞች የተመሠረተ የኮሚኒስቶች ማኅ
በር ነው ። ኮሚኒስት ሊግ ከመቋቋሙ
በፊት ሠራተኛው መደብ ከቡርዧዚው ጋር
ያደረገው ትግል የተበታተነ ነበር ። ሠራ
ተኛው በተበታተነ ትግል ከብዝበዛና ከጭ
ቆና ሊላቀቅ ያለመቻሉን እየተረዳና የትግ
ሉንም ዓለም አቀፋዊ ይዘት እየተገነዘበ
በመምጣቱ ኃይሉን ለማቀናጀት የተለያዩ
የሙያና ፖለቲካ ነክ ማኅበሮችን በማቋ
ቋም መታገል ጀመረ ። ከነዚህም ውስጥ በፈ
ረንሳይ "የፍትህ ሊግ" ፣ በእንግሊዝ "የኮሚኒ
ስት የግንኙነት ኮሚቴ" ና በቤልጅግ "የዲ
ሞክራቲክ ኅብረት" ጥቂቶቹ ናቸው ። ሆኖም
እነዚህም ድርጅቶች ቢሆኑ ሳይንሳዊ ርዕዮተ
ዓለም ያልጨበጡና የጠራ ድርጅታዊ አመ
ራር ያላገኙ በመሆናቸው የሠራተኛውን
መደብ ትግል ለድል የሚያበቁት አልነበ
ሩም ። ማርክስና ኤንግልስ ግን የሠራተኛው
አብዮታዊ ትግል በካፒታል ላይ ድልን
ለመጐናፀፍ የሚችለው በጠራ ሳይንሳዊ
ርዕዮተ ዓለም ሲመራና ጠንካራ ድርጅታዊ
አመራር ሲቀዳጅ ብቻ መሆኑን ከመጀመሪያው
ተገንዝበው ነበር ። ኮሚኒስት ሊግ የመጀመሪ
ያው የወዝአደሩ ፓርቲ ጥንስስ ሲሆን በመ
ተዳደሪያ ደንቡ ላይ በግልጽ እንደተመለከ
ተው ዓላማው የቡርዧውን አገዛዝ በመገር
ሰስና የወዝአደሩን አገዛዝ በመተካት በመደብ
ቅራኔዎች ላይ የተመሠረተውን አሮጌ ሥር
ዓተ ማኅበር በማጥፋት መደብ አልባና የግል
ሀብት የሌለበትን አዲስ ኅብረተሰብ መመሥ
ረት ነው ።

የኮሚኒስት ሊግ አባላት ከፈረንሳይ ፣
ከጀርመን ፣ ከኢጣሊያ ፣ ከስዊትዘርላንድ ፣ ከሩሲ
ያና ከሌሎችም የአውሮፓ ሀገሮች የተሰደዱ
ምሁራንና ሠራተኞች ነበሩ ። ይህ ድርጅት በመ
ቅቱ በሠራተኛው ላይ ቡርዧዚው ከሚያደ
ርገው ከፍተኛ ተፅዕኖ የተነሣ ይንቀሳቀስ

የነበረው በጎቡእ ነበር ። ኮሚኒስት ሊግ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን መሪያው ያደረገ ፣ በአሠራሩ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን የተከተለ ፣ የራሱ ደንብና ፕሮግራም የነበረው ነው ።

ኮሚኒስት ሊግ ከ1848—1850 በመላ አውሮፓ በተቀጣጠለው የቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ወቅት የሠራተኛውን አብዮታዊ ትግል ለማስተባበርና ለመምራት ያደረገው ጥረት በሙሉ ባይሳካም ያደረገው አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚገመት አልነበረም ። ኮሚኒስት ሊግ ከትግል ልምድ ማነስ ፣ በውስጡ በተከሰቱት የቀኝና የግራ አዝማሚያዎች ፣ እንዲሁም በቡርዧዚው በተቀናጀ ዘመቻ ሳቢያ በ1852 ሊፈርስ ችሏል ።

## ኮሚኒስት ማኒፌስቶ
(*Communist Manifesto*)

የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ ኮሚኒስት ድርጅት በ1847 ከኅዳር 29 እስከ ታህሣሥ 8 ድረስ በለንደን ባደረገው ሁለተኛ ጠቅላላ ጉባኤው የድርጅቱን ፕሮግራም እንዲያረቅ ኃላፊነቱን ለማርክስ በሰጠው መሠረት ከፍሬደሪክ ኤንግልስ ጋር በመሆን የነደፉትና በየካቲት 1848 የወጣ የመጀመሪያው የኮሚኒስት ፓርቲ ፕሮግራም ነው ።

ኮሚኒስት ማኒፌስቶ በይዘቱ መሠረታዊ የሳይንሳዊ ኮሚኒዝም መርሆች የሠፈሩበት ሰነድ ነው ። "ቡርዧዚና ወዝአደሮች" በሚለው የመጀመሪያ ምዕራፉ ከጥንታዊው የጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር በቀር ኅብረተሰብ በመደብ ከተከፋፈለበት ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ ያለው የኅብረተሰብ ታሪክ የመደብ ትግል ታሪክ ነው ከሚለው ሳይንሳዊ ግንዛቤ በመነሣት ማርክስና ኤንግልስ የካፒታሊዝም መውደቅና የአዲስ ማኅበራዊ ሥርዓት ማለትም የኮሚኒዝም መመሥረት የማይቀር መሆኑን አረጋግጠዋል ። በዚሁ ክፍል ወዝአደሩን አሮጌውን ሥርዓት በማንኮታኮት አዲሱ ኅብረተሰብ የሚገነባና ለመላው ሥርቶ አደር ሕዝብ የቆመ መሪ ኃይል መሆኑን በግልጽ አመልክተዋል ።

"ወዝአደሮችና ኮሚኒስቶች" በሚለው ሁለተኛ ምዕራፍ ደግሞ ማርክስና ኤንግልስ የሠራተኛው መደብ አካልና ግንባር ቀደም ኃይል የሆነውን የኮሚኒስት ፓርቲን ታሪካዊ ሚና በግልጽ አሳይተዋል ። በዚህም የኮሚኒስቶች የአጭር ጊዜ ዓላማ የወዝአደሩን መደባዊ አቋም ማጠናከር ፣ የቡርዧዚውን የበላይነት መገርሰስና ወዝአደሩ የፖለቲካ ሥልጣን እንዲይዝ ማድረግ መሆኑን አስረድተዋል ። በተጨማሪም የወዝአደሩን የበላይ ገዥነት ጽንሰ ሐሳብ በማንሣት ኮሚኒስቶች ከቤተሰብና ከንብረት ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነትና እናት ሀገርን አስመልክቶ ሊኖራቸው ስለሚገባው አቋም በማብራራት ወዝአደሩ ሥልጣን ሲጨብጥ መወሰድ ስለሚገባው የኢኮኖሚ ርምጃ ዘርዝረዋል ።

"የሶሻሊስትና የኮሚኒስት ጽሑፎች" በሚለው ሦስተኛ ምዕራፍ አንጋፋዎቹ የወዝአደር መሪዎች በሶሻሊዝም ስም ቡርዧዚውና ንዑስ ከበርቴው በሚያራምዷቸው የተሳሳቱ አዝማሚያዎች ላይ ጠንካራ ትችት በማቅረብና በማውገዝ በተምኔታዊ ሶሻሊዝምና በኮሚኒዝም ላይ ያላቸውን አቋም ግልጽ አድርገዋል ። የመጽሐፉ የመጨረሻ ክፍል በሆነው "አሁን ባሉ የተለያዩ የተቃውሞ ፓርቲዎች ላይ የኮሚኒስቶች አቋም" በተሰኘው ርዕስ ሥርም እንደዚሁ የተቃውሞ ፓርቲዎችን አስመልክቶ ኮሚኒስቶች ሊከተሉት ስለሚገባው ታክቲክ ትክክለኛውን መንገድ ቀይሰዋል ። ኮሚኒስት ማኒፌስቶ በመደምደሚያው ላይ ቀድሞ "ሰዎች ሁሉ ወንድማማች ናቸው" የሚለውንና መደባዊ ይዘት የሌለውን የተምኔታዊ ሶሻሊስቶችን መፈክር "የሁሉም ሀገር ሠራተኞች ተባበሩ" በሚለው አብዮታዊ ጥሪ በመተካት ለወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት መሠረት ጥሏል ።

ባጠቃላይ ማርክሲዝም ለመጀመሪያ ጊዜ በተቀነባበረና በተዋሀደ መልክ የሠፈረው በኮሚኒስት ማኒፌስቶ ውስጥ ሲሆን ሠራተኛው መደብ ለሶሻሊዝም በሚያደርገው ረዥምና ውስብስብ ትግል ሊከተለው ስለሚገባው ስትራቴጂና ታክቲክ እንዲሁም ሊወስዱ ስለሚገባቸው እርምጃዎች መሠረቱ የተጣለው በዚሁ ሰነድ ነው ። በዚ

ሀም ሠራተኛው መደብ በፓርቲው መሪነት
ካፒታሊዝምን የሚያጠፋበትንና ፍትሀ ፤
ነፃነት ፤ እኩልነትና ብልጽግና የሰፈነበት
የኮሚኒስት ኅብረተሰብ የሚገነባበትን መን
ገድ በግልጽ ያመለከተ መመሪያ ነው ።
በውስጡም የሠፈሩት ሳይንሳዊ መርሆች
ለእያሌ ዓመታት በተግባር የተፈተኑና ዛሬም
ለዓለም አቀፉ የሠራተኛው መደብና የኮሚ
ኒስት ንቅናቄ ሳይንሳዊ የተግባር መመሪያን
ታቸው የተረጋገጠላቸው ናቸው ።

## ኮሚኒስት ክፍፍል መርህ (የ—)

*(Principle of Communist Distribution)*

የኮሚኒስት ክፍፍል መርህ ‘‘ከእያንዳንዱ
እንደችሎታው ለእያንዳንዱ እንደፍላጐቱ’’
የሚል ነው ። ወደዚህ የኮሚኒስት ክፍፍል
መርህ ለመድረስ በተቀዳሚ የምርት ኃይሎች
እጅግ ከፍተኛ የሆነ የዕድገት ደረጃ ላይ
መድረስና የኅብረተስቡን ቁሳዊና ባህላዊ
ፍላጐት ለማሟላት የሚያስችል የተትረፈረፈ
ምርት መኖር አለበት ። ይህ ወቅት ሥራ
እንደ ችሎታ መሥራት በግዳጅና የተወሰነ
ጥቅምን ለማግኘት ሳይሆን እንደባህል የሚ
ወሰድና የኅብረተሰቡ አባሎች ሥራን መሥ
ራት የሕይወት ተቀዳሚ ፍላጐት እንደሆነ
አድርገው የሚቆጥሩበት የዕድገት ደረጃ ነው።

‘‘ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያን
ዳንዱ እንደ ፍላጐቱ’’ የሚለው መርህ ተፈ
ጻሚነት የሚኖረው በኮሚኒስት የዕድገት
ደረጃ ቢሆንም ከሶሻሊስት የክፍፍል መርህ
ጋር ጐን ለጐን በመሄድ ቀስ በቀስ ሥራ
ላይ የሚውል ነው ። ይህም የሚሆነው ከሶሻ
ሊዝም ወደ ኮሚኒዝም በሚደረገው ዕድገት
አብዛኛው ቁሳዊና ባህላዊ ሀብት ለኅብረተሰቡ
አባላት የሚከፋፈለው በሥራ መጠንና
ጥራት ብቻ ሳይሆን ከዚህም ባሻገር እንደ
ቤት ፤ እንደ ሕክምና ፤ እንደ ትምህርት ፤ እንደ
ሕፃናት መንከባከቢያ ተቋሞችና እንደ መዝ
ናኛ በመሳሰሉት በነፃ የመጠቀም መብት
በመኖሩ ነው ።

(የሶሻሊስት ክፍፍል መርህን ይመለከ
ቷል ።)

## ኮሚኒዝም

*(Communism)*

የሶሻሊዝም ከፍተኛው ደረጃ ፤
የምርት ማከናወኛዎች በሙሉ በሕ
ዝብ ይዞታ ሥር የሚገኙበት ፤ የኅብረተሰቡ
አባላት በሙሉ ማኅበራዊ እኩልነት የሚቀ
ዳጁበት መደብ አልባ ማኅበራዊ ሥርዓት
ነው ። በታሪክ ከታዩት ዋና ዋና ማኅ
በራዊ ሥርዓቶች ውስጥ በጣም ያደገና የዳ
በረ ፤ ከማኅበራዊ ቅራኔዎች በተለይም ከተ
ፃራሪ ቅራኔዎች ነፃ የሆነ ፤ በሰዎች መሀከል
የሚፈጠሩት ግንኙነቶች ከብዝበዛና ከጭቆና
የተላቀቁበት ፤ በትብብርና በጋራ ጥቅም ላይ
የሚመሠረት ሥርዓተ ማኅበር ነው ።

እንደ ሶሻሊዝም የንብረት ይዞታ በመ
ንግሥትና በኅብረት እርሻ የተከፋፈለ ሳይ
ሆን ንብረት በሙሉ በሕዝብ ይዞታ ሥር
የሚገኝበት በመሆኑ በሠራተኛው መደብ ፤
በኅብረት አራሹና በምሁሩ መሀከል ያሉት
ማኅበራዊ ክፍፍሎች የሚያከትሙበት ነው ።
ይህ የኅብረተሰቡ ክፍፍል የሚከስምበት
ምክንያት የምርት ኃይሎች በጣም ከፍተኛ
ደረጃ ላይ በመድረሳቸውና ሥራም የፍጆታ
መለኪያነቱ አብቅቶ ‘‘ከያንዳንዱ እንደ ችሎ
ታው ለያንዳንዱ እንደ ፍላጐቱ’’ የሚለው
መርህ ተግባራዊ ስለሚሆን ነው ። እያንዳንዱ
ዜጋ ከፍተኛና የተሟላ ዕውቀት የቀሰመና
የአእምሮአዊ ችሎታው የዳበረ በመሆኑ
የኅብረተሰቡ የምርት ደረጃ ከዕለት ፍጆታ
በማለፍ ማናቸውንም የሰው ፍላጐት በተሟላ
መንገድ የሚያረካ ነው ። የምርት ኃይሎች
ከፍተኛ ደረጃ ላይ ከመድረሳቸው የተነሣ
በሶሻሊዝም የነበሩት የሸቀጥና የገንዘብ ግን
ኙነቶች ጠፍተው ማኅበራዊ ሀብት በቀጥታ
እንዲከፋፈል ይደረጋል ።

ኮሚኒዝም የዳበሩ የምርት ኃይሎች
የሚገኙበት ሳይንስ ፤ ቴክኖሎጂ ፤ ባህልና
ኮሚኒስታዊ የራስ በራስ አስተዳደር የሚስፋ
ፋበት በመሆኑ ከፍተኛ ማኅበራዊ ሥርዓት
ነው ። ሥራ የደስታ ምንጭ በመሆን እያን
ዳንዱ ለሁሉም ፤ ሁሉም ለእያንዳንዱ ጥቅምና
ዕድገት በማሰብ በከፍተኛ ፍላጐት ፤ በንቁ
ተሳትፎና ሥነ ምግባር ሁሉም ያመርታል ።
ሥራም የሕይወት ዋነኛና ከፍተኛ መርህ
ይሆናል ። እያንዳንዱ ዜጋ ነፃና ንቁ አምራች

የሚሆንበት ፥ ችሎታውንም ለሕዝቡ ከፍተኛ ግልጋሎት የሚያውልበት ሥርዓት ነው ።

የካፒታሊስቱ ሥርዓት በግል ይዞታ ላይ የተዋቀረ በመሆኑ የአምራቹ የሥራ ውጤት የሆኑት የማምረቻ መሣሪያዎች መልሰው በአምራቹ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖና ቁጥጥር ያሳድራሉ ። አምራቹ የማሽኑ ተቀጥላ በመሆኑ ሰብ እናውን እንዲያጣ ከመደረጉም በላይ ከማሽኑ ፍጥነት ጋር እኩል እንዲንቀሳቀስ ስለሚገደድ የማሽኑ ተገዥ ነው ። በኮሚኒዝም ፥ ውስጥ ግን ማሽኑ አምራቹን የሚታዘዝ ፥ በአምራቹ ቁጥጥር ሥር የሚሆንና እርሱንም የሚያገለግል በመሆኑ አምራቹ ከፍተኛ ሰብእናን ይጐናፀፋል ። የማምረት ብቃቱም የዳበረ በመሆኑ በሥራ ላይ የሚያሳልፈው ጊዜ ስለሚያንስ የመዝናኛ ጊዜው ከፍተኛ ይሆናል ። ይህም ችሎታውንና ልምዱን ፥ እእምሮታዊ ደረጃውን ይበልጥ ለማዳበር በቂ ዕድል ይከፍትለታል ።

ከላይ የተዘረዘሩት በኢኮኖሚ ዘርፍ የሚታዩ ለውጦች በላዕላይ መዋቅሩም ውስጥ ለውጥ ያስከትላሉ ። በኮሚኒስት ሥርዓት ውስጥ ፖለቲካዊና ሕጋዊ ተቋሞች እንዲሁም ከነርሱ ጋር ተዛምደው የሚገኙት ፖለቲካዊና ርዕዮተዓለማዊ ክስተቶች ይከስማሉ ። በዚህ ጊዜ ሰዎች አንድ ወጥነትና ተቀባይነት ባላቸው በኮሚኒስታዊ የሥነ ምግባርና የአኗኗር ደንቦችና መርሆች ይመራሉ ። መንግሥትና ፓርቲም ታሪካዊ ተልዕኮአቸውን በመፈጸማቸውና አስፈላጊ የሚያደርጓቸው ማኅበራዊና ታሪካዊ የመደብ ሁኔታዎች በመጥፋታቸው ይከስማሉ ።

ኮሚኒዝም የጉልበትንና የአእምሮን ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል ፥ በገጠርና በከተማ መሀከል ያሉትን ልዩነቶች ያጠፋል ። በብሔሮችም መሀከል የሚታዩ ልዩነቶች እየጠፉ ስለሚሄዱ የልዩ ልዩ ሀገሮች ብሔራዊ ወሰን የሚጠፋበት ፥ እያንዳንዱ ግለሰብም የዳበረና የተሟላ ሰብእና የሚያገኝበት ፥ መንፈሳዊ ሀብትን ከሥነ ምግባራዊ ጥራት ጋር ያቀናጀ በመሆኑ በኅብረተሰቡና በግለሰቡ መሀከል የተጣጣሙ ግንኙነቶች የሚፈጠሩበት ሥርዓት ነው ። በተጨማሪም ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍልና ከርሱም ጋር ተዛምደው የሚገኙት መደቦች በመክሰማቸው የኮሚኒስት ሥርዓት የዕድገት መሠረት በሰው (በኅብረተሰብ) እና በተፈጥሮ መሀከል ያለውን ቅራኔ ለመፍታት የሚደረገው በዕቅድ ላይ የተመሠረተ ትግል ይሆናል ።

( ሶሻሊዝምን ይመለከቷል ። )

## ኮሚንፎርም

*(Comminform)*

የኮሚኒስቶችና የሠራተኞች ፓርቲዎች የመረጃ ቢሮ በመባል ይታወቃል ። ድርጅቱ ከ1947 -1956 የብዙዎች የኮሚኒስትና የሠራተኛ ፓርቲዎች ማዕከል በመሆን አገልግሏል ። ዓላማውም በኮሚኒስት ፓርቲዎች መካከል የልምድ ልውውጥን ማደራጀትና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም እንቅስቃሴያቸውን ማቀናጀት ነበር ።

የመረጃ ቢሮው የተቋቋመውም በ1947 መስከረም ወር መጨረሻ በፖላንድ ውስጥ በተደረገው የኮሚኒስቶችና የሠራተኞች ፓርቲዎች ስብሰባ ነበር ። ከ1948 - 1949 በተከታታይ በተለያዩ ሀገሮች ባካሄዳቸው ስብሰባዎች ስለመረጃ ልውውጥንና የፓርቲዎችን እንቅስቃሴ ስለማቀናጀት ፥ ሰላምን ስለመጠበቅና በጦርነት ቆስቋሾች ላይ ትግልን ስለማካሄድ እንዲሁም ስለሠራተኛው መደብ ኅብረትና የኮሚኒስትና የሠራተኛ ፓርቲዎች ተግባራትን በሚመለከት ብዙ ውሳኔዎችን አስተላልፏል ።

ጽሕፈት ቤቱ (ከ1947 - 48) በቤልግሬድ ፥ ቀጥሎም በቡካሬስት (ከ1947-1956) ነበር ። በሚያዝያ ወር 1956 እንቅስቃሴውን አቆመ ።

(ሦስተኛው ኢንተርናሽናልን ይመለከቷል ።)

## ኮሚዩናርድ

*(Communard)*

በ1871 በፓሪስ ተቋቁሞ ለነበረው ለፓሪስ ኮሚዩን መሪዎችና ተከታዮች የተሰጠ መጠሪያ ነው ። የሠራተኛው ትክክለኛ አመፅ በሆነው በፓሪስ ኮሚዩን ንቅናቄ የተካፈሉት የፈረንሳይ ዜጎች ብቻ ሳይሆኑ የአንደኛው ኢንተርናሽናል መሪዎችና የብዙ የአውሮፓ

ሀገሮች ሠራተኞች ነበሩ ፡፡ የፓሪስ ኮሚዩን ከወደቀ በኋላ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኮሚ ዩናርዶች ተይዘው ታሥረዋል ፡፡ ብዙዎችም በአድኃሪው የቡርዧ መንግሥት የሞት ቅጣት ተፈጽሞባቸዋል ፡፡ የቀሩት በልዩ ልዩ የአውሮፓ ሀገሮችና በሌሎችም የዓለም አካባቢዎች በስደት ተንከራትተዋል ፡፡

(የፓሪስ ኮሚዩንን ፣ አንደኛው ኢንተርናሽናልን ይመለከቷል ፡፡)

## ኮምሶሞል

*(Komsomol)*

የሶቭዬት ኅብረት ሌኒናዊ የወጣት ኮሚኒስቶች ድርጅት ነው ፡፡ በሶቭዬት ኅብረት ኮሚኒስት ፓርቲ መመሪያና ዓላማ ሥር ፣ በመላው ሶቭዬት ኅብረት ውስጥ ያሉትን ወጣቶች የሚያስባስበው ይህ ድርጅት በሌኒን አነሣሽነትና በወጣት ሠርቶ አደሮች ቀስቃሽነት ጥቅምት 29 ቀን 1918 በተደረገው የመጀመሪያው ጉባኤ ተመሠረተ ፡፡ በሐምሌ ወር 1926 ለሶቭዬት ኅብረት ወጣቶች በማኅበር መደራጀት ከፍተኛ ጥረት ያደረገውን የቭላዲሚር ኢሊዬች ሌኒንን ስም በመውረስ የመላው ሌኒኒስት የወጣት ኮሚኒስቶች ሊግ (ኮምሶሞል) ተባለ ፡፡

ኮምሶሞል የሶቭዬት ኅብረት ወጣቶች ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን የሚያጠኑበት ፣ ንድፈ ሐሳብን ከተግባር የሚያዋህዱበትና በአጠቃላይ በኮሚኒስታዊ ሥነ ምግባር የሚታነፁበት ድርጅት ሲሆን ፣ አባል ለመሆን የሚችሉትም ዕድሜአቸው ከ14-28 ዓመት የሆናቸው ወጣቶች ናቸው ፡፡

የኮምሶሞል አባል የሚሆን ማንኛውም የሶቭዬት ኅብረት ወጣት የሩሲያ የወጣት ኮሚኒስት ሊግ ፌደሬሽን ስድስተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ያስተላለፈውን መግለጫ (ማኒፌስቶ) የተቀበለ መሆን አለበት ፡፡ በማኒፌስቶው ውስጥ የሰፈረው ዓላማ በሶቭዬት ኅብረት ውስጥ ሠራተኛውን በጠቅላላው ከወጣቱ ግንባር ቀደም መሪ ከኮምሶሞል ጋር በአንድ ፍላጐትና በጽኑ ቁራጥነት ማስተባበር ፣ መኖር ፣ መሥራት ፣ መማርና በሌኒኒስት መሥመር በመታገል የሌኒንን መመሪያዎች በሥራ ማዋል ነው ፡፡

በዚህ መሠረት ኮምሶሞል በማንኛውም ጉዳይ የኮሚኒስት ፓርቲው ተቀዳሚ ደጋፊና የፓርቲው የወደፊት አባላት መሠልጠኛና መገኛ ነው ፡፡

የኮምሶሞል አሠራር እንደፓርቲ ሁሉ የዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን መርህ የተከተለ ሲሆን በድርጅታዊ መዋቅር የመጨረሻው የበላይ አካል ጠቅላላው ጉባኤ ነው ፡፡

ኮምሶሞል አብዮታዊና ኮሚኒስታዊ ተግባሩን በሶቭዬት ኅብረት ውስጥ ብቻ ሳይወስን ከሶሻሊስትና ከካፒታሊስት ሀገሮች ታጋይ ወጣቶች ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር በፀረ ኢምፔሪያሊስት ፣ በፀረ ቅኝ አገዛዝና በፀረ ዘረኝነት አቋም ለጭቁን ሕዝቦች አርነት ይታገላል ፡፡ ከዓለም የወጣት ዲሞክራሲያዊ ኅብረትና ከዓለም አቀፍ የተማሪዎች ፌደሬሽን ጋር የትግል አንድነት በመመሥረት ዓለም አቀፍ ግዴታውን በመወጣት ላይ ይገኛል ፡፡

## ኮስሞፖሊታኒዝም

*(Cosmopolitanism)*

ብሔራዊ ባህልንና ልምዶችን ፣ ሀገር ወዳድነትን ፣ የመንግሥታዊና የብሔራዊ ልዕልናን አስፈላጊነት የማይቀበልና የዓለምን መንግሥት ወይም ዜግነት የሚሰብክ አድኃሪ የቡርዧ ርዕዮተዓለም ገጽታ ነው ፡፡

በታሪክ እንደታየው የኮስሞፖሊታኒዝም ባሕርይ በተለያየ መልኩ ሲንፀባረቅ ቆይቷል ፡፡ በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት ውስጥ በጥንታዊት ግሪክ የትልቁ እስክንድርን መንግሥትና ከዚያ በኋላ የሮማን ግዛት አፄ በማመልከት መላው የዓለም ሕዝብ በአንድ ተመሳሳይ በሆነ ሕግ መገዛት አለበት የሚል ይዘት ነበረው ፡፡ በፊውዳሊዝም ወቅት ደግሞ የነበረውን የፊውዳል ክፍፍል አስወግዶ የዓለም መንግሥትና ዜግነት የመፍጠር ዓላማ ይዞ ተነሥቷል ፡፡ የቡርዧ ኮስሞፖሊታኒዝም ደግሞ ከካፒታል ባሕርይ ጋር የተያያዘና ቡርዧዚውም የበለጠ ትርፍ ለማግኘት ካለው ዓላማ የመነጨ ነው ፡፡ የቡርዧ ኮስሞፖሊታኒዝም የጨቋኝ ብሔርን ተፅዕኖ የሚያወግዝ ሳይሆን እንዲያውም ከጨቋኝነት ፍላጐት የሚመነጭ ነው ፡፡ በኢምፔሪ

ያሊዝም ወቅት ካፒታል የበለጠ ዓለም አቀፋዊ ባሕርይ እየያዘ ስለሚሄድ የኮስሞፖሊታኒዝም አስተሳሰብም ይህንኑ ተጨባጭ ሁኔታ ያንፀባርቃል ።

በአሁኑ ጊዜ የኮስሞፖሊታኒዝም አስተሳሰብ ለሰው ልጅ ደኅንነት ቆመናል የሚሉ ሰላም አክራሪዎችም እያራመዱት ነው ። አንድ የዓለም መንግሥት ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ የተቋቋመ ፌደሬሽን ይመሥረት ከሚል ዓላማ በመነሣት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ወደዓለም መንግሥትነት ይለወጥ ይላሉ ። ዛሬ በዓለም የተለያዩ ሥርዓተ ማኅበሮች የሚከተሉ መንግሥታት እያሉና ለብሔራዊና ለማኅበራዊ ነፃነት በየበታው ሕዝቦች በመታገል ላይ እያሉ አንድ የዓለም መንግሥት ይቋቋም የሚለው ሐሳብ ተምኔታዊ ነው ።

ወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነትና የቡርዧ ኮስሞፖሊታኒዝም ተፃራሪ ናቸው ። ኮስሞፖሊታኒዝም የሀገሮችን ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ ሳያጤን የግድ መዋሃድ አለባቸው ሲል ማርክሲዝም ግን ይህ ሊሆን የሚችለው የኮሚኒስት ሥርዓት ማለትም ጭቆናና ብዝበዛ የሌለበት ሥርዓት በመላው ዓለም ቀስ በቀስ ሲመሠረት ነው በማለት ያስተምራል ።

(ወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነትን ይመለከቷል።)

## ኮርፖሬሽን
*(Corporation)*

የተወሰኑ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በአንድ ላይ በመሆንና በአንድ ስም ሥር በመደራጀት ከአንድ በላይ የሆኑ የኢኮኖሚ ድርጅቶችን የሥራ እንቅስቃሴ የሚመሩበትና ከሥራ እንቅስቃሴውም አንፃር የሚገኘውን ጥቅም በተወሰነ ደንብ መሠረት የሚከፋፈሉበት ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ነው ። ከዚህም የተነሣ ለመክሰስና ለመከሰስ ፣ ንብረት ለመያዝ ፣ ለመበደር ፣ ለማበደርና ለመዋስ ይችላል ። በአንድ ኮርፖሬሽን ሥር ያሉ ድርጅቶች ያላቸውን ካፒታልና የሰው ኃይል በማቀናበር ሰፋፊ ሙአለ ንዋዮችን ሥራ ላይ በማዋል የተለያዩና የተያያዙ የኢኮኖሚ የሥራ እንቅስቃሴዎችን ያከናውናሉ ። ለምሳሌ አንድ ኮርፖሬሽን የንግድ ፣ የምርትና የአገልግሎት ሥራ እንቅስቃሴዎችን በማቀናጀት ሊያከናውን ይችላል ።

በአውሮፓ ውስጥ በመካከለኛው ዘመን ኮርፖሬሽኖች የነጋዴዎችና የእደ ጥበብ ባለሙያዎች ድርጅት በመሆን አገልግለዋል ። በዚህ ሁኔታም በተለይ በወቅቱ ለሞኖፖሊያዊ የንግድ ሥራ ጠቃሚ መሣሪያ ነበሩ ። በካፒታሊዝም በተለይም በሞኖፖል ካፒታሊዝም ወቅት ኮርፖሬሽኖች በጋራ አክሲዮን ማኅበር መልክ በመዋቀር ለካፒታሊስት ኢኮኖሚ መዳበር ፣ ለካፒታል መማከልና መከማቸት ከፍተኛ መሣሪያ ሆነዋል ። በአሁኑ ጊዜም ድንበር ዘለል ኩባንያዎችና ባለብዙ ብሔር ኩባንያዎች በኮርፖሬሽን መልክ ተደራጅተው ከፍተኛ የትርፍ ማጋበስ እንቅስቃሴ በካፒታሊስቱ ዓለም ውስጥ በማካሄድ ላይ ይገኛሉ ። እነዚህ ኮርፖሬሽኖች ትልቅ የካፒታል ይዞታ ፣ የብዙ የምርትና የአገልግሎት ድርጅቶች ባለቤትነት ስላላቸው እነዚህን የጥቅም ማግኛ አውታሮች በመዘርጋት በተለይ የካፒታሊስት የዕድገት ጐዳናን በሚከተሉ ኋላቀር ሀገሮች ውስጥ ከፍተኛ ትርፍ በየቀኑ ያገኛሉ ። የኢኮኖሚ ጥቅሞቻቸውንም ለማስከበር ልዩ ልዩ የፖለቲካ ተፅዕኖዎች ያደርጋሉ ።

በሀገራችን ኮርፖሬሽኖች በመባል የሚታወቁት ተቋሞች በሥራቸው የተወሰኑ የምርትና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን በአንድ ላይ በማቀፍ የተመሠረቱ ተቋሞች ናቸው ። በዚህም ሁኔታ በአንድ ኮርፖሬሽን ሥር የታቀፉት ድርጅቶች በውስጣቸው አንድ ዓይነት የሥራ አመራርና ቅልጥፍና እንዲኖራቸው ከማስቻሉም በላይ በተቀራራቢ የምርትና የአገልግሎት ሥራ መስኮች የተሰማሩትና በአንድ ኮርፖሬሽን ሥር የተዋቀሩት ድርጅቶች በጋራ የሚያስፈልጋቸውን ጥሬ ዕቃ እንዲያገኙ ፣ የገበያ ቅንጅት እንዲኖራቸውና በአንድ ወጥ ማዕከላዊ አመራር ሥር እንዲተዳደሩ ያስችላል ። በተጨማሪም የዚህ ዓይነቱ አወቃቀር ለምርታማነት ዕድገት ተስማሚ ሁኔታን የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ ለማዕከላዊ ዕቅድ አፈጻጸም ለሚደረግ ክትትልና ቁጥጥር አመቺ ነው ።

በሶሻሊስት ሀገሮች ውስጥ ኮርፖሬሽኖች ኢንተርፕራይዝ በመባል ይጠራሉ ።

እነዚህም ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው የመንግሥትና የኅብረት ኢንተርፕራይዞች ናቸው ። የመንግሥት ኢንተርፕራይዞች የሶሻሊስት መንግሥት የሚያቀርብላቸውን የቁሳዊና የፋይናንስ ንብረት ምርታማና ትርፋማ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ እንዲያውሉ ግዴታ ያለባቸው ድርጅቶች ናቸው ። የመንግሥትም ሆኑ የኅብረት ይዞታ ኢንተርፕራይዞች እርስ በርሳቸው ሕጋዊ ውልና ስምምነት የማድረግ መብት ያላቸው ሲሆን ፣ ግዴታቸውንም የማሟላት ኃላፊነት አለባቸው ።

(የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ይመለከቷል።)

## ኮርፖሬት መንግሥት (የ—)

*(Corporate State)*

ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በአጠቃላይ በካፒታሊዝም ቀውስ መካከል ያደገ እጅግ ፋሺስታዊና አድኃሪ የሆነ የቡርዧው የበላይ ገዥነት አንዱ መልክ ነው። ቀደም ያለ ምንጩ ግን የኢንዱስትሪ አብዮትን ለመግታት ሲባል ከሃይማኖት ወገኖችና ከወግ አጥባቂዎች የታየ ዝንባሌ መሆኑ ይታመናል ። በሮማው ሊቀ ጳጳስ በሊዮ አሥራ ሦስተኛ በ1891ና በፒዩስ አሥራ አንደኛ በ1931 የወጡት ሃይማኖታዊ መመሪያዎች ይህንኑ ይጠቁማሉ ።

የኮርፖሬት መንግሥት የሠራተኛና የሙያ ማኅበራትን በማፈረስ ሕዝቡን ካፒታሊስቶች፣ ሠርቶ አደሮች፣ የቢሮ ሠራተኞች ወዘተ ... በሚባሉ ኮርፖሬሽኖች ይከፋፍለዋል ። እንደዚሁም በሕዝብ የሚሰየመውን ፖርላማ በመበተን "የኮርፖሬት ውክልና" በሚል ይተካዋል ። የዚህም ውጤት ሠርቶ አደሩ የሲቪል መብቱን ማጣት ሲሆን በኮርፖሬሽኖች መሣሪያነት በሞኖፖሎች የሚፈጸምበት ብዝበዛ ከወትሮው የከፋ ይሆናል ። ፋሺስት ኢጣሊያና የሳላዛር ፖርቱጋል ኮርፖሬት መንግሥታት መሆናቸው ታውጆ ነበር ። የጀርመን ብሔራዊ ሶሻሊዝም ሌላው ኮርፖሬት መንግሥት ነበር ።

የኮርፖሬት መንግሥት ዋና ዓላማ በፋሺስት መንግሥት ሥርና በኮርፖሬት መዋቅር ውስጥ "የመደቦች ሽርክና ወይም የጥቅም ስምምነት" ያለ በማስመሰል የሞኖፖል ካፒታል የበላይ ገዥነትን በመሸፋፈን ማስገንበት ነው ። ከዚህ ጋር ካፒታል በጉልበት ላይ ያለውን ፍጹም ተቆጣጣሪነት ማጠናከር ነው ። ይህንንም ከኮርፖሬት መንግሥት ደንቦች በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል ። ለምሳሌ በ1927 በወጣው የፋሺስት ኢጣሊያ ቻርተር ውስጥ "የግላዊ የምርት ድርጅት ተግባር ብሔራዊ ጉዳይ ስለሆነ የሥራ ድርጅት ባለቤት የምርትን አቅጣጫ በሚመለከት ከመንግሥት መመሪያ የመቀበል ኃላፊነት አለበት ። ተቀጣሪው በንቁ ተሳትፎ ከድርጅቱ ጋር መተባበር ሲኖርበት ድርጅቱን የመምራት ሙሉ ኃላፊነት ያለው አሠሪው ነው "የሚል አንቀጽ ይገኝበታል።

በሌላ አገላለጽ በኮርፖሬት መንግሥት አሠሪው ወይም ካፒታሊስቱ ሠርቶ አደሩን በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር አውሎ እንደፈለገ የሚበዘብዝበት ሕጋዊ ሥልጣንና መሣሪያ አለው ማለት ነው ። ስለዚህም ነው ኮርፖሬት መንግሥት የሞኖፖል ካፒታል የበላይ ገዥነት የመጨረሻው አስከፊ ገጽታ ነው የሚባለው ።

(ፋሺዝምን ፣ መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝምን ይመለከቷል ።)

## ኮንሰርን

*(Concern)*

በልዩ ልዩ የኢኮኖሚ መስኮች የተሰማሩ የካፒታሊስት ድርጅቶች በከፍተኛ ደረጃ ኅብረት በመፍጠር የሚመሠርቱት የሞኖፖል ቅርፅ ነው። የኮንሰርን አመሠራረት ልዩ ልዩ ገጽታ ሊኖረው ይችላል ። አንደኛ አንድን ሸቀጥ በማምረት አልፎም በማሰራጨት ሂደት ውስጥ በልዩ ልዩ ደረጃዎች ማለትም በመጀመሪያ ደረጃ የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን ከማምረት ጀምሮ ለፍጆታ ዝግጁ የሆነውን የሸቀጥ ዓይነት እስከማምረትና ለፍጆታ እስከ ማቅረብ ድረስ ባሉ ደረጃዎች የተሰማሩ የኢኮኖሚ ድርጅቶች ኅብረት ሊፈጥሩ ይችላሉ ። ለምሳሌ በነዳጅ ማውጣት በነዳጅ ማጣራት ስው ሠራሽ

ጐማ ፥ ፕላስቲክና ማዳበሪያ እንዲሁም ሌሎች
ከነዳጅ ማጣራት ጋር የተያያዙ የምርት ዓይ
ነቶችን በማምረትና በማሰራጨት ተግባር
የተሰማሩ ድርጅቶች በማበር ኮንሰርን ሊመ
ሠርቱ ይችላሉ ። ሁለተኛ በምርት ሂደት
ውስጥ ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸውን
ወይንም ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውንና የሌላ
ቸውን ሸቀጦች የሚያመርቱና ግልጋሎቶ
ችን የሚሰጡ ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ድርጅቶች
እንደዚሁ ኅብረት በመፍጠር ኮንሰርን የሚ
መሠርቱበት ሁኔታ አለ ። ለምሳሌ በልዩ ልዩ
የኢንዱስትሪ ክፍሎች በባንክ ፥ በመድን ፥
በንግድና በመገናኛ የተሰማሩ ልዩ ልዩ
የኢኮኖሚ ድርጅቶችን ያቀፈ ኮንሰርን ለመ
መሥረት ይቻላል ።

ኮንሰርን በመጀመሪያ ጊዜ የተመሠረ
ተው ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ጀር
መን ውስጥ ነው ። ኋላም በሌሎች ሀገሮች
በብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎች ፥ ድንጋይ
ከሰልንና ነዳጅን በሚያመርቱ ኢንዱስትሪ
ዎችና በሌሎችም ኢንዱስትሪዎች የምርት
መሰባሰብ እያደገ ከመምጣቱ ጋር ኮንሰር
ንም እየዳበረ መጣ ። ባሁኑ ጊዜ የአንድ ኮን
ሰርን አባል ድርጅቶች የሚሰማሩባቸው የኢ
ኮኖሚ መስኮች እጅግ በርካታ ሊሆኑ ከመቻ
ላቸውም በላይ ኮንሰርን በኢምፔሪያሊስት
ሀገሮች ዋነኛው የሞኖፖል ቅርፅ ሊሆን
ችሏል ።

አንድ ወይንም ጥቂት ትላልቅ የፋይና
ንስ ካፒታሊስቶች የኮንሰርን አመራርን ይይ
ዙና አባል ድርጅቶችን በቁጥጥራቸው ሥር
ያደርጓቸዋል ። አንዳንዴም በልዩ ልዩ አባል
ድርጅቶች ውስጥ ባለው የአክሲዮን መጠን
አማካይነት ድርጅቶችን በቁጥጥሩ ሥር
ለማዋል ለየት ያለ ኩባንያ (ሆልዲንግ ካም
ፓኒ) ተቋቁሞ እነዚሁ ጥቂት ትላልቅ
የፋይናንስ ካፒታሊስቶች በዚሁ ኩባንያ
አማካይነት የኮንሰርኑን እንቅስቃሴ ይመራሉ ።
ያም ሆነ ይህ በኮንሰርን አማካይነት አንድ
ትልቅ ካፒታሊስት ወይንም ቁጥራቸው ጥቂት
የሆኑ ትላልቅ ካፒታሊስቶች በከፊል ብቻ
በባለቤትነት ከያዙት ካፒታል በብዙ እጥፍ
የሚበልጥ ካፒታል በቁጥጥራቸው ሥር ያው
ላሉ ።

ኮንሰርን ልዩ ልዩ ሸቀጦችን በስፋትና
በተቀነባበረ መንገድ ማምረትን ፥ አዳዲስ
ቴክኖሎጂዎችን በሥራ ላይ ማዋልን ፥ አዳ
ዲስ የምርት ዓይነቶችን አምርቶ በገበያ ላይ
ማሰራጨትንና የመሳሰሉትን በመሥራት ለካፒ
ታሊስቶች ትርፍ ለመሰብሰብ አመች ሁኔታን
ይፈጥራል ።

## ኮንት ፥ አጉስት
*(Comte, Auguste)*

ከ1798 - 1857 የኖረ ፥ የፈረንሳይ ሐሳ
ባዊ ፈላስፋ ሲሆን የተጨባጭዊነት ፍልስፍና
መሥራች በመሆን የታወቀ ነው ። ይህንኑ
ፍልስፍና በሚመለከት "ፖዘቲቭ ፊሎዞፊ"
በሚል ርዕስ አምስት ተከታታይ መጻሕፍት
ደርሷል ።

ኮንት ከተፈጥሮ ጥናት ይልቅ ለሰው
ልጅ በይበልጥ ጠቃሚነት ያለው የኅብ
ረተሰብ ጥናት መሆኑን የሚያምን ስለነበር
ካሉት ሳይንሶች የበላይ አድርጎ የሚመለ
ከተው ሥነ ኅብረተሰብን ነበር ። ፍልስፍ
ናንም የሳይንሶች ውጤት አጠቃላይ ጥናት
በማለት ሰይሞታል ።

በሕይወቱ መጨረሻ አካባቢ ኮንት
"የሰው ልጅ ሃይማኖት" የሚል የሰው ዘር
የሚመለክበት አዲስ ሃይማኖት ለመመሥረ
ትና ለማሰራጨት ጥሮ ነበር ።

( ተጨባጭዊነትን ይመለከቷል ። )

## ኮንዲያክ ፥ ኤትየን ቦኖ ደ
*(Condillac, Etienne Bonnot de)*

ከ1715 - 1780 የኖረ ፥ የካቶሊክን ቤተ
ክርስቲያን በቅስና ያገለገለ፥በኋላም በአጠቃላይ
ዕውቀት ባደረገው በርካታ ምርምር ሃይማ
ኖትን ከሚቃወሙ መደምደሚያዎች ላይ የደ
ረሰ ፈረንሳዊ ሐሳባዊ ፈላስፋ ነው ።

የዕውቀትን ንድፈ ሐሳብ በሚመለከት
የሎክ ተከታይ ነበር ፤ ነገር ግን በሕዋ
ሳት ከሚገኘው ዕውቀት በተጨማሪ ነፀ
ብራቅ የዕውቀት ምንጭ መሆኑን አይቀበ
ልም ። በሰው ሕውስታና በውጫዊ ነገሮች
መካከል ያለውን ግንኙነት ባለመረዳቱና ፥
የነገሮችን መኖር ከዐዋቂው ኅሊና ግንዛቤ
እንፃር ብቻ በመመልከቱ የኅሊናዊ ሐሳባዊ
ነትን አመለካከት አራምዷል ።

ኮንዲያክ እንደሚያምነው ሕውሰታዎች በውጫዊ ነገሮች ይፈጠራሉ ፤ ነገር ግን በእነዚህ ሕውስቶችና በሕውሰት ፈጣሪ ውጫዊ ነገሮች መካከል የጋራ የሆነ ባሕርይ የለም ። በኮንዲያክ አስተሳሰብ አእምሮን ከውጫዊ ዓለም የሚያገናኘው ሕውስታ ብቻ እንደመሆኑ የአእምሮ ተደራጊ ሕውሰታዎች ጠቅላላ ድምር ነባራዊው ዓለም አይደለም ። የኮንዲያክ ሕውሰታዊነት በ18ኛው ምዕት ዓመት ለነበረው የፈረንሳይ ቁሰአካልነት ስፉ አስተዋጽኦ ነበረው ። ከዋና ዋና ድርሰቶቹ መካከል "ለ ትሬቴ ደ ሲስተም" ፣ (1749) «ለ ትሬቴ ደ ሳን ሳሲዎን» (1754) የተባሉት ይገኙበታል ።

(ሎከን ፣ ሕዋሰታዊነትን ይመለከቷል)

## ኮንፉሺያኒዝም
*(Confucianism)*

በኮንፊሽስ (ከክርስቶስ ልደት በፊት 551-479) ተቀምሮ በጥንታዊት ቻይና ውስጥ ከነበሩት በርካታ የፍልስፍና አዝማሚያዎች አንዱ የነበረና በፊውዳል ቻይናም ለረጅም ጊዜ የመሪነቱን ቦታ ይዞ የቆየ ሐሳባዊ አስተሳሰብ ነው ።

በኮንፊሺያኒዝም አስተሳሰብ መሠረት የሰው ዕድል (ዕጣ) በፈጣሪ የሚወሰን ሲሆን ሰዎች በሙሉ "ጨዋ" ወይም "ተራ" ናቸው ፤ ወጣቱ ለአዛውንቱ ወይም ለአንጋፋዎቹ ፣ የበታች ለበላይ መገዛትና እራሱን አሳልፎ መስጠት አለበት ። ከዕውቅ ተከታዮቹ ውስጥ አንዱ ሚንግ ዙ ሲሆን በርሱም አስተሳሰብ መሠረት በኅብረተሰብ ውስጥ ማኅበራዊ እኩልነት ያለመኖሩ ጉዳይ "በፈጣሪ ፈቃድ" የተነሣ ነው የሚል ነው። ሌላው ዕውቅ ተከታዩ ደግሞ ሁሱን ዙ ሲሆን በርሱም አመለካከት መንግሥተ ሰማይ የተፈጥሮ አካል እንጂ የራሱ ኀሊና የለውም የሚል ቁሰአካላዊ አስተምህሮ ለመቅረፅ ሞክሯል ። በእርሱም አስተሳሰብ የነገሮችን ሕግጋት ያወቀ ሰው የራሱን ጥቅም ለማስከበር በእነዚህ ሕግጋት መጠቀም ይኖርበታል ።

ባጠቃላዩ ሲታይ የኮንፊሺያኒዝም ዋና ሐሳብ በፈጣሪ ፈቃድ ሰም የበዝባዥ መደቦችን ጥቅም ማስከበርና ኅብረተሰብን ለአገዛዝ እንዲያመች ማድረግ ነው ።

## ኮንፌደሬሽን
*(Confederation)*

ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ መንግሥታት እርስ በርስ ለመረዳዳትና የጋራ መከላከያ ለመፍጠር የሚመሠርቱት ኅብረት ነው ። በኮንፌደሬሽን እያንዳንዱ አባል መንግሥት በራሱ የውስጥም ሆነ የውጭ ፖሊሲ ላይ የማዘዝ ሥልጣን አለው ። በዚህም ኮንፌደሬሽን የፖለቲካ አስተዳደር አንድነት በመፍጠር ከሚመሠረተው ፌደሬሽን ይለያል ። ፌደሬሽን የጠበቀ የፖለቲካ አንድነት ያለውና በውስጡ ባሉት አባል መንግሥታት ላይ ቀጥተኛ የሆነ ሥልጣን ሲኖረው ኮንፌደሬሽን ግን የዚህ ዓይነት ሥልጣን የለውም ።

በታሪክ በተለያዩ አካባቢዎችና ጊዜያት ኮንፌደሬሽኖች ተመሥርተዋል ። ለምሳሌ ከ1778 ጀምሮ አሜሪካ (ዩ.ኤስ.ኤ) ፌደሬሽን እስከሆነችበት እስከ1787 ድረስ በኮንፌደሬሽን ስትተዳደር ቆይታለች ። በጀርመንም ከ1815 እስከ 1866 የጀርመን ኮንፌደሬሽን ተመሥርቶ ነበር ። ኔዘርላንድም እንዲሁ ከ1580 እስከ 1795 በኮንፌደሬሽን ሥር ነበረች ። ስዊትዘርላንድ ግን ምንም እንኳ ዛሬም ኮንፌደሬሽን ብትባልም ወደ ፌደሬሽን የምትጠጋ ናት ። በኮንፌደሬሽን የተጠቃለሉ መንግሥታት የሚተባበሩና የጋራ መከላከያ በመፍጠር እርስ በርስ የማይዋጉ ቢሆንም እያንዳንዳቸው ነፃ ሕጋዊ ህልውናና ዓለም አቀፋዊ ተዐውቆ አላቸው ። ኮንፌደሬሽን ከፌደራላዊ ግንኙነት የሚለይበት አንዱም መንገድ ይህ ነው ።

(ፌደሬሽንን ይመለከቷል ።)

# ወ

## ወለድ
*(Interest)*

እንድ ሰው የተወሰነ ገንዘብ ለተወሰነ ጊዜ ተበድሮ በመጠቀሙ የሚያደርገው ክፍያ ሲሆን በካፒታሊስት ሥርዓት አበዳሪው ካፒታሊስት የሚያገኘው የተረፈ እሴት አካል ነው ። የገንዘብ ካፒታል እንቅስቃሴ በብድር መልክ ሲከናወን ለባለካፒታሉ በተወሰነ ጊዜ ከወለድ ጋር ይመለስለታል ። በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ተበዳሪው ካፒታሊስት የገንዘብ ካፒታሉን ወደ ምርታዊ ካፒታል በመቀየር ከሚያገኘው ተረፈ እሴት ውስጥ በገንዘቡ ከመጠቀሙ የተነሣ የተወሰነውን መጠን ለአበዳሪው ካፒታሊስት ከወለድ ጋር በመመለስ ይከፍላል ። ስለዚህም ወለድ የገንዘብ ካፒታል የመሸጫ ዋጋ ሆኖ ይቀርባል ።

ወለዱ የሚሰላው ለብድር ከተሰጠው የገንዘብ ካፒታል አንፃር ከመቶ እጅ ነው ፤ ለምሳሌ በመቶ ብር በአንድ ዓመት ውስጥ ለመጠቀም ብር 6.00 ከተከፈለ ወለዱ ስድስት በመቶ (6%) ይባላል ። ስለዚህም ወለዱ በዓመት ከመቶ ሒሳብ ተሰልቶ በወር ፣ በሦስት ወር ፣ በመንፈቅ ወይም ከዚህ በላይና በታች በሆነ ጊዜ ሊከፈል ይችላል ። በካፒታሊስት ሀገሮች መንግሥት የሞኖፖሊስቶች መሣሪያ በመሆን የወለድ መጣኔውን እንደ አመችነቱ ከፍና ዝቅ ያደርገዋል ። በካፒታሊዝም የወለድ መጣኔ በአማካይ ትርፍ አካባቢ የሚዋዥቅ ይሆናል ። ይህም በየጊዜው ከሚኖረው የብድር ካፒታል የአቅርቦትና የፍላጐት ሁኔታዎች ጋር የተያያዘ ነው ። በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ብድር የአጭር ወይም የረዥም ጊዜ ሊሆን ይችላል ።

በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ወለድ አምራች ድርጅቶች ያስገኙት የተረፈ ምርት አካል የሆነ ለባንኮች ወይም ለአስቀማጮች የሚደረግ ክፍያ ነው ። ወለድ የሚከፍሉት የሶሻሊስት የምርት ድርጅቶች ብቻ ሳይሆኑ ማንኛውም የሶሻሊስት ሀገር ዜጋ ከአበዳሪ ድርጅቶች ገንዘብ ተበድሮ ወለድ ይከፍላል ። በሶሻሊስት ኢኮኖሚም ገንዘብን በባንክ በማስቀመጥ ወለድ ይገኛል ። በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የወለድ መጣኔ በማዕከላዊ ደረጃ በመንግሥት የሚወሰን ነው ።

የሶሻሊስት ባንኮች ተበዳሪዎችን የሚጠይቁት ወለድ ባጠቃላይ የኢኮኖሚውን ልዩ ልዩ ዘርፎች እንቅስቃሴ ለማቀነባበርና የሥራ ቅልጥፍናን ለማሳደግ ፣ ብኩንነትን ለመቆጣጠር የሚረዳ ነው ።

## ወለድ መጣኔ (የ—)
*(Rate of Interest)*

የብድር ካፒታልን በማዳበር የሚገኘው ዓመታዊ ገቢና የተሰጠው ጠቅላላ የብድር ካፒታል ጥምርታ ነው ። ለምሳሌ አንድ መቶ ሺ ብር ካፒታል በብድር መልክ ቢሰጥና ይህንንም ብድር በመስጠት የሚገኘው ዓመታዊ የወለድ ገቢ አምስት ሺ ብር ቢሆን የወለድ መጣኔው አምስት በመቶ ይሆናል ማለት ነው ። ይህም በስሌት ሲሠራ ፡—

$$\frac{5,000}{100,000} \times 100 = 5\% \text{ ይሆናል ።}$$

በካፒታሊስት ኢኮኖሚ የወለድ መጣኔው የሚወሰነው በተወሰነ የገበያ ወቅት የገንዘብ ካፒታል በገበያው ውስጥ ባለበት የአቅርቦትና የፍላጐት ሁኔታና ከዚሁም ጋር በተያያዘ መንገድ በወቅቱ ባለው የአማካይ ትርፍ መጣኔው ነው ። ለምሳሌ በተወሰነ የገበያ ወቅት ብዙ ነፃ የገንዘብ ካፒታል ካለና ለብድር ካፒታል ደግሞ ያለው ፍላጐት አነስተኛ ከሆነ የወለድ መጣኔው ዝቅተኛ ይሆናል ። በተቃራኒው ደግሞ በተወሰነ የገበያ ወቅት ለብድር ካፒታል ያለው ፍላጐት ከፍተኛ ከሆነና አቅርቦቱ አነስተኛ ከሆነ የወለድ መጣኔው ከፍተኛ ይሆናል ።

የወለድ መጣኔ በተለይ የሚያድገው በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ድራት ወቅት ነው ።

ካፒታሊስቶች ሥራቸውንና ድርጅታቸውን በማስፋፋት በወቅቱ በገበያ ላይ ያለውን ከፍተኛ ትርፍ ለማግኘት በሚያስችል ሁኔታ ለመጠቀም ተጨማሪ የገንዘብ ካፒታል ይፈልጋሉ ። ይህንን ተጨማሪ የገንዘብ ካፒታል ለማግኘት የሚፈልጉ ካፒታሊስቶች በሚኖሩበት ወቅት አንዳንድ ካፒታሊስቶች ደግሞ በወቅቱ ለጊዜው ሥራ ላይ የማያውሉት የገንዘብ ካፒታል ይኖራቸዋል ። ለመሣሪያዎች ማደሻና መተኪያ የሚውለው ፣ ለደመወዝ ክፍያ የሚቀመጠው ለጊዜው ካፒታሊስቱ በትርፍ መልክ አግኝቶ ያስቀመጠው ገንዘብ ፣ በምርታዊ ሥራ ላይ ያልዋለ የገንዘብ ካፒታል ነው ። ይህን ሥራ ላይ ያልዋለ የገንዘብ ካፒታል ብድር የሚፈልጉ ካፒታሊስቶች ይበደሩታል ።

የካፒታሊስት ኢኮኖሚ በድራት ወቅት ውስጥ ሲገባ ለገንዘብ ካፒታል የሚኖረው ፍላጐት ከፍ ስለሚል የወለድ መጣኔውም ከፍ ይላል ። የወለድ መጣኔው በካፒታሊስት ኢኮኖሚ የቀውስ ወቅትም ቢሆን ያድጋል ። ምክንያቱም ካፒታሊስቶቹ ከኪሣራ አደጋ ለመዳን በሚያደርጉት ጥረት የገንዘብ ካፒታል ለመበደር ከፍተኛ ፍላጐት ስለሚኖራቸው ነው ። ሆኖም ከቀውስ ወቅት በኋላና የምርት ሁኔታ በዝቅጠት ደረጃ ላይ ሲከሰት የወለድ መጣኔው ዝቅ ይላል ። አጠቃላዩ የወለድ መጣኔ የማቆልቆል አዝማሚያ ያሳያል ። ይህም ከአማካይ ትርፉ መጣኔ በአጠቃላይ የመቀነስ ዝንባሌ ጋር የተያያዘ ነው ።

የካፒታሊስት ኢኮኖሚ የብድር ሥርዓት እየተስፋፋ ሲሄድና አበዳሪ ካፒታሊስቶችም እየበዙ ሲሄዱ የቡርዧ ኅብረተሰብን ልዩ ልዩ መደቦች ገቢና በቁጠባ መልክ የተጠራቀመ ገንዘብ አበዳሪ ካፒታሊስቶች በባንኮቻቸው ውስጥ ሰብስበው ወደ ብድር ካፒታል በመቀየር ከፍተኛ ጥቅም ያገኙበታል ። በአንዳንድ የካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ ያሉ ከፍተኛ የሞኖፖል ባንኮች ከሚያበድሯቸው ሌሎች ሀገሮች ከፍተኛ ወለድ በመጠየቅ ከፍተኛ ብዝበዛ ያካሂዳሉ ።

በሶሻሊስት ሀገሮች ውስጥ ባንኮች በመንግሥት ይዞታ ሥር ስለሆኑ የወለድ መጣኔያቸው በማዕከላዊ መንግሥት የሚወሰን ነው። ከዚህም በላይ የባንኮች የወለድ መጣኔ በማዕከላዊ ዕቅድ ተቀናብሮ የሚቀርብ ፣ የኢኮኖሚውን ውጤታማነት ፣ ቅልጥፍናና ምርታማነት ለማሳደግ የሚረዳ የመቆጣጠሪያ ስልት ሆኖ ያገለግላል ። የሶሻሊስት ሀገሮች ለኋላቀር ሀገሮች ለሚያበድሩት ካፒታል የሚጠይቁት የወለድ መጣኔ ዝቅተኛ ሲሆን በአብዛኛው የልማት ዕቅዶችን ለማስፈጸም የሚውል ነው ።

(ወለድን ይመለከቷል ።)

## ወላንድ

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ኩታ ገጠም በሆኑ ወልባዎች መካከል ለሚፈጠር ውህደት የተሰጠ ስያሜ ነው ።

የአምራች ኅብረት ሥራ ማኅበራት የቴክኖሎጂ ደረጃ አድጎ የማምረት ኃይላቸው ሲሰፋና በተወሰኑ የሥራ መስኮች ላይ ማተኮር አስፈላጊ እየሆነ ሲመጣ ያለውን የሰው ኃይልና ቁሳቁስ ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ማዋል እንዲቻል በወልባ ደረጃ የተቋቋሙት ማኅበራት ይዋሃዳሉ ። በዚህም ጊዜ የእያንዳንዱ ማኅበር የሕግ ሰውነት ተሰርዞ በውህደቱ ለተፈጠረው አዲስ አካል የሕግ ሰውነት ይሰጣል ።

እያንዳንዱ አምራች የኅብረት ሥራ ማኅበር የነበረው የማምረቻ መሣሪያና ንብረት በአንድ ማዕከላዊ አስተዳደርና አመራር ሥር ይውላል ። አንድ ወለንድ በአማ፣ ይ 4,000 ሄክታር ይዞታና 2,500 አባላት ይኖሩታል ። ወላንድ በተጨማሪም የአገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራትንም ተግባራት ያከናውናል ። ወላንድ በስፋትና በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ከፍ ያለ ስለሚሆን በሥሩ ልዩ ልዩ የቴክኒክ ክፍሎች ፣ የሒሳብና የአስተዳደር ሠራተኞች ይኖሩታል ።

(ወልባን ይመለከቷል ።)

## ወልባ

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ከፍተኛ የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበርን ለማመልከት የተሰየመ ቃል ነው ።

በወልባ ደረጃ በግል ይዞታ ሥር የነበሩት የእርሻ እንስሳትና መሣሪያዎች የጋራ ንብረት ሲሆኑ ለእያንዳንዱ አባል ቤተሰብ

ለጓሮ እርሻ ብቻ የሚሆን ከአንድ ሺ ካሬ ሜትር የማይበልጥ መሬት ይሰጣል ። በዚህ ደረጃ የማኅበሩ አባላት ከማኅበሩ ገቢ የሚያገኙት ድርሻ የሚመሠረተው በሚያበረክቱት የሥራ መጠንና ጥራት ስለሆነ "ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ፣ ለእያንዳንዱ እንደሥራው" የሚለው የሶሻሊስት የክፍፍል መርህ በሥራ ይተረጐማል ።

ወልባ በሚቋቋምበት ጊዜ አባላት ከሚኖራቸው ከአንድ ሺ ካሬ ሜትር ባልበለጠ የግል ይዞታ ላይ የጓሮ አትክልት መትከልና ጥቂት እንስሳት ማርባት ይችላሉ ። ይህንንም ማድረግ የሚቻለው የማኅበሩን ደኅንነት የማይፃረር መሆኑን ማኅበሩ አረጋግጦ ሲፈቅድ ብቻ ነው ።

(ማልባን ፣ ወላንድን ይመለከቷል ።)

## ወሳኛዊነት

*(Determinism)*

የፈቃድ ድርጊቶች ፣ የተፈጥሮና የሥነ ልቡና ሂደቶች ፣ ማኅበራዊ ክንዋኔዎች ፍጹም መንሥኤያዊ በሆኑ ግንኙነቶች የሚወሰኑ ናቸው የሚል አስተምህሮ ነው ። ይህም ማለት ማንኛውም ነገር መንሥኤ አለው ማለት ብቻ ሳይሆን የነገሮች አመጣጥና ምንነት ሙሉ በሙሉ የተወሰነ በመሆኑ ጨርሶ ሌላ ሊሆን አይችልም የሚል አመለካከት ነው ። ፍልስፍናው የመነጨው ከጥንት አቶማውያን ሲሆን በተፈጥሮ ሳይንስ ዕድገት አማካይነትም በ17ኛውና በ18ኛው ምዕት ዓመት ቁስአካላውያን ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ ነበር ።

ለወሳኛዊነት መነሻ የሆነውና በኋላም የከረረ አቋም እንዲይዝ ያደረገው ከሐሳባዊነት ጋር የነበረው ግጭት ነው ። ሐሳባውያን ዓለምና በውስጡ ያሉ ነገሮች ዲበ አካላዊና ግባዊ ከሆነ ፈቃድ እንደሚመነጩና የሰውንም ፈቃድ ባለሙሉ ሥልጣን አድርገው በማቅረባቸው ቁስአካላውያን ይህን አመለካከት ለመዋጋት ዓለምም ከፈቃድ እንዳልመነጨ ለማስረዳት ወደ ወሳኛዊነት አምርተዋል ። በተጨማሪም ተፈጥሮአዊ ሳይንስ ማንኛውም ክስተት ቁሳዊ መንሥኤ አለው በሚለው መላምት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የወሳኛዊነትን ፍጹማዊነትና ሁለንታዊነት እንዲያረጋግጥ ተደርጎ ተወስዷል ።

ወሳኛዊነት የተመሠረተው በተናከእታዊ ቁስአካልነት ላይ መሆኑ ግልጽ ነው ። መንሥኤ የተባለው ከተናከእታዊ ግንኙነት የሚመጣውን በመሆኑ ወሳኛዊነት ዓለም የሚሠራው እንደ ማሺን ነው የሚለውን አመለካከት የሚደግፍ ነው ። ይህ የከረረ አቋም ለዕድልና ለአጋጣሚ ምንም ቦታ አይሰጥም ። ውስብስብ ሥርዓቶችም የሚገዙት በውስብስብ ሕጎች በመሆኑ ተናከእታዊ ወሳኛዊነት ሥርዓቶችን አስመልክቶ ግንዛቤ ሊሰጥ አይችልም ። እንዲያውም እዋጋዋለሁ ያለውን ሐሳባዊነት በከረረ አቋሙ በተዘዋዋሪ ማጠናከር ይሆናል ። ምክንያቱም ሁሉም ነገር በፍጹማዊ ሁኔታ የተወሰነ ከሆነ የሰዎች እንቅስቃሴና ፈቃድ ምንም ቦታ ላይ ኖረውና ሰው ሙሉ በሙሉ ተገዥና ተገብሮት ሊሆን ነው ማለት ነው ።

ስለዚህ ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት የመንሥኤን ነባራዊነት የሚቀበል ቢሆንም ፍጹማዊ ግዴታ አድርጐ አይወስደውም ። የነገሮች ውስጣዊ ምንነት የሚወሰነው በተናከእት ብቻ ሳይሆን በቅራኔ ሕግ ነው ። ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ይህ የቅራኔ ሕግ ለውስብስብ ሥርዓቶች መከሰት ምክንያት መሆኑን የሚያስረዳ ከመሆኑም በላይ ለአጋጣሚና ለዕድልም ቦታ ይሰጣል።

(ተናከእታዊ ቁስአካልነትን ፣ ግዴታና አጋጣሚን ፣ ፈቃዳዊነትን ይመለከቷል ።)

## ወረቀት ገንዘብ (የ—)

*(Paper Money)*

የወርቅ ገንዘብን በመወከል የሚያገለግል ፣ የወርቅ ገንዘብ የሚኖረውን የዝውውርና የክፍያ ተግባር ለማሟላት የሚያስችል የእሴት የገንዘብ ምልክት የሆነ ፣ በመንግሥት የሚተታምና በሕግ አስገዳጅነት በሸቀጦች ዝውውርና በክፍያ ተግባር ላይ የሚውል ልዩ ሰነድ ነው ።

የወረቀት ገንዘብ ቀደም ሲል ሸቀጦችን ለማዘዋወር ያገለግሉ ከነበሩት ከነሐስ ፣ ከብርና በተለይም ከወርቅ ሽርፍራፊዎች የመነጨና ወርቅን በመወከል የሚሠራ ነው ። የሸቀጥ ምርት ተስፋፍቶ ንግድ ከሀገር አቀፍ ደረጃ በማለፍ የተለያዩ ሀገሮችን ማገናኘት በጀመረበት ጊዜ የተለያዩ ሽርፍራፊዎች በብዛት በመዘዋወራቸው እያረጁና እየተበሉ

ሲሄዱ እሴታቸው እየቀነሰ መጣ ። ከዚህም በተጨማሪ ወርቅ የራሱ የልውውጥ እሴት ብቻ ሳይሆን የጠቀሜታ እሴት ያለው ሸቀጥ በመሆኑ ከዝውውር እየወጣ ለጌጣ ጌጥ ሥራና ለመሳሰሉት እንዲያገለግል በመደረጉ በዝውውር አማካይነት ማገልገል ያለበትን መጠን ቀነሰ ፤ ይህም በሸቀጦች ጤናማ ዝውውር ላይ ቀውስ እያስከተለ መጣ ። ከዚህም የተነሣ በራሱ የጠቀሜታ እሴት ሳይኖረው ወርቅን በመወከል ብቻ ለልውውጥ የሚያገለግል ሌላ ነገር አስፈላጊ ሆነ ፤ ይህም ሁኔታ የወረቀት ገንዘብ መፈጠርን አስከተለ ።

በአንድ ወቅት የሚሰራጨው የወረቀት ገንዘብ ከእርግጠኛው ገንዘብ (ወርቅ) በላይ ከሆነ የወረቀት ገንዘቡ የመግዛት ኃይል ይቀንሳል ። በአጠቃላይ በአንድ ሀገር ውስጥ ያለው የወረቀት ገንዘብ መጠን የፈለገውን ያህል ቢሆን እውነተኛ እሴቱ በዚያን ወቅት የሸቀጦችን ዝውውር ለማከናወን ከሚያስፈልገው እርግጠኛ ገንዘብ (ወርቅ) ጋር ተመጣጣኝ ይሆናል ።

የወረቀት ገንዘብ በጥቅም ላይ መዋል የጀመረው በ17ኛው ምዕት ዓመት መጨረሻ ላይ በሰሜን አሜሪካ ሲሆን በኋላም ከካፒታሊዝም መዳበር ጋር በአውሮፓ ውስጥ በሥራ ላይ ሊውል ችሏል ።

ካፒታሊዝም እያደገ ወደ ኢምፔሪያሊዝም ደረጃ ላይ በደረሰበት ጊዜ ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ጦርነት ለማካሄድ በኢኮኖሚ ቀውስ ጊዜና በሌሎችም ምክንያቶች የወረቀት ገንዘብ ከሚወክለው እርግጠኛ ገንዘብ በላይ በብዛት እንዲሰራጭ ያደርጋሉ ። ይህም ሁኔታ የወረቀት ገንዘብን የመግዛት ኃይል በመቀነስ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ንረት ያስከትላል ።

የወረቀት ገንዘብ በሶሻሊስት ሀገሮች ያለው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ባሕርይ በካፒታሊስት ሀገሮች ካለው ባሕርይ የተለየ ነው ። የሶሻሊስት መንግሥት የወረቀትን ገንዘብ የሚጠቀምበት በምርትና በዝውውር ሂደት የሶሻሊስት ይዞታን ለማጠናከር ነው ። የሶሻሊስት ኢኮኖሚ በዕቅድ የሚመራ ኢኮኖሚ እንደመሆኑ የምርቱ መጠንና ምርቱን ለማዘዋወር የሚያስፈልገው የገንዘብ መጠን በዕቅድ የሚተመን ይሆናል ። የሶሻሊስት መንግሥት ተፈጥሮ ባስከተለው ችግር ወይም እናት ሀገርን ከወራሪ ለመከላከል በሚደረገው ትግል አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር እንደ ካፒታሊስት መንግሥት ሸቀጦችን ለማዘዋወር ከሚያስፈልገው በላይ የወረቀት ገንዘብ እያተመ አያወጣም ።

በኢትዮጵያ ውስጥ የወረቀት ገንዘብ ለመጀመሪያ ጊዜ በሥራ ላይ የዋለው ካፒታሊዝም መግባት በጀመረበት አካባቢ በአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ነው ።

(ገንዘብን ፣ የዋጋ ንረትን ይመለከቷል ።)

## ወዝአደሩ የበላይ ገዥነት (የ—)

*(Dictatorship of the Proletariat)*

ካፒታሊስት ወይም ከፊል ካፒታሊስት የብዝበዛ ሥርዓት በሶሻሊስት አብዮት ከተደመሰሰና የቡርዧው መንግሥታዊ መዋቅር ከተገረሰሰ በኋላ የሚመሠረት የወዝአደሩ መደብ መንግሥታዊ ሥልጣን ነው ። ይህ መንግሥታዊ ሥልጣን በወዝአደሩ ፓርቲ መሪነትና በወዝአደሩና በገበሬው መደቦች ኅብረት ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ ጠንካራ ሕዝባዊ መሠረት አለው ።

የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት ግንባር ቀደም በሆነው በወዝአደሩ መደብና በሠርቶ አደሩ ሕዝብ መካከል የሚፈጠር የተለየና የላቀ መደባዊ ኅብረት ሲሆን ኅብረቱ ካፒታልን የሚፃረር ፣ የቡርዧዚውንና የአድኅሮትን ጥቃትና ደባ በሚገባ በመቋቋም ሶሻሊዝምን ለመገንባት ቆርጦ የሚነሣ ኃይል ነው ። የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት በሠርቶ አደሩ ሕዝብ ፍላጐትና ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ህልውና የሚያገኝ በመሆኑ ሕዝባዊ ሥልጣን የሚረጋገጥበት ነው ።

የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት የሶሻሊስት አብዮት ዓይነተኛ ውጤት ብቻ ሳይሆን ዋና ይዘቱና የድሉም ዋስትና ነው ። በመሆኑም ጽንሰ ሐሳቡ በማርክሳዊ ሌኒናዊ ንድፈ ሐሳብ ውስጥ ቁልፍ ቦታን ይዟል ። ከተግባሮቹ መካከል አድኃሪ ኃይሎች እንዳያንሰራሩ ንቅቶ መጠበቅና ከተነሡም መደምሰስ ፣ የውጭ ወራሪ ኃይሎችን ሴራና ወረራ ማክሸፍ ፣ የአብዮቱን ድሎች መንከባከብና

መጠበቅ ፣ በወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት መርህ መሠረትም የጭቁን ሕዝቦችን የትግል አንድነት ማጠናከር ፣ ሠርቶ አደሩን ሕዝብ በኅብረት እንቅስቃሴ በፓርቲው መሪነት በሶሻሊስት ኢኮኖሚና የባህል ግንባታ በንቃት ማሳተፍ ዋና ዋናዎቹ ናቸው ። በዚህም የፓርቲው ዓላማና ፖሊሲ ማስፈጸሚያ መሣሪያነቱን ያረጋግጣል ።

የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት በተለያዩ ሀገሮች በተለያዩ ቅርፆች ተከስቷል ። በ1871 በፈረንሳይ ለአጭር ጊዜ የታየው የፓሪስ ኮሚዩን የዚህ ሥልጣን ጥንስስ ሲሆን የርሱን ልምድ በመውሰድና በማዳበር በታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት ማግስት በሩሲያ የተመሠረተው የሶቭዬት ሥልጣን የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት የወሰደው አዲስ ቅርፅ ነበር ። ቆይቶም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በምሥራቅ አውሮፓና በደቡብ ምሥራቅ እስያ የተመሠረቱት የሕዝባዊ ዲሞክራሲ መንግሥታት የዚሁ ሥልጣን ለየት ያለ ቅርፅ ናቸው ። ምንም እንኳ የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት የተለያየ ቅርፅ የወሰደና ለወደፊትም ሊወስድ የሚችል ቢሆንም ፣ በይዘቱ ወዝአደራዊ የሆነና በዓላማውም ብዝበዛና ጭቆናን አጥፍቶ ፍትህ ፣ ሰላምና ብልጽግና የሰፈነበትን ሶሻሊስት ከዚያም ኮሚኒስት ኅብረተሰብ መገንባት ነው ።

የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት የዚህ አዲስ ኅብረተሰብ ግንባታ መሣሪያ እንጂ በራሱ ግብ አይደለም ። የኮሚኒስት ኅብረተሰብ የመጀመሪያ ደረጃ የሆነው ሶሻሊዝም ተገንብቶ ወደ ኮሚኒዝም ሽግግር ሲደረግ ይህ ሥልጣን እየከሰመ ስለሚሄድ ታሪካዊ ተልዕኮውና አስፈላጊነቱ ያበቃል ። ኅብረተሰቡ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበትም አዲስ ሁኔታ ይዳብራል ።

(ሶሻሊስት አብዮትን ፣ ፓርቲን ይመለከቷል ።)

## ወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት
*(Proletarian Internationalism)*

የሁሉም ሀገር ወዝአደሮችና ሠርቶ አደሮች ለነፃነት ፣ ለእኩልነትና የሰው በሰው መበዝበዝ ለሌለበት ሥርዓት ከካፒታሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር በሚያደርጉት ትግል በአንድነት የሚያስልፋቸውና የሚያስተሳስራቸው የሠራተኛው መደብ መርህ ነው ። ይህም መርህ የሁሉም ሀገር ሠርቶ አደሮች የጋራ ጥቅምና የጋራ ኃላፊነት ያለባቸው ፣ የማይነጣጠሉ የአንድ መደብ አካል ናቸው ከሚለው አመለካከት የመነጨ ነው ። ካፒታል ብሔራዊ ድንበር ጥሶ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተዘረጋ ኃይል ሲሆን ከእርሱ ጋር የሚደረገውን ትግል ለማጠናከር የሠርቶ አደሮች ዓለም አቀፍ የትግል አንድነት አስፈላጊ ሆነ ።

ዓለም አቀፋዊነት ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ከመከሰቱ በፊት በግብታዊው የወዝአደሩ እንቅስቃሴ ውስጥ የትግል አንድነት ስሜት ይታይ የነበረ ቢሆንም ሳይንሳዊ ይዘት ይዞ የወጣው በኮሚኒስት ንቅናቄ ነው ። በ1847 የኮሚኒስት ሊግ ፕሮግራም በወጣ ጊዜ "የሁሉም ሀገር ሠራተኞች ተባበሩ" የሚለው መደባዊ ይዘት ያለው የመጀመሪያው ዓለም አቀፋዊ መርህ ወጣ ።

በቡርዧው ብሔረተኝነት አንፃር ለተበዝባዥ መደብ ነፃነትና ለጭቁን ሕዝቦች ብሔራዊ አርነት በሚደረገው ትግልና የሁሉም ሀገር ሠርቶ አደሮች በአንድ የኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲዋሃዱ ለማዘጋጀት የወዝአደሩ መደብ ዓለም አቀፋዊ አንድነት በመርህና በተግባር የሚገለጽበት ነው ።

በሠርቶ አደር ሕዝቦች መካከል ያለ ዓለም አቀፋዊነት የቀለምና የዘር ልዩነትን ሁሉ የሚያጠፋ ነው ። ለምሳሌ በካፒታሊስት ሀገሮች "ከሠለጠኑት ነጭ ሠርቶ አደሮችና" በቅኝ ግዛት ጭቁን ሕዝቦች መካከል መናር ስላለበት ዓለም አቀፋዊነት ማርክስ ሲያስረዳ ለጥቁር ቆዳ ነፃ መውጣት የማይታገል ነጭ ሠራተኛ ራሱ ነፃ ሊሆን እንደማይችል አብራርቷል ።

እያንዳንዱ የአብዮታዊ ንቅናቄ ኃይል ወይም የአንድ ሀገር ሠርቶ አደር ሕዝብ የካፒታልን አገዛዝ አሽቀንጥሮ የሠራተኛውን ሕዝብ ሥልጣን መመሥረቱ የካፒታልን ዓለም አቀፍ የኃይል ሰንሰለት ማስልሰል ስለሆነ ከፊል ዓለም አቀፍ ግዴታውን በቅድሚያ እንደተወጣው ቢቆጠርም ፣ ከዚህ አልፎ ተርፎ የሌሎች ሀገሮች ሠርቶ አደሮች ከካፒታል ጋር በሚያካሂዱት ትግል የተቻለውን ሁሉ ድጋፍ መስጠት የዓለም አቀፋዊነት ግዴታው ነው ።

በአንድ ሀገር ወይም ቀበሌና አካባቢ የሚገኙ ብዙ ብሔረሰቦች የሚፈጥሩት በእኩልነትና በጋራ ብልጽግና ላይ የተመሠረተ አንድነት የዓለም አቀፋዊነት ሌላው ገጽታ ነው ።

ይህ የዓለም አቀፋዊነት ገጽታ ሌሎችን ለመርዳት ከበጐ ፈቃድ መንፈስ የመነጨ ሳይሆን የአንድ ሀገር ብሔራዊ ነፃነትና ተራማጅ እንቅስቃሴ የዘለቄታ ህልውና ሊረጋገጥ የሚችለው የሁሉም ሀገር ሠርቶ አደሮች በኢምፔሪያሊዝምና በካፒታሊዝም ላይ የማያዳግም የመጨረሻ ድል ሲቀዳጁ ብቻ ስለሆነ ነው ። ስለዚህም የእያንዳንዱ ሀገር ተራማጅ ንቅናቄ ወይም ኃይል የራሱን ቀጥተኛ ፍላጐት እያሟላ በተጨማሪ በዓለም ላይ የሚካሄዱትን ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ካፒታሊስት ትግሎች በተቻለው መጠን መርዳትና የሶሻሊስት ማኅበረሰቦችን ዕድገትና ኅብረት ማጠናከር አለበት ።

የዓለም አቀፋዊነት መርህ በከፍተኛ ደረጃ በተግባር የዋለበት የመጀመሪያው ታሪካዊ ወቅት የፓሪስ ኮሚዩን ነበር ። በፓሪስ ኮሚዩኑ እንቅስቃሴ የተለያዩ ሀገሮች ተወላጆች ተካፋይ ሆነው ነበር ። ኮሚዩኑ ወድቆ ከጭፍጨፋ የተረፉት መሪዎች በየቦታው ሲሰደዱ የአንደኛው ኢንተርናሽናል አባላት ከፍተኛ ሞራላዊና ቁሳዊ እርዳታ አድርገውላቸዋል ። እንደዚሁም በጥቅምቱ አብዮት ማግሥት የኢምፔሪያሊስት ኃይሎች በመጀመሪያዋ ሶሻሊስት ሀገር (በሶቭዬት ኅብረት) ላይ የወረራ ጦርነት በከፈቱበት ወቅት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የሌሎች ሀገሮች ወዝአደሮች "ከሶቭዬት ኅብረት ላይ እጃችሁን እንሡ" የሚል መፈክር በማንሣት ከሶቭዬት ኅብረት ቀይ ጦር ጎን ተሰልፈው ተዋግተዋል ።

በ1936 በእስፓኝ የእርስ በእርስ ጦርነት ወቅት የብዙ ሀገሮች ኮሚኒስቶች ከሪፑብሊካኖች ጐን ተሰልፈው ፋሺስቶችን በመዋጋት ዓለም አቀፍ ግዴታቸውን ፈጽመዋል ።

የምሥራቅ አውሮፓ ሀገሮች ከፋሺዝም ጭቆናና ጭፍጨፋ ነፃ እንዲወጡ ሶቭዬት ኅብረት የከፈለችው ከፍተኛ መሥዋዕት ፣ ከጦርነቱ በኋላም ሶቭዬት ኅብረትና ሌሎች ሶሻሊስት ሀገሮች ለአፍሪካ ፣ ለእስያና ለላቲን አሜሪካ የአርነት ንቅናቄዎች ያደረጉትና የሚያደርጉት እርዳታ በዚሁ ዓለም አቀፋዊነት መርህ ላይ የተመሠረተ ነው ።

እንዲሁም ኢምፔሪያሊዝምና የአካባቢው አድኃሪ ኃይላት በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ላይ ወረራ በከፈቱበት ወቅት ሶቭዬት ኅብረት ፣ ኩባና ሌሎችም ሶሻሊስት ሀገሮች ከሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ተሰልፈው በሕይወትና በቁሳቁስ ያደረጉት ድጋፍ በዓለም አቀፋዊነት መርህ ላይ የተመሠረተ ነበር ።

ኢትዮጵያ በበኩልዋ በተለይ ለአፍሪካና ለሌሎችም የብሔራዊ አርነት ንቅናቄዎች የተቻላትን ድጋፍ በመስጠት የዓለም አቀፋዊነት ግዴታዋን በመፈጸም ላይ ትገኛለች ።

## ወዝአደር
*(Proletariat)*

ፕሮሌታሪያት (ወዝአደር) ፕሮሌታሪየስ ከሚል የላቲን ቃል የመጣና በዚህ ትርጉሙም በጥንታዊት ሮማ ምንም ንብረት ስሌላቸውና የነበረውን መንግሥት ለሚያገለግሉ ፣ ልጆች ለመውለድ ብቻ ይጠቅማሉ ተብለው ለሚገመቱ ምዝብር የኅብረተሰብ ክፍሎች የተሰጠ ስያሜ ነበር ። ዛሬ ግን ወዝአደር ማለት የምርት መገልገያ መሣሪያዎች ባለቤት ያልሆነ ፣ ስህልውናውም ሲል የሥራ ኃይሉን ለካፒታሊስቱ በመሸጥ በዘመናዊ ፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የሚሠራ የካፒታሊስት ኅብረተሰብ ክፍል ነው ።

ምንም እንኳ ቀደም ሲል ከፊል ጊዜያቸውን በእርሻና በሌላም ሥራ ፣ ከፊል ጊዜያቸውን ደግሞ ጉልበታቸውን ለከበርቴዎች በመሸጥ የሚተዳደሩና ተለማማጅ ሠራተኞች ፣ ተዘዋዋሪ ሠራተኞችና ሌሎችም በተለያዩ ስሞች የሚታወቁ ሠራተኞች ቢኖሩም ፣ እነዚህ ሁሉ እንደትክክለኛው ትርጉም ከሆነ ወዝአደሮች አልነበሩም ። ወዝአደር በመደብነት የተከሰተው ከአሥራ ስምንተኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ጀምሮ ከፍተኛ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት በታየበት ማለትም በኢን

ዱስትሪ አብዮት ወቅት ነው ። ይህም ሁኔታ ወዝአደሩ ከዘመናዊ የማምረቻ መሣሪያዎች (ማሽን) ጋር በቀጥታ በተያያዘ አመራረት ጉል በቱን ለቡርዧዚው እንደሸቀጥ በመሸጥ ለአስ ከፊ ብዝበዛ የተዳገረበት ነበር ። ለወዝአደሩ መደብ አባላት መበራከት ምንጭ የሆኑትም ካፒታል ከከተማ አልፎ ወደገጠር ሲገባ በመሬት ከበርቴዎች ተፅዕኖ ከመሬታቸው በገፍ የተፈናቀሉት ገባሮችና በከተሞችም ከከፍተኛዎቹ ካፒታሊስቶች ጋር መወዳደር ባለመቻላቸው እየከሰሩ ወደ ወዝአደርነት የተ ለወጡት ቀድሞ በግል ያመርቱ የነበሩ ንዑስ ከበርቴዎች ናቸው ።

ወዝአደር በካፒታሊስቱ ሥርዓት ዋነ ኛው አምራች ኃይል ቢሆንም የምርት መገ ልገያዎች ባለቤት ባለመሆኑ በአነስተኛ ምንዳ የሚበዘበዝ ፣ በዚህም ምክንያት በቡርዧው ሥርዓት ውስጥ ከቡርዧዚው ጋር በማይታረቅ ቅራኔ ተፋጥጦ ያለ ነው ። ወዝአደሩ የቡርዧው ሥርዓት እንዲፈርስ በካፒታሊስቱ መደብ ላይ በቆራጥነት የሚነሣ ፣ በሥራ ጠባዩና በአስከፊ የኑሮ ሁኔታው ሳቢያ አብዮታዊ በመሆኑ በተደራጀ ሁኔታ ካፒታሊዝምን ደምስሶ ብዝበዛና ጭቆና የሌለበትን ኮሚኒ ስት ኅብረተሰብ የመገንባት ታሪካዊ ተል ዕኮ ያለው መደብ ነው ።

የወዝአደሩ መደብ በዘመናዊ ኢንዱስ ትሪዎችና ፋብሪካዎች ውስጥ በመሥራት የኅብረተሰቡ ህልውናና ዕድገት መሠረት የሆነውን ምርት የሚያመርት፣ በዘመናዊ የማ ምረት ዘዴና ጥበብ የተካነ ፣ ከሥራ ሁኔታ ውም የተነሣ በአንድ ላይ የተሰባሰበና የራሱ የሆነ ጠንካራ ዲሲፕሊን ያለው ነው ። ዘመናዊ ኢንዱስትሪ እየተስፋፋና ሌሎች መደቦች ህልውናቸውን እያጡ ሲሄዱ የወዝ አደሩ መደብ ግን እያደገና እየሰፋ የሚሄድ በመሆኑ እስከመጨረሻው ለግል ሀብት መጥ ፋት ሊቆም የሚችል ዘላቂ መደብ ነው ። ሆኖም የወዝአደሩ መደብ ለሶሻሊዝም ፣ ብሎም ለኮሚኒዝም እስከመጨረሻው ሊታ ገል የሚችለው በጠንካራ ኮሚኒስት ፓርቲ ሲመራ ብቻ ነው ።

(ወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነትን ፣ የመጀመ ሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችትን ይመለከቷል።)

## ወዝአደር መሳፍንት (የ—)
*(Labour Aristocrats)*

በሠራተኛ ማኅበራት ፣ በተለይ በአመ ራሩ ላይ ሆነው የቡርዧውን ርዕዮተ ዓለምና ፖለቲካ በማሰራጨት የሠራተኛውን መደብ አብዮታዊ ተልዕኮ ለማዘናጋትና የቡርዧዚው ተከታይ ለማድረግ የሚጥሩ ፣ ድርጅቱን የመደብ እርቅ መሰበኪያና የራሳቸው ጥቅም ማስጠበቂያ የሚያደርጉ ናቸው ። የወዝ አደር መሳፍንት ከሞኖፖሎች በሚያገ ኙት ጥቅም የሠራተኛውን መሠረታዊ ዓላማ ለመሸጥ ፣ ሠራተኛውን በጥቅም በመደለል ለመደባዊ ዓላማውና ለሶሻሊዝም የሚያደ ርገውን ትግል በጊዜያዊና በጥገናዊ ለውጥ ለመተካትና የቡርዧውን አገዛዝ ለማሰንበት ይጥራሉ ። የወዝአደር መሳፍንት ከሠራተ ኛው መደብ የወጡ ቢሆኑም በጥቅም ተገ ዝተው በአመለካከታቸውና በአኗኗራቸው ከመነጩበት መደብ የተነጠሉና ተስፋቸው ንና ህልውናቸውን ከሞኖፖሊስቶች ጋር ያስተሳሰሩ ወገኖች ናቸው ።

የወዝአደር መሳፍንት ህልውና ኢኮኖ ሚያዊ መሠረት ሞኖፖል ካፒታሊዝም ነው ። ካፒታሊዝም ከነፃ ውድድር ደረጃ አልፎ ወደ ሞኖፖል ወይም ወደ ኢምፔሪያሊ ዝም ዕድገት በተሸጋገረበት ወቅት ካፒታል ከአንድ ሀገር ድንበር አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተፅዕኖ ማድረግ ጀመረ ። በዚህ መሠ ረት ሞኖፖል ካፒታሊስቶች ካለፈው ምዕት ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ መጨረሻ ጀምሮ ለኢንዱስትሪዎቻቸው ጥሬ ዕቃ በገፍ ለማግኘት ፣ ለሸቀጦቻቸው ሰፊ ገበያ ለማመ ቻቸትና የሌሎች የዓለም አካባቢ ሕዝቦችን ጉልበት በርካሽ ዋጋ ለመበዝበዝ በነበራቸው ዓላማ መሠረት ሕዝቦችን በቅኝ ግዛት ሥር በማዋል ከፍተኛ ትርፍ ለማካበት ችለዋል ። ከቅኝ ግዛቶች ብዝበዛ የተገኘው ከፍተኛ የሞኖፖል ትርፍ የቅኝ ግዛት ሕዝቦችን ማስመዝበሩ ብቻ ሳይሆን የራሳቸው የኢም ፔሪያሊስት ሀገሮች ወዝአደሮች በሚያደር ጉት ፀረ ካፒታል ትግል ላይ ከፍተኛ ተፅ ዕኖ አድርጓል ። ሞኖፖሊስቶች ባካበቱት ትርፍ በመጠቀም በሠራተኛ ማኅበራት ውስጥ የወዝአደር መሪዎችን ፣ የሙያ ትም ህርት ያላቸውንና ነቃ ያሉትን ሠራተኞች በጥቅም በመደለል በሠራተኛው ትግል ላይ

ለጊዜውም ቢሆን አፍራሽ ተፅዕኖ አሳድረዋል ። እነዚህን የመሰሉ የሠራተኛ ማኅበራት መሪዎችም ለጥቅም በመገዛት በሞኖፖሊስቶች ላይ የሚደረገውን ዲሞክራሲያዊና አብዮታዊ ትግል በማጠናከር ፈንታ ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር በመመሳጠር የቡርዧው ብሔረተኝነት ፣ ትምክህተኝነትና ፀረ ሶሻሊስት አፈቀላጤ በመሆን አገልግለዋል ።

## ወገናዊነት

*(Partisanship)*

በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የተወሰኑ መደቦችን ጥቅምና ፍላጎት ማንፀባረቅና ለዚያም መቆምን የሚያመለክት ነው ። በፍልስፍና ወገናዊነት ማለት ከሁለቱም ከቁስአካልነትና ከሐሳባዊነት የአንደኛው ተከታይ ወይም ደጋፊ መሆን ነው። በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መስክ ወገናዊነት ለወዝአደሩ መደባዊ ጥቅም መቆምን ያሳያል ። በአጠቃላይ ይህ መደባዊ ወገናዊነት በየትኛውም የኅብረተሰቡ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ የሚንፀባረቅ ነው ።

ቡርዧ ምሁራን የሚከተሉት ፍልስፍና ፣ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ወዘተ... የመደቦችን ሁሉ ጥቅምና ፍላጎት የሚያንፀባርቅ አድርገው ያቀርባሉ ። በተግባር ግን የቡርዧዚውን ጥቅምና ፍላጎት ሲያራምዱ ይታያሉ ።

በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ ቁስአካልነትና ሐሳባዊነት ሁለት በተፃራሪነት የቆሙ ፈናዎች ሆነው ቆይተዋል ። ባለንበት በአሁኑም ዘመን የሚካሄደው ርዕዮተዓለማዊ ትግል ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም የሚደረገውን ታሪካዊ ሽግግር የሚያንፀባርቅ ነው ። ቡርዧዚው በፀረ ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ሶሻሊዝምንና ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ያጥላላል ። በቡርዧው ሥርዓት ውስጥ ያሉትን ተፃራሪ ቅራኔዎች አድበስብሶ ለማቅረብ ሌት ተቀን ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል ። ወዳቂ የሆነው የካፒታሊስቱ ሥርዓት ለሰው ልጅ ነፃነት ፣ እኩልነትና ብልጽግና የቆመ ብቸኛው መድኅን እንደሆነም ይሰብካል ። የቡርዧው መንግሥት ለሁሉም መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች ጥቅም እኩል እንደቆመና የካፒታሊስቶች ፍላጎት የመላው የሰው ልጅ ፍላጎት እንደሆነ አስመስሉ ለማቅረብ በሚነዛው ውዥንብር ሕዝቡን ያወናብዳል ። ይሁን እንጂ በሚገባ ሲጤን በዚህ ሁሉ የቡርዧው ርዕዮተዓለም መደባዊ ወገናዊነት እንዳለውና አድልዎ እንደሚያደርግ በግልጽ ይታያል ።

ማርክሳውያን ግን በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ ገለልተኛ ወይንም ከመደብ በላይ መሆን የማይቻል መሆኑን ይገልጻሉ ፤ ወገናዊነታቸው ለወዝአደሩ መደብ መሆኑንም በይፋ ይናገራሉ ።

ማርክሲዝም ምን ጊዜም ከዚህ ወገናዊነት በመነሣት ዲያሌክቲካዊና ታሪካዊ ቁስአካልነት ሠራተኛው መደብ ካፒታሊዝምን ገርስሶ በመጣል ለኮሚኒዝም በሚያደርገው ትግል ሳይንሳዊ የትግል መሣሪያው እንደሆነ ያረጋግጣል ። ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍና ንድፈ ሐሳብንና ተግባርን በሚገባ የሚያዋህድና እውነታን በትክክል የሚያንፀባርቅ ፣ ሐሳባዊነትን ፣ ዲበአካላዊ አመለካከትን ፣ ከላሽነትንና ቀኖናዊነትን ያስርገሩ የሚዋጋና የሠራተኛው መደብና የጭዝብር ሕዝቦች መደባዊ ወገናዊነት በሁሉም መስክ የሚገለጽበት አጠቃላይ አመለካከት ነው ።

ማርክሳውያን ወገናዊነታቸውን ለወዝአደሩ መደብ የሚያደርጉት ይህን መደብ እንዲሁ ለመደገፍ ፈልገው ሳይሆን የታሪክ ሂደትን በማጤንና እውነታን በትክክል ሊያንፀባርቅ የሚችል ርዕዮተዓለሙም ሳይንሳዊና ተራማጅ የሆነ ይህ መደብ መሆኑን በመገንዘብ ነው ። ዛሬ ካሉት መደቦች ሁሉ ጥቅምና ፍላጎቱ ከኅብረተሰቡ ዕድገትና ደኅንነት ጋር የሚገጥም የወዝአደሩ መደብ ብቻ ነው ። ምክንያቱም የተቀሩት መደቦች ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ ዕድገት ጋር እየተፈረካከሱ ሲሄዱ እየተጠናከረ የሚሄደው ይህ መደብ በመሆኑ ነው ።

ቡርዧዚው በነፃ ውድድር ካፒታሊዝም ጊዜ አድኃሪ የፊውዳል ሥርዓትን በመዋጋትና የምርት ኃይሎችን በማሳደግ በጊዜው የተራማጅነት ሚና ቢጫወትም ዛሬ ካፒታሊዝም በሞኖፖል ካፒታሊዝም ደረጃ በሚገኝበት ወቅት የምርት ኃይሎችን ዕድ

ንት የሚገታ ፣ የኅብረተሰቡን ዕድገትና እርምጃ የሚያደናቅፍ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል ። ስለሆነም የቡርዧው ርዕዮተ ዓለም አድኃሪና ተቃች ሊሆን በቅቷል ። ወዝአደሩ ግን ዕድገቱና ፍላጐቱ ከምርት ኃይሎች ዕድገት ጋር የተያያዘ በመሆኑ አመለካከቱ ሳይንሳዊ ነው ። የማርክሳውያን ወገናዊነት ልዩ ባሕርይም ይህ ሳይንሳዊነትና ተራማጅነት ነው ።

## ወግ አጥባቂ ወይም ቡርዧ ሶሻሊዝም
*(Conservative or Bourgeois Socialism)*

የሚታዩቸውን ማኅበራዊ ጉስቁልናዎችና ችግሮች እያሻለው የቡርዧውን ኅብረተሰብ ህልውና ለማቆየት የሚመኙ የቡርዧው ክፍሎች ማለትም ኢኮኖሚስቶች ፣ ለሠራተኛው ከንፈራቸውን የሚመጡ ሰብአውያን ፣ በጐ አድራጊዎች ወዘተ... የሚሰብኩት ሶሻሊዝም ነው ። የቡርዧ ሶሻሊስቶች ከዘመናዊ ኅብረተሰብ የሚገኘውን ጥቅም ይፈልጋሉ ። ግን ይህ ኅብረተሰብ በቡርዧዚው ላይ ሊያመጣ የሚችለውን አደጋ ይፈራሉ ። ለጊዜው ያለው የኅብረተሰብ አቋም ያለምንም ተቀናቃኝ እንዲኖር ይመኛሉ ፤ እነሱ ከላይ የተፈናጠጡበት ዓለም ውብ እንደሆነና ወዝአደሩም ያለውን ጥላቻና ትግል አስወግዶ ወደዛ ውብ ዓለም ለመግባት እንዲጣጣር ይሰብካሉ ።

ሁለተኛው የተሻለና ግን ዘዴ የሚያንሰው የቡርዧ ሶሻሊዝም ደግሞ ለወዝአደሩ የሚጠቅመው የፖለቲካ ሥልጣን ሳይሆን ለኑሮ የሚያስፈልጉ ቁሳዊ ሁኔታዎችና የኢኮኖሚ ግንኙነቶች መለወጥ ነው በማለት ሠራተኛው ለአብዮታዊ እንቅስቃሴ ያለውን ስሜት ለመስለብ የሚጥር ነው ። ለኑሮ የሚያስፈልጉ የቁሳዊ ሁኔታዎች መለወጥ ማለትም የቡርዧው የምርት ግንኙነት በአብዮታዊ ትግል መደምሰስን ሳይሆን የካፒታልና የጉልበት ግንኙነት ሳይቃወስ የሚገኘውን የአስተዳደር መሻሻልን መሻት ማለት ነው ። የቡርዧው ሶሻሊዝም የሚሰጠው ትርጉም ሌላ ሳይሆን ቡርዧዚው ቡርዧዚ የሆነው ለወዝአደሩ ጥቅም ሲል ነው የሚል ይሆናል ።

## ወጣት አጥፊነት (የ—)
*(Juvenile Delinquency)*

ከ15 ዓመት የበለጠ ዕድሜ ኑሮዋቸው ነገር ግን አካለ መጠን ያልደረሱ ወይም በብዙ ሀገሮች እንደተደነገገው አሥራ ስምንት ዓመት ያልሞላቸው ወጣቶች የሚፈጽሙት ወንጀል የወጣት አጥፊነት ይባላል ። የወጣት አጥፊነት በዕድሜ አነስተኛ ወይም ከአሥራ አምስት ዓመት በታች የሆኑ አዳጊ ሕፃናት ከሚፈጽሙት ጥፋት በተለየ ደረጃ የሚታይ ነው ። ታዳጊ ሕፃናት ለማኅበራዊ ኑሮ አደገኛ የሆነ ተግባር ሊፈጽሙ ቢችሉም በኃላፊነት አይጠየቁም ።

ብዝበዛ በሰፈነበት ኅብረተሰብ ውስጥ ለወጣት አጥፊነት ዋናው ምክንያት የኅብረተሰቡ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መዋቅር ነው ። በቡርዧ ኅብረተሰብ ውስጥ ወጣቶችን የሚያስጨንቁና ተስፋ የሚያስቆርጡ ማኅበራዊ ክስተቶች የተለመዱና የማያቋርጡ በመሆናቸው የወጣት አጥፊነትም እየጨመረ ይሄዳል ። ሥራ አጥነት ፣ በወደፊቱ ኑሮ አለመተማመን ወዘተ... የወጣቱን ሕይወት የሚያጨልሙ ሁኔታዎች ናቸው ። የዕፅ ሱሰኝነት ፣ ቁማር ፣ ስርቆት ፣ ውንብድናና ሌላውም የወጣት አጥፊነት እየበረከተ የሄደውም በቡርዧው ሥርዓት ነው ። በሶሻሊስት ሥርዓት ግን የወጣቱ የወደፊት ዕድል የሰፋና ያለው በመሆኑና ለተደላደለ የወደፊት ኑሮው አስፈላጊው ዝግጅት ስለሚደረግለት ከጭንቀትና ከተስፋ መቁረጥ ነፃ ይሆናል ። ስለዚህም ወደ አጥፊነት ለሚመሩ ሁኔታዎች አይጋለጥም ። ይህም ሲባል ወጣት አጥፊዎች አይገኙም ማለት አይደለም ። አልፎ አልፎ በወጣቶች በተናጠል የሚፈጸሙ ጥፋቶች ያጋጥማሉ ። ይህም ሆኖ ወጣት አጥፊነት እንደኅብረተሰቡ መሠረታዊ ችግር የሚቆጠር አይደለም ።

## ወጪ ንግድ
*(Export Trade)*

አንድ ሀገር ሸቀጦችን ወደ ሌሎች ሀገሮች በመላክ የሚያደርገው የንግድ እንቅስቃሴ ወጪ ንግድ ይባላል ።

አንድ ሀገር በመሠረቱ ከፍጆታ በላይ የሆነን ሸቀጥ ወይም በሀገር ውስጥ ገበያ

ሸቀጡ የሚያስገኘው ገቢ በውጭ ገበያዎች ከሚያስገኘው ገቢ ያነሰ ከሆነ ወይም በሌሎች ምክንያቶች ሸቀጦችን ወደ ውጭ ይልካል ። ወደ ውጭ የሚላኩ ሸቀጦችም የውጭ ምንዛሪን ያስገኛሉ ።

የካፒታሊስት ሀገሮች በሀገራቸው ገበያ ውስጥ ሊጣሩ ያልቻሉትን ሸቀጦቻቸውን ወደ ኋላቀር ሀገሮች ይልካሉ ። በተለይም ሞኖፖል ካፒታሊስቶች ኋላቀር ሀገሮችን የዕቃዎቻቸው ማራገፊያ በማድረግ ፣ ሸቀጦቹንም በሞኖፖል ዋጋ በማትረብ ከፍተኛ ትርፍ ያጋብሳሉ ። በአንፃሩ እነዚሁ ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ኋላቀር ሀገሮች በወጪ ንግድ አማካይነት የሚልኳቸው ሸቀጦች በልዩ ልዩ ተፅዕኖዎች እንዳይገቡ የማገጃ እርምጃዎችን ይወስዳሉ ፤ እንዲገቡ ከፈቀዱም በዝቅተኛ ዋጋ እንዲሸጡ ያደርጋሉ ።

ኋላቀር ሀገሮች ለልማታቸው የሚያስፈልጓቸውን ሸቀጦች ለመግዛት የሚያስችላቸውን የውጭ ምንዛሪ የሚያገኙት በመሠረቱ በወጪ ንግድ አማካይነት ከሚያገኙት ገቢ በመሆኑ የሚልኳቸው ሸቀጦች ዋጋ ዝቅተኛ እየሆነ መሄድ የኢኮኖሚ ዕድገታቸውን ይገታዋል ። የነዚህም ሀገሮች የወጪ ንግድ እንቅስቃሴ ገበያቸው ውሱን በሆነ በጥሬ ዕቃነት በሚያገለግሉ ጥቂት የእርሻና የማዕድን ውጤቶች ላይ በመሆኑ ችግራቸው ይበልጥ ይባባሳል ።

የሞኖፖል ካፒታሊስት መንግሥታት ወደ ውጭ ሸቀጦችን ለሚልኩ የሞኖፖል ድርጅቶች ልዩ ልዩ ድጐማዎችን ያደርጋሉ ። ለምሳሌ ድርጅቶቹ ዕቃዎችን በመላካቸው የተነሣ ከልዩ ልዩ የውስጥ ቀረጦች ክፍያ ነፃ እንዲሆኑ ያደርጋሉ ፤ ወይንም ዝቅተኛ ክፍያ ብቻ እንዲያደርጉ ይወስናሉ ። ከዚህም ሌላ የወጪ ንግድ ለማዳበር በተቋቋሙ አስመጪና ላኪ ባንኮች አማካይነት ወደ ውጭ ለሚልኩ ነጋዴዎች ብድር በመስጠትና ተያዥ በመሆን እንዲሁም የውጭ ሀገር ድርጅቶች ወይም መንግሥታት ከላኪው ሀገር ዕቃዎችን እንዲገዙ ለማስቻል የወጪ ንግድ ብድር በመስጠት ይረዳሉ ።

(የውጭ ንግድን ይመለከቷል ።)

## ወጪና የገቢ ማወዳደሪያ ሒሳብ (የ—)

*(Cost Accounting)*

ኢኮኖሚን ለማንቀሳቀስ ልዩ ልዩ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት የሚያወጡትን ወጪና ሊያገኙ የሚችሉትን ገቢ በቅድሚያ የሚገመግሙበት የሒሳብ ስልት ነው ። ዓላማውም በዝቅተኛ ወጪ ከፍተኛ ውጤት ማስገኘት ሲሆን እያንዳንዱ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የተወሰነለትን ግብ መምታቱን የሚቆጣጠርበት ዘዴ ነው ።

እነዚህ ድርጅቶች ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩ ፣ ባላቸው ሥልጣን ሠራተኞችን የሚቀጥሩ ፣ የሚያሳድጉና የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን የሚሰጡ ፣ የራሳቸውን የገቢና የወጪ ሒሳብም የሚይዙ ናቸው ። ይህ ሥልጣን ያላቸው ሥራ አስኪያጆች በማምረት ሂደት ውስጥ ለሚከሰቱ ችግሮች የተቀላጠፈ ውሳኔ ለመስጠት እንዲያስችላቸው ያላቸውን ንብረትና ገንዘብ ያለውጣ ውረድ ለማንቀሳቀስ ይችላሉ። ይህም አሠራር በተቻለ መጠን በአነስተኛ ወጪ የዕቅድ ግብን ለመምታት ያስችላቸዋል ።

በሶሻሊዝም የወጪና የገቢ ማወዳደሪያ ሒሳብ ዓላማ በአነስተኛ ወጪ ከፍተኛ ውጤት አስገኝቶ የኅብረተሰቡን ፍላጐት በይበልጥ ማርካት ነው ። በአንፃሩ በካፒታሊስት ሥርዓት የወጪና የገቢ ማወዳደሪያ ሒሳብ የሚያገለግለው ዋጋን በማናርና ወጪን በመቀነስ በተለይም የሥራ ዕምቀትን በመጨመርና ለሥራ አካባቢ ደኅንነት የሚወጡ ወጪዎችን ቀንሶ ትርፍ በማካበት የካፒታሊስቱን የግል ጥቅም ማዳበር ነው ።

## ዋርሶ ቃል ኪዳን ድርጅት (የ—)

*(Warsaw Pact)*

በአውሮፓ ሰላም ንና ደኅንነትን ለማረጋገጥ በአልባንያ ፣ (እስከ 1968) በቡልጋሪያ ፣ በሀንጋሪ ፣ በጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ፣ በፖላንድ ፣ በሩማንያ ፣ በሶቭዬት ኅብረትና በቼኮዝሎቫኪያ መካከል ግንቦት 14 ቀን 1955

በዋርሶ ከተማ የተደረገ የወዳጅነት ፣ የትብብ ርና የመረዳዳት ስምምነት ነው ።

የዋርሶ ቃል ኪዳን ድርጅትን ማቋቋም ያስፈለገበት ምክንያት የምዕራብ አውሮፓ ሀገሮች በ1949 የሰሜን አትላንቲክ ቃልኪዳን ድርጅት ኔቶን በማቋቋም በሶሻሊስት ሀገሮች ሰላምና ደኅንነት ላይ አስጊ ሁኔታ መፍጠ ራቸውና በ1954 ምዕራብ ጀርመን አባል እንድትሆን መፍቀዳቸው ነው ።

የዋርሶ ቃልኪዳን ድርጅት የአባል ሀገሮቹን ደኅንነት ለመጠበቅና በአውሮፓ ሰላም ለማስፈን አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳል ። በመሆኑም አባል ሀገሮች በዓለም አቀፍ ግንኙነታቸው በጦር ኃይል እንደማያ ስፈራሩና ወረራ እንደማይፈጽሙ ወስነዋል ፤ ይሁን እንጂ በአንዳቸው ላይ በጦር መሣሪያ አማካይነት ጥቃት ቢደርስ ሁሉም በአስቸ ኳይ አግባብ ባለው መንገድ በጦር ኃይልም ጭምር የመርዳት ቃልኪዳን ገብተዋል ። ስምምነቱ የእያንዳንዱ አባል ሀገር ብሔራዊ ነፃነት እንዲጠበቅና አንዱ በሌላው ሀገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገባ ይከለክላል። በዓለም አቀፍ ጉዳዮችም ላይ የአባል ሀገሮችን ጥቅም የሚነኩ ከሆነ የጋራ ምክክር ይደረ ጋል ።

የዋርሶ ቃልኪዳን ድርጅት በመጀመሪያ የተቋቋመው ለ20 ዓመት ጊዜ ሆኖ ከዚሁ ጊዜ በኋላ ግን አንድ ሀገር ከድርጅቱ ለመ ውጣት በጽሑፍ ካላሳወቀ በስተቀር ለ10 ዓመት በቀጥታ እየታደሰ እንደሚሄድ በውሉ ላይ ተጠቅሷል ። በተጨማሪም የአውሮፓ ሀገ ሮች ሁሉ በሚፈርሙት ስምምነት መሠረት የአውሮፓን ሀገሮች ደኅንነት ለማስጠበቅ የሚቻልበት ሁኔታ ከተፈጠረ ድርጅቱ ወዲ ያው የሚፈርስ እንደሆነ ስምምነቱ ያመለክ ታል ።

## ዋንኛና መለስተኛ ባሕርያት

*(Primary and Secondary Qualities)*

የነገሮችን ባሕርያት ከነባራዊነት ወይም ከኅሊናዊነት አንፃር ለመለየት ይጠቅማሉ ተብለው የተወሰዱ ፈርጆች ናቸው ። በዚህ አመለካከት መሠረት ዋንኛ ባሕርያት የሚባሉት ከቁስአካል በሐሳብ እንኳን ልንለ ያቸው የማንችል ባሕርያት ናቸው ። ለምሳሌ ቅርፅ ፣ ስፋት ፣ ቅስቃሴ ከቁስአካል ሊለዩ አይችሉም ። ስፋት የሌለው ነገር ቁሳዊ ሊሆን አይችልም ። በመሆኑም ቅርፅ ፣ ስፋት፣ ቅስቃሴ ፣ መጠን ወዘተ... ከቁስአካል ሊገነ ጠሉ ስለማይችሉ የሱ ዋንኛ ማለትም ነባራዊ ጠባዮች ናቸው ። መለስተኛ ባሕርያት የተባ ሉት የቁስአካል ነባራዊ ባሕርያት ሳይሆኑ ነገር ግን በሱ አማካይነት በተለይም በሕዋ ሳት ሥር ላይ ባላቸው ተገብሮት በሐሳባችን ውስጥ የሚፈጠሩ ሕውስታዎች ናቸው ። የእነ ዚህ ዓይነቶቹ እውንነት ኅሊናዊ ብቻ ነው ለምሳሌ ቀለም ፣ ሽታ ፣ ድምፅ ፣ ሙቀት ወዘተ ... የቁስአካል መለስተኛ ዐይነቶች ናቸው ። ሙቀትን ብንወስድ ሕውስታ እንጂ እራሱ ሞቃቱ ነገር የሚሰማው ነባራዊ ጠባይ ነው ለማለት አይቻልም ።

የቁስአካል ባሕርያትን ነባራዊና ኅሊናዊ በማለት ለመከፈል የሚጥር ይህ አመለካከት የተዛባ አስተሳሰብን የሚያንፀባርቅ ነው ። የቁስአካል ዓይነት ሆኖ ነባራዊ አይደለም ብሎ መናገር የቁስአካልን ዋና ባሕርይ ማለ ትም ነባራዊነቱን ማዛባት ይሆናል ። ውስ ብስቡን የንቃተ ኅሊናን የማንፀባረቅ ችሎታን በትክክል መገንዘብ ከማስፈለጉም በላይ ችሎ ታው እራሱ ቁሳዊ መሠረት እንዳለው መገንዘብ ያሻል ። ይህ ቁሳዊ መሠረት ያለውን የዕድገት ደረጃ የማንፀባረቁን ጠባይ ውስብስብ ያደርገዋል ። ቁስአካል ነባራዊ ያል ሆኑ ዓይነቶች አሉት የሚለው አመለካከት በርክሌይና ሂዩም ለተባሉት ሐሳባውያን ፈላስፎች የቁስአካልን መኖር ለመካድ ጠቅ ሟቸዋል ። ቀለም ኅሊናዊ ከሆነ ቀለም ስለሌ ለው ስፋት ለማሰብ ስለማይቻል ስፋት እራሱ ኅሊናዊ ነው በማለት በርክሌይ የቁስአካልን ዓይነቶች ሁሉ ኅሊናዊ በማድረግ ቁስአካል ህልውና የለውም ለማለት በቅቷል ።

(ተናክአታዊ ቁስአካልነትን ይመለከቷል ።)

## ዋጋ

*(Price)*

የሸቀጦች እሴት የገንዘብ መልክ ወይም ገንዘባዊ መግለጫ ነው ። ስለዚህም የዋጋ የመጨመር ወይም የመቀነስ ሂደት የሚሽ ከረከረው በሸቀጦች እሴት አካባቢ ነው ። የአንድ ሸቀጥ አቅርቦት ሲጨምር የዚያ

ሸቀጥ ዋጋ ከሸቀጡ እሴት ዝቅ ሲል ፣ ለሸቀጡ ያለው ፍላጐት ሳይለወጥ የሸቀጡ አቅርቦት ሲቀንስ ደግሞ የዚያ ሸቀጥ ዋጋ ከዚያ ሸቀጥ እሴት ከፍ ይላል ። የአንድ ሸቀጥ እሴትና ዋጋ እኩል ሊሆን የሚችለው በገበያ ላይ የዚሁ ሸቀጥ አቅርቦትና ፍላጐት ተመጣጣኝ በሚሆንበት ጊዜ ብቻ ነው ።

| የሸቀጥ ዋጋ (በብር) | የሸቀጥ አቅርቦት | የሸቀጥ ፍላጐት |
|---|---|---|
| 10 | 500 | 100 |
| 9 | 400 | 200 |
| 8 | 300 | 300 |
| 7 | 200 | 400 |
| 6 | 100 | 500 |

በዚህ ሠንጠረዥ መሠረት የሸቀጡ አቅርቦትና ፍላጐት እኩል ሆኖ የሚታየው የሸቀጡ ዋጋ ብር 8 ሲሆን ነው ። ይህም ዋጋ የሚያሳየው ያን የተወሰነ ሸቀጥ ለማምረት የፈሰሰው የሰው የሥራ ኃይል በገንዘብ ሲመነዘር ስምንት ብር መሆኑንና ይህም ስምንት ብር የሸቀጡ ትክክለኛ እሴት መሆኑን ነው። የሸቀጡ አቅርቦት ከሸቀጡ ፍላጐት በታች ወይም በላይ ሲሆን ዋጋው ከእሴቱ ዝቅና ከፍ ሲል ይታያል ።

በካፒታሊዝም የነፃ ውድድር ደረጃ ተመሳሳይ የሆኑ ሸቀጦችን የሚያመርቱ ብዙ ካፒታሊስቶች በመኖራቸውና እያንዳንዱ ካፒታሊስት በተናጠል ለገበያ የሚያቀርበው ሸቀጥ አነስተኛ በመሆኑ ዋጋን የሚወስነው ገበያው ነው ። ማለትም በዚህ ደረጃ የማናቸውም ወደ ገበያ የሚቀርብ ሸቀጥ ዋጋ የሚወስነው ሸቀጡ ገበያ ውስጥ በቀረበበት መጠንና (አቅርቦት) ለዚያ ሸቀጥ በገበያ ውስጥ ባለው ፍላጐት አንፃር ነው ማለት ነው ። በካፒታሊዝም የነፃ ውድድር ደረጃ ሻጮች ለተወሰነ የሸቀጥ መጠን የሚጠይቁት ዋጋ በዚያ በተወሰነ ገበያና በተወሰነ ጊዜ ሸማቾች ለመክፈል ከሚፈልጉት ዋጋ ጋር እኩል የመሆን አዝማሚያ ያሳያል ።

ካፒታሊዝም ከነፃ ውድድር ደረጃ አልፎ ወደ ሞኖፖል ካፒታሊዝም ደረጃ በሚሸጋገርበት ጊዜ ለገበያ የሚቀርቡ ሸቀጦችን የሚያመርቱ ጥቂት ሞኖፖሊስቶች ብቻ በመሆናቸው የሸቀጦች ዋጋ የሚወስነው እንደ ዝቅተኛው የካፒታሊዝም የዕድገት ደረጃ በገበያው ሳይሆን በጥቂት ሞኖፖሊስቶች ይሆናል ። በመሆኑም በሞኖፖል ካፒታሊዝም ደረጃ ሞኖፖሊስቶች የሸቀጦችን ዋጋ በየጊዜው በማናር የሞኖፖል ትርፍ እያካበቱ የሠርቶ አደር ሕዝቦችን ብዝበዛ በከፍተኛ ደረጃ ያባብሱታል ።

በሶሻሊዝም የሸቀጥና የገንዘብ ግንኙነት በመኖሩ ለልውውጥ የሚመረቱ ሸቀጦች ሁሉ ዋጋ ይኖራቸዋል ። ይሁንና በሶሻሊዝም የማይሸጡና የማይለወጡ እንደተፈጥሮ ሃብት ፣ የማይንቀሳቀስ ንብረት (እንደ ፋብሪካ ፣ እንደ ኃይል ማመንጫ ወዘተ...) ፣ እንደሥራ ኃይል ያሉ ነገሮች የገበያ ዋጋ አይኖራቸውም ። በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ዋጋ የምርትና የፍጆታ መጠንን እንዲሁም የሕዝቡን የመግዛት ዐቅም መሠረት በማድረግ በዕቅድ አውጭ አካላት የሚወሰን ነው ።

የሶሻሊስት አምራች ድርጅቶች በትርፍና በኪሣራ ስሌት መሠረት የሚያመርቱ እንደመሆናቸው ዋጋ ለዕቅድ አውጭ አካላት በምርትና በፍጆታ መካከል ያለውን ግንኙነትና የግንኙነቱንም አዝማሚያ የሚጠቁማቸው መግሪያ ስለሆነ የዕቅዱን ትክክለኛ መሆንና አለመሆን እንዲያውቁ ይረዳቸዋል ።

በዳበረ ሶሻሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የግል ንግድ ባለመኖሩ የሚመረቱ ሸቀጦች በሙሉ የሚከፋፈሉት በመንግሥት ፣ በኅብረት አከፋፋይ ድርጅቶችና በሕዝብ የሸማቾች ማኅበራት ነው ። ይህም በመሆኑ በመንግሥት የዕቅድ አውጭ አካላት የተወሰነው የሸቀጦች ዋጋ የሚጣስበት ሁኔታ የለም ። በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ዋጋ እንደካፒታሊስቱ ኢኮኖሚ ለካፒታሊስቱ ትርፍ መካበት ሲባል በየጊዜው የማያድግ ከሠራተኛው ሕዝብ ገቢ መጨመር ጋር ሁልጊዜም የማይጨምርና ለረዥም ጊዜ የተረጋጋ በመሆኑ የኑሮ ሁኔታ መሻሻልን ያስከትላል ።

ንግድ በሀገር አቀፍ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም የተስፋፋ እንደመሆኑ ከሀገር አቀፍ ዋጋ የተለየ የዓለም ዋጋም አለ ። በተለይ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የዓለም ገበያ ሲባል የዓለም አቀፍ የካፒታሊስትንና የሶሻሊስትን ገበያ የሚመለከት በመሆኑ በሁለቱ የዓለም ገበያዎች ውስጥ የዋጋ ይዘት የተለያየ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ። የዓለም የካፒታሊስት ገበያ ከፍ

ተኛ ፉክክር የሚካሄድበት ፣ ያልተረጋጋና በግብታዊነት የሚንቀሳቀስ ከመሆኑም በላይ የሸቀጦች ዋጋ በኢምፔሪያሊስት ሀገሮች የሚወሰን በመሆኑ የዓለም የካፒታሊስት ገበያ ዋጋ ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ባልተመጣጠነ ንግድ ሳቢያ ኋላቀር ሀገሮችን የሚበዘብዙበት ዓይነተኛ መሣሪያ ነው ። በአንፃሩ የዓለም የሶሻሊስት ገበያን በሚመለከት ዋጋ የሚተመነው የእኩያዊ ልውውጥና የጋራ ጥቅም መርህን መሠረት በማድረግ ነው ።

ዋጋ በኮሚኒዝም ደረጃ ከሸቀጥና ከገንዘብ ግንኙነት መክሰም ጋር አብሮ የሚከስም ታሪካዊ የሆነ የኢኮኖሚ ፈርጅ ነው ።

(እሴትን ፣ አቅርቦትን ፣ ፍላጐትን ይመለከቷል ።)

## ዋጋ ርግበት (የ—)
*(Deflation)*

በገበያ ውስጥ ካሉ ሸቀጦችና አገልግሎቶች አንፃር በዝውውር ውስጥ ያለ ገንዘብ መጠን አንሶ ሲገኝ ወይም በአንዳንድ የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ምክንያት ሰዎች ገንዘባቸውን ከማውጣትና ዕቃ ከመግዛት በመቆጠባቸው የገንዘብ የዝውውር መጣኔ በሚቀንስበት ወቅት አጠቃላይ የዋጋ ደረጃ መቀነስ ይታያል ። እንዲህ ዓይነት አጠቃላይ የዋጋ ደረጃ መቀነስ ሲታይ የዋጋ ርግበት አለ ይባላል ። ይህ ሁኔታ በካፒታሊስቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ሲደርስ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ይቀንሳል ፤ ሥራ አጥነት ይጨምራል ፤ ብሔራዊ ገቢ ያንሳል ፤ የሠራተኛው ምንዳም ይቀንሳል ።

የዋጋ ርግበት ብዙውን ጊዜ ከገንዘብ ፖሊሲ ለውጥ ጋር የተያያዘ ነው ። በተለይም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በካፒታሊስት ሀገሮች ከመጠን በላይ የበዛውን የወረቀት ገንዘብ በመቀነስ የዋጋ ንረትን ዕድገት ለመቆጣጠር አልፎ አልፎ በተግባር ላይ ለማዋል የተሞከረ ፖሊሲ ነው ። ይህን ፖሊሲ የካፒታሊስት መንግሥታት ተግባር ላይ ያዋሉት የወለድ መጠንን በመጨመርና የዱቤ መጠንን በመወሰን ፣ የዱቤ አሰጣጥን በመቆጣጠር ፣ ታክስ በመጨመር ለማኅበራዊና ባህላዊ ጉዳዮች የሚወጣውን ወጪ በመቀነስ ፣ የምንዳና የደመወዝ ጭማሪን በማቆምና ተመሳሳይ እርምጃዎችን በመውሰድ ነው ።

ይህ ዓይነት እርምጃ ደግሞ የኢኮኖሚ ዕድገት መጠንን በመቀነስ የሠርቶ አደር ሕዝቦች የኑሮ ሁኔታ እያቆለቆለ እንዲሄድ የሚያደርግ በመሆኑ በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ያለውን የመደብ ትግል በይበልጥ እንዲካረር ያደርገዋል ።

(የዋጋ ንረትን ይመለከቷል ።)

## ዋጋ ንረት (የ—)
*(Inflation)*

የተመረቱና በገበያ ላይ የወጡ ሸቀጦችን ለማዘዋወር አስፈላጊ ከሆነው በላይ የወረቀት ገንዘብም ሆነ የዱቤ ገንዘብ መጠን በመጨመሩ ምክንያት የሚከተለው አጠቃላይ የሸቀጦች ዋጋ ማሻቀብ ነው ። ይህ ሁኔታ ሲፈጠር የወረቀት ገንዘብ የመግዛት ኃይል ይቀንሳል ።

የዋጋ ንረት ከወረቀት ገንዘብ በፊት የተለያዩ መሀለቆች እንደዝውውር አማካይ ሆነው ያገለግሉ በነበረበት ጊዜ ሁሉ የነበረ ክስተት ነው ። ይሁን እንጂ ቃሉ በኢኮኖሚያዊ ጽንሰ ሐሳብነት መጠቀስ የጀመረው በ19ኛው ምዕት ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ላይ ሲሆን በስፋት በተግባር ላይ መዋል የጀመረው ግን በ20ኛው ምዕት ዓመት ነው ።

ከወረቀት ገንዘብ በፊት የዋጋ ንረት ይከሰት የነበረው መንግሥት መሀለቆችን በብዛት ሠርቶ ሲያወጣ ወይም ሕገወጥ በሆነ መንገድ የተሠሩ ሙሉ እሴት የሌላቸው መሀለቆች በዝውውር ላይ ሲውሉ ወይም የይስሙላ እሴት ባላቸው የነሐስ መሀለቆች ምትክ የመዳብ መሀለቆች ሲተኩ ነበር ። ይህ ሁኔታ የመሀለቆች የመግዛት ኃይል እንዲቀንስ ፣ ከእውን ገቢ አንፃር ሲታይ የገንዘብ እሴት እንዲያቆለቁል ከማድረጉም በላይ በከተማና በገጠር መካከል ይካሄድ የነበረውን የሸቀጥ ልውውጥ በመግታት በተለይም ከገጠር የእርሻ ውጤት ወደ ከተማ እንዳይገባ በማድረግ ቀውስ ይፈጥር ነበር ። ከዚህም ሁኔታ ለመውጣት መንግሥት ከዝ

ውውር ውስጥ ትርፍ የሆኑ የመዳብ መሀለቆችን ለማውጣት ወይም የመሀለቆችን የይስሙላ እሴት ለመቀነስ ይገደድ ነበር ።

ከወረቀት ገንዘብ መከሰት በኋላ በመሀለቆች አማካይነት ይከሰት የነበረው ንረት ወደ ወረቀት ገንዘብ ንረት ተሸጋገረ ። በ18ኛውና በ19ኛው ምዕት ዓመት ይህ የዋጋ ንረት ሁኔታ በተለያዩ የካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ ተከስቶ ነበር ።

ከካፒታሊዝም መዳበርና ከካፒታሊዝም የኢኮኖሚ ቀውስ እየተካረረ መምጣት ጋር በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የዋጋ ንረት ቋሚና ሁለንታዊ ጠባይ እየያዘ መጣ ። ካፒታሊዝም አሁን በደረሰበት የመንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም ደረጃ የኢኮኖሚ ቀውስ የሚከሰትበት ዓይነተኛው መልክ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሄድ ላይ በሚገኝ የዋጋ ንረት ነው ። ይህም ሁኔታ አንድ ሀገር ከወጪ ንግድ የሚገኘውን ገቢ በመቀነስ የውጭ ምንዛሪ መጠኑን የሚያሳንስ ከመሆኑም በላይ በዚያ ሀገር ውስጥ አጠቃላይ የሆነ የኑሮን ውድነት ያስከትላል ።

የዋጋ ንረት በሚታይበት ወቅት የሠራተኞች ምንዳ ከሸቀጦች ዋጋ ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ የሚሆንበት ፥ እውን ምንዳ የሚቀንስበትና በምንዳ የሚተዳደሩ የኅብረተሰብ ክፍሎችና የአነስተኛ ሸቀጥ አምራቾች የኑሮ ሁኔታ እየከበደ የሚሄድበት ወቅት ነው ። በካፒታሊስት ሥርዓት የዋጋ ንረት ዓይነተኛ የሆነ የመበዝበዣ መሣሪያ የሚሆነው ዋጋ የሚጨመረው በእያንዳንዱ ካፒታሊስት ሳይሆን የገንዘብ መጠንን በሚቆጣጠረው በቡርዧው መንግሥት አማካይነት አጠቃላዩን የካፒታሊስት መደብ በሚጠቅምበት መንገድ ስለሆነ ቀጥተኛ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ የሠራተኛው መደብና ሌሎችም ሠርቶ አደሮች የሚበዘበዙበት ዘዴ ነው ። የዋጋ ንረት እየባሰ ሲሄድ የአንድን ሀገር አጠቃላይ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚያናጋና በመደቦች መካከል የሚካሄደውን ትግል ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚያደርስ ነው ።

በሶሻሊስት ኢኮኖሚ በዝውውር ውስጥ የሚሰራጨው የወረቀት ገንዘብ መጠን በዝውውር ውስጥ ከሚገኙ ሸቀጦች ጋር እንዲጣጣም ስለሚደረግ የዋጋ ንረት ቀውስ ሊኖር አይችልም ። በሶሻሊዝም የሸቀጦች ዋጋ በመንግሥት የሚተመን በመሆኑ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሚመረተውም ሸቀጥ እንደዚሁ በዕቅድ የሚወሰን ስለሆነ ሸቀጦችን ለማዘዋወር የሚያስፈልገውን የወረቀት ገንዘብ መጠን ለመተመንና ለመቆጣጠር ሁኔታው አመች ነው ። ሆኖም በጦርነት ጊዜ ፥ ዕቅድን በሚገባ ባለማሟላት ወይም በዕቅድ ነዳፊው አካል በሚፈጸሙ አንዳንድ ስህተቶች ምክንያት በዝውውር ሂደት ውስጥ አስፈላጊ ከሆነው በላይ የወረቀት ገንዘብ ሊጠራቀም ይችላል ። ይህ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ ወዲያውኑ የገንዘብ ፖሊሲ ለውጥ በማድረግና የአጭር ጊዜ ዕቅድን ከብሔራዊ ኢኮኖሚው ሁኔታ አንፃር በማስተካከል ለማስወገድ ይቻላል ።

እንደ ካፒታሊስቱ ኢኮኖሚ ሳይሆን የሶሻሊስት ኢኮኖሚ የወረቀት ገንዘብን መረጋጋት የሚያረጋግጡ አጠቃላዩን ብሔራዊ ኢኮኖሚ የፋይናንስ ዕቅድ በማውጣት ሂደት ውስጥ የኢኮኖሚው በገንዘብና በቁሳዊ ጎኖች መካከል ያለውን ተመጣጣኝነት በመጠበቅ ነው ።

## ውል

*(Treaty)*

በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት ሁለት ወይም ከሁለት የሚበልጡ መንግሥታት የተስማሙበትን ነገር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ ግዴታ የሚገቡበት ስምምነት ነው ።

ውል የተለያየ ቅርፅ ሊኖረው ይችላል ። የተለመደው የውል ዓይነት ሁለት ወይም ከሁለት የበለጡ መንግሥታትን ግዴታ የሚያስገባው ኮንትራት የተሰኘው ነው ። ይህም የተወሰነ ዓላማና ዕቅድ ይኖረዋል ፤ የሚጸናበት የጊዜ ገደብም አለው ። የጋራ መግለጫና የመልእክት ልውውጥ መልክ ሊኖረው ይችላል ።

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና በቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶቹ ፥ በልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ማኅበራት እንዲሁም በመንግሥታት በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ውሎች ተፈጽመዋል ።

ውል በሁለት ወይም ከሁለት በበለጡ መንግሥታት መካከል በሙሉ ፈቃደኝነትና

ስምምነት የሚያረግ ነው ይባል እንጂ በአንዱ ወገን ተፅዕኖ የሚፈጸምበትም ጊዜ አለ ። ለምሳሌ የጃፓን መንግሥት በ1951 የፈረመው የሰላም ውል የጃፓን መልዕክተኞች አስቀድመው የተደራደሩበትና የተስማሙበት አልነበረም ። የአሜሪካ መንግሥት ውሉን በግሉ ነድፎ በማቅረብ የጃፓን መንግሥት እንዲቀበለው ጠየቀ ። እንደዚሁም በ1951 በመስከረም ወር የተጠራው የሳንፍራንሲስኮው ጉባኤ አስቀድሞ የተዘጋጀውን ውል ያላንዳች ለውጥና ውይይት መንግሥታት በይፋ እንዲፈርሙበት የተጠራ ነበር ። ሶቪዬት ኅብረት ፣ ሌሎች ሶሻሊስት ሀገሮችና ህንድ በዚህ ሁናቴ እንፈርምም ብለዋል ።

በኢምፔሪያሊስት መንግሥታትና በአዳጊ ሀገሮች መካከል የሚደረጉት ውሎች አብዛኛውን ጊዜ ለኢምፔሪያሊስቱ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ ጥቅሞች የሚያደሉ ናቸው ። ምክንያቱም የኢምፔሪያሊዝም ሀልውና በብዝበዛ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ እኩል ተጠቃሚነትን ሊቀበል ስለማይችል ነው ።

በውሎች ላይ የቋንቋ ጉዳይ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠውና ብዙ ጊዜም ችግር የፈጠረ ነው ። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን በሚመለከት ረገድ በይፋ የታወቁት አምስት ቋንቋዎች እንግሊዝኛ ፣ ፈረንሳይኛ ፣ እስፓንኛ ፣ ሩሲኛና ቻይንኛ ናቸው ።

በሁለት መንግሥታት መካከል የሚደረጉ ውሎች አብዛኛውን ጊዜ የሚጻፉት በሁለት ቅጅ ፣ ማለትም በእያንዳንዱ መንግሥት መደበኛ ቋንቋ ሲሆን የሁለቱ መንግሥታት እንደራሴዎች በሁለቱም ላይ ይፈርማሉ ። ስለሌላው ቋንቋ ትክክለኛ ትርጓሜ የተለየ አስተያየት እንዳይፈጠር ለመጠንቀቅም በዓልም የታወቀ ሦስተኛ ቋንቋ ፣ አብዛኛውን ጊዜ እንግሊዝኛን ወይም ፈረንሳይኛን መጨመር የተለመደ ነው ።

ውልንና ቋንቋን በሚመለከት በሀገራችን ጥሩ ምሳሌ ሆኖ ዘወትር የሚጠቀሰው የውጫሌ ውል ነው ። የዚህ ውል አንዱ አንቀጽ በአማርኛውና በጣሊያንኛው የተለያየ ትርጉም ይዞ መገኘት መሠረታዊው ምክንያት ባይሆንም ለአድዋው ጦርነት መቀስቀስ ሰበብ ሆኗል ።

## ውስብስብ ሥራ
*(Complex or Skilled Labour)*

ውስብስብ ሥራ ለአንድ የተወሰነ የሙያ ዘርፍ ሥልጠናንና ልምድን የሚጠይቅ ሥራ ነው ።

ሥልጠናንና የሥራ ልምድን ለመቅሰም ወይም ለማግኘት የሚደረገው ወጭ የሥራ ኃይሉን እሴት ከፍ ያደርገዋል ፤ የሥራውንም ውስብስብነት ያመለክታል ። ለምሳሌ ግንበኛ ፣ ቀያሽና መሐንዲስ የሚሠሩት ውስብስብ ሥራ ቢሆንም ውስብስብነቱ የተለያየ ደረጃ ይኖረዋል ። በተለያየ ደረጃ ላይ ውስብስብ ሥራ የሚሠሩ ሰዎች የሚያስገኙት እሴት ቀላል ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ከሚያገኙት እሴት ከፍተኛ ስለሚሆን የሚያስገኙትም ክፍያ ቀላል ሥራ ከሚሠሩ ሠራተኞች በዚያው መጠን ከፍ ይላል ።

(ቀላል ሥራን ይመለከቷል ።)

## ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር
*(Organic Composition of Capital)*

በቋሚ ካፒታልና በተለዋዋጭ ካፒታል መካከል ያለው ጥምርታ እሴታዊ ጥንቅሩ በቴክኒካዊ ጥንቅሩ እስከተወሰነና የዚህንም ቴክኒካዊ ለውጥ እስከአሳየ ድረስ ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር ይባላል ።

ካፒታል በተከማቸ መጠን የካፒታል ጥንቅሩ እየተለወጠ ይሄዳል ። ይህንን ለውጥ በአካላዊ መልኩ ስንመለከት ምን ያህል ሕንፃዎች ፣ ማሽኖች ፣ ጥሬ ዕቃዎች ፣ ነዳጅና የመሳሰሉት ከምን ያህል የሥራ ኃይል ጋር እንደተቀናጁ ወይንም ቴክኒካዊ የካፒታል ጥንቅሩን ሲያሳየን ፤ በእሴት መልኩ ደግሞ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በምርት መገልገያዎች እሴትና (በቋሚ ካፒታል) በሥራ ኃይል እሴት (በተለዋዋጭ ካፒታል) መካከል ያለውን ቅንጅት የሚያሳይ ነው ።

በውስጣዊ የካፒታል ጥንቅርና በቴክኒካዊ የካፒታል ጥንቅር መካከል የጠበቀ ግንኙነት አለ ። ቴክኒካዊ የካፒታል ጥንቅሩ ባደገ መጠን ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅሩም

እንዲሁ እየተለወጠ ይሄዳል ። በቴክኒካዊ የካፒታል ጥንቅር ዕድገት ሳቢያ ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅሩ የሚያሳየው የዕድገት ለውጥ መጠን የሚወሰነው በምርት መገልገያዎች እሴትና በስግዊ ምንዳ ለውጥ አኳያ ነው ።

ከረዥም ጊዜ አንፃር ሲታይ የካፒታል ክምችት እያደገ በሄደ መጠን ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅሩም እያደገ ይሄዳል ። በመሆኑም ጥቅም ላይ የሚውለው የሥራ ኃይል መጠን ዕድገት ከጠቅላላ ማኅበራዊ ካፒታሉ ዕድገት አኳያ ሲታይ እየቀነሰ ስለሚመጣ ለተጠባባቂ ሥራ አጥ ሠራዊት መበራከት ምክንያት ይሆናል ። በተጨማሪም የካፒታል ክምችቱ አነስተኛ አምራቾችን በማፈናቀል የሥራ ኃይል አቅርቦቱ መጠን እንዲያድግ ስለሚያደርግ የሥራ አጥ ሠራዊቱ ቁጥር እንዲጨምርና ሁኔታው እንዲባባስ ምክንያት ይሆናል ።

(የካፒታል ክምችትን ፣ ቴክኒካዊ የካፒታል ጥንቅርን ይመለከቷል ።)

## ውስጣዊና ውጫዊ ቅራኔዎች

*(Internal & External contradictions)*

ውስጣዊ ቅራኔ የሚያመለክተው በአንድ ነገር ውስጥ ያሉትን የሁለት ተቃራኒ ልዝማሚያዎች ግንኙነትና ትግል ሲሆን ውጫዊ ቅራኔ ደግሞ የሚገልጸው ነገሩ ከአካባቢው ጋር ያለውን ግንኙነት ነው ። ወሳኝ ሚና የሚጫወተው ማለትም የነገሩን ምንነትና የመጨረሻ ውጤት የሚወስነው ውስጣዊ ቅራኔ ነው ። ነገሩ የሚደርስበት ለውጥና ዕድገት ከውስጥ እንቀሳቃሽ ኃይል የሚመነጨ እንጂ በውጭ ተፅዕኖ የሚደረጉ ባለመሆናቸው ውስጣዊ ቅራኔ ዋናውን ቦታ ይይዛል ።

ሆኖም አንድ ነገር ከራሱ ጋር ብቻ የሚገናኝ ባለመሆኑና ከአካባቢው ነገሮች ጋር የተለያዩ ግንኙነቶች ስላሉት ዕድገቱ ከውጭ ተፅዕኖ ነፃ ሊሆን አይችልም ። ይህም ሲባል የውጭ ተፅዕኖ ነገሩን እንዳመቸው ይለውጠዋል ማለት አይደለም ፤ ምክንያቱም ማንኛውም የውጭ ቅራኔ ተፅዕኖ ሊያደርግ የሚችለው የነገሩ ውስጣዊ ቅራኔ በሚፈቅድለት መንገድ ብቻ ነው ። በመሆኑም የውጭ ቅራኔ የነገሩን ዕድገት ሊያፋጥን ወይም ሊጐትት ይችላል እንጂ እስከ መጨረሻው ሊገታው ወይም ወደ ሌላ ሁኔታ ሊቀይረው አይችልም ።

ለምሳሌ ኅብረተሰብን እንውሰድ ። የኅብረተሰቡ የውስጥ የመደብ ቅራኔ ውስጣዊው ቅራኔ ነው ፤ ከሚያካብበው ተፈጥሮ ወይም ከጐረቤት ሀገር ጋር ያለው ግንኙነት ውጫዊ ቅራኔ ነው ። የአካባቢው ሁኔታ ለምሳሌ ያለው የተፈጥሮ ሀብት የኅብረተሰቡን ዕድገት ሊያፋጥን ወይም ሊጐትት ይችላል ። እንዲሁም ከጐረቤት ሀገር ጋር ያለው ጥሩ ወይም መጥፎ ግንኙነት በዕድገቱ ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል ። ሆኖም በመጨረሻ ዕድገቱን የሚወስነው ማለትም አቅጣጫውን የሚቀይሰውና ውጤቱን የሚያስገኘው በውስጡ ያለው የመደብ ቅራኔ ሂደት ነው ።

## ውበት

*(Beauty)*

ሰው የሥነ ጥበብ ሥራዎችን ሆነ እውነታን በመመልከት የሚያገኘውን ሕውስታዊ ደስታ የሚገልጽ የሥነ ውበት ፈርጅ ነው ። ውበት ሕውስታዊ በሆነ መንገድ በየመስኩ የሚያንፀባርቀው የሰውን ነፃ ፈጠራና የግንዛቤ ችሎታ ነው ።

በሐሳባውያን አመለካከት የውበት ጠባይና ህልውና መንፈሳዊ ነው ማለትም ውበት የሐሳብ ወይም የንቃተ ኅሊና ብቸኛ ንብረት ነው ። በቅድመ ማርክሳዊ ቁስአካላውያን አስተሳሰብ ውበት ነባራዊነት ያለው ቢሆንም ከነገሮች የተለያዩ ክፍሎች አካላዊ መጣጣም የሚነጭ በማድረግ በተፈጥሮአዊ ባሕርይ ብቻ የሚወሰን አድርገው ተርጉመውታል ።

ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ውበትን የማኅበራዊ ታሪክ ተግባር ውጤት አድርጎ ይገነዘባል ። ውበት የሚከሰተው ሰው በማኅበራዊ ኑሮ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት ውስጥ በመፍጠር ችሎታው ሙሉ በሙሉ ሲጠቀም ነው ። የሚፈጠረው ደስታም የሚገልጸው ሰው የሕውስታዊ ዓለም ተደራጊዎች ባለቤት መሆኑንና አካላዊና አእምሮአዊ ችሎታዎች

በመጣጣም አብረው መሥራታቸውን ነው ። ውበትን የመፍጠር ኃይል ሙሉ በሙሉ የሚከሰተው በሥነ ጥበባዊ ሥራዎች ውስጥ ነው ።

ውበት በኅብረተሰብ ውስጥ የሚጫወተው የግንዛቤና የትምህርት ሚና ከፍተኛ ነው ። ተራማጅ ሚና ያለውም እውነታ የሚያንፀባርቀው ውበትን ነው ። የኮሚኒስት ሥርዓት ግንባታ ፣ ባለው አብዮታዊ ግብና በሚጠይቀው ቆራጥ ትግል ከመቼውም ይበልጥ የውበትን ስሜት የሚያፈልቅ ሁኔታ ነው ።

(ሥነ ውበትን ይመለከቷል።)

## ውዥምብር
*(Confusion)*

በጥሬ ትርጉሙ ግራ መጋባት ፣ ትርምስምስ ፣ ግልጽ ያልሆነ ተጨባጭነት የሌለው ፣ ሊታመን የማይቻል ፣ የተምታታና አደናጋሪ ድርጊት ፣ ሁኔታ ወይም የወሬ ስርጭት ነው ። የሰዎችን እምነት ለማዳከም ፣ ቆራጥነታቸውን ለማላላት ፣ ሞራላቸውን ለማላሸቅ ጠላት በወሬና በአሉባልታ የሚያካሂደው ሥነ ልቡናዊ ዘመቻ ነው ።

በኢትዮጵያ አብዮት መጀመሪያ ዓመታት ላይ የአብዮቱ ጠላቶች በውስጥና በውጭ ሴራቸውን በማፋፋም አብዮቱን በከፍተኛ ፈተና ላይ በጣሉበት ወቅት የውዥምብር ንዛታን ጠላት በሰፊው ይጠቀምበት የነበረ ዘመቻ ነበር ። ውዥንብር የመንዛት ዓላማውም ሰፊው ሕዝብ በሀገሪቱ ውስጥ ሕግና ሥርዓት እንደሌለ አድርጐ እንዲቆጥርና በአብዮቱ ላይ እምነት እንዳይኖረው ለማድረግና በዚህም ሁኔታ በመጠቀም ለአብዮት ቅልበሳ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ነበር ።

ውዥምብር ለፀረ አብዮት ቅስቀሳ እንዲያመች አድርጐ ነገሮችን በማጋነን ፣ በማዛባትና ያልሆነውን እንደሆነ አድርጐ በማውራትና በማስወራት በሰፊው ሕዝብ አእምሮ ውስጥ ጭንቀት ለመፍጠር ፣ ለማወናበድ ፣ በዚህም የአብዮቱን ሠፈር አዳክሞ ለመበታተን ፀረ አብዮተኞች የሚያካሒዱት የሐሳብ ጦርነት በመሆኑ የአብዮቱ ወገኖች ሕዝቡ ለዚህ ለጠላት የማወናበጃ ዘዴ እንዳይገበረ ከከ በተቀናጀ ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ሥራ የማስተማርና ትክክለኛውን ነገር በማሳወቅ በሐቀኛው መሥመር የመምራት ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው ።

## ውጭ ምንዛሪ (የ—)
*(Foreign Exchange)*

የተለያዩ የወረቀት ገንዘቦች ባላቸው ሀገሮች መካከል የሚካሄድ የክፍያ ሥርዓት የውጭ ምንዛሪ ይባላል ። የውጭ ምንዛሪ በአንድ ሀገር ባንኮች ውስጥ የሚገኙትን የውጭ ገንዘቦች ወይም ለባንኩ ከውጭ ሀገሮች ገቢ የሚሆኑትን ገንዘቦች እንዲሁም የወርቅን ክምችት ያጠቃልላል ። በሀገሮች መካከል በንግድ ፣ በሙአለ ንዋይና በመሳሰሉት የተነሣ የሚኖሩት የክፍያ ግንኙነቶች የሚከናወኑት በውጭ ምንዛሪሥርዓት ነው ። በውጭ ምንዛሪ አማካይነት መንግሥታትና ድርጅቶች ዕዳቸውንና ሌላ የክፍያ ግዴታቸውን በብሔራዊ ባንኮች ወደሌላ ሀገር በማስተላለፍ ይወጣሉ ።

ኋላቀር ሀገሮች ከውጭ የሚያስመጧቸው የልማትና የፍጆታ ዕቃዎች ፣ እንዲሁም ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚያከናውኗቸው ክፍያዎች መጠን እነርሱ ወደውጭ ከሚልኳቸው የእርሻ ፣ የማዕድን ወዘተ... ውጤቶች ከሚያስገኙት ገቢ ጋር ስለማይመጣጠን በየጊዜው የውጭ ምንዛሪ ጉድለት ያጋጥማቸዋል ። የሶሻሊስቱን የዕድገት ፈለግ የሚከተሉ ሀገሮች የውጭ ምንዛሪ አቋማቸው ጤናማ እንዲሆን በየጊዜው የተለያዩ እርምጃዎችን ይወስዳሉ ። የካፒታሊስት የዕድገት ጐዳናን የሚከተሉት ኋላቀር ሀገሮች ግን ኢኮኖሚያቸው ከዳበሩ ካፒታሊስት ሀገሮች ጋር በጥብቅ የተሳሰረ በመሆኑ ከተፅዕኖ ነፃ የሆኑ እርምጃዎችን ለመውሰድ ባለመቻላቸው ለውጭ ምንዛሪ አቋማቸው መዛባት ዘላቂ መፍትሔ ለማግኘት አይችሉም ።

(የንግድ ሚዛንን ፣ የክፍያ ሚዛንን ይመለከቷል።)

## ውጭ ንግድ (የ—)
*(Foreign Trade)*

የውጭ ንግድ አንድ ሀገር ከሌሎች ሀገሮች የሚያስገባውን ሸቀጥና አገልግሎት እንዲሁም ወደሌሎች ሀገሮች የሚልከውን

ሸቀጥና አገልግሎት የሚይዝ ሥርዓት ነው ። የውጭ ንግድ መሠረት በሀገሮች መካከል ያለው የሥራ ክፍፍል ነው ። በቅድመ ካፒታሊስት ኅብረተሰቦች የዕድገት ታሪክ ውስጥ የውጭ ንግድ ለምርት ዕድገትና ለገንዘብ ሸቀጥ ግንኙነቶች መዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል ። ይህ ሁኔታም በአንድ ሀገር ውስጥ በሚከናወኑ የምርት የሥራ ዘርፎች ውስጥ ፣ በዓለም ደረጃም በሀገሮች መካከል የሥራ ክፍፍል እንዲዳብር ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል ።

የካፒታሊስትን ስልተ ምርት ማዳበርና ማሳደግ ካስቻሉት ሁኔታዎች ውስጥ ዋንኛው የውጭ ንግድ ነበር ። የውጭ ንግድ መዳበርና የዓለም ገበያ መፈጠር ለካፒታሊስት ኢኮኖሚ ማደግና መዳበር አመች ሁኔታን ፈጥሮአል ። የካፒታሊስት ስልተ ምርት ከዳበረ በኋላ የውጭ ንግድን በከፍተኛ ደረጃ አስፋፍቷል ። የካፒታሊስት ስልተ ምርት በዘመናዊ የማሺን ምርት ያመረታቸው ሸቀጦች ከሀገር ውስጥ የገበያ ፍላጐት በማለፍ የውጭ ገበያዎችን መፈለግ ግዴታ በመሆኑ ይኸ ሁኔታ የውጭ ንግድን መስፋፋት አስከትሏል ።

የካፒታሊስት ሀገሮች በየሀገሮቻቸው እንፃራዊ የሆነ በላጥ ምርት ይገጥማቸዋል ። ይህንንም ችግር የሚፈቱት በውጭ ገበያ አማካይነት ነው ። በውጭ ገበያነት ከሚያገለግሉትም መካከል የኋላቀር ሀገሮችም ይገኙባቸዋል ። በእነዚሁ የኋላቀር ሀገሮች ገበያ ለመጠቀም ካፒታሊስቶች ከፍተኛ ሽሚያ ያካሂዳሉ ። የዚህ ሽሚያ ዋናው ምክንያት በሀገራቸው ከሚሸጡት ዋጋ በላይ በኋላቀር ሀገሮች ገበያ ላይ ሸቀጦችን አቅርበው በውድ በመሸጥ ከፍተኛ ትርፍ ለማግኘት መቻላቸው ነው ።

አንድ መንግሥት ከውጭ በሚገቡ ሸቀጦች ላይ የገቢ ቀረጥ በመጣል ገቢ ያገኛል ። በተጨማሪም አንዳንድ ጊዜ የሀገር ውስጥ ምርቶች በሀገር ውስጥ ገበያ ላይ ከውጭ በሚገቡ ሸቀጦች የሚደርስባቸውን ፉክክር ለመቋቋም የሚያስችል የገቢ ቀረጥ ይጥላል ። አንድ ሀገር ወደውጭ በሚልካቸው ሸቀጦችና አገልግሎቶች የውጭ ምንዛሪ የሚያገኝ ሲሆን ፣ ወደሀገር ውስጥ ለሚያስገባቸው ሸቀጦችና አገልግሎቶች ደግሞ የውጭ ምንዛሪ ይከፍልባቸዋል ።

(የንግድ ሚዛንን ፣ የሥራ ክፍፍልን ይመለከቷል።)

# ዘ

## ዘረኝነት
*(Racism)*

ከቀለም ወይም ከዝርያ ልዩነት የተነሣ እራስን የተሻለ አድርጐ በመገመት ሌላውን መናቅ ፣ መጨቆን ፣ የበታች አድርጐ ማየትና ሲቻልም ማስገበር ማለት ነው ። የዚህ ዓይነቱ የዘረኝነት ተግባርም በአንድ ሀገር ውስጥ ባሉ ልዩ ልዩ ጐሳዎች ፣ ነገዶች ወይም ዝርያዎች መካከል ወይንም ደግሞ በዘር ፣ በቀለም ፣ በመሳሰሉትና በተለያዩ ምክንያቶች ላይ ተመርኩዞ ልዩነቶችን በመፍጠር የአንድ ሀገር ሕዝብ በሌላው ሀገር ሕዝብ ላይ ሊፈጽመው የሚችል ነው ። ይሁን እንጂ ዘረኝነት በተለይ በቀለማቸው በተለያዩ ክፍሎች (ለምሳሌ በጥቁርና በነጭ ሕዝቦች) መካከል ሲፈጸም የጐላና የከረረም ሆኖ ይገኛል ። በቋንቋና በባህል ልዩነት ምክንያትም የዘረኝነት ድርጊት የሚፈጸምባቸው ሁኔታዎች ብዙ ናቸው ።

ዘረኝነትን እንደመመሪያቸው አድርገው የሚጠቀሙ ወገኖች ወይም መንግሥታት ለድርጊታቸው የተለያዩ ምክንያቶች ቢሰጡም መሠረታዊ ዓላማቸው የተወሰኑ ክፍሎችን የኢኮኖሚ መብት ማሳጣት ፣ የራሳቸውን ቁሳዊ ጥቅምና ማኅበራዊ ክብር ከፍ ማድረግ ነው ። ለዚህም እንዲያመቻቸው እንደ ዝቅተኛ ዘር የሚቆጥሯቸውን ክፍሎች የሥራ ኃይል በርካሽ ዋጋ ለመበዝበዝና በአጠቃላይም ማኅበራዊና ባህላዊ አቋማቸውን በተዋራጅ ደረጃ ለመገደብ የሚያስችላቸውን ሥርዓትና ሕግ ያወጣሉ ።

በታሪክ ሂደት የዘረኝነት ምክንያቶችና የአፈጻጸም ገጽታዎች በተለያዩ መልኮች ተከስተዋል ። በተለይም አንዱ ሕዝብ ከሌላው ጋር ጦርነት እየገጠመ ድልን ሲቀዳጅ ተሸናፊውን ወገን አገልጋይና ተገዥ የማድረጉ ሁኔታ ሲስፋፋና ይህም በተወሰኑ ሕዝቦች ላይ ሲደጋገም አንዱ ዘር ታላቅና ተከባሪ ፣ ሌላው ደግሞ ተዋራጅና የበታች የመሆን ሁኔታ የቋሚነት ባሕርይ ሲሰጠው ይታያል ።

በዘመናዊ ዕድገትም ላይ አንዱ ዘር የሌላውን መሠረታዊ ጥቅም የሚሻማ መስሎ ሲገኝ በዘር ልዩነት አስታከ መቃወምና አንዱን ወገን በሌላው ላይ ማነሣሣት የብዙ በዛ ሥርዓት አቀንቃኞች መመሪያ ሆኖ ተከስቷል ። መሠረቱ ኢኮኖሚያዊ የሆነውን ይህን የዘረኝነት አቋም ትክክለኛ ለማስመሰል ዘረኞች ከሚጠቀሙባቸው ሰውር ዘዴዎች መካከል ሊጨቁኑት የሚፈልጉትን ወገን የትምህርት ዝቅተኛነት ፣ የዕድገት ኋላ ቀርነትና የመሳሰሉትን እንደምክንያት በመስጠት "እናሠለጥናቸዋለን" ፣ "ራሳቸውን ለማስተዳደር አይችሉም" ወይንም ይህ መሰክና ሁኔታ ለነሱ አይገባም እያሉ በትምክህተኝነት በሌላው ላይ ገኖ መገኘትን እንደ መብት ማቅረብ ዋና ዋናዎቹ ስልቶቻቸው ናቸው ።

ምንም እንኳ አንድ ሕዝብ ወይም የኅብረተሰብ ክፍል የራሱን ባህልና አኗኗር ከሌላው የተሻለ አድርጐ መገመትና መኩራራት ቀደም ሲልም የነበሩ አዝማሚያዎች ቢሆኑም በተለይ የዘረኝነት ባሕርያት ከባሪያ አገዛዝና ከቅኝ ግዛት መስፋፋት ጋር ያደጉ የአውሮፓ ፣ በኋላም የዩናይትድ ስቴትስ "አቅኚ" ነን ባይ ነጮች የፈጠሯቸው ጠንቆች ናቸው ። ይህንንም ሐቅ ስመገንዘብ ቀደም ያሉት የቅኝ ግዛት አስፋፊዎች ስፓኝ፣ ፖርቱጋልና ሆላንድ ፣ በኋላም ፈረንሳይና እንግሊዝ በአፍሪካ ፣ በእስያና በላቲን አሜሪካ የፈጸሙትን ፣ በኋላም አሜሪካን እናቀናለን በሚል ሰበብ የሀገሪቱን ቀይ ህንዶች የጨፈጨፉበትን ፣ ከአፍሪካ ጥቁሮችን በማጋዝ ለባርነት የዳረጉበትን የዩናይትድ ስቴትስ ነጮችንና ፣ ጀርመኖች አይሁድን የጨፈጨፉበትን የናዚ የዘረኝነት ታሪክ ማውሳቱ ይበቃል ።

በአሁኑ ጊዜም የዚሁ የዘረኝነት ጠንቅ በተለይ በደቡብ አፍሪካ የአፓርታይድ ሥርዓት ይፋ ይሁንታ አግኝቶ በመቀጠል ላይ ሲሆን በዩናይትድ ስቴትስም ውስጥ ቢሆን ገና ሙሉ በሙሉ አልተወገደም ። በሌሎችም የምዕራብ አውሮፓ ሀገሮች ውስጥ እንዲሁ

በተለያዩ ስውር መንገዶች እየተገለጸ ድር ጊቱ ከሚፈጸምባቸው ጥቁሮች ፣ ህንዶችና ሌሎችም ክፍሎች ቅዋሜን በማስከተል ላይ ነው ። ዘረኝነት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሕግ የተወገዘና እንዲወገድም አያሌ ውሳኔዎች የተላለፉበት ጉዳይ ነው ። ይሁን እንጂ በተለይ እንደ ደቡብ አፍሪካ ፋሺስት የነጭ ትምክህተኞች ያሉ አምባገነኖች የዓለምን ሕዝብ አስተያየት በመናቅ የዘረኝነት ጭቆናቸውን እንደቀጠሉ ናቸው ።

(ፋሺዝምን ፣ ብሔራዊ ሶሻሊዝምን ፣ የብሔር ትምክህተኝነትን ይመለከቷል ።)

## ዝቅጠት

*(Depression)*

በካፒታሊስት የማምረት ሥርዓት ውስጥ አንድ የኢኮኖሚ ቀውስ ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ የሚቀጥለው የኢኮኖሚ ቀውስ እስከሚጀምርበት ጊዜ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ከሚገኙ አራት ልዩ ልዩ የኢንዱስትሪ ዑደት ደረጃዎች መካከል ከቀውስ ቀጥሎ የሚመጣው ደረጃ ዝቅጠት ይባላል ። በዝቅጠት ጊዜ የኢንዱስትሪ ምርት ሳይንቀሳቀስና ሳያድግም በአነስተኛ ደረጃ ተወስኖ ይቆያል ። በሌላ አነጋገር በዚህ ደረጃ የቀውሱ መባባስ ያቆማል ። የሸቀጣ ሸቀጦች ዋጋ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል ። የንግድ እንቅስቃሴ በዝቅተኛ ደረጃ ይካሄዳል ። ሥራ አጥነት በመጀመሪያው ማለትም በቀውሱ ደረጃ እንደነበረው ተስፋፍቶና ምንዳም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል ። በመጋዘን ውስጥ ተከማችቶ የነበረው ሸቀጥ በከፊል እንዲወድም ይደረጋል ። ከፊሉም በቅናሽ ዋጋ ይሸጣል ። ለብድር ካፒታል ያለው ፍላጐት አነስተኛ በመሆኑ የብድር ወለድ መጣኔ ይቀንሳል።

ካፒታሊስታዊ የማምረት ተግባር በዚህ አኳኋን ይቆይና ቀስ በቀስ ካፒታሊስቶች በመካከላቸው ባለው ውድድር ገበያንና የጥሬ ዕቃን ምንጮች በቁጥጥራቸው ሥር ለማዋል ይጥራሉ ፤ ፋብሪካዎቻቸውንም ማደስ ይጀምራሉ ። ካፒታሊስቶች አዳዲስ የአመራረት ቴክኒኮችንና ዘዴዎችን በሥራ ላይ በማዋልና ወጪአቸውን በመቀነስ የሸቀጦች ዋጋ ዝቅተኛም ቢሆን ትርፋቸውን ያሳድጋሉ ። በዚህ አኳኋን ቀስ በቀስ የምርትን መጠን ለማሳደግ ሲባል ለቋሚ ካፒታል ያለው ፍላጐት እያደገ ይሄዳል ። ወደ ሚቀጥለው የኢንዱስትሪ ዑደት ደረጃ ማለትም ወደ ግገማ ለሚደረገው ሽግግርም ቅድመ ሁኔታዎች ቀስ በቀስ እየተሟሉ ይሄዳሉ ።

(የኢኮኖሚ ቀውስን ፣ ግገማን ይመለከቷል።)

# የ

## ዩሮ ኮሚኒዝም
*(Euro-Communism)*

የዳበሩ ካፒታሊስት ኅብረተሰቦችን በዲሞክራሲያዊ ፥ በፓርላማዊና በሕገ መንግሥታዊ የትግል ስልቶች ተጠቅሞ ወደ ሶሻሊዝም ማሸጋገር የሚያስችል የሶሻሊዝም ስትራቴጂና የዘመናችን አብዮታዊ ንቅናቄዎች አቅጣጫ ነው በማለት አንዳንድ የምዕራብ አውሮፓ ኮሚኒስት ፓርቲዎች የሚያራምዱት የፖለቲካ መሥመር ነው ።

ይህ ንቅናቄ በሠራተኛው መደብ ትግልና በዓለም የፖለቲካ ሂደት ውስጥ በፕሮግራምና በድርጅት ቅርፆች መታየት የጀመረው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቢሆንም በአዝማሚያነት የተከሰተው ካፒታሊዝም ከነፃ ውድድር ወጥቶ በሞኖፖል ደረጃ በተጠናከረበትና በአገኘውም አንፃራዊ የተረጋጋ የሰላም ወቅት ተጠቅሞ ባካበተው ሀብት ሕዝባዊ ትግሎችን በተለያዩ ስልቶችና አቅጣጫዎች ወደማፈን ደረጃ ማምራት ከጀመረበት ጊዜ ወዲህ ነው ።

ምንም እንኳን የዚህ ንቅናቄ መሪዎች ከወቅቱ የካፒታሊስት ሀገሮች ኢኮኖሚያዊ ፥ መንግሥታዊና ማኅበራዊ መዋቅሮች ዕድገት ጋር የሚጣጣም አብዮታዊ ታክቲክና ስትራቴጂ 'የዲሞክራሲያዊ ሶሻሊዝም መንገድ' ነው በማለት ለማሳመን ቢሞክሩም ርዕዮተ ዓለማዊ አቋማቸውና ማኅበራዊ ተግባሮቻቸው ካፒታሊዝምን በአብዮታዊ መንገድ መለወጥ ቀርቶ ለጥገናዊ ለውጦችም የሚያበቁ አይደሉም ። የመደብ ትግልን ፥ በተለይም የሶሻሊስት አብዮትን ፥ የአብዮታዊ አመፅ አስፈላጊነትን ፥ የወዝአደሩ የበላይ ገዥነትንና የካፒታሊስቱን መንግሥት እንደ ማንኛውም ጨቋኝ መደብ እስከ መሣሪያ ትጥቅ በሚደርስ ትግል የመደምሰስ አስፈላጊነትን ይቃወማሉ ። ሶሻሊዝም በዲሞክራሲያዊ ዘዴዎች ማለትም በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ በሚወሰዱ ማኅበራዊ ፥ ባህላዊና ትምህርታዊ እርምጃዎች ቀስ በቀስ ህልውና ያገኛል ይላሉ ። ለለውጡም ቡርዧዚውን በሚወክሉ ተቋሞች የመጠቀምን አስፈላጊነት ይሰብካሉ ።

ከካፒታሊዝም ወደ ኮሚኒዝም ለሚደረገው የሽግግር ወቅት የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት የታሪክ እውነታ በመሆኑ የሚፃረሩት አድኃርያንም ሆኑ በተለያዩ ዘዴዎች ሊያለዝቡት የሚፈልጉ የኮሚኒስት ፓርቲዎች ጉባኤዎችም እንኳ ሊያስቀሩት አይችሉም ። የቡርዧዚውን የበላይ ገዥነት በወዝአደሩ የበላይ ገዥነት መተካት አማራጭ የሌለው ሲሆን የመሀል መንገድ ፍለጋ አቋም መያዝ ሶሻሊዝምን መካድ ነው ።

"በዲሞክራሲያዊ ሶሻሊዝም" ንድፈ ሐሳባቸው መሠረት ዩሮ ኮሚኒስቶች ከካፒታሊዝም ወደ ኮሚኒዝም የሚደረገው ሽግግር የካፒታሊዝምንና የሶሻሊዝምን ሥርዓቶች አብሮ መሄድና የኢኮኖሚያቸው መቀላቀልን ያስከትላል ። ስለዚህ ዩሮ ኮሚኒስቶች ካፒታሊዝምን በአብዮታዊ መንገድ የመለወጡን አስፈላጊነት በመተው የመደብ ትግልን በርዕዮተ ዓለም ደረጃ ማለትም በሐሳቦች ትግል ብቻ ይወስኑታል ። ነባሩ የካፒታሊዝም ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት በአብዮታዊ እርምጃ እንዳይናድ የሚጥሩ ናቸው ።

ዩሮ ኮሚኒስቶች በወዝአደሩ አብዮት ፥ በዲሞክራሲ ፥ በመንግሥት ፥ በመደብ ኃይሎች ሚና ፥ በሶሻሊዝምና በመሳሰሉት ወሳኝ የለውጥ ጥያቄዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት መርህ ላይም የተዛባ አቋም አላቸው ። የሞኖፖል ቡርዧ መንግሥት ዓለምን በራሱ የተፅዕኖ ክልሎች አደላድሎ ሕዝባዊ አብዮትንና የነፃነት ንቅናቄዎችን ህልውና በሚፈታተንበት ለሰላም፥ ለማኅበራዊ ዕድገትና ለሕዝቦች እውነተኛ ነፃነት የዓለም አብዮታዊ ኃይሎች ኅብረት አስፈላጊነቱ ከማንኛውም ጊዜ ይበልጥ በጎላበት የታሪክ ወቅት ላይ የተለያዩ ሀገሮችን የሶሻሊዝም ሞዴሎች እያሉ የአብዮታውያንን አንድነት ለማናጋት ይሞክራሉ ።

ከዚህም ሌላ የ‘ሶቭዬት ሞዴል ፣ የ‘ሶቭዬት ቢሮክራሲ’፣‘የሶቭዬት ጣልቃ ገብነት’ ወዘተ… የሚሉ ፀረ ሶቭዬት ዘመቻዎችን ያስፋፋሉ ።

## ዩኒቨርስ
*(Universe)*

ዓለማትን (ፕላኔቶች) ፣ ሀዋን ፣ ከዋክብትንና ሌሎችንም ቁጥር ስፍር የሌላቸውን ነገሮች ሁሉ የሚያጠቃልል ነው ። ዳር ድንበር ፣ መነሻና መድረሻ የሌለው ዘለዓለማዊ የሆነና ተፈጥሮን አጠቃሎ ያቀፈ ነው ። ከዩኒቨርስ ውጭ የሆነ ምንም ነገር የለም ።

## ይስሙላ ካፒታል (የ—)
*(Fictitious Capital)*

እንደ አክሲዮንና እንደ አረቦን ያሉ የካፒታል ባለቤትነትን የሚገልጹ ሕጋዊ የምስክር ወረቀቶች ዋጋ የይስሙላ ካፒታል ይባላል ። ይህ ዋጋ ባንድ በኩል በምርትና በልውውጥ ሂደት ውስጥ ባለ ቁሳዊ ሀብት ፣ (ማለትም እውን ካፒታል) ላይ ቢመሠረትም መውጣት መውረዱ የእውን ካፒታልን የመጠን ለውጥ ላይከተል ይችላል ። ለምሳሌ የአክሲዮን ገበያ በሚደራበት ጊዜ የኀብረተሰብ ቁሳዊ ሀብት መጠን ሳይወጣ ሳይወርድ ይህንኑ ሀብት የሚወክለው የአክሲዮኖች ዋጋ ይንራል ። ይኸው ገበያ በወደቀበት ጊዜ ደግሞ አሁንም የኀብረተሰቡ ሀብት ሳይለወጥ አክሲዮኖች ዋጋ ያጣሉ ። የይስሙላ ካፒታል ጽንሰ ሐሳብ ይህን በምርትና በልውውጥ ሂደት በሚንቀሳቀስ ቁሳዊ ሀብትና በአክሲዮን ገበያ ባለው ተመኑ መካከል ያለውን ተቃርኖ ይገልጻል ።

## ይዘትና ቅርፅ
*(Content and Form)*

ይዘት አንድ ነገር በውስጡ የያዛቸውን ወይም ያቀፋቸውን ነገሮች የሚያሳይ ሲሆን ፣ ቅርፅ ደግሞ የአንድን ነገር መልክ ፣ ገጽታና ቁመና የሚያመለክት ነው ።

በማርክሳዊ ሌኒናዊ ግንዛቤያቸው ይዘትና ቅርፅ የቁሳዊ ነገሮችን ወይም ክስተቶችን ዕድገት ፣ ውህደትና ውስጣዊ ግንኙነቶች ለማሳየት የሚረዱ የፍልስፍና ፈርጆች ናቸው። ይዘት አንድ ነገር ወይም ክስተት የተገነባባቸውን ጠቅላላ አካሎች ፣ የባሕርያቱን አንድነትና የእነርሱንም ውስጣዊ ሂደቶች ፣ ግንኙነቶችና ቅራኔዎች ፣ ከዚህም የተነሣ የሚፈጠሩትን የዕድገት አዝማሚያዎች የሚያሳይ ፈርጅ ነው ።

ቅርፅ የይዘት አደረጃጀት ነው ። የይዘትን ውጫዊ መልክ ፣ የይዘትን አካሎች የተወሰነ እርጋታና ዓይነት የሚያሳይ ነው ። ይዘት ካለው አደረጃጀትና አወቃቀር አንፃር ሲታይ ቅርፅ ይሆናል ። ቅርፅ የይዘቱ ውጫዊ መልኩ እንጂ ለይዘቱ ባዕድ ሆኖ ከውጭ የሚሰጠው ሽፋን አይደለም ።

ይዘትና ቅርፅ ተቃራኒዎች ቢሆኑም ውህደት አላቸው ። ይዘት ያለቅርፅ እንዲሁም ቅርፅ ደግሞ ያለ ይዘት ሊኖሩ አይችሉም ። ይዘትና ቅርፅ ውህደት ያላቸው የአንድ ነገር ሁለት ተቃራኒ ጎኖች ቢሆኑም ይዘት ቀዳማይነትና ወሳኝነት አለው ። ምክንያቱም ይዘት ከሌለ ቅርፅ ሊኖር አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን ቅርፁ በይዘቱ ዓይነት የሚወሰን በመሆኑም ጭምርና የይዘት ለውጥ የቅርፅ ለውጥንም ስለሚፈጥር ነው ።

ይዘት አንድ ነገር የተገነባባቸውን አካሎችና ባሕርያት ያቀፈ በመሆኑና በእነዚህም መሀከል መስተጋብር ስለሚኖር ይዘት ሁልጊዜ በእንቅስቃሴ ፣ በለውጥና በዕድገት ላይ ይገኛል ። ቅርፅ አንድ ይዘት ለውጥ እስኪያሳይ ድረስ የማይለወጥ በመሆኑ የረጋ ቢሆንም ቅርፅ በይዘት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል ።

የይዘትና የቅርፅ ዕድገት የአሮጌው ቅርፅ መፍረስንና የይዘት መለወጥን የሚያመለክት ነው ። የይዘትና የቅርፅ ውህደት አንፃራዊና ጊዜያዊ ነው ። ይህ ውህደት በይዘትና በቅርፅ መሀከል በሚካሄደው ትግልና ለውጥ የሚፈርስ ነው ።

በይዘትና በቅርፅ መሀከል ያለው ቅራኔ የሚመነጨው ሁለቱም በዕድገት ውስጥ ካላቸው የተለያየ ሚና የተነሣ ነው ። ይዘት የአንድ ነገር የዕድገት መሠረት

ሲሆን ቅርፅ ግን የአንድ ነገር የህልውና መግለጫ ስልት ነው ። ይዘት የራሱ እንቅስቃሴ ያለው ሲሆን ቅርፅ በይዘቱ ላይ የሚመሠረት ነው ። ይዘት ወሰን የለሽ ዕድገት የማድረግ ውስጣዊ ባሕርይ ሲኖረው ቅርፅ ግን ይህንን የይዘት ዕድገት የመገደብ አዝማሚያ አለው ። ይዘት በዕድገት ላይ የወሳኝነት ሚና ቢኖረውም ቅርፅ ዕድገትን የማፋጠን ወይም የመጐተት ሚና ለመጫወት ስለሚችል አንፃራዊ ነፃነት አለው ። ይህ አንፃራዊ ነፃነት ጐልቶ የሚታየው በቅርፁ የአርጅና ወቅት ነው ። ቅርፅ ከይዘት እኩል ካላደገ በተለይ ከይዘት አንፃር ወደኋላ ከቀረ የይዘቱን ዕድገት ሊጐትት ይችላል ። ለምሳሌ የምርት ግንኙነቶች (የአንድ ስልተ ምርት ቅርፅ) ከምርት ኃይሎች አንፃር ኋላቀር ከሆኑ የምርት ኃይሎችን (የስልተ ምርት ይዘት) ዕድገት ለመጐተት ፣ ከምርት ኃይሎች ጋር ከተጣጣሙ ደግሞ ዕድገትን ለማፋጠን ይችላሉ ። በስልተ ምርት አንፃር ሲታይ ይዘትና ቅርፅ (በምርት ግንኙነቶችና በምርት ኃይሎች አማካይነት) በምሳሌው ውስጥ በተመለከተው ሁኔታ ይጠቀሱ እንጂ ሥርዓተ ማኅበሮችን በሚመለከት ግን ሁኔታው የተለየ መልክ አለው ። ሥርዓተ ማኅበሮች እርስ በርሳቸው የሚለያዩት በስልተ ምርቶቻቸው በመሆኑና የምርት ኃይሎችም ማኅበራዊ ባሕርይ በምርት ግንኙነቶች የሚገለጽ በመሆኑ የምርት ግንኙነቶች ይዘት ይሆናሉ ። ስለሆነም ማኅበራዊ ሥርዓቶችን የምንገልጻቸው በምርት ኃይሎች ዕድገት ደረጃ ሳይሆን በምርት ግንኙነቶች በመሆኑ የምርት ግንኙነቶች የሥርዓተ ማኅበራት መለያና ይዘት ናቸው ። አንድ ይዘት የተለያዩ ቅርፆችን ሊይዝ ይችላል ፤ ለምሳሌ የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት መንግሥት (ይዘት) በሶቭዬት መልክ (ሶቭዬት ኅብረት) ወይም በሕዝባዊ ዲሞክራሲ መልክ (በምሥራቅ አውሮፓ ሶሻሊስት ሀገሮች) ። እንዲሁም አንድ ቅርፅ በርካታ ይዘቶችን ሊገልጽ ይችላል ። የተለያዩ ባሕርያት ያሏቸውን የተፈጥሮ ክስተቶችን በአንድ ቀመር መግለጽ ይችላል ለማለት ነው ።

የቅርፅ ለውጥ የሚከሰተው የይዘት ለውጥ ሲኖር ነው ። ይሁን እንጂ የቅርፅ ለውጥ ወይም መፍረስ በአንድ ጊዜ የሚፈጸም ሳይሆን በይዘትና በቅርፅ መሀከል ያለው ቅራኔ የመካረር ሂደት ውጤት ነው ። ከዚህም በተጨማሪ ከይዘት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸው ውጫዊ ሁኔታዎችና ግንኙነቶች በቅርፅ ላይ ተፅዕኖ በማሳደር ለጊዜው እንዳይለወጥ ሊያደርጉ ይችላሉ ። ቅርፅ የረጋ በሚሆንበት ደረጃ ላይ ለይዘት ዕድገት አመቺ ሁኔታን ሲፈጥር ከተወሰነ ወቅት በኋላ ግን የይዘትን ዕድገት የሚያደናቅፍ ይሆናል ። የቅርፅ ከይዘት ጋር አለመጣጣም በተለይም የቅርፅ ከይዘት ወደኋላ ቀርቶ መገኘት በሁለቱ መሀከል ሊኖሩ ከሚችሉት የቅራኔ ገጽታዎች አንዱ ነው ። በይዘትና በቅርፅ መሀከል ያለው ቅራኔ መፍትሔ ይዘትና ቅርፅ ባላቸው ባሕርይ ፣ የዕድገት ደረጃና ሁኔታ ላይ የሚመሠረት ነው ። ይህ ቅራኔ መፍትሔ ሊያገኝ የሚችለው ቅርፅ በይዘት ውስጥ ከሚታዩ ለውጦች ጋር ተጣጥሞ ሲለወጥ ፣ የይዘት ለውጥ ከአዲሱ ቅርፅ ጋር ተጣጥሞ ሲገኝ ፣ አሮጌው ቅርፅ ሙሉ በሙሉ ሲፈርስ እንዲሁም አሮጌው ቅርፅ የአዲሱ ይዘት ተገዥ ሲሆን ነው ። ከአንድ ዓይነት ወደ ሌላ ዓይነት ሽግግር በሚደረግበት ጊዜ አሮጌው ቅርፅ ሊፈርስ ወይም ሊለወጥ ይችላል ። ይሁን እንጂ ወደ ተሻሻለው ቅርፅ ለሚደረገው ሽግግር አስፈላጊ የሆኑት ቅድመ ሁኔታዎችና አካሎች በአሮጌው ቅርፅ ውስጥ ተሟልተው እስከልተገኙ ድረስ አሮጌው ቅርፅ ሙሉ በሙሉ ሊፈርስ እንደማይችል ሁሉ አዲሱም ቅርፅ በአንድ ጊዜ የበላይነትን ሊይዝ ወይም ዕድገትን ሊያፋጥን አይችልም ። አሮጌው ቅርፅ ቀስ በቀስ እየጠፋ ሲሄድ አዲሱም ቅርፅ ቀስ በቀስ ዕድገትን የሚያፋጥንና የበላይነትን የሚይዝ ይሆናል ።

(ለውጥን ፣ የዓይነት ለውጥን ፣ አዝጋሚ ለውጥን ፣ የመጠን ለውጥን ይመለከቷል ።)

# ደ

## ደመነፍስ

*(Instinct)*

እንስሶች ከአካባቢያቸው ጋር በመስማማት ሂደት ውስጥ ባገኙዋቸው ሥነ ሕይወታዊ የህልውና ቅርፆች አማካይነት የሚያደርጉት ንቁ ያልሆነ ከንዋኔ ደመነፍስ ይባላል ። ደመነፍስ ከእንስሶች ጋር አብሮ የሚፈጠርና በዘር የሚተላለፍ ችሎታ ነው ። ንቁ ከንዋኔ በግብና በዕውቀት የሚመራና ተፈጥሮን የመቀየር አዝማሚያ ያለው በመሆኑ ከደመነፍስ ይለያል ። ሰው በእንስሳነቱ ደመነፍሳዊ እንቅስቃሴዎች ይኖሩታል ። ሆኖም የማንፀባረቅና የማሰብ ችሎታ ስላለው ደመነፍሳዊ ከንዋኔዎቹ አነስተኛ ናቸው ። ሰው ከልምድ የሚማርና የተለያዩ ከንዋኔዎችን ከኅብረተሰብ የሚቀስም በመሆኑ በሰው ዘንድ ደመነፍስ ወሳኝ ሚና የለውም ።

አንዳንድ ሐሳባውያን ደመነፍስ ግንዛቤአዊ ሚና አለው በማለት ተናግረዋል ። በተለይም ምርምርና ምክኑያዊ አስተሳሰብ ሊደርስባቸው የማይችሉት ዲበአካላዊ ጥያቄዎች ደመነፍስ በሚፈጥረው ስሜታዊ ግምት መልስ ሊያገኙ ይችላሉ ይላሉ ። ይህ አመለካከት ሳይንሳዊ ያልሆነና ዕውቀትን ምሥጢራዊና ሊረጋገጥ የማይችል በማድረግ ወደ ጭፍን እምነት የሚለውጥ በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም ።

## ደምሳሽነት

*(Liquidationism)*

ከሩሲያ ቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መክሸፍ በኋላ በሜንሺቪክ ማኅበራዊ ዲሞክራቶች መካከል የተከሰተና ለሩሲያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ሌበር ፓርቲ መፍረክረክና ለሕዝባዊው አብዮት መቀልበስ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የተነሣ አፍራሽ አዝማሚያ ነው ። ወቅቱ ሜንሺቪኮች በአብዮቱ ጊዜያዊ ሽንፈት ተስፋ በመቁረጥና በአድኃሮት ኃይላት የበቀል እርምጃ በመደናገጥ በኅቡእ ይንቀሳቀስ የነበረው ፓርቲ ከእንግዲህ ወዲያ ለሠራተኛው ነፃነት ዕድገት ታሪካዊ አስፈላጊነት የለውም በማለት ሊበትኑት የተነሡበት ነበር ።

የፓርቲውን ህልውናና በአጠቃላይም አብዮቱን በመፃረር የተነሡት ሜንሼቪኮች ሠራተኛው በዘውድ አገዛዝ ላይ የሚያካሂደውን ትግል እንዲተው ጥሪ ማቅረባቸውና በአድኃሪው መንግሥት ቁጥጥር ሥር የሆነ ሌላ የፖለቲካ ድርጅት ለማቋቋም የተነሡ የቡርዧ አፈቀላጤዎች መሆናቸው በተግባር ተረጋግጧል ። ቦልሼቪኮች ግን እነዚህን በቆራጥነት በመታገል ከሃዲነታቸውን አጋልጠዋል ። በመጨረሻም በ1912 በፕራግ በተደረገው የፓርቲው ስብሰባ ደምሳሾች ከፓርቲው እንዲባረሩ ተደርጓል ።

## ደብተራዊነት

*(Clericalism)*

በልዩ ልዩ የማኅበራዊ ኑሮ ዘርፎች ላይ የሃይማኖትን ተፅዕኖ ለማጠናከር የሚሞክር ማኅበራዊና ፖለቲካዊ አዝማሚያ ደብተራዊነት ይባላል ። ዋናው ዓላማ ሠራተኛው መደብ የኮሚኒስትን ርዕዮተዓለም እንደ ትግል መሣሪያው አድርጐ እንዳይዝ መከላከልና የቡርዧውን የበላይነት ማጠናከር ነው ። ደብተራዊነት በፈረንሳይ ፣ በኢጣልያ ፣ በጀርመን ፌደራል ሪፑብሊክ ፣ በኦስትሪያ ፣ በስፓኝና በብዙ የላቲን አሜሪካ ሀገሮች ከባድ ተፅዕኖ አለው ። በዘመናችን ይህ እምነት እየተጠናከረ የሄደው ካፒታሊዝም በቀድሞው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ኃይሉ ለመራመድ ካለመቻሉ የተነሣ የቤተክህነት መሪዎች ከሞኖፖል ቡርዧዎች ጋር በመስማማት ለካፒታሊዝም የሃይማኖት ሽፋን እየሰጡ በተዘዋዋሪ መልክ ለማጠናከር ከሚያደርጉት ከንቱ ሙከራ የተነሣ ነው ። ይህን አጉል እምነት ንቃተ ኅሊናቸው ዝቅ ያለ የነዚህ ሃይማኖት ተከታዮች የሚከተሉት ሲሆን የሃይማኖትም ድርጅቶች የመብቶቻቸው መከታ እንደሚሆንላቸው አድርገው እንዲያዩት ለማሳመን ይሞክራሉ ። ከዚህም የተነሣ ደብተ

ራዊነት የሠራተኛውን ማኅበር ፥ የወጣቶችን ፥ የሴቶችንና የሌሎችን ሕዝባዊ ድርጅቶች በመቦርቦርና በመቆጣጠር ፥ አንዳንዴም እነዚህንና የራሱንም ፓርቲ ጭምር በመፍጠር የቤተክርስቲያንን ተፅዕኖ እያጠናከረ የሠራተኛውን መደብ የመታገያ ድርጅት ያዳክማል ። በነዚህም ድርጅቶች አማካይነት የቤተ ክህነት ሰዎች የካፒታሊስትን የብዝበዛ ሥርዓት ተገቢነት ለማሳመን በመሞከር ጉታች የሆነውን "ማኅበራዊ ሰላም" ብለው የሚጠሩትን አጉል የመደቦች እርቅ እምነት ይሰብካሉ ። ስለዚህም ለእውነተኛ የሕዝቦች ሰላም ፥ ለዲሞክራሲ ፥ ለማኅበራዊ ዕድገትና ለሳይንሳዊ ርዕዮተዓለም መታገል ማለት የደብተራዊነትን አድኅሪ ጠባይ ማጋለጥ ማለት ነው ።

## ዲሞቅሪጦስ (የአብደራው)

*(Democritus of Abdera)*

ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ460—370 የኖረ ጥንታዊ የግሪክ ቁስአካላዊ ፈላስፋ ነው ።

ዓለም ከአቶምና ከአልባ ማለትም ከባዶ የተገነባች ነች ፤ አቶሞች አንድ ወጥ የሆኑ ፥ የማይከፋፈሉ ፥ የማይሰነጠቁ የመጨረሻው አነስተኛና ለሕዋሳት የተሰወሩ ነገሮች ሲሆኑ በባዶ ውስጥ ያለማቋረጥ ይንቀሳቀሳሉ የሚለው የአቶሚዝም ንድፈ ሐሳብ ቀማሪ ነው ። ነገሮች የሚለዩት በአላቸው የአቶሞች አወቃቀርና አደረጃጀት (ስፋት ፥ መጠን ፥ አቀማመጥ ፥ ዓይነት ወዘተ) ነው ። ይህም ማለት የዓይነት ልዩነት የሚገኘው ከመጠን ልዩነት ነው ፤ ለምሳሌ ዛፍና ሰው የሚለዩት በአቶሞች አደረጃጀት ነው ። ይህ የአቶሞች መገናኘት አጋጣሚ ሲሆን ከተደራጁ በኋላ ግን የሚገዙት በግዴታ ሕግ ይሆናል ።

የዕውቀት ንድፈ ሐሳቡ ፥ ነገሮችን የምናውቀው በሕዋሳትና በማሰብ ነው ፤ ሕዋሳት የዕውቀት የመጀመሪያው ደረጃ ሲሆኑ ማሰብ ደግሞ የዓለምን ዓይነተኛ ባሕርይ ማለትም አቶምንና አልባን ለማወቅ የሚያስችለን ከፍተኛው ደረጃ ነው የሚል ነው ።

ዲሞቅሪጦስ ሰዎችን ከአምልኮና አምልኮ ከሚያስከትለው ፍርሐት ለማላቀቅ የጣረ ሲሆን በፖለቲካ አስተሳሰቡም የባሪያ አሳዳሪውን ሥርዓት ተቃዋሚ ነበር ።

ማርክስ ዲሞቅሪጦስ ሰፊ ዕውቀት የነበረው መሆኑን ሲገልጽ ፥ ሌኒን ደግሞ የጥንታዊት ግሪክ ከፍተኛና የግብታዊ ቁስአካልነት ገላጭ ነው ብሏል ።

ዲሞቅሪጦስ የአቶምን ጽንሰ ሐሳብ መቀመሩ ባንድ በኩል ዓለምን ከተለየ ክስተት ሳይሆን ሁለንታዊነት ካለው ነገር ማመንጨቱ ጥሩ ሙከራ ሲሆን በሌላ በኩል ከቁስአካል የተገኘውን አቶምን የቁስ አካል ምንጭ ማድረጉ የሚፋለስ አመለካከት ነው ። ክስተቶችን ደግሞ ያጋጣሚ ውጤት ማድረጉ አመለካከቱ ተናክአታዊ መሆኑን ያሳያል ። በተፈጥሮ ውስጥ የዕድገት አዝማሚያ መኖሩ ማለትም ከቀላል ወደ ውስብስብ የመሄዱ ሁኔታ አጋጣሚ ብቻ ሳይሆን የዕድገትን ሕግ የተከተለ ነው ።

(አቶሚዝምን ይመለከቷል ።)

## ዲሞክራሲ

*(Democracy)*

ጥቂቶች ለብዙኃን ተገዥ የሚሆኑበትና ለሁሉም እኩል መብትና ነፃነት እሰጣለሁ የሚል የፖለቲካ ሥርዓት ቅርፅ ነው ። ሆኖም ይህ የዲሞክራሲ አጠቃላይ ፍች በተለያዩ ስልተ ምርቶች ውስጥ በተለያዩ ተግባራት ተተርጉሟል ።

ለመጀመሪያ ጊዜ የፖለቲካ ሥርዓት ዲሞክራሲያዊ ቅርፅ ያገኘው በግሪክ የባሪያ አሳዳሪ ሥርዓት ውስጥ ነበር ። በዚህ ጊዜ ዲሞክራሲ የነበረው ፍች ከባርነት ነፃ የሆኑትን የፖለቲካ መብታቸውን ማስከበር ስለነበር ፥ ነፃ የሆኑትን በባርነት ሥር ካሉት የሚለይ ሥርዓት ነበር ። በግሪኮች አባባል ነፃ ማለት ከጉልበት ሥራ ነፃ የሆነ ማለት ስለነበረ ፥ ዲሞክራሲ የፖለቲካ መብቶችን ነፃ ለሆነው ክፍል ብቻ መስጠቱ የሚገልጸው የመደብ ይዘት እንደነበረውና በባርነት ሥር ላሉት የፖለቲካ መብት በመንፈግ ሙሉ በሙሉ ለነፃው መደብ ተገዥ ያደርጋቸው እንደነበር ነው ። ሆኖም ከመኳንንታዊና ከንጉሣዊ አገዛዝ የሚለይበት ነጥብ ነበረው ። ነፃ

የሆነው መደብ የራሱን የፖለቲካ ሥልጣን የሚመሠርተው በምርጫ ስለነበርና ይህም የመጠየቅ ፣ የመንቀፍ ፣ ከሥልጣን የማውረድ ወዘተ… መብት ስለሚሰጠው ከፍጹማዊ አገዛዝ ይለየው ነበር ። በዚህ መልኩ ነው ሥርዓቱ የዲሞክራሲ ቅርፅ የነበረው ።

ቡርዧዚው የፊውዳሊዝምን ፍጹማዊና ንጉሣዊ አገዛዝ ለመዋጋትና ለማሸነፍ የዲሞክራሲ መርሆችን በማስተጋባት ብዙኃኑን በሥሩ ለማሰባሰብ ችሏል ። መርሆቹ የሚጠይቁት የፖለቲካ መብቶች (የመምረጥ ፣ የንግግር ነፃነት ፣ የመደራጀት ወዘተ…) ለፊውዳል ሥርዓት ፍጹም ተፃራሪ ነበሩ ። የቡርዧዚው ዲሞክራሲያዊ ጥያቄ ኢኮኖሚያዊ መሠረት የነበረው በመሆኑ ለቡርዧው አገዛዝ አመቺ የፖለቲካ ቅርፅ ነበር ። የግል ሃብት የበላይ ሆኖ ሊዳብርና ወዝአደሩ ነፃ ሆኖ ጉልበቱን ለገበያ ሊያቀርብ የሚችለው ማንኛውንም ነገር መሸጥና መለወጥ ሲችል በመሆኑ የቡርዧው ዲሞክራሲ የሚገልጸው የግል ንብረት ባለሙሉ ሥልጣን መሆንን ነበር ።

ሆኖም ሥርዓቱ በውስጣዊ ቅራኔ ላይ የተመሠረተ ነበር ። በአንድ በኩል ለሕዝቡ የንግግር ፣ የመሰብሰብ ፣ የመምረጥ ወዘተ… መብት የሰጠ ቢሆንም በሌላ በኩል በዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ የማይገባ በመሆኑ በተለይም ኢኮኖሚያዊ ልዩነቶችንና የብዝበዛን ሥርዓት ከማጥፋት ይልቅ የግል ሃብት ክምችትን የሚያዳብር በመሆኑ ለብዙኃኑ የሚሰጠው መብት ቅርፃዊ ብቻ ነበር ። ቅርፃዊም ቢሆን የሰውን የመብት እኩልነት ማወጁ ፣ ሰዎች በመደራጀት ጥቅማቸውን በጋራ እንዲያስከብሩ መፍቀዱ ወዘተ… በሠራተኛውና በቡርዧዚው መካከል የሚካሄደውን የመደብ ትግል የሚያከርና ርዕዮተ ዓለማዊ ብስለት የሚሰጥ ነበር ።

እነዚህ የፖለቲካ መብቶች ቅርፃዊ ብቻ ሳይሆኑ በኢኮኖሚያዊ ፣ በማኅበራዊና በመንፈሳዊ ይዘት እንዲተረጎሙ ለማድረግ ነው የሠራተኛውና የሶሻሊስት እንቅስቃሴ ዲሞክራሲያዊ ጥያቄዎችን በማንሣት ከቡርዧዚው ጋር በተራው የሚታገለው ። ለእነዚህ በቡርዧዚው በቅርፃዊነት ብቻ ቀጭቶ ላስቀራቸው ዲሞክራሲያዊ መብቶች ይዘት የመስጠቱ ጉዳይ በቀጥታ የሚያመራው ወደ ሶሻሊስት ኅብረተሰብ ጥያቄ ነው ። በዚህ ጊዜ ዲሞክራሲ ማለት አባባሉ እራሱ በትክክል እንደሚገልጸው የብዙኃኑ ጥቅምና ፍላጐት የበላይ የሆነበትና የበላይነቱን ለማግኘት ሆነ ለማስከበር ሠራተኛው ሕዝብ በዲሞክራሲያዊ መብቶች በመጠቀም (ድርጅት ፣ ምርጫ ፣ ጥበቃ ፣ ሕጋዊ ይዘት…) በዝባዥ መደቦችን የሚጨቁንበትና የሚያጠፋበት የፖለቲካ ሥርዓት ማለት ነው ። የሠራተኛው መደብ በዚህ በፖለቲካ የበላይነት እየተጠቀመ መደቦችን ሲያጠፋ ዲሞክራሲም አብሮ ይከስማል ። ምክንያቱም የፖለቲካ ሥልጣን የሚያንፀባርቀው የመደቦችን ትግል እስከሆነ ድረስ የመደቦች መጥፋት በኅብረተሰቡ ውስጥ በገዥና በተገዥ መካከል ያለውን ክፍፍል ስለሚያጠፋ በምትኩ ራስን በራስ የማስተዳደር ሥርዓት ይመሠረታል ።

(ሶሻሊዝምን ይመለከቷል ።)

## ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት
*(Democratic Centralism)*

የኮሚኒስት ፓርቲ አባላት ከፖለቲካ ውሳኔ ላይ እንዴት እንደሚደርሱ ፣ የደረሱበትን ውሳኔ እንዴት በሥራ ላይ እንደሚያውሉ ፣ በአባላት መካከል ያለው የሥራ ግንኙነት ምን እንደሆነ እንዲሁም በከፍተኛና በዝቅተኛ አካላት መካከል ያለው የኃላፊነት ድርሻ ምን እንደሚመስል የሚገልጽ ድርጅታዊ መርህ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ይባላል ። ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት የጋራ ኮሚኒስታዊ ግብ ያላቸው አባላት ሁሉ በፈቃደኛነትና በንቃት የሚከተሉት ድርጅታዊ አሠራር ነው ። በዚህም መሠረት ፓርቲው ከቀመለት መሠረታዊ ዓላማና ከሚፈጽመው ሕዝባዊ ተግባር የሚመነጭ ሲሆን ከቡርዧ ፓርቲዎች ቢሮክራሲያዊ የተፅዕኖ አሠራር ፍጹም የተለየ ነው ።

ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት የሁለት ጽንሰ ሐሳቦች ማለትም የዲሞክራሲና የማዕከላዊነት ዲያሌክቲካዊ ውህደት ነው ። ዲሞክራሲ የፓርቲው አባላት አንድነት ባለው ድርጅታዊ አሠራር ኃይላቸውንና ዕውቀታቸውን በማስተባበር የትግል ተላትፎ እንዲያደርጉ ሰፊ መብትና ነፃነት ይሰጣቸዋል ። በዚህ መሠረት በአብዮታዊ ፓርቲ አሠራር

ውስጥ ዲሞክራሲ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ያሟላል ፣

1. እያንዳንዱ አባል የፓርቲውን የፖለቲካ መሥመር ፣ ዕቅድና ግብ የማወቅ ፣ በማንኛውም የድርጅቱ ጉዳይ ላይ የመወያየት ፣ ድምፅ የመስጠትና ኂስ የማቅረብ መብት አለው ።

2. በየትኛውም ደረጃ የፓርቲው አመራር በኅብረት የተያዘ መሆን አለበት ። ይህም የግለሰብ አምባገነንነትን ከመከላከሉም ሌላ አባላቱ ጉዳዮችን በተለያዩ አቅጣጫዎች በማየትና ሰፊ ውይይት በማድረግ ከትክክለኛ ውሳኔዎች ላይ እንዲደርሱ ይረዳል ።

3. ከላይ እስከታች በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ መሪዎች በቀጥታ በአባላቱ ወይም በተወካዮቻቸው አማካይነት በድምፅ ብልጫ ይመረጣሉ ። አባላቱ በነዚህ የፓርቲ መሪዎች ላይ ኂስ ለመሰንዘር ፣ ካስፈለገም በደንቡ መሠረት ከሥልጣናቸው እንዲነሡ ለማድረግ መብት አላቸው ።

4. የበታች የፓርቲ አካላት ከፓርቲው ዓላማና ከልል ሳይወጡ በአካባቢ ጥያቄዎችና ችግሮች ላይ ውሳኔ የመስጠትና መፍትሔ የመሻት መብት አላቸው ።

ማዕከላዊነት ደግሞ በፓርቲ ሕይወት ውስጥ አብዮታዊ ሥነ ሥርዓትን ፣ የዓላማና የድርጅት አንድነትን በማጠናከር የሠራተኛውን መደብና የመላውን ሠርቶ አደር ሕዝብ መብትና ፍላጎት ለማረጋገጥ የሚያስፈልገውን አመራር ለመስጠት የሚያስችል ነው ። ይህም በሚከተሉት መንገዶች ይገለጻል ፤

1. የሠራተኛው መደብ ጠንካራ ኃይል ሊሆን የሚችለው በድርጅቱ ቁሳዊ አንድነት ላይ በተመሠረተ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተዓለማዊ አንድነት በመሆኑ ፓርቲው አንድ ርዕዮተ ዓለም ፣ አንድ መሪ ማዕከል ፣ አንድ ፕሮግራምና አንድ ደንብ ብቻ ይኖረዋል ።

2. የበታች አካላት ለበላይ አካላት ውሳኔ ፣ ትዕዛዝና መመሪያ ተገዥ ይሆናሉ ፤ ይህንንም በጠንከረ ዲሲፕሊን በሥራ ይተረጉማሉ ፤ ለራሳቸውም ሆነ ለበላይ የፓርቲ አካላት ስለ ውጤቱ በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባሉ ።

3. በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲ አካላት ውስጥ ማንኛውም አባል የተቃወመውንም ጭምር ፣ በአብዛኛው የተደገፈውን ውሳኔ ተቀብሎ ያለአንዳች ማወላወልና ቅሬታ ሥራ ላይ ያውላል ። ሆኖም ተቃውሞ ያለው አባል ውሳኔው እንደጸና ሆኖ የሚጠበቅበትን ግዴታ ሳያቋርጥ ቅሬታውንና በውሳኔው ላይ የታየውን ድክመት እንዴት መታረምና መሻሻል እንዳለበት በመጠቆም ለሚመለከተው የበላይ አካል ለማሳሰብና ውሳኔው እንደገና እንዲታይ ለመጠየቅ ይችላል ።

4. በድምፅ ብልጫ የተላለፈውን ውሳኔ ሥራ ላይ ለማዋል አካሎች ሁሉ ኃላፊነት አለባቸው ።

ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት በፓርቲ አሠራር የውይይት ነፃነት እንዲኖርና በአብዛኞቹ የተደገፈ የፖለቲካ አቋምና ውሳኔ በትክክል ሥራ ላይ እንዲውል የሚያስችል መሣሪያ ነው ። ዲሞክራሲ ያለ ማዕከላዊነት ገደብ የሌለው ነፃነት በመሆኑ አንጃኝነት እንዲሰፍንና ድርጅቱ ተዝረክርኮ ውሳኔዎቹ በተግባር እንዳይተረጐሙ የሚያደርግ ይሆናል ። ማዕከላዊነት ደግሞ ያለ ዲሞክራሲ የሥራ ማነቆ ሊፈጥር ፣ ሲብስም የግለሰብ ወይም የጥቂት ሰዎችን አምባገነንነት ሊያስከትል ይችላል ። ስለሆነም ዲሞክራሲና ማዕከላዊነት አንድ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ ሥራውን በተቀላጠፈ መልክና ሥርዓት ባለው አኳኋን እንዲያከናውን ያስችሉታል ።

## ዲሲፕሊን
*(Discipline)*

ኅብረተሰብ የሚከተላቸውን ልምድና ወግ ወይም ለመመሪያዎች ፣ ለውሳኔዎችና ለትዕዛዝ ራስን በማስገዛት አንድ ሰው የሚያሳየው ሥነ ምግባር ዲሲፕሊን ይባላል ። ሰዎች በማኅበር ሲኖሩ የሚችሉት ፣ የሚመሩበትንም ሥርዓት የሚያከብሩት ዲሲፕሊን ሲኖራቸው ብቻ ነው ። ይሁን እንጂ የዲሲፕሊን ባሕርይና የማስከበሪያውም መሣሪያና ዘዴ የሚወሰነው ባለው የምርት ግንኙነት ነው ።

የሠራተኛው መደብ ታሪካዊ ሚናውን መጫወት ሲጀምር አብዮታዊ ዲሲፕሊን ተከሰተ ። ይህም ኋላ በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ለታየው ለከፍተኛውና ለአዲሱ ዓይነት ዲሲፕሊን መቅድም ሆኗል ። የሠራተኛው መደብ ተደራጅቶ የመደብ ጠላቱን ሊቋቋምና ድል ሊመታ የቻለው የርዕዮተ ዓለም ትጥቃቸው የተጠናከረ ፣ ድርጅታቸው አስተማማኝ ደረጃ ላይ የደረሰ ፣ በዲሲፕሊን የታነፁ ፣ በንቃትና በፈቃደኝነት የሚያገለግሉ የፓርቲ አባላትን በማሰባሰቡ ነው ።

የምርት መገልገያዎችና ምርትም የጋራ በሆነበት ፣ ሠራተኛውም ለኅብረተሰቡ የጋራ ጥቅም በተሰለፈበት በዘመነ ሶሻሊዝምና ኮሚኒዝም ዲሲፕሊን በመተማመን ፣ በጓዳዊነት ፣ በመከባበር ፣ በነፃነትና በራስ ፍላጐት ላይ የተመሠረተ ነው ። ለዚህ ዲሲፕሊን መስፈን ምክንያት የሆነው የሶሻሊስት የምርት ግንኙነት ሲሆን ሥር ሊሰድ የሚችለውም የጥንቱ የብዝበዛ ሥርዓት ያስከተለውን ልምድና ወግ በጥብቅ በመዋጋት የሠርቶ አደሩ ሶሻሊስታዊ ግንዛቤ ሲያድግ ነው ። በሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የሥራ ፣ የውትድርና ፣ የትምህርት ፣ የሙያ ማኅበር ፣ የፓርቲ ወዘተ... ዲሲፕሊን አለ ። ከነዚህም ሁሉ የሚበልጠው ግን አንድ ሰው ለፓርቲው ራሱን በማስገዛት የሚኖረው ዲሲፕሊን ነው ። ወደ ኮሚኒዝም ለመሸጋገር የሚያስፈልገውን ንቃትና ድርጅት ለማዳበር የሚቻለውም ለፓርቲ ዲሲፕሊን ራስን ፍጹም ተገዥ በማድረግ ነው ።

(የፓርቲ ደንብን ፣ የፓርቲ ፕሮግራምን ፣ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን ይመለከቷል።)

## ዲበ አካል
*(Metaphysics)*

ዲበ በላይ ወይም ባሻገር ማለት ሲሆን አካል ደግሞ የሚዳሰስ የሚጨበጥ ማለት ነው። ስለዚህ ዲበ አካል ማለት ከቁሳዊ ነገሮች ባሻገር የሚገኙ የረቂቅ ነገሮች ጥናት ማለት ነው ።

ዲበ አካል የሚለው ጽንሰ ሐሳብ በአገልግሎት ላይ መዋል የጀመረው ከክርስቶስ ልደት በፊት ከአንደኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ ሲሆን አገባቡም የአርስጣጣሊስን የፍልስፍና ፈርጅ እንደሚያመለክት ሆኖ ነበር ። አርስጣጣሊስ "የመጀመሪያው ፍልስፍና" ብሎ የጠራውና በኋላ ግን ዲበ አካል ተብሎ የተሰየመው የፍልስፍና ፈርጅ የማናቸውም ህልውና ያለው ነገር ከፍተኛ መርህ ጥናት ሲሆን በሕዋሶቻችን እርዳታ ልንደርስባቸው የማንችላቸውን ነገር ግን በማሰላሰል ላይ በተመሠረተ ትንታኔ ልናውቃቸው የምንችላቸውንና ለሳይንስ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን የሚመለከት ነው ። ዲበ አካል በዚህ ትርጉሙ ለረጅም ጊዜ በፍልስፍና ውስጥ ሲያገለግል ቆይቷል ።

በመካከለኛው ዘመን ጽንሰ ሐሳቡ በሃይማኖታዊ ፍልስፍና ተውጦ ከቆየ በኋላ በግምት ከአሥራ ስድስተኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ ሥነ ኑባሬ ከሚለው ጽንሰ ሐሳብ ጋር አንድ እንደሆነ ተደርጎ ይተረጐም ነበር ። በአሥራ ሰባተኛው ምዕት ዓመት ውስጥ ከተፈጥሮና ከኅብረተሰብ ሳይንሶች ጋር የቅርብ ግንኙነት ኖሮት ከቆየ በኋላ በአሥራ ስምንተኛው ምዕት ዓመት ላይ ግንኙነቱ ተቋርጧል ።

በማርክሳዊ ሌኒናዊ አመለካከት ዲበ አካል ነገሮችንና ክስተቶችን ዝንተዓለማዊ ፣ የማይለወጡና እርስ በርሳቸው ያልተያያዙ አድርጎ የሚያቀርብ ፣ በተፈጥሮና በኅብረተሰብ ውስጥ የሚታዩ ለውጦችና ዕድገቶች ምንጫቸው ውስጣዊ ቅራኔ መሆኑን የማይገነዘብና የዕውቀትንም ሂደት በተዛባና ባልተመጣጠነ መልክ የሚመለከት ፀረ ዲያሌክቲካዊ የአጠናን ፣ የምርምርና የአስተሳሰብ ዘዴ ነው ።

ይህም በመሆኑ ነው ዲበ አካል ዕድገትን የመጠን መጨመር ወይም መቀነስ ፣ እንቅስቃሴን በስፍራና በጊዜ ውስጥ የሚታይ ለውጥ ፣ የተፈጥሮ ክስተቶችን የድግግሞሽና የዑደት እንቅስቃሴ አድርጎ የሚወስደው ።

የዲበ አካል ባሕርይና ፍች ሊመነጭ የቻለው በጥንት ጊዜና በተሃድሶ ዕውቀት ዘመን ሳይንሳዊ ዕውቀት እያደገና ጥልቀት እያገኘ በመምጣቱ ተፈጥሮን በየፈርጁ እየለያዩ የሚያጠኑ ሳይንሶች በመፈጠራቸውና እያንዳንዱ ሳይንስ ልዩ ልዩዎቹን የተፈጥሮ ዘርፎች በተናጠል እንደማይገናኙ አድርጎ ማጥናትና መግለጽ በመጀመሩ ነው ። በሌላም በኩል ከካፒታሊዝም መከሰትና ማደግ ጀምሮ የፊዚክስና የሜካኒክስ ሳይንሶች ይበልጥ ሊያድጉ በመቻላቸው ባመዛኙ ሳይንቲስቶች ራሳቸው ፈላስፎች ስለነበሩ በነዚህ የፊዚክስና የሜካኒክስ ሕግጋት ማኅበራዊ ሕይወትንና ክስተቶችን ለመግለጽ ሙከራ ይደረግም ስለነበር ነው ።

የዲበ አካል ፀረ ዲያሌክቲክስ ገጽታን ለመጀመሪያ ጊዜ ያሳየው ሄግል ቢሆንም ለዚህ ገለጻው በቂ ትንታኔና መሠረት አልሰጠውም ነበር ።

(ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነትን ይመለከቷል ።)

## ዲያሌክቲካዊ ሥነ አመክንዮ
*(Dialectical Logic)*

ዲያሌክቲካዊ ሥነ አመክንዮ በሰው አእምሮ ውስጥ የሚከሰቱትን የነባራዊውን ዓለም የዕድገትና የለውጥ ነፀብራቅ ቅርፆችንና ሕግጋትን እንዲሁም የእውነትን ግንዛቤ የሚገዙትን ሕግጋት የሚያጠና ሳይንስ ነው ።

ዲያሌክቲካዊ ሥነ አመክንዮ በጥንታዊ ፍልስፍና ውስጥ ባልዳበረ መልኩ በተለይም በሄራቅሊጦስ ፍልስፍና ውስጥ የተቀረፀ ቢሆንም ሳይንሳዊነት ያገኘው ግን የማርክሳዊ ፍልስፍና ክፍል ሆኖ ከወጣበት ጊዜ አንሥቶ ነው ። ከዚህ በፊት ግን በየዘመኑ የነበሩ ዕውቅ ፈላስፎች አዳባሪ ሐሳቦች በመሰንዘር ለዕድገቱ አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

ከነዚህም ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ የሚይዘው ሄግል ነው ። የሄግል ፍልስፍና ሐሳባዊ ቢሆንም ዲያሌክቲካዊ ሥነ አመክንዮን ስፋትና ጥልቀት ባለው መንገድ ሥርዓት በማስያዝ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

ዲያሌክቲካዊ ሥነ አመክንዮ ሳይንሳዊ መሠረት ከመያዙ በፊት ቅርፃዊ ሥነ አመክንዮ ለረጅም ጊዜ የአሳቦት ሕግጋትና መልኮች ብቸኛ አስተምህሮ በመሆን አገልግሏል ። ሆኖም ከ17ኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ የተፈጥሮ ሳይንሶችና የፍልስፍና ዕድገት የፈጠሩዋቸውን ሁኔታዎች ቅርፃዊ ሥነ አመክንዮ ለመግለጽ ባለመቻሉ የተሻሉ አጠቃሳይ የአሳቦትና የግንዛቤ መርሆችና ዘዴዎች መፈጠር አስፈላጊ እየሆነ በመምጣቱ ለማርክሳዊ ዲያሌክቲክስ መከሰት አንዱ ምክንያት ሆኗል ።

የማርክሳዊ ሥነ አመክንዮ አስተምህሮ ሰፊና ጠቃሚ የሆኑትን የሰውን ልጅ የዕውቀት ዕድገት ውጤቶች በመውረስና በመለወጥ ኀብር ወዳለው የሳይንስነት ደረጃ ከፍ አድርጓቸዋል ። ስለሆነም ዲያሌክቲካዊ ሥነ አመክንዮ የሰው አሳቦት ታሪክና የኀብረተሰብ ዕድገት አጠቃሳይ ዕውቀት ነው ። ዲያሌክቲካዊ ሥነ አመክንዮ ከቅርፃዊ ሥነ አመክንዮ ጠቃሚ ሐሳቦችን በመውሰድ ኑባሬንና የኑባሬን ነፀብራቅ ያዋሀደ ነው ።

ዓለም በማያቋርጥ የዕድገትና የለውጥ ሂደት ላይ የምትገኝ በመሆኗ የአሳቦት ቅርፆች እንዲሁም ጽንሰ ሐሳቦችና ፈርጆችም በዕድገት መርሆች ላይ የተመሠረቱ ናቸው ። ስለሆነም የዲያሌክቲካዊ ሥነ አመክንዮ ዓይነተኛ ተግባር ቅስቃሴን ፣ ዕድገትን ፣ የክስተቶችን ውስጣዊ ቅራኔና ከአንዱ ደረጃ ወደ ሌላው የሚደረገውን ሽግግር ጥራት ባለው መንገድ መግለጽ ነው ።

ከዲያሌክቲክስ አንፃር ሲታይ የግንዛቤ ሕግጋት አሳቦት ከውጫዊ ወደ ውስጣዊው ፣ ከክስተቱ ወደ ፍሬ ነገሩ ፣ ከረቂቁ ወደ ተጨባጩና ከአንፃራዊው ወደ ፍጹማዊው እውነት ከዚህም በተገላቢጦሽ የሚያደርገውን ዕድገት የሚገዙ ናቸው ። ዲያሌክቲካዊ ትንታኔንና ንጥረ ሐሳብን ፣ መስተጋብእንና ምንጨታን እንዲሁም ዳሰሳዊ ግንዛቤን ከንድፈ ሐሳባዊ ግንዛቤ በመለየትና እያንዳንዳቸውን ከሌላው ጋር

ሳይለያይ በጥምረታቸው ይገነዘባቸዋል ። ለዚህም ነው ዲያሌክቲክስ የግንዛቤ አጠቃላይ ሥነ አመክንዮአዊ መሠረት ነው የሚባለው።

(ቅርፃዊ ሥነ አመክንዮን ፣ ሥነ አመክንዮን፣ መስተጋብአዊ ሥነ አመክንዮን ፣ ምንጩታዊ ሥነ አመክንዮን ይመለከቷል።)

## ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት
*(Dialectical Materialism)*

የማርክሲዝም ፍልስፍና መሠረትና ሳይንሳዊ ንጽረተ ዓለም ነው ። ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት በማርክስና በኤንግልስ ከተመሠረተ በኋላ በሌኒንና በሌሎች ማርክሳውያን ሲዳብር ችሎአል ። ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት የተከሰተው በ1840ዎቹ ሲሆን አመሠራረቱ ከሳይንሳዊ ዕውቀትና ከሠራተኛው መደብ አብዮታዊ ንቅናቄ ጋር የተሳሰረ ነው ። የዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት መከሰት በሰዎች የአስተሳሰብና የፍልስፍና ታሪክ ውስጥ አብዮታዊ ለውጥ ፈጠረ ። ይህ በፍልስፍና ውስጥ የታየው አብዮት በሰው ልጅ አስተሳሰብ ውስጥ ተራማጅና ከፍተኛ የሆኑትን ሐሳቦች ከነበሩባቸው ድክመቶች አላቆ አዲስ ዓይነት አመለካከትን ፈጥሯል ። ከዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት በፊት ፍልስፍና ሲዳብር የቻለው በቁስአካላዊ ፍልስፍናና በሐሳባዊ ፍልስፍና መካከል በነበረው ቅራኔና ትግል ነው ። ሆኖም ማርክስና ኤንግልስ ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነትን በቀመሩበት ጊዜ የቀደምት ቁስአካላውያንን አስተሳሰቦችና የሐሳባውያንን ዲያሌክቲክስ እንዳለ ተቀብለው በመገጣጠም አልተገለገሉበትም ። ከዘመኑ የተፈጥሮ ሳይንስ ግኝቶችና ከሰዎች ታሪካዊ ልምድ በመነሣት ቁስአካልዊነት ሳይንሳዊና የማያወላውል ሊሆን የሚችለው ዲያሌክቲካዊ ሲሆን ብቻ እንደሆነና ዲያሌክቲክስም በተራው ሳይንሳዊ ሊሆን የሚችለው ቁስአካላዊ ሲሆን ብቻ እንደሆነ አረጋገጡ ።

የቀድሞ ቁስአካላዊ ፍልስፍና ዓለምን በመግለጽ ላይ ብቻ ተወስኖ የቆየ ሲሆን ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ግን የተፈጥሮን ፣ የኅብረተሰብንና የሰውን አስተሳሰብ ሂደት ከማጥናቱም በላይ በአብዮታዊ መንገድና በተግባር ዓለምን ለመቀየር የሚታገል ፍልስፍና ነው ። ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት መደብ አልባ ኅብረተሰብን (የኮሚኒስት ኅብረተሰብን) ገንቢ ለሆነው ለወዝአደሩ መደብ የፍልስፍና መሠረት ነው ። ይህም በመሆኑ ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ለኮሚኒስት ፓርቲዎች ፕሮግራሞች እስትራቴጂ ፣ ታክቲኮችና እንቅስቃሴዎች ፍልስፍናዊ መሠረት ነው ።

ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት የራሱ የሆነ የጥናት መስክ ያለው ንጽረተዓለም ነው ። የጥናቱም መስክ ኅብረተሰብን ፣ ተፈጥሮንና የሰውን ዕውቀት ሂደት የሚገዙትን አጠቃላይ ሕግጋትን ፣ የነባራዊ እውነታን መሠረትና የርሱም በኅሊናችን ውስጥ የመንፀባረቅ መርሆችን ያጠቃልላል ። ዓለም ቁሳዊ አካል ነች ፤ በዓለም ውስጥ ከቁስ አካል ፣ ከዕድገቱና ከእንቅስቃሴው ሌላ ምንም ነገር የለም የሚለው መርህ የዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ዋንኛ መርህ ነው ። ተፈጥሮ እያደገ በመምጣት ሕይወትንና የሚያስብ ቁስአካልን (ሰውን) ለማስገኘት የቻለው በራሱ ዕድገትና የዕድገት ሕግጋት እንጂ በማንኛውም መለኮታዊ ኃይል ፈጠራ አይደለም ።

(ተናከአታዊ ቁስአካልነትን ፣ ቁስአካልን ፣ ዲያሌክቲክስን ይመለከቷል ።)

## ዲያሌክቲክስ
*(Dialectics)*

በጥንታዊት ግሪክ የቁም ትርጉሙ በጥያቄና መልስ የሚደረግ የክርክር ስልት ፣ በክርክር ውስጥ ከተቃራኒው ሰው ሐሳብ ውስጥ ቅራኔን በማውጣት ከትክክለኛው አስተሳሰብ ላይ የመድረስ ጥበብ ማለት ሲሆን በማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍችው የተፈጥሮን ፣ የኅብረተሰብንና የአስተሳሰብን ዕድገት የሚገዙትን አጠቃላይ ሕግጋት የሚያጠና ሳይንስ ነው ። ዲያሌክቲክስ ረጅም ታሪክ ያለውና በተለያዩ ወቅቶችም የተለያዩ ትርጉሞች የነበሩት ነው ።

ከሶቅራጥስ በፊት የነበሩት ጥንታውያን ፈላስፎች ዲያሌክቲክስ በሚለው ቃል ባይጠቀሙም ማናቸውም ህልውና ያለው ነገር በሙሉ እንደሚለወጥና ዓለምም በሂደት ላይ እንዳለች ፣ የማናቸውም ነገር ባሕርያት ወደ ተቃራኒዎቻቸው እንደሚለወጡ ይቀበሉ

ነበር ። ዲያሌክቲክስ የሚለውም ቃል በአገልግሎት ላይ መዋል በጀመረበት ጊዜ የነበረው ትርጉም በክርክር ጊዜ በጥያቄና በመልስ አማካይነት እውነትን የማውጣት ጥበብ ሊሆን የቻለው ማናቸውም ነገር ቅራኔ ያዘለ፣ ነጠላና ጣምራዊነት ያለው ፣ ዘለዓለማዊና ተሸጋጋሪ ፣ የማይለወጥና ተለዋዋጭ ፣ በዕረፍትና በቅስቃሴ ላይ እንደሚገኝ ተደርጐ በመወሰዱ ነበር ።

በፊውዳል ኅብረተሰብ ፍልስፍና ውስጥ ደግሞ ዲያሌክቲክስ የማይፋለሱ የአስተሳሰቦች ሥርዓት (ሥነ አመክንዮ) ተደርጐ ይተረጐም ነበር ። ዲበ አካል አይሎ በነበረበት በመጀመሪያው የካፒታሊዝም የዕድገት ደረጃ ላይ የነበሩ አንዳንድ ፈላስፎች ዲያሌክቲክስን "የተቃራኒዎች ግንኙነት" አድርገው ተርጉመውት ነበር ።

በቅድመ ማርክሳዊ ዲያሌክቲክስ የዕድገት ሂደት ውስጥ ዲያሌክቲክስን የእውነታ ግንዛቤ ከፍተኛ ደረጃ ብቻ ሳይሆን የተግባር መሠረትም አድርጎ የተጠቀመበት የጀርመን ሐሳባዊ ፈላስፋ ሄግል ነበር ። በሄግል ፍልስፍና ውስጥ ማናቸውም ነገር ቅራኔን እንደያዘና በዕድገትም ወደ ራሱ ሽረት እንደሚያመራ ፣ ይህም የውስጣዊ ቅራኔው ውጤት እንደሆነ ተገልጾ ነበር ። ይሁን እንጂ ይህ ትንታኔ በፍጹማዊ ሐሳባዊነት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ አመለካከቱ የተዛባና ራሱን የሚቃረን ነበር ።

ዲያሌክቲክስ ከሐሳባዊ ይዘቱ ተላቆ በማርክስና በኤንግልስ አማካይነት በማርክሳዊ ሌኒናዊ የታሪክ ሂደትና በዕውቀት ዕድገት በቁስ አካላዊ ግንዛቤ ሳይና በተፈጥሮ ፣ በኅብረተሰብና በዕውቀት ውስጥ በሚካሄዱ ተጨባጭ ለውጦች ትንታኔ ላይ በመመሥረት ሳይንሳዊ ሊሆን ችሏል ። ዲያሌክቲክስ የእውነታን የዕድገት ሕግጋት ከግንዛቤ ሂደት ሕግጋት ጋር ያዋህዳል ። ስለሆነም ቁስአካላዊ ዲያሌክቲክስ የኑባሬና የሥነ ዕውቀት አስተምህሮ ነው።

ቅራኔ የቁስአካላዊ ዲያሌክቲክስ መሠረታዊ ፊርጅ ነው ፤ ምክንያቱም ቅራኔ የማናቸውንም ነገር አንቀሳቃሽ ኃይልና የዕድገትን ምንጭ የሚያሳይ በመሆኑ ነው ። ቁስአካላዊ ዲያሌክቲክስ ተፈጥሮንና ኅብረተሰብን የምናጠናበት የፍልስፍና ዘዴ ነው ።

ዲያሌክቲክስ ማናቸውም ነገር በእንቅስቃሴ ላይ ያለ መሆኑንና ይህም እንቅስቃሴ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ፣ ከቀላል ወደ ውስብስብ ፣ ከመጠን ወደ ዓይነት ፣ ከአሮጌ ወደ አዲስ ሽግግር መኖሩን ያሳያል ። ዲያሌክቲክስ የቅስቃሴ ሕግ ጥናት በመሆኑ የማኅበራዊ ዕድገት ታሪካዊ ሁኔታዎችን የምንረዳበት ፣ በአሮጌው ቅርፆች (መልኮች) እና በአዲሱ ይዘት መካከል ያለውን ግንኙነትና ልዩነት ተረድተን ኅብረተሰብን የምንለውጥበት ሳይንስ ነው ።

(ሳይንሳዊ ዲያሌክቲክስን ፣ ዲያሌክቲካዊ ቁስ አካልነትን ፣ የዲያሌክቲክስ ሕግን ይመለከቷል።)

## ዲያሌክቲክስ ሕግ (የ—)

*(Law of Dialectics)*

የተፈጥሮን ፣ የኅብረተሰብንና የሐሳብን እንቅስቃሴና ዕድገት የሚያጠና ሕግ ነው ። የእንቅስቃሴ መነሻ ምክንያት የቅራኔዎች አንድነትና ትግል መሆኑና ይህም ትግል በሚጠይቀው መፍትሔ ነገሮች ከትንሽ ወደ ትልቅ ፣ ከቀላል ወደ ውስብስብ ፣ ከመጠን ወደ ዓይነት እንደሚሸጋገሩና በሽግግሩም አሮጌው በአዲሱ እየተሻረ እንደሆነ ያሳያል ። በሂደት ውስጥ በተወሰነ ደረጃ ላይ በዓይነታቸው አዲስና ከፍተኛ የሆኑ ክስተቶች እንደሚፈጠሩ የሚያስረዱ የእንቅስቃሴንና የዕድገትን አጠቃላይ ሕጐች የሚያጠና ሳይንስ ነው።

ሕግ የሚለው ጽንስ ሐሳብ የሚያመለክተው የነገሮች እንቅስቃሴና ለውጥ በዘፈቀደ ወይም በአጋጣሚ የሚደረግ ሳይሆን በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ ብቻ የሚከናወን መሆኑን ነው። ሕግ ግዴታን ያዘለ ነው፤ ማንኛውም ነገር ደግሞ በቅራኔ መከፋፈሉና የቅራኔው ትግል ወደ ከፍተኛው የዕድገት ደረጃ ማምራቱ ሕግ ነው ።

ዲበ አካላዊ የሕግ ግንዛቤ ግን ነገሮች ሳይለዋወጡ በመመሳሰልና በመደጋገም አዝማሚያ ላይ ብቻ እንደሆኑ አድርጎ መረዳት ነው ። በእርግጥም አንድ ነገር ሳይለዋወጥ በአንድ ሁኔታ ብቻ የሚደጋገም ከሆነ ሁልጊዜ የሚሰጠው ውጤት ተመሳሳይ ነው

ብሎ ለመናገር ይቻላል ። ነገር ግን ይህ ሁኔታ ድግግሞሽን ብቻ የሚያመለክት አይደለም ። የዲያሌክቲክስ ሕግ የሚያስረዳን አዲስና ከፍተኛ ክስተቶች በሂደት ውስጥ የመፈጠራቸው ጉዳይ የማይቀር ግዴታ መሆኑንም ጭምር ነው ። የነገሮች መደጋገም በተወሰነ ጊዜና ቦታ የሚታይ ቢሆንም በአጠቃላይ የነገሮችን ውስጣዊ አንድነት ስንመለከት የቅራኔዎች ትግል እውነታን በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች የሚያስኬድና የሚያስተሳስር መሆኑን የዲያሌክቲክስ ሕጐች አረጋግጠዋል ።

(ሕግን ፣ ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነትን ፣ የዲያሌክቲክስ ሕጎችን ይመለከቷል ።)

## ዲያሌክቲክስ ሕጎች (የ—)

*(Dialectical Laws)*

የዲያሌክቲክስ ሕጎች የቁስአካልን የዕድገት አቅጣጫና በነገሮች ሁለንታዊ ባሕርይ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገልጹ የማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍና መሠረታዊ ሕጎች ናቸው ። ዕውቀትን ጨምሮ ማንኛውም ኑባሬ በቅስቃሴ ፣ በለውጥና በዕድገት ላይ ያለ ነው ። በዚህ የቅስቃሴ ፣ የለውጥና የዕድገት ሂደት ማንኛውም ክስተት በራሱና በተናጠል የሚኖር ሳይሆን ከሌሎች ነገሮችና ክስተቶች ጋር ግንኙነት፣ ድግግፍና መስተጋብር አለው ። የዲያሌክቲክስ ሕጎች የክስተቶችን ዕድገትና ግንኙነት የሚገዙ ሁለንታዊ ሕጎች ናቸው ። ሁለንታዊ ሕጎች የምንላቸው በማናቸውም ቦታና ጊዜ የተፈጥሮን ፣ የኅብረተሰብንና የዕውቀትን ዕድገት ፣ ቅስቃሴና ለውጥ የሚገዙና የሚመሩ አጠቃላይ ሕጎች በመሆናቸው ነው ። የቁስአካላዊ ዲያሌክቲክስ መሠረታዊ ሕጎች ሦስት ናቸው ፤ እነሱም ፦—

አንደኛ ፣ የተቃራኒዎች አንድነትና ትግል ሕግ ፣ በማንኛውም ማኅበራዊና ተፈጥሮአዊ ኑባሬ ውስጥ የእርስ በርስ ግንኙነትና መስተጋብር ያላቸው በአንድነትና በልዩነት የሚኖሩ ሁለት ባሕርያት መኖራቸውን የሚገልጽ ሕግ ነው ። የተቃራኒ ባሕርያት አንድነት ጊዜያዊ ሲሆን ትግላቸው ግን ፍጹማዊ ነው ።

ሁለተኛ ፣ የዓይነትና የመጠን ለውጥ ሕግ ፤ ማንኛውም ክስተት በዕድገት ሂደቱ ከመጠን ወደ ዓይነት ወይንም ከዓይነት ወደ መጠን ሽግግር የሚያደርግ መሆኑን የሚያመለክት ሕግ ነው ። በዚህ ሕግ መሠረት የአንድ ነገር መጠናዊ ለውጥ ቀስ በቀስ ተከማችቶ የክስተቱን ዓይነታዊ ለውጥ ያስከትላል ፤ ይህም አሮጌው በአዲሱ መተካቱን ያሳያል ።

ሦስተኛ ፣ የሽረት ሽረት ሕግ ፤ በዕድገት ሂደት አሮጌውን አዲሱ እየሻረው ፣ በአሮጌው ፍርስራሽ ላይ አዲሱ ማደጉን የሚገልጽ ሕግ ነው ። በዚህ ሕግ መሠረት አሮጌውን አዲሱ ይሽረዋል ፤ አዲሱ አሮጌውን ሲሽረው ግን ለአዲሱ ተስማሚ ያልሆኑትን ባሕርያት ብቻ እያጠፋ ለአዲሱ ዕድገት ጠቃሚ የሆኑ ባሕርያትን ከአሮጌው እየወሰደ ያዳብራቸዋል ፤ ወደላቀና ለአዲሱ ሁኔታ ተስማሚ ወደሆነ ደረጃም ከፍ ያደርጋቸዋል ። አንዳንድ ጊዜም ታዳጊው ክስተት አሮጌው ያለፈባቸውን ሁኔታዎች ቢያንፀባርቅም ከበፊቱ በላቀና በተሻለ መልክ ነው ።

(የተቃራኒዎች አንድነትና ትግል ሕግን ፣ የሽረት ሽረት ሕግን ይመለከቷል።)

## ዲደሮ ፣ ደኒ

*(Diderot, Denis)*

ከ1713 — 1784 የኖረ ፣ የፈረንሳይ ቁስአካላዊና አብራሂ ፈላስፋ ነው ። ዲደሮን በይበልጥ ታዋቂ ያደረገው በ1751 ለመጀ

መሪያ ጊዜ ለታተመው "ኢንሳይክሎፒዲያ"
በአዘጋጅነትና በበላይ ተቆጣጣሪነት ያደ
ረገው አስተዋጽኦ ነው ።

በጻፉቸው መጻሕፍት ውስጥ (ፓንሴ
ፊሎዞፊክ ፥ አንትረትየ አንትር ዳላምቤር ኤ
ዲደሮ ፥ ሰሬቭ ደ ዳላምቤር) ቁስአካላዊ አመለካ
ከቱን ደጋግሞ ገልጿል ። በተለይም ከሃይማ
ኖት የሚመነጩ አመለካከቶችን በመቃወም
ጽፏል ። ሰውንና እንስሳን የሚለየው የቁስ
አካል አደረጃጀት መሆኑንና ተፈጥሮም በማ
ያቋርጥ እንቅስቃሴና ለውጥ ላይ እንደሚገኝ
ተናግሯል ።

የማኅበራዊ ክስተቶችን ምክንያት ሲያ
ስረዳም ተቃራኒ የሆኑ ሐሳቦችን ያቀረበ
በመሆኑ ቁስአካላዊ አመለካከቱ የጠራ አልነ
በረም ። ስለእንቅስቃሴ ፥ ስለማኅበራዊ
ሆነ ስለተፈጥሮ ክስተቶች የነበረው ግንዛቤ
ተናክአታዊና ዲበ አካላዊ መሆኑ የአመለካከ
ቱን ውሱንነት ያሳያል ።

## ዳሰሳዊ ዕውቀት

### *(Empirical Knowledge)*

የመጀመሪያና መነሻ የሚሆነን ከልምድ
የምናገኘው ዕውቀት ነው ። ይህ ዕውቀት የሚ
ገኘው በቀጥታ ሕዋሳት በሚሰጡን መረጃዎች
ቢሆንም ከመደጋገም የተነሣ እነዚህ መረጃ
ዎች መለስተኛና አጠቃላይ መልክ በማግኘ
ታቸው በቃላት አማካይነት የነገሮችን ሂደት
መግለጽ ይቻላል። ለምሳሌ ደመና ስናይ ዝናብ
እንደሚያስከትል እንጠብቃለን ። ይህ ሊሆን
የሚችለው ደመና በተደጋጋሚ ዝናብ እንደ
ሚያስከትል በመረዳታችን ነው ። ዳሰሳዊ
ዕውቀት የሚባለውም የደረስንበት አጠቃላይ
ግንዛቤ አንዴ ባየነው ብቻ ሳይሆን በተወ
ሰነ ሥርዓት ከክስተቶች መደጋገም የተነሣ
የምናገኘው በመሆኑ ነው ። ዳሰሳዊ ዕው
ቀት ጥልቀት የሌለው መሆኑ ግልጽ ነው።
ነገሮች እንደሚመስሉና እንደሚከታተሉ እን
ረዳለን እንጂ ለምን እንዲህ ሆኑ የሚለውን
ጥያቄ ይህ ዕውቀት ሊመልስ አይችልም ።
የነገሮች ፍሬ ነገር ምክንያትና ውስጣዊ
መስተጋብር ለሕዋሳት የማይገለጹ በመሆ
ናቸው አንዱ ክስተት ሌላ ክስተት እንደ
ሚያስከትል በልምድ እንናገራለን እንጂ ጠል
ቀን ምክንያቱን አልተረዳንም ። ለምሳሌ
በኅብረተሰብ ውስጥ በኑሮ ደረጃ የተለያዩ
ግለሰቦች እናያለን ። በልምድም የከበርቴ
ልጅ ከበርቴ እንደሚሆን ፥ የደሀው ደግሞ
ደሀ ሆኖ እንደሚቀር ለመናገር እንችላለን ።
ለምን እንዲህ ሆነ ለሚለው ጥያቄ ግን ባየ
ነውና በለመድነው ብቻ ልንመልስ አንች
ልም ። ምክንያቱን ለማግኘት ወደ መደብ ፥
ወደ ምርት ግንኙነትና ወደመሳሰሉት ጽንሰ
ሐሳቦች መሸጋገር ይኖርብናል ።

ይህንን በማየት ይመስላል ሐሳባዊ ፈላ
ስፎች ዕውቀት ከሐሳብ እንጂ ከሕዋሳት
አይመጣም ያሉት ። ሆኖም ይህ አባባል
የሚዘነጋው ተጨባጭ ሁኔታ በሕዋሳት አማ
ካይነት እንደሚገለጽልንና የደረሱን መረጃ
ዎች የዕውቀት መነሻና መድረሻ መሆና
ቸውን ነው ። ዕውቀት ከሕውሰታዊ መረጃ
ዎች ካልተነሣና በነሱም ላይ ካልተመረ
ኮዘ ፥ ደግሞም እነሱ የሚያሳዩትን ክስ
ተቶች ካሳብራራ ምንነታቸውንና ምክንያታ
ቸውን ካልገለጸ ተጨባጭ ዕውቀት መሆኑ
ይቀራል ፤ ተፈጥሮንና ማኅበራዊ ኑሮን ለመ
ቆጣጠር መሣሪያ ሊሆነንም አይችልም ።

(ዳሳሽነትን ፥ ጽንሰ ሐሳብን ፥ ምክኑያዊነትን
ይመለከቷል።)

## ዳሳሽነት

### *(Empiricism)*

ሥነ ዕውቀትን በሚመለከት በአንድ
ጐኑ ወደ ተናክአታዊ ቁስአካልነት የሚ
ያደላ በሌላው ጐኑ ደግሞ በኅሊናዊ ሐሳ
ባዊነት ውስጥ የሚጠቃለል በአጠቃላይ
አስተሳሰቡ ግን ምክኑያዊነትን የሚቃወም
የዕውቀት ንድፈ ሐሳብ ነው ።

ከምክኑያዊነት የሚለየው ዋና ነጥብ
የዕውቀት ምንጭ አመክንዮ ሳይሆን ልምድ
ነው የሚለው አቋሙ ነው ። የአስተሳሰቡን
ፍሬ ነገር ለመረዳት ዳሳሽነት ስለ ሐሳብ ያለ
ውን ግንዛቤ በቅድሚያ መረዳት ያስፈልጋል።
ሐሳብ በተፈጥሮ የሚያገኘው ጽንሰ ሐሳብ
የለውም ፤ ምክኑያዊነት እንደሚለው ሳይሆን
ማንኛውም ጽንሰ ሐሳብ የሚገኘው ከልባ
ዌና ከልምድ ነው ። ሐሳብን በመጀመሪያ
ደረጃ ምንም ያልተጻፈበት ነጭ ወረቀት
አድርገን መውሰድ ይኖርብናል ። ምክንያቱም
ሰው ሲወለድ ምንም ዕውቀት ይዞ አይመ

ጣም ፤ የሚያገኘው ዕውቀት ሁሉ የሚመጣው ከልምድ ብቻ ነው ።

እንዴት ልምድ የዕውቀት ምንጭ ይሆናል ? በመጀመሪያ በሕዋሳት አማካይነት ስለአካባቢ መረጃዎች እናገኛለን ። ቀለምን ፥ ክብደትን ፥ ስፋትን ፥ እንቅስቃሴን ፥ ቦታን ፥ ጊዜን ወዘተ . . . በሚመለከት ሐሳቦች በአእምሮአችን ውስጥ ይቀረፃሉ ። ሆኖም እነዚህ መረጃዎች በመረጃነታቸው ብቻ ዕውቀት አይሰጡንም ፤ ዕውቀት የሚገኘው ከሕግጋት አንፃር ነገሮችን ስናያይዝ ነውና ። በመሆኑም አንድን ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ ብቻ ስናየው ምንም ዓይነት ዕውቀት ሊሰጠን አይችልም ። ነገር ግን ሁኔታው ሲደጋገም ጽንሰ ሐሳቦች በአእምሮአችን ውስጥ እንዲቀረፁ ምክንያት ይሆናል ። ከመረጃ ወደ ጽንሰ ሐሳብ የምንሸጋገረው በልምድ ይሆናል ማለት ነው ። ለምሳሌ ለመጀመሪያ ጊዜ እሳት ብናይ እሳት ውሃን ወደ እንፋሎት ይቀይራል ብለን ለመናገር አንችልም ። ነገር ግን በተደጋጋሚ ውሃ እሳት ሲነካው ወደ እንፋሎት መቀየሩን ስንመለከት አንዱ የሌላው መንሥኤ መሆኑን እንረዳለን ። መንሥኤ የሚለው ጽንሰ ሐሳብ ምክኑያዊነት እንደሚለው በተፈጥሮ የሚገኝ ሳይሆን ሁኔታዎች በተደጋጋሚ የሚከታተሉ በመሆናቸው ይህንኑ ለመግለጽ ከልምድ የምናገኘው ጽንሰ ሐሳብ ነው ። ስለዚህም ማንኛውም ጽንሰ ሐሳብ የሚመጣው ከልምድ ነው ።

ከልምድ የምናገኘው ዕውቀት ደግሞ ምንም ጊዜ ትክክለኛ ነው ፤ ምክንያቱም ይህን ዕውቀት እኛ የፈጠርነው ሳይሆን ከተጨባጩ ያገኘነው ዕውቀት በመሆኑ ነው ። በአእምሮአችን ውስጥ የሚገኙት ሕውስታዎችና ጽንሰ ሐሳቦች የተፈጥሮ ሁኔታና ሥርዓት ግልባጭ በመሆናቸው ከልምድ የሚገኘው ዕውቀት በግድ ተጨባጭነት ይኖረዋል ። የማንኛውንም ጽንሰ ሐሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከየትኛው ተጨባጭ መረጃና ልምድ እንዳገኘነው ምን ጊዜም መጠየቅ እንችላለን። ከልምድ ያልመነጨ ሐሳብ ካለን ይህ ሐሳብ ፈጠራ መሆኑን በቀላሉ እንረዳለን ።

ዳሳሽነት እንዳቀራረቡ ተቀባይነት ያለው ይመስላል ። ነገር ግን ጠጋ ብለን ስናይ በውስጡ ያዘለው መላምትና አስተሳሰብ የተዛባ ነው ። በመጀመሪያ ደረጃ ዳሳሽነት ስለ ነባራዊ እውነታና ስለ ዕውቀት ነባራዊነት ትክክለኛ አቋም ሊወስድ አይፈልግም ፤ ሊወስድም አይችልም ። የዕውቀት ምንጭ ልምድ ነው ስንል መታየት ያለበት ይህ ልምድ ኅሊናዊ መሆኑ ነው ። የዕውቀት ምንጭ ነባራዊ ወይም ቁስአካል ሳይሆን ነባራዊው በኛ አእምሮ ውስጥ የሚፈጥረው የሐሳብ ክስተት ነው ። እነዚህ ሐሳቦች ነባራዊውን ይመስላሉ ወይ ለሚለው ጥያቄ ዳሳሽነት መልስ ለመስጠት አይፈልግም ። ለዚህ የሚሰጠው ምክንያት ሐሳብ ሊመስል የሚችለው ሌላን ሐሳብ በመሆኑ ከሐሳባችን ውጭ ወጥተን ሞዴሉን ማለትም ምንጩን በሐሳባችን ውስጥ ካሉት ክስተቶች ጋር ለማወዳደር አንችልም የሚል ነው ። ክብደት ፥ ቀለም ፥ ስፋት ወዘተ ...ስንል እነዚህ ነገሮች የኛ ሐሳብ ናቸው ፤ ከኛ ውጭ በነባራዊነት በዚህ ሁኔታ ፥ በዚህ መልክና ይዘት አሉ ለማለት አይቻልም ። በመሆኑም ዳሳሽነት የሚያመራው ወደ ኢታዋቂነት መሆኑን እንረዳለን ።

የዳሳሽነት ሁለተኛው ድክመት ግዴታን ያለመቀበሉ ነው ። በእርግጥ እሳት የእንፋሎት መንሥኤ ነው ወይ ለሚለው ጥያቄ ዳሳሽነት መልስ የለውም ። ምክንያቱም ዕውቀት በልምድ ብቻ የተገኘ እስከሆነ ድረስ በግዴታ ግንዛቤ ሊተረጎም አይችልም ። ልምድ ነገሮች እስካሁን ወይንም በአጋጣሚ እንዲህ ናቸው ለማለት ያስችላል እንጂ በግድ እንዲህ ይሆናሉ ለማለት አያመችም ። ዳሳሽነት እንደሚለው ነገሮችን በግዴታ ለማገናኘት የማይቻለው መንሥኤና ተገብሮት ሁሌም የተለያዩ ክስተቶች በመሆናቸው ነው ። እሳት እንፋሎትን በግድ ያስከትላል ለማለት የሚቻለው ሁለቱ በቅርፅና በይዘት ተመሳሳይነት ቢኖራቸው ነበር ። ስለዚህ በልምድ ብቻ አንዱ የሌላው መንሥኤ ነው ብለን እንናገራለን እንጂ ሁለቱንም የሚያገናኝ ግዴታ ለኛ የማይፈታ ምሥጢር ነው ። መንሥኤ የምንለው በልምድ የእሳት ሐሳብና የእንፋሎት ሐሳብ በአእምሮአችን ውስጥ መተሳሰራቸውን እንጂ ነባራዊ ግንኙነቶችን የሚያመለክት ሆኖ አይደለም ። መንሥኤ የሐሳቦች መያያዝ በመሆኑ ነው. እሳትንና ውሃን ስናይ ከልምድ እንፋሎት የምንጠብቀው ። ከሐሳባችን ውጭ ግን አንዱ

እንዴት ወደሌላው እንደሚቀየር ስለማናውቅ ሕግጋት (የተፈጥሮ) የምንለው የሐሳቦችን ግጥምጥሞሽ ብቻ ነው ።

ነባራዊው ሐሳብ ነው ወይስ ቁስ አካል በሚለው ጥያቄ ላይ ግልጽ አቋም ባለመውሰዱ ዳሳሽነት ለእምነት ቦታ የሚተው መሆኑ ገሃድ ነው ። ስለዚህም በሐሳባዊ ፍልስፍና ውስጥ ይመደባል ። ስለነባራዊው ምንነት አላውቅም ማለት ከኋላ ሆኖ ሐሳባዊነትን መደገፍ መሆኑ ግልጽ ነው ። ይህ ንድፈ ሐሳብ ከገኸራው መደብ ጋር ያለውን የውስጥ ስምምነትም መረዳት ይቻላል ። ዕውቀት ከልምድ ነው የሚመጣው ማለትና ከልምድ ውጭ ምንም መናገር አይቻልም ማለት ኅብረተሰብን በሚመለከት በገኸርና በተገኸር መከፋፈሉ ከልምድ የምናየው በመሆኑ መቀበል ይኖርብናል ማለት ነው ። ከዚህ ውጭ ሌላ የምናስበው ነገር ሊኖር አይችልምና ሁኔታዎችን የመለወጥ ወይም ያለውን አለመቀበል ከዳሳሽነት የማይዛመድ አመለካከት ነው ። ዳሳሽነት ለንድፈ ሐሳብ የሚሰጠው አነስተኛ ግምት የሚያስረዳን ነገሮችን አርቆ የመመልከት ፍላጐት እንደ ሌለው ነው ። በመሆኑም ከልምድ ብቻ ለመማር የሚደረገው ጥረት ውሱን የሆነ አስተሳሰብን ያስከትላል ፤ ከጥገና ለውጥ ውጭ ሁኔታዎችን ለመለወጥ አያደፋፍርም ። ሰውን ፣ ኅብረተሰብንና ተፈጥሮን ከልምድ ብቻ ነው የምናውቃቸው ማለት አሁን ባላቸው ሁኔታ ብቻ እንድንወስን በማድረጉ የነገሮችን ውስጣዊ ምንነት በተለይም እንቅስቃሴያቸውንና አዲስ ሁኔታ የመፍጠር ኃይላቸውን እንድንዘነጋ የሚገፋፋ ሥነ ዕውቀት ነው።

(ምክኑያዊነትን ፣ ሂዩምን ፣ በርክሌይን ፣ ኢታዋቂነትን ፣ ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀትን ይመለከቷል ።)

## ዳርዊኒዝም
*(Darwinism)*

የሕያውን ዓለም ታሪካዊ ዕድገት ወይም የሥነ ሕይወትን ዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሐሳብ ባፈለቀውና የሰው ልጅ ከሰው መሰል እንስሳት የተገኘ ለመሆኑ ሳይንሳዊ ማረጋገጫ ባቀረበው እንግሊዛዊ የተፈጥሮ ሳይንቲስት በቻርለስ ዳርዊን ስም የተሰየመ አስተምህሮ ነው ።

የዳርዊን የሥነ ፍጥረት ንድፈ ሐሳብ ባጠቃላይ "ተፈጥሮአዊ ማጣሪያ" እና "ስህልውና መታገል" በሚሉ ጽንሰ ሐሳቦች ላይ የተመሠረተ ነው ። ዳርዊኒዝም ማንኛውንም ተፈጥሮአዊ ሆነ ማኅበራዊ ነገርና ክስተት ከእነዚህ ጽንሰ ሐሳቦች አንፃር ለመመርመር የሚያደረገውን ጥረት የሚገልጽ አስተምህሮ ነው ። አስተምህሮው የሰውን ልጅ የተፈጥሮ ዕድገት ከፍተኛ ውጤት አድርጐ በመውሰድ ባሕርያቱንና ጠባያቱን ከተፈጥሮአዊ ምንጭ አንፃር ለመተንተን የሚሻ ነው ። ዳርዊኒዝም በሰውና በተፈጥሮ አንድነት ላይ ትኩረት የሚሰጥ የቅድመ ማርክሳዊ ቁስአካልነትን ዓይነተኛ ባሕርይ የሚገልጽ ንድፈ ሐሳብ ነው።

ዳርዊኒዝም የሰው ልጅ ከእንስሳት የመጣ መሆኑን ቢገልጽም የሰውን ልጅ ከእንስሳው ዓለም ሊለየው ያስቻለውን ማኅበራዊ መንሥኤ አላመለከተም ። በዚህ ሽግግር ውስጥ በተለይ ሥራ የነበረውን ሚናና በኋላም ሥራ ተፈጥሮንም ሆነ ሰውን ራሱን ለመለወጥ የሚኖረውን ቦታ አልገለጸም ።

(ዳርዊንን ፣ ይመለከቷል ።)

## ዳርዊን ፣ ቻርለስ ሮበርት
*(Darwin, Charles Robert)*

ከ1809—1882 የኖረ ፣ በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ የተማረ እንግሊዛዊ የተፈጥሮ ሳይንስ ሊቅ ነው ።

ዳርዊን ከ1831—1836 በዓለም ዙሪያ በመርከብ በመጓዝ በጂኦሎጂ ፣ በፕላንቶሎጂ፣ በአንትሮፖሎጂና በኢትኖሎጂ ብዙ ምርምሮችን አካሒዷል ። በወቅቱ የነበሩትን የተፈጥሮ ሳይንስ ግኝቶች ከራሱ የጥናት ውጤቶች ጋር በማጣመር የዝግመተ ለውጥን ንድፈ ሐሳብ ቀምሯል ። "ዘ ኦርጅን ኦቭ ስፒሽስ ባይ ሚንስ ኦቭ ናቹራል ሰሌክሽን ኦር ዘ ፕሪዘርቬሽን ኦቭ ፌቨርድ ሬስስ ኢን ዘ ስትራግል ፎር ላይፍ" (1859) በተሰኘው ጽሑፉ ስለዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሐሳብ መሠረታዊ አስተሳሰቦችን አስፍሯል ።እንዲሁም "ዘ ቫሪየሽን ኦቭ አኒማልስ ኤንድ ፕላንትስ አንደር ዶሜስቲኬሽን" በሚለው

በ1868 በወጣው ጽሑፍ በሰው ሠራሽ ማጣሪያ የለማዳ እንስሳትንና የዕፀዋትን አመጣጥ በሰፊው ገልጿል ። "ዘ ዲሰንት ኦቭ ማን ኤንድ ሴሌክሽን ኢን ሪሌሽን ቱ ሴክስ" በተሰኘው በ1871 በወጣው ጽሑፍ የሰው ልጅ ከእንስሳት እንዴት እንደመጣ ሳይንሳዊ ማብራሪያ አቅርቧል ፤ ይሁን እንጂ የሰው ልጅ ከእንስሳት የሚለይበት ማኅበራዊ ምክንያት ሥራው ፥ ቋንቋውና አኗኗሩ መሆኑን በመግለጽ የተሟላ ሳይንሳዊ መደምደሚያ የሰጠው ኤንግልስ ነው ።

ዳርዊን ቁስአካላዊ አመለካከት የነበረው ፥ ግብታዊ ዲያሌክቲክስን የሚያራምድና ኢአማኒ ነበር ። ይህ አቋሙ ከአንዳንድ የቡርጂ አስተሳሰቦች የጸዳ ባይሆንም ሥራው በሥነ ሕይወት መስክ ለሳይንሳዊ ምርምር በር ከፍቷል ። በተጨማሪም በሐሳባዊነት ፥ በሥነ መለኮትና በዲበ አካል ላይ ለሚደረገው ትግል አስተዋጽኦ ከማበርከቱም በላይ የተፈጥሮ ሳይንስ በዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ላይ እንዲመሠረት ረድቷል ።

(ዳርዊኒዝምን ፥ ማኅበራዊ ዳርዊኒዝምን ይመለከቷል።)

## ዳበረ ሶሻሊዝም (የ—)
*(Developed Socialism)*

ከአንድ የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ደረጃ ወደ ሌላው የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ደረጃ የሚደረገው ሽግግር በቁሳዊ ምርት ፥ በኢኮኖሚ ሥርዓትና በማኅበራዊ ፖለቲካዊ ሥርዓት ከሚታየው የለውጥ ዕድገት ጋር የተያያዘ ነው ። በመሆኑም የዳበረ ሶሻሊዝም ዕድገት ውስብስብ ነው ። በዚህ እንፃራዊ በሆነ መንገድ ሲታይ ረጅም ጊዜ በሚወስደው የዳበረ ሶሻሊዝም ግንባታ ወቅት የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ዕድገት ዋስትና የተረጋገጠ ይሆናል ። የኮሚኒዝም ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረትም ይጣላል ።

የዳበረ ሶሻሊስት ኅብረተሰብ የሚታወቅባቸው ባሕርያት ሶሻሊዝም በሚያጐናፅፋቸው ሰፊ ጥቅሞች መሠረት የሳይንስና የቴክኖሎጂ ግኝቶች ከሶሻሊስት ኢኮኖሚ ሥርዓት ጋር በማያቋርጥ ሁኔታ እንዲቀናጁ መደረጉ ነው ። እንዳንድ የዳበሩ የሶሻሊዝም ገፅታዎች ከመጀመሪያው የሚታዩ ሲሆኑ ሌሎቹ ቀስ በቀስ ብቅ ብቅ የሚሉ ናቸው ።

ከዳበረ ሶሻሊዝም ጋር የተያያዙ ብዙ ሂደቶች አሉ ። በኢኮኖሚው መስክ ማኅበራዊ ምርት በከፍተኛ ደረጃ ያድጋል ፤ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ግኝቶች በምርት ሥራ ላይ ይውላሉ ፤ ከፍ ወደአለ የተስፋፋ እርባታም ሽግግር ይደረጋል ። በማኅበራዊ ይዞታና በጠቅላላ የምርት ግንኙነት በኩልም ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ይታያል ። ብሔራዊ ገቢ የኅብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ ለማሳደግና የያንዳንዱ ግለሰብ ዕድገት ከፍ እንዲል ለማድረግ በሚያስችል ሁኔታ ይመደባል ።

በማኅበራዊ ፖለቲካ በኩል የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት ወደ መላው ሕዝብ መንግሥትነት ይለወጣል ፤ የብሔሮችና የብሔረሰቦች የተሟላ እኩልነት ይስፍናል ፤ ማኅበራዊ ዲሞክራሲ በከፍተኛ ደረጃ ያድጋል ፤ ሠራተኛው ሕዝብ በኢንዱስትሪና በሕዝብ ጉዳዮች ላይ በሰፊው ይሳተፋል ።

በባህል ረገድም የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ርዕዮተዓለም የበላይነት ሙሉ በሙሉ ይረጋገጣል ፤ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ለሁሉም ዜጎች ይሰጣል ፤ ባህልና ሥነጥበብ ያብባሉ ።

ሶሻሊዝም እያደገና እየዳበረ በሄደ መጠን ወደ ከፍተኛው ማለትም ወደ ኮሚኒዝም ደረጃ ለመሸጋገር የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች ቅርፅ ይይዛሉ ።

(ሶሻሊዝምን ፥ ኮሚኒዝምን ይመለከቷል ።)

## ዴታንት
*(Détente)*

በካፒታሊስትና በሶሻሊስት ሀገሮች መካከል በልዩ ልዩ መስክ ግንኙነትንና ትብብርን ለማጠናከር ፥ መንግሥታዊ ግንኙነትን ለማሻሻልና ውጥረትን ለማርገብ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚደረግ ጥረት ነው ።

የዴታንት ፖሊሲ በ1960ዎቹ መጨረሻ ገደማ የተጀመረ በሁሉቱም ስልተ ምርት ጉራዎች የሚገኙ ሀገሮች ምንም እንኳ መሠረታዊ ቅራኔ ያላቸውና እንዱ ሌላውን ለማ

ዳከምና ለማሸነፍ መጣሩ የማይቀር ቢሆንም፣ አሁን ባለንበት የኒውክሌር ዘመን በቀጥታ መጋፈጥ ለማንም የማይበጅና እልቂት የሚፈጥር መሆኑን በመገንዘብ በተለያዩ መንገዶች በመቻቻል ትብብራቸውን እንዲያጠናከሩ ፣ በዚህም ሳቢያ ከመተማመን ደረጃ ላይ ሲደርሱ የጦር መሣሪያ ቅነሣ እንዲያደርጉ የሚያበረታታ የፖለቲካ ፈር ነው ። ፖሊሲው ተግባራዊ እንዲሆን ተቀዳሚ አስተዋጽኦ ያደረጉት የቀዝቃዛው ጦርነት ፖለቲካ በሕዝቦች ግንኙነት ላይ ያስከተለውን ጉዳት የተገነዘቡ የሶሻሊስትና የካፒታሊስት ሀገሮች ተራማጅ ኃይሎች ናቸው ። የዴታንት ፖሊሲ በሥራ ላይ መዋል ሕዝቦች የቀረበ ግንኙነትን እንዲመሠርቱና እንዲያዳብሩ ፣ በመካከላቸው በእኩልነትና በመከባበር ላይ የተመሠረተ ግንኙነት እንዲኖርና የብሔራዊ አርነት ኃይሎች እንዲጠናከሩ እገዛ አድርጓል ። ዴታንት በዓላማው ከሌኒናዊው በሰላም አብሮ የመኖር መርህ ጋር ተመሳሳይ ነው ።

(በሰላም አብሮ የመኖር መርህን ይመለከቷል።)

## ዴካርት ፣ ረኔ
*(Descartes, René)*

ከ1596—1650 የኖረ በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ ታላቅ አስተዋጽኦ ያደረገ ፣ በማቲማቲክስና በፊዚክስ ግኝቶችን ያበረከተ የፈረንሳይ ሐሳባዊ ፈላስፋ ነው ። የዴካርት ፍልስፍና የተመራበት መሠረታዊ ሐሳብ ሁለታዊነት ሲሆን ይህም ፍልስፍና የተገለጸው "ዲስኩር ዶ ላ ሜቶድ" "ሌ ሜዲታሲዮን" "ፕሪንሲፕ ዶ ላ ፊሎሶፊ" በተባሉት ዓበይት ጽሑፎች ውስጥ ነው ።

(ካርቴዚያኒዝም ይመለከቷል ።)

## ድምፅን በድምፅ የመሻር ሥልጣን
*(Veto Power)*

ድምፅን በድምፅ የመጣል ወይም ውድቅ የማድረግ መብት ነው ። ይህ ቃል በሰፊው የሚሠራበት በተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ውስጥ ሲሆን የሚጠቀሙበትም የድርጅቱ ቋሚ አባላት ማለትም ሶቭዬት ኅብረት ፣ አሜሪካ ፣ ፈረንሳይ ፣ እንግሊዝና ቻይና ናቸው ። እነዚህ ቋሚ አባላት እያንዳንዳቸው ድምፅን በድምፅ የመሻር መብታቸውን የሚጠቀሙበት የፀጥታውን ምክር ቤት ሥነ ሥርዓት የሚመለከቱ ባልሆኑ ጉዳዮች ማለትም ከበድ ባሉ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ እንዳይሰጥ ለማገድ በሚፈልጉበት ጊዜ ነው ።

በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ላይ እንደሰፈረው ድርጅቱ በሁሉም አባላት የእኩልነት መርህ ላይ የተመሠረተ ነው ቢባልም በቋሚ መቀመጫዎች ድልድል እምስቱ ሀገሮች ልዩ መብት አግኝተዋል ። እነዚህ ሀገሮች ይህን ልዩ መብት ሊያጡ የሚችሉት ቻርተሩ ሲሻሻል ብቻ ነው ። ይህም ራሱ የፀጥታውን ምክር ቤት ስምምነት መጠየቁ አይቀርም ።

(የተባበሩት መንግሥታት ፀጥታ ምክር ቤትን ይመለከቷል።)

## ድራት
*(Boom)*

በካፒታሊስታዊ የማምረት ሥርዓት ውስጥ አንድ የኢኮኖሚ ቀውስ ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ የሚቀጥለው የኢኮኖሚ ቀውስ እስከሚጀምርበት ጊዜ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ከሚገኙ አራት ልዩ ልዩ የኢንዱስትሪ ዑደት ደረጃዎች መካከል የመጨረሻው ድራት ይባላል ። በዚህ ደረጃ ቀውሱ ከመጀመሩ በፊት ተደርሶበት ከነበረው የበለጠ ምርት ይመረታል ። ካፒታሊስቶች ትርፍ ለማካበት በሚያደርጉት መሯሯጥ ምርት በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ ያደርጋሉ ። ለንግድና ለብድር ካፒታል ያለው ፍላጐት ያድጋል ። ሸቀጣ ሸቀጦች በብዛት ተመርተው ገበያውን ያጥለቀልቁታል ።

ሆኖም የሸቀጣ ሸቀጦች ምርት ከሠራተኛው ሕዝብ የመግዛት ኃይል ጋር የማይመጣጠን ከፍተኛ ዕድገት ማሳየቱን እንደገና ይጀምራል ። የበላጥ ምርት መጠን እያደገ ሄዶ በመጋዘን ውስጥ ይከማቻል ። ኋላም በዚሁ ደረጃ ሸማች አጥተው በገበያ ውስጥ የተከማቹ የሸቀጣ ሸቀጦች መጠን ከፍተኛ መሆኑ ግልጽ እየሆነ ይመጣል ። ከዚህ በኋላ

ካፒታሊስቶች በመካከላቸው የሚያደርጉትን ውድድር ያከሩና የሸቀጣ ሸቀጦች ዋጋ እንዲቀነስ ያደርጋሉ ። ይህም ወደሚቀጥለው ቀውስ ያመራል ። በዚህ አኳኋን የኢንዱስትሪ ዑደት እንደገና ይጀምራል ።

(የኢኮኖሚ ቀውስን ፣ ግገማን ፣ ቀውስን ይመለከቷል ።)

## ድርድር
*(Compromise)*

አንድ ወገን ወይም አንድ የፖለቲካ ቡድን ከሌላ ወገን ወይም የፖለቲካ ቡድን ጋር በተጨባጭ ሁኔታዎች አስገዳጅነት ካሉት ጥቅሞች ወይም ከሚታገልላቸው ጥያቄዎች አንዳንዶቹን በመተው የሚያደርገው ስምምነት ነው ። ኮሚኒስቶች በምንም ዓይነት በመሠረታዊ ዓላማ ወይም ጥያቄ ላይ አይደራደሩም ። ይህን የሚያደርጉ ጠጋኞች ናቸው ።

መርህን አሳልፎ የማይሰጥ ድርድር ተገቢና ሊቀርም የማይችል ነው ። ይህም ሲሆን መደራደር የሚቻለው እንድን የተወሰነን ከፍል ወይም ክልል የሚመለከቱ ጥያቄዎችን ወይም ከወቅቱ አጣዳፊ ጥያቄዎች አንዳንዶቹን በመተው ነው ። ኮሚኒስቶች የዚህ ዓይነቱን ድርድር ከገለልተኛ ወገኖችና ከጠላት ኃይሎችም ጋር የሚያደርጉት በተጨባጭ ሁኔታዎች አስገዳጅነት ሲሆን ግባቸውም የሠራተኛውን ንቅናቄና ሶሻሊስት ዓላማቸውን ለመጠበቅና ለማጠናከር ነው ።

ድርድር ለማድረግ የሚያስገድድ ሁኔታ ሲደርስ በምንም ዓይነት መንገድ በአድርባይ ክህደት መርህ እንዳይሸጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግና ነቅቶ መጠበቅ ያስፈልጋል ። ስለዚህ በተጨባጭ ሁኔታዎች አስገዳጅነት በሚደረጉ ድርድሮችና በአድርባይነት የሠራተኛውን መደብና የመላውን ሠርቶ አደር ሕዝብ መሠረታዊ ዓላማና ፍላጐት በጥቅም በመሸጥ በሚደረጉ ድርድሮች መካከል ያለውን ልዩነት በአንክሮ ማጤን ይገባል ።

## ድርጅት
*(Organization)*

ሰዎች አንድ የጋራ ዓላማን ወይም ተግባርን ከግብ ለማድረስ በተወሰነ ደንብና ፕሮግራም ዕውቀታቸውን ፣ ጉልበታቸውን ፣ ገንዘብና ሌላውንም ቁሳዊ ሀብታቸውን መልከና ሥርዓት ባለው መንገድ በማስተባበርና በማቀናጀት በአንድ ላይ ተሰባስበው የሚመሠርቱት ማኀበር ወይም ኅብረት ነው ። በዚህ መሠረት ድርጅት ከአጠቃላይ የመዋቅር ይዘት የተነሣ በውስጡ ያሉት አካሎችና ግለሰቦች ግንኙነታቸውን የሚያስተባብሩበትንና የሚያቀናጁበትን ውስጣዊ ሥርዓትና ግንኙነቱም ይበልጥ እየዳበረና እያደገ ወደ ላቀ ደረጃ የሚሸጋገርበትን አጠቃላይ ሂደት ያመለክታል ።

የድርጅት ጽንሰ ሐሳብ ሥነ ሕይወታዊ ቅንብሮችን ፣ ማኀበራዊ ቅንጅቶችንና ቴክኒካዊ አቋሞችን ያጠቃልላል ። በመሠረቱ ሁለት ዓበይት ነገሮችን ያቀፈ ሲሆን እነሱም መዋቅርና ሥርዓት ናቸው ። በድርጅት ውስጥ ሥርዓት የውስጣዊ ሕግጋትን ተጨባጭ ባሕርይ ፣ የውስጣዊ አካላቱን መዋቅራዊ ውህደትና መስተጋብር እንዲሁም የዓላማንና የተግባርን መጣጣም ያረጋግጣል ። የሥነ ሕይወት ቅንብርን በሚመለከት ረገድ ሕዋስ እንደመጀመሪያው ደረጃ ድርጅታዊ ቅንብር ሆኖ ሊቆጠር ይችላል ። ሰፋ ባለ ትርጓሜው ማኀበራዊ ድርጅት የግለሰቦችና የማኀበራዊ ቡድኖች ተግባር የሚመራበትንና የሚታዘዝበትን ሁኔታ ያመለክታል ። በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት በየዘርፉና በየደረጃው የሚያቅፉት የማኀበራዊ ድርጅቶች ቅንጅታዊ አሠራር ወይም ስልት የግለሰብ ተግባር ወይም ክንውን በማኀበራዊ ሥርዓት ቁጥጥር የሚደረግበት መሆኑን ያረጋግጣል ።

ቤተሰብ ቀላሉና አነስተኛው ማኀበራዊ ድርጅት ነው ማለት ይቻላል ። በዚህ አጠቃላይ መግለጫ ሥር ማናቸውንም ዓይነት ማኀበራዊና ቴክኒካዊ ድርጅት ማስቀመጥ

ይቻላል ። ለምሳሌ ፋብሪካዎች ፣ ትምህርት ቤቶች ፣ ሐኪም ቤቶች ፣ ወታደራዊ ክፍሎች ፣ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ፣ መንግሥት ፣ ነፃ አውጭ ግንባሮች ፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ፣ የሙያ ማኅበራት ወዘተ... ለተለያዩ ዓላማዎች የተመሠረቱና የሚመሠረቱ ድርጅቶች ናቸው ። የድርጅቱ መዋቅርና ሥርዓትም እንደዓላማውና እንደ ተግባሩ ይለያያል ።

## ዶሚኒየን
*(Dominion)*

ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርና ነፃ የሆነ የእንግሊዝ ኮሙንዌልዝ አባል ሀገር መጠሪያ ነው ። ሆኖም ይህ ስያሜ የቀድሞውን የእንግሊዝን ተፅዕኖ የሚያንፀባርቅ ሆኖ በመታየቱ ከጥቅም ውጭ እየሆነ መጥቷል ። ከራሷ ከእንግሊዝ ሌላ በርካታ የኮመንዌልዝ አባል ሀገሮች ቢኖሩም አብዛኛዎቹ በዚህ ስም አይጠሩም ።

# ጀ

## ጀምስ ፣ ዊሊያም
*(James, William)*

ከ1842—1910 የኖረ ፣ የገቢራዊነት ፍልስፍና ዋንኛ አራማጅ ፣ የሥነ ልቡና ሊቅና ቁስአካልነትን አጥብቆ የተቃወመ አሜሪካዊ ሐሳባዊ ፈላስፋ ነው ። ጀምስ ዲበ አካላዊ የአጠናን ዘዴን የተቃወመ ቢሆንም በምትኩ ያንፀባረቀው ኢምክኑያዊነትን ነበር ። አእምሮን ሲያጠናም ፈቃድና ስሜት ወሳኝ ኃይል እንደሆኑ በመቁጠር ነው ።

ጀምስ የገቢራዊነትን መርሀ ከጠቀሜታ አንፃር በመመልከትና የእውነት መለኪያም ጠቀሜታ እንደሆነ አድርጐ በመቁጠር ማንኛውንም ነገር ጠቃሚ ሆኖ እስከአገኘነው ድረስ ያለአመክንዮና ያለማረጋገጫ ልንቀበለው እንችላለን ይላል ። ይህም አመለካከት ዕውቀትን ከነባራዊነት በመነጠል ወደ ተራ እምነት ዝቅ ለማድረግ በመሞከሩ ለሃይማኖት ድጋፍ ሰጥቷል ። በነበረው የዳሳሽነት አቋም የተነሣ እውነታን ወደ ኅሊናዊ ክስተት ዝቅ አድርጓል ። ቁስአካልና መንፈስ የምንላቸው የልምድ ሁለት ገጽታዎች ናቸው በማለት ገለልተኛ የሆነ የአንዳዊነት አቋም ለመያዝ ሞክሯል ።

ጀምስ እነዚህን አመለካከቶቹን "ፕሪንስፕል ኦቭ ሳይኮሎጂ"፣ "ዘ ቫራይቲስ ኦቭ ሪሊጅየስ ኤክስፔርየንስ" እና "ፕራግማቲዝም" በተሰኙት ሥራዎቹ አንፀባርቋል ።

(ገቢራዊነትን ይመለከቷል ።)

## ጀርመን ወይም "እውነተኛው" ሶሻሊዝም (የ—)
*(German or "True" Socialism)*

ወገናዊነትንና ፀረ ቡርዧ ትግልን ይገልጽ የነበረው የፈረንሳይ ሶሻሊስታዊና ኮሚኒስታዊ ሥነ ጽሑፍ በጊዜው በነበሩ የጀርመን ፈላስፎች ከፋኛ ተኮላሽቶ የጀርመን ወይም "እውነተኛው" ሶሻሊዝም የሚለውን ስያሜ በመያዝ የአድኃርያንን ጥቅም የሚያንፀባርቅ አመለካከት ነው ። የፈረንሳይ ሶሻሊስትና ኮሚኒስት ሥነ ጽሑፍ የተጀመረው ቡርዧዚው ሥልጣን ይዞ በተደላደለበት ወቅት ሲሆን ዓላማውም የቡርዧዚውን ሥልጣን በመቃወም የሚደረገውን ትግል ማስተጋባት ነበር ። ይህ ሥነ ጽሑፍ ወደ ጀርመን የተሻገረው ገና የጀርመኑ ቡርዧዚ ከፊውዳሉ ፍጹማዊነት ጋር መፎካከር እንደጀመረ ነበር ።

የጀርመን ፈላስፎች የፈረንሳይንና የጀርመንን ማኅበራዊ ሁኔታ ልዩነት ሳይገነዘቡ ይህን ሥነ ጽሑፍ የሙጥኝ በማለታቸው ተግባራዊ እንዳይሆን አድርገውታል ። ፈላስፎቹ ከጥንታዊ የፍልስፍና አመለካከታቸው ሳይላቀቁ የትግል መግለጫ የነበረውን አዲሱን ሥነ ጽሑፍ ፍሬ ከርስኪ ከሆኑ መንፈሳዊ አስተሳሰቦች ጋር አዋሃዱት ፤ አንዳንድ ሐረጎችንም በማውጣት የራሳቸውን አስተሳሰብ አከሉበት ። የወዝአደሩን ፍላጐት ሳይሆን ከየትኛውም መደብ የሌለ በፍልስፍና ጭጋግ ውስጥ የታያቸውን በቅዠት የፈጠሩትን ሰው እንደሚወክል አድርገው አቀረቡት። ይህ የተኮላሸ አመለካከት ለጀርመኖች የሰውን "እውነተኛ" ፍላጐት የሚያንፀባርቅ ስለመሰላቸው "እውነተኛው" ሶሻሊዝም ይህ ብቻ ነው ብለው አስፋፉት ።

"እውነተኛው" ሶሻሊዝም የቡርዧዚውን ንቅናቄ ለሚፃረሩ የፊውዳል ፈላጭ ቆራጮችና ግብዝ ንዑስ ከበርቴዎች መሣሪያ በመሆን አገለገለ ። ንዑስ ከበርቴው የቡርዧዚውን ጭቆና የሚቃወምና የወዝአደሩንም አምባገነንነት የሚፈራ በመሆኑ የጀርመን ሶሻሊዝምም ከነዚህ ከሁለቱ አደጋዎች የሚያድነው መስሎ ስለታየው አስፋፋው ። ፍልስፍናውም በበኩሉ የግብዝ ንዑስ ከበርቴ ጠንካራ ወኪል መሆኑን ኮሚኒዝምን በቀጥታ እንደሚቃወምና ለመደብ ትግሉም ያለውን የማያወላውል ጥላቻ በማወጅ አስመሰከረ ።

## ጀርመን ብሉይ ፍልስፍና (የ–)
*(The German Classical Philosophy)*

ከ18ኛው እስከ 19ኛው ምዕት ዓመት የመጀመሪያ አጋማሽ ድረስ በጀርመን ተስፋፍቶና ገንኖ የነበረው ፍልስፍና የጀርመን ብሉይ ፍልስፍና በመባል ይታወቃል ። በካንት ፣ በፊሽተ ፣ በሼሊንግና በሄግል የተገነባውና የተስፋፋው የዚህ ፍልስፍና ክፍል ሐሳባዊ ፍልስፍና ሲሆን ይህም ኅሊናዊውንና ነባራዊውን የሐሳባዊ ፍልስፍና ክፍሎች ያጠቃልላል ። ይህን ሐሳባዊ ፍልስፍና ከከፍተኛ ደረጃ ያደረሰው ሄግል ሲሆን እርሱም በወቅቱ ገንኖ የነበረውን ተናክእታዊና ዲበ አካላዊ ቁስአካላዊ ፍልስፍናን በመቃገልና በዲያሌክቲክስ የምርምርና የአስተሳሰብ ዘዴ በመጠቀም ዲያሌክቲክስ እንዲያድግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ። ሆኖም የሄግል ዲያሌክቲክስ ፍጹም ሐሳባዊ ነበር ።

በዚህ ዘመን ውስጥ በእንግሊዝ የኢንዱስትሪ አብዮት መካሄድ ፣ የሳይንሳዊ ዕውቀት መዳበርና የካፒታሊዝም ማደግ ለቁስአካላዊ ፍልስፍና ዕድገት አመች ሁኔታዎችን ፈጥሮአል ። በፈረንሳይ ውስጥ ደግሞ የአብራሆያን ፍልስፍና ለፈረንሳይ የቡርዧ አብዮት ርዕዮተዓለማዊ መሠረት ጥሎ ለቡርዧው አብዮት መካሄድና ለካፒታሊዝም ማደግ አስተዋጽኦ አበርክቷል ። ይህም ለቁስአካላዊ ፍልስፍና ዕድገት የሚረዱ ሁኔታዎችን ፈጥሮአል ። በጀርመን ውስጥ ግን ፊውዳሊዝም ተጠናክሮ ጀርመን ተከፋፍላ የነበረችበትና ቡርዧዚውም ደካማ የነበረበት ወቅት ነበር ። ካርል ማርክስ እንዳለው በዚህ ወቅት በፈረንሳይና በእንግሊዝ ውስጥ ተግባራዊ ትግልና ለውጥ ሲካሄድ የጀርመን ፈላስፎች በሌላ ሁኔታ ተመስጠውና በሐሳብ ክልል ውስጥ ተወስነው በአውጠንጣኝ ፍልስፍና የተጠመዱበት ጊዜ ነበር ። ይህም የወቅቱን የጀርመንን ፍልስፍና ሐሳባዊና ለቁስአካላዊ ፍልስፍና ዕድገት ከፍተኛ ዕንቅፋት እንዲሆን አድርጓል ።

ሌላው በብሉይ የጀርመን ፍልስፍና ሥር የሚጠቃለለው የፎየርባኽ ቁስአካላዊ ፍልስፍና ነው ። ፎየርባኽ ሐሳባዊ ፍልስፍናን ባጠቃላይ ፣ የሄግልን ሐሳባዊ ፍልስፍና በተለይ በመቃገል ቁስአካላዊ ፍልስፍናን ከሐሳባዊነት በማላቀቅ እንዲያንሰራራና እንዲጠናከር አድርጓል ። ይህም ሆኖ የፎየርባኽ ቁስአካልነት የዲበ አካላዊነት ደካማ ጐን ነበረው ።

ማርክስና ኢንግልስ የፎየርባኽን ቁስአካልነትና የሄግልን ዲያሌክቲክስ ከድክመታቸውና ከስህተታቸው በማጽዳት ሳይንሳዊውን የቁስአካላዊ ዲያሌክቲክስን ፍልስፍና አቀነባበሩ ። ስለሆነም ብሉይ የጀርመን ፍልስፍና ለማርክሳዊ ፍልስፍና እውን መሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

(ካንትን ፣ ፊሽተን ፣ ሼሊንግን፣ሄግልን ፣ ፎየርባኽን ይመለከቷል ።)

## ጀብደኝነት
*(Adventurism)*

ተጨባጭ ሁኔታዎች በሚገባ ሳይጤኑ አስፈላጊ ያልሆኑ ችኩል እርምጃዎችን የመውሰድ ወይም በውል ያልተጠኑ የኃይል እርምጃዎች እንዲወሰዱ የመገፋፋት እፍራሽ አዝማሚያ ነው ። በተለይ በመደብ ትግል ሂደት ውስጥ ጀብደኝነት በዘፈቀደና በስሜት ብቻ በመዋዋ የሚወሰድ እቋም በመሆኑ እጅግ አደገኛ ከመሆኑም በላይ የተስተዋለንና የተቀነባበረን አብዮታዊ የትግል ስልት ይፃረራል ።

ጀብደኝነት የሰፊውን ሕዝብ የቅርብና የሩቅ ጊዜ ግቦች በትክክል ያገናዘበ ባለመሆኑ በረጅም የትግል ሂደት ውስጥ ሊገኝ የሚችለውን ድል በፍላጐት ብቻ በመገፋፋት ዛሬውኑ ለማከናወን ያልማል ። በዚህም ሰፊውን ሕዝብ ጥምር ወቅቱና ሁኔታው ባልፈቀደው ፍልሚያ ውስጥ በመዝፈቅ ለጥፋት የሚዳርግና አብዮታዊ እንቅስቃሴንም በአድኃርያን የሚያስመታ በመሆኑ ኮሚኒስቶች በጽኑ ይታገሉታል ።

(ፀኮይዝምን ፣ አድርባይነትን ይመለከቷል ።)

## ጁንታ
*(Junta)*

አብዮታዊ ሁኔታ ሳይኖር በግብታዊም ሆነ በተደራጀ የሕዝብ አመፅ ሳይደገፉ በሥ

ልጣን ጥማት በመቀስቀስ ፥ ጥቂት ግለሰቦች አብዛኛውን ጊዜ በወታደራዊ ኃይል መፈን ቅለ አገዛዝ በማካሔድ ሥልጣን የሚይዝ ቡድን ጁንታ ይባላል ። ጁንታዉ ሥልጣን ሲይዝ ከሚወስዳቸው እርምጃዎች ውስጥ ፥ ነባሩን ሕገ መንግሥት ማገድ ፥ የቀድሞ አገዛዝ መሪዎችን ማስወገድና በልዩ ፍርድ ቤት ማቅረብ ወዘተ... ዋነኞቹ ናቸው ። በነዚህና በሌሎችም ድንጋጌዎች የሥልጣ ኑን ዕድሜ ያራዝማል ፤ ተቃዋሚዎቹን ያጠፋል ።

የጁንታ አባሎች ሥልጣን እንደያዙ ተቀባይነት ለማግኘት በወቅቱ አንገብጋቢ የሆኑትን የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ጥያቄዎች ቀድመው በማንሣት መፈክሮችን ያስተጋባሉ ። አንዳንድ ለጊዜው ጠቃሚ መስለው የሚታዩ እርምጃዎችንም ይወስዳሉ ። ነገር ግን አብዛ ኛውን ጊዜ የገዥ መደብ አባሎችና የቡር ዧው መደብ አቀንቃኞች በመሆናቸው በዘለቄታው ለሕዝብ ጥቅም የቆሙ አይ ደሉም ። ይልቁንም "ሕግንና ሥርዓትን ለማ ስከበር" በሚል ሽፋን የሠራተኛውን መደብ እንቅስቃሴ ያፍናሉ ። መሪዎቹንም የኮሚኒስት ወኪሎች በማለት ያስሯቸዋል ፤ ይገሏቸዋል።

ጁንታዎች አብዛኛውን ጊዜ የሥልጣን ዕድሜያቸውን ለማራዘም ከሁሉ በፊት የብ ሔራዊ የሞራልና የባህል ፋይዳዎች እንዲከ በሩ በሚል ሽፋን ብሔረተኝነትን ይቀሰቅ ሳሉ ። የኅብረተሰቡን በመደብ መከፋፈል በመካድም ሁሉንም ዜጐች በእነዚህ ፋይዳዎች ዙሪያ በአንድ ሁልአቀፍ በሆነ ድርጅታዊ መዋቅር ለማሰባሰብና ለመምራት ፥ ሕዝ ቡም በታዛዥነትና በጭፍን እንዲከተላቸው ለማድረግ ይጥራሉ ። ይህ ሁኔታ እየገፋ ሄዶ በሚስፋፋበት ጊዜና በሁለገብ ባሕርይው አምባገነን ሲሆን ወደ ፋሺዝም ያመራል ።

(ፋሺዝምን ፥ አብዮታዊ ሁኔታን ፥ ሕዝባዊ አመፅን ይመለከቷል ።)

## ጆቮንስ ፥ ዊልያም ስታንሊ
*(Jevons, William Stanley)*

ከ1835–1882 የኖረ እንግሊዛዊ ቡርዧ ኢኮኖሚስት ፥ ስታትስቲሺያንና ፈላስፋ ነበር ። ጆቮንስ በማንቼስተርና (1866—76) በለንደን (1876—80) የሥነ አመክንዮ ፥ የፍ ልስፍናና የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ፕሮፌሰር ሆኖ ሠርቷል ።

ጆቮንስ በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ጥናት ውስጥ የማቲማቲክስ ዘዴን በስፋት መጠ ቀም ከጀመሩት ቡርዧ ኢኮኖሚስቶች መካ ከል አንዱ ነው ።

ጆቮንስ ከጽሑፎቹ ውስጥ በበለጠ የታወ ቀለት በ1871 የታተመው "ዘ ቲየሪ ኦቭ ፖለቲካል ኢኮኖሚ" የተሰኘው መጽሐፍ ነው ። የተጨማሪ እርካታ ንድፈ ሐሳብ በመባል በቡርዧ ኢኮኖሚክስ የታወቀው ንድፈ ሐሳብ መሥራች ከሆኑት ኢኮኖሚስቶች አንዱ የሆ ነው ጆቮንስ ፥ የፍላጐትን ጥናት በተጨማሪ የእርካታ ማሽቆልቆል ሕግ ላይ በመመሥ ረትና እሴትን በተጨማሪ እርካታ ንድፈ ሐሳብ ለማስረዳት በመሞከር ማርክሳዊውን የእሴት ሥራ ንድፈ ሐሳብ የሚቃረን ኢሳይንሳዊና የቡርዧ ርዕዮተዓለም አንፀባራቂ የሆነ አስተ ሳሰብ ሰንዝሯል ። ኤንግልስም ከጆቮንስ ጠ ባብ አስተሳሰብ በመነሣት ይህንኑ የቡርዧ ንድፈ ሐሳብ "የበሰበሰና ግልብ" ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በማለት ገልጾታል ።

## ጅምላ ንግድ (የ—)
*(Wholesale Trade)*

የአንድ ሀገር የውስጥ ንግድ አንድ አካል ሲሆን ሸቀጦች ከአምራች ድር ጅቶች ወደችርቻሮ ድርጅቶች የሚተላለፉ በት ወይም የማምረቻ ዕቃዎች ከተመረ ቱበት ስፍራ ለምርት ሥራ ወደሚጠቀ ሙባቸው የኢንዱስትሪ ድርጅቶች የሚዘዋወሩ በት የንግድ ክፍል ነው ። ለምሳሌ ስኳር አምራች ድርጅት ስኳሩን ለጅምላ ነጋዴ ያቀ ርባል ፤ ጅምላ ነጋዴው ደግሞ ስኳሩን ለቸር ቻሪዎች (የችርቻሮ ድርጅቶች) ያቀርባል ፤ ወይም ደግሞ የጅምላ ነጋዴው ስኳሩን ለኢ ንዱስትሪ ሥራ ለሚጠቀሙበት ለምሳሌ ለለ ስላሳ መጠጥ አምራች ድርጅቶች ሊያቀርብ ይችላል ።

የጅምላ ንግድ የሸቀጦች ዝውውር የመጀመሪያ ደረጃ ነው ፤ ይህም ሸቀጦች ከምርት መስክ ወደ ዝውውር መስክ የሚተላለፉበት ደረጃ ነው ። በጅምላ ንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ የማምረቻ ዕቃዎች የጅምላ ንግድና የፍጆታ ሸቀጦች የጅምላ ንግድ ይገኛሉ ።

በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የጅምላ ንግድ በመሠረቱ በኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱና በንግድ ካፒታሊስቱ መካከል ያለ ንግድ ነው ፤ በተጨማሪም በንግድ ካፒታሊስቶች መካከል የሚካሄድ ንግድ ነው ። ምንም እንኳን የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቱ ዓላማ የተመረተውን ሸቀጥ በዝውውር መልክ ወደገንዘብ መለወጥን ቢጨምርም ሸቀጦች እስኪሸጡ ድረስ መጠበቁ የምርት ሂደት መቋረጥን ስለሚያስከትልና የካፒታል መገላበጥን ፍጥነት ስለሚቀንስ ሸቀጦችን ወደገንዘብ የመለወጡን ሥራ ለንግድ ቡርዧዚው ማስተላለፍን ይመርጣል ። ይህም የሥራ ክፍፍል የኢንዱስትሪ ቡርዧዚው የተወሰነውን ተረፈ እሴት ለንግድ ቡርዧዚው እንዲያካፍል ስለሚያስገድደው የጅምላ ንግድ የመሸጫ ዋጋ ከችርቻሮ ንግድ መሸጫ ዋጋ እንዲያንስ ያደርጋል ።

በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የጅምላ ንግድ የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶች በማምረቱ ተግባር ላይ በማትኮር የሥራ ክፍፍል እንዲያዳብሩ ለማድረግ ያስችላል ። የምርት ድርጅቶች ያመረቷቸውም ውጤቶች ጥቅም ላይ ወደሚውሉባቸው የኢኮኖሚ ክፍሎች በፍጥነት እንዲተላለፉ ፣ ትርፍም በፍጥነት እንዲገኝና የእርባታው ሂደት እንዲቀላጠፍ ይረዳል ። በዚህም አኳኋን የብዝበዛውን ሁኔታ በማጠናከር የካፒታሊስቶችን ገቢ ለማሳደግ ይረዳል ።

በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የጅምላ ንግድ ድርጅቶች በመንግሥት ይዞታ ሥር የሚገኙ ሲሆን ዓላማቸውም የሶሻሊስት የምርት ግንኙነትን ማጠናከር ነው ። በተለይም በክፍላተ ኢኮኖሚ መካከል ያለውን የተቀነባበረ መተሳሰር የሚያጠናክሩ ፣ የርስ በርስ ዕድገታቸውን በማቀላጠፍ አንፃር የሚሠሩ ፣ በማዕከላዊው ዕቅድ መሠረት የጥሬ ዕቃና የኢንዱስትሪ መሣሪያዎችን ለምርት ድርጅቶች የሚያቀርቡ እንዲሁም የፍጆታ ሸቀጦችን ወደችርቻሮ ድርጅቶች የሚያደርሱ ተቋሞች ናቸው ። የሶሻሊስት ጅምላ ንግድ ድርጅቶች የመሸጫ ዋጋ በምርት ውጤቶች ላይ የወጣውን ማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜና የድርጅቱንም ውጤታማነት የሚያንፀባርቅ ዋጋ ነው ።

በሽግግር ወቅት ያለው የኢኮኖሚ ይዞታ ቅይጥ እንደመሆኑ የጅምላ ንግዱም በመንግሥት ፣ በኅብረት ሥራ ማኅበራትና በግል ይዞታዎች ሥር ያለ ነው ። በተለይም ከፍተኛ የጅምላ ንግድ ድርጅቶች ቀደም ሲል በውጭ ካፒታሊስቶች የተቋቋሙና ከፍተኛም የሆኑ የራሳቸው የውስጥ አውታሮች የነበሯቸው ስለሆኑ እነዚህ በመንግሥት ይዞታ ሥር ሲመጡ አዲስ የውስጥ አደረጃጀት መሠረት ስልት እንዲከተሉ ይደረጋል ። በአዲሱ ስልት በቅልጥፍና መንቀሳቀስ እስከሚለምዱ ድረስ ብዙ ዝርዝር ችግሮች ሊከሰቱ ይችላሉ ። ከዚህም ሌላ በሽግግር ወቅት የተወሰኑ የጅምላ ንግድ ድርጅቶች በግል ይዞታ ሥር ስለሚሆኑ ከግል ይዞታው ክፍለ ኢኮኖሚ ጋር ሌሎች ልዩ ልዩ ዘርፎች በተቀነባበረ መንገድ በመመሳጠር ልዩ ልዩ አሻጥሮችን ይፈጽማሉ ። ሆኖም እነዚህን ሁኔታዎች በሽግግር ወቅት በተቀነባበሩ ልዩ ልዩ አብዮታዊ እርምጃዎች አማካይነት መቆጣጠር አስፈላጊ ነው ። ከዚህም ውስጥ በተለይ መንግሥታዊና ሕዝባዊ የጅምላ ንግድ ድርጅቶችን ማጠናከርና ማስፋፋት እንዲሁም ጥብቅ የዋጋ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ዋናዎቹ እርምጃዎች ናቸው ። በዚህ አኳኋን የመንግሥትና የኅብረት የጅምላ ንግድ ተቋሞች እየተጠናከሩ በመሄድ የግል ካፒታልን ከጅምላ ንግድ ቀስ በቀስ በማስወጣት የንግዱ ዘርፍ ሙሉ በሙሉ ሶሻሊስታዊ ፈር የሚይዝበት ሁኔታ ሊመቻች ይችላል ።

# ገ

## ገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄ (የ—)
*(Non–Aligned Movement)*

የገለልተኝነት መርህ አንድ ሀገር ከተለያዩ የጦር ጉራዎች ከአንዱም ጋር በአጋርነት ላለመሰለፍና የሀገሩንም የየብስ ፣ የጠፈር ወይም የባህር ክልል ለተፋላሚዎች መጠቀሚያ ላለማድረግ በመወሰን በአጠቃላይ ከዚህም ከዚያም አልሆንም በሚል አቋምና ለዓለም ሰላም መረጋጋት ይጠቅማል ከሚል የውጭ ፖሊሲ የመነጨ ነው ። ይህ የገለልተኝነት መርህ በዓለም አቀፍ ፖለቲካ ውስጥ እያደገ የመጣው ከሁለተኛው የኢምፔሪያሊስቶች ጦርነት ወዲህ ነው ። በተለይም በርካታ የአፍሪካ ፣ የእስያና የላቲን አሜሪካ ሀገሮች አርነታቸውን ሲያገኙ የፖለቲካ ነፃነታቸውን ከማወጅ ጋር በውጭ ፖሊሲአቸው ረገድ የገለልተኝነትን መርህ በመከተላቸው መርሁ ይበልጥ እየታወቀና የሚጠቀሙበትም ሀገሮች ቁጥር እየበዛ ሄዷል። ይህንንም መርህ የሚከተሉት ሀገሮች ገለልተኛ ሀገሮች በመባል ይታወቃሉ ።

የዚህ መርህ ሕጋዊ መሠረት እያንዳንዱ ሀገር ተገቢ መስሎ ሲያገኘው የዚህ መርህ ተከታይ መሆኑን ማወጁ ብቻ ነው ። በዚህ መልክ የአፍሪካ ፣ የእስያ ፣ የላቲን አሜሪካና በርከት ያሉ የአውሮፓ ሀገሮች የገለልተኝነት መርህ ተከታይ ናቸው ።

ምንም እንኳ ለገለልተኝነት አቋም የረዥም ጊዜ ጥረት የተደረገ ቢሆንም ፖሊሲው ተሰሚነት ያገኘው "ቀዝቃዛው ጦርነት" በተፋፋመበትና የሁለቱ ኃያላን ጉራዎች መካረር የጦርነት ሥጋትን ባጠናከረበት ወቅት ነው ። ይህንኑ የተገነዘቡ የአፍሪካና የእስያ ሀገሮች በ1955 ባንዱንግ (ኢንዶኔዥያ) ውስጥ ያደረጉት ስብሰባ እንደጥንስስ ሆኖ ሃያ አምስት ሀገሮች በ1961 የመጀመሪያውን የገለልተኛ ሀገሮች ጉባኤ በቤልግሬድ አደረጉ ። የጉባኤውም ትኩረት የሰላም መስፈን ስለነበር የሰላም ልዑካን ወደዋሽንግተንና ወደ ሞስኮ በመላክ ይህንኑ አቋሙን አሳውቋል ፤ እነሱም ለሰላም እንዲጥሩ ጥሪ አድርጓል ።

ከዚያም ሁለተኛው የገለልተኛ ሀገሮች መሪዎች ጉባኤ በ1964 በካይሮ ፣ ሦስተኛው በ1970 በሉሳካ ፣ አራተኛው ጉባኤ በ1973 በአልጀርስ ፣ አምስተኛው በ1976 በኮሎምቦ ፣ ስድስተኛው በ1979 በሃቫና እንዲሁም ሰባተኛው በ1983 በኒውዴልሂ ተደርጓል ። በነዚህም የመሪዎች ስብሰባ መካከል በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ፣ በንቅናቄው አስተባባሪ ቢሮና በሌሎችም የልማት ዘርፎች ከፍተኛ ተጠሪዎቻቸው ስብሰባዎች ተደርገው በተለያዩ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ውይይቶች ተካሂደዋል ፤ ውሳኔዎችም ተላልፈዋል ። በተለይ የሁሉም ትኩረት ያመዘነው በፀረ ቅኝ አገዛዝና በፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግሎች መጠናከር ፣ በዓለም ሰላም ፣ በሕዝቦች ደኅንነትና በሰላም አብሮ የመኖር ፖሊሲ ላይ ሲሆን ለነዚህም መከበር በጦር መሣሪያ ቅነሳና አካባቢዎችን የሰላም ቀጣና በማድረግ ረገድ ሰፊ ጥረት እንዲደረግ በማሳሰብ ላይ ነበር ።

ምንም እንኳ ገለልተኛ ሀገሮች በነዚህና በመሳሰሉት አጠቃላይ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ጉዳዮች ላይ የጋራ አቋም ቢኖራቸውም በንቅናቄው ውስጥ ሶሻሊስት የሆኑ ፣ የሶሻሊዝምን ዕድገት ጉዳና የሚከተሉ ፣ እንዲሁም ከካፒታሊስቱ ዓለም ጋር የቅርብ ግንኙነትና ተሳስሮት ያላቸው በፊውዳሊዝም ሥር የሚገኙ ሀገሮችም ጭምር ስለሚገኙ አልፎ አልፎ ውዝግብና ቅራኔም በመካከላቸው ይታያል ። ኢምፔሪያሊስቶችም በዚህ ቀዳዳ በመጠቀም አባላቱን ለመከፋፈልና ንቅናቄውን ለማዳከም ይሞክራሉ ። የሆነው ሆኖ በንቅናቄው ውስጥ ካሉት የአፍሪካ ፣ የእስያና የላቲን አሜሪካ ሀገሮች ብዙዎቹ የተራማጅነት አቋማቸውን እያጠናከሩ ከመምጣታቸው ጋር የሶሻሊስቱ ጉራ ለንቅናቄው የሚሰጠውም ድጋፍ እየጨመረ በመሄዱ ፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስት አቋሙ እየጎላ በተለይም ብዝበዛ የሌለበትና በራስ በመተማመንና በርስ በርስ መረዳዳት ላይ የተመሠረተ አዲስ የፖለቲካና

የኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲሁም ሰላም በዓለም እንዲሰፍን የሚያደርገው ትግል እየተጠና ከረ መጥቷል ።

## ገለልተኛ ማድረግ

*(Neutralize)*

በትግል ወቅት የተሰባሰበና የተጠናከረ ጠላትን በአንድ ጊዜ ደራርቦ መምታት አዳጋች ስለሚሆን ለጊዜው ቀንደኛ ያልሆኑትን ጠላቶች ከሌሎች ዋና ጠላቶች ነጥሎ ብቸኛ እድርጐ ለመምታት የሚያገለግል የትግል ስልት ነው ። ይህም ሊሆን የሚችለው በጠላት ሠፈር ያለውን ውስጣዊ ቅራኔ አጥንቶ እንዲባባስ በማድረግ ነው ። ጠላትም በበኩሉ ተመሳሳይ ዘዴ በመጠቀም የአብዮቱን ሠፈር ለማዳከምና ለመበታተን ሌት ተቀን የሚጥር እንደመሆኑ የውስጥ ጥንካሬን እያረጋገጡ ጠላትን በዚህ መንገድ ማዳከም አስፈላጊና ተገቢ ነው ።

## ገበሬ

*(Peasantry)*

በግል ወይም በኅብረት ሥራ ማኅበር በተያዙ የምርት መገልገያ መሣሪያዎች በመጠቀም የእርሻ ምርት የሚያመርቱ አባላትን ያቀፈ ማኅበራዊ ክፍል ነው ። ገበሬ በመደብነት የተከሰተው ጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት በመፈራረስ ላይ በነበረበት ወቅት ሲሆን የሚጠፋውም የማኅበራዊ ምርት እደረጃጀት ከፍተኛ ደረጃ ላይ በሚደርስበት ፣ በኢንዱስትሪና በእርሻ ሥራ መካከል ያለው ልዩነት በሚወገድበት በኮሚኒስት ሥርዓተ ማኅበር ነው ።

በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ያልተመጣጠነ ዕድገት ሳቢያ ሦስት ዓይነት የገበሬ ክፍሎች ሊኖሩ ይችላሉ ። እነሱም ወዝአደርና ደሃ ገበሬዎች (በካፒታሊስቶችና በትላልቅ የመሬት ከበርቴዎች የሚበዘበዙ የእርሻ ወዝአደሮችና ደሀ ገበሬዎች) መካከለኛ ገበሬዎችና ሀብታም ገበሬዎች ናቸው ። ገበሬዎቹ በሠርቶ አደርነታቸው ፣ ሠራተኛው መደብ የሞኖፖሎችን የበላይነት በመቃወምና ለሶሻሊዝም በሚያደርገው ትግል የቅርብ አጋር ናቸው ። በታዳጊ ሀገሮች ገበሬዎች ከፍተኛውን የኅብረተሰብ ክፍል የሚያጠቃልሉ በመሆናቸው የብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴ ዋና ኃይል ናቸው ።

በሶሻሊስት ሥርዓት ገበሬው ከግል ሸቀጥ አምራችነት ማሽኖች ፣ የኤሌክትሪክ ኃይልና ኬሚካሎች በሰፋት ጥቅም ላይ ወደሚውሉበት በጋራ በሚተዳደር ሕዝባዊ ይዞታ ወደአለው የእርሻ አምራችነት ይቀየራል ። ገበሬው በአኗኗሩና በሥራው ወደ ሠራተኛው መደብ የአኗኗርና የአሠራር ሁኔታ ይበልጥ እየተጠጋ ፣ የኋላ ኋላም አንድ ወጥ በሆነው የኮሚኒስት ኅብረተሰብ ውስጥ ከሠራተኛውና ከምሁሩ ጋር ይዋሀዳል ።

(ፊውዳሊዝምን ፣ የሠራተኛው መደብና የአርሶ አደሩ ኅብረትን ፣ ኢካፒታሊስታዊ የዕድገት ፈለግን ይመለከቷል ።)

## ገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር (የ—)

*(Peasant Producers' Co-opratives)*

ገበሬዎች በግል የያዙትን የማምረቻ መሣሪያ በፈቃደኝነት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የወል ንብረት በማድረግ የጋራ ጥቅማቸውን የሚያስከብሩበትና የሚያዳብሩበት የኢኮኖሚ ድርጅት ነው ።

የገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው ፤—

1. በግል የተያዙትን የማምረቻ መሣሪያዎች ወደ ወል ንብረትነት በመለወጥ የካፒታሊዝምን ብዝበዛ ማስቀረት ፤ ይህ ሥርዓት እንዳያቆጠቁጥ መከላከል ፤
2. ዘመናዊ የእርሻ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ከአነስተኛና የተበጣጠሰ እርሻ ወደ ሰፋፊ እርሻ በመሸጋገር ምርትን ማሳደግ ፤
3. የተናቁ ሙያዎች እንዲዳብሩና ወደ አነስተኛ ኢንዱስትሪ እንዲለወጡ ማድረግ ፤
4. በገጠር የሶሻሊስትን ሥርዓት በመመሥረትና በማስፋፋት የአርሶ አደሩን ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶች ማስከበር ፤
5. ኢኮኖሚውን በዕቅድ ለመምራት እንዲቻል አመቺ ሁኔታን መፍጠር ፤

የገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ከ1917 ታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት በኋላ በመጀመሪያ በሶቭዬት ኅብረት ፣ ከዚያም በሌሎች ሶሻሊስት ሀገሮች በሌኒናዊ የኅብረት ሥራ መርሀ መሠረት እንደየሀገሩ ተጨባጭ ሁኔታ ተቋቁመዋል ።

በሀገራችንም ታሪካዊውን የመሬት አዋጅ መሠረት በማድረግ በገጠር ሶሻሊዝምን ለመገንባት እንዲያስችል በኢትዮጵያ አቆጣጠር በሰኔ 1971 የገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር መመሪያ ወጥቷል ። በመመሪያውም መሠረት በገጠር የገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት በመቋቋም ላይ ይገኛሉ ።

የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ሀገራችን የተያያዘችውን ታሪካዊ የግንባታ ምዕራፍ ለማራመድ የሽግግሩ ወቅት ኢኮኖሚ ሕግጋትና የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በሚገኙበት ተጨባጭ ሁኔታ ላይ በመመሥረት የልማት ስትራቴጂውን በአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር ላይ መሥርቷል።

የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ የሕዝቡን የምግብ ፍላጐት ለማርካት ፣ ለኢንዱስትሪ የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን ለማምረትና ለኢንዱስትሪ የምርት ውጤቶች ገበያ ለመፍጠር ፣ የውጭ ምንዛሪ ለማስገኘት ፣ በአጠቃላይ ለሶሻሊዝም ግንባታ አስፈላጊውን ክምችት በማቅረብ ረገድ የሚጠበቅበትን በሚገባ ማሟላት እንዲችል የገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት መስፋፋትና መጠናከር ወሳኝነት አለው ።

(የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ፣ ማልባን ፣ ወልባን ፣ ወላገድን ይመለከቷል ።)

## ገቢራዊነት

*(Pragmatism)*

ገብረ (አደረገ ፤) ከሚለው የግዕዝ ቃል የመጣ ሲሆን ገቢራዊነት አንድን ነገር ለማመስገንም ሆነ ለመንቀፍ የተግባሩን ውጤት ማወቅ ያሻል ፤ ከንድፈ ሐሳብ ይልቅ በአመዛኙ በተግባር ውጤት ላይ ማትኮር ያስፈልጋል የሚል አስተምህሮ ነው ።

ዕውቀት ከተግባር ግዴታ ይመነጫል የሚልና የዕውቀትን ትክክለኛነት ወይም እውነትነት የሚያረጋግጥ ተግባር እንደሆነ አድርጐ ለመውሰድ የሚሞክር ሐሳባዊ ፍልስፍና ነው ። እውነትንና ጥቅምን አንድ አድርጐ የሚወስድ ፣ እውነት ማለት ጥቅም (ጠቀሜታ)፣ ጥቅም ማለት ደግሞ እውነት እንደሆነ የሚሰብክ ፣ ዕውቀትን አስመልክቶ በአዲስ መልክ የቀረበ ፣ ዳሳሽነትንና ምክኑያዊነትን ለማስታረቅ የሚጥር ንድፈ ሐሳብ ነው ።

ይህ ንድፈ ሐሳብ በ19ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ መጨረሻ ላይ ከአሜሪካ ተነሥቶ ወደ አውሮፓ ተስራጭቷል ። እንደገቢራዊነት አባባል ፍልስፍና ውጤት በሌላቸው ንትርኮች ላይ ሲያተኩር ሳይንስ ግን በተጨባጭ ሁኔታዎችና በተግባር በመመራት ጠቃሚ ውጤቶችንና ሁለንታዊ ያስተሳሰብ ዘዴን ፈጥሮአል ።

ስለሆነም ፍልስፍና በአውጠንጥኖት ላይ ብቻ ሳይወሰን እንደሳይንስ ውጤት ለማስገኘት በተግባር በመመራት የትክክለኛ ዕውቀት መመዘኛ መርሀ ተግባር መሆኑን መቀበል ይኖርበታል ።

በገቢራዊነት አመለካከት የእውነት መለኪያ ተግባር ነው ፤ ማንኛውም ሐሳብና እርምጃ ለተግባር ጠቃሚ ከሆነ እውነት ነው ፤ ከብዙ ተቃራኒ ሐሳቦች ውስጥ ነጥሮ የሚወጣውና የበላይ የሚሆነው ሐሳብ ከፍተኛ ተግባራዊ ግልጋሎት ያለው ሐሳብ ብቻ ነው ። ለምሳሌ በፍልስፍና ውስጥ ሰው በተፈጥሮ ነፃ ነው ወይስ አይደለም ለሚለው ጥያቄ አንዱ ክፍል ሰው ነፃነት ከሌለው ለሚያስበውና ለሚሠራው ተጠያቂና ኃላፊ ሊሆን አይችልም በማለት ሰው ነፃ ነው ሲል ተቃራኒው ክፍል ደግሞ ሰው የተፈጥሮ አካል በመሆኑ እንደ ተፈጥሮ በግዴታ ስለሚገዛ ነፃ ሊሆን አይችልም ይላል ። በገቢራዊነት አስተሳሰብ ይህ ክርክር ሊነሣ የቻለው የጥያቄው መልስ ለተግባር የሚሰጠውን ጥቅም ወይም ጉዳት ባለማጤን ነው ። ሰው ነፃ ካልሆነ ለተግባር አይገፋፋም ። ስለዚህ እውነት ሰውን ሊያበረታታ የሚችለው ፣ ክብርና ኃላፊነት የሚሰጠውና ለተግባርም የቆመ ኃይል መሆን ስለሚገባው ሰው ነፃ ነው የሚለው አቋም ለተግባር ጠቃሚ ነውና እውነትነት አለው ይላል።

ገቢራዊነት የእውነት መመዘኛ ተግባር ነው ማለቱ ትክክል ቢመስልም ፣ ሐሳብ ከነባራዊ ሁኔታ ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት እንዳለው ማለትም ዕውቀት እውነት የሚሆነው ከነባራዊ ሁኔታ ጋር ሲጣጣም ነው የሚለውን መሠረታዊ ሐሳብ ከቶም አይቀበለ

ውም ። ለምሳሌ ማንኛውም እምነት (በገቢራዊነት አስተሳሰብ ጥንቆላንም ጨምሮ) እስከታመነበት ድረስ የሚያበረታታና የሚያጽናና ስለሚሆን እንደ እውነት ሊቆጠር ነው ። ይህ ግን ስሕተት ነው ፤ ምክንያቱም እምነት (ሃይማኖት) አማኙን በማጽናናቱና በማበረታታቱ ብቻ እውነት ሊሆን አይችልም ነው ። ይህንን በማጤን ነው ሌኒን ገቢራዊነትን ሲኄስ አንድ ንድፈ ሐሳብ እውነት የሚሆነው በጠቃሚነቱ ሳይሆን ጠቃሚ የሚሆነው በመጀመሪያ ደረጃ እውነት በመሆኑ ነው ያለው ።

ገቢራዊነት የንድፈ ሐሳብን አስፈላጊነትና ወሳኝነት የተረዳ አይመስልም ። በፍልስፍና ውስጥ የሚታዩት ቅራኔዎችና ክርክሮች ከአስተሳሰብ ስህተት የመጡ ሳይሆኑ የመደቦችን ግጭት የሚያንፀባርቁ በመሆናቸው የቀረበው የእውነት መመዘኛ የአስታራቂነትን ጥረት የሚያሳይ እንጂ እውነቱ የየትኛው ክፍል እንደሆነ አያመለክትም ። ዓላማው ግን ግልጽ ነው ፤ እውነተኛው ሐሳብ ለመደቦች በእኩል የሚበጀውና የሚጠቅመው ሐሳብ ነው መባሉ መደቦችን ለማስታረቅ ቅራኔውን አድበስብሶ ልቅ በሆነ አስተሳሰብ ትግሉን ለማዳከም የሚደረግ ጥረት ነው ። በማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍና ግን ንድፈ ሐሳብ ወሳኝነት የሚያገኘው በማስታረቅ ሳይሆን እንደተሳሰለ ቢላዋ ነገሮችን ፣ ሁኔታዎችን ፣ አስተሳሰቦችን በትክክል በቅራኔው መሥመር ቆርጦና ለይቶ ሲያስቀምጥ ፣ ለሁሉ ሳይሆን ለእውነቱ ማለትም ለተገቢው መደብ ሲሰለፍ ነው ። ንድፈ ሐሳብ ለእውነት መከሰት መሣሪያ ሊሆን የሚችለው በማስማማት ሳይሆን ወደ ወሳኙ ትግል ሲያራምድ ነው ። እውነት የሚመዘነው በተግባር ነው ከተባለ ፣ ቅራኔንና ትግልን ከተግባር ለይቶ እውነትን አስታራቂ ማድረግ እንደማይቻል ተግባር ራሱ ስለሚያስተምረን የገቢራዊነት የተሳሳተ አቋም እራሱ በተቀበለው መመሪያ ይጋለጣል ። የገቢራዊነት የእውነት መለኪያ ማኅበራዊ ፖለቲካዊ ግንዛቤ በዝባዥ ሥርዓቶች እንዲቆዩ ወይም እንዲጠናከሩ የሚወስዱትን ፖለቲካዊ እርምጃ ሙሉ በሙሉ የሚደግፍ ነው ።

(ነፃነትንና ግዴታን ይመለከቷል ።)

## ገቢ ንግድ
*(Import Trade)*

አንድ ሀገር ከሌላ ሀገር ወይንም ሀገሮች በንግድ መልክ ዕቃዎችን የማስገባቱ እንቅስቃሴ ገቢ ንግድ ተብሎ ይጠራል ። ከውጭ ለሚገቡትም ዕቃዎች የሚደረገው ክፍያ አብዛኛውን ጊዜ በውጭ ምንዛሪ አማካይነት የሚከናወን ሲሆን አልፎ አልፎም በዓይነት ለውጥ ሊደረግ ይችላል ። ሸቀጦች የአንድን ሀገር ብሔራዊ ክልል አልፈው በሚገቡበት ጊዜ የገቢ ቀረጥ ይከፈልባቸዋል ።

በሜርካንቲሊዝም ዘመን የውጭ ንግድን በሚመለከት ረገድ መንግሥታት ይከተሉት የነበረው ፖሊሲ ከውጭ ወደሀገር ውስጥ የሚገቡ ሸቀጦችን በዝቅተኛ መጠን መወሰንና ከሀገር ውስጥ ወደውጭ የሚላኩትን ሸቀጦች ደግሞ በከፍተኛ መጠን ማካሄድ ነበር ፤ የዚህም ዓላማ በገቢ ንግድ አማካይነት ለሚገቡት ዕቃዎች የሚከፈለውን ወርቅና ብር ማዳንና በአንፃሩም ከሌላ ሀገር በወጭ ንግድ አማካይነት ወርቅና ብር ማከማቸት ነበር ። የካፒታሊዝም የነፃ ንግድ ደረጃ መርህ በገቢ ሸቀጦችና በወጪ ሸቀጦች ላይ ምንም ዓይነት እገዳ አይደረግም የሚል ነው ። በሞኖፖል ካፒታሊዝም ወቅት ግን በተለይ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ቀውስ በሚባባስበት ጊዜ ካፒታሊስት ሀገሮች የገቢ ንግድን የመገደብ ከፍተኛ አዝማሚያ ይታይባቸዋል ።

ኋላቀር ሀገሮች በገቢ ንግድ አማካይነት ለልማትና ለፍጆታ የሚያስፈልጓቸውን ሸቀጦች ያስገባሉ ። ሆኖም እነዚህ ከኢምፔሪያሊስት ሀገሮች የሚገዟቸው የኢንዱስትሪ ውጤቶች ዋጋ በየጊዜው እየናረ በመሄድ ላይ በመሆኑ ክፍያውን ለማከናወን ከፍተኛ ችግር ላይ ወድቀዋል ። በተለይም ይህ ችግር የካፒታሊስትን የዕድገት ጐዳና በሚከተሉ ሀገሮች ላይ በጣም ጐልቶ ይታያል ።

ሶሻሊስት ሀገሮች ገቢ ንግዳቸውን በማዕከላዊ ዕቅድና በመንግሥት ይዞታ አማካይነት በመምራት ለጠቅላላ ዕድገታቸው በሚጠቅምና የሶሻሊስት ሀገሮችን የጋራ ብልጽግናና መተሳሰብን በሚያዳብር መንገድ እንዲከናወን ያደርጋሉ ።

አብዮታዊት ኢትዮጵያ በቅድመ አብዮት ከኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ጋር በጥብቅ ተሳስሮ የነበረውንና በእኩልነት ላይ ያልተመሠረተውን ገቢ ንግድ ደረጃ በደረጃ ለማላቀቅና ለልማቷ በሚረዳ መንገድ ለማካሄድ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች ።

## ገንዘባዊ የእሴት መልክ
*(Money Form of Value)*

ገንዘባዊ የእሴት መልክ እስከተከሰተበት ጊዜ ድረስ የነበረው የሥራ ክፍፍል በከብት ርቢና በእርሻ መካከል የተከናወነው የመጀመሪያውና ዋነኛው ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል ነበር ። ገንዘባዊ የእሴት መልክ የተከሰተው እደ ጥበብ ከእርሻ ተገንጥሎ ከወጣበት ከሁለተኛው ከፍተኛ ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል በኋላ ነው ። ከከብት ርቢና ከእርሻ ይልቅ የእደ ጥበብ ሥራ ራሱን የቻለ የሥራ ዘርፍ ሆኖ መከሰቱ ለገበያ የሚቀርቡ ሸቀጦችን መጠን ከመጨመሩም በላይ የገበያውን ክልል እያሰፋው ሊሄድ ችሏል ።

ቀደም ሲል እነስ ባሉ ገበያዎች እንደ ጋራ መገበያያ (ሁለንታዊ እኩያ) ሲያገለግሉ የነበሩ ሸቀጦች ገበያው እየሰፋና እየተራራቀ በሄደ ጊዜ (በአንድ ቦታ የተለመደ ሸቀጥ ራቅ ባለ ቦታ ላይ ለመድረስ ስለሚችል) የተለያዩ የልውውጥ አማካዮች በመሆን በተደጋጋፊነት ወይም በተወዳዳሪነት ተከሰቱ ። ይሁንና በሸቀጥ ምርት ማደግ ምክንያት ንግድ ከአካባቢው አልፎ ሰፋ ያለ አካባቢን ፣ ከዚያም አልፎ የተወሰኑ ሀገሮችን ማገናኘት በጀመረበት ጊዜ ፣ በዛ ያሉ እንደየ አካባቢው የተለያዩ የጋራ መገበያያዎች ለዚህ ጉዳይ ሊያገለግሉ አልቻሉም ። በመሆኑም ለገበያ የቀረቡ ሸቀጦችን ዋጋ የሚገልጽ በሁሉም አካባቢ ተቀባይነት ያለው አንድ የጋራ መገበያያ መኖር አስፈላጊ ሆነ ። ለዚህም ተግባር የከበሩ ማዕድናት ተስማሚ ሆነው በመገኘታቸው እንደ ከብት ፣ እንደ ዓሣ ፣ ከፀጉር የተሠሩ ልብሶችና አሞሌ ጨው የመሳሰሉትን መተካት ጀመሩ ።

እነዚህም የከበሩ ማዕድናት ብረት ፣ ነሐስ ፣ መዳብ ፣ ብርና ወርቅ ናቸው ። ከእነዚህም ውስጥ ወርቅ ቀስ በቀስ ገንዘብ ወይም የጋራ መገበያያ ሆኖ ወጣ ። ወርቅም እራሱ ባለው የልውውጥ እሴት አማካይነት የሌሎች ሸቀጦችን የልውውጥ እሴት የሚገልጽ የተለየ ሸቀጥ ሆነ ። ለዚህ ተግባር የተመረጠበትም ምክንያት ፣

ሀ. በሁሉም ሀገር የሚገኝ ወርቅ ተመሳሳይ በመሆኑ ፤

ለ. በተፈለገ መጠን (እንደ ምንዛሪ) ሊከፋፈል በመቻሉ ፤

ሐ. ከሌሎች ጋር ሲነፃፀር ለብዙ ጊዜ ሳይዝግና እሴቱን ሳይቀንስ ሊቆይ በመቻሉ ፤

መ. አነስተኛ በሆነ የወርቅ መጠን ውስጥ ከፍተኛ የሥራ ጊዜ የፈሰሰበት በመሆኑ ፤

ሠ. ትንሽ የወርቅ መጠን እያሌ ሸቀጦችን ለመለወጥ በመቻሉ ነው ።

ወርቅ ባለው ልዩ ባሕርይ የልውውጥ እሴት ብቻ ሳይሆን የጠቀሜታ እሴትም ያለው በመሆኑ ሰዎች ወርቅን ከዝውውር በብዛት ማስወጣት ስለጀመሩና በገበያ ላይ ሸቀጦችን ለመለወጥ የሚችለው የወርቅ መጠን እያነሰ በአንፃሩም ለገበያ የሚቀርበው ሸቀጥ በመብዛቱ በሸቀጦች የዝውውር ሂደት ላይ ከፍተኛ መሰናክል ተፈጠረ ። በመሆኑም ሸቀጦችን ለማዘዋወር እንደአማካይ ሆኖ የሚያገለግለው ገንዘብ የልውውጥ እሴት ብቻ እንጂ በራሱ የጠቀሜታ እሴት የሌለው እንዲሆን አስፈለገ ። በዚህም ምክንያት የወረቀት ገንዘብ የወርቅን ዝውውር ደረጃ በደረጃ እየተካ መጣ ።

አንድ ሀገር የወረቀት ገንዘብ የሚያትመው በተወሰነ ወቅት ካለው ጠቅላላ የምርት ውጤት ጋር በማዛመድ ነው ። የገንዘቡን መጠንና የምርቱን ውጤት ለማጣጣም በሚደረገው ጥረት ለአንድ ሀገር ወሳኙ መሠረታዊ ሁኔታ በአንድ በተወሰነ ወቅት አጠቃላይ ምርትን ለማሳደግና ለፍጆታ የሚያስፈልጉትን ሸቀጦች ከዓለም ገበያ ለማስመጣት ባለው የመግዛት ኃይል ነው ። ይህም የመግዛት ኃይል የሚገለጸው እንደ ሀገር ባለው የወርቅ ወይም የውጭ ምንዛሪ ክምችት ነው ፤ ስለዚህ አንድ ሀገር እንደየ ሁኔታው የሚያትመው የወረቀት ገንዘብ መጠን ሀገሩ ሊኖረው በሚችለው የወርቅ መጠን ወይም በከፍተኛ ደረጃ ወርቅን ሊወክሉ ከሚችሉ የውጭ ምንዛሪ ማለትም የአሜሪካ ዶላር ፣ የእንግሊዝ ፓውንድ ፣ የጀርመን ማርክ ፣ የጃፓን ዩን ወዘተ... ጋር በማነፃፀር ነው ።

# ገንዘብ

*(Money)*

ገንዘብ የሌሎች ሸቀጦች ሁለንታዊ እኩያ በመሆን እሴታቸው የሚገለጽበት ፣ እንደ ሁለንታዊ ወይም አጠቃላይ የሸቀጦች የዝውውር ማዕከል(መሣሪያ) በመሆን የሚያገለግል የተለየ ሸቀጥ ነው ።

ከገንዘብ መከሰት በፊት ሸቀጥ በሸቀጥ ይለወጥ ነበር ። የሸቀጥ ምርት እየተስፋፋና የሸቀጦችም ልውውጥ እየዳበረ ሲሄድ ፣ የአንድ ሸቀጥ እሴት በሌላ ሸቀጥ የጠቀሜታ እሴት የሚገለጽበት ሁኔታ ተፈጠረ ። ይህም የእሴት ጥንተ መልክ የሚባለው ነው ። በኋላም አንድ ሸቀጥ ከአንድ በላይ የሆኑ ሸቀጦችን በተናጠል የሚለውጥበት ደረጃ ሲደርስ የእሴት ጥንተ መልክ ወደ ተስፋፋ የእሴት መልክ አደገ ።

የሸቀጥ ምርት እያደገና የሥራ ክፍፍል እየተስፋፋ ሲሄድ ፣ በብዛት የሚለዋወጠው አንድ ሸቀጥ የልውውጥ አማካይ በመሆን ማገልገል ጀመረ ። በዚህ ሁኔታ ግብታዊ በሆነ መንገድ የተስፋፋ የእሴት መልክ ቀስ በቀስ ወደ ሁለንታዊ ወይም አጠቃላይ የእሴት መልክ ተለወጠ ። የሁለንታዊ እኩያ ሚና ከአንድ ከተለየ ሸቀጥ ጋር ሲያያዝ ፣ ይህም ሸቀጥ ሌሎች ሸቀጦችን በማንኛውም ስፍራና ጊዜ ሊለውጥ ሲችል ፣ ይህ ሸቀጥ ገንዘብ ይሆናል ፤ የእሴት መልኩም የገንዘብ የእሴት መልክ ይባላል ።

ገንዘብ እራሱ ሸቀጥ ነው ። ይሁንና ከሌሎች ሸቀጦች የሚለየው ባሕርይ የሁሉም ሸቀጦች እሴት የሚለወጥበት ሁለንታዊ እኩያ መሆኑ ነው ። ገንዘብ ሸቀጥ እንደመሆኑ ማኅበራዊ ሥራ የፈሰሰበትና በሸቀጥ አምራቾች መካከል ያለው የኢኮኖሚ መተሳሰር ማኅበራዊ ግንኙነት የሚገለጽበት ነው ።

የሸቀጥ ምርት እየዳበረና እየሰፋ ሲሄድ በዚያው ልክ ገንዘብ የሚያሟላቸው ተግባሮች እየሰፉ ሄደዋል ። በዳበረ የሸቀጥ ምርት ውስጥ ገንዘብ እንደ እሴት መለኪያ ፣ እንደ ዝውውር አማካይ ፣ እንደ ክምችት መሣሪያ፣ እንደ ክፍያ መሣሪያና እንደ ዓለም አቀፍ የልውውጥ መሣሪያ በመሆን ያገለግላል ።

## 1. ገንዘብ እንደ እሴት መለኪያ

*(Money as a measure of value)*

ገንዘብ ከሚያሟላቸው ተግባሮች አንዱ እንደ እሴት መለኪያ በመሆን ማገልገሉ ሲሆን ይህም ሁለንታዊ የእኩያነት ሚናው የሚገለጽበት ነው ። ገንዘብ የሁሉንም ሸቀጦች ዋጋ ሊገልጽ የሚችል በመሆኑ የየአንዳንዱን ሸቀጥ እሴት ለመለካት ያስችላል ። ስለዚህም ገንዘብ ይህን ተግባር እንዲያሟላ ሲፈለግ የግድ-ታ በጥሬ ገንዘብ መልክ በእጅ መገኘቱ አስፈላጊ አይሆንም ። ለምሳሌ አንድ ሰው በኪሱ ምንም ገንዘብ ሳይዝ ወደ ሱቅ በመሄድ የሸቀጦችን ዋጋ ጠይቆ ሊረዳ ይችላል ። ባለሱቁም የሸቀጦቹን ዋጋ የሚተምነው ከመሸጡ በፊት ነው ። እንግዲህ እዚህ ላይ ገንዘብ በጥሬ ገንዘብ መልክ በቦታው ባይገኝም የተፈለገውን ሸቀጥ እሴት በመግለጽ በመለኪያነት ሲያገለግል ይታያል ።

የገንዘብ እንደ እሴት መለኪያ ሆኖ ማገልገል በርከት ያሉ ተግባራዊ ጥቅሞች አሉት ። በተለያዩ የኢኮኖሚ ስሌቶች ለምሳሌ ባጀት በማዘጋጀት ፣ ብሔራዊ ገቢን በመቀመር ፣ ያንድን ፋብሪካ ሆነ ድርጅት ንብረት በመገመት ወዘተ... ሁለንታዊ እኩያነቱ ለመዝገብ እያያዝ ምቹ ያደርገዋል ።

ይህን የእሴት መለኪያነት ተግባሩን ሲያሟላ ገንዘብ በቦታው መገኘት የለበትም ቢባልም ራሱ እሴት ሳይኖረው ይህን ተግባር ሊያሟላ ይችላል ማለት አይደለም ። ራሱ ክብደት የሌለው ነገር ለክብደት መለኪያነት ማገልገል እንደማይችል ሁሉ እሴት የሌለው ነገርም የእሴት መለኪያ ሊሆን አይችልም ። ስለሆነም ይህን ተግባር ሊያሟላ የሚችል ሸቀጥ ራሱ እሴት ያለው መሆን ይኖርበታል ። ይህም ደግሞ ሄዶ ሄዶ መጨረሻ ላይ በወርቅ መገለጡ ግዴታ ይሆናል ። አንድ ጫማ ሃምሳ ብር ያወጣል ብንል ይህ ሃምሳ ብር የተወሰነ ያህል ወርቅ ተክቶ ያለ በመሆኑ የጫማው እሴት በወርቅ እሴት ተገለጠ ማለት ነው ።

## 2. ገንዘብ እንደ ዝውውር አማካይ

*(Money as a medium of circulation)*

ገንዘብ ከመምጣቱ በፊት ሸቀጥ በሸቀጥ (ሸ—ሸ) በቀጥታ ይለወጥ ነበር ። ለም

ሳሌ አንድ ኮርቻ በአምስት ቁና ጤፍ ይለወጣል ። ገንዘብ ከተከሰተ በኋላ ግን ሸቀጦች በገንዘብ አማካይነት መለወጥ ጀመሩ ። በምሳሌአችን መሠረት ኮርቻው በሃያ ብር ይሸጥና በሃያ ብሩ ጤፍ ይገዛል እንበል ። እንደምናየው በዚህ ዝውውር ውስጥ ገንዘብ የሸቀጥ ዝውውር አማካይ (ሸ—ገ—ሸ) በመሆን ያገለግላል ። ይህንንም ተግባር ለማሟላት የገንዘብ በቦታው መገኘት አስፈላጊ ይሆናል ።

በሸቀጥ ዝውውሩ ወቅት የልውውጡ ሂደት ሁለት የተለያዩ መልኮችን እንደሚይዝ እናያለን ። መጀመሪያ ኮርቻ በገንዘብ (ሸ—ገ) ይለወጣል ። ይህም ሽያጭ ነው ። ከዚያ ገንዘብ በጤፍ ይለወጣል ። (ገ—ሸ) ይህ ደግሞ ግዥ ነው ። ሽያጭና ግዥ በተለያዩ ቦታና ጊዜ ሊፈጸሙ ይችላሉ ። ኮርቻውን አንድ ሰው ገበያ አውጥቶ መሸጡ በዚያው ቀን ፣ ከዚያው ገበያ ጤፍ መግዛቱን አያስከትልም ። ከወር ወይንም ከዓመት በኋላ ከሌላ ቦታ ሊገዛም ይችላል ማለት ነው ። ቀደም ሲል ግን ሸቀጥ በሸቀጥ (ሸ—ሸ) ይለወጥ በነበረ ጊዜ ሽያጭና ግዥ የግዴታ ባንድ ቦታ ፣ ባንድ ወቅት መካሄድ ነበረባቸው ። የገንዘብ መምጣትና ብሎም የሽያጭና የግዥ ሁለት የተለያዩ ድርጊቶች ሆኖ መውጣት የኢኮኖሚ ቀውስ መንሥኤ ሊሆን ችሏል ። ምክንያቱም አንድ ባለሸቀጥ ሸቀጡን ከሸጠ በኋላ በገንዘቡ ሌላ ሸቀጥ ካልገዛ ሌላ ባለሸቀጥ ሸቀጡን መሸጥ ያቅተዋል ፤ ሊሸጥ አለመቻሉም ደግሞ ከሌላ ሦስተኛ ሰው ሸቀጥ መግዛት እንዳይችል ያደርገዋል ። ሁኔታው እንዲህ እያለ ስለሚቀጥል በገበያ ላይ በርከት ያሉ ሸቀጦች ሳይሸጡ ሊቀሩ ይችላሉ ። ቀላል የሸቀጥ ምርት በስፈነበት ኢኮኖሚ ውስጥ ይህ ዓይነቱ ችግር ጎልቶ አይታይም ። የተስፋፋ እርባታ ስለማይካሄድ በቀላል የሸቀጥ ምርት ኢኮኖሚ ውስጥ ቀውስ ሊኖር አይችልም ። ቀውሱ የሚታየው ሁኔታዎች ተሟልተው በሚቀርቡበት በዳበረ የካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት ውስጥ ነው ።

ቀደም ሲል ያነሣነውን ምሳሌ ብናይ ሽያጭና ግዥ ከተፈጸመ በኋላ ኮርቻና ጤፍ ከዝውውሩ መስክ ሲወጡ ገንዘብ ግን ሌላ ሽያጭና ግዥን በአማካይነት ማገልገሉን ይቀጥላል ። ገንዘብ በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ በመዋል የሚያገለግል ከሆነ የሸቀጥ ዝውውርን ለማካሄድ ምን ያህል ገንዘብ ያስፈልጋል ብሎ መጠየቅ ይቻላል ። ዝርዝሩን ብንተው ወሳኝ ነጥቦቹን እንደሚከተለው መግለጽ ይቻላል ፣

$$\text{የገንዘብ መጠን} = \frac{\text{የሸቀጦች ጠቅላላ ዋጋ}}{\text{የገንዘብ የዝውውር ፍጥነት}}$$

ከላይ ባቀረብነው እኩለት መሠረት የሸቀጦች መጠን ወይንም ዋጋቸው (ወይንም ሁለቱም) እየጨመረ ከሄደ ለዝውውር አማካይነት የሚያስፈልገውም ገንዘብ መጠን እየጨመረ የሚሄድ ሲሆን የገንዘብ የዝውውር ፍጥነት መጨመር ግን የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን አነስተኛ ያደርገዋል ።

## 3. ገንዘብ እንደ ክምችት መሣሪያ *(Money as a means of hoarding)*

የገንዘብ መከሰት ሽያጭና ግዥ በሁለት የተለያዩ ድርጊቶች እንዲከፈሉ ማድረጉን ቀደም ሲል ተመልክተናል ። ሸቀጥ ተሸጦ ካበቃ በኋላ ግዥ ሳይከተል ከቀረ ወይንም ዝውውሩ ከተገታ ገንዘቡ እንደክምችት መሣሪያ ሆኖ ማገልገል ይይዛል ። እዚህ ላይ ለግዥ የታቀደና ለጊዜው ግን በእጅ ላይ ያለ ገንዘብ ለምሳሌ ወጪውን ለወር ለማብቃቃት ሲል ከደመወዙ የተወሰነውን በኪሱ የሚይዘው ሠራተኛ ገንዘብ እንደ ክምችት ሊቆጠር የማይችል ነው ።

ገንዘብ ካለ በስማይ መንገድ አለ እንዲሉ በተፈለገበት ጊዜና ቦታ ገንዘብን ወደ ሸቀጥ መለወጥ የሚቻል መሆኑ የገንዘብን በእጅ መገኘት ጥቅም ጉልህ አደረገው ። ይሁንና ሳይሸጡ ለመግዛት ቀደም ሲል ሸጦ ሳይገዙ መቀመጥ አስፈላጊ ይሆናል ። የሸቀጥ ምርት እየተስፋፋ ሄዶ ገንዘብም ከፍተኛ ኃይልና ግምት እያገኘ ሲሄድ ሽጠው ግዥን ሳያስከትሉ ገንዘብ ማከማቸትን እንደ ግባቸውና እንደ ህልውናቸው መሠረት አድርገው የሚያዩ ሰዎች በረከቱ ። ገንዘብን ከዝውውር አውጥቶ በማሰሮ እያደረጉ መቅበር ወይንም መደበቅ ሥራቸው ሆነ ። እንዲህ ላሉ ሰዎች ብዙ መሥራት ፣ ንፉግነትና ፍቅረ ንዋይ መሠረታዊ መርሀቸው ሲሆን ማርክስ እንደሚለው ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያቸው ሲጠቃለል የተቻለውን ያህል እየሸጡ ግዥን በዚያው ልክ ማሳነስ ነው ።

ካፒታሊዝም እያደገ መጥቶ የሃብት መበርከትም የሥራ ኃይልን ገዝቶ የሥራ ኃይልን በመበዝበዝ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ይህ ዓይነቱ ጥንታዊ ሃብት የማከማቸት ዘዴ ለካፒታሊስታዊ ዓይነት ክምችት ቦታውን ለቀቀ ። ካፒታሊስታዊ ክምችት የተመሠረተው ገንዘብን በመቅበር ላይ ሳይሆን በየጊዜው የበለጠ ትርፍን ለማግኘት ገንዘብን ሥራ ላይ ቶሎ ቶሎ በማዋል ፣ በማያቆም የዝውውር ሂደት ውስጥ በማስገባት ነው ። ይህም ሂደት ገንዘብ — ሸቀጥ — ገንዘብ (ገ—ሸ—ገ) በሚለው ቀመር ይገለጣል ።

ካፒታሊስቶች በወቅቱ የማይጠቀሙበትን ገንዘብ በባንክ ያኖራሉ ። ባንክም የእነዚህን ካፒታሊስቶችና የሌሎችንም የሚያጠራቅሙ ሰዎች ገንዘብ በማሰባሰብ ለሚጠቀሙበት ሰዎች በማበደር ወደ ዝውውር ያስገባዋል ።

ገንዘብ እንደ ክምችት መሣሪያ ሆኖ ሲያገለግል ለዚህ ተግባር ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው ወርቅ ብቻ ነው ። የወረቀት ገንዘብ ለዚህ ተግባር ቢውል የዋጋ ንረት ባለበት ሁኔታ የመግዛት ዐቅሙ ስለሚወድቅ ጉዳት ያስከትላል ።

## 4. ገንዘብ እንደ ክፍያ መሣሪያ

*(Money as a means of payment)*

ግዥ (ገ—ሸ) ሽያጭን (ሸ—ገ) ቀድሞ በሚመጣበት ጊዜ ገንዘብ እንደ ክፍያ መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል ። ለምሳሌ አንድ ገበሬ አዝመራው ገና ሳይሰበሰብ ልብስ መግዛት ቢፈልግና ገንዘብ በእጁ ባይኖረው ያለው ምርጫ ከነጋዴው ጋር በመስማማት በብድር መግዛት ይሆናል ። በገንዘብ ስፍራም ወደፊት የሚከፍልበትን ጊዜና ባለዕዳነቱን የሚገልጽ ደረሰኝ ሰጥቶ ልብሱን ይወስዳል ። እዚህ ላይ ነጋዴው አበዳሪ ፣ ገበሬው ተበዳሪ በመሆን ውሉ የሚካሄድ ሲሆን ገበሬው ልብሱን ሲገዛ ምንም የሚከፍለው ገንዘብ አይኖረውም ። ስለዚህም ገንዘብ እንደ ክፍያ መሣሪያ እንጂ እንደ ዝውውር አማካይ ሆኖ አላገለገለም ። ገበሬው ገና ወደፊት አዝመራው ሲሰበሰብ እህሉን ሸጦ ቀደም ሲል ለገዛው ሸቀጥ ክፍያውን ይፈጽማል ማለት ነው ። ግዥ ሽያጭን ቀደመ ስንልም ይህንኑ ለማመልከት ነው ።

በክፍያ መሣሪያነቱ ገንዘብ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰው በዳበረ ካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ነው ። በካፒታሊዝም ሥር የብድር ግንኙነትና የባንክ አገልግሎት እያደገ መምጣት አዲስ የዝውውር መሣሪያ ማለትም የደረሰኝ ወይንም የብድር ገንዘብ መስፋፋትን አስከተለ ። በመሆኑም በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ገንዘብ ከዝውውር አማካይነቱ ይልቅ የክፍያ መሣሪያነቱ እየጨመረ ይሄዳል ። እንደዝውውር አማካይ ሆኖ ሲያገለግል የሚታየው በችርቻሮ ንግድ ውስጥ ሲሆን በጅምላ ንግድና በሀገሮች መካከል በሚካሄድ ዓለምአቀፍ ንግድ ግን ገንዘብ በመሠረቱ የሚያገለግለው እንደ ክፍያ መሣሪያ በመሆን ነው ።

የባንክ አገልግሎት መስፋፋት እንደ ቼክ ፣ እንደ ድራፍት ፣ እንደ ባንክ ኖት ፣ እንደ ተስፋ ሰነድ ያሉ የብድር ገንዘቦችን ተግባራዊ በማድረግ የገንዘብን በክፍያ መሣሪያነት ማገልገል አሳድጎታል ።

## 5. ገንዘብ እንደ ዓለም አቀፍ የልውውጥ መሣሪያ

*(Money as a universal means of payment or an international means of purchase)*

የሸቀጥ ልውውጥ እያደገ ሄዶ ከድንበር በማለፍ በሀገሮች መካከል የሸቀጥ ልውውጥንና የገንዘብንም በዓለም ገበያ ላይ ማገልገል አስከተለ ።

በዓለም ገበያ ላይ በሚካሄድ የሸቀጥ ልውውጥ ገንዘብ በመሠረቱ እንደ ዝውውር አማካይ ሳይሆን እንደ ክፍያ መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል ። የዚህ ምክንያት ግልጽ ነው ። በሀገሮች መካከል ያለ ክፍያ የሚፈጸመው በጥሬ ገንዘብ ሳይሆን በባንኮች አማካይነት በሚካሄድ የደረሰኝ ልውውጥ ነው ። ለምሳሌ ኢትዮጵያ 5 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ቡና ወደ ጀርመን ልካ 6 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ማሽን ብታስመጣ ያለባት አንድ ሚሊዮን ብር የሚከፈለው በጥሬ ገንዘብ ሳይሆን በባንክ በኩል በሚፈጸም የባለ ዕዳነት (የመተማመኛ ሰነድ) ደረሰኝ ይሆናል ። ቀሪውን የአንድ ሚሊዮን ብር ዕዳ የምታወራርደው ተጨማሪ ለዕዳው ተመጣጣኝ የሚሆን ቡና ወይም ሌላ ሸቀጥ በመላክ ነው ። ይሁንና

እንዲህ ባለ የጋራ ልውውጥ ዕዳን ማወራረድ ሳይቻል ከቀረ ወርቅን ከሀገር ወደ ሀገር በማዛወር ዕዳን መክፈል አስፈላጊ ይሆናል ። ይህ ሲሆን ገንዘብ እንደ ዓለም አቀፍ የልውውጥ መሣሪያ አገለገለ ይባላል ። ይሁንና ሰላማዊ ግንኙነት በመንግሥታት መካከል ባለበት ጊዜ ይህ ሁኔታ አይደርስም ። ጦር ነት ሲኖር ፣ በዓለም ደረጃ ከፍተኛ ውጥረት ሲታይ ፣ በመንግሥታት መካከል መደበኛ ሰላማዊ ግንኙነት ሲቃወስ ወዘተ... ብቻ ሸቀጦችን በጥሬ ገንዘብ መግዛት አስፈላጊ ሆኖ ይገኛል ።

በዓለም አቀፍ የልውውጥ መሣሪያነት ገንዘብ በወርቅ ጥፍጥፍ መልኩ ቢቀርብም የአንድ ሀገር የወረቀት ገንዘብም የዚህ ምትክ በመሆን በዓለም አቀፍ ንግድ (ልውውጥ) ውስጥ ሊያገለግል ይችላል ። ይሁንና ገንዘብ ይህን ዓይነት ሚና ሊጫወት የሚችለው የገ ንዘቡ ምንጭ የሆነው ሀገር በዓለም የኢኮ ኖሚ ግንኙነት ውስጥ ከፍተኛ ወይንም መሪ ቦታ ይዞ የሚገኝ ሲሆን ነው ። ብሔራዊ ገን ዘብ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሊያገለግል የሚች ለው የዚያ ሀገር ብሔራዊ ባንክ ወይንም መንግሥት የወረቀትን ገንዘብ በወርቅ ለመለወጥ ለመጣ ሰው በወቅቱ ባለው የል ውውጥ መጠን መሠረት ለመለወጥ ፈቃ ደኛ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው ። ይህ ሲሆን የዚያ ሀገር ገንዘብ ጠንካራ ገንዘብ በመባል ይታወቃል ። ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በፊት የእንግሊዝ ፓውንድ ስተርሊንግ ይህን ዓይነቱን የዓለም ገንዘብነት ሚና ይጫወት ነበር ። ከዚያ በኋላ የአሜሪካ ዶላር ሊተ ካው በቅቷል ። ይሁንና ከ1971 ወዲህ አሜ ሪካ ዶላርን በወርቅ መለወጥ አቁማለች ። ይህም የዓለም ካፒታሊስት ሥርዓት ከፍተኛ የገንዘብ ቀውስ ውስጥ እንዳለ ከማስረዳቱም በላይ ምንም ቢሆን ሁለንታዊ ገንዘብ ሆኖ ማገልገል የሚችል ወርቅ ብቻ ለመሆኑ ጥሩ ማረጋገጫ ነው ።

ከታሪክ አንፃር ሲታይ ገንዘብ ከካፒ ታል ይቀድማል ። ግብታዊ በሆነ የገበያ እንቅስቃሴ ውስጥ የገንዘብ ኢኮኖሚ መስ ፋፋት የአነስተኛ የሸቀጥ ምርት መዳከምንና የካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት መዳበርን አስከ ተለ ። በካፒታሊስት ሥርዓት የገንዘብ ተግ ባራት የካፒታል ተግባራት በመሆን ያገለ ግላሉ ። በመሆኑም በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ገንዘብና የገንዘብ ተግባራት በዚህ ሥርዓት ውስጥ ያሉትን ተፃራሪ ቅራኔዎች ይገልጻሉ ።

የሸቀጥ ምርት ባለበት ኢኮኖሚ ውስጥ ገንዘብ የግዴታ ስለሚኖር የሸቀጥ ምርት ባለበት የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ውስጥም ገን ዘብ አለ ። ይሁንና በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ገንዘብ የሚኖረው ጠባይ በካፒታሊ ስት ኢኮኖሚ ውስጥ ካለው ጠባይ የተለየ ነው ። ይኸውም በመጀመሪያ ደረጃ በካፒታ ሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የአምራቾች ሀልውና በገበያ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ገንዘብ በሰዎች ላይ “መለኮታዊ” ተፅዕኖ አለው ፤ ማለትም ገንዘብ እንደ “ፈጣሪ” ወይም እንደ ሌላ ኃያል ጣዖት ይመለካል ። የሶሻሊ ስት ኢኮኖሚ በምርት መገልገያዎች ማኅበ ራዊነት ላይ የተገነባ ፣ የኢኮኖሚ ግንኙነቱ በዕቅድ የሚመራና የሠራተኛውን ሕዝብ መሠረታዊ ጥቅም የሚያንፀባርቅ በመሆኑ ገንዘብ በዕቅድ በሚመራው ኢኮኖሚ ውስጥ እንደ መሣሪያ ሆኖ ከማገልገል ውጭ እንደ ካፒታሊስት ኢኮኖሚ የ“ተመላኪነት” ኃይል የለውም ፤ ሊኖረውም አይችልም ።

በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ገንዘብ የሸቀጦች ሁሉ ሁለንታዊ እኩያ በመሆን ምን ያህል ማኅበራዊ የሥራ ኃይል እንደፈ ሰሰ የሚቆጣጠር ኢኮኖሚውን በዕቅድ ለመምራትና ለማደራጀት የሚያገለግል ፣ ብሔ ራዊ ምርት ከሶሻሊስት ኢኮኖሚያዊ ሕጎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ መከፋፈሉን የሚያ ረጋግጥ መሣሪያ ነው ።

(የወረቀት ገንዘብን ይመለከቷል ።)

## ገንዘብ ምንዛሪ ዋጋ ቅነሳ (የ—)
*(Devaluation)*

የአንድ ሀገር ገንዘብ በእኩያነት የሚ ለወጥበትን የወርቅ ወይንም የሌላ ሀገር ገንዘብ የምንዛሪ መጠን ይፋ በሆነ መንገድ መቀነስ የገንዘብ ምንዛሪ ዋጋ ቅነሳ ይባላል ።

ለምሳሌ አንድ የኢትዮጵያ ብር በአ ንድ ወቅት 5 ግሬይንስ ወርቅ የሚወክል ቢሆንና አሁን ግን 4 ግሬይንስ ወርቅ እንዲ ወክል ቢደረግ ፣ ወይም አንድ የኢትዮጵያ ብር በ0.48 የአሜሪካ ሣንቲም ሲለወጥ

ቆይቶ አሁን በ0.40 የአሜሪካ ሣንቲም እንዲለወጥ ቢደረግ በኢትዮጵያ ብር ላይ የገንዘብ ምንዛሪ ዋጋ ቅነሳ ተደረገ ይባላል ።

የገንዘብ ምንዛሪ ዋጋ ቅነሳ የካፒታሊስት ሥርዓት አጠቃላይ ቀውስ አንደኛው ገጽታ ነው ። የገንዘብ ምንዛሪ ዋጋ ቅነሳ የገንዘብ እሴት መቀነሱን ከማመልከቱም በላይ ለረዥም ጊዜ የቆየ የክፍያ ሚዛን ኪሣራ እንዳለ የሚያመለክት ነው ። የገንዘብ ምንዛሪ ዋጋ ቅነሳ የአንድን ሀገር የውጭ ንግድ የሚያስፋፋ ነው ቢባልም የዚያን ሀገር የውጭ ዕዳ የሚጨምርና ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች ዋጋ እንዲወደድ የሚያደርግ ነው ። በመሆኑም የገንዘብ ምንዛሪ ዋጋ ቅነሳ የካፒታሊዝምን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ቅራኔ በይበልጥ እንዲፋፋም ያደርገዋል ። የገንዘብ ምንዛሪ ዋጋ ቅነሳ በመሠረቱ የዋጋ መናርንና የቀረጥ መጨመርን ስለሚያስከትል የኑሮ ውድነት እየተባባሰ እንዲሄድ በማድረግ ሠርቶ አደሮችን የሚጐዳ በመሆኑ በካፒታሊስት ሥርዓት ለመደብ ትግሉ መፋፋም ዓይነተኛ ምክንያት ነው ።

የገንዘብ ምንዛሪ ዋጋ ቅነሳ በንግዱና በብድሩ ዘርፍ ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ኋላቀር ሀገሮችን የሚበዘብዙበት አንደኛው ዘዴ ነው ። የውጭ ንግዳቸውን ከዓለም አቀፍ የካፒታሊስት ገበያ ጋር ያቆራኙ ኋላቀር ሀገሮች በኢምፔሪያሊስቶች ቁጥጥር ሥር በሚገኙ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች አስገዳጅነት አልፎ አልፎ የገንዘባቸውን የምንዛሪ ዋጋ እንዲቀንሱ ይገደዳሉ ። የገንዘባቸውን የምንዛሪ ዋጋ እንዲቀንሱ የሚገደዱ ኋላቀር ሀገሮች ከውጭ የሚገዙአቸው ሸቀጦች ዋጋ ስለሚንር በነዚህ ሀገሮች ውስጥ የኑሮ ውድነት ይባባሳል ። ኋላቀር ሀገሮች የገንዘባቸውን የምንዛሪ ዋጋ ከቀነሱ ወደውጭ የሚልኳቸው ሸቀጦች መጠን ይጨምራል ቢባልም ለውጭ ገበያ የሚያቀርቧቸው ሸቀጦች በአብዛኛው ተመሳሳይ በመሆናቸውና አንዱ ኋላቀር ሀገር የሌላውን ኋላቀር ሀገር ገበያ በመጋፋት የሚያድግ በመሆኑ ችግራቸውን ለማሻሻል የሚያስችል እርምጃ ሊሆን አይችልም ። የገንዘቡን የምንዛሪ ዋጋ የሚቀንስ ኋላቀር ሀገር ከውጭ ምንዛሪ ጋር ሲነፃፀር የገንዘቡ ዋጋ ስለሚቀንስ ብድሩን በውጭ ምንዛሪ ለመክፈል መጠኑ የበዛ የሀገር ውስጥ ገንዘብ ያስፈልገዋል ። ስለዚህ የገንዘብን የምንዛሪ ዋጋ መቀነስ የኋላቀር ሀገሮችን የውጭ ዕዳ በማሳደግ እነዚህን ሀገሮች ለበለጠ የኢምፔሪያሊስት ብዝበዛ የሚዳርግ ይሆናል ።

## ገንዘብ ምንዛሪ ዋጋ ጭመራ (የ—)
*(Revaluation)*

ይፋ በሆነ መንገድ የአንድ ሀገር ገንዘብ በእኩያንነት የሚለወጥበትን የወርቅ ወይንም የሌላ ሀገር ገንዘብ የምንዛሪ መጠን መጨመር ወይም በአንድ ሀገር ውስጥ ቀደም ሲል የልውውጥ እሴቱን ቀንሶ የነበረን ገንዘብ ወደ ቀድሞ ቦታው መመለስ የገንዘብ ምንዛሪ ዋጋ ጭመራ ይባላል ።

የገንዘብ ምንዛሪ ዋጋ ጭመራ የሚያስከትለው የኢኮኖሚ ተፅዕኖ የገንዘብ ምንዛሪ ዋጋ ቅነሳ በኢኮኖሚው ላይ ከሚያደርሰው ተፅዕኖ ጋር ተቃራኒ ነው ። አንድ ሀገር ገንዘቡ ከሌሎች ሀገሮች ጋር የሚለወጥበትን የምንዛሪ መጣኔ ሲጨምር ወደውጭ የሚልካቸው ዕቃዎች ይወደዳሉ ። በመሆኑም በዓለም ገበያ ላይ ያለው ድርሻ ይቀንሳል ። ይህም በመሆኑ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የውጭ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዋጋ ስለሚቀንስ የገቢ ንግድ ይጨምራል ።

የገንዘቡን ምንዛሪ ዋጋ በጨመረ ሀገር ውስጥ ያሉ የውጭ ካፒታሊስቶች በልዋጭ የሚያገኙት የሀገር ውስጥ ገንዘብ አነስተኛ ስለሚሆን የውጭ ሙአለ ንዋይን መጠንና ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ቱሪስቶችን ቁጥር ይቀንሳል ። በአንፃሩም የገንዘቡን ምንዛሪ ዋጋ የጨመረ ሀገር ካፒታሉን ወደ ውጭ ሲልክ በልዋጩ የሚያገኘው የውጭ ሀገር ገንዘብ መጠን ስለሚጨምር አትራፊ ይሆናል ። የሀገሬው ሰዎች በቱሪስትነት ወደ ውጭ ሲሄዱ ገንዘባቸው ከሌሎች ሀገሮች ገንዘብ ጋር ሲነፃፀር በዛ ብሎ ስለሚመነዘር የውጭ ቱሪዝምን ያስፋፋል ።

የገንዘብ ምንዛሪ ዋጋ ጭመራ የካፒታሊስት መንግሥታት የዋጋ ንረትን ለመግታት የሚጠቀሙበት አንደኛው ዘዴ ነው ። ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባውን የሙአለ ንዋይ መጠን መቀነስ በዝውውር ውስጥ ያለውን የወረቀት ገንዘብ መጠን ለመቀነስ ያስችላል ። በሌላ በኩል ደግሞ የገንዘብ ምን

ዛሪ ዋጋ ጭመራ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ ዕቃዎች የሚወጣውን ወጪ ስለሚያሳንስ (ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች በሀገር ውስጥ ገንዘብ ሲገዙ ዋጋቸው ስለሚያንስ) የሀገር ውስጥ የዋጋ ደረጃን ለመቀነስ ይረዳል ። በኢምፔሪያሊስት ሀገሮች መካከል ከሚካሄደው ንግድ አንፃር የአንዱ የንግድ ሚዛን ብልጫ የማሳየቱ ሂደት ረዘም ላለ ጊዜ ሲቀጥል ሌላው ኢምፔሪያሊስት ሀገር ይህን ሁኔታ ለመከላከል በንግድ ሚዛኑ ብልጫ ያሳየው ሀገር የገንዘቡን ምንዛሪ ዋጋ እንዲጨምር የተለያየ ተፅዕኖ ያሳድርበታል ።

## ጊልድ
*(Guild)*

ጊልድ እየተባሉ የሚጠሩት በአሥራ ሁለተኛው ምዕት ዓመት መቋቋም የጀመሩና የእደ ጥበብ ባለሙያዎችንና የነጋዴዎችን ጥቅም ለማስከበርና ሙያቸውን ለማዳበር በተለይ በአውሮፓ ሀገሮች የተከሰቱ የመረዳጃ ማኅበር መልክ ያላቸው ድርጅቶች ነበሩ ። በአሥራ አራተኛው ምዕት ዓመት በአውሮፓ ውስጥ እነዚህ ድርጅቶች እጅግ ተስፋፍተውና ተጠናክረው በያንዳንዱ የሙያ ዘርፍ ተደራጅተው ነበር ።

የእደ ጥበብ ባለሙያዎች ከግብርና እየተላቀቁ በከተሞች አካባቢ እንዲሰባሰቡ አመች ሁኔታ የተፈጠረው ፊውዳሊዝም እያረጀና በአንፃሩ ንግድና አነስተኛ ኢንዱስትሪ እየተስፋፋ በመሄዳቸው ነበር ። በከተሞች ውስጥ የሚገኙት የእደ ጥበብ ባለሙያዎች ጊልድ የሚባሉትን ድርጅቶች የፈጠሩት ከፊውዳሎች የሚደርስባቸውን በደልና በተጨማሪም በየጊዜው ወደከተማ የሚጎርፉትን የገጠር የእደ ጥበብ ባለሙያዎችን ውድድር ለመቋቋም ነበር ። በደንቡ መሠረት አንድ ጊልድ የሚያቅፈው አንድ ዓይነት ሙያ ያላቸውን ሰዎች ሲሆን የእነዚህ ድርጅቶች ሽያጭ ፣ የሥራ ጊዜ ፣ የሥልጠና ጊዜ ፣ የተቀጣሪ ፣ የእደ ጥበብ ባለሙያዎችና የረዳቶች ቁጥር ፣ የገበያ ዋጋ ፣ የመዋጮ ክፍያ በደንብ የተወሰኑ ነበሩ ። በአጠቃላይ የድርጅቱ ዋና ተግባር የምርት ሂደት እንቅስቃሴን መቆጣጠር ነበር ። እነዚህ ድርጅቶች በመጀመሪያ ዘመናቸው የእደ ጥበብ ሙያ ውጤቶች በመጠንና በዓይነት እንዲዳብሩ አስችለው ነበር ። ሆኖም የሸቀጥ ምርትና ልውውጥ እየተስፋፋ ሲመጣ ጊልዶች ለምርት ኃይሎች ዕድገት ዕንቅፋት በመሆናቸው ቀስ በቀስ እየከሰሙ በፋብሪካ ያሠራር ዘዴ ተተክተዋል ። ከእደ ጥበብ ባለሙያዎች በተጨማሪ ነጋዴዎችም በጊልድ ተደራጅተው እንደነበረ የታወቀ ነው ።

## ጊልድ ሶሻሊዝም
*(Guild Socialism)*

ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በፊት በእንግሊዝ የሙያ ማኅበራት ውስጥ የተከሰተ ጠጋኝ ዝንባሌ ነው ። ጊልድ ሶሻሊስቶች ፣ የመንግሥትን መደባዊ ጠባይ በመካድ በአሉት የሙያ ማኅበራት መሠረትነት የአምራቾችን የኅብረት ሥራ ማኅበራት አደራጅቶና በፌደሬሽን አዋሀዶ ኢንዱስትሪያዊ አመራርንና አስተዳደርን እንዲተኩ በማድረግ ያለመደብ ትግል ብዝበዛን ለማጥፋት ፣ ቀስ በቀስም የሶሻሊስት ኅብረተሰብን ለመገንባት ይቻላል በማለት በሠራተኛው መካከል ውዥንብር የነዙ ፣ ከጥቅምቱ የሶሻሊስት አብዮት (በሩሲያ) በኋላም ፕሮፓጋንዳቸውን ለማስፋፋት የመደብ ትግሉንና የወዝአደሩን የበላይ ገዥነት በንድፈ ሐሳባቸው ውድቅ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ያደረጉ ናቸው ። ሆኖም በ1920ዎቹ ጊልድ ሶሻሊዝም በእንግሊዝ ወዝአደር ዘንድ የነበረውን ተቀባይነት አጥቷል ። የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ንድፈ ሐሳብ 'በሩሲያ በተግባር' መተርጎም የጊልድ ሶሻሊዝምን ተምኔታዊነት አረጋግጧል ።

## ጊዜ ምንዳ (የ—)
*(Time Wages)*

የተወሰነ የሥራ ጊዜን መሠረት በማድረግ ለወዝአደሩ ክፍያ የሚደረግበት አንድ ዓይነት የምንዳ መልክ ነው ። ይህም ዓይነት ክፍያ በሰዓት ፣ በቀን ፣ በሳምንት ፣ በወር ወዘተ... ሊወሰን ይችላል ።

ካፒታሊስቱ በዚህ የምንዳ አከፋፈል ዘዴ ብዝበዛውን በሁለት መንገዶች ሊያሳድግ ይችላል ። ይኸውም አንደኛው የወዝአደሩን ምንዳ ሳይጨምር የቀኑን የሥራ

ሰዓት በማራዘም ሲሆን ሌላው ደግሞ የሥራ ዕምቀትን ከፍ በማድረግ ነው ።

የጊዜ ምንዳን ከቁርጥ. ሥራ ምንዳ የተለየ የሚያደርገው ከፍያው ከምርታማነትና ከሥራ ዕምቀት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት የሌለው መሆኑና ይህ ደግሞ የወዝ አደሩን የማምረት ፍላጐት የሚቀንስ መሆኑ ነው ። በመሆኑም ቡርዧዚዎች ከጊዜ ምንዳ ይልቅ ወደ ቁርጥ ሥራ ምንዳ አዘንብለው ቢቆዩም ዛሬ በተደረሰበት የቴክኖሎጂ ዕድገት ደረጃ አንድን ሠራተኛ በከፍተኛ የሥራ ዕምቀትና በተወሰነ የምርታማነት ደረጃ ማሠራት የሚያስችሉ መሣሪያዎች በመሠራታቸው የጊዜ ምንዳ እንደገና በተስፋፋ ሁኔታ እየተሠራበት ነው ።

(የቁርጥ ሥራ ምንዳን ፣ የሥራ ዕምቀትን ይመለከቷል ።)

## ጋራ አመራር (የ—)
## *(Collective Leadership)*

በአንድ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ ውስጥ በየደረጃው በአባላት የሚመረጡት የአመራር አካላት ማንኛውንም ውሳኔ በጋራ በመወያየት ፣ በመመካከርና በመተማመን የሚያሳልፉት የአሠራር መርህ የጋራ አመራር ይባላል ። የፓርቲው አመራር በግለሰቦች ፈቃድና ትእዛዝ ሳይሆን በአባላቱ የጋራ አስተሳሰብና የተስተዋለ ውሳኔ አሰጣጥ መርህ ላይ የተመሠረተ ነው ። ይህም የሚሆንበት ምክንያት በተለያየ ደረጃ የፓርቲውን የአመራር ኃላፊነት የሚረከቡት የፓርቲው አባላት በዲሞክራሲያዊ ምርጫ የመጡና ለድርጅታቸው ዓላማ ተግባራዊነት የወል ኃላፊነትና ተጠያቂነትም ያላቸው በመሆኑ ነው ። ስለዚህ ፓርቲው ከጋራ ዓላማውና ከተግባሩ ለሚያፈነግጥ ግለሰባዊ ወይም ቡድናዊ ውሳኔ ቦታ የለውም ።

በፓርቲው ውስጥ የጋራ አመራር መርህ መኖር ፓርቲው ዲሞክራሲያዊ ባሕርይን ይዞ እንዲያድግ የሚረዳ ፣ ህልውናው በአምባገነን ግለሰቦች ወይም በአንጃዎች ተፅዕኖ ሥር እንዳይወድቅ ለማድረግና በአባላቱ ገንቢ ኂሶችና አስተያየቶች በመጠቀም ለችግሮች የማያዳግሙ መፍትሔዎች ለመስጠት የሚያስችል ነው ። የጋራ አመራር የኮሚኒስቶችን ኃይል ፣ ዕውቀትና ልምድ ለማሰባሰብ ፣ ድርጅታዊ ሥራን ለማቀላጠፍና አጥጋቢ ውጤት ለማስገኘት ሰፊ ዕድል ይሰጣል ። በተጨማሪም የተለያዩ ጉዳዮች ከአንድ አቅጣጫ ብቻ እንዳይታዩና የፓርቲው የበላይ አካላት ከሠርቶ አደሩ ሕዝብ እንዳይነጠሉ ይረዳል ። በፓርቲው ውስጥ በአንድ ዓላማ ጥላ ሥር የተሰባሰቡ ኮሚኒስቶች እርስ በርስ ሊማማሩ የሚችሉበትም አሠራር ነው ።

የጋራ አመራር መኖር እያንዳንዱ የፓርቲ አባል በተሰጠው ሥራ የሚኖረውን የኃላፊነት ድርሻ የሚሽር አይሆንም ። እያንዳንዱ የፓርቲ አባል በግል የተሰጠውን ሥራ በሚገባ ማከናወኑ ወይም አለማከናወኑ በግለሰቡ ላይ የተጣለና በሉም ትግልና ጥረት የሚፈጸም መሆን አለበት ። ስለሆነም የጋራ አመራር እያንዳንዱ አባል በተሰጠው የተወሰነ የሥራ ድርሻ ከመጠየቅ የሚያድነው ሳይሆን ከዚሁ ኃላፊነት ጋር የተያያዘ ይሆናል ። ስለዚህ የጋራ አመራር የመሪዎችንና የግለሰብ አባላትን ችሎታ ፣ ልዩ ተሰጥኦ ፣ ታታሪነትና የሥራ ስሜት የሚጫን ሳይሆን እንዲያውም ለግለሰብ አባላት ተሳትፎና የትግል ልምድ መዳበር ሰፊ ዕድል የሚሰጥ ነው።

(ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን ይመለከቷል።)

## ጋራ አክሲዮን ኩባንያ(የ—)
## *(Joint Stock Company)*

ቁጥራቸው በዛ ያሉ ካፒታሊስቶች ካፒታላቸውን በማሰባሰብ የሚያቋቁሙት የጋራ ድርጅት ነው ።

የጋራ አክሲዮን ኩባንያ መከሰት የጀመረው በ16ኛውና በ17ኛው ምዕት ዓመት ውስጥ ነበር ፤ ከመጀመሪያዎቹም ውስጥ "ብሪቲሽ ኢስት ኢንድያ" ኩባንያና "ደች ኢስት ኢንድያ" ኩባንያ በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ ።

በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የካፒታሊስቶች ለመስፋፋት መፈለግና የያዙት ካፒታል ደግሞ የፍላጐታቸውን ያህል በቂ ሆኖ አለመገኘት ፣ እንዲሁም ካፒታሊስቶች ለመ

በዶር ቢፈልጉም የብድሩ መጠን አበዳሪዎች ሊያበድሩ ከሚችሉት መጠን በላይ ሲሆን የማስፋፊያ ካፒታሉን እጥረት ለመቋቋም ካፒታሊስቶቹ የየግላቸውን ካፒታል (በአክሲዮን አማካይነት) እሰባስበው ይሠራሉ ።

የጋራ አክሲዮን ኩባንያ ካፒታል ለመሰብሰብ ከአክሲዮን ሽያጭ ሌላ አረቦን በመሸጥ ይከናወናል ። የጋራ አክሲዮን ኩባንያ የያዘው ካፒታል የጋራ አክሲዮን ካፒታል ይባላል ። ኩባንያውን በባለቤትነት የሚይዙት የአክሲዮን ባለቤቶች ናቸው ።

የኩባንያው የአክሲዮን ባለቤቶች በየዓመቱ አጠቃላይ ስብሰባ እያደረጉ የተለያዩ የኩባንያውን የአመራር አካላት ይሰይማሉ ። በኩባንያው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ አንድ አባል ድምፅ የሚሰጠው እንደያዘው አክሲዮን መጠን ነው ። ጥቂት ትላልቅ ካፒታሊስቶች በኩባንያው ውስጥ በቀላሉ ከፍተኛ ድምፅ ለማግኘት የሚያስችላቸውን አክሲዮን ስለሚገዙ የኩባንያውን አመራር የሚይዙት እነዚሁ ትላልቅ ካፒታሊስቶች ናቸው ። የኩባንያውን አመራር ለመያዝ የሚያስችሉት የአክሲዮን ቁጥሮች የመቆጣጠሪያ አክሲዮን ይባላሉ ። ይሁንና የጋራ አክሲዮን ኩባንያውን የዕለት ተዕለት ተግባራት የሚያከናውኑት ተቀጣሪ ሥራ አስኪያጆች ናቸው ።

በጋራ አክሲዮን ኩባንያ አማካይነት ትላልቅ ካፒታሊስቶች በአነስተኛ ካፒታሊስቶች ካፒታልና በሠርቶ አደሮች ተቀማጭ ገንዘብ በመጠቀም ትርፋቸውን ያደልባሉ ።

(አክሲዮንን ፣ አረቦንን ይመለከቷል ።)

## ጋራ ኢኮኖሚ ተራድኦ ምክር ቤት (የ—)

*(Council for Mutual Economic Assistance CMEA)*

የጋራ ኢኮኖሚ ተራድኦ ምክር ቤት የሶሻሊስት መንግሥታት የኢኮኖሚ ድርጅት ሲሆን የተመሠረተውም በ1949 የቡልጋሪያ ፣ የቼኮዝሎቫኪያ ፣ የሀንጋሪ ፣ የፖላንድ ፣ የሩማንያና የሶቪዬት ኅብረት ተወካዮች ባደረጉት ስብሰባ ውሳኔ መሠረት ነው ። በየካቲት 1949 የድርጅቱ አባል የነበረችው አልባንያ በ1961 ከድርጅቱ በፈቃዷ ወጥታለች ። ጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ በ1950 ፣ ሞንጎሊያ በ1962 ፣ ኩባ በ1972 ፣ ቬትናም በ1978 የድርጅቱ አባል ሀገሮች ሆነዋል ።

ድርጅቱ የተመሠረተባቸው ዓላማዎች የሶሻሊስት ሀገሮች ሕዝቦችን ይበልጥ ማቀራረብ ፣ የቅርብ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ቅብብሮች ማድረግ ፣ ሰላምን ማረጋገጥና ለሶሻሊዝምና ለኮሚኒዝም ግንባታ አመች ሁኔታዎችን መፍጠር ናቸው ። በነዚህ ዓላማዎች አማካይነትም ያልዳበሩ የድርጅቱን አባል ሀገሮች የኢንዱስትሪ ዕድገት ለማፋጠንና በጠቃላይም በአባል ሀገሮች መካከል ፈጣን የኢኮኖሚና የቴክኖሎጂ ዕድገት ለማስገኘት ነው ።

የጋራ የኢኮኖሚ ተራድኦ ምክር ቤት አባል ሀገሮች የኢኮኖሚ ፣ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ትብብር የተመሠረተው በሶሻሊስታዊ ዓለም አቀፋዊነት መርህና በፈቃደኝነት ላይ ነው ። በተጨማሪም የአባል ሀገሮችን ብሔራዊ ነፃነትና ብሔራዊ ልዕልና በማክበር ፣ በአባል ሀገሮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ባለመግባት ፣ ሙሉ እኩልነትን ፣ የጋራ ጥቅምና ጓዳዊ ትብብርን ማካሄድ በሚሉት መርሆች ላይ የተገነባ ነው ። እነዚህን ሁሉ መርሆች ተግባራዊ በማድረግ በአባላት መካከል ያልተቋረጠ የሥራ ምርታማነት ዕድገት በማድረግ የኑሮ ደረጃ ለማሳደግ ከፍተኛ ትግል ያደርጋል ።

የአባል ሀገሮችን ብሔራዊ ዕቅዶች በማስተባበርና በአጠቃላይ የትብብር ዕቅድ በመንደፍ ፣ የተፈጥሮን ሀብት በአግባቡ በመጠቀም ፣ የምርት ኃይሎችን ዕድገት ማስገኘትና የአባል ሀገሮችን በተለያዩ የኢኮኖሚ መስኮች የማተኮር ተግባር ማራመድ የድርጅቱ የዕድገት ስልቶች ናቸው ። በነዚህም ስልቶች ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ፣ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ችግሮች በየጊዜው መፍትሔ ያገኛሉ ። የዚህ የተቀነባበረ ሂደት ውጤት በሶሻሊስት ዓለም አቀፍ የሥራ ክፍፍል መሠረትነት የሚከሰት የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ውህደት ነው ። በጋራ ኢኮኖሚ ተራድኦ ምክር ቤት አባል ሀገሮች መካከል የሥራ ክፍፍል በቅንብር የሚካሄድ ነው ። በድርጅቱ ውስጥ የሚደረጉ ማንኛዎቹም ውሳኔዎችና የሥራ ሐሳቦች በአባል መንግሥታት ስምምነት ብቻ ይከናወናሉ ።

የጋራ ኢኮኖሚ ተራድኦ ምክር ቤትን ዓላማዎችና መመሪያዎች ለመቀበልና የድርጅቱንም ግዴታዎች ለማሟላት ፈቃደኛ የሆነ ማንም ሀገር የድርጅቱ አባል መሆን ይችላል ። የድርጅቱ አባል ያልሆኑ ሀገሮች ከድርጅቱ ጋር የተለያዩ ስምምነቶችን በማድረግ በልዩ ልዩ ደረጃዎች ሊካፈሉ ይችላሉ ። በዚህ መሠረት ዩጎዝላቪያና ሕዝባዊት ኮሪያ ከ1964 ጀምሮ ፣ ፊንላንድ ከ1975 ጀምሮ ባደረጓቸው የትብብር ውሎች የተነሣ በልዩ ልዩ ደረጃዎች ከድርጅቱ ጋር ይሠራሉ ። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አንዳንድ የሶሻሊስት ዕድገት ፈር የሚከተሉ ታዳጊ ሀገሮች በምክር ቤቱ ጉባኤ በተመልካችነት ይሳተፋሉ ፤ ለዕድገታቸውም ልዩ ድጋፍ ያገኛሉ ።

የምክር ቤቱ የበላይ አካል ጉባኤው ሲሆን የዕለት ተዕለት ሥራውንም የሚመራው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ነው ። ምክር ቤቱ ልዩ ልዩ ቋሚ ኮሚቴዎችና ኮሚሽኖች አሉት ። እነዚህ ለምሳሌ እንደዕቅድና ትብብር ኮሚቴ ፣ እንደ ሳይንስና የቴክኖሎጂ ትብብር ኮሚቴ ፣ እንደቁሳቁሳዊና የቴክኒክ አቅርቦት ኮሚቴ ያሉት ሲሆኑ ወደ ሃያ የሚጠጉ ቋሚ ኮሚሽኖችም አሉት ። ምክር ቤቱ ከፍተኛ የጥናትና የምርምር ተቋሞች አሉት ። የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት የሚገኘው በሞስኮ ነው ።

የጋራ ኢኮኖሚ ተራድኦ ምክር ቤትን እንቅስቃሴዎች ከታሪክ አንፃር ከፍሎ ለማየት ይቻላል ። በዚህም መሠረት ከ1949—58 ያለው የምሥረታ ወቅት ሲሆን ይህም በአባል ሀገሮች መካከል የውጭ ንግድ ፣ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ትብብሮችን ለማጠንከር እርምጃዎች የተወሰዱበት ወቅት ነበር ። ከ1958—62 ያለው ደግሞ በአባላት መካከል ኢኮኖሚያዊ የሥራ ክፍፍል መሠረት የተጣለበት እንዲሁም ከ1962—69 ያለው የአባል ሀገሮች የኢኮኖሚ ፣ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ትብብሮች ይበልጥ ተጠናክረው የተካሄዱበት ወቅት ነበር ። ከዚያ ወዲህ ደግሞ ያለው በአባል ሀገሮች መካከል የረዥም ጊዜ የልማት ዕቅዶች ትብብርና ቅንጅት እየዳበረ የመጣበት ወቅት ነው ። የጋራ ኢኮኖሚ ተራድኦ ምክር ቤት ከኋላቀርነት ለመላቀቅ ከፍተኛ ትግል ለሚያደርጉ ሀገሮች ከፍተኛ የቴክኒክ ፣ የቁሳቁስና የኢኮኖሚ ድጋፍ ይሰጣል ።

## ግለሰብ

*(Individual)*

ከሰው ልጅ ዘር አንዱን በተናጠል ስንወስደው ግለሰብ ይባላል ። ይህም ግለሰብ ተፈጥሯዊና ማኅበራዊ ባሕርያት አሉት ። ተፈጥሯዊ ባሕርዩ ሕይወት ያለው መሆኑ ሲሆን ማኅበራዊ ባሕርዩ ደግሞ ግለሰቡ የማኅበረሰብ አካል ፣ የማኅበራዊ ግንኙነት ውጤት መሆኑ ነው ። የማኅበረሰቡ አካል እንደመሆኑም የሰውን አጠቃላይ ባሕርያት ይይዛል ። በሌላም በኩል እያንዳንዱ ግለሰብ የራሱ የሆኑ ልዩ ባሕርያት አሉት ።

በማርክሳዊ ሌኒናዊ አመለካከት ግለሰብ የማኅበራዊ ግንኙነቶች ድምር ውጤት ነው ። ይህም ማለት ግለሰብ መታየት ያለበት ከሚገኝበት ታሪካዊ ወቅትና ማኅበራዊ ሥርዓት አኳያ ነው ። አንድን ግለሰብ ከሌሎች የሚለዩት ሥነ ልቡናዊ ባሕርያት ስሜቱ ፣ ችሎታውና አመለካከቱ የሚቀረፁት ከቤተሰብ ጀምሮ እስከ ኅብረተሰብ ባለው ማኅበራዊ ግንኙነት አንፃር ነው ። ለምሳሌ የግል ሀብትና ግላዊ ውድድር በሰፈነበት ሥርዓት ንብረት አከማችነት ፣ ግለኝነት ፣ ራስ ወዳድነት ፣ በግለሰቡ ባሕርያት ውስጥ ጐልተው ይታያሉ ። እነዚህ የግለሰቡ ሥነ ልቡናዊ አመለካከቶች ሊለወጡ የሚችሉት ከሶሻሊስት ማኅበራዊ ግንኙነት ለውጥ ጋር ተከትሎ በሚመጣው የርዕዮተ ዓለም ትምህርት ነው ።

በጋራ ሀብት ላይ በተመሠረተው ሶሻሊዝም ውስጥ የግለሰቡ አመለካከት ጋርዮሻዊ ነው ። ሶሻሊዝም የግለሰቡ አመለካከት በመተባበርና በመረዳዳት ላይ እንዲመሠረት ሰፊ መድረክ ይከፍታል ። በግንባታው ሂደትም ውስጥ በአእምሮው የበሰለ ፣ በሥነ ምግባሩ የጠራ ፣ በአካል የዳበረ ግለሰብ ይፈጠራል ። ይህም ግለሰብ ከግለኝነትና ከስግብግብነት ነፃ የሆነና “ሰው ለሰው ወንድሙ ፣ ጓደኛውና ጓዱም ነው” የሚለውን መርህ የሕይወቱ መመሪያ የሚያደርግ ነው ።

(ሰውን ይመለከቷል ።)

## ግለሰብና ኅብረተሰብ

*(Individual and Society)*

በግለሰብና በኅብረተሰብ መካከል ያለውን ታሪካዊ ግንኙነት በትክክል የገለጸው ማርክሲዝም ነው ። ሐሳባውያን ግለሰብ ራሱን ችሎ እንደተፈጠረ ነገር አድርገው ስለሚወስዱ ማኅበራዊ ኑሮን የሚመለከቱት ተጨማሪ ወይም ቅጥያ አድርገው ነው ። በነሱ አመለካከት ኅብረተሰብ በግለሰብ ውስጥ ተፈጥሮአዊ መሠረት ስለሌለው ቅድሚያና ከፍተኛ ፋይዳ የሚሰጠው የሰው ግላዊ ባሕርይ ነው። ይህ የሐሳባውያን አመለካከት ጨርሶ በታሪክ የተደገፈ አይደለም ። ታሪክ የሚያስተምረው በተለይም ጥንታዊ ማኅበረሰቦችን አስመልክቶ እንደሚለው ግለሰቡ ከኅብረተሰቡ የተለየ ነገር እንደሌለውና ከሱም ጋር አንድ እንደነበረ ነው ። ግለሰቡ ከማኅበረሰቡ እራሱን ለይቶ ማየት የጀመረው ኅብረተሰቡ እያደገና ውስብስብ እየሆነ ሲሄድ ነው ። በተለይም ካፒታሊዝም ለግላዊነት ኢኮኖሚያዊ መሠረት (የግል ንብረት) በመስጠቱ ግላዊነት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ከመድረሱም በላይ ግለሰቡንና ኅብረተሰቡን ተፃራሪ ኃይሎች አድርጐ አስልፏቸዋል ።

የጋራን ጥቅምና የግለሰብን ጥቅም ተደጋጋፊ በማድረግ የተስተካከለ ግንኙነት እንዲኖራቸው ሊያደርግ የሚችለው የኮሚኒስት ሥርዓት ነው ። የግለሰቡ ጥቅም ሊረካ የሚችለው በወል ጥቅም ማደግ ፣ የወል ጥቅም ማደግ የሚችለው በግለሰቡ ንቁ ተሳትፎ መሆኑን በማስተማርና በተራድኦ ላይ የተመሠረተ የምርት ግንኙነት በመቀየስ ኮሚኒዝም በሁለቱ መካከል የጥቅምና የፍላጐት አንድነት በመፍጠር ተደጋጋፊ ኃይሎች ያደርጋቸዋል ።

(ግለኝነትን ይመለከቷል ።)

## ግለሰብ ንብረት-በሶሻሊዝም (የ—)

*(Personal Property under Socialism)*

በሶሻሊዝም ውስጥ ግለሰቦች በሠሩት መጠን ያገኙት ገቢ ፣ ከገቢያቸው ያደረጉት ቁጠባና በፍጆታ ዕቃዎች ላይ ያላቸው ባለቤትነት ነው ።

በሶሻሊዝም የግለሰብ ንብረት መሠረታዊ ምንጭ በመንግሥት ይዞታ ሥር ያሉ ድርጅቶች ሠራተኞች የሚያገኙት ደመወዝ ፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባል የሆኑ ዜጐች በአባልነታቸው የሚያገኙት ድርሻ ነው ። በተጨማሪም ከአነስተኛ የግለሰብ የጓሮ እርሻ የሚገኘውም ገቢ ፣ ለማኅበራዊ ፍጆታ ከሚውለው ገንዘብ ውስጥ ለአዛውንቶች መጦሪያ የሚመደበው ፣ እንዲሁም በድጐማና በስጦታ መልክ የሚሰጠው ገንዘብ የግለሰብ ንብረት ተጨማሪ ምንጭ በመሆን ያገለግላል ።

በሶሻሊዝም የምርት መገልገያዎች በማኅበራዊ ንብረትነት የተያዙ በመሆናቸው የግለሰብን ንብረት አንድ ሰው ሌላውን ለመበዝበዝ ሊጠቀምበት አይችልም ።

በሶሻሊዝም ውስጥ የግለሰብ ንብረት እያንዳንዱ ባበረከተው የሥራ ድርሻ መጠንና ዓይነት ላይ የተመሠረተ መሆኑ ሠራተኛው በትጋት እንዲሠራ የሚያበረታታና ማኅበራዊ ጥቅምና የግለሰብ ጥቅም መጣጣም የሚገለጽበት ፈርጅ እንዲሆን አድርጐታል።

የግለሰብ ንብረት የምርት ኃይሎች በሚገኙበት የዕድገት ደረጃ ፣ ሶሻሊዝም እንደሚገነባበት ተጨባጭና ታሪካዊ ፣ ብሔራዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ደረጃና ልዩነት የሚለዋወጥ ታሪካዊ ፈርጅ ነው ።

በሶሻሊስት ሀገሮች ውስጥ የግለሰብ ንብረት በሕግ የሚከበር ወይንም የተደገፈ ነው ። ለምሳሌ በሶቭዬት ኅብረት ሕገ መንግሥት ውስጥ የግለሰብ ንብረት እንደአንድ መሠረታዊ የሶቭዬት ዜጐች መብት ተደንግጓል ። በዚህም መሠረት እያንዳንዱ ዜጋ የግለሰብ ንብረቱን ለመሸጥ ፣ ለመለወጥ ፣ ለማዋስና ለሌላ ሰው ለመስጠት የመቻል መብቱ የተጠበቀ ነው ።

በሌላ በኩል የፍጆታ እምላኪነት ባሕርይንና በሶቭዬት ዜጐች መካከል ያለውን የኑሮ ልዩነት ለማጥበብ እንዲቻል አንዳንድ ገደቦችም በሕጉ ውስጥ እንዲጠቃለሉ ተደርጓል ። ለምሳሌ የአንድ ግለሰብ ንብረት ሊሆን የሚችለው መኖሪያ ቤት ስፋትና የኅብረት ሥራ ማኅበር አባል የሆነ ገበሬ ሊኖረው የሚችለው የጋማም ሆነ የቀንድ ከብት ከፍተኛው ቁጥር በሕግ የተደነገገ ነው ።

## ግለኝነት

*(Individualism)*

ግለሰብ የሕይወት መሠረትና እንቀሳቃሽ ኃይል በመሆኑ የኅብረተሰቡ የበላይና ባለሙሉ መብት ነው የሚል ሐሳባዊ አስተምህሮ ነው ። ይህ አመለካከት የተመሠረተው ግለኝነት የሰው ተፈጥሮአዊ ባሕርይ ነው በሚለው ብያኔ ላይ ነው ።

የግለኝነት መደባዊ ትርጉም ግልጽ ነው ። ኅብረተሰቡን በግል ጥቅሞች ለማስገዛት ማለትም የግል ንብረትን ሕጋዊ አድርጎ ለማቅረብ ሰው በተፈጥሮ ግለኛ ነው የሚለው አመለካከት አስፈላጊ ነው ። የግል ንብረት የበላይነት በበኩሉ አስተሳስብን እየለወጠ ሲመጣ ግለኝነት የሰው የተፈጥሮ ባሕርይ ነው የሚለውን እምነት ይፈጥራል ። የኃይልን የበላይነት የሚሻ ፥ በሰዎች መካከል ተፈጥሮአዊ ልዩነት አለ የሚሉ ነፃዊና ኅሊናዊ አመለካከቶችን የሚከተሉ ፈላስፎች የግለኝነት አራማጆች ናቸው ።

በአንፃሩም አመለካከቱ የሚዘነጋው ጭቆናና ብዝበዛ ባለበት ሥርዓት ውስጥ የግለሰቡ ችሎታና ስጦታ ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ ሊውልና ሊዳብር እንደማይችል ነው ። ግለሰቡን ማሳደግ ማለት ግለኝነት እንደሚለው ከኅብረተሰቡ ጋር ማጋጨት ሳይሆን ተራድኦአዊ ግንኙነቶችን በመመሥረት የግለሰቡ ዕድገት ማኅበራዊ ድጋፍ እንዲያገኝ ማድረግ ነው ።

(ግለሰብና ኅብረተሰብን ይመለከቷል ።)

## ግላዊ ካፒታል

*(Individual Capital)*

እያንዳንዱ ካፒታሊስት ግለሰብ ወይም ድርጅት በተናጠል ያለው ካፒታል ግላዊ ካፒታል ይባላል ። በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የኅብረተሰብ ምርት የሚካሄደው በግለሰብ ካፒታሊስቶችና ድርጅቶች መካከል ተከፋፍሎ ነው ። እያንዳንዱ ካፒታሊስት ድርጅት በአንድ ካፒታሊስት ወይንም ቁጥራቸው በተወሰነ ካፒታሊስቶች በግል በመያዝ ከሌሎች ካፒታሊስት ድርጅቶች ነፃ ሆኖ ይሠራል ። ጠቅላላ የኅብረተሰቡ ካፒታል በዚህ ዓይነት በግለሰብ ካፒታሊስቶች እጅ ተከፋፍሎና ተይዞ ይገኛል ። እነዚህም ካፒታሊስት ድርጅቶች ከፍተኛ ትርፍ ለማግኘት ባላቸው ዓላማ ላይ ተመሥርተው በዚህ ዓይነት የምርት እንቅስቃሴውን ሲያካሂዱ እንቅስቃሴያቸው ያልተቀናጀ ከመሆኑም በላይ ኢኮኖሚው በአጠቃላይ በዕቅድ ስለማይመራ በየጊዜው ለሚከሰቱ ልዩ ልዩ ቀውሶች የተጋለጠ ነው ። የሚመረቱትም የምርት ዓይነቶች በዓይነትና በብዛት አንፃር ሲታዩ ከኅብረተሰቡ ፍላጐት ጋር የሚጣጣሙ አይደሉም ።

(ማኅበራዊ ካፒታልን ይመለከቷል ።)

## ግልብ ቁስአካልነት

*(Vulgar Materialism)*

ለወጉ ያህል በቁስ አካል ቀዳማይነት ላይ የተመሠረተ ፥ ነገር ግን መሠረታዊ የሆኑትን የቁስአካላዊ ፍልስፍና መርሆችን በጥልቀት ሳይሆን ላይ ላዩን ብቻ የተረዳ ፥ በአሥራ ዘጠነኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ላይ በጀርመን ውስጥ የታየ የፍልስፍና አዝማሚያ ነው ። ይህ የፍልስፍና አዝማሚያ ከተፈጥሮ ሳይንሶች ዕድገት ጋር የቅርብ ግንኙነት ስለነበረውና የእነርሱንም አዳዲስ ግኝቶች በመጠቀም የሐሳባውያንና የነዚህም ቀደምት የሆኑትን የሃይማኖታዊያንን ንጽረተዓለም በአጠቃላይ ፥ በተለይም ደግሞ የጀርመን ሐሳባውያንን ንጽረተዓለም ቁንጽል በነበረው የቁስአካልነት ግንዛቤው መሣሪያነት ይታገል ነበር ።

ግልብ ቁስአካልነት የፍልስፍናን ሚና በመካድ ለፍልስፍና ነክ ጥያቄዎች በሳይንስ የምርመራ ውጤቶች አማካይነት መፍትሔ ለመሻት ይጥር ነበር ። ግልብ ቁስአካልነት እንደ ዲበ አካላዊ ቁስአካልነት ኅሊናና አስተሳሰብ በአካሎቻችን ውስጥ የሚከናወኑት የነርቮች እንቅስቃሴ ውጤቶች ናቸው ይላል ። በአመጋገባችንና በአካባቢው ጠባይ ላይ የተመሠረቱ እንደሆኑም አድርጐ ይወስዳቸዋል ። ከቁስ አካል ጋር አንድ እንደሆኑ አድርጎ በመውሰዱ "የእሞት ከረጢት እሞትን እንደሚያመነጭ ሁሉ አእምሮአችን ደግሞ ሐሳብን ያመነጫል" በማለት ሐሳብ ከቁስአካል ጋር ተመሳሳይ ነው ይላል ።

ማርክሲዝም ግን ሐሳብ ከቁስአካል ባይገነጠልም ሐሳባችን "በአእምሮአችን ውስጥ የሚገኝ የእውነታ ምስል እንጂ ቁስአካል አይደለም" በማለት በኅሊናዊ ክስተቶችና በቁስአካል መሀል ያለውን ግንኙነትና ልዩነት ያሳያል ።

(ኅሊናን ይመለከቷል ።)

## ግልብ እውንነት
*(Naïve Realism)*

ነገሮች ከሰዎች ኅሊና ውጭ ይኖራሉ የሚልና በማንኛውም ሰው አመለካከት ውስጥ የሚገኝ ግብታዊ ቁስአካላዊ አመለካከት ነው ። ይህ አመለካከት ስለነገሮች ንድፈ ሐሳባዊና ሳይንሳዊ ግንዛቤ አይሰጥም ። በተለይም ስለሐሳብና ስለቁስአካል ልዩነት አይመራመርም ። በመሆኑም እንደነበርክሌይና እንደነማች ያሉት ፈላስፎች ለግልብ እውንነት ኅሊናዊ ሐሳባዊ ትርጉም በመስጠት ኅሊናዊውንና ነባራዊውን ወደሚያጥህደው ሕውስታዊነት አምርተዋል ።

(ሕውስታዊነትን ፣ በርክሌይን ይመለከቷል ።)

## ግልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ
*(Vulgar Political Economy)*

ኢሳይንሳዊ የሆኑ የቡርዧ ኢኮኖሚ ንድፈ ሐሳቦች የተጠራቀሙበት አመለካከት ሲሆን የኢኮኖሚ ሂደቶችን ውስጣዊ ይዘት ሳይሆን በውጫዊ እይታቸው ላይ የሚያተኩር ለካፒታሊስት ሥርዓት ቀይታ የቆመና የሚታገል የቡርዧ ኢኮኖሚ አመለካከት ነው ።

ግልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የተከሰተው በኢንዱስትሪ አብዮት አማካይነት ወዝአደሩ መደባዊ ንቃተ ኅሊናው መዳበር በጀመረበትና የቡርዧው መደብ ከተራማጅነት ወደ አድኅሪነት በተቀየረበት ወቅት ነው ።

ግልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን የተካ የኢኮኖሚ አመለካከት ነው ። በኢኮኖሚ አመለካከት ረገድ የግልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ገና መውጣት በቡርዧ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ቀውስ መጀመሩን አመለከተ ።

የግልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ዕድገት በአራት ዋና ዋና ደረጃዎች የተከፋፈለ ነው ። እነሱም ፣

1ኛ/ በሮበርት ማልተስና በጆን ባቲስት ሴይ አማካይነት በ19ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ላይ ከብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የተለየና እራሱን የቻለ አመለካከት በመሆን መከሰቱ ፤

2ኛ/ ከ1830ዎቹ ጀምሮ እስከ 1870ዎቹ ዓመታት ባለው ጊዜ ውስጥ በሚል ፣ በናሳው ሲኒዮር ፣ በፍሬደሪክ ባስቲያት፣ በሽር ሂልደርባንድና በኬሪ አማካይነት መስፋፋትና የበላይነትን የያዘ የኢኮኖሚ አመለካከት ለመሆን መቻሉ ፤

3ኛ/ በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም በተለይም ደግሞ ከ1870ዎቹ ጀምሮ እስከ 1920ዎቹ ዓመታት ድረስ የኅሊናዊና የሥነ ልቡናዊ አመለካከት አራማጅ በነበሩት በነቦም ባቬርክ ፤ በነአልፍሬድ ማርሻል ፣ በነክላርክ ፤ በነሽሞለር እና በነስቶልዝማን አማካይነት ዕድገቱን መቀጠሉ ፤

4ኛ/ በቅርቡም ካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ ውስጥ ከገባ ጀምሮ በሹምፒተር ፣ በሀይክ ፣ በሚዝስና በመሰሎቻቸው አማካይነት የመጨረሻ የዕድገት ደረጃው ላይ መድረሱ ናቸው ።

ግልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ከብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ኢሳይንሳዊ የሆኑ አመለካከቶችን በመምረጥ "ሥርዓት" ባለው መንገድ ለማቅረብ በመሞከር ለብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አስተምህሮ መፍረስ ምክንያት ሆነ ። ግልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በመጀመሪያዎቹ ሁለቱ የዕድገት ደረጃዎች በካፒታሊዝም ውስጥ ያለውን ብዝበዛ ለመሸፈን ፣ ተምኔታዊና ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን ለመዋጋት በማሰብ የኢኮኖሚ ግንኙነቶች ጥናት በውስጣዊ ይዘት ሳይሆን በውጫዊ እይታ ላይ እንዲያተኩር አድርጓል ።

ለምሳሌ የእሴት የሥራ ንድፈሐሳብን በመሻር ፣ በመጀመሪያ እሴትን በምርት ወጪ ንድፈ ሐሳብ ፣ በኋላም በኅሊናዊ የእሴት ንድፈ ሐሳብ ተክቶታል ። በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የሠራተኛው እንቅስቃሴ መጠናከርና

የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መስፋፋት ባስከተለው ግፊት ካፒታሊዝምን ከውድቀት ለማዳን ገልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አዳዲስ ዘዴዎችን መቀየስ ጀመረ ። በዚህም መሠረት የኢኮኖሚ ሂደት የሚመራባቸውን ሕጎች ከኢኮኖሚ ጥናት ውጭ አደረገ ።

የዘመናችን ገልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በዛ ያሉ የቡርዧ ኢኮኖሚ ንድፈ ሐሳቦች ይገኙበታል ። እነዚህ ሁሉ አመለካከቶች ዞር ዞር ለካፒታሊስት ሥርዓት ህልውና መጠበቅና መጠናከር የቆሙ ናቸው ።

በአሁኑ ወቅት ገልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የኢኮኖሚ ግንኙነቶችን በሚመለከት የተዋሀደ ንድፈ ሐሳብ ባይኖረውም አንዳንድ አጠቃላይ የሆኑ መለያ ጠባዮች አሉት ። በመጀመሪያ ደረጃ ገልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ማኅበራዊና ታሪካዊ ክስተቶች ነባራዊና ተጨባጭ የሆኑ ጠባዮች ያላቸውና በተወሰኑ ሕጎችም የሚመሩ መሆናቸውን አይቀበልም ። በአንፃሩ በማኅበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ለተጨባጭ ሕጎች ሳይሆን ለኅሊናዊ ሁኔታዎችና አመለካከቶች ቅድሚያ ይሰጣል ። በመሆኑም የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ጥናት ተጨባጭ በሆኑ የማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሕጎች ላይ ሳይሆን “በበቂ መጠን በማይገኙ ሀብቶች አጠቃቀም” ላይ ፣ “ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን በማግኘት ዘዴ” ብቻ እንዲያተኩር ያደርጋል ።

ገልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ካፒታሊዝም አላፊና ጠፊ የሆነ ሥርዓተ ማኅበር መሆኑን አይቀበልም ። በእሴት የሥራ ንድፈ ሐሳብ ምትክ በልውውጥ ሂደት የሸቀጦች እሴት የሚለካው ጠቀሜታ በሚል ኅሊናዊ በሆነ የእሴት ንድፈ ሐሳብ ወይም እሴትን ሳይሆን ዋጋ የሚመሠረተው በአቅርቦትና በፍላጐት መጣጣም ነው በሚል ተክቶታል ።

የካፒታልን ማኅበራዊ ሚናም በሚመለከት የገልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አመለካከት የተዛባ ነው ። በመጀመሪያ ገልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ካፒታልን ማኅበራዊ ግንኙነት ሳይሆን ከማኅበራዊ ግንኙነት ውጭ ለብቻው እንደቆመ የምርት መገልገያ ፣ ሸቀጥና ገንዘብ እንደሆነ አድርጐ ያቀርበዋል ። ለዚህም ነው በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የገቢ ምንጭ ሥራ ፣ መሬትና ካፒታል ናቸው የሚለው ኢሳይንሳዊ አመለካከት የመነጨው ። በዚህ ኢሳይንሳዊ አመለካከት መሠረት ኪራይ ከመሬት እንደሚመነጭ ፣ ወለድ ከካፒታል ፣ ምንዳ ከሥራ የሚገኝ በመሆኑ እያንዳንዱ ምርትን ለማምረት አስፈላጊ የሆነው ነገር ሁሉ የሚገባውን ያገኛል ። ማለትም የገልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አመለካከት ወዝአደሩ ሥራ ሠርቶ ምንዳ እንደሚያገኝ ሁሉ ካፒታሊስቱ ደግሞ ካፒታሉን ለግል ፍጆታው ከማዋል ይልቅ ለምርት ሥራ በማዋሉ ትርፍ ማግኘቱ ተገቢ ነው ። ይህ በመሆኑ ገልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በካፒታሊዝም ውስጥ ብዝበዛ ለሚባል ነገር ቦታ አይኖረውም ይላል ።

የካፒታሊስቱን ሥርዓት በየጊዜው ወደ ቀውስ የሚዘፍቀው የበላጥ ምርት ቀውስ በገልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አመለካከት ጨርሶ ቦታ እንደሌለው ወይም በሥርዓቱ ውስጥ ሊታረም የሚችል እንደሆነ አድርጎ ያቀርባል።

(ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን ይመለከቷል ።)

## ገልገል
*(Arbitration)*

ሠራተኞችን በካፒታሊስቱ መንግሥት እግር ብረት የሚቀፈድድ ማለትም ዘለዓለም የምንዳ ባሮች ሆነው እንዲቀሩ ለማድረግ የሚጥር ጠንቀኛ የፀረ ሠራተኛ መደብ አቋም ነው ። ገልገል “መንግሥት አስታራቂ ነው ፣ መንግሥት ከካፒታሊስቱ ወይም ከሠራተኛው ጐን የተሰለፈ ሳይሆን ገለልተኛ ነው” ለሚለው የተሳሳተ አባባል ጥሩ ምሳሌ የሚሆን ነው ።

በካፒታሊስት ሀገሮች ሠራተኞችንና አሠሪዎችን ለመገላገል (ማስማማት) ሲባል የኢንዱስትሪ ኮሚሽን ወይም ሕጋዊ ሥርዓት ያለው የፍርድ ቤት ተቋም ይመሠረታል። በተግባር የሚያከናውነው ግን የሥራ ማቆም አድማን መከላከል ፣ ሠራተኞች ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃን እንዲቀበሉ በሕግ ማስገደድ ፣ ሆን ተብሎ ሠራተኞችን በጥቅም መከፋፈል ፣ በሠራተኛው ማኅበራት ውስጣዊ ጉዳይ ጣልቃ መግባትና የመሳሰሉት ናቸው ።

የመደብ ትብብርን የሚሰብኩ ጠጋኞች የገልገል ጽኑ ደጋፊዎች ናቸው ። እንደእውነቱ ከሆነ ግን ከገልገል ጋር የተቆ

ራኙ የሠራተኛ ማኅበር የካፒታሊስቶችን የመደብ ፖሊሲ በሥራ ላይ እንደሚያውል ተወካይ ወይም መሣሪያ ይቆጠራል ። ምክንያቱም ሠራተኛው አልፎ አልፎ የሚያስገኘውም መጠነኛ ጥቅም ቢሆን በማኅበሩ ተጠናክሮ ሲገኝ ብቻ ነው

(የመደብ ዕብረትን ይመለከቷል ።)

## "ግራ" ክንፍ ኮሚኒዝም
*("Left" Wing Communism)*

ብስለት ከማጣት የተነሣ ስህተቶችን የሚፈጽም ፣ በኮሚኒስት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚከሰት አዝማሚያ ነው ። "ግራ" ክንፍ ኮሚኒዝም የአብዮት ሕጎችን የማይረዳ ፣ ተጨባጭ ሁኔታዎችን የማይመለከት ፣ ችኩልና በስሜት ኃይል ብቻ የሚንቀሳቀስ ነው ። አብዮታዊ ሁኔታዎች ባልበሰሉበት ወቅት የአመፅ ጥሪ ማስተላለፍ ፣ በፓርቲ] ውስጥ መኖር ያለበትን ጠንካራ ዲሲፕሊን አለመቀበል ፣ የቡርዧ ፖለቲካዊ ሥርዓት በሚፈቅዳቸው ዲሞክራሲያዊ መድረኮች ለመጠቀም አለመፈለግ፣ ሁኔታዎች የሚጠይቁትን አንዳንድ ድርድሮች ለማድረግ ፈቃደኛ አለመሆን ወዘተ... የ"ግራ" ክንፍ ኮሚኒዝም ገጽታዎች ናቸው ።

"ግራ" ክንፍ ኮሚኒዝም የትግልን ስልት የማይረዳና ከተጨባጩ ውጭ የሚቆም በመሆኑ ለአብዮታዊ እንቅስቃሴ አደገኛ ሁኔታ የሚፈጥር ፣ በአንፃሩም አብዮቱን በማስጠቃት ተሸናፊ የሚያደርግ አዝማሚያ ነው ።

(አድርባይነትን ፣ ጽንፋዊነትን ይመለከቷል ።)

## ግብ
*(Purpose)*

በአእምሮ ውስጥ የታቀደና ሰው በተግባር ሊያከናውነው የተነሣሣበት ማንኛውም ነገር ግብ ይባላል ። በሐሳባውያን አመለካከት የግብ በአሳቦት ውስጥ በቅድሚያ መቀረፅ የሚገልጸው የሐሳብን የበላይነትና አድራጊነት ነው ። ከዚህም በመነሣት ሐሳባውያን ዓለምና በዓለም ውስጥ ያሉ ነገሮች በሙሉ ታቅደው የተሠሩ ናቸው በማለት ሐሳብን ፈጣሪ አድርጉ ለማቅረብ ሞክረዋል ።

ሆኖም የግብ ትክክለኛ ትርጉም ሐሳባውያን እንደሚሉት አይደለም ። ግብ የሚጸነሰው በሐሳብ ውስጥ ቢሆንም መነሥኤውና ምንጩ ነባራዊው እውነታ ነው ። ግብ ከተጨባጭ ሁኔታ ካልተነሣ በራሱ ሐሳባዊ ኃይል ብቻ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም። ይህ የሚያስረዳው ነባራዊው ሁኔታ ቀዳሚ መሆኑንና ግብ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለውም ተጨባጩ በትክክል የተገመገመ እንደሆን ነው ።

(ሥነ ግብን ይመለከቷል ።)

## ግብታዊነት
*(Spontaneity)*

ነገሮችን በጥልቀት ሳያጤኑ የሁኔታዎችንም ውጤት ሳያመዛዝኑ በነሲብ የሚፈጸም አድራጐት ነው ። ሆኖም ግብታዊነት ፈጽሞ ግንዛቤ የሌለው ነው ማለት አይደለም። የግብታዊው ተግባር ፈጻሚ ተግባሩን አሳቀደውም ፣ ሂደቱን አልተቆጣጠረውም ፣ የሚያስከትለውንም ውጤት አልተገነዘበውም ፣ ቢገነዘበውም ግንዛቤው ያጋጣሚ በመሆኑ የተሟላ አይደለም ማለት ነው ። በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ፍልስፍና ግን ግብታዊነት ራሱን የቻለ ያንድ ግለሰብ ፣ ቡድን ወይም መደብ ማኅበራዊ ተግባር ሆኖ ከዚህም የሚመነጭን ማኅበራዊ ሂደትና ባሕርይ ይጠቁማል ።

በግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ተግባር መደባዊ ባሕርይ እንዳለው ሁሉ ግብታዊነትም የመደብ ባሕርይ አለው ። አብዛኛውን ጊዜ አብዮታዊ እንቅስቃሴዎችና ሕዝባዊ አመፆች የሚነሡት በግብታዊነት ሲሆን መሠረታቸው የፍትህና የእኩልነት አለመኖርና ይህንንም ሁኔታ በአብዮታዊ እንቅስቃሴ የመለወጥ ምኞት ነው ። ይህ ሁኔታ ሕዝቡን ለማደራጀትና ለፓርቲ አመራር መንገድ ጠራጊ ነው ። ስለዚህ ነው ሌኒን ግብታዊነት የግ

ንዛቤ ጽንስ ነው ያለው ። ይሁን እንጂ ግብታዊነት በአደረጃጀቱ የተመሰቃቀለ ፣ ታክቲክ አልባና ለፀረ አብዮተኞች ቅልበሳ አመች ሁኔታ የሚፈጥር ነው ። ስለዚህ የሠራተኛው ፓርቲ በግብታዊነት የተነሣሣውን ሕዝብ በፖለቲካና በርዕዮተዓለም በማንቃትና በማደራጀት የግንዛቤውን ደረጃ ከፍ ማድረግ ይኖርበታል ። ስለሆነም የኮሚኒስቶች ተግባር ግብታዊነትን መዋጋት ይሆናል ።

ግብታዊነት በአብዛኛው የቅድመ ሶሻሊዝም ሥርዓተ ማኅበሮች ዓይነተኛ ባሕርይ ነው። በተለይም በካፒታሊዝም ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሕይወት በዕቅድ የሚመራ አለመሆኑና የምርት ሥርዓት አልበኝነት መኖር ለማኅበራዊ ሕይወት በግለኝነት መበታተንና ለግብታዊ አሠራር መስፈን አመች ሁኔታን ፈጥሯል ። በአንፃሩም ደግሞ በሶሻሊዝም የማዕከላዊ ዕቅድና የጠንካራ የፓርቲ አመራር መኖር ለሕዝባዊ ዲሲፕሊንና ለታቀደ ሕይወት መዳበር መሠረት ነው ።

## ግብታዊ ዲያሌክቲክስ

*(Spontanious Dialectics)*

ተፈጥሮ በሐሳብ ላይ ያለው ተፅዕኖ ለሰዎች ግልጽ ሳይሆንላቸውና እራሳቸውም ሳያውቁት በዲያሌክቲክስ አስተሳሰብ መጠቀማቸውን የሚገልጽ የቁስአካላዊ ዲያሌክቲክስ የአስተሳሰብና የምርምር ዕድገት ዝቅተኛ ደረጃ ነው ። ይህም የሰዎች አስተሳሰብ ከተሟላ የግንዛቤ ደረጃ ላይ ባለመድረሱና ሥርዓት ባለው ሁኔታ ባለመገለጹ ግብታዊ ዲያሌክቲክስ ከተሳሳቱ አመለካከቶች (ለምሳሌ ዲበ አካላዊ አመለካከት) ጋር በመደባለቁ የተጣራና የተጠናከረ አልነበረም ። በእርግጥም የተፈጥሮ ዕድገት ዲያሌክቲካዊ እንደመሆኑ ሰዎች ስለተፈጥሮ የሚኖራቸው አስተሳሰብ ምንም ጊዜ ቢሆን ከዲያሌክቲካዊ አስተሳሰብ ሙሉ በሙሉ ነፃ ሊሆን አይችልም ።

የግብታዊ ዲያሌክቲክስ መኖር ራሱ የዲያሌክቲክስን ሕግ የሚገልጽ ነው ። ነገሮችና ክስተቶች ከትንሽ ወደ ትልቅ ፣ ከቀላል ወደ ውስብስብ ፣ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ እንደሚያድጉ ሁሉ ሐሳብም ዕድገቱን በግብታዊ ዲያሌክቲክስ በመጀመር የዕድገት ሕግን እየተከተለ ከሳይንሳዊ ዲያሌክቲክስ ደረጃ ላይ ይደርሳል ። ይህ ዕድገት ግን እራሱ በራሱ የሚመጣ ሳይሆን የተወሰነ ሳይንሳዊ ዕውቀትን ፣ የነገሮችን ውስጣዊ ግንኙነትና የዕድገትን ውስብስብ ጎዳና መረዳትን ይጠይቃል ። የካፒታሊዝም ማደግ ፣ የምርት ኃይሎች መሻሻልና የምርት ዕድገት ከፍተኛ የአስተሳሰብ ዘዴን የሚጠይቅ በመሆኑና ግብታዊ ዲያሌክቲክስም ለዚህ የሚረዳ ሆኖ ባለመገኘቱ ግብታዊ የነበረው ዲያሌክቲክስ ሳይንሳዊ መሠረት አግኝቶ ወደ ቁስአካላዊ ዲያሌክቲክስ ደረጃ ተሸጋግሯል ።

(ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነትን ይመለከቷል ።)

## ግንባር

*(Front)*

ለጋራ ዓላማ በአንድ አመራር ሥር በመጠቃለል የሚታገሉ የተለያዩ ኃይሎች የሚሰባሰቡበት የፖለቲካ መድረክ ነው ።

በዓለም ሠራተኞች እንቅስቃሴ ታሪክ ውስጥ በግንባር እየተደራጁ ዲሞክራሲያዊ ትግል ማካሄድ የተለመደ ነበር ። የግንባሩ አባል ድርጅቶች በተወሰነ ፕሮግራም ላይ የዓላማ አንድነት ይፈጥሩና ባንድ አመራር ሥር ሆነው ትግላቸውን አካሂደው ግባቸውን ከመቱ በኋላ የኅብረቱ ውል ያከትማል ፤ ግንባሩም ይበተናል ። በዚህ አገባቡ ግንባር ጊዜያዊ ቡድን ነው ።

የብሔራዊ እርነት ኃይሎች ተከስተው ፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግል ከጀመሩ በኋላ "ግንባር" የተረጋጋና ሳይንሳዊ መለኪያዎች ያሉት ፈርጅ ለመሆን በቃ ። የግንባር ድርጅቱ ከፍ ያለ ዘለቄታም ያለው ሆነ ። በግንባሩ ሥር የሚሰባሰበው ለብሔራዊ እርነት የቆመው ሰፊው ሕዝብ ነው ። ዓይነተኛ ዓላማው ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እርነትን መቀዳጀት ስለሆነ የግንባሩ አባላት ሁሉ ባንድ ዘላቂ ፕሮግራም ይተሳሰራሉ ። በፖለቲካ ነፃነት ትግል ውስጥ ግንባሩ አንድ ወጥ የሚሆንበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል ።

(ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ይመለከቷል።)

## ማንባር ቀደም
*(Vanguard)*

በሠራተኛው መደብ እንቅስቃሴ ውስጥ መሪ ኃይል የሆነው የሠራተኛው መደብ ፓርቲ ግንባር ቀደም ይባላል ። አንድ ግን ባር ቀደም ኃይል እውነተኛ ግንባር ቀደም የሚሆነው ብዙኀኑን አንቅቶና አደራጅቶ መምራትና ማራመድ ሲችል ብቻ ነው። ይህ የግንባር ቀደምትነት ሚና ባስተማማኝ ሁኔታ ሊሳካ የሚችለው ፓርቲው በሳይንሳዊ ንድፈ ሐሳብ ሲመራ ብቻ ነው ።

(ፓርቲን ይመለከቷል ።)

## ግንዛቤ
*(Cognition)*

ከተግባር ጋር በተሳሰረ ሁኔታና የኅብ ረተሰብ የዕድገት ሕጎች በሚወስኑት አንፃር እውነታን በሰው አሳቦት ውስጥ መቅረ ፅና ማንፀባረቅ ግንዛቤ ይባላል ። የግንዛቤ ዋና ግብ ከነባራዊ እውነታ ላይ መድረስ ነው ።

ግንዛቤ ውስብስብ የሆነን ዲያሌክቲካዊ ሂደት የሚያሳይ በተለያዩ መልኮች የሚከሰ ትና የራሱ የዕድገት ደረጃ ያለው ነው ። በልምድና በተግባር ላይ በመመሥረት ግን ዛቤ የሚጀምረው ከሕውስታና ከልባዌ ነው። ሰው አካባቢውን ሊቃኝ የሚችለው ስለ ነገሮች ሕውስታ ሲኖረው በመሆኑ የሕውስታ ሚና ከፍተኛ ነው ። በሕውስታና በልባዌ ሰው ነገሮችን (ቀለምን ፣ ሽታን ፣ ክብደትን ወዘተ...) ይለያል ። በአእምሮ ውስጥ በሚፈ ጠረው የነገሮች ምስል አማካይነትም ግንኙ ነቶችን ነፃ በሆነና በረጋ መንፈስ ይመለከ ታል ። ሆኖም የሕውስታ አስፈላጊነት ከፍተኛ ቢሆንም ወደ ነገሮች ምንነትና የእውነታ ሕጎች በሕውስታ ብቻ ለመድረስ አይቻልም ።

የግንዛቤ ዋና ሚና የሚታየው እነዚህን ሕውስታዊ መረጃዎች በሰው የግንዛቤ ከፍተኛ መሣሪያዎች (አርቅቆት ፣ ምክንያዊ አስተ ሳሰብ ወዘተ...) አማካይነት በጽንሰ ሐሳብ ፣ በብያኔና በድምደማ መልክ ሲጠቃለል ነው ። በዚህ በማጠቃለል ሂደት ውስጥ ቋንቋ ፣ ምንጩታና መስተጋብእ ከፍ ያለ ሚና ይጫ ወታሉ ።

ግንዛቤ የሚሰጠው ኅሊናዊ ሐሳቦችን በመሆኑ የእነዚህ ሐሳቦች ከእውነታ ጋር የመዛመድ ጥያቄ መነሣቱ አይቀርም ። ይህ ጥያቄ መልስ የሚያገኘው በንድፈ ሐሳባዊ አውጠንዋናት ሳይሆን በማኅበራዊ ታሪካዊ ሂደት ውስጥ ነው ። የግንዛቤ እውነትነት የሚረጋገጠው ማኅበራዊ ተግባር በግንዛቤው አማካይነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተፈ ጥሮአዊና ማኅበራዊ ኃይሎችን መቆጣጠር ሲችል ነው ።

(አርቅቆትን ፣ ሕውስታን ፣ ዕውቀትን ይመ ለከቷል ።)

## ግዛተ አፄ
*(Empire)*

በንጉሥ ነገሥት የሚመራ ንጉሣዊ አገዛዝ የተመሠረተበት መንግሥት ነው ። ግዛተ አፄ አብዛኛውን ጊዜ በጣም ሰፊ ግዛት ሲሆን ሌሎችን ሕዝቦችና መንግሥ ታት በመውረር ከራሱ ሀገር ጋር ቀላቅሎ የሚገዛ ነው ። አንዳንድ ግዛተ አፄዎች በሥራቸው የሚተዳደሩ ብዙ የንጉሥች ግዛ ቶች ይኖሯቸዋል ።

ከክርስቶስ ልደት በፊት በአንደኛው ምዕት ዓመት መገባደጃ ላይ አውግስጦስ ቄሳር ሥልጣን ከያዘ በኋላ የሮማ ግዛተ አፄ ትመሠረተ ። ሌሎችም ግዛተ አፄዎች በአን ዳንድ ሀገሮች ተቋቁመው ነበር ። ሩሲያ በ1721 ከነገሠው ከቀዳማዊ ጴጥሮስ ጀምሮ የዘውድ አገዛዙ እስከተገረሰሰበት እስከ 1917 ድረስ ግዛተ አፄ ነበረች ።

ግዛተ አፄ የሚለው ቃል ብዙ ቅኝ ግዛቶች ለነበሯቸው ሀገሮችም የተሰጠ መጠ ሪያ ነው ። ለምሳሌ የእንግሊዝ ግዛተ አፄ ታላቋ ብሪታንያንና ቅኝ ግዛቶቿን የሚያ ጠቃልል ነበር ።

## ግዴታና አጋጣሚ
*(Necessity and Chance)*

በቁስአካላዊው ዓለም ውስጥ የሚገኙ ሁለት ዓይነት ነባራዊ ግንኙነቶችን የሚ ገልጹ የፍልስፍና ፈርጆች ናቸው ።

ግዴታ ከክስተቶች ውስጣዊ ፍሬ ነገር (ባሕርይ) የሚመነጭና ድግግሞሻቸውን ፣ ሥርዓትና እወቃቀራቸውን የሚያመለክት ነው ። ግዴታ ከነገሮችና ከክስተቶች ምንነትና ውስጣዊ ባሕርይ የሚመነጭ እንጂ ውጫዊ ገጽታቸው አይደለም ። ግዴታ በአንድ ሁኔታ ውስጥ ሊገታ የማይችል ፣ መሆን (መፈጸም) ያለበት ፣ ቋሚና ጽኑ ነው ።

አጋጣሚ የዕድል ጉዳይን ፣ በአንድ ሁኔታ ውስጥ ሊሆን ወይም ላይሆን የሚችልን ግንኙነት የሚያመለክት ነው ። አጋጣሚ ከነገሮች ወይም ከክስተቶች ውስጣዊ ባሕርይ ወይም ምንነት (ፍሬ ነገር) የሚመነጭ ሳይሆን የሌሎች ውጫዊ ክስተቶች ተፅዕኖ ውጤት ነው ። አጋጣሚ ከክስተቶች ውስጣዊ ባሕርይ የማይመነጭ በመሆኑ ውጫዊ ፣ ቋሚ ያልሆነ ፣ ተለዋዋጭና ጊዜያዊ ነው ። ተፈጻሚነት ላይኖረውና ሊገታ የሚችል የግንኙነት መልክ ነው ።

ዲበ አካል በግዴታና በአጋጣሚ መሀከል ያለውን ሁለንታዊ ግንኙነት አይቀበልም ። በአንድ በኩል እንዳንድ ዲበ አካላዊ ፈላስፎች የግዴታን መኖር በመካድ አንዳንድ ክስተቶችን ወደ አጋጣሚ ደረጃ ዝቅ ሲያደርጉ ሌሎቹ ደግሞ የአጋጣሚ መኖርን በመካድ ማናቸውንም ነገር ከግዴታ የሚመነጭ እንደሆነ አድርገው ይወስዳሉ ። ሁለቱም ቢሆኑ የአጋጣሚንና የግዴታን ግንኙነት አንድ ገጽታ ብቻ በማጋነንና ወሳኝም እንደሆነ አድርገው በመውሰዳቸው የተሳሳቱ ናቸው ።

የግዴታን ሚና የሚክደው አመለካከት የክስተቶችን እንቅስቃሴ ወይም የዕድገትን አዝማሚያ ወይም አቅጣጫ ፣ ሰው ያለውን የመገንዘብና ለርሱም እንደሚጠቅሙት አድርጎ የመለወጥን ችሎታ የሚክድ ነው ። ስለሆነም ሰው ስለተፈጥሮና ስለኅብረተሰብ እንቅስቃሴና ዕድገት ሕግጋት ለማወቅ እንደማይችል የሚያስመስል ፣ የአጋጣሚና የዕድል ተገዥ የሚያደርግ ነው ። የአጋጣሚ ነገር ሊመጣ ወይም ላይመጣ ስለሚችል ስለተፈጥሮና ስለማኅበራዊ ክስተቶች ምንነት ፣ አነሣሥ ፣ ዕድገትና እንቅስቃሴ ፣ እነዚህንም ክስተቶች የሚገዙትን ሕግጋት ለማወቅ እንደማይችል አድርጎ ስለሚያቀርብ ደግሞ የሳይንሳዊ ዕውቀትን ዕድገት ከመካዱም በላይ ሰውን የአምልኮ ተገዥ ያደርጋል ። ምክንያቱም ማናቸውም ነገር በአጋጣሚ እንደተነገ ተደርጎ የሚከሰት ከሆነ እንዴትና መቼ ሊመጣ እንደሚችል ለማወቅ ፣ በቅድሚያ ለማየትና ጉዳቱን ለመቀነስ የሚረዱ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ስለማይቻል ግብታዊነትንና አምልኮን ይፈጥራል ።

በሌላም በኩል ቢሆን የአጋጣሚን ሚና የሚክደው አመለካከት ማናቸውንም ነገር ወይም ክስተትና ድርጊት ግዴታ አድርጎ የሚያቀርብ በመሆኑ የሰውን ሚና ዝቅ የሚያደርግ ነው ። ማናቸውም ክስተት በግዴታ መሆን ወይም መፈጸም ያለበት ከሆነ ሰው ሁኔታውን ሊለውጥ ወይም እንዳይሆን ለማድረግ አይችልምና "በቅድሚያ እንዲሆኑ የተወሰኑ ነገሮች" ተገዥ እንዲመስል ያደርገዋል ። የድርጊቶች ተፈጻሚነት የግዴታ ከሆነ ሰው ሊለውጣቸው ስለማይችል ሊያደርሱበት የሚችሉትን ጉዳት ሊያስቀርለት የሚችል ሌላ ውጫዊ ኃይል እንዲፈልግ ወይም እንዲማጠን ያስገድደዋልና ለአምልኮ በር የሚከፍት የተሳሳተ የግዴታና የአጋጣሚ ግንዛቤ ነው ።

ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ግን በግዴታና በአጋጣሚ መሀከል ያለውን ሁለንታዊ ግንኙነት በትክክል ስለሚገነዘብ ለተጠቀሱት ዓይነት ችግሮች ሳይንሳዊ መፍትሔ ይሰጣል ። ምክንያቱም ክስተቶች ሁለንታዊ በሆኑ ውስጣዊ ግንኙነቶች የተያያዙ በመሆናቸው እያንዳንዱ ክስተት ከሌሎች ክስተቶች ጋር በሚያስፈልጉ ወይም በማያስፈልጉ ግንኙነቶች ተያይዞ ሊገኝ ይችላል ማለት ነው ። ስለሆነም በአንድ ወይም በበርካታ ክስተቶች እንዲሁም በየእንዳንዱ ሂደት ውስጥ ከሚገኙት በርካታ ባሕርያት ውስጥ አስፈላጊ (የግዴታ) ወይም የማያስፈልጉ (አጋጣሚ) ባሕርያትን (ግንኙነቶችን) ለይቶ ለማውጣት ይቻላል ። በሂደቶች ውስጥ ግዴታ እንደዋነኛው አቅጣጫና የዕድገት አዝማሚያ የሚከሰት ቢሆንም ይህ የዕድገት አዝማሚያና አቅጣጫ ግን በበርካታ አጋጣሚ ሁኔታዎች ውስጥ የሚያልፍ ነው ።

ግዴታና አጋጣሚ ዲያሌክቲካዊ ተቃርኖ ቢኖራቸውም ማምራ ህልውና ያላቸው በመሆናቸው አንዱ ካለሌላው ሊኖር የሚችል አይደለም ። እያንዳንዱ ድርጊት የራሱ ምክ

ንያት ያለው በመሆኑ የሁለንታዊ መንሥኤና ተገብሮት ግንኙነት አንድ ክፍል ነው ። ግዴታ ይህን ግንኙነት የሚገልጽ በመሆኑ ከሁለንታዊው የማይገነጠል ፣ እንዲሁም ፍጹማዊና ሁለንታዊ ግንኙነቶችን የሚያቅፍ ነው ። እያንዳንዱ ክስተት የሚከሰተው በውስጣዊ ግዴታ የተነሣ ሲሆን ይህ ክስተት ግን ህልው እንዲሆን ከሚረዱት በርካታ ውጫዊ ሁኔታዎች ጋር የተዛመደ ነው ። ከነዚህ በርካታና ውጫዊ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ወይም ሁለቱ በቀጥታ ከድርጊቱ ጋር መዛመዳቸው ግን የአጋጣሚ ጉዳይ ነው ። ለምሳሌ የአንድ ሰው መሞት ግዴታ ሲሆን በጦርነት ፣ በመኪና ፣ በኤሌክትሪክ ወይም በሌላ አደጋ በመጠጥ ፣ በቁንጣን ወይም በበሽታ መሞቱ የአጋጣሚ ጉዳይ ቢሆንም በአንዱ ወይም በሌላው መሞቱ ምክንያት እስከሆነ ድረስ የግዴታ ውጤት ነው ። ይህም ማለት አንድ ድርጊት አጋጣሚ ቢሆንም አጋጣሚው ግን ምክንያት ያለው ነው ። ከላይ በተጠቀሰው ምሳሌ ላይ እንደተመለከተው ሰውየው በአንዱ ሁኔታ መሞቱ አጋጣሚ ቢሆንም በአንዱ ሁኔታ የተነሣ የሰውየው መሞት ግን የሞቱ ምክንያት ነው ። ይህ ነጥብ አጋጣሚ ምክንያት እንዳለው ብቻ ሳይሆን አጋጣሚው ምክንያት በመሆን ወደ ግዴታ የሚለወጥ እንደሆነ ያሳያል ። ግዴታም የራሱን ዕድል (አጋጣሚ) ይፈጥራል ።

(መንሥኤንና ተገብሮትን ፣ ይሁንታና እውነታን ፣ ፈርጆችን ይመለከቷል ።)

## ግገግ

(*Recovery*)

በካፒታሊስታዊ የማምረት ሥርዓት ውስጥ አንድ የኢኮኖሚ ቀውስ ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ የሚቀጥለው ያኢኮኖሚ ቀውስ እስከሚጀምርበት ጊዜ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ከሚገኙ አራት ልዩ ልዩ የኢንዱስትሪ ዑደት ደረጃዎች መካከል ሦስተኛው ግገግ ይባላል ። ግገግ የሚመጣውም ከዝቅጠት ቀጥሎ ነው ። ምርት በሚያገግምበት በዚህ ደረጃ በቀውሱ ጊዜ ከስረው ከመዘጋት የዳኑ ድርጅቶች በዝቅጠት ደረጃ የጀመሩትን ቋሚ ካፒታል የማደሱን ተግባር ይቀጥላሉ ፤ ምርታቸውንም ማሳደግ ይጀምራሉ ። ምርትና ዝውውርም ቀስ በቀስ በማደግ ቀውስ ከመጀመሩ በፊት ከነበሩበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ ። ንግድ ይስፋፋል ፤ የሸቀጣ ሸቀጦች ዋጋ ከፍ ይላል ፤ ሥራ አጥነትም ቀስ በቀስ ይቀንሳል ። ካፒታሊስቶችም ከፍተኛ ትርፍ ያጋብሳሉ ። የካፒታሊስት ምርት በዚህ አኳኋን መጠኑ እያደገ ሄዶ ቀውሱ ከመጀመሩ በፊት የደረሰበትን ከፍተኛ ደረጃ መብለጥ ሲጀምር ግገግ ወደ አራተኛው ደረጃ ማለትም ወደ ድራት የሚያደርገውን ሽግግር ይጀምራል ።

(ቀውስን ፣ ድራትን ይመለከቷል ።)

## ጎታ ፕሮግራም (የ—)

*(Gotha Programme)*

በ1875 የጀርመን ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ ያጸደቀው የኅብረት ፕሮግራም ነው ። በዚህ ፕሮግራም መሠረት የሶሻል ዲሞክራቲክ የሠራተኞች ፓርቲና የጀርመን ሠራተኞች ጠቅላላ ማኅበር "የጀርመን ሶሻሊስት ሠራተኛ ፓርቲ" ለመመሥረት ተባበሩ ። የኅብረቱ ዓላማ የሠራተኛውን መደብ ነፃ ለማውጣትና በጀርመን ምድር ሶሻሊዝምን ለማስፈን ነበር ።

የሶሻል ዲሞክራቲክ የሠራተኛ ፓርቲ ለኅብረቱ መመሥረት ከፍተኛ ጉጉት ስለነበረው ወትሮ የማያምንባቸውንም አንዳንድ መርሆች ለመቀበል ተገደደ ። በኅብረቱ ፕሮግራም መሠረት ከሠራተኛው መደብ ውጭ የሆኑ መደቦች ሁሉ (ገበሬውም ጭምር) የአድኃርያን ጥርቅሞች ናቸው ። ምንም እንኳ ሠራተኛውን ነፃ ማውጣትና ሶሻሊዝምን ማስፈን የፕሮግራሙ ዓላማ ቢሆንም ይህን ግብ ሊያስመታ የሚችለው ቁልፍ ነጥብ ማለትም የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት መርህ ፈጽሞ አልተነሣም ። ወዝአደሩን ለድል ባለቤትነት የሚያበቁት ትግሎች ሁሉ በፕሮግራሙ ውስጥ ምንም ትኩረት ስላልተሰጣቸው የአድርባዮች ተፅዕኖ በጉልህ ታየ ። በተለይም ምንዳን በሚመለከት የሶሻል ዲሞክራቲክ ሠራተኛ ፓርቲ የነበረውን ማርክሳዊ አቋም ሽሮ የተሳሳተውን የላሳልን መርህ ተቀበለ ። በመሆኑም ማርክስ "ክሪቲክ ኦፍ ዘ ጐታ ፕሮግራም" በተሰኘው መጽሐፉ የፕሮግራሙን ጉድለቶች ሁሉ ግልጽ አድርጎ አሳይቷል ።

የጀርመን ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ በ1891 በኤርፉርት ከተማ ባደረገው ጉባኤ ላይ የዚህን ፕሮግራም ጉድለቶች በግል ጿት ከፍተኛ አርምጃ አሳይቷል ። ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን በሠራተኛው መደብ ትግል ውስጥ ዋነኛውን ቦታ የያዘው ፣ ማለትም የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት ጥያቄ በኤርፉርት ፕሮግራምም ውስጥ ትኩረት አላገኘም ።

(ላሳሊዝምን ይመለከቷል ። )

## ጓድ
*(Comrade)*

ለሶሻሊዝምና ለኮሚኒዝም ድል አድራጊነት በሚደረገው የመደብ ትግል በግንባር ቀደምትነት ሰፊውን ሕዝብ በመምራት በመሥዋዕትነት የታገሉና የሚታገሉ ተራማጅ ኃይሎች ፣ ታጋይ አብዮታውያንና የሰፊው ሕዝብ ወዳጆች እርስበርስ የሚጠራሩበት የትግል አንድነትን የሚገልጽ የወል ስም ነው ። በመሆኑም የትግል አጋርነትን ፣ የሰፊው ሕዝብ ቤዛነትን ፣ ሰብአዊ እኩልነትንና አንድነትን የሚጠቁም ጽንሰ ሐሳብ ነው ።

ቃሉ ማንም ሰው ተነሥቶ በራሱ የሚካነው ወይም የሚሞካሸበት ተራ ስም ሳይሆን ለሕዝባዊ ዓላማ በቁርጠኝነት መታገልንና መሥዋዕት ለመሆን ዝግጁ መሆንን የሚያመለክት ጥልቅ ትርጉምና መልዕክት ያለው ክቡርና ታላቅ መጠሪያ ነው ።

(ተራማጅን ፣ ኮሚኒስትን ይመለከቷል ።)

# ጠ

## ጠርጣሪነት
*(Scepticism)*

በሕዋሳት አማካይነት ከምናገኛቸው መረጃዎች እንሥቶ እስከ ከፍተኛው ረቂቅ ዕውቀት ድረስ ያሉትን በሙሉ ያለአንዳች ልዩነት አጠራጣሪና ሊታመኑ የማይችሉ መሆናቸውን ለማስገንዘብ የሚጥር የሐሳባዊ ፍልስፍና ገጽታ ነው ። በሕዋሳት አማካይነት በአእምሮአችን ውስጥ የሚቀረፁ ሐሳቦች ከኛ ውጭ በሚገኙ ነገሮች የተፈጠሩ በመሆናቸው እነዚህ ሐሳቦች የሚያንፀባርቋቸውን ነገሮች ይመስላሉ ለማለት አይቻልም የሚል አቋም አለው ። ስለእውነታ ነባራዊ ዕውቀት ለማግኘት የሚቻል መሆኑን የሚጠራጠር እንዲያውም የማይቀበል በመሆኑ ጠርጣሪነት ከኢታዋቂነት ጋር ተመሳሳይነት አለው ። አጠቃላይ ተቀባይነት ያለውንና በተግባር ሊረጋገጥ የሚችልን ዕውቀት ለማግኘት መቻልን መጠራጠር የጠርጣሪነት ሁለንታዊ ባሕርይ ነው ። ጠርጣሪነት ዋና ባላንጣ አድርጎ የሚመለከተው ቀኖናዊነትን በመሆኑ የዕውቀትን እውነትነት አጠራጣሪ መሆን ለማሳየት የሚጥር ከፍልስፍና መጸነስ ጀምሮ የነበረ አቋም ነው ።

ጠርጣሪነት በኅብረተሰብ ዕድገት ውስጥ ተስፋፍቶ የሚገኘው አሮጌዎቹ ማኅበራዊ አስተሳሰቦች ለመውደቅ በሚንገዳገዱበትና አዲሶቹ አስተሳሰቦች ደግሞ ገና ተጠናክረው በማይገኙበት ወቅት ነው ። የአንደበተኞችን ፈለግ በመከተል የመጀመሪያዎቹ ጠርጣሪዎች ዕውቀት አንፃራዊ እንደሆነ ፣ የዕውቀትን ትክክለኛነት በፍጹም ለማረጋገጥ እንደማይቻልና ዕውቀትም በተለያዩ ሁኔታዎች እንደሚወሰን ይገምቱ ነበር ። ለምሳሌ አንድን ጠረጴዛ ስንመለከት የተወሰነ ቁመት ፣ ስፋት ወዘተ... ያለው ይመስለናል ፤ ሆኖም ያንኑ ጠረጴዛ ራቅ ካለ ቦታ ሆነን ብንመለከት ቁመቱና ስፋቱ ተቀይሮ (አንሶ) እናገኘዋለን ። ጠረጴዛው ያው ሆኖ ይህን የመሰለ ልዩነት መገንዘባችን በሕዋሶቻችን አማካይነት የምናገኘው መረጃ አጠራጣሪ መሆኑን ያሳያል ። በአእምሮአችን ውስጥ የሚገኘው ሐሳብ ብቻ በመሆኑ የሐሳብ ምንጭ ቁስአካል ወይም ሐሳብ ነው ለማለት አይቻልም ። ስለዚህ መሆን ያለበትና ትክክለኛው አቋም እውነትን ጨብጫለሁ ማለት ሳይሆን ዕውቀታችን አጠራጣሪ መሆኑን ተረድተን ዕውቀት የዓለምን ምሥጢር እንዲፈታልን ከመጠየቅ ይልቅ ለተግባር እንደ ሁኔታው በመጠቀም ያለጠብና ያለ ክርክር በመስማማት የይመስለኛል አቋም ይዞ ለመኖር መሞከር ያሻል ይላል ።

በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ የጠርጣሪነትን ሚና ከሁለት አቅጣጫዎች ማየት ያስፈልጋል ። የዕውቀት እርግጠኛ አለመሆን አመለካከቱ አፍራሽ ነውና በኅብረተሰቡ ውስጥ በተወሰነ ጊዜ ታምናባቸው ለአገዛዝ ይጠቅማሉ የተባሉ ሐሳቦችን በተለይም በሃይማኖት መሠረታዊ እምነት (በእግዚአብሔር መኖር ፣ በነፍስ ዘለዓለማዊነት ወዘተ ...) ላይ ጥርጣሬ የሚያሳድር በመሆኑ የገዥውን መደብ ርዕዮተዓለማዊ አመለካከት ያናጋል ። ሰዎች እውነትን ወይም ትክክለኛውን ዕውቀት ለማግኘት እንዲጥሩ ስለሚያደርግ ለምርምር በር ይከፍታል ። ስለሆነም የዚህ ፍልስፍና ተከታዮች በተለያዩ ጊዜያት የገዥው መደብ ጥቃት ደርሶባቸዋል ። ሆኖም ጠርጣሪነት መሀን የሆነ ፍልስፍና ነው ። ነገሮችን በጥርጣሬ ደረጃ ላይ ብቻ ከማስቀመጥ (መወሰን) በስተቀር አፍራሽ የሆነውን ትራኔ ነጥሉ በማውጣት ስለማይታገል ፣ ነገሮችን እንዳሉ የመቀበል ወይም የገዥ መደቦችን ጥቅም ያለመቃወምን አዝማሚያ ማስከተሉ አይቀርም ። ምክንያቱም ስለነገሮች ምንም ትክክለኛ ዕውቀት ለማግኘት አይቻልም ማለቱ ጠርጣሪነት ነገሮችን ለመለወጥ የሚረዳ የማያቀርበው የተለየና ተቃዋሚ አመለካከትና እውነት ስለሌለው ነው ፤ አሮጌውን አፍርሶ አዲስ ሥርዓት ለመገንባት የሚያስችል ሐሳብ ሊወልድ ስለማይችል ነው ።

በሁለተኛ ደረጃ ጠርጣሪነት በሕዋሳት መረጃ ላይ የሚፈጥረው ጥርጣሬ ደካማ በመሆኑ ተቀባይነት አያገኝም ። በሌላ

በኩል ሐሳባዊ ፍልስፍናን ለመዋጋት የሚረዳ ትክክለኛ ዘዴ የለውም ። ዕውቀት ምንም ጊዜ እርግጠኛ ሲሆን ባለመቻሉ ማናቸውንም ነገር መጠራጠር ያስፈልጋል ማለት ብቻ ሐሳባዊ ፍልስፍናን ለማዳከም በቂ አይደለም ። የሐሳባዊ ፍልስፍና ዋና ድክመት በተጨባጩ ሁኔታ ላይ አለመመሥረቱ ሲሆን እሱን ለመዋጋት ዋናው ዘዴ የተጨባጩን ሁኔታ ነባራዊነት አጥብቆ በመረዳትና በዚህ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ አመለካከት በመቅረፅ ሐሳባዊነትን መታገል ነው ። ስለሆነም ሁለንታዊ ጥርጣሬ እራሱ ጠርጣሪነትን ከሐሳባዊ ፍልስፍና የተለየ አያደርገውም ።

(ኢታዋቂነትን ፣ አንፃራዊና ፍጹማዊ ዕውነትን ይመለከቷል ።)

## ጠቀሜታ እሴት (የ—)

*(Use Value)*

ማናቸውም የሰው ጉልበት የፈሰሰበት ምርት አንድን የተወሰነ የሰው ፍላጐት የሚያረካ መሆን ይኖርበታል ። ሰዎች የሰውን ፍላጐት ለማርካት ለማይጠቅሙ ነገሮች ጉልበታቸውን በከንቱ አያባክኑም ። ስለዚህ የሰው ጉልበት ውጤት ምንጊዜም የሰዎችን ፍላጐት ለማርካት የሚውል ነው ። (የሥራ ኃይል ውጤት ያልሆኑ የጠቀሜታ እሴት ያላቸው እያሌ ነገሮች አሉ ። ለምሳሌ አየር ፣ ውሀ ፣ የፀሐይ ብርሃን ፣ ወፍ ዘራሽ ተክል ወዘተ . . )

የአንድ ምርት ወይም የሥራ ኃይል ውጤት የሰውን ፍላጐት የማርካት ኃይል ወይም የማርካት ባሕርይ የጠቀሜታ እሴት ይባላል ። ማናቸውም የጠቀሜታ እሴት የሚከስተው በፍጆታ ሂደት ውስጥ ነው ። ለምሳሌ የእርሳስ የጠቀሜታ እሴት የሚገለጸው ለጽሑፍ አገልግሎት ስንጠቀምበት ይሆናል ። እንዲሁም የአንድ ማረሻ የጠቀሜታ እሴት የሚገለጸው ሲታረስበት ነው ። የጠቀሜታ እሴት የሰውን ፍላጐት ለማርካት በሚውልበት መልኩ ሲታይ በሁለት መሠረታዊ ክፍሎች ይከፈላል ፤

1. የፍጆታ ዕቃዎች ፤— እነዚህ ማናቸውንም የሰዎችን ፍላጐት በቀጥታ ለማርካት የሚጠቅሙ ነገሮችን የሚያጠቃልሉ ሲሆን በጣም መሠረታዊ ከሆኑት ከምግብ ፣ ከልብስ ፣ ከመጠለያና ከመሳሰሉት አንሥቶ ለቅንጦት እስከሚፈለጉ እስከ ጌጣጌጥ ፣ እስከ ሽቶ ፣ ወዘተ... ድረስ ያሉትን የሚያጠቃልሉ ናቸው ።
2. የምርት መገልገያዎች ፤— በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ የሰውን ፍላጐት ለማርካት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለማምረት የምንጠቀምባቸው የማምረቻ መሣሪያዎች ፣ ጥሬ ዕቃዎች ፣ የማምረቻ ሕንፃዎችና የመሳሰሉትን ያጠቃልላሉ ።

የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጐቱን ለማርካት የሚጠቀምባቸው ነገሮች በብዛትም በዓይነትም ከሳይንስና ከቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር እያደጉ መጥተዋል ። እንደሚታወቀው የሰው ልጅ በብረት መጠቀም የጀመረው ከተወሰነ የዕድገት ደረጃ ላይ ሲደርስ ነው ። በተመሳሳይ መልኩ ሰው በታሪኩ ውስጥ በከሰል ፣ በነዳጅ መጠቀም የጀመረው ከጥቂት መቶ ዓመታት ወዲህ ነው ። ከሳይንስና ከቴክኖሎጂ ዕድገት ጋርም የብዙ ነገሮች የጠቀሜታ እሴት እየሰፋ መጥቷል ። ለምሳሌ በአንድ ወቅት ለኃይል ምንጭነት (ለማገዶነት)ና ለቤት መሥሪያነት ብቻ ይጠቅም የነበረው እንጨት ዛሬ ወደ 30ሺ የሚጠጉ የተለያዩ የጠቀሜታ እሴት ያላቸውን ነገሮች ለማምረት እንደሚጠቅም ታውቋል ። በሌላ በኩል የሥራ ኃይል ውጤት የሰዎችን ፍላጎት የማርካት ባሕርዩ ከማናቸውም ሥርዓተ ማኅበር ጋር ያልተያያዘ በመሆኑ የጠቀሜታ እሴት በማናቸውም ዕድገት ደረጃ የሚኖር ክስተት ነው ።

## ጠቃሚያዊነት

*(Utilitarianism)*

የማንኛውም ግብረገብ ትክክለኛነት መመዘኛው የሚሰጠው ጥቅም ነው የሚል የቡርዧ ሥነ ምግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ነው ። ይህም ንድፈ ሐሳብ በያንዳንዱ ግለሰብ ጊዜያዊና ግላዊ ፍላጐት መሟላት ላይ የተመሠረተና የማንኛውም ተግባር ትክክለኛነት ወይም ስህተተኛነት በሚያስከትለው የደስታ ወይም የሥቃይ መጠን እንደ ሒሳብ ስሌት ሁሉ ሊተመን ይችላል የሚል ነው ።

እንደጠቃሚያዊነት አመለካከት ሕግና መንግሥት መደባዊ መሠረትና ይዘት የላቸውም ። ስለዚህም ሕግና መንግሥት ለመላው ኅብረተሰብ እንደቆሙ በመቁጠር መኖራቸውን ጠቃሚ አድርጎ ይቀበላል ። ይህ አመለካከት በግላዊ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተና የነገሮችን ውስጠ ባሕርይ ጠልቆ የማይመራመር ነው ። ነገሮችን ከጠቀሜታቸው አንፃር የማየት መርህ እያደረ ገቢራዊነት ለተባለው የቡርዧ ፍልስፍና መነሻ ሆኗል ።

(ገቢራዊነትን ፣ ተጨባጫዊነትን ፣ ዊሊያም ጀምስን ይመለከቷል ።)

## ጠቅላላ ማኅበራዊ ምርት
*(Gross Social Product)*

በአንድ ኅብረተሰብ ወይንም ሀገር በአንድ በተወሰነ የጊዜ ክልል ፣ በአንድ ዓመት ውስጥ የሚመረቱትን ቁሳዊ ምርቶች የሚያጠቃልል ነው ። ይህም ማለት ጠቅላላ ማኅበራዊ ምርት የሚመለከተው በአንድ ኅብረተሰብ በአንድ ዓመት ውስጥ ቁሳዊ ምርቶችን በማምረት ተግባር ላይ የተሰማሩ አምራች ድርጅቶች ሁሉ በሚያደርጉት የማምረት እንቅስቃሴ አማካይነት የሚመረቱ ጠቅላላ ቁሳዊ ምርቶችን ነው ።

በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ልዩ ልዩ ቁሳዊ ምርቶች ያለማቋረጥ ለፍጆታ የሚውሉ ስለሆኑ የማምረት ሂደት ያለማቋረጥ ከዓመት ወደ ዓመት መካሄድ አለበት ። የማምረት ሂደት ያለማቋረጥ ካልተካሄደ የኅብረተሰቡ ህልውና ሊቀጥል አይችልም ። ስለዚህ የማንኛውም ኅብረተሰብ ህልውና መሠረት ቁሳዊ ሀብትን ያለማቋረጥ ማምረት ነው ።

ጠቅላላ ማኅበራዊ ምርት የሚመረተው ምርታዊ በሆኑ እንደ ኢንዱስትሪ ፣ እንደ እርሻ ፣ እንደ ሕንፃ ሥራ በመሳሰሉ መስኮች በመሆኑ ሊያድግ የሚችለውም በእነዚሁ መስኮች ቁሳዊ ነገሮችን በማምረት የተሰማሩ ሠራተኞች ቁጥር ሲጨምርና ምርታማነታቸውም ሲያድግ ነው ።

ጠቅላላ ማኅበራዊ ምርትን በቁሳዊና በእሴት መልኩ ማየት ይቻላል ። ከቁሳዊ መልኩ አንፃር ሲታይ ጠቅላላ ማኅበራዊ ምርት በሁለት ይከፈላል ። አንደኛው ክፍል እንደምግብና እንደ ልብስ ያሉ የሰውን ፍላጐት በቀጥታ ለማርካት የሚችሉትን የፍጆታ ምርቶች ያጠቃልላል ። ሁለተኛው ክፍል ደግሞ እንደ ሞፈርና እንደ እርሻ መኪና ያሉ የሰውን ፍላጐት በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ማለትም የፍጆታ ዕቃዎችን ለማምረት በማስቻል ሊያረኩ የሚችሉ ቁሳዊ የምርት ዓይነቶችን ፣ የምርት መገልገያዎችን ይመለከታል ።

ከእሴት አንፃር ሲታይ ጠቅላላ ማኅበራዊ ምርት እንደገና በሁለት ይከፈላል ። እነዚህም እንደማምረቻ መሣሪያዎችና እንደ ጥሬ ዕቃዎች ያሉ የምርት መገልገያዎችን ለማምረት ተግባር በመዋላቸው አዲስ ወደ ተመረቱት ዕቃዎች የሚለወጠው የእሴታቸው መጠንና በሠራተኛው አማካይነት በሥራ ሂደት ውስጥ አዲስ የተፈጠረው እሴት መጠን ናቸው ። በምርት ሂደት ውስጥ ወደተመረቱት ዕቃዎች የሚተላለፈው የምርት መገልገያዎች እሴት መጠን በሥራ ላይ የዋሉትን የምርት መገልገያዎች በዓመቱ መጀመሪያ እንደነበሩ አድርጎ ለማደስ ከሚያስችለው የእሴት መጠን ጋር አንድ ሲሆን አዲስ የተፈጠረው እሴት ደግሞ ብሔራዊ ምርት ወይንም ብሔራዊ ገቢ እየተባለ የሚጠራው ነው ።

በካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የሚመረተው ጠቅላላ ማኅበራዊ ምርት ከእሴት አንፃር ሲታይ በሦስት ይከፈላል ። አንደኛ አዲስ ወደተመረቱት ሸቀጦች የሚለወጠው በማምረት ተግባር ላይ የዋሉ የምርት መገልገያዎች እሴት መጠን የሆነው ቋሚ ካፒታል ፣ ሁለተኛ ተለዋዋጭ ካፒታልና ሦስተኛ ተረፈ እሴት ናቸው ። ተለዋዋጭ ካፒታልና ተረፈ እሴት በማምረት ሂደት ውስጥ አዲስ የተፈጠረው እሴት መጠን ነው ። ተለዋዋጭ ካፒታል ካፒታሊስቶች በኅብረተሰቡ ደረጃ ለሥራ ኃይል መግዣ ያወጡት ወይንም ለሠራተኞች ምንዳ ከፍያ ያዋሉት እሴት መጠን ነው ። ተረፈ እሴት የተመረቱት ሸቀጦች በሚሸጡበት ጊዜ የትርፍን ቅርፅ ይዞ ወደ ካፒታሊስቶች ኪስ የሚገባው የጠቅላላ ማኅበራዊ ምርት ክፍል ነው ።

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የሚመረተው ጠቅላላ ማኅበራዊ ምርት ከእሴት

አንፃር ሲታይ የሚያጠቃልለው አዲስ ወደ ተመረቱት ሸቀጦች የሚለወጠውን በማምረት ተግባር ላይ የዋሉ የምርት መገልገያዎችን እሴት መጠንና በሥራ አማካይነት አዲስ የተፈጠረውን እሴት መጠን ነው ። አዲስ የተፈጠረው እሴት እንደገና በአስፈላጊ ምርትና በተረፈ ምርት ይከፈላል ። አስፈላጊ ምርት ቁሳዊ ምርትን በማምረት ተግባር ላይ ለተሰማሩ ሠራተኞች ግላዊ ፍጆታ ሲውል ተረፈ ምርት ደግሞ በመንግሥትና በኅብረት ይዞታዎች ሥር በመዋል ለከምችትና የኅብረተሰቡን ሌሎች ፍላጐቶች ለማሟላት ይውላል ።

(ብሔራዊ ገቢን ይመለከቷል ።)

## ጠጋኝነት
*(Reformism)*

የመደብ ትግልን፣ የሶሻሊስት አብዮትን፣ የወዝአደሩን የበላይ ገዥነትን አስፈላጊነት የሚክድ፤ ካፒታሊዝም ቀስ በቀስ ወደ ሶሻሊዝም ተለውጦ ሁሉም የሚተሳሰብበት ፣ ወንድማማችነት ፣ ብልጽግናና ሰላም የሚሰፍንበት ኅብረተሰብ ይፈጠራል የሚልና ሠራተኛው ለመሠረታዊ ጥቅሙና ለመጨረሻ ግቡ የሚያደርገውን አብዮታዊ ትግል የሚያዳክም የፖለቲካ መሥመር ነው ። የጠጋኝነት ማኅበራዊ መሠረት የ"ሠራተኛው መሳፍንት"ና የዚሁ ንድፈ ሐሳብ አራማጅ የሆኑ ምሁራን ሲሆኑ ኢኮኖሚያዊ ምንጩ ደግሞ ኢምፔሪያሊዝም ነው ።

ኮሚኒስቶች ለጥገናዊ ለውጥ የሚደረገውን ትግል እንደአስፈላጊነቱ ይደግፋሉ ። ይህ ድጋፋቸው ግን የጥገናዊ ለውጥን ውጤት እንደመጨረሻው ግባቸው አድርገው በመውሰድ ሳይሆን ይህ በሚፈጥረው አመች ሁኔታ በመጠቀም በሠራተኛው እንቅስቃሴ ውስጥ ሶሻሊስት አስተሳሰብን ለማስረጨትና ለውጡ የሠራተኛውን ድርጅቶች በማጠናከር በካፒታሊዝም ላይ የሚካሄደውን የመደብ ትግል ለማፋፋም ነው ።

## ጣልቃገብነት
*(Interventionism)*

አንድ ሀገር ወይም ብዙ ሀገሮች ከራሳቸው ጥቅም አንፃር በመመልከት በአንድ ሀገር የውስጥ ጉዳይ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በወታደራዊ ኃይል ያለሀገሪቱ ፍላጐት የሚፈጽሙትን ድርጊት የሚገልጽ ነው ።

ዓለም አቀፍ ሕግ ጣልቃገብነትን አጥብቆ ይቃወማል ። አንድ ሀገር ወይም ብዙ ሀገሮች በአንድ ሀገር የውስጥ ጉዳይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ጣልቃ የመግባት መብት የላቸውም ። በአንድ ሀገር የፖለቲካ ነፃነት ሆነ የግዛት አንድነት ላይ የሚሰነዘር ጣልቃግቦት የዓለም አቀፍ ሕግን መጣስ ነው ።

ጣልቃገብነትን በማስመልከት ብዙ ዓለም አቀፍ ውሳኔዎችና ስምምነቶች ተደርገዋል ። በተባበሩት መንግሥታት ቻርተርም ውስጥ የተከለከለ ጉዳይ ነው ። ማንኛውም በሀገሮች መካከል የሚነሣው አለመግባባት መፈታት ያለበት በሰላማዊ መንገድ ነው ።

ምንም እንኳን ጣልቃገብነት በተባበሩት መንግሥታት አባል ሀገሮች ዘንድ የተወገዘና በቻርተሩም ውስጥ የሰፈረ ቢሆንም ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች በተለይም የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት በሌሎች ሀገሮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባቱን አላቆመም ። ኢምፔሪያሊስቶች ሰውር ዓላማቸውን ለማራመድ በሬድዮ ፣ በቴሌቪዥንና በመሳሰሉ የዜና ማሰራጫ መሣሪያዎች የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ያካሂዳሉ ፤ ከዚህም አልፈው ሰላዮችን በየሀገሩ እያሰማሩ ሽብር ፈጣሪዎችንና ፀረ ሕዝብ ኃይሎችን ያደራጃሉ ፤ የገንዘብና የቁሳቁስ ዕርዳታ ይሰጣሉ ፤ እንዲያም ሲል በቀጥታ በወታደራዊ ኃይል በመጠቀም ወረራ ይፈጽማሉ ።

## ጥምር መንግሥት
*(Coalition Government)*

በቡርዧው ዲሞክራሲ ሥርዓት ያንድን መንግሥት የአስተዳደር ሥልጣን ይዞ ለማቆየት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ፓርቲዎች የሚፈጥሩት የትብብር መንግሥት ነው ።

በቡርዧው ዲሞክራሲ ወግ ጠቅላላ የፓርላማ ምርጫ በሚደረግበት ጊዜ ልዩ ልዩ ፓርቲዎች የየራሳቸውን ፕሮግራም ይዘው ለምርጫ ይቀርባሉ ። ከምርጫው ጠቅላላ

ድምፅ ከግማሽ በላይ ያገኘ ፓርቲ አሸናፊ ሆኖ አስተዳደሩን ይረከባል ። ያሸናፊው ፓርቲ መሪ እንደ ሁኔታው ፕሬዚዳንት ወይም ጠቅላይ ሚኒስትር ይሆናል ። የተሸነፉት ፓርቲዎች በተቃዋሚነት ከአሸናፊው ፓርቲ ጋር በፓርላማ ውስጥ የተወሰኑ መቀመጫዎች ይይዛሉ ።

ነገር ግን የምርጫው ውጤት ለየትኛውም ፓርቲ ፍጹም የበላይነትን የሚያቀዳጅ ካልሆነ ማለትም ከምርጫው ድምፅ ጠቅላላ ቁጥር 2/3ኛውን ካላገኘ በስተቀር አሸናፊው ፓርቲ በሥልጣን የመቆየቱ ጉዳይ አጠራጣሪ ይሆናል ። በተለየዩ ምክንያቶች አንድ የሕግ ረቂቅ ለክርክር ብሎም ለውሳኔ በሚቀርብበት ወቅት በሥልጣን ላይ ያለው ፓርቲ በቂ ድጋፍ በማጣት በተቃዋሚዎቹ ሊሸነፍ ይችላል ። ይህን የመሰለ ውድቀት ደጋግሞ የደረሰበት ፓርቲ በሥልጣን ላይ ሊቆይና ፕሮግራሙንም ተግባራዊ ሊያደርግ አይችልም ።

መጠነኛ የድምፅ ብልጫ ያገኘው ፓርቲ ተቀዋሚዎቹን በሚገባ ለማሸነፍና ፕሮግራሙን ተግባራዊ ለማድረግ ሲል ሊግባባው የሚችለውን አንዱን የተቃዋሚ ፓርቲ ስትብብር ይጋብዘዋል ። ሁለቱም ፓርቲዎች ፕሮግራማቸውን አቻችለው ባንድነት ወይም ከእነርሱ ውጭ ሌሎችንም በመጨመር ጥምር መንግሥት ይፈጥራሉ ። ጥምር መንግሥት የሚፈጠረው ቦስምምነት ቢሆንም ይህ ስምምነት ተባባሪዎቹ ፓርቲዎች በቂ ድጋፍ ለማግኘት በየፊናቸው መራሎቻቸውን ከማስባሰብና ከማስተባበር አያግዳቸውም ።

## ጥምጥማዊ (ሙሽዙራዊ) ዕድገት
*(Spiral Development)*

በምስል የሚገልጸው የሽረት ሽረት ሕግ የሚያስገኘውን የዕድገት ዓይነትና ውጤት ነው ። የዕድገት ሂደት የከስተቶችን ወደኋላ የመመለስን ስሜት ይፈጥራል ፤ ማለትም የበታች ወይም በፊት የነበረው በከፍተኛው ወይም በአዲሱ ውስጥ ይደጋገማል ማለት ነው ። ይህ ሂደት በጥምጥማዊ (ሙሽዙራዊ) የለውጥ ቅርፅ ይገለጻል ።

የከስተቶች መደጋገም የሚታየው በከፍተኛ ደረጃ ላይ በመሆኑ ይህ የመደጋገም ሁኔታ በራሱ ላይ እየተሽከረከረና እየስፋ ወደ ላይ የሚወጣ የዕድገት ቅርፅ ያስከትላል። ለምሳሌ የኅብረተሰብ ዕድገት ከመደብ አልባ ኅብረተሰብ ተነሥቶ ወደ ኮሚኒዝም ማለትም ወደ መደብ አልባ ሥርዓት መጓዙ ወደ ኋላ የመመለስን ስሜት ይፈጥራል ። ይሁን እንጂ መደብ ሽሬ ሆኖ እራሱ በተራው ተሽሮ ኮሚኒዝም ማለትም መደብ አልባ ሥርዓት ሲወለድ ይህ ሥርዓት ከቀድሞው ጋር አንድ አይደለም ። የመደብ አልባነት መደገም የሚፈጸመው አዲስና ልዩ በሆነ መሠረት ላይ በመሆኑ ሂደቱ የሚገልጸው የኮሚኒስት ሥርዓት የኅብረተሰብ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ መሆኑን ነው ። አንድን የአትክልት ዘር ለማሻሻል ከተፈለገ ፍሬው ተዘርቶ ወደ አትክልት ተለውጦና አስፈላጊው እንክብካቤ ተደርጐለት እንደገና ወደ ዘር ማለትም ወደ ፍሬ መለወጥ እንዳለበት ሁሉ የኅብረተሰብ ዕድገትም የተለያዩ ለውጦችና አዲስ ሁኔታዎች ሊያከማች የሚችለው በጥምጥማዊ የዕድገት ሂደት ነው ።

(የሽረት ሽረት ሕግን ይመለከቷል ።)

## ጥብቅ ሀገር
*(Protectorate)*

በራሱ የውስጥ ጉዳይ የራሱ ቁጥጥር ያለው ፤ ነገር ግን በሌላ ጥብቅነት ሥር ያለና አብዛኛውን ጊዜ የውጭ ግንኙነቱ በሌላ ሀገር ማለትም በጠባቂው ሀገር የሚካሄድ ግዛት ነው ። ጥብቅ ሀገር እንደ ብለምግዚት ሀገሮች ተቀባይነት ያገኙ መሪዎች ሲኖሩት በቡድን የሚኖሩ ነገዶችን ያቀፈ ሳይሆን ጠበቅ ያለ አንድነት ያለው ሀገር ነው ። የጥብቅ ሀገር ሥልጣን የሚወሰነው ከጠባቂው መንግሥት ጋር ባለው ውል መሠረት ነው ። ለምሳሌ በደቡብ ምዕራብ ፓሲፊክ ውቅያኖስ የምትገኘውና ብዙ ትናንሽ ደሴቶች ያሏት ቶንጋ በ1970 ነፃነቷን እስከ ተጐናጸፈችበት ጊዜ ድረስ ለሰባ ዓመታት ያህል ራሷን ያስተዳደረች ብትሆንም የእንግሊዝ ጥብቅ ሀገር ነበረች ።

## ጥናት ክበብ (የ—)
*(Study Circle)*

በፖለቲካ አሠራር መዋቅር ሥር የመነሻ ነቁጥ በመሆን ስለማርክሳዊ ሌኒናዊ አስተ

ምህሮ ፥ ስለሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ወቅታዊ ሁኔታዎች ፥ ስለኅብረተሰብ የመደብ ትግል ታሪክ ወዘተ... በተወሰነ ቁጥር ተመድቦ ሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር የሚካሄድበት ቡድን ነው ።

ይህ የጥናት ክበብ የቡድኑ አባላት እርስ በርስ ለመተዋወቅ ፥ ለመግባባት ፥ በኮሚኒስታዊ ሥነ ምግባር ለመኮትኮት ፥ ንቃተ ኅሊናን ለማዳበር ፥ ፖለቲካዊ የአሠራር ዘዴን ለመማርና ተግባራዊ ተሳትፎን ለማዳበር የትግል ዝግጅት የሚያደርጉበት ኀይለኛ መድረክ ነው ።

## ጥገኛ ሀገር
*(Client State)*

በስም ነፃ የሆነ ፥ ነገር ግን ይነስም ይብዛ በውጭ ካፒታል ጣልቃ ገብነት በኢምፔሪያሊስት የፖለቲካ ተፅዕኖ ሥር የወደቀ ሀገር ነው ። ጥገኛ ሀገር የራሱ መንግሥት ያለው ቢሆንም በፖለቲካ ፥ በኢኮኖሚ ፥ በመከላከያና በመሳሰሉት የውጭ ተፅዕኖ ስላለበት ፖሊሲዎችን የሚቀይሰው የራሱን ሕዝብ ፍላጐትና ጥቅም በመከተል ሳይሆን ከኢምፔሪያሊስቶች ዓላማ አንፃር ነው ። ስለሆነም ይህ ዓይነቱ ሀገር ሙሉ ነፃነት አለው ለማለት አያስደፍርም ።

## ጦረኝነት
*(Militarism)*

ኢምፔሪያሊስቶችና ሌሎች አድኃሪ መንግሥታት በዲፕሎማሲና በሌሎች ተቀባይነት ባላቸው ዓለም አቀፍ ግንኙነቶች ፍላጐታቸውን ማሳካት ሲሳናቸው መሰሎቻቸውን በማስተባበር ሌሎች ሕዝቦችን ለመጫንና ለመበዝበዝ የሚከተሉት የኃይል ፖሊሲ ጦረኝነት ይባላል ።

ታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት ድል ከተጐናፀፈ በኋላ ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ሕዝባዊውን ትግል በኃይል ለማፈንና በጦር ኃይል አብዮቱን ለመቀልበስ ጥረው ነበር ። ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከመፈንዳቱ በፊትም ጦረኝነት በፋሺስት ጀርመንና በኢጣሊያ እንዲሁም በጃፓን እንካይነት ተከስቶ ነበር ። ከጦርነቱም ፍጻሜ በኋላ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች የወዝአደሩን እንቅስቃሴ በየአካባቢው ለማፈን ሲሉ "ኔቶ ፥ ሴንቶ" እንዲሁም "ሲያቶ" ወዘተ... የተባሉ የጦር ድርጅቶች አቋቁመው በየአቅጣጫው በፈጸሙት የጠብ አጫሪነትና የጭቁን ሕዝቦች ትግል አፈና የኮሪያ ፥ የቬትናምና ሌሎች ብዙ የአልቂት ጦርነቶችን በታዳጊው ዓለም ላይ አካሂደዋል ።

የኢምፔሪያሊስቶች የኑክሊየር ጦር መሣሪያ ክምችትና የጦረኝነት ግፊት የዓለምን ሕዝብ በአስጊ ሁኔታ ላይ ጥሏል ። ይሁን እንጂ የዓለም ሠርቶ አደሮች ኃይላቸውን በማስተባበር የሰላም ዋንኛ ኃይል የሆነውን ሶሻሊዝምን እያጠናከሩ ለሰላምና ለሰው ልጅ ደኅንነት የሚያደርጉትን ትግል አላቋረጡም ።

## ጦር መሣሪያ ቅነሳ (የ—)
*(Disarmament)*

የጦር መሣሪያዎችን በገፍ የማምረት የማከማቸትና የመሸጥ አሽቅድምድም ከሚያደርሰው አስከፊ የጦርነት አደጋ ለመዳን የጦር መሣሪያን ምርት ለመቀነስ ፥ ጨርሶም ለማቆም እርምጃዎች እንዲወሰዱ ከፍተኛ ጥረት የሚደረግበት አንዱ የትግል ገጽታ ነው ።

የጦር መሣሪያዎች እንደማንኛውም ሸቀጥ በገፍ እየተመረቱ ለገበያ እንዲቀርቡ መደረጉ በዓለም ላይ ሰላም እንዳይሰፍን ፥ ውጥረትና የሕዝቦች እርስ በርስ መተላለቅ እንዲባባስ አድርጓል ። በተለይም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ የተሠሩት የኑክሊየር መሣሪያዎች ፥ የኬሚካልና የባክቴሪዮሎጂ መርዛመርዞች ፥ የኒውትሮን ቦምብና የመሳሰሉት እንዲሁም እነዚህን የሚያወነጭፉ አህጉር ለአህጉር አቋርጭ ሮኬቶች በብዛት እየተመረቱ መውጣታቸው የሰውን ልጅ ሕይወት ከከፍተኛ ስጋትና አደጋ ላይ ጥሎታል ።

የጦር መሣሪያዎችን በገፍ ማምረት ፥ ማስራጨትና መጠቀም የሚያስከትለውን አስከፊ እልቂት ለመገመት የጦር መሣሪያ

ቅነሳ እንዲደረግ በመንግሥታት ደረጃ ከ1918 ጀምሮ ሙከራ ሲደረግ ቆይቷል ። በዚህ መሠረት ከተደረጉት ጥረቶች በጣም የታወቀው ከ1933 እስከ 1935 የተካሄደው የጄኔቫ የጦር መሣሪያ ቅነሳ ጉባኤ ነው ። ይህ ጉባኤ በቀድሞው የመንግሥታት ማኅበር (ሊግ ኦፍ ኔሽንስ) አማካይነት የተደረገ ሲሆን ስድሳ ሦስት አባልና አባል ያልሆኑ ሀገሮች ተሳትፈውበታል ። የጉባኤው ዓላማ የጦር መሣሪያ እንዲገታ መንግሥታትን ዓለም አቀፍ ግዴታ ውስጥ ማስገባት ቢሆ ንም ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ባንድነት ሆነው የራሳቸው የመሣሪያ ክምችት እንዲያ ድግ ፥ ተወዳዳሪዎቻቸው (በተለይም ጀር መን) ግን ፈጽሞ እንዳያመርቱ የሚከለከል ውሳኔ በማሳለፋቸው ከጉባኤው የተፈለገው ውጤት ሊገኝ አልቻለም ። በጊዜው ተቀባይ ነት ባያገኝም የሶቪዬት መንግሥት አንድ የውሳኔ ረቂቅ ለመንግሥታቱ ጉባኤ አቅርቦ ነበር ። ይህ በሶቪዬት መንግሥት የቀረበው ረቂቅ ሐሳብ አባል መንግሥታት ሁሉ ጠቅላላ የጦር መሣሪያ ቅነሳ እንዲያደርጉና ሠራዊ ታቸውንም እንደዐቅማቸው እንዲቀንሱ የሚጠይቅ ነበር ።

ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላም ጥረቱ ቀጥሎ በተባበሩት መንግሥታት ቻር ተር አንቀጽ 26 መሠረት የፀጥታው ምክር ቤት የጦር መሣሪያዎችን አመራረት ፥ ክም ችትና ስርጭት ለመቆጣጠር የሚያስችል ድንጋጌ እንዲያወጣ ሥልጣን ተሰጥቶታል ። በዚህም መሠረት ለምሳሌ በ1946 ማኅበሩ የኑክሊየር ኃይል ለጥፋት እንዳይውል የሚ ቆጣጠር የአቶሚክ ኃይል ኮሚሽን አቋቁ ሟል ። በ1968 ደግሞ የኑክሊየር መሣሪያ ባለቤት የሆኑ አምስት ሀገሮች (ሶቪዬት ኅብረት ፥ አሜሪካ ፥ እንግሊዝ ፥ ፈረንሳይና ቻይና) 'የኑክሊየር መሣሪያ ስርጭት መግቻ ውል' ተፈራርመዋል ። ይህም ውል የኑክሊ የር መሣሪያ አመራረት ጥበብ ከነዚህ ሀገ ሮች ውጭ እንዳይስራጭ የሚከለክልና ጥበቡም የሌላቸው ሀገሮች ከሌሎች ለማግ ኘት እንዳይሞክሩ የሚያግድ ነበር ።

ለጦር መሣሪያ ቅነሳ የሚደረገው ትግል ለዓለም ሰላምና ለሰው ልጆች ደኅንነት በቆሙ ሶሻሊስትና ሰላም ወዳድ ኃይሎችና ይህንኑ ዓላማ በሚፃረሩ ፥ በጦረኝነት ፖሊሲ አቸው ዓለምን በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው ለመበዝበዝ በሚሹ የኢምፔሪያሊስትና የአ ድኅሮት ኃይላት መካከል ትግሉ ተካርሮ ይገኛል ። በዚህም በተለይ ሶቪዬት ኅብረት አሜሪካ ዓለምን ወደ አጠቃላይ የኑክሊየር ጦርነት ለማምራት የምታደርገውን ጥረት ለማክሸፍና በሕዝቦች መካከል መተማመንና አብሮ በሰላም መኖር እንዲጠናከር ያልተቆ ጠበ ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች ። ይህ ንንም የተቀሩት ሶሻሊስት ሀገሮች ፥ የዓለም ተራማጅና ሰላም ወዳድ ኃይሎች ሁሉ ከልብ ይደግፉታል ።

## ጦርነት

*(War)*

የአንድን መደብ ዓላማ ወይም ፖሊሲ ለማስፈጸም በትጥቅ አማካይነት የሚካሄድ የፖለቲካ ትግል ከፍተኛ ደረጃ ነው ። ለጦርነት መንሥኤው የግል ሀብት በኅብ ረተሰቡ ውስጥ የበላይነትን መያዝ ነው ።

የቡርዧ ፈላስፎች ጦርነት ከሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ባሕርይ ጋር እንደተያያዘና ዘለዓለማዊ እንደሆነ አድርገው ይሰብካሉ። ይህ ግን ፍጹም የተሳሳተ አመለካከት ነው ። የጦርነት መሠረቱ የግል ሀብት በመሆኑና ኅብረተሰቡ ደግሞ በተፃራሪ መደቦች እስከተከፈለ ድረስ ጦርነት የማ ይቀር ነው ። ነገር ግን በሁሉም ሀገሮች የሶሻሊስት አብዮት ተካሂዶ በዓለም አቀፍ ደረጃ የግል ሀብት ፥ ከዚያም መደቦች ሲጠፉ ጦርነትም አብሮ ያከትማል ።

ጦርነቶች በመነሻቸውና በዓላማቸው ስለሚለያዩ ሕጋዊ አለያም ሕገወጥ ተብለው ይታወቃሉ ። ለብሔራዊ ነፃነት ማለትም ሕዝቦችን ከቅኝ አገዛዝ ፥ አንድን ሀገር ከውጭ ወራሪዎች ለማዳን ፥ ጭቆና ችን ከብዝበዛ ለማላቀቅ ፥ ሕዝባዊ አብዮ ትን ከግብ ለማድረስ የሚደረጉ ጦርነቶች ሁሉ ሕጋዊ ጦርነቶች ናቸው ። በዝባዥ መደቦች በሠራተኛው ሕዝብ ፥ በአብዮታ ዊና ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴዎች ፥ በሶሻሊ ስትና በዕድገት ኋላ ቀር በሆኑ ሀገሮች ላይ የሚከፍቷቸውና በዓለም ላይ ለኢኮኖሚና ለፖለቲካ የበላይነት የሚያካሂዷቸው ጦርነ ቶች ሁሉ ሕገወጥ ጦርነቶች ናቸው ።

ጦርነት ምን ጊዜም በሰፊው ሕዝብ ዘንድ የተጠላ ነው ፤ የሰላም ኃይሎች በተደራጀ መልክ የጦርነት ፖሊሲ የሚያራምዱትን ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ለመቋቋም የቻሉት ከታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት ወዲህ ነው ። ሶሻሊዝም በአጭር ጊዜ ውስጥ በኢኮኖሚም ሆነ በመከላከያ ረገድ ጐልብቶ ራሱን የቻለ የዓለም ሥርዓት ሆኖ መውጣቱ የሰላም ኃይሎችን ከመቼውም ጊዜ በይበልጥ በማስተባበሩና በማጠናከሩ ጦርነት ምንጊዜም ሊቀር የማይችል ነው የሚለውን የጦርነት ናፋቂዎችን አድኃሪ አስተሳሰብ ውድቅ አድርጎታል ። የኮሚኒዝም ታሪካዊ ተልዕኮም ጦርነትን ከነጸ ምድር ፍጹም አስወግዶ ፍትህና እኩልነት በሰፈነበት ኅብረተሰብ ውስጥ ዘላቂ ሰላምን ማረጋገጥ ነው ።

## ጦርነት ኮሚዩኒዝም (የ—)

*(War Communism)*

ከ1918—1921 በሶቭዬት አብዮት ውስጥ በከፍተኛ የመንግሥት ቁጥጥርና ክትትል በሥራ ላይ የዋሉ አጣዳፊ የኢኮኖሚ እርምጃዎች የተወሰዱበት የኢኮኖሚ አመራር ነው ። በወቅቱ በጦርነት ላይ በነበረችው ሶቭዬት ኅብረት ውስጥ ኢንዱስትሪዎች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ውለው የሚያስፈልጓቸውን ጥሬ ዕቃዎች ከመንግሥት በነፃ እያገኙ ምርቶቻቸውንም ለመንግሥት ማስረከብና ወዝአደሮችም ያለክፍያ መሥራት ነበረባቸው ። በአንፃሩ ምግብና የሚያስፈልጓቸውን ቀላል የሸቀጥ ዕቃዎች በነፃ ለማግኘት የሚችሉበት ሁኔታም ነበር ።

በእነዚሀ የኢኮኖሚ እርምጃዎች አዲሱ የሶቭዬት መንግሥት በአብዮቱ መጀመሪያ ላይ ከደረሰበት የውስጥ ፀረ አብዮት ደባና የውጭ ኢምፔሪያሊስቶች ከባበና ወረራ እንዲሁም ከዚሀ የተነሣ የነበረበትን ከባድ የኢኮኖሚ ችግር ለመቋቋም ችሏል ። ሀገሪቱ ከዚሀ አጅግ ውስብስብና አስቸጋሪ ሁኔታ በድል አድራጊነት ከወጣች በኋላ ግን ለተወሰኑ ዓመታት አዲሱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የሚባለው ይሀንን የጦርነት ኢኮኖሚ አመራር ሲተካ ፤ በዘለቄታው ደግሞ በሶሻሊስት ዕቅድ ላይ የተመሠረተ ጠንካራ የኢኮኖሚ ግንባታ ሥራ ላይ ውሏል ።

(አዲሱ የኢኮኖሚ ፖሊሲን ይመለከቷል ።)

# ጨ

## ጭልታ
*(Intuition)*

በቅድመ ማርክሳዊ ፍልስፍና ውስጥ ጭልታ ከሥነ አመክንዮአዊ ግንዛቤ በፊት ወይም ውጭ የሚመጣና በእውነት ላይ በቀጥታና በድንገት የሚደርስ ችሎታ ሆኖ ታይቷል ። በተጨማሪም ጭልታ ባለው ቀጥተኛነትና ገላጭነት ማረጋገጫ እንደማያስፈልገው ሆኖ ተቆጥሯል ። በአንዳንድ ቅድመ ማርክሳዊ ፈላስፎች አመለካከት በጭልታ የተገኘውን ዕውቀት ምንጩታዊ ሥነ አመክንዮ የሚዘረዝርና የሚያዳብር ነው ። የዘመኑ ሐሳባዊ ፍልስፍና ጭልታን የሚመለከተው እንደተማልሎታዊ የዕውቀት ችሎታ ሲሆን የሚገኘውም ዕውቀት ከሥነ አመክንዮና ከተግባር ጋር እንደማይጣጣም ይናገራል ። አመለካከቱ የሚገልጸው ሐሳባዊነትን ከሳይንስ በላይ በማድረግ ምሥጢራዊ ዕውቀት እንደሆነ ለማሳመን የሚደረገውን ጥረት ነው ።

ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ማንኛውም ዲበ ምክኑያዊና ተማልሎታዊ ነኝ የሚልን ዕውቀት የሚቃወም በመሆኑ ጭልታን እንደተለየ የዕውቀት ደረጃ አድርጎ አይወስደውም ። በሳይንሳዊና በሥነ ውበታዊ ግንዛቤ ውስጥ ያለውን የአጋዥነት ሚና በማሳየት ከሥነ አመክንዮና ከተግባር ሕጎች ውጭ እንዳልሆነም ያስረዳል ። ጭልታ በድንገት የሚገኝ ዕውቀት መስሎ የሚታየው ከኋላ በመሆን እንደመሠረት የሚያገለግለውን የልምድንና የዕውቀትን ክምችት ካለማስተዋል የተነሣ ነው ። የጭልታ ውጤቶች በራሳቸው እውነትነት ያላቸው ሳይሆኑ እንደ ማንኛውም ዕውቀት በሥነ አመክንዮና በተግባር መፈተን ይኖርባቸዋል ።

(ጭልታዊነትን ይመለከቷል)

## ጭልታዊነት
*(Intuitionism)*

የግንዛቤ ብቸኛና አስተማማኝ ምንጭ ሊሆን የሚችለው ስለነገሮች በድንገት የምናገኘው ብልጭታ ወይም ቅጽበታዊ መረጃ ነው የሚል የሐሳብና የእውነትን ምንነትና ከየት መጥነት ሳያገናዝቡና ሳይመረምሩ በቀጥታ እንዳለ መቀበልን የሚያስተምር የሐሳባዊ ፍልስፍና መሥመር ነው ። ጭልታም የሚፈጠረው አድራጊውና ተደራጊው ሲዋሀዱ ፥ በመሀከላቸውም ያለው ቅራኔ ሲፈታ ነው ። ጭልታዊነት ከምክኑያዊ ዕውቀት ጋር የሚቃረንና ከተማልሎአዊነት ጋር በቅርብ የሚመሳሰል ነው ። በተናከኦታዊ አጠናን ዘዴ ላይ የተመሠረተ ፥ የስዎች ገጠመኝ ከሕውስታ ክልል ሊያልፍ አይችልም የሚልና ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነትን የሚቃወም ነው ። ጭልታንና አእምሮን ተቃራኒ እንደሆኑ አድርጎ የሚወስድ ፀረ አእምሮታዊ ነው ። ሆኖም ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ጭልታዊነትን መቃወሙ ለጭልታ ስፍራ አይሰጥም ማለት አይደለም ። ምክንያቱም ጭልታ በድንገት የሚገኝ ሳይሆን ከተጠራቀመ ልምድና ከሥነ አመክንዮአዊ አስተሳሰብ ጥረት የሚመነጭ በመሆኑ ነው ፤ በግንዛቤ ሂደትም ውስጥ የተወሰነ ሚና የሚጫወት እንጂ ጭልታዊነት እንደሚለው የዕውቀት ብቸኛ ምንጭ አይደለም ።

(አመክንዮን ፥ ሥነ አመክንዮን ይመለከቷል ።)

## ጭብጥ
*(Concrete)*

የቃሉ አገባብ እንደሚገልጸው ከኛ ሐሳብ ውጭ በመገኘቱ ተቋጥሮና ተሳስሮ የሚቀርብልን ማንኛውም ነገር ነው ። በአንፃሩም ጽንስ ሐሳቡ የሚገልጸው የዕውቀትን ሚናና ዘዴ ነው ። ምክንያቱም ማወቅ ማለት የጭብጡን ውስጠ ሁኔታ መረዳት ስለሚሆን ዕውቀት የተቋጠረውን መፍታት ይኖርበታል ።

ጭብጥ ይህን ማርክሳዊ ፍች ከማግኘቱ በፊት በሐሳባዊ ፍልስፍና ውስጥ የተዛባ ትርጉም ተሰጥቶት ነበር ። ነባራዊ ሐሳባውያን ጭብጥንና ረቂቅ ሐሳብን በማወዳደር

የጭብጥ መቋጠር ፣ ሽፍንና ግላዊ መሆን ፤ የረቂቅ ሐሳብ ደግሞ ለግንዛቤ ግልጽ መሆንና ሁለንታዊነትንና ቅርፃዊ ጥራትን ማሳየቱን በመመልከት ጭብጥ ከሐሳብ የተገነጠለና የሱም የደረቀና የተሸማቀቀ ቁራጭ አድርገው ተርጉመውታል ። ኀሊናዊ ሐሳባውያን በበኩላቸው የረቂቅ ሐሳብን ደብዛዛነትና ቅርፃዊነት ፣ የጭብጥን ይዘትነት ፣ ደማቅነትና ግላዊነት ፣ ለሕዋሳት ያለውን ተገሳጭነት በመመልከት ረቂቁን ደብዛዛ ጭብጥ ወይም የጭብጥ ቅጅ በማድረግ ጭብጥን የዕውቀት መነሻ አድርገውታል ። ሆኖም ረቂቅ ሐሳብን (ግንዛቤን) የጭብጥ ደብዛዛ ቅጅ ብቻ በማድረጋቸው ከጭብጥ የሚነሣው ዕውቀት ነገሮችን ጠልቆ ማየት ባለመቻሉ ግንዛቤያችን ስለነገሮች ውስጣዊ ዕውቀት ሊኖረው አይችልም የሚል የኢታዋቂነትን አመለካከት አንፀባርቀዋል ።

ማርክሲዝም ስለጭብጥ የሰጠው አመለካከት ከላይ የተጠቀሱትን የሐሳባውያን የፍች አተረጓጐም ስህተት ከማረም የመነጨ ነው ። ከሐሳብ ውጭ የሚኖረው ቁስአካላዊ ነገር ሁሉ በተቋጠረና ድፍን በሆነ መልኩ ለሐሳብ የሚቀርብ በመሆኑ ጭብጥ ነው ። ይህ ማለት ግን ጭብጥ ለሁሌም ተደፍኖ የሚቀር ኢታዋቂ ነገር ነው ማለት አይደለም ። ጭብጥ የዕውቀት መነሻ እንደመሆኑ የዕውቀት የመጀመሪያ ተግባር ጭብጡን መፍታት ፣ በተለያዩ ክፍሎቹ ፣ ጠባዮቹ አንፃር መከፋፈል ይሆናል ። ይህ የሐሳብ አድራጎት ረቂቅ የሆኑ ሐሳቦችን ይሰጠናል ። እነዚህ ከጭብጡ ያመነጨናቸው ረቂቅ ሐሳቦች ነባራዊ ሐሳባውያን እንደሚሉት የራሳቸው ህልውና ያላቸው አይደሉም ። ጭብጡም የነዚህ ሐሳቦች የተቆሳሰፈ ሁኔታ አይደለም ። ከትንተናና ከአርቅቆት የሚገኙ አጠቃላይ ሐሳቦች ናቸው። በመሆኑም የጭብጡን ዕውቀት ለማግኘት ሐሳቦችን የማጣመር ተግባርን ማከናወን ይኖርበታል ። ከውጭ ያለው ጭብጥ በሐሳባችን ውስጥ ቅጂውን እስከሚያገኝ ድረስ የተለያዩትን ሐሳቦች ማሰባሰብ ፣ አንዱን ሐሳብ ከሌላው ማሳካት ያስፈልጋል ። በሐሳብ የተበታተነውን እንደገና በሐሳብ መገጣጠም ከቻልን ለዚህ ሥራ የጠቀመን መሪ ሐሳብ የጭብጡ ውስጣዊ መዋቅር ዕውቀት መሆኑን እንረዳለን ። ይህ በሐሳባችን ውስጥ የምናደርገው የሐሳቦች መዋቅር የውስጣዊ ጭብጥ ቅጅ የሐሳብ ጭብጥ ነው ።

ለምሳሌ የውሀን ምንነት ዕውቀት እንዴት እንደምናገኝ እንመልከት ። ውሀ ለሕዋሳት ሲገለጽ ድፍን በሆነ መልኩ የሚቀርብ ነው ። ይህ የመነሻ ጭብጥ ነው ። በተለያዩ የትንተና ዘዴዎች በመጠቀም ውሀ ከሚያቅፋቸው ንጥረ ነገሮች ላይ እንደርሳለን ። ከሚያሳዩት ጠባይ አንፃር እነዚህን ንጥረ ነገሮች ኦክሲጂንና ሀይድሮጅን ብለን እንሰይማቸዋለን ። የምናሰባቸው ከግላዊ ነገር ጋር በማያያዝ ሳይሆን ከአጠቃላይ መለያ ባሕርያቸው አንፃር በመሆኑ ረቂቅ ሐሳቦች ወይም ጽንሰ ሐሳቦች ናቸው ። የሚቀረው ዋናው ጥያቄ በምን አኳኋን ፣ በምን ዓይነት መስተጋብር ሁለቱ ተዋሀደው ውሀን እንደሚፈጥሩ ነው ። ለውሀ መከሰት ምክንያት የሆነው ሁለት ሀይድሮጂን አቶም ከአንድ ኦክሲጂን አቶም ጋር መዋቀር መቻሉ ነው የሚለው መሪ ሐሳብ ወይም ሕግ የሚገልጽልን ጭብጥ የሆነውን የውሀን ውስጣዊ መዋቅር ነው ።

(ዕውቀትን ፣ አርቅቆትን ይመለከቷል ።)

# ጸ

## ጸለምት መቶዎች

*(Black Hundreds)*

እስክንድር ኢቫኖቪች ዱብሮቪን የተባለ ሰው ከሌሎች ተባባሪዎቹ ጋር ሆኖ በ1905 የመሠረተውና የሩሲያን አድኃሪ አገዛዝ በበለጠ የማጠናከር ዓላማ የነበረው የአድኃርያን ድርጅት ነው ። የጸለምት መቶዎች ዓይነተኛ ዓላማ የሩሲያ የዘውድ አገዛዝ በበለጠ ተጠናክሮ እንዲኖር ፣ የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የቀድሞ ልዩ መብትና ሥልጣን እንዲመለስላት የሚጠይቅ ፣ በመጨረሻም በቄሳሩ ግዛት ውስጥ በነበሩት ልዩ ልዩ ሕዝቦች ላይ የሩሲያ ብሔር የበላይነት እንደነበረ እንዲቀጥል ማድረግ ነበር ። ይህ ድርጅት ግልጽ ፀረ አይሁዳዊ አቋም የነበረው ከመሆኑም በላይ በልዩ ልዩ አጋጣሚ በአይሁድ ላይ አሰቃቂ የሆነ ጭፍጨፋና የዝርፊያ ተግባር ፈጽሟል ። በዚህ አቋሙ እስከ 1910 ድረስ በአንድ ወጥነት የአድኅሮት ተግባሩን ሲያከናውን ከቆየ በኋላ ተበታትኖ በልዩ ልዩ የዘውድ ናፋቂ ድርጅቶች ቅርፅ አዲስ ህልውና አግኝቶ እስከ 1917 ድረስ ቆይቷል ።

ከታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት ድል በኋላ ግን ድርጅቱ እየተዳከመ በመሄድ ፈጽሞ ህልውናው ሊያከትም ችሏል ። ከአብዮቱም ድል በኋላ ጸለምት መቶዎች ወደ አሜሪካ ተሰደው በመሄድ ለተወሰነ ጊዜ የተለመደ ፀረ አይሁዳዊ ተግባራቸውን ሲያካሂዱ ቆይተዋል ። ጸለምት መቶዎች "የሩሲያው ማኅበር" በሚል መጠሪያም ይታወቁ ነበር ። ከዚሁ ጋር ድርጅቱ ሩስኮይ ዝናሚያ (የሩሲያ ሰንደቅ) በሚል የሚታወቅና በራሱ በእስክንድር ኢቫኖቪች አዘጋጅነት የሚወጣ ልሳን ነበረው ።

## ጽናት አልበኝነት

*(Philistinism)*

በሶሻሊዝም "የማመን"ና ለሶሻሊዝም መምጣት "ተስፋ የማድረግ" ነገር ግን በመደብ ጦርነቶች ወቅት ገና ከመጀመሪያው ከትግሉ ሜዳ የመፈርጠጥ ፣ ሆደ ቡቡነትና የፍርሀት ተገዥ የመሆን አዝማሚያ ነው ። ጽናት አልባ ወደ ትንኮሳ የሚያመራና "የሰላም ጊዜ ጓደኛ" በመሆን በትግል ወቅት የሚከዳ ነው ፤ ይከተል የነበረውን መርህ የሚከዳ ብቻ ሳይሆን ወደፊት የአብዮታዊ ሶሻሊዝም ተከታይ ተብሎ እንዳይጠረጠር የአድኅሮት ኃይሎች መጣሪያ በመሆንም ያገለግላል ።

ጽናት አልበኝነት የቡርዧዚውን ለዘብተኛ ዝንባሌም ሊያንፀባርቅ ይችላል ። ለምሳሌ "ዘ ኒው ስቴትስማን ኤንድ ኔሽን" የሚባለውና ሌሎች በአሜሪካና በእንግሊዝ የሚታተሙ ተመሳሳይ መጽሔት አሳታሚዎች ሶሻሊስት ነን ብለው በይፋ ባይናገሩም የኅብረተሰቡን የዕድገት አርማ ያነገቡ መሆናቸውን ይለፍፋሉ ። ነገር ግን ጽናት አልባና አድኃሪ እንደመሆናቸው በማንኛውም ፈታኝ ወቅት ከትግሉ በመሸሽ ለካፒታሊዝም ያጐበድዳሉ ። ከዚያም አልፈው ኮሚኒስቶችንና የሠራተኛውን ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ በመቃወም የትንኮሳ ተግባር እስከ መፈጸም ይደርሳሉ ።

## ጽንሰ ሐሳብ

*(Concept)*

ነገሮችን በተናጠል ፣ በልዩነታቸውና በግላዊነታቸው ብቻ ሳንመለከት በአጠቃላይ ሁኔታቸውና በተመሳሳይነታቸው ሲጤኑ የሚገኝ ግንዛቤ ወይም ሐሳብ ነው ። ለምሳሌ ሰው ስንል ይህ አንድ ጽንሰ ሐሳብ ነው ፤ ምክንያቱም የምናስበው የተለየን ግለሰብ ሳይሆን ሴት ወንድ ሳይል ቁመት ፣ መልክ ፣ ዜጋ ፣ ወዘተ . . . ሳይለይ አጠቃላይ ትርጉምና ተመሳሳይ ባሕርይ የሚገልጽ በመሆኑ ነው ። ይህም የሚያስረዳው ጽንሰ ሐሳብ ረቂቅ መሆኑንና በሕዋሳት መረጃዎች ብቻ የተወሰነ አለመሆኑን ነው ።

በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ ጽንሰ ሐሳብ ነባራዊነት አለው ወይስ የለውም የሚሰው

ጥያቄ ብዙ ክርክር አስነሥቷል ። አንደኛው ክፍል ነባራዊነት ያለው ተጨባጩ ማለትም በሕዋሳት አማካይነት የምንገነዘበው ብቻ ነው ይልና ጽንሰ ሐሳብ ረቂቅ በመሆኑ ለስያሜ ብቻ እንደሚያገለግል አድርጐ ይመለከተዋል ። ተቃራኒው ክፍል ደግሞ ዋና ነባራዊነት ያለው ጽንሰ ሐሳብ እንደሆነና ልዩነትና ግላዊነት በሁለተኛ ደረጃ የሚታዩና ከጽንሰ ሐሳብ የሚመነጩ ጊዜያዊ ክስተቶች እንደሆኑ ለማሳመን ይሞክራል ። እነዚህ አባባሎች የተለያዩ ቢመስሉም አንደኛው ኀሊናዊ ፣ ሁለተኛው ነባራዊ ሐሳባዊ በመሆናቸው በሐሳባዊ ፍልስፍና ውስጥ ይጠቃለላሉ ።

በማርክሳዊ አመለካከት ተጨባጩ ነባራዊነት ቢኖረውም ጽንሰ ሐሳብ ደግሞ ስያሜ ብቻ አይደለም ። የጽንሰ ሐሳብን አመጣጥ ስንመለከት የዲያሌክቲክስ አስተሳሰብም እንደሚያስረዳው ነገሮች በተናጠል መታየት እንደሌለባቸውና ልዩነትም ደግሞ አንድነት እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል ። ግለሰቡ ለምሳሌ በቀለ ሰው ነው ስንል ግለሰቡ (በቀለ) ሁለንታዊነት (ሰው) እንዳለው እንገነዘባለን ። ይህ ማለት ሁለንታዊነት ወይም ጽንሰ ሐሳብ ከግላዊነት ተገንጥሎ ብቻውን በረቂቅነት ይኖራል ማለት አይደለም ። ጽንሰ ሐሳብ ግን ዛቢ እንደመሆኑ ከሕዋሳት መረጃዎች ባሻገር ነገሮችን በማገናዘብና በማወዳደር የነባራዊ እውነታን ውስጣዊ ግንኙነቶች ለመረዳት የሚያስችል ነው ። ሰው ስንል ልዩነት ነው (ከአውሬ ይለያል) ፤ ልዩነት ደግሞ ሁለንታዊነት ነው ፤ ማለትም ባሕርይ ነው ። ሁለቱን አጣምሮ ማየት ነገሮችን ከሕግጋት አንፃር መገንዘብ ይሆናል ። ግላዊ ካልሆነ ነዋሪነት የለውም ፤ ሁለንታዊ ካልሆነ ደግሞ ሕግ የለውም ፤ ምክንያቱም ሕግ ማለት ለሁሉ የሚሠራ ነውና ።

(ስማዊነትን ፣ እውነትን ፣ ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀትን ይመለከቷል ።)

## ጽንፋዊነት
*(Extremism)*

በፖለቲካዊ ፣ በኢኮኖሚያዊና በማኅበራዊ ጥያቄዎች ላይ ያልተገናዘበና የከረረ አቋም መያዝ ማለት ነው ። ጽንፋዊነት አንድን ጥያቄ በሚመለከት የጉዳዩን ታሪካዊ አመጣጥ ፣ የወቅቱን ተጨባጭ ሁኔታና የወደፊቱን አቅጣጫ ካለማጤንና ሳይንሳዊ መፍትሔ ለመሻት ካለመቻል የሚመነጭ ነው ። ጽንፋዊነት በቀኝ ወይም በግራ አክራሪነት ዝንባሌ ሊከሰት ቢችልም አብዮታዊ እንቅስቃሴን ወደኋላ በመጐተት ፣ አለያም ትግሉ የሚካሄድበት ተጨባጭ ሁኔታ ሳይፈቅድ ጀብደኛ አቋም በመውሰድ ሕዝባዊውን ትግል ለውድቀት የሚዳርግ ፀረ አብዮት አቋም ነው ።

(ጀብደኝነትን ፣ አድርባይነትን ፣ "ግራክንፍ" ኮሚኒዝምን ይመለከቷል ።)

## ጽዮናዊነት
*(Zionism)*

አይሁዳውያን የሚያራምዱት አድኃሪና ብሔረተኛ ንቅናቄ ነው ። አጀማመሩም በተለያዩ ሀገሮችና የዓለም ክፍሎች ተበታትነው የነበሩትን አይሁዳውያን የባህልና የሃይማኖት አንድነት ስሜት የሚያንፀባርቅ ነበር ።

ኋላ ግን ከአሥራ ዘጠነኛው ምዕት ዓመት መግቢያ ጀምሮ የተከሰተውን ፀረ አይሁድነት በመቋቋም ምክንያት የፖለቲካ ቅርፅ አግኝቶ የኃሳ ንቅናቄ እየሆነ መጥቷል ።

ጽዮናዊነት በፖለቲካ ዓላማውና ይዘቱ ተጠናክሮ የወጣው በሀንጋሪ በተወለደውና በቪየና ውስጥ ይኖር በነበረው አይሁዳዊ ጋዜጠኛ በቲዮዶር ሄርዝል (1864—1904) ነው ። ከ1894—1906 በነበረው ወቅት ድሬይፈውስ የተባለ አይሁዳዊ ወታደራዊ መኰንን በፈረንሳይ ሀገር የሀገሪቱን ወታደራዊ ምሥጢር ለጀርመኖች አሳልፈህ ሰጥተሀል በመባል በሀሰት ተከሶ ይንገላታል ። ምንም እንኳ ሄርዝል ከሚኖርበት ኅብረተሰብ ጋር የተዋሀደ ቢሆንም ፣ በወቅቱ አይሎ የነበረ ውን ፀረ አይሁድነትና በተለይም በድሬይፈውስ ሁኔታ ስሜቱ ተከፋኛ ስለተነካ አይሁዳውያን የራሳቸውን ሀገርና ብሔራዊ መንግሥት ካላቋቋሙ በስተቀር በዓለም ላይ ለህልውናቸው ምንም ዋስትና የላቸውም የሚል ጽሑፍ በጋዜጣ ከመጻፉ በላይ የጽዮናውያንን ጉባኤ በመጥራትና ሌሎችንም በማስተባበር ለዚህ ዓላማ መታገል ጀመረ ። ኋላም ቼይም ዊይዝማንና

ተከታዮቹ የዚህ ዓይነቱ የአይሁድ መንግሥት በየትም ቦታ ሳይሆን በፍልስጥኤም ውስጥ ብቻ ሊመሠረት የሚችል መሆኑን በማመን ለዓላማው መሳካት ጥረት ማድረግ በመጀመራቸው ንቅናቄው እየሰፋና እየተጠናከረ ሄደ ።

ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የጽዮናዊነት ስሜት በአይሁዳውያን ዘንድ በጣም በመጠናከሩ በፍልስጥኤም መሬት ላይ መስፈርና በዚያም የአይሁድ መንግሥት መመሥረት ቁርጠኛ ዓላማቸው ሆነ ። በዚያን ጊዜ በተለይ በ1917 በተደረገው የባልፎር ስምምነት የእንግሊዝ ቅኝ ገዥዎች ከአይሁዳውያን ጐን በመቆምና ከፍተኛ ድጋፍ በመስጠት አይሁዳውያን በተለያዩ ሀገሮች የደረሰባቸውን መከራና ሥቃይ ምክንያት በማድረግ በፍልስጥኤም መሬት ላይ እንዲሰፍሩ ተደረገ። ይህም ሁኔታ ለጽዮናዊነት የፖለቲካ ዕድገት ወሳኝ እርምጃ ነበር ። እርግጥ በአፈጻጸም ስልት ረገድ በጽዮናውያን መካከል ሙሉ በሙሉ አንድ ዓይነት አመለካከት አልነበረም። የፍልስጥኤምን አረብ ሕዝብናአይሁዳውያን ያቀፈ መንግሥት እንዲመሠረት የደገፉ ተራማጅ ኃይሎችም ይገኙበት ነበር ። ነገር ግን በሚቀጥሉት ዓመታት የጽዮናዊነት ዓላማ ተግባራዊነት ከአረብ ሕዝቦችና በተለይም ከፍልስጥኤም ሕዝብ መንግሥታዊ ህልውና ማግኘትና የራስን ዕድል በራስ ከመወሰን ጥያቄ ጋር ፍጹም የሚጋጭ መሆኑ በግልጽ ታየ ።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት በተለይ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ አይሁዳውያን በፋሺዝም በግፍ መጨፍጨፍ ፣ ለአይሁዳውያን በፍልስጥኤም መሬት ላይ መስፈርና የራሳቸውን መንግሥት መመሥረት ከፍተኛ ተቀባይነት ከማስገኘቱም በላይ አጣዳፊ ተግባርም ሆነ ። ብዙም ሳይቆይ ከጦርነቱ በኋላ በኢምፔሪያሊዝም ከፍተኛ ድጋፍ በእስራኤል መንግሥት መቋቋም (1948) የጽዮናዊነት ዓላማ ተግባራዊ ሊሆን ቻለ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የፍልስጥኤም ሕዝብ ሕጋዊ የህልውና መብቱን በማጣት ለስደት ፣ ለአስከፊ ጭቆናና ለጭፍጨፋ ተዳርጓል ። በአካባቢው የሚገኙ ጐረቤት የሆኑ የአረብ ሀገሮችም መሬታቸውን የተነጠቁ ከመሆናቸውም በላይ በየጊዜው የዕብሪት ወረራና ጭፍጨፋ ይካሄድባቸዋል ። ሆኖም የዓለም ኮሚኒስትና ተራማጅ ኃይሎች ሁሉ ይህን በዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ድጋፍና አስተባባሪነት የሚካሄደውን የጽዮናዊነት ፍጹም አድኃሪ ፣ ብሔረተኛና ዘረኛ ፖሊሲ ያወግዛሉ ፤ የፍልስጥኤምን ሕዝብ ሕጋዊ መብት ለማረጋገጥ በሚደረገውም ትግል የየበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ።

(ዘረኝነትን ፣ ብሔረተኝነትን ይመለከቷል ።)

# ፀ

## ፀረ አብዮት
*(Anti–Revolution)*

የፖለቲካ ሥልጣናቸውን ከመነጠቃቸው የተነሣ የአብዮትን ሂደት በምንም መልክ ይሁን ለመግታት ፡ ለማደናቀፍ ፡ ለመቀልበስና ቀድሞ የነበረውን የብዝበዛ ሥርዓት ለመመለስ አዲሱን ማኅበራዊ ሥርዓት በሚታገሉት መደቦችና የአድኅሮት ኃይሎች የሚካሄድ ግልጽ ወይም ስውር ድርጊትና ደባ ነው ። ይዘም ፀረ አብዮት ድርጊት ዓላማው የወደቀውን ሥልጣን መልሶ ለማቋቋምና ብዝበዛውን ለመዘርጋት ቢሆንም እንደሁኔታው ከኢኮኖሚና ከፖለቲካ አሻጥር እስከ ግልጽ የመሣሪያ ትግል ቅርፅ ሊይዝ ይችላል ። ቡርዧዚውም ሆነ የቡርዧው አፈቀላጤዎች ማለትም የ"ግራ" እና የቀኝ አድርባዮች ሁሉ የሕዝባዊ አብዮት መሳካት ጥቅማቸውን የሚነካና ሥልጣናቸውን የሚፃረር በመሆኑ ፀረ አብዮት ድርጊት የሚፈጽሙናቸው ።

(አድኃሪን ፣ ይመለከቷል ።)

## ፀረ አይሁድነት
*(Anti–Semitism)*

እውነተኛ መንሥኤው የካፒታሊስት ብዝበዛ የሆነውን የሠራተኞች ቁጣና አመፅ ወደ ሌላ አቅጣጫ ለመለወጥና ትክክለኛ ምክንያቱን ለማድበስበስ የታቀደ አይሁድን ክፉኛ የማጥላላትና የማናናቅ የፖለቲካ አስተምህሮ ነው ። ቀድሞ በሃይማኖት ሳቢያ የተመሠረተው ፀረ አይሁድነት ከ19ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ጀምሮ ንጹህ የአርያን ዘርና የኖርዲክ ዘር ከሚሉ አድኃሪና ዘረኛ ንድፈ ሐሳቦች ጋር በተያያዘ መንገድ ይበልጥ በዘር ጥላቻ ላይ የተመሠረተ ሆነ ።

በተለይ የናዚ ፋሺስቶች በጀርመን ለደረሰው ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች ሁሉ አይሁድን ተጠያቂ በማድረግ ፀረ አይሁድነትን ዓይነተኛ የትግል መሣሪያቸው አድርገው ተጠቅመውበታል ። በዚህም አይሁድ በተፈጥሮ ዝቅተኛና ወንጀለኛ እንደሆኑ ተቆጠሩ ። የዜግነት መብታቸውንም በማጣት ከሥራቸውና ከኑሮአቸው ተፈናቅለው ተሰደዱ ፤ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩትም እየተጋዙ በግፍ ተጨፈጨፉ ። እስከ ዛሬም ኢምፔሪያሊስቶችና አድኀሮት በአይሁድና አይሁድ ባልሆኑ ሠራተኞችና ሕዝቦች መካከል ቅራኔን በመፍጠር በመካከላቸው መደባዊ የትግል አንድነት እንዳይኖር በማድረግ ሥርዐ አደሩን የሚከፋፍሉበት አንዱ ዘዴ ፀረ አይሁድነት ነው ።

## ፀረ ኮሚኒዝም
*(Anti–Communism)*

የሞኖፖል ካፒታልን ጥቅም የሚያንፀባርቅ በኮሚኒስት ንድፈ ሐሳብና ተግባር ላይ የተነሣ የኢምፔሪያሊዝም ፖሊሲና ርዕዮተ ዓለማዊ አቋም ነው ። የማኅበራዊ ዕድገት ጠላቶች ሁሉ ማለትም የፋይናንስ መሳፍንት፣ ወታደራዊ ቡድኖች ፣ ፋሺስቶች ፣ ቅኝ ገዥዎች ፣ የመሬት ከበርቴዎች በአጠቃላይ ኢምፔሪያሊዝምና ግብረአበሮቹ ይህን መፈክር በማንገብ ግንባር ፈጥረዋል ።

የፀረ ኮሚኒዝም ዋና ይዘት ማኅበራዊ አብዮቶችን በተለያዩ ስልቶች ለመቀልበስ መጣር ሲሆን ፣ ለዚህ ዓላማ መሳካት የሶሻሊስትን ሥርዓት ማጥላላት ፣ የማርክሲዝም ሌኒኒዝም አስተምህሮ ትክክል እንዳልሆነና በተምኔት ላይ እንደተመሠረተ አድርጎ ለማሳየት መሞከር ፣ የኮሚኒስት ፓርቲዎች ፖሊሲዎች ተጨባጭነት እንደሌላቸውና ለጠብ አጫሪነት እንደሚያገለግሉ አድርጎ ማቅረብ ዓቢይ ታክቲኩ ነው ። ኢምፔሪያሊስቶች "የኮሚኒዝምን አደጋ መከላከል" በሚል የተሳሳተ መፈክር ሥር የኮሚኒስቶች አስተሳሰብና ፖሊሲ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንዳያገኝ ለማድረግ ፣ የሠራተኛውን መደብ እንቅስቃሴ ለመበታተን ፣ የዴታንትን ሂደት ለማደናቀፍና የጦር መሣሪያ እሽቅድድምን ተገቢ አድርጎ

ለማቅረብ ይጥራሉ ፤ በኮሚኒስቶች ላይ ብቻ ሳይሆን በሶሻሊዝም ፥ በዲሞክራሲና በማኅበራዊ ዕድገት ላይ ከፍተኛ ዘመቻ ያካሂዳሉ ፤ ማንኛውንም ተራማጅና አብዮታዊ የሆነ ኃይል ሁሉ ያሳድዳሉ ፤ ይጨፈጭፋሉ ።

ፀረ ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ በብሔራዊ ፖሊሲ ደረጃ የታቀደና በማንኛውም የሕዝብ መገናኛ ዘዴ የሚሰራጭ ነው ። ይህ አቋም ርዕዮተዓለማዊ ትግልን የሚያንፀባርቅ ብቻ ሳይሆን ኮሚኒስቶችን ፥ ሠራተኞችንና የብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴዎችን ለማፈን የታቀደ መንግሥታዊ መሣሪያ ነው ።

የለየለት አድኃሪ ፥ ጦረኛና የፋሺዝም ደጋፊ ከሆነው አክራሪ ፀረኮሚኒዝም የተለየ ለዘብተኛ ፀረ ኮሚኒዝም አቋም የያዙ አንዳንድ የቡርዧ ርዕዮተዓለም ደጋፊዎች ተከስተዋል ። እነዚህ ለዘብተኛ ፀረኮሚኒዝም አቋም ያላቸው የቡርዧ ርዕዮተዓለማውያን የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መሥራቾች ለማኅበራዊ ንድፈ ሐሳብ ዕድገት ያደረጉትን ሳይንሳዊ አስተዋጽኦ ቢቀበሉም ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ለዳበረው የቡርዧ ኅብረተሰብ አያገለግልም በማለት የኮሚኒስት ርዕዮተዓለምን ለማዛባት ይጥራሉ ። ይህ የቡርዧውን ርዕዮተዓለም ዝቅጠት የሚያመለክተው ፀረ ኮሚኒዝም አቋማቸው በርዕዮተዓለማዊና በፖለቲካዊ ቀውስ ውስጥ እንዲገቡና ለመንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም እንዲያጎበድዱ መንሥኤ ሆኗል ። ፀረ ኮሚኒዝምና ፀረ ሶቪዬትነት የዘመኑ የቡርዧ ፖለቲካና ርዕዮተዓለም አክራሪ ቀኝ ክንፍ የሚከተለው የሳይንሳዊ ኮሚኒዝምን ንድፈ ሐሳብና ተግባር ለማዛባት ሆን ተብሎ የታቀደ የአድኅሮት መግለጫ ነው ።

# ፊ

## ፈረንሳይ ቁስአካልነት ፣ የ18ኛው ምዕት ዓመት (የ—)
*(French Materialism af 18th Century)*

ከ17ኛው ምዕት ዓመት ቁስአካልነት በጥልቀትም ሆነ በአጠናን ዘዴ የተሻለና ብሔራዊ ክልልን አልፎ አስተዋጽኦ በማድረግ ቁስአካልነትን ከከፍተኛ ደረጃ ላይ ያደረሰ ፍልስፍና ነው ። የእንግሊዝ የ17ኛው ምዕት ዓመት ቁስአካልነት የሚያንፀባርቀው የቡርዧዚውንና የፊውዳል መኳንንቱን ስምምነት ነበር ። የፈረንሳይ ቁስአካልነት ግን የሚገልጸው የተራማጅ ቡርዧውን አመለካከት ስለነበር በኅብረተሰቡ ውስጥ በይበልጥ ጠልቆ ለመግባት ችሏል ። የፍልስፍናው ቀማሪዎችም የላቲን ቋንቋን በመተውና በፈረንሳይኛ ቋንቋ በመጠቀም መዝገበ ቃላት፣ ኢንሳይክሎፒዲያና መጣጥፎች በማዘጋጀት ሐሳባቸውን ለማስራጨት ሞክረዋል ። የዴካርትን ሐሳባዊ አዝማሚያ ወደ ጐን በመተውና ተናክአታዊ አመለካከቱን ብቻ በማዳበር ዕውቀት ከልምድ ስመገኘቱንና ፖለቲካና ትምህርት በኅብረተሰቡ ውስጥ ያላቸውን ወሳኝ ሚና አስተምረዋል ። ከዚህም ጥናት በመነሣት ጠቃሚ የሆኑ የፖለቲካ ንድፈ ሐሳቦችን ቀምረዋል ። ሃይማኖትን በይፋ በመዋጋት ኢአማኒነትን አሰራጭተዋል ። ደ ላሜትሪ ፣ ሄልቬትዮስ ፣ ዲደሮና ሆልባኽ የዚህ ፍልስፍና ታዋቂ አራማጆች ናቸው ።

(ካርቴዥያኒዝምን ይመለከቷል ።)

## ፈርጆች
*(Categories)*

በተፈጥሮ ፣ በኅብረተሰብና በዕውቀት የሚገኙ ክስተቶች የሚያሳዩዋቸውን አጠቃላይና መሠረታዊ ባሕርያት ፣ ገጽታዎችና ግንኙነቶች የሚያንፀባርቁ ጽንሰ ሐሳቦች ናቸው ። ፈርጆች የሚቀረፁት በማኅበራዊ ተግባር ላይ ተመሥርቶ በሚያደገው የዕውቀት ታሪካዊ ሂደት ውስጥ ነው ። በመሆኑም ሰው ስለአካባቢው የጠለቀ ዕውቀት እንዲያገኝ ይረዳሉ ።

የፈርጆች ጽንሰ ሐሳብ ከፍልስፍና ዕድገት ጋር እያደገና እየዳበረ የመጣ ነው ። ለምሳሌ ጥንታውያን ፈላስፎች በዓለም ያሉ ክስተቶች ሁሉ "መነሻ ንጥረ ነገሮች" ከሚሏቸው እንደ ውሀ ፣ እንደአየር ፣ እንደ መሬት ፣ እንደእሳት ፣ ከመሳሰሉት የመነጩ ናቸው በማለት የክስተቶችን ባሕርያት ሁሉ ከነዚህ ንጥረ ነገሮች ባሕርያት አንፃር ለማብራራት ሞክረዋል ።

በፍልስፍና ዕድገት ውስጥ የተከሰቱ አመለካከቶችን መነሻ በማድረግ ስለፈርጆች ዲያሌክቲካዊና ቁስአካላዊ መሠረት የጣለው ማርክሲዝም ነው ። በዚህም መሠረት ፈርጆች የሰው ልጅ ድምር ዕውቀት መግለጫ ፣ የክስተቶች ሁሉ ልዩነትና አንድነት መገንዘቢያ ፣ የዕድገታቸውም ሕግ መረጃ ሆነዋል ። የፍልስፍና ፈርጆች የሰው ልጅ ስለ ቁስአካላዊው ዓለም ያለው ግንዛቤ ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ ተነሥተን ክስተቶችን ሁሉ በተናጠል ወይም እንደተመሳሳይነታቸው በቡድን እየመደብን ከአጠቃላይ ባሕርይና ግንኙነታቸው አንፃር ለመመርመርና ስለቁስአካላዊው ዓለም ያለንን ግንዛቤ በሕዋሳቶቻችን አማካይነት ከምናገኘው ሕውስታዊ መረጃ ወደ ረቂቅ ማሰላሰል ፣ ስለነገሮች ካለን የተናጠል ዕውቀት ወደ ሁለንታዊ ዕውቀት የሚደረግ የውስብስብ ሂደት ውጤት ናቸው ። ስለዚህ ጽንሰ ሐሳቦችንና ፈርጆችን መቅረፅ የረቂቅ አስተሳሰብ ዓይነተኛ ባሕርይ ነው ። ይህም በመሆኑ ፈርጆች የነባራዊውን ዓለም ሕግጋት ለመገንዘብ በሚደረገው ጥረት ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ ። የማናቸውም ነገር ፍሬ ነገርና የዕድገት ሕግጋት ግን በውጫዊ ገጽታ ብቻ የማይገለጹ በመሆናቸው በሕውስታዎቻችን ብቻ ልንደርስባቸው አንችልም ። ከዚህም የተነሣ ከነገሩ ውጫዊ ገጽታ በማለፍና ፍሬ ነገሩን ለመጨበጥ ፈርጆች ስለሚረዱን ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀትን

ለመቅረፅና የሳይንሶችን ሕግጋት ለመረዳት እንችላለን ።

ሁለንታዊ የዕድገት ሕግጋት በፈርጆች እማካይነት የሚገለጹ ስለሆኑ ሕግጋትን ለመረዳት ፈርጆችን መገንዘብ ፣ ፈርጆችን ጠንቅቆ ለማወቅ ሕግጋትን መረዳት ያስፈልጋል ። ይህም የሚያሳየን ፈርጆች በእውነታና በአስተሳሰብ ውስጥ የሚገኙ ክስተቶችን ጠንቅቆ ለማወቅ በሚደረግ የአጠናን ዘዴ ጠቀሜታ እንዳላቸው ነው ።

ፈርጆች የማይለወጡ አይደሉም ፤ ሰዎችም እንዳሻቸው አይፈጥሯቸውም ። በእውነታ ውስጥ የሚገኙ ነገሮችና ክስተቶች እንደሚያድጉ ሁሉ ፈርጆችም እየዳበሩ ይሄዳሉ ። ይህም በአስተሳሰብና በህልውና መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲሁም የፈርጆችንና የዕውቀትን ዲያሌክቲክስ ያሳያል ።

እያንዳንዱ ፈርጅ የነባራዊ እውነታን የተወሰነ ዘርፍ የሚያንፀባርቅ ሲሆን ፈርጆች በድምሩ ወይም በጥቅሉ የተፈጥሮን ዘለዓለማዊ የዕድገትና የቅስቃሴ ሕግጋት እስከ ተወሰነ ደረጃ ይገልጻሉ ።

ፈርጆች በነባራዊ እውነታና በዕውቀት ዕድገት ሕግጋት መሠረት እንዳቸው ከሌላቸው የሚመነጩ ፣ የተያያዙና ሥርዓት ያላቸው ናቸው ።

(ስፍራንና ጊዜን ፣ ይዘትንና ቅርፅን ፣ መንሥኤንና ተገብሮትን ፣ ግዴታንና አጋጣሚን ይመለከቷል ።)

## ፈቃዳዊነት
*(Voluntarism)*

ፈቃድን የዓለም መሠረት በማድረግ ፈቃድ ከተፈጥሮና ከኅብረተሰብ ነባራዊ ሕጐች በላይ ነው የሚልና የሰው ፈቃድ የአካባቢው ሁኔታ ተገዥ መሆኑን የሚክድ የሐሳባዊ ፍልስፍና አዝማሚያ ነው ። ፈቃዳዊነት በተለያዩ መልኮች የሚገለጽ ቢሆንም መሠረታዊ አስተሳሰቡ የተገነባው በፈቃድ የበላይነትና ቀዳሚነት ላይ ነው ።

እንደ ፈቃዳውያን አባባል በዓለም ውስጥ ያሉ ነገሮችን ፣ ክስተቶችን ፣ የሚፈጸሙ ሁኔታዎችንም የምንረዳው የአንድ የተደበቀ ፈቃድ ውጤት መሆናቸውን ስንቀበል ነው ። በነሱ አነጋገር ቁስአካል በጭፍን ተናክአታዊ ሕጎች የሚገዛ በመሆኑ የነገሮች ምንጭና መሠረት ሊሆን አይችልም። የዓለም መሠረት ሐሳብ ነው የሚለውንም (የሐሳባውያን) አመለካከት አይቀበሉትም ፤ ምክንያቱም ሐሳብ እራሱ የፈቃድ ውጤት ከመሆኑም በላይ ነገሮችን የመገንዘብ ችሎታ እንጂ የመወሰን ፣ የማመንጨት፣ የመፈጸም ኃይል የለውም ብለው ስለሚያምኑ ነው ።

ፈቃዳዊነት ወደ ምሥጢራዊነት የሚያመራ ከመሆኑም በላይ የፍልስፍናው መንፈስ ብዙውን ጊዜ የሚገልጸው የኃይልን አምልኮ ነው ። ፈቃድን ከሁሉ በላይ ለማድረግ የሚያሳየው ጥረት የሚያመራው ወደ ኢምክኑያዊ አስተሳሰብ ነው ። ሰውን ለማይታወቅ ኃይል ተገዥ ከማድረግም አያመልጥም፤ ምክንያቱም ፈቃድ በነገሮች ላይ ተፅዕኖ ሊኖረው የሚችለው ከነባራዊ ሕጎች በላይ በመሆን ሳይሆን ሕጎችን ዐውቆ ችሎታውን አመዛዝኖ በዚያው መሠረት ሲንቀሳቀስ ነው ። ከፈቀድኩ ሁሉ ይቻለኛል ማለት የነገሮች ተገዥ ያደርጋል እንጂ በነሱ ላይ ቁጥጥር ለማድረግ አያስችልም ። ሾፐንሀወርና ኒቼ የዚህ ፍልስፍና አራማጅ ከሆኑት ውስጥ ዋናዎቹ ናቸው ።

## ፈቃድ
*(Will)*

ወደ ንቁና አስቀድሞ ወደ ተወሰነ ክንዋኔ የተመራ ተግባርና አንድ ነገር መሆን አለበት ወይም መደረግ አለበት የሚል ግምት ወይም ውሳኔ ነው ። ባጭሩ ፈቃድ የተወሰነ ክንዋኔ ወይም ክንዋኔዎችን ለማካሄድ ሰዎች የሚኖራቸውን ንቁና ቁርጠኛ ውሳኔን የሚገልጽ ጽንሰ ሐሳብ ነው ።

ሐሳባውያን ፈቃድ ከነባራዊው ዓለም የተገነጠለና በነባራዊ ግዴታ ላይ ያልተመሠረተ እንደሆነ በመቁጠር የሰዎችን እንቅስቃሴና ባሕርይ ሐሳባዊ በሆነ መንገድ ለመግለጽ ነፃ ፈቃድ የሚለውን አስተሳሰብ ያራምዳሉ። ሐቁ ግን የማናቸውም ፈቃድ ወይም ንቁና

አስቀድሞ የተወጠነ ዓላማ ያለው የሰው ልጅ ከንዋኔ ምንጭ ነባራዊው ዓለም መሆኑ ነው ። ነባራዊው ዓለም ከግለሰቡ ውስጣዊ ሁኔታዎች ማለትም ፍላጐት ፣ ጥቅም ፣ ምኞት ዕውቀት ወዘተ... አኳያ ሲታይ ግለሰቡ የተለያዩ ዓላማዎችን እንዲወጥንና እንዲወስን ፣ በዚህኛው ወይም በዚያኛው መንገድ እንዲያከናውን ያስገድደዋል ። ስለዚህም ከነባራዊው ግዴታ ተነጥሎ በሐሳባዊ ምኞት ብቻ የሚመረጥ ፈቃድ ነፃ ሊሆን አይችልም ፤ ፈቃድ ነፃ ሊሆን የሚችለው ግን በነባራዊ ግዴታ መሠረት በትክክል የተመረጠ ሲሆን ብቻ ነው ።

ባጠቃላይ ነፃነት ማለት ግዴታን መገንዘብ ፣ ከግዴታ ውጭ መኖር አለመቻልን ማወቅ ማለት ነው ። ግዴታ እስከአልታወቀና ከዚሁ ጋር እስካልተገናዘበ ድረስ ደግሞ ነፃነት እርባና የለውም ። ነፃነት ከተፈጥሮአዊ ሕግጋት ነፃ በመሆን በቅዠት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን እነዚህን ሕግጋት በማወቅና ዕውቀቱ በተቀናበረ መንገድ ወደ ተወሰነ አቅጣጫ ማምራት እንዲችል በሚከፍተው ዕድል ላይ የተመሠረተ ነው ። ይህም ልናያቸው በማንችላቸው ሁለት የሕግ ክፍሎች ማለትም ከውጫዊ የተፈጥሮ ሕግጋት አኳያም ሆነ የሰዎችን አካላዊ ወይም መንፈሳዊ ህልውና ከሚገዙት ሕግጋት አኳያ ተፈጻሚነት ያለው ነው ። ስለዚህም ፍሬደሪክ ኤንግልስ እንዳለው ነፃነት ማለት በአድራጊው ዕውቀት ላይ ተመሥርቶ ውሳኔዎችን ለመወሰን መቻል ማለት ነው ።

የፈቃድ ምንነት ጐልቶ የሚታየው አንድ ግለሰብ አስቀድሞ የወጠነውን ዓላማ ዳር ለማድረስ የተወሰኑ ውስጣዊና ውጫዊ ዕንቅፋቶችን አሸንፎ ለመውጣት ሲታገል ነው ። የፈቃድ የመጀመሪያው ደረጃ ዓላማን የመቀየሱና የመረዳቱ ጉዳይ ነው ። ለክንዋኔው የሚደረገው ውሳኔ ፣ ይህንንም ሥራ ላይ ለማዋል አመች የሆኑትን ዘዴዎች መምረጡ ሁለተኛውን ደረጃ ይይዛል ። አንድ ክንዋኔ የፈቃድ ክንዋኔ ነው ተብሎ ሊገለጽ የሚችለው ከውሳኔ የመነጨ እስከሆነ ድረስ ብቻ ነው ። ፈቃድን የመፈጸም ኃይል የተፈጥሮ ስጦታ አይደለም ። ዓላማን የመምረጥ ዐቅምና ችሎታ ፣ ትክክለኛ ውሳኔዎችን መወሰንና ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም አንድን የተጀመረ ተግባር አጠናቆ መፈጸም የዕውቀት ፣ የልምድ ፣ የትምህርትና እራስን የማስተማር ውጤት ናቸው ። ለምሳሌ ታሪክ የሰዎች ክንዋኔ ውጤት ቢሆንም ሰዎች ግን ታሪክን የሚሠሩት በዘፈቀደ ሳይሆን በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መሀል ያለውን ቅራኔ ተገንዝበው ቁሳዊ ሁኔታቸው የሚፈቅድላቸውን ችሎታ ሲመርጡ ነው ።

(ዕውቀትን ፣ ተግባርን ፣ አብዮትን ይመለከቷል ።)

## ፈጠራ
## *(Creativity)*

አዲስ ቁስአካላዊ እሴቶችንና መንፈሳዊ ፋይዳዎችን የመፍጠር ችሎታንና እንቅስቃሴን ያመለክታል ። ፈጠራ በሂደተ ሥራ ውስጥ የተገኘና በተፈጥሮአዊ ክስተቶች ላይ ሰው ዕውቀቱን አክሎ የተለያዩ ሰብአዊ ፍላጐቶቹን የሚያሟሉ አዳዲስ ነገሮችን የማመንጨቱ ችሎታ ነው ። ሐሳባውያን የፈጠራ ሥራን ምንጭ ዲበ አካላዊ ወይም ደመነፍሳዊ ወዘተ... አድርገው ይመለከቱታል ። ነገር ግን በማርክሳዊ ሌኒናዊ ትክክለኛ አመለካከት የፈጠራ ሥራ የሰው ጠቅላላ አእምሮአዊና ቁሳዊ ኃይሎች ማለትም ምናቡ ፣ ልምዱ ፣ የችሎታ ደረጃውና ሥራው ተዳምረው አዲስ እውነታ ለመፍጠር የሚሳተፉበት ሂደት ነው ። ይህም በልምድና በተግባር የሚገኝና የሚዳብር ነው ።

(ሥራን ፣ ሶሻሊስታዊ የሥራ ውድድርን ይመለከቷል ።)

## ፉሪየ ፣ ፍራንሷ ማሪ ሻርል
## *(Fourier, François Marie Charles)*

ከ1772—1837 የኖረ ፣ ከአንድ ፈረንሳዊ ነጋዴ ቤተሰብ የተወለደ ተምኔታዊ ሶሻሊስት ነው ። ፉሪየ የፈረንሳይ አብዮት ርዕዮተዓለማውያን በሚሉትና በተጨባጩ እውነታ መካከል ያለውን ቅራኔ ፣ በሀብታሞችና በድሆች መካከል ያለውን ተፃራሪነት ፣ የአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ መውደቅን ይፋ በማውጣት በቡርዧው ኅብረተሰብ ላይ ጥልቀት ያለው ጊስ የሰነዘረ ምሁር ነው ።

ቆሚለታለሁ የሚለውን የሶሻሊስት ሥርዓት ትክክለኛ አድርጎ ለማቅረብ የተጠቀመው ስብእናን ለመቅረፅ አካባቢና ትምህርት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ በሚለው በፈረንሳይ ቁስአካላውያን በኩረ ሐሳብ ነው ።

በፉሪየ አመለካከት የሰው ባሕርያት በሙሉ እንከን የለሽ ናቸው ። ስህተት የሰው ባሕርይ አይደለም ፤ የስህተት ምንጩ ሰው የሚኖርበት ኅብረተሰብ ነው ። የሰውን ፍላጐት ማፈን ተገቢም አስፈላጊም አይደለም ፤ ይልቁንም የሰው ፍላጐት በተሻለ ሁኔታ የሚረካበትንና የሚያድግበትን ኅብረተሰብ መፍጠር አስፈላጊ ነው ። በአእምሮና በጉልበት ሥራ ፣ በከተማና በገጠር መካከል ያለው ቅራኔ መፈታት ምርታማነትን ይጨምራል ፤ ሀብት እንዲትረፈረፍ ያደርጋል ። ክፍፍልም በሥራና በችሎታ መጠን ይሆናል ።

ፉሪየ ስለመጪው ኅብረተሰብ የሰነዘራቸው ሐሳቦች ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው ናቸው ። ይሁን እንጂ የወዝአደሩን ታሪካዊ ተልዕኮና ማኅበራዊ አብዮትን በሚመለከት ትክክለኛ ግንዛቤ ማጣቱ በሌሎቹ ተምኔታውያን ሶሻሊስቶች ላይ የታየው ድክመት የሱም ድክመት መሆኑን ያሳያል ።

(ተምኔታዊ ሶሻሊዝምን ይመለከቷል ።)

## ፌሽተ ፣ ዮሐን ጎቲሊብ

*(Fichte, Johann Gottlieb)*

ከ1762—1814 የኖረ ፣ ከካንት ቀጥሎ የተነሣ የጀርመን ብሉይ ሐሳባዊ ፍልስፍና መሪ ነበር ። የጀርመንን መዋሀድ የሚደግፍና የፊውዳላዊ ስሪትና በርሱም ላይ ተመሥርቶ ይገኝ የነበረው ጥቅምና ማዕረግ እንዲጠፋ የታገለ ፣ "ተግባራዊ" የሆነ ፍልስፍናን ፣ ሥነ ምግባርን ፣ መንግሥትንና ሕጋዊ ሥርዓትን በጣም የሚደግፍ ፈላስፋ ነበር ። ሆኖም ፊሽተ "ተግባርን" የተረዳው የሥነ ምግባራዊ ክዋኔ ብቻ እንደሆነ አድርጎ ሲሆን "ተግባራዊ" ፍልስፍና በሥራ ሊገለጽ የሚችለው የሳይንሳዊ ዕውቀት ሥርዓት በቅድሚያ ሲመቻችለት ነው ብሎ ያምን ነበር ። ዓለምን የፈጠረው ግላዊ ያልሆነ ነገር ግን ፍጹማዊነት ያለው አንድ ኃይል ነው ፤ የሰው እኔ የመነጨው ከፍጹማዊው እኔ ሲሆን የሰው እኔ ግን ውሱንና ከተፈጥሮ ጋር የሚታገል ነው ይላል ።

አእምሮአችን እውነትን ለማስተዋል የሚችለው የምክኑያዊ ዕውቀት አንዱ ክፍል በሆነው በአእምሮታዊ ጭልታ አማካይነት ነው ። ምክኑያዊ ዕውቀት የተመሠረተው በእንብሮ ፣ በተቃርኖና በአስተፃምሮ ሥነ አመክንዮአዊ ሂደት ላይ ነው ። ይህም የሚገልጸው በእኔና እኔ ባልሆነ ማለትም በሰዎችና በተፈጥሮ መካከል ያለውን ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት ነው ። በሥነ ምግባርም ረገድ የፊሽተ አስተሳሰብ ነፃነት ምክንያት አልባ የሆነ ክንዋኔ ሳይሆን ሰዎች ስለ ግዴታ (ስለ አስገዳጅ ሁኔታዎች) ባላቸው ሐሳብ ላይ ተመሥርተው የሚፈጽሙት ድርጊት ነው ይላል ። ለሰዎች የሚሰጠው የነፃነት መጠን በግለሰቡ ጥበብ የሚወሰን ሳይሆን ግለሰቡ በሚገኝበት ታሪካዊ ወቅት የሚወሰን ነው ብሎም ያምናል ። በወቅቱ በጀርመን ውስጥ ፊውዳሊዝም የተንሰራፋ ስለነበር ካፒታሊስታዊ ዕድገት ይበጃል ብሎ ያሰበው "ዝግ የነጋዴዎች" መንግሥት ሲመሠረት እንደሆነ ማለትም የጀርመን ቡርዧዚ ኢንዱስትሪን ያሳድግ ዘንድ መንግሥት ኢኮኖሚውን ከውጭ ተፎካካሪዎች ዝግ ሲያደርግና ሲከላከል ነው የሚል ነበር ። በዚህ ተምኔታዊ መንግሥት ውስጥ አንዳንድ አድኃሪ ገጽታዎች (ጠባብ የጀርመን ብሔር የበላይነት ስሜት) ቢታይበትም በጀርመን ውስጥ የሚርካንቲሊዝምን ማቆጥቆጥ የሚያግዝ ነበር ።

የፊሽተ አስተሳሰብ ከመሠረቱ ሐሳባዊ ቢሆንም ከላይ እንደተጠቀሰው ለካፒታሊዝም ዕድገት በወቅቱ የቆመ በመሆኑና ትክክለኛው መንግሥት የሚጠፋና የሚከስም መንግሥት ነው በማለቱ ተራማጅ ነበር ። ለዚህም ነው አንጋፋዎቹ የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መሥራቾች የፊሽተን አስተምህሮ አድኃሪና ተራማጅ ገጽታዎች በጥልቀት ካጠኑ በኋላ እርሱ የሰጠውን አስተዋጽኦ በማድነቅ በተለይም ኤንግልስ ከጀርመን ፈላስፎች መካከል ከሚኒስቶች ስፊሽተ ታላቅ ክብር ይሰጣሉ ያለው ።

## ፊውዳሊዝም
*(Feudalism)*

ፊውድ ማለት ሰፋፊ የመሬት ይዞታ ማለት ሲሆን ፊውዳሊዝም ሰፋፊ መሬቶች የምርት ዋነኛ መሠረቶች የሆኑበትና በግል የተያዙበት ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ማለት ነው ።

የጥንታዊ ጋርዮሽ ወይም የባሪያ አሳዳሪ ሥርዓቶች ተንከታኩተው ከወደቁ በኋላ የሚመጣና ከሞላ ጐደል በሀገሮች ውስጥ ሁሉ የታየ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ነው ። ፊውዳሊዝም ከባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት ቀጥሎ ሁለተኛው ኅብረተሰብ በመደብ የተከፋፈለበት የታሪክ የዕድገት ደረጃ ነው ። የፊውዳሉ ሥርዓት መሠረታዊ መደቦች የመሬት ባለቤቱና ገበሬው ሲሆኑ የገዥው መደብ በልዩ ልዩ ማኅበራዊ ክፍሎች (ሰሻል እስቴት) የተከፋፈለና ዝቅተኛ የእስቴት ክፍል በከፍተኛው ክፍል ሥልጣንና ኃይል ሥር የሚወድቅበት ሥርዓት ነው ። በዚህ ሥርዓት ውስጥ ከሚገኙት ከፍተኛ ፊውዳሎች ውስጥ ቤተክህነት አንዷ ናት ።

የፊውዳሉ ሥርዓት የምርት ግንኙነት የሚመሠረተው የማምረቻ መሣሪያዎች በተለይም መሬት በአብዛኛው በፊውዳሉ መደብ በሚያዝበትና ገበሬው የፊውዳሉ መደብ ጥገኛ እንዲሆን በሚያደርገው የከፊል የማምረቻ መሣሪያዎች ባለቤትነት ላይ ነው ። ከዚህ ይዞታ የተነሣ ገበሬው ለፊውዳሉ መደብ እንዲሠራና ግናቸውንም የጉል በት አገልግሎት እንዲሰጥ የሚያደርግ ሥር ዓት ነው ። ለፊውዳሉ መደብ በጉልበትና በሌላም መልክ መስጠት ያለበትን ኪራይ ከከፈለ በኋላ ገበሬው የራሱን አነስተኛ መሬት ስለሚያርስና የምርቱም ተጠቃሚ ስለሚሆን ለማምረቻ የሚገለገልባቸውን መሣሪያዎች የማሻሻል ፍላጐት ይኖረዋል ። ስለሆነም በፊውዳሉ ሥርዓት ውስጥ የምርት ኃይሎች የሚያድጉት ጥገኛ በሆነውና (የቤት ዕቃዎች ፣ አነስተኛ መሣሪያዎች) በሥራው ላይ የተወሰነ ቁሳዊ ጥቅም ባለው የገበሬው ጉልበት (ሥራ) አማካይነት ነው ።

የፊውዳሉ ስልተ ምርት ዓይነተኛ ባሕርይና የብዝበዛ መልክ የመሬት ኪራይ ሲሆን ይህም የመሬት ኪራይ የጉልበት ፣ የዓይነትና የገንዘብ መልኮች አሉት ። የመሬት ኪራይ በአብዛኛው ጊዜ ጭሰኛው በትርፍ ጉልበቱ የሚያስገኘውን ምርት ብቻ ሳይሆን በእርሻ ላይ ጉልበቱ ከሚያፈራው ምርት የተወሰነ መጠንንም ጭምር ያጠቃልላል ።

ፊውዳሊዝም ገጠሩ በከተማው ላይ ተፅዕና የሚያሳድርበትና የሚበዘበዙበት ፣ ኢኮኖሚው ተፈጥሮአዊ ግለትም ምርቱ ለፍጆታ እንጂ ለገበያ የማይመረትበት ማኅበራዊ ሥርዓት ነው ። ቴክኖሎጂ የጐላ ዕድ ገት የማያሳይበት ፣ የአካባቢዎች (ማኅበረሰቦች) ተበታትነና ተነጣጥሎ መገኘት ፣ የመገናኛና የመጓጓዣ አገልግሎቶች አለመ ስፋፋት ፣ ከወግ ፣ ከልማድና ከሃይማኖት ከፍተኛ ጫናና ጥብቅ ቁጥጥር የተነሣ የም ርት ኃይሎች ዕድገት ዝቅተኛ የሆነበት ሥር ዓት ነው ። የምርት ዋነኛ መሠረት ሰፋፊ የመሬት ይዞታ የሆነበትና በርካታ ብዙሰሞቹ መሬቶች ግን በገበሬው የሚያዙበት ፣ ገበሬውም በፊውዳሉ መደብ ኢኮኖሚያዊ ጥገኝነት ሥር የሚገኝበትና የርሱም ሥልጣን ታዛዥ የሆነ በት ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ነው ። በዚህ ሥር ዓት ማኅበር የከተማው ነጋዴ በግልጽ ተደራ ጅቶ ሥራውን ቢያከናውንም የፊውዳል ገዥ መደብ አባላት ለቅንጦት የፍጆታ ዕቃ ዎች ከፍተኛ ገንዘብ ስለሚያወጡ ለማምረቻ መሣሪያዎች መሻሻል የሚያደርጉት ጥረት በጣም ዝቅተኛ ነው ።

የፊውዳሉን ሥርዓት ላዕላይ መዋቅር ልዩ የሚያደርጉት የራሱ የሆኑ ባሕርያት አሉት ፤ እነዚህም የፊውዳሉ መንግሥት ቅርፅ ፍጹማዊ ንጉሠ ነገሥታዊ አገዛዝ መሆን ፣ በኅብረተሰቡ ኅሊናዊ ሕይወት ውስጥ ደግሞ ሃይማኖታዊ ርዕዮተዓለም የበላይነትን መያዝና በአጠቃላዩ ሲታይ የኅብረተሰቡ ማኅበራዊ አስተሳሰብ ዕድገት ሃይማኖታዊ መልክ መያዝ ናቸው ። እያንዳንዱ ፊውዳል ሰፋፊ መሬቱን ከሌሎች ለመከላከል ፣ ሰፍረው የሚገኙትን አራሾች ረግጦ ግብር ለማስከፈ ልና ለመበዝበዝ የሚያስችለው የራሱ ወታደ ራዊ ኃይል አለው ። በዚህ ዓይነት ከላይ እስከታች የተዋቀረው የፊውዳሉ ሥርዓት ቁንጮ ንጉሠ ነገሥቱ እንደመሆኑ ሃይማኖ ትም ከላይ እስከታች ድረስ በተዋረድ ከሥር ዓቱ ጋር ተዋቅሮ ይገኛል ። ዝቅተኛው እስ ቴት በከፍተኛው ሥር እንዳለ ሁሉ ንጉሠ

ነገሥቱም በእግዚአብሔር የተመረጠና የእግዚአብሔር የበታች እንደሆነ ይሰብካል ።

እንደማንኛውም በመደብ የተከፋፈለ ኅብረተሰብ ሁሉ የፊውዳሉ ኅብረተሰብ ታሪክ በመደብ ትግል ላይ የተመሠረተ ነው ። የነበረው መደብ በገጠር ውስጥ ተበታትኖ የሚኖር እንደመሆኑ ቅራኔውና ትግሉ ጐልቶ አይታይም ፤ ለማስተባበርም አስቸጋሪ ነው ። ነገር ግን በከተማ ውስጥ በግልጽ ተደራጅቶ የሚገኘው የከተማ ነጋዴ የተሰባሰበ በመሆኑና ይዞም ኃይል ስለሚሰጠው የፊውዳሉ ሥርዓት ቅራኔ ጐልቶ የሚታየው በከተማ ውስጥ በፊውዳሉና ወደ ቡርዧዚነት በሚለወጠው ነጋዴ መሀል ነው ። የነበረው እመፅ ሃይማኖታዊ ሽፋን ቢይዝም የፊውዳሉን ሥርዓት በማናጋት ውድቀቱን አፋጥኖታል ። ከዚህም የተነሣ የፊውዳሉ ሥርዓት በካፒታሊስቱ ማለትም በሦስተኛውና በመጨረሻው የመደብ ኅብረተሰብ ተተካ ።

(የቡርዧ አብዮትን ፣ ካፒታሊዝምን ይመለከቷል ።)

## ፊውዳላዊ የመሬት ኪራይ
*(Feudal Ground Rent)*

የፊውዳሉ ሥርዓት የገዥ መደብ አባላት መሬትን በግል ንብረትነት በመያዝ ከገባሮቻቸው የሚወስዱት ክፍያ ፊውዳላዊ የመሬት ኪራይ ይባላል ። ፊውዳላዊ የመሬት ኪራይ ገባሮች የሚፈጥሩትን ተረፈ ምርት ሙሉ በሙሉ ያጠቃልላል ። ፊውዳላዊ የመሬት ኪራይ የሚይዘው ቅርፅ የጉልበት ሥራ ፣ የምርት ክፍያ ወይንም የገንዘብ ክፍያ ሊሆን ይችላል ። በተለይ በፊውዳሉ ዘመን የመጀመሪያ ክፍል ላይ በቀጥታ በጉልበት መልክ የተደረገ ብዝበዛ ዋናው የኪራይ ዓይነት ነበር ። በዚህ የብዝበዛ ዓይነት መሠረት ገባሩ በሳምንት ለተወሰኑ ቀናት ለፊውዳል ገዥው እንዲሠራ ይገደድ ነበር ። የፊውዳሉ ሥርዓት እያደገ ሲሄድ በምርት ዓይነት የሚደረግ ብዝበዛ እየተጠናከረ በጉልበት ሥራ መልክ ከሚደረገው ብዝበዛ ጋር ጐን ለጐን ፣ እያደርግም እየተካው መሄድ ጀመረ ። በዚህ የክፍያ ቅርፅ አማካይነት ገባሩ የራሱ ይዞታ በሆነው መሬት ላይ ያፈራውን እህል ፣ ከብት ፣ ዶሮ ፣ ሌሎች የእርሻ ምርት ዓይነቶች እንዲሁም ልዩ ልዩ የእደ ጥበባት ምርቶች ለፊውዳል ገዥው ለመስጠት ይገደድ ነበር ። በተለይ በፊውዳሉ ዘመን መጨረሻ ክፍል የሸቀጥ ምርትና የገንዘብ ልውውጥ እያደገ በመሄዱ የፊውዳል ገዥዎች በዓይነት ይቀበሉት የነበረውን ክፍያ በይበልጥ በገንዘብ መልክ ይቀበሉ ጀመር ። የሸቀጥ ምርትና የገንዘብ ልውውጥ መስፋፋት የፊውዳል ገዥዎች ለሀብት የነበራቸውን ጥም በማባባስ የፊውዳሉ ሥርዓት ብዝበዛ እየከፋ እንዲሄድ አድርጐታል ።

## ፊውዳል ሶሻሊዝም
*(Feudal Socialism)*

በከፊል ሐዘንና ትካዜን ፣ በከፊል ስድብና ዘለፋን ያዘለ ፣ በከፊል ያለፈውን ዘመን (የፊውዳሉን) ጥሩነትና የመጪውን ዘመን አስፈሪነት የሚያስተጋባ በቡርዧው ሥልጣን መያዝ የተቀጡ መሳፍንት የቂም መወጫ ልፈፋ ነው ። የሕዝብን ድጋፍ ለማግኘት ሲል ለይስሙላ የመሳፍንቱን ጥቅም ችላ በማለትና ለተበዝባዥ የሠራተኛ መደብ ተቆርቋሪ በመምሰል የቡርዧውን ኅብረተሰብ የተቃወመና የነቀፈ አስተሳሰብ ነው ። መሳፍንቱ ቡርዧዚውን በፖለቲካ ትግል እንደማይቋቋሙት ስለተረዱ ዘመቻቸውን በሥነ ጽሑፍ ጦርነት ብቻ እንዲወሰኑ በመገደዳቸው በቡርዧዚው ላይ መራራ ፣ መሰሪና አጥንት ሰብረው የሚገቡ ሂሶችን ሰንዝረዋል ። ሆኖም የፊውዳል ሶሻሊዝም የታሪክን ግስጋሴ ያልተገነዘበ በመሆኑ መሣቂያ መሳለቂያና ውድቅ ሆኗል ።

## ፊዚዮክራሲ
*(Physiocracy)*

በ18ኛው ምዕት ዓመት በፈረንሳይ ውስጥ ተጠናቅሮ የቀረበ የብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አካል ነው ። ፊዚዮክራሲ የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም የተፈጥሮ ኃይል ማለት ነው ። በፊዚዮክራሲ ጥናት

ውስጥ በይበልጥ የሚታወቁት መሥራቹ ፍራንኳ ኪኔና የሱ ዋና ተከታይና አዳባሪው ሮቤር ዣክ ቱርጎ ናቸው ።

ፊዝዮክራሲ የተባለው የኢኮኖሚ አስተሳሰብ ሀብት የሚመነጨው ከልውውጥ ወይም ከንግድ ነው የሚለውን የሚርካንቲሊዝም አስተያየት በመቃወም ሀብት የሚፈጠረውና ለክምችት የሚሆን የተጣራ ገቢ የሚገኘው በምርት መስክ ነው የሚል አስተሳሰብ የሚያራምድ ነው ። ሆኖም የተጣራ ገቢ ወይም የሀብት ምንጭ ማንኛውም የምርት ተግባር ሳይሆን የእርሻ ሥራ ብቻ ነው በማለትና ይህም ሀብት ከተፈጥሮ የተገኘ (ከመሬት) ጸጋ ነው በማለት የቀረበ አስተያየት ነው ። ይህንን የኢኮኖሚ አስተያየት የመሠረተውና በተቀናበረ መንገድ ያቀረበው ፈረንሳዊው ፍራንኳ ኪኔ ነበር ።

ኪኔ እርባታ የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ በጥናቱ ውስጥ ተጠቅሞ ያቀረበ ሊቅ ነበር ። የኪኔ ዋናው የኢኮኖሚ ጥናት በ1758 ያቀረበው "ኢኮኖሚክ ቴብል" የተባለው ነው ። በዚህ ሠንጠረዥ ውስጥ ከእርሻ ሥራ የሚገኘውን እሴት በኪኔ አጠራር የተጣራ ገቢ ተብሎ የተሰየመው ተረፈ እሴት እንዴት በየኅብረተሰቡ መደቦች መካከል እንደሚሰራጭና በየዓመቱም የእርባታው ሁኔታ እንዴት እንደሚካሄድ በማሳየት ቀርቧል ።

በኪኔ አመለካከት የተጣራ ገቢ ከእርሻ ምርት ላይ ልዩ ልዩ የምርት ወጪዎችና የገበሬው ፍጆታዎች ተቀንሰውለት የሚቀረውና ገበሬው ለባለመሬቱ ፣ ለንጉሡና ለቤተ ክህነት በገንዘብ ወይም በዓይነት መልክ የሚሰጠው ድርሻ ነው ። በሠንጠረዡ ውስጥ ኪኔ እርባታው በቀላል እርባታ እንደሚካሄድ አድርጎ አቅርቧል ። ሠንጠረዡ በመሠረቱ የእርባታና የዝውውር ሂደትን የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ የጠቅላላውን ብሔራዊ ኢኮኖሚ እርባታና ስርጭት ሂደት ሥርዓት ባለው መንገድ ለማቅረብ ለመጀመሪያ ጊዜ የተደረገ ሙከራ ነው ። ይህ ዘዴም ብሔራዊ ገቢን ለማስላት ጠቀሜታ አለው ። በተጨማሪም ሠንጠረዡ የእርባታ ሂደት ያለማቋረጥ እንዴት እንደሚከናወን ያሳያል ። ኪኔ እርባታ የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ በጥናቱ ውስጥ ተጠቅሞ ያቀረበ ሊቅ ነበር ። ካርል ማርክስ ኪኔ የጠቅላላ ማኅበራዊ ሀብትን የአመራረትና የእርባታን ሂደት በሠጠረዥ በማቅረቡ ከፍተኛ ግምት ሰጥቶታል

ኪኔ በወቅቱ የፈረንሳይን ኅብረተሰብ በሦስት መደቦች በመከፈል ገበሬዎችን ምርታማ መደብ ፣ ባለመሬቶችን ደግሞ የባለንብረት መደብ ፣ የእደ ጥበብ ሠራተኞችን ፣ ካፒታሊስቶችንና ወዝአደሮችን ደግሞ በአንድ ላይ መካን መደብ በማለት ሰይሟቸዋል ። ከዚህም ሌላ ኪኔ ስለ ተዘዋዋሪ ካፒታልና ስለ ቋሚ ካፒታል በተዘዋዋሪ መንገድ በመናገር የካፒታልን የተለያዩ ክፍሎች ለመግለጽ ለመጀመሪያ ጊዜ ሙከራ ያደረገ ተመራማሪ ነበር ።

የፊዝዮክራሲ ተከታይና አዳባሪ የነበረው ሮበር ዣክ ቱርጎ በርካታ የኢኮኖሚ ምርምሮችን አድርጓል ። ካደረጋቸውም ውስጥ ስለገንዘብ፣ ስለ ወረቀት ገንዘብ፣ስለእርሻ ሀብት አፈጣጠርና ክፍፍል ስለ ሸቀጦች ዋጋና ስለ ካፒታል ልዩ ልዩ መልኮች ይገኙበታል ።

የፊዝዮክራሲ አስተያየት ዋና ዋና ድክመቶች ምርታማ ሥራን የእርሻ ሥራ ብቻ አድርጎ ማየቱ ፣ የእርሻ ሀብት የተፈጥሮ ጸጋ ውጤት ነው ማለቱ ፣ ሌሎች ምርታማ ተግባሮች ሀብት እንደማይፈጥሩ አድርጎ መመልከቱና የተጣራ ምርት እርሻ እንደ ሆነ አድርጎ ማቅረቡ ናቸው ።

ፊዝዮክራቶች ከእንግሊዝ ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መሥራቾች አንፃር ሲታዩ አመለካከታቸው በተወሰነ ደረጃ ከኋላ ቀርነት ያልተላቀቀ በመሆኑና የካፒታሊዝምም ዕድገት በፈረንሳይ ውስጥ በወቅቱ ከእንግሊዝ ሁኔታ ጋር ሲወዳደር በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ ስለነበር አመለካከታቸው የእርሻን ሥራና የእርሻን ሁኔታ በማጋነንና በማዳነቅ ላይ ሊያተኩርና ስለ ኢንዱስትሪ የነበራቸው ግምት ደግሞ እጅግ ዝቅተኛ ሊሆን ችሏል ።

(ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን ይመለከቷል ።)

## ፋሺዝም
*(Fascism)*

እንደ ራሱን የቻለ ማኅበራዊ ሥርዓት ሳይሆን በካፒታሊዝም አጠቃላይ ቀውስ ወቅት የሚከሰት ፣ የካፒታሊዝም ውድቀትና ቀውስ ውጤት የሆነ ፍጹም አድኃሪ የፖለቲካ አዝማሚያ ወይንም ንቅናቄ ነው ።

ይህም ሁኔታ ከሚከሰትባቸው ገጽታዎች ውስጥ ሽብር ፈጠራ ፣ ፀረ ፓርላማዊ ዲሞክራሲነት ፣ ጭፍን ፀረ ኮሚኒስትነት፣ ብሔራዊና ማኅበራዊ ትምክህተኝነት ሊሆኑ የተለያዩ ነፃ ሕዝባዊ ድርጅቶችን በተለይም ሠራተኛው መደብ የሚደራጅባቸውን ማኅበራትና ተቋሞችን ማፍረስ ወይም ማፈን ዋና ተግባሩ ነው ።

በማኅበራዊ ይዘቱ ፋሺዝም ውጥንቅጥ ይዘት የሚኖረው ቢሆንም በአብዛኛው ንዑስ ከበርቴውን ፣ ቦዘኔውንና በኑሮ ቀውስ የተነካ ተስፋ የቆረጠውን የሠራተኛውን መደብ ክፍል የሚጨምር ነው ። የፋይናንስ ምንጩ ትላልቅ ባለኢንዱስትሪዎች ፣ የመሬት ከበርቴዎችና የገንዘብ ድርጅቶች ባለቤቶች ፣ በአጠቃላይም የሠራተኛውን መነሣሣት የሚቃወሙና ማንኛውንም አብዮታዊ የሠራተኛ መደብ እንቅስቃሴ ለማፈን የሚጥሩ ወገኖች ናቸው ። በመሆኑም ኮሚንተርን በትክክል እንደገለጸው ፋሺዝም ግልጽና የለየለት አድኃሪ ፣ ትምክህተኛና ኢምፔሪያሊስት የሆነ የፋይናንስ ካፒታል ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ነው ።

ፋሺዝም የካፒታሊዝም ፣ የኢምፔሪያሊዝምና የአድኅሮት ኃይሎች በሂደት ከሚያጋጥማቸው ታሪካዊ ሁኔታዎች የሚመነጭ እንደመሆኑ በተለይ ፣

— የካፒታሊስት ግንኙነት ተረጋግቶ መቀጠል ሲያቅተውና ቀውስ ሲደርስበት ፣

— ከከተሞች ዕድገት ጋር በነዚሁ ውስጥ ከሚኖሩት ምሁራን ፣ ንዑስ ከበርቴዎችና በመጠኑም ከሠራተኛው መደብ መካከል በተለያዩ ምክንያቶች የአቋም መናወጥ ደርሶባቸው በተወሰነ መደባዊ አመለካከት ከመጽናት ይልቅ የመዋዠቅ ሁኔታ ሲዛመት ፣

— እንዲሁም የገጠሩ ንዑስ ከበርቴ ክፍል ባለበት የኑሮ ሁኔታ በመበሳጨት የተቃውሞ አዝማሚያ ሲይዝና ፣ ነገር ግን ይህ አዝማሚያ ከትክክለኛ መደባዊ አመራር እጦት የተነሣ በውዥንብር ሁኔታ ውስጥ ሲሆን የሚፈጠር የዘቀጠ የካፒታሊዝም አስከፊ ውጤት ነው ።

በኅብረተሰቡ ውስጥ የካፒታሊስቱ ቀውስ በሚፈጠርበት ጊዜ ፋሺስቶች ለዚህ ቀውስ መፍትሔ የሚያስገኙ መስለው ለመታየት አንዳንድ ፀረ ካፒታሊስት ሐረጎችን ይወረውራሉ ፤ ለሕዝቡ መረጋጋትና ለችግሩ መፍትሔ የሚሆኑ መሠረታዊ ለውጦች እንደሚያደርጉም ሆነው ይቀርባሉ ። ሥልጣን ከያዙ በኋላም አንዳንድ ቁልፍ የማምረቻ ተቋሞችን ለሕዝብ ጥቅም በሚል ሽፋን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያውላሉ ። ኃይላቸውን ካጠናከሩ በኋላ ግን ፍጹም ፀረ ሠርቶ አደር የሆነና ትላልቅ ካፒታሊስቶችን ይበልጥ የሚያደነድን የትብብር ሁኔታ በመፍጠር የሕዝባዊ ዲሞክራሲ መሠረቶችን ሁሉ ያጠፋሉ ። በተለይ ለሠራተኛው መደብ ትግል የሚያግዙ ሁኔታዎችን ሁሉ ይደመስሳሉ ።

የፋሺስት መንግሥት ሕዝባዊ ድጋፍ ለማግኘትና ለአምባገነንነት ርምጃ የኢኮኖሚ ምንጩን ለማጠናከር ሲል አንዳንድ ቁልፍ የማምረቻ ተቋሞችን ቢይዝም ከሞኖፖሊስቶቹ ጋር በመመሳጠርና በመደጋገፍ ስለሚሠራ የግል ንብረትን አያጠፋም ። እንዲያውም የካፒታሊስት ሥርዓትን የኃይል መሠረት ይበልጥ በተሰባሰበና በተካበተ ሁኔታ እንዲቀጥል በማድረጉ የሠርቶ አደሩን ኢኮኖሚ ጥቅምና ሕዝባዊ የፖለቲካ ትግሉን ይበልጥ የሚፃረር ሁኔታ ይፈጥራል ። በተለይም ወዝአደሩን አፋኝ በሆኑ ሕጎችና ተቆጣጣሪዎች አማካይነት በማስገደድ እንዲሠራ ያደርጋል ። ሥራ ማቆምንና አድማ መምታትን ፈጽሞ ስለሚከለክልና የሠራተኛ ማኅበራትንም በሙሉ ቁጥጥር ሥር ስለሚያውል ሠራተኛው ብሶቱን የሚገልጽባቸው መድረኮች የሉትም ፤ መብቱን የሚያስከብርበት ኃይልም አይኖረውም ። በአጠቃላይ የፋሺዝም ዋነኛ ዓላማ የሠራተኛውን መደብ ትግል መቅጨት ፣ በተለይም የዚህ ትግል ግንባር ቀደም የሆኑትን ኮሚኒስቶችና ድርጅታቸውን ማጥፋት ነው ።

በአጠቃላይ ፋሺዝም የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ሥርዓት መናጋትና የአንዳንድ ኅሊናዊ ሁኔታዎች መቃወስ የሚፈጥሩት እንደመሆኑ ቡርዧዚዎች ከዚህ ማጥ ለመውጣት በከተሞችና በገጠሮች በሚገኙ በመካከለኛ ቡርዧዚዎችና በንዑስ ከበርቴው የወላዋይነት ባሕርይ ንቃተ ኅሊናቸው

ዝቅተኛ በሆኑ ወገኖች በመጠቀም ፡ በብሔራዊ ስሜት ፣ በዘር ትምክህተኝነትና በመሳሰሉት አድኃሪ ስልቶች ውዥምብር በመፍጠር የወዝአደሩንና የድሀ ገበሬዎችን መደባዊ ንቅናቄ የሚመቱበት ሥልጣን ነው ።

ከሀገራቸውም አልፈው በአጐራባች ሀገሮችና በዓለም አቀፍ ደረጃም ሳይቀር የትምክህተኝነት ወረራ ያደርጋሉ ፤ ለዚህም የሁለተኛውን የኢምፔሪያሊስቶች ጦርነት ቀስቃሽ በመሆን የዓለምን ሕዝብ ለእልቂት ያበቁትን ፋሽስቶች ማለትም የኢጣልያኑን ሞሶሎኒ ፣ የጀርመኑን ሂትለርንና የጃፓኑን ቶጆን መጥቀስ ይበቃል ። ፋሽስቶች የሠርቶ አደሩን አመፅ ለማፈን ሕዝቦችን ለመውረር እንዲረዳቸው የጦር ኃይልና የስለላ ድርጅት ያስፋፋሉ ፤ መመሪያቸውም በማስፈራራትና በሌላው ላይ ኃያል በመሆን ላይ የተመሠረተ ነው ። በሥልጣን መባለግ ፣ መሠረታዊ የሆኑ ማኅበራዊ መብቶችን መድፈርና በአጠቃላይ የነጭ ሽብር አገዛዝን ማስፈን የፋሺዝም ባሕርያት ናቸው ። ፋሺስታዊ አገዛዝን ለመቋቋምና ለመደምሰስ ሰፊ ፀረ ፋሺስት ግንባር መፍጠር አስፈላጊ ነው ።

(ብሔራዊ ሶሻሊዝምን ፣ የኮርፖሬት መንግሥትን ይመለከቷል ።)

## ፋይናንስ ምስፍና (የ—)

*(Financial Oligarchy)*

ቁጥራቸው እጅግ አነስተኛ የሆነ ትላልቅ የፋይናንስ ካፒታሊስቶች በኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ውስጥ ኢኮኖሚውንና ፖለቲካውን በቁጥጥራቸው ሥር በማዋል የሚመሠርቱት አገዛዝ የፋይናንስ ምስፍና ይባላል ።

የፋይናንስ ምስፍና አባላት በልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ፣ የፖለቲካና የቤተሰብ ግንኙነት የተሳሰሩ ናቸው ። እነዚህ በአንድነት የፋይናንስ ሞኖፖል ቡድን በመባል የሚታወቁ ቁጥራቸው አነስተኛ የሆነ ትላልቅ የፋይናንስ ካፒታሊስቶች የኢንዱስትሪ ፣ የባንኮች ፣ የብድር ፣ የመድን የመጓጓዣ ፣ የንግድና የመሳሰሉትን ሞኖፖል ኩባኒያዎች በግል ወይንም በጋራ በቁጥጥራቸው ሥር ያውላሉ ።

የፋይናንስ ሞኖፖል ቡድን በኢኮኖሚው ላይ የበላይነት እንዲኖረው ለማድረግ የሚጠቀምበት አንድ ዋና ዘዴ በአንድ ትልቅ ወይም መሪ ወይም እናት ኩባንያ ውስጥ የመቆጣጠሪያ አክሲዮን ይዞ ኩባንያውን በቁጥጥሩ ሥር ማድረግና ይህ ኩባንያ ደግሞ በበኩሉ ሌሎች ኩባንያዎችን እንዲሁ በቁጥጥሩ ሥር እንዲያውል ማድረግ ነው ። በአንድ ኩባንያ ውስጥ አክሲዮኖች በብዙ ባለአክሲዮኖች መካከል ሲከፋፈሉ ከጠቅላላው 10% (አሥር ከመቶ) ያህል እንኳ አክሲዮን ያለው ባለአክሲዮን ኩባንያውን በቁጥጥሩ ሥር ለማዋል ይችላል ። በዚህ በመቆጣጠሪያ አክሲዮን አማካይነት አንድ ወይንም የተወሰኑ የፋይናንስ ካፒታሊስቶች ኩባንያውን በቁጥጥራቸው ሥር ያውሉታል ።

ይህ ኩባንያ ደግሞ በበኩሉ ከሌሎች የጋራ አክሲዮን ኩባንያዎች የመቆጣጠሪያ አክሲዮን በመግዛት ተቀጥላው ያደርጋቸዋል ። አሁንም ደግሞ እነዚህ የጋራ አክሲዮን ኩባንያዎች በበኩላቸው በሌሎች እነስ ባሉ የጋራ አክሲዮን ኩባንያዎች ውስጥ የመቆጣጠሪያ አክሲዮን ይገዛሉ ። በዚህ ዓይነት የተሳሰሩት ቁጥራቸው በርካታ የሆነ ኩባንያዎች ካፒታልም ከዋናው መሪ ኩባንያ ካፒታል እጅግ የሚበልጥ ይሆናል ። በዚህም አኳኋን ጥቂት ትላልቅ የፋይናንስ ካፒታሊስቶች መጠኑ እጅግ ከፍተኛና ንብረትነቱ የሌሎች የሆነ ካፒታል በቁጥጥራቸው ሥር በማዋል ከፍተኛ የሞኖፖል ትርፍ ያገኛሉ ።

በኩባንያዎቹ የቁጥጥር አክሲዮን ባለቤት ከመሆን ሌላ የፋይናንስ ሞኖፖል ቡድን ኢኮኖሚውን በቁጥጥሩ ሥር ለማዋል የሚጠቀምበት አንድ ዋና ዘዴ የብዙ የጋራ አክሲዮን ኩባንያዎችን የዲሬክተሮች ቦርዶች በቁጥጥሩ ሥር ማዋል ነው ። የፋይናንስ ሞኖፖሊስቶችና ወኪሎቻቸው ቁጥራቸው በርካታ በሆነ የኢንዱስትሪ ፣ የባንክና የንግድ ሞኖፖሎች የዲሬክተሮች ቦርዶች አባላት በመሆን የሞኖፖሎቹ እንቅስቃሴዎች ከጥቅማቸው መዳበር ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ ።

ባሁኑ ጊዜ የፋይናንስ ምስፍና የኢምፔሪያሊስት ሀገሮችን ኢኮኖሚ በቁጥጥሩ

ሥር አውሉት ይገኛል ። ለምሳሌ በአሜሪካ ከአጠቃላዩ የአክሲዮን መጠን ከመቶ አጅ ሰባ ሁለቱን በግል ባለቤትነት ይዞ የሚገኘው ከአጠቃላዩ ሕዝብ ከመቶ አንዱ ብቻ ነው ። በግል ከተያዘው ከጠቅላላው የሀገሪቱ ሀብትም ከመቶ 53ቱን ይዘው የሚገኙት የግል ሀብት ባለቤት ከሆኑት ውስጥ ከመቶ አምስቱ ብቻ ናቸው ።

የፋይናንስ ምስፍና አባላት በግል ባለቤትነት የያዙትም ንብረት ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ ዕድገት በማሳየት ላይ ይገኛል ። ለምሳሌ አሁንም በአሜሪካ ውስጥ በ1920ዎች ዓመታት የሮስቻይልድ ቤተሰብ አባላት ንብረት 660 ሚሊዮን ዶላር እንደደረሰ ይነገራል ፤ በአሁኑ ጊዜ ወደ 4 ቢሊዮን እንደደረሰ ይገመታል ። በዚያው ጊዜ ውስጥ የፎርድ ቤተሰብ አባላት የግል ንብረት ከ660 ሚሊዮን ወደ 3.8 ቢሊዮን ዶላር ፣ የሚሎንስ ቤተሰብ አባላት ከ450 ሚሊዮን ወደ 4.6 ቢሊዮን ዶላር ፣ እንዲሁም የዱ. ፖ. ቤተሰብ አባላት የግል ንብረት ከ239 ሚሊዮን ወደ 5 ቢሊዮን ዶላር ሊያድግ ችሏል ።

የፋይናንስ ምስፍና አባላት በቁጥጥራቸው ሥር የሚያውሉት የካፒታል መጠን በግል ሀብትነት ከያዙት ሀብት በብዙ እጥፍ በልጦ ይገኛል ። ለምሳሌ ሚሎንስ ከ50 ቢሊዮን ዶላር የበለጠ ካፒታል በቁጥጥሩ ሥር ሊያውል ችሏል ። አሁንም በአሜሪካ ለምሳሌ ሞርጋን የተሰኘው የሞኖፖል ድርጅት ከ250 ቢሊዮን ዶላር ፣ የሮክፌለር ቤተሰብ ከ160 ቢሊዮን ዶላር እንዲሁም የአሜሪካ ባንክ ከ170 ቢሊዮን ዶላር በላይ የሆነ የካፒታል መጠን በሥራቸው በሚገኙ ኩባንያዎች አማካይነት በቁጥጥራቸው ሥር ሊያውሉ ችለዋል ። በፋይናንስ ምስፍና አባላት መካከል በተካበተ የግል ሀብት መጠንም ሆነ በቁጥጥራቸው ሥር በሚገኝ ካፒታል መጠን ረገድ አልፎ አልፎ መሸጋሸግ ቢኖርም የሚታየው አጠቃላይ ሁኔታ ሀብትና የፖለቲካ ሥልጣን በጥቂት ሰዎች እጅ እየተሰባሰበ መምጣቱ ነው ።

(የፋይናንስ ካፒታልን ይመለከቷል ።)

## ፋይናንስ ካፒታል
*(Finance Capital)*

በባንክ ሞኖፖሎች ካፒታልና በኢንዱስትሪ ሞኖፖሎች ካፒታል ጥምረት ምክንያት የሚፈጠረው ካፒታል የፋይናንስ ካፒታል ይባላል ። ስለዚህ የፋይናንስ ካፒታል የባንክ ካፒታል ወይንም የኢንዱስትሪ ካፒታል ሳይሆን በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የተፈጠረ አዲስ ዓይነት ካፒታል ነው ።

የፋይናንስ ካፒታል ታሪካዊ አመጣጥ እንደሚከተለው ነው ። በ20ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ላይ በአንዳንድ በኢንዱስትሪ በዳበሩ ካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ የባንክ ካፒታል መሰባሰብ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በመድረሱ የካፒታሊስት ብድርን በቁጥጥሩ ሥር አዋለ ። ለዚህ ለባንክ ካፒታል በሞኖፖል መያዝም የኢንዱስትሪ ምርት መሰባሰብና በሞኖፖል መካሄድ ቁሳዊ መሠረት ጣለለት ። ትላልቅ የኢንዱስትሪ አምራች ድርጅቶች ትናንሽ ባንኮች ሊሰጡ የማይችሉት መጠኑ ከፍተኛ የሆነና አብዛኛውን ጊዜም የረጅም ጊዜ ብድር ፈላጊ ሆኑ ። ይህም ትናንሽ ባንኮች ኅብረት እንዲፈጥሩና ካፒታላቸው እንዲማከል አደረገ ። በዚህ ዓይነት እየተሰባሰበና እየተማከለ የመጣው ካፒታል የባንክ ሞኖፖሎችን መፈጠር አስከተለ ።

የባንክ ሞኖፖሎች መፈጠር በበኩሉ በባንኮችና በኢንዱስትሪ ሞኖፖሎች መካከል የግንኙነት ለውጥ አመጣ ። የባንክ ሞኖፖሎች ለኢንዱስትሪ ሞኖፖሎች ብድር ከመስጠት አልፈው በአክሲዮን ግዥ አማካይነት የኢንዱስትሪ ድርጅቶችን በከፊል በባለቤትነት መያዝ ጀመሩ ። የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶችም በበኩላቸው በትላልቅ ባንኮች ውስጥ ባለአክሲዮን በመሆን ከባንኮቹ ጋር ያላቸው ግንኙነት ይበልጥ እንዲጠናከር አደረጉ ። በዚህ ዓይነት የባንክ ካፒታልና የኢንዱስትሪ ካፒታል ትላልቅ ባለቤቶች ጥቅም የተሳሰረ ሆነ ። የኢንዱስትሪና የባንክ ሞኖፖሎች ጥምረትም በዚህ አኳኋን ተጀመረ ። የዚህም ውጤት በማንኛውም የኢኮኖሚ መስክ ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር የቻለውና ማንኛውንም የኢኮኖሚ መስክ ከጥቅሙ ጋር እንዲተሳሰር ያደረገው አዲስ ዓይነት ካፒታል ፣ የፋይናንስ ካፒታል መከሰት ሆነ ።

የፋይናንስ ካፒታሊስቶች በሌሎች ድርጅቶች ውስጥ የመቆጣጠሪያ አክሲዮን በመግዛት በቁጥጥራቸው ሥር የሚገኘው የካፒታል መጠን እንዲያድግ በኢኮኖሚው ላይ ያላቸውም ቁጥጥር እንዲጠናከር ያደርጋሉ ።

ከያዝነው ምዕት ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ መጀመሪያ አካባቢ ወዲህ ደግሞ የፋይናንስ ካፒታል አዳዲስና በልዩ ልዩ መስክ የተሰማሩ የፋይናንስ ድርጅቶችን በማቋቋምና በማደራጀት ዕድገቱን ሊያፋጥን ችሏል ። ከነዚህም መካከል የባንክና የኢንዱስትሪ ካፒታል በአንድነት የሚያቋቁሟቸውንና የሚያጠናክሯቸውን ለምሳሌ የመድን ኩባንያዎችን ፣ የቁጠባ ባንኮችን ፣ የሙአለንዋይ ኩባንያዎችንና የመሳሰሉትን ለመጥቀስ ይቻላል ። በእነዚህ ድርጅቶች አማካይነትም ሞኖፖሊስቶች የካፒታል ክምችት ምንጮችን በማበራከት የኅብረተሰቡን ልዩ ልዩ ክፍሎች ተቀማጭ ገንዘብ በቁጥጥራቸው ሥር በማዋል የበለጠ ለመበልጸግና በካፒታሊስት ሀገሮች ኢኮኖሚና ፖለቲካ ላይ ያላቸውን ቁጥጥር ለማጠናከር ችለዋል ። በድንበር ዘለል ኩባንያዎችም አማካይነት የፋይናንስ ካፒታል ወደኋላቀር ሀገሮች እየተዛመተ ከፍተኛ ብዝበዛ ያካሂዳል ፤ የፖለቲካ ተፅዕኖም ያሳድራል ።

(የፋይናንስ ምስፍናን ይመለከቷል ።)

## ፋይዳ
*(Value)*

ነገሮች ፣ ክስተቶች ፣ ሐሳቦች ፣ ደንቦች ፣ ሕጎች ወዘተ... ለሰዎች የሚሰጡት ጠቀሜታ ፣ ያላቸው ጥሩነትና ተፈላጊነት ፣ የሚፈጥሩት ብያኔ በአጠቃላይ ፋይዳ ይባላል ። በሐሳባውያን አመለካከት ፋይዳዎችና ሳይንሳዊ ብያኔዎች በዓይነት የተለያዩ ናቸው ። ሳይንሳዊ ብያኔዎች ተጨባጭና ነባራዊ ሲሆኑ ፋይዳ ግን የሚገልጸው መሆን ያለበትን ነው ። ለምሳሌ መሬት ፀሐይን ትዞራለች የሚለው ሳይንሳዊ ብያኔ ነው ፤ ትክክለኛው ኅብረተሰብ መደብ አልባ የሆነው ኅብረተሰብ ነው የሚለው ግን ኅብረተሰብ መሆን ያለበትን የሚገልጽ ብያኔ በመሆኑ ፋይዳ ነው ።

ሁለቱን መለያየት ለግንዛቤ ጠቃሚ ነው ቢባልም ፋይዳ ተጨባጭ መሠረት የለውም ወደሚለው ሐሳባዊ አመለካከት እንዳያመራ መጠንቀቅ ይገባል ። ፋይዳ እውን መሆን ያለበት መሆኑ የሚገልጸው የሰው የተግባር ውጤት መሆኑን እንጂ ከሌላ መንፈሳዊ ዓለም የሚመጣ መሆኑን አይደለም ። ሐሳባውያን ለመካድ የሚሞክሩት ፋይዳ የሰው ቁሳዊ እንቅስቃሴ ውጤትና ቁሳዊ ምንጭ ያለው መሆኑን ነው ። ሰው በራሱ ጥረት የሚያመነጨውን ነገር እንደ ስጦታ መቁጠሩ የሚገልጸው ባይተዋር የሆነን አመለካከት ነው ። በመሆኑም መሆን ያለበት ነገር የሚፈልቀው እውን ከሆነው መሆን ይኖርበታል ። ይህ ካልሆነ ደግሞ መሆን ያለበት ለእውነታ ባይተዋር ስለሚሆን ምናባዊ ወይም ተምኔታዊ ብቻ ይሆናል ።

ማርክሲዝም አስተሳሰብ ፣ ሕግ ፣ ሥነ ውበት ፣ ሥነ ምግባር ፣ ወዘተ.. የላዕላይ መዋቅር ክፍል መሆናቸውንና የሚመነጩትም ከቁሳዊ መሠረት መሆኑን በማሳየት ሳይንሳዊ የሆነ የፋይዳ አጠናን ዘዴ ቀይሷል ። ነገሮች የፋይዳ መልክ የሚይዙት የምርት ግንኙነት በሚጠይቀው አመለካከት አንፃር መሆኑ ፋይዳዎች የመደብ ይዘት እንዳላቸው ያስረዳል ። ሰናይና እኩይ ፣ እውነት ፣ ፍትህ ፣ ዲሞክራሲ ወዘተ... ብለን የምንጠራቸው ፋይዳዎች የሚያንፀባርቁት የመደቦችን የትግል ኅሊናዊ ሁኔታ ነው ። የፋይዳዎች ታሪካዊነት የሚገልጸው ተለዋዋጭ መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን እያደጉና እየሰፉ ማለትም ወደ ሁለንታዊነት እየተሰወጡ እንደሚሄዱ ነው ። ለምሳሌ ነፃነት በመደብ ጥቅም ክልል የተወሰነ ሲሆን የገዥውን መደብ መብት ብቻ የሚገልጽ ይሆናል ። መሠረቱ ደግሞ እየሰፋ ሲሄድና ከመደብ ይዘቱ ሲላቀቅ ሁለንታዊ በሆነ መንገድ በኮሚኒስት ሥርዓት ውስጥ ይከሰታል ። ይህ ሁለንታዊነት የሚያረጋግጠው የእውነንና የመሆን ያለበትን ማለትም የአምሳልን ውህደት ይሆናል ።

(ሥነ ፋይዳን ፣ አምሳልን ይመለከቷል ።)

## ፌቢያን ሶሻሊዝም
*(Fabian Socialism)*

ከመሠረታዊና ሥር ነቀል ለውጥ ይልቅ ለአዝጋሚና ለጥገናዊ ለውጥ የቆመ ፣ ማርክሲ

ዝም ሌኒኒዝምን አጥብቆ የሚፈራ የንዑስ ከበርቴ ሶሻሊዝም ነው ። ይህ አድኃሪ ዝን ባሌ በተለይ በእንግሊዝ ከፍተኛ ተቀባይነትን ከማግኘቱም በላይ ብዙ ተከታዮችንም ያፈራ ነው ።

የዚህ አዝማሚያ አራማጆች ወጣት ምሁራን ሲሆኑ ከነዚህም መሀል እንደ ሲድኒ ፣ እንደ ግራሀም ዋላስና እንደ ጆርጅ በርናንድ ሾው ያሉት በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ናቸው ። አዝጋሚ ለውጥ "በኅብረተሰብ ውስጥ መካሄዱ የማይቀር ነው" በሚል እምነት ፌቢያውያን በሕዝባዊ ድርጅቶች ተሰባስበ መታገልን አጥብቀው ይቃወማሉ ፤ ከዚህ ይልቅ በሥልጣን ላይ ላሉት ሰዎች ያላሰለሰ ምክር በመስጠት ኅብረተሰብን ለመለወጥ ትናንሽ የምሁራን ቡድኖች ማቋቋምን ይመርጣሉ ። ከዚህም በመነሣት ባለ ሥልጣኖች ለኅብረተሰብ መልካሙን እንዲያደርጉ ምክር የሚሰነዝሩበትን "ፌቢያን ኤሴይስ" የተሰኘ ልሳናቸውን በ1889 ማውጣትና ማሰራጨት ጀመሩ ። ፌቢያን ሶሻሊዝም ከመሠረታዊ ለውጥ ይልቅ ለጥገናዊ ለውጥ ፤ ከመደብ ትግል ይልቅ ለድርድር ያጎበደደ በመሆኑ ለኅብረተሰቡ ነፃነት የሚጠቅም ሆኖ አልተገኘም ።

(ጠጋኝነትን ይመለከቷል ።)

## ፌዴሬሽን
*(Federation)*

ሁለት ወይንም ከሁለት በላይ የሆኑ ሀገሮች በወል የሚመሠርቱት የፖለቲካና የአስተዳደር አንድነት ነው ። በፌዴሬሽን ውል የገባው እያንዳንዱ ወገን ለጋራው የፖለቲካ አንድነት ሲል በውጭ ጉዳይ ፣ በመከላከያና በሌሎችም ዋና ዋና ጉዳዮች ሥልጣኑን ከራሱ አሳልፎ ለጋራ ተቋሙ ይሰጣል ። ነገር ግን በግዛቱ ክልል የፌዴሬሽኑን ዓላማ በማይፃረር ሁኔታ በውስጥ ጉዳይ ላይ የተወሰነ ሥልጣን ይኖረዋል ።

በፌዴሬሽን የሚዋሃዱትን ወገኖች የሥልጣን ክልል የሚወስን የፌደራል ሕገ መንግሥት አለ ። ከዚሁ ጋር የፌደራሉ መንግሥት በየጊዜው የሚያወጣቸው ሕጐችና የሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች ሕገ መንግሥቱ በሚፈቅደው መሠረት መሆናቸውን የሚያረጋግጥና በዚህ ላይ ሲነሡ የሚችሉትን ውዝግቦች የሚፈታ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይኖራል ። ፍርድ ቤቱ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የሠፈሩትን አጠቃላይ ሕጎችና በነዚሁ ላይ ተመሥርተው የሚወጡትን ሌሎች ሕጎች የማብራራትና የመተርጐም ሥልጣን አለው ። ሕገ መንግሥቱም እንዲሻሻል ከተፈለገ ተፈጻሚነት የሚያገኘው የተወሰኑ የፌዴሬሽኑ አባል ወገኖች ሲስማሙበት ብቻ ይሆናል ። የፌደሬሽን ሕገ መንግሥት ከአንድ ወጥ መንግሥት የሚለየው በአንድ ወጥ መንግሥት ሕግ የሚያወጣ አንድ ሕግ አውጭ አካል ብቻ መኖሩ ነው ።

በታሪክ እንደታየው በተለያዩ ሀገሮችና ጊዜያት የፌደሬሽን አቋም ያላቸው መንግሥታት ተመሥርተዋል ። ከነዚህም ውስጥ የሶቭዬት ሶሻሊስት ፌደሬሽን ፣ የዩናይትድ ስቴትስ ፣ የአርጀንቲና ፣ የብራዚል ፣ የሜክሲኮ ፣ የካናዳ ፣ የማሌዥያ ፣ የአውስትራሊያና የቬኑዙዌላ ፌደራላዊ መንግሥታት ጥቂቶቹ ናቸው ። ነገር ግን ብዙ ሀገሮች የፌደሬሽን መንግሥታዊ አቋም ያላቸው ቢሆኑም ዓላማና ይዘታቸው ተመሳሳይ አይደለም ። ለምሳሌ የአሜሪካ (ዩ. ኤስ. ኤ) ሕገ መንግሥት በፌደሬሽን ውል መሠረት የተገናኙ ወገኖች በግላቸው ከሌሎች መንግሥታት ጋር ስምምነት እንዳያደርጉ ይከለክላል ። የሶቭዬት ኅብረት ሕገ መንግሥት ግን ይህን እስከተወሰነ ደረጃ ይፈቅዳል ። በተግባር ይህን መብት መጠቀሙ አስፈላጊ ሆኖ ባይገኝም የኅብረት ሪፐብሊኮች የራሳቸው ወታደራዊ ኃይል ጭምር ሊኖራቸው እንደሚችል ይጠቅሳል ። እንደዩክሬንና ቤሎሩሲያ ያሉት የኅብረት ሪፑብሊኮች ደግሞ በተባበሩት መንግሥት ጉባኤዎች ላይ ጭምር የራሳቸውን ተወካዮች የመላክ መብት አላቸው ።

በካፒታሊስት ሀገሮች መካከል የሚመሠረት የፌደሬሽን መንግሥታዊ ተቋም ተልዕኮ የተለያዩ ግዛቶችንና ወይም ሀገሮችን ባንድ ላይ በማምጣት ለካፒታል ብዝበዛ ስፌ የጥሬ ሀብት ፣ የሰው ጉልበት ምንጭና የሸቀጥ ማራገፊያ ገበያ በመፍጠር ካፒታ

ሊዝም እንዲጠናከርና እንዲስፋፉ ማድረግ ነው ። ይህም የቡርዧውን የበላይነት የሚያ ጠናክር ይሆናል ። በአንፃሩ የሶሻሊስት ፌደ ሬሽን ብዙ ብሔሮችንና ብሔረሰቦችን በወዝ አደራዊ ዓለም አቀፋዊነት መርህ መሠረት መደባዊ አንድነታቸውን በማጠናከር ካፒ ታሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን በመደምሰስ ሰው በሰው የማይበዘበዝበትን ጠንካራ ሶሻ ሊስት ሥርዓት ብሎም ኮሚኒስት ኅብረተ ሰብን ለመገንባት የሚያስችል ሁኔታን የሚ ፈጥር ነው ። በሶሻሊስት ሥርዓት የፌደሬሽን መንግሥታዊ አቋም የሚያስፈልገው ብዙ ብሔሮች ባሉባቸው ሀገሮች ውስጥ የብሔርን ጥያቄ በሳይንሳዊ መንገድ ለመፍታት ነው ።

(የብሔር ጥያቄን ይመለከቷል ።)

## ፍልስፍና

*(Philosophy)*

የኑባሬንና (የተፈጥሮ ፣ የኅብረተሰብ...) የሐሳብን ግንኙነት የሚያጠና የዕውቀት ፈርጅ ነው ። የአጠናኑ መርህና ዘዴ የሚገ ዛው ቀዳማይ ሐሳብ ወይም ቁስአካል በሚ ለው ጥያቄ ነው ። ለዚህ ጥያቄ ከሚሰጠው መልስ አንፃር ፍልስፍና ተቃራኒ በሆኑ ሐሳባዊና ቁስአካላዊ አመለካከቶች ይከፈላል። የቅራኔው አንድነት ሂደት የፍልስፍና የዕድ ገት ታሪክ መሠረት ነው ።

የፍልስፍና መሠረታዊ ጥያቄ ሲተነተን ሥነ ዕውቀታዊና ማኅበራዊ ምንጮች እንዳ ሉት እንረዳለን ። የዓለም ታዋቂነት ሊረጋገጥ የሚችለው ዕውቀት በቁስአካል ወይም በሐሳብ ቀዳሚነት ላይ ሲመሠረት ነው የሚ ለው ጥያቄ በአእምሮና በጉልበት ሥራ መካ ከል ያለውን ፋክክር የሚያንፀባርቅ በመሆኑ ፍልስፍና መደቦች ስበላይነት የሚያደርጉ ትን ትግል የሚገልጽ ነው ። ፍልስፍና በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት ውስጥ መወለዱ የሚያረጋ ግጠው ማኅበራዊ ምንጭ ያለው መሆኑን ነው ።

ዓለም ታዋቂ ናት አይደለችም የሚለው ጥያቄ እራሱ ብዙ ጥያቄዎችን ያቀፈ ነው ። የእውነት መመዘኛ ፣ የትክክለኛ ሐሳብ ሕግ ጋት ፣ የዕውቀት ምንጭ ወሰንና የአጠቃ ቀም ስልት ወዘተ...ምንድን ናቸው በሚሉ ንዑስ ጥያቄዎች የሚዘረዘር ነው ። ለጥ ያቄዎቹ ትክክለኛ መልስ ሊገኝ የሚች ለው በቁስአካል ወይም በሐሳብ ቀዳሚ ነት ላይ ስንመሠረት ነው የሚለው አቋም አከራካሪ ሊሆን የሚችለው የሰዎች ሀልውና፣ ጥቅምና ክብር በነዚህ ጥያቄዎች ስለሚመ ዘኑ ነው ።

ሐሳባዊነት እንደሚለው ከሆነ ሁለቱ ማለትም ዕውቀትና ዓለም ከሐሳብ የመነጩ ሲሆን ነው ዕውቀት ለሰው ጠቃሚ ፣ ዓለ ምም ታዋቂ ሊሆኑ የሚችሉት ። ምክንያቱም የኑባሬ በሐሳብ ሕግጋት መገዛት ሐሳብን የበላይና ሁሉን ገዥ ያደርገዋል ። የዚህ አመ ለካከት መደባዊ ፍች ግልጽ ነው። ፍልስፍናው ከቁሳዊ ምርት ነፃ የሆነው መደብ ገዥ፣ አስተ ዳዳሪና መሪ መሆኑን ትክክለኛ ከማድረጉም በላይ ለአገዛዙ ንድፈ ሐሳባዊ ድጋፍና ሥነ አመክንዮአዊ አመለካከት በመስጠት በጥቅ ሙም አንፃር እውነትንና ስህተትን፣ ሰናይንና እኩይን (ሥነ ምግባር) ውብንና ጥፉን ፣ (ሥነ ውበት) ለይቶ እንዲደነግግ ያደርገዋል ። በአን ፃሩም ይህን አመለካከት የሚቃወም ፣ ለሰው ልጅ ደኅንነት፣ ክብርና አንድነት የሚበጀው በቁስአካል ቀዳማይነት ላይ የተመሠረተ ዕው ቀት ነው የሚል ከተጨባጭ ሁኔታ በመነሣት ለብዙኃኑ ማለትም ለአምራቹ ነፃ መውጣት የሚታገል ከኢሳይንሳዊ አመለካከት ለመላቀቅ በቁስአካላዊው ሀልውና ተጠቃሚ ለመሆን አስፈላጊውን ሥነ አመክንዮአዊ ፣ ሥነ ዕው ቀታዊ፣ ሥነ ምግባራዊና ሥነ ውበታዊ አመ ለካከቶች የሚቀርፅ ቁስአካላዊ ፍልስፍና ይከሰ ታል ። በሁለቱ መካከል ገለልተኛ ወይም አስ ታራቂ በመምሰል ዓለም ታዋቂ አይደለችም እያለ ኅብረተሰቡን ጥርጣሬ ውስጥ በመክተት የሁለቱን ቅራኔ ለማድበስበስ የሚጥር ፣ በስውር ለሐሳባዊነት ወገናዊ የሆነ የኢታዋ ቂነት ፍልስፍናዊ አመለካከትም በትግሉ ውስጥ ይሰለፋል ። የፍልስፍና ታሪክና ዕድ ገት የተመሠረተው በነዚህ በተቃራኒ አመለ ካከቶች ግጭትና እርስበርስ መወሳሰን ነው ።

ፍልስፍና የሚያቅፋቸው የጥናት መስ ኮች ሁሉ ( ሥነ ዕውቀት ፣ ሥነ ምግባር ፣ ሥነውበት ፣ ፖለቲካዊ ፍልስፍና ፣ ሥነ አመክ ንዮ ፣ ወዘተ...)አጠቃላይ ግንዛቤን የሚጠይቁ ናቸው ። ይህ አጠቃላይ ባሕርይ የሚገልጸው ፍልስፍና በሰው ልጅ ባህላዊ ታሪክ ውስጥ የሚጫወተውን ሚና ነው ። ፍልስፍና አጠ ቃላይ በመሆኑ የተለያዩ ዕውቀቶችንና ልም

ዶችን አንድ መልክ በመስጠትና መርሆች በማቀነባበር የተዋቀረ አመለካከት የሚያስገኝ የዕውቀት ክፍል ነው ። የማኅበራዊ ኅሊና ፈርጅ መሆኑም በዚህ አጠቃላይ ሚናው ይረጋገጣል ። በማሰባሰብና በማዋቀር ከፍተኛ አካሉን አንጥሮ አወጣ ፤ መሪ አደረገ ከሚለው አጠቃላይ ፍች አንፃር ሲታይ ፍልስፍና ለሰዎች ከተወሰነ ሁኔታ አንፃር የተዋቀረ አመለካከት ስለሚሰጥና ልዩነት ወደ ዳበረ አንድነት ስለሚቀየር ይህም የንቃተ ኅሊናን ዕድገት የሚያመለክት በመሆኑ ለኅሊና ዕድገት የሚያደርገው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን እንረዳለን ።

ይህ የዳበረ ማለትም የተዋቀረና ውስብስብ የሆነ ንቃተ ኅሊና ከፍተኛ ደረጃ ሊደርስ የሚችለው ከመደባዊ ውሱን አመለካከት ሲላቀቅ ነው ። በመሆኑም ከቁስአካላዊ ሁኔታ በመነሣት ብዙኅኑን አቅፎ ጭቆናንና ብዝበዛን በማስወገድ አንዱ ከሌላው የሚነጥቅ ሳይሆን በነፃ ተራድኦ ሥርዓት ላይ የተመሠረተ ዕድገት እንዲስፍን የሚታገለው ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍና ታሪካዊ የበላይነት ይኖረዋል ። ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍና የፍልስፍናን የሩቅ ዓላማ ማለትም በአንድነት የተዋቀረና የዳበረ ንቃተ ኅሊና ማስገኘቱን በተግባር እውን የሚያደርግ በመሆኑ የሐሳባዊና የቁስአካላዊ ፍልስፍናን ቅራኔ የሚፈታ የትግላቸው ከፍተኛና በዓይነትም የተለየ ውጤት ነው ።

(ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነትን ፤ ኅሊናዊ ሐሳባዊነትን ፣ ነባራዊ ሐሳባዊትን ይመለከቷል።)

## ፍልስፍና መሠረታዊ ጥያቄ (የ—)

*(Fundamental question of philosophy)*

ጥያቄው የሚመለከተው በአሳቦትና በቁስአካል መካከል ያለውን ግንኙነት ነው ። ከሁለቱ ቀዳማይ የትኛው ነው የሚለውን ጥያቄ የሚመረምር ሲሆን ከጥያቄው ጋር የተያያዘውን የሰው ዕውቀት ነባራዊ መሆን አለመሆኑንም አብሮ ይመለከታል ። ጥያቄው መሠረታዊ የተባለበት ምክንያት በፍልስፍና ውስጥ ያሉትን ሁለት ተቃራኒ አዝማሚያዎች በግልጽ የሚያስቀምጥና የማንኛውንም ፍልስፍናዊ ጥያቄ አመለካከትና አቋም የሚገልጸው ከዚህ አንፃር በመሆኑ ነው ።

በሐሳባውያን አመለካከት ቀዳሚው ሐሳብ ሲሆን ቁስአካል በሐሳብ የተፈጠረና በሱም የሚገዛ ነው ። ሆኖም በሐሳባዊ ፍልስፍና ውስጥ ኅሊናዊ ሐሳባውያን የሰው ዕውቀት ነባራዊ አይደለም የሚል አቋም አላቸው ። በቁስአካላውያን አመለካከት ቁስአካል ቀዳሚ ሲሆን ሐሳብ የሱ ውጤት ነው ። ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት አሳቦትን የቁስአካል ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ በማድረግ የውጭው ዓለም ነፀብራቅ እንደሆነ ያስረዳል ። አሳቦትም በነባራዊው ዓለም ላይ ያለውን ተፅዕኖ በማጤን ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት ስለአሳቦትና ስለኑባሬ ግንኙነት የሚሰጠው የተሟላ ማለትም ዲያሌክቲካዊ መልስ ነው ።

(ፍልስፍናን ፣ ተግባርን ፣ ገድፈ ሐሳብን ፣ ነፀብራቅን ይመለከቷል ።)

## ፍልስፍና ታሪክ (የ—)

*(History of philosophy)*

የፍልስፍናን አመጣጥ ፣ የዕድገቱን ሕጎችና ዋና ዋና ምዕራፎች እንዲሁም በአዝማሚያዎች መካከል የሚካሄደውን ትግል የሚያጠና የፍልስፍና ክፍል ነው ። ይህ የዕውቀት ክፍል የተመሠረተው በተለያዩ ፍልስፍናዊ ሥርዓቶች መካከል የጠበቀ የውስጥ ሥነ አመክንዮአዊ ግንኙነቶች እንዳሉና የፍልስፍና ዕድገትም ከአጠቃላይ የኅብረተሰብና የዕውቀት ዕድገት ጋር ግንኙነት እንዳለው ከተከሰተ በኋላ ነው ። በዚህ ሐሳብ እስከ መጨረሻው ገፍቶ የፍልስፍና ታሪክ ሥርዓት እንዳለው ያስረዳው ሄግል ነው ። በሄግል አመለካከት እውነት በታሪክ ሒደት ብቻ የሚገለጽ ሳይሆን እራሱ የታሪክ ውጤት ነው ። በመሆኑም ማንኛውንም ግላዊ የፍልስፍና ሥርዓት ወይም አመለካከት ከፊላዊና ውሱን ነው ። እውነት ማለት የእነዚህ ግላዊ ፍልስፍናዎች አጠቃላይ ሥርዓት ሲሆን የነሱ ወጤት የሆነው አዲሱና አጠቃላይ ፍልስፍና የፍልስፍና ከፍተኛ ደረጃ ነው ። ይህ ሄግሊያዊ የፍልስፍና ታሪክ የሚያንፀባርቀው ዲያሌክቲካዊ አመለካከትን ቢሆንም በሄግል አስተሳሰብ ዕድገቱ የሚገልጸው የሐሳቡን ዕድገትና ታሪክ ብቻ በመሆኑ የአስተሳሰቡ ቁሳዊ መሠረት ማጣት ፍልስፍናውን የተዛባ አድርጎታል ።

የፍልስፍና ታሪክ ትክክለኛ መሠረት ያገኘው በዲያሌክቲካዊ ቁስአካላዊ አመለካከት ነው ፣ ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት

ፍልስፍናን የማኅበራዊ ንቃተኅሊና ክፍል አድርጐ በመመልከትና በመሠረትና በላዕላይ መዋቅር መካከል ያለውን ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት በማጤን የፍልስፍና ታሪክ ከኅብረተሰብና ከዕውቀት ታሪክ ጋር የተያያዘበትን ተጨባጭ ሕግ አስገንዝቧል ። በተለይም የፍልስፍና ታሪክ መሠረታዊ ሕግ በቁስአካልነትና በሐሳባዊነት መካከል የሚካሄደው ትግል መሆኑን በማሳየት ፍልስፍናዊ አመለካከቶች ከየት እንደሚመነጩ ፣ የየትኛውን ማኅበራዊ ኃይል ጥቅም እንደሚያንፀባርቁና በማንዛቤአዊ ይዘታቸው እንዴት እርስ በርስ እንደሚወሳሰኑ ለማስረዳት በመቻሉ ሥነ አመክንዮአዊ የሆነ የፍልስፍና ታሪክ አቀነባብሯል ።

(ፍልስፍናን ይመለከቷል ።)

## ፍሮይድ ፣ ዚግመንድ
*(Freud, Sigmund)*

ከ1856 — 1939 የኖረ ፣ የአእምሮ ሕመምን መንሥኤ ምልክቶችና የሕክምና ሂደት በማጥናት የሳይኮአናሊስስን ንድፈ ሐሳብና ዘዴ የቀመረ ኦስትሪያዊ የሥነ አእምሮ ሊቅ ነው ። ከዕውቅ ሥራዎቹ መካከልም "ጀኔራል ኢንትሮዳክሽን ቱ ሳይኮአናሊስስ" ፣ "ሳይኮፓቶሎጂ ኦቭ ኤቭሪደይ ላይፍ" ፣ "ሲቪሊዜሽን ኤንድ ኢትስ ዲስኮንቴንትስ" የሚባሉት ይገኙባቸዋል ።

ፍሮይድ ባደረገው የሥነ አእምሮ ጥናት ከሱ በፊት የነበሩት ግልብ ቁስአካላውያን የአእምሮአዊ ክንዋኔን ለውጦች ከአካላዊ መንሥኤዎች አንፃር ለመግለጽ ያደረጓቸውን ሙከራዎች ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግ ከቁስአካላዊ አመለካከት የራቀ ኅሊናዊ ንድፈ ሐሳብ ቀምሯል ። በፍሮይድ አስተሳሰብ መሠረት አእምሮአዊ ክንዋኔ ከቁሳዊ ሁኔታዎችና እነሱም ከሚፈጥሯቸው መንሥኤዎች የተለየና ከቁሳዊ ሂደቶች ጐን ለጐን በመሆን የራሱ የሆነ ነፃ ህልውና ያለው ነው ። እንቅስቃሴውም የሚገዛው ከንቁው ባሻገር ባሉ በማይታወቁ ዘለዓለማዊ ልቡናዊ ኃይሎች አማካይነት ነው ተብሎ ይታመናል።

ፍሮይድ በሰው ልጅ መንፈስ ውስጥ ጥረቱ ሁሉ ደስታን መቀዳጀት በሚሻው ንቁ ባልሆነው ከሁሉም በላይ ደግሞ ወሲባዊ በሆነው አእምሮና የእውነታ ሕግ መካከል የከረረ ግጭት አለ ይላል ። ከዚህም በመነሣት ፍሮይድ ማንኛውንም አእምሮአዊ ሁኔታ ፣ የሰዎች ክንዋኔዎችና ታሪካዊ ትርዕይቶች እንዲሁም ማኅበራዊ ክስተቶች ንቁ ያልሆነው ወሲባዊ የሆነው አእምሮ ግፊት ውጤት አድርጐ ይተነትናቸዋል ። በትንታኔውም መሠረት የማይታወቀው ፣ ንቁ ያልሆነው ወሲባዊ አእምሮ የግብረገብ ፣ የሥነጥበብ ፣ የሳይንስ ፣ የሃይማኖት ፣ የመንግሥት ፣ የሕግ ፣ የጦርነቶች ወዘተ... ባጠቃላይ የሰው ልጅ ታሪክ መንሥኤ ነው ብሎ ይናገራል ።

ፍሮይድ ቀደም ሲል በተጠቀሰው "ሲቪሊዜሽን ኤንድ ኢትስ ዲስኩንቴንትስ" በተባለው ጽሑፉ የዘመኑን ሥልጣኔ ጉዞ በሁለት መሠረታዊ የሰዎች ደመነፍሳዊ ሕይወት ተንትኖታል ። ይኸውም በአንድ በኩል ሰው የመውደድና የመተባበር ግፊት ያለው ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የማጥቃትና የማጥፋት ግፊት አለው የሚል ሆኖ ባጠቃላይ የሥልጣኔ ህልውና በመጀመሪያው ግፊት ላይ የተመሠረተ ይሁን እንጂ የሥልጣኔ እርምጃ የሁለቱ ግጭት ውጤት እንደሆነ ያስረዳል ። ከዚህም በመነሣት የግል ንብረት መጥፋት ግላዊና ማኅበራዊ ቅራኔን ስለማያጠፋ ፍቅርና መተባበር ብቻውን ሊኖር አይችልም በማለት ጦርነት ከቶውኑ ሊቀር እንደማይችል ለማሳመን ይሞክራል ። ባጠቃላይ የፍሮይድ የሳይኮአናሊስስ ንድፈ ሐሳብና ዘዴ ነባራዊ ቁስአካላዊ መሠረት የለውም ። ይሁንና በጊዜው ከፍተኛ ተቀባይነት ነበረው ። ለዚህም ዋነኛ ምክንያቱ የፍሮይድ ተከታዮች ወዝአደሩ የግል ንብረትን በማጥፋት ፍቅርና ወንድማማችነት የሰፈነበት የኮሚኒስት ሥርዓት ለመመሥረት የሚያካሂደውን አብዮታዊ ትግል በመቃወም ያለውን አድኃሪ ስሜት ለማቆየት ካላቸው ፍላጐት የተነሣ ማርክሳዊውን ፍልስፍና ከመሠረቱ ያናጋ ስለመሰላቸው ነው ። ሆኖም የፍሮይድ አስተሳሰብ በተለይም በሥነ አእምሮ መስክ የነበረው ተቀባይነት እያደር እያቆለቆለ መጥቷል ። ይሁን እንጂ

ዛሬም ቢሆን የፍሮይድ አስተሳሰብ በካፒ ታሊስቱ ኅብረተሰብ ውስጥ በተለያዩ የባ ህል መስኮች በተለይም በሥነ ጥበብ ሥራ ዎች ንድፈ ሐሳብ አንፃር ከፍተኛ ተቀባይ ነት አለው ።

## ፍንገጣ

*(Deviation)*

በኮሚኒስት ፓርቲ ውስጥ ከማርክሳዊ ሌኒናዊ መሥመር ለምሳሌ ወደ ማኅበራዊ ዲሞ ክራሲ አቅጣጫ ማዘንበል ፍንገጣ ይባላል ። ሆን ተብሎ ይሁን ሳይታሰብ ከአብዮታዊ መሥመር ለመውጣት የሚደረግ ማንኛውም የፍንገጣ አዝማሚያ አብዮታዊውን ትግል የሚያዳክምና ድርጅቱን የሚያናጋ ነው ። ስለዚህም አንድ ኮሚኒስት ፓርቲ አብዮቱንና ህልውናውን ለመጠበቅ በማንኛውም መልኩ የሚከሰትን ፍንገጣ ይዋጋል ።

ፍንገጣ ሁለት መልኮች አሉት ። አንደ ኛው የ"ግራ" ፍንገጣ ሲሆን ይህም በአ ንድ ወቅት የመደብ ኃይል አሰላለፍን በሚገባ ባለማጤን የሚመጣ ነው ። በሠራተኛው መደብና በጭቁን ሕዝቦች ኃይል ላይ እም ነት ስለሌለው ሕዝቡን ለማደራጀትና ትግ ሉን ለመምራት አይችልም ። የ"ግራ" ፍን ገጣ በፖሊሲ ረገድ ጀብደኝነትን ስለሚከ ተል አብዮታዊ ሁኔታው ከሚፈቅደው ውጭ ሠራተኛውን ሕዝብ ለግብታዊ የትጥቅ አመፅ በማነሣሣት በቡርዧዚው የሚያስጨፈ ጭፍና አብዮታዊውን እንቅስቃሴ የሚያ ስመታ ነው ።

ሁለተኛው የፍንገጣ መልክ የቀኝ ፍንገጣ ሲሆን ለካፒታሊስቱ ሥርዓት ጥብ ቅና የሚቆም ፣ የመደብ ትግሉን የሚያቀዘ ቅዝ ፣ ፓርቲውን ለካፒታሊስቶች ሴራ አጋ ልጦ የሚሰጥና ወደ ዝቅጠት የሚያመራ በአጠቃላይም ለካፒታሊዝም ህልውና መቀ ጠል ሁኔታዎችን የሚያመቻች ነው ። ለም ሳሌ በአሜሪካ (ዩ.ኤስ.ኤ.) በ1933 የጀመረው የብሮውደሪስት የቀኝ ፍንገጣ በ1944 በፓር ቲው መፍረክረክ አከትሟል ። በሶቭዬት ኅብረትም ከ1928—33 የቀኝ አፈንጋጮች ፓርቲው ፈጣን የኢንዱስትሪ ግንባታን በማስፋፋት ሶሻሊዝምን ለመገንባትና የሀ ብታም ገበሬዎችን(ኩላክ) መደብ ለማስወገድ ያወጣውን ፖሊሲ በመቃወም ለሀብታም ገበ ሬዎች ጥብቅና ቆመው ነበር ። ነገር ግን በሐቀኛ የፓርቲው አባላት በተደረገ መራራ ትግል የፓርቲው ፖሊሲ ከመቀልበስ ድኗል ።

("ግራ" ክንፍ ኮሚኒዝምን ፣ አድርባይነትን፣ ይመለከቷል ።)

## ፍጆታ

*(Consumption)*

በተመረተ ምርት ወይም በተዘጋጀ አገልግሎት በመጠቀም የተወሰነ ፍላጐትን የማርካት ድርጊት ፍጆታ ይባላል ። ለምሳሌ ዳቦ መብላት ፣ ልብስ መልበስ ፣ ሽቶ መቀባት በኤሌክትሪክ ኃይል መጠቀምና የመሳሰሉት ድርጊቶች ፍጆታ ናቸው ። ፍጆታ በመሠረቱ ሁለት ዓይነት ነው ማለት ይቻላል ። አን ደኛው ዓይነት ምርታዊ ፍጆታ ሲሆን ይህም የማምረቻ መሣሪያዎችን ፣ ጥሬ ዕቃ ዎችን የሥራ ኃይልንና ሌላ የኃይል ምንጭን በመጠቀም የተለያዩ ፍላጐቶችን የሚያረኩ ሌሎች ምርቶችን ለማምረት የሚደረግ ፍጆታ ነው ። ሁለተኛው ዓይነት ደግሞ ኢም ርታዊ ፍጆታ ወይም ቀጥተኛ ፍጆታ ነው ። ይህም የተመረተን ምርት ለፍላጎት ማርኪያ መጠቀም ነው ። ለምሳሌ በስንዴ ዱቄት ተጠቅሞ ዳቦ መጋገር ምርታዊ ፍጆታ ሲሆን ዳቦ መብላት ግን ኢምርታዊ ፍጆታ ነው ። ሁለቱ የፍጆታ ዓይነቶች እንደ ሂደት ቢታዩ በምርታዊ ፍጆታ የሚመረትን ምርት በኢም ርታዊ ፍጆታ ጥቅም ላይ በማዋል ሲከሰት የማያቋርጥ የምርት እንቅስቃሴ አካል ናቸው ።

ፍጆታ በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚከናወ ነው የእርባታ ክንዋኔ ማጠቃለያ ደረጃ እንደ መሆኑ መጠን ከምርት ፣ ከክፍፍልና ከልው ውጥ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው ። በተለይ ምርትና ፍጆታ በየትኛውም ስልተ ምርት ውስጥ ቢሆን የማይነጣጠሉ አካሎች ናቸው ። ምክንያቱም የተመረተ ነገር ከሌለ ለፍጆታ ሊውል የሚችል ነገር የለም ። ፍጆታም ከሌለ ምርት ትርጉም የለሽ ድርጊት ይሆናል ። በመሆኑም ምርት መነሻ ሲሆን ፍጆታ መድ

ረሻ ፡ ልውውጥና ክፍፍል ደግሞ በመካከል ሆነው ሁለቱን የሚያገናኙ ድልድዮች ናቸው። ይሁንና ምርትና ፍጆታ ካለልውውጥና ካለክፍፍል በድልድይነት ሳይገናኙ የሚችሉበትም ሁኔታ እንዳለ መታወቅ አለበት ። ለምሳሌ አንድ ገበሬ ያመረተውን እህል ለራሱ ሲጠቀም ምርትና ፍጆታ በቀጥታ ይገናኛሉ ። ገበሬው ለባለመሬቱ እርቦ የሚሰፍርና ባለመሬቱ እህሉን የሚጠቀምበት ሲሆን ግን ምርቱ ለፍጆታ የዋለው በክፍፍል አገናኝነት ነው ። እንዲሁም ገበሬው ያመረተውን እህል ለጨው ለውጦ በጨዉ ቢጠቀምበት ጨው ለፍጆታ የዋለው በልውውጥ በኩል አልፎ መሆኑ ይታያል ። ከላይ በምሳሌ እንዳየነው በማኅበራዊ አመራረት ፍጆታ ከምርት ፡ ከልውውጥና ከክፍፍል ጋር የተሳሰረ ድርጊት በመሆኑ ትኩረቱ የምርት ግንኙነትን ማጥናት በሆነው በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሳይንስ ውስጥ ፍጆታም ይጠቃለላል ።

በየትኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ ያለው አጠቃላይ የፍጆታ ደረጃ የሚወሰነው በዚያው ኅብረተሰብ ውስጥ የምርት ኃይሎች ባሉበት የዕድገት ደረጃ ሲሆን በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉት የተለያዩ የኅብረተሰቡ አባላት የፍጆታ ደረጃ የሚወሰነው ደግሞ በዚያው ኅብረተሰብ ውስጥ ባለው የምርት ግንኙነት በሚወሰነው የሀብትና የገቢ ድልድል ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ የአንድ ኅብረተሰብ የኢኮኖሚ ዕድገት መጣኔ የሚለካው ከተመረተው ምርት ውስጥ ለቀጥታ ፍጆታ በሚውለውና ለምርታዊ ፍጆታ ወይም ለክምችት በሚውለው መጠን መካከል ባለው ግንኙነት ነው። ለምርታዊ ፍጆታ የሚውለው ክፍል ከፍተኛ ሲሆን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትን ይጠቁማል ። ለምሳሌ የአንድ ሀገር ዓመታዊ የክምችት መጠን ከተመረተው ብሔራዊ ገቢ ውስጥ 25% ብቻ ቢሆን የመጀመሪያው ሀገር ካለበት ደረጃ ወደከፍተኛ ደረጃ ለመሸጋገር የያዘውን የኢኮኖሚ ዕድገት ሂደት የሚያፋጥን ይሆናል ። ከዚህ አንፃር የኋላቀር ሀገሮችን ሁኔታ ስንመለከት እጅግ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ በሚገኙ የምርት ኃይሎች ላይ የተመሠረተ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኢኮኖሚያቸው ከፍጆታ አልፎ ጠቀም ያለ ክምችት ስለማያስገኝላቸው ዕድገታቸውን ለማራመድ ይቸገራሉ ። በዚህም ላይ ኢምፔሪያሊዝም በተለያዩ መልኮች ይበልጡኑ ገቢያቸውን የሚነጥቃቸው በመሆኑ ለማደግ ያላቸውን ዕድል ጨርሶ ያዳክመዋል ።

(ማምረትን ፡ ክፍፍልን ፡ ልውውጥን ይመለከቷል ። )

## ፍጆታ ምድብ (የ—)

*(Consumption Fund)*

የብሔራዊ ገቢ አንድ ክፍል ነው ። የአንድ ሀገር ብሔራዊ ገቢ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የተመረቱትን ጠቅላላ የፍጆታ ዕቃዎችንና እንደዚሁም ብሔራዊ ምርትን ለማሳደግና ለማስፋፋት ተግባር የሚውሉትን የምርት ውጤቶች የሚያጠቃልል ነው ። የፍጆታ ምድብ የኅብረተሰቡን ፍላጐቶች ማለትም የምግብ ፡ የልብስ ፡ የጫማ ፡ የቤት ውስጥ ዕቃዎች ፡ ለባህላዊ ግልጋሎት የሚውሉ ዕቃዎችና አጠቃላይ የኅብረተሰቡን ፍላጐት ለማርካት የሚያስፈልጉ ጉዳዮችን ለማሟላት የሚመደብ የብሔራዊ ገቢ አንድ ክፍል ነው ።

ለፍጆታ የሚውለው ሀብት በቁሳዊ ምርት ለተሰማሩት ሠራተኞች እንደሥራቸው መጠንና ጥራት የሚከፋፈልና ለሕዝባዊ ፍጆታ የሚውል ተብሎ በሁለት ይከፈላል ። ሕዝባዊ ፍጆታ በተለይም በሶሻሊዝም ለማኅበራዊና ለባህላዊ ፍላጐቶች (ለትምህርት ፡ ለሳይንስ ፡ ለጤና ፡ ለኪነ ጥበብ) ለማኅበራዊ አገልግሎቶች (ለጡረታ ፡ ለቤተሰብ መደጐሚያ ወዘተ...) ለመንግሥት አስተዳደርና ለመከላከያ ኃይል የሚውለውን ሁሉ ያጠቃልላል ። በመሆኑም የፍጆታ ምድብ የግልን ፍላጐት ለማርካት የሚመረተውን ምርትና ከጠቅላላው ተረፈ ምርት ውስጥ ለልዩ ልዩ ማኅበራዊ ፡ ባህላዊና ሌሎች ሕዝባዊ ፍላጐቶች የሚውለውን የሚያጠቃልል ነው ።

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ ፍጆታ የሚውለው የብሔራዊ ገቢ ክፍል ውሱን የሆነና አንፃራዊ በሆነ መንገድ እያሽቆለቆለ በመሄድ ላይ የሚገኝ ነው ። በአንፃሩ ለገዥው መደብ አባላት የግል ፍጆታና ለጦር መሣሪያ እሽቅድምድም የሚውለው የብሔራዊ ገቢ ክፍል ፈጣን ዕድገት በማሳየት ላይ ይገኛል ።

በሶሻሊዝም የፍጆታ ምድብ በተለይም የማኅበራዊ ፍጆታ ምድብ ክፍል በዓይነትም ሆነ በመጠን እጅግ እየተስፋፋ በመሄድ የሕዝቡ የኑሮ ሁኔታ ያለማቋረጥ በማደግ ላይ ይገኛል ። ብሔራዊ ምርት በከፍተኛ መጣኔ እያደገ መሄዱን ሲቀጥል ለፍጆታ የሚመደበው የሀብት መጠን እንደዚሁ ይጨምራል ። ከፍተኛ ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት በተጣለበት በኮሚኒስት ሥርዓት ውስጥ የፍጆታ ምድብ በከፍተኛ ደረጃ ዐድጐ የኅብረተሰቡን አባላት ፍላጐት ሙሉ በሙሉ የሚያሟላ ይሆናል ።

(ብሔራዊ ገቢን ይመለከቷል ።)

## ፍጹማዊ ሐሳብ
*(Absolute Idea)*

በሐሳባዊ ፍልስፍና ውስጥ አንድን ወሰን የሌለው ዘለዓለማዊና የራሱ መሠረት የሆነ ፣ ሙሉ በሙሉ እራሱን አሟልቶ የሚገኝ የዓለም መሠረትና ፈጣሪ የሆነ ፣ ከሰዎች አእምሮ ውጭ በነባራዊነት ይኖራል ተብሎ የሚገመተውን ሐሳብ የሚገልጽ ነው ። ይህ የፍጹማዊ ሐሳብ ትርጉም የነባራዊ ሐሳባዊነትን መሠረተ ሐሳብ ቢያጠቃልልም ለፍልስፍናው መነሻ ፍሬ ሐሳብ መግለጫ ያደረገው ግን ሄግል ነው ። ባጠቃላይ በዚህ ሐሳባዊ ፈላስፋ አስተሳሰብ የዕድገት መሠረትና ምንጭ ነባራዊው ዓለም ሳይሆን ፍጹማዊ ሐሳብ በውስጡ በያዛቸው ሁለት ተቃራኒ ኃይሎች መካከል የሚካሄደው ትግል ነው ፤ የተፈጥሮም ሆነ የኅብረተሰብ ዕድገት ታሪክ የፍጹማዊ ሐሳብ ዕድገት ነፀብራቅ ነው ።

ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ከጊዜና ከስፍራ ውጭ የሚገኝ ነገር ሊኖር እንደማይችል ያስረዳል ። ሐሳብ ራሱን የቻለ በራሱ መሠረትነት የሚኖር ሳይሆን የቁስአካል ነፀብራቅ እንደ ሆነ በመግለጽ ማርክሲዝም የሄግልን ፍጹማዊ ሐሳብ ኢሳይንሳዊነት አረጋግጧል ። ማርክሲዝም ከዚህም በተጨማሪ የፍጹማዊና የአንፃራዊ ዕውቀትን ዲያሌክቲክስ በማብሰር ሁሉ አቀፍና ዘለዓለማዊ የሆነ ፣ ዕውቀት ሊኖር እንደማይችል ይገልጻል ።

(ፍፁማዊና አንፃራዊ እውነትን ፣ ነባራዊ ሐሳባዊነትን ፣ ሄግሊያኒዝምን ፣ ሄግልን ይመለከቷል ።)

## ፍጹማዊ ተረፈ እሴት
*(Absolute Surplus Value)*

የካፒታሊስቶች መሠረታዊ ፍላጐት ተረፈ እሴትን በማሳደግ ሀብትና ካፒታል ማድለብ ነው ። ለዚህም በተለያዩ ዘዴዎች ይጠቀማሉ ። ካፒታሊስቶች ብዝበዛቸውን ለማባባስ ከሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች አንዱ የወዝአደሩን የቀን የሥራ ሰዓት ማራዘም ነው ። ለምሳሌ ወዝአደሩ በቀን ስምንት ሰዓት ይሠራል እንበል ፤ ከዚህ ውስጥ 4 ሰዓት አስፈላጊ የሥራ ጊዜ ፣ ቀሪው 4 ሰዓት ደግሞ ትርፍ የሥራ ጊዜ ቢሆንና የሥራው ሰዓት ወደ አሥር ሰዓት ከፍ እንዲል ቢደረግ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ ሳይለወጥ የሠራተኛው ትርፍ የሥራ ጊዜ ወደ 6 ሰዓት ከፍ ይላል። በዚህ አኳኋን 100% የነበረው የተረፈ እሴት መጣኔ በዚህ የሥራ ሰዓት መራዘም ወደ 150% ከፍ ይላል ፤ የብዝበዛውም ደረጃ በዚሁ መጠን ያድጋል ። በዚህ መልክ የሚገኝ ተረፈ እሴት ፍጹማዊ ተረፈ እሴት ይባላል ።

ፍጹማዊ ተረፈ እሴት በቀጥታ በወዝአደሩ የሥራ ሰዓት መራዘም ብቻ ሳይሆን በሥራ ጊዜ ዕረፍት በማሳጣት ፣ ሥራን በማፋጠንና በሌሎች ልዩ ልዩ ድብቅ መንገዶች ሊፈጠር ይችላል ።

በተለይ በመጀመሪያው የካፒታሊዝም የዕድገት ደረጃ ላይ ሠራተኛው ፍጹማዊ ተረፈ እሴትን እንዲፈጥር ማድረግ ካፒታሊስቱ ካፒታሉን የሚያደልብበት ዘዴ ነበር ፤ ነገር ግን የወዝአደሩ መደብ አባላት በቁጥርም በድርጅትም እየተጠናከሩና ንቃተ ኅሊናቸውም እየዳበረ ሲሄድ ካፒታሊስቱ የሥራ ሰዓትን በማራዘም ዘዴ ብዝበዛውን ለማባባስ አዳጋች እየሆነበት መጣ ። ካፒታሊስቱ ብዝበዛውን በማባባስ ተረፈ እሴቱን ለማሳደግ አስፈላጊ የሥራ ጊዜን እንደመቀነስ ባሉ ዘዴዎች ላይ ማተኮር ጀመረ ።

(አንፃራዊ ተረፈ እሴትን ይመለከቷል ።)

## ፍጹማዊነት
*(Absolutism)*

ፍጹማዊነት በማንኛውም መስክ ምንም አዲስ ነገር እንደማይገኝና ሁሉንም ነገር እንደአለቀለት ነገር አድርጎ የሚያቀርብ ወግ አጥባቂ አስተምህሮ ነው ። ለምሳሌ ከታሪክ አንፃር ታሪክ አልቋል ፣ ወደፊት በዚህ በኩል አዲስ ነገር አይኖርም የሚል አቋም አለው ። ከዕውቀት ንድፈ ሐሳብም አኳያ ፍጹማዊነት የአድራጊና የተደራጊን ፍጹም ተመሳሳይነት የሚያራምድ አስተሳሰብ ነው ። የነገሮች የተሟላና የመጨረሻ ዕውቀት ሊገኝ ይችላል በማለት የዕውቀትን አንፃራዊ ገጽታ ይክዳል ።

በእርግጥ ያለቀላቸውና የተሟሉ ፍጹማዊ ዕውቀቶች ተብለው ሊጠቀሱ የሚችሉ ዕውቀቶች ይኖራሉ ። ለምሳሌም በኢትዮጵያ አቆጣጠር የካቲት 25 ቀን 1967 ኢትዮጵያ ውስጥ በአዋጅ የገጠር መሬት የሕዝብ መደረጉ በሁኔታዎች ሊስተካከል የማይችል ፣ የተሟላና ያለቀለት ፍጹማዊ ዕውቀት ነው ። ይሁንና ይህ እውነትን ያዘለ ፍጹማዊ ዕውቀት የሚያመለክተው በጠቅላላ በዓለም ውስጥ የተደረገውን ፣ ወደፊትም የሚሆነውን ፤ ያለውን ሁሉ ሳይሆን አንድ የተወሰነ ገጽታን ብቻ በመሆኑ ከዚህ አጠቃላይነት አኳያ ሲታይ አንፃራዊ ነው ።

በመሠረቱ በመርህ ደረጃ በዓለም ውስጥ ያለውን ማንኛውንም ነገር ለማወቅ ይቻላል ፤ ከእውነታ አኳያ ይህ ችሎታ ፍጻሜ በሌለው ሂደት ይተረጎማል ። ስለዚህም የነገሮችን ዙሪያ ገባ የሆነ ዕውቀት ማግኘት ተግባራዊነት የሌለው ሲሆን የዕውቀት መገኘት በዲያሌክቲክስ ምንጊዜም ከአንፃራዊ ወደ ፍጹማዊ ዕውቀት የሚደረግ የማያቋርጥ ሂደት ነው ።

(አድራጊና ተደራጊን ፣ አንፃራዊና ፍጹማዊ እውነትን ይመለከቷል ።)

## ፍጹማዊ የኑሮ ሁኔታ ቁርቁዝና
*(Absolute Impoverishment)*

ፍጹማዊ የኑሮ ሁኔታ ቁርቁዝና የሚባለው በካፒታሊስት ክምችት ሳቢያ የወዝ አደሩ መደብ የኑሮና የሥራ ሁኔታ እንዲሁም ማኅበራዊ አቋሙ ፍጹማዊ በሆነ መንገድ እያቆለቆለ የሚሄድ መሆኑን የሚያመለክት ነው ።

ፍጹማዊ የኑሮ ሁኔታ ቁርቁዝና እንደ ማንኛውም በካፒታሊዝም ውስጥ እንደሚከናወን ሂደት ባልተመጣጠነ መንገድ የሚከሰት እንጂ በተከታታይ የሚታይ ላይሆን ይችላል ። የወዝአደሩ መደብ የኑሮና የሥራ ሁኔታ ዕለት በዕለት ሲታይ አንዳንዴ ከፍ ፣ አንዳንዴ ዝቅ ቢልም በረጅም ሂደቱ ሲታይ ግን እያሽቆለቆለ የሚሄድበት ሁኔታ ነው ። ካርል ማርክስ የወዝአደሩ መደብ ፍጹማዊ የኑሮ ሁኔታ ቁርቁዝና የመጀመሪያው ሁኔታ በካፒታል ክምችት ሳቢያ የኢንዱስትሪ ተጠባባቂ ሠራዊት መፈጠር ነው ይላል ።

በካፒታሊዝም ውስጥ የፍጹማዊ የኑሮ ሁኔታ ቁርቁዝና ዓይነተኛ መለኪያ በሥራ ኃይል እሴትና በእውን ምንዳ መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ መሄዱ ነው ። የፍጆታ ዕቃዎችን በሚያመርቱ የኢንዱስትሪ መስኮች የሚገኘው የሥራ ምርታማነት ዕድገት የሥራ ኃይል እሴትን የመቀነስ አዝማሚያ ቢኖረውም በሳይንስና በቴክኖሎጂ ዕድገትና በቁሳዊ የኑሮ ሁኔታ ማደግ ምክንያት እያደገ በመጣው ፍላጎት ሳቢያ የሥራ ኃይል እሴት ባጠቃላይ የሚያድግበት ሁኔታ ይፈጠራል ። ለምሳሌ በዳበሩ የካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ የወዝአደሩ መደብ አባላት በሚኖሩባቸው ቤቶች ውስጥ እንደማቀዝቀዣ ፣ እንደ ዘመናዊ ምድጃና ፣ እንደ ቴሌቪዥን የመሳሰሉት መኖራቸው የወቅቱ የኅብረተሰቡ የዕድገት ደረጃ የሚጠይቀው ሆኗል ። በዚህ መሠረት የወዝአደሩ የኑሮ ሁኔታ መለወጥ ከላይ እንደ ተጠቀሰው የሥራ ኃይል እሴት እንዲያድግ ያደርጋል ። ከዚህ አንፃር የወዝአደሩ መደብ የሚያገኘው እውን ምንዳ ዕድገት ከሥራ ኃይል እሴት ዕድገት ጋር እኩል ሊራመድ ስለማይችል በወዝአደሩ መደብ ኑሮ ላይ ፍጹም በሆነ መንገድ የኑሮ ሁኔታ ቁርቁዝናን ያስከትላል ።

ፍጹማዊ የኑሮ ሁኔታ. ቁርቁዝና በካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ እያደገ በመጣ ጠንቀኛ የሥራ ሁኔታ መበርከት ጭምርም ይገለጻል ። በካፒታሊስት ሀገሮች የምርት መገልገያ መሣሪያ ባለቤት የሆነው የቡርዧው መደብ ያለውን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ ከሚጠቀምባቸው ዘዴዎች መካከል አንዱ ወጪውን መቀነስ መሆኑ የታወቀ ነው ። በመሆኑም እንደኢንዱስትሪው ጠባይ አመቺ የሥራ ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችሉ የአደጋ መከላከያ ጥንቃቄዎችን መውሰድ ተጨማሪ ወጪዎችን ስለሚያስከትልባቸው ወዝአደሩን ለጠንቀኛ የሥራ ሁኔታ ማጋለጡን ይመርጣሉ ። በዚህ ሳቢያ ዛሬ በካፒታሊስቱ ዓለም የተወሰኑ የበሽታ ዓይነቶች (ከመታፈን ፣ ከጭንቀት ፣ ዕረፍት ከማጣት የሚመጡ) የወዝአደሩን መደብ አባላት በይበልጥ የሚያጠቁ መሆናቸው ተረጋግጧል ።

የወዝአደሩን መደብ ፍጹማዊ የኑሮ ሁኔታ ቁርቁዝና ከሚያባብሱት ምክንያቶች ውስጥ እንደ ቤት ኪራይ ፣ እንደ ታክስ ፣ እንደ የትምህርትና የጤና ወጪዎች ማደግም ይገኙበታል ።

የካፒታሊስት ክምችት እያደገ በሄደ መጠን የወዝአደሩ መደብ የኑሮና የሥራ ሁኔታ ፍጹማዊና አንፃራዊ በሆነ መንገድ እያቆለቆለ የሚሄድ መሆኑ ወዝአደሩን ለበለጠ ትግል የሚያዘጋጅና በብዝበዛ ላይ የተመሠረተውን ካፒታሊስታዊ የምርት ግንኙነት በሶሻሊዝም ለመተካት የሚያስችል ነባራዊና ኅሊናዊ ሁኔታዎችን የሚፈጥር ነው ። የካፒታሊስት ክምችት ታሪካዊ ዝንባሌም ይኸው መሆኑን በመረዳት ነው ካርል ማርክስ ቀደምት የቡርዧ ምሁራን "ካፒታሊዝም ዘለዓለማዊ ሥርዓት ነው" ሲሉ ያስተጋቡትን መፈክር በመሻር ካፒታሊዝም በሶሻሊዝም መተካቱ የታሪክ ግዴታ መሆኑን ያስተማረው ።

## ፍጹማዊ ኪራይ
*(Absolute Rent)*

በካፒታሊስት ኅብረተሰብ የእርሻ ሠራተኞች ከሚፈጥሩት ተረፈ እሴት ውስጥ መሬትን በሞኖፖል በግል ባለቤትነት ለያዙ ባለመሬቶች የመሬት ኪራይ ይከፈላል ። በለምነቱ እጅግ ዝቅተኛ ለሆነው ማሳና ለሌሎችም ማሳዎች የሚከፈል መደበኛ የሆነ የመሬት ኪራይ ፍጹማዊ ኪራይ ይባላል ።

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ለፍጹማዊ ኪራይ መኖር ምክንያት የመሬት በሞኖፖል ባለቤትነት መያዝ ነው ። ይህ የመሬት በሞኖፖል መያዝ ውድድርን በመግታት ካፒታሊስቶች ካፒታላቸውን ከኢንዱስትሪ ወደ እርሻ እንዲያዛውሩ ያደርጋል ። በዚህም ምክንያት ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር በኢንዱስትሪው ዘርፍ ከፍ ፣ በእርሻው ዘርፍ ዝቅ ያለ ይሆናል ። ይህም ካፒታሊስቱ እንድን የተወሰነ የካፒታል መጠን በኢንዱስትሪ መስክ በሥራ ላይ ከሚያውለው ይልቅ በእርሻ ላይ ቢያውለው የበለጠ ተረፈ እሴት ሊፈጠርለት ይችላል ማለት ነው ። ካፒታል ከኢንዱስትሪ ወደ እርሻ ለመዛወር ቢችል ኖሮ በእርሻው መስክ የሚፈጠረው ተጨማሪ ተረፈ እሴት በኢንዱስትሪና በእርሻ መስኮች መካከል በተከፋፈለ ነበር ። ይህ እንዳይሆን ግን የመሬት በሞኖፖል ባለቤትነት መያዝ ያግደዋል ። ባለመሬቱም ይህን ተጨማሪ ተረፈ እሴት በፍጹማዊ ኪራይ መልክ መሬቱን ከተከራየው ካፒታሊስት ይወስዳል ።

ፍጹማዊ ኪራይ በካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ የእርሻን ምርቶች የዋጋ ውድነት ከሚያስከትሉ ምክንያቶች አንዱ በመሆን የሰፊውን ሕዝብ የኑሮ ደረጃ ያቆረቁዛል ።

በሶሻሊስት ሥርዓት ውስጥ መሬት ከትላልቅ ባለመሬቶች ተነጥቆ በሰፊው አርሶ አደር እጅ ስለሚሆን ፍጹማዊ ኪራይ ይጠፋል ። የፍጹማዊ ኪራይ መጥፋትም ሰፊውን አርሶ አደር የመሬት በሞኖፖል መያዝ ከሚያስነሣው ቅራኔ ያላቅቀዋል ። የእርሻ ምርት ዋጋም ዝቅ እንዲል በማድረግ የሰፊውን ሕዝብ የኑሮ ደረጃ ያሳድጋል ።

(የልዩነት ኪራይን ይመለከቷል ።)

## ፎርዲዝም
*(Fordism)*

በ1914 አሜሪካ ውስጥ ሥራ ላይ የዋለ የሥራ አደረጃጀትና የክፍያ ዘዴ ነው ። ይህ ዘዴ መጠሪያውን ያገኘው ዘዴውን ለመጀ

መሪያ ጊዜ በፋብሪካ ውስጥ ሥራ ላይ ካዋለው ከአሜሪካዊው ዲታ ከሄንሪ ፎርድ ነው ።

በዚህ የሥራ አደረጃጀትና ክፍያ ዘዴ መሠረት በአጓጓዥ ቀበቶ (ኮንቬየር ቤልት) አማካይነት የተወሰነ ዕቃ በተወሰነ ፍጥነት በተወሰኑ ወዝአደሮች ፊት ቀርቦ እንዲከናወን ይደረጋል ። ክፍያውም በዚሁ መሠረት ይከናወናል ። የአጓጓዡን ቀበቶ ፍጥነት እንደተፈለገ መጨመር ስለሚቻል ካፒታሊስቱ በዚህ ዘዴ ተጠቅሞ የሥራ ዕምቀትን በመጨመር ብዝበዛውን ለማሳደግ ይችላል።

ብዝበዛና ምዝበራ በተወገደበት ፣ የምርታማነት ዓላማና ግብ የኅብረተሰቡን መሠረታዊ ፍላጐት መሟላት ቅድሚያ በሰጠበት በሶሻሊስት ሥርዓት ውስጥ ግን ይህ ዘዴ ጎጂ የመበዝበዣ ስልት መሆኑ ቀርቶ ሠርቶ አደሩ ሕዝብ የተትረፈረፈ ምርት ለማምረት የሚጠቀምበት መሣሪያ በመሆን ያገለግላል ።

## ፎኮይዝም
*(Focoism)*

ያለሰፊው ሕዝብ ተሳትፎ በጥቂት ሰዎች ተዋጊነት ብቻ "አብዮት" ለማካሄድ የሚደረግ የትጥቅ ትግል ፎኮይዝም ይባላል ። ፎኮይስቶች ፣ አብዮታዊ ሁኔታ ከተጨባጩ የኢኮኖሚና የፖለቲካ አቋም ጋር ግንኙነት እንደሌለው በመቁጠር ጥቂት ሰዎች የትጥቅ ትግል ከአካሄዱ ሥርነቀል የኅብረተሰብ ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ ብለው ያምናሉ ። ስለዚህም የአንድን ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ በሳይንሳዊ መንገድ ከመተንተናቸው በፊት ለትጥቅ ትግል ይጣደፋሉ ። የትጥቅን ትግል በጥቂት የነሱ "ጀግና ጦረኛ" ብቻ የሚከናወን ስለሚያደርጉት ሕዝቡን ለማደራጀቱና ለማንቃቱ ተግባር ትኩረት አይሰጡትም ። አብዮታዊ ፓርቲ ሊፈጠር የሚችለው ጥቂት ተዋጊዎቻቸው የደፈጣ ውጊያ ካፋፋሙ በኋላ እንጂ ከዚያ በፊት ሊሆን አይችልም በማለት ፎኮይስቶች የፓርቲን ሚና ይዘነጋሉ ። ፎኮይስቶች ከሕዝቡ ይልቅ በጥቂት ተዋጊዎች ላይ ስለሚተማመኑ ዓላማቸው ዘላቂነትና ተፈጻሚነት የለውም ።

(ጀብደኝነትን ፡ ይመለከቷል ።)

## ፊየርባኽ ፡ ሉድቪግ
*(Feuerbach, Ludwig)*

ከ1804 — 1872 የኖረ ፣ በ19ኛው ምዕት ዓመት በጀርመን ፍልስፍና ውስጥ ገኖ የነበረውን ሐሳባዊ አመለካከት በጽኑ በመታገል ለቁስአካልነት ፍልስፍና ዕድገት ታላቅ አስተዋጽኦ ያደረገና በአስተምህሮውም የማርክስንና የኤንግልስን ስሜት የሳበ ኢአማኒ ጀርመናዊ ፈላስፋ ነው ። ፊየርባኽ ከጻፋቸው ዋና ዋና ጽሑፎቹ መካከል ጥቂቶቹ «ሱርክሪቲክ ዴር ሄግሊሽን ፊሎሶፊ ፤» "ዳዝ ቬዝን ዴስ ክሬስትንቱምዝ" የተባሉት ናቸው ።

የፊየርባኽ ፍልስፍና እነሣሥ ሄግል ስለሰው ልጅ ምንነት አስመልክቶ በሰነዘረው ሐሳባዊ ግንዛቤ ላይ በሰጠው ኂስ ላይ የተመሠረተ ነው ። በሃይማኖት ላይ ባካሄደው ትግል የተነሣም አመለካከቱን በጊዜው ከነበረው የወጣት ሄግልያውያን ሐሳብ ወደቁስአካልነት ሊያሸጋግረው ችሏል ። የቁስአካላዊነቱም ዓይነተኛ ጠባይ ሰውን ከፍተኛው የተፈጥሮ ውጤት አድርጐ በመውሰድ የሰውን የተለዩ ባሕርያት በተፈጥሮአዊ ምንጫቸው መግለጹ ነበር ።

ፊየርባህ ለቁስአካላዊ ፍልስፍና ካደረጋቸው አስተዋጽኦዎች አንዱ በሐሳባዊነትና በሃይማኖት መካከል ያለውን ግንኙነት ማጋለጡ ነው ። ፍልስፍና በሐሳብ ደረጃ ባሉ ጉዳዮች ላይ ብቻ ሳይወሰን ተፈጥሮንና ሰውንም ማጥናት እንዳለበት ገልጿል ። በሱ አስተሳሰብ ተፈጥሮ ከሰው ኅሊና ውጭ በነባራዊነት የሚገኝ ቀዳሚ እውነታ ነው ፤ ሰውም የተፈጥሮ አካልና የረጅም ዘመን የዕድገት ውጤቱ ሲሆን ንቃተ ኅሊናም የተፈጥሮ ነፀብራቅ እንጂ ቀዳሚ አይደለም ። በዕውቀት ንድፈ ሐሳብም በኩል ነባራዊ እውነታ ሊታወቅ የሚችልና ሰው በሕዋሳቱ አማካይነት የሚገነዘበው ነገር መሆኑን በመግለጽ ኢታዋቂነትን በጽኑ በመቃወም የዳሳሽነትንና የሕውስታዊነትን አመለካከቶች አራምዷል ። በዚህም ጥረቱ አሳቤ በግንዛቤ ውስጥ ያለውን ሚና ሳይከድ ተደራጊውን ከአድራጊው እንቅስቃሴ ጋር አያይዞ ለመመርመር በመሞከር የሰውን ልጅ ዕው

ቀትና ንቃተ ኅሊና ማኅበራዊ ጠባይ ገልጿል።
ሆኖም ግን ፎየርባኽ የሰውን ምንነትና በዓ
ለም ውስጥ ያለውን ሰፍራ በትክክል ባለመ
ረዳቱ ምንነቱን ከተፈጥሮ አኳያ በማየት
ብቻ ሊወሰን በቅቷል ። ይኸውም ፎየርባኽ
ሰውን እንደ ንጹህ ሥነ ሕይወታዊ ኑባሬ
ማለትም እንደእንስሳ ከመቁጠሩ የተነሣ
የነጠረ ቁስአካላዊ መሥመር ሊከተል አልቻ
ለም ነበር ።

ባጠቃላይ ፎየርባኽ ምንም እንኳን ተፈ
ጥሮን በቅስቃሴና በዕድገት ውስጥ እንደም
ትገኝ አድርጐ ለመረዳት ቢጥርም ፍልስፍ
ናው ከቅድመ ማርክሳዊ ዲበ አካላዊ ቁስ
አካልነት አውጠንጣኝ ባሕርይ ጨርሶ ሊላ
ቀቅ አልቻለም ። የቅራኔዎች አንድነት በስ
ዎች አስተሳሰብ ውስጥ ብቻ እንጂ በነባራ
ዊው ዓለም ውስጥ ሊኖር አይችልም በሚል
እምነት የሄግልን ፍልስፍና ጠንካራ ጐን
ማለትም ዲያሌክቲክሱን ከፍልስፍናው ጋር
አጠቃሎ በማውገዙ በተፈጥሮ ውስጥ ያለ
ውን ቅራኔ ለመረዳት አልቻለም ነበር ።
በመሆኑም በታሪክ ግንዛቤው ሙሉ በሙሉ
በሐሳባዊ አመለካከት ውስጥ በመዘፈቁ የኅብ
ረተሰብን ዕድገት ከዚሁ አኳያ ለመመልከት
ሞክሯል ። በርሱ አስተሳሰብ ዋነኛው የኅብ
ረተሰብ ዕድገት አንቀሳቃሽ ኃይል ግብረ
ገብነትና በሰዎች መካከል ያሉ ግብረገባዊ
ግንኙነቶች ናቸው ። ከዚህም አልፎ እነዚህ
ግንኙነቶች ራሳቸው በኢኮኖሚ ግንኙነቶች
ላይ ማለትም በምርት ግንኙነቶች ላይ የሚ
መሠረቱ መሆናቸውን ለመረዳት ተስኖታል።

# ፐ

## ፓሪስ ኮሚዩን

*(Paris Commune)*

ከመጋቢት 18 እስከ ግንቦት 28 ፣ 1871 በፈረንሳይ በተለይም በፓሪስ ለሰባ ሁለት ቀናት በሥልጣን ላይ የቆየ በሠራተኛው መደብ የትግል ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው የሠራተኛው መንግሥት ነው ። የፓሪስ ኮሚዩንን የፓሪስ ሠራተኞችና የሰፊው ሕዝብ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ያስገኘው የሶሻሊስት አብዮት ጥንስስ ነው ። ኮምዩኑም የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት ጅምር ነው ።

በሐምሌ 1870 በፈረንሳይና በጀርመን መካከል በተቀሰቀሰው ጦርነት ፈረንሳይ ተሸንፋ ሣልሳዊ ናፖሊዮን ተማረከ ። አልሳስና ሎሬን የተባሉት ሁለት የፈረንሳይ ግዛቶችም በጀርመኖች በመያዛቸው ሁለተኛው የፈረንሳይ ግዛተ አፄ ፈረሰ ። በሉዊ ናፖሊዮን መንግሥት ቦታ ለጊዜው የሠራተኛውና የሰፊው ሕዝብ ድጋፍ የነበረውና በአዶልፍ ቲየር የሚመራው የለዘብተኛ ቡርዧ መንግሥት ሥልጣን ያዘ ። የጀርመን ጦር ፓሪስን ለመውረር ዝግጅት በማድረግ ላይ መሆኑን በመመልከት በአብዛኛው ከሠራተኛው የተውጣጡት የፓሪስ ብሔራዊ ጦር አባሎች ከየካቲት 15 ፣ 1871 ጀምሮ ሃያ አምስት አባላት ያሉት አንድ ማዕከላዊ ኮሚቴ በማቋቋም ፓሪስን መቆጣጠር ጀምረው ነበር ። በዚህ ኮሚቴ የሚመራው የፓሪስ ብሔራዊ ጦር የቡርዧው መንግሥት የፓሪስን ሠራተኛና ሕዝብ አመፅ በመፍራት ከተማይቱን ለጀርመኖች አሳልፎ ለመስጠት የሚያደርገውን ሴራ ለማክሸፍ ሲጠባበቅ የካቲት 26 1871 የቲየር መንግሥት እንደተፈራው ፓሪስን ለጀርመን ጦር አሳልፎ ለመስጠት ከቢስማርክ ጋር ውል አደረገ ። ይህንን በመቃወም በመላ ፓሪስ ከፍተኛ አመፅ ተነሣ ። የቲየር መንግሥት በዚህ በመደናገጥ ብሔራዊ ጦሩን ለማንበርከክና የሠራተውን አመፅ ጨርሶ ለመደምሰስ መጋቢት 18 ፣ 1871 ጦሩን በሕዝቡ ላይ ባዘመተበት ወቅት በተደረገው ጦርነት መላው የፓሪስ ሕዝብ ለብሔራዊ ጦሩ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሙሉ ድጋፍ በመስጠቱና ከጐኑም ቆሞ በመዋጋቱ ሙከራውን አከሸፈ ። የዚህ ሕዝባዊ አመፅ ውጤትም የቲየር መንግሥት ጦር ድል መመታት ፣ የቡርዧው መንግሥት ሸሽቶ ቨርሳይ መግባትና በምትኩ የፓሪስ ኮሚዩን ህልውና ማግኘት ነበር ።

የብሔራዊ ጦር ማዕከላዊ ኮሚቴ ጊዜያዊ መንግሥት በመሆን ከአድኃርያን የሚሰነዘሩትን ጥቃቶችም በመቋቋም በአጭር ጊዜ ውስጥ ሥልጣን ለሕዝብ ለማስረከብ ቅድመ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ጀመረ ። በዚህም መሠረት መጋቢት 26 ቀን በተደረገው ጠቅላላ ምርጫ አብዮታዊ ኃይሎች የበላይነት በማግኘት አሸነፉ ። ዘጠና ሁለት አባላት ያሉት የፓሪስ ኮሚዩን ተቋቁሞ የአዲሱ አስተዳደር አሥራ ዘጠኝ አባላትን በያዘ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይመራ ጀመር ። በፓሪስ ጠቅላላ ምርጫ ምንም እንኳ የቡርዧ ወኪሎችና እንደ ብላንኪስቶች ፣ የጃኮቢን ተከታዮችና ፕሮዱኒስቶች የመሳሰሉ የንዑስ ከበርቴው የቀኝና “የግራ” አፈንጋጮች በኮሚዩኑ ውስጥ መግባታቸው ባይቀርም ፣ አመራሩ አብዮታዊ ኃይሎች የበላይነትን የያዙበት ስለነበር በጣም አጭር በሆነ ጊዜ ውስጥ አያሌ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እርምጃዎችን ሊወስዱ ችለዋል ።

የፓሪስ ኮሚዩን በሠራተኛው መደብ መሪነት ፣ በሠራተኛውና በከተማው ንዑስ ከበርቴ አብዮታዊ ኅብረት ላይ የተመሠረተ ሕዝባዊ ሥልጣን ነበር ። በውስጡም የተለያዩ ኃይሎች በመሰግሰጋቸው ብዙም ሳይቆይ በሚወሰዱት እርምጃዎች ላይ ልዩነቶች እየጐሉ ሄዱ ። ባንድ በኩል በቁጥራቸው በዛ የሚሉት ብላንኪስቶችና የጃኮቢን ተከታዮች ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የፕሮዱን ተከታዮች ሆነው ሥልጣንን በተግባር በመተርጐም ረገድ ባለው ገደብና ማዕከላዊነት እንዲሁም ከፀረ አብዮተኞች ጋር በሚደረገው ትግል በሁለት ወገኖች መካከል ጠቡ እየከረረ ሄደ ። የኮሚዩኑ አባላት

የነበሩት ቡርዧ ሪፐብሊካኖች የሠራተኛውንና የሕዝቡን ሁኔታ ስለፈሩ ከኮሚዩኑ በመውጣት ቨርሳይ ከነበረውና ፓሪስን ከከበበው የጠላት ጦር ጋር ተደባለቁ ። የአድኀሮት ኃይል ተጠናክሮ ፓሪስን መክበብ ሲጀምር የኮሚዩኑ መውደቅ የማይቀር መሆኑን ሲገነዘቡ ወላዋይ ንዑስ ከበርቴዎች በብዛት ከኮሚዩኑ ወጡ ። የፓሪስ ሠራተኞችና ሰፊው ሕዝብ ግን በቆራጥ አብዮታውያን መሪነት እስከመጨረሻው ለኮሚዩኑ ህልውና ተዋድቀዋል ። በዚህም ጦርነት ከ30,000 እስከ 40,000 የሚደርሱ ኮምዩናርዶችና( የፓሪስ ኮሚዩን ጀግኖች) ደጋፊዎቻቸው እንደ ቅጠል ረግፈዋል ። በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሌሎች ደግሞ በግፍ ታሰረዋል ፤ ከሀገርም ተሰደዋል ። በዚህም የፓሪስ ኮሚዩን በአድኃርያን በትር ከፋኛ ተመትቶ በተመሠረተ በ72ኛው ቀን ህልውናው አከተመ ።

ለፓሪስ ኮሚዩን መውደቅ መሠረታዊው ምክንያት በአጠቃላይ ለሶሻሊስት አብዮት የነባራዊና የኀሊናዊ ሁኔታዎች በስለውና ተሟልተው አለመገኘት ሲሆን ይህም በተለያየ መልክ ተንፀባርቋል ። በሳይንሳዊ ርዕዮተዓለም የሚመራ ጠንካራ ፓርቲ ባለመኖሩ በፓሪስ ኮሚዩናርዶች ዘንድ አንድ ዓይነት አመለካከትና የፖለቲካ ግብ አልነበረም ። ስለዚህ ለቡርዧ ሪፐብሊክና ለሶሻሊዝም በሚደረጉ ትግሎች መካከል ያሉትን ልዩነቶች ማጤን ባለመቻላቸው ከባድ ስህተት ላይ ወድቀዋል ። ከሥልጣን የወረደውን የአድኃሪ መንግሥት ጦር እስከ መጨረሻው ተከታትለው አልደመሰሱም ። ከፓሪስ ውጭም ከገበሬው ጋር ግንኙነት አልፈጠሩም ። ባንኮችን ባለመውረሳቸው የቡርዧዚውን የገንዘብ ምንጭ ሊያደርቁ አልቻሉም ።

በአንፃሩ ደግሞ ኮሚዩኑ ድንቅ እርምጃዎችን ወሰዷል ። በፓለቲካው ረገድ የአሮጌውን መንግሥታዊ አውታር በማፈራረስ የሠራተኛውን የበላይ ገዥነት መሥርቷል ። የቡርዧውን ቋሚ ጦር አፍርሶ በሕዝባዊ ጦር ተክቷል ። የመንግሥት ባለሥልጣኖች በሕዝብ እንዲመረጡ በማድረግ በወዝአደራዊ ሕግ አውጪና የጋራ አመራር መርህ መሠረት ኮሚዩኑ ሕግ አውጪና አስፈጻሚ ሆኗል ። በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ ረገድም የምርት መገልገያዎች ለኀብረተሰቡ የጋራ ጥቅምና ዕድገት እንዲውሉ ጥረት አድርጓል ። የሕዝቡን ኑሮ ለማስተካከልና በሥራ አጥንትና በደመወዘተኝነት መካከል የነበረውን ከፍተኛ ልዩነት ለማስወገድ እርምጃዎችን ወስዷል። ጦርነቱ በፈጠረው ችግር ምክንያት ቀደም ሲል ያልተከፈሉትን የብድርና የኪራይ ዕዳዎች ሰርዟል ። ያለአግባብ የተወሰዱ ንብረቶችም እንዲመለሱ አድርጓል ። የትምህርት ተቋሞችን ከሃይማኖት ተፅዕኖ ለማላቀቅ መንግሥትንና ቤተክህነትን ለይቷል ። የዘር ፣ የቋንቋና የቀለም ልዩነትን የሚያስወግድ ሕግ አውጥቷል። ነፃ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም አውጆአል ። የተለያዩ ክበቦች ፣ የሙያ ማኅበራትና የኢንተርናሽናሉ ማኅበር ቅርንጫፍ በከፍተኛ ደረጃ እንዲደራጁና እንዲጠናከሩ ጥረት አድርጓል ።

ፓሪስ ኮምዩን በአጭሩ ቢቀጭም ለዓለም አቀፉ የሠራተኛና የኮሚኒስት እንቅስቃሴ ሰፊ ልምድና ትምህርት ሰጥቷል ። ሠራተኛው መደብ ሥልጣን በመያዝ ብቻ ሳይሆን የተቀሩትንም የተጨቆኑ ወገኖች ሁሉ ነፃ የማውጣት ታሪካዊ ኃላፊነት የተጣለበት ፣ ሶሻሊዝምን ከዚያም ኮሚኒዝምን መገንባት የሚችል አብዮታዊ መደብ እርሱ ብቻ መሆኑን አረጋግጧል ። ለአድኃርያን ጊዜና ፋታ ሳይሰጥ እስከመጨረሻው ተከታትሎ መደምሰስና ዲሞክራሲያዊ አብዮትንና ሶሻሊስት አብዮትን በቅጡ መለየት ፣ ጊዜያዊና ዘላቂ ወዳጅን በሚገባ ማጤን የወዝአደሩን የበላይ ገዥነት ለማረጋገጥ እጅግ የሚያስፈልግ መሆኑና ለዚህ ሁሉ አብዮታዊ ተግባር መቃናት በማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተዓለም የሚመራ የአብዮታዊ ፓርቲ አስፈላጊነት አማራጭ የሌለው መሆኑን ከፓሪስ ኮሚዩን አነሣሥ ፣ ከወሰዳቸው እርምጃዎችና ከውድቀቱ ከተገኙ ልምዶች ዋነኞቹ ናቸው ።

## ፓርቲ

*(Party)*

የመደብ ዓላማቸውን በፖለቲካ ፣ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ መስክ በፕሮግራም ያስተሳሰሩና ለእንቅስቃሴያቸው ርዕዮተዓለማዊ መሠረት በመስጠት ለበላይነት የሚታገሉ የአንድ መደብ ግንባር ቀደም አባላትን ያቀፈ የፖለቲካ ድርጅት ፓርቲ ይባላል ።

የፖለቲካ ድርጅት ወይም ፓርቲ የተከሰተው በቡርዧው ሥርዓት ውስጥ ነው ። በካፒታሊስት ሀገሮች ሁለቱን መሠረታዊ መደቦች ማለትም ቡርዧዚውንና ወዝአደሩን የሚወክሉ ፓርቲዎች አሉ ። የሁለቱ መደቦች ለየብቻ መደራጀትና መታገል ለጥቅማቸው ተፃራሪነት ጉልህ ማስረጃ ነው ። የቡርዧው መደብ በፓርቲው ተደራጅቶ የፊውዳሉን ሥርዓት ለመገርሰስ ባደረገው ትግል "ነፃነት ፣ እኩልነት ፣ ወንድማማችነት" በሚለው መፈክር ሥር ለጊዜውም ቢሆን ሠርቶ አደሩን ሕዝብ (ሠራተኛውን ፣ ገበሬውን ፣ ተራማጅ ንዑስ ከበርቴውን ወዘተ...) በዙሪያው ለማሰለፍና ፊውዳሊዝምን ለመዋጋት በመቻሉ ለተወሰነ ወቅት ተራማጅ ሚና ተጫውቷል ። በሠርቶ አደሩም ሕዝብ ትብብርና ድጋፍ ፊውዳሊዝምን ጥሎ የራሱን የበላይ ገዥነት ከመሠረተና እርሱም በተራው የመጨቆኛ ሥርዓትን ካጠናከረ በኋላ ግን የነዚህን መደቦችና የሌሎችንም ጭቁን የኅብረተሰብ ክፍሎች ዲሞክራሲያዊ ጥያቄዎች ለመመለስ አልቻለም ። እንዲያውም ስመ ብታቸው መከበር የሚያደርጉትን ተራማጅ እንቅስቃሴ ሁሉ ጨርሶ ለመደምሰስ ፊት ለፊት ይዋጋቸው ጀመር ። በዚህም በተለይ የሠራተኛው መደብ በትግል ካገኘው ልምድ እውነተኛ ነፃነቱና ሙሉ መብቱ ሊረጋገጥ የሚችለው በራሱ የፖለቲካ ድርጅት ተደራጅቶ ለመታገል ሲችል ብቻ እንደሆነ ለመገንዘብ ችሏል ።

በ1847 በአንጋፋዎቹ የወዝአደር ምሁራንና መሪዎች ፣ በካርል ማርክስና በፍሬደሪክ ኤንግልስ ግንባር ቀደም መሪነት በለንደን የተቋቋመው ኮሚኒስት ሊግ የመጀመሪያው የወዝአደር ፓርቲ ጥንስስ ነው ። ይህም ዓለም አቀፋዊ ድርጅት የኮሚኒስት ማኒፌስቶ የተሰኘውን ሳይንሳዊ ፕሮግራምና በዚሁ ላይ በመመርኮዝ የተዘጋጀውን መተዳደሪያ ደንብ በማውጣት ለካፒታሊዝም መደምሰስና ለኮሚኒዝም በዓለም መስፈን መታገል የጀመረ አብዮታዊ ድርጅት ነው ። በኋላም የተፈጠሩት አንደኛው ኢንተርናሽናልና ሁለተኛው ኢንተርናሽናል የርሱን ፈለግ በመከተል ታግለዋል ። ይሁን እንጂ በሁለተኛው ኢንተርናሽናል ውስጥ በቡርዧዚው በጥቅም የተገዙ ፓርቲዎች ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን በዓለም አቀፉ የሠራተኛና የኮሚኒስት ንቅናቄ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል ።

የሠራተኛው መደብ አብዮታዊ ትግል ጥራትና ጥንካሬ እያገኘ በመሄዱ ምክንያት አዲሱ ዓይነት ፓርቲ ህልውና አገኘ ። ይህም ሠራተኛውን የቡርዧዚው መሣሪያ ለማድረግ ከተነሡት አድርባይና ከላሽ የቀድሞ ፓርቲዎች ጋር ባደረገው ከፍተኛ የርዕዮተዓለም ትግል በነሌኒን የተመሠረተውና ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ተግባራዊ መመሪያው ያደረገ ፓርቲ ነው ። ሌኒናዊው አዲሱ ዓይነት ፓርቲ መጀመሪያ በቦልሼቪክ ፓርቲ መልክ ቢከሰትም ኋላ በተለያዩ ሀገሮች የተለያየ ቅርፅ እየያዘ መጥቷል። ሆኖም ሁሉም ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መመሪያቸው በማድረግ በርግጥ ለሶሻሊዝም ከዚያም ለኮሚኒዝም ዓላማ ለመታገል ቆርጠው የተነሡ በመሆናቸው በዓላማና በይዘት አንድ ናቸው ።

አዲሱን ዓይነት ፓርቲ ከቡርዧውና ከአድርባይ ፓርቲዎች ልዩ የሚያደርገው ለሠራተኛው መደብና ለመላው ሠርቶ አደር ሕዝብ ጥቅምና ዓላማ የቆመ መሆኑ ፣ አባላቱም የሳይንሳዊ ርዕዮተዓለም ትጥቅ ያላቸው የሠራተኛው መደብ ግንባር ቀደም ተዋጊዎች መሆናቸው ነው ። የዚህ ፓርቲ መሠረታዊ ዓላማ ሠራተኛው መደብ ታሪካዊ ተልዕኮውን በሚገባ እንዲወጣ ማስቻል ሲሆን ይኸውም በአጋር ኃይሎች ትብብርና ድጋፍ በዝባዡን ሥርዓት በመገርሰስና በወዝአደሩ የበላይ ገዥነት መሣሪያነትም ሰው በሰው የማይበዘበዝበትን ሶሻሊስት ብሎም ኮሚኒስት ሥርዓት መገንባት ነው ።

(የፓርቲ ጉባኤን ፣ ማዕከላዊ ኮሚቴን ፣ ፖለቲካ ቢሮን ፣ አንደኛው ኢንተርናሽናልን ፣ ሁለተኛው ኢንተርናሽናልን ይመለከቷል ።)

## ፓርቲ መሠረታዊ ድርጅት (የ—)

*(Party Primary Organization)*

በኢንዱስትሪ ፣ በፋብሪካ ፣ በመንግሥት እርሻ ፣ በኅብረት ሥራ ማኅበራት ፣ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሕዝባዊ ድርጅቶች ፣ በትምህርት ቤቶች ወዘተ... የሚቋቋም የፓርቲ መሠረታዊ አካል ነው ። የፓርቲው አባላት በርዕዮተዓለምና በድርጅት የሚተሳሰሩበትና በኮሚኒስት ሥነ ምግባር የሚታነጹበት የመጀመሪያ አካል ነው ። የሌኒናዊ ፓርቲ ዋና የአባልነት መርህ ከሆኑት አንዱ የአባላት ከፓርቲው ድርጅታዊ አካላት በአንዱ መሳተፍ ሲሆን

ይህ መርህ በተጨባጭ የሚተረጐመውና አባላት ለፓርቲው ዓላማ መቆማቸውን የሚያረጋግጡበት መድረክ መሠረታዊ ድርጅት ነው ።

መሠረታዊ ድርጅት ፓርቲውን ከሕዝብ ጋር የሚያገናኝ ነው ። ፓርቲው በፕሮግራሙ ውስጥ የሚያስፍራቸውን ዓላማዎች ፣ የሚያወጣቸውን መመሪያዎችና የሚያሳልፋቸውን ውሳኔዎች ለሕዝብ የሚያስረዳበትና ሕዝቡም አብሮ ተሰልፎ ከግቡ እንዲደርስ ሳቸው የሚያደርገው በመሠረታዊ ድርጅቱ አማካይነት ነው ። በዚህም ምክንያት መሠረታዊ ድርጅት የሕዝቡን ፍላጎት ፣ ስለፓርቲው ያለውን ሐሳብና በአጠቃላይም በግንባታው ሂደት ውስጥ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በመከታተልና የሕዝቡን ችግሮች በመፍታት ረገድ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ነው ። መሠረታዊ ድርጅት በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ግንባታ ኮሚኒስቶች በግንባር ቀደምትነት ንቁ ተሳትፎ የሚያደረጉበት ፣ በፖለቲካና በርዕዮተዓለም ነጥረው የሚወጡበትና ለፓርቲው ዓላማና ፖሊሲ በትክክል በተግባር መተርጐም የተቀናጀ አመራር የሚሰጡበት መድረክ ነው ። መሠረታዊ ድርጅት የሕዝቡ የሥራና የኑሮ ሁኔታ እንዲሻሻል ፣ ንቃተ ኅሊናው እንዲዳብርና ለሥራ ያለው አክብሮትና ፍቅር እየጨመረ እንዲሄድ ለማድረግ ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋል ።

የፓርቲ መሠረታዊ ድርጅት ለፓርቲው አባልነትና ለሚፈለገውም አዳዲስ ትግል በጥራትና በብቃት ማን እንደሚመጥን በቅርብ ስለሚያውቅ ፓርቲው አዳዲስ አባላትን የሚመለምለውና ታጋዮችን አሰተምሮና አንቅቶ ለፓርቲው ተግባር የሚያሰልፈው በመሠረታዊ ድርጅት በኩል ነው ። ለፓርቲው ጉባኤ ተወካዮች የሚመረጡትና መሪ አካላትም ተጨምቀው ከውስጡ የሚወጡት ከታች ጀምሮ በየደረጃው በሚከናወነው ምርጫ ስለሆነ በዲሞክራሲያዊነት መርህ መሠረት ኮሚኒስቶች መሪ አካላትን ለማቋቋም በሚያደርጉትም ምርጫ መሠረታዊ ድርጅት ከፍተኛ ድርሻ አለው ።

መሠረታዊ ድርጅት ኮሚኒስቶች በጋራ የፓርቲውን መሥመር ለማብራራትና ለማራመድ የሚችሉበት ፣ እያንዳንዱ አባል በፓርቲው ፕሮግራም ፣ ውሳኔዎች ፣ መመሪያዎችና ዕቅዶች ላይ ተወያይቶ አስተያየቱን የሚሰጥበት ፣ በተግባር ለመግለጽ አቋም የሚወስድበት ፣ በሂስና በግለሂስ የሚታረምበትና የሚጠናከርበት መድረክ ነው ። የዚህ ዓይነቱ ከፓርቲው ፕሮግራምና ደንብ ክልል ሳይወጣ የሚደረግ ዲሞክራሲያዊ ውይይት ደግሞ የፓርቲው መሥመር ከኅብረተሰቡ ዕድገትና ፍላጐት ጋር የተገናዘበ መሆኑን ለማረጋገጥ ዋስትና ነው ።

## ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ (የ—)

*(Party Central Committee)*

የፓርቲ ጉባኤ የሚመርጠው አካል ከጉባኤው ቀጥሎ የሚገኝ ፣ በጉባኤዎች መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ የፓርቲውን ሥራ የሚያካሂድ ከፍተኛው የአመራር አካል ነው ። ማዕከላዊ ኮሚቴ ኃላፊነቱና ተጠሪነቱ ለፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ነው ።

ማዕከላዊ ኮሚቴው በፓርቲው ደንብ ውስጥ የተመለከቱትንና በጉባኤው የሚሰጡትን ተግባራት ያስፈጽማል ። እነዚህንም ተግባራት የሚያስፈጽመው በሚመርጣቸው ሁለት ከፍተኛ የአመራር አካላት ማለትም በፖለቲካ ቢሮውና በሴክሬታሪያቱ አማካይነት ነው ። ኮሚቴው እንደፓርቲው ዕድገትና የሥራ ሁኔታ የርዕዮተዓለም ፣ የድርጅት ፣ የውጭ ግንኙነት ወዘተ... ክፍሎችን የያዘ ነው ። በነዚህም አማካይነት በጉባኤው የተላለፉትን ውሳኔዎችና መመሪያዎች ማስፈጸም ዋነኛ ተግባሮቹ ናቸው ።

ማዕከላዊ ኮሚቴው የፓርቲውን አንድነት የማጠናከር ከፍተኛ ኃላፊነት አለበት ። ለዚህ ድርጅታዊ አንድነት መሠረቱ የማዕከላዊ ኮሚቴው አባላት የዓላማ አንድነት ፣ የተግባራዊ እንቅስቃሴ ቅንጅትና የአመራሩ አስኳል ጥራትና ብቃት ነው ። ስለዚህ በማዕከላዊ ኮሚቴው ውስጥ እንዲያገለግሉ የሚመረጡት ግለሰቦች በርዕዮተዓለም ብስለታቸው የላቁና በትግል ልምድ የደረጁ ብቻ ሳይሆኑ በሚመደቡበት የሥራ ዘርፍም በቂ የሙያ ችሎታ ያላቸው ቆራጥ ታጋዮች መሆን ይገባቸዋል ።

(ፓርቲን ፣ የፓርቲ ፖለቲካ ቢሮን ይመለከቷል ።)

## ፓርቲ ደንብ (የ—)
*(Party Statute)*

ለአንድ የተወሰነ ዓላማ የሚቋቋም ፓርቲ ለአባልነት የሚያበቁትን መመዘኛ ነጥቦች ፣ የአባላትን መብትና ግዴታ ፣የፓርቲውን ድርጅታዊ መዋቅርና ውስጣዊ አመራር ፣ በፓርቲው የውስጥ ሕይወት ሊኖር የሚገባውን የአባላት ዲሲፕሊን እንዲሁም አባላት ፓርቲውን የሚረዱበትን ሁኔታ የሚገልጽ መሠረታዊ የፓርቲ ሰነድ ነው ።

የፓርቲ ደንብ የፓርቲው ፕሮግራም በአባላቱ የነቃ ተሳትፎ በተግባር የሚገለጽበት መመሪያ ነው ። በፓርቲ ፕሮግራም ውስጥ የተተለሙት ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ዓላማዎች በተግባር ሊተረጐሙ የሚችሉት አባላት በደንቡ ውስጥ በተጠቀሱት ድርጅታዊ መርሆች መሠረት በሚያደርጉት ግንባር ቀደም እንቅስቃሴና ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ በሚሰጡት የተቀናጀ ጠንካራ ድርጅታዊ አመራር ነው ። የፓርቲው ድርጅታዊ አንድነትም የሚረጋገጠው በዚሁ በፓርቲው ተግባራዊ አንድነት ነው ።

የፓርቲው ደንብ አባላት በማንኛውም ጊዜና ቦታ በድርጅታዊ አሠራራቸው የዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን መርህ በጥብቅ እንዲያከብሩና በሥራ እንዲተረጉሙ ይጠይቃል ። የደንቡ አለመኖር ወይም መጣስ በፓርቲው ውስጥ ውዥንብር የሚፈጥርና የፓርቲውን ማዕከላዊ አመራር ፣ ድርጅታዊ አንድነትና ዲሲፕሊን የሚያናጋ ይሆናል።

የፓርቲው ደንብ እንዲሻሻል ሁኔታዎች ካስገደዱ ሊሻሻል የሚችለው በፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ነው ። በፓርቲው ደንብ ላይ የሚደረጉት ማሻሻያዎችና ተጨማሪ ሐሶቦች በፓርቲው ድርጅታዊ ቅርፅና አሠራር ላይ ተፅዕኖ ቢኖራቸውም መሠረታዊ ድርጅታዊ መርሆችን የሚያጠናክሩና የሚያዳብሩ እንጂ የሚፃረሩና የሚለዋወጡ አይደሉም ።

(ዲሲፕሊንን ፣ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን ይመለከቷል ።)

## ፓርቲ ጉባኤ (የ—)
*(Congress)*

እንደአስፈላጊነቱ የሚሰበሰብና አጠቃላይ መመሪያዎችን የሚያወጣ ከፍተኛው የፓርቲ አካል ጉባኤ ይባላል ። የፓርቲ ጉባኤ በተለያየ ደረጃ ከሚገኙ የፓርቲው ድርጅታዊ አካላት የተውጣጡ የፓርቲ አባሎች የሚሳተፉበት በመሆኑ ቁጥራቸው በርከት ያለ ተወካዮችን የሚይዝ ነው ። በዚህም ምክንያት የሚሰበሰበው ረዘም ባለ ወቅት ሲሆን በጉባኤው ላይ እንዲሳተፉ የሚላኩት ተወካዮች እንደየሁኔታው ከመሠረታዊ ድርጅቶች ጀምሮ በየደረጃው እየተመረጡና እየተጠቃለሉ የሚመጡ ናቸው ። በጉባኤው ላይ የሚገኙ ተወካዮች የጉባኤውን አጀንዳ ያጸድቃሉ ፤ አጠቃላይ ሪፖርት ያዳምጣሉ ፤ ውሳኔዎች ያስተላልፋሉ ፤ የፓርቲውን ደንብ ያሻሽላሉ ፤ የአመራር አካላት አባላትንም ይመርጣሉ ።

በፓርቲ ጉባኤ ላይ የስትራቴጂና የታክቲክ ጥያቄዎች ተመርምረው ይወሰናሉ ። ድርጅታዊና ርዕዮተዓለማዊ ተግባሮች ይቀየሳሉ ። የግንባታ ዕቅድ ይጸድቃል ። የጉባኤውን ውሳኔና መመሪያ በተግባር እንዲተረጐም የሚያደርጉት ማዕከላዊ ኮሚቴው ፣ ፖለቲካ ቢሮውና የፓርቲው ሴክሬታሪያት ይሆናሉ ። እነዚህ የአመራር አካላት በሚሰጡአቸው መመሪያዎች ፣ በሚቀይሷቸው ዕቅዶችና በሚያወጧቸው ፕሮግራሞች በየደረጃው ያሉት የፓርቲው አባላትና ፓርቲው የመንግሥት ሥልጣን በያዘበት ሰፍራ የመንግሥት አካሎችና ሕዝባዊ ድርጅቶች የጉባኤውን ውሳኔዎች ተግባራዊ ያደርጋሉ ።

(ፓርቲን ፣ የፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴን ይመለከቷል።)

## ፓርቲ ፍልስፍና (የ—)
*(Party Philosophy)*

የፓርቲ ፍልስፍና የመደብ ፍልስፍና ሌላው አባባል ወይም አጠራር ነው ። ፓርቲ መደብን የሚወክል ፣ ለአንድ መደብ የቆመ የመደቡ የፖለቲካ ድርጅት እንደመሆኑ ከቆመለት መደብ የተለየ ፍልስፍና ሊኖረው አይችልም ።

(መደባዊ ፍልስፍናን ፣ ወገናዊነትን ይመለከቷል ።)

## ፓርቲ ፕሮግራም (የ—)

*(Party Programme)*

አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በሚመራበት ርዕዮተ ዓለም መሠረት ለአጭርና ለረጅም ጊዜ ዕቅዱ ግብ መምታት የሚነድፈውና የሚያወጣው የትግልና የተግባር መመሪያ ፕሮግራም ይባላል። ለአንድ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ ድርጅታዊ ደንብና ፕሮግራም ዋነኞቹ ሰነዶች ናቸው ።

ፕሮግራም አንድ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ በሚያራምደው ርዕዮተዓለም ላይ ተመሥርቶ የሚነደፍ እንደመሆኑ የኅብረተሰብን ዕድገት ሕግጋት የሚያሳይ ፤ ሶሻሊዝም የማይቀር ሂደት መሆኑን ፤ የሥርዓቱን ጠቀሜታ ባሕርይና የኃይሎቹን ምንነት የሚያስረዳ ነው ።

በአጠቃላይ አንድ የማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ ፕሮግራም ድርጅቱ ለአዲሱ ኅብረተሰብ የሚቀይሰውን የረዥም ጊዜ ትልምና የትግሉንም ስትራቴጂ በመንደፍ ፤ ዲሞክራሲያዊ ሶሻሊስት የትግል ፈርጆች በተቀናጀ ዕቅድ የሚከናወኑበትን ሁኔታ የሚያመለክት መሠረታዊ ሰነድ ነው ።

አንድን ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ ፕሮግራም የሚያሻሽለውም ሆነ የሚያጸድቀው የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ነው ። ለአንድ ፓርቲ ዋነኛ መመሪያው አንድ ወጥ ፕሮግራም ብቻ ስለሆነ ፕሮግራሙ ለፓርቲው የዓላማና የተግባር አንድነትም መሠረት ነው ።

(ፓርቲን ፤ ለትራቴጂና ታክቲክን፤ የፓርቲ ደንብን ይመለከቷል።)

## ፓን አፍሪካኒዝም

*(Pan–Africanism)*

በ19ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ላይ የተከሰተ ፤ የአፍሪካዊነትን ስሜትና ክብር ለማስጠበቅ ፤ በአፍሪካ ዜግነት ላይ ተመሥርቶ ለአህጉሩ ተወላጆች ነፃነትና መብት ለመሟገት የቆመ አመለካከት ነው ። ይኸው አስተሳሰብ በአሜሪካና በካሪቢያን ሀገሮች በነበሩ ጥቂት ግለሰቦች ከተወጠነ በኋላ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ውስጥ የነበሩ የአፍሪካ ዝርያ ያላቸው ጥቁር ምሁራንን ድጋፍ እያገኘ የንቅናቄነት ባሕርይ ሊይዝ ችሏል። የፓን አፍሪካኒዝም አስተሳሰብ በ19ኛው ምዕት ዓመት መጨረሻ ላይ አፍሪካ ውስጥ ሥር መስደድ ጀምሮ በተለይም በሃያኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ላይ ጥቁር ሕዝቦች ለአርነታቸውና ለአህጉራዊ አንድነታቸው ያካሄዱት የነበረው ትግል ማንቀሳቀሻና ማስተባበሪያ ዓርማ ለመሆን በቅቷል ።

ቀደም ሲል በዩናይትድ ስቴትስና በዌስት ኢንዲስ የነበሩ ጥቁር ምሁራን ለአፍሪካ አንድነት ያደርጉት የነበረውን ትግል ፈለግ በመከተል የፓን አፍሪካኒዝምን አስተሳሰብ በአፍሪካ ካስፋፉትና ድርጅታዊ መሠረትም ከሰጡት አንዱ የኒያሳላንድ (የአሁኗ ማላዊ) ዜጋ የነበረው የባብቲስት ሚሲዮናዊ ዮሴፍ ቡዝ እንደነበር ይነገራል ። ዮሴፍ ቡዝ በ1897 ባቋቋመው የአፍሪካ ክርስቲያን አንድነት በተሰኘውና ሃይማኖታዊ ገጽታ በነበረው ድርጅት አማካይነት የአፍሪካዊነትን መንፈስ በማጠናከር ጥቁሮችን በአህጉራዊ ንቃተ ኅሊና ለመቀስቀስ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

የፓን አፍሪካኒዝምን መንፈስና የትግል ዓላማውንም በተለይ በዓለም አቀፍ ደረጃ በማዛመት ከፍተኛ ሚና ከተጫወቱት ጥቁር አሜሪካውያን መካከል የታወቀው የማኅበራዊ ኑሮ ተመራማሪ ምሁር ዱ ቧ በግንባር ቀደምትነት የሚታወስ ነው ። ዱ ቧ ለአፍሪካ ጥቁሮች አንድነት ፤ ነፃነትና መብት መከራከር ከመጀመሩ በፊት የአሜሪካ ጥቁሮችን በማስተባበር የዘር ልዩነትን የሚታገሉበትን ብሔራዊ የጥቁር ሕዝቦች መብት አስከባሪ ማኅበር የመሠረተ ነበር ። ለዚህም ድርጅቱ ጥረት መሳካት "ክራይሲስ" የተሰኘ ልሳን በማቋቋም ዋና አዘጋጅ ሆኖ ከፍተኛ ዘመቻ አካሂዷል ። በኋላም በዚሁ ጋዜጣ በመጠቀም የአፍሪካ ሕዝቦች ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር ነፃ እንዲወጡና በየአህጉሩ የሚገኙት ጥቁሮችም ለዚሁ ዓላማ እንዲነሣሡ ከፍተኛ ቅስቀሳ አድርጓል ።

የዱ ቧና የሌሎችም ታጋዮች ጥረት እየተጠናከረ በመሄድ የአፍሪካ ብሔራዊ ስሜት ያላቸው ምሁራንን ለማሰባሰብ በመቻሉ በ1900 ለንደን ላይ የመጀመሪያውን የፓን አፍሪካ ጠቅላላ ጉባኤ ለማካሄድ አስችሏል ። የትሪኒዳድ ጠበቃ በሆኑት ሲልቬስተር ዊል

ያምስ አዘጋጅነት የተሰበሰበው ጉባኤ የመጀመሪያው እንደመሆኑ ለአፍሪካውያን አንድነት ያስገኘው ቀጥተኛ ውጤት የተወሰነ ቢሆንም ጥቁር ምሁራን ስፊ ውይይት በማካሄድ ያደረጉት የሐሳብ ልውውጥ ከአንዳንድ የጋራ አመለካከት ላይ ለመድረስ ረድቷቸዋል።

ከዚያ በኋላ በዱ ቧ የተዘጋጁ አራት የፓን አፍሪካኒዝም ጉባኤዎች ተካሂደዋል ። ሁለተኛው ጉባኤ ፓሪስ ከተማ የተሰበሰበው ከአንደኛው የኢምፔሪያሊስቶች ጦርነት በኋላ በ1919 ኃያላን መንግሥታት ቨርሳይ ላይ የሰላም ውል በተፈራረሙበት ወቅት ነበር ። ምንም እንኳ ኃያላን መንግሥታት ጉባኤው በራሳቸው ስብሰባ ሰሞን እንዳይደረግ ቢቃወሙም ጥቁሮች በወቅቱ ጉባኤያቸውን አካሂደው በአጋጣሚው በመጠቀም መልዕክታቸውን ለኃያላን መንግሥታቱ ተወካዮች ጭምር ለማስተላለፍ ችለዋል ። በጉባኤው ላይ ከተለያዩ ሀገሮች የተወከሉ 57 ጥቁሮች ተሳትፈዋል ። በውሳኔአቸውም የዓለም አቀፍ ሕጎች የአፍሪካውያንን መብት እንዲያስከብሩና አፍሪካውያን በየሀገሮቻቸው መንግሥታዊ መዋቅሮች ውስጥ ሥልጣን እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል ።

በ1921 በለንደንና በብራስልስ ፣ በ1923 በለንደንና በሊዝቦን እንዲሁም በ1927 በኒዮርክ በተካሄዱት የፓን አፍሪካኒዝም ጉባኤዎችም ላይ ተመሳሳይ ውሳኔዎች የተላለፉ ሲሆን በተለይም ለአፍሪካውያን ራስን በራስ የማስተዳደር መብት እንዲሰጣቸው የስፈረው ጥያቄ የጐላ ነበር ።

ከነዚህና ከመሳሰሉት ቡድኖች ሌላ አንዳንድ ግለሰቦችም ለፓን አፍሪካኒዝም ስሜት መዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ለምሳሌ ማርከስ ጋርቬይ የተባለው የጃማይካ ተወላጅ በ1920 የጥቁሮች ፓርላማ የተሰኘ ድርጅት አቋቁሞ ጥቁሮችን በማሰባሰብ "ወደ አፍሪካ እንመለስ" በሚል መፈክር ሥር ብዙ ታግሏል ።

ወቅቱ ቅኝ ገዥዎችና ተባባሪዎቻቸው ካፒታሊስት ሀገሮች የገነኑበት እንደ መሆኑ የጥቁሮች ድምፅ ተሰሚነት ዝቅተኛ የነበረበት፣ ለጥቁር መብት እንታገላለን ከሚሉትም መካከል ብዙዎቹ የርዕዮተዓለም ጥራት የጐደላቸውና በአቋም ቆራጥ ያልነበሩበት ፣ ብዙዎቹም ከአፍሪካ ነባራዊ እውነታ ርቀው በስሜት ብቻ የሚታገሉበት ስለነበር ውጤቱ የሚያመረቃ እንዳልነበር ግልጽ ነው ። ሆኖም እነዚያ የ1920ዎቹ ጥረቶች ከሶሻሊዝም በሶቭዬት ኅብረት መመሥረት ጋር ከሁለተኛው የኢምፔሪያሊስቶች ጦርነት በኋላ ለተፋፋመው የፀረ ቅኝ አገዛዝ ፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስትና የአፍሪካ አንድነት ትግል እርሾ በመሆን ከፍተኛ የአስተሳሰብ አስተዋጽኦ እንዳደረጉ እሙን ነው ።

በዚሁ መሠረት ቀደም ሲል በአውሮፓ የተቋቋሙ የአፍሪካውያን ተማሪዎች ማኅበራትና የፖለቲካ ድርጅቶች በ1944 ተዋሀደው የፈጠሩት ፌደሬሽን በ1945 በእንግሊዝ ሀገር ማንቼስተር ውስጥ ጉባኤ አድርጓል ። በዚህም ስብሰባ ላይ የፓን አፍሪካኒዝም ዓላማዎች ተጠናክረው ከመቅረባቸውም በላይ በኋላ ወደ አፍሪካ ተመልሰው ከፍተኛ የነፃነት ተጋድሎ ያደረጉና የሀገር መሪ ለመሆንም የበቁ ታጋዮች ተሳትፈዋል። ከነዚህም መካከል የጋናው ዶክተር ክዋሚ ንክሩማህ ፣ ዶክተር ኩርንኪ ቴይለርና ጆ. አፒያ ፣ ከናይጄሪያ ኤስ. ኤል አኪንተላና ኦ. ኤች. ዴቪስ ፣ እንዲሁም ኬንያዊው ጆሞ ኬንያታ ይገኙባቸዋል ። አንጋፋው የፓን አፍሪካኒዝም ጉባኤዎች አዘጋጅ ዱ ቧም ነበሩበት ።

ከማንቼስተሩ ጉባኤ በኋላ የፓን አፍሪካኒዝም አመራር በአፍሪካውያን እጅ ከመግባቱ ሌላ አፍሪካ ሙሉ ነፃነት እንድትቀዳጅ የሚለው ጥያቄም ተጠናክሮ ቀረበ ። ዘመቻውም በየአህጉሩ ባሉት ጥቁሮች በተለይም በየትምህርት ቤቶች ባሉ አፍሪካውያን ተማሪዎችና ምሁራን ዘንድ ይበልጥ አስተጋባ ። ይኸው ሁኔታ በአፍሪካ ውስጥ ይካሄዱ ከነበሩት የአርነት ትግሎች ጋር በመተጋገዙና በሶሻሊዝም መዳበር ምክንያት በዓለም ውስጥ በመጠናከር ላይ የነበረውን ፀረ ኢምፔሪያሊዝም ሂደት በመደገፉ በ1960ዎቹ የአፍሪካ ሕዝቦች ነፃነት በተከታታይ ከሞላ ጎደል እውን ሊሆን በቃ ። የዛሬው የአፍሪካ አንድነት ድርጅትም ከዚሁ ከፓን አፍሪካኒዝም ዓላማ በመነሣት የተገነባ የአህጉሩ የአንድነት መድረክ ነው ።

## ፔቲ ፣ ዊልያም
*(Petty, William)*

ከ1623—1687 የኖረ ፣ እንግሊዛዊ ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚስት ነው ። ፔቴ በወጣትነት ዘመኑ ወደ ፈረንሳይና ወደ ሆላንድ በመሄድ በሆላንድ ውስጥ በአንድ የእጅ ሥራ ሱቅ ውስጥ ተቀጥሮ ሠርቷል ። በፓሪስ በነበረበትም ጊዜ የታወቀው ፈላስፋ የቶማስ ሆብስ ልዩ ፀሐፊ ሆኖ አገልግሏል ። በነዚሁ ሀገሮችም ውስጥ በከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች ውስጥ የሕክምና ትምህርት ተከታትሏል ። በለንደን ከተማም በጂስዊት ኮሌጅ ውስጥ ተምሯል ። በኋላም በ1649 በኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ በሕክምና የዶክትሬት ዲግሪ በማግኘት በዚሁ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የአናቶሚ ፕሮፌሰር በመሆን ሠርቷል ።

ዊልያም ፔቲ በእንግሊዝ ስብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሀልዎና ማግኘት ዋናውን ጥርጊያ ጉዳና የከፈተ የመጀመሪያው የኢኮኖሚ ተመራማሪ ነበር ። ከዚህም የተነሣ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መሥራችና አባት እየተባለ ይጠራል ።

ፔቲ የተለያዩ በርካታ የኢኮኖሚ ጥናቶችን አቅርቧል ። ስራ ጥናት ካደረገባቸው ርዕሶች ውስጥ ስለ እሴት ፣ ስለምንዳ ፣ ስለኪራይ ፣ ስለወለድ ፣ ስለገንዘብና ስለሥራ ክፍፍልና ስለስታቲስቲክስ ይገኞሉ ። የዊልያም ፔቲ የመጀመሪያውና ትልቁ የኢኮኖሚ የምርምር ጽሑፍ በ1662 ያቀረበው "አ ትሪትስ ኦቭ ታክስ ኤንድ ኮንትሪቢዩሽን" የተሰኘው ነበር ። በዚህ ጥናት ውስጥ ፔቲ ከፍተኛ ትኩረት የሰጠው ለእሴት ሥራ ንድፈ ሐሳብ ነው ። በተጨማሪም በዚህ ጥናቱ ውስጥ ፔቲ ያደረገው ትንተና ለ "ረቂቅ ሥራ" ጽንሰ ሐሳብ ተቀናብሮ መመንጨት አስተዋጽኦ አድርጓል ። ይህንን የዊልያም ፔቲን ጥናት ካርል ማርክስ ከመረመረ በኋላ በዚህ የጥናት ጽሑፍ ውስጥ ፔቲ የሸቀጦችን እሴት በውስጣቸው ባለው የሥራ መጠን ይወስናቸዋል በማለት አድናቆቱን ገልጿል ። ስለዚህም ዊልያም ፔቲ የ "እሴትን የሥራ ንድፈ ሐሳብ" ያገኘው የመጀመሪያው ሰው በመባል ይታወቃል ።

ፔቲ በዚህ ጥናቱ ውስጥ ያቀረበው ሌላ ዋና ነጥብ ደግሞ የወዝአደሩ ምንዳ የሚወሰነው ወዝአደሩ ራሱንና ቤተሰቡን ለማቆያ በሚያስፈልገው ዝቅተኛ ወጪ ነው ማለቱ ነው ። በዚህ ትንተናው ውስጥ በወዝአደሩ ሥራ የሚፈጠረው እሴት ከሚከፈለው የበለጠ መሆኑን ገልጿል ። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ፔቲ የመንግሥትን የገቢ ምንጮችና የወጪ መልኮች በሚመለከትም ትንታኔ አቅርቧል ።

ዊሊያም ፔቲ ስለዋጋ ባቀረበው ሌላ ጥናት ውስጥ "የተፈጥሮ ዋጋ" የ "ገበያ ዋጋ" አንዳንዴም "የፖለቲካ ዋጋ" የተሰኙ ጽንሰ ሐሳቦችን ጠቅሷል ።

·የዊልያም ፔቲ ሌላው ትልቁ ጥናታዊ ጽሑፍ በ1672 ተደርሶ በ1690 ታትሞ የወጣው " ፖለቲካል አርቲሜቲክ " የተሰኘው ጽሑፍ ነበረ ። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የመንግሥታዊ ስታቲስቲክስ አገልግሎት ስጪ ድርጅትን ስለማቋቋም ጉዳይና መረጃዎች የሚሰበሰቡባቸውንና የሚጠናቀሩባቸውን ዘዴዎች በሚመለከት ለመጀመሪያ ጊዜ ጥናት አቅርቧል ። በዚህም የተነሣ ዊልያም ፔቲ የስታቲስቲክስ ሳይንስ መሥራችና አባት ተብሎ ይጠራል ።

ዊልያም ፔቲ በዚህ ጥናት አጠንክሮ ካቀረበው ጉዳይ ውስጥ የአንድን ሀገር ብሔራዊ ገቢና ብሔራዊ ሀብት የማስላትን አስፈላጊነትና ጥቅም በሚመለከት ያቀረበው ይገኛል ። የእንግሊዝንም ብሔራዊ ሀብት ለማስላት ለመጀመሪያ ጊዜ በ1664 ሙከራ ያደረገ ተመራማሪ ነበር ። ሌላው የዊልያም ፔቲ የኢኮኖሚ ጥናት አስተያየት በኢኮኖሚ ውስጥ ተጨባጭ የኢኮኖሚ ሕጎች መኖራቸውን በሚመለከት ያቀረበውና እነዚህንም ተጨባጭ የኢኮኖሚ ሕጎች ከተፈጥሮ ሕጐች ጋር ለማወዳደር ያደረገው ሙከራ ነው ።

## ፕሩዶን ፣ ፒየር ጆሴፍ
*(Proudhon, Pierre-Joseph)*

ከ1809–1865 የኖረ ፣ የፈረንሳይ ንዑስ ከበርቴ ሶሻሊዝምና የሥርዓት አልበኝነት አመለካከት መሥራች ነው ።

ፕሩዶን ሊታወቅ የቻለው በ1840 በጻፈው "ኬስ ክ ላ ፕሮፕሪዬቴ?" በተሰኘው መጽሐፉ አማካይነት ነው ። በዚህ መጽሐፉ ውስጥ የካፒታሊስት የሀብት ክምችትን በመገምገም "ንብረት ማለት ስርቆት ነው" ከሚል መደ

ምደሚያ ላይ ደረሰ። በ1846 በጸፈውና ማርክስ ከፍተኛ ሒስ ባካሄደበት "ላ ፊሎሶፊ ደ ፡ ላ ፡ ሚዜር" በተሰኘው መጽሐፉ ፣ ፕሩዶን ኮሚኒዝምን በመቃወም የካፒታሊስት ኅብረተሰብን ለመለወጥ የሚቻለው ሰላማዊ በሆነ መንገድ በካፒታሊስት ምርት የብድርና የልውውጥ መስክ ውስጥ አንዳንድ ለውጦችን በማምጣት ነው የሚል አስተሳሰብ አራምዶ ነበር ። ማርክስ "ፖቨርቲ ኦቭ ፊሎሶፊ" በተሰኘው ዝነኛ ጽሁፉ ይህን የፕሩዶንን ንዑስ ከበርቴ አዊ አመለካከት ኢሳይንሳዊነት በሚገባ አሳይቷል ።

ፕሩዶን የተከማቸን የካፒታሊስት ንብረት "ስርቆት" ብሎ ቢጠራና የቡርዧውን መደብ ቢፃረርም ፣ ለንዑስ ከበርቴው መደብ ጥቅም በራስ ጉልበት ለተገኘው አነስተኛ የሀብት ይዞታ የቆመ እንደመሆኑ ያራምድ የነበረው አመለካከት ካፒታሊዝም በአብዮታዊ መንገድ ከሥረ መሠረቱ መገርሰስ አለበት የሚለውን ማርክሳዊ አመለካከት የሚፃረርና በጥገናዊ ለውጥ ላይ የተመሠረተ ነው ። ፕሩዶን የብዝበዛ ምንጭ ምን እንደሆነ ሊገነዘብ ባለመቻሉ በካፒታሊስት ሥርዓት ብዝበዛ የሚመነጨው ከምርት ሂደት ሳይሆን ባልተመጣጠነ ንግድ ሳቢያ ከልውውጥ መስክ ነው ብሎ ያምን ነበር ። በመሆኑም እንደ ፕሩዶን አመለካከት በካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ብዝበዛ ሊጠፋ የሚችለው በሸቀጦች ዝውውር ሂደት (በንግድ መስክ) አንዳንድ ኢኮኖሚያዊ ለውጦችን በማድረግ ፣ ሸቀጦችን አለገንዘብ በመለዋወጥና ወለድን በማጥፋት ነው ። ይህ ከተደረገ በፕሩዶን አመለካከት የግል ሀብት ሳይጠፋ ሠርቶ አደሮች በሙሉ ወደ ነጻ አምራችነት ይቀየራሉ ፤ ሸቀጦችና አገልግሎቶችን በእኩያዊ ልውውጥ መሠረት በመለዋወጥ የጋራ ትብብር ይመሠርታሉ ፤ ብዝበዛም ይጠፋል ።

ከዚህ የንዑስ ከበርቴ ተምኔታዊ ንድፈ ሐሳብ በመነሣት ፕሩዶን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ፣ በወዝአደሩ መደብና በቡርዧዚው መካከል ኅብረት በመፍጠር "ማኅበራዊ አብዮት" ለማካሄድ እንደሚቻል ለፈፈ ። ፕሩዶን የፖለቲካ ትግል ማካሄድን ጨርሶ የሚቃወም ከመሆኑም በላይ በኅብረተሰብ ውስጥ ለመደቦች ክፍፍሎሽና ለመደብ ጭቆና ምንጩ የግል ሀብት ሳይሆን መንግሥት እንደሆነ አድርጐ ይመለከት ነበር ። ለዚህም ነው በአንዳንድ ጽሑፎቹ ውስጥ "መንግሥትን ስለማጥፋት "አስፈላጊነት በመጻፍ ለሥርዓት አልበኝነት መሠረት ሊጥል የቻለው ።

ፕሩዶን በኅብረተሰብ ውስጥ ማኅበራዊ ቅራኔ ሊወገድ የሚችለው በተፃራሪ መደቦችና በማኅበራዊ ክፍሎች መካከል ተመጣጣኝነት ሲኖር ነው በማለት ያምናል ። እንደፕሩዶን አስተሳሰብ ማኅበራዊ ለውጥን ለማስገኘት የሚቻለው የመደብ ትግልን በማካሄድ የብዝበዛ ምንጭ የሆነውን የግል ሀብት በማጥፋት ሳይሆን ፣ በሰው ሰብእና ውስጥ የሥነ ምግባር ፍጹምነትን በማስገኘትና የእኩልነትና የፍትህ አስተሳሰብን እውን በማድረግ ነው ።

ፕሩዶን ወደ መጨረሻው ስለመንግሥት መጥፋት ቀደም ሲል የነበረውን አመለካከት ለወጥ በማድረግ ማዕከላዊ መንግሥታት ወደ ትናንሽ መንግሥታት እንዲከፋፈሉና በነዚህም ትናንሽ መንግሥታት መካከል ፌደራላዊ ግንኙነት እንዲመሠረት በማለት ካፒታሊዝም ጠንካራ ብሔራዊ መንግሥታትን የመፍጠሩን ሂደት ተቃውሟል ። የካፒታሊዝም መስፋፋት የግዴታ የተከማቸ ሀብትን መፍጠሩ የታሪክ ሂደት በግድ ያስከተለው መሆኑን በመገንዘብ ወደ ኋላ ፕሩዶን ትላልቅ ኢንዱስትሪና የባቡር ሐዲድ ወደ ወዝአደሮችና ወደ ካፒታሊስቶች የጋራ ንብረትነት እንዲቀየሩ የሚል አስተሳሰብ ቢያራምድም ፣ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችንና የእርሻ የምርት መገልገያ መሣሪያዎችን በግል መያዝ ያስፈልጋል በሚል አመለካከቱ ግን እስከ መጨረሻው ጸንቶ ቆይቷል ።

(ሥርዓት አልበኝነትን ይመለከቷል።)

## ፕሮፓጋንዳ
*(Propaganda)*

ጠለቅ ያለ ርዕዮተዓለማዊ ይዘትና የስርጭት ስልት ያለው ፣ በአንድ በተወሰነ ጉዳይ ላይ ለጥቂት ወይም በዛ ላሉ ሰዎች ብዙ ሐሳቦች የሚተላለፉበት ስልት ነው ። የኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ስሜትን በሚማርክ ቋንቋ ውሸትን እውነት አስመስሎ በማቅረብ ሠርቶ አደሩን ለአድኃሪ ዓላማው ከሚያ

ሰልፈው የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ በይዘትም ሆነ በአቀራረቡ ፍጹም የተለየ ነው ።

የማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ ፕሮፓጋንዳ ዓላማ የማርክሲዝም ሌኒንዝም አስተሳሰቦችንና የፓርቲ ፖሊሲን በሠርቶ አደሩ ሕዝብ መካከል በማሰራጨት ፣ በተጨባጭ ነገሮች ላይ ተመርኩዞ ሳይንሳዊ ትንታኔ በማድረግና በትክክል በማሳመን ላይ የተመሠረተ ነው ። በዚህ መሠረት የኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ፓርቲው የሠራተኛውን መደብና የሠርቶ አደሩን ሕዝብ መሠረታዊ ጥቅምና ፍላጐት ተጨባጭ ለማድረግ በሚያደርገው ትግል ሕዝቡን በአብዮታዊ አስተሳሰብ የሚያንጽበት ዓይነተኛ የፖለቲካ መሣሪያ ነው ።

የፕሮፓጋንዳ ሥራ ጥራትና ውጤት የሚወሰነው ፓርቲው በሚከተለው መሥመር ፣ ፕሮፓጋንዳው በሚካሄድበት ተጨባጭ ሁኔታና ሥራውን በሚመሩና በሚያካሂዱ የፓርቲ ካድሬዎች (ፕሮፓጋንዲስቶች) ንድፈ ሐሳባዊ ግንዛቤና ብስለት ነው ።

ሠራተኛው መደብ ለሥልጣን ባልበቃበት ሁኔታ የፓርቲ ፕሮፓጋንዳ ዋና ተግባር ሠርቶ አደሩ ሕዝብ አድኃሪውን ሥርዓት በመደምሰስ ለአዲሱ ኅብረተሰብ መታገል እንዳለበት ራሱ ከሚደርስበት ብዝበዛና ጭቆና ተገንዝቦ ለትግል እንዲነሣሣ ማድረግ ነው ። በውስጥ የርስ በርስ ጦርነትና የውጭ ወረራም ባለበት ጊዜ የፕሮፓጋንዳው ሥራ የሚያተኩረው የሕዝቡን ሞራል በመጠበቅ ፣ ፖለቲካዊ ፣ ብሔራዊና ወታደራዊ አንድነትን በማጠናከር ፣ የውስጥና የውጭ ጠላቶችን በማጋለጥና በመዋጋት ላይ ይሆናል ። ፓርቲው በኅቡእ ለመታገል በሚገደድበት ጊዜ የፕሮፓጋንዳውም ሥራ ውስጥ ለውስጥ በሕዝቡ መካከል በፓርቲው ጋዜጣና በሌሎችም ሁኔታው በፈቀደው ዘዴ ይካሄዳል ። አብዮታዊው ትግል ድልን ተጎናፅፎ ፓርቲው ሥልጣን ሲጨብጥ አዳዲስ ሁኔታዎችና ተግባሮች ከፊቱ ስለሚደቀኑ የአብዮቱን ድሎች ለመጠበቅ ፣ ለማጠናከርና የበለጠም ለማስፋት የፓርቲው ፕሮፓጋንዳ በይዘቱ ፣በስፋቱና በአቀራረብ ዘዴው ከአብዮቱ ዕድገት ፣ ከሕዝቡ ፍላጐትና የንቃት ደረጃ ጋር እየተሻሻለና እየዳበረ ይሄዳል ። በዳበረ የሶሻሊስት ኅብረተሰብም ቢሆን ለኮሚኒዝም ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት ለመጣል በሚደረገው የተወሳሰበ ሂደት ፕሮፓጋንዳ ሠርቶአደሩን ሕዝብ በኮሚኒስት አስተሳሰብና የኑሮ ዘይቤ በማነጽ ፣ የተለያዩ የኮሚኒዝም ግቦችን በሚገባ በማስረዳትና በማሳወቅ በግንባታው በንቃት እንዲሳተፍ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ።

በፕሮፓጋንዳ ሥራ ላይ የሚሰማሩት ካድሬዎች ለሶሻሊዝም ፍጹም ታማኝና ቆራጥ ታጋይ ሊሆኑ ይገባል ። ለዚህ ታላቅ ዓላማ ብቁ ሆነው እንዲገኙም የሚሰጣቸው የርዕዮተ ዓለም ትምህርት ይዘት ፣ ስፋትና ጥልቀት እንዲኖረው ማድረግና በተግባር በማዋሉም ረገድ የአጠቃቀሙን ስልትና ዘዴ በሚገባ ከወቅቱ ሁኔታ ጋር አገናዝቦ ማስጨበጥ እጅግ አስፈላጊ ነው ። የፓርቲ ትምህርት በየጊዜው ከአብዮቱ ዕድገት ጋር እየታደሰና እየዳበረ ካልሄደ ጠቃሚነት ስለማይኖረው በፕሮፓጋንዳ ሥራ ላይ የተሰማሩትን የፓርቲ አባሎች ሳያቋርጡ ማሠልጠንና በተግባራዊ ክንውናቸውም እየተከታተሉ ማጠናከር የፓርቲው የማያቋርጥ ተግባር ይሆናል ።

## ፖለቲካ
*(Politics)*

“ፖሊቲ” ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን ይህም የጥንታዊት ግሪክ ትናንሽ መንግሥታዊ ተቋሞች መጠሪያ ነበር ። ፖለቲካ የኅብረተሰብ አደረጃጀትን ፣ የመንግሥት ይዘትን ፣ ዓይነትን ፣ ቅርፅንና ተግባርን ፣ መደቦችና የኅብረተሰቡ ክፍሎች መሠረታዊ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ የሚያደርጉትን ትግል ፣ በመንግሥታት መካከል የሚፈጠሩትን ግንኙነቶች ማለትም የውጭ ግንኙነት ፖሊሲንም በሚመለከት የተወሰነ መደብ የሚኖረውን ንድፈ ሐሳባዊ ግንዛቤና ከዚሁ የሚመነጨውን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ያጠቃልላል ። ፖለቲካና ፖለቲካዊ ትግል በኅብረተሰብ ታሪክ የተከሰተው ከመንግሥት ህልውና ማግኘት ጋር ነው ።

በመደቦች መካከል የሚፈጠሩት ፖለቲካዊ ግንኙነቶች የሚመነጩት በኅብረተሰቡ ሕይወት ውስጥ መደቦች ካላቸው የኢኮኖሚ አቋምና ከዚህም የተነሣ በኅብረተሰቡ ውስጥ በሚጫወቱት ሚና ነው ።

በዚህ ውስጥ የፖለቲካ አስተሳሰቦችና
ተቋሞች የኅብረተሰቡ የኢኮኖሚ መሠረት
ነጸብራቅ የሆነው የላዕላይ መዋቅሩ አካል
ናቸው ። ፖለቲካ ከፍተኛው የኢኮኖሚ መሠ
ረት መግለጫ ነው ፤ ይህ ማለት ግን ፖለቲ
ካው በኢኮኖሚው ላይ ምንም ተፅዕኖ የማ
ያደርግና ፣ የኢኮኖሚው ነጸብራቅ ብቻ የሆነ
ነው ማለት አይደለም ። ፖለቲካ ታላቅ የኅ
ብረተሰብ ለውጥ መሣሪያ የመሆኑን ያህል ፣
መልሶ በኢኮኖሚዉ መሠረታዊ ባሕርይ
ላይ የራሱን ተፅዕኖ ያደርጋል ።

የቡርዧው ፖለቲካ የኅብረተሰብን
አብዮታዊ ዕድገት ይፃረራል ። የሠራተኛው
መደብ ፖለቲካ ግን ለኮሚኒስቶች ዓላማና
በአጠቃላይም ለማኅበራዊ ዕድገት ለሚያስ
ፈልገው ድርጅታዊ አሠራር ሁሉ መሪ ኃይል
ነው ። የዚህ ዓይነቱ ፖለቲካ በሳይንሳዊ የኅብ
ረተሰብ ዕድገት ሕግጋት ላይ የተገነባ ፣ የሠ
ርቶ አደሩን ሕዝብ ፍላጎቶች የሚያንፀባር
ቅና በተጨባጭ ለመረጋገጣቸውም ዋስትና
የሚሰጥ ነው ። የሠራተኛውን መደብ ፖለ
ቲካም የሚመራው የሠራተኛው መደብ
ፓርቲ ነው ።

(ፓርቲን ፣ መንግሥትን ይመለከቷል።)

## ፖለቲካ መሥመር (የ—)
*(Political Line)*

አንድ ዓይነት ርዕዮተዓለም ያላቸው
የፖለቲካ ድርጅቶች አንግበው የተነሡትን
ዓላማ ከግቡ ለማድረስ የሚከተሉት የትግል
ፈር ወይም የሚወስዱት አቋም ነው ። በአ
ንድ ሕዝባዊ ሂደተ ትግል ውስጥ ፖለቲካዊ
መሥመር በንድፈ ሐሳብ ፣ በፕሮፓጋንዳና
ቅስቀሳ ሥራ ብቻ ሳይሆን በዕለት ተዕለት
ተግባራዊ እንቅስቃሴም ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ
ስለሚያደርግ በአብዮቱ ሂደት ላይ ወሳኝ
ሚና ይኖረዋል ። ከዚህም የተነሣ አንድ ርዕ
ዮተዓለም በሚከተሉና ለአንድ ዓላማ በተሰ
ለፉ ኃይሎች መካከል በስትራቴጂና በታክ
ቲክ ልዩነት ምክንያት የሚፈጠሩ የተለያዩ
የትግል አቅጣጫዎች የአብዮትን ዕድል የሚ
ወስኑ በመሆናቸው በአንድ ላይ ለብዙ ጊዜ
ሊጓዙ አይችሉም ። በመሆኑም ሐቀኛ አብዮ
ታውያን ትክክለኛው ፖለቲካዊ መሥመራ
ቸው በአሸናፊነት እንዲወጣ ወደ ተሳሳተ
አቅጣጫ የሚወስደውን የፖለቲካ አቅጣጫ
ወይም ወደዚያ የሚመራ አዝማሚያን በጽኑ
ሊታገሉት ይገባል ።

## ፖለቲካ ሥልጣን (የ—)
*(Political Power)*

አንድ መደብ ጥቅሙን ለማስከበርና
የበላይነቱን ለማረጋገጥ የሚመሠርተው መን
ግሥታዊ ሥልጣን ነው ። በመደብ በተከፋፈለ
ኅብረተሰብ በመደቦች መካከል የሚደረገው
ትግል ዓላማ በቅድሚያ የፖለቲካ ሥልጣን
መጨበጥ ነው ። ለፖለቲካ ሥልጣን የሚደ
ረገው ትግል ኅብረተሰብ በመደብ ከተከፋፈለ
በት ጊዜ ጀምሮ የተከሰተ ቢሆንም ውስብ
ስብ የሆነውና የፓርቲ አመራርን የጠየቀው
በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ነው ። ሌሎች
ገዥ መደቦች በፖለቲካ ሥልጣናቸው የተ
ጠቀሙት ጭቆናንና ብዝበዛን ለማስፈን
ሲሆን ወዝአደሩ ግን በፖለቲካ ሥልጣን
የሚጠቀመው የጨቋኙንና የበዝባዡን ሥር
ዓት ለማፈራረስ ፣ የማምረቻ መሣሪያዎችን
የሕዝብ ለማድረግ ፣ የሰው በሰው ብዝበዛን
ለማስወገድና ፍትህ ፣ እኩልነትና ሰላም
የሰፈነበትን ኅብረተሰብ ለመመሥረት ነው ።
ምዝብርና ጭቁን መደቦች ፖለቲካዊ ሥል
ጣን በእጃቸው እስካላደረጉ ድረስ ሙሉ
መብታቸው ሊከበር አይችልም ። የፖለቲካዊ
ሥልጣን ጥያቄ የማንኛውም አብዮት ዓቢይ
ጥያቄ የሚሆነውም በዚሁ ምክንያት ነው ።

## ፖለቲካ ቢሮ
*(Political Bureau)*

በማዕከላዊ ኮሚቴው መደበኛ ስብሰባ
ዎች መካከል ባለው ጊዜ የፓርቲውን ተግባር
የሚመራ ፣ ውሳኔዎችንና መመሪያዎችን የሚያ
ስፈጽም በተለይም የፓርቲውን የዕለት ተዕ
ለት ተግባሮች የሚያከናውን አካል ነው ።
ፖለቲካ ቢሮዉ በተለይ የሚያተኩረው
በዋና ዋና ብሔራዊና ዓለምአቀፍ ጉዳ
ዮች ላይ ነው ። አባላቱም በፓርቲው
መዋቅር ውስጥ በቋሚነት የሚሠሩ ብቻ
ሳይሆኑ ፣ በከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ

ነት ቦታዎች ላይ የሚገኙ የፓርቲ አባላትም ሊሆኑ ይችላሉ ። ፖለቲካ ቢሮው ተጠሪነቱ ለማዕከላዊ ኮሚቴው ነው ።

(ፓርቲን ፣ የፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴን ፣ የፓርቲ ጉባኤን ይመለከቷል ።)

## ፖለቲካዊ የሥራ ማቆም አድማ
*(Political Mass Strike)*

ጠቅላላው ወይም አብዛኛው ሠራተኛ ከካፒታሊስቱ መደብና የካፒታሊስቱን መደብ ከሚወክለው መንግሥት ጋር ለሚያካሂደው ፖለቲካዊ ትግል እንደመግሪያ አድርጐ የሚወስደው የሥራ ማቆም ርምጃ ነው ። ፖለቲካዊ የሥራ ማቆም አድማ እውን ሊሆን የሚችለው በሀገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ ቀውስ ተፈጥሮ ልዩ ልዩ መደቦችን ተሳታፊ ሲያደርጋቸውና የካፒታሊስቱ መንግሥት የተፈጠረውን ትርምስና አስቸጋሪ ሁኔታ ሊቋቋመው በማይችልበት ወቅት በየቦታው ሠራተኞችና ሌሎችም መደቦች ተቃውሞአቸውን ሥራ በማቆም ሲገልጹ ነው ። ሠራተኛው ኮሚኒስት ፓርቲ ባለበት ሁኔታ በፓርቲው መሪነት የሥራ ማቆም አድማውን ፖለቲካዊ ቅርፅና ይዘት በማስያዝ በካፒታሊስቱ ሥርዓት ላይ የማጥቃት ርምጃ ይወስዳል ። የኢንዱስትሪና የመገናኛ መግሪያ ሠራተኞች በሥራ ማቆም አድማው ተካፋይ መሆን ትግሉን የበለጠ ያከረዋል ። ይህ ኃይለኛ የትግል ተፅዕና የመካከለኛውን መደብ ዝቅተኛ ክፍልና ኋላ ቀር የሆኑትን የሠራተኛውን መደብ ክፍሎች እንኳን ሳይቀር የትግሉ ተሳታፊ ያደርጋቸዋል ።

(ፖለቲካዊ አብዮትን ፣ ተናሥኦትን ፣ አመፅን ይመለከቷል ።)

## ፖለቲካዊ ትግል
*(Political Struggle)*

ከኢኮኖሚያዊና ከርዕዮተዓለማዊ ትግል ሂደት የሚመነጭና አይቀሬ የሆነ የወዝአደሩ ከፍተኛው የትግል ደረጃ ነው ። በዚህ ትግል ውስጥ ወዝአደሩ የሚታገለው የግል አሠሪውን ሳይሆን በአጠቃላይ የቡርዧውን መደብና የእሱ ደጋፊ የሆነውን የካፒታሊስት መንግሥት ነው ። ይህ ትግል ወሳኝና መሠረታዊ እንደመሆኑ ሊካሄድ የሚችለው ወዝአደሩ ትክክለኛ መደባዊ ንቃተ ኅሊና ኖሮት የመደብ ጥቅሙን ለይቶ ሲያውቅና ሥልጣን በመያዝ ጥቅሙን ሊያስከብር የተዘጋጀ ሲሆን ነው ። ይህ ሁኔታም በትክክል የሚፈጸመው ለወዝአደሩ የቆመ ፓርቲ ትግሉን ሲመራ ነው ።

የትግሉ ግብ የካፒታሊስትን ሥርዓትና ግንኙነቶች መደምሰስና የመንግሥት ሥልጣን መያዝ ነው ። ይህም ማለት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቅራኔዎች የመጨረሻውን መሠረታዊ መፍትሔ ሊያገኙ የሚችሉት በፖለቲካዊ ትግል አማካይነት ነው ።

እንደተጨባጩ ሁኔታና እንደ ትግሉ ስልት ፖለቲካዊ ትግል ብዙ መልኮች ሊይዝ ይችላል ። ትዕይንተ ሕዝብ ፣ ፓርላማዊ ምርጫ ወዘተ... የትግሉ የተለያዩ መልኮች ሲሆኑ የትጥቅ ትግል ግን የዚህ ትግል ከፍተኛው ደረጃ ነው ።

(የመደብ ትግልን ፣ ኢኮኖሚያዊ ትግልን ርዕዮተዓለማዊ ትግልን ፣ አብዮትን ይመለከቷል ።)

## ፖለቲካዊ አብዮት
*(Political Revolution)*

ፖለቲካዊ አብዮት የመንግሥት ሥልጣን ከአንድ ገዥ መደብ ወደ ሌላ ተራማጅ መደብ የሚሸጋገርበት ነው ። ይህ ፖለቲካዊ ሥልጣን ተራማጁ መደብ በኅብረተሰብ ልዩ ልዩ ማኅበራዊ ሕይወት ዘርፎች ውስጥ መሠረታዊ ለውጥ የሚያመጣበት ወይም ለማምጣት የሚታገልበት ነው ። ፖለቲካዊ አብዮት የመንግሥት ሥልጣን ከአንድ መደብ ወደ ሌላው መደብ የሚሸጋገርበት ቢሆንም ማንኛውም ፖለቲካዊ ሥልጣን ከአንድ መደብ ወደ ሌላው መሸጋገሩ ግን ፖለቲካዊ አብዮት አያሰኘውም ። ምክንያቱም አንድ አድኃሪ መደብ ከአንድ ተራማጅ መደብ ፖለቲካዊ ሥልጣን ቢነጥቅ ድርጊቱ ፀረ አብዮት እንጂ አብዮት አይደለምና ነው።

የቡርዧው መደብ የምርት ግንኙነት በፊውዳሉ ሥርዓት ውስጥ ተጸንሶ ለማደግ ስለሚችል ፣ ቡርዧዚው የፖለቲካ የበላይነት ባይኖረውም በኢኮኖሚው እያደገና እየተጠና

ክረ ፣ የሸቀጥ ምርቱን እያስፋፋ ይሄዳል ። ስለሆነም ቡርዧዚው በፖለቲካዊ አብዮት ሥልጣን የሚይዘው ኢኮኖሚው ካደገ በኋላ በመሆኑ ዋናው ተግባሩ ኢኮኖሚውንና ፖለቲካውን ማጣጣም ይሆናል ። የወዝአደሩ መደብ ግን የሶሻሊስት የምርት ግንኙነትን በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ሊመሠርት ስለማይችል የካፒታሊስቱን ሥርዓት የምርት ግንኙነቶችና ቡርዧዚውን ለመደምሰስ በግድ በመጀመሪያ የፖለቲካ ሥልጣን መጨበጥ ይኖርበታል ። ስለዚህም ለወዝአደሩ በፖለቲካዊ አብዮት አማካይነት ሥልጣን መጨበጥ የመጨረሻ ግቡ ሳይሆን ታሪካዊ ተልዕኮውን ለመወጣት የሚረዳውን ሁኔታ የሚያዘጋጅበት መሣሪያ ነው ።

(ማኅበራዊ አብዮትን ፣ የቡርዧ አብዮትን ፣ ሶሻሊስት አብዮትን ይመለከቷል ።)

## ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ
*(Political Economy)*

በሂደተ ምርት ውስጥ በሰዎች መካከል የሚፈጠረውን የኢኮኖሚ ግንኙነት ማለትም ምርትን ፣ ክፍፍልን ፣ ልውውጥንና ፍጆታን የሚገዙ ማኅበራዊ ሕጎችን የሚያጠና ሳይንስ ነው ።

ሰዎች ፍላጐቶቻቸውን ለማርካት የሚያመርቱበትና የሚለዋወጡበት ሁኔታ ከሀገር ሀገር ብቻ ሳይሆን በአንድ ሀገርም ውስጥ ከዘመን ዘመን የሚለያይ እንደመሆኑ በሁሉም ሀገሮች ውስጥ በማናቸውም ታሪካዊ ወቅት አንድ ዓይነት የሆነ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሊኖር አይችልም ። በድንጋይና በግርድፍ ብረት የሚያመርቱት ኅብረተሰቦችና በእንፋሎት ኃይል የሚጠቀሙት ኅብረተሰቦች ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በጣም የተለያየና የተራራቀ ነው ። ኅብረተሰብ በየደረሰባቸው የዕድገት ደረጃዎች የሚከሰቱትን የአመራረትና የክፍፍል ሁኔታዎች ከሚገዙት አጠቃላይ ሕጎች ላይ ለመድረስ የእያንዳንዱን ደረጃ የአመራረትና የአከፋፈል ሁኔታ በጥልቀት ማጥናትን ይጠይቃል ። በዚህ ዓይነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ተለዋዋጭ የሆኑ ታሪካዊ ክስተቶችን የሚያጠና ቢሆንም በሌላ በኩል ለአንድ ለተወሰነ የአመራረትና የአከፋፈል ስልት የሚሠሩትን ሕጎች ተመሳሳይ የአመራረትና የአከፋፈል ሁኔታ በተከሰተባቸው በማናቸውም ሀገሮችና ታሪካዊ ወቅቶች ገዥነት ይኖራቸዋል ።

ለዚህ ሳይንስ መጠሪያ ስሙን የሰጠው አንቷን ደሞክሬትየን የተባለ ፈረንሳዊ በ1615 "ትሬቴ ደ. ለ ኢኮኖሚ ፖለቲክ" በተሰኘው መጽሐፉ ውስጥ ሲሆን እርሱም በቃሉ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመው ቀደም ሲል በጥንታዊት ግሪክ ተለምዶ የነበረውን "ኤከስኖሞስ" የተባለውን ቃል "ፖሊቲያ" ከሚለው ጋር በማቀናጀት ነው ። ኤከስኖሞስ የተባለው ቃል በጥንታዊት ግሪክ ፈላስፎች አጠቃቀም ኤኮስ (ቤት) ኖሞስ (ሕግ) ከሚሉት ሁለት የግሪክ ቃላት ቅንጅት የቤተሰብ አኗኗር የማኔጅመንት ሕግ ለማለት ያህል የተቀረፀ ሲሆን አንቷን ደሞክሬትየን በዚህ ቃል ላይ ፖሊቲያ (መንግሥት) የተሰኘውን ቃል የጨመረው እርሱ በመጽሐፉ ውስጥ ያሰፈረው መልእክት በጠባቡ ስለ ቤተሰብ አኗኗር ሕግ የሚመለከት ሳይሆን በሰፊው የመንግሥትን ወይንም የሀገርን ኢኮኖሚ የሚመለከት መሆኑን ለማሳየት ነው ።

ለሳይንሱ ስሙን የሰጠው አንቷን ደሞክሬትየን ይሁን እንጂ ጥናቱ የተመሠረተው የምርት ግንኙነት አንደኛው ዘርፍ በሆነው በልውውጥ ላይ ብቻ በመሆኑ ከርሱ ይልቅ በሳይንሱ መሥራችነት ጥረት በማድረጋቸው የሚታወቁት እንግሊዛውያኑ ሰር ዊልያም ፔቲ ፣ አዳም ስሚዝና ዴቪድ ሪከርዶ ናቸው ።

የእነዚህ እንግሊዛውያን ጥናት ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የሚል መጠሪያ አግኝቶ የማርክሳዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አንዱ ምንጭ ሲሆን ጥናታቸው የተከናወነው ግን የቡርዧው መደብ በተራማጅ መደብነት በታሪክ በተከሰተበትና ፣ ለዕድገቱ ዕንቅፋት የሆነውን የፊውዳሉን ስልተ ምርት ለማጥፋት ትንቅንቅ በአካሄደበት በወዝአደሩና በቡርዧዚው መካከል ያለው የመደብ ትግል ጐልቶ ባልወጣበት ወቅት ነበር ። እነዚህ ምሁራን ምንም እንኳን አያሌ ጠቃሚና ለሳይንሱ መዳበር የረዱ ግኝቶችን ቢያበረክቱም ግኝቶቻቸው በሚወክሉት የቡርዧው መደብ ጥቅም አንፃር ላይ ብቻ የሚያተኩሩ በመሆናቸው የካፒታሊዝምን በሌላ ሥርዓት ተተኪ መሆን ሊገነዘቡ አልቻሉም ።

የወዝአደሩ መደብ ታላቅ መሪዎችና አስተማሪዎች የሆኑት ካርል ማርክስና ፍሬ ደሪክ ኤንግልስ ካፒታሊስት ስልተ ምርትን በጠለቀና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በማጥና ታቸው ፤ ሀ/የእሴትን ንድፈ ሐሳብ ከነበረበት ድክመት ሁሉ አጽድቶ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መሠረት በማድረግ ፤ ለ/ የሥራ ኃይል የሚ ሸጥበትንና የሚገዛበትን ታሪካዊ ሁኔታ አብራርቶ በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የብዝበዛን ምንጭ በማሳየት ፤ ሐ/ በአማ ካይ ትርፍ ንድፈ ሐሳብም ላይ በመመርኮዝ የቡርዧው መደብ ባንድነት እንዴት ከወዝ አደሩ መደብ ጋር ተፃራሪ የኢኮኖሚ ጥቅም እንዳለው በመተንተን ፤ መ/ የካፒታሊስት ሥርዓትም በቀውስ የተወጠረ ሥርዓት መሆ ኑን በማሳየትና ሠ/ በመጨረሻም በካፒታሊ ስት ክምችት ሕግ ላይ በመመርኮዝ ካፒ ታሊዝም ዘለዓለማዊ ሥርዓት ሳይሆን የግድ በሶሻሊዝም የሚተካ መሆኑን በመግለጽ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን በሳይንሳዊ መሠረት ላይ ከመገንባታቸውም በላይ የሰው ልጅ የዕድገት ጉዞ ወደ ሶሻሊዝም መሆኑን አረጋግጠዋል ። ይህ የማርክሳዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ጥናት የሰ ፈረበት መጽሐፍ (የካርል ማርክስ ካፒታል) ከወጣ ከግማሽ ምዕት ዓመት በኋላም ታላቁ የወዝአደሩ መምህር ቭላዲሚር ኢሊዬች ሌኒን "ኢምፔሪያሊዝም የካፒታሊዝም ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ" በተሰኘው መጽሐፉ አዲሱን የካፒታሊዝም የዕድገት ደረጃ በተ ጨባጭ በመመርመር ሳይንሱን በበለጠ አዳብሯል ።

ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ከመደብ በላይ ያለ ወይንም ሁሉንም መደብ በእኩል የሚያገለ ግል ሳይሆን ወገናዊ ሳይንስ ነው ። ምክን ያቱም የካፒታሊስት ስልተ ምርትን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በመመርመር ይህ ሥርዓት በግድ በሶሻሊዝም ይተካል የሚለው የማር ክሳዊ ሌኒናዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መደምደ ሚያ ከወዝአደሩ ጥቅም ጋር የተቆራኘና የቡርዧውን መደብ ጥቅም የሚፃረር ሲሆን የቡርዧው ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ደግሞ በመሠረቱ የቡርዧውን መደብ ጥቅም የሚያስከብር መሣሪያ በመሆኑ ነው ። እንዲ ያውም ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ከተመሠረተ ወዲህ በምዕራቡ ዓለም ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በሚለው ቃል ምትክ ኢኮኖሚክስ የተባለው መጠሪያ ይበልጥ ጉልቶ ይታያል ። ኢኮኖሚክስ በመሠረቱ እንደ ፖለቲካዊ ኢኮ ኖሚ የምርት አደረጃጀትን ፣ የሸቀጥ ሽያ ጭንና የመሳሰሉትን የኢኮኖሚ ሳይንሶች ያቀፈ ሲሆን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን በዚህ ቃል የመተካቱ ዓላማ ግን ዝርዝር ነገሮችን በማጉ ላት ፣ መሠረታዊ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ጥያቄ የሆኑትን የኢኮኖሚ ግንኙነቶች ለማድበስበስና ለመሸፈን ሲባል የተሰየመ ነው ።

ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ማርክሲዝም ሌኒኒ ዝም ከተገነባባቸው ሦስቱ ክፍሎች አንዱ ነው። የተቀሩት ሁለቱ የማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍል ስፍናና የሳይንሳዊ ኮሚኒዝም ንድፈ ሐሳቦች ናቸው። ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የማንኛውም ኅብረ ተሰብ የዕድገት መሠረት የሆነውን ነባራዊ የኢ ኮኖሚ ግንኙነት የሚያጠና ሳይንስ እንደመ ሆኑ የኅብረተሰብን ዕድገት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለመረዳት ከማስቻሉም በላይ ብዝበዛ ንና ጭቆናን አስወግደው እኩልነት የሰፈነበት የኮሚኒስት ሥርዓት ለመገንባት ለሚታገሉ የኮሚኒስትና የሠራተኛ ፓርቲዎች ተግባራዊ እንቅስቃሴ ዓይነተኛ መሣሪያ ነው ። በሌላ በኩል የሶሻሊስት ኅብረተሰብ መመሥረትና የሶሻሊስት የኢኮኖሚ ሕጎች መከሰት ለሶሻ ሊስት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሳይንስ መኖር ምክንያት ሆኗል ። የሶሻሊስት ፖለቲካዊ ኢኮ ኖሚን ሳይንስ ዓይነተኛ የሚያደርገው የኢ ኮኖሚያዊ ሕጎችን ነባራዊነት በመቀበል የሰው ልጅ ለራሱ ሊጠቅሙት በሚችሉበት መን ገድ በሚገለገልባቸው የኅብረተሰብ ጥናት ላይ የተመረኮዘ መሆኑ ነው ።

(ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን ፣ ግልብ ፖለቲ ካዊ ኢኮኖሚን ይመለከቷል።)

## ፖፑሊዝም

*(Populism)*

ፖፑሊዝም በ19ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ላይ በአሜሪካና በአውሮፓ ምሁራን አካባቢ ማቆጥቆጥ የጀመረ ለሕዝብ ቆሚ ያለሁ የሚል አዝማሚያ ነው ። አስተሳሰቡ የንድፈ ሐሳብ ጥራትና የፕሮግራም ጥንካሬ የጎደለው ፣ ይበልጡንም ግብታዊነት የሚ ያጠቃው ስለነበር ዘላቂ ውጤት አላስገኘም ። ቢሆንም ብልጭ ድርግም ባለ ሂደቱ አን ዳንድ ሁኔታዎችን ትቶ አልፏል ።

ከ1920 ጀምሮ በፈረንሳይ ድምፃቸውን ያሰሙ የነበሩ የፖፑሊዝም ተከታዮች በፈረንሳይ ከተሞችና በገጠርም የሚኖሩ ድሆች አስቃቂ ሁኔታ በግልጽ ታውቆ አኗኗራቸው እንዲሻሻል ብዙ ወትውተዋል። በዚህ ረገድ በተለይ በመምህራን ፣ በደራሲያንና በመሳሰሉት ወገኖች ይሰነዘር የነበረው ትችት ከፍተኛ ነበር ።

ቀደም ሲልም በተመሳሳይ አመለካከት በአሜሪካ የተስፋፋው የፖፑሊዝም ሁኔታ ይኸው ነበር ። በተለይም በ19ኛው ምዕት ዓመት መጨረሻ ላይ ተከታዮቹ ፖፑሊስት ፓርቲ በሚል ስም ተደራጅተው ለፕሬዝዳንትነት ዕጩ እስከማቅረብና አንድ ሚሊዮን የሚሆን ድምፅ እስከ ማግኘትም ደርሰዋል ። በፕሮግራማቸውም ውስጥ የሕዝባዊነት ባሕርይ ያላቸው ጥያቄዎችን ያቀረቡ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ የኮርፖሬሽኖች ትርፍ መሬት ተወርሶ ለሰፋሪዎች እንዲሰጥ ፣ የባቡር መሥመሮች ፣ የቴሌግራፍና የቴሌፎን ተቋሞችና የመሳሰሉት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ፣ የሥራ ጊዜ በቀን 8 ሰዓት እንዲሆን የሚሉና የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል ።

ነገር ግን እነዚህም ሆኑ ሌሎች ፖፑሊስቶች ለድሃው ሕዝብ አዛኝና ተቆርቋሪ መስለው ቢቀርቡም የጠራ ንድፈ ሐሳብ ፣ የተወሰነ የፖለቲካ መሥመርና ተግባራዊ የለውጥ ፕሮግራም ይዘው ስላልተነሡ ፣ ተከታዮቻቸውም የመደብ አንድነት የሌላቸው በመሆናቸው ውጤታማ ሊሆኑ አልቻሉም ።

ፖፑሊዝም በተለይ በሶቭዬት ኅብረት የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ሰፊ ቦታ ያለው አዝማሚያ ሆኖ ለረዥም ጊዜ ቆይቷል ። በሩሲያ ፖፑሊዝም የምሁራን ርዕዮተ ዓለምና ንቅናቄ ሆኖ ፀረ ፊውዳል በሆነውና ተምኔታዊነት በሚያጠቃው አስተሳሰብ የገባርነትን ሥርዓትና የካፒታሊስቱን የዕድገት ጐዳና በመቃወም ለአርሶ አደሩ ዲሞክራሲያዊ መብት ብዙ ትግል አካሂዷል ። በዚህ ሂደት ከ1860 በኋላ በነበሩት የመጀመሪያዎቹ የለውጥ ዓመታት የሩሲያ ፖፑሊዝም የቡርዧ ዲሞክራሲና የለዘብተኝነት አዝማሚያ የጐላበት ሲሆን ከ1880 በኋላ ግን አቋሙን ጠንክር በማድረግ አርሶ አደሩን በአመፅ ለማነሣሣት ጥምር በመታገል በተለይ እስከ 1895 በወቅቱ የቡርዧ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል ።

የሩሲያ ፖፑሊዝም ንድፈ ሐሳብ መሠረት ዋንኛው የትግል ኃይል አርሶ አደሩ እንደሆነ በመቁጠር ሠራተኛውን እንደተቀጥላ የሚመለከት ፣ ትኩረቱንም በገጠሩ አብዮት ላይ የሚያደርግ ነበር ። በፖፑሊዝም አመለካከት ሀገሪቱ ዕድገቷን መምራት ያለባት ካፒታሊስት ባልሆነ ፈለግ ሲሆን ለዚህም እውን መሆን የአርሶ አደሩን የጋርዮሽ (የኮሚዩን) አኗኗር በማቆየትና በዚህም በመጠቀም ኅብረተሰቡን ወደ ሶሻሊዝም የጋርዮሽ ኑሮ መለወጥ ይቻላል የሚለውን አስተሳሰብ የሚያራምድ ነበር ።ይህንን መሥመር ተግባራዊ ለማድረግ መወሰድ ካለባቸው ሥር ነቀል ርምጃዎች ውስጥ የመሬት ከበርቴነትን ማጥፋት ፣ መሬትን ለአራሹ ማከፋፈልና ዲሞክራሲያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ማቋቋም ዋነኞቹ ነበሩ ።

በተለይም በመጨረሻዎቹ የቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ዓመታት የቀድሞውን ለዘብተኛ ፖፑሊዝም በ "አብዮታዊ" ፖፑሊዝም የቀየሩት የናሮድኒክ ንቅናቄ ወገኖች ከላይ በተመለከቱት ጥያቄዎቻቸው አማካይነት ለትግሉ የሚያስፈልገውን ስትራቴጂና ታክቲክ ከመቀየሳቸው በላይ ንቅናቄውን ፕሮግራም ባለው መሠረት ላይ አጠናክረው ቀራጭ ፈላጩን የቄሳር መንግሥት ተጋፍጠዋል ። ይሁን እንጂ በታክቲኩ የፖለቲካ ሴረኝነት የጐላበትና በተለይም የሽብር ፈጣሪነት ባሕርይ ያጠቃው ፣ የርዕዮተዓለምና የመደብ አሰላለፍ ጥራትም ያነሰው ስለነበር ፖፑሊዝም ዘላቂነት ሊኖረው አልቻለም ።

ይልቁንም ከ1880 በኋላ ካፒታሊዝም በሩሲያ ውስጥ እየተስፋፋ ሲሄድ የሠራተኛው ንቅናቄም አደገ ። ማርክሳዊ አስተሳሰብም ሥር እየሰደደ በመጣ መጠን የትግሉ ይዘት ይበልጥ በወዝአደራዊ ርዕዮተዓለምና በሠራተኛው መደብ አመራር ተጠናከረ ። ከዚህም የተነሣ ፖፑሊዝም ምንም እንኳ ከማርክሳዊ አስተሳሰብም አንዳንድ አመለካከቶችን በጥራዝነጠቅነት ያከለ ቢሆንም የጀብደኝነት እንጂ የተደራጀ የመደብ ትግል መሠረት ስላልነበረው የሩሲያን ሰፊ ሕዝብ

ነፃ ለማውጣት በነበረው ትግል ውስጥ ይዞት የነበረውን የመሪነት ሚና ለአብዮታዊ ማኅበራዊ ዲሞክራሲ ኃይሎች ለመልቀቅ ተገደደ ። የአብዮቱም ግንባር ቀደም ኃይል በማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ የሚመራው ሠራተኛው መደብ ሆነ ።

በተለይም የወዝአደሩ አብዮት በተፋፋመበት ወቅት ፖፑሊስቶች ከአብዮታዊ ሁኔታዎች ይበልጥ እየራቁ ፣ በቁሳሩና በኋላም በቡርዧው አገዛዝና በሕዝቡ መካከል የነበረውን መሠረታዊ ቅራኔ በመሸፈን ለአንዳንድ የጥገና ለውጦች ብቻ መከራከርን ፣ እያደርም በፍጹም አድርባይነት ከሕዝባዊ አቋም ማፈግፈግን ተያያዙት ። በዚህም ንዑስ ከበርቴና ተምኔታዊ አቋማቸው የደረሱበትን ዝቅጠት በመገንዘብ ቀደም ሲል ፕሌካኖቭ ፣ በኋላም ሌኒን ከፍተኛ ሂስ አቅርበውባቸዋል ። አፍራሽና አድኃሪ አቋማቸውንም በመታገል አሸንፈዋቸዋል ።

(ናሮዲዝምን ይመለከቷል።)

# ማውጫ

## 1. አማርኛ — እንግሊዝኛ

### ሀ


| | | |
|---|---|---|
| ሁለተኛው ኢንተርናሽናል | *Second International* | 1 |
| ሁለተኛ ደረጃ ቅራኔ | *Secondary Contradiction* | 2 |
| ሁለታዊነት | *Dualism* | 3 |
| ሁለንታዊ | *Universal* | 3 |
| ሁልእምላክነት | *Pantheism* | 4 |
| ሁሰርል ፥ ኤድመንድ | *Husserl, Edmund* | 4 |
| ሂንዱኢዝም | *Hinduism* | 4 |
| ሂዩም ፥ ዴቪድ | *Hume, David* | 5 |
| ሂደት | *Process* | 6 |
| ሃይማኖት | *Religion* | 7 |
| ሄልቬትዩስ ፥ ክሎድ አድርዩን | *Helvetius, Claude Adrien* | 8 |
| ሄራቅሊጦስ — (የኤፌሶኑ) | *Heraclitus of Ephesus* | 8 |
| ሄግሊያኒዝም | *Hegelianism* | 9 |
| ሄግል ፥ ጊዮርግ ቪልሄልም ፍሪድሪሽ | *Hegel, George Wilhelm Friedric* | 10 |
| ህልውናነት | *Existentialism* | 10 |
| ሆልባህ ፥ ፓውል ፥ ሃንሪ ዲትሪሽ | *Holbach, Paul Henri Dietrich* | 12 |
| ሆብስ ፥ ቶማስ | *Hobbes, Thomas* | 12 |
| ሆ ቺ ሚን | *Ho Chi minh* | 13 |


### ሐ


| | | |
|---|---|---|
| ሐሳበ ግትር | *Die - Hard* | 15 |
| ሐሳባዊነት | *Idealism* | 15 |
| ሐሳባዊ ዲያሌክቲክስ | *Idealist Dialectics* | 16 |
| ሐሳብ | *Idea* | 16 |
| የሐሳቦች ግጥምጥሞሽ | *Association of Ideas* | 17 |
| ሐሳዊ መሲህ | *Demagogue* | 17 |

| | | |
|---|---|---|
| ሕሡም | *Ugly* | 17 |
| ሕውስታ | *Sensation* | 18 |
| ሕውስታዊነት | *Sensationalism* | 18 |
| ሕዝባዊ ሠራዊት | *People's Militia* | 18 |
| ሕዝባዊ ቁጥጥር | *People's Control* | 19 |
| ሕዝባዊ አመፅ | *Insurrection* | 19 |
| "ሕዝባዊ" ካፒታሊዝም | *"People's" Capitalism* | 20 |
| ሕዝባዊ ውሳኔ (ውሳኔ ሕዝብ) | *Referendum* | 21 |
| ሕዝባዊ ዲሞክራሲ | *People's Democracy* | 21 |
| ሕዝባዊ ድርጅት | *Mass Organization* | 22 |
| ሕዝብ ደኅንነት ጥበቃ ኮሚቴ | *People's Defence Committee* | 22 |
| ሕይወታዊነት | *Vitalism* | 23 |
| ሕገ መንግሥት | *Constitution* | 23 |
| ሕጋዊ መድረክ | *Legal Forum* | 24 |
| ሕጋዊ ማርክሲዝም | *Legal Marxism* | 24 |
| ሕጋዊ ንቃተ ኅሊና | *Legal Consciousness* | 25 |
| ሕግ | *Law* | 25 |


## ኀ


| | | |
|---|---|---|
| ኂስና ግለኂስ | *Critisism and Self-Critisism* | 27 |
| ኃብር | *"Habr"* | 28 |
| በኃይል ማቀላቀል | *Annexation* | 28 |
| ኅሊና | *Conscience* | 28 |
| ኅሊናዊ | *Subjective* | 28 |
| ኅሊናዊ ሁኔታ | *Subjective Condition* | 29 |
| ኅሊናዊ ሐሳባዊነት | *Subjective Idealism* | 29 |
| የኅሩያን ምስፍና | *Aristocracy* | 30 |
| ኅቡእ | *Clandestine* | 31 |
| ኅብረት ሥራ ማኅበር (የ—) | *Co-operative* | 31 |

## ለ


| | | |
|---|---|---|
| ለውጥ | *Change* | 33 |
| ለዘብተኛነት | *Liberalism* | 33 |
| ሉዓላዊነት | ***Sovereignty*** | 34 |
| ላ ሚትሪ ፣ ዡሊየ እፍሯ ደ | *La Mettrie, Julien Offroy de* | 34 |
| ላሳሊዝም | *Lassallism* | 35 |
| ላዕላይ መዋቅር | *Superstructure* | 35 |
| ላይብኒትዝ ፣ ጐትፍሪድ ቪልሄልም | *Leibniz, Gottfried Wilhelm* | 36 |
| ሌሴፌር | *Laissez-Faire* | 37 |
| ሌኒኒዝም | *Leninism* | 38 |
| ሌኒናዊ የፓርቲ ሕይወት ድንጋጌዎች | *Leninist Standards of Party Life* | 39 |
| ሌኒን ፣ ቭላድሚር ኢሊች | **Lenin, Vladimir Ilyich** | 39 |
| ልምድ | *Experience* | 40 |
| ልሳን | *Organ* | 40 |
| ልቡና | *Psyche* | 40 |
| ልባዊ | *Perception* | 41 |
| ልብወለዳዊነት | *Romanticism* | 41 |
| ልውውጥ | *Exchange* | 41 |
| ልውውጥ እሴት (የ—) | *Exchage Value* | 42 |
| ልዩነት ኪራይ (የ—) | *Differential Rent* | 43 |
| ልዩና ሁለንታዊ | *Particular and Universal* | 44 |
| ሎክ ፣ ጆን | ***Locke, John*** | 45 |


## መ


| | | |
|---|---|---|
| መላምት | *Hypothesis* | 45 |
| መልማት ላይ ያሉ ሀገሮች (በ—) | *Developing Countries* | 46 |
| መሠረተ ልማት | *Infrastructure* | 47 |
| መሠረታዊ ቅራኔ | *Basic Cantradiction* | 48 |
| መሠረታዊና ኢመሠረታዊ መደቦች | *Basic and Non-Basic Classes* | 49 |

| | | |
|---|---|---|
| መሠረታዊ ፍላጐቶች | *Basic Necessities* | 49 |
| መሠረት (ታህታይ መዋቅር) | | 50 |
| መሠረትና ላዕላይ መዋቅር | *Basis and Superstructure* | 50 |
| መስተጋብር | *Interaction* | 51 |
| መስተጋብአዊ ሥነ አመክንዮ | *Inductive Logic* | 52 |
| መሪር | *Tragic* | 53 |
| መሬት ከበርቴ (የ—) | *Landlord* | 53 |
| መብትና ግዴታ | *Right and Duty* | 53 |
| መንሥኤና ሁኔታ | *Cause and Condition* | 54 |
| መን ፣ ቶማስ | *Mun, Thomas* | 55 |
| መንሥኤና ተገብሮት | *Cause and Effect* | 55 |
| መንደርደሪያና ክትያ | *Ground and Consequence* | 56 |
| መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም | *State Monopoly Capitalism* | 56 |
| መንግሥታዊ ሶሻሊዝም | *State Socialism* | 58 |
| መንግሥታዊ ካፒታሊዝም | *State Capitolism* | 58 |
| መንግሥታዊ ዱማ | *State Duma* | 60 |
| መንግሥት | *State* | 60 |
| መንግሥት በጀት (በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም) (የ—) | *State Budget (Under capitalism and Socialism)* | 61 |
| መንፈሳዊነት | *Spiritualism* | 62 |
| መካከለኛ የኅብረተሰብ ክፍሎች | *Middle Strata* | 63 |
| መዋቅራዊነት | *Structuralism* | 63 |
| መደባዊ ንጽረት | *Class Outlook* | 64 |
| መደባዊ ፍልስፍና | *Class Philosophy* | 65 |
| መደብ | *Class* | 65 |
| መደብ ትግል (የ—) | *Class Struggle* | 66 |
| መደብ ንቃተ ኅሊና (የ—) | *Class Consciousness* | 67 |
| መደብ ዕብረት (የ—) | *Class Collaboration* | 67 |
| መድልዎ | *Segregation* | 67 |
| መጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት | *Primitive Accumulation of Capital* | 68 |
| መገንጠል | *Secession* | 69 |

| | | |
|---|---|---|
| መጠን ለውጥ (የ—) | *Quantitative Change* | 70 |
| ከመጠን ወደ ዓይነት ከዓይነት ወደ መጠን ለውጥ ሕግ | *The Law of Transformation of Quantity into Quality and Vice Versa* | 70 |
| መፈብረክ | *Manufacture* | 71 |
| መፈንቅለ አገዛዝ | *Coup d'Etat* | 72 |
| መፈክር | *Slogan* | 72 |
| ሙአለንዋይ | *Investment* | 73 |
| ሙከራዊ ሳይንስ | *Experimental Science* | 73 |
| ሙያ ማኅበራት | *Professional Associations* | 73 |
| ሚል ፣ ጀምስ | *Mill, James* | 74 |
| ሚል ፣ ጆን ስትዋርት | *Mill, John Stuart* | 74 |
| ሚና | *Role* | 74 |
| ማኅበራዊ ሕግጋት | *Social Laws* | 75 |
| ማኅበራዊ ምርት ክፍል አንድና ክፍል ሁለት | *Department I ond Department II of Social Production* | 76 |
| ማኅበራዊ ትምክህተኛነት | *Social Chauvinism* | 76 |
| ማኅበራዊ ኑባሬ | *Social Being* | 76 |
| ማኅበራዊ ንቃተኅሊና | *Social Consciousness* | 77 |
| ማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ | *Socially Necessary Labour Time* | 78 |
| ማኅበራዊ አብዮት | *Social Revolution* | 78 |
| ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት | *Socio–Economic Formation(Social System)* | 79 |
| ማኅበራዊ ካፒታል | *Social Capital* | 80 |
| ማኅበራዊ ዲሞክራሲ | *Social Democracy* | 81 |
| ማኅበራዊ ዳርዊኒዝም | *Social Darwinism* | 82 |
| ማልባ | *"Malbo"* | 82 |
| ማልተስ ፣ ቶማስ ሮበርት | *Malthus, Thomas Robert* | 83 |
| ማመዛዘን ሥርዓት — በዕቅድ (የ—) | *System of Balance in Planning* | 84 |
| ማምረት | *Production* | 84 |
| ማምረቻ መሣሪያዎች (የ—) | *Instruments of Production* | 85 |

| | | |
|---|---|---|
| ማምረቻ ወጪ (የ—) | *Cost Price of Production* | 85 |
| ማርሻል ፥ አልፍሬድ | *Marshall, Alfred* | 86 |
| ማርክሲዝም | *Marxism* | 86 |
| ማርክሲዝም ሌኒኒዝም | *Marxism-Leninism* | 86 |
| ማርክስ ፥ ካርል | *Marx, Karl* | 87 |
| ማሽን ምርት (የ—) | *Machine Production* | 88 |
| ማኦ ትሴ-ቱንግ | *Mao Tse-tung* | 88 |
| ማዕቀብ | *Sanction* | 89 |
| ማኪያቬሊ ፥ ኒኮሎ ፥ ዲ ፥ ቤርናርዶ | *Machiavelli, Niccolo di Bernardo* | 89 |
| ማዘዋወሪያ ወጪ (የ—) | *Cost of Circulation* | 90 |
| ሜርካንቲሊዝም | *Mercantilism* | 90 |
| ሜንሼቪኮች | *Mensheviks* | 91 |
| ሜይ ዴይ | *May Day* | 91 |
| ምሁራን | *Intelligentsia* | 92 |
| ምርታማ ሥራ | *Productive Labour* | 93 |
| ምርት ኃይሎች (የ—) | *Productive Forces* | 93 |
| ምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች ዲያሌክቲክስ (የ—) | *Dialectics of Productive Forces and Relations of Production* | 94 |
| ምርት መገልገያዎች (የ—) | *Means of Production* | 95 |
| ምርት ሥርዓት አልባነት (የ—) | *Anarchy of Production* | 95 |
| ምርት ግንኙነት (የ—) | *Relations of Production* | 96 |
| ምትሃት | *Illusion* | 97 |
| ምናብ | *Imagination* | 98 |
| ምንነትና አይታ | *Essence and Appearance* | 98 |
| ምንዳ | *Wages* | 99 |
| ምንዳ ደረጃ አወሳሰን ሥርዓት በሶሻሊስት ሀገሮች (የ—) | *Grading System of Wages in Sociolist Countries* | 99 |
| ምንጪታዊ ሥነ አመክንዮ | *Deductive Logic* | 100 |
| ምክነያ | *Rationalization* | 101 |
| ምክኑያዊነት | *Rutionalism* | 101 |
| ሞር ፥ ቶማስ | *More, Thomas* | 102 |

| | | |
|---|---|---|
| ሞንትስኪየ ፣ ሻርል ደ | *Montesquieu, Charles de* | **102** |
| ሞኖፖል ትርፍ (የ—) | *Monopoly Profit* | **103** |
| ሞክሬቲየ ፣ አንቷን ደ | *Montchretien, Antoine de* | **103** |


## ሠ


| | | |
|---|---|---|
| ሠራተኛ ማኅበር (የ—) | *Trade Union* | **105** |
| ሠራተኛው መደብና የአርሶአደሩ ኅብረት (የ—) | *The Alliance of the Working Class and the Peasontry* | **106** |
| ሠርቶ አደር | *Working People* | **106** |
| ሥራ | *Labour* | **107** |
| ሥራ ኃይል (የ—) | *Labour Power* | **107** |
| ሥራ ኃይል የልውውጥ እሴት (የ—) | *Exchange Value of Labour Power* | **108** |
| ሥራ ኃይል የጠቀሜታ እሴት (የ—) | *Use Value of Labour Power* | **109** |
| ሥራ መገልገያዎች (የ—) | *Means of Labour* | **109** |
| ሥራ ማቆም አድማ (የ—) | *Strike* | **109** |
| ሥራ ማከናወኛዎች (የ—) | *Instruments of Labour* | **110** |
| ሥራ ምርታማነት (የ—) | *Productivity of Labour* | **110** |
| ሥራ ተገብሮች (የ—) | *Objects of Labour* | **111** |
| ሥራ እጥነት | *Unemployment* | **111** |
| ሥራ እምቀት (የ—) | *Intensity of Labour* | **112** |
| ሥራ ክፍፍል (የ—) | *Division of Labour* | **113** |
| ሥርዓት | *System* | **114** |
| ሥርዓት አልበኝነት | *Anarchism* | **114** |
| ሥርወ መንግሥት | *Dynasty* | **115** |
| ሥነ ልቡናዊ ዘይቤ | *Psychological Make-up* | **115** |
| ሥነ መለኮት | *Theology* | **115** |
| ሥነ ምግባር | *Ethics* | **116** |
| ሥነ ተረት | *Mythology* | **117** |

| | | |
|---|---|---|
| ሥነ ኑባሬ | *Onthology* | 117 |
| ሥነ አመክንዮ | *Logic* | 117 |
| ሥነ ዕውቀት | *Epistemology* | 118 |
| ሥነ ክስተት | *Phenomenology* | 119 |
| ሥነ ውበት | *Aesthetics* | 120 |
| ሥነ ግብ | *Teleology* | 121 |
| ሥነ ፋይዳ | *Axiology* | 122 |
| ሦስተኛው ኢንተርናሽናል | *The Third International* | 122 |
| ሦስቱ ጣምራ ጠላቶች | *The Triad Enemies* | 124 |


## ሰ


| | | |
|---|---|---|
| ሰላማዊ ሰልፍ | *Demonstration* | 125 |
| ሰላማዊ ሽግግር | *Peaceful Transition* | 125 |
| ሰላም አብሮ የመኖር መርህ (በ—) | *Peaceful Co-existence* | 126 |
| ሰላም አክራሪነት | *Pacifism* | 126 |
| ሰላም ውል (የ—) | *Non-Aggression Pact or Peace Treaty* | 127 |
| ሰላም ፕሮግራም (የ) | *Peace Programme* | 127 |
| ሰሜን አትላንቲክ ቃል ኪዳን ድርጅት (የ—) | *North Atlantic Treaty Organization (NATO)* | 128 |
| ሰርጎ ገብ | *Infiltrator* | 128 |
| ሰብእነት | *Personalism* | 129 |
| ሰብአዊ መብት | *Human Rights* | 129 |
| ሰብአዊነት | *Humanism* | 130 |
| ሰናይና እኩይ | *The Good and the Evil* | 131 |
| ሰን ሲሞን ፣ ክሎድ አንሪ | *Saint-Simon, Claude Henri* | 132 |
| ሰው | *Man* | 133 |
| ሰውኛነት | *Anthropomorphism* | 133 |
| ሱቦትኒክ | *Subbotnik* | 134 |
| ሲስሞንዲ ፣ ሲስሞንድ ደ | *Sismondi, Sismonde de* | 134 |

| | | |
|---|---|---|
| ሲኒየር ፣ ናሳው ዊሊያም | *Senior, Nassau William* | 135 |
| ሲንዲካሊዝም | *Syndicalism* | 136 |
| ሲንዲኬት | *Syndicate* | 136 |
| ሳርትር ፣ ዣን ፖል | *Sartre, Jean Paul* | 136 |
| ሳንሱር | *Censorship* | 136 |
| ሳይንሳዊ ርዕዮተዓለም | *Scientific Ideology* | 137 |
| ሳይንሳዊ ኮሚኒዝም | *Scientific Communism* | 137 |
| ሳይንሳዊ ዲያሌክቲክስ | *Scientific Dialectics* | 137 |
| ሳይንስነት | *Scientism* | 138 |
| ሴቶች ቀን (የ-) | *Women's Day (International Working Women's Day)* | 138 |
| ሴቶች ዓለምአቀፍ ዲሞክራቲክ ፌዴሬሽን (የ-) | *Women's International Democratic Federation* | 139 |
| ሴቶች ጥያቄ (የ-) | *Women's Question* | 139 |
| ሴይ ፣ ዣን ባቲስት | *Say. Jean Baptiste* | 140 |
| ስልተምርት | *Mode of Production* | 140 |
| ስሚዝ ፣ አዳም | *Smith, Adam* | 141 |
| ስማዊ ምንዳ | *Nominal Wages* | 142 |
| ስማዊነት | *Nominalism* | 143 |
| ስታሊን ፣ ጆሴፍ | *Stalin, Joseph* | 143 |
| ስታኽኖቪዝም | *Stakhanovism* | 144 |
| ስትራቴጂና ታክቲክ | *Strategy and Tactic* | 144 |
| ስትራቴጂያዊ የጦር መሣሪያ ቅነሳ ድርድር (ሶልት) | *Strategic Arms Limitation Talks (SALT)* | 145 |
| ስቶይሲዝም | *Stoicism* | 145 |
| ስፍራና ጊዜ | *Space and Time* | 146 |
| ስፒኖዛ ፣ ባሩክ | *Spinoza. Baruch* | 147 |
| ስፓርታኪስት (ስፓርታሲስት) | *Spartakist (Spartacist)* | 148 |
| ስፔንሰር ፣ ሄርበርት | *Spencer, Herbert* | 149 |
| ሶሻሊስታዊ የሥራ ውድድር | *Socialist Emulation* | 149 |
| ሶሻሊስት የሸቀጥ ምርት | *Socialist Commodity Production* | 150 |

| | | |
|---|---|---|
| ሶሻሊስት የአኗኗር ዘይቤ | *Socialist Way of Life* | 151 |
| ሶሻሊስት ሰብአዊነት | *Socialist Humanism* | 151 |
| ሶሻሊስት ንብረት | *Socialist Property* | 152 |
| ሶሻሊስት አብዮታውያን | *Socialist Revolutionaries* | 153 |
| ሶሻሊስት አብዮት | *Socialist Revolution* | 153 |
| ሶሻሊስት ኢንተርናሽናል | *Socialist International* | 154 |
| ሶሻሊስት የኢኮኖሚ ዕቅድ | *Socialist Economic Planning* | 155 |
| ሶሻሊስት የኢኮኖሚ ጥምረት | *Socialist Economic Integration* | 156 |
| ሶሻሊስት እውንነት | *Socialist realism* | 156 |
| ሶሻሊስት ክምችት | *Socialist Accumulation* | 157 |
| ሶሻሊስት የክፍፍል መርህ (የ—) | *Principle of Socialist Distributian* | 158 |
| ሶሻሊዝም | *Socialism* | 158 |
| ሶቅራጥስ | *Socrates* | 160 |
| ሶቪዬት | *Soviet* | 160 |
| ሶቪዬት ኅብረት ኮሚኒስት ፓርቲ (የ—) | *Communist Party of the Soviet Union* | 162 |


## ረ


| | | |
|---|---|---|
| ረቂቅ ሥራ | *Abstract Labour* | 164 |
| ሩሶ ፣ ዣን ዣክ | *Rausseau, Jean-Jacques* | 164 |
| ሪካርዶ ፣ ዴቪድ | *Ricardo, David* | 165 |
| ሪፐብሊክ | *Republic* | 166 |
| ራስንቃተ ኅሊና | *Self-Consciousness* | 167 |
| ራሳዊነት | *Solipsism* | 167 |
| ራስን መቻል | *Self-Reliance* | 167 |
| ራስገዝነት | *Autonomy* | 168 |
| ርምደት | *Progress* | 168 |
| ርዕዮተዓለማዊ ትግል | *Ideological Struggle* | 169 |
| ርዕዮተዓለም | *Ideology* | 169 |

## ሸ


| | | |
|---|---|---|
| ሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር (የ—) | *Consumers' Co-operatives* | **171** |
| ሸቀጥ | *Commodity* | **172** |
| ሸቀጥ በሸቀጥ ለውጥ (የ—) | *Barter* | **172** |
| ሼሊንግ ፡ ፍሪድሪሽ ቪልሄልም | *Schelling, Friedrich Wilhelm* | **173** |
| ሽምቅ ውጊያ | *Guerrilla Warfore* | **174** |
| ሽረት ሽረት ሕግ (የ—) | *Law of Negation of the Negation* | **174** |
| ሽብር | *Terror* | **175** |
| ሽግግር ወቅት (የ—) | *Transition Period* | **175** |
| ሽፍን ተረፈ ሕዝብ | *Latent Surplus Population* | **177** |
| ሾፐንሀወር ፡ አርተር | *Schopenhour, Arthur* | **178** |


## ቀ


| | | |
|---|---|---|
| ቀላል ሥራ | *Simple (Unskilled) Labour* | **179** |
| ቀላል የሸቀጥ ምርት | *Simple Commodity Production* | **179** |
| ቀላል እርባታ | *Simple Reproduction* | **179** |
| ቀላል የካፒታሊስት ትብብር | *Simple Copitalist Co-operation* | **181** |
| ቀኖናዊነት | *Dogmatism* | **181** |
| ቀውስ | *Crisis* | **182** |
| ቀዝቃዛ ጦርነት | *Cold War* | **183** |
| ቀያጭነት | *Eclecticism* | **183** |
| ቀይ ጦር | *Red Army* | **183** |
| ቁስአካል | *Matter* | **184** |
| ቁስአካልነት | *Materialism* | **185** |
| ቁርጥ ሥራ ምንዳ (የ—) | *Piece—Wages* | **186** |
| ቅስቀሳ | *Agitation* | **186** |
| ቅስቃሴ (እንቅስቃሴ) | *Motion* | **187** |
| ቅስቃሴ ቅርፆች (የ—) | *Forms of Motion* | **188** |

| | | |
|---|---|---|
| ቅራኔ | *Contradiction* | 188 |
| ቅራኔ ሕግ (የ—) | *Law of Contradiction* | 189 |
| ቅራኔዎች ልዩነትና ሁለንታዊነት (የ—) | *Particularity and Universality of Contradictions* | 190 |
| ቅርፃዊ ሥነ አመክንዮ | *Formal Logic* | 190 |
| ቅርፃዊነት | *Formalism* | 191 |
| ቅኝ አገዛዝ | *Colonialism* | 191 |
| ቅኝ ግዛት | *Colony* | 191 |
| ቋሚ ካፒታል | *Constant Capital* | 192 |
| ቋንቋ | *Language* | 192 |


# በ


| | | |
|---|---|---|
| በርክሌይ ፣ ጆርጅ | *Berkeley, George* | 193 |
| በርግሰን ፣ አንሪ | *Bergson, Henri* | 194 |
| ቡርዧዚ | *Bourgeoisie* | 195 |
| ቡርዧ አብዮት (የ—) | *Bourgeois Revolutlon* | 196 |
| ቡንድ | *Bund* | 197 |
| ቡዋጊልቤር ፣ ፒየር | *Boisguillebert, Plerre* | 198 |
| ቢሮክራሲ | *Bureaucracy* | 199 |
| ባህላዊ ብሔራዊ ራስገዝነት | *Cultural-National Autonomy* | 200 |
| ባህል | *Culture* | 200 |
| ባህል አብዮት (የ—) | *Cultural Revolution* | 201 |
| ባህርዮት | *Substance* | 201 |
| ባለሞግዚት ግዛቶች | *Trusteeship Territories* | 202 |
| ቫልራ ፣ ሌዮ | *Walras, Leon* | 202 |
| ባበፍ ፣ ግራኩስ | *Babeuf, Gracchus* | 203 |
| ባንክ | *Bank* | 203 |
| ባንክ ትርፍ (የ—) | *Banker's Profit* | 204 |
| ባንክ ኖት (የ—) | *Bank - Note* | 205 |

| | | |
|---|---|---|
| ቤከን ፣ ፍራንሲስ | *Bacon, Francis* | 205 |
| ብሔረሰብ | *Nationality* | 206 |
| ብሔረተኛነት | *Nationalism* | 206 |
| ብሔራዊ ሶሺሊዝም | *National Socialism* | 207 |
| ብሔራዊ ነፍስ ወከፍ ገቢ | *National Per Capita Income* | 208 |
| ብሔራዊ የአርነት ንቅናቄ | *National Liberation Movement* | 209 |
| ብሔራዊ ዕዳ | *National Debt* | 209 |
| ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት | *National Democratic Revolution* | 210 |
| ብሔራዊ ገቢ | *National Income* | 211 |
| ብሔራዊ ገቢ ክፍፍልና ዳግም ክፍፍል (የ—) | *Distribution and Redistribution of National Income* | 212 |
| ብሔር | *Nation* | 213 |
| ብሔር ትምክህተኛነት (የ—) | *National Chauvinism* | 213 |
| ብሔር ጥያቄ (የ—) | *National Question* | 214 |
| ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ | *Classical Political Economy* | 214 |
| ብላንኪ ፣ ሉዊ ኦጊዩስት | *Blanqui, Louis Auguste* | 217 |
| ብላንኪዝም | *Blanquism* | 217 |
| ብዝበዛ | *Exploitation* | 218 |
| ብያኔ | *Judgement* | 218 |
| ብይትውርና | *Alienation* | 219 |
| ብድር ካፒታል (የ—) | *Loan Capital* | 219 |
| ቦልሼቪክ | *Bolshevik* | 220 |
| ቦም-ባዌርክ ፣ ኦይገን | *Böhm-Bawerk, Eugen* | 221 |


## ተ


| | | |
|---|---|---|
| ተለዋዋጭ ካፒታል | *Variable Capital* | 222 |
| ተግልሎአዊነት | *Mysticism* | 222 |
| ተምህርነት | *Scholasticism* | 222 |
| ተምኔታዊ ሶሺሊዝም | *Utopian Socialism* | 223 |

| | | |
|---|---|---|
| ተስፋፋ የእሴት መልክ (የ—) | *Extended Form of Value* | 224 |
| ተስፋፋ እርባታ (የ—) | *Extended Reproduction* | 224 |
| ትርፍ ምርት | *Surplus Production* | 227 |
| ትርፍ ሥራ | *Surplus Labour* | 228 |
| ትርፍ እሴት | *Surplus Value* | 229 |
| ትርፍ እሴት መጣኔ (የ—) | *Rate of Surplus Value* | 229 |
| ትርፍ እሴት እከብ (የ—) | *Mass of Surplus Value* | 230 |
| ተራማጅ | *Progressive* | 230 |
| ተቃራኒዎች አንድነትና ትግል ሕግ (የ—) | *The Law of the Unity and Struggle of Opposites* | 230 |
| ተቃርኖ | *Antithesis* | 232 |
| ተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (የ—) | *United Nations Organization* | 232 |
| ተባበሩት መንግሥታት ፀጥታ ምክር ቤት (የ—) | *United Nations Security Council* | 233 |
| ተናሥእት | *Uprising* | 234 |
| ተናክእታዊ ቁስአካልነት | *Mechanical Materialism* | 234 |
| ተንገዋላይ ትርፍ ሕዝብ | *Floating Surplus Population* | 235 |
| ተዘዋዋሪ ካፒታል | *Circulating Capital* | 236 |
| ተግባር | *Practice* | 236 |
| ተጣራ የማዟዟሪያ ወጪ (የ—) | *Net or Genuine Cost of Circulation* | 236 |
| ተጨማሪ የማዟዟሪያ ወጪ | *Additional Cost of Circulation* | 237 |
| ተጨማሪ ትርፍ እሴት | *Extra Surplus Value* | 237 |
| ተጨባጫዊነት | *Positivism* | 238 |
| ተጨባጭ ሥራ | *Concrete Labour* | 239 |
| ተፃራሪና ኢተፃራሪ ቅራኔዎች | *Antagonistic and Non-Antagonistic Contradictions* | 239 |
| ተፈጥሮ ሕግጋት (የ—) | *Natural Laws* | 239 |
| ተፈጥሮአዊነት | *Naturalism* | 240 |
| ተፈጥሮአዊ ኢኮኖሚ | *Natural Economy* | 241 |
| ቱርጐ ፣ ሮቤር ዣክ | *Turgot, Robert Jacques* | 241 |
| ቱጃሮች ምስፍና (የ—) | *Oligarchy* | 242 |
| ታህታይ መዋቅር | *Basis* | 242 |
| ታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት | *The Great October Socialist Revolution* | 242 |

| | | |
|---|---|---|
| ታሪካዊ ቁስአካልነት | *Historical Materialism* | 243 |
| ታሪክነት | *Historicism* | 243 |
| ታሪክ ፍልስፍና (የ—) | *Philosophy of History* | 244 |
| ቴክኒካዊ የካፒታል ጥንቅር | *Technical Composition of Capital* | 244 |
| ቴክኖሎጂ አብዮት (የ—) | *Technological Revolution* | 244 |
| ቴይለሪዝም | *Toylorism* | 245 |
| ትላልቅ ኢንዱስትሪዎችና ትናንሽ ኢንዱስትሪዎች | *Large-Scale Industries and Small Scale Industries* | 246 |
| ትረስት | *Trust* | 246 |
| ትርፍ | *Profit* | 246 |
| ትርፍ መጣኔ(የ—) | *Rate of Profit* | 247 |
| ትርፍ ክፍያ | *Profit Sharing* | 248 |
| ትሮትስኪዝም | *Trotskyism* | 248 |
| ትንታኔ | *Analysis* | 249 |
| ትንኮሳ | *Provocaticn* | 250 |
| ትግል | *Struggle* | 250 |
| ቶሚዝም | *Thomism* | 250 |


# ቸ


| | | |
|---|---|---|
| ቻርቲስት ንቅናቄ (የ—) | *Chartist Movement* | 252 |
| ችርቻሮ ንግድ (የ—) | *Retail Trade* | 253 |


# ነ


| | | |
|---|---|---|
| ነባራዊ | *Objective* | 254 |
| ነባራዊ ሁኔታ | *Objective Condition* | 254 |
| ነባራዊ ሐሳባዊነት | *Objective Idealism* | 255 |
| ነባራዊነት | *Objectivism* | 255 |
| ነባራዊ እውነት | *Objective Trtuh* | 256 |

| | | |
|---|---|---|
| ነባራዊ ዕውቀት | *Objective Knowledge* | 257 |
| ነባር ካፒታል | *Fixed Capital* | 258 |
| ነገድ | *Tribe* | 258 |
| ነጭ ዋርድዮች | *White Guards* | 259 |
| ነጸሮት | *Contemplation* | 259 |
| ነፀብራቅ | *Reflection* | 259 |
| ነፃነት | *Freedom* | 260 |
| ነፃነትና ግዴታ | *Freedom and Necessity* | 261 |
| ነፃዊነት | *Liberalism* | 261 |
| ነፃ ውድድር | *Free Competition* | 262 |
| ነፍሳዊነት | *Animism* | 263 |
| ኑባሬ | *Being* | 263 |
| ኒቼ ፡ ፍሪድሪሽ ቪልሄልም | *Nietzsche, Friedrich Wilehelm* | 263 |
| ኒውተን ፡ ይስሐቅ | *Newton, Isaac* | 264 |
| ናሮዲዝም | *Narodism* | 265 |
| ንቁ | *Conscious* | 265 |
| ንቃተኅሊና | *Consciousness* | 265 |
| ንዑስ ከበርቴ | *Petty Bourgeoisie* | 266 |
| ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀት | *Theoretical Knowledge* | 266 |
| ንድፈ ሐሳብ | *Theory* | 267 |
| ንጉሣዊ አገዛዝ | *Monarchy* | 268 |
| ንግድ ሚዛን (የ—) | *Balance of Trade* | 268 |
| ንግድ ትርፍ (የ—) | *Commercial Profit* | 269 |
| ንግድ ካፒታል (የ—) | *Commercial Capital* | 270 |
| ንጽረተ ዓለም | *World Outlook* | 271 |


## አ


| | | |
|---|---|---|
| አመክንዮ | *Reason* | 273 |
| አማተርነት | *Amaterishness* | 273 |
| አማኒነት | *Theism* | 273 |

| | | |
|---|---|---|
| አግዕከሎሰብነት | *Antropocentrism* | 274 |
| አማካይ ትርፍ | *Average Profit* | 274 |
| አምላከኛነት | *Deism* | 274 |
| አምልኮተ ሸቀጥ | *Fetishism of Commodities* | 274 |
| አምሳል | *Ideal* | 275 |
| አምስተኛ ረድፍ | *Fifth Column* | 276 |
| አምነስቲ ኢንተርናሽናል | *Amnesty International* | 276 |
| አሣቂ | *Comic* | 276 |
| አስመሳይ አብዮተኛ | *Pseudo-Revolutionary* | 277 |
| አስተምህሮ | *Doctrine* | 277 |
| አስተፃምሮ | *Synthesis* | 277 |
| አስታራቂነት | *Conciliationism* | 277 |
| አስፈላጊ ምርት | *Necessary Product* | 278 |
| አስፈላጊ ሥራ | *Necessary Labour* | 279 |
| አረብ ሊግ | *Arab League* | 279 |
| አረብ ሶሻሊዝም | *Arab Socialism* | 280 |
| አረቦን | *Bond* | 280 |
| አርስጣጣሊስ | *Aristotle* | 281 |
| አርሶ አደር | *Peasantry* | 283 |
| አርቅቆት | *Abstraction* | 283 |
| አርበኝነት | *Patriotism* | 283 |
| አሻንጉሊት | *Puppet* | 284 |
| አሻጥር | *Sabotage* | 284 |
| አቅርቦትና ፍላጐት | *Supply and Demand* | 284 |
| አቋም | *Stand* | 285 |
| አባዊ ሥርዓት | *Patriarchate* | 285 |
| አብርሆት | *Enlightenment* | 286 |
| አብዮተኛ | *Revolutionary* | 286 |
| አብዮታዊ ሁኔታ | *Revolutionary Conditions* | 286 |

| | | |
|---|---|---|
| አብዮታዊ ሽግግር | *Revolutionary Transition* | **287** |
| አብዮታዊ ዲሞክራሲ | *Revolutionary Democracy* | **287** |
| አብዮታዊ ጦር | *Revolutionary Army* | **289** |
| አብዮት | *Revolution* | **289** |
| አቶሚዝም | *Atomism* | **290** |
| አናርኮ ሲንዲካሊዝም | *Anarcho-Syndicalism* | **290** |
| አናክሲማንደር (የሚሌቱሱ) | *Anaximander of Miletus* | **291** |
| አናክሲሚኒስ (የሚሌቱሱ) | *Anaximenes of Miletus* | **291** |
| አንብሮ | *Thesis* | **292** |
| አንደበተኛነት | *Sophism* | **292** |
| አንደኛው ኢንተርናሽናል | *First International* | **293** |
| አንደኛ ደረጃ ቅራኔ | *Primary Contradiction* | **293** |
| አንዳዊነት | *Monism* | **294** |
| አንዱና ብዙው | *The One and the Multiple* | **294** |
| አንጃ | *Faction* | **294** |
| አንገብጋቢ ጥያቄ | *Burning Issue* | **295** |
| አንፃራዊ ተረፈ እሴት | *Relative Surplus Value* | **295** |
| አንፃራዊነት | *Relativism* | **295** |
| አንፃራዊ ነፃነት | ***Relative Independence*** | **296** |
| አንፃራዊ የኑሮ ሁኔታ ቁርቁዝና | *Relative Impoverishment* | **297** |
| አንፃራዊ የእሴት መልክ | *Relative Form of Value* | **298** |
| አንፃራዊና ፍጹማዊ እውነት | *Relative and Absolute Truth* | **298** |
| አኩዊናስ፣ ቶማስ | *Aquinas, Thomas* | **299** |
| አክሲዮን | *Share* | **300** |
| አክሲዮን ክፍያ (የ—) | *Dividend* | **300** |
| አክሲዮን ገበያ (የ—) | *Stock Exchange* | **300** |
| አውሮፓ ኢኮኖሚ ማኅበር (የ—) | *European Economic Community* (EEC) | **301** |
| አውቶኖሚ (ራስ ገዝነት) | *Autonomy* | **302** |
| አውዳሚነት | *Nihilism* | **302** |
| አውጠንጣኝ ፍልስፍና | *Speculative Philasophy* | **303** |

| | | |
|---|---|---|
| አዝጋሚ ለውጥ | *Evolution* | **303** |
| አዲሱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ | *The New Economic Policy (NEP)* | **303** |
| አዲሱ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት | *The New International Economic Order* | **304** |
| አድኀሪ | *Reactionary* | **305** |
| አድራጊ — ተደራጊ | *Subject-Object* | **305** |
| አድራጐታዊነት | *Behaviourism* | **306** |
| አድርባይነት | *Opportunism* | **307** |
| አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበር (የ—) | *Service Co-operatives* | **307** |
| አጓዳኝነት | *Parallelism* | **308** |
| አጠቃላይ ማኅበራዊ ምርትን የማጣራት ችግር | *Problems of Realization of Gross Social Product* | **309** |
| አጠቃላይ (ሁለንታዊ) የእሴት መልክ | *General (Universal) Form of Value* | **310** |
| አፍላጦን | *Plato* | **310** |
| አፍሪካ ሶሻሊዝም (የ—) | *African Socialism* | **312** |
| አፍሪካ አንድነት ድርጅት (የ—) | *Organization Of African Unity (OAU)* | **312** |
| አፍሪካና እስያ ሕዝቦች አንድነት ድርጅት (የ—) | *Afro-Asian Peoples Solidarity Organization* | **313** |
| አፓርታይድ | *Apartheid* | **314** |
| ኢመሠረታዊ ቅራኔ | *Non basic Contradictions* | **314** |
| ኢመደባዊ ፍልስፍና | *Non-Class Philosophy* | **315** |
| ኢምርታዊ ሥራ | *Non-Productive Labour* | **315** |
| ኢምክኑያዊነት | *Irrationalism* | **316** |
| ኢምፔሪያሊዝም | *Imperialism* | **316** |
| ኢሰብአዊ ጭፍጨፋ | *Genocide* | **319** |
| ኢስክራ | *Iskra* | **319** |
| ኢታዋቂነት | *Agnosticism* | **320** |
| ኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን (የ—) | *Commission for Organizing The Party of the Working People of Ethiopia (COPWE)* | **321** |
| ኢንተርናሽዮናል (መዝሙር) | *International (Proletarian Hymn)* | **321** |

| | | |
|---|---|---|
| ኢንተርፕራይዝ | *Enterprise* | 232 |
| ኢንተርፕራይዝ ትርፍ (የ—) | *Enterprise Profit* | 322 |
| ኢንዱስትሪ ተጠባባቂ ሠራዊት (የ—) | *Industrial Reserve Army* | 323 |
| ኢንዱስትሪ አብዮት (የ—) | *Industrial Revolution* | 323 |
| ኢንዱስትሪ ካፒታል (የ—) | *Industrial Capital* | 324 |
| ኢእማኒነት | *Atheism* | 325 |
| ኢእኩያዊ ልውውጥ | *Unequal Exchange* | 326 |
| ኢካፒታሊስታዊ የዕድገት ፈለግ | *Non-Capitalist Way of Development* | 327 |
| ኢኮኖሚያዊ ሕግ | *Economic Law* | 329 |
| ኢኮኖሚያዊ ማዕቀብ | *Economic Sanction* | 330 |
| ኢኮኖሚያዊ ትግል | *Economic Struggle* | 330 |
| ኢኮኖሚዝም | *Economism* | 331 |
| ኤንግልስ ፣ ፍሬደሪክ | *Engels, Frederick* | 331 |
| ኤፊቆሮስ | *Epicurus* | 332 |
| እመርታ | *Leap* | 333 |
| እማዊ ሥርዓት | *Matriarcate* | 334 |
| እምነታዊነት | *Fideism* | 334 |
| እሳቤ | *Conception* | 334 |
| እሳቦት | *Thought* | 334 |
| እሴት | *Value* | 335 |
| እሴት ሕግ (የ—) | *Law of Value* | 335 |
| እሴት መልክ (የ—) | *Form of Value* | 336 |
| እሴት ጥንተ መልክ (የ—) | *Elementary Form of Value* | 336 |
| እርስ በርስ ጦርነት (የ—) | *Civil War* | 336 |
| እርባታ | *Reproduction* | 337 |
| እርካታ | *Complacency* | 337 |
| እንስታዊነት | *Feminism* | 338 |
| እኩልታነት | *Equalitarianism* | 338 |
| እኩያዊ የእሴት መልክ | *Equivalent Form of Value* | 339 |

| | | |
|---|---|---|
| እውነት | *Truth* | 339 |
| እውን | *Real* | 340 |
| እውን ምንዳ | *Real Wages* | 340 |
| እውንነት | *Realism* | 341 |
| እደጥበብ ባለሙያዎች እምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበር (የ—) | *Handicraft Producers' Co-Operatives* | 341 |
| እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ | *Neo-Colonialism* | 342 |
| እግዚእብሔር | *God* | 343 |
| እግዚእብሔር ህልውና ማረጋገጫዎች(የ—) | *Proofs of the existence of God* | 344 |
| እግዳት | *Stagnation* | 345 |
| እግድ ተረፈ ሕዝብ | *Stagnant Surplus Population* | 345 |
| ኦውን ፣ ሮበርት | *Owen, Robert* | 345 |


# ዐ


| | | |
|---|---|---|
| ዓለም ሂደተ እብዮት (የ—) | *World Revolutionary Process* | 347 |
| ዓለም የመልሶ ግንባታና የልማት ባንክ (የ—) | *International Bank far Reconstruction and Development* | 347 |
| ዓለም ሠራተኞች ማኅበር ፌዴሬሽን (የ—) | *World Federation of Trade Unions* | 349 |
| ዓለም ሰላም ምክር ቤት (የ—) | *World Peace Council* | 349 |
| ዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት (የ—) | *World Socialist System* | 350 |
| ዓለምአቀፍ ሞኖፖል | *International Monopoly* | 351 |
| ዓለምአቀፍ የሥራ ክፍፍል (በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም) | *International Division of Labour (under Capitalism and Socialism)* | 353 |
| ዓለምአቀፍ ተማሪዎች ኅብረት (የ—) | *International Union of Students* | 354 |
| ዓለምአቀፍ የነፃ ሠራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን | *World Free Trade Union Confederation* | 354 |
| ዓለምአቀፍ ኮሚኒስት ንቅናቄ | *World Communist Movement* | 355 |
| ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት | *International Monetary Fund (IMF)* | 355 |
| ዓለም ዲሞክራሲያዊ ወጣቶች ፌዴሬሽን (የ—) | *World Federation of Democratic Youth* | 356 |
| ዓይነት ለውጥ (የ—) | *Qualitative Change* | 357 |
| ዕውቀት | *Knowledge* | 357 |
| ዕድገት | *Development* | 358 |

# ከ


| | | |
|---|---|---|
| ክላሽነት | *Revisionism* | 360 |
| ከባድ ኢንዱስትሪና ቀላል ኢንዱስትሪ | *Heavy Industry and Light Industry* | 361 |
| ከፊል ቅኝ ግዛት | *Semi-Colony* | 361 |
| ኩላክ | *Kulak* | 361 |
| ኪርከጋርድ ፣ ሰረን | *Kierkegard, Sören* | 362 |
| ኪነ ጥበብ | *Art* | 363 |
| ኬኔ ፣ ፍራንሷ | *Quesnay, François* | 363 |
| ካምፓኔላ ፣ ቶማሶ | *Campanella, Tommaso* | 364 |
| ካርቴል | *Cartel* | 364 |
| ካርቴዢያኒዝም | *Cartesianism* | 364 |
| ካንሺያኒዝም | *Kantianism* | 366 |
| ካንት ፣ አማኑኤል | *Kant, Immanuel* | 368 |
| ካዴት | *Cadet* | 368 |
| ካድሬ | *Cadre* | 369 |
| ካፒታሊስታዊ የመሬት ኪራይ | *Capitalist Ground Rent* | 369 |
| ካፒታሊስታዊ የሸቀጥ ምርት | *Capitalist Commodity Production* | 369 |
| ካፒታሊስታዊ ዱቤ | *Capitalist Credit* | 370 |
| ካፒታሊስት ሞኖፖሎች | *Capitalist Monopolies* | 370 |
| ካፒታሊዝም | *Capitalism* | 371 |
| ካፒታሊዝም ያልተመጣጠነ የዕድገት ሕግ (የ—) | *Law of Uneven Development of Capitalism* | 373 |
| ካፒታሊዝም ኢኮኖሚያዊ ቀውስ (የ—) | *Economic Crisis of Capitalism* | 374 |
| ካፒታል | *Capital* | 375 |
| ካፒታል መማከል (የ—) | *Centralization of Capital* | 376 |
| ካፒታል መሰባሰብ (የ—) | *Concentration of Capital* | 377 |
| ካፒታል መገላበጥ (የ—) | *Turn-over of Capital* | 378 |
| ካፒታል ክምችት (የ—) | *Accumulation of Capital* | 378 |
| ካፒታል ዙረት (የ—) | *Circuit of Capital* | 380 |

| | | |
|---|---|---|
| ኬይንስ ፣ ጆን ሜይናርድ | *Keyness, John Maynard* | 381 |
| ክላሎታዊነት | *Protectionism* | 382 |
| ክላርክ ፣ ጆን ቤትስ | *Clark, John Bates* | 383 |
| ክስተታዊነት | *Phenomenalism* | 383 |
| ክስተት | *Phenomenon* | 383 |
| ክርስቲያን ሶሻሊዝም | *Christian Socialism* | 384 |
| ክፍያ ሚዛን (የ—) | *Balance of Payments* | 384 |
| ኮመንዌልዝ | *Commonwealth* | 385 |
| ኮሚሳር | *Commissar* | 385 |
| ኮሚሽን | *Commission* | 385 |
| ኮሚኒስት | *Communist* | 386 |
| ኮሚኒስት ሊግ | *Communist League* | 386 |
| ኮሚኒስት ማኒፌስቶ | *Communist Manifesto* | 387 |
| ኮሚኒስት ክፍፍል መርህ (የ—) | *Principle of Communist Distribution* | 388 |
| ኮሚኒዝም | *Communism* | 388 |
| ኮሚንፎርም | *Comminform* | 389 |
| ኮሚዩናርድ | *Communard* | 389 |
| ኮምሶሞል | *Komsomol* | 390 |
| ኮስሞፖሊታኒዝም | *Cosmopolitanism* | 390 |
| ኮርፖሬሽን | *Corporation* | 391 |
| ኮርፖሬት መንግሥት (የ—) | *Corporate State* | 392 |
| ኮንሰርን | *Concern* | 392 |
| ኮንት ፣ ኦገስት | *Comt. August* | 393 |
| ኮንዲያክ ፣ ኤትየን ቦኖ ደ | *Condillac, Etienne Bonnlt de* | 393 |
| ኮንፉሺያኒዝም | *Confucianism* | 394 |
| ኮንፌዴሬሽን | *Confederation* | 394 |


## ወ


| | | |
|---|---|---|
| ወለድ | *Interest* | 395 |
| ወለድ መጣኔ (የ—) | *Rate of Interest* | 395 |

| | | |
|---|---|---|
| ወላንድ | Weland | 396 |
| ወልባ | Welba | 396 |
| ወሳኛዊነት | Determinism | 397 |
| ወረቀት ገንዘብ (የ—) | Paper Money | 397 |
| ወዝአደሩ የበላይ ገዥነት (የ—) | Dictatorship of the Proletariat | 398 |
| ወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት | Proletarian Internationalism | 399 |
| ወዝአደር | Proletariat | 400 |
| ወዝአደር መሣፍንት (የ—) | Labour Aristocrats | 401 |
| ወገናዊነት | Partisanship | 402 |
| ወግአጥባቂ (ቡርዧ) ሶሻሊዝም | Conservative or Bourgeois Socialism | 403 |
| ወጣት አጥፊነት (የ—) | Juvenile Delinquency | 403 |
| ወጪ ንግድ | Export Trade | 403 |
| ወጪና የገቢ ማወዳደሪያ ሒሳብ (የ—) | Cost Accounting | 404 |
| ዋርሶ ቃልኪዳን ድርጅት (የ—) | Warsaw Pact | 404 |
| ዋንኛና መለስተኛ ባሕርያት | Primary and Secondary Qualities | 405 |
| ዋጋ | Price | 405 |
| ዋጋ ርግበት (የ—) | Deflation | 407 |
| ዋጋ ንረት (የ—) | Inflation | 407 |
| ውል | Treaty | 408 |
| ውስብስብ ሥራ | Complex or skilled Labour | 409 |
| ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር | Organic Composition of Capital | 409 |
| ውስጣዊና ውጫዊ ቅራኔዎች | Internal and External Contradictions | 410 |
| ውበት | Beauty | 410 |
| ውዥንብር | Confusion | 411 |
| ውጪ ምንዛሪ (የ—) | Foreign Exchange | 411 |
| ውጪ ንግድ (የ—) | Foreign Trade | 411 |

## ዘ

| | | |
|---|---|---|
| ዘረኛነት | *Racism* | **413** |
| ዝቅጠት | *Depression* | **414** |

## የ

| | | |
|---|---|---|
| ዩሮ — ኮሚኒዝም | *Euro-Communism* | **415** |
| ዩኒቨርስ | *Universe* | **416** |
| ይስሙላ ካፒታል (የ—) | *Fictitious Capital* | **416** |
| ይዘትና ቅርፅ | *Content and Form* | **416** |

## ደ

| | | |
|---|---|---|
| ደመነፍስ | *Instinct* | **418** |
| ደምሳሽነት | *Liquidationism* | **418** |
| ደብተራዊነት | *Clericalism* | **418** |
| ዲሞቅሪጦስ (የአብደራው) | *Democritus of Abdera* | **419** |
| ዲሞክራሲ | *Democracy* | **419** |
| ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት | *Democratic Centralism* | **420** |
| ዲሲፕሊን | *Discipline* | **422** |
| ዲበአካል | *Metaphysics* | **422** |
| ዲያሌክቲካዊ ሥነ አመክንዮ | *Dialectical Logic* | **423** |
| ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት | *Dialectical Materialism* | **424** |

| | | |
|---|---|---|
| ዲያሌክቲክስ | *Dialectics* | 424 |
| ዲያሌክቲክስ ሕግ (የ—) | *Law of Dialectics* | 425 |
| ዲያሌክቲክስ ሕጎች (የ—) | *Dialectical Laws* | 426 |
| ዲደሮ ፣ ደኒ | *Diderot, Denis* | 426 |
| ዳሰሳዊ ዕውቀት | *Empirical Knowledge* | 427 |
| ዳሳሽነት | *Empiricism* | 427 |
| ዳርዊኒዝም | *Darwinism* | 429 |
| ዳርዊን ፣ ቻርለስ ሮበርት | *Darwin, Charles Robert* | 429 |
| ዳበረ ሶሻሊዝም (የ—) | *Developed Socialism* | 430 |
| ዴታንት | *Dètente* | 430 |
| ዴካርት ፣ ሬኔ | *Descartes, Rene* | 431 |
| ድምፅን በድምፅ የመሻር ሥልጣን | *Veto Power* | 431 |
| ድራት | *Boom* | 431 |
| ድርድር | *Compromise* | 432 |
| ድርጅት | *Organization* | 432 |
| ዶሚንየን | *Dominion* | 433 |


## ጀ


| | | |
|---|---|---|
| ጀምስ ፣ ዊልያም | *James, William* | 434 |
| ጀርመን ወይም እውነተኛው ሶሻሊዝም (የ—) | *German or "True" Socialism* | 434 |
| ጀርመን ብሉይ ፍልስፍና (የ—) | *The German Classical Philosophy* | 435 |
| ጀብደኝነት | *Adventurism* | 435 |
| ጁንታ | *Junta* | 435 |
| ጀቮንስ ፣ ዊሊያም ስታንሊ | *Jevons, William Stanley* | 436 |
| ጅምላ ንግድ | *Wholesale Trade* | 436 |


## ገ


| | | |
|---|---|---|
| ገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄ (የ—) | *Non-Aligned Movement* | 438 |
| ገለልተኛ ማድረግ | *Neutralize* | 439 |

| | | |
|---|---|---|
| ገበሬ | *Peasantry* | 439 |
| ገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር (የ—) | *Peasant Producers' Co-operatives* | 439 |
| ገቢራዊነት | *Pragmatism* | 440 |
| ገቢ ንግድ | *Import Trade* | 441 |
| ገንዘባዊ የእሴት መልክ | *Money Form of Value* | 442 |
| ገንዘብ | *Money* | 443 |
| ገንዘብ ምንዛሪ ዋጋ ቅነሣ (የ—) | *Devaluation* | 446 |
| ገንዘብ ምንዛሪ ዋጋ ጭመራ (የ—) | *Revaluation* | 447 |
| ጊልድ | *Guild* | 448 |
| ጊልድ ሶሻሊዝም | *Guild Socialism* | 448 |
| ጊዜ ምንዳ (የ—) | *Time Wages* | 448 |
| ጋራ አመራር (የ—) | *Collective Leadership* | 449 |
| ጋራ አክሲዮን ኩባንያ (የ—) | *Joint-Stock Company* | 449 |
| ጋራ ኢኮኖሚ ተራድኦ ምክር ቤት (የ—) | *Council for Mutual Economic Assistance (CMEA)* | 450 |
| ግለሰብ | *Individual* | 451 |
| ግለሰብና ኅብረተሰብ | *Individual and Society* | 452 |
| ግለሰብ ንብረት በሶሻሊዝም (የ—) | *Personal Property Under Socialism* | 452 |
| ግለኝነት | *Individualism* | 453 |
| ግላዊ ካፒታል | *Individual Capital* | 453 |
| ግልብ ቁስአካልነት | *Vulgar Materialism* | 453 |
| ግልብ እውኑነት | *Näive Realism* | 454 |
| ግልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ | *Vulgar Political Economy* | 454 |
| ግልግል | *Arbitration* | 455 |
| "ግራ" ክንፍ ኮሚኒዝም | *"Left" Wing Communism* | 456 |
| ግብ | *Purpose* | 456 |
| ግብታዊነት | *Spontaneity* | 456 |
| ግብታዊ ዲያሌክቲክስ | *Spontanious Dialectics* | 457 |
| ግንባር | *Front* | 457 |

| | | |
|---|---|---|
| ግንባር ቀደም | *Vanguard* | 458 |
| ግንዛቤ | *Cognition* | 458 |
| ግዛተ አጼ | *Empire* | 458 |
| ግዴታና አጋጣሚ | *Necessity and Chance* | 458 |
| ግገማ | *Recovery* | 460 |
| ጉታ ፕሮግራም (የ—) | *Gotha Programme* | 460 |
| ጓድ | *Comrade* | 461 |

## ጠ

| | | |
|---|---|---|
| ጠርጣሪነት | *Skepticism* | 462 |
| ጠቀሜታ እሴት (የ—) | *Use Value* | 463 |
| ጠቃሚያዊነት | *Utilitarianism* | 463 |
| ጠቅላላ ማህበራዊ ምርት | *Gross Social Product* | 464 |
| ጠጋኝነት | *Reformism* | 465 |
| ጣልቃገብነት | *Interventionism* | 465 |
| ጥምር መንግሥት | *Coalition Government* | 465 |
| ጥምጥማዊ (ሙሻዙራዊ) ዕድገት | *Spiral Development* | 466 |
| ጥብቅ ሀገር | *Protectorate* | 466 |
| ጥናት ክበብ (የ—) | *Study Circle* | 466 |
| ጥገኛ ሀገር | *Client State* | 467 |
| ጦረኛነት | *Militarism* | 467 |
| ጦር መሣሪያ ቅነሳ (የ—) | *Disarmament* | 467 |
| ጦርነት | *War* | 468 |
| ጦርነት ኮሚኒዝም (የ—) | *War Communism* | 469 |

## ጨ

| | | |
|---|---|---|
| ጭልታ | *Intuition* | 470 |
| ጭልታዊነት | *Intuitionism* | 470 |
| ጭብጥ | *Concrete* | 470 |

## ጸ


| | | |
|---|---|---|
| ጸለምት መቶዎች | *Black Hundreds* | 472 |
| ጽናት አልበኝነት | *Philistinism* | 472 |
| ጽንሰ ሐሳብ | *Concept* | 472 |
| ጽንፋዊነት | *Extremism* | 473 |
| ጽዮናዊነት | *Zionism* | 473 |


## ፀ


| | | |
|---|---|---|
| ፀረ አብዮት | *Anti—Revolution* | 475 |
| ፀረ አይሁድነት | *Anti-Semitism* | 475 |
| ፀረ ኮሚኒዝም | *Anti—Communism* | 475 |


## ፈ


| | | |
|---|---|---|
| ፈረንሳይ ቁስአካልነት (የ—) (18ኛው ምዕተ ዓመት) | *French Materialism (18th Century–)* | 477 |
| ፈርጆች | *Categories* | 477 |
| ፈቃዳዊነት | *Voluntarism* | 478 |
| ፈቃድ | *Will* | 478 |
| ፈጠራ | *Creativity* | 479 |
| ፉሪየ ፣ ፍራንሷ-ማሪ-ሻርል | *Fourier, François-morie-charles* | 479 |
| ፊኸተ ፣ የሐን ጐቲሊብ | *Fichte, Johann Gottlieb* | 480 |
| ፊውዳሊዝም | *Feudalism* | 481 |
| ፊውዳላዊ የመሬት ኪራይ | *Feudol Ground Rent* | 482 |
| ፊውዳል ሶሻሊዝም | *Feudal Socialism* | 482 |
| ፊዚዮክራሲ | *Physiocracy* | 482 |
| ፋሺዝም | *Fascism* | 483 |
| ፋይናንስ ምስፍና (የ—) | *Financial Oligarchy* | 485 |

| | | |
|---|---|---|
| ፋይናንስ ካፒታል | *Finance Capital* | **486** |
| ፋይዳ | *Value* | **487** |
| ፌቢያን ሶሻሊዝም | *Fabian Socialism* | **487** |
| ፌዴሬሽን | *Federation* | **488** |
| ፍልስፍና | *Philosophy* | **489** |
| ፍልስፍና መሠረታዊ ጥያቄ (የ—) | *Fundamental Question of Philosophy* | **490** |
| ፍልስፍና ታሪክ (የ—) | *History of Philosophy* | **490** |
| ፍሮይድ ፣ ዚግመንድ | *Freud, Sigmund* | **491** |
| ፍንገጣ | *Deviation* | **492** |
| ፍጆታ | *Consumption* | **492** |
| ፍጆታ ምድብ (የ—) | *Consumption Fund* | **493** |
| ፍጹማዊ ሐሳብ | *Absolute Idea* | **494** |
| ፍጹማዊ ተረፈ እሴት | *Absolute Surplus Value* | **494** |
| ፍጹማዊነት | *Absolutism* | **495** |
| ፍጹማዊ የኑሮ ሁኔታ ቁርቁዝና | *Absolute Impoverishment* | **495** |
| ፍጹማዊ ኪራይ | *Absolute Rent* | **496** |
| ፎርዲዝም | *Fordism* | **496** |
| ፎኮይዝም | *Focoism* | **497** |
| ፎየርባህ ፣ ሉድቪግ | *Fouerbach, Ludwig* | **497** |


## ፐ


| | | |
|---|---|---|
| ፓሪስ ኮሚዩን | *Paris Commune* | **499** |
| ፓርቲ | *Party* | **500** |
| ፓርቲ መሠረታዊ ድርጅት (የ—) | *Party Primary Organization* | **501** |
| ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ (የ—) | *Party Central Committee* | **502** |
| ፓርቲ ደንብ (የ—) | *Party statute* | **503** |
| ፓርቲ ጉባኤ (የ—) | *Party Congress* | **503** |
| ፓርቲ ፍልስፍና (የ—) | *Party Philosophy* | **503** |

| | | |
|---|---|---|
| ፓርቲ ፕሮግራም (የ—) | *Party Programme* | 504 |
| ፓን አፍሪካኒዝም | *Pan-Africanism* | 504 |
| ፔቲ ፣ ዊሊያም | *Petty, William* | 506 |
| ፕሩዶን ፣ ፒየር ጆሴፍ | *Proudhon, Pierre Joseph* | 506 |
| ፕሮፓጋንዳ | *Propaganda* | 507 |
| ፖለቲካ | *Politics* | 508 |
| ፖለቲካዊ መሥመር (የ—) | *Political Line* | 509 |
| ፖለቲካዊ ሥልጣን (የ—) | *Political Power* | 509 |
| ፖለቲካ ቢሮ | *Political Bureau* | 509 |
| ፖለቲካዊ የሥራ ማቆም አድማ | *Political Mass Strike* | 510 |
| ፖለቲካዊ ትግል | *Political Struggle* | 510 |
| ፖለቲካዊ አብዮት | *Political Revolution* | 510 |
| ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ | *Political Economy* | 511 |
| ፖፑሊዝም | *Populism* | 512 |

## II. እንግሊዝኛ — አማርኛ

### A


| | | |
|---|---|---|
| *Absolute Idea* | ፍጹማዊ ሐሳብ | 494 |
| *Absolute Impoverishment* | ፍጹማዊ የኑሮ ሁኔታ ቁርቁዝና | 495 |
| *Absolute Rent* | ፍጹማዊ ኪራይ | 496 |
| *Absolute Surplus Value* | ፍጹማዊ ተረፈ እሴት | 494 |
| *Absolutism* | ፍጹማዊነት | 495 |
| *Abstraction* | አርቅቆት | 283 |
| *Abstract Labour* | ረቂቅ ሥራ | 164 |
| *Accumulation of Capital* | የካፒታል ክምችት | 378 |
| *Additional Cost of Circulation* | ተጨማሪ የማሧሧሪያ ወጪ | 237 |
| *Adventurism* | ጀብደኝነት | 435 |
| *Aesthetics* | ሥነ ውበት | 120 |
| *African Socialism* | የአፍሪካ ሶሻሊዝም | 312 |
| *Afro-Asian Peoples Solidarity Organization* | የአፍሪካና የእስያ ሕዝቦች አንድነት ድርጅት | 313 |
| *Agitation* | ቅስቀሳ | 186 |
| *Agnosticism* | ኢታዋቂነት | 320 |
| *Alienation* | ብይትውርና | 219 |
| *Alliance of the Working Class and the Peasantry* | የሠራተኛው መደብና የአርሶ አደሩ ኅብረት | 106 |
| *Amateurishness* | አማተርነት | 273 |
| *Amnesty International* | አምነስቲ ኢንተርናሽናል | 276 |
| *Analysis* | ትንታኔ | 249 |
| *Anarchism* | ሥርዓት አልበኝነት | 114 |
| *Anarchy of Production* | የምርት ሥርዓት አልባነት | 95 |
| *Anarcho-Syndicalism* | አናርኮ ሲንዲካሊዝም | 290 |
| *Anaximander of Miletus* | አናክሲማንደር የማሌቱሱ | 291 |
| *Anaximenes of Miletus* | አናክሲሚኒስ የማሌቱሱ | 291 |

| | | |
|---|---|---|
| *Animism* | ነፍሳዊነት | 263 |
| *Annexotion* | በኃይል መቀላቀል | 28 |
| *Antagonistic and Non Antagonistic Contradictions* | ተፃራሪና ኢተፃራሪ ቅራኔዎች | 239 |
| *Anti-Communism* | ፀረ ኮሚኒዝም | 475 |
| *Anti-Revolution* | ፀረ አብዮት | 475 |
| *Anti-Semitism* | ፀረ አይሁድነት | 475 |
| *Antithesis* | ተቃርኖ | 232 |
| *Anthropocentrism* | አማክሎሰብነት | 274 |
| *Anthropomorphism* | ሰውኛነት | 133 |
| *Apartheid* | አፓርታይድ | 314 |
| *Aquinas, Thomas* | አኩዊናስ ፣ ቶማስ | 299 |
| *Arab Leogue* | አረብ ሊግ | 279 |
| *Arab Socialism* | አረብ ሶሻሊዝም | 280 |
| *Arbitration* | ግልግል | 455 |
| *Aristocracy* | የኅሩያን ምስፍና | 30 |
| *Aristotle* | አርስጣጣሊስ | 281 |
| *Art* | ኪነጥበብ | 363 |
| *Association of Ideas* | የሐሳቦች ግጥምጥሞሽ | 17 |
| *Atheism* | ኢአማኒነት | 325 |
| *Atomism* | አቶሚዝም | 290 |
| *Autonomy* | አውቶኖሚ (ራስገዝነት) | 302 |
| *Average Profit* | አማካይ ትርፍ | 274 |
| *Axiology* | ሥነ ፋይዳ | 122 |


## B


| | | |
|---|---|---|
| *Babeuf, Gracchus* | ባበፍ ፣ ግራኩስ | 203 |
| *Bacon, Francis* | ቤከን ፣ ፍራንሲስ | 205 |
| *Balance of Payments* | የክፍያ ሚዛን | 384 |
| *Balance of Trade* | የንግድ ሚዛን | 268 |

| | | |
|---|---|---|
| *Bank* | ባንክ | 203 |
| *Bank Note* | የባንክ ኖት | 205 |
| *Bankers' Profit* | የባንክ ትርፍ | 204 |
| *Barter* | የሸቀጥ በሸቀጥ ለውጥ | 172 |
| *Basic Contradiction* | መሠረታዊ ቅራኔ | 48 |
| *Basic Needs (Necessities)* | መሠረታዊ ፍላጎቶች | 49 |
| *Basic and Non-Basic Classes* | መሠረታዊና ኢመሠረታዊ መደቦች | 49 |
| *Basis* | መሠረት | 50 |
| *Basis and Superstructure* | ታህታይና ላዕላይ መዋቅር | 50 |
| *Beauty* | ውበት | 410 |
| *Behaviourism* | አድራጎታዊነት | 306 |
| *Being* | ኑባሬ | 263 |
| *Bergson, Henri* | በርግሰን ፡ አንሪ | 194 |
| *Berkeley, George* | በርክሌይ ፡ ጆርጅ | 193 |
| *Black Hundreds* | ጸለምት መቶዎች | 472 |
| *Blanqui, Louis Auguste* | ብላንኪ ፡ ሉዊ አጊዩስት | 217 |
| *Blanquism* | ብላንኪዝም | 217 |
| *Böhm-Bawerk, Eugen* | ቦም-ባዌርክ ፡ ኦይገን | 221 |
| *Boisguillebert, Pierre* | ቡዋጊልቤር ፡ ፒየር | 198 |
| *Bolshevik* | ቦልሸቪክ | 220 |
| *Bond* | አረቦን | 280 |
| *Boom* | ድራት | 431 |
| *Bourgeoisie* | ቡርዧዚ | 195 |
| *Bourgeois Revolution* | የቡርዧ አብዮት | 196 |
| *Bund* | ቡንድ | 197 |
| *Bureaucracy* | ቢሮክራሲ | 199 |
| *Burning Issue* | አንገብጋቢ ጥያቄ | 295 |

# C


| | | |
|---|---|---|
| *Cadet* | ካዴት | 368 |
| *Cadre* | ካድሬ | 369 |
| *Campanella, Tommaso* | ካምፓኔላ ፣ ቶማሶ | 364 |
| *Capitol* | ካፒታል | 375 |
| *Capitalism* | ካፒታሊዝም | 371 |
| *Capitalist Commodity Production* | ካፒታሊስታዊ የሸቀጥ ምርት | 369 |
| *Capitalist Credit* | ካፒታሊስታዊ ዱቤ | 370 |
| *Capitalist Grbund Rent* | ካፒታሊስታዊ የመሬት ኪራይ | 369 |
| *Capitalist Monopolies* | ካፒታሊስት ሞኖፖሎች | 370 |
| *Cartel* | ካርቴል | 364 |
| *Cartesianism* | ካርቴዥያኒዝም | 364 |
| *Categories* | ፈርጆች | 477 |
| *Cause and Condition* | መንሥዔና ሁኔታ | 54 |
| *Cause and Effect* | መንሥዔና ተገብሮት | 55 |
| *Censorship* | ሳንሱር | 136 |
| *Centralization of Capital* | የካፒታል መማከል | 376 |
| *Change* | ለውጥ | 33 |
| *Chartist Movement* | የቻርቲስት ንቅናቄ | 252 |
| *Christian Socialism* | ክርስቲያን ሶሻሊዝም | 384 |
| *Circulating Capitol* | ተዘዋዋሪ ካፒታል | 236 |
| *Circuit of Capital* | የካፒታል ዙረት | 380 |
| *Civil War* | የእርስ በርስ ጦርነት | 336 |
| *Clandestine* | ኅቡዕ | 31 |
| *Clark, John Bates* | ክላርክ ፣ ጆን ቤትስ | 383 |
| *Class* | መደብ | 65 |
| *Class Collaboration* | የመደብ ዕብረት | 67 |
| *Class Consciousness* | የመደብ ንቃተ ኅሊና | 67 |
| *Class Outlook* | መደባዊ ንጽረት | 64 |
| *Class Philosophy* | መደባዊ ፍልስፍና | 65 |

| | | |
|---|---|---|
| *Class Struggle* | የመደብ ትግል | 66 |
| *Classical political Economy* | ብሉይ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ | 214 |
| *Clericalism* | ደብተራዊነት | 418 |
| *Client State* | ጥገኛ ሀገር | 467 |
| *Coalition Government* | ጥምር መንግሥት | 465 |
| *Cognition* | ግንዛቤ | 458 |
| *Cold War* | ቀዝቃዛ ጦርነት | 183 |
| *Collective Leadership* | የጋራ አመራር | 449 |
| *Colonialism* | ቅኝ አገዛዝ | 191 |
| *Colony* | ቅኝ ግዛት | 191 |
| *Comic* | አሳቂ | 276 |
| *Comminform* | ኮሚንፎርም | 389 |
| *Commercial Capitol* | የንግድ ካፒታል | 270 |
| *Commercial Profit* | የንግድ ትርፍ | 269 |
| *Commissar* | ኮሚሳር | 385 |
| *Commission* | ኮሚሽን | 385 |
| *Commission for Organizing The Party of the Working People of Ethiopia (COPWE)* | የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን (ኢሠፓአኮ) | 321 |
| *Commodity* | ሸቀጥ | 172 |
| *Commonwealth* | ኮመንዌልዝ | 385 |
| *Communard* | ኮሚዩናርድ | 389 |
| *Communism* | ኮሚኒዝም | 388 |
| *Communist* | ኮሚኒስት | 386 |
| *Communist League* | ኮሚኒስት ሊግ | 386 |
| *Communist Manifesto* | ኮሚኒስት ማኒፌስቶ | 387 |
| *Communist Party of the Soviet Union* | የሶቪዬት ኅብረት ኮሚኒስት ፓርቲ | 162 |
| *Complacency* | እርካታ | 337 |
| *Complex or Skilled Labour* | ውስብስብ ሥራ | 409 |

| | | |
|---|---|---|
| *Compromise* | ድርድር | 432 |
| *Comrade* | ጓድ | 461 |
| *Comte, Auguste* | ኮንት ፣ አጉስት | 393 |
| *Concentration of Capital* | የካፒታል መሰባሰብ | 377 |
| *Concept* | ጽንሰ ሐሳብ | 471 |
| *Conception* | አሳቤ | 334 |
| *Concern* | ኮንሰርን | 392 |
| *Conciliationism* | አስታራቂነት | 277 |
| *Concrete* | ጭብጥ | 470 |
| *Concrete Labour* | ተጨባጭ ሥራ | 239 |
| *Condillac, Etionne Bonnot de* | ኮንድያክ ፣ ኤትየን ቦኖ ደ | 393 |
| *Confederation* | ኮንፌዴሬሽን | 394 |
| *Confucianism* | ኮንፉሽያኒዝም | 394 |
| *Confusion* | ውዥንብር | 411 |
| *Conscience* | ኅሊና | 28 |
| *Conscious* | ንቁ | 265 |
| *Consciousness* | ንቃተኅሊና | 265 |
| *Conservative or Bourgeois Socialism* | ወግአጥባቂ ወይም ቡርዧ ሶሻሊዝም | 403 |
| *Constant Capital* | ቋሚ ካፒታል | 192 |
| *Constitution* | ሕገ መንግሥት | 23 |
| *Consumers' Co-operatives* | የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር | 171 |
| *Consumption* | ፍጆታ | 492 |
| *Consumption Fund* | የፍጆታ ምድብ | 493 |
| *Contemplation* | ነጽሮት | 259 |
| *Content and Form* | ይዘትና ቅርፅ | 416 |
| *Contradiction* | ቅራኔ | 188 |
| *Co-operatives* | የኅብረት ሥራ ማኅበራት | 31 |
| *Corporate State* | የኮርፖሬት መንግሥት | 392 |
| *Corporation* | ኮርፖሬሽን | 391 |

| | | |
|---|---|---|
| *Cosmopolitanism* | ኮስሞፖሊታኒዝም | 390 |
| *Cost Accounting* | የወጪና የገቢ ማወዳደሪያ ሒሳብ | 404 |
| *Cost of Circulation* | የማዟዟሪያ ወጪ | 90 |
| *Cost of Production* | የማምረቻ ወጪ | 85 |
| *Council for Mutual Economic Assistance (CMEA)* | የጋራ ኢኮኖሚ ተራድኦ ምክር ቤት | 450 |
| *Coup d'Etat* | መፈንቅለ አገዛዝ | 72 |
| *Creativity* | ፈጠራ | 479 |
| *Crisis* | ቀውስ | 182 |
| *Criticism and Self Criticism* | ሂስና ግለሂስ | 27 |
| *Cultural National Autonomy* | ባህላዊ ብሔራዊ ራስገዝነት | 200 |
| *Cultural Revolution* | ባህል አብዮት | 201 |
| *Culture* | ባህል | 200 |


# D


| | | |
|---|---|---|
| *Darwin, Charles Robert* | ዳርዊን ፣ ቻርልስ ሮበርት | 429 |
| *Darwinism* | ዳርዊኒዝም | 429 |
| *Deductive Logic* | ምንጨታዊ ሥነ አመክንዮ | 100 |
| *Deflation* | የዋጋ ርግበት | 407 |
| *Deism* | አምላክኛነት | 274 |
| *Demagogue* | ሐሳዊ መሢሀ | 17 |
| *Democracy* | ዲሞክራሲ | 419 |
| *Democratic Centralism* | ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት | 420 |
| *Democritus of Abdera* | ዲሞቅሪጦስ ፣ የአብደራው | 419 |
| *Demonstration* | ሰላማዊ ሰልፍ | 125 |
| *Department I and Department II of Social Production* | ማኅበራዊ ምርት ክፍል አንድና ክፍል ሁለት | 76 |
| *Depression* | ዝቅጠት | 414 |
| *Descartes, Rene´* | ዴካርት ፣ ሬኔ | 431 |

| | | |
|---|---|---|
| *Detente* | ዴ ታንት | 430 |
| *Determinism* | ወሳኛዊነት | 397 |
| *Devaluation* | የገንዘብ ምንዛሪ ዋጋ ቅነሳ | 446 |
| *Developed Socalism* | የዳበረ ሶሻሊዝም | 430 |
| *Developing Countries* | በመልማት ላይ ያሉ ሀገሮች | 46 |
| *Development* | ዕድገት | 358 |
| *Deviation* | ፍንገጣ | 492 |
| *Dialectical Logic* | ዲያሌክቲካዊ ሥነ አመክንዮ | 423 |
| *Dialectical Materialism* | ዲያሌክቲካዊ ቁስአካልነት | 424 |
| *Dialectical Laws* | የዲያሌክቲክስ ሕጎች | 426 |
| *Dialectics* | ዲያሌክቲክስ | 424 |
| *Dialectics of Productive Forces and Relations of Production* | የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች ዲያሌክቲክስ | 94 |
| *Dictatorship of the Proletariat* | የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት | 398 |
| *Diderot, Denis* | ዲደሮ ፣ ደኔ | 426 |
| *Die-hard* | ሐሳበ ግትር | 15 |
| *Differential Rent* | የልዩነት ኪራይ | 43 |
| *Disarmament* | የጦር መሣሪያ ቅነሳ | 467 |
| *Dlscipline* | ዲሲፕሊን | 422 |
| *Distribution and Redistribution of National Income* | የብሔራዊ ገቢ ክፍፍልና ዳግም ክፍፍል | 212 |
| *Dividend* | የአክስዮን ክፍያ | 300 |
| *Division of Labour* | የሥራ ክፍፍል | 114 |
| *Doctrine* | አስተምህሮ | 277 |
| *Dogmatism* | ቀኖናዊነት | 181 |
| *Dominion* | ዶሚኒዮን | 433 |
| *Dualism* | ሁለታዊነት | 3 |
| *Dynasty* | ሥርወ መንግሥት | 115 |

# E


| | | |
|---|---|---|
| *Ecclecticism* | ቀያጭነት | 183 |
| *Economic Crisis of Capitalism* | የካፒታሊዝም ኢኮኖሚያዊ ቀውስ | 374 |
| *Economic Laws* | ኢኮኖሚያዊ ሕጎች | 329 |
| *Economic Sanction* | ኢኮኖሚያዊ ማዕቀብ | 330 |
| *Economic Struggle* | ኢኮኖሚያዊ ትግል | 330 |
| *Economism* | ኢኮኖሚዝም | 331 |
| *Elementary* | | |
| *Form of Value* | የእሴት ጥንተ መልክ | 336 |
| *Empire* | ግዛተ አጼ | 458 |
| *Empirical Knowledge* | ዳሰሳዊ ዕውቀት | 427 |
| *Empiricism* | ዳሳሽነት | 427 |
| *Engels, Frederick* | ኤንግልስ፣ፍሬደሪክ | 331 |
| *Enlightenment* | እብርሆት | 286 |
| *Enterprise* | ኢንተርፕራይዝ | 322 |
| *Enterprise profit* | የኢንተርፕራይዝ ትርፍ | 322 |
| *Epicurus* | ኤፊቆር | 332 |
| *Epistemology* | ሥነ ዕውቀት | 118 |
| *Equalitarianism* | እኩልታነት | 338 |
| *Equivalent Form of Value* | እኩያዊ የእሴት መልክ | 339 |
| *Essence and Appearance* | ምንነትና እይታ | 98 |
| *Ethics* | ሥነ ምግባር | 116 |
| *Euro-Communism* | ዩሮ ኮሚኒዝም | 415 |
| *European Economic Community* | የአውሮፓ ኢኮኖሚ ማኅበር | 301 |
| *Evolution* | አዝጋሚ ለውጥ | 303 |
| *Exchange* | ልውውጥ | 41 |
| *Exchange Value* | የልውውጥ እሴት | 42 |
| *Exchange Value of Labaur Power* | የሥራ ኃይል የልውውጥ እሴት | 108 |

| | | |
|---|---|---|
| *Existentialism* | ሀልውናነት | 10 |
| *Experience* | ልምድ | 40 |
| *Experimental Science* | ሙከራዊ ሳይንስ | 73 |
| *Exploitation* | ብዝበዛ | 218 |
| *Export Trade* | ወጪ ንግድ | 403 |
| *Extended Form of Value* | የተስፋፋ የእሴት መልክ | 224 |
| *Extended Reproduction* | የተስፋፋ እርባታ | 224 |
| *Extra Surplus Value* | ተጨማሪ ተረፈ እሴት | 237 |
| *Extrenism* | ጽንፋዊነት | 473 |


# F


| | | |
|---|---|---|
| *Fabian Socialism* | ፌቢያን ሶሻሊዝም | 487 |
| *Faction* | እንጃ | 294 |
| *Fascism* | ፋሺዝም | 483 |
| *Federation* | ፌደሬሽን | 488 |
| *Feminism* | እንስታዊነት | 338 |
| *Fetishism of Cammodltles* | እምልኮተ ሸቀጥ | 274 |
| *Feudal Ground Rent* | ፊውዳላዊ የመሬት ኪራይ | 482 |
| *Feudalism* | ፊውዳሲ.ዝም | 481 |
| *Feudal Socialism* | ፊውዳል ሶሻሊዝም | 482 |
| *Fictitious Capital* | የይስሙላ ካፒታል | 416 |
| *Fideism* | እምነታዊነት | 334 |
| *Fifth Column* | አምስተኛ ረድፍ | 276 |
| *Finance Capital* | ፋይናንስ ካፒታል | 486 |
| *Finance Oligarchy* | የፋይናንስ ምስፍና | 485 |
| *Fichte, Johann Gattlieb* | ፊኽተ ፣ዮሐን ጎትሊብ | 480 |
| *First Internatianal* | አንደኛው ኢንተርናሽናል | 293 |
| *Fixed Capital* | ነባር ካፒታል | 258 |
| *Floating Surplus Populatian* | ተንገዋላይ ተረፈ ሕዝብ | 235 |

| | | |
|---|---|---|
| *Focoism* | ፎኮይዝም | 497 |
| *Fordism* | ፎርዲዝም | 496 |
| *Foreign Exchange* | የውጭ ምንዛሪ | 411 |
| *Foreign Trade* | የውጭ ንግድ | 411 |
| *Formalism* | ቅርፃዊነት | 191 |
| *Formal Logic* | ቅርፃዊ ሥነ አመክንዮ | 190 |
| *Form of Value* | የእሴት መልክ | 336 |
| *Forms of Motion* | የቅስቃሴ ቅርጾች | 188 |
| *Fouerbach, Ludwing* | ፎየርባህ ፣ ሎድቪግ | 497 |
| *Fourier, François-Marie-Charles* | ፉርየ ፣ ፍራንሷ ማሪ ሻርል | 479 |
| *Free Competition* | ነፃ ውድድር | 262 |
| *Freedom* | ነፃነት | 260 |
| *Freedom and Necessity* | ነፃነትና ግዴታ | 261 |
| *French Materialism of* 18*th Century* | የፈረንሣይ ቁስአካልነት (የ18ኛው ምዕት ዓመት) | 477 |
| *Front* | ግንባር | 457 |
| *Freud, Sigmund* | ፍሮይድ ፣ ዚግመንድ | 491 |
| *Fundamental Question of Philosophy* | የፍልስፍና መሠረታዊ ጥያቄ | 490 |


## G


| | | |
|---|---|---|
| *General (Universal) Form of value* | አጠቃላይ (ሁለንታዊ) የእሴት መልክ | 310 |
| *Genocide* | ኢሰብአዊ ጭፍጨፋ | 319 |
| *German Classical Philosophy* | የጀርመን ብሉይ ፍልስፍና | 435 |
| *German or «True» Socialism* | የጀርመን ወይም "እውነተኛው" ሶሻሊዝም | 434 |
| *God* | እግዚአብሔር | 343 |
| *Good and Evil* | ሰናይና እኩይ | 131 |
| *Gotha Programme* | የጎታ ፕሮግራም | 460 |

| | | |
|---|---|---|
| *Grading system of Wages in Socialist Countries* | የምንዳ ደረጃ አወሳሰን ሥርዓት በሶሻሊስት ሀገሮች | 99 |
| *Great October Socialist Revolution* | ታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት | 242 |
| *Gross Social Product* | ጠቅላላ ማኅበራዊ ምርት | 464 |
| *Ground and Consequence* | መንደርደሪያና ክትያ | 56 |
| *Guerrilla Warfare* | ሽምቅ ውጊያ | 174 |
| *Guild* | ጊልድ | 448 |
| *Guild Socialism* | ጊልድ ሶሻሊዝም | 448 |


# H


| | | |
|---|---|---|
| *Handicraft Producers' Co-operatives* | የዕደጥበብ አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት | 341 |
| *Heavy Industry and Light Industry* | ከባድ ኢንዱስትሪና ቀላል ኢንዱስትሪ | 361 |
| *Hegel, George Wilhelm* | ሄግል ፣ ጊዮርግ ቪልሄልም | 10 |
| *Hegelianism* | ሄግሊያኒዝም | 9 |
| *Helvetuis, Claude Adrien* | ሄልቬትዩስ ፣ ክሎድ አደርየን | 8 |
| *Heraclitus of Ephesus* | ሄራቅሊጦስ ፣ የኤፌሶኑ | 8 |
| *Hinduism* | ሂንዱይዝም | 4 |
| *Historical Materialism* | ታሪካዊ ቁስአካልነት | 243 |
| *Historicism* | ታሪካዊነት | 243 |
| *History of philosophy* | የፍልስፍና ታሪክ | 490 |
| *Hobbes, Thomas* | ሆብስ ፣ ቶማስ | 12 |
| *Ho chi minh* | ሆ ቺ ሚን | 13 |
| *Holbach, Paul Heneri Dietrieh* | ሆልባህ ፣ ፓውል ሄንሪ ዲትሪሽ | 12 |
| *Humanism* | ሰብአዊነት | 130 |
| *Human Rights* | ሰብአዊ መብት | 129 |

| | | |
|---|---|---|
| *Hume, David* | ሂዩም ፥ ዴቪድ | 5 |
| *Husserl, Edmund* | ሁሰርል ፥ ኤድመንድ | 4 |
| *Hypothesis* | መላምት | 46 |


# I


| | | |
|---|---|---|
| *Idea* | ሐሳብ | 16 |
| *Ideal* | አምሳል | 275 |
| *Idealism* | ሐሳባዊነት | 15 |
| *Idealist Dialectics* | ሐሳባዊ ዲያሌክቲክስ | 16 |
| *Idealogical Struggle* | ርዕዮተዓለማዊ ትግል | 169 |
| *Idealogy* | ርዕዮተዓለም | 169 |
| *Illusion* | ምትሀት | 97 |
| *Imagination* | ምናብ | 98 |
| *Imperialism* | ኢምፔሪያሊዝም | 316 |
| *Import Trade* | ገቢ ንግድ | 441 |
| *Individual* | ግለሰብ | 451 |
| *Individual and Society* | ግለሰብና ኅብረተሰብ | 452 |
| *Individual Capital* | ግላዊ ካፒታል | 453 |
| *Individualism* | ግለኝነት | 453 |
| *Inductive Logic* | መስተጋብአዊ ሥነ አመክንዮ | 52 |
| *Industrial Capital* | የኢንዱስትሪ ካፒታል | 324 |
| *Industrial Reserve Army* | የኢንዱስትሪ ተጠባባቂ ሠራዊት | 323 |
| *Industrial Revolution* | የኢንዱስትሪ አብዮት | 323 |
| *Infiltrator* | ሰርጎገብ | 128 |
| *Inflation* | የዋጋ ንረት | 407 |
| *Infrastructure* | መሠረተ ልማት | 47 |
| *Instinct* | ደመነፍስ | 418 |

| | | |
|---|---|---|
| *Instruments of Labour* | የሥራ ማከናወኛዎች | 110 |
| *Instruments of Production* | የማምረቻ መሣሪያዎች | 85 |
| *Insurrection* | ሕዝባዊ አመጽ | 19 |
| *Intelligentsia* | ምሁራን | 92 |
| *Intensity of Labour* | የሥራ ዕምቀት | 112 |
| *Interaction* | መስተጋብር | 51 |
| *Interest* | ወለድ | 395 |
| *Internal and External Contradictions* | ውስጣዊና ውጫዊ ቅራኔዎች | 410 |
| *Internationale (proletarian Hymn)* | ኢንተርናሲዮናል (መዝሙር) | 321 |
| ***International** Bank for Reconstruction and Development* | የዓለም የመልሶ ግንባታና የልማት ባንክ | 347 |
| *International Division of Labour (Under Capitalism and socialism)* | ዓለምአቀፍ የሥራ ክፍፍል (በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም) | 353 |
| *International Monetary Fund (IMF)* | ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት | 355 |
| *International Monopoly* | ዓለምአቀፍ ሞኖፖል | 351 |
| *International Union of Students* | ዓለምአቀፍ የተማሪዎች ኅብረት | 354 |
| *Interventionism* | ጣልቃገብነት | 465 |
| *Intuition* | ጭልታ | 470 |
| *Intuitionism* | ጭልታዊነት | 470 |
| *Investment* | ሙአለንዋይ | 73 |
| *Irrationalism* | ኢምክኑያዊነት | 316 |
| *Iskra* | ኢስክራ | 319 |


# J


| | | |
|---|---|---|
| *James, William* | ጀምስ ዊልያም | 434 |
| *Jevons, William Stanley* | ጀቮንስ ፣ ዊልያም ስታንሊ | 436 |
| *Joint- Stock Company* | የጋራ አክሲዮን ኩባንያ | 449 |
| *Judgement* | ብያኔ | 218 |

| | | |
|---|---|---|
| *Junta* | ጁንታ | 435 |
| *Juvenile Delinquency* | የወጣት አጥፊነት | 403 |


## K


| | | |
|---|---|---|
| *Kantianism* | ካንሺያኒዝም | 366 |
| *Kant, Immanuel* | ካንት ፥ አማኑኤል | 368 |
| *Keynes, John Maynard* | ኬይንስ ፥ ጆን ሜይናርድ | 381 |
| *Kierkegaard, Sören* | ኪርከጋርድ ፥ ሰረን | 362 |
| *Knowledge* | ዕውቀት | 357 |
| *Komsomol* | ኮምሶሞል | 390 |
| *Kulak* | ኩላክ | 361 |


## L


| | | |
|---|---|---|
| *Labour* | ሥራ | 107 |
| *Labour Aristocrats* | የወዝአደር መሳፍንት | 401 |
| *Labour Power* | የሥራ ኃይል | 107 |
| *Laissez-Fair* | ሌሴፌር | 37 |
| *La Mettrie, Julien Offroy de* | ላ ሜትሪ ፥ ዡሊየ አፍሯ ዶ | 34 |
| *Landlord* | የመሬት ከበርቴ | 53 |
| *Language* | ቋንቋ | 192 |
| *Large Scale Industries and Small Scale Industries* | ትላልቅ ኢንዱስትሪዎችና ትናንሽ ኢንዱስትሪዎች | 246 |
| *Lassalism* | ላሳሊዝም | 35 |
| *Latent Surplus Populatipn* | ሽፍን ተረፈ ሕዝብ | 177 |
| *Law* | ሕግ | 25 |
| *Law of Contradiction* | የቅራኔ ሕግ | 189 |
| *Law of Dialecties* | የዲያሌክቲክስ ሕግ | 426 |

| | | |
|---|---|---|
| *Law of Negation of the Negation* | የሽረት ሽረት ሕግ | 174 |
| *Law of Transformation of Quantity into quality and Vice Versa* | ከመጠን ወደ ዓይነት ከዓይነት ወደ መጠን ለውጥ ሕግ | 70 |
| *Luw of Uneven Development of Capitalism* | የካፒታሊዝም ያልተመጣጠነ ዕድገት ሕግ | 373 |
| *Law of the Unity and Struggle of Opposites* | የተቃራኒዎች አንድነትና ትግል ሕግ | 230 |
| *Low of Value* | የእሴት ሕግ | 335 |
| *Leap* | እመርታ | 333 |
| *«Left» Wing Communism* | "ግራ" ክንፍ ኮሚኒዝም | 456 |
| *Legal Consciousness* | ሕጋዊ ንቃተኅሊና | 25 |
| *Legal Forum* | ሕጋዊ መድረክ | 24 |
| *Legal Marxism* | ሕጋዊ ማርክሲዝም | 24 |
| *Leibniz ,Gottfried Welhelm* | ላይብኒትዝ ፣ ጐትፍሪድ ቬልሄልም | 36 |
| *Lenin, Vladimir Ilyich* | ሌኒን ፣ ቭላድሚር ኢሊች | 39 |
| *Leninism* | ሌኒኒዝም | 38 |
| *Leninist Standards of Party Life* | ሌኒናዊ የፓርቲ ሕይወት ድንጋጌዎች | 39 |
| *Liberalism* | ለዘብተኝነት | 33 |
| *Liberalism* | ነፃዊነት | 261 |
| *Liquidationism* | ደምሳሽነት | 418 |
| *Loan Capital* | የብድር ካፒታል | 219 |
| *Locke, John* | ሎክ ፥ጆን | 45 |
| *Logic* | ሥነ አመክንዮ | 117 |


# M


| | | |
|---|---|---|
| *Machiavelli, Niccolo di Bernardo* | ማኪያቬሌ ፣ ኒኮሎ ዲ ቤርናርዶ | 89 |
| *Machine Production* | የማሽን ምርት | 88 |
| *Malthus, Thomas Robert* | ማልተስ ፣ ቶማስ ሮበርት | 83 |

| | | |
|---|---|---|
| *Man* | ሰው | 133 |
| *Manufacture* | መፈብረክ | 71 |
| *Mao Tse–tung* | ማኦ ትሴ-ቱንግ | 88 |
| *Marshall, Alfred* | ማርሻል ፣ አልፍሬድ | 86 |
| *Marxism* | ማርክሲዝም | 86 |
| *Marx, Karl* | ማርክስ ፣ ካርል | 87 |
| *Marxism-Leninism* | ማርክሲዝም ሌኒኒዝም | 86 |
| *Mass Organization* | ሕዝባዊ ድርጅት | 22 |
| *Mass of Surplus Value* | የተረፈ እሴት እክብ | 230 |
| *Materialism* | ቁስአካልነት | 185 |
| *Matriarchate* | እማዊ ሥርዓት | 334 |
| *Matter* | ቁስአካል | 184 |
| *May Day* | ሜይ ዴይ | 91 |
| *Means of Labour* | የሥራ መገልገያዎች | 109 |
| *Means of Production* | የምርት መገልገያዎች | 95 |
| *Mechanical Materialism* | ተናክአታዊ ቁስአካልነት | 234 |
| *Mensheviks* | ሜንሸቪኮች | 91 |
| *Mercantilism* | ሜርካንቲሊዝም | 90 |
| *Metaphysics* | ዲበአካል | 422 |
| *Middle Strata* | መካከለኛ የኅብረተሰብ ክፍሎች | 63 |
| *Militarism* | ጦረኝነት | 467 |
| *Mill, James* | ሚል ፣ ጄምስ | 74 |
| *Mill, John Stuart* | ሚል ፣ ጆን ስትዋርት | 74 |
| *Mode af Production* | ስልተ ምርት | 140 |
| *Monarchy* | ንጉሣዊ አገዛዝ | 268 |
| *Maney* | ገንዘብ | 443 |
| *Maney form of Value* | ገንዘባዊ የእሴት መልክ | 442 |
| *Monism* | አንዳዊነት | 294 |
| *Monopoly Prafit* | የሞኖፖል ትርፍ | 103 |
| *Montckretien, Antoine de* | ሞክሬቲየን ፣ አንቷን ዶ | 103 |

| | | |
|---|---|---|
| *Montesquieu, Charles de* | ሞንተስኪየ ፣ ሻርል ደ | 102 |
| *More, Thomas* | ሞር ፣ ቶማስ | 102 |
| *Motion* | ቅስቃሴ | 187 |
| *Mun, Thomas* | ሙን ፣ ቶማስ | 55 |
| *Mysticism* | ተማልሎታዊነት | 222 |
| *Mythology* | ሥነ ተረት | 117 |

# N

| | | |
|---|---|---|
| *Naive Realism* | ግልብ እውነነት | 454 |
| *Naradism* | ናሮዲዝም | 265 |
| *Nation* | ብሔር | 213 |
| *National Chauvinism* | የብሔር ትምክህተኝነት | 213 |
| *National Debt* | ብሔራዊ ዕዳ | 209 |
| *National Democratic Revolution* | ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት | 210 |
| *National Income* | ብሔራዊ ገቢ | 211 |
| *Nationalism* | ብሔረተኝነት | 206 |
| *Nationality* | ብሔረሰብ | 206 |
| *National Liberation Movement* | የብሔራዊ አርነት ንቅናቄ | 209 |
| *National Per capita Income* | ብሔራዊ ነፍስ ወከፍ ገቢ | 208 |
| *National Question* | የብሔር ጥያቄ | 214 |
| *National Socialism* | ብሔራዊ ሶሻሊዝም | 207 |
| *Natural Economy* | ተፈጥሮአዊ ኢኮኖሚ | 241 |
| *Naturalism* | ተፈጥሮአዊነት | 240 |
| *Natural Laws* | የተፈጥሮ ሕግጋት | 239 |
| *Necessary Labour* | አስፈላጊ ሥራ | 279 |
| *Necessary Product* | አስፈላጊ ምርት | 278 |
| *Necessity and chance* | ግዴታና አጋጣሚ | 458 |
| *Neo-Colonialism* | የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ | 342 |
| *Net or Genuine Cost of Circulation* | የተጣራ የማዘዋወሪያ ወጪ | 236 |

| | | |
|---|---|---|
| *Neutralize (To-)* | ገለልተኛ ማድረግ | 439 |
| *New Economic Policy* | አዲሱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ | 303 |
| *New International Economic Order* | አዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት | 304 |
| *Newton, Isaac* | ኒውተን ፥ ይስሐቅ | 264 |
| *Nietzsche, Friedrich Wilhelm* | ኒቸ ፥ ፍሬድሪሽ ቪልሄልም | 263 |
| *Nihilism* | አውዳሚነት | 302 |
| *Nominalism* | ስማዊነት | 143 |
| *Nominal Wages* | ስማዊ ምንዳ | 142 |
| *Non-Aggression pact or peace Treaty* | የሰላም ውል | 127 |
| *Non-Aligned Movement* | የገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄ | 438 |
| *Non-Basic Contradiction* | ኢመሠረታዊ ቅራኔ | 314 |
| *Non-Capitalist Way of Development* | ኢካፒታሊስታዊ የዕድገት ፈለግ | 327 |
| *Non-Class Philosophy* | ኢመደባዊ ፍልስፍና | 315 |
| *Non-Productive Labour* | ኢምርታዊ ሥራ | 315 |
| *North Atlantic Treaty Organization (NATO)* | የሰሜን አትላንቲክ ቃልኪዳን ድርጅት (ናቶ) | 128 |


## O


| | | |
|---|---|---|
| *Objective* | ነባራዊ | 254 |
| *Objective Condition* | ነባራዊ ሁኔታ | 254 |
| *Objective Idealism* | ነባራዊ ሐሳባዊነት | 255 |
| *Objective Knowledge* | ነባራዊ ዕውቀት | 257 |
| *Objective Truth* | ነባራዊ እውነት | 256 |
| *Objectivism* | ነባራዊነት | 255 |
| *Objects of Labour* | የሥራ ተገብሮች | 111 |
| *Oligarchy* | የቱጃሮች ምስፍና | 242 |
| *One and the Multiple (The-)* | አንዱና ብዙው | 294 |
| *Ontology* | ሥነ ኑባሬ | 117 |
| *Opportunism* | አድርባይነት | 307 |

| | | |
|---|---|---|
| *Organ* | ልሳን | 40 |
| *Organic Composition of Capital* | ውስጣዊ የካፒታል ጥንቅር | 409 |
| *Organization* | ድርጅት | 432 |
| *Organization of African Unity* | የአፍሪካ አንድነት ድርጅት | 312 |
| *Own, Robert* | አውን ፣ ሮበርት | 345 |


# P


| | | |
|---|---|---|
| *Pacificism* | ሰላም አክራሪነት | 126 |
| *Pan-Africanism* | ፓን አፍሪካኒዝም | 504 |
| *Pantheism* | ሁልአምላክነት | 4 |
| *Paper Money* | የወረቀት ገንዘብ | 397 |
| *Parallelism* | አጓዳኝነት | 308 |
| *Paris Commune* | ፓሪስ ኮሚዩን | 499 |
| *Particular and Universal* | ልዩና ሁለንታዊ | 44 |
| *Particularity and Universality of Contradictions (The-)* | የቅራኔዎች ልዩነትና ሁለንታዊነት | 190 |
| *Partisanship* | ወገናዊነት | 402 |
| *Party* | ፓርቲ | 500 |
| *Party Central Committee* | የፓርቲ ማዕከላዊ ኰሚቴ | 502 |
| *Party Congress* | የፓርቲ ጉባዔ | 503 |
| *Party Philosophy* | የፓርቲ ፍልስፍና | 503 |
| *Party Primary Organization* | የፓርቲ መሠረታዊ ድርጅት | 501 |
| *Party Programme* | የፓርቲ ፕሮግራም | 504 |
| *Party Statute* | የፓርቲ ደንብ | 503 |
| *Patriarchate* | አባዊ ሥርዓት | 285 |
| *Patriotism* | አርበኝነት | 283 |
| *Peaceful Co-existence* | በሰላም አብሮ የመኖር መርህ | 126 |
| *Peaceful Transition* | ሰላማዊ ሽግግር | 125 |

| | | |
|---|---|---|
| *Peace Programme* | የሰላም ፕሮግራም | 127 |
| *Peasantry* | አርሶ አደር | 283 |
| *Peasantry* | ገበሬ | 439 |
| *Peasants Producers' Cooperative Association* | የገበሬዎች አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበር | 439 |
| *"People's" Capitalism* | "ሕዝባዊ" ካፒታሊዝም | 20 |
| *Peoples, Control* | ሕዝባዊ ቁጥጥር | 19 |
| *Peoples' Defence Committee* | የሕዝብ ደኅንነት ጥበቃ ኰሚቴ | 22 |
| *Peoples' Democracy* | ሕዝባዊ ዲሞክራሲ | 21 |
| *Peoples' Militia* | ሕዝባዊ ሠራዊት | 18 |
| *Perception* | ልባዌ | 41 |
| *Personalism* | ሰብነት | 129 |
| *Pcrsonal Property Under Socialism* | የግለሰብ ንብረት በሶሻሊዝም | 452 |
| *Petty Bourgeoisie* | ንዑስ ከበርቴ | 266 |
| *Petty, William* | ፔቲ ፥ ዊልያም | 506 |
| *Phenomenalism* | ክስተታዊነት | 383 |
| *Phenomenology* | ሥነ ክስተት | 119 |
| *Phenomenon* | ክስተት | 383 |
| *Philistinism* | ጽናት አልባነት | 472 |
| *Philosophy* | ፍልስፍና | 489 |
| *Philosophy of History* | የታሪክ ፍልስፍና | 244 |
| *Physiocracy* | ፊዚዮክራሲ | 482 |
| *Piece Woges* | ቁርጥ ሥራ ምንዳ | 186 |
| *Plato* | አፍላጦን | 310 |
| *Political Bureau* | ፖለቲካ ቢሮ | 509 |
| *Political Economy* | ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ | 511 |
| *Political Line* | ፖለቲካዊ መሥመር | 509 |
| *Political Mass Strike* | ፖለቲካዊ የሥራ ማቆም አድማ | 510 |

| | | |
|---|---|---|
| *Political Power* | ፖለቲካዊ ሥልጣን | 509 |
| *Political Revolution* | ፖለቲካዊ አብዮት | 510 |
| *Political Struggle* | ፖለቲካዊ ትግል | 510 |
| *Politics* | ፖለቲካ | 508 |
| *Populism* | ፖፑሊዝም | 512 |
| *Positivism* | ተጨባጫዊነት | 238 |
| *Practice* | ተግባር | 236 |
| *Pragmatism* | ገቢራዊነት | 440 |
| *Price* | ዋጋ | 405 |
| *Primary Contradiction* | አንደኛ ደረጃ ቅራኔ | 293 |
| *Primary and Secondary Qualities* | ዋንኛና መለስተኛ ባሕርያት | 405 |
| *Primitive Accumulation of Capital* | መጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት | 68 |
| *Principles of Communist Distribution* | የኮሚኒስት ክፍፍል መርህ | 388 |
| *Principles of Socialist Distribution* | የሶሻሊስት ክፍፍል መርህ | 158 |
| *Problems of Realization of Gross Social Product* | አጠቃላይ ማኅበራዊ ምርትን የማጣራት ችግር | 309 |
| *Process* | ሂደት | 6 |
| *Production* | ማምረት | 84 |
| *Productive Labour* | ምርታዊ ሥራ | 93 |
| *Productive Forces* | የምርት ኃይሎች | 93 |
| *Productivity of Labour* | የሥራ ምርታማነት | 110 |
| *Professional Associations* | የሙያ ማኅበራት | 73 |
| *Profit* | ትርፍ | 246 |
| *Profit sharing* | የትርፍ ክፍያ | 248 |
| *Progress* | ርምደት | 168 |

| | | |
|---|---|---|
| *Progressive* | ተራማጅ | 230 |
| *Proletarian Internationalism* | ወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት | 399 |
| *Proletariat* | ወዝአደር | 400 |
| *Praofs of the existence of God* | የእግዚአብሔር ሕልውና ማረጋገጫዎች | 344 |
| *Propaganda* | ፕሮፓጋንዳ | 507 |
| *Protected State* | ጥብቅ ሀገር | 466 |
| *Protectionism* | ከላሎታዊነት | 382 |
| *Proudhon, Pierre Joseph* | ፕሩዶን ፣ ፒየር ጆሴፍ | 506 |
| *Provocation* | ትንኮሳ | 250 |
| *Pseudo-Revolutionary* | አስመሳይ አብዮተኛ | 277 |
| *Psyche* | ልቡና | 40 |
| *Psychological Make-up* | ሥነ ልቡናዊ ዘይቤ | 115 |
| *Puppet* | አሻንጉሊት | 284 |
| *Purpose* | ግብ | 456 |


# Q


| | | |
|---|---|---|
| *Qualitative Change* | የዓይነት ለውጥ | 357 |
| *Quantitative Change* | የመጠን ለውጥ | 70 |
| *Quesnay François* | ኬኔ ፣ ፍራንሷ | 363 |


# R


| | | |
|---|---|---|
| *Racism* | ዘረኝነት | 413 |
| *Rate of Interest* | የወለድ መጣኔ | 395 |
| *Rate Of Profit* | የትርፍ መጣኔ | 247 |
| *Rate Of Surplus Value* | የተረፈ እሴት መጣኔ | 229 |
| *Rationalism* | ምክንያዊነት | 101 |

| | | |
|---|---|---|
| *Rationalization* | ምክንያ | 101 |
| *Reactionary* | አድኃሪ | 305 |
| *Real* | እውን | 340 |
| *Realism* | እውንነት | 341 |
| *Real Wages* | እውን ምንዳ | 340 |
| *Reason* | አመክንዮ | 273 |
| *Recovery* | ግገማ | 460 |
| *Red Army* | ቀይ ጦር | 183 |
| *Referendum* | ሕዝባዊ ውሳኔ | 21 |
| *Reflection* | ነፀብራቅ | 259 |
| *Reformism* | ጠጋኝነት | 465 |
| *Relation Of Production* | የምርት ግንኙነት | 96 |
| *Relative and Absolute Truth* | አንፃራዊና ፍፁማዊ እውነት | 298 |
| *Relative form of Value* | አንፃራዊ የእሴት መልክ | 298 |
| *Relative Impoverishment* | አንፃራዊ የኑሮ ሁኔታ ቁርቁዝና | 297 |
| *Relative Independence* | አንፃራዊ ነፃነት | 296 |
| *Relative Surplus Value* | አንፃራዊ ተረፈ እሴት | 295 |
| *Relativism* | አንፃራዊነት | 295 |
| *Religion* | ሃይማኖት | 7 |
| *Reproduction* | እርባታ | 337 |
| *Republic* | ሪፐብሊክ | 166 |
| *Retail Trade* | የችርቻሮ ንግድ | 253 |
| *Revaluation* | የገንዘብ ምንዛሪ ዋጋ ጭመራ | 447 |
| *Revisionism* | ክላሽነት | 360 |
| *Revolution* | አብዮት | 289 |
| *Revolutionary* | አብዮተኛ | 286 |
| *Revolutionary Army* | አብዮታዊ ጦር | 289 |
| *Revolutionary Conditions* | አብዮታዊ ሁኔታ | 286 |
| *Revolutionary Democracy* | አብዮታዊ ዲሞክራሲ | 287 |
| *Revolutionary Transition* | አብዮታዊ ሽግግር | 287 |

| | | |
|---|---|---|
| *Ricarda, David* | ሪካርዶ ፣ ዴቪድ | 165 |
| *Right and Duty* | መብትና ግዴታ | 53 |
| *Romanticism* | ልብወለዳዊነት | 41 |
| *Rale* | ሚና | 74 |
| *Rausseau, Jean Jacques* | ሩሶ ፣ ዣን ዣክ | 164 |

# S

| | | |
|---|---|---|
| *Sabotage* | ሻጥር | 284 |
| *Saint-Simon, Cluade Henri* | ሰን ሲሞን ፣ ክሎድ አንሪ | 132 |
| *Sanction* | ማዕቀብ | 89 |
| *Sartre, Jean Paul* | ሳርትር ፣ ዣን ፖል | 136 |
| *Say, Jean Baptiste* | ሴይ ፣ ዣን ባቲስት | 140 |
| *Schelling, Friedrich Welhelm* | ሺሊንግ ፣ ፍሬደሪሽ ቪል ሄልም | 173 |
| *Scholasticism* | ተምህሮነት | 222 |
| *Schopenhaur, Arthur* | ሾፐንሀወር ፣ አርተር | 178 |
| *Scientific Communism* | ሳይንሳዊ ኮሚኒዝም | 137 |
| *Scientific Dialectics* | ሳይንሳዊ ዲያሌክቲክስ | 137 |
| *Scientific Ideology* | ሳይንሳዊ ርዕዮተዓለም | 137 |
| *Scientism* | ሳይንስነት | 138 |
| *Secessian* | መገንጠል | 69 |
| *Secand International* | ሁለተኛው ኢንተርናሽናል | 1 |
| *Secondary Contradiction* | ሁለተኛ ደረጃ ቅራኔ | 2 |
| *Segregation* | መድልዎ | 67 |
| *Self-consciausness* | ራስ ንቃተ ኅሊና | 167 |
| *Self-Reliance* | ራስን መቻል | 167 |
| *Semi–Calony* | ከፊል ቅኝ ግዛት | 361 |

| | | |
|---|---|---|
| *Senior, Nassaw William* | ሲኒየር ፡ ናሳው ዊልያም | 135 |
| *Sensation* | ሕውስታ | 18 |
| *Sensationalism* | ሕውስታዊነት | 18 |
| *Service Co-operatives* | የአገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራት | 307 |
| *Share* | አክሲዮን | 300 |
| *Simple Capitalist Co-operation* | ቀላል የካፒታሊስት ትብብር | 181 |
| *Simple Commodity Production* | ቀላል የሸቀጥ ምርት | 179 |
| *Simple (unskilled) Labour* | ቀላል ሥራ | 179 |
| *Simple Reproduction* | ቀላል እርባታ | 179 |
| *Sismondi, Slsmonde de* | ሲስሞንዲ ፡ ሲሞንድ ደ | 134 |
| *Skepticism* | ጠርጣሪነት | 462 |
| *Slogan* | መፈክር | 72 |
| *Smith, Adam* | ስሚዝ ፡ አዳም | 141 |
| *Social Being* | ማኅበራዊ ኑባሬ | 76 |
| *Social Capital* | ማኅበራዊ ካፒታል | 80 |
| *Social Chauvinism* | ማኅበራዊ ትምክህተኝነት | 76 |
| *Social Consciousness* | ማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና | 77 |
| *Social Darwinism* | ማኅበራዊ ዳርዊኒዝም | 82 |
| *Social Democracy* | ማኅበራዊ ዲሞክራሲ | 81 |
| *Socialism* | ሶሻሊዝም | 158 |
| *Social Laws* | ማኅበራዊ ሕግጋት | 75 |
| *Social Revolution* | ማኅበራዊ አብዮት | 78 |
| *Socialist Accumulation* | ሶሻሊስት ክምችት | 157 |
| *Socialist Commodity Production* | ሶሻሊስት የሸቀጥ ምርት | 150 |
| *Socialist Economic Planning* | ሶሻሊስት ዕቅድ | 155 |
| *Socialist Economic Integration* | ሶሻሊስት የኢኮኖሚ ጥምረት | 156 |
| *Socialist Emulation* | ሶሻሊስታዊ የሥራ ውድድር | 149 |
| *Socialist Humanism* | ሶሻሊስት ሰብአዊነት | 151 |
| *Socialist International* | ሶሻሊስት ኢንተርናሽናል | 154 |

| | | |
|---|---|---|
| *Socialist Property* | ሶሻሊስት ንብረት | 152 |
| *Socialist Realism* | ሶሻሊስት እውንነት | 156 |
| *Socialist Revolution* | ሶሻሊስት አብዮት | 153 |
| *Socialist Revolutionaries* | ሶሻሊስት አብዮታውያን | 153 |
| *Socialist Way of Life* | ሶሻሊስት የአኗኗር ዘይቤ | 151 |
| *Socially Necessary Labour Time* | ማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ | 78 |
| *Socio-Economic Formation (Social System)* | ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት | 79 |
| *Socrates* | ሶቅራጥስ | 160 |
| *Solipsism* | ራሳዊነት | 167 |
| *Sophism* | አንደበተኛነት | 292 |
| *Soviet* | ሶቭዬት | 160 |
| *Sovereignty* | ሉዓላዊነት | 34 |
| *Space and Time* | ስፍራና ጊዜ | 146 |
| *Spartakist (Spartacist)* | ስፓርታኪስት | 148 |
| *Speculative Philosophy* | እውጠንጣኝ ፍልስፍና | 303 |
| *Spencer, Herbert* | ስፔንሰር ፣ ሄርበርት | 149 |
| *Spinoza, Baruch* | ስፒኖዛ ፣ ባሩክ | 147 |
| *Spiral Development* | ጥምጥማዊ (ሙሻዙራዊ) ዕድገት | 466 |
| *Spiritualism* | መንፈሳዊነት | 62 |
| *Spontaneity* | ግብታዊነት | 456 |
| *Spontaneous Dialectics* | ግብታዊ ዲያሌክቲክስ | 457 |
| *Stagnant Surplus Population* | እግድ ተረፈ ሕዝብ | 345 |
| *Stagnation* | እግዳት | 345 |
| *Stakhanovism* | ስታኻኖቪዝም | 144 |
| *Stalin, Joseph* | ስታሊን ፣ ጆሴፍ | 143 |
| *Stand* | አቋም | 285 |
| *State* | መንግሥት | 60 |
| *State Budget (Under Capitalism and Socialism)* | የመንግሥት በጀት (በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም) | 61 |

| | | |
|---|---|---|
| *State Capitalism* | መንግሥታዊ ካፒታሊዝም | 58 |
| *State Duma* | መንግሥታዊ ዱማ | 60 |
| *State Monopoly Capitalism* | መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም | 56 |
| *State Socialism* | መንግሥታዊ ሶሻሊዝም | 58 |
| *Stack-exchange* | የአክሲዮን ገበያ | 300 |
| *Staicism* | ስቶይሲዝም | 145 |
| *Strategic Arms Limitatlon Talks (SALT)* | ስትራቴጂያዊ የጦር መሣሪያ ቅነሳ ድርድር (ሶልት) | 145 |
| *Strategy and Tactics* | ስትራቴጂና ታክቲክ | 144 |
| *Strike* | የሥራ ማቆም አድማ | 109 |
| *Structuralism* | መዋቅራዊነት | 63 |
| *Struggle* | ትግል | 250 |
| *Study circle* | የጥናት ክበብ | 466 |
| *Subbotnik* | ሱቦትኒክ | 134 |
| *Substance* | ባህርዮት | 201 |
| *Subjective* | ኅሊናዊ | 28 |
| *Subjective Condition* | ኅሊናዊ ሁኔታ | 29 |
| *Subjective Idealism* | ኅሊናዊ ሐሳባዊነት | 29 |
| *Subject- Object* | አድራጊ ተደራጊ | 305 |
| *Superstructure* | ላዕላይ መዋቅር | 35 |
| *Supply and Demand* | አቅርቦትና ፍላጐት | 284 |
| *Surplus Labour* | ተረፈ ሥራ | 228 |
| *Surplus Product* | ተረፈ ምርት | 227 |
| *Surplus Value* | ተረፈ እሴት | 229 |
| *Syndicalism* | ሲንዲካሊዝም | 136 |
| *Syndicate* | ሲንዲኬት | 136 |
| *Synthesis* | አስተፃምሮ | 277 |
| *System* | ሥርዓት | 114 |
| *System Of Balance in Planning* | የማመዛዘን ሥርዓት በዕቅድ | 84 |

# T


| | | |
|---|---|---|
| *Taylorism* | ቴይለሪዝም | 245 |
| *Technical Composition of Capital* | ቴክኒካዊ የካፒታል ጥንቅር | 244 |
| *Technological Revolution* | ቴክኖሎጂ አብዮት (የ–) | 244 |
| *Teleology* | ሥነ ግብ | 121 |
| *Terror* | ሽብር | 175 |
| *Theism* | አማኒነት | 273 |
| *Theology* | ሥነ መለኮት | 115 |
| *Theoretical Knowledge* | ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀት | 266 |
| *Theory* | ንድፈ ሐሳብ | 267 |
| *Thesis* | አንብሮ | 292 |
| *Third International (The)* | ሦስተኛው ኢንተርናሽናል | 122 |
| *Thomism* | ቶሚዝም | 250 |
| *Thought* | እ[illegible]ባት | 334 |
| *Time Woges* | የጊዜ ምንዳ | 448 |
| *Trade Union* | የሠራተኛ ማኅበር | 105 |
| *Triad Enemies* | ሶስቱ ጣምራ ጠላቶች | 124 |
| *Tragic* | መሪር | 53 |
| *Transition Period* | የሽግግር ወቅት | 175 |
| *Treaty* | ውል | 408 |
| *Tribe* | ነገድ | 258 |
| *Trotskyism* | ትሮትስኪዝም | 248 |
| *Trust* | ትረስት | 246 |
| *Trusteeship Territories* | ባለሞግዚት ግዛቶች | 202 |
| *Truth* | እውነት | 339 |
| *Turgot, Robert Jacques* | ቱርጎ ፣ ሮቤር ዣክ | 241 |
| *Turnover of Capital* | የካፒታል መገለባበጥ | 378 |

# U


| | | |
|---|---|---|
| *Ugly* | ሕሡም | 17 |
| *Unemployment* | ሥራ አጥነት | 111 |
| *Unequal Exchange* | ኢእኩያዊ ልውውጥ | 326 |
| *United Nations Organization* | የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት | 232 |
| *United Nations Security Council* | የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታ ምክር ቤት | 233 |
| *Universal* | ሁለንታዊ | 3 |
| *Universe* | ዩኒቨርስ | 416 |
| *Uprising* | ተናሥኦት | 234 |
| *Use Value* | የጠቀሜታ እሴት | 463 |
| *Use Value of Labour Power* | የሥራ ኃይል የጠቀሜታ እሴት | 109 |
| *Utilitarianism* | ጠቃሚያዊነት | 463 |
| *Utopian Socialism* | ተምኔታዊ ሶሻሊዝም | 223 |


# V


| | | |
|---|---|---|
| *Value* | እሴት | 335 |
| *Value* | ፋይዳ | 487 |
| *Vanguard* | ግንባር ቀደም | 458 |
| *Variable Capital* | ተለዋዋጭ ካፒታል | 222 |
| *Veto Power* | ድምፅን በድምፅ የመሻር ሥልጣን | 431 |
| *Vitalism* | ሕይወታዊነት | 23 |
| *Voluntorism* | ፈቃዳዊነት | 478 |
| *Vulgar Materialism* | ግልብ ቁስአካልነት | 453 |
| *Vulgar Political Economy* | ግልብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ | 454 |


# W


| | | |
|---|---|---|
| *wages* | ምንዳ | 99 |
| *Walras, Leon* | ቫልራ ፥ ሌዮ | 202 |

| | | |
|---|---|---|
| *War* | ጦርነት | 468 |
| *War Communism* | የጦርነት ኮሚኒዝም | 469 |
| *Warsaw Pact* | የዋርሶ ቃልኪዳን ድርጅት | 404 |
| *White Guards* | ነጭ ዋርድዮች | 259 |
| *Wholesale Trade* | ጅምላ ንግድ | 436 |
| *Will* | ፈቃድ | 478 |
| *Women's Day(International Working Women's Day)* | የሴቶች ቀን (ዓለምአቀፍ የሠራተኛ ሴቶች ቀን) | 138 |
| *Women's International Democratic Federation* | የሴቶች ዓለምአቀፍ ዲሞክራቲክ ፌደሬሽን | 139 |
| *Women's Question* | የሴቶች ጥያቄ | 139 |
| *Working People* | ሠርቶ አደር | 106 |
| *World Communist Movement* | ዓለም አቀፍ ኮሚኒስት ንቅናቄ | 355 |
| *World Federation of Democratic Youth* | የዓለም ዲሞክራሲያዊ ወጣቶች ፌደሬሽን | 356 |
| *World Federation of Trade Unions* | የዓለም ሠራተኛ ማኅበራት ፌዴሬሽን | 349 |
| *World Free Trade Unions Confederation* | ዓለምአቀፍ የነፃ ሠራተኞች ማኅበራት ኮንፌደሬሽን | 354 |
| *World Outlook* | ንጽረተ ዓለም | 271 |
| *World Peace Council* | የዓለም ሰላም ምክር ቤት | 349 |
| *World Revolutionary Process* | የዓለም ሂደተ አብዮት | 347 |
| *World Socialist System* | የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት | 350 |

# Z

| | | |
|---|---|---|
| *Zionism* | ጽዮናዊነት | 473 |

# ዋቢ መጻሕፍት

ይህ መዝገበ ቃላት የተዘጋጀው በይፀልጥ በኢትዮጵያ አብዮት ተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ በመመርኮዝ ስለሆነ አዘጋጅ ኮሚቴው የጥናቱ መሠረት አድርጎ የተጠቀመባቸው ምንጮች የኢሠፓአኮን ማዕከላዊ ኮሚቴ ሠነዶችና በኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ ምሥረታ ወቅትና ከዚያም በኋላ የወጡትን ልዩ ልዩ ጽሑፎች ነው ። በተጨማሪም ቀጥሎ በተመለከቱት መጻሕፍት ብዙ ተጠቅሟል ።


1. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ፤ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ፤ 1948 ፤ አዲስ አበባ ።
2. ደስታ ተክለ ወልድ ፤ አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ፤ 1962 ፤ አዲስ አበባ ።
3. *Frolov, I. ed., A Dictionary of Philosophy, Progress Publishers, Moscow,* 1980.
4. *Fundamentals of Marxist Leninist Philosophy, Progress Puublihers, Moscow,* 1974.
5. *Great Soviet Encyclopedia. Mac Millan, INC, New york, Collier Mac-Millan Publishers, London,* 1981.
6. *Kozlov,ed., Political Economy of Capitalism, Progress Publishers, Moscow,* 1977
7. *Kozlov,ed., Political Economy of socialism, Progress Publishers, Moscow,* 1977
8. *Philosophisches Worterbuch, Vol.* 1-2 *VEB Bibliographisches Institut, Lipzig,* 1977.
9. *Rumyantsev. A.M. Political Economy, Progress Publishers, Moscow,* 1983.
10. *Szentes, Tomas, The Political Economy of Underdevelopment, Akademia Kiodo, Budapest,* 1976.
11. *Foster, Z. William, History of the Three Internationals, International Publishers, New York,* 1955.